# መድሎተ ጽድቅ

## (የእውነት ሚዛን)

አዘጋጅ፡-

ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ

መጋቢት ፳፻፯ (2007) ዓ. ም.

አዲስ አበባ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡

©

*All Rights Reserved*

የመጀመሪያ ዕትም፡- መጋቢት ፳፻፯ (2007) ዓ. ም.

ስልክ ቁጥር - 0911 477244
0911 482865

Email - deaconyaregal@yahoo.com

Yaregal99@gmail.com

## የሽፋን ሥዕል መግለጫ

በመጽሐፉ ሽፋን ላይ ሚዛን ይታያል፡፡ በሚዛኑ በአንድ በኩል (በግራ) የተሐድሶ መናፍቃን የሚያሰራጩቸው የተለያዩ መጻሕፍትና መጽሔቶች፣ በሌላ በኩል (በቀኝ) ደግሞ ከቤተ ክርስቲያናችን ታላላቅ ሊቃውንት አባቶቻችን መካከል አንዱ የሆነው ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ሰፊና ጥልቅ ትምህርቶቹን ከያዙት መጻሕፍት መካከል አንዱን መጽሐፉን ብቻ በእጁ ይዞ ሲመዝኑ ይታያል፡፡

በሚዛን ሲመዘኑም የተሐድሶዎች ትምህርት የሌሎች ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት አባቶችን ትምህርት ሳይጨምር፣ ከቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ትምህርትም ገና አንዱ መጽሐፍ ብቻ ወደ ሚዛኑ ብቅ ሲል የአንዱን መጽሐፍ ጥላ ያህል እንኳ ለመመዘን የማይችል መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

# መታሰቢያነቱ


የዚህ መጽሐፍ መታሰቢያነቱ፡-

1. ጥልቅ የነገረ ሃይማኖት እውቀትን ከብሕትውና ሕይወት ጋር፣ ዓላማን ከጽናት ጋር፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ነባራዊ ሁኔታ የወደፊቱን ዘመን እጅግ አርቆ ከማየትና ከመረዳት ጋር፣ ሃሳብን ከተግባር ጋር አዋሕደው ይዘው እግዚአብሔር በሰጣቸው አነስ ያለ ዕድሜ ተገቢ የሆነ አዎንታዊ ለውጥ በሚያመጣ መንገድ ታላላቅ ሥራዎችን ለሠሩት፣ ጠንካራ ጭብጥ ያላቸውን መጻሕፍት ጽፈውልን ላለፉት፣ እጅግ ለሚወዷትና ብዙ ሥራ ላቀዱላት ቤተ ክርስቲያናቸው አገልግሎት ሲወጡና ሲወርዱ በመኪና አደጋ ሕይወታቸው ላለፈው፣ በአጠቃላይ ትውስታቸው ጽናትና ልዩ ብርታት ለሚፈጥረው ለብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ (1932 - 1982 ዓ. ም.)፣

እና

2. የቤተ ክርስቲያን ጠላቶችና ክፉዎች ሠራተኞቻቸው በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ለከፈቱት ግብሯን የማክፋፋትና ስሟን የማጥፋት ዘመቻ መሣሪያ እንዲሆኗቸው በማሰብ በጻፏቸው መጻሕፍት ላይ ድንቅና ጥልቅ በሆነ ሁኔታ "ኵሉሐ ሃይማኖት" እና "መድሎተ አሚን" የተሰኙ መጻሕፍትን ለጻፉት፣ በእነዚህ ድንቅ መጻሕፍቶቻቸውም የሐሰት ሰዎች የደረቡትን የበግ ለምድ ገፍፈው ተኩላነታቸውን ላጋለጡትና ባዶነታቸውን ላሳዩት፣ ዘመናቸውን ቀድመው ለተረዱትና ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋትን ዘመኑን የዋጀ የኖላዊነት አገልግሎት በሚገባ ላስተዋሉት፣ ለኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት መጠበቅ የሚቻላቸውን ሁሉ ላደረጉት ለመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ (1885 – 1962 ዓ. ም.)

ይሁንልኝ!



ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ

(1932 - 1982 ዓ. ም.)



መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ

(1885 – 1962 ዓ. ም.)

# ምስጋና

በበመጀመሪያ የሁሉም ነገር ባለቤት፣ መልካም ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ ቸርና ይቅር ባይ፣ መሐሪና ርህሩኅ የሆነው፣ ስለ እኛ ሁሉን ነገር ያደረገው ልዑለ ባሕርይ ቅዱስ እግዚአብሔር ይህን መጽሐፍ እንዳዘጋጅ ስላደረገኝ "ስለማነገር ሥጦታው እግዚአብሔር ይመስገን" እላለሁ። የእግዚአብሔር ስሙ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ የተመሰገነ ይሁን፣ አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን!

አባታዊ ትምህርታቸውና ምክራቸው ለሚያግዘኝ፣ እንዲሁም ረቂቁን ለተመለከቱልኝና ጠቃሚ አስተያየታቸውን ለሰጡኝ ለአባቴ ለየኔታ መምህር ደጉ ዓለም ካሣ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ሂደት ረቂቁን ከመመልከት ባሻገር ዘርፈ ብዙ በሆነ መልኩ ለረዱኝና ጠቃሚ ምክራቸውንና አስተያየታቸውን ለሰጡኝ ለቀሲስ ዶ/ር ስሙ ምትኩ፣ ለዲያቆን ብርሃኑ አድማስ እና ለሳሙኤል ፈቃዱ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ። እንዲሁም ረቂቁን ከመመልከትና ሁለንተናዊ ከሆነ ሃሳብና ምክር ጀምሮ ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት የሚያስፈልጉትን መጻሕፍት በማሰባሰብና በመሳሰለው ሂደት ሁሉ ዘወትር ድጋፋቸው ያልተለየኝን እኅቴን ወ/ሮ ዘውዴ ገ/እግዚአብሔርን እና ወንድሜን ኢ/ር ኃይለ ዓለም ወርቁን አመሰግናለሁ። ሁላችሁም በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ሂደት በሃሳብና በተግባር አብራችሁኝ ደክማችኋልና እግዚአብሔር ድካማችሁን ድካመ ቅዱሳን ያድርግላችሁ እላለሁ።

እንዲሁም የዚህን መጽሐፍ የሽፋን ሥዕል መልካም አድርጐ ለሠራው ሠዓሊ ለዘሪሁን ገ/ወልድ፣ የመጽሐፉን የውስጥ ገጽ ቅንብር ለሠራችው አዜብ ጌታቸው ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ። ከእነዚህም ጋር ለአቶ ተስፋዬ ቢሆነኝ፣ ለአቶ ተሻለ ሞላ፣ ለአቶ ደጀኔ ኢብሳ እና ለአቶ መስፍን መንግሥቱ ከነቤተሰቦቻቸው ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ከእነዚህም በተጨማሪ ከሃሳብና ከምክር ጀምሮ በጸሎትና አስፈላጊ በሆነው ሁሉ የረዱኝን፣ ሥራው የት ላይ እንደ ደረሰ በመጠየቅና እንዲፈጸም በማበረታታት እና በመሳሰለው ሁሉ የተሳተፉትን ሌሎችንም ሁሉንም ልዑል እግዚአብሔር በቸርነቱ ደጉን ዋጋ ይከፍላቸው ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁን፣ አሜን።

## የይዘት ማውጫ

ገጽ


መቅድም ........ 11

መግቢያ ........ 18

## ምዕራፍ አንድ

## መኃትው

1.1 የተሐድሶዎች መነሻዎችና መሠረቶች ........ 31
1.1.1 በ "መሰለኝ" ማመን ........ 31
1.1.2 በሐሰት መናገር ........ 35
1.1.3 ከእምነት ይልቅ በስሜት ሕዋሳትና (በማየት፣ በመስማት. . .) በቀላሉ በሚደረስበት ላይ መመሥረት ........ 42
1.1.4 ተገቢ ያልሆኑ አባባሎችና አገላለጾችን መጠቀም ........ 44
1.1.5 የነገረ ሃይማኖታዊ እውቀት ድህነት መገለጫዎች ........ 44

1.2 መኃትወ ታሪክ ዘመናፍቃን ........ 46
1.2.1 "መናፍቅ" ምንድን ነው? ለምንስ ይባላል? ........ 46
1.2.1.1 ሃይማኖት ምንድን ነው? ........ 46
1.2.1.2 ኑፋቄ ምንድን ነው? ........ 48

1.2.2 በዘመናት የነበሩ ዋና ዋና መናፍቃንና ኑፋቄያቸው በአጭሩ ........ 49
1.2.2.1 ግኖስቲኮች ........ 49
1.2.2.2 አርዮስ እና አርዮሳዊነት ........ 52
1.2.2.3 ንስጥሮስ እና አስተምህሮው ........ 53
1.2.2.4 ሄሊቪዲየስ (Helividius) ........ 57
1.2.2.5 ጆቪኒየን (Jovinian) ........ 57
1.2.2.6 ቪጂላንቲየስ (Vigilantius) ........ 59
1.2.2.7 አርዮስ ዘሴባስቴ (Arius of Sebaste) ........ 59
1.2.2.8 ማርቲን ሉተር ........ 60

## ክፍል አንድ

## የመዳን ትምህርት (ነገረ ድኅነት)

## ምዕራፍ ሁለት

2.1 ተሐድሶዎች ስለ መዳን የሚያስተምሩት ትምህርት ........ 66
2.2 የመዳን ትምህርት በዘመናት ሂደት ውስጥ - አጭር ዳሰሳ ........ 76
2.2.1 የነገረ ድኅነት ትምህርት በዘመናት ሂደት ውስጥ - በምዕራቡ ዓለም ........ 71
2.2.2 ስኮላስቲሲዝም (Scholasticism) ........ 78
2.2.3 የትሬንት ጉባኤ (1545 – 1563) ........ 78

# ምዕራፍ ሦስት

## ኦርቶዶክሳዊ የመዳን ትምህርት (ነገረ ድኅነት)


መግቢያ ... 84
3.1 መዳን ለምን አስፈለገ? ... 85
3.2 ሰውን ሊያድነው የሚችለው ማን ነበር? ... 89
3.3 የሰው ልጅ ድኅነት (መዳን) የእግዚአብሔር ዓላማ መሆኑ ... 94
3.4 መዳን ማለት ምን ማለት ነው? ... 97
3.5 የሚድኑ እነ ማን ናቸው? ... 119
3.6 መዳን (ድኅነት) - የእግዚአብሔር ስጦታ? ወይስ የሰው የሥራው ውጤት? ... 120
3.7 ለመዳን እያንዳንዱ ሰው ምን ማድረግ ያስፈልገዋል? ... 122
3.7.1 እምነት (ማመን) ... 124
3.7.2 ለድኅነት መሠረታዊ የሆኑ ምሥጢራትን መፈጸም ... 126
3.7.2.1 ምሥጢረ ጥምቀት ... 127
3.7.2.1.1 የተሐድሶዎች አስተምህሮ ስለ ጥምቀት ... 127
3.7.2.1.2 ጥምቀት - በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ... 128
3.7.2.1.3 ጥምቀት በጥንት ሊቃውንት አባቶች አስተምህሮ ... 136
3.7.2.1.4 ስለ ምሥጢረ ጥምቀት - ማጠቃለያ ... 142
3.7.2.2 ምሥጢረ ሜሮን ... 142
3.7.2.2.1 ስለ ምሥጢረ ሜሮን የተሐድሶዎች ትምህርት ... 142
3.7.2.2.2 ምሥጢረ ሜሮን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ... 142
3.7.2.2.3 ምሥጢረ ሜሮን በአበው ሊቃውንት ትምህርት ... 146
3.7.2.2.4 ስለ ምሥጢረ ሜሮን - ማጠቃለያ ... 148
3.7.2.3 ምሥጢረ ቁርባን ... 148
3.7.2.3.1 ተሐድሶዎች ስለ ምሥጢረ ቁርባን የሚያስተምሩት ትምህርት ... 148
3.7.2.3.2 ምሥጢረ ቁርባን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ... 150
3.7.2.3.3 ምሥጢረ ቁርባን በአበው ትምህርት ... 158
3.7.2.3.4 ቅዱስ ቁርባን "መሥዋዕት" ይባላልን? ... 169
3.7.2.3.4.1 የቅዱስ ቁርባን መሥዋዕትነት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ... 170
3.7.2.3.4.2 የቅዱስ ቁርባን መሥዋዕትነት በቀደምት አበው ትምህርት ... 172
3.7.2.3.4 ምሥጢራት - ማጠቃለያ ... 177
3.7.3 በተቀበሉት ጸጋ መጽናት፣ መንፈሳዊ ተጋድሎና ክርስቲያናዊ መልካም ሥራ ... 182
3.7.3.1 የተሐድሶዎች ትምህርት ስለ ተጋድሎና ክርስቲያናዊ ሥራ ... 182
3.7.3.2 "በእምነት" መዳን እና "በእምነት ብቻ" መዳን ... 188
3.7.3.3 በተቀበሉት ጸጋ መጽናት፣ ተጋድሎና ክርስቲያናዊ መልካም ምግባር ለመዳን ያላቸው ሚና - በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ... 191
3.7.3.4 መጽናት፣ ተጋድሎና ክርስቲያናዊ ሥራ ለመዳን ያላቸው ሚና - በአበው ሊቃውንት ትምህርት ... 205

## ምዕራፍ አራት

## ጾም፣ ምጽዋት እና ቀኖና


4.1 ጾም .......... 219
4.1.1 ጾም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት .......... 219
4.1.1.1 የጾም አስፈላጊነትና ጠቀሜታ .......... 219
4.1.1.2 ጾም የታወቀ ጊዜ ያለው መሆኑ .......... 222
4.1.1.3 በጾም ወቅት የማይበሉ ምግቦች ስለ መኖራቸው .......... 224
4.1.1.4 ጾም በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ ያለው ስለ መሆኑ .......... 224
4.1.2 ጾም በቅዱሳን አባቶች ትምህርት .......... 225

4.2 ምጽዋት .......... 233
4.2.1 ምጽዋት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት .......... 233
4.2.2 ምጽዋት በአበው ትምህርት .......... 236

4.3 ንስሐ (ቀኖና) ለምን? እንዴት? .......... 241
4.3.1 የተሐድሶዎች ትምህርት ለካህን ስለ መናዘዝና ቀኖና ስለ መቀበል .......... 241
4.3.2 ለንስሐ አባት መናዘዝና ቀኖና - በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት .......... 244
4.3.2.1 ለካህን መናዘዝና ቀኖና መቀበል .......... 246
4.3.2.2 ቀኖና የሚሰጥባቸው ምክንያቶች .......... 248
4.3.3 ንስሐ አባትና ቀኖና - በአበው ትምህርት .......... 253

4.4 ማጠቃለያ - የክፍል አንድ .......... 261


## ክፍል ሁለት

## በእንተ ወላዲተ አምላክ

## ምዕራፍ አምስት

## እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም


5.1 በእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ውስጥ የሰው ሱታፌ .......... 266
5.2 በእግዚአብሔርና በሰዎች ግንኙነት ሂደት ውስጥ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ቦታ .......... 270
5.3 እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም "ወላዲተ አምላክ" ትባላለችን? ለምን? .......... 275
5.4 "ወላዲተ አምላክ" .......... 276
5.4.1 የቃሉ ትርጉም .......... 276
5.4.2 የቃሉ ነገረ መለኮታዊ ፋይዳ .......... 277
5.4.3 የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክነት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት .......... 279
5.4.4 የእመቤታችን ወላዲተ አምላክነት - በቀደምት አበው ትምህርት .......... 283

5.5 ማጠቃለያ .......... 244

# ክፍል ሦስት

# በእንተ ቅዱሳን

## ምዕራፍ ስድስት


6.1 ስለ ቅዱሳን መማርና ማስተማር ለምን አስፈለገ? ........ 296
6.2 ቅዱሳን ከሞት በኋላ ስለሚኖራቸው ማወቅ/አለማወቅ ጉዳይ ........ 307
  6.2.1 የተሐድሶዎች ትምህርት በዚህ ጉዳይ ላይ ........ 307
  6.2.2 እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው የጸጋ መጠን ወሰንና ዳርቻ ........ 309
  6.2.3 ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ ስለሚኖራቸው አዋቂነት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት 313
6.3 የቅዱሳን አማላጅነትን በተመለከተ ........ 323
  6.3.1 ተሐድሶዎች የሚያነሷቸው የተሳሳቱ አባባሎችና ፍረጃዎች ........ 323
  6.3.2 የቅዱሳን አማላጅነት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ........ 347
    6.3.2.1 የቅዱሳን አማላጅነት አግባብነት ........ 348
    6.3.2.2 አማላጅነት ለምን? ........ 351
    6.3.2.3 የቅዱሳን አማላጅነት በሕይወተ ሥጋ ........ 357
    6.3.2.4 የቅዱሳን አማላጅነት በዓጸደ ነፍስ ........ 363
  6.3.3 የቅዱሳን አማላጅነት - በቀደምት አበው ሊቃውንት ትምህርት ........ 364
6.4 ቤተ ክርስቲያንን በቅዱሳን ስም መሰየምና መጥራት ........ 374
  6.4.1 በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ........ 374
  6.4.2 ቤተ ክርስቲያንን በቅዱሳን ስም መሰየምና መጥራት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ........ 378
  6.4.3 ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳን ስም እንደሚሰየም - በቀደምት አበው ሊቃውንት ትምህርት ........ 382
6.5 ስለ ቅዱሳን መጻፍ መቼ ተጀመረ? ........ 383
6.6 ስለ ቅዱሳን የጻፉ አባቶች ........ 387


# ክፍል አራት

# በእንተ ምንኩስና ወሕይወት ገዳማዊ

## ምዕራፍ ሰባት፡- ምንኩስና እና ገዳማዊ ሕይወት


7.1 በምንኩስናና በገዳማዊ ሕይወት ላይ ተቃዋሚዎች የሚያነሷቸው ነገሮች ........ 392
7.2 ምንኩስናና ገዳማዊ ሕይወት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ........ 399
7.3 የተሐድሶ እቀንቃኝ የነበረው ማርቲን ሉተር ምንኩስናንና ገዳማዊ ሕይወትን የተቃወመባቸው ምክንያቶች ........ 412
7.4 ክርስቲያናዊ መልካም ሥራ በቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ........ 416
7.5 የክርስቲያናዊ መልካም ሥራ - በቅ. ጴጥሮስ፣ በቅ. ዮሐንስ፣ በቅ. ያዕቆብ እና በቅ. ይሁዳ መልእክታት ........ 424
7.6 ምንኩስና እና ገዳማዊ ሕይወት "የአረማውያን ፍልስፍና" ነውን? ........ 426
7.7 የገዳማዊ ሕይወት ታሪካዊ ሂደት - በአጭሩ ........ 431
  7.7.1 በዘመነ ብሉይ ........ 431
  7.7.2 በዘመነ ሐዲስ ........ 433
7.8 ምንኩስና እና ገዳማዊ ሕይወት "ስብከተ ወንጌልን ያዳክማል" የሚለው የተቃውሞ ነጥብ 438
7.9 ድንግልና፣ ምንኩስናና ገዳማዊ ሕይወት - በቀደምት አበው ሊቃውንት ትምህርት 445

## ክፍል አምስት

## ለሞቱ ወገኖች የሚደረግ ጸሎት (ጸሎተ ፍትሐት) እና ተዝካርና ዝክር

### ምዕራፍ ስምንት:- ለሞቱ ክርስቲያኖች የሚደረግ ጸሎት (ጸሎተ ፍትሐት) እና ተዝካርና ዝክር


8.1 ጸሎተ ፍትሐት ........ 454
8.1.1 በጸሎተ ፍትሐት ላይ የተሐድሶዎች ትምህርት ........ 454
8.1.2 ጸሎተ ፍትሐት የሚደረግባቸው መሠረታዊ ምክንያቶች ........ 455
8.2 ተዝካርና ዝክር ........ 462
8.2.1 የተሐድሶዎች ትምህርት - በዝክርና ተዝካር ላይ ........ 462
8.2.2 ተሐድሶዎች ጸሎተ ፍትሐትን በተመለከተ ከሚሏቸው ነገሮች ዋና ዋናዎቹ ውሸቶችና ስህተቶች ........ 463
8.3 በቁርባን ጊዜ የሞቱ ነፍሳት ስም ለምን ይጠራል? ........ 466
8.4 ለሞቱ ወገኖች ጸሎተ ፍትሐት ማድረግና በቁርባን ጊዜ ስማቸውን መጥራት ........ 467


## ክፍል ስድስት - ልዩ ልዩ

### ምዕራፍ ዘጠኝ - ቅዱሳት መካናትን መሳለምን በተመለከተ


9.1 የተሐድሶዎች ትምህርት - መሳለምን በተመለከተ ........ 477
9.2 የቦታን፣ የጊዜን፣ የመሳሰሉ ነገሮችን ቅድስና(ክብር) በተለመከተ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ........ 478
9.3 የተቀደሱ ቦታዎችን መሳለም - ለምን? ........ 481
9.4 በቅዱሳት መካናት ዐጸድ መቀበር ለምን? ........ 486
9.5 ክርስቲያኖች በመካነ ቅዱሳን ለመቀበር የሚፈልጉባቸው ምክንያቶች ........ 490
9.6 የመሳለም ታሪካዊ ሂደት በአጭሩ ........ 491
9.7 ቅዱሳት መካናትን መሳለምንና በእነርሱ መቀበርን በተመለከተ የአበው ቀደምት ትምህርት ........ 493


### ምዕራፍ አሥር - በዓላት


10.1 በዓላትን በተመለከተ የተሐድሶዎች ትምህርት ........ 501
10.2 በበዓላት ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶች ........ 502
10.3 በዓላት ለምን አስፈለጉ? ........ 506
10.4 የቅዱሳን መታሰቢያ በዓላትን ማድረግ ተገቢ ስለ መሆኑ - የአበው ቀደምት ትምህርት ........ 513

ማጠቃለያ ........ 517

ዋቢ መጻሕፍት ........ 519

# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

## መቅድም

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ድንቅና ልዩ በሆኑ በብዙ ጸጋዎች አክብሮ ፈጥሮታል፡፡ ከእነዚህ ጸጋዎች መካከል አንዱና ታላቁ፣ የጸጋዎች ሁሉ አክሊል ሊባል የሚችለው፣ "ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ - ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" ብሎ በአርአያውና በአምሳሉ መፍጠሩ ነው፡፡ ዘፍ. 1፡26 ይህ "አርአያ" እና "አምሳል" የሚለው ነገር በጣም ጥልቅና ሰፊ ሲሆን ከዚህ ጸጋ ውስጥ አንዱ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የወደደውን የማድረግና ያለማድረግ ነጻ ፈቃድ ያለው አድርጎ መፍጠሩ ነው፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው በፈለገው ነገር ማመን ወይም አለማመን ሰው በመሆኑ የተሰጠው ተፈጥሯዊ ጸጋ ነው፡፡ ይህን መብት የሰጠውም የነጻነት አምላክ የሆነው ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰውን እኔ ፈጥሬሁ፣ እኔ የፈጠርኩትን አየርና ውኃ፣ ፀሐይና መሬት ወዘተ እየተጠቀምህ እኔን አለማመን አትችልም ወይም እኔን ከማመን ውጭ ሌላ አማራጭ የለህም አይልም፡፡ እርሱ በግዴታ ሳይሆን በነጻነት ወደነውና መርጠነው እናመልከው ዘንድ፣ ካልፈለግንም ልንተወው እንችል ዘንድ በፍጹም ነጻነት ፈጥሮናል፡፡ ስለዚህ ማንም ሰው የሚያምነውን ነገር መከተል ነጻነቱም መብቱም ነው፡፡

በዓለማችን ላይ ከጥንት ጀምሮ የተለያዩ እምነታዊ አስተሳሰቦችና ልማዶች የኖሩትና ያሉትም ከዚህ እግዚአብሔር ለሰው ከሰጠው ፍጹም ነጻነት የተነሣ ነው፡፡ እግዚአብሔር አባትነቱንና አምላክነቱን ሽተውና ወድደው እርሱን የሚፈልጉትና የሚያፈቅሩት ሰዎች ብቻ በእውነተኛ መንገድ እንዲያመልኩት እንጂ ማንም ሰው ያለ ውዴታው በግድ እንዲያመልከው አይፈልግም፤ ይህ ከእውነተኛ ፍቅርና ከነጻነት ጋር አብሮ አይሄድምና፡፡ እውነተኛ ፍቅርና ነጻነት ማለት ሌላውን አስገድዶ የራስን ፈቃድ ማስፈጸም ሳይሆን የሌላውንም ፍላጎትና ምርጫ ማክበር ነውና፡፡ ስለዚህም ሰነፎች የሆኑ ሰዎች "እግዚአብሔር የለም" ሲሉ፣ አሕዛብ ደግሞ ፈጣሪያቸውን ዘንግተው ለሰው መገልገያ የተፈጠሩትን ልዩ ልዩ ፍጥረታት ሲያመልኩ፣ መናፍቃን ደግሞ የሕይወት መጽሐፍ ከሆነው ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ለእነርሱ አስተሳሰብና አካሄድ የሚመቹ የመሰሏቸውን ጥቂት ጥቅሶች ወይም ሃሳቦች ብቻ ዘግነው ወይም አጠቃላይ ሃሳቡን አዛብተው ሲነጉዱ ...እርሱ የነጻነት አምላክ ነውና ድርጊታቸው ስህተትና ኃጢአት ቢሆንም እርሱ ግን በትዕግሥት ይመለከታቸዋል፡፡

ይህም የዚህ ዓለም አኗኗር እስከሚፈጸምበት ጊዜ ድረስ ይቀጥላል፡፡ እስከዚያ ድረስ ግን መልካሙ ገበሬ እርሱ (ጌታችን) መልካሙን ዘር ይዘራል፣ ጠላትም እንክርዳዱን ይዘራል፡፡ እስከ መከር (እስከ ኅልቀተ ዓለም) ድረስ ልዩ ልዩ ዓይነት የክህደትና የስህተት ትምህርቶች ከምድራችን በተለያየ መልኩ ይኖራሉ፤ "እስከ መከር ድረስ አብረው ይደጉ" ተብሏልና፡፡ በመጨረሻ ግን ምእመናንንም የእምነት ዋጋቸውን ይቀበላሉ፣ መናፍቃንና ከሃድያንም እንዲሁ የዘሩትን የክፉ ዘር ፍሬ ሞትንና ስቃይን ያጭዳሉ፡፡ ራሱ ባለቤቱ "በመከር ጊዜም አጫጆችን፦ እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ልቀሙ፣ በእሳትም ለማቃጠል በየነዶው እሰሩ፣ ስንዴውን ግን በጎተራዬ ክተቱ እላለሁ" ብሏልና፡፡ ማቴ. 13፡30

ሰዎች የሚያምኑበትን እምነት መኖር ብቻ ሳይሆን እርሱን በተመለከተ መጻፍና ማስተማርም መብታቸው ነው፡፡ ሆኖም ግን አንድ ሰው እርሱ የማያምንበትን ሌላ ሃይማኖት እንደሚያምንበት በማስመሰል ለማጥቃት ሲሞክር፣ ወይም በውስጡ በሌለበትና በማያምንበት ሃይማኖት ስም እየተጠራ ያን እምነት ለመፈተን ሲነሣ ነገሩ የማይመችና ከበድ ያለ ይሆናል፡፡

ከዚያ አልፎ ደግሞ የእርሱን አስተሳሰብና የእምነት ትምህርት በሌላው ሃይማኖት አስተምህሮ ላይ "የእናንተ እምነት እንዲህ ነው" እያለ በግድ ለመጫን ያለ ይሉኝታ ሲሞክር ማየት ደግሞ በእጅጉ ዕረፍት ይነሣል፡፡ ይህም የራስን ነጻነት ተጠቅሞ የሌላውን መንፈግና ያልሆኑትን በመምሰል የማጥቃት ስልት (ስትራቴጂ) ነው፡፡

ለራሳቸው "ተሐድሶ" የሚል ስም ሰጥተው ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እየተዋጉ ያሉ አካላት አካሄዳቸውና ስልታቸው እንዲህ ዓይነት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ እነዚህ ወገኖች ጥልቅ የሆነ ጥላቻንና ንቀትን በሚገልጽ ጽሑፋቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሐዋርያዊ የሆነውን የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ያብጠለጥላሉ፡፡ የእነርሱን ጽሑፍ በየዋህነት ብቻ ለተመለከተ ሰው ምናልባትም ቤተ ክርስቲያኒቱ እግዚአብሔርን የማታውቅ፣ በክርስቶስ አዳኝነት የማታምን፣ ትምህርቷም ከጌታችን ከመድኃኔ ዓለም ከኢየሱስ ክርስቶስ መምህርነት የተገኘው፣ በቅዱሳን ሐዋርያትና በቅዱሳን ሊቃውንት የታመነውና የተሰበከው ሳይሆን ከሆነ ጊዜ ወዲህ በሰዎች ልማድ የተጀመረ ሰው ሠራሽ መስሎ እንዲታየው ለማድረግ ያልተጠቀሙበት ዘለፋና ነቀፋም ሆነ ነውረኛ ቃላትና አገላለጽ አለ ለማለት ያስቸግራል፡፡

እነዚህ ራሳቸውን "ተሐድሶ" ብለው የሚጠሩ አካላት ለራሳቸው ከማመን አልፈው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ያልሆነ መልክ በመስጠት ፕሮቴስታንታዊ የሆነውን የራሳቸውን አዲስ ትምህርት በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ በግድ ለመጫን እየተንቀሳቀሱ ነው፡፡ የእነዚህ አካላት ዋና ዋና ስልቶች ሦስት ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

1) አንደኛው ስልት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነትና አስተምህሮ፣ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊውና ከቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ትምህርት የተለየና የራቀ አስመስሎ ለማሳየት መሞከር ነው፡፡ ይህም የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን አስተምህሮዋንና እምነቷን፣ ምሥጢራቷንና ሥርዓቷን፣ ይትበሃሏንና ትውፊቷን፣ በአጠቃላይ ሁለንተናዊ ሕይወቷን በሙሉ ከጥንቱ ከጌታችንና ከሐዋርያት እንዲሁም ከሊቃውንት ትምህርት የራቀና የሚቃረን አስመስሎ ማሳየት ነው፡፡ ይህም ለቤተ ክርስቲያኒቱ መልኳ ያልሆነውን ሌላ መልክ በመስጠት ሰዎች ከልቡናቸው ውስጥ እንዲያወጧትና እንዲጠሏት ለማድረግ ይረዳናል በሚል ነው፡፡ ለዚህ ዓላማቸውም ቤተ ክርስቲያኒቷ የምታምነውን እንደማታምን፣ የማታምነውን ደግሞ እንደምታምን፣ የምትለውን እንደማትል፣ የማትለውን ደግሞ እንደምትል እያስመሰሉ ያለ ይሉኝታና ያለ ኃፍረት ደጋግመው ጽፈዋል፡፡

ተሐድሶዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ሐዋርያዊ እና ኦርቶዶክሳዊ የሆነውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ጥላሸት ለመቀባት ይረዳናል ያሉትን ነገር ሁሉ አንዳችም ሳይስቀሩ አሟጥጠው ለመጠቀም ሞክረዋል፡፡ ጽሑፋቸው ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን በመንቀፍና በማጥላላት ላይ ያተኮረና ያመዘነ ነው፡፡ ለዚህም እነርሱ ሌሎችን የሚነቅፉበትን ነገር ሳይቀር ለራሳቸው ሲሆን ደግሞ በአዎንታ ተቀብለው ተጠቅመውበታል፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሆኑ ብዙ ምንጮችንና ነገሮችን ከመጠቀማቸው ባሻገር ባለቤታቸው የሚታወቁም ሆነ የማይታወቁ ተረቶችንና ወጎችን እንኳ ሳይቀር ቤተ ክርስቲያኒቱን ለመንቀፍ የሚጠቅም መስሎ እስከ ታያቸው ድረስ ለመጠቀም ሞክረዋል፡፡ አንድን ነገር ደግመው ደጋግመው በመመላለስና ስድቡና ነቀፋውም ቢሆን መልኩን ከሚለውጥ በስተቀር ያለቀባቸው መሆን አፍ አውጥቶ እስኪናገር ድረስ ያንኑ ነገር በየመጣጥፎቻቸውና በየገጹ ያቀርባሉ፡፡

> ተቀባይነታቸውን ለማስፋት ሲሉም "ኦርቶዶክስ" የሚለውን ከሁለት በመክፈል ራሳቸውን "የጥንቱ ኦርቶዶክስ" ብለው ሲመድቡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምታምነውንና የምታደርገውን ደግሞ ከጥንቱ የተለየ ነው ለማለት "የአሁኑ ኦርቶዶክስ" የሚል ታርጋ ሊለጥፉላት የሞከሩም አሉ፡፡ ይህም ራሳቸውን "ፕሮቴስታንት" አይደለንም፣ "ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ነን" ለማለት ነው፡፡ ይህን መጠቀም የሚፈልጉትም ቤተ ክርስቲያኒቷን ከውስጥ ሆነው ሙሉ በሙሉ ቀስ በቀስ በሂደት በመሸርሸር ኦርቶዶክሳዊ ማንነቷን በማሳጣት ፕሮቴስታንት የማድረግ ስውር ዓላማቸውን ከዳር ለማድረስ እንዲረዳቸው ነው፡፡

2) በመቀጠልም እንዲህ ባለ ሁኔታ ለቅድስትና ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ሌላ መልክና ስም ለመፍጠር ከሞከሩ በኋላ ራሳቸውን የእውነተኛው የሐዋርያትና የሊቃውንት ትምህርት አማኞችና ጠበቆች አድርገው ለማቅረብ ሞክረዋል፡፡ ፕሮቴስታንቲዝምን በኢትዮጵያ ለማስፋፋት ከአውሮፓ ከመጡት ሚሲዮናውያን እግር ሥር ቁጭ ብሎ ፕሮቴስታንታዊነትን

የቀጸለው መሠረት ስብሐት ለአብ የተባለው ግለሰብ በ1951 ዓ. ም. "ስምዓ ጽድቅ ብሒራዊ" ብሎ በጻፈው መጽሐፉ ላይ ይህን ስልትና ዓላማውንም በፊሊጥ ለዘብ አድርጎ ለማሳየት ሞክሯል፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ፕሮቴስታንት ለማድረግ በስልት ይሠሩ የነበሩት ሚሲዮናውያን የእነ ዳቪድ ስቶክስ ደቀ መዝሙር የነበረው መሠረት በጻፈው መጽሐፉ ላይ እንዲህ ብሏል፡-

> "ሊብራሩ ሲገባቸው በዘመን ብዛትና በአገር ላይ በሚሆን ተለዋዋጭ ሁናቴ፣ በመንፈሳዊ እውቀት ማነስ፣ በመናፍቃን ስሕተቶች ምክንያት <u>የተቀበሩና የተሸፈኑ ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን መምህራን</u> ዋና ዓላማ አድርገው ሲሠሩባቸውና ሲያስተምሩባቸው የኖሩ ብዙ ነገሮች እንዳሉ የአሁኖቹ ደጋጎች መምህራን ሁሉ የሚያውቁት ነገር ነው፡፡" ገጽ 12-13

መሠረት ስብሐት ለአብ በዚህ መጽሐፉ ላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ <u>"የተቀበሩና የተሸፈኑ የነገረ ሃይማኖት ትምህርቶችና እውነቶች"</u> እንዳሉና እነዚያን ለማውጣት እነርሱ የጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን መምህራንን ዓላማ ለማሳካት እንደሚሠሩ አስመስሎ ለማቅረብ ሞክሯል፡፡ ከዚያ በኋላ የተነሡ ሌሎች የተሐድሶ ሠራተኞች የቀጠሉት በዚሁ መሠረት ስብሐት ለአብ ከፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን የተቀበለውን ተልእኮ በመከተል በቀደደው ቦይ ነው፡፡ ለአብነትም ተሐድሶዎቹ የሚጽፏቸው መጻሕፍት መሠረት ስብሐት ለአብ "... በመናፍቃን ስሕተቶች ምክንያት <u>የተቀበሩና የተሸፈኑ</u> ... ብዙ ነገሮች እንዳሉ የአሁኖቹ ደጋጎች መምህራን ሁሉ የሚያውቁት ነገር ነው" ያለውን በመከተል "የተቀበረ መክሊት"፣ "መቅደስ የገቡ መናፍቃን"፣ ወዘተ እያሉ ነው፡፡ ከዚህ የተነሣ እነርሱ የሚጽፏቸውን መጻሕፍትና መጽሔቶች እውነተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርትና እምነት እንደ ሆነ አስመስለው ለማቅረብ በመጻሕፍቶቻቸውና መጣጥፎቻቸው ግርጌዎች "የጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ" የሚል መግለጫ ይጽፋሉ፡፡ እነ ዳቪድ ስቶክስ ለፕሮቴስታንታዊ ዓላማቸው መሳካት ይረዳቸው ዘንድ የሀገር ቤት ሰዎችን መመልመልና አሠልጥኖ ማሰማራት ሁነኛ መንገድ መሆኑን ተገንዝበው ለዚሁ ዓላማቸው የመለመሉት መሠረት ስብሐት ለአብ "ስምዓ ጽድቅ ብሒራዊ" ከሚለው ከመጽሐፉ ርእስ ሥር" በጥንታውያን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መምህራን ፍለጋ" የሚል መግለጫ አስቀምጧል፡፡

የእርሱን ስውር ሥልጣና ተከታትለው የእርሱ ደቀ መዛሙርት የሆኑት ሌሎችም የሚጽፉት በዚሁ ስልት ነው፡፡ ለአብነትም "መቅደስ የገቡ መናፍቃን" የሚለው የተሐድሶዎች መጽሐፍ ከርእሱ ሥር ላይ "የጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን (ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ) አስተምህሮን መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ" የሚል መግለጫ ተጽፎበታል፡፡

መጥቅዕ የሚለው ጋዜጣቸውም ከርእሱ ግርጌ ላይ "በጥንታውያት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል መምህራንና ሊቃውንት አስተምህሮ መሠረት የምትዘጋጅ መንፈሳዊ ጋዜጣ" ይላል፡፡ (ኅዳር 2002፣ ሰኔ 2003)፡፡ "የተቀበረ መክሊት" በተባለው መጽሐፋቸው የመጀመሪያ ቅጠል የውስጥ ገጽ ላይም "ጥንታውያንና ፍለጋቸውን የተከተሉ የዘመናችን ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እንዳስተማሩት" ይላል፡፡ እነዚህ ሁሉ ማስታወቂያዎች ራሳቸውን "የጥንት ሊቃውንት ተከታዮች" አድርገው ለማቅረብ የተደረጉ ሙከራዎችና ጥረቶች ናቸው፡፡ እንግዲህ እነዚህ ሁሉ መግለጫዎች የሚያሳዩት አማናዊቷን ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ቢቻላቸው አጥፍተው ራሳቸውን በእርሷ ላይ ለማንገሥና ስሟን በመውረስ የእርሷ ያልሆነውን የእነርሱን የኑፋቄ ትምህርት በቀደምት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሽፋን አስርገው ለማስገባትና በኦርቶዶክሳዊው ትምህርት ቦታ እርሱን ለመተካት ምን ያህል እንደሚተጉ ነው፡፡

ይህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ከጥንታዊው የሐዋርያትና የሊቃውንት ትምህርት እንደ ራቀች አድርጎ ማቅረብ፣ በአንጻሩ ራሳቸውን ደግሞ "በጥንታውያን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መመህራንና ሊቃውንት አስተምህሮ ላይ የተመሠረትን ነን" የሚለው የተሐድሶዎች አባባል ዛሬ የተጀመረ ስልት አይደለም፡፡ መናፍቃን ከጥንትም ጀምሮ ቢሆን ሲነሡ "ቤተ ክርስቲያንን አቅጣጫዋን ስታለች፣ ስለዚህ እኛ የተነሣነው ወደ እውነተኛው የሐዋርያት ትምህርት ልንመልሳት ነው" በሚል ሽፋን ነበር፡፡ ለምሳሌም በ2ኛው መቶ ዓመት የተነሣው መርቅያን የተባለው መናፍቅ "ተልእኮዬ ቤተ ክርስቲያንን ማደስ ነው" ይል ነበር፡፡ ከአራቱ ወንጌል አንዱን ብቻ (የሉቃስ ወንጌልን፣ ከዚያውም እርሱ በመሰለው መንገድ እየቀነሰና እየጨመረ) ይቀበል የነበረውና የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን "የክፉው አምላክ ናቸው" በማለት ሙሉ በሙሉ ይጠላቸውና ፈጽሞ አይቀበላቸው የነበረው መናፍቁ መርቅያን "ቤተ ክርስቲያን የሙሴን ሕግ እየተከተለች ወንጌልን ጥላለች፣ ሐዋርያት ጌታ ያስተማረውን እምነትና ትምህርት በርዘውታል፣ አበላሽተውታል፣ ስለዚህም ክርስቶስ ጳውሎስን የላከው ሐዋርያት የጣሉትን እውነት እንዲያስተምር ነው" በማለት ራሱን የእውነት ጠበቃና አዳኝ አድርጎ ለማቅረብ የሚችለውን ሁሉ ሞክሯል፡፡[1]

ይህ ስልት ሌሎች መናፍቃንም እየተጠቀሙበት ለዘመናት ዘልቋል፡፡ አርዮስም ኦርቶዶክሳውያን አባቶችን አንድ ገጽ የሚለውን የሰባልዮስን ኑፋቄ የሚከተሉ "ሰባልዮሳውያን ናቸው" እያለ ራሱን የእውነተኛው ሃይማኖት ጠበቃና መምህር አድርጎ ለማቅረብ ይሞክር ነበር፡፡ አርዮስ ኑፋቄው እየታወቀ ሲሄድ የእስክንድርያ ፓትርያርክ የነበረው ቅዱስ እለእስክንድሮስ እንዲመለስ ሲነግረው ከስሁቱ በመመለስ ፋንታ ፓትርያርክ ቅዱስ እለእስክንድሮስ የቅድስት ሥላሴን አንድነት ቡተመለከተ ባስተማረ ጊዜ "እለእስክንድሮስ አንድ ገጽ የሚለው የመናፍቁ የሰባልዮስ ተከታይ ነው" እያለ ስሙን ለማጥፋትና ለማስወራት ሞክሮ ነበር፡፡[2] በዚህም አርዮስ ብዙዎች ሰዎችን ለማሳትና ከጎኑ ለማሰለፍ ችሎ ነበር፡፡

እነ ማርቲን ሉተርና መሰሎቹም ፕሮቴስታንታዊ ኑፋቄያቸውን ይዘው ብቅ ባሉ ጊዜም ዋና ስልታቸው ይኸው ነበር፤ "ቤተ ክርስቲያንን ወደ ጥንቱ የሐዋርያት እምነትና ትምህርት እንመልሳለን" የሚል፡፡[3] ተሐድሶዎች የተከተሉት ይህንኑ የአባቶቻቸውን መንገድ ነው፡፡

3) ሦስተኛው ስልታቸው ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የእምነት አስተምህሮ ላይ ያቀረቡትን ነቀፋና ማሳጣት እውነት ለማስመሰል ከመጽሐፍ ቅዱስ እና ከቀደምት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ትምህርቶች መካከል ለሃሳባቸው ድጋፍ ይሆኑናል ያሏቸውን የተወሰኑ ነገሮችን ለመጠቃቀስ መሞከር ነው፡፡

መሠረት ስብሐት ለአብ ይህን አስመሳይ ተንኮሉን "ስምዓ ጽድቅ ብሔራዊ" በተባለው መጽሐፉ ላይ እንዲህ ሲል ገልጿል፦ "እንግዲህ መጽሐፉ አብነቱ ከብሉይና ከሐዲስ ኪዳን ሆኖ በጥንታውያን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ጎዳና ተያይዞና ተጠናቅቆ ተጽፏል፡፡" (ገጽ 9) ሆኖም "ከጥንታውያን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባቶች" ተብለው የተጠቀሱት የሊቃውንት ጥቅሶች በየጉዳዩ ላይ በጣም ጥቂቶች (በብዙዎቹ ጉዳዮች ላይ ከአንድና ከሁለት የማይበልጡ) ሲሆኑ እነዚያም ከአጠቃላይ ሃሳባቸው (Context) ተነጥለው የማይሉትን እንደሚሉ ለማስመሰል ተጠምዝዘው የቀረቡ ናቸው፡፡

---

1 W. P. Hares, A History of the Christian Church of the First Six Centuries, The Christian Literature Societies, 3rd ed., 1984.

2 Atiya Aziz S., The Coptic Encyclopedia, New York, Macmillan Publishing Co., 1991.

3 Charles R. Biggs (Pastor), The Story of Martin Luther, the Reformation and the Life of Martin Luther until the Diet of Worms (1521).

እንዲሁም ከጠቀሷቸው ጥቅሶች መካከል ብዙዎቹ ተሐድሶዎቹ እነርሱን ለድጋፍ ይሆኑናል ብለው ከጠቀሱበት ርእስ ጉዳይ ጋር የማይሄዱ ናቸው፡፡ እንዲሁ "አባቶች ሊቃውንትም እንዲህ ብለዋል" ብሎ ለማስመሰልና ገባ ብሎ ይዘታቸውን ሳይመረምር እንዲሁ በጥቅሶች መኖር ብቻ ደንገጥ የሚል ሰው ብናገኝ በሚል የቀረቡ ናቸው፡፡ ከዚህም በላይ ደግሞ እገሌ እንዲህ ብሏል ተብለው የተጠቀሱት እነዚያው ጥቅሶች ያ ብሏል የተባለው አባት የት ላይ እንዳላቸውና ከየት እንደ ተገኙ ምንጫቸው አልተገለጠም፡፡

ከሊቃውንት አባቶች ትምህርት ብቻ ሳይሆን ከመጽሐፍ ቅዱስም የተወሰኑ ጥቅሶችን መጥቀስና ከመሠረተ ሃሳባቸው ነጥሎ ሌላ ነገር እንደሚሉ አስመስሎ ማቅረብ የመናፍቃን ጠባይ ነው፤ እንኳን አማኝ ነኝ የሚል ሰው ቀርቶ ሰይጣንም ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳልና፡፡ እነርሱም ከመጽሐፍ ቅዱስ ተቃራኒ የሆነ ኢክርስቲያናዊ ትምህርታቸውን ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ተቆርቋሪዎች መስለው ሐሰቱን እውነት አስመስለው ለማቅረብ ሞክረዋል፡፡ መናፍቃን በየዘመናቱ ያነሡትንና የፕሮቴስታንቶች ትምህርት የሆነውን የታወቀና ግልጽ ኑፋቄያቸውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት አስመስለው ለማቅረብ ሞክረዋል፡፡ ለዚህም መጽሐፍ ቅዱስንና የቀደምት አበው ሊቃውንት ትምህርት የእነርሱ ደጋፊዎች አስመስለው ለማቅረብ ሞክረዋል፡፡

በዚህም ላይ ጸሐፊዎቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነትና አስተምህሮ እየነቀፉና እየወቀሱ ሲጽፉ ብዙዎቹ እውነተኛ ማንነታቸውን ደብቀው የብዕር ስም እየተጠቀሙ ነው፡፡ እንዲህ ባለ መንገድ ጸሐፊያቸው በውል የማይታወቁ መጻሕፍትን ይጽፋሉ፤ የተለያዩ መጣጥፎችንና ጽሑፎችን ይበትናሉ፤ ያሠራጫሉ፡፡ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያናችን ሰዎች ለመምሰል እና ምልባትም "የአሁን ዘመን ሰው ብዙም አይረዳውም . . ." በሚል እሳቤ ለብዙ ጽሑፎቻቸው ማስረጃ አስመስለው ጥቅሶችን በግእዝ ይጽፋሉ፡፡

እንግዲህ ይህ ሁሉ እንዲህ ሲሆን ዝም ብሎ መመልከት እንዴት ይቻላል? ክህደትና ኑፋቄ በኦርቶዶክሳዊነት ሽፋን ሲነዛ፣ ሐሰት እውነት መስሎ ሲነገር፣ ማሩን አምርረው ወተቱን አጥቁረው የሚጽፉና የሚናገሩ ሰዎች ግምታቸውንና ኑፋቄያቸውን ሁሉ እንደ እውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት እያስመሰሉ እንዳሻቸው ሲናገሩ እያዩ እጅን አጣጥፎ፣ ወይም እያዘኑና እየተበሳጩ መቀመጥ ብቻ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ የተነሣሡባቸው መሠረታዊ ምክንያቶች ከላይ የተገለጹት ናቸው፡፡

ስለዚህ የዚህ መጽሐፍ ዓላማም በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮና እምነት ፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሐዋርያዊ መሆኑን በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ማሳየት ሲሆን በመቀጠልም የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ከቀደምት ሊቃውንት አባቶቻችን እምነትና ትምህርት ጋር አንድ መሆኑንና እውነተኛውን የቀደምት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እምነትና ትምህርት የያዘችው ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንጂ ተሐድሶዎች አለመሆናቸውን ሕሊናዊ ሚዛን ያለው ማንኛውም ሰው ሊረዳው በሚችል ሁኔታ በተጨባጭ ለማሳየት ነው፡፡

በሦስተኛም ይህን በተጨባጭ ለማስረዳትና ለማረጋገጥ በየሚነሡት ነገረ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመቀጠል ከሐዋርያት ዘመን ቀጥሎ ከተነሡት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጀምሮ እስከ ስድስተኛው መቶ ዓመት ድረስ የነበሩት አባቶች እምነታቸውና ትምህርታቸው ምን እንደ ነበረ ሰፋ ያለ ማስረጃ በማቅረብ ማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህም እንዲሁ "የቀደምት ሊቃውንት ልጆች እኛ ነን" በሚል ማስታወቂያ ሳይሆን የቀደምት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ልጆች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች የሆንነው እኛ ነን? ወይስ ተሐድሶዎች ናቸው? የሚለውን ማንኛውም አንባቢ በመረጃው መሠረት እርግጠኛውን ማወቅና በራሱ መወሰን እንዲችል ማገዝ ነው፡፡ ስለዚህም በየነገረ ሃይማኖታዊ ጉዳዩ ላይ መጀመሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፣ በመቀጠልም የቀድምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ትምህርት ሰፋ ብሎ ቀርቧል፡፡

በዚህ ረገድ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ጽንፈኛ አርዮሳዊ የነበረው ዩኖሚየስ (Eunomius) ለጻፈው የክህደት መጽሐፍ ሁለተኛ የመልስ መጽሐፉን (Answer to Eunomius' Second Book) ሲጽፍ መጽሐፉን ስለ ጻፈበት ምክንያት የተናገረው የእኔንም ሃሳብ ይገልጥልኛልና እርሱን ልጥቀስ፤ እንዲህ ይላል፡-

> ከዚህ ክፉ ጠላት ጋር [ከአርዮሳዊው ዩኖሚየስ ጋር] ዕርቅ የሌለውና ጽኑ የሆነ ውጊያን ለመዋጋት የጀመርኩት ከትዕቢት የተነሣ ነው ወይም የሰዎችን ክብር በመሻት ነው ብሎ የሚያስብ ማንም ሰው አይኑር፡፡ በራሴ ላይ ጦርነትን በመቀስቀስ ሰላሜንና ጸጥታዬን ከማጣ ይልቅ ከማንም ሰው ጋር ሳልጋጭ የሰላም ሕይወት ለመኖር ብችልና ቢፈቀድልኝ ኖሮ ለእኔ ለግል ሰብእናዬና ጠባዬ በእጅጉ ይሻለኝ ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን የእግዚአብሔር ከተማ የሆነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በጠላት ተከባ እያለች፣ ታላቁ የእምነት አጥርና ቅጥር ዙሪያውን በከበቡት የኑፋቄ የጦር መሣሪያዎች እየተመታ ከመሆኑ የተነሣ እየተነቀነቀና እየተናወጸ እያለ፣ ከዲያብሎሳዊ ተንኮላቸውና ጥቃታቸው የተነሣ የእግዚአብሔርን ቃል ለጥፋታቸውና ለኑፋቄያቸው ምርኮኛ ሊያደርጉት ቀላል በማይባል ሲጋት ላይ ጥለውት እያየን፣ በዚህ ሁኔታ ላይ በዚህ የክርስትና ጦርነት አለመሳተፍና ድርሻን አለመወጣት አስጨናቂና አሳዛኝ ነገር እንደ ሆነ በማሰብ ወደዚህ ሰልፍ ውስጥ ገብቻለሁ፡፡
>
> እያንዳንዱ ሰው ሐዋርያው እንዳለ እንደየ ድካሙ ዋጋውን እንደሚቀበል ሁሉ ከዓቅሙ አንጻር መድከም የነበረበትን ያህል ድካም ያልደከመ ሰው ደግሞ ቅጣት ይጠብቀዋልና፡፡ . . . ስለዚህም ዳዊት "እግዚአብሔር አምላኬ ይባረክ፣ ለእጆቼ ሰልፍን፣ ለጣቶቼም ዘመቻን የሚያስተምር" (መዝ. 143፥1) እንዳለ እነዚህን ኑፋቄያዊ አስተሳሰቦችና አባባሎች አፈርሳቸው ዘንድ የምጽፍበትን እጄን አምላካዊ ኃይል እንዲመራልኝ፣ ጣቶቼ ደግሞ የእነርሱን ክፉ ሰልፍ አፈርስ ዘንድ ሃሳቤንና አመላለሴን ሁሉ በጥበብና በትክክል ይሆን ዘንድ ተስፋዬን በእርሱ በማድረግ ነው፡፡
>
> (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ Answer to Eunomius' Second Book)

አዎ፣ ውሸትን በተለያዩ ሰዎችና ጊዜያት ደጋግሞ በመናገር እውነት ለማስመሰል፣ በዚህም እውነተኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሐዋርያዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት አጥፍቶ ሰው ሠራሽና ልብ ወለዳዊ አስተሳሰብን በቤተ ክርስቲያን ምእመናን ላይ ለመጫን የሚደረገውን ዘርፈ ብዙ ሩጫና ዘመቻ ዝም ብሎ ማየት አይቻልም፡፡ የዮሴፍ ወንድሞች ወንድማቸውን ወደ ግብጽ እንደ ሸጡት እንጂ ክፉ አውሬ እንዳልበላው እያወቁ፣ ነገር ግን ከመጀመሪያው ጀምሮ "ክፉ አውሬ በልቶታል" እያሉ ለአባታቸውም ለሌላውም ሰው ሲናገሩ ስለ ኖሩ ይኸንኑ ውሸት ስለ ለመዱት እየቆየ ሲሄድ ለራሳቸውም እንኳ ሳይቀር እውነት እየመሰላቸው ሄዶ ነበር፡፡ ሐሰት ብዙዎችን የማሳሳት ሰፊ ዕድል ከማግኘቱ በፊት ሐሰትነቱ በጊዜው ሊገለጥ፣ እውነትም እንዲሁ ሊመሰከር ይገባዋልና ይህን ለማድረግ ይቻል ዘንድ ይህን መጽሐፍ አዘጋጀሁ፡፡ ታላቁ ሊቅ ነባቤ መለኮት ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ በዘመኑ የተነሣውን የአቡሊናርዮስን ኑፋቄ በተመለከተ ለአንድ ሌላ አባት ሲጽፍለት እንዲህ ብሎ ነበር፡-

> . . . ይህን ለሕዝቡ በጉባኤ ፊት እንድትገልጽና እንድታውጅ እሻለሁ፣ ይህም ይህን የመሰለውን ክፉ ነገር ችላ በማለት እንዳንወቀስና በእግዚአብሔር ፊት እንዳንጠየቅ፤ እንዲሁም ይህ ክፉ ትምህርት ከእኛ ዝም ማለትና ግድየለሽነት የተነሣ እውነት እየመሰለ እንዳይሄድና ኃይልና ብርታት እንዳያገኝ ነው፡፡ (መልእክት ኀበ ክሌዶኒየስ ካህን በእንተ አቡሊናርዮስ፣ መልእክት 101[4])

ይኸው አባት ለራሳቸው የፈጠሩ ትምህርትና ኦርቶዶክሳዊውን አስተምህሮ ለማጥቃት በሚመቻቸው መንገድ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰኑ ጥቅሶችን ብቻ መዝዘው እያንጠለጠሉ ቤተ ክርስቲያንን በእጅጉ ሲያውኩ ስለ ነበሩት አርዮሳውያንና መሰሎቻቸው ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

> የመናፍቃን ጥንካሬያቸው በራሳቸው አስተምህሮ ላይ ሳይሆን እንደ ዝንቦች የእኛን ቁስሎችና ደካማ ጎኖች በመፈለግና እነዚያ ላይ በመረባረብ ላይ ነው፡፡ ስለዚህም እኛን የሚነቅፉበትና የሚያጠቁበት መግቢያ ቀዳዳ ለማግኘት ሲሉ ደካማ ጎናችንን አጥብቀው ይፈልጋሉ፡፡ ዝንቦች

[4] To Cledonius the Priest Against Apollinarius, Ep. CI.

> ቁስል ፍለጋ 'ሀር' እያሉ ከቁስል ወደ ቁስል እንደሚዘዋወሩ ሁሉ እነርሱም በእኛ ላይ ይዘምታሉ። ስለዚህ ስለ ራሳችን የማናውቅ፣ በእነዚህ ነገሮች ላይም ሊደረግ ስለሚገባው ነገር ጠንቅቀን የማንገነዘብና ግድ የለሾች እንሁን። (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ የአምስቱ ተከታታይ ነገረ መለኮታዊ ትምህርቶች መግቢያ፣ 5)

በመጽሐፍ ቅዱስ "ክፉ ሠራተኞች" ተብለው የተገለጹት አጽራረ ጽድቅ መናፍቃን ስልታቸውና አካሄዳቸው እንደየጊዜው ይለዋወጣል። ሆኖም ከማይለወጠው መሠረታዊ ባሕርያቸው መካከል አንዱና ዋናው ነገራቸው ሙሉ ኃይላቸውን የሚያውሉት ሌላውን ያልሆነ መልክ በመስጠት የማይለውን እንደሚል፣ የሚለውን ደግሞ እንደማይል እያስመሰሉ በማሳየት ለማስጠላትና ለማስነወር ጥረት በማድረግ መሆኑ ነው። ይህን የመናፍቃንን ተንኮል በተመለከተ ይኸው ታላቅ አባት በቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ የዕረፍት ቀን መታሰቢያ ላይ ባደረገው ትምህርታዊ ንግግር ላይ "ይህ አሁን የምናገረው ነገር የሚመለከተው የራሳቸውን ክህደትና ክፋት ሌሎችን በመውቀስና ስማቸውን በማጥፋት ሊሸፍኑ በሚሞክሩ ሰዎች ላይ ነው"[5] ብሏል። (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ በቅዱስ ባስልዮስ የዕረፍት ቀን መታሰቢያ ላይ ያደረገው ንግግር፣ ቁ. 68)

ሆኖም ፍጻሜያቸው ምን እንደሚሆን ደግሞ እነዚያው መናፍቃን በተለያየ ሴራና ተንኮል ከመንበሩ አሳድደውትና ብዙ መከራ እያደረሱበት ለነበረው ለቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ በጻፈለት መልእክት ላይ እንዲህ ብሏል፦

> እየደረሰብህ ያለው መከራ በጣም አብዝቶ አያሳዝንህ። በነገሮች ብዙም ባልተበሳጨንባቸውና ባላዘንንባቸው መጠን አሳዛኝነታቸው ያነሰ ይሆናልና። መናፍቃን ከረምት ሲወጣ ከየጉድጓዳቸው እንደሚወጡ ነፍሳት ብቅ ብቅ ማለታቸውና በጊዜው ያሉትን ለእነርሱ የተመቹ የሁኔታዎችን አመችነት ለመጠቀም መሞከራቸውና በእነዚህ እየተበረታቱ ማድረግ የሚችሉትን ነገር ሁሉ ለማድረግ መሞከራቸው እንግዳ ነገር አይደለምና። ሆኖም በእውነቱና በሂደቱ ማንነታቸው እየተገለጠና እየታወቁ ስለሚሄዱ እንደ እባብ ያለ ድምፃቸውን የሚያሰሙት ለአጭር ጊዜ እንደሚሆንና ከዚያ በኋላ ተመልሰው ራሳቸውን እንደሚቀብሩ አውቃለሁ። ይህ የበለጠ የሚሆነው ደግሞ እኛም ነገሩን የበለጠ ለባለቤቱ ለእግዚአብሔር በሰጠነው መጠን ነው።" (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ መልእክት ኀበ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ቁ. 72)

ስለዚህ ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀበት ዋናው ዓላማ ሐዋርያዊ እና ኦርቶዶክሳዊ የሆነውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የተሐድሶ መናፍቃን ከሚሉት አንጻር በመመዘን እውነቱን በተቻለኝ መጠን ለመግለጥ መሞከር ነው። ይህ መጽሐፍ በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምታምነውንና የምታስተምረውን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተሐድሶዎቹ በይፋ በጻፏቸው መጻሕፍቶቻቸው የገለጿቸውን ትምህርቶቻቸውን፣ ሁለቱንም በመጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት እንዲመዘኑ ያደርጋል። በመቀጠልም በቀደምት አበው ትምህርት እንዲመዘኑ ያደርጋል። ከዚያም በመጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፣ በመቀጠልም በቀደምት አበው ሊቃውንት ትምህርት ሚዛንነት ሲመዘን ትክክለኛ ሆኖ የሚገኘውና ከሚዛን ቀልሎ የሚገኘው የትኛው እንደሆነ በራሱ ግልጽ ይሆናል። መጽሐፉ <u>"መድሎተ ጽድቅ - የእውነት ሚዛን"</u> የሚል ርእስ (ስያሜ) የተሰጠውም ለዚህ ነው።

**ተሐድሶዎች የሚያነሷቸው ጉዳዮችና የሚያሰራጩአቸው የስህተት ትምህርቶች በጣም ብዙ ስለሆኑ በዚህ መጽሐፍ ያልተዳሰሱትን ሌሎች ጉዳዮች እንደ እግዚአብሔር መልካም ፈቃድ በቀጣይ ሌላ መጽሐፍ እንመለከታቸዋለን።**

[5] ("My remarks are directed against those evil disposed persons who shelter their own vices under cover of their calumnies against others.")

# መግቢያ

## የመጽሐፉ ይዘት

ይህ መጽሐፍ በስድስት (6) ክፍሎች እና በአሥር (10) ምዕራፎች የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ መንትው ሲሆን ይህም ሁለት ጉዳዮችን ይዳስሳል፡፡ እነዚህም የተሐድሶዎች መነሻዎችና መሠረቶች ምን እንደሆኑ እና በዘመናት የተነሡ ዋና ዋና ኑፋቄዎችንና መናፍቃን ናቸው፡፡ ዋና ዋናዎቹ የተሐድሶዎች መነሻዎቸና መሠረቶች በነገረ ሃይማኖትና ቤታሪክ ላይ "ይመስለኛል" እያሉ መናገርና ማመን፣ በሐሰት መናገር፣ ከእምነት ይልቅ በሚታየውና በሚሰማው መታመንና በመሳሰሉት የተመሠረቱ ናቸው፡፡ በዚህም ላይ ተገቢ ያልሆኑ አባባሎችንና አገላለጾችን መጠቀም ከመገለጫዎቻቸው መካከል አንዱ ነው፡፡ በመናፍቃን ታሪክ መንትው ላይ ከግኖስቲኮች እስከ ማርቲን ሉተር ያሉ ስምንት ዋና ዋና መናፍቃንና ኑፋቄዎቻቸው በአጭሩ ተዳስሰዋል፡፡ ይህ የተደረገበት ምክንያትም በተሐድሶወች እምነትና ትምህርት የምናገኛቸው ብዙዎቹ ነገሮች በእነዚህና በመሰሎቻቸው መናፍቃን ፋቄዎች ውስጥ የምናገኛቸው በመሆኑ ምንጫቸው ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡

በክፍል አንድ ውስጥ ሦስት (3) ምዕራች አሉ፡፡ ይህ ክፍል የመዳን ትምህርትን (ነገረ ድኅነትን) በተመለከተ ያሉ ጉዳዮችን በስፋት የሚዳስስ ክፍል ነው፡፡ በምዕራፍ ሁለት ተሐድሶዎች ስለ መዳን የሚያስተምሩት ትምህርት፣ የመዳን ትምህርት በዘመናት ውስጥ የመጣበትን ሂደት በተመለከተ አጭር ታሪካዊ ዳሰሳ እና በእነዚህ ዙሪያ ያሉ ጉዳዮች ተዳስሰዋል፡፡ ምዕራፍ ሦስት ኦርቶዶክሳዊ የመዳን ትምህርት (ነገረ ድኅነት) ከመሠረቱ ጀምሮ ሰፋ ባለ ሁኔታ የቀረበበት ክፍል ነው፡፡በዚህ ምዕራፍ መዳን ለምን አስፈለገ?፣ ሰውን ሊያድነው የሚችለው ማን ነበር?፣ መዳን ማለት ምን ማለት ነው?፣ መዳን (ድኅነት) - የእግዚአብሔር ስጦታ ነው ወይስ የሰው የሥራው ውጤት?፣ ለመዳን እያንዳንዱ ሰው ምን ማድረግ ያስፈልገዋል? የሚሉ መሠረታዊ ጉዳዮች ተዳስሰዋል፡፡

በእያንዳንዱ መሠረታዊ ጉዳይ ላይም ተሐድሶዎቹ የሚሉት ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ እና ከአበው ቀደምት ሊቃውንት ትምህርት አንጻር ተመዝኗል፡፡ ከዚያም አጠር ያለ ማጠቃለያ በእያዳንዱ መሠረታዊ ጉዳይ ላይ ተሰጥቷል፡፡ የዚህ ክፍል የመጨረሻ ምዕራፍ የሆነው ምዕራፍ አራት ስለ ጾም፣ ምጽዋት እና ቀኖና ያትታል፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይም መጀመሪያ ተሐድሶዎቹ የሚሉት ከዚያም መጽሐፍ ቅዱስና አበው ሊቃውንት የሚሉት ከቀረቡ በኋላ የተሐድሶዎች አስተምህሮ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከሊቃውንት ትምህርት ጋር የሚስማማ መሆን አለመሆኑ ተገልጧል፡፡

ክፍል ሁለት አምስተኛውን ምዕራፍ (5) የያዘ ሲሆን በዋናነት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መባሏን በተመለከተ ያሉ ጉዳዮችን የያዘ ክፍልና ምዕራፍ ነው፡፡ በአንድ በኩል ተሐድሶዎች በዚህ ጉዳይ ላይ የሚያነሡትን ተቃውሞ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስንና የአበው ሊቃውንትን ትምህርት የዳሰሰ ክፍል ነው፡፡

ክፍል ሦስት "በእንተ ቅዱሳን" የሚለውን ምዕራፍ ስድስትን (6) የያዘ ነው፡፡ በውስጡም ስለ ቅዱሳን መማርና ማስተማር ለምን እንዳስፈለገ፣ ቅዱሳን ከሞት በኋላ ስለሚኖራቸው ማወቅ/አለማወቅ ጉዳይ፣ የቅዱሳን አማላጅነትን በተመለከተ፣ ቤተ ክርስቲያንን በቅዱሳን ስም መሰየምና መጥራትን በተመለከተ፣ ስለ ቅዱሳን መጻፍ መቼ እንደ ተጀመረ የሚሉ ነጥቦችን መጀመሪያ ተሐድሶዎች የሚያቀርቧቸውን ተቃውሞዎችና አስተምህሯቸውን በማቅረብ በመቀጠል ደግሞ የእነርሱን አባባሎችና ትምህርቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ እና ከአበው ሊቃውንት ምህርት አንጻር ይመዝናል፡፡ በመጨረሻም አጠር ያለ ማጠቃለያ ይሰጣል፡፡

ክፍል አራት (4) ሰባተኛውን ምዕራፍ (7) የያዘ ሲሆን ምንኩስና እና ገዳማዊ ሕይወትን በተመለከተ ያሉ መሠረታዊ ጉዳዮችን የሚዳስስ ክፍል ነው፡፡ በመጀመሪያ በምንኩስናና በገዳማዊ ሕይወት ላይ ተቃዋሚዎች የሚያነሷቸው የተለያዩ ነገሮች ከተለያየ አቅጣጫ ተመዝነዋል፡፡ በመቀጠልም የምንኩስና እና የገዳማዊ ሕይወት ምንነት እና የገዳማዊ ሕይወት ታሪካዊ ሂደት በአጭሩ ተገልጸዋል፡፡ ምንኩስና እና ገዳማዊ ሕይወትን በተመለከተ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እና የቀደምት አበው ሊቃውንት ትምህርት ቀርቧል፡፡ በመጨረሻም የተሐድሶዎች ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስና በአበው ሊቃውንት ካለው ትምህርት ጋር ያለውን ሁኔታ በተመለከተ ማጠቃለያ ተሰጥቷል፡፡

ክፍል አምስት (5) ምዕራፍ ስምንትን (8) የያዘ ሲሆን ለሞቱ ክርስቲያኖች የሚደረግ ጸሎት (ጸሎተ ፍትሐት) እና ተዝካርና ዝክር ለሞቱ ወገኖች የሚደረግ ጸሎት (ጸሎተ ፍትሐት) እና ተዝካርና ዝክርን በተመለከተ የሚነሡ ጉዳዮችን የሚመለከት ክፍልና ምዕራፍ ነው፡፡ በመጀመሪያ በጸሎተ ፍትሐት እና በዝክርና በተዝካር ላይ ተሐድሶዎች የሚያስተምሩት ትምህርትና የሚያነሡት ተቃውሞ፣ በመቀጠልም በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ እና የአበው ቀደምት ትምህርቶች ቀርበዋል፡፡ በመጨረሻም ይህ ክፍል በማጠቃለይ ይፈጽማል፡፡

የመጨረሻው ክፍል - ክፍል ስድስት (6) ልዩ ልዩ ጉዳዮችን የያዘ ሲሆን በውስጡም ሁለት ምዕራፎች አሉ፡፡ ምዕራፍ ዘጠኝ (9) - ቅዱሳት መካናትን መሳለምን በተመለከተ ሲሆን ምዕራፍ አሥር ደግሞ በዓላትን በተመለከተ ነው፡፡ ምዕራፍ ዘጠኝ መሳለምን በተመለከተ የተሐድሶዎች ትምህርት ከቀረበ በኋላ በዚህ ጉዳይ ላይ ያለው መጽሐፍ ቅዱሳዊና የአበው ሊቃውንት ትምህርት ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ አሥር (10) ደግሞ በዓላትን በተመለከተ የተሐድሶዎች ትምህርት፣ በመቀጠልም በዓላት ለምን እንዳስፈለጉና እንደ ተሠሩ እና በእነዚህና በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ እና የአበው ቀደምት ትምህርት ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ ዘጠኝ እና አሥር በመጨረሻ አጠር ያለ ማጠቃለያ በመስጠት ይደመድማሉ፡፡ ከሁሉም ፍጻሜ በኋላም መጽሐፉ የመጨረሻ ማጠቃለያ በማቅረብ ይፈጽማል፡፡

## የመጽሐፉ አጠቃላይ አካሄድ

ይኸ መጽሐፍ እያንዳንዱን መሠረታዊ ጉዳይ መጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ መሠረት የተሐድሶዎችን አስተምህሮ ይመዝናል፣ ከዚያም እውነተኛውን ትምህርት ይገልጣል፡፡ በመቀጠልም በቀደምት ሊቃውንት አባቶች ትምህርት መሠረት እንደዚሁ ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም በአጭር ማጠቃለያ ይደመድማል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመቀጠል የቀደሙ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ትምህርቶች በየጉዳዮቹ ለምስክርነት የምንጠቅስባቸው ምክንያቶች ብዙዎች ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1) ተሐድሶዎች ራሳቸውን ሲጠሩ "የቀደሙ ሊቃውንት ልጆች ነን"፣ እንዲሁም "የጥንታውያን ሊቃውንት ትምህርት ተከታዮች ነን" እያሉ ስለሚጠሩና እንደዚያ እንደ ሆኑ ለማስመሰል ስለሚሞክሩ በእርግጥ ትምህርታቸው እነርሱ እንደሚሉት በቀደሙት አባቶች ትምህርት የሚደገፍና ከእነዚያ ያልወጣ ነው? ወይስ ተቃራኒ ነው? የሚለውን ለማሳየትና የለበሱትን የማታለያ የበግ ለምድ መግፈፍ አስፈላጊ በመሆኑ፣ ለዚህ ደግሞ ተሐድሶዎች ባሳተሟቸውና ባሰራጯቸው በመጻሕፍቶቻቸው ያሉትን ይፋዊ ትምህርቶቻቸውን እነርሱም ከጠቀሷቸውደምት አባቶች ስተምህሮ ጋር ማስተያየትና ማነጻጸር ተገቢ በመሆኑ፣

2) እነዚህን ቀደምት ኦርቶዶክሳውያን ቅዱሳን አባቶቻችንን ተሐድሶዎቹም የእነርሱን ኑፋቄና ክህደት የሚደግፉ አስመስለው ስላቀረቧቸው እውነቱ የትኛው እንደ ሆነ በግልጥ እንዲታወቅ ለማድረግ የአባቶቻችንን እውነተኛ ትምህርት ማየት አስፈላጊ በመሆኑ፣

3) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያሉ አስተምህሮዎችንና ትውፊቶችን በጥንት በቀደሙ ሊቃውንት አባቶች ዘመን እንዳልነበሩና በኋላ ዘመን ሲፈልጉ በኢትዮጵያ ብቻ የተጀመሩ፣ ሲፈልጉ ደግሞ በ15ኛው መቶ ክ/ዘ በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ የተፈጠሩና በግድ የተጫኑ ነገሮች እንደ ሆኑ አስመስለው ስለሚያቀርቧቸው እነዚህ ነገሮች እነርሱ (መናፍቃኑ) እንደሚሉት ናቸውን? ወይስ ከጥንት ከነበሩት ከቅዱሳን ሊቃውንት አባቶች ዘመንም የነበሩ ትምህርቶችና ይትበሃሎች ናቸው? የሚለውን እውነት ለማሳየት፣ እና

4) በክርስቶስ የተሰጠውንና በቅዱሳን ሐዋርያት የተሰበከውን የክርስትና ትምህርት የምንረዳበትንና የምንገነዘብበትን ድባብና መሠረት እሳቤ በተግባር የምናየው ከሐዋርያት ጀምሮ በየዘመናቱ እየተነሡ ባስተማሩት በቀደምት ሊቃውንት አባቶች ትምህርት በመሆኑ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን የእምነቷ መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው፡፡ የቅዱሳት መጻሕፍትን አተረጓጎማቸውን የምንረዳበት መንፈስና መንገድ ግን እያንዳንዱ ሰው ለራሱ በመሰለውና ደስ ባለው መንገድ ሳይሆን ከቅዱሳን ሐዋርያት ጀምሮ የተነሡ አባቶች በተረጎሙበትና በተረዱበት መንገድ ብቻ ነው፡፡ ከጥንት ጀምሮ "ቅዱሳት መጻሕፍት እና አባቶች"[6] ተብለው አብረው ተጣምረው ይጠቀሱ የነበረው ከዚህ የተነሣ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በየዘመናቱ ተጠብቆ ለመዝለቁ ምስክሮቹም የቅዱሳን አባቶች ትምህርትና ሕይወት ናቸው፡፡ በነገረ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ የእነዚህ ቀደምት አበው ምስክርነት አስፈላጊ የሚሆነው የቤተ ክርስቲያን እምነት ሳይለወጥና ሳይፋለስ መኖሩን የምናገኘው ከቀደሙት አበው በመሆኑም ነው፡፡

ተሐድሶዎች የእነርሱ ኑፋቄ ደጋፊዎች እንደ ሆኑ አስመስለው ካቀረቧቸውና ከጠቀሷቸው ታላላቅ ቀደምት አባቶች መካከልም የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡-

- ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ (ጮራ ቁ. 9 ገጽ 7፣ ጮራ ቁ. 16 ገጽ 2፣ ጮራ ቁ. 9 ገጽ 8)
- ቅዱስ አቡሊዲስ ሊቀ ጳጳሳት ዘሮሜ (ጮራ ቁ. 32፣ ገጽ 6)
- ቅዱስ ዲዮናስዮስ፣ (መቅደስ የገቡ መናፍቃን ገጽ 151)
- ቅዱስ አትናቴዎስ፣ (መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ ገጽ 122)
- ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ - (ጮራ ቁ. 31.፣ ገጽ 18)
- ቅዱስ ኤጲፋንዮስን - (መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ ገጽ 49፣ 121. 151)
- ቅዱስ ቄርሎስ፣ (መቅደስ የገቡ መናፍቃን ገጽ 64፣ 121)
- ቅዱስ ያሬድ - (ጮራ ቁ. 6፣ ገጽ 20፤ ዋኖተ ብርሃን፣ መጋቢት 2002፣ ገጽ 7፣ ጮራ ቁ. 12 ገጽ 7፣ ጮራ ቁ. 13 የውጭ ሽፋን ላይ)

ከቅዱስ ያሬድ ከጠቀሷቸው መካከል ለአብነት የተወሰኑትን እንመልከት፡-

> "ፍሬምናጦስ ስለ መሠረታት ማኅበር ስያሜ ምንነት የሚያወሱትን ከፍሬምናጦስ ዘመን በኋላ ሁለት መቶ ዓመታት ያህል ቆይቶ በዜማ የተደረሱትን የያሬድ ድርሰቶችን ብሩሃን ገጾች የዓይናችንን መጋረጃ አስወግደን እስኪ እንያቸው፡-
>
> 1. "አንቲ ተሐንጸት በስሙ፣ ወተቀደሰት በደሙ ወተዐትበት በዕፀ መስቀሉ ጽዮን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መዓዛሆሙ ለቅዱሳን ጽርሕ ንጽሕት አማኅዚት አንቲ የዓውዱ ሰብሐት"
> 2. "በደሙ ቤዘዋ ወበማይ ዘውኅዘ እምዝብሁ አጥመቃ በዕፀ መስቀሉ ዐተባ . . ."
> 3. "ይቤላ ልዑል ለቅድስት ጽዮን አንስ በደምየ ከበር ቀደስኩኪ . . ."
>
> (ጮራ ቁ. 6፣ ገጽ 20)

6 (*kerygma* and *exegesis* — *hê graphê kai hoi pateres*- the Scriptures and the Fathers)

ትርጓሜ ቅዳሴ ማርያምን - (ጮራ ቁ. 7፣ ገጽ 8)

"ሊቀ ጳጳሳት ዘዲበ ሀገረ አበዊነ . . . " የሚለውን ንዑዳን አባቶች ሲተረጉሙት . . . ይሉና "ርእስ ማለት አክሱም፣ ሀገር ማለት መላዋ ኢትዮጵያ" በማለት "ትርጓሜ ቅዳሴ ማርያም ይመልከቱ" ከሚል ምሬት ጋር ማብራሪያ ይሰጡበታል፡፡ (ጮራ ቁ. 7፣ ገጽ 8)

- ቅዳሴ ሐዋርያትን - (ጮራ ቁ. 8፣ ገጽ 30)
- ገድለ ሰማዕታትን - (ጮራ ቁ. 12 ገጽ 24)
- ትምህርተ ኅቡዓትን - (ጮራ ቁ. 6፣ የውጭ ሽፋን ላይ)
  "አኮ ከመ ይትረአይ አላ ከመ ይትኀለይ ውእቱ ዝንቱ መስቀል" [ምንጩን ባይናገሩትም ቃሉ የተወሰደው ግን ትምህርተ ኅቡዓት ከተባለው የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ነው፡፡]
- ሌሎች አበውን በጥቅሉ ሲጠቅሱ - " . . . ይህም ሁሉ ሆኖ ከእግዚአብሔር ቃልና ከቅዱሳን አበው የሕይወት ታሪክ እንደምንረዳው . . ." (ጮራ ቁ. 16፣ ገጽ 28)
- ገድለ ሰማዕታትን፣

ከዚህም በተጨማሪ መልካ መልኮችንም ጠቅሰዋል፡፡ ለምሳሌም መልክዐ ኢየሱስን - ለኀንብርትከን (ጮራ ቁ. 8፣ ገጽ 16)፣ መልክዐ ሥላሴን (ኆኅተ ብርሃን፣ መጋቢት 2002፣ ገጽ 20)፣ መልክዐ ማርያምን (ጮራ ቁ. 26፣ ገጽ 12 ሰላም ለዝክረ ስምኪ ዘመንክር ጣዕሙን ከመልክዐ ማርያም ያለ መስሏቸው ነው) ጠቃቅሰዋል፡፡

ከዚህም በላይ ደግሞ የደረሱባቸውን ያህል የመንደር ወጎችንና ተረቶችንም ሳይቀር ጠቅሰዋል፡፡

እንግዲህ እነዚህ ሁሉ ለኑፋቄያቸውና ለእነርሱ አስተሳሰብ ድጋፍ ያገኙ መስሏቸው ከመካከል መዝዘው በማውጣት ይረዱናል ብለው የጠቀሷቸው ናቸው፡፡

የሚገርመው ነገር ግን እነርሱ ሲያመቻቸው እንደዚህ የጠቀሷቸውን የአባቶችን ትርጓሜያትና ትምህርቶች፣ ገድላትን፣ መልካ መልኮችንና ሌሎችንም አዋልድ መጻሕፍት እንደ ገና መልሰው እንዲህ ሲሉ ጥላሸት ይቀቧቸዋል፡- "የሀገራችን አዋልድ መጻሕፍት በተለይ ከ15ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ እንደ አሸን እየፈሉ፣ መናፍስትን የሚያሞጋግሱ፣ ሰው ለመዳን (ለመጽደቅ) ቢፈልግ ይድንበት ዘንድ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ሳያምንና ሳይጠመቅ በእነዚህ መናፍስት አማካይነት ሊድን እንደሚችል አዋልድ መጻሕፍቱ ያስተምራሉ፡፡" (ጮራ ቁ. 20፣ ገጽ 11-12) በመቀጠልም "አዋልድ የሚለው ስም ተአምራት፣ ገድላት፣ ድርሳናት፣ መልክአት እየተባሉ በቅዱሳን ስም ለተሰየሙ መናፍስት የተደረሱና [ለመናፍስት] መሳቢያዎች (ምስሃባት) ለሆኑ መጻሕፍት የተሰጠ ስያሜ ሆኗል" ይላሉ፡፡ (ጮራ ቁ. 25፣ ገጽ 9) እንግዲህ ይህ "ሳይፈጅኝ በእጄ፣ ሲፈጀኝ በማንኪያዬ" ዓይነት አካሄዳቸው በየቦታው የሚጠቀሙበት ቋሚ ስልታቸው ነው፡፡

ከመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ከቀደምት አበው መጥቀስ ብቻውን የትክክለኛነት መለኪያ አለመሆኑ ግልጽ ነው፤ ሰይጣንም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅሶ የቃሉን ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስን ሊፈትነው እስኪሞክር ድረስ ደፍሯልና፡፡ ማቴ. 4፡6 የሰይጣን የግብረ አበሮቹ ዋና መገለጫ ጥቅሶችን አለ ቦታቸውና አለ አገባባቸው በመጥቀስ ትክክለኛ ሃሳባቸውን ለሰዎች እዛብቶና አበላሽቶ ማቅረብና ማሳሳት ነው፡፡ አንድ ይህን ሁኔታ የታዘበ ሰው "የመናፍቃን አእምሮ ለቅዱሳት መጻሕፍት የተበላሸ ወይም ያልሆነ መልክ እንዲፈጥርና እንዲያሳይ እንደሚያደርግ እንደ ተበላሸና እንደ ዛገ መጥፎ መስተዋት ነው"[7] ያለው ለዚህ ነበር፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም የእግዚአብሔር ቃል እንዲሁ እያንዳንዱ እንዳሻውና እንዳገኘ የሚቀርበው ሳይሆን ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው መሆኑን ሲናገር "ሰው በጨለማ ስፍራ ለሚበራ መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ፡፡ ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም" በማለት በመንፈስ ቅዱስ ያስጠነቅቀናል፡፡ 2 ጴጥ. 1፥19-20

[7] "The minds of the heresiarchs were to Scripture as bad mirrors, reflecting distorted images."

መጻሕፍትን ለራሳቸው የጥፋት ትምህርት ደጋፊ ለማድረግ ሲሉ የሚጠመዝዙና የሚያጣምሙ ስለ መኖራቸውም "በእነዚያ ዘንድ ለማስተዋል የሚያስቸግር ነገር አለ፤ ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ሌሎችን መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ" በማለት ገና ከጥንት አስቀድሞ ተነግሮናል፡፡ 2 ጴጥ. 3፥16

በመሆኑም የዚህ መጽሐፍ ዋና ዓላማ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሐዋርያዊ የሆነው አስተምህሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ወይስ የተሐድሶዎቹ? መሆኑ ጥርት ብሎ እንዲታወቅ ለማድረግ ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተሐድሶዎች ራሳቸውን "የጥንቱ ኦርቶዶክስ ነን" በሚል ሹምብል የደበቁት ማንነታቸውና አስተምህሯቸው ፕሮቴስታንታዊ እንጂ ኦርቶዶክሳዊ አለመሆኑ ፍንትው ብሎ እንዲታይ ለማድረግ ነው፡፡ ፕሮቴስታንቶች እስከ ሆኑ ድረስ ደግሞ ራሳቸውን በይፋ ፕሮቴስታንት መሆናቸውን መግለጽ እንጂ ግብሩን ወድደው ስሙን ጠልተው አይሆንምና፤ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ደግሞ ስሟን ወድደው እምነቷን ጠልተው አይሆንምና ሚናቸውን እንዲለዩ፤ ከዚህ በላይ ደግሞ ሌላው በሚገባ ውስጠ ምንነታቸውን ጥርት አድርጎ እንዲያውቃቸው ለማድረግ ነው፡፡

በዚህም መሄድ ያለባቸው ወደሚመስላቸው የእምነት ቡድን እንጂ በሃይማኖት ከማይመስሏት ከኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንዳችም ነገር የሌላቸው መሆኑ ይገለጥ ዘንድ ነው፡፡

ይህም በእኛ ኃይል ሳይሆን የቃሉ ባለቤት በሆነው በራሱ በእግዚአብሔር ኃይል ይፈጸማል፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ በክርክር ፈሊጥና በእውቀቱ ይመካ ለነበረው ዩኖሚየስ ለተባለው አርዮሳዊ ለጻፈው መጽሐፍ የመልስ መጽሐፍ ሲጽፍ መግቢያው ላይ "ጠንካራ ለሆነ ሰውነት የአካል ክፍል የሆነች በጣም ትንሽ አካል ከመላው ሕይወት ጋር ካላት አንድነት የተነሣ ተቆርጦ ከወደቀና ከተለየ፣ ከዚህም የተነሣ ብቻውን ከሆነ ከትልቅ አካል ይልቅ የበረታችና ኃያል ናት፤ ምክንያቱም ሕይወቷ ጠንካራና ሕያው ከሆነው ሰውነት ጋር የተዋሐደና ኅብረት ያላት በመሆኑ ነው" በማለት እንደ ገለጸው ነው፡፡[8]

የተሐድሶዎች አስተምህሮ ብለን የወሰድነው በዚሁ ዓላማ መሰማራታቸውን ከጻፏቸው መጻሕፍትና የተለያዩ መጣጥፎች ርእስ ጀምሮ በይዘቱ የገለጹባቸውን መጻሕፍት ነው፡፡ በአጠቃላይ ራሳቸውን በይፋ ፕሮቴስታንት ነን ሳይሉ፣ ወይም የሌላ የእምነት ስም ለራሳቸው ሳይሰጡ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ውስጥ ያሉ መስለው፣ ነገር ግን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ዒላማቸው አድርገው በተጻፉ መጻሕፍት ውስጥ ያሉት የተሐድሶዎች አስተምህሮዎች ሆነው ተወስደዋል፡፡

## የተሐድሶዎችን አስተምህሮ የወሰድንባቸውና መልስ የተሰጠባቸው የእነርሱ መጻሕፍትና መጽሔቶች

1. "ሖሩ" መጽሔት - ከቁጥር 1 እስከ 41
2. "መጥቅዕ" መጽሔት
3. "የተቀበረ መክሊት"
4. "በውኑ በማርያም ማመን ይገባሃልን?"
5. "ጦማረ ጽድቅ"
6. "መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት"
7. "የለውጥ ያለህ!!!"
8. "መሠረታዊ የክርስትና እምነት መግቢያ"
9. "ትምህርተ ድኅነት"
10. "ኖኅተ ብርሃን"
11. "መቅደስ የገቡ መናፍቃን"
12. "ስምዓ ጽድቅ ብሔራዊ"

---

[8] "The very smallest member of a vigorous body would, by virtue of the unity of its life with the whole, be found stronger than one that had been cut away and was dying, however large the latter and small the former."

# “ጮራ” መጽሔት እና “ስምዓ ጽድቅ ብሒራዊ” መጽሐፍ

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በትምህርትም የበሰሉ የሚባሉ ሰዎች እንኳ ሳይቀር ቤተ ክርስቲያን ከምታምነውና ከምታስተምረው ትምህርት ውጪ የሆነና በፍልስፍና የተበረዘ ትምህርት ሲያስተምሩ እየተገኙ ተመክረው ባለመመለሳቸው ከቤተ ክርስቲያን አንድነት እንዲወጡ መደረጋቸው ይታወቃል። ለአብነትም እነ አርዮስንና እነ አቡሊናርዮስን ማስታወስ ይቻላል፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ተመሳሳይ ታሪኮች በየዘመናቱ ተከስተዋል፡፡ ሆኖም ግን ብዙዎቹ የስሁተት ትምህርታቸው ሲገለጥ በይፋ ወጥተው የሚከራከሩ፣ እምነታቸውንም ሳይሸሽጉ ገልጸው ወይ እምነው በቀኖና የሚመለሱ፣ አለዚያም በይፋ ተወግዘው ከቤተ ክርስቲያን አንድነት የሚለዩ ነበሩ፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በአለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ ጠንሳሽነት እና “ማኅበረ በኵር” በሚል ስም ለዓላማው ማሳኪያ ብሎ ባቋቋመው ድርጅት ዋና አስተባባሪነት የሚካሄደው “የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን እናድሳት” ዘመቻ ራስን ሰውሮ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ እርሷ የማትቀበለውን እምነትና ትምህርት ማስፋፋት አንዱና ዋነኛ ተልእኳቸው ሆኗል፡፡ እነዚህ ሰዎች ከአለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ ጀምሮ የእርሱ ተልእኮ አስፈጻሚዎች የሆኑት እምነታቸውና አስተምህሯቸው ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተለየ፣ ፕሮቴስታንታዊ ሆኖ ሳለ እነርሱ ግን የቤተ ክርስቲያኒቱን ምእመናንና አባቶች ለማሳሳትና በጥፋት ተልእኳቸው ውስጥ ለማስገባት ይመቻቸው ዘንድ “ኦርቶዶክሳውያን ነን” እያሉ ያልሆኑትን መስለው ለመታየትና ያሰቡትን ከዳር ለማድረስ ከፉ ሠራተኞች ሆነው እየሠሩ ይገኛሉ፡፡

መሠረት አባቱ የቤተ ክርስቲያናችን መምህርና የርዕሰ አድባራት ወገዳግት አኵሱም ጽዮን አገልጋይ እንደ ነበር የሚነገር ቢሆንም እርሱ ግን ለትምህርት በተለያየ ቦታ በተዘዋወረበት ወቅት የኢትዮጵያን የክርስትና ትምህርት በፕሮቴስታታዊ ትምህርት ለመለወጥ አልመው ወደ ሀገራችን ከመጡት የአውሮፓ የፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን ከነ ዳቪድ ስቶክስ (የሠራዊተ ክርስቶስ ማኅበር መሥራች) እና ከመሳሰሉት ሚሲዮናውያን ጋር “የስብከት ዘዴ ለመማር” በሚል ሰበብ ተወዳጀ፡፡ ቀስ በቀስም የሚሲዮናውኑን ፍልስፍናና አስተምህሮ ተቀብሎ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ለመለወጥ ብዙ ደከሟል፤ - ባይሳካለትም፡፡

ደበላ ቢሪ በተባለ[9] ሰው አባባል “የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሉተር” የሚል ቅጽል የተሰጠው ይህ ሰው የስህተት (የተሐድሶ) ትምህርቱን በ1950ዎቹ ጀምሮ በተለያዩ ቦታዎች (በሸዋ፣ በጎንደር፣ በጎጃም) ለማስፋፋት ሞክሮ የተለየ እምነትና አስተምህሮ ያለው መሆኑ እየታወቀበት ከሁሉም የተባረረ ሲሆን በኋላም በእነ ሚስተር ዳቪድ ስቶክስ ጠቋሚነትና ስለ “ዘመናዊ አስተሳሰቡ” በሰጡት ምስክርነት የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ሴሚናሪ ሲጀመር እንዲገባ ተፈልጎ ከፍተኛ ትምህርት ቤቱ ከተከፈተ ከሁለት ዓመታት በኋላ ለስብከት ከሄደበት ቦታ ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ ወደ ሴሚናሪው ገብቶ ነበር፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ትምህርት ቤትም ያው የተለመደውን ፕሮቴስታንታዊ የሆነውን የሚሲዮናውያኑን ትምህርት ማስፋፋት ሲሞክር ተደርሶበት ከዚያም በቅዱስ ፓትርያርኩ ትእዛዝ ተባርሮ ወጥቷል፡፡ በመቀጠልም ወዳስተማሩትና በእምነት ወደሚመስሉት ወደ ሚሲዮናውያን ዘንድ በመጠጋት በመካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ቦታዎች፣ በተለይም እነርሱ በኋላ በአዲስ አበባ ባቋቋሙት ሴሚናሪ እስከ ኅልፈተ ሕይወቱ ድረስ ሲያገለግል ቆይቷል፡፡

አለቃ መሠረት የተለያዩ መጻሕፍትን እንደ መረመረና የአሁኗ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነት የተሳሳተ መሆኑን “ደረሰበት” ተብሎ በታሪኩ ላይ ተገልጿል፡፡

[9] Debela Birri (Dr.) Divine Plan Unfolding, The Story of Ethiopian Evangelical Church Bethel, Lutheran University Press, 2014.

በኚህ ሰው አገላለጽ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ለኢትዮጵያ የተሰበከው ክርስትና በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የተመሠረተ ቢሆንም በኋላ ዘመን በተለይም በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ አማካኝነት የተጨመሩ የሚላቸው "የቅዱሳን አማላጅነትና የመንፈሳዊ ተጋድሎ በተመለከተ ያሉ አስተምህሮዎች፣ የቅዱሳንን ገድልና ትሩፋት መማርና ማወቅ ወዘተ" በመጨመራቸው ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ ማንነቷ ተቀይሯል፤ አንድ ጊዜ በመልዕልተ መስቀል የተፈጸመውን የሰው ልጅ ድኅነት ዘንግተው ዛሬም ኃጢአት ያለ ይመስል ቅዳሴ በመቀደስ እንደ አሪቱ መሥዋዕት ይሠዋሉ፤ በክርስቶስ የማዳኑ ሥራ ማመንና መጽደቅ ሲበቃ ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት፣ የመሳሰሉትን መንፈሳዊ ተጋድሎ መጋደል ለሰው ልጅ የጽድቅ ጎዳና ይጠቅማል የሚሉ አዳዲስ ትምህርቶች በመጨመራቸው ቤተ ክርስቲያን መታደስና መለወጥ አለባት ብሎ ያምን እንደ ነበር የእርሱን ታሪክ የሚያወሱ የተለያዩ ጽሑፎች ይገልጻሉ፡፡[10]

መሠረት በ1951 ዓ.ም. በታተመው እና "ስምዓ ጽድቅ ብሔራዊ፣ በጥንታውያን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መምህራን ፍለጋ" በተሰኘው መጽሐፉ[11] መቅድም ላይ "ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ያነሣሣኝ ምክንያት ነጻነት ያገኘችው ቤተ ክርስቲያናችን ቀዋሚውን ሃይማኖት ሳይሆን ያለ ሃሳብ የገባውን ልማድ እንድታሻሽልና ጥንታዊውን የሃይማኖት መሠረት ግልጽ አድርጋ በማስተማር እንድትታደስ ነው" (ገጽ 9) በማለት በገለጸው መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ለማደስ እና እርሱ እንደሚለው ትምህርቷን ወደ ጥንታውያኑ መምህራን አስተምህሮ ለመመለስ ብቻውን ጥቂት ሰዎችን በድብቅ እያስተማረ ከመሄድ አልፎ ከሌሎች ቤተ እምነቶች ጋር መተባበርና የጋራ ማንባር መፍጠር እንደሚገባ በማመኑ ከተለያዩ የፕሮቴስታንት ድርጅቶች ጋር ለዚሁ ዓላማው የሚረዳ ኅብረት መፍጠር ችሏል[12]፡፡

ለዓላማቸው ማስፈጸሚያም ከወዳጆቹ ጋር በመሆን "ማኅበረ በኵር" የተሰኘ ማኅበር አቋቋመ፡፡ የማኅበሩ ዓላማም በግልጽ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞችን ከቤተ ክርስቲያናቸው ሳይወጡ ባሉበት ሆነው እምነታቸውን እንዲለውጡ በማስተማር በመጨረሻም ቤተ ክርስቲያኒቱን በእነርሱ ዓይነት ፕሮቴስታንታዊ ትምህርት ማደስ ነው፡፡ ትምህርታቸውን ለሚፈልጓቸው አካላት ለማዳረስም ከሌሎች የእምነት ድርጅቶችና ከልዩ ልዩ አካላት በሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ በመታገዝ "ጮራ" የሚባል መጽሔት በቋሚነት በማዘጋጀት በነጻ ያድላሉ፡፡ ጮራ መጽሔት የዚህ ማኅበር ዋነኛ ዓላማ ማስፈጸሚያ ሆኖ አሁንም ድረስ እያገለገለ የሚገኝ ሲሆን ከተጀመረ ጊዜ አንሥቶ እስከ 13ኛው ቀጥር (እስከ ሞተበት ዓመት) ድረስ መሠረት "የእምነት መሠረት" የሚለውን ጽሑፉን በተከታታይ ያሰራጭባት እንደ ነበር ይታወቃል፡፡

በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡት ጽሑፎች ከሌሎቹ የፕሮቴስታንት መጽሔቶች የሚለዩበት ዓይነተኛው ምክንያት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታውያን መጻሕፍት ውስጥ ለነርሱ የሚስማማ የመሰላቸውን ሃሳብ በግእዝ እየጠቀሱ የሚጽፉና ስለ እምነታቸውም ሲገልጹ አሳሳች በሆነ መንገድ "የእኛ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን" እያሉና ማሩን ከመርዙ እየቀላቀሉ ስለሆነ ዓላማቸውን ላልተረዱ አንባብያን ሊያሳስት ይችላል፡፡ በጮራ መጽሔት የውጭ ሽፋኖች ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጽሔት ለማስመሰልና ለማሳሳት ይረዳቸው ዘንድ የጌታችንን፣ የእመቤታችንና የመሳሰሉትን ቅዱሳት ሥዕላት ይጠቀማሉ፡፡

---

[10] Dirshaye Menberu, - Meseret Sebhat Leab (Aleqa), 1926 - 1996, Mekane Yesus Church Ethiopia. "*Dictionary of African Christian Biography*". Available at: www.dacb.org/stories/ethiopia/meseret_.html.

[11] ይኸው መጽሐፍ፡ የፕሮቴስታንታዊ ትምህርት በማስፋፋት ጠቃሚ ሆኖ በመገኘቱ በ1992 በመካነ የሱስ ሴሚናሪ በድጋሚ ታትሟል።

[12] Loren Bliese, Mehretab Bekele, and Walda Estifanos, 2013, "Aleqa Meseret Sebhat Leab: A biography", *in a book titled "Cataloge of the Ethiopic Manuscript Imaging Project (EMIP)" Vol. 7, Codices 601-654. The Meserete Sebahat Le-ab Collection of Mekane Yesus Seminary*, by Kesis Melaku Terefe, Steve Demarter, Jeremy Brown (Editors), Addis Ababa.

በመሆኑም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በሎሬ መጽሔት የተጠቀሱትን ሃሳቦች እንዳለ በመጥቀስ በየክፍሉ መልስ ለመስጠት ሞክሬያለሁ፡፡ መጽሔቱን ደጋግሜ የጠቀስኩበት ዋነኛው ምክንያትም ከላይ የገለጽኩት ምክንያት ሲሆን የብዙዎቹ የተሐድሶ መናፍቃን መጻሕፍትም ከዚሁ መንፈስ የተቀዱ በመሆናቸው የተሐድሶ አራማጆች ዋነኛ የትምህርታቸው ምንጭ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

## ለምስክርነት የምንጠቅሳቸው አባቶች

በየርእሱ የሚነሡትን ጉዳዮች በተመለከተ መጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ ያለውን እውነተኛ ትምህርት እናሳያለን፡፡ በመቀጠልም እነዚያኑ ርእሰ ጉዳዮች በተመለከተ ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ያስተማሩትን ትምህርት እንመለከታለን፡፡ በእነዚህ በሁለቱ፣ ማለትም በመጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በመቀጠልም በቀደምት ኦርቶዶክሳውያን አባቶች ትምህርት መሠረት የተሐድሶዎች ትምህርት ይመዘናል ማለት ነው፡፡ በዚህም የተሐድሶዎች ትምህርት እነርሱ እንደሚሉት ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ትምህርት ጋር የሚስማማ መሆን አለመሆኑ ይመዘናል፡፡ ለመሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት የምንጠቅሳቸው አባቶች እስከ ስድስተኛው (6ኛው) መቶ ዓመት ማብቂያ ድረስ የነበሩትን ታላላቅ ኦርቶዶክሳውያን አባቶች ብቻ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት ተሐድሶዎች በአንድ በኩል ዛሬ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያለውን ትምህርትና እምነት በኋላ ዘመን የመጣና ኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠረ የኑፋቄ ትምህርት እንደ ሆነ አስመስለው ስለሚያቀርቡ ይህ ስህተታቸው እንዲታወቅ ነው፡፡ እንደዚሁም እነዚህን አባቶች እነርሱም የራሳቸውን ኑፋቄዎች የሚደግፉ አስመስለው ምስክር አድርገው የጠቀሷቸው ስለሆነና የእነርሱ ልጆች ነን ስለሚሉ በዋናነት እነዚህን ብቻ መጥቀሳችን እነርሱም የጠቀሷቸውን እነዚህን ቀደምት አበው እንቀበልም ለማለት የሚችሉበት አንዳችም ምክንያት እንዳይኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡

ለታሪካዊ ነገሮች የምንጠቅሳቸው ደግሞ ከእነዚህ አባቶች በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ጽፈው ያቆዩልንና ለዚህም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከጥንት ጀምሮ እውቅና ያላቸውን አውሳብዮስ ዘቂሳርያን፣ ስኮላስቲኩስ ሶቅራጥስን፣ ሄርሚያስ ሶዞሚኑስን እና ሩፊኖስን ሲሆን ለአንዳንድ ታሪካዊ ጉዳዮች የሰሜን አፍሪቃ ሊቅ የነበረውን ጠርጠሉስን ጠቅሰናቸዋል፡፡

### ለመሠረታዊ ትምህርተ ሃይማኖት በዋናነት የተጠቀሱት አባቶች

| | | የነበረበት ዘመን |
|---|---|---|
| 1. | ቅዱስ አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ[13] | 50 – 117 ዓ. ም. (ግ.) |
| 2 | ቅዱስ ፖሊካርፐስ | (ግ.) 69 – 156 ዓ. ም. |
| 3 | ቅዱስ ሄሬኔዎስ[14] | (130 ወይም 142 – 202 ዓ. ም. (ግ.)[15] |
| 4. | ቅዱስ ቆጵርያኖስ[16] ሰማዕት | 200 –258 ዓ. ም. |
| 5. | ቅዱስ አቡሊዲስ | (ግ.) 170 – 236 ዓ. ም. |
| 6. | ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ | 298 – 373 ዓ. ም. |

[13] ቅዱስ አግናጥዮስ ከባልንጀራው ከቅዱስ ፖሊካርፐ ጋር የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ደቀ መዝሙር ነበር። የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን 3ኛው (ከጴጥሮስና ከኢቮዲዮስ ቀጥሎ) ጳጳስ ነበር።

[14] ቅዱስ ሄሬኔዎስ የቅዱስ ፖሊካርፐ ደቀ መዝሙር ነበር።

[15] (ግ.) ገደማ ማለት ሲሆን ይህም የተወለዱበት ዘመን በእርግጠኝነት የማይታወቀውን አባቶች መነሻ ዘመን ለማመልከት ነው። የአብዛኛዎቹ ቅዱሳን የልደት ዘመናቸው በእርግጠኝነት አይታወቅም። በእርግጠኝነት የሚታወቀው የዕረፍታቸው ጊዜ ነው። ይህ እስከ ቀኑ ሳይቀር በሚገባ ይታወቃል። ሆኖም ቅዱሳን ሲወለዱ ምን እንደሚሆኑ ከሚያውቃቸው ከፈጣሪያቸው በቀር ወላጆቻቸውም ሆኑ ኅብረተሰቡ በአብዛኛው ማንነታቸውን ስለማያውቅ የተወለዱበት ዘመን ተጽፎ አይገኝም። ከዚህም የተነሣ የተወለዱበትን ቀን ይህ ነው ለማለት የሚቻለው ከትምህርታቸው ውስጥ ያሉ አመልካች መረጃዎችንና ለዚሁ የሚረዱ ሌሎች ነገሮችንም በመጠቀም ነው። ዋናው ጉዳይም የቅዱሳን ሕይወታቸውና ትምህርታቸው ነው እንጂ የተወለዱበትም ሆነ ያረፉበት ቀኑ በትክክል ከመታወቅ አለመታወቁ ላይ አይደለም።

[16] (St. Cyprian of Carthage) ይህ ቆጵርያኖስ በስንክሳር መስከረም 21 ቀን ከቅድስት ዮስቴና ጋር ሰማዕትነትን ስለ መቀበሉ የተጻፈለት ሳይሆን ሌላ ቆጵርያኖስ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የምንጠቅሰው ቅዱስ ቆጵርያኖስ የሰሜን አፍሪካዋ የካርቴጅ ጳጳስ የነበረና በ258 ዓ. ም. ቫሊሪያኖስ በተባለው ቄሣር ሰማዕትነትን ተቀብሎ ያረፈ ነው። ከቅድስት ዮስቴና ጋር ሰማዕት የሆነው ቅዱስ ቆጵርያኖስ ግን አንጾኪያዊና በ304 ዓ. ም. በዲዮቅልጥያስ የመከራ ዘመን በሰማዕትነት ያረፈ ነው።

| | | የነበረበት ዘመን |
|---|---|---|
| 7. | ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም | 315 – 386 ዓ. ም |
| 8. | ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ | 330 - 379 ዓ. ም. |
| 9. | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ | 329 - 390 ዓ. ም. |
| 10 | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ | 330 - 395 ዓ. ም. |
| 11. | ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ | 347 – 407 ዓ. ም. |
| 12 | ቅዱስ ኤጲፋንዮስ | (ገ.) 315 – 403 ዓ. ም. |
| 13 | ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ | 376 – 444 ዓ. ም. |
| 14 | ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ | 459 - 538 ዓ. ም. |
| 15 | ቅዱስ ያሬድ | 505 - 571 ዓ. ም. |

በቤተ ክርስቲያናችን "ሃይማኖተ አበው" ተብሎ የሚታወቀው መጽሐፍ ቀደምት ኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን የሊቃውንትን ትምህርት በዋናነት በምሥጢረ ሥላሴ እና በምሥጢረ ሥጋዌ ላይ ያተኮሩ ትምህርቶቻቸውን ከግሪክ፣ ከሱርስትና ከዐረብኛ (ከላቲንና ከሌሎች ቋንቋዎችም በተወሰነ ደረጃ) ወደ ግእዝና ቅርብ ጊዜም ወደ አማርኛ ተርጉመው ያዘጋጁልን መጽሐፍ ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተረፈ ቄርሎስ፣ መጻሕፍተ መነኩሳት፣ ግብረ ሕማማት፣ ገድለ ቅዱሳን፣ ግእዝ በግእዝ የሆኑና ሌሎችም ትርጓሜያት፣ እና ሌሎችንም የተለያዩ የቀደምት አባቶች መጻሕፍትና ትምህርቶች ወደ ግእዝ ቋንቋ ተርጉመውልናል፡፡ ሆኖም አሁን ተሐድሶዎች ያነሷቸው ብዙዎቹ ጉዳዮች ከምሥጢረ ሥላሴና ከምሥጢረ ሥጋዌ ባሻገር ያሉ ሌሎች ብዙ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ስለሆኑና በእነዚህ ዙሪያ ያሉት የቀደምት ሊቃውንት አባቶቻችን ትምርቶች ደግሞ ብዙዎቹ በአገርኛ ቋንቋ ስላልተተረጐሙልን[17] የቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን ሊቃውንት ትምህርቶችን በየርእሰ ጉዳዩ ከጽርዕ (ከግሪክ ቋንቋ) እና ከሱርስት ወደ እንግሊዝኛ ከተተረጎሙበት መጻሕፍት ወደ አማርኛ ተተርጉመው ቀርበዋል፡፡

በዚህ ሂደትም በአንድ በኩል በዚያን ዘመን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ አልፈው የግሪክና የሱርስት፣ የዐረብኛና የላቲን፣ እንዲሁም ሌሎች ቋንቋዎችንም አጥንተው ወደ ግእዝና ወደ አማርኛ የተረጐሙልን የቀድሞ አባቶቻችን እውቀታቸውና ትምህርታቸው ምን ያህል ዓለም አቀፋዊና ሁለንተናዊ እንደ ነበር በግልጽ ያስረዳናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ የሚያግዙ ነገሮች ባሉበት በእኛ ዘመን ላይ ሆነን እንኳ የአባቶቻችንን ጥልቅ ትምህርት ወደ ሌላ ቋንቋ መተርጐም ቀርቶ በግእዝ ተርጉመው ያስቀመጡልንን መረዳትና መጠቀም እንኳ እንዲህ ቀላል አለመሆኑን ስንመለከት በዚያን ዘመን ሁኔታ ሆነው የተለያዩ የቀደምት አበው ትምህርቶችን የተረጐሙልንን የአባቶቻችንን ድካም በእጅጉ እንድናደንቅና ታላቅ አክብሮት እንድንሰጥ ያደርገናል፣ የውለታቸውም ታላቅነት አካል ነሥቶ ይታየናል፡፡ የቅዱሳን አባቶቻችንን መጻሕፍት ከጥንተ ቋንቋቸው ከግሪክና ከሱርስት ወደ እንግሊዝኛ በመተርጎም አንድ ደረጃ ወደ እኛ እንዲቀርቡ ያደረጓቸውን ሰዎችም ለድካማቸው እውቅና መስጠት ይገባናል፡፡

እነዚህ ወደ ግእዝና ወደ አማርኛ ያልተተረጎሙት የቀደምት አባቶቻችን ትምህርቶችና መጻሕፍት በአብዛኛው የተወሰዱት ወደ እንግሊዝኛ ከተተረጐሙበት መጻሕፍት ስለሆነ በእንግሊዝኛው ትርጉም የተገለጹበትን ስያሜ እና ወደ አማርኛ ሲመለሱ በዚህ መጽሐፍ ላይ የተሰጣቸውን ስያሜ ለአንባቢ ግንዛቤ ግልጽ ይሆን ዘንድ ከዚህ በታች ተመልክቷል፡፡

---

[17]ወይም ደግሞ ተተርጕመው፣ ነገር ግን መኖራቸውን ያላወቅናቸውና ያላገኘናቸው ሊሆኑ ይችላሉ።

| | ከግሪክ (የተወሰኑት ከላቲን) ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጎሙ የተሰጣቸው ርእስ | የጻፈው አባት | በዚህ መጽሐፍ ላይ የተሰጣቸው ርእስ |
|---|---|---|---|
| 1 | Contra Gentes (Against the Heathen) | ቅዱስ አትናቴዎስ | በእንተ አሕዛብ |
| 2 | On The Incarnation of the Word | ቅዱስ አትናቴዎስ | በእንተ ተሠግዎተ ቃል |
| 3 | Defence Against the Arians | ቅዱስ አትናቴዎስ | በእንተ አርዮሳውያን |
| 4 | Life of Antony (Vita Antoni) | ቅዱስ አትናቴዎስ | ገድለ እንጦንስ |
| 5 | Against the Arians (Orationes contra Arianos) | ቅዱስ አትናቴዎስ | ትምህርት በእንተ አርዮሳውያን |
| 6 | On the Holy Spirit | ቅዱስ ባስልዮስ | በእንተ መንፈስ ቅዱስ |
| 7 | The Hexæmeron | ቅዱስ ባስልዮስ | አክሲማሮስ[18] |
| 8 | The Letters | ቅዱስ ባስልዮስ | መልእክታት |
| 9 | Treatise Concerning the Christian Priesthood. | ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ | በእንተ ክህነት |
| 10 | Homilies on S. Ignatius and S. Babylas | ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ | በእንተ ቅዱስ አግናጥዮስ ወቅዱስ ባቢላስ |
| 11 | Homilies on the Statues | ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ | ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት |
| 12 | Homilies on the Acts of the Apostles and the Epistle to the Romans | ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ | ትርጓሜ ግብረ ሐዋርያት ወመልእክተ ሮሜ |
| 13 | Homilies on the Epistles of Paul to the Corinthians | ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ | ትርጓሜ መልእክተ ቆሮንቶስ |
| 14 | Homilies on Galatians, Ephesians, Philippians, Colossians, Thessalonians, Timothy, Titus, and Philemon | ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ | ትርጓሜ መልእክተ ገላትያ፣ ኤፌሶን፣ ፊልጵስዩስ፣ ቆላስይስ፣ ተሰሎንቄ፣ ጢሞቴዎስ፣ ቲቶ ወፊልሞና |
| 15 | Homilies on the Gospel of Saint Matthew | ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ | ትርጓሜ ወንጌል ማቴዎስ |
| 16 | On Repentance and Remission of Sins, and Concerning the Adversary | ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም | በእንተ ንስሐ ወሥርየተ ኃጢአት ወጸላኢ |
| 17 | On Baptism | ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም | በእንተ ጥምቀት |
| 18 | On the Ten Points of Doctrine | ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም | በእንተ እሠርቱ ነገራተ እምነት |
| 19 | On Faith | ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም | በእንተ እምነት |
| 20 | On the Clause, And Shall Come in Glory to Judge the Quick and the Dead; Of Whose Kingdom There Shall Be No End. | ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም | ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋን ወሙታነ . . . |
| 21 | On the Holy Ghost | ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም | በእንተ መንፈስ ቅዱስ |
| 22 | Concerning the Unity of God. On the Article, I Believe in One God. | ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም | ስለ እግዚአብሔር አንድነት |

[18] አክሲማሮስ - በዚህ ስም የሚታወቅ የቅዱስ ኤጲፋንዮስ መጽሐፍ በግእዝና በአማርኛ አለ። ሆኖም ግን አክሲማሮስ (ሄክሳሜሮን - Hexaemeron ማለት እግዚአብሔር ፍጥረታትን የፈጠረባቸው ስድስቱ ቀናትና በእነዚያ ቀናት የተፈጠሩትን ሥነ ፍጥረታት በተመለከተ የተጻፈ የሐተታ መጽሐፍን የሚመለከት ነው። በግሪክ (ሄክሳ ኤሜሮስ - hexa emeros — six days) ማለት ስድስት ቀናት ማለት ነው። የስድስቱን ቀን ሥነ ፍጥረት በተመለከተ የተጻፉና በዚህ ስም (አክሲማሮስ በሚል) የሚታወቁ የተለያዩ አባቶች ትምህርቶችን የያዙ መጻሕፍት አሉ። ከእነዚህም አንዱ ቅዱስ ባስልዮስ የጻፈው መጽሐፍ ነው።

| | ከግሪክ (የተወሰኑት ከላቲን) ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጎሙ የተሰጣቸው ርእስ | የጻፈው አባት | በዚህ መጽሐፍ ላይ የተሰጣቸው ርእስ |
|---|---|---|---|
| 23 | On the Words, And in One Holy Catholic Church, and in the Resurrection of the Flesh, and the Life Everlasting | ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም | በእንተ አሐቲ ቅድስት ኵላዊት ቤተ ክርስቲያን ወትንሣኤ ሥጋ ወሕይወት ዘለዓለማዊ |
| 24 | First Lecture on the Mysteries. Lecture 19 | ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም | በእንተ ምሥጢራት |
| 25 | On the Mysteries II: Of Baptism. Lecture 20 | ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም | በእንተ ጥምቀት |
| 26 | On the Mysteries. III: On Chrism. Lecture 21 | ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም | በእንተ ሜሮን |
| 27 | On the Mysteries. IV: On the Body and Blood of Christ. Lecture 22 | ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም | በእንተ ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ |
| 28 | On the Mysteries. V: On the Sacred Liturgy and Communion. Lecture 23 | ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም | በእንተ ቅዱስ ቁርባን ወነገረ ቅዳሴ |
| 29 | Panegyric on His Brother S. Cæsarius. | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት (ዘእንዚናንዙ) | ትምህርት በእንተ ዕረፍተ እኁሁ |
| 30 | Theological Orations | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት | ነገረ መለኮታዊ ትምህርቶች |
| 31 | On the Arrival of the Egyptians. | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት | በእንተ በጺሖተ ግብጻውያን |
| 32 | On Easter and His Reluctance. | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት | በእንተ ትንሣኤ ወምክንያተ ኅንድዮቱ |
| 33 | On the Words of the Gospel, 'When Jesus Had Finished These Sayings,' Etc., Matt. xix. 1 | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት | በእንተ ቃላተ ወንጌል ዘይቤ "ሶበ ፈጸመ እግዚእ ኢየሱስ ዘንተ ነገረ . . ." ማቴ. 19፡1-15 |
| 34 | On the Theophany, or Birthday of Christ | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት | በእንተ አስተርእዮቱ (ዕለተ ልደተ ክርስቶስ) |
| 35 | The Oration on Holy Baptism | ቅ. ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት | ትምህርት በእንተ ቅዱስ ጥምቀት |
| 36 | Funeral Oration on the Great S. Basil, Bishop of Cæsarea in Cappadocia | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት | ትምህርት በእንተ ዕረፍቱ ለቅዱስ ባስልዮስ |
| 37 | The Second Oration on Easter | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት | ትምህርት ካልአይ በእንተ ትንሣኤ፤ |
| 38 | Select Letters of Saint Gregory Nazianzen | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት | መልእክታት |
| 39 | Against Eunomius | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ | በእንተ ዩኖሚየስ |
| 40 | Answer to Eunomius' Second Book | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ | በእንተ ዩኖሚየስ ሁለተኛ መጽሐፍ |
| 41 | On Virginity | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ | በእንተ ድንግልና |
| | On the Making of Man | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ | በእንተ ፍጥረተ ሰብእ |
| 42 | The Life of Moses | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ | በእንተ ሕይወቱ ለሙሴ |
| | | | |

| | ከግሪክ (የተወሰኑት ከላቲን) ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጎሙ የተሰጣቸው ርእስ | የጻፈው አባት | በዚህ መጽሐፍ ላይ የተሰጣቸው ርእስ |
|---|---|---|---|
| 43 | On the Soul and the Resurrection | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ | በእንተ ነፍስ ወትንሣኤ ሙታን |
| 44 | The Great Catechism | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ | ዐቢይ ትምህርተ ክርስትና |
| 45 | Funeral Oration on Meletius | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ | ትምህርት በእንተ ዕረፍቱ ለጳጳስ መላጥዮስ |
| 46 | On the Baptism of Christ | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ | በእንተ ጥምቀተ ክርስቶስ |
| 47 | Against Heresies | ቅዱስ ሄሬኔዎስ | በእንተ መናፍቃን |
| 48 | Fragments from the Lost Writings of Irenæus | ቅዱስ ሄሬኔዎስ | ቅሬታት |
| 49 | On the Unity of the Church. | ቅዱስ ቆጵርያኖስ | በእንተ ዋሕድናሃ ለቤተ ክርስቲያን |
| 50 | On the Lapsed | ቅዱስ ቆጵርያኖስ | ከሃይማኖት አድጠው ስለ ነበሩና ስለ ተመለሱ ተነሣሕያን የተሰጠ ትምህርት |
| 51 | On the Lord's Prayer | ቅዱስ ቆጵርያኖስ | በእንተ ጸሎተ እግዚእነ |
| 52 | On Works and Alms | ቅዱስ ቆጵርያኖስ | ስለ የጽድቅ ሥራዎችና ስለ ምጽዋት ያስተማረው ትምህርት፣ |
| 53 | Letters | ቅዱስ ቆጵርያኖስ | መልእክታት |

## መለያ ምልክቶች

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ምልክቶችና የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው፡-

- ◉ ይህ ምልክት መጀመሪያ ላይ ያለባቸው ጥቅሶች የተሐድሶዎቹ ትምህርቶችና ሃሳቦች ናቸው፡፡
- ➢ በዚህ ምልክት የተገለጹት ከዋናው ሐተታና ትንተና በፊት በተሐድሶዎቹ አስተምህሮዎችና አባባሎች ላይ የተሰጡ አጭር ሐተታዎችና ምልከታዎች ናቸው፡፡
- ❖ በዚህ ምልክት የተገለጹት ደግሞ የቅዱሳን ሊቃውንት አባቶቻችን ትምህርቶችና አልፎ አልፎም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች ናቸው፡፡

## ጸሎት

- ✣ አቤቱ፣ የእውነት ባለቤት የሆንክ እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፣ በሰው ዘንድ የማይቻለው በአንተ ዘንድ ይቻላልና ሐሰት እንዲያፍር እውነት ደግሞ እንዲታወቅ፣ የበግ ለምድ ለብሰው ከበጎች መንጋ ገብተው በጎችን እንደ ልባቸው እየመረጡ ለመብላት እያደቡ ያሉ ተኩላዎችንና ቀበሮዎችን በተፈጥሯቸው እንደ እኛ ያሉ ሰዎችና፣ በሥጋቸውም ወንድሞቻችን ናቸውና ለእነርሱም መሞትና በአንተ ፊት መቅረብ አለና ይህን የሚያስብ ልብ እንድትሰጣቸው፣ በጎችህንም እንድትጠብቃቸው እንማጸንሃለን፡፡
- ✣ አቤቱ፣ ቸርና ሰውን ወዳጅ የሆንክ አምላካችንና አባታችን እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህ መጽሐፍ በቅድስትና ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያንህ ላይ በዕብሪትና በትዕቢት የተሰነዘሩ ጽርፈቶችና ሐሰቶች የሚጋለጡበትና የሚያፍሩበት፣ ሕይወትና እውነት የሆነው ቅዱስ ቃልህ ደግሞ የሚመሰከርበትና የሚገለጥበት ታደርገው ዘንድ መልካም ፈቃድህ ይሁን፡፡

- አቤቱ ይቅር ባይ አምላካችን ሆይ፣ የሰውነታችንን ደካማነት የአእምሯችንን ሕጸጽ ሳትመለከት እውነትን በቀና ልቡና የሚፈልጉ የእጆችህ ሥራ የሆኑ ፍጥረቶችህ የሰው ልጆች ስንዴውን ከእንክርዳዱ፣ ምርቱን ከግርዱ ለመለየት የሚረዳቸውን መልካም ነገር ለማድረግ እንችል ዘንድ ቅዱስ ፈቃድህ ይሁንልን፣ አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን።

- የእናታችን የቅድስተ ቅዱሳን ንጽሕተ ንጹሐን የወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ምልጃና ጸሎት፣ እንዲሁም ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋዌው በሠራት በአንዲቷ ኦርቶዶክሳዊትና ሐዋርያዊት የክርስትና መንገድ የተጓዙና የወጡ የወረዱ፣ እርሱን ያገለገሉና ከእርሱ ጋር የኖሩ የቅዱሳን አባቶቻችንና እናቶቻችን ሁሉ ኃይለ ጸሎታቸውና ክንፈ ረድኤታቸውም ይርዳን፣ አሜን።

# ምዕራፍ አንድ

# መንትው

## 1.1 የተሐድሶዎች መነሻዎችና መሠረቶች

ወደ ዋናዎቹ ነገረ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ከመግባታችን በፊት ተሐድሶዎች "እምነት"፣ "እውነት" የሚሏቸውን ነገሮች የሚገልጹባቸውንና የተመሠረቱባቸውን ነገሮች፣ እንዲሁም አስተሳሰባቸውንና አካሄዳቸውን አመልካች የሆኑ የተወሰኑ ነጥቦችን ብቻ በአጭሩ ተመልክተን እናልፋለን፡፡ እነዚህ የተሐድሶዎች መገለጫዎችም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

### 1.1.1 በ "መሰለኝ" ማመን

ሃይማኖትን ያህል መሠረታዊና ጥልቅ ጉዳይ ተሐድሶዎች "ለእኛ የመሰለንን" እያሉ እንደ ስብሰባ አስተያየት እምነታቸው ለእነርሱ የመሰላቸው ሃሳብ ወይም ግምት መሆኑን በየጽሑፎቻቸው ይገልጻሉ፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን አባባሎቻቸውን እንመልከት፡፡

- *"ለየንዳንዳችን የመሰለንንና ያመንበትን፣* ከሊቃውንትም የተማርነውን ሃሳብ እውነት መሆኑንና ጠቃሚነቱን ከተቀበልነው ዘንድ ለሌሎች ማስገንዘብ ይገባል በማለት እነሆ "ጮራ" የተሰኘውን መንፈሳዊ መጽሔት ለማሳተም ተነስተናል፡፡" (ጮራ ቁ. 1፣ ገጽ 3)

እንግዲህ እዚህ ላይ ለሌሎች ሊያስገነዝቡ የተነሡት እምነት *ለእያንዳንዳቸው የመሰላቸውን* መሆኑን በግልጽ ተናግረዋል፡፡ ይህ ደግሞ ቢያንስ ሁለት መሠረታዊ ችግሮችን ያስከትላል፡፡ አንደኛው እነርሱ ለእኛ ሊያስተምሩን የተነሡት የእምነታቸው መሠረት እነርሱን *የመሰላቸው* መሆኑ ነው፡፡ እነርሱ የመሰላቸው ነገር እውነት፣ ያልመሰላቸው ነገር ደግሞ ስህተት ከሆነ ለዚያ እነርሱ መሰለን ለሚሉት ነገር ትክክለኛነት ማረጋገጫው ምንድን ነው? መነሻውም መድረሻውም፣ መለኪያውም ማረጋገጫውም እነርሱው ብቻ ናቸው ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም የሆነን ነገር "እመኑ" ብለው ለእኛ የሚነግሩን እነርሱን ሲመስላቸው ስለሆነ፣ ይህን እነርሱ የሚመስላቸውን ነገር ደግሞ በቋሚነት ማወቅ ስለማይቻል ነው፡፡ መሰለኝ የሚለው ነገር በጎደሎ መረጃና በስሜትም ላይ የተመሠረተ ስለሆነ እነዚህ ነገሮች ደግሞ ቋሚነት የሌላቸው ተለዋዋጭ ነገሮች በመሆናቸው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከእግዚአብሔር ይልቅ እምነትን በሰዎች ላይ ማድረግ ነው፡፡ ይህን ግን ቅዱስ መጽሐፍ በጽኑ ይከለክለዋል፤ እንዲህ ሲል፡- "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- በሰው የሚታመን፣ ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ፣ ልቡም ከእግዚአብሔር የሚመለስ ሰው ርጉም ነው።" ኤር. 17፡5

ሁለተኛው ችግር ደግሞ የሚመስላቸው ነገር ለእያንዳንዳቸው ግለሰቦች የተለያየ ሊሆን ስለሚችል (የሚመስላቸው ነገር አንድ ስለ መሆኑ ማወቅ አይቻልምና) ከእነርሱ ውስጥ የትኛው የመሰለውን ሲነግረን እንደምንሰማና እንደማንሰማ ሊያሳውቅ የሚችል ነገር አለመኖሩ ነው፡፡ ምክንያቱም *"ለየንዳንዳችን የመሰለንን"* ስላሉ ብዛት እንዳላቸው ገልጸዋልና ለአንዱ የመሰለው ነገር ለሌላው ላይመስለው ስለሚችል ሌላው መሰለኝ ካለው ነገር ጋር ባይስማማ የየትኛውን ልንሰማ እንደሚገባ መለኪያ ስላልነገሩን ነው፡፡

ለሰው ልጆች መዳኛ ትሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር የተሰጠችው አንዲቷ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ክርስትና ግን በሰዎች ግለሰባዊ አስተሳሰብና "መሰለኝ" በሚል ግምትና መላ ምት የተገኘች ሳትሆን ከራሱ ከእግዚአብሔር የተሰጠች ናት፡፡ ለስም አጠራሩ ክብርና ምስጋና ይግባውና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም "የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀበሉት" በማለት እርሱ ሰጪ፣

እኛ ሰዎች ደግሞ ተቀባዮች መሆናችንን በአምሳካዊ ቃሉ ተናግሯል፡፡ ዮሐ. 17፥8 ሃይማኖት ከእግዚአብሔር የተሰጠና እኛ ደግሞ ተቀብለነው ኖረንበትና ሕይወትን አግኝተንበት ለሌሎችም የምናወርሰውና የምናስተላልፈው መሆኑን ሲናገር ቅዱስ ጳውሎስ "እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ" ይላል፡፡ 1 ቆሮ. 15፥3 እንደዚሁም "ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና" በማለት የሰው ልጆች ድርሻ ከጌታ መቀበልና በእርሱ በሕይወት መኖር፣ እንዲሁም ያንን እንዳለ መጠበቅና ማስተላለፍ መሆኑን ይኸው ሐዋርያ በአጽንዖት ይናገራል፡፡ 1 ቆሮ. 11፥23 ስለዚህ እኛ የምናምነው እነርሱ "መሰለኝ" እያሉ እንደ አየር ትንበያ የሚገምቱትን ሳይሆን እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት የገለጠልንና ከአባቶቻችን የተቀበልነውን እውነት ብቻ ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ሃይማኖት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስለ መሆኑ ደጋግሞ ይናገራል፡፡ "ወዳጆች ሆይ፣ . . . ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ" በማለት ያሳስበናል፡፡ ይሁ. 3 ሃይማኖት ከእግዚአብሔር የተሰጠ፣ ያውም አንድ ጊዜ የተሰጠ እንጂ ሰዎች በመሰላቸው ወይም ባልመሰላቸው ጊዜ እንደሚወስኑት ወይም እንደሚሽሩት የስብሰባ አጀንዳ አይደለም፡፡ ስለዚህ በሃይማኖት አሰጣጥና አቀባበል ሂደት እግዚአብሔር በሃይማኖት ውስጥ የሚታመነውን እውነት የገለጠና የሰጠ ሲሆን የሰዎች ድርሻ ደግሞ ያንን እውነት "አሜን" ብሎ መቀበልና በእርሱ መኖር፣ እንዲሁም ጠብቆ ማስተላለፍ ነው፡፡

በሃይማኖት ታሪክና ሂደት ዓለም አቀፋዊም ሆኑ አካባቢያዊ እንዲሁም ጊዜያቸውን ጠብቀው በየወቅቱ የሚደረጉ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት (ሲኖዶሳት) እንኳ ድርሻቸውና ተግባራቸው ያን አንድ ጊዜ የተሰጠውን ሃይማኖት መጠበቅ፣ ሲያስፈልግም ያን ማብራራትና ከእውነቱ የሚጣላ ነገር ይዘው ብቅ ያሉ መናፍቃን ካሉ እነርሱን መክሮና አስተምሮ መመለስ፣ ካልተቻለ ደግሞ እነርሱን ከነስህተቶቻቸው አውግዞ መለየት ነው፡፡ ከዚያ ያለፈ በሃይማኖት ላይ የመጨመርም ሆነ የመቀነስ አንዳችም ሥልጣን የላቸውም፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የኬልቄዶንን ጉባኤ የማትቀበልበት ዋና ምክንያትም ጉባኤው እምነትን ከመጠበቅ ወሰኑ አልፎ እምነትን እንደ አዲስ ልሥራ፣ ልመሥርት ስላለ እና ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ከተሰጣት እምነት ጋር የማይስማማ አንቀጽ ላርቅቅ በማለቱ ነው፡፡

ስለሆነም ተሐድሶዎች እነርሱ የመሰላቸውን እንንገራችሁ ቢሉን እኛ የምናምነው እናንተን በመሰላችሁ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረን እና ቅዱሳን አባቶቻችን ባስተላፉልን ሐዋርያዊ እምነት እንጂ ከዚያ ወጥታችሁ "እኔን የሚመስለኝ እንዲህ ነውና እባካችሁ ስሙኝ" የምትሉትን ልንሰማችሁ እንደማንችል ስንገልጽላችሁ በትሕትና ነው፡፡ ምክንያቱም ታላቁ መምህራችን ቅዱስ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ". . . የሚያናውጧችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ እንጂ። ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን። አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፣ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን" ሲል በታላቅ ቃል ግዝት ስላስጠነቀቀን ነው። ገላ. 1፥7-9

ይህ በመሰለኝና በይሆናል መናገራቸው ይቀጥልና እንዲህ ይላሉ፡-

- "... አቡነ ተክለ ሃይማኖትና አባ ኤዎስጣቴዎስ በአስተምህሮ የነበራቸውን ልዩነት በዝርዝር ለመገንዘብና ለማስገንዘብ ለረጅም ጊዜ የታሪክ ጥናት ማድረግን ይጠይቃል፡፡ . . . እነዚህን ከመሳሰሉት ጥቃቅን ልዩነቶች በስተ ጀርባ የተለያዩ የስብከተ ወንጌል ድርጅቶችን ወደ ማቋቋም ያደረሱ መጠነ ሰፊ ልዩነቶች <u>ሳይኖሩ እንዳልቀሩ ይገመታል፡፡</u>" (ሙራ ቁ. 16፣ ገጽ 29)

- "እንደ እውነቱ ከሆነ አባ እስጢፋኖስ የተከሰሰባቸውን ነጥቦች ስንመረምር መሠረተ እምነቱ

  የሙታንን ነፍሳት ከመማጸን (እምተማኅፅኖተ ነፍሳተ ሙታን)
  መናፍስትን ተስፋ ከማድረግ (እምተሰፍዎተ መናፍስት)
  ከቅርጻ ቅርጽ አምልኮ (እምአምልኮ ኪነት) *የጸዳ እንደ ነበር ልንገምት እንችላለን፡፡*" (ሙራ ቁ. 18፣ ገጽ 22)

ከእንደዚህ ዓይነት ታላላቅ ድምዳሜዎች ላይ ሲደርሱ ከግምት ያለፈ አንዳችም ነገር ሳይይዙ መሆኑ ያሳዝናል፡፡ አሁንም ጉዳዮችን የራሳቸው ደጋፊ አስመስለው ለማቅረብ ካላቸው ጉጉት የተነሣ ብቻ በታሪክ ራሱን በቻለ ሁኔታ ሊጠና የሚገባውን ጉዳይ በመቆንጸል አንዳችም ማስረጃ ሳያቀርቡ እንዲሁ በግምት ብቻ "*ይገመታል፣ ልንገምት እንችላለን*" ብለው ደፍረው መናገራቸውን ሲያዩት በአንድ በኩል በትምህርት በኩል ያለባቸውን መጎዳት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በባዶው ደፋር መሆናቸውን ይመሰክርላቸዋል፡፡

ገና ሲጀምሩ "*ለያንዳንዳችን የመሰለንና ያመንበትን* . . . ሃሳብ ለሌሎች ማስገንዘብ ይገባል" ብለው የተናገሩትን ቃል በመጠበቅ ከእነርሱ እያንዳንዳቸው የመሰላቸውን ነገር "ይመስላል፣ ይሆናል፣ ሳይሆን አይቀርም" በሚል ግምት ለእኛ ሊነግሩን በየቦታው ሞክረዋል፡፡ ለምሳሌም፡-

- "መዝሙረ ዳዊት 10 (11)፣ 1-7 ላይ ያለው ቃል ከሌዋውያን መካከል የሆነው የመዘምራኑ አለቃም ዝማሬውን የሚመራ ሲሆን፣ ሌዋውያን መዘምራንና *ምናልባትም ሕዝቡ ጭምር* በተሰጥዎ መልክ ምላሹን እያዜሙ በማስተዛዘል አምልኮ የሚያቀርቡበት መዝሙር *ሳይሆን አይቀርም፡፡*" (ሙራ ቁ. 28 ገጽ 3)

- "ወንጌላዊው ሉቃስ በስሙ የሚታወቀውን ወንጌል ለመጻፍ የተነሳሳበትን ምክንያት በመጀመሪያው ምዕራፍ ውስጥ መዝግቧቸዋል፡፡ ቃሉን እንዲያገለግሉ የተመረጡትና የዓይን ምስክሮች የሆኑት ደቀ መዛሙርት ያስተላለፉት ማስረጃ መኖሩን ይጠቁማል፡፡ . . . በእርግጥም ሉቃስ የቃሉ አገልጋዮች ሲል የሆኑት ምስክሮች ያስተላለፉት የጠቀሰው ማስረጃ እርሱው ራሱ የሐዋርያት ሥራ በተባለው መጽሐፍ ውስጥ "የሐዋርያት ትምህርት" በማለት የዘገበው ነው *ቢባል ያስኬዳል፡፡*" (ሙራ ቁ. 28፣ ገጽ 13)

- ". . . ፍጹም አምላክ የሆነ ቃል ፍጹም ሰው ሆነ ብላ ቤተ ክርስቲያን በሙሉ አንደበቷ የምትመሰክርለት ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤ በኋላ ፍጹም አምላክ እንጂ ፍጹም ሰው ሊባል አይገባም የሚል ሃሳብ *ሲነገር ተሰምቷል፡፡*" (ሙራ፤ ቁ. 16፣ ገጽ 1)

- "ወንጌል በአክሱም ከተማ ከቤተ መንግሥት ጀምሮ ተሰበከ ቢባልም፣ እንደሚገባው እንዳይስፋፋና በመላ ሀገራችን እንዳይሠራጭ የነገደ ኩሽ በምድር ፍጥረታት የማምለክ መንፈስ፣ የነገደ ሳባ በሰማይ ሠራዊት የማምለክ መንፈስ፣ . . . በግልጽም በስውርም ለመዋጋት ኃይላቸውን አጣምረው ይቃወሙ እንደ ነበር *መገመት ይቻላል፡፡*" (ኖኅተ ብርሃን፣ መጋቢት 2002፣ ገጽ 7)

እንግዲህ ይህ ሁሉ የሚያሳየው እምነታቸውና ትምህርታቸው ምን ያህል በግምትና በሳይሆን አይቀርም ላይ የተመሠረተ መሆኑን ነው፡፡ ገና አዲስ "እምነት" እየሞከሩ ስለሆነ "እንዲህ ቢባል ያስኬዳል"፣ "እንዲህ እንደ ነበር መገመት ይቻላል" እያሉ ገና በሙከራ ላይ ናቸው፡፡ የሚገርመው ግን የራሳቸውን ግምትና መላምት ለእኛ እናስተምራችሁ ብለው መነሣታቸው ነው፡፡

ከዚሁ ጋር ደግሞ ለእነርሱ ኑፋቄ የማይመች ሲሆን "አንድም" እየተባለ መተርጎም የለበትም ብለው ይቃወማሉ፡፡ ለአብነትም እንዲህ ያሉትን እንመልከት፡-

- "የእግዚአብሔር ቃል ሲተላለፍልን እንደ ተላለፈልን መልእክት መያዝና በዚያም ቃል መኖር እንጂ እኛ በፈለግነው ነገር ላይ ብቻ ለማጠንጠን ስንል አንድም እያልን የእውነት ማደበስበሻና ጭብጥ ሀሳቡን ማሳቻ /ማዛቢያ/ ይሆንብናል፡፡ ለምን ብንል ለአንድ እውነት አንድ እንጂ ሁለት ወይም ሦስት እውነታዎች የሉምና፡፡" ("መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ መግቢያ)

አሁንም ተቃውሟቸውን በማጠናከር ይህንኑ ትርጓሜን ሲነቅፉ እንዲህ ብለዋል፡-

- "... ስህተቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲገቡ ሰፊ በር የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ችግር ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን የሚታወቀው አንድምታ የተሰኘው የትርጓሜ ስልት ... እውነትን አፍኖ ስሁትትን በማራመድ ረገድ ብዙ ረድቷል፡፡ አንድምታ በአንድ የእግዚአብሔር ቃል ላይ የተለያዩና ፊተኛው ትርጉም በኋለኛው የሚፈርስበት ብዙ ትርጉሞችን ስለሚሰጥ ሰው አንድ ተጨባጭ የሆነ ቁም ነገር እንዲይዝ አያስችለውም፡፡ በዮሐ. 1፥49 ላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለናትናኤል "ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች ሳለህ አየሁህ" ብሎ የተናገረው ግልጽ የሆነ ቃል በባለ አንድምታዎች ዘንድ ሌላ ድብቅ ምስጢር እንዳለው ተቆጥሮ ስድስት ዓይነት አንድምታዊ ትርጓሜዎች መሰጠታቸውን በምሳሌነት እንመልከት፡- ... (ስድስቱም ተዘርዝረዋል) በዚህ መልክ የሌለውን ድብቅ ምሥጢር ለማውጣት ሲባል የእግዚአብሔርን ቃል ማስጨነቅ ትርፉ የፈጠራ ድርሰትና ታሪክ መፈልሰፍ ሲሆን ኪሳራው ደግሞ ከእግዚአብሔር አሳብ ርቆ መሳሳት ነው፡፡ ..." (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 95-96)

ሆኖም ለእነርሱ የሚስማማና የሚደግፋቸው መስሎ ሲታያቸው ግን ያንኑ የነቀፉትን የትርጓሜ ስልት ይጠቀሙበታል፡፡ ለምሳሌም ከመሠረቱ የተለዩ ስለሆኑ ከአበው ቀደምት የትርጓሜ ትምህርትና ሃሳብ ምንም ባልተገናኘ መንገድ በለመዱት የግምትና የ "ሊሆን ይችላል" አካሄድ እንዲህ ሲሉ ይቀጥላሉ፡-

- "<u>አንደኛ</u> ትውፊት ራእይም፣ የራእይ ግብም አይሆንም፣ ... ጠቢባኑ (ሰብአ ሰገል) ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ፡፡ ማንነታቸው በግልጽ ባይነገርም የመሲሕን መገለጽ ሲጠባበቁና ሲናፍቁ ከቆዩት ወገኖች መካከል መሆናቸው አያጠያይቅም፡፡ <u>ምናልባት</u> ወደ ባቢሎን ተማርከው ከሔዱ በኋላ እስከ ሕንድ ድረስ ተበትነው ከነበሩትና ሳይመለሱ እዚያው ከቀሩት እስራኤላዊ ዝርያካላቸው መካከል ሊሆኑ ይችላሉ፤ <u>ወይም</u> ከልዩ ልዩ ሀገር ወደ ባቢሎን ተማርከው የባቢሎናውያንን ጥበብ ከእነ ዳንኤል ጋር ከተማሩ በኋላ በዳንኤል ሥር የተመደቡት ጠቢባን ዝርያዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡" (ጮራ ቁ. 11፣ ገጽ 5)

አሁንም ለእነርሱ አካሄድ የሚደግፍ ሲመስላቸው ያንኑ "የእውነት ማድበስበሻና ጭብጥ ሀሳቡን ማሳቻ/ማዛቢያ/ ያሉትን አንድምታ ለራሳቸው ይጠቅሱታል፡፡ ለአብነትም ይህን እንመልከት፡-

- "... ይህን የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ሁለትን የጥንቶቹ ዓይናማ የሆኑ የኦርቶዶክስ ሊቃውንት ክፍሉን ለምልጃ አይጠቅሱትም፡፡ እንዲያውም የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ የሆነው አንድምታ ትርጓሜ የሚባለው "ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ ምንት ብየ ምስሌኪ ኦ ብእሲቶ" የሚለውን ሲተረጉም <u>አንድም</u> በአምላክነቱ አገዛዙ ታዝዞ እንደ ሌለበት ለማጠየቅ ነው፡፡ <u>አንድም</u> ውኃውን ጠጅ አድርጌ የማጠጣቸው በእኔ ፈቃድ ነው እንጂ በአንቺ ትእዛዝ ነውን አላት ይላል፡፡ 'አዲ ኢበጽሐ ጊዜየ' ነገር ግን ጊዜየ አልደረሰም፣ ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር እንዲል ሥራውን የሚሠራበት ጊዜ አለውና በማለት ሰፊ ትንታኔ ይሰጣል፡፡" /አንድምታ ወንጌል/ ("መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ ገጽ 39)

ታዲያ እንዲህ የነቀፉትንና "ከእግዚአብሔር ሃሳብ አርቆ ያሳስታል" ያሉትን አንድምታ መልሰው ለራሳቸው ድጋፍና ምስክር አድርገው ለምን ጠቀሱት? ለእነርሱ የሚደግፍና የሚመች ሲመስላቸው የነቀፉትን ነገር ይጠቀሙበታል፡፡ ይገርማል! ለራሳቸው ሲሆን "አንድምታ" ይፈቀዳል፣ ለሌላው ሲሆን ግን አይፈቀድም፤ ለእነርሱ ሲሆን ልክ ይሆናል፣ ለሌላው ሲሆን ደግሞ ስህተት ይሆናል! ለዚህ ነው በ"መሰለኝ" ማመን መነሻውም መድረሻውም፣ መለኪያውም የግለሰቦች ምኞትና ፍላጎት ብቻ ስለሚሆን አስቸጋሪ ነው ያልነው፡፡

አሁንም በግምት ሊያስተምሩን ይቀጥላሉ፤

- "... በዚሁ መሠረት አጼ ዓምደ ጽዮን ታላቁና ታናሿ በመባል በንግሥትነት የተሰየሙ ሁለት ሚስቶችና ቁጥራቸው የማይታወቁ ዕቁባቶች ነበሩት፡፡ በዚህም ሥራው ከቤተ ክህነት ተቃውሞ አልደረሰበትም፡፡ <u>ምናልባትም</u> ለሁለቱም ንግሥታት ሥርዓተ ንግሥ ፈጻሚዋ ቤተ ክህነት <u>ልትሆን እንደምትችል ማሰብን የሚከለክል አንዳችም ነገር የለም</u>፡፡" ጮራ ቁ. 15፣ ገጽ 26

*በአጼ ዓምደ ጽዮን ታሪክ ዙሪያ በነበረው ነገር ቤተ ክርስቲያንን ለመውቀስና ለመክሰስ ሲሉ ብቻ ባልተረጋገጠ መላ ምት "ምናልባትም ለሁለቱም ንግሥታት ሥርዓተ ንግሥ ፈጻሚዋ ቤተ ክህነት ልትሆን እንደምትችል ማሰብን የሚከለክል አንዳችም ነገር የለም"* አሉ፡፡ የሃይማኖት ሰው ነኝ ለሚል ይቅርና በዚህ ዓለም ሕግ እንኳ አንድን ሰው በማስረጃ ኃይል (On the strength of evidence) ነገሩን አስረድቶ በዳኛ ሳያስፈርዱ "ወንጀለኛ" ነው ማለት አግባብ አይደለም፡፡ ተሐድሶዎች ግን ላሉት ነገር አንዳች እንኳ ማስረጃ ሳያቀርቡ ገና ለገና እነርሱ የጠሏትን ቤተ ክርስቲያን የንጉሡ የስህተት ተጋሪ ሳትሆን አትቀርም ብሎ ከማሰብ ማንም አይከለክለንም ይላሉ፡፡ አዎ፣ አእምሮ ለሌለው ሰው ምንም ነገር ከማሰብ የሚከለክለው ነገር የለም፡፡ ድሮስ ቢሆን ልዋሽ ላለ ሰው ምን ድንበር አለውና! አእምሮ ላለው ሰው ግን ያለ በቂ ማስረጃ እንኳን ቤተ ክርስቲያንን፣ ያውም ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት በሆነ ታሪክ ዙሪያ ላይ ያለ ነገርን ይቅርና አንድን ግለሰብና በቅርብ ጊዜ የተፈጸመ ጉዳይን በተመለከተ እንኳ በቂ ማስረጃ በሌለበት በአሉታና በወንጀለኛነት መፈረጅ በእጅጉ ይከብደዋል፡፡

ስለ እምነት እንቁረቁራለን ባዮቹ ተሐድሶዎች እምነትን የሚያስረዱበት መንገድና ሁኔታ እንዲህ ያለ ነው፤ "ይመስላል"፣ "ይሆን ይሆናል"፣ "መገመት ይቻላል"፣ "ያስኬዳል"፣ ወዘተ በሚሉ ሃሳቦች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ሃይማኖት ግን ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳለው "እመኒ እወ እወ ወእመኒ አልቦ አልቦ ወፈድፋደሰ እምእሉ እምእኩይ ውእቱ - ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፤ ከነዚህም የወጣ ከክፉው ነው" ባለው መሠረት እውነቱን እውነት፣ ሐሰቱን ሐሰት ማለት እንጂ ከዚያ ወጥቶ "ይመስላል"፣ "ሊያስኬድ ይችላል" ወዘተ እያሉ መቀባጠር ምናልባት ለሰብአዊ አስተሳሰቦችና ለምድራዊ ርእዮቶች ካልሆነ በስተቀር ለክርስትና ቦታም አግባብነትም የለውም፡፡ ማቴ. 5፡37 ሌላው ነገሩን የበለጠ አሳዛኝ የሚያደርገው እነዚህን መላ ምቶች የሚፈጥሯቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮና ታሪክ ለመንቀፍና ጥላሸት ለመቀባት መሆኑ ነው፡፡ ሲሆን ሰው በሚያየው ነገር እንኳ ከመፍረድ ተቆጥቦ ወደ መረዳትና በዘመኑ የነበረውን ነገር ወደ ማገናዘብ ቢሄድ መልካም ነበር፤ ይህ ከእነርሱ አንጻር ከዐቅማቸው በላይ ቢሆንባቸው እንኳ ጠንካራ መረጃ ሳያገኙ ለስድብና ለማጥላላት ሲሉ ብቻ "ሊያስኬድ ይችላል" እያሉ መነሣት ወይ ሰማዕያኑ አያውቁብኝም ብሎ መናቅ ነው፤ አለዚያም ደግሞ ምን ሊያስከትል እንደሚችልነማሰብ አለመቻል ነው፡፡

### 1.1.2 በሐሰት መናገር

ሌላው የተሐድሶዎች መገለጫ በሐሰት መናገር (ውሸት) ነው፡፡ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የማታምነውንና የማትቀበለውን እንደምታምን እያስመሰሉ በሐሰት መጻፍና መናገር ዋና ጠባያቸው ነው፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት፡-

- "ቤተ ክርስቲያኒቱ የሁለት ተቃራኒ ድርሰቶች ባለቤት ናት፡፡ . . . በትግራይ ክ/ሀገር በአዲግራቱ የቤተ ክህነት ጽ/ቤት ፈቃድ፣ በክልሉ ቢሮ እንዲሁም በባህልና ቱሪዝም መሥሪያ ቤት ትብብር በተጻፈው መጽሐፍ የጉንዳ ጉንዶ ደብረ ገሪዛን ማርያም አበምኔት የነበሩትን አባ ደቅ እስጢፋን ለእምነታቸው የሞቱ፣ ሰማዕት፣ ጻድቅና ቅዱስ አባት ብላ መቀበሏ በሊቃነ ጳጳሳትና በቤተ ክርስቲያኗ ሊቃውንት ከግእዝ ወደ አማርኛ የተተረጎመው መጽሐፍ ያስረዳናል፡፡ (ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳ ጉንዲ፣ 1966፣ ገጽ 1) በተቃራኒው ደግሞ እኒሁን ጻድቅ አባት ቆዳቸውን ገፍፎ በስቃይ የገደለና የእርሳቸው ደቀ መዛሙርት የነበሩትን ከ300 በላይ የገዳሙን መነኰሳት በሰይፍና በገደል ውስጥ ከብት በመንዳት የገደለውን ንጉሥ [አጼ ዘርዓ ያዕቆብን]፣ ጻድቅ፣ በምልጃቸው የሚረዱን ብላ ታቦት ቀርጻ ምስል ስላ ታስተምራለች፡፡" ("መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ መቅድም)

እሁንም ይቀጥላሉ፡-

◉ "እኒሁ ጻድቅ የተባሉት ንጉሥ [አጼ ዘርዓ ያዕቆብ] መነኩሳትንና የመጽሐፍ መምህራንን ከማስጨፍጨፋቸውም በላይ የምንኩስና ቆባቸውን ጥለው ሲነግሡ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት (በተክሊል) ሁለት ሚስቶችን እንዳገቡ ዜና ገድላቸውም ይናገራል፡፡ . . . እኒህ ሰው ሁለት ሚስት ሲያገቡ ሥርዓቱን መፈጸም አልነበረባትም፡፡ ይሁን እንጂ በመቃወም ፋንታ "አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት" የሚለውን መለኮታዊ ትእዛዝ ንጉሡ ሲጥሱ ለኃጢአታቸው ተባባሪነቷ ሳያንስ "ጻድቅ አባት፣ የሃይማኖት ሐዋርያ፣ የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ደንጋጊና ወሳኝ" በማለት ነፍስ ገዳይን ሰው ቅዱስና ጻድቅ ብላ እስካለንበት ዘመን ድረስ ታቦት ቀርጻ መልክዐ ደርሳ ስታወድስ የመታሰቢያም በዓል ስታከብር ትገኛለች፡፡ ይህን እውነታ ከወንጌል አብልጠን በምናየው እሑድ እሑድ ሳንሳለመው በማንውለው ተአምረ ማርያም በተባለው መጽሐፍ ውስጥ እናገኘዋለን፡፡" ("መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ መቅድም)

እንግዲህ በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱት አንቀጾች ውስጥ የታጨቁ በጣም ብዙ ውሸቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከልም ዋና ዋናዎቹን ውሸቶች እንመልከት፡-

1. አንደኛው ሐሰት፡- "አባ ደቅ እስጢፋን ለእምነታቸው የሞቱ፣ ሰማዕት፣ ጻድቅና ቅዱስ አባት ብላ ተቀብላለች" የሚለው ነው፡፡

ይህ ደረቅ ሐሰት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህን ሰው ጻድቅና ቅዱስ ብላ አልተቀበለችም፡፡ የሆነ ሰው "ገድል" በሆኑ ሰዎች አማካይነት ከግእዝ ወደ አማርኛ ተተረጎመ ማለት ቅድስናውን ቤተ ክርስቲያን ተቀበለችው ማለት አይደለም፤ በቤተ ክርስቲያኗ ትውፊትና ታሪክ እንደዚህ ሆኖም አያውቅም፡፡ ሆኖም ይህን የምትሉት የቤተ ክርስቲያኗን አስተምህሮና ይትበሃል ስለማታውቁት ብቻ ሳይሆን ሆን ብላችሁ ታሪኩን በሐሰት ያልሆነ መልክ ለመስጠት ከማሰብም የመነጨ እንደሆነ ቀጣዮቹ ሌሎቹ ተደራራቢ ውሸቶቻቸው ያሳያሉ፡፡

አንድ ሰው ገድል ስለ ተጻፈለትና መልክ ስለ ተደረሰለት በቤተ ክርስቲያኒቱ ዘንድ በቅዱስነት ተቀባይነት አግኝቷል ማለት አይደለም፡፡ እንደዚሁም ደግሞ በየቦታው ኖረው ብዙም ሰው (ብዙዎችን ማንም ሰው) ሳያውቃቸው ያለፉ፣ ገድልና መልክ ሊጻፍላቸው ቀርቶ ከነስማቸው እንኳ ሳይታወቁ ያለፉ ብዙ ቅዱሳን አሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹ ቅዱሳን ገድል ሊጻፍላቸውና መልክ ሊደረስላቸው ይቅርና ስለ መኖራቸውም እንኳ ከፈጣሪያቸውና እርሱ ከገለጠላቸው አንዳንዶች በስተቀር ሕይወታቸው ሁሉ በእግዚአብሔር የተሰወረ ነበር፡፡ ስለዚህ ለሆነ ሰው ገድል ስለ ተጻፈለት ወይም ስለ ተደረገለት፣ እንዲሁም የዚያ የገድል ድርሰት ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ ስለ ተተረጎመበት ብቻ ቤተ ክርስቲያኒቷ ያን ሰው "ሰማዕት፣ ጻድቅና ቅዱስ" ብላ ተቀብላዋለች ማለት አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየትኛውም ድንጋጌዋ ወይም ቀኖናዋ ላይ አባ እስጢፋኖስን ጻድቅ፣ ለእምነቱ የሞተ ብላ የተቀበለችበት ውሳኔ የለም፡፡

2. ሁለተኛው ሐሰት፡- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አጼ ዘርዓ ያዕቆብን "ጻድቅ፣ በምልጃቸው የሚረዱን ብላ ታቦት ቀርጻ፣ መልክዐ ደርሳ፣ ምስል ስላ ታስተምራለች" ማለታቸው ነው፡፡ እንዲሁም ይህንኑ ንጉሥ የመታሰቢያም በዓል ሠርታ ታወድሳለች፣ ታከብራለች ይላሉ፡፡

አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በኢትዮጵያ ውስጥ ከነገሡት ነገሥታት አንዱ ሲሆን በዘመኑ ለሀገሩም ሆነ ለቤተ ክርስቲያኑ ብዙ ታላላቅ አስተዋጽዖዎችን አድርጓል፡፡ ሆኖም ሰው እንደ መሆኑ ስህተቶችና አነጋጋሪ ተግባራትንም ፈጽሟል፡፡ ልበ አምላክ ተብሎ የሚጠራው ንጉሥ ዳዊትም ቢሆን ከስህተት የጸዳ ንጹሕ ሰው አልነበረም፡፡ ታማኝ አገልጋዩ የነበረውን ኦርዮን አስገድሎ ሚስቱን ቀምቶ ታላቅ ኃጢአት ሠርቷል፡፡ ሆኖም ግን ከልቡ ንስሐ ስለ ገባ እግዚአብሔር በነቢዩ በናታን አማካይነት "*እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልሃል፤ አትሞትም*" ብሎታል፡፡ 2 ሳሙ. 12፡13 ስለሆነም ንስሐ ገብተው ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀው ሊሆን የሚችሉ ያለፉ ሰዎችን ኃጢአት ማንሳት ቁስል ለቁስል የሚሄዱ ዝንቦችን መምሰል ነው፡፡

ዋናው ነገር ግን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አፄ ዘርዓ ያዕቆብን "ጻድቅ፣ በምልጃቸው የሚረዱን" የማትል መሆኗ ነው፡፡ ለአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ታቦትም አልቀረጸችም፣ ምስልም አትቀርጽም፡፡ ይኽ ደረቅ ውሸት ብቻ ነው፡፡ በዚያውም ላይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሁለት እይታ (Two-dimensional) ብቻ ያላቸውን ሥዕላትን እንጂ ሦስት እይታ (Three dimensional) ያላቸውን ምስሎችን አትቀበልም፡፡ እነርሱ ግን የሥዕልንና የምስልን ልዩነት ስለማያውቁ፣ እንዲሁም ምንጫቸው የሆኑት አካላት የሚቀበሉት ሦስት እይታ ያላቸውን ምስሎችን ስለሆነ የማያውቋት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም እንደ እነዚያው መሰላቸው ነው፡፡

ለአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ግን ቤተ ክርስቲያኒቷ ታቦት አልቀረጸችም፣ መልክም አልደረሰችም፣ የመታሰቢያ በዓል ሠርታም አታወድሰውም፡፡ ሆኖም አንድ ቢታሪክ የታወቀ ሰው እንደ ታሪካዊ ሰውነቱ በቤተ ክርስቲያን በኩል ባይሆንም እንኳ በተለያዩ አካላት ሥዕል ሊሳልለት፣ ሐውልት ሊቆምለት ወዘተ ይችላል፡፡ ሆኖም ማንም ሰው እንደ ዜግነቱ የሚያደርገውን ሁሉ ቤተ ክርስቲያኒቱ ቅዱስ ብላ ስለ ተቀበለችው ነው ማለት የአላዋቂነት ብቃት ላይ መድረስ ነው፡፡ ለምሳሌ የሆኑ ሰዎች ለአፄ ኃይለ ሥላሴ መልክ ደርሰውላቸው ነበር፡፡ ታዲያ መልክ የተደረሰለት ሁሉ ቅዱስ ተብሏል ማለት ነው? በጭራሽ!

እንዲሁም "ይህንኑ ንጉሥ የመታሰቢያም በዓል ሠርታ ታወድሳለች፣ ታከብራለች" ያላችሁት እስኪ የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ በዓል ተደርጎ የተሠራው መቼ ነው? በየትኛው ቀኖናስ ላይ ነው የተሠራው? ይህን የመሰለ ውሸት መዋሸት ከቶ ማንን ለማስደሰት ይሆን? ምንስ ለማግኘት ይሆን? በመጽሐፍ ቅዱስ "ውሐሰት ርእሰ ዓመጻ - ሐሰት የኃጢአት ሁሉ ራስ ነው" የተባለውን ባይሰሙ ይሆን? ወይስ ባያምኑበት?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን "ለአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ታቦት ቀርጻለች"፣ "ጻድቅ ብላ ታከብረዋለች" እያሉ ይህን ያህል ሐሰት የሚናገሩ ተሐድሶዎች፣ ታዲያ ሌላውን ነገራቸውን ማን ሊያምናቸው ይችላል? ይህን የመሰለውን ማንም ሰው በቀላሉ ጠይቆ እውነቱን ሊያውቀው የሚችለውን ነገር የሚዋሹት ሳያውቁ ከሆነ ይህን ቀላል የሆነ ታሪካዊ ጉዳይ ካላወቁ ሌላውን ጥልቅና ረቀቂ የሆነውን ነገረ ሃይማኖታዊ ጉዳይ እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ? እንዲህ የጻፉት ይህ ነገር ሐሰት መሆኑን እያወቁ ዋሽተው ከሆነ ደግሞ እንደዚህ ያለውን ማንም ሰው ሊያውቀው የሚችለውን ነገር ያለ ሐፍረትና ፍርሃት የሚዋሹ ከሆነ ሌላው የሚሉት ነገርስ ውሸት ላለመሆኑ ምን ዋስትና አለ? ሌላው ነገራቸው ሁሉ ሐሰትና ማታለል መሆኑንም በየምዕራፉ ላይ የምናያቸው ነገሮች በግልጽ ይነግሩናል፡፡

3. ሦስተኛው ሐሰት፡- ቤተ ክርስቲያን አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ሁለት ሚስት ሲያገባ ሥርዓተ ተክሊል ፈጽማለታለች ማለታቸው ነው፡፡

◉ "እኚሁ ጻድቅ የተባሉት ንጉሥ ... በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት (በተክሊል) ሁለት ሚስቶችን እንዳገቡ ዜና ገድላቸውም ይናገራል፡፡ ... እኚህ ሰው ሁለት ሚስት ሲያገቡ ሥርዓቱን መፈጸም አልነበረባትም፡፡ ይሁን እንጂ በመቃወም ፋንታ "አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት" የሚለውን መለኮታዊ ትእዛዝ ንጉሡ ሲጥሱ ለኃጢአታቸው ተባባሪነቷ ሳያንስ . . ."

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በሁለት ማስት እንኳን ሥርዓተ ተክሊል ልትፈጽም ቀርቶ የእንዲህ ዓይነትን ድርጊት ስህተትነት ታስተምራለች እንጂ አትቀበልም፡፡ ይህን የመሰለ ነገር አድርጋም አታውቅም፡፡ ነገሥታት ይቅርና ማንኛውም ሰው የመሰለውን ማድረግ መብቱ ነው፤ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ቃልና ትእዛዝ ትናገራለች ታስተምራለች እንጂ ከዚያ አልፋ አታስገድድም፡፡ ስለሆነም ንጉሡ በራሱ መንገድ ያደረጋቸው ነገሮች የራሱ ድርጊቶች እንጂ የግለሰቦችን ስህተቶች ከቤተ ክርስቲያን ለማስጠጋትና ለማሳበብ መሞከር ፍጹም ስህተት ነው፡፡ በዚያውም ላይ ይህን ነገር "በተአምረ ማርያም መጽሐፍ ላይ እናገኘዋለን" የሚለው ሌላው ውሸት ነው፡፡ ተአምረ ማርያም ከላይ የተናገሯቸውን ሐሰቶች (ከ 1-3 የተገለጹትን) አይልም፡፡ ተአምረ ማርያም "አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ቅዱስ ነው፣ መታሰቢያ በዓል አለው፣ ሁለት ሚስት ሲያገባ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ተክሊል ፈጽማለታለች" አይልም፡፡

4. "ተአምረ ማርያምን ከወንጌል አብልጣ ታየዋለች" ማለታቸው

ይህም እንደ ተለመደው ለማደናገሪያ የቀረበ ውሸት ነው፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከማንኛውም መጽሐፍ በላይ ምንም ሊነጻጸርና ሊወዳደር በማይችል መልኩ አክብራና አልቃ የምታምነው መጽሐፍ ቅዱስን ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን ሌሎች መንፈሳዊ መጻሕፍትን እንደ አግባብነታቸው ታከብራቸዋለች፣ ትጠቀምባቸዋለችም፡፡ ከእነዚህ መካል አንዱ የእመቤታችንን ተአምር የያዘው ተአምረ ማርያም የተባለው መጽሐፍ ነው፡፡ ሆኖም ተአምረ ማርያም ከወንጌል በላይ ይከብራል ማለት ሐሰት ነው፡፡

እንግዲህ እነዚህን ለመግቢያ ያህል ለማሳያ አቀረብን እንጂ በየመጻሕፍቶቻቸው ገጾች ላይ የታጨቁት ይህን የመሳሰሉ ውሸቶች ብዙ ናቸው፡፡ ከብዙ ውሸቶቻቸው መካከል አንድ ሁለት ብቻ እንመልከትና ወደ ሌላው ጉዳይ እንሄዳለን፡፡

◎ "አንድ መልአክ በሁሉም ቦታ ይገኛል፣ መላእክት ምሉእ በኩለሄ ናቸው ብላ ቤተ ክርስቲያን ማስተማሯ . . ." በማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ብቻ የሆነውን በሁሉ ቦታ መኖርና መገኘት ለመላእክትም እንደምትሰጥ አድርገው አቅርበዋል፡፡ (መቅደስ የገቡ መፍቃን፣ ገጽ 26)

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መላእክት ምሉእ በኩለሄ ናቸው ብላ አታስተምርም፣ ይኸ ከእርሷ ይራቅ! ሁሉን አዋቂነት (ማእምረ ኩሉ)፣ ሁሉን ቻይነት (ከሃሊ ኩሉ)፣ በሁሉም ቦታ መገኘት (ምሉእ በኩለሄ) የሚባሉት ነገሮች ለእግዚአብሔር ብቻ የሚነገሩ፣ የእርሱ መገለጫዎች ብቻ የሆኑ ነገሮች ናቸው እንጂ የፍጡራን ገንዘቦች አይደሉም፡፡ ስለዚህም "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መላእክት በሁሉም ቦታ ይገኛሉ ብላ ታስተምራለች" ማለት ፍጹም ሐሰት ነው፡፡ የምትለውን ትምህርቷን መቃወም ሲያቅት የማትለውን ትላለች እያሉ መጻፍና የሐሰት ወሬ ማውራት የአቅመ ቢስነት መገለጫ ነው፡፡

◎ "በሌላ በኩል እግዚአብሔር በእርሷ ታላቅ ነገርን ሊያደርግ ከእንስተ ዓለም የመረጣትና ያከበራት የጌታችን እናት ቅ/ማርያምን ልንመለከት እንችላለን፡፡ በመልአኩ ብሥራት እንደተገለጸው ጸጋ የሞላባት ናት፡፡ ይህ ማለት ግን እንደ እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ ትገኛለች፣ ሁሉን ታውቃለች ወደሚል ድምዳሜ አያደርሰንም፡፡ . . . በእርግጥ በፈጣሪና በፍጡር መካከል ያለውን የባሕርይና የእውቀት ልዩነት ካላወቅን ትልቅ ስሕተት ውስጥ እንገባለን፡፡ ፍጡራንን ከፈጣሪ ጋር አስተካክለው የሚያዩ ወገኖች ችግርም ይኸው ነው፡፡" (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 164-5)

ይህም እንደዚሁ ከላይ እንደ ተገለጸው ያለ ተመሳሳይ ከንቱ የሐሰት ውንጀላ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም የምትሰጠው ክብር ግልጽና የታወቀ ነው፡፡ እርሱም መልዕልተ ፍጡራን መትሕተ ፈጣሪ ማለትም ከፍጡራን በላይ፣ ከፈጣሪ በታች የሚል ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ግን "እንደ እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ ትገኛለች፣ ሁሉን ታውቃለች" የሚል እምነትም ሆነ አስተምህሮ የለም፡፡ በሁሉ ስፍራ መገኘት (ምሉዕ በኩለሄነት) እና ሁሉን አዋቂነት (ማእምረ ኩሉ መሆን) የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቦች ብቻ መሆናቸው የታወቀ ነው፡፡ ስለዚህ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ፈጣሪና ፍጡርን አሳምራ ለይታ የምታውቅ ናት እንጂ "ፍጡራንን ከፈጣሪ እኩል ማድረግና ማስተካከል" የሚለው አይመለከታትም፡፡ የራስን አለማወቅ ወይም ችግር እንደ አጠቃላይ እውነታና የሌላውም ሁሉ ችግር እንደ ሆነ አድርጎ ማሰብ ጤነኛነት አይደለም፡፡ እኛ ይህን የቅድስት ቤተ ክርስቲያን እምነት እየገለጽን ያለነው፣ ወደፊትም በየጉዳዩ የምንገልጸውና ምስክር የምንጠቅሰው ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቀደምት ኦርቶዶክሳውያን አባቶች ትምህርት ስለሆነ እናንተም ከእነዚህ ምስክር አለን የምትሉ ከሆነ ማቅረብ እንጂ በስማ በለውና በይመስላል፣ እንዲሁም ደግሞ ለግል ጸሎትና ለታሪክ፣ እንዲሁም ይህን ለመሳሰለው ተግባር ያሉትን ነገሮች በመጥቀስ አይደለም፡፡

- "የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ በራሳቸው መካከል ከሚገኘው አነስተኛ መለያየት አይበልጥም።" (ኆኅተ ብርሃን፣ መጋቢት 2002፤ ገጽ 15)

ይህም ሌላ ከባድ ውሸት ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እነርሱ "ወንጌላውያን" ካሏቸው የፕሮቴስታንት ክፍልፋይ ድርጅቶች ጋር የሚነጻጸር አይደለም። ልዩነቱም የመዳንና ያለ መዳን ጉዳይ ስለ ሆነ ከሰማይና ምድር በላይ ይራራቃል። ተሐድሶዎቹ እንዳሉት የእነርሱ (በፕሮቴስታንት ውስጥ ያሉት ክፍልፋዮች) የእርስ በርስ ልዩነት የአንድ አባት ልጆች ስለሆኑ አነስተኛ ሊሆን ይችላል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከእነዚህ ድርጅቶች ጋር ያላት ልዩነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ላይ፣ በመዳን ትምህርት ላይ፣ በነገረ ክርስቶስ ላይ፣ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ላይ፣ በነገረ ቤተ ክርስቲያን ላይ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜና ዘይቤ ላይ፣ በሐዋርያዊነትና በትውፊት ላይ፣ በነገረ ቅዱሳን ላይ፣ ወዘተ ሁሉ በጣም የተራራቀ ነው። ስለዚህ "የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ በራሳቸው መካከል ከሚገኘው አነስተኛ መለያየት አይበልጥም" ያሉት ነገር ለመጠጋጋትና ለመመሳሰል ሲሉ ያደረጉት የማታለያና የማወናበጃ ውሸት ነው። ስንዴና እንክርዳድ ስለ ተመሳሰሉ ልዩነታቸው አነስተኛ ነው ሊባል አይችልም። ሆኖም ይህ አባባላቸው ወገንተኛነታቸውና አቅጣጫቸው ወዴት መሆኑን ግን ያሳያል።

ሌላው ውሸታቸው ደግሞ የኒቅያን ጉባኤ "የሐዋርያትን ሲኖዶስ የሚቃወም ሲኖዶስ" ማለታቸውና ከዚህም ጋር ሌሎች ሐሰቶችን መናገራቸው ነው። እንዲህ ይላሉ፦

- "በአራተኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ አካባቢ ላይ <u>የሐዋርያትን ሲኖዶስ በመሻር አይሁድን የሚበቀል</u> <u>ውሳኔ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች መነጨ</u>። አይሁድ ክርስትናን የሚቀበሉ ከሆነ በቅድሚያ ወደ አሕዛብነት መፍለስ አለባቸው ተባለ። . . . አይሁድ ወደ ወንጌል ሲመጡ (ክርስቲያን ሲሆኑ) የግዝረትን ሕግ፣ ሕገ ኦሪትን፣ የመሥዋዕትና የመቅደስ ሥርዓታቸውን፣ ከምድረ ግብጽ የወጡበትን የነጻነት በዓላቸውን (ፋሲካን)፣ እነዚህንና የመሳሰሉትን የማንነታቸውን መታወቂያዎች ማስቀመጥና የአሕዛብ ማንነት የተንጸባረቀባቸውን መታወቂያዎች መያዝ አለባቸው ተብሎ በኒቅያ ጉባኤ ሲወሰን ውሳኔው አይሁድን ከወንጌል ውጭ አደረጋቸው። "አይሁዶች ግርማዊነትዎ" የተሰኘው መጽሐፍ ደራሲ ዶክተር ዮራን ላርሰን ይህን ውሳኔ "በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እንደ አንድ ትልቅ አሳዛኝ ጉዳይ አድርጌ እመለከተዋለሁ" ይላሉ።" (ጮራ ቁ. 24፤ ገጽ 1-2)

እንግዲህ ይህ ደግሞ ሌላ የለየለት ጉድና ሐሰት ነው። በኒቅያ ጉባኤ የተሰበሰቡት ቅዱሳን አባቶች አርዮስና መሰሎቹ ይዘውት የተነሡትን የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነትና ከአብ ጋር በባሕርይ አንድ (Homoousios) መሆኑን የሚቃወም ጸረ ክርስትና የሆነና ለሰው ልጅ በእግዚአብሔር ቸርነት የተሰጠውን መዳን ከንቱ ሊያደርግ የተነሣውን ከባድ ኑፋቄ በጉባኤው ተከራረው አርዮሳውያንንና ግብረ አበሮቹን መልስ አሳጥተው ረትተው ቤተ ክርስቲያን ከጌታ የተቀበለችውን ሃይማኖት አጽንተው ይህን የሚገልጽ አንቀጸ ሃይማኖት አርቅቀው ተለያዩ። ከዚህም ጋር የትንሣኤ በዓል የሚውልበትን ዕለት አወሳሰን በተመለከተ የይትበሃል ልዩነቶች ስለ ነበሩ እነርሱን ወደ አንድነት የሚያመጡ ውሳኔዎችን ወሰኑ። ከዚህም ጋር ሃያ ቀኖናትን ቀንነዋል። ከእነዚያ ውስጥ ግን ተሐድሶዎች "<u>የሐዋርያትን ሲኖዶስ በመሻር አይሁድን የሚበቀል ውሳኔ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች መነጨ። አይሁድ ክርስትናን የሚቀበሉ ከሆነ በቅድሚያ ወደ አሕዛብነት መፍለስ አለባቸው ተባለ</u>" እንደሚሉት ያለ ውሳኔ ግን ፈጽሞ አልተወሰነም። እስኪ የትኛው የኒቅያ ጉባኤ ቀኖና ወይም አንቀጽ ነው እንዲህ የሚለው? ከሃያው የኒቅያ ቀኖናዎች መካከል "አይሁድ ክርስትናን የሚቀበሉ ከሆነ በቅድሚያ ወደ አሕዛብነት መፍለስ አለባቸው" የሚል አንድም ቀኖና የለም።

ስለዚህ "አይሁድ ወደ ወንጌል ሲመጡ (ክርስቲያን ሲሆኑ) የግዝረትን ሕግ፣ ሕገ ኦሪትን፣ የመሥዋዕትና የመቅደስ ሥርዓታቸውን፣ ከምድረ ግብጽ የወጡበትን የነጻነት በዓላቸውን (ፋሲካን)፤ እነዚህንና የመሳሰሉትን የማንነታቸውን መታወቂያዎች ማስቀመጥና የአሕዛብ ማንነት የተንጸባረቀባቸውን መታወቂያዎች መያዝ አለባቸው ተብሎ በኒቅያ ጉባኤ ሲወሰን ውሳኔው አይሁድን ከወንጌል ውጭ አደረጋቸው" ያሉት ሐሰት ነው፤ ምክንያቱም በኒቅያ ጉባኤ ላይ እንዲህ ያለ ውሳኔ አልተወሰነምና፡፡ በዚያውም ላይ የግዝረት ሕግ፣ የመሥዋዕትና የመቅደስ ሥርዓታቸው፣ የኦሪቱ በዓላት ሁሉም ለሐዲሰ ኪዳን ጥላዎችና ምሳሌዎች ነበሩ እንጂ አካሉ የሆነው አማናዊው ክርስቶስ ከመጣ በኋላ እንዳለ የሚቀጥሉ አልነበሩም፡፡ ስለዚህም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ፋሲካን በትንሣኤው፣ በዓለ ሰዊትን በበዓለ ጰራቅሊጦስ፣ በዓለ መጸለትን በበዓለ ጥምቀት፣ ግዝረትን በጥምቀት፣ የኦሪቱን መሥዋዕት በራሱ መሥዋዕትነት ተክቷቸዋል፡፡ ለምሳሌም የበዓለ ፋሲካን በክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው መተካቱን ሲገልጽ ቅዱስ ጳውሎስ "ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና" ይላል፡፡ 1 ቆሮ. 5፥7

በሐዋርያት ዘመን ከአይሁድ ወገን ወደ ክርስትና ይገቡ ከነበሩት መካከል ሕገ ኦሪቱን፣ ግዝረቱንና የመሳሰለውን ሥርዓተ ኦሪት ከጥምቀትና ከወንጌል ጋር አብረን እንይዛለን ብለው ሲያስቸግሩ የነበሩ "ቢጽ ሐሳውያን - ሐሰተኞች ወንድሞች - Judaizing Christians" የተባሉ ወገኖች ነበሩ፡፡ ለቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያዊ ተልእኮ ዋና ፈተናና መሰናክል ሆነው ሲያስቸግሩት የነበሩት እነዚያ ነበሩ፡፡ የመጀመሪያው የሐዋርያት ጉባኤ በኢየሩሳሌም የተካሄደው በዚህ ችግር ምክንያት ነበር፡፡ የሐዋ. 15 ተሐድሶዎች ሆይ፤ ወደ ክርስትና የሚገቡ አይሁድ ከነኦሪታቸውና መሥዋዕታቸው እንዳለ መግባት ነበረባቸው እያላችሁ መቆጨታችሁ በእውነት ማንነታችሁን ፍንትው አድርጎ ያሳያል፡፡ እናንተም የእነርሱ ወገኖች ናችሁ ማለት ነዋ! የሐዋርያት ስብከት፣ የሊቃውንት ድካም ሁሉ ለምን ሆነና? ይህም የሚሳየው በአንድ በኩል የመዋሸት ብቃታችሁ እያደገ መሄዱን ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎችን ከወንጌል ወደ ኦሪት፣ ከጥምቀት ወደ ግዝረት ለመመለስ ያላችሁን ስውር ዓላማ ነው፡፡

"በአራተኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ አካባቢ ላይ 'አይሁዶች ግርማዊነትዎ' የተሰኘው መጽሐፍ ደራሲ ዶክተር ዮራን ላርሰን ይህን ውሳኔ "በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እንደ አንድ ትልቅ አሳዛኝ ጉዳይ አድርጌ እመለከተዋለሁ" አለ ያሉትን ሰውዬውን አላውቀውም፡፡ ነገር ግን ምናልባት ሰውዬው አይሁዳዊ ወይም አይሁድ ዘመም ከሆነ ለእርሱ የኒቅያ ጉባኤ ውሳኔ እንዳለው "አሳዛኝ" ሊሆንበት ይችላል፡፡ የኒቅያ ጉባኤ ውሳኔ ለአርዮሳውያንና ለአይሁዳውያን በእውነትም አክርካሪያቸው የተመታበት "አሳዛኝ" ጉባኤ ነበር፤ ምክንያቱም የእነርሱ ስህተታቸው የተጋለጠበትና በዓለም አቀፋዊ መድረክ የተወገዘበት ውሳኔ ስለሆነ ነው፡፡ ከውሸታችሁ ባሻገር የአርዮሳውያንና የአይሁዳውያን ሐዘን ሐዘናችሁ መሆኑ እናንተ ከእነ ማን ወገን መሆናችሁን ነግሮናልና እንድናውቃችሁ ስለ ረዳችሁን እናመሰግናችኋለን፡፡

እንዲህ በግልጽ ለአይሁድና ለአርዮሳውያን የሚቆጩ፤ በአንጻሩ ደግሞ በኒቅያ ተሰብስበው ሃይማኖትን የጠበቁና ያጸኑ ቅዱሳን አባቶቻችን ሠለስቱ ምእትን የሚነቅፉ እነዚህ "ክርስቲያን ነን" ለማለት ይችላሉን? የሠለስቱ ምእትን ጉባኤና ውሳኔዎቹን እንደማይቀበሉ እንደዚህ በይፋ የሚናገሩ እነዚህ "የቀደሙ ሊቃውንት አባቶች ልጆች ነን" ሲሉ የሠለስቱ ምእት ልጆች ካልሆኑ የቀደሙ ሊቃውንት ሲሉ እነ ማንን ማለታቸው ነው? የሠለስቱ ምእት ልጆች ካልሆኑና እነርሱን ከነቀፉ "የቀደሙ ሊቃውንት" የሚሏቸው እነ አርዮስንና መሰል መናፍቃንን ነው ማለት ነዋ! እነርሱው ራሳቸው ነገሩን እኮ! ታዲያ በክርስትናው ዓለም በሙሉ ተቀባይነት ያለውን የኒቅያን ጉባኤና ሠለስቱ ምእትን የማይቀበሉ እነዚህ በኢትዮጵያ የነበሩ ነገሥታትንና የተለያዩ ሰዎችን ቢያብጠለጥሉ ምን ይገርማል? በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቀው ታሪክ ላይ እንኳ ለመዋሸት ይህን ያህል ከደፈሩ በኢትዮጵያ ብቻ ሊታወቁ በሚችሉ ታሪኮች ላይ ቢዋሹ ምን ይገርማል!

- "የሰው ዘር ሁሉ በራሱ ስፍራ፣ በህል፣ *ሃይማኖት* ውስጥ እንዳለ ሆኖ በወንጌል የተገለጸውን የእግዚአብሔር ጽድቅ መቀበል መቻሉ መዘንጋት የለበትም።" (ሎራ ቁ. 24፣ ገጽ 1)

ይህ ደግሞ የሚገርም ነገር ነው። ሰው በራሱ ስፍራና ባህል ሆኖ ወንጌልን መቀበል መቻሉ እውነት ነው። ሆኖም "በራሱ ሃይማኖት ውስጥ እንዳለ ሆኖ በወንጌል የተገለጸውን የእግዚአብሔር ጽድቅ መቀበል መቻሉ መዘንጋት የለበትም" የሚለው ግን የሚገርም ነው። እያንዳንዱ ሃይማኖት ስለ ሕይወት፣ ስለ ሰው መዳን፣ ስለ ጽድቅና ኩነኔ፣ ወዘተ የሚለው የየራሱ ትምህርት አለው። በወንጌል የተገለጸው የእግዚአብሔር ጽድቅ ደግሞ በሌላ በማንኛውም ሃይማኖት ከተገለጸው የመዳን መንገድ የተለየ ነው። ለምሳሌ ስለ ሰው ሕይወትና ስለ መዳን ምንነትና እንዴትነት፣ ስለ ሰው ሕይወት ግብና ፍጻሜ፣ ወዘተ ቡድሂዝም የሚለው እስልምና ከሚለው፣ እነዚህ የሚሉት ፓንቴይዝም ከሚለው፣ እነዚህ የሚሉት ደግሞ ዞራስትሪያኒዝም ከሚለው፣ ዞራስትሪያኒዝም የሚለው ሂንዱይዝም ከሚለው፣ . . . አንዱ የሚያምነውና የሚለው ሌላው ከሚያምነውና ከሚለው የተለየ ነው፤ ክርስትና የሚለው ደግሞ ከእነዚህ ሁሉ የተለየ ነው። እንዲያማ ባይሆን ኖሮ በክርስትና እና በሌሎቹ እምነቶች መካከል ልዩነት ባልኖረ ነበር።

ታዲያ እንዲህ ስለ መዳን የተለየ የሆነ እምነትና መንገድ ባለው በሌላ ሃይማኖት ውስጥ ያለ ሰው ከዚያ እምነትና አስተምህሮ ሳይወጣ በወንጌል የተነገረውን የመዳን መንገድ ደርቦ ሊቀበል የሚችለው እንዴት አድርጎ ነው? እንደ እነርሱ አባባል ከሆነ አንድ ሰው ሂንዱ ሆኖም ሂንዱነቱን ሳይተው ክርስቲያን መሆን፣ እስላም ሆኖም ከእስልምናው ሳይወጣ ክርስቲያን መሆን፣ ፓንቴይስት ሆኖም ክርስቲያን መሆን፣ ወዘተ ይችላል ማለት ነው! የማምነው እምነት ልክ ነው ብሎ ለሚያምን ሰው ግን እንደ እናንተ ተቃራኒ ነገሮችን በይምሰል መቀበልና አጫፍሮ ማመን አይቻልም። ቅዱስ መጽሐፍ የሚለን እንዲህ ነውና፦

> ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው? ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም ከጣዖት ጋር ምን መጋጠም አለው? 2 ቆሮ. 6፥14-16

ይህ አስተሳሰብ አሁን አሁን እየተንጸባረቀ ያለው "ሁሉም ሃይማኖት ትክክል ነው፣ ወደ እግዚአብሔር ያደርሳል" እየተባለ ያለው የዩኒቨርሳሊዝም አስተሳሰብ ነው። በውጭ ሲታዩ ስለ ክርስቶስ ብቸኛ መድኃኒትነትና አዳኝነት የሚሰብኩ ለመምሰል ይሞክራሉ፤ በተግባር ውስጣቸውን ሲገልጡት ግን እንደዚህ ዓይነት ሆነው ይገኛሉ። ስለዚህ "የሰው ዘር ሁሉ በራሱ *ሃይማኖት* ውስጥ እንዳለ ሆኖ በወንጌል የተገለጸውን የእግዚአብሔር ጽድቅ መቀበል ይችላል" የሚለው አባባል ስለ ሃይማኖት ምንነት ካለማወቅ እና መጽሐፍ ቅዱስን ካለማመን የመጣ ስህተት ነው።

በርግጥም ትልቁ ችግራቸውና የችግራቸው ሁሉ ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ በሙሉ አለ መቀበላቸውና አለማመናቸው ነው። ለዚህም ማሳያ የሚከተሉት አባባሎቻቸው እንመልከት፦

- ". . . ጌታ ኢየሱስ 'ግፍየሙ እግዚኦ ለእለ ይገፍዑኒ ጽብየሙ እግዚኦ ለእለ ይጸብዑኒ - አቤቱ በእኔ ላይ ግፍ የፈጸሙትን ሰዎች ፍዳ ግፍዕ ክፈላቸው። እየተጣሉኝ ያሉትንም ተጣላቸው' ሲል ለአባቱ ከስ አቅርቦ ነበር የሚሉ የሐሰት ምስክሮች ምንም ዛሬ ቢቆሙበትም ቅንጣት ታህል እውነትነት እንደ ሌለበት የታወቀ ነው።" (ሎራ ቁ. 3፣ ገጽ 25-26)

- ". . . እንባቢ ሆይ! ሰይጣን ግን ዛሬ በአረማውያን አፍ ሳይሆን ክርስቲያን ነን በሚሉ አፍ 'ግፍየሙ እግዚኦ ለእለ ይገፍዑኒ ጽብየሙ እግዚኦ ለእለ ይጸብዑኒ' እያለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግፍ የዋሉበትን ከሷቸው ነበር ብሎ ያውም ስቅለቱ በሚታሰብበት ዕለት ስሙን እያጠፋው ነው።" (ሎራ ቁ. 6፣ ገጽ 25)

እንግዲህ እዚህ ላይ ምን ለማለት እንደ ፈለጉ ግልጽ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን በዕለተ ስቅለት በውርድ ንባብ በዜማ ማኅዘኒ የሚደርሰውን ንባብ ማለታቸው ነው፡፡ ይህ "ግፍዖሙ እግዚኦ ለእለ ይገፍዑኒ ጽብዖሙ እግዚኦ ለእለ ይጸብዑኒ - አቤቱ የሚበድሉኝን በድላቸው፣ የሚዋጉኝንም ተዋጋቸው" የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመዝሙረ ዳዊት በመዝሙር 34 (35) ላይ የሚገኝ ቃል ነው፡፡ ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለን የእግዚአብሔር ቃል መናገር ኃጢአት ከሆነ ጽድቁ ምን ሊሆን ነው? በዚያውም ላይ ደግሞ *"ጌታ ኢየሱስ 'ግፍዖሙ እግዚኦ ለእለ ይገፍዑኒ ጽብዖሙ እግዚኦ ለእለ ይጸብዑኒ - አቤቱ በእኔ ላይ ግፍ የፈጸሙትን ሰዎች ፍዳ ግፍዕ ክፈላቸው፡፡ እየተጣሉኝ ያሉትንም ተጣላቸው' ሲል ለአባቱ ክስ አቅርቦ ነበር የሚሉ የሐሰት ምስክሮች ምንም ዛሬ ቢቆሙበትም . . ."* የተባለው ያው የተለመደ ውሸት ነው፡፡ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎ ለአባቱ ክስ አቅርቦ ነበር ብላ አታውቅም፡፡ ሆኖም ቃሉ የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ስለሆነ ይነበባል፡፡ ከአንዱ የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል መካከል "ይሄ ይባላል፣ ያ ግን አይባልም፤ ይህ ቅዱስ ነው፣ ያ ደግሞ ርኩስ ነው" እያሉ ለመከፋፈል ማን ሥልጣን ሰጣቸው? ራሳቸውን ከቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል በላይ ያደርጉ ዘንድ እስከዚህ ድረስ ትዕቢትንና ዕብሪትን ከየት አገኙት? የእነዚህ ምንጫቸው ይታወቃልና ያው ከአባታችሁ ካልሆነ በስተቀር ከየት ይሆናል?

እንግዲህ ይህ ቢያንስ ሁለት *መሠረታዊ* ማንነታቸውን ያሳየናል፡፡ እነዚህም በአንድ በኩል ከጥላቻቸው የተነሣ ቤተ ክርስቲያን የማትለውን እንደምትል እያስመሰሉ በሐሰት *መ*ክሰስ ("ለአባቱ ክስ አቅርቦ ነበር የሚሉ የሐሰት ምስክሮች ምንም ዛሬ ቢቆሙበትም" በማለት) ዋና ግብራቸውና ስልታቸው *መሆኑን* ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ *መጽሐፍ* ቅዱስን ሙሉ በሙሉ የማያምኑበት *መሆኑን* ነው፡፡ *መዝሙረ* ዳዊት እንቀበለዋለን ከሚሉት ከስልሳ ስድስቱ *መጽሐፍ* ቅዱስ ውስጥ ያለ ነው፡፡ እንቀበለዋለን ከሚሉት *መጽሐፍ* ቅዱስ ውስጥ አንዱ ከሆነው *መጽሐፍ* ከመዝሙረ ዳዊት ውስጥ የማይቀበሉት ክፍል ካለ እንዲህ እንዲህ እያሉ *መመ*ዘኛቸው እነርሱን የመሰላቸው ብቻ ስለሆነ ባልመሰላቸው ቁጥር እየቀነሱትና እያወጡት ይሄዳሉ ማለት ነው፡፡ የዚህ አካሄድ *መዳረሻው* የት ይሆን?

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ *መዳን* የምታስተምረውን ሽምጥጠው በመካድ የሚዳነው በዚህ *መንገድ* ነው ያለች ለማስመሰል የእነርሱን የስህተት ትምህርት ተቀብሎ በእነርሱ የሞት *መንገድ* የማይሄደውን ሰው ሁሉ "በሽታውን ቢያውቅም *መድኃኒቱን መውሰድ* ባልጀመረ በሽተኛ" ይመስሉትና በመቀጠልም እንዲህ ይላሉ፡- "የታዘዘለትን *መድኃኒት* በመውሰድ ፋንታ ከቤተ ክርስቲያን ፀውድ በሚገዙ ጉዝጓዝ፣ ፅጣንና ሰንደል ወዘተ የሚታጀበውን የቡና *መንፈስ* ይማለላል፡፡" (ጮራ ቁ. 8፣ ገጽ 22) እስኪ ሕሊና ላለው ሰው የቤተ ክርስቲያኒቷ የመዳን ትምህርት ይህ ነውን? ይህን ቤተ ክርስቲያን የምትደግፈውና አድርጉ የምትለው ነው ብሎ *መጻፍ* ምን ያህል ያውቁብኛል አለማለትና የክፋት ዳርቻ ነው!

## 1.13 ከእምነት ይልቅ በስሜት ሕዋሳት (በማየት፣ በመስማት . . .) ላይ መመሥረት

ሌላው የተሐድሶዎች *መሠረታዊ መነሻ* ከእምነት ይልቅ በስሜት ሕዋሳት በሚዳሰሰውና በሚታየው ነገር ላይ የተመሠረተ *መሆኑ* ነው፡፡ ለማሳያም የሚከተሉትን እንመልከት፡-

- "አብርሃም በፀጸደ ነፍስ ባለበት ሁኔታ በምድር የሚደረገውን ሁሉ ያውቃል ማለት የሚታመን ቀርቶ የማይመስል ነው፡፡" (ጮራ ቁ. 38፣ ገጽ 17)
- "ጌታችን ስለ አብርሃም ሲናገር አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤትን አደረገ፣ አየም፣ ደስም አለው ብሏል፡፡ (ዮሐ. 8፡56) ጌታችን በተወለደ ጊዜ አብርሃም በአካለ ሥጋ አልነበረም፣ ታዲያ እንዴት አድርጎ አይቶ ደስ አለው? በፀጸደ ነፍስ ሆኖ ስላወቀ ነው እንጂ ስለ ተባለው፡- ጌታ ስለ አብርሃም የተናገረው ይህ ቃል አብርሃም ከሞተ በኋላ በፀጸደ ነፍስ ሳለ የተከናወነና ከጌታ ልደት ጋር የተያያዘ ስለ መሆኑ የሚጠቁም ፍንጭ በጥቅሱ ውስጥ ፈጽሞ አይገኝም፡፡ . . . ከዚህ ይልቅ ጥቅሱ አብርሃም ከሞተ በኋላ ሳይሆን በፀጸደ ነፍስ ሳለ የተከናወነን ድርጊት *የሚገልጽ መሆኑን በቃሉ መሠረት ማስረዳት ይቀላል፡፡*" (ጮራ ቁ. 38 ገጽ 17)

የሃይማኖት መሠረቱ መምሰልና መስሎ መታየት ነውን? ወይስ ደግሞ ለማስረዳት ቀላል ሆኖ መገኘት ነውን? ረቂቅ ስለ ሆነው ነገረ ሃይማኖት ይቅርና በዚህ ዓለምና በዙሪያዋ ያሉ ነገሮችን በተመለከተ ሊታወቅ ስለሚችለው እውቀት መገኛና የማወቂያ መንገድ ጉዳይ እንኳ በራሽናሊስቶች (Rationalists) እና በኢምፒሪሲስቶች (Empiricists) መካከል ከፍተኛ ክርክርና የተራራቀ አስተሳሰብ አለ፡፡ ኢምፒሪሲስቶች እውቀት የሚገኘው በቅርብ ከሚገኘውና በስሜት ሕዋሳቶቻችን አማካይነት ልናየው፣ ልንጨብጠውና ልንደርስበት ከምንችለው ነገር በመነሣት ነው ሲሉ ራሽናሊስቶች ደግሞ ይህን በመቃወም የስሜት ሕዋሳቶቻችን አስተማማኝ የእውቀት ምንጮች አይደሉም ሲሉ ይሞግታሉ፡፡ ሃሳባቸውን ሲያስረዱም ለምሳሌ ይላሉ፣ ቀስተ ደመና ከሩቅ ሲያዩት ቀለም ሠርቶ አካል ገዝቶ ግዘፍ ነሥቶ ያለ ይመስላል፣ ሲጠጉት ግን አይጨበጥም፡፡

እንዲሁም ሜዳ ላይ ለጥ ያለን አስፋልት ቀን በጠራራ ፀሐይ ሲያዩት ውኃ የተኛበት ይመስላል (Mirage)፤ ሲሄዱበት ግን ውኃ የለውም፡፡ ስለዚህም የስሜት ሕዋሳት አስተማማኝ የእውቀት ምንጭ አይደሉም በማለት የኢምፒሪሲስቶችን መነሻና አካሄድ ስህተትነት ለማሳየት ይከራከራሉ፡፡ እንግዲህ በሰዎች ምርምር ሊታወቅ ስለሚችለውና በሥነ ፍጥረት ዓለም ውስጥ ስላለው ነገር የእውቀት አገኛኘት እንኳ የስሜት ሕዋሳቶች ይህን ያህል የሚሞገቱ ከሆነ ከእግዚአብሔር ለተገለጠው ረቂቅና ሰማያዊ ለሆነው ሃይማኖታዊ እውቀት መነሻውና መሠረቱ የአንድ ነገር ለሰዎች መስሎ መታየቱ ወይም ለማስረዳት ቀላል ሆኖ መገኘቱ ሊሆን የሚችለው በምን አግባብ ነው?

የሃይማኖት መለኪያው ለማስረዳት ቀላል ሆኖ መገኘት ከሆነ የክርስትና ሃይማኖት ሁለንተናው ለማስረዳት ከባድ በሆኑ ነገሮች የተሞላ ስለሆነ ለእነርሱ ዓይነት ሰዎች ሊገባቸው አይችልም ማለት ነው፡፡ እስኪ በክርስትና ሃይማኖት ለማስረዳት ቀላል ነው የሚባለው የትኛው ምሥጢር ነው? ምሥጢረ ሥላሴ ነው? ወይስ የአምላክ ሰው የመሆን ምሥጢር (ምሥጢረ ሥጋዌ)? ወይስ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን? ወይስ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነቱን ሳይተው ባሕርዩ ሳይለወጥ ሰው ሆነ ብሎ መናገር? ወይስ አምላክ ስለ እኛ ሲል በመስቀል ላይ ሞተ ብሎ ማስተማር? ቅዱስ ጳውሎስ "ጥበበኛ የት አለ? ጻፊስ የት አለ? የዚች ዓለም መርማሪስ የት አለ? እግዚአብሔር የዚችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አላደረገምን? በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን በጥበቧ ስላላወቀች በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኗልና። . . . ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባልና፣ የእግዚአብሔርም ድካም ከሰው ይልቅ ይበረታልና" ያለው ለከንቱ ነውን? 1 ቆሮ. 1፡20-25 እንደዚሁም "እንግዲህ ሁል ጊዜ ታምነን በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና" የተባለውስ ለከንቱ ኖሯልን? 2 ቆሮ. 5፡6

ሃይማኖት ማለት ለሰዎች ለማስረዳት ቀላል የሆነውን ነገር መከተል ቢሆን ኖሮ "ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ መከራ ቢቀበልም፣ ቢሞትም በባሕርዩ ከአብ ጋር አንድ ነው፣ የባሕርይ አምላክ ነው" ከሚለው ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ ይልቅ የእነ አርዮስ "የወልድ ባሕርይ ከአብ ባሕርይ የተለየ (ሌላ) ነው፣ የሞተውም የባሕርይ አምላክ ስላልሆነ ነው" የሚለው የተሻለ ቀላል ነበር፡፡ አርዮስ ለጊዜውም ቢሆን ብዙ የሃሳቡ ደጋፊዎችና ተከታዮች አግኝቶ የነበረውም አስተሳሰቡ ከእነ አሪስቶትል የግሪካውያን ፍልስፍናና በዚያን ዘመን ከነበረው የግሪኩ ዓለም አጠቃላይ አስተሳሰብ ጋር የተቀራረበና ለእነርሱ የተስማማ ስለ ሆነ ነበር፡፡ "እግዚአብሔር አንድ ነው፣ በአንድነቱ ውስጥ ልዩ ሦስትነት አለው" ከማለት ይልቅ እንደ አይሁድና እስማኤላውያን "አንድ ገጽ ነው" ማለት ለመረዳት የበለጠ አይቀልምን? ሆኖም የእውነት መለኪያው ለማስረዳትና ለመረዳት ያለው ቅለትና ክብደት አይደለም፡፡

እንኳንስ በነገረ ሃይማኖት ይቅርና በቁስ አካል ጠባይ ጥናት እንኳ የነገሩ ርቀትና ውስብስብነት የሚወሰነው ባለው ተጨባጭ እውነታ ላይ እንጂ በሰዎች የመረዳት መጠን ወይም በሰዎች ዘንድ ለመታወቅ ባለው ቅለትና ምቾት አይደለም፡፡ ለምሳሌ በጣም ጥቃቅን ነገሮች ናቸው የሚባሉትን

አቶሞች በመፈልቀቅ የሚገኘው የኑክሌር ኃይልና በዚያ ዙሪያ ያለው ውስብስብ ጥልቅ ተፈጥሯዊ ነገር እግዚአብሔር ባስቀመጠው ሁኔታ እንጂ በመረዳትና በማስረዳት ቅለት ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡ ስለሆነም የተሐድሶዎች የእምነት መነጽራቸው የዛገና የተበላሸ ነው፣ ሚዛናቸውም የተሳሳተ ነው፡፡

## 1.1.4 ተገቢ ያልሆኑ አባባሎችንና ጸያፍ አገላለጾችን መጠቀም

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በየመጻሕፍቶቻቸው ካሉት አግባብ ያልሆኑ ጸያፍ አባባሎቻቸው መካከል የተወሰኑትን ለአብነት እንመልከት፡፡

- " . . . ስለዚህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ <u>ከራሱ ልምምድ በመነሳት</u> እያንዳንዱን የእናንተን ችግርና ኃዘን እንደዚሁም <u>እያንዳንዱን ፈተናችንን አውቆ</u> በእነዚህ ሁሉ አሸናፊዎች እንድንሆን <u>በሙሉ መረዳት</u> ከጎናችን ይቆም ይችል ዘንድ እንደ እኛው ሰው ሆኖ ከኃጢአት በቀር በሆነው ሁሉ ሊካፈል ወደ ኑሯችን ገባ፡፡" (ጠማረ ጽድቅ፣ ገጽ 45)

    - ይህ አባባል እርሱ ሰው ከመሆኑ በፊት የእኛን ማንነት ሙሉ በሙሉ ኢየውቅ የነበረና ፍጹም እውቀት ያልነበረው ያስመስለዋል፡፡ እንዲሁም እንደ ፍጡራን በልምምድ ያገኘው እውቀት ያለው የሚያስመስል አባባል ነው፡፡ ሆኖም ሰው በመሆኑ ግን እኛን ሊያድነን መጣ እንጂ ቀድሞ የጎደለው እውቀት ኖሮ አሁን ሰው በመሆኑ የተጨመረለት አንዳችም እውቀት የለም፡፡

- "ጴጥሮስ ኃጢአት ውስጥ እንዳይገባ ክርስቶስ ይጸልይለት ነበር፡፡ . . . <u>ኢየሱስ በፍቅር የተናገረው ግቡን አልመታም</u>፡፡" (ጠማረ ጽድቅ፣ ገጽ 65)

    - የጌታችን ቃል ሳይፈጸም የቀረና ዓላማውን ያላሳካ የሚያስመስል የተሳሳተ አባባል ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት አባባሎች የሚያሳዩት ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ዕሩቅ ብእሲ (ሎቱ ስብሐት) የመቁጠር አደገኛ አርዮሳዊ አዝማሚያን ነው፡፡ ፕሮቴስታንታዊነት በውስጡ ስውር አርዮሳዊነት (Latent Arianism) ያለው መሆኑ የታወቀ ነው፡፡

- "ክርስቶስ ለዓለም በመስቀል ላይ የውርደትን ሞት የሞተና በዓለም ታርዶ የተቀበረ ችግረኛ ነው፡፡" (ጠማረ ጽድቅ፣ ገጽ 90)

    - ይህ በጣም ጸያፍ አነጋገር ነው፡፡

- "ዮሴፍ የ17 ዓመት ወጣት በነበረ ጊዜ የአባቱን መንጋዎች ለማሰማራት ከባላና ከዘለፋ ከተወለዱት ወንድሞቹ ጋር ይሄድ ነበር፡፡ ማታ ማታ ወደ ቤት ሲመለሱ ዮሴፍ ወንድሞቹ ያደረጉትን መጥፎ ነገር ሁሉ ለአባቱ ይናገር ነበር፡፡ ዮሴፍ ምንም እንኳ ያደገ ሰው ቢሆን በሰው ላይ ማሳበቅን ገና አልተወም ነበር፡፡ . . . ከቤተሰቡ እንደ ማዕድን የተቆፈረው ዮሴፍ እነሆ ከመጠን በላይ ስለ ራሱ የሚያስብ፣ ትዕቢተኛና ስለ ሌሎች ሰዎች ጥፋት የሚያወራ ወጣት ነበረ፡፡" (ፅሙራ ቁ. 21፣ ገጽ. 19-20)

    - ይህ ከልጅነቱ ጀምሮ እጅግ አስተዋይና የዋህ ከነበረው፣ ረድኤተ እግዚአብሔር ያደረበት ስለ መሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚነግረን ከዮሴፍ ታሪክ ተቃራኒ የሆነ የዮሴፍን መልካምነት ጥላሸት ለመቀባት ሲባል የተፈጠረ እንግዳ ድርሰት ነው፡፡

## 1.1.5 የነገረ ሃይማኖታዊ እውቀት ድህነት መገለጫዎች

በየጽሑፎቻቸው ላይ የነገረ ሃይማኖታዊ እውቀት ድህነት፣ በተለይም ደግሞ ኦርቶዶክሳዊውን የክርስትና አስተምህሮ ከማወቅ በጣም ሩቅ የመሆናቸው ነገር ጎሆድ ወጥቶ ይታያል፡፡ በጥቂቱ ለማሳያ ብቻ የሚከተሉትን እንይ፦

◉ "<u>ሰውን ኃጢአተኛ ባሰኘው ኃጢአተኛ ባሕርዩና ከኃጢአተኛ ባሕርዩ የተነሣ ሰው በሠራው ኃጢአት ላይ መለኮታዊ ቁጣ ሊገለጽ ተገባ፡፡ እንዲሁም ከሆነ ሰው ኃጢአትን የሚሠራው በኃጢአተኛ ባሕርዩ ግፊት እንደ ሆነ ይታወቃል</u>፡፡ ማቴ. 7፥16-18" (ሥራ ቁ. 2፤ ገጽ 6)

- ኃጢአት የሰው የባሕርዩ አይደለም፤ የሰው ባሕርዩ ኃጢአተኛ አይደለም፡፡ ኃጢአት የባሕርያችን ቢሆንማ ኖሮ ኃጢአትን መሥራት አያስፈርድብንም ነበር፤ ምክንያቱም አንድ ነገር በባሕርዩ ያለን ነገር አለማድረግ አይችልምና፡፡ ለምሳሌ ብርሃን ሆኖ መጨለም፣ እሳት ሆኖ አለመሞቅ አይቻልም፡፡ ሰውም ሆኖ አለመራብና አለመጠማት፣ አለማዘንና አለመደሰት አይችልም፤ ይህ የባሕርዩ ነውና፡፡ ኃጢአት ግን የባሕርይ ሳይሆን ሰው በነጻ ፈቃዱ ወድዶና ፈቅዶ የሚያደርገው፣ ሲፈልግ ደግሞ እርግፍ አድርጎ ሊተወው ሥልጣንና መብት ያለው ነገር ነው፡፡ ንስሐ መግባት የተቻለውም እኮ ኃጢአት የባሕርይ ባለመሆኑ ነው፤ የባሕርይ ቢሆንማ ኖሮ ንስሐ መግባት፣ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ መመለስ ባልተቻለ ነበር፡፡ ስለዚህ ይህን አባባላቸውን በቅንነት እንመልከተው እንኳ ብንል የነገረ ሃይማኖት እውቀት ድህነት ውጤት ነው፡፡

◉ "ለምንድን ነው ሰው ኃጢአትን ያለ መቸገር በቀላሉ የሚሠራው? ምክንያቱም <u>ልቡ ከተፈጥሮው ክፉ ስለሆነ ነው</u>፡፡" (ጠማረ ጽድቅ፣ ገጽ 22)

- ይህም ከላይ እንደ ተገለጠው ያለማወቅ የፈጠረው ስሕተት ነው፡፡ የሰው ልቡ ከተፈጥሮው ክፉ አይደለም፡፡ ከተፈጥሮው ክፉ ሆኖ ተፈጠረ ከተባለማ አንደኛ ክፉ አድርጎ የፈጠረው እግዚአብሔር ነው ያሰኛል፤ ይህም ይቅር ይበለንና እግዚአብሔርን ክፉ ወደ ማድረግ ይሄዳል፡፡ እንደዚሁም የሰው ልቡ ከተፈጥሮው ክፉ ከሆነ ክፉ ብንሆንና ክፉ ብናደርግ እኛ ሊፈረድብን አይገባም ያሰኛል፡፡ ምክንያቱም ችግሩ የእኛ ሳይሆን ስንፈጠር ክፉ ሆነን መፈጠራችን ነው ያሰኛልና፡፡}

- መጽሐፍ ስለ ሰው ክፋት ጻርቶ ሲናገር እንኳ የሚለው "የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው፤ ማንስ ያውቀዋል?" ይላል እንጂ ወደ ተፈጥሮው ሄዶ "ተፈጥሮው ክፉ ነው" አይልም፡፡ ሰው ክፉና ተንኰለኛ የሚሆነው በተፈጥሮው እንዲያ እንዲሆን ሆኖ በመፈጠሩ ሳይሆን በራሱ ነጻ ፈቃድ በሚመርጠው ነጻ ምርጫ ምክንያት ነው፡፡ ለዚህ ነው ከዚሁ ቃል በመቀጠል እግዚአብሔር "እኔ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ እንደ መንገዱ፥ እንደ ሥራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ ልብን እመረምራለሁ ኩላሊትንም እፈትናለሁ" ያለው። ኤር. 17፥9-10 ክፋት የሰው የራሱ ምርጫው ሳይሆን በግዴታ የተጣበቀበት የባሕርዩ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ሰው ወድዶና መርጦ ባላደረገው ነገር "ለሰው ሁሉ እንደ መንገዱ፣ እንደ ሥራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ ልብን እመረምራለሁ፣ ኩላሊትንም እፈትናለሁ" ለምን ይላል? በዚህም ላይ የሰው ልቡ በተፈጥሮ ክፉ ከሆነ ከሰዎች ወገን ደጋጎችና ጻድቃን የሆኑ እንዴት ሊገኙ ቻሉ? ስለሆነም ይህ ዓይነቱ ሃሳቡና አባባል ነገረ ሃይማኖትን በግምትና በድፍረት ከመናገር የሚመጣ ስሁተት ነው፡፡

◉ "በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሁሉ የኃጢአትን ይቅርታ ብቻ ሳይሆን በአዲስ ልደት አዲስ ሕይወት እንደሚያገኝ ተረድተናል፡፡ ከእግዚአብሔር ይወለዳል፡፡ ከዚህም የተነሣ <u>የመለኮታዊ ሕይወትና የመለኮታዊ ባሕርይ ባለቤት ይሆናል</u>፡፡" (ጠማረ ጽድቅ፣ ገጽ 56)

- ይህ ደግሞ በእግዚአብሔር ባሕርይ (Ousia) እና በእግዚአብሔር ባሕርይ መገለጫዎች (Energia) መካከል ያለውን ልዩነት በተመለከተና በዚህ መሠረታዊ ጉዳይ ዙሪያ ያሉ ነገሮችን ካለማወቅ የመጣ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ከታች በመዳን ትምህርት ክፍል ላይ ተዳስሷልና እዚያ ላይ መመልከት ይቻላል፡፡

# 1.2 ጥንተ ታሪክ ዘመናፍቃን

## 1.2.1 "መናፍቅ" ምንድን ነው? ለምንስ ይባላል?

*ስለ መናፍቃን ምንነት ለመረዳት መጀመሪያ ስለ ሃይማኖት ምንነት ማንሣት ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም መመዘኛው ሃይማኖት ነውና፡፡*

### 1.2.1.1 ሃይማኖት ምንድን ነው?

ሃይማኖት እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጅ የገለጠው መግለጥ ነው፤ ሃይማኖት የሰው ልጅ ሊቀበለው በሚችለው መጠን እግዚአብሔር ስለ ራሱ ማንነት ለእኛ የገለጠው እውነታ ነው፡፡ ሃይማኖት እግዚአብሔር ራሱን ያሳየበትና ወደ እርሱ ታደርሰን ዘንድ የሰጠን መንገድ ናት፡፡ ስለ ሃይማኖት መንገድነት በመጽሐፍ ቅዱስ ተደጋግሞ ተነግሯል፡፡ በነቢዩ በሆሴዕ "ይህን ነገር የሚያስተውል ጠቢብ፥ የሚያውቃትም አስተዋይ ማን ነው? <u>የእግዚአብሔር መንገድ ቀን ነው፥</u> ጻድቃንም ይሄዱበታል፥ ተላላፊዎች ግን ይወድቁበታል" በማለት ሃይማኖትን "የእግዚአብሔር መንገድ"ሲል ገልጿታል፡፡ ሆሴ. 14፥9 እንዲሁም "ነገር ግን ቃሌን ስሙ፥ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ፣ እናንተም ሕዝብ ትሆኑኛላችሁ፤ መልካምም ይሆንላችሁ ዘንድ <u>ባዘዝኋችሁ መንገድ ሁሉ ሂዱ</u> ብዬ በዚህ ነገር አዘዝኋቸው" ይላል፡፡ ኤር. 7፡23 በሐዋርያው በቅዱስ ያዕቆብም "ኃጢአተኛን <u>ከተሳሳተበት መንገድ</u> የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን፥ የኃጢአትንም ብዛት እንዲሸፍን ይወቅ" በማለት ሃይማኖት መንገድ መሆኗን ያስረዳል፡፡ ያዕ. 5፡20 ይህቺ ሃይማኖትም ራሱ አካላዊ ቃል ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በቃልና በተግባር ያስተማራት፥ በሞቱና በትንሣኤው ያረጋገጣትና በቤተ ክርስቲያን ስትመሰከርና ስትጠበቅ የምትኖረው የክርስትና ሃይማኖት ናት፡፡

ሃይማኖት ከራሱ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ወይም የተገለጠ ነው፡፡ በሃይማኖት የሚገኘው እውቀት ሰው ተመራምሮ የደረሰበት እውቀት ወይም ያገኘው ግኝት አይደለም፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነቱን ለዓለም ሊገልጥ በወደደ ጊዜ ፊልጶስ ቂሣርያ ከሚባለው ቦታ ሲደርስ ደቀ መዛሙርቱን "ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል?" ብሎ ከጠየቀ በኋላ በማስከተል ደቀ መዛሙርቱን "እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ?" በማለት ጠየቃቸው፡፡ በዚያን ጊዜ ስምዖን ጴጥሮስ መልሶ፦ "አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ" ብሎ መለሰ፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መልሶ እንዲህ አለው፦ "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ።" ማቴ. 16፥15-17

የሃይማኖት ምንጩ ሰማያዊ አባት እግዚአብሔር ባይሆን ኖሮ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት በተመለከተ ደቀ መዛሙሩ ስምዖን ጴጥሮስ የሚኖረው እውቀት በዘመኑ ከነበሩት ሌሎች ሰዎች የተለየና የተሻለ ሊሆን አይችልም ነበር፡፡ ነገር ግን ከሥጋና ደም (በዚህ ዓለም ምርምርና ፍልጋ) ውጭ የሆነው እግዚአብሔር እውነቱን ገለጠላቸው፡፡ ለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስጠነቅቅ "እምነታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበረ እንጂ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም" በማለት የተናረው፡፡ 1 ቆሮ. 2፡4-5

እግዚአብሔር ሃይማኖትን ሰጠ፤ እኛ ደግሞ ተቀበልን፡፡ የሰው ልጅ ሃይማኖትን ይቀበላል እንጂ ሃይማኖትን ሊሠራ ወይም ሊያሻሽል አይችልም፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *"የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፣ እነርሱም ተቀበሉት"* በማለት የገለጸው ይህን ነው፡፡ ዮሐ. 17፡8 እንዲሁም *"ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው"* ያለው ለዚህ ነው፡፡ ስሙንም፣ ማንነቱንም ሊገባን በሚችለው መጠን የገለጠልን ራሱ እግዚአብሔር ነው እንጂ ሃይማኖት የሰው ልጅ በምርምር የደረሰበት ግኝት አይደለም፡፡ ዮሐ. 17፡6

ሃይማኖት አንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነው፡፡ "ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት" እንደ ተባለ (ይሁዳ 3) ምግባሩዋ እንደየ ዘመኑ ይለያያል፤ ይዘቱ ግን ያው አንድ ነው፡፡ ለምሳሌ ሕፃን ልጅ በሕፃንነቱ ወተትና ፍትፍት፣ ሲያድግ ደግሞ ጠንከር ያለ ምግብ ይሰጠዋል፡ የሰውነት ባሕርዩ ግን ያው አንድ ነው፤ አይለዋወጥም፡፡ ሃይማኖትም በዘመነ አበው፣ በዘመነ ኦሪት፣ በዘመነ ወንጌል የምግባሩዋ ሁኔታ እንደየ ዘመኑ የሰዎች የመረዳት ዓቅምና ሁኔታ ቢለያይም ይዘቱ (ጭብጡ) ግን ያው አንድ ነው፡፡ *"ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞ ዘመናትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን"* ያለው ይህን የሚገልጽ ነው፡፡ ዕብ. 1፥1-2 የቅዱሳን መላእክት፣ የአበው ቀደምት የእነ አዳም፣ ኖኅ፣ አብርሃም፣ ሙሴ፣ ዳዊት፣ የነቢያት፣ ኋላም የሐዋርያትና የሰማዕታት፣ የጻድቃንና የሊቃውንት ሃይማኖት አንድ ነው፡፡ ስለዚህ ሃይማኖት የተሰጠው አንድ ጊዜ፣ ያውም ፈጽሞ (ያለ መቀናነስና ያለ ቀረኝ) ስለ ሆነ ተሐድሶ ወይም ለውጥ አያስፈልገውም ማለት ነው፡፡ ሃይማኖትን ይቀበሉታል፣ ይጠብቁታል፣ ያወርሱታል እንጂ ሳድሰው፣ ሳሻሽለው አይባልም፡፡ እግዚአብሔር የሰጣት፣ አባቶቻችን ከእርሱ ተቀብለው ኖረውባት ለእኛ ያወረሱን ሃይማኖት ፍጽምትና አንድ ጊዜ የተሰጠች ናት፣ ብልየት እርጅና የለባትም፡፡

ሃይማኖት ከእግዚአብሔር የተቀበልነው እንደ መሆኑ መጠን የሰዎች ድርሻ አምኖ መቀበልና በዚያ በመጠቀም የዘለዓለም ሕይወትን መውረስ ብቻ ነው፡፡ ይህም ማለት በዚህ ዓለም ያለ ማንም ግለሰብም ሆነ አካል እግዚአብሔር በሰጠው እውነት (ሃይማኖት) ላይ የመጨመርም ሆነ የመቀነስ ሥልጣን የለውም ማለት ነው፡፡ ሲኖዶሳት እንኳ የሚያደርጉት ሃይማኖትን ለማጽናት አስፈላጊ የሆኑ ውሳኔዎችን መወሰንና ቀኖናትን መቀነን እንጂ በሃይማኖት ላይ መጨመርም ሆነ መቀነስ አላደረጉም፣ ሊያደርጉም አይችሉም፡፡ በኒቅያ፣ በቁስጥንጥንያ እና በኤፌሶን ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ላይ የተደረገው ይኸው ነው፤ የቤተ ክርስቲያንን ሃይማኖት ሊለውጡ የተነሡ መናፍቃንን ስህተታቸውን በመለየት (በማውገዝ) እውነተኛውን ሃይማኖት አጸኑ እንጂ አዲስ የሃይማኖት ውሳኔ አልወሰኑም፡፡ በኒቅያ ጉባኤ የተሰበሰቡት 318ቱ አባቶች የትንሣኤ በዓል የሚከበርበትን ዕለት በተመለከተ ይህ ሃይማኖት ሳይሆን ሃይማኖት የሚገለጥበት የበዓል አከባበር ዕለት ጉዳይ ስለ ነበር ውሳኔ ወስነዋል፡፡ ሃይማኖትን በተመለከተ ግን የተቀበሉትን አጸኑ እንጂ አዲስ ውሳኔ አልወሰኑም፡፡ ይህን በተመለከተ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ በኒቅያ ስለ ተሰበሰቡት አባቶችና ስለ ውሳኔያቸው በጻፈው ጦማሩ ላይ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡-

> በኒቅያ የተሰበሰቡት አባቶች የትንሣኤ በዓል የሚውልበትን ቀን መወሰንን በተመለከተ 'የሚከተለው ተወስኗል' ብለው ጻፉ፡፡ ይህ የተወሰነው በዚያን ጊዜ ነበርና ከዚያ ጀምሮ ሁሉም ሊታዘዙት ይገባል፡፡ ሃይማኖትን በተመለከተ ሲጽፉ ግን 'ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ታምናለች' ብለው ጻፉ እንጂ 'እንዲህ ተወስኗል' አላሉም፡፡ በዚህም የሚያምኑትን መሰከሩ፡፡ ይህን ያደረጉትም ውሳኔያቸው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመጣ አዲስ ሃሳብ ሳይሆን ከሐዋርያት ጀምሮ የመጣ መሆኑን ለማሳየት፤ የጻፉትም የራሳቸው የፈጠራ ሃሳብ ሳይሆን በሐዋርያት የተሰበከውን ሃይማኖት መሆኑን መግለጥ ነው፡፡[19] [20]

[19] "The Fathers of the Ecumenical Council of Nicaea, without prefixing consulate, month, and day, wrote concerning Easter" 'The following has been decided.' And it was at that time decided that all should comply. But concerning matters of faith, they did not write: 'It has been decided,' but 'Thus the Catholic Church believes.' And thereupon they confessed how they believed. This they did in order to show that their judgment was not of more recent origin, but was in fact of Apostolic times; and that what they wrote was no discovery of their own, but is simply that which was taught by the Apostles."

[20] Letter Concerning The Councils of Rimini and Seleucia, 361/362 A. D.

## 1.2.1.2 ኑፋቄ ምንድን ነው?

ኑፋቄ ማለት እግዚአብሔር የገለጠውን ሃይማኖት እንደ ምእመናን ሙሉ በሙሉ ሳይቀበሉ፣ እንደ ኢአማንያንም ሙሉ በሙሉ ሳይክዱ፣ የተወሰነውን ተቀብሎ ሌላውን ደግሞ አለመቀበል ወይም መጠራጠር ነው፡፡ እንዲህ የሚያደርጉት ሰዎች ደግሞ መናፍቃን (ተጠራጣሪዎች) ይባላሉ፡፡ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ መናፍቃንን እንዲህ ገልጸዋቸዋል፡-

> የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሳይሆኑ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች መስለው ወይም ከቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ግማሹን ይዘው ግማሹን ያልያዙ ጎደሎዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች እንክርዳድ ስንዴ መስሎ እንዲያድግ በክርስቶስ ዐጸደ ወይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የበቀሉ አሳሳቾች ናቸው፡፡ ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን የውስጥ ጠላቶች ናቸው፡፡ (የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣ ገጽ 50)

መናፍቃን የሚባሉት እግዚአብሔር እንድንበት ዘንድ የሰጠውን መንገድ (የክርስትናን ሃይማኖት) ተቀብለናል፣ እናምናለን ካሉ በኋላ ያን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠውን የመዳን መንገድ ለእነርሱ የመሰላቸውን ያህል ቆንጽለውና ከፍለው እንጂ እንዳለ ሙሉ በሙሉ የማይቀበሉ ናቸው፡፡ ኢአማንያን የሚባሉት ከመጀመሪያውም የክርስትና ሃይማኖትን ያልቀተበሉ ሲሆን መናፍቃን የሚባሉት ግን ክርስቲያኖች ነን እያሉ ነገር ግን ከክርስትና አስተምህሮ ውስጥ ለራሳቸው አስተሳሰብና ምኞት የሚመችውን ብቻ ተቀብለው ሌላውን የማይቀበሉና የሚጠራጠሩ፣ በእውነተኛው ትምህርት ፋንታም የራሳቸውን የፈጠራ ትምህርት የሚያስተምሩ ናቸው፡፡

እንደዚህ ያሉት ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ አገላለጾች ተገልጸዋል፡፡ ለምሳሌም "በመልካሙ እርሻ ጠላት የዘራው እንክርዳድ" (ማቴ. 13፡25-26)፣ "የክፉው ልጆች" (ማቴ. 13፡39)፣ "ሐሰተኞች ወንድሞች"፣ "ክፉዎች ሠራተኞች"፣ "ውሾች" (ፊል. 3፡2)፣ "መናፍቃን" (2 ጴጥ. 2፡1 ፤ የሐዋ. 24፡ 5) በሚል መጠሪያ ተጠርተዋል፡፡ ይህም ስድብ ሳይሆን የግብራቸው መገለጫ ነው፡፡ ለምሳሌ የሚሰርቅ ሰው "ሌባ" መባሉ የግብሩ መገለጫ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ ሰው የአንድን ነገር ግብሩን ወድዶ ስሙን ብቻ ቢጠላ ትርጉም አይኖረውም፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅም "በሃይማኖት ላይ የሚጨምር 'ደፋር'፣ የሚቀንስ ደግሞ 'ሌባ' ነው" ሲል ይገልጻል፡፡

ቅዱሱ መጽሐፍ የኑፋቄን ከባድ ኃጢአትነትና አጥፊነት አበክሮ ይገልጻል፡፡ "ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ፣ እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ፤ እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ <u>የሚያጠፋ ኑፋቄን</u> አሹልከው ያገባሉ"፡፡ 2 ጴጥ. 2፡1 ኑፋቄ የእግዚአብሔርን መንግሥት የማያስወርስ ነው፤ "መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ... እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።" ገላ. 5፡21

ክርስቲያኖች መስለው የክርስቶስን ስም እየጠሩ፣ ነገር ግን የስህተት ትምህርት የሚያስተምሩ መናፍቃን እንደሚነሡ ጌታችን አስቀድሞ እንዲህ ሲል አስጠንቅቆናል፡- "በዚያን ጊዜ ማንም እነሆ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፤ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፣ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ። እነሆ አስቀድሜ ነገርኋችሁ። እንግዲህ እነሆ በበረሀ ነው ቢሏችሁ አትውጡ፤ እነሆ በእልፍኝ ነው ቢሏችሁ አትመኑ" ማቴ. 24፡23-26 ጌታችን ካስተማረውና ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከጌታ ከተቀበለችው የድኅነት አስተምህሮ የተለየ ትምህርት የሚያስተምር መናፍቅ የተረገመ መሆኑንና ልንቀበለውም የማይገባ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ "ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን።

አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን" ሲል በጽኑ አስጠንቅቋል። ገላ. 1፡8-9 እንዲህ ካለ መናፍቅ መለየት እንደሚገባም "ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ፥ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት" ሲል ቅዱስ መጽሐፍ ያስጠነቅቀናል። 2 ዮሐ. 10

ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊም እንዲህ ብሏል፡-

> ከመጀመሪያው ጀምሮ ከባለቤቱ ከጌታችን የተሰጣት የኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ትውፊት፥ ትምህርትና እምነት በሐዋርያት የተሰበከ እና በአባቶች የተጠበቀ ነው። ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በዚህ ላይ ነው፤ ከዚህ የሚያፈነግጥ ማንም ቢሆን ክርስቲያን አይደለም፥ ክርስቲያን ተብሎ ሊጠራም አይገባውም። (ለጳጳስ ሴራፒዮን ዘትሙይስ የተላኩ አራት መልእክታት[21])

ኑፋቄ ታላቅ ኃጢአት ነው። ኃጢአት ብቻም ሳይሆን በሰውነት ድክመት በምግባር ፍኖት ከሚፈጸሙ ኃጢአቶች ሁሉ በላይ የመጨረሻ ከባድ ኃጢአት ነው። ምክንያቱም በሃይማኖት ውስጥ ያለ ሰው የሚሠራው ኃጢአት ንስሐ ከገባ ሥርየትንና ምሕረትን ሊያገኝ ይችላል፤ ኑፋቄ ግን ሥርየትና ምሕረት በሚገኝበት በራሱ በሃይማኖት ላይ የሚፈጸም ኃጢአት በመሆኑ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው ቢታመም በመድኃኒት አማካይነት ሊፈወስ ይችል ይሆናል። ሆኖም ያ በሽተኛ በመድኃኒቱ ላይ የሚያምጽና የሚቀልድ ከሆነ ግን የመዳን ተስፋ እንኳ የለውም፥ ምክንያቱም በመድኃኒቱ ላይ አምጿልና። ለሰው ልጅ የተሰጠው ታላቁ ሀብትና ጸጋ እምነት ነው። ኑፋቄ ደግሞ ይህን ታላቅ ጸጋ የሚያሳጣ ስለሆነ እጅግ ከባዱ ኃጢአት እርሱ ነው።

ሰዎች ወደ ኑፋቄ የሚገቡባቸው ከተለያዩ ምክንያቶች መካከል እውነተኛውን የክርስትና ትምህርት አለማወቅና በተሳሳቱ ሰዎች ትምህርት መለከፍ፥ በራስ አስተሳሰብና ስሜት ብቻ መመራት፥ እኔ አውቃለሁ ማለት፥ ከትዕቢት የተነሣ ስህተትን ሲነገሩ አለመቀበልና በራስ መንገድ ብቻ መጓዝ፥ አንድ ጥቅስ ወይም በጣም ጥቂት ጥቅሶች ላይ ብቻ መንጠልጠል፥ እምነትን ለቁሳዊ ጥቅም ማግኛ መንገድ ማድረግ፥ በዘመኑ ያሉ ኃይላትን ለማስደሰትና ሹመትና ሥልጣንን ለማግኘት ማሰብ ይገኙባቸዋል።

ቅዱሳን አባቶቻችን የኑፋቄ መሥራቾችና ተከታዮች የሆኑ መናፍቃንን ከሁሉም ይልቅ ከፉዎች መሆናቸውን ይናገሩ ነበር። ለአብነትም ቅዱስ ፖሊካርፐስ መርቅያን የተባለውን መናፍቅ "የዲያብሎስ የበኩር ልጅ" ይለው ነበር። ቅዱስ አግናጥዮስ ደግሞ መናፍቃን መርዝን የተመሉ ናቸው ይላቸው ነበር፥ እንዲሁም በሰው መልክ ያሉ አራዊት ናቸው ይላቸው ነበር። ሰማዕቱ ቅዱስ ዮስጢኖስ ደግሞ መናፍቃንን ዲያብሎስ ያነቃውን ስህተት የሚከተሉ ይላቸው ነበር። አባ ሄሮኒመስ ደግሞ መናፍቃንን የሰይጣን ምኩራቦች ይላቸው ነበር።

## 1.2.2 በዘመናት የነበሩ ዋና ዋና መናፍቃንና ኑፋቄያቸው በአጭሩ

### 1.2.2.1 ግኖስቲኮች

በ2ኛውና በ3ኛው መ/ክ/ዘ ቅድስትና ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያንን ሲያውኳትና ሲፈትኗት የነበሩት መናፍቃን ብዙዎች ነበሩ። ከእነዚያ መካከል በተለይም ግኖስቲኮች የተባሉት አካሄዳቸው አደገኛ ነበር። ግኖስቲኮች "ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ትምህርት ርቃለች፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ካስተማረው ትምህርት ተቃራኒ ቆማ ሌላ እንግዳ ትምህርት ታስተምራለች" እያሉ ይቃወሟትና ያብጠለጥሏት ነበር።

[21] Four Letters to Bishop Serapion of Thmuis

ግኖስቲኮች እውነተኛው የክርስቶስ ትምህርት አለ የሚሉት ከእነርሱ ዘንድ ብቻ የነበረ ሲሆን በተለያዩ ጽሑፎቻቸው ይፋዊ በሆነ ሁኔታ በውስጧ ምእመናንና ካህናትን ይዛ በጳጳሳት ስትመራ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን በኑፋቄ ይከስሷትና አበክረው ይነቅፏት ነበር፡፡ ግኖስቲኮች እውነተኛ ክርስቲያኖች አድርገው የሚቆጥሩትም ራሳቸውን ብቻ ነበር፡፡

እንዲሁም ግኖስቲኮች በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያፌዙና ይሳለቁ ነበር፡፡ ለምሳሌም በምሥጢረ ጥምቀት የሚገኘውን ጸጋ አምነው በምሥጢሩ ሂደት በሚሳተፉ ሰዎች ላይ "ወደ ውኃ ውስጥ ገብተው ምንም ነገር ሳይይዙ በባዶው የሚወጡ" እያሉ ሊቀልዱባቸውና ሊያፌዙባቸው ይሞክሩ ነበር፡፡ ግኖስቲኮች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የነበሩ ጳጳሳትን "ሙሰኞች፣ ሥልጣን የጠማቸው፣ ስስታሞች" ወዘተ እያሉ መራራና ጠንካራ በሆኑ ቃላት ይሰድቧቸውና ሕዝበ ክርስቲያኑ እንዲጠላቸውና እንዲጸየፋቸው በማድረግ ከቤተ ክርስቲያን እየኮበለለ ወደ እነርሱ ጎራ እንዲገባ ለማድረግ ከፍተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻ ያካሂዱ ነበር፡፡ ግኖስቲኮች ይሰብኩት የነበረው "ክርስትና" አንድና ወጥ የሆነ አስተምህሮ ያላትና መዋቅር ያላት አንዲት ቤተ ክርስቲያን የሌለችበትና ደስ ባላቸው መንገድ እንዳሻቸው ሊያደርጉት የሚችሉት ውጥንቅጡ የወጣ የተበጣጠሱ ቡድኖች እንዲፈጠሩ በሚያደርግ ሁኔታ ነበር፡፡ ትምህርታቸውም ራሳቸው ብቻ ፈራጆችና አድራጊ ፈጣሪዎች የሆኑበት ስብስብ፣ ክህነትና ካህናት የሌለባት ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ምሥጢራት የሚባሉ ነገሮች የማይታወቁበት ዓይነት "ልዩ ክርስትና" ነበር፡፡

እነዚህ መናፍቃን ስለ መዳን ሲያስተምሩ በክርስቶስ አካል - በቤተ ክርስቲያን - ስለማያምኑ ግላዊ መዳን (በግል መዳን) የሚል ትምህርት ነበራቸው፡፡ ይህም ማለት "እያንዳንዱ ሰው በመዳን ሂደት ውስጥ የክርስቶስ አካል ይሆናል፣ በዚህም የክርስቶስ አካላት (ብልቶች) ከሆኑ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በክርስቶስ ራስነት አንድ ይሆናል" የሚለውን ትምህርት ትተው እያንዳንዱ ሰው ክርስቶስን እርሱ በተረዳው መንገድ በማመን ያለ ምሥጢራት አስፈላጊነት ይድናል ብለው ያስተምሩ ነበር፡፡ እነርሱ ከሚሉት ከዚህ ዓይነቱ የእነርሱ "ክርስትና" ውጭ የሆነን ሁሉ "የወንጌል ጸር፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ፣ አረመኔ፣ ጌታ ያልተሰበከለት" ወዘተ የሚል ቅጽል ይደርቡለት ነበር፡፡[22] ከግኖስቲኮች መሪዎች መካከል ባሲሊደስ፣ ቄሬንተስ፣ ቫሌንቲኑስ እና መርቅያን ዋና ዋናዎቹ ነበሩ፡፡

ግኖስቲኮች ቁስ አካላዊ የሆነ ነገር ሁሉ፣ የሰውን ሰውነት ወይም ሥጋን ጨምሮ፣ ክፉ (ኃጢአት) ነው፣ የእግዚአብሔር ፍጥረትም አይደለም ይሉ ነበር፡፡ ከዚህ የተነሣም እግዚአብሔር ጸጋውን ለመስጠት እንዲህ ክፉ ነው ያሉትን ቁስ አካልን ይጠቀማል ማለት በእነርሱ አስተሳሰብ ነውር ነበር፡፡ በሚታዩ ነገሮች አንጻር ጸጋ እግዚአብሔር የሚሰጥባቸው ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በእነርሱ ዘንድ የማይታሰቡ ነበሩ፤ ምክንያቱም ኃጢአት ወይም ክፉ በሆነ በቁስ አካል አንጻር (በውኃ ጥምቀት፣ በሜሮን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ፣ በኅብስቱና በወይኑ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ) እንኳን ጸጋ እግዚአብሔር ሊሰጥባቸው ይቅርና እንደዚህ ካሉት ቁስ አካሎች በተቻለ መጠን አብዝቶ መራቅና መለየት ይገባል እያሉ ያስተምሩ ስለ ነበር ነው፡፡

ቅዱስ አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ፣ ቅዱስ ፖሊካርፐስ፣ ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ ቅዱስ ሚሊጦስ ዘሳርዲስ እና ሌሎችም የ2ኛውና የ3ኛው መቶ ዓመት አባቶች የእነዚህን መናፍቃን ስህተት ለማጋለጥና እውነተኛውን ሐዋርያዊ ክርስትና ከግኖስቲኮች ብረዛ ለመጠበቅ በአፍም በመጽሐፍም ጽኑ ተጋድሎን ተጋድለዋል፡፡ ሆኖም የግኖስቲኮች ልብ ወለዳዊ የፈጠራ ትምህርት መልኩንና ዓይነቱን እየለዋወጠ በየዘመናቱ ሐዋርያዊት የሆነችውን አንዲት ቤተ ክርስቲያን ማወኩ አልቀረም፡፡ እግዚአብሔር በሐዋርያው በቅዱስ ጳውሎስ ቃል "ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ እንዲያቦካ አታውቁምን? እንግዲህ ያለ እርሾ እንዳላችሁ አዲሱን ሊጥ ትሆኑ ዘንድ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ" ሲል የመከረንና ያስጠነቀቀን ለዚህ ነበር፡፡ 1 ቆሮ. 5፥6-7

---

[22] Georges Florovsky, The Ascetic Ideal and The New Testament, Reflections on the Critique of the Theology of the Reformation, The Collected Works, Vol. X.

ይህን የግኖስቲኮች እርሾ በእነዚህ በተሐድሶዎች የፈጠራ ትምህርት ውስጥም ጥላውን ጥሎ እናገኘዋለንና በጊዜው ጊዜ ከቦታው ስንደርስ እናነሳዋለን፡፡ በየጊዜው አዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ አረዳድና ልዩ መገለጥ እየተባሉና እየመሰሉ የሚወጡ ነገሮች አብዛኛዎቹ የጥንቶቹ መናፍቃን የግኖስቲኮች፣ የአርዮሳውያንና የንስጥሮሳውያን እርሾዎችና ልቅምቃሚዎች የሆኑ ኑፋቄዎችን በተለያየ መጠንና ቅርጽ በማቡካትና በመጋገር የሚፈጠሩ ናቸው እንጂ አዲስ አይደሉም፡፡ በእነ ማርቲን ሉተር፣ በእነ ጆን ካልቪን፣ በእነ ኡልሪች ዝዊንግሊ፣ በአሁኑ በአገራችንም ራሳቸውን "ተሐድሶ" ብለው በሚጠሩ አካላት የምናየው ይህንኑ ነው፡፡ ወደፊት በምናያቸው የተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተሐድሶ መናፍቃንን ትምህርት ጥንቱንና የትመጣውን ስናይ ይህ የበለጠ ግልጽ እየሆነ ይሄዳል፡፡ ለጊዜው ግን "የግል አዳኝ"፣ "ጌታን በተረዳኸው መንገድ ግለጠው"፣ "ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ለመዳን አያስፈልጉም"፣ ወዘተ የሚሉት የፕሮቴስታንትና የተሐድሶ ባህሎች ምንጫቸው ግኖስቲካዊ እርሾ መሆኑን ማስተዋል ይቻላል፡፡

ግኖስቲኮች የመናፍቃን ዋና መገለጫ የሆነውን የተዘበራረቀና በወጥነት ይህ ነው ተብሎ ሊገለጽ የማይችል፣ ነገር ግን እንደየ ግለሰቦቹና መሪዎቹ ስሜትና ምኞት የተቃኘ የተለያየና የተምታታ አስተምህሮ ነበራቸው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ግኖስቲኮችን በዋናነት በሁለት ከፍሏቸዋል፡፡ እነዚህም "አፍቃርያነ ትህርምት" እና "አፍቃርያነ ኃጢአት"[23] በሚል ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ቡድኖች ቁስ አካል በሆነው ሰውነት ውስጥ የታሰረችውን ነፍስ ነጻ ለማውጣት ጽኑ ትህርምት ማድረግን፣ ጋብቻን መጸየፍንና መከልከልን ይሰብኩ የነበረ ሲሆን እነዚህኞቹ ደግሞ ሰውነት ምንም ሊፈወስ በማይችልበት ሁኔታ የተበላሸ ስለሆነ በእውቀት የበለጸገች ነፍስ ሰውነቷ ምንም ዓይነት ኃጢአት ቢሠራ አንዳችም ጉዳት አይደርስባትም ባዮች ነበሩ፡፡ ለእነዚህኞቹ ኃጢአት ነው የሚባል ምንም ዓይነት ድርጊት አልነበረም፡፡

ለዳነች ነፍስ የሚጎዳት ምንም ዓይነት የርኩሰትም ሆነ የኃጢአት ድርጊት የለም ይሉ ስለ ነበር ኃጢአትን ሁሉ ንቅስ ጥቅስ እያደረጉ መሥራትን ይሰብኩና ያበረታቱ ነበር፡፡ ይህን የግኖስቲኮች እርሾ በተሐድሰዎች ትምህርት ውስጥ እናገኘዋለንና በቦታው ስንደርስ እናየዋለን፡፡ ለምሳሌም ተሐድሶዎች "በእምነት ለዳነ ሰው ኃጢአት ቢሠራም ያገኘው ጸጋ አይወሰድበትም፣ ራሱን ለመግዛትና ከኃጢአት ጋር ለመጋደል ጥረት ማድረግ የለበትም፣ ኃጢአት ማድረጉ በእግዚአብሔር ልጅነቱ ላይ የሚያመጣው አንዳችም ለውጥ የለም" እያሉ እንደ አባቶቻቸው እንደ ግኖስቲኮች ሲናገሩ እናገኛቸዋለን፡፡

ሌላው የግኖስቲኮች ትምህርት ስለ ብሉይ ኪዳን እና የኦሪትን ሕግ ስለ ሰጠው አምላክ ያላቸው የፈጠራ ትምህርት ነበር፡፡ ግኖስቲኮች "ብሉይ ኪዳንን የሠራው የአይሁድ አምላክ ክፉው አምላክ ነው፣ በሐዲስ ኪዳን ሰው ሆኖ የመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳኑ አምላክ የተለየ ከሆነው ከደጉ አምላክ ተልኮ የመጣ ነው" ይሉ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሣ እንደ መርቅያን ያሉት ጽንፈኛ ግኖስቲኮች "መጽሐፍ ቅዱስ" በሚለው መድበል ውስጥ የሚቀበሉት ሐዲስ ኪዳንን፣ ያውም ሁሉንም የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሳይሆን ከወንጌል የሉቃስን ወንጌል ብቻ እና የቅዱስ ጳውሎስን (አሥሩን መልእክታት ብቻ) ነበር፡፡

ግኖስቲኮች ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት መካከል መሠረታዊ እሳቤውንና ጽንሰ ሃሳቡን ሳይረዱ ሕገ ኦሪትን የሚነቅፍ የሚመስላቸውን በእጅጉ እያጎሉ ለማሳየት ይሞክሩ ነበር፡፡ ከሐዋርያት መካከል የኢየሱስ ትምህርት የገባው ጳውሎስ ብቻ ነው ይሉ ነበር፡፡ በአጠቃላይ ለብሉይ ኪዳን ሕግና ያን የሠራው አምላክ ለሚሉት ከነበራቸው ከፍተኛ ጥላቻ የተነሣ ብሉይ ኪዳንን አጥብቀው ይጸየፉና ይጠሉ ነበር፡፡ መርቅያን የአይሁድ አምላክ ብሎ ለሚጠራው ብሉይ ኪዳንን ለሠራው አምላክ ከነበረው ጥላቻ የተነሣ እርሱ ዕረፍት ትሁን ብሎ ያዘዛትን ቀዳሚት ሰንበትን ተከታዮቹ እንዲጾሟት አዝዞ ነበር፡፡

[23](into the *ascetic* and *licentious* sects, Strom. iii.5)

መርቅያን ተቀበልኩት ያለውን የሉቃስን ወንጌል እንኳ ከብሉይ ኪዳን ጋር የሚያገናኙትን ታሪኮች በየጊዜው ትዝ ባለው ቁጥር እየነቀሰ እያወጣና እንደ አዲስ እየጻፈ እርሱ "ትክክለኛ ወንጌል" የሚለውን ጽፎ ሳይጨርስ ነበር የሞተው፡፡ ከፍተኛ ዋጋና ቅድሚያ ይሰጥ የነበረውም ለቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ገላትያ፣ ለቆሮንቶስ ካልእ እና ለሮሜ መልእክት ነበር፡፡ከእነዚህ ከተቀበላቸው መጻሕፍት እንኳ ሳይቀር ከእርሱ ንድፈ ሃሳብ (ቲዎሪ) ጋር የማይሄዱትን ሃሳቦች እየነቀሰ ያወጣቸው ነበር፡፡ ከዚያም የራሱን ሃሳብ በምትካቸው ያስገባ ነበር፡፡
በዚህ ረገድ በግኖስቲኮች ዘንድ የነበሩት ዋና ዋና የስህተት ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ብሉይ ኪዳንን (የሕጉን መጻሕፍት፣ የነቢያትን መጻሕፍት እና ይዘታቸውን) አምርረው መጥላታቸው፣
- ሌሎችን ሐዋርያት የኢየሱስን ትምህርት እንዳበላሹና እንደ ለወጡ አድርጎ ማሰብና ጳውሎስ የተላከው የእነዚያን ስህተት ለማስተካከል ነው ብለው ማሰባቸውና ማስተማራቸው፣ ለዚህም መርቅያን ቅዱስ ጳውሎስን ምስክር አድርጎ (በተለይ የገላትያ መልእክቱን) ለማሳየት መሞከሩ፣
- ኢየሱስ ክርስቶስን "ከደጉ አምላክ እየወጡ የሚመጡ ነጸብራቆች ወይም ብናኞች (Aeons) አሉ" ይላሉና ከእነዚያ መካከል አንዱ አድርገው መቁጠራቸው፣
- ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ትምህርቶች ውስጥ ይደግፉናል የሚሏቸውን አንዳንድ ጥቅሶች ብቻ በማንጠልጠል ያን ቃል ወይም ሀረፍተ ነገር ከተባለበት ዳራና ርእሰ ጉዳይ አንጻር መረዳትን ትተው ለራሳቸው አስተሳሰብ ደጋፊ አድርገው ለማቅረብ መታገል ነበሩ፡፡

እነዚህን የግኖስቲኮች እርሾዎች በተሐድሶዎች አስተሳሰብና ጽሑፎች ላይ በሰፊው እናገኛቸዋለንና በጊዜው ጊዜ እናያቸዋለን፡፡

### 1.2.2.2 አርዮስ እና አርዮሳዊነት

የአርዮስ ኑፋቄ ጥልቅና ሥር ነቀል የሆነ ጸረ ክርስትና የፈጠራ ትምህርት በመሆኑ በዚህ መጽሐፍ ላይ በዝርዝርና በስፋት አናየውም፡፡ ሆኖም የእርሱ ኑፋቄ የብዙዎቹ የኋላ መናፍቃን መፈልፈያ ኩሬ በመሆኑ፣ ኑፋቄውም ለኋላ አረመኔያዊ የአሕዛብ ትምህርቶች መነሻ ሆኖ ያገለገለ በመሆኑ በአጭሩ እንዳስሰዋለን፡፡ አርዮስ ከእርሱ በፊት የተነሣው ሰባልዮስ የተባለው መናፍቅ የአካላዊ ቃልን ቀዳማዊና ራሱን የቻለ ህልውና ክዶ አንዱ እግዚአብሔር በሆነ ዘመን የተገለጠበት የመገለጫ መንገድ (Modes of Divine Manifestation) ብቻ ነው የሚል ክህደት ይዞ ተነሥቶ ብዙ ሞኞችን ሲያስከትልና ግራ ሲያጋባ ነበር፡፡ ይህን የሰባልዮስን ኑፋቄ በመቃወምና አጸፋዊ መልስ ለመስጠት አካላዊ ቃል የራሱ የሆነ ህልውና አለው በማለት የተነሣው አርዮስ ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስን "በአብ የተፈጠረ ነው" (ሎቱ ክብር ወስብሐት አምልኮ ወስግደት) በማለት ለሰማይ ለምድር የሚቀፍ ክህደት ሲናገር ይህ የእርሱ አስተሳሰብ ኢየሱስ ክርስቶስን "ከአንዱ አምላክ እየተከፈሉ ከሚመጡ ብናኞች አንዱ ነው" የሚለውን የግኖስቲኮችን አስተሳሰብ ቅርጹን ለውጦ መልሶ የሚያመጣ መሆኑን መመልከት አልቻለም ነበር፡፡

አርዮስ በድፍረት ኢየሱስ ክርስቶስን በባሕርዩ ከአብ ጋር አንድ ያልሆነ፣ ከአብ ያነሰ፣ ያነሰ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ሌሎች ፍጥረታትን ለመፍጠር ይጠቀምበት ዘንድ መጀመሪያ የፈጠረው "ፍጡር" ነው ይል ነበር፡፡ የአርዮስ ተከታዮች እና የእርሱን ኑፋቄ በተለያየ ደረጃ የጠጡት እነ መቅዶንዮስና መሰል መናፍቃን ወልድን እና መንፈስ ቅዱስን ግኖስቲኮች ከአምላክ እየወጡ ይመጣሉ እንደሚሏቸው ኤዎኖች (Aeons) አድርገው ይመለከቷቸው ነበር፡፡

በዋናነት የአርዮስ ክህደት አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን ከአብ አሳንሶ ማሳየቱ፣ ፍጡር ነው ማለቱ ነው፡፡ ይህ ወልድን ከአብ የማሳነስ የመጨረሻ የክህደት ጥልቀት (Subordinationism) አርዮስ ተክሎት

የሄደው መርዝ ነበር፡፡ ይህ ወልድን ከአብ አሳንሶ ማሰብና ማስተማር በተሐድሶዎችም የሚታይ በሽታ ነው፡፡ ራሳቸውን ክርስቲያን ነን ብለው በሚጠሩ የተለያዩ ድርጅቶች ዘንድ የሚታየው ኢየሱስ ክርስቶስን "ወንድሜ፣ ጓዴ፣ . . ." የሚሉት አስተሳሰቦችና ሌሎችም ለመናገር የሚከብዱ ነገሮቻቸው ከአብ ጋር በባሕርይ አንድ መሆኑንና የባሕርይ አምላክነቱን በግልጽም ባይሆን በስውር ካለማመን የሚመነጩ ሰወር ያሉ አርዮሳዊነት (Latent Arianism) ናቸው፡፡ ከላይ በ 1.1.4 ላይ ያየናቸው የተሐድሶዎች አባባሎችም የዚህ ማሳያዎች ናቸው፡፡

### 1.2.2.3 ንስጥሮስ እና አስተምህሮው

የንስጥሮስ ትምህርት በአጭሩ ሲገለጽ መለኮትን እና ትስብእትን እንደ ሁለት ተጓዳኞች ወይም ጎረቤቶች አድርጎ የሚያስብ ትምህርት ነው፡፡ የመለኮትን እና የትስብእትን አካላዊም ሆነ ባሕርያዊ ተዋሕዶ የማይቀበል ሲሆን የሁለቱ ተዋሕዶ ወይም አንድነት አፍአዊ (ውጫዊ) በሆነ መገለጫቸው (προσοπον - prosopon) ደረጃ ብቻ ነው ይል ነበር፡፡ ንስጥሮስ "ትስብእት እና መለኮት፣ እያንዳንዳቸው የየራሳቸውን ባሕርይና ግብር ጠብቀው ጎን ለጎን የኖሩ መሆን አለባቸው" ይል ነበር፡፡

እንደ ንስጥሮስ አስተሳሰብ የቃልና የትስብእት ተዋሕዶው በአፍአዊ መገለጫ (Prosopon) ደረጃ ብቻ ነው፡፡ ይህን ለመግለጽ የሚጠቀመው ቃልም ከተዋሕዶ (Union) ይልቅ ጣምራነትን (Conjunction) የሚያመለክት ነበር፡፡ "የእግዚአብሔር ቃል ከሰው ሰውነት እና ከነፍስ ጋር ያደረገው ተዋሕዶ ባሕርያዊም አካላዊም አይደለም፣ የፈቃድ ብቻ ነው እንጂ"[24] ይል ነበር፡፡

በእርሱ አስተምህሮ መሠረት ተዋሕዶው በውጫዊው መገለጫ ደረጃ ብቻ ነው (Prosopic Union)፤ ውሳጣዊ የሆነ የቃልና የትስብእት ተዋሕዶ (Hypostatic Union) የለም፡፡ ሕማማቱን በተመለከተ 'ሥግው ቃል አልሞተም፣ ነገር ግን ያደረበትን ሥጋ አስነሣው' ይላል፡፡ ሆኖም ንጉሥ ሐውልቱ ሲቃለል ወይም ሲመታ በሚሰማው ዓይነት ሁኔታ ቃል መከራ ተቀበለ ሊባል የሚችልበት የተወሰነ ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ያስረዳ ነበር፡፡

"ወላዲተ አምላክ" የሚለውን ቃል በመቃወም የተጠቀለለውና የተገለጸው የንስጥሮስ አስተምህሮ የመለኮትና የትስብእት ግንኙነት በቃልና በተራ ሰው መካከል ያለ ውጫዊ ግንኙነት ብቻ ነው ያሰኛል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይም ሥጋዌው ምትሀት ሆነ፣ ባዶ ቃላትና ታይታ ብቻ ሆነ ማለት ነው፡፡ በዚህም መዳናችን ችግር ላይ ወደቀ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ አስተሳሰብ ከተሄደ የክርስቶስ ሕማማትና የማዳን ሥራዎች የሥግው ቃል ሳይሆኑ የሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) ናቸው ያሰኛልና፡፡

እንዲሁም ክርስቶስ የወደቀውን የሰው ልጅ ዳግመኛ ያከበረውና ያድሰው ዘንድ ቃል ከትስብእት ጋር ንስጥሮስ ከሚለው ተጋውሮ (ጉርብትና) ባለፈ ሁኔታ እውነተኛና ውሳጣዊ አንድነት ያስፈልገው ነበር፡፡ ከሁሉም በላይ፣ ንስጥሮስ ምሥጢረ ቁርባንን ሕይወት የመስጠት ኃይሉን ገፎታል፣ ይህን ምሥጢርም ወደ "ሰው በላነት" (Cannibalism) አውርዶታል፡፡ ምክንያቱም በእርሱ አስተሳሰብ በጻሕሉ ላይ የሚቀርበውና የሚሠዋው የሰው አካል ብቻ ነው እንጂ መለኮት የተዋሐደው የሥግው ቃል አካል አይደለምና፡፡

እውነተኛው ኦርቶዶክሳዊ የክርስትና አስተምህሮ ግን እንዲህ ነው፡፡ ንስጥሮሳውያን እንደሚሉት አካላዊ ቃል ከእመቤታችን የነሣውና የራሱ ገንዘብ አድርጎ የተዋሐደው ትስብእት እግዚአብሔር ቃል በማኅፀን የእርሱ አድርጎ ከተዋሐደበት ከዚያ ቅጽበት በፊት በራሱ አልኖረም፣ በህልውናው በየትኛውም ጊዜ ወይም ሂደት ቢሆን ሰው ተብሎ በራሱ ህልውና አይታሰብም፤ በእመቤታችን ማኅፀን ከተፀነሰበትና መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ የራሱ ገንዘብ ያደረገው የቃል ነው እንጂ፡፡

[24] "The union of God the Word with them (i.e. the body and human soul) is neither "hypostatic" nor "natural", but voluntary."

ስለሆነም ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ አማኑኤል አንድ ነው እንጂ ሁለት አይደለም፡፡ ቃል በባሕርዩ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ እንዲሁም ደግሞ የድንግል ማርያም ልጅ ነው፣ ምክንያቱም ከእርሷ ማኅፀን የተፀነሰው የራሱና የእርሱ ብቻ ነውና፡፡ በቅዱስ ወንጌል የእግዚአብሔር ልጅ የተባለውም፣ የሰው ልጅ የተባለውም ያው አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እንጂ ተከፍሎ የለበትም፡፡ ቅዱስ ሉቃስ የጌታችንን የሥጋዌ የዘር ሐረግ ከታች ጀምሮ ወደ ላይ ሲቆጥር "የአዳም ልጅ፥ የእግዚአብሔር ልጅ" በማለት የገለጸው ይህን እውነታ ነው፡፡ ሉቃ. 3፡23-38 በተዋሕዶ ምሥጢርም የቃል ገንዘብ ለትስብእት፣ የትስብእትም ገንዘብ ለቃል ሆኗል፡፡ ይህም ከፍጹም ተዋሕዶ የተነሣ ነው፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ "እንቲአሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእንቲአሁ ዘሥጋ ኮነ ለቃል" ብሎ የገለጸው ይህን ነው፡፡[25]

ቅዱስ መጽሐፍ ስለ ጌታችን ሲናገር የሚናገረው ይህንኑ ነው፡፡ ለምሳሌም ሁለት ጥቅሶችን ብቻ እንመልከት፡፡ ጌታችን "ከሰማይም ከወረደ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፣ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው" አለ፡፡ ዮሐ. 3፡13 ትስብእት የተገኘው ከዚህ ዓለም ሲሆን ገና ወደ ሰማያት ከማረጉ በፊት ይህን ትስብእትን "በሰማይ የሚኖር" አለው፡፡ በሰማይ መኖር ለባሕርይ ተገቢነቱ ለመለኮት ሲሆን በተዋሕዶ ግን ይህ ለትስብእትም ተነግሯል፤ ከተዋሕዶ በኋላ የእካልም ሆነ የባሕርይ ምንታዌ (ሁለትነት) የለምና፡፡ እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ "አውቀውስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር" አለ፡፡ 1 ቆር. 1፡8 የክብር ጌታ የተባለ መለኮት ብቻ ነው እንዳንል "ሰቀሉት" አለ፤ መሰቀል ጥንቱን ለትስብእት እንጂ ለመለኮት አይስማማምና፡፡ የተሰቀለ ትስብእት ብቻ ነው እንዳንል ያን "ሰቀሉት" ያለውን "የክብር ጌታ" አለው፡፡ ስለዚህ የተሰቀለው ያው አንዱ ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ በተዋሕዶ ነው ማለት ነው፡፡ የትስብእት ብቻ ገንዘብ የነበረ መሰቀል ለመለኮትም ተነገረ፣ የመለኮት ብቻ የነበረ የክብር ጌትነት ለትስብእትም ተነገረ፡፡ እስመ ተዋሕዶ አእተታ ለምንታዌ - ተዋሕዶ ሁለትነትን አጥፍቷልና፡፡

በአንጾኪያ የነበረው የነገረ ሃይማኖት ትምህርት ቤት መሥራቾቹና ኋላም የተነሡት ብዙዎቹ መምህራን በአመዛኙ የሚከተሉት ገጸ ምንባብ ላይ ያተኮረ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ሲሆን የክርስትና ሃይማኖትን የተመለከቱ እውነታዎችንና አስተምህሮዎችን ለመረዳትና ለመተንተን አመክንዮአዊ አካሄዶችን ይመርጡና ወደ እነዚህ ያደሉ ነበር፡፡ የዚህ አስተሳሰብ መሥራቾችና አባዳጊ ሞግዚቶች የነበሩትም የጠርሴስ ጳጳስ የነበረው ዲያድርስ (Diodore of Tarsus) እና፣ በወጣትነቱ በገዳማዊ ሕይወት ለመኖር ወስኖ ከነበረ በኋላ ወደ ኃጢአት ጫፍ ደርሶ በቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ከፍተኛ ምክርና ተግሣጽ ወደ ቀደመ ዓላማው መመለስ የቻለውና ኋላም የሞፕሶስቲያ ጳጳስ የሆነው ቴዎዶር (Theodore of Mopsuestia) ናቸው፡፡

እነዚህ የአንጾኪያ የነገረ ሃይማኖት መምህራን የቃልን እና የትስብእትን ተዋሕዶ፣ በተዋሕዶ ሰው የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ሲያስረዱ የሚጀምሩት በታሪክ ከሚታወቀው፣ በምድረ ፍልስጥኤም ከኖረው ታሪካዊ ጭብጥ ነው፡፡ ይህ በሰዎች ዘንድ ከሚታወቀውና ከታሪካዊው ጭብጥ እንነሣ የሚለው አካሄዳቸውም የአሪስቶትል የፍልስፍና አካሄድ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ በኋላም በተለያዩ ፈላስፎች የዳበረው ኢምፒሪሲዝም (Empiricism) የተባለው የእውቀት መንገድ ነው፡፡ በዚህ ነገረ መለኮታዊ አካሄዳቸው ሄደው ሄደው መጨረሻ የደረሱትም ከተሳሳተ ድምዳሜ ላይ ነበር፡፡

የእስክንድርያ ትምህርት ቤት አባቶች ደግሞ በአመዛኙ ወደ ምሥጢራዊ የአተረጓጎም ዘይቤ ያደላ አካሄድን የሚከተሉ የነበረ ሲሆን ነገረ ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን አመክንዮአዊ ከሆነው መንገድ ይልቅ ምሥጢራዊነታቸውን በመቀበል ላይ ያመዘነና ወደዚህ ያደላ አካሄድ ነበራቸው፡፡ የቃልንና የትስብእትን ተዋሕዶ ሲያብራሩና ሲያትቱም መነሻ የሚያደርጉትና ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጡት በቃል የባሕርይ አምላክነት ላይ ነው፡፡ ይህም "ቃል ሥጋ ሆነ" በሚለው የዮሐንስ ወንጌል መሠረታዊ ትምህርት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ አንጾኪያውያን ደግሞ ሰው መሆኑ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡

[25] (Communion of Idioms)

የቴዎዶር ዘሞፖስቲያ እና የዲያድርስ እንዲሁም የተከታዮቻቸው አስተምህሮ በክርስቶስ ሰውነት ላይ ከመጠን በላይ የሆነ አጽንዖት ያደርግ ነበር፡፡ እንዲሁም አካላዊ ቃል አደረበት የሚሉትን ኢየሱስን እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ካደረባቸው ከነቢያትና ከሌሎች ሰዎች ትንሽ ብቻ ከፍ ያለ እንጂ ከዚያ ውጭ ምንም የተለየ ነገር የሌለው እያደረጉ ማስተማራቸውን አጠንክረው ገፉበት፡፡ በሁለቱ መካከል አንድነት አለ ቢሉ እንኳ የተለያዩ ነገሮች ቀንጀኝነት ወይም አፍአዊ ጥምረት እንጂ ተዋሕዷዊ ነው አይሉም ነበር፡፡ ይህ አስተምህሮቻቸውም አንዱን ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ሁለት አካል፣ ሁለት ባሕርይ እና ሁለት ፈቃድ የሚከፍል ሆነ፡፡

እስክንድርያውያን ከላይ፣ ከቀዳማዊነቱ፣ ከመለኮታዊ ባሕርዩ ሲነሡ፤ አንጾኪያውያን ደግሞ ከታች፣ ሰው ከመሆኑ፣ በታሪክ የታወቀ በምድረ እስራኤል የኖረና የተመላለሰ ከሆነው ከምድራዊ አኗኗሩ ይነሣሉ፡፡ ይህ አነሳሣቸውና ትኩረታቸው ቀስ በቀስ ወደ ተለያየ አረዳድና አተረጓጎም፣ ብሎም ወደ ተቃራኒ አቋም አደረሳቸው፡፡ የአንጾኪያዎቹ ነገረ ተዋሕዶን የተመለከተት ክርስቶሳዊ አቀማመጥ ነበር፣ የተጠቀሙት የአመክንዮ መንገድም ከትንሹ ወደ ከባዱ የሚደረግን የአጠቃልሎ መንገድ (Inductive method) ነበር፡፡ በአንጾኪያው ትምህርት ቤት ይትበሃል ዋና ተጠቃሽ የሚባለው ቴዎዶር ዘሞፕሶስቲያ ትንታኔውንና ሐተታውን ከሚታየውና ከሚጨበጠው - ከሰውነቱ - ጀመረ፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ ደግሞ ምሥጢራዊና ረቂቅ ከሆነው - ከአምላክነቱ - ጀመረ፡፡ ከቅዱስ ቄርሎስም በፊት ሆነ በኋላ፣ በራሱ በቅዱስ ቄርሎስም በአጠቃላይ የእስክንድርያ አባቶች መሠረታዊ ማጠንጠኛ የነበረው ነገር ለሰው አእምሮ እጅግ ረቂቅና ምጡቅ የሆነው የአካላዊ ቃል ከትስብእት ጋር በማይመረመር ምሥጢር የመዋሐዱ ነገር ነበር፡፡

የእስክንድርያ አባቶች ምን ጊዜም የቃልን እና የሥጋን ተዋሕዶ እና የዚህን የሥግው ቃል አምላክነት በአጽንኦት ከመግለጽ ተቆጥበው አያውቁም ነበር፡፡ አንጾኪያውያን ግን አካሄዳቸው ኢየሱስ ክርስቶስን የሁለት ልጆች (የእግዚአብሔር ልጅ እና ከድንግል ማርያም የተወለደው) ውጫዊ ጥምረት ብቻ ወደ ማድረግ አደረሳቸው፡፡ ቴዎዶር ዘሞፕሶስቲያ "መለኮት ከድንግል ማርያም በተገኘው ትስብእት አደረበት" ብሎ የኀድረትን ትምህርት አስተማረ፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ እና ከድንግል ማርያም የተገኘው የእርሷ ልጅ አንድነታቸው በውጫዊ መገለጫቸው (Only at the level of prosopon) ብቻ ነው አለ፡፡ ፕሮሶፖን (προσoπov – prosopon) የሚባለው በመድረክ ላይ አንድን የሆነ ገጸ ባሕርይን ወክሎ ለመተወን ሲሉ የድራማ ወይም የትርኢት ተዋናዮች ፊታቸውን ለመሸፈን የሚያጠልቁት ጭምብል ነበር፡፡ ፕሮሶፖን በአጠቃላይ አንድን ግለሰብ ከሌላው ግለሰብ የሚለየው ውጫዊ ነገር ማለት ነው፡፡ ቴዎዶር በአንድ ውጫዊ የጋራ መገለጫ ውስጥ ያሉ ሁለት ሰዎች (Two Persons in one prosopon) ብሎ ያስተምር ነበር፡፡ አንድነታቸውም በፕሮሶፖን ደረጃ ብቻ ነው አለ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስንም "እግዚአብሔር ያደረበት ሰው" ይሉት ነበር፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምንም "ወላዲተ ሰብእ - የእግዚአብሔር ቃል የሚያድርበትን ሰው የወለደች" የሚሏት ከዚህ መሠረታዊ ስሁተት የተነሣ ነበር፡፡

በእርግጥ ከሁለቱም ትምህርት ቤት ታላላቅ አባቶችም መናፍቃንም ተገኝተውባቸዋል፡፡ ሆኖም ብዛቱን ስናይ ግን ከእስክንድርያ የወጡት መናፍቃን (አቡሊናርዮስ) ያራመዱት አቋም ትምህርት ቤቱ የማይቀበለው ሲሆን ቁጥራቸውም በጣት የሚቆጠር ነው፡፡ ከአንጾኪያ ትምህርት ቤት ግን በእሾህ መካከል እንደ በቀለ ልዩ ጽጌረዳ ከእነ ዲያድርስ ጋር ኖሮና ተምሮ ልዩና ደገኛ ኦርቶዶክሳዊ የሃይማኖት አባት ሆኖ ከተገኘው ከቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በቀር ሌላ ደኅና ተደርጎ ሊጠቀስ የሚችል ኦርቶዶክሳዊ አባት ብዙም አልነበረም፡፡ በአንጾኪያ ወደ ኋላ ላይ እንደ ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያና ቅዱስ ፊልክስዮስ የመሳሰሉ አዲስ ኦርቶዶክሳዊ ትውልድ እስከ በቀሉበት እስከ አምስተኛው መቶ ዓመት ማብቂያ ድረስ ብዙዎቹ የዲያድርስ እና የቴዎዶር ዘሞፕሶስቲያ አስተሳሰብ ደጋፊዎችና አቀንቃኞች ነበሩ፡፡

ይህን የእነ ዲያድርስና በተለይም የቴዎዶር ዘሞፕሶስቲያ ክርስቶስን የሁለት ሰዎች ጥምረት (ተጋውሮ - መለኮታዊው ለብቻው፣ ትስብእት ለብቻው) አድርጎ የማሰብና የማስተማር አስተሳሰብ ወደ መድረክ ያወጣውና ፀሐይ እንዲሞቀው ያደረገው ንስጥሮስ ነው፡፡ ከዚያ በፊት በአብዛኛው በትምህርት ቤት ደረጃ ተወስኖ የነበረውን ይህን መሠረታዊ ስህተት ንስጥሮስ በቁስጥንጥንያ መንበር ላይ ፓትርያርክ በሆነ ጊዜ ወዲያውኑ በአንድ ጊዜ ናኘው፡፡ ከዚያም ነገሩ ከማይመለስበት ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡ በ431 ዓ. ም. በኤፌሶን በተካሄደው 3ኛው ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ንስጥሮስና ትምህርቱ ተወገዘ፡፡

ሆኖም ልዮናውያንና ፕሮቴስታንቶች ይህን የንስጥሮስን የ "ሁለት ባሕርይ ሁለት አካል" ትምህርት በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ "አንድ አካል ሁለት ባሕርይ" በሚል ካባ እንደ ገና ሸፈንፈን አድርገው እስከ ዛሬ ድረስ ይዘውት ይገኛሉ፡፡ እንደ ቅዱስ ቄርሎስ "ከተዋሕዶ በፊት ከሁለት ባሕርይ፣ ከተዋሕዶ በኋላ ግን ያለ መለያየት ያለ መከፋፈል፣ ያለ መጠፋፋት ያለ መቀላቀል በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ - One Incarnate Nature of God the Word" ብለን በተዋሕዶ የምናምነውን ግን "ሞኖፊሳይትስ - Monophysites" በሚል የተሳሳተ ቃል ስማችንንና ግብራችንን ሲያጠፉ ኖረዋል፡፡ እኛ ግን በተዋሕዶ የምናምን "ሚያፊዚት - Miaphysite" እንጂ "ሞኖፊዛይት" አይደለንም፡፡[26] እኛ የምናምነው በቅዱስ መጽሐፍ የተገለጸውን፣ በሦስቱ ጉባኤያት የተብራራውን እና በታላቁ የተዋሕዶ ምሥጢር ጠበቃና ማኅተም በቅዱስ ቄርሎስ የቃልና የትስብእት ተዋሕዶ አካላዊም ባሕርያዊም ስለሆነ ከተዋሕዶ በኋላ ያለ መለያየትና ያለ መከፋፈል፣ ያለ መጠፋፋትና ያለ መቀላቀል አንድ ሥጋው ቃል (μία φύσις τοῦ θεοῦ λόγου σεσαρκωμένη - *mia physis tou theou logou sesarkōmenē* - one (*mia*) nature of the Word of God Incarnate") ብሎ የገለጸውን ነው፡፡[27]

ሆኖም በየጽሑፎቻቸው ሁሉ በተዋሕዶ የምናምነውን ኦርቶዶክሳውያን እኛነታችንን የማይገልጽ ስም በመለጠፍ የራሳቸውን ንስጥሮሳዊ ይትበሃል ለመሸፈን ዛሬም ድረስ ዋናው መሣሪያቸውና ስልታቸው አድርገው ይዘውት መገኘታቸውን ስናይ ግብዝነታቸው በእጅጉ ያሳዝናል፡፡ እኛን በምናምነው ጥርት ያለ የተዋሕዶ እምነትና ትምህርት መንቀፍና ስህተት ማግኘት ሳይቻላቸው ሲቀር የራሳቸውን ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው እና ከአባቶች ትምህርት መውጣት ማሳየት ሲያቅታቸው እኛ ላይ እኛ የማናምነውንና ያልሆንነውን በግድ "ናችሁ" በማለት ሌላውም እንዲያ እንዲያስብ በማድረግ ሲያጭበረብሩ ኖረዋል፡፡ የጉዳዩ ጭብጥ ምንነት እንዳይፈተሽና ውስጠ ማንነታቸው እንዳይመረመርና ስህተታቸው እንዳይታወቅባቸው ለማድረግ ይህን የፕሮፓጋንዳ ስልት እስከ አሁንም ድረስ ለአንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመታት ያለ መታከት እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡

እነዚህ ንስጥሮስ ዘመም ኬልቄዶናውያንና ከእነርሱ የተወለዱት ፕሮቴስታንቶች፣ እንዲሁም ልጆቻቸው ተሐድሶዎች ለቅዱስ ቄርሎስ ብዙም በጎ የሆነ አመለካከት የላቸውም፡፡ ለአብነትም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሰብእናቸውና ድርጊቶቻቸው ብዙ ውዝግብ ለሚያስነሱ የተለያዩ ሰዎች ሳይቀር ከጥንት ጀምሮ ደስ ሲላት የቅድስና መዓርግ እየሰጠች የነበረች ሲሆን "ዓምደ ሃይማኖት"፣ "ማኅተመ አበው" እየተባለ ለሚጠራውና ነገረ ተዋሕዶን ጥርትና ፍንትው አድርጎ ያስተማረውን ታላቁን ሊቅና አባት ቅዱስ ቄርሎስን ግን እንደ መምህርና አባት እንኳ እውቅና የሰጠችው ካረፈ (444 ዓ. ም.) ከአንድ ሺህ አራት መቶ ዓመት በላይ ቆይታ በ19ኛው መቶ ዓመት ማብቂያ ገደማ (በ1882 ዓ. ም. እ. ጎ. አ) ነው፡፡ ይህ በአጋጣሚ የሆነ ነው ሊባል ይቻል ይሆን? የቅዱስ ቄርሎስ ትምህርት ስህተታቸውንና ውስጠ ንስጥሮሳዊነታቸውን ስለሚጋልጥባቸው ነው፡፡

---

[26] "Mono - physite" ማለት ነጠላ አንድ ባሕርይ ማለት ሲሆን "Mia - physite" ማለት ግን ከሁለት ነገሮች የተዋሐደ አንድ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ሰው አንድ ነው፤ ሆኖም ግን አንድነቱ ነጠላ (Mono) አንድነት ሳይሆን ከነፍስ እና ከሥጋ ተዋሕዶ የተገኘ አንድነት (Mia) ነው፡፡

[27] (St. Cyril of Alexandria, "Against Nestorius," I, 1, 6, 33)

በተሐድሶዎችም ይህን ንስጥሮሳዊ አስተሳሰብና ውጤቱን በቦታው ላይ ስንደርስ እናገኘዋለን፡፡ በአጠቃላይ የተሐድሶዎች አስተሳሰብና ትምህርት እንደ ሌጌዎን[28] ያለ ነው፤ ከተለያዩ መናፍቃንና ኑፋቄዎቻቸው የተቃረመና የተቀየጠ ነው፡፡

## 1.2.2.4 ሄሊቪዲየስ (Helividius)

ሄሊቪዲየስ በ4ኛው መቶ ዓመት የነበረ ሮማዊ ሲሆን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከጌታችንና ከሐዋርያት ከተቀበለችው ተቃራኒ የሆነ "ድንግልና ሕይወት ምንም ጥቅም የለውም፣ ጋብቻ ከድንግልና ይበልጣል፣ ከዚህም የተነሣ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ጌታችንን ከወለደች በኋላ ሌሎች ልጆችን ወልዳለች" የሚል አዲስና የፈጠራ ትምህርት ይዞ ብቅ ያለ መናፍቅ ነበር፡፡

በእርሱ የስህተት ትምህርት ላይ መልስ የጻፈው አባ ሄሮኒመስ (ጀሮም) የሄሊቪዲየስ ትምህርት ቤተ ክርስቲያን ስምታው የማታውቀው እንግዳ ነገር መሆኑን ሲናገር "በቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት ጀምሮ ከነበረውና ካለው እውነት ጋር መታገል ምን ይጠቅምሃል? በቅዱሳት መጻሕፍት እንዲሁም ከእነርሱ በፊት በነበሩት አባቶች በእነ አግናጥዮስ፣ በእነ ፖሊካርፐስ፣ በእነ ሄሬኔዎስ፣ በእነ ዮስጢኖስ ሰማዕት፣ እና በሌሎችም ቀደምት አባቶቻችን ተሰምቶ የማያውቅ እንግዳ ነገርን ከየት አገኘኸው?" ሲል ይሞግተዋል፡፡ ሄሊቪዲየስ መልስ አልነበረውም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በራሱ መንገድ አጣምሞ ከመተርጎም ውጭ ሄሊቪዲየስ ራሱ ለፈጠረው አዲስ አረዳድና ትምህርት ከእርሱ በፊት ከነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች አንድም ምስክር አልነበረውም፡፡ ይህም ቅዱሳት መጻሕፍትን መረዳት የሚገባው በራስ መንገድ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያን በምታስተምረውና በምትረዳው መንገድ እንደ ሆነ፣ ሊሆን የሚገባውም ይህ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ ሆኖም ግን ሄሊቪዲየስ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ጥቂት ተከታዮችን አፍርቶ ነበር፡፡ ይህን የሄሊቪዲየስን ስህተት በተሐድሶዎች ውስጥም ተንሰራፍቶ እናገኘዋለንና አሁንም ቦታው ላይ ስንደርስ እናነሳዋለን፡፡

ሄሊቪዲየስ የድንግልና ሕይወትን ከሥሩ ለማጥቃት የእመቤታችንን ዘለዓለማዊ ድንግልና ማጥቃት አዋጭ ስልት ነው ብሎ በማሰብ ከዚያ ጀመረ፡፡ አባ ጀሮም ትምህርቱ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን በሚያሳይ መልኩ ጠንከር ያለ መልስ ጽፎበታል፡፡ ይህን የሄሊቪዲየስን ሃሳብ የያዙ ተሐድሶዎችም በዘመናችን "ቅንዓት አኃዞሙ ለሕዝብ አብዳን - ሰነፎች ሰዎችን ቅንዓት አቃጠላቸው" እንደ ተባለው የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ድንግልና በእነርሱ ስም ማጥፋት የሚቀርና ክብሯ የሚቀንስ እየመሰላቸው በማጥላላት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህንም በቦታው እናየዋለን፡፡ ይህን የሄሊቪዲየስን አስተሳሰብ በአውሮፓ የተነሡት ተሐድሶዎች እንኳ ሁሉም አልተቀበሉትም ነበር፣ ለምሳሌም ማርቲን ሉተር እንኳ የእመቤታችንን ዘለዓለማዊ ድንግልና ከሚቃወሙት ጋር አይስማማም ነበር፡፡ በሀገራችን የተነሡት ተሐድሶዎች ደግሞ ከአባታቸው ከሉተር ላቅ ብለው በመገኘት እንደ ሄሊቪዲየስ ያለ አስተሳሰብ ያራምዳሉ፡፡

## 1.2.2.5 ጆቪኒያን (Jovinian)

ጆቪኒያን በመጀመሪያ ሕይወቱ መጠን አለፍ በሆነ ጽኑ ብሕትውናና ትህርምት ታዋቂና ተደናቂ የነበረ ሮማዊ መነኩሴ ነበር፡፡ ሆኖም በአስተሳሰቡ እንዳሻኝ ማሰብ እችላለሁ፣ ነጻ ሰው ነኝ ባይ ዓይነት ሰው ስለ ነበር ቀስ በቀስ በሂደት ተሸርሽሮ አለቀና ወደ ኋላ ላይ የምንኩስና አርማውን አወላልቆ እንደ ማንኛውም ሰው መኖር ጀመረ፡፡ የተለያዩ ባእድ ትምህርቶችንም ማስተማር ጀመረ፡፡ ከእነዚህም መካከል፡-

[28] ሌጌዎን ማለት ቃሉ በውስጡ ብዙ ወታደር የያዘ የጦር ክፍል ማለት ሲሆን በዋናነት ግን ቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በአንድ ሰው ውስጥ ተሰባስበው ያደሩ ቁጥራቸው በጣም ብዙ የሆኑ አጋንንትን (የአጋንንት ስብስብ) ይገልጻል፡፡ በዚህ አገባብ ሌጌዎን ማለት የብዙ ስህተቶች ጥርቅም ማለት ነው፡፡ ማቴ. 5፡9 (Easton's Bible Dictionary, Thomas Nelson, 1987)

(1) ያገባች ሴትም ሆነች በድንግልና የኖረች ሴት በእግዚአብሔር ዘንድ ምንም ልዩነት የለውም፣
(2) መብላትም ሆነ መጾም አንዳችም ልዩነት የለውም፣
(3) በመንፈስም ሆነ በውኃ የተጠመቀ ሰው ኃጢአት ሊሠራ አይችልም፣
(4) ሁሉም ኃጢአት እኩል ነው፣
(5) በሚመጣው ዓለም ያለው ቅጣትም ሆነ ክብር ለሁሉም አንድ ዓይነት (እኩል) ነው፣
(6) እመቤታችን ጌታን ስትፀንሰው ድንግል ነበረች፣ ስትወልደው ግን አይደለችም የሚሉ አስተምህሮዎች ነበሩ።

ከዚያ በኋላም ጌጠኛ ልብስ መልበስና መኩነስነስ ያዘወትር ነበር፡፡ በ390 ዓ. ም. ገዳማ ምንኩስናንና የድንግልና ሕይወትን የሚነቅፍ መጽሐፍ ጽፎ ነበር፡፡ መጀመሪያ ላይ ጆቪኒያን በ390 ዓ. ም. በሮም በተካሄደ ጉባኤ (ሲኖዶስ) ላይ ከስምንት ግብረ አበሮቹና ተከታዮቹ ጋር ተወገዘ፡፡ በመቀጠልም ለቅዱስ አምብሮስ ለማስረዳትና ከግዝቱ ያስፈታው ዘንድ ለመለመን ወደ ሚላን ሄደ፡፡ ሆኖም የሚላኑ ጳጳስ የነበረው ቅዱስ አምብሮስ ጆቪኒያንን ከነትምህርቱ በድጋሚ አወገዘው፡፡ ሆኖም በሚላን የነበሩ ከጆቪኒያን ጋር ተመሳሳይ አቋም የነበራቸው ሁለት መነኰሳት ነበሩና እነዚያ ክኅኑ ለመሰለፍና ጆቪኒያንን ለመደገፍ ሞከሩ፡፡[29]

ጆቪኒያን በዘመኑ የነበረውን ፖለቲካዊ ትኩሳትና ሁኔታ በመጠቀም ዓላማውን ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት ያደርግ ነበር፡፡ ጆቪኒያን ኑፋቄውን ለማስፋፋት እየጣረ ባለበት በዚያን ጊዜ ምሥራቁንና ምዕራቡን የሮማ ግዛት አንድ ላይ ጠቅልሎ እየገዛ በነበረው በታላቁ ንጉሥ በቴዎዶስዮስ ላይ መንግሥቱን ለመቀማት የተነሣ አውጌንዮስ የተባለ ሰው ነበር፡፡ አውጌንዮስ በደጋፊዎቹ ወታደሮች ንጉሥ ተብሎ ተሰይሞም ነበር፡፡ አውጌንዮስ "ከቀናኝና ቴዎዶስዮስን ድል አድርጌ ከነገሥሁ የጥንቱ የሮማ አማልክት እንደ ቀድሞው ዘመን ልማድ እንዲመለኩና መሥዋዕት እንዲቀርብላቸው አደርጋለሁ" የሚል ቃል ለሮማውያን ገብቶላቸው ነበር፡፡ ያን ጊዜ ፍቅረ ጣዖት ያልወጣላቸውና በክርስትና መስፋፋት ውስጣቸው ሲበሳጭ የነበሩ መፍቀርያነ ጣዖታት ሰዎች ከኅኑ ተሰለፉ፡፡

አውጌንዮስም የአሕዛብ ጣዖታት አምላኪዎች ተወርሶባቸው የነበረውን ቤተ መቅደስና ንብረት መለሰላቸው፡፡ አብሮ ለጳጳሳትም ስጦታ ሰጣቸው፡፡ በክርስትና መስፋፋት ፈርሰውና ተትተው የነበሩ የተለያዩ ጣዖታት እንደገና እንዲሠሩና መሥዋዕት እንዲቀርብላቸው ማድረግ ጀመረ፡፡ በዚህ ሁሉ ድርጊቱ የሚላኑ ታላቅ አባት ቅዱስ አምብሮስ እውቅና እንዲሰጠው ደጋግሞ ቢለምነውም ቅዱስ አምብሮስ ክርስትናን እየተዋጋ ካለ ሰው ጋር አንዳችም ኅብረት አይኖረኝም በማለት ምንም እውቅና ሳይሰጠው ቀረ፡፡ ሊገናኘው እርሱ ወደ ነበረበት ቦታ ሲመጣም ጥሎት ወደ ሌላ ቦታ ሄደ፡፡

ጆቪኒያን እንዲህ ባለው ሁኔታ ውስጥ ነበር አፍቃሬ ጣዖታት ጸላኤ ክርስቶስ በሆነው በአውጌንዮስ ለመጠቀምና ዓላማውን ለማስፋፋት የወሰነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ከክርስትና ጠላቶች ጋር ማበራቸውና ዓላማቸውን ለማስፈጸም ቤተ ክርስቲያንን ከሚጠሏትና በግልጽም ሆነ በስውር ከሚያሳድዷት አካላት ጋር ማበራቸው የነበረ ነገር ነው፡፡ ግርግር ይመቻቸዋልና በዚያ ለመጠቀም ይመኛሉ፡፡ ሆኖም አውጌንዮስ በ393 ዓ. ም. በተካሄደ ጦርነት በቴዎዶስዮስ ተሸነፈ፤ እርሱም ተገደለ፡፡ በእርሱ ላይ ተስፋ አድርጎ የነበረው ጆቪኒያንም ቤተ ክርስቲያንን የማወክ ተስፋው አብሮ ሞተ፡፡

አውጌንዮስ ከቴዎዶስዮስ ጋር ሊዋጋ ወደ ነበረው ጦርነት እየሄደ ሳለ ከነጦር አዛገኖቹ በድል ሲመለሱ "ሚላን የነበረውን ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ወደ እህል ጎተራነት እንለውጠዋለን፣ ካህናትንም በውትድርና እንዲያገለግሉ እናደርጋቸዋለን" ብለው ዝተው ነበር፡፡ ከቆስጠንጢኖስ ጀምሮ የጦር ሠራዊቱ ዓርማ የነበረውን የክርስቶስ መስቀል በጣዖት ምልክት ቀየሩት፡፡

[29] (St. Ambrose, *Epistles*)

ቴዎዶስዮስ ደግሞ በጸሎትና በምህላ እግዚአብሔር በእነዚህ ጸረ ክርስቶስ መናፍቃርያን ማየት ላይ ድል ይሰጠው ዘንድ አጥብቆ አምላኩን ይማጸን ነበር፤ ክርስቲያኖችም እንዲሁ ከእርሱ ጋር፡፡ አቂላ (Aquileia - ጣሊያን ሀገር ውስጥ) በተባለችው ቦታ ላይ በተደረገው ጦርነት የዛቱት አውጌንዮስና ጀነራሎቹ ሁሉም የተገደሉት ተገደሉ፣ ሌሎችም ራሳቸውን አጠፉ፡፡ ንጽሕናንና ገዳማዊ ሕይወትን ይጠሉ የነበሩት፣ ከመምለክያነ ጣዖታት ከእነ አውጌንዮስና ዘውጎቻቸው ጋር ተባብረው ቤተ ክርስቲያንን በጋራ ለማጥቃት ተነሥተው የነበሩት የእነ ጆቪኒያን ምኞትም በአጭሩ ተቀጨ፡፡

በዚያን ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች ጆቪኒያንን "የክርስቲያኖች ኤፒኩረስ[30]" ይሉት ነበር፡፡ ቅዱስ ጀሮምም (አባ ሄሮኒመስ) ጆቪኒያንን "የጥፋት ባሪያ፣ ከሰማይ ይልቅ መሬትን የመረጠ፣ ከቅድስና ይልቅ ርኩሰትን፣ ከክርስቶስ ይልቅ ክርሱን የመረጠ የክርስቲያን ኤፒኩሪያን" ይለዋል፡፡ ጆቪኒያን ራሳቸውን በድንግልና ለመኖር ለእግዚአብሔር የሰጡ ደናግላንን ብጽዓታቸውንና የኖሩበትን ሕይወታቸውን ትተው ባል እንዲያገቡ ደገፋፋቸውና ይሰብካቸው ነበር፡፡ ከአይሁድነት ወደ ፕሮቴስታንትነት የተለወጠውና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ላይ ሰፊ ምርምርና ጥናት ያደረገው ኒያንደር የተባለው ሰው ጆቪኒያንን ከሉተር ጋር ያነጻጽረዋል (ያመሳስለዋል)፤ ምክንያቱም ሁለቱም ጠንካራ የሆነ ጸረ ምንኵስናና ጸረ ገዳማዊ ሕይወት አቋም ያሳደሩትና ያራመዱት መነኰሳት ሳሉ በራሳቸው ሕይወት ካሳለፉት ሁኔታ አንጻር ስለ ነበር ነው፡፡ ሁለቱም ምንኩስና ስለ ከበዳቸውና በጀመሩት የሕይወት መንገድ መቀጠል ስላስቸገራቸው ያን ሕይወት መንቀፍና አምርረው መጥላት፣ ከዚያም ጸረ ምንኵስናና አጠቃላይ አዲስ የሆነ የራሳቸውን መንገድ መቀየስ ጀመሩ፡፡ የጆቪኒያንን ትምህርት የተቀበሉ በሮም የነበሩ አንዳንድ መነኰሳትና መነኮሳዪያት ምንኩስናቸውን እየተው ማግባት ጀምረው ነበር፡፡

## 1.2.2.6 ቪጂላንቲየስ (Vigilantius)

ቪጂላንቲየስ በ4ኛው መቶ ዓመት ማብቂያና በ5ኛው መጀመሪያ ላይ የነበረ ቄስ ሲሆን ዋና ተቃውሞውም በሌሊት በቤተ ክርስቲያን የሚደረጉ የሲጠን፣ የማኅሌት እና የመሳሰሉትን ጸሎታት (Vigils) ማድረግን አጥብቆ ይቃወም ነበር፡፡ አባ ሄሮኒመስ ቪጂላንቲየስን ግብሩ እንደ ስሙ ሳይሆን በተቃራኒው ስለሆነ "ቪጂላንቲየስ - Vigilantius - ትጉሁ" መባሉ ቀርቶ "ዶርሚቲያኖስ - Dormitianus - እንቅልፋሙ" ቢባል ይሻላል ያለው ለዚህ ነበር፡፡ ከዚህም ጋር ለዐጽመ ቅዱሳን ክብር መስጠትን ይቃወም ነበር፡፡ ክርስቲያኖችን "ዐጽም አምላኪዎች"፣ "መተተኞች" እንዲሁም "ጣዖት አምላኪዎች" እያለ ይሰድባቸው ነበር፡፡

ቪጂላንቲየስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማታና የሌሊት ጸሎት ማድረግን አምርሮ ይነቅፍ ነበር፡፡ ከዚህም ጋር ጾምን፣ ራስን መግዛትን፣ ድንግልናን፣ ንጽሕናን ሁሉ ይነቅፍና ይዘልፍ ነበር፡፡ ቅዱሳን የጾሟቸውን አጽዋማት ይቃወም ነበር፡፡ መዝሙረ ዳዊት መጸለይ (መደገም) ያለበትም የተድላና የደስታ ቀናት በሆኑ በዓላት ቀን ብቻ መሆን አለበት ይል ነበር፡፡

## 1.2.2.7 አርዮስ ዘሴባስቴ (Arius of Sebaste)

ይህ አርዮስ ሌላ አርዮስ ሲሆን በፖንተስ ኤዎስጣቴዎስ ከተባለው የሴባስቴ ጳጳስ ጋር የነበረ ካህን ነበር፡፡ መጀመሪያ ላይ በ360ዎቹ ዓ. ም. ገደማ የኤዎስጣቴዎስ ዘሴባስቴ የብሕትውና እንቅስቃሴ አካል ነበር፣ እርሱ ራሱም ተሐራሚ ባሕታዊ ነበር፡፡ ሆኖም ወደ ኋላ ላይ ጾምን እና በዓመቱ ውስጥ ክርስቲያኖች ሁሉ በአንድነት የሚጾሙበት የታወቀ የጾም ጊዜ መኖሩን ይቃወም ነበር፡፡ እርሱና ተከታዮቹ በሰሙነ ሕማማት መጾምን ይቃወሙ ነበር፡፡ ሆኖም በሰንበተ ክርስቲያን በፈቃዳቸው ይጾሙ ነበር፡፡ እንዲሁም የአይሁዳውያን ተረፍ ነው በማለት የትንሣኤን በዓል ማክበርን ይቃወም ነበር፡፡ እንዲሁም ለሙታን ጸሎት ማድረግንም ይቃወም ነበር፡፡ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ደግሞ አርዮሳዊም ነበር ይለዋል፡፡

[30] ኤፒኩረስ የተባለው ግሪካዊ ፈላስፋ ዋናው የሰው ሕይወት ዓላማ (ግብ) በዚህ ዓለም ማግኘት የሚችለውን ያህል ደስታ ማግኘት ነው ይል የነበረ ፈላስፋ ነበር፡፡

## 1.2.2.8 ማርቲን ሉተር

በ16ኛው መቶ ዓመት በምድረ አውሮፓ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን በመቃወምና በመገንጠል የፕሮቴስታንቲዝምን እንቅስቃሴ ያስከተለውን የማርቲን ሉተርን አስተምህሯዊ፣ ታሪካዊ እና ፖለቲካዊ ዳራዎችና ምንነቶች እዚህ ላይ በዝርዝርና በጥልቀት ባንመለከተቻውም መሠረታዊ የሆኑትን ጉዳዮች ብቻ በአጭሩ እንሥተናቸው እናልፋለን፡፡ ይህም ሉተርና እንቅስቃሴው ከራሱ ግለሰባዊ ሰብእና ባሻገር በነበረበት ዘመን የነበሩት ሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማኅበረሰባዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ዳራ የተፈጠሩ በመሆናቸው ነው፡፡ ሰብእናውም ከእነዚህ ነገሮች ተለይቶ ሊታይ አይቻልም፡፡

በነገረ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ከአነ ልዮን ጀምሮ በይፋ እውነትን በመግፋት ጉዞዋን የጀመረችው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት ትምህርት እየወጣችና እየራቀች የፖፑን የበላይነትና አይሳሳቴነት[31] ዋና ጉዳይዋና ትኩረቷ አድርጋ እየያዘች የመጣችውና በኬልቄዶን ጉባኤ በይፋ ከተቀበለችው ንስጥሮሳዊ "ከተዋሕዶ በኋላ ሁለት ባሕርይ"[32] ትምህርት በተጨማሪ በየጊዜው የተለያዩ የስህተት ትምህርቶችን መጨመሯን ቀጠለች፡፡ ከእነዚህ ከጨመረቻቸው ስህተቶች መካከልም "መንፈስ ቅዱስ ከወልድም ይሠርፃል[33]" የሚል፣ "ፖፑ አይሳሳትም፣ የክርስቶስ እንደራሴ ነው" የሚል፣ "ከሞት በኋላ መካነ ንስሐ የሚባል የተለየ ቦታ አለ"[34] የሚል፣ እንዲሁም በጸጋ የከበሩ ቅዱሳን ያ ጸጋቸው ከእነርሱ መዳን አልፎ ለሌሎችም ሊተርፍና በድኅነት ጉዞ ላሉት ሊተርፋቸውና ሊረዳቸው ስለሚችል ("Treasury of merits") ያንን ለሚያስፈልገው ለሌላ ሰው ሊሰጡት ይችላል[35] የሚሉት ይገኙባቸዋል፡፡[36]

ይህ በመጨረሻ የተገለጸው አስተሳሰብና ልማድ ደግሞ በቀላሉ ወደ ስህተት ሊያመራና አላግባብ ሊተረጎም የሚችል ነገር ስለ ነበር ችግሩ በተግባር መከሰት ጀመረ፡፡ ፖፑ የክርስቶስ እንደራሴ ስለ ሆነና የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ ስላለው የእነዚህን ጸጋዎች ("merits") ከአንዱ ለሌላው መተላለፍ በተመለከተ ሥልጣኑ ያለው እርሱ ነው ይሉ ጀመር፡፡[37] እነዚህን ጸጋዎች ("merits") ወደሚያስፈልገው ሰው የማስተላለፉ ሂደት ነበር "የሥርየት ካርድ - indulgence" የሚባለው፡፡ ከዚህም የተነሣ በዘመኑ የነበረው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፖፕ በጣም ታላቅ የሆነ ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት በሚል ብዙ ገንዘብ ለማግኘት ከነበረው ከፍተኛ ፍላጎት ጋር ተዳምሮ ይህ ሁኔታ የሥርየት ካርድ መሸጥ እስከ መጀመር የደረሰ የተወሳሰበ ችግር ውስጥ እንድትገባ አደረጋት፡፡ ይህ የቅዱሳን የተትረፈረፈ ጸጋ የሚሉት ነገር በላቲን ቤተ ክርስቲያን ብቻ የተፈጠረ እንጂ በምሥራቃውያን (በኦርቶዶክሳውያን - በምሥራቅ ኦርቶዶክስም ሆነ በኦሬንታል ኦርቶዶክስ) ዘንድ ግን እንዲህ ያለ ነገር ፈጽሞ የለም፡፡ ሉተር ሲነሣ ባደገባትና በኖረባት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከፊቱ ነበሩ፡፡ ሉተር በዚያ ዓይነት ሁኔታ ላይ የነበረችው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መነኩሴ ነበር፡፡

---

31 (Papal Supremacy and Infallibility)

32 (Two Natures after the union)

33 Filioque, or the double Procession of the Holy Ghost from the Father and Son - ካቶሊካውያን ይህን የሃይማኖታቸው ዶግማ አድርገው ያወጁት በ4ኛው የላተራን ጉባኤ (Fourth Lateran Council) በ1215 ዓ. ም.፣ በሊዮ 2ኛ ጉባኤ (The Second council of Lyons -1274)፣ እና በፍሎረንስ ጉባኤ (The Council of Florence - 1438-1445) ነው፡፡

34 (Purgatory) - ካቶሊካውያን ይህን ያወጁት በፍሎረንስ ጉባኤ (The Council of Florence) እና በትሬንት ጉባኤ ነው፡፡

35 A doctrine of the "right of transfer" of these "merits" from the "treasury of merits" to those persons in need of spiritual help on the road to salvation.

36 Catholic Encyclopedia Online, በጥር 2006 እና በታኅሣሥ 2007 ዓ. ም. የተወሰደ

37 Georges Florovsky, The Ascetic Ideal and The New Testament, Reflections on the Critique of the Theology of the Reformation, The Collected Works, Vol. X.

በዘመነ ሉተር በማኅበረሰባዊውና በፖለቲካዊው ሁኔታ የነበረው ነገር በጣም ሰፊና ውስብስብ ስለሆነ እዚህ ላይ ማንሣት ቦታው አይደለም፡፡ በአጠቃላይ ግን በአውሮፓ የጥንቶቹን የቄሣሮች ቦታ ይዛ ነገሥታትን በየሀገሩ ስታነግሥና ስትሽር፣ ግብር ስታስገብርና እንዳሻት ስትፈልጥና ስትቆርጥ ከነበረችው የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተጽእና ነጻ የመሆንና ያለ መገበር ብሄራዊ ስሜቶች በየሀገራቱ በተለይ ደግሞ በሰሜኑ የአውሮፓ ክፍል በየጊዜው እያደገ ነበር፡፡ ሉተር ሲነሣ ይህ ፖለቲካዊ ትኩሳት በአገሩ በጀርመንና በሌሎችም አገሮች ተቀጣጥሎ የነበረበት ወቅት ስለ ነበር ሉተር እነዚያን ብሔራዊ ስሜቶችና ትኩሳቶች ለመጠቀም ክብሪት መጫር ብቻ በቂው ነበር፤ አደረገውም፡፡ በተቃራኒው የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በሕዝቡ ደረጃ ምን እየሆነ እንደ ሆነና ተገቢው መፍትሔ ካልተበጀለት በስተቀር ምን አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ማሰብ በማይችሉና በማይፈልጉ፣ እንዲሁም በሕዝቡ ዘንድ ስለ ነበረው ተጨባጭ ሁኔታ እውቀቱም፣ ለማወቅ ፍላጎቱም ባልነበራቸው ፓፓዎችና ግብረ አበሮች የምትመራ ተቋም ነበረች፡፡[38]

በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ላይ የነበረችው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መነኩሴ የነበረው ማርቲን ሉተር ወደ ምንኩስና ሕይወት የገባው አስቦበት ሳይሆን በድንገተኛ ክስተት ተነሣቶ በወሰነው ውሳኔ ነበር፡፡ ቤተሰቦቹን ጠይቆ ወደ ተማረበት ዩኒቨርሲቲ እየተመለሰ መንገድ ላይ ሳለ በድንገት መብረቅ ከፊቱ ላይ ወደቀበት[39]፡፡ ከመደንገጡና በጣም ከመፍራቱ የተነሣ ወደ ቅድስት ሐና ጮኸ፣ ከዚያ መዓት ቢተርፍ መነኩሴ እንደሚሆን ቃል ገባ (ተሳለ)፡፡[40] ከዚህም በተጨማሪ ከዚያው ጊዜ ቀጥሎ የሚወደው ጓደኛው በድንገት ስለ ሞተበት በእጅጉ አዝኖ ነበር፡፡ በስእለቱ መሠረት እንዲሁም በጓደኛው ሞት ከደረሰበት ሐዘን የተነሣ በ22 ዓመቱ ገዳም ገብቶ መነኮሰ፡፡[41] ሆኖም አውጥቶና አውርዶ አስቦበት በዓላማ ሳይሆን እንዲሁ በድንገት የገባበት የምንኩስና ሕይወት እየከበደው መጣ፤ በየጊዜውም ጭንቀት የማይለየው ሰው ሆነ፡፡ ኋላ ላይም ሉተር ራሱ ይህ ውሳኔው ድንገተኛና በፍርሃት ላይ የተመሠረተ እንደ ነበር "ገዳም የገባሁትና መነኩሴ የሆንኩት አስቤበትና ፈልጌ ሳይሆን በድንገትና በፍርሃት በተፈጠረብኝ ሁኔታ ነበር"[42] ሲል ተናግሯል፡፡

በሕይወቱ የሚያስጨንቀውም ከእግዚአብሔር መሐሪነትና ፍቅር ይልቅ የእግዚአብሔር ገናናነትና ፈራጅነት ስለ ነበር እርሱ ያለበትን ሁኔታ እያሰበ ኃጢአተኛ ሰው ገናና በሆነው በእግዚአብሔር ፊት ሊቀርብ የሚችለው እንዴት እንደሆነ በማሰብ ይጨነቅ ነበር፡፡ መነኩሴው ማርቲን ሉተር በገዳም ሳለ መንፈሳዊ አባቱ ለነበረው ስታውፒትዝ[43] በየጊዜው በቶሎ በቶሎ እየሄደ ጭንቀቱን ይነግረው ነበር፡፡[44] መንፈሳዊ አባቱም በሉተር ሁኔታ በጣም ግራ ይጋባና ይቸገር ነበር፡፡ በአንድ ወቅት ሉተርን "በአንተ ላይ እግዚአብሔር የተቆጣ ሳይሆን ይልቁንስ በእግዚአብሔር ላይ እየተቆጣህ ያለኸው አንተ ነህ"[45] ብሎታል፡፡ አባቱ የሉተር አእምሮ የሚያብሰለስለው የእግዚአብሔርን ቸርነትና ፍቅር ወደ ጎን ትቶ ስለ ኃጢአትና ቅጣት ብቻ መሆኑ የሥነ ልቡና ችግር ያለበትና የታመመች ነፍስ ምልክት መሆኑን ይመለከት ነበር፡፡[46]

ሉተርም በየጊዜው ጭንቀቱ እየባሰበት ሄደ፡፡ ሌሊት ያቃዠው ነበር፣ በነፋስ ድምጽ ሳይቀር ይርበተበትና ይፈራ ነበር፡፡ አባቱ ስታውፒትዝ ሉተርን ከዚህ ችግሩ ለመርዳት ያደረገው ጥረት ሁሉ መፍትሔ አላስገኘም፡፡ ሉተርም ተስፋ ወደ መቁረጥ ሄደ፡፡ ስታውፒትዝ ለሉተር በየጊዜው

[38] Nicholas S. Davidson, Counter-Reformation, Joh Wiley & Sons, Inc., 1987
[39] July 2, 1505
[40] James L. Schaff, Martin Luther, Fortress Press, Philadelphia, 1985.
[41] Schwiebert E. G., Luther and His Times, Concorda Publishing House ST. Louis, 1950
[42] Denis Robelot, De l'influence de la réformation de Luther sur la croyance religieuse, la politique el les progrès des lumières, Rusand, Lyon, 1822
[43] (Dr. Staupitz)
[44] Roland Bainton, A Life of Martin Luther, Penguin, New York, 1995.
[45] At one point he told Luther that it was not God who was angry at him but Luther who was angry at God.
[46] Froom, Le Roy Edwin, The Prophetic Faith of our Fathers, Review and Herald Publishing Association, Washington D. C., 1948.

ጥሩ ምክር ይሰጠው ነበር፡፡ መንፈሳዊ ሕይወትን እያወሳሰበውና ከሚገባው በላይ እያከበደው ያለው ራሱ መሆኑንና ዋናው የሚያስፈልገው ነገር እግዚአብሔርን መውደድ (ፍቅረ እግዚአብሔር) መሆኑን ይነግረው ነበር፡፡ ለሉተር ገናና የሆነ እግዚአብሔር ኃጢአተኛና ደካማ የሆነን ሰው እንዴት ሊወደው እንደሚችል ማሰብ ወይም መረዳት አልቻለም ነበር፤ ከዚህም ጋር ደካማና ኃጢአተኛ የሆነው ሰው እግዚአብሔርን እንዴት ሊወድ እንደሚችል መረዳት አልቻለም ነበር፡፡ ለእርሱ የሚታየው የእግዚአብሔር ፈራጅነቱና ኃጢአተኛን ተጸያፊነቱ ነበር፡፡

በዚህ አስተሳሰቡና ተስፋ መቁረጡ ላይ እያለ የአውግስጢኖስን የቅድመ ምርጫ (ውሳኔ)[47] እና የጥንተ አብሶ[48] አስተምህሮ አነበበ፡፡ የአውግስጢኖስ የቅድመ ምርጫ አስተምህሮ በአጭሩ የሰው ልጅ ሁሉ በጥንተ አብሶ የተበከለ ስለሆነ ማንም ለዘለዓለማዊ ሕይወት የበቃ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ ሁሉም ሰው ከኃጢአተኛነቱ የተነሣ ቅጣት ይገባዋል፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር በማይመረመር ውሳኔው የተወሰኑትን ሰዎች ይድኑ ዘንድ ለሕይወት አስቀድሞ መርጧቸዋል፡፡ የዘለዓለም ሕይወትን የሚያገኙት እነዚያ እግዚአብሔር አስቀድሞ ለዚሁ የመረጣቸውና የወሰናቸው ብቻ ናቸው የሚል ነው፡፡ ሉተር ይህን ማንበቡ ደግሞ ምናልባት እኔም ለመዳን ካልተመረጡትና ከሚኮነኑት መካከል ብሆንስ የሚል ጭንቀትና ተስፋ መቁረጥ ፈጠረበት፡፡ የሚድኑት አስቀድመው የተመረጡት ብቻ ከሆኑ እኔ ሊድኑ ከተመረጡት ባልሆንስ? በሚል፤ ይልቁንም ለኩነኔ ከተወሰኑባቸው እንዳልሆን በሚል ጭንቀቱና ተስፋ መቁረጡ ተባባሰ፡፡ በዚህም በየጊዜው ከተስፋ መቁረጥ ወደ ባሰ ተስፋ መቁረጥ እየተሸጋገረ ሄደ፡፡

በእንዲያ ዓይነት ሁኔታ ላይ የነበረው ሉተር መጽሐፍ ቅዱስን እንደገና ማንበብና በራሱ መንገድ ለመረዳትና አዲስ አስተምህሮና አተረጓጎም ይዞ ብቅ ወደ ማለት የሄደው ከዚህ በኋላ ነበር፡፡ በጭንቀት፣ በቅዠትና በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሲናጥ የነበረው የሉተር አእምሮ ከዚያ ይገላግለኛል ያለውን "መዳን በእምነት ብቻ" የሚል አዲስና እንግዳ ትምህርት ይዞ ብቅ አለ፡፡[49] ይህም እኔ ምግባሬ ምንም ይሁን ምን በማመን ብቻ እድናለሁ የሚል ከጭንቀቱ የመገላገያ መንገድ ለራሱ ማዘጋጀቱ ነበር፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ያለው "በእምነት መዳን" የሚል እንጂ "መዳን በእምነት ብቻ ነው" የሚል አንዳችም ጥቅስ የለም፡፡ ሆኖም ሉተር ለራሱ አስተሳሰብ እንዲመቸው ለማድረግ ሲል "በእምነት መዳን" በሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ውስጥ "ብቻ" የሚል የራሱን የፈጠራ ቃል ጨመረበት፡፡[50] የዚህ ቃል መጨመር የሚያመጣው የሃሳብ ልዩነት እጅግ መሠረታዊ ነው፡፡

ሰው እንዴት እንደሚድን ሲናገርም ራሱ ሰው ምንም ነገር የማያደርግበት፣ በራሱ መዳን ውስጥ ድርሻና ሱታፌ የሌለውና እንደ ግኡዝ ነገር ከውጭ ብቻ የሚመጣበትና በላዩ ላይ የሚጫንበት (Passive) "መዳን" እንደሆነ አድርጎ ያስተምር ነበር፡፡ ይህም ነጻ ተደርጎ በተፈጠረው በሰው ልጅ ላይ እግዚአብሔር ያደረገው ማዳን ሳይሆን የሉተር ቅዠት የፈጠረው ነጻነት በሌላቸው በግኡዛዊ ፍጥረታት ላይ እንደሚፈጸም ዓይነት ድርጊት ነው፡፡ ይህን አዲስ የፈጠራ አተረጓጎሙንም ሲገልጽ "*There is a totally other face of the entire Scripture showed itself to me . . .* ቀድሞ ያልታየ ፈጽሞ አዲስ የሆነ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጽታ ለእኔ ታየኝ" ብሏል፡፡

በአጠቃላይ ሉተር ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቀደምት አባቶች ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ከሚታመነው ልዩና ተቃራኒ የሆነ ትምህርት "ፈጠረ"፡፡ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት በትክክል የተረዳሁት እኔ ብቻ ነኝ፤ ከእኔ በፊት የነበሩት ማንም በሚገባ ማን እንደ እኔ አልተረዱትም ይል ጀመር፡፡

[47] Predestination
[48] Original sin
[49] Markus Wriedt, 2003, Luther's Theology, the Cambridge Companion's to Luther, Cambridge University Press, New York.
[50] The Smalcald Articles, 2005, I Concordia: The Lutheran Confessions, Concordia Publishig House, St. Louis, Part Two, Article 1.

ከእርሱ አረዳድና አተረጓጎም በስተቀር ከቀደሙ አባቶች ማንንም ቢሆን እንዳይቀበሉ ተከታዮቹን በጥብቅ አሳሰበ፤ እንዲህ ሲል፡- "እነዚህን ቃላትና ሐረጎች [የቅዱስ ጳውሎስን] እንደዚህ ያለ ትርጉም ካልሰጠናቸው በስተቀር የጳውሎስን የሮሜ መልእክትም ሆነ ሌላውን መጽሐፍ ቅዱስ ፈጽማችሁ ልትረዱት አትችሉም፡፡ ስለዚህ እነዚህን ቃላትና ሐረጎች እኔ ከተረዳሁበትና ከተረጐምኩበት በተቃራኒ ከተረዱና ከተረጎሙ መምህራን ማንም ይሁኑ ማን፣ ጀሮምም ሆነ አውግስጢኖስ፣ አምብሮስም ሆነ አርጌንስ፣ ወይም ከእነርሱ የበለጠ የተከበረ የምትሉትም ቢሆን፣ ብቻ ሌላ ማንም በሉት ማን፣ ከእርሱ ተጠንቀቁ፡፡"[51]

ሆኖም ይህን አዲስ አረዳድና መገለጥ ያለውን አዲስ ትምህርቱን ወደያውኑ ይፋ አላደረገም፤ ምቹ የሆነ ፖለቲካዊና ማኅበረሰባዊ ጊዜውን ጠበቀ እንጂ፡፡ ትክክለኛ ጊዜው ነው ብሎ ሲያስብና ጉዳዩ ተራውን ሰው ሳይቀር ያካተተ እንቅስቃሴ ወደ መሆን በተሸጋገረ ጊዜ በይፋ 95ቱ መግለጫዎች (*Ninety-Five* Theses) በሚል በዊተንበርግ (Wittenberg) በይፋ ለጠፋቸው፡፡

የካቶሊክ መነኩሴ የነበረው ማርቲን ሉተር ምንኩስናውን ትቶ ገዳማዊ ሕይወታቸውን እንዲተው ካሳመናቸው አሥራ ሁለት (12) መነከሳዪያት መካከል አንዷ የነበረችውን ካታሪና የተባለችውን በ41 ዓመቱ አገባ፡፡[52] ማግባቱም የፕሮቴስታንቲዝም አራማጅ ከነበሩት ጓደኞቹ ሳይቀር አገራሞትንና ነቀፌታን አስከትሎበታል፡፡ የተሐድሶ እንቅስቃሴውን ከጀመረ በኋላ እንኳ ለአንድ ጓደኛው በጻፈው ደብዳቤ ላይ "መቼም ቢሆን ሚስት አላገባም፡፡ ይህን የምለው ግን የሥጋዊ ፈቃድ ስሜት ስለሌለኝ አይደለም (እንጨት ወይም ድንጋይ አይደለሁምና)፤ ሆኖም ግን አእምሮዬ ከጋብቻ የራቀ ነው፡ ምክንያቱም በየቀኑ አንድ ቀን የመናፍቅ ሞት ሊደርስብኝ እንደሚችል ስለምጠብቅ ነው" ብሎ ነበር፡፡ ካገባ በኋላ ሌሎችም የእርሱን አርአያ እንዲከተሉና ምንኩስናን እየጣሉ እንዲያገቡ ያስተምርና ምንኩስናን በመንቀፍ እንዲጠሉት የማድረግ ዘመቻውን በከፍተኛ ሁኔታ ያካሂድ ነበር፡፡

ሉተር "መዳን በእምነት ብቻ ነው" ከሚለውና ከግኡዛዊ የመዳን ትምህርቱ በተጨማሪ የቅዱስ ቁርባንን አማናዊ መሥዋዕትነት (መታሰቢያ ብቻ ነው በማለት) እና ለሙታን የሚደረግ ጸሎትን (መጀመሪያ ላይ በተወሰነ መጠን ያስፈልጋል ይል ነበር) ተቃወመ፡፡ እንዲሁም የገብቶ ወጦች (Apostates) ዋና መገለጫ እንደ መሆኑ ቀድሞ የነበረበትን የምንኩስናና የገዳማዊ ሕይወት በየጽሑፎቹ ሁሉና ባገኛቸው አጋጣሚዎች ሁሉ በጣም አድርጎ ይወቅስና ይዘልፍ ነበር፡፡ ከዚህም ጋር በክርስትና ያለውን ገዳማዊ ሕይወት ከአሪት ሕግና ሥራ ጋር አንድ እያደረገ ለማሳየት በዓቅሙ ሁሉ ታግሏል፡፡

ሉተር ስለ ቤተ ክርስቲያን ታሪክና ስለ ቀደምት አበው አስተምህሮ፣ እንዲሁም ከሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውጭ ስለ ነበረው ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮና ገዳማዊ ሕይወት የነበረው እውቀት በእጅጉ ደካማ ነበር፡፡ ከቀደምት አባቶች አብዝቶና ደጋግሞ ያነበበው አውግስጢኖስን ነበር፡፡ ትምህርታቸውን ያነበባቸው ቀደምት አባቶች በጣም ጥቂቶችና ከእነዚያም በጣም ውስን ድርሰቶቻቸውን ብቻ ቢሆንም ሉተር ስለ ቀደምት አባቶች ካነበበውና ካወቀው በላይ ብዙ ብሏል፡፡ ስለ ቅዱስ አግናጥዮስ፣ ስለ ቅዱስ ሂሬኔዎስ፣ ስለ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ወዘተ እንዳችም አያውቅም ነበር፡፡ ታላላቆቹን አባቶች ከእርሱ የተለየ አስተምህሮ ስለ ነበራቸውና እርሱን የሚደግፍ ነገር ስላልነበራቸው ብቻ ሲዘልፋቸው መጠን እንኳ አልነበረውም፡፡ ለአብነትም ጀሮምን "ስለ ጾም ብቻ የሚጽፍ"፣ "አፍቃሬ ምንኩስና" ወዘተ ይለዋል፡፡

[51](Beware, then, of all teachers who use these terms differently, no matter who they may, whether Jerome, Augustine, Ambrose, Origen, or their like; or even persons more eminent than they.)
[52] Philip Schaff, History of the Christian Church, Vol. VII, Ch. V, ccel.org.

ታላቁን ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊውን "ምንም የተለየ ነገር ያልነበረውና አንዳችም ነገር ያልጨመረ" ይለዋል፡፡ በቤተ ክርስቲያን በአጠቃላይ ለቅዱስ ባስልዮስ የነበረውን ከፍ ያለ አመለካከትና ክብርም ይቃወም ነበር፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙን (ነባቤ መለኮት) "ምንም ነገር ያልሆነ ባዶ"[53] ይለዋል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅን ለመንቀፍ ደግሞ አጋጣሚውን ባገኘ ቁጥር ሁሉ ወደ ኋላ አይልም ነበር፡፡ "እምነትን የተወና ስለ ተጋድሎና መልካም ሥራ ብቻ ማውራት የሚወድ" ይለው ነበር፡፡[54]

ከሉተርና መሰሎቹ የአውሮፓ የተሐድሶ አራማጆች አንድ መሠረታዊ እውነታ አለ፡፡ ይህም እነ ሉተር የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን መሠረታዊ ችግር አግኝተውት ነበር፤ ሆኖም መፍትሔውን ግን አላገኙትም፡፡ በዚህም በሽታውን በትክክል መርምሮ ካገኘው" በኋላ የተሳሳተ መድኃኒት እንደ ተሰጠው በሽተኛ ዓይነት ሆኑ፡፡ የአውሮፓ ተሐድሶዎች መፍትሔ ብለው የተጓዙበት አቅጣጫ ችግሩን የሚፈታ ሳይሆን የበለጠ የሚያባብስና ከድጡ ወደ ማጡ የሚያደርግ ነበር፡፡ ስለዚህም ከእሾህ ሸሽቶ ከጋሬጣ መውደቅ ሆነባቸው፡፡ በካቶሊክ ፓፓዎች ቁሣራዊ ጠባይ የተበላሸውን ተሐድሶዎች ሁሉንም ነገር በማቃለልና በማጣጣል ለጊዜው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥቃትና ለማሸነፍ ይረዳናል ያሉትን ነገር ሁሉ በመጠቀማቸው ያ አካሄዳቸው በክርስትና ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተጽእኖ እንኳ ለማሰብ አልቻሉም፡፡ በአጠቃላይ ነገረ ሃይማኖትን አቃላይና አዋራጅ የሆነው የተሐድሶዎች አካሄድም ዛሬ በብዙ ምዕራባውያን ሀገሮች ዘንድ "እምነት አልባ ኅብረተሰብ" እንዲፈጠር በማድረግ አሳዛኝ የሆነ ሚና ተጫውቷል፡፡ ማነጽ እንደ ማፍረስ፣ መሥራት እንደ መተቸትና መቃወም ቀላል አይደለምና!

በሉተር የተጀመረው የመገንጠልና የመቆራረጥ እንቅስቃሴ በየጊዜው በሚበቅሉ "የእብድ ገላጋዮች" እየጨመረ በመሄድ ለተቃውሞ አንድ ሆነው ቢጀምሩም ገና አንድ ትውልድ እንኳ ሳይጓዙ እርስ በርሳቸው የሚጣላሉና የሚከፋፈሉ አንጃዎችን ማፍራት ጀመሩ፡፡ እነ ካልቪን፣ ዝዊንግሊ፣ ሜላንክተን እና ሌሎችም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን በመቃወም አንድ ሆነው ቢነሡም በተለያዩ ነገረ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች እርስ በርሳቸው ባለመስማማታቸው በእነርሱው እድሜ እንኳ ቁጥራቸው ብዙ የሆኑ የተለያዩ የእምነት ቡድኖችን ወልደው፣ የልጅ ልጆችም አይተው ለመሞት "ታድለዋል"፡፡ በዚህ እነርሱ በቀደዱት ፈር በመከተል ፕሮቴስታንቲዝም ዛሬ በዓለም ላይ በየጊዜው ራሱን እየቆረጠ እንደሚባዛው እንደ አሜባ እየተቆራረጠ በመከፋፈልና በመብዛት በብዙ ሺዎች ከመቆጠር ደርሷል፡፡

---

[53] "nothing" — "Nazianzenus est nihil."
[54] Martin Luther, The Table Talk of Martin Luther, retrieved - December 10, 2014

# ክፍል አንድ

## የመዳን ትምህርት (ነገረ ድኅነት)

የመዳን ትምህርት (ነገረ ድኅነት) እግዚአብሔር ሰውን ከምን እንዳዳነውና እንዴት እንዳዳነው፣ "መዳን" ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ፣ እንዲሁም እያንዳንዱ ሰው ለመዳን ምን ማድረግ እንዳለበት የሚነገርበት ትምህርት ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ዋናውና መሠረታዊ ትምህርቷ የመዳን ትምህርት ነው፡፡ አንዱን እምነት ከሌላው የሚለየው መሠረታዊ ጉዳይም ስለ መዳን ያለው አስተምህሮ ነው፡፡

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ከሌሎች ቤተ እምነቶች የሚለያት በዋናነት የመዳን ትምህርቷ ነው፡፡ ከተሐድሶዎች ጋር ያለን ዋናውና መሠረታዊው ልዩነትም በመዳን ትምህርት ላይ ያለን ልዩነት ነው፡፡ ምናልባት ለአንዳንዶች ልዩነቱ በቅዱሳን አማላጅነት ወይም በአንዳንድ ሥርዓታዊና ቀኖናዊ ጉዳዮች ላይ እንጂ በመዳን ትምህርት ላይ ያንም ያህል ልዩነት የሌለን ሊመስላቸው ይችል ይሆናል፤ ይህ ግን ታላቅ ስሁተት ነው፤ ጠለቅ ብሎ ካለማወቅ የሚመጣ ነው፡፡ በርቀት ለሚያያቸውና ቀረብ ብሎ ውስጣቸውን ለማያውቃቸው ሰው አሞራና እውርፕላን ተመሳሳይ ሆነው ሊታዩት ይችሉ ይሆናል፤ መስለው መታየታቸው ግን አንድ አያደርጋቸውም፡፡ የሚመስል ነገር ሁሉ የሆነ አይደለምና፡፡ ስለሆነም በግምት ላይ ተመሥርቶ ከሚደረስ የተሳሳተ ድምዳሜ ለመጠበቅ በጥንቃቄ ማወቅና መረዳት የግድ ይላል፡፡

ስለዚህ በዚህ ክፍል መጀመሪያ የምንመለከተው ተሐድሶዎች ስለ መዳን የሚያስተምሩትን ትምህርት ነው፡፡ በመቀጠል ደግሞ በመጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ ቀጥሎም ቀደምት አባቶቻችን ሊቃውንት ስለ መዳን ያስተማሩትን ትምህርት እንመለከታለን፡፡ በዚህም የተሐድሶዎች ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስለ መሆን አለመሆኑ እንዲሁም ከአበው ቀደምት ትምህርት ጋር የሚስማማ ወይስ የሚቃረን መሆኑ ግልጽ ሆኖ ይታያል ማለት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2.1 ተሐድሶዎች ስለ መዳን የሚያስተምሩት ትምህርት

ስለ መዳን በይፋ ከጻፉትና ካስተማሩት መካከል በመጻሕፍቶቻቸውና በመጽሔቶቻቸው ከጻፏቸው ውስጥ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡ ለጊዜው ለአንዳንዶቹ አባባሎቻቸው ብቻ ወደ ዝርዝሩ ሳንገባ የስህተታቸውን አቅጣጫ በአጭሩ መልከት አድርገን እናልፋለን፡፡

- "እንግዲህ ሰውን ለማዳን <u>ኢየሱስ ክርስቶስን በተለዋጭነት ከመስጠት በስተቀር</u> ሌላ የማዳኛ መንገድ እግዚአብሔር አላገኘም፡፡ . . . በአንዳንድ ቦታ ይህን ወንጌል በማናናቅ የሰውን ነፍስ ለማዳን የሚከፈለው ከዓመን ዋጋ ያነሰ እንደ ሆነ በማስመሰል በእልህ እየተሰበከ ነው፡፡ ለአንድ ድሀ አሥር ሳንቲም መስጠት ዋጋ አለው፡፡ ይህን ማለት ግን የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት የጠየቀውን ሰውን የማዳን የዋጋ ተመንን እንኳን አሥር ሳንቲም ይቅርና ዓለምን ሁሉ መስጠት ቢቻል እንኳ ያሟላል ማለት እንዳይደለ ልንዘነጋ አይገባም፡፡" (ምሥራ ቁ. 7፣ ገጽ 18-19)

  - ይህ "ኢየሱስ ክርስቶስን በተለዋጭነት ከመስጠት በስተቀር" የሚለው አባባል የማስመሰል ሰም የተቀባና ንጹሕ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ትምህርት ነው፤ ይልቁንም በአንዳንድ የስኮላስቲሲዝም አቀንቃኞች የተቀመረው የቅጣት ምትክነት ንድፈ ሃሳብ (Penal Substitution Theory) ነጸብራቅ ነው፡፡ በእነ አንሰለም (Anselem) የተቀመረው ይህ <u>የቅጣት ምትክነት ንድፈ ሃሳብ (Penal Substitution Theory)</u> አስተሳሰብ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ትውፊታዊ መሠረት ላይ ከመመሥረት ይልቅ በፍልስፍናና በሎጂክ ላይ የተመሠረተ ስለነበር በኋላ ላይ ለተነሡት ለአውሮፓ ተሐድሶዎች መነሻ ጥሎላቸው አልፏል፡፡ እነ ሉተርና ካልቪንም በዚሁ መንገድ ቀጥለዋል፡፡

  - በዘመኑ ተሐድሶ ይህ የአንሰለም የወንጀለኛ ምትክ ቲዎሪ በዘመናቸው ከነበረው ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንጻር ተቃኝቶ ተሻሽሎ ቀረበ፡፡ ይህም በአጭሩ ሲጠቀለል ክርስቶስ በእግዚአብሔር ፊት ወንጀለኞችን ሁሉ ወክሎ ቀርቧል፤ ስለዚህም ሁሉም ኃጢአተኞች የኃጢአታቸው ቅጣት በሙሉ ተወካያቸው በሆነው በክርስቶስ ላይ ስላረፈ ከዚያ በኋላ የወንጀል ተጠያቂነትና የሕግ ፍርድ ጥያቄ ሊያቀርብባቸው የሚችለው ቀረኝ የለም የሚል ነው፡፡ ይህም ክርስቶስ ስለ እኛ መከራ ተቀበለ ከሚለው አልፎ ክርስቶስ ስለ እኛ ተላልፎ ተሰጥቶ በእኛ ቦታ ቅጣትን (መከራን) ተቀበለ የሚል ነው፡፡

  - የክርስቶስ ሞቱና መከራው ለቤዛነት መሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ነው፤ ሆኖም ይህን ለጥጦ ወደ ምትክና የወንጀለኞች ቅጣት ተወካይ ወይም ምትክ ንድፈ ሃሳብ መለጠጥና ማበላሸት ግን በኋላ ላይ በእነ አንሰለም እና ኋላም በእነ ካልቪን የተፈጠረ ሰው ሰራሽ ሃሳብ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ ክርስቶስ ስለ ሰው ሁሉ ተገብቶ በኃጢአት ሁሉ የተቀጣ ስለሆነ ሰው በሚሠራው በማንኛውም ኃጢአቱ አይጠየቅም፣ ምክንያቱም ክርስቶስ ቅጣቱን አስቀድሞ ከፍሎለታልና የሚል ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ በየጽሑፎቻቸው ተደጋግሞ ሲንጸባረቅ የምናገኘው ነው፡፡ ይህም ፕሮቴስታንታዊነታቸውን የሚገልጽ ነው፡፡ በአጠቃላይ ይህ አስተምህሮ ብዙ ችግሮች ያሉበት ነው፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ይህን ያህል ካመላከትን ይህን በዚሁ ይዘን ወደሚቀጥለው እንሂድ፡፡

- "ወንድሜና እኅቴ! እንደ እኔ ኃጢአተኞች መሆናችሁን የምታምኑ ከሆነ የኃጢአታችንን ዕዳ እንዴት እንደ ተከፈለ ትረዱ ዘንድ ወደዚያች ዕለተ ዓርብ መለስ በሉና ከጌቴሴማኒ እስከ ቀራንዮ በመንፈስ በመጓዝ የሆነውን ሁሉ በመንፈስ ቃኙት፡፡" (ምሥራ ቁ. 7፣ ገጽ 19)

- ይህ አባባል ጌታችን ድኅነትን የሰጠን ከብሥራቱና ከፅንሰቱ አንሥቶ እስከ ዕርገቱ ድረስ ባደረጋቸው የማዳን ሥራዎች በሙሉ መሆኑን ያልተረዳና ዕለተ ዓርብ ላይ ብቻ የተንጠለጠለ ጠባብ እይታ ነው፡፡ ይህም የፕሮቴስታንቶችና የተሐድሶዎች የጌታችንን ማዳን በተመለከተ ያላቸው ጠባብና የተሳሳተ አረዳድ መገለጫ ነው፣ ከመሠረቱ ሳይሆን ሁሉንም ነገር ከጫፍ ከጫፉ መቅጨት ጠባያቸው ስለሆነ ነው፡፡ የጌታችን ስቅለቱና ሞቱ ብቻ ሳይሆን ከፅንሰቱ ጀምሮ ያደረጋቸው ሥራዎች እያንዳንዳቸው በመዳናችን ሂደት ውስጥ አስፈላጊዎች ነበሩ፡፡ ጌታችን በብሥራተ መልአክ በማኅፀነ ድንግል ማርያም በድንግልና ተጸንሶ በድንግልና ከመወለዱ ጀምሮ ያደረጋቸው ነገሮች ሁሉ ያለ ምክንያት የተደረጉ አልነበሩም፡፡ ስለዚህ "ወደዚያች ዕለተ ዓርብ መለሰ በሉና ከጌቴሴማኒ እስከ ቀራንዮ በመንፈስ በመንዝ" የሚለው አባባል ሌላውን ሁሉ የሚያስረሳና መዳንን በምልዐት እንዳንረዳ የሚያደርግ ቁንጽል አስተሳሰብ ነው፡፡

◉ "ጠበቃችን ተከራካሪና ተሟጋች ወይም አማላጅ ብቻም አይደለም፣ የኃጢአታችን ማስተስረያ ነው እንጂ፡፡ በእርሱ በኩል ለሚቀርብ ተናዛዥ ይህማ እኔ የተወጋሁለት የደማሁለት የቆሰልሁለት በመስቀል ኅዳና ሞትን የተቀበልሁለት መሆኑን ያመነ ኃጢአተኛ ነው፡፡ ሥርየት በተሰጠበት ማስተስረያ ሊጠየቅ አይገባውም በማለት የኃጢአት ማስተስረያ የሆነበትን ማስረጃ በማሳየት ይለፍ ያሰኛል ማለት ነው፡፡" (ፋሬ ቁ. 8 ገጽ 30)

  - ይህም ከላይ የተገለጸው የቅጣት ምትክነት ንድፈ ሃሳብ (Penal Substitution Theory) አስተሳሰብ ውጤት ነው፡፡

◉ "አንድ ቀን ወደ አንድ ትልቅ አባት መኖሪያ ቤት ለጉብኝት ስንገባ ጸሎት ያደርሱ ነበር፡፡ ጸሎታቸውን እንደ ጨረሱ ባንድ የሰው ሥዕል ፊት ደጋግመው ሰገዱ፡፡ እኛም የሚያደርጉትን ሁሉ በጥሞና ስንከታተል ቆየን፡፡ በተከፈተው ውይይት እግዚአብሔር ለሚድኑ ሰዎች ሁሉ የመዳኛ መንገድን ማዘጋጀቱን አነሣን፡፡ በሰማይና በምድር ካሉ ግኡዛንና ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ ለሰው ተለዋጭ (ቤዛ) የሚሆንለት ሊገኝ እንዳልቻለ፣ እግዚአብሔር ግን አንድያ ልጁን ቤዛ እንደ ሰጠለት በሚናገረው በእግዚአብሔር ቃል ተስማማን፡፡ <u>በእግዚአብሔር ቸርነት የተሰጣቸውን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት ሳይቀበሉ በምንም በምንም ለመዳን ያሳለፉትን ጊዜ ርዝመት ሲያስሉት አዘኑ</u>፡፡ <u>በመጨረሻም እጃቸውን ለጌታ ሰጡ</u>፡፡" ፋሬ ቁ. 13 ገጽ 2

◉ " . . . ከሥላሴ የአንዱን አካል ቤዛ መሆንን የጠየቀው የሰው ድኅነት ክፍልና ምዕራፍ ተሰጥቶት በዋናነት አይጻፍም፣ አይነገርም፡፡ ለምሳሌ በ318ቱ አባቶች በኒቅያ የተዘጋጀውን የእምነት መግለጫ እንደ ማስረጃ ብናቀርበው፣ ጽሑፉ ከእግዚአብሔር ቃል በተወሰዱ በብዙ እውነቶች የተገነባ ውብና ክቡር በሆኑ ቃላት የተሞላ ጥራት ያለው የእምነት መግለጫችን ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ ክቡርና ቅዱስ ሕይወት መሥዋዕት የሆነበትን የሰው ድኅነን በሚመለከት የሰፈረው ገለጻ ግን አንድ ሙሉ ዐረፍተ ነገር የማይወጣው ነው፡፡ ግማሽ ገጽ ያህል በተሰጠው አንቀጸ ሥጋዌ እንደ ታሪክ ከቀረቡት ገለጻዎች መካከል ብርቅዬ የትምህርተ ድኅነ ቃላት ውሱን ናቸው፡፡ . . . ብዙ የሃይማኖት ድርጅቶች በምልአት መሰበክ ለሚገባው ለዚህ የደኅንነት ወንጌል በቂ የመጻሕፍት ገጾችንና ክፍለ ጊዜን ባለመመደባቸው በስመ ክርስትና የተመዘገቡ አባሎቻቸው ስለ መዳናቸው እርግጠኛ ሳይሆኑ እንደ ተንከራተቱና እንደ ተጨነቁ ያለ እርካታና ያለ ዕረፍት ዕድሜያቸውን እንዲገፉ ይገደዳሉ፡፡ "ድነሃልን?" ተብለው ሲጠየቁም "እንዴት ብዬ" ከመሞቴ በፊት መዳኔን በምን ላረጋግጥ እችላለሁ? ብለው ጥያቄውን በጥያቄ ይመልሳሉ፡፡" (ፋሬ ቁ. 10 ገጽ 4-5)

- ይህ እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ያደረገውን እና ሰው ለመዳን ማድረግ ያለበትን ነገር አምታትቶና አደባልቆ ማቅረብ ነው፡፡ እንዲሁም መዳንን ቅጽበታዊ በሆነ መንገድ የመረዳት ስሁተት ነው፡፡ በተጨማሪም ከላይ እንዳየነው እነርሱ የማይቀበሉትንና "የሐዋርያትን ውሳኔ የሚቃረን እሳቤ ውሳኔ ወሰኑ" ያሏቸውን ሠለስቱ ምእትን መንቀፋቸው ነው፡፡ አንድ ነገር እንደ እነርሱ ለባውን እስኪያጣ ድረስ መልሶ መላልሶ ካልተጻፈ ብለው ነው እንጂ ትምህርቱስ በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ ጥንቅቅ ባለ አገላለጽ አለ፡፡ በዚያውም ላይ በጉባኤው አንቀጽ አባቶቻችን ያካተቷቸው መናፍቃን ክርክር ያነሱባቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ነው እንጂ ሁሉንም የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በተመለከተ አልነበረም፡፡

◉ "እነዚህ ሰዎች (ኦርቶዶክሳውያን) ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝህና ጌታህ መሆኑን እመን ተቀበል ቢባሉ ግን ከቅድም አያቶቻቸው ቅድም አያት ጀምሮ በመቁጠር ኢየሱስ ክርስቶስን በቅብብሎሽ (በትውፊት) የሚያምኑበት መሆናቸውን በአጽንዖት ይናገራሉ፡፡ ዳሩ ግን ኢየሱስን ቢያምኑበት ኖሮ መዳናቸውን ባረጋገጡ ነበር፡፡ . . . የሚያምኑበት ኢየሱስ ሌላ ነው፤ የማያድን ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አልተቀበሉትም፡፡" (ሙራ ቁጥር 10፤ ገጽ 5)

- ኢየሱስ ክርስቶስን እነርሱ በሚሉት የተሳሳተ መንገድ የማይቀበለውንና የእነርሱ የኑፋቄያቸው ማኅበረተኛ ያልሆነውን ሁሉ እንዲህ ማለታቸው የተለመደ ስልት ነው፡፡ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግን በሁለንተና አምልኮዋና ተግባሯ የምታመልከው ኢየሱስ ክርስቶስን ነው፡፡ ማኅሌቱ ሲጀምር *"ስምዓኒ እግዚኦ ጸሎትየ ሃሌ ሉያ ወይብጻሕ ቅድሜከ ገዐርየ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ወኢትሚጥ ገጸከ እምኔየ በዕለተ ምዳቤየ አጽምእ ዕዝነከ ኀቤየ . . . ሃሌ ሉያ ዘውእቱ ብሂል ንወድሶ ለዘሀሎ እግዚአብሔር ልዑል ሰቡሕ ወውዱስ ዘሣረረ ኩሎ ዓለመ በአሓቲ ቃል - አቤቱ ጸሎቴን ስማኝ፣ ጩኸቴም ወደ አንተ ይድረስ። በመከራዬ ቀን ፊትህን ከኔ አትመልስ፣ ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፤ በጠራሁህ ቀን ፈጥነህ ስማኝ፡፡ . . . ያለና የሚኖር ልዑል እግዚአብሔርን እናመስግነው፣ ዓለምን ሁሉ በአንዲት ቃል ያጸና እርሱ ምስጉንና ገናና ነው*[55] ብሎ ነው፡፡ መዝ. 101፥1-2

- ሰዓታቱም ሲጀምር እንዲህ እያለ ነው፡- "ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ አስተብ ወእትነሣእ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሠለስተ አስማት እትመረጐዝ እመኒ ወደቁ እትነሣእ ወእኒ ሖርኩ ውስተ ጽልመት እግዚአብሔር ያበርህ ሊተ በእግዚአብሔር ተወከልኩ (ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ፣ ሃሌ ሃሌ ሉያ፣ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አማትባለሁ፣ እነሣለሁም፤ በሦስቱ ስም እመረኮዛለሁ፣ ብወድቅም በሦስቱ ስም እነሣለሁ፣ በጨለማ መካከል እንኳ ብሄድ እግዚአብሔር ያበራልኛል፤ በእግዚአብሔር ታምኜያለሁና፡፡ መዝ. 22፥4፤ 10፥1) . . . ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ዘገብረ ዐቢየ ወመንክረ ባሕቲቱ ወይትባረክ ስመ ስብሐቲሁ ቅዱስ ወይምላዕ ስብሐቲሁ ኩሎ ምድረ ለይኩን ለይኩን (ብቻውን ተአምራትን የሚያደርግ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ። የምስጋናው ስም ለዓለምና ለዘላለም ይባረክ፤ ምስጋናውም ምድርን ሁሉ ይምላ፤ ይሁን ይሁን። መዝ. 71፥18-19) ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ (ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣ የቅድስናው ክብርና ምስጋና ሰማያትንና ምድርን ሁሉ ሞልቷል። ኢሳ. 6፥3)፡፡ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘእምቅድመ ዓለም ሀሎ ወይሄሉ እስከ ለዓለም (ከዓለም በፊት ያለና እስከ ዘለዓለም የሚኖር ቅዱስ እግዚአብሔር፡፡ ኢሳ. 43፥10፤ 44፥6)"[56] እያለ ነው፡፡

- የማኅሌቱና የሰዓታቱ፣ የስብሐተ ነግሁና የአደራረሱ፣ የኪርያሙና የአርባእት መወድሱ አገልግሎት ሁሉ ማሳረጊያ የሆነው ጸሎተ ቅዳሴም ሲጀምር "አሐዱ አብ ቅዱስ፣ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፣ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" ብሎ ነው፡፡ ጸሎተ ቅዳሴው ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ጌታችን በቤተ ልሔም ተወልዶ እስከ ቀራንዮና እስከ ጎልጎታ ድረስ የፈጸመውን የማዳን ሥራ በተግባር የሚያሳይ ነው፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ስሙን ስትጠራም "ጌታችን፣ አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ መድኃኔ ዓለም፣ ወልደ እግዚአብሔር፣ ሥግው ቃል፣ አማኑኤል" እያለች በታላቅ አክብሮትና በልዩ ፍቅርና ስስት ነው፡፡ "ኢየሱስ" የሚለው ስም ልዩና የከበረ በመሆኑም ምሥዋዕ የሆነውን ጽላቱን የሚያከብረው ይህ ገናና ስም መሆኑን በትምህርቷ፣ በማኅሌቷ፣ በቅዳሴዋ፣ በሁለንተናዋ ትገልጻለች፤ በተግባርም ትኖረዋለች እንጂ ተሐድሶዎቹ እንደሚሉት ኢየሱስ ክርስቶስን ያልተቀበለች አይደለችም፡፡ መልክአ ኢየሱስም ሲጀምር "ሰላም ለዝክረ ስምከ ስመ መሐላ ዘኢይደኀሱ፤ ዘእንበረ ቅድመ እግዚአብሔር በአትሮንሱ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዳዊት ባሕርየ ክርሡ፤ እክሊለ ስምከ እንዘ ይትቄጸል ዘርእሱ፣ አሕጉረ ጽር ወረሰ ኢየሱ" ብሎ ነው፡፡ ይህን ክቡርና ቅዱስ ስሙንም እንዲህ እያለች በአክብሮትና ከፍቅር በሆነ ፍርሃት በጸሎትና በማኅሌት ታመሰግነዋለች፡፡

---

[55] መዝሙረ ዳዊት ምስለ ነግሥ ዘማኅሌት
[56] መጽሐፈ ሰዓታት

- እንዲሁም "ኢየሱስ ክርስቶስን በቅብብሎሽ (በትውፊት) የሚያምኑበት መሆናቸውን በአጽንዖት ይናገራሉ" ብለው ይህን እንደ ነውርና ስህተት አድርገው ማቅረባቸው ድሮውንስ ቢሆን ሐዋርያት የሰበኩትን አባቶቻችን ያመኑበትን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጂ በየዘመኑ "አዲስ ኢየሱስ" ሊመጣ ኖሯልን? መጽሐፍ ቅዱስ "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘለዓለም ያው ነው" ይላል እንጂ በየጊዜው ሌላ ኢየሱስ ይመጣል አላለንም፡፡ ዕብ. 13፥8 መጽሐፍ ቅዱስም እግዚአብሔርን "ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነ - የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ" በማለት እግዚአብሔርን የአባቶቻችን አምላክ ብሎ መጥራት የተገባ መሆኑን ያስተምረናል እንጂ ይህን ስህተት ነው አይለንም፡፡ ዕዝ. 7፥27-28 በየጊዜው እንደ ፋሽን "አዲስ ጌታ ይመጣልና ተቀበሉ" አልተባለም፤ ይልቁንም ወደ ኋላ ዘመን ሐሳዊ መሢሕን (ሐሰተኛ ክርስቶስን) የሚሰብኩ ሐሰተኞች እንደሚነሡ በመናገር እንድናውቅባቸውና እንዳንቀበላቸው ያስጠነቅቀናል እንጂ፡፡ ለስም አጠራሩ ክብርና ምስጋና ይግባውና ባለቤቱ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማይታበል ቃሉ "በዚያን ጊዜ ማንም እነሆ፥ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፤ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ። እነሆ፥ አስቀድሜ ነገርኋችሁ። እንግዲህ እነሆ፥ በበረሀ ነው ቢሏችሁ አትውጡ፤ እነሆ በእልፍኝ ነው ቢሏችሁ አትመኑ" በማለት አስቀድሞ አስጠንቅቆናል፡፡ ማቴ. 24፥23-26 ከዚህም ጋር "የሚያምኑበት ኢየሱስ ሌላ ነው" በማለታቸው የእነርሱ "ጌታ" ከእኛ ጌታ የተለየ መሆኑን እነርሰው ራሳቸው መስክረዋል፡፡

◉ "ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የተሰቀለውና የተቀበለው ሥቃይና የሞተው ሞት የእኔን ኃጢአት ዕዳ ለመክፈል ስለሆነ እኔም ይህንኑ እምኜ በመቀበሌ ዛሬ ባመንኩበት ቅጽበት ድኛለሁ፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ እኔ በኃጢአቴ አልጠየቅም፡፡" (ሥራ ቁ. 10፥ ገጽ 5)

  - ከላይ የተገለጸው የቅጣት ምትክነት ንድፈ ሃሳብ (Penal Substitution Theory) አስተሳሰብ ውጤት ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትም እንዲሁ የዚሁ አስተሳሰብ መገለጫዎች ናቸው፡፡ ይህ ሃሳብ "በቅጽበት መዳን" "ከመንኩ በኋላ በኃጢአቴ አልጠየቅም" እና የመሳሰሉትን መሠረታዊ ስሁተቶች የያዘ ሲሆን ይህም ወደፊት በቦታው ላይ በሰፊት የምናየው ጉዳይ ይሆናል፡፡

◉ "ጽድቅ፥ መጽደቅ፡- ዕዳው የተከፈለለትና በዕዳ ከመጠየቅ የዳነ ለመሆኑ ማስረጃ ያቀረበውን ባለ ዕዳ የነበረ ተከሳሽ ጉዳይ ዳኛው መርምሮ ብይን በመስጠት ነጻ መሆኑን ያውጅለታል፥ ያጸድቀዋል፡፡ ዳኛው በባለ ዕዳው ስም የተመዘገበው ዕዳ ለመከፈሉ የሚቀርበውን ማስረጃ መርምሮ ይቀበለዋል እንጂ አንተ ስላልከፈልከው፥ ሌላ ሰው (ዘመድ) ስላንተ ሆኖ የከፈለልህ በመሆኑ ማስረጃውን አልቀበልም አይልም፡፡ እንደዚሁም በኃጢአት ምክንያት በሕግ ተከሶ ከፍርድ በታች የነበረው ሰው በኃጢአት ዕዳ ከመጠየቅ የዳነ ወይም ነጻ የወጣ ለመሆኑ የሚያቀርበውን ስለ እርሱ የተከፈለውን የኢየሱስ ክርስቶስን የቤዛነት መሥዋዕት የእምነት ማስረጃ ብቁነት በማረጋገጥ "ከተከሰስክበት የኃጢአት ዕዳ ነጻ ነህ፥ አያስጠይቅህም" የሚለው ከመንፈስ ቅዱስና ከእግዚአብሔር ቃል ለአማኙ ሕሊና የሚሰጥ የብይን ማረጋገጫ ነው፡፡ ከኃጢአት ዕዳ ተጠያቂነት መዳኑ ሕጋዊነት ያለው ለመሆን ከመለኮታዊ ዙፋኑ የሚወጣ በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም የተረጋገጠ የዳኝነት ውሳኔ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ኃጢአተኛው ከተበየነለት (ከጸደቀ) በኋላ ረታ ይባላል፡፡ ተከሳሽ ግን በዚህ ውሳኔ ተረታ ተፈረደበት ማለት ነው፡፡" (ሥራ ቁ. 11፥ ገጽ 15)

◉ "... ወደ ፍርድ ቀርቤ ይፈረድብኛል የሚል ፍርሃት የለብህም፡፡" (ጠማሪ ጽድቅ ገጽ 21)

◉ "አማኞች ሆነን ኃጢአት ብንሠራ የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን የተሰጠንን መብት ይቀይረዋል ወይ?... ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ያገኘነው ቤዛነት እስከ ዘላለም በማረጋገጫ የታተመ ነው፡፡" (ጠማሪ ጽድቅ፥ ገጽ 60)

◉ "...በእምነት ከጸደቅን በኋላ ኃጢአት ፈጽመን ብንገኝ እንኳ ከጽድቅ ተለይተን አንቆነንም፥ ስለ ኃጢአታችን በተለያዩ ቅጣቶች እንቀጣለን እንጂ፡፡" (የተቀበረ መክሊት፥ ገጽ 189)

> ➢ እነዚህ ሁሉ የቅጣት ምትክነት ንድፈ ሃሳብ (Penal Substitution Theory) አስተሳሰብ ውጤቶች ናቸው፡፡ መብት የሚለውም የሕግ ነክ አይታቸው ነጸብራቅና ውጤት ነው፡፡ ይህንም እዚህ ላይ መነካካት እንዳይሆንብን ወደፊት በቦታው ላይ በሚገባ እናየዋለን፡፡

◉ "የወይን ግንድ ቅርንጫፍ ፍሬን የሚያፈራው ከመጨነቅ፣ ከመሞከር የተነሣ እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ ከግንዱ ከሚገኘው መግቦት የተነሣ ለቅርንጫፉ የዕድገቱ የጥንካሬውና ፍሬን የማፍራቱ እንቅስቃሴ ሁሉ ያለ መጨነቅ የሚሠራ ባሕርያዊ ክንውን ይሆናል፡፡ . . . ሌሎች ክፍሎች ደግሞ አባሎቻቸው የወይን ፍሬን ማፍራት ይችሉ ዘንድ ጥብቅ የቅድስና ድንጋጌዎችን በሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ እንደ ሆነ ያስተምራሉ፡፡ ድንጋጌዎቻቸው በከባድ ቅጣት የታጀቡ ስለሆነ ሕግ ተላላፊዎችን በመቅጣት "የወይን ፍሬን" እንዲያፈሩ ለማስደረግ እንደሚቻል የሚያምኑ ይመስላሉ፡፡" (ሙራ ቁ. 11፣ ገጽ 17)

◉ "እርሱን ለማስደሰት የምታደርጉትን ሁሉ ሊቀበል የሚችልበትን መንገድ ባለማወቃችሁ አልተቀበለውም እንጂ ክፍቅሩ የተነሣ የምታደርጉት ሁሉ ከሰው ዐቅም በላይ ነው፡፡ ስለዚህም ያደረጋችሁትን ሁሉ ያልተቀበለበትንና እንዲያውም የተጸየፈበትን ምክንያት ልታውቁት ይገባል፡፡ እርሱን ያስደስትልናል ብላችሁ ብዙ ነገር የሠራችሁበት ባሕርይ ከእግዚአብሔር ጋር የተጣላ አዳማዊ ባሕርይ ነው፣ ኃጢአተኛ ባሕርይ ነው፣ የረከሰ ባሕርይ ነው፡፡ ከዚህ የተነሣ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ሕግን በመሥራት በእግዚአብሔር ፊት አይጸድቅም ተባለ፡፡ እናንተ በሕግ የታዘዘውን ሁሉ በማድረግ ፈጽመናል፤ እንዲያውም በሕግ ከታዘዘው በላይ በመሥራት "ትሩፋትን" አበርክተናልና እንጸድቃለን ብላችሁ ስትጣባበቁ፣ ሕግን በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት አይጸድቅም በማለት የእግዚአብሔር ቃል መንገዱን ዘግቶባችኋል፡፡ ምክንያቱ ግልጽ ነው፡፡ ሥጋ የለበሱ ሁላቸው በኃጢአት ከተበከለው ከአዳምና ከሔዋን ከሥጋቸውና ከባሕርያቸው ተከፍለው የተወለዱ በመሆናቸው ነው፡፡ መዝ. 51፡5 ሕግን ጠብቅን ትሩፋትንም ሠራን የሚሉበት ጠቅላላው አቋማቸው ረክሷል ማለት ነው፡፡ አሁንም ኢሳይያስ ከእግር ጫማ አንሥቶ እስከ ራስ ድረስ ጤና የለውም፣ ጎስቁሏልና ይለዋል፡፡ ኢሳ. 1፡5-6 በኢዮብ መጽሐፍም "ከርኩስ ነገር ንጹሕን ሊያወጣ ማን ይችላል?" ሲል ከጠየቀ በኋላ "አንድ እንኳ የሚችል የለም" በማለት ራሱ መልስ ይሰጣል፡፡ ኢዮ. 14፡4 ከሔዋን የተወለደውን ሰው እግዚአብሔር እንዲሁ በጸጋው ካላጸደቀው በስተቀር በጥረቱ ራሱን ጻድቅ ሊያደርግና እግዚአብሔርን በጽድቁ ሊያስደስተው እንደማይችል የታወቀ ሆኗል፡፡ እስኪ በግብረ ሐዋርያት ምዕራፍ 10 እና 11 የቆርኔሌዎስን ታሪክ እናንብብና መልእክቱን እናስተውለው፡፡ ቆርኔሌዎስ በጎ ሰው ነበር፡፡ በራሱ ጥረት ጽድቅን ያደርግ ነበር፡፡ . . . ይህ ሁሉ መልካም ጥረት ቢሆንም ቆርኔሌዎስና ቤተሰዎቹን አላዳናቸውም፡፡ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን የመዳኛ መንገድ የሚጠቁማቸው ሰው ያስፈልጋቸው ነበር፡፡ . . ." (ሙራ ቁ. 10 ገጽ 7-8)

እነዚህ ትምርቶቻቸው በብዙ ስህተቶች የተሞሉ ናቸው፡፡ ይህንም በቦታው ላይ በሚገባ እናየዋለን፡፡

◉ "የጸደቀ ተክል ለመጽደቁ ማረጋገጫ የሚሆነውን የእምነቱን ፍሬ ፈጥኖም ሆነ ዘግይቶ ማፍራቱ በአብዛኛው በይሆዋ እንደ ተወሰነ እንደ ተፈጥሮ ሥርዓት ሕጋዊነት ሊወሰድ ይችላል፡፡" (ሙራ ቁ. 6 ገጽ 8)

> ➢ መልካም ምግባር ያለ ምንም ድካምና የሰው ጥረት በራሱ ጊዜ በግድ ይመጣል ለማለት ነው፡፡ ይህም ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ተጋድሎና ምግባር ትሩፋት አያስፈልጋቸውም የሚል የስህተት ትምህርት ነው፡፡

◉ "ጳውሎስም ጸጋና ሕግ እርስ በርስ ተቃራኒ እንደሆኑ ገልጿል፡፡ . . . ያዕቆብስ ቢሆን "ሥራ፣ (ምግባር) እያለ የጠራው ምግባረ አሪትን ነው ቢባል መልሱ አይደለም ነው፡፡ <u>ፍቅር</u>፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ በሐዲስ ላይ የበቀለው የሕያው እምነት ፍሬዎች ናቸው እንጂ ከዐሠርቱ ትእዛዛት መካከል አይደሉም፡፡ . . . በሥራዬ እጸድቃለሁ ባዩን የእፍ ክርስቲያን ሕይወት የመንፈስ ፍሬ ምክንት ያጠቃዋል፡፡" (ሙራ ቁ. 8፣ ገጽ 20)

- ዐሠርቱ ትእዛዛትን የሠራቸውና ለእኛ የሕይወት መመሪያ ይሆኑን ዘንድ የሰጠን እኮ እግዚአብሔር እንጂ ሰይጣን አይደለም፡፡ ኋላም በሐዲስ ኪዳን እነዚያኑ ትእዛዛት "እንሰ አስከሙ - እኔ ግን እላችኋለሁ" እያለ ያጸናቸው ራሱ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ተሐድሶዎች ለአሪትና ለዐሠርቱ ትእዛዛት ያላቸው ከባድ ጥላቻ የእነ መርቅያንና የእነ ማኒ እርሾ ነው፡፡ የጌታችን ሕግጋትና ትእዛዛት ፍቅር እንጂ ሸክም ወይም ቀንበር አይደሉም፡ ፡ ቅዱስ መጽሐፍ "ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና" በማለት ትእዛዛተ እግዚአብሔርና ፍቅረ እግዚአብሔር የሚቃረኑ ሳይሆን የሚዋሐዱ መሆናቸውን ይነግረናል፡፡ 1ዮሐ.5፥3 አስቀድሞ ትእዛዛቱን የሰጠውም፣ ኋላ ሰው ሆኖ ያጸናቸውም ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ይህ ትእዛዛተ እግዚአብሔርን አክፋፍቶና ጥላሸት ቀብቶ በተለይም ነገረ አሪትን አስጸይፎ ማሳየት የማኒስቲኮችና የመነናውያን እርሾ ነው፡፡

◉ "እንደዚህ ያለ ጥልቅና አስደናቂ ምስጢርን ይዞ በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ላይ የተመሠረተው መሠረተ እምነታችን በተረት መጻሕፍት በመቀበሩ ድኅነት በፍጡራን ይገኛል የሚለው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ እንደ እንጉዳይ በቅሎ ይታያል፡፡" (ሥራ ቁ. 19፣ ገጽ 1)

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመዳን ትምህርት "ድኅነት በፍጡራን ይገኛል" አይልም፤ ይህን እንደምትል አስመስለው የሚያቀርቡት ያው እንደ ልማዳቸው የሐሰት ክስ ነው፡፡ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመዳን ትምህርት ምንጯም መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን፣ በዚህም ላይ አስተምህሮዋ በሐዋርያትና ከእነርሱ በወረሱ በአበው ሊቃውንት ትምህርት ላይ የተመሠረተ እንጂ ተሐድሶዎች እንደሚሉት በተረት መጻሕፍት ላይ የተመሠረተ አለመሆኑን ማሳየት የዚህ መጽሐፍ ዋና ዓላማ ስለሆነ በጉዳዮቹ ላይ በስፋትና በጥልቀት በቦታው እናየዋለን፡፡

◉ "ወንጌላዊው መዳንን የሚፈልግ ሰው ወደ ቅድስት ሀገር ይሒድና የታሪክ ቦታዎችን ይጎብኝ ወይም ወርቅና ብር ይክፈልና ይግዛ፣ ወይም ሰባት ዓመት በራሱ ይቁምና ይጸልይ፣ ወይም በአንዱ በረሓ ውስጥ ገብቶ በረሃብና በጥም ራሱን ይግደል አላለም፡፡ እንደዚህማ ባለ መንገድ የሰው ነፍስ ልትድን ብትችል ኖሮ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ተለዋጭ ሆኖ ይሞት ዘንድ ባላስፈለገን ነበር፡፡ አሁንም የሰው ድርሻ ሆኖ የቀረበው በተፈጸመው የእግዚአብሔር ሥራ ማመን ብቻ ነበረ፡፡ ቃሉን የሚሰማ ሰው ራስን ለማዳን ከእንግዲህ ወዲያ የሚሠራው ግዳጅ እንደ ወደቀበት ሆኖ አይሰማውም፡፡ በኃጢአትህ ምክንያት ባንተ ላይ ሊያርፍ የነበረው የእግዚአብሔር ፍርድ ባንተ ላይ ማረፉና መፈጸሙ ቀረና ቤዛ ሆኖ በተሰጠህ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ወረደ፡፡" (ሥራ ቁ፣ 7፣ ገጽ 20-21)

- ይህ ደግሞ ለመዳን እያንዳንዱ ሰው ማድረግ የሚገባውን ነገር እግዚአብሔር ካደረገልን የማዳን ሥራ ጋር አምታትቶ በማቅረብ በዚሁ ተጠግቶ በጸጋው ብቻ ስለ ዳንኩ መንፈሳዊ ተጋድሎ አያስፈልገኝም፣ የፈለግሁትን ኃጢአት እንዳሻኝ ልሠራ እችላለሁ ለማለት ነው፡፡ በዚያውም ላይ የኢትዮጵያ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን - መዳን የሚፈልግ ሰው የታሪክ ቦታዎችን በመጎብኘት ወይም ወርቅና ብር ከፍሎ በመግዛት ነው የምትል ለማስመሰል የቀረበ ማስመሰል ነው፡፡ ስለዚህ አባባላቸው በሐሰት በስሁተት የተመላ ነው፡፡ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ስለ መዳን የምታስተምረውን ትምህርት በቦታው ላይ ስለምንደርስበት ይቆየን፡፡

**"መልካም ሥራ ለመዳን ምንም ድርሻ የለውም" በሚል ርእስ ሥር በሰፊው ሲያትቱ ደግሞ እንዲህ ብለዋል፡-**

◉ "የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብ መዳን በእግዚአብሔር ጸጋ፣ በእምነት ነው" የሚለውን የማያወላውል እውነት እናገኛለን፡፡ . . . መልካም ሥራ ለማዳን ምንም ድርሻ የሌለው ከሆነ የማደርገው በጎ ሥራ ሁሉ ትርጉምና ዋጋ የለውም ማለት ነውን? ደግሞም በኢየሱስ ክርስቶስ እስካመንኩ ድረስ የፈለግሁትን ኃጢአት ብሠራ አልጠየቅምን? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ መሰጠት ያስፈልጋል፡፡ . . . ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት አምኖ ለመዳን ለምን ይወስናል? ኃጢአትን ስለሚጠላና በኃጢአትም ምክንያት የሚመጣውን ዘላለማዊ ሞት ስለሚፈራ አይደለምን? . . . የኃጢአት ፍቅር በልቡ ካለና መዘዙንም ካልፈራ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት አምኖ መዳንን በልቡ አልፈለገም

> ማለት ነውና፣ በኢየሱስ ክርስቶስ "አመንኩ" ማለቱ ውሸት መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ . . . በኢየሱስ ክርስቶስ አምኜ ከኃጢአት ድኛለሁ ብሎ የመሰከረው ክርስቲያን አሁን እየኖረ ያለው ለኃጢአት በሞተና በተቀበረ አሮጌ እኔነትና፣ ትንሣኤ አግኝቶም ለጽድቅና ለቅድስና ሕያው በሆነ አዲስ እኔነት ነው፤ የሞተና የተቀበረ በድን ኃጢአትን ሊሠራ አይችልም፡፡ ሆኖም ገና ኃጢአትን የሚወድድና በመሥራቱም የሚጸና ከሆነ በስሜቱ ያመነ መሰለው እንጂ አላመነም፡፡" (ሙራ ቁ. 17፤ ገጽ 30-32)

እንዲህ ካሉ በኋላ (የሞተና የተቀበረ በድን ኃጢአትን ሊሠራ አይችልም፡፡ ሆኖም ገና ኃጢአትን የሚወድድና በመሥራቱም የሚጸና ከሆነ በስሜቱ ያመነ መሰለው እንጂ አላመነም ካሉ በኋላ) ደግሞ የሚከተለውን ብለዋል፡-

- ◉ *"ምንም እንኳ ክርስቲያን ቢሆንም አሮጌው ሰው ከእርሱ ጋር አለና አሮጌው ፍጥረት ደግሞ እግዚአብሔርን ከማስደሰት ይልቅ ኃጢአትን ቢሠራ ይመርጣል፡፡ ሰይጣን አማኙን የሚገናኝበት ቦታ ደግሞ አሮጌው ፍጥረት ላይ ነው፡፡ አሮጌውን ተፈጥሮ በመጠቀምም ሰይጣን ሰውየውን አሳስቶ ኃጢአት በማሠራት ድል የማድረግ አጋጣሚ ሊያገኝ ይችላል፡፡" (ጠማረ ጽድቅ፣ ጥቅምት 1991 ዓ.ም.፤ ገጽ 43)*
    - ➢ እነዚህ ሁለት አባባሎች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ናቸው፡፡ በአንድ በኩል "ያመነ ሰው የሚኖረው በሞተና ኃጢአት በማይሠራ በድን ሰውነት ነው፣ በእውነት ያመነ ከሆነ ኃጢአትን አይሠራም፣ ኃጢአትን የሚሠራ ከሆነ ደግሞ በእውነት አላመነም ማለት ነው" ብለውን ነበር፡፡ ይህን ካሉ በኋላ እንደገና መልሰው "አሮጌውን ተፈጥሮ በመጠቀምም ሰይጣን ሰውየውን አሳስቶ ኃጢአት በማሠራት ድል የማድረግ አጋጣሚ ሊያገኝ ይችላል" አሉ፡፡ ሰውዬው ከሞተና ከተቀበረ አሮጌው ሰውነት ከየት ይገኛል? ሰው ሰራሽ ትምህርት እንዲህ ነው፤ በአንድ በኩል ሲይዙት በሌላ በኩል ያመልጣል፡፡ ይህ ሁሉ የፈጠራ ድርደራና ሐተታ ሰው እንዴ ከዳነና ሁሉም ነገር ካለቀ፣ ለምን በኃጢአት ይፈተናል? ለሚለው መልስ ለመስጠት የተደረገ ሙከራ ነው፡፡ ቀጥተኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊውንና የእውነተኛ አባቶቻችንን ትምህርት ቢያውቁትና ቢያምኑት ኖሮ ከዚህ ሁሉ መንገዳገድ ነጻ ያወጣቸው ነበር፡፡ አሁንም የራሳቸው እልከኛ ልቡና ካላገዳቸው በስተቀር እድሉ አላቸው፡፡
- ◉ *"ጥምቀት ወደ መንግሥተ ሰማያት ከመግባት ጋር አንዳች ግንኙነት የለውም፡፡" (ጠማረ ጽድቅ፣ ጥቅምት 1991 ዓ.ም. ገጽ 88)*
- ◉ "ሐዋርያው ጳውሎስ ከጌታ ከተገናኘ በኋላ በአጋጣሚ ከመጠመቁ በፊት ሞቶ ቢሆን እንኳን ገነት ይገባ ነበር፡፡ . . . ጥምቀት ከዓለም እኩያ ሊኖረን ከሚገባው ውጫዊ ስፍራ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው፡፡" (ጠማረ ጽድቅ፣ ጥቅምት 1991 ዓ.ም. ገጽ 93)

እንደዚሁም የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ተለውጦ እነርሱ በሚሉት አዲስ ትምህርት ይተካ ዘንድ በተለያዩ መጻሕፍቶቻቸው አበክረው ይናገራሉ፡፡ ለአብነትም "የለውጥ ያለህ!!!" የተባለው መጽሐፋቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮ ወደ ፕሮቴስታንታዊነት ይለወጥ ዘንድ የሚጣራና የሚጮኽ መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፉ በራሱ ሥልጣን እንዲህ ሲል ይደመድማል፡-

- ◉ ". . . የኢትዮጵያ ለውጥ የሚያስፈልጋት በመሆኑ ላይ ክርክር አይኖርም፡፡ . . . በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ለውጥ ለማምጣት ሲፈለግ ከሁሉ ነገር በፊት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው አስተምህሮው ነው፡፡" (የለውጥ ያለህ!!! ፤ ገጽ 153)
- ◉ ". . . ስለዚህ አስተምህሮአዊ ለውጥ ከሁሉ በፊት ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል፡፡" (የለውጥ ያለህ!!፣ ገጽ 154)

ይህ የተሐድሶዎች ዘመቻም ፕሮቴስታንቶቹ ከአዝማቾቻቸው ጋር ሆነው ከብዙ ጊዜያት በፊት ያዘጋጁትና ያቀናበሩት፣ አሁንም እየመሩት ያሉት እነርሱው (ፕሮቴስታንቶች) መሆናቸውን ራሳቸው የሚናገሩት የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡ የተሐድሶው ዘመቻ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ውስጥ እየተካሄደ መሆኑን ራሳቸው ፕሮቴስታንቶቹም እየመሰከሩ ይገኛሉ፡፡ ለአብነት ያህልም "ከሌሊቱ

ስንት ሰዓት ነው?" በሚል ርእስ የሙሉ ወንጌል ተከታይ በሆነው በቀለ ወልደ ኪዳን በተባለው ግለሰብ በ2003 ዓ. ም. የተዘጋጀውና "በሙሉ ወንጌል አማኞች ቤ/ክ" የታተመው መጽሐፍ ገጽ 112-113 ላይ እንዲህ ይላል፡-

> በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየተቀጣጠለ ያለው የተሐድሶ እንቅስቃሴ ሌላው የሚጠቀስ ጉዳይ ነው፡፡ በከተማም ሆነ በገጠር ያልነካካው ደብር የለም፡፡ በቤተ ክርስቲያኒቱ የውስጥ ሰዎች በየዓመቱ በቁጥር ጥቂት የማይባሉ መጻሕፍት ይታተማሉ፡፡ . . . ይህ ጩኸት የብዙዎች ጩኸት እየሆነ ነው፡፡ በቅርቡ ጩኸቱም ምላሹም አገር አቀፋዊ ሳይሆን እንደማይቀሩ ነው እኔ የማምነው፡፡ እንቅስቃሴው ከጀመረ 20 ዓመት አልፎታል፡፡ ከውስጥ የጸረ ተሐድሶ (Counter Reformation) እንቅስቃሴ ... ቢፈታተነውም እንቅስቃሴው ግን እስከ አሁን ድረስ ጋብ የማለት አዝማሚያ አይታይበትም፡፡ ... ምናልባት ሌላ ማንሣት ያለብኝ ነገር ብዙ አገልጋዮች እየተዘጋጁ የመሆናቸው ነገር ነው፡፡ እነዚህ አገልጋዮች በአብዛኛው ገና ያልተገለጡ ናቸው፡፡ በአብዛኛው ሕዝበ ክርስቲያን ዘንድ ገና አይታወቁም ማለቴ ነው፡፡ ቁጥራቸውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣት ላይ ነው፡፡ . . . ("ክሊሲቱ ስንት ሰዓት ነው?"፣ በቀለ ወልደ ኪዳን፣ 2003 ዓ. ም.፣ ገጽ 112-113)

እንግዲህ ብዙ ጥቅሶችን ከተለያዩ ምንጮቻቸው የወሰድነው ከዚህ በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ እና በአበው ሊቃውንት ትምህርት የምንመዝነው አስተምህሯቸው እነርሱው በትክክል ደግመው ደጋግመው የሚናገሩትና የሚያስተምሩት አቋማቸው መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ እንዲገባ ነው፡፡

በመዳን ትምህርታቸው ውስጥ ያሉት ዋና ዋና ነጥቦች ሲጠቃለሉ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነትና የማዳን ሥራውን በምልዓት ሳይሆን በጥበት፤ ከብሥራት ከፅንሰትና ከልደት ጀምሮ መላውን ሥጋዌውን ሳይሆን የዕለተ ዓርቡን ብቻ ነጥለው ይወስዳሉ፡፡ በኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ ግን የጌታችን አዳኝነት ዕለተ ዓርብ ላይ ብቻ የተወሰነና የተገደበ ሳይሆን መላው ሥጋዌው - ከፅንሰቱ እስከ ዕርገቱ - ለመዳናችን አስፈላጊ ነበር፡፡

2. እነርሱ ድኗል የሚሉት ሰው መንግሥተ ሰማያት ስለ መግባቱ ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች ነን ብለው ይፎክራሉ፡፡ ኦርቶዶክሳውያንን ሲነቅፉ "'ድነሃልን?' ተብለው ሲጠየቁም 'እንዴት ብዬ' ከመሞቴ በፊት መዳኔን በምን ላረጋግጥ እችላለሁ? ብለው ጥያቄውን በጥያቄ ይመልሳሉ" የሚሉትም ለዚህ ነው፡፡ ይህም በእያንዳንዱ ሰው የመዳን ሂደት ውስጥ ያሉትን መሠረታዊ ነገሮች ለይቶ ካለመረዳትና ከማደባለቅ የመጣ ስህተት በመሆኑ በቦታው ላይ በስፋት እንመለከተዋለን፡፡

3. ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን ወዲያውኑ ስለሚድን ከዚያ በኋላ ኃጢአት ቢሠራ አይፈረድበትም፣ አይጠየቅበትም ይላሉ፡፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የተሰቀለውና የተቀበለው ሥቃይና የሞተው ሞት የእኔን ኃጢአት ዕዳ ለመክፈል ስለሆነ እኔም ይህንኑ አምኜ በመቀበሌ ዛሬ ባመንኩበት ቅጽበት ድኛለሁ፡፡ *ከእንግዲህ ወዲህ እኔ በኃጢአቴ አልጠየቅም*" ይላሉ፡፡ ይህንኑ በማጠናከርም፡- "አማኞች ሆነን ኃጢአት ብንሠራ የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን የተሰጠንን መብት ይቀይረዋል ወይ? . . . ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነትና ያገኘነው ቤዛነት እስከ ዘላለም በማረጋገጫ የታተመ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል፡፡ ይህም ዝምድና አይሻርም" ይላሉ፡፡ (ጠማረ ጽድቅ፣ ገጽ 60) በዚህም ሰው አመንኩ ካለ በኋላ የፈለገውን ኃጢአት ቢሠራ በእግዚአብሔር ዘንድ አያስጠይቀውም፣ ፍርድና ቅጣትም አያመጣበትም በማለት ሰዎችን የሐሰት ትምህርት በማስተማር ወደ ኃጢአት እንዲገፋፉና ኃጢአትን ለመታገል መንፈሳዊ ኃይላቸው እንዲደክም ለማድረግ የዲያብሎስ ሠራተኞች ሆነው ያገለግላሉ፡፡ በዚህም የክርስትናን ዓላማ በግልጽ እየተቃወሙ ለአለቃቸው ለዲያብሎስ የውስጥ አርበኞች ሆነው ይሠራሉ፡፡

4. መዳን የሚገኘው በእምነት ብቻ፡(ያለ ጥምቀት፣ ያለ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ፣ . . . ያለ መንፈሳዊ ምግባር) ነው ይላሉ፡፡ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን (ምሥጢረ ጥምቀት፣ ምሥጢረ ሜሮን እና ምሥጢረ ቁርባን) ለመዳን ምንም አስፈላጊነት የላቸውም ይላሉ፡፡

5. ክርስቲያናዊ ተጋድሎና መልካም ሥራ ለመዳን ምንም ድርሻ የላቸውም ይላሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ኦርዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ስለ መዳን የማትለውንና የማታምነውን እንደምትል እያስመሰሉ በነቀፋና በዘለፋ ከሚናገሯቸው ነጥቦች መካከል ደግሞ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፦

1. ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት ትታ በእርሱ ምትክ ፍጡራንን አዳኝ አድርጋ እንደምታምን አስመስለው ማቅረባቸው፦

   ◉ "በሰማይና በምድር ካሉ ግኡዛንና ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ ለሰው ተለዋጭ (ቤዛ) የሚሆንለት ሊገኝ እንዳልቻለ፤ . . . በእግዚአብሔር ቸርነት የተሰጣቸውን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት ሳይቀበሉ በምንም በምንም ለመዳን ያሳለፉትን ጊዜ ርዝመት ሲያስቡት አዘኑ፡፡ በመጨረሻም እጃቸውን ለጌታ ሰጡ፡፡" (ሙራ ቁ. 13፣ ገጽ 2)

ይህ ደጋግመው የሚናገሩትና በመደጋገም እውነት የሆነ እንዲመስል ለማድረግ በየቦታው እስኪሰለች ድረስ የሚመላለሱት የማታለያ ፕሮፓጋንዳ ነው፡፡ ለአብትነም በሙራ ቁ. 19፣ ገጽ 1 "እንደዚህ ያለ ጥልቅና አስደናቂ ምስጢርን ይዞ በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ላይ የተመሠረተው መሠረተ እምነታችን በተረት መጻሕፍት በመቀበሩ ድነነት በፍጡራን ይገኛል የሚለው ኢ.መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ እንደ እንጉዳይ በቅሎ ይታያል" ብለዋል፡፡ ይህ የለየለት ውሸትና የስም ማጥፋት ዘመቻ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አዳኝ ማን እንደ ሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠውን እውነት ሳትጨምርና ሳትቀንስ አክብራ የያዘችና የምትጠብቅ ናት፡፡ ሆኖም አለፍ አለፍ እያሉ ሥጋና ደም ካቀበላቸው አስተሳሰብ ጋር የሚስማማቸውን ጥቂት ጥቅሶችን ብቻ ዘገን ዘገን አድርገው እነዚያን በቅል ውስጥ እንዳሉ ጥቂት ባቄላዎች እያንኳኩ እንደሚረብሹት እንደ እነርሱ ስላልሆነች "ጨኽቴን ቀማኝ" እንደ ተባለው የራሳቸውን ክህደት ለመሸፈን እርሷን ያልሆነ መልክ ለመስጠት መሞከራቸው የአጥፊዎች ጠባይ ስለሆነ አይገርመንም፡፡ የኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን የመዳን ትምህርቷን በቦታው እናየዋለን፡፡

2. ክርስቲያናዊ መልካም ሥራንና መንፈሳዊ ተጋድሎን ከመዳን ጋር አምታትተውና አዘበራርቀው ያቀርቡታል፡፡ ለአብነትም፦

   ◉ "ወንጌላዊው መዳንን የሚፈልግ ሰው ወደ ቅድስት ሀገር ይሒድና የታሪክ ቦታዎችን ይጎብኝ ወይም ወርቅና ብር ይክፈልና ይግዛ፣ ወይም ሰባት ዓመት በራሱ ይቁምና ይጸልይ፣ ወይም በአንዱ በረሓ ውስጥ ገብቶ በረሃብና በጥም ራሱን ይግደል አላለም፡፡ እንደዚህማ ባለ መንገድ የሰው ነፍስ ልትድን ብትችል ኖሮ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ተለዋጭ ሆኖ ይሞት ዘንድ ባላስፈለገን ነበር፡፡ አሁንም የሰው ድርሻ ሆኖ የቀረበው በተፈጸመው የእግዚአብሔር ሥራ <u>ማመን ብቻ</u> ነበረ፡፡ ቃሉን የሚሰማ ሰው ራሱን ለማዳን ከእንግዲህ ወዲያ የሚሠራው ግዳጅ እንደ ወደቀበት ሆኖ አይሰማውም፡፡" (ሙራ ቁ፡ 7፣ ገጽ 20-21)

ይህም ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን መዳን የሚገኘው ወደ ቅድስት ሀገር በመሄድ ወይም የታሪክ ቦታዎችን በመጎብኘት ነው የምትል ለማስመሰል ነው፡፡ ወይም ደግሞ መዳን ወርቅና ብር በመክፈል ይገዛል፣ ወይም በጾምና በጸሎት ብቻ ወይም በበረሓ ውስጥ ገብቶ በመጋደል ብቻ ይገኛል የምትል ለማስመሰል የቀረበ ነው፡፡

3. ቦታውን የት እንደሆነ ባይነግሩንም *"በአንዳንድ ቦታ ይህን ወንጌል በማናናቅ የሰውን ነፍስ ለማዳን የሚከፈለው፣ ከጎመን ዋጋ ያነሰ እንደ ሆነ በማስመሰል በአልሀ እየተሰበከ ነው"* ብለዋል፡፡ እንግዲህ ይህ ማለት መዳን የተገኘው እነርሱ እንዳሉት ከጎመን ዋጋ ባነሰ መሆኑን የሚሰብከው ማን ነው? የሚሰበከውስ የት ነው?

4. በክርስቶስ ያመኑ ክርስቲያን የሚያደርጋቸውን ምግባረ ወንጌል በሕገ ኦሪት ከታዘዘው ድርጊት ጋር እያደበላለቁና እያምታቱ ማቅረብ፣

◉ "ጳውሎስም ጸጋና ሕግ እርስ በርስ ተቃራኒ እንደ ሆኑ ገልጿል፡፡ . . . ያዕቆብስ ቢሆን "ሥራ፣ (ምግባር) እያለ የጠራው ምግባረ ኦሪትን ነው ቢባል መልሱ አይደለም ነው፡፡ <u>ፍቅር</u>፣ ቸርነት፣ በጎነት፤ በሐዲስ ላይ የበቀለው የሕያው እምነት ፍሬዎች ናቸው እንጂ ከዐሠርቱ ትእዛዛት መካከል አይደሉም፡፡"

በመጀመሪያ ዐሠርቱ ትእዛዛትን የሠራቸው እግዚአብሔር እንጂ ሰይጣን አይደለም፡፡ በኦሪቱ በሙሴ አማካይነት አሥሩን ትእዛዛት ለሕዝቡ የሰጣቸው ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ በሐዲስ ኪዳንም እነዚያን ትእዛዛት አልሻራቸውም፣ ይልቁንም "ሰማእክሙ ዘተብህለ ለቀደምትክሙ፣ አንሰ እብለክሙ - ለቀደሙት የተባለውን ሰምታችኋል፣ እኔ ግን አሁን እንዲህ እላችኋለሁ" እያለ ሕግጋቱን የበለጠ ፍጹማን አደረጋቸው እንጂ አልሻራቸውም፡፡ በኦሪቱ "አትግደል" ብቻ የነበረውን በሐዲሱ ወደ መግደል የሚያደርሰውን መንስዔ ከሥሩ በመቁረጥ "አትቆጣ" በሚል ፍጹም አደረገው፡፡ ያ ድርጊታዊ ነበር፣ ይህ ግን ሕሊናዊም ጭምር ነው፡፡ በኦሪቱ "አታመንዝር" ብቻ ነበር፤ በሐዲሱ ግን "አትመኝ" በማለት የበለጠ ፍጹም አደረገው፡፡ በዚያ የተከለከለው ድርጊቱ ሲሆን አሁን ግን ሐልዮውንም (ሃሳቡን) ጭምር ከለከለ፡፡ ይህም ጌታችን የመጣው ሥጋችንን ብቻ ለመቀደስ ሳይሆን መንፈሳችንንም ለመቀደስና የእርሱ ቤተ መቅደስ ለማድረግ ስለሆነ ነው፡፡ "እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም" ያለው ለዚህ ነው። ማቴ. 5፥17

ሆኖም ግን ሰው የሚድነው በሕገ ኦሪት ስላልሆነ አካላዊ ቃል ሰው ሆነ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "ከሥጋ የተነሣ ስለ ደከመ ለሕግ ያልተቻለውን፥ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጓልና፤ እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኰነነ" በማለት የገለጸው ይህን ነው፡፡ ሮሜ 8፥3-4 "የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና" የተባለውም ለዚህ ነው። ሮሜ 10፥4

እንግዲህ ይህ የተሐድሶዎች በብሉይ ኪዳን ዘመን የተሰጠውን ሕጉንና ትእዛዛቱን መጥላትና መጸየፍ ከግኖስቲኮች የወረሱት እርሾ ነው፡፡ ከላይ መኃትው በሚለው ክፍል ላይ እንደ ተመለከትነው ግኖስቲኮቹ እነ መርቅያንና እነ ማኒ ሕገ ኦሪትን እና እርሷን ሠርቷል የሚሉትን አምላክ አምርረው ይጠሉና ይጸየፉ ነበር፡፡ የብሉይ ኪዳኑን አምላክ ጨካኝና ምሕረት የማያውቅ ክፉ አምላክ፣ የሐዲስ ኪዳኑ ደግሞ ደግ አምላክ ብለው ምንታዌን (የሁለት አምላክ ትምህርት) ያስተምሩ ነበርና የዚያ ነጸብራቅ ነው፡፡

"በዚያውም ላይ <u>ፍቅር</u>፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ በሐዲስ ላይ የበቀለው የሕያው እምነት ፍሬዎች ናቸው እንጂ ከዐሠርቱ ትእዛዛት መካከል አይደሉም" በማለት ዐሠርቱ ትእዛዛትን ከፍቅር የተለዩና ከጭካኔ የመጡ አስመስለው አቅርበዋቸዋል፡፡ ይህም በውስጣቸው ያለው ግኖስቲካዊ አስተሳሰብ ያመጣው ነው፡፡ ተሐድሶዎች ሆይ፣ የዐሠርቱ ትእዛዛት መሠረታቸው ፍቅር መሆኑን ጌታችን የተናገረውን አልሰማችሁምን? መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ እነርሱ ያለ አንድ ሕግ አዋቂ ነኝ ባይ ሊፈትነው "መምህር ሆይ፥ ከሕግ ማናቸይቱ ትእዛዝ ታላቅ ናት?" ብሎ በጠየቀው ጊዜ የመለሰለትን መልስ እንስማ፡- *"ኢየሱስም እንዲህ አለው፡- ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም*

ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፤ እርሷም፦ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል።" ማቴ. 22፡36-40 ታዲያ የዐሥሩ ትእዛዛት መነሻቸውም መድረሻቸውም ፍቅር ነው እንጂ ከፍቅር ውጭ አይደሉም፡፡ ትእዛዛተ እግዚአብሔር ፍቅር እንጂ ሸክም ወይም ቀንበር አይደሉም፡፡ ይህ ትእዛዛተ እግዚአብሔርን እንደ ሸክምና ቀንበር አድርጎ ማሰብና መመልከት በግኖስቲኮቹ በእነ መርቅያን የተጀመረ፤ በኋላም በእነ ሉተርና ካልቪን የተቀነቀነና በምዕራቡ ዓለም እንዲስፋፋ የተደረገ አመለካከት እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ኦርቶዶክሳዊ አይደለም፡፡

ሌላው ቀርቶ በኦሪቱ "ዓይን ቤዛ ዓይን ወስን ቤዛ ስን - ዓይን ያጠፋ ዓይኑ ይጥፋ፤ ጥርስ የሰበረ ጥርሱ ይሰበር" የሚል ሕግ የሰጠው ራሱ እግዚአብሔር ሲሆን ያን ያደረገውም ከአባታዊ ቸርነቱና ለሰው ካለው ፍጹም የሆነ ደግነትና አሳቢነት የተነሣ እንጂ የቂምካኔ ወይም ሰውን ለመጉዳት የተሰጠ ሕግ አልነበረም፡፡ ያን ያደረገበት ምክንያትም ዘመኑ ኦሪት የሰው ልጅ ከፈጣሪው ተለይቶ ከጸጋው የተራቆተበትና ከዚህም የተነሣ በአእምሮውና በሰውነቱ ኃጢአት የነገሠበት፤ ራሱን መቆጣጠርና መግዛት ያልቻለበት ዘመን ነበር፡፡ ያ ዘመን የእርስ በርስ መጎዳዳትና መጋደል፤ ጦርነትና ጥፋት የሠለጠነበት ዘመን ስለ ነበር ከዚያ ከነበረው ከሰዎቹ ሁኔታ እንጻር የተሠራ ሕግ ነበር፡፡ አንድ ሰው የሌላውን ሰው ዓይን ለማጥፋት እስኪነሣ የደረሰ ጨካኝ ከሆነ ለወንድሙ ዓይን መጥፋት ወይም ለጥርሱ መሰበር ግድ የሌለው ክፉ ከሆነ ሌላው ላይ ጉዳት ካደረሰ በኋላ የእርሱም ዓይን እንደሚወጣ ወይም ጥርሱን እንደሚከፍል አስቀድሞ በሕግ ሲነገር ቆም ብሎ እንዲያስብና ለሌላው ወንድሙ አዝኖና ራርቶ ከክፋት ባይመለስ እንኳ ቢያንስ በራሱ ላይ በሕጉ መሠረት የሚደርስበትን አስቦ በሌላው ላይ ጉዳት ከማድረስ እንዲቆጠብ ለመግታትና ለማስተማር ነበር፡፡ እግዚአብሔር የሰጠው የኦሪቱ ሕግ ዓላማ ማስተማርና መጠበቅ እንጂ ማጥፋት አልነበረም፡፡ በዓለማዊ ሕግ እንኳ ወንጀለኞች የሚቀጡበት ዋናው ምክንያት ለማስተማር ነው፡፡ ስለዚህ ሕገ ኦሪትን እንደ ቂምካኔ ሕግ፤ የሠራትንም አምላክ እንደዚያው አድርጎ ማሰብ መርቅያናዊና ግኖስቲካዊ ስህተት ነው፡፡

እንግዲህ በአንድ በኩል የእነርሱን የመዳን ትምህርት ምን እንደ ሆነ፤ በሌላ በኩል ደግሞ እነርሱ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ መዳን ያላትን አስተምህሮ በተመለከተ እንዴት እንደሚገልጹዋት ከተመለከትን ከዚህ በመቀጠል የቤተ ክርስቲያንን የመዳን ትምህርት ከመሠረቱ ጀምረን እንመለከታለንና ወደዚያ እንሂድ፡፡ በመጀመሪያ ግን የመዳን ትምህርት በዘመናት ሂደት ውስጥ ያለፈበትን ታሪካዊ ሂደት በአጭሩ እንዳስሳለን፡፡ እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን፡፡

## 2.2 የመዳን ትምህርት በዘመናት ሂደት ውስጥ - አጭር ዳሰሳ

ክርስትና ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ወደ ልዩ ልዩ የዓለም ክፍሎች እየተሰበከ በሄደባቸው የመጀመሪያዎቹ ሁለት እና ሦስት መቶ ዘመናት ላይ ክርስቲያኖች የኢየሱስ ክርስቶስን መድኃኒትነትና አዳኝነት አጠንክረው ይሰብኩና ያስተምሩ ነበር፡፡ የትምህርታቸው ዋና ጭብጥም ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት አምነው፤ ለመዳን አስፈላጊ የሆኑ ምሥጢራትን (ጥምቀትን፤ ሜሮንን፤ ቁርባንን) ፈጽመው የዘለዓለም ሕይወትን እንዲያገኙ ማስተማር ነበር፡፡ ለምሳሌም በበዓለ ሃምሳ ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች በዓል ለማክበር ኢየሩሳሌም ተሰብስበው ለነበሩት አይሁድ ቅዱስ ጴጥሮስ ባስተማረው ትምህርት ላይ ዋና ጉዳይ አድርጎ የሰበከው እነርሱ (አይሁድ) የሰቀሉት ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና መድኃኒት መሆኑን ነበር፡፡ከዚያም ትምህርቱን የሰሙት ሰዎች ልባቸው በተነካና ባመኑ ጊዜ ቅዱሳን ሐዋርያትን "ምን እናድርግ?" ሲሏቸው ቅዱስ ጴጥሮስ "ንስሐ ግቡ፤ ኃጢአታችሁም ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ" በማለት የጸጋ እግዚአብሔር መገኛ ምንጮች የሆኑትን ምሥጢራት ቤተ ክርስቲያንን ይፈጽሙ ዘንድ አስተማራቸው። የሐዋ. 2፡37-38

በእነዚያ የመጀመሪያዎቹ ዘመናት የነበሩት ክርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱስ - በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ያሉትን ስለ መዳን የሚናገሩትን ጥቅሶች "እግዚአብሔር ያዳነን እንዴት ነው? . . ." ወደሚለው ነገረ መለኮታዊ ጥያቄ ዝርዝር ውስጥ ሳይገቡ ይሰብኩ ነበር፡፡ ሆኖም ክርስቲያኖች የኢየሱስ ክርስቶስን መድኃኒትነት አምነው ከተቀበሉ በኋላና አማንያን ቁጥራቸው እየበዛ፣ የሚሰጠው ትምህርትም ሰፋ፡ቱና ጥልቀቱ እየጨመረ ሲሄድ "እግዚአብሔር አዳነን ስንል ምን ማለት ነው? ያዳነንስ ከምንድን ነው? መዳን ማለትስ ምንድን ነው?" ወዘተ የሚሉት ነገረ መለኮታዊ ጥያቄዎች በተለያዩ አካላት በተለያየ መንገድ መነሣታቸውና መዳሰሳቸው አልቀረም፡፡ በተለይም ደግሞ በየጊዜው እንግዳ ነገር እየያዙ ብቅ የሚሉ የመናፍቃንን ኑፋቄ ስህተትነት ለመግለጥና ሐዋርያዊውን አስተምህሮ ለማሳወቅ ለመጠበቅ በሚደረጉ ጥረቶች ወደ እንዲህ ዓይነት ነገረ መለኮታዊ ጉዳዮች መግባቱ ሁኔታዎች የግድ የሚሉት ነገር እየሆነ ሄደ፡፡

በግኖስቲኮችም ሆነ በአርዮሳውያን፣ በንስጥሮስም ሆነ በልዮናውያን "ኢየሱስ ክርስቶስ ማን ነው?" በሚለውና በባሕርዩ ዙሪያ የተነሡት ልዩነቶችና ክርክሮች ሁሉ መሠረታቸውና ማጠንጠኛቸው የመዳን ጉዳይ ነበር፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት እድሜ ልኩን እውነቱን በማስረዳት የተጋደለውና ጥብቅና የቆመው ኢየሱስ ክርስቶስ አርዮስ ይለው እንደ ነበረው "ፍጡር" ቢሆን ኖሮ ፍጡር ፍጡርን ሊያድነው ስለማይችል ነገሩ እንደ አርዮስ አባባል ቢሆን ኖሮ ሰውን ያልዳነ የሚያደርግ አደገኛ ኑፋቄ በመሆኑ ነበር፡፡ ሰው ካልዳነ ደግሞ ክርስትና ትርጉም አይኖረውም፡ ሃይማኖትም ፋይዳ አይኖረውም፣ የክርስትና ሃይማኖት የመዳን ሃይማኖት ነውና፡፡

የንስጥሮስን ኑፋቄ እነ ቅዱስ ቄርሎስ የተቃወሙትና ስህተቱን በመግለጥ የተጋደሉትም ለዚሁ ነበር፤ መለኮታዊ አካልና መለኮታዊ ባሕርይ ከትስብእት ጋር እውነተኛ ተዋሕዶን የተዋሐዱ ካልሆነ በስተቀር መዳን (ድኅነት) አይኖርምና ነው፡፡ መለኮት ሥጋን ብቻ እንጂ ነፍስን አልተዋሐደም የሚለውን የአቡሊናርዮስን ኑፋቄ የተቃወሙትም ያልተዋሐደውን (ገንዘቡ ያላደረገውን) አያድነውምና ነፍስን አልተዋሐደም ከተባለ ነፍስን ያልዳነች ስለሚያደርጋት ነው፡፡ በአጠቃላይ አባቶቻችን ሌሎችንም ኑፋቄዎች ሲመዝኑበትና ሲለኩበት የኖሩት "ቀኖና - መለኪያ" የመዳን ትምህርት ነው፡፡ እንደዚሁም ኑፋቄዎችን ሁሉ ጸንተው ሲታገሉ የኖሩት በእግዚአብሔር ቸርነት የተሰጠውን የሰውን መዳን ከንቱ የሚያደርጉ ስለ ነበሩና ስለሆኑ ነው፡፡ ነገረ ድኅነት እና ነገረ ክርስቶስ የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸውና፡፡

እስከ 5ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያዎቹ አካባቢ መላው የክርስትና ዓለም አንድ ሆኖ የክርስቶስን አዳኝነት ከመናፍቃን እየጠበቀ፣ ኑፋቄን በአካባቢያዊም በዓለም አቀፋዊም ጉባኤያት ቢጋራ እያወገዘና እውነቱን እያስረዳ ቀጠለ፡፡ ሆኖም ከዚያ በኋላ ግን ቀስ በቀስ የአመለካከትና የአረዳድ ልዩነቶች እየተፈጠሩ ሄዱ፡፡ ያን አስቸጋሪ እየሆነ የሄደውን አዝማሚያ ባልገባው ጉዳይ ውስጥ እንደ እርጎ ዝንብ ጥልቅ ያለው ርጉሙ ልዮንና ሥልጣናቸውን መከታ ያደረጉት የቁስጥንጥንያው ንጉሥና ንግሥት (መርቅያንና ብርክልያ) ተባብረው በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ እንዳይመለስ አድርገው መስመሩን በደም አሰመሩት፡፡ ሂደቱም እየቀጠለ በመሄድ በምሥራቁ እና በምዕራቡ የክርስትና ዓለም በዚህ ጉዳይ ላይ (በመዳን ጉዳይ ላይ) ያለው አስተምህሮና አተናተን የየራሱን መስመር እየያዘ ሄደ፡፡

## 2.2.1 የነገረ ድኅነት ትምህርት በዘመናት ሂደት ውስጥ - በምዕራቡ ዓለም

የምዕራቡ ዓለም የሚባለው የጥንቷ ሮም ግዛት አካል የነበረው ሲሆን ያ ክፍለ ዓለም ነገሮችን የሚመለከተው፡ ሃይማኖታዊ ጉዳዮችንም ጭምር የሚያየው በሕግ ጽንሰ ሐሳብ መሠረትነት (Legalistic and judicial) ነበር፡፡ የሮማ ክፍለ ዓለም በነገረ ሕግ የሠለጠነ ስለ ነበር በዚያው ክፍለ ዓለም የነበሩት ሰዎች ነገሮችን ሁሉ የሚመለከቱትና የሚተነትኑት ከሕግ አንጻር ነበር፡፡ ስለሆነም ያ ሕግ ነክ (Legalistic) የሆነው አመለካከታው በሁለንተናዊ ነገራቸውና አስተሳሰባቸው ሁሉ ወደ ውስጥ ዘልቆ የገባ ስለ ነበረ ክርስትናውን ሲቀበሉም በዚያው መንፈስ ነበር የተቀበሉት፡፡

በመሆኑም ነገረ ሃይማኖታዊ ግንዛቤያቸውና አረዳዳቸው ሁሉ በዚያው በሥነ ሕግ መንፈስ የተቃኘና የተዋጀ ነበር፡፡ የሰውን መዳንና የእግዚአብሔርን አዳኝነትም የሚረዱትና የሚተነትኑት ከዚያው ከሥነ ሕግ ግንዛቤያቸው አንጻር (Legal or judicial aspect) ነበር፡፡ ይህ አሳቤያቸው ቀስ በቀስ እያደገ፡ሄዶ በ12ኛው መቶ ዓመት ላይ በሚገባ የተብራራ ራሱን የቻለ የአስተሳሰብ መንገድ ሆነ፡፡ ይህም ስኮላስቲሲዝም (Scholasticism) የሚባለው ነው፡፡

## 2.2.2 ስኮላስቲሲዝም (Scholasticism)

የመጀመሪያው የስኮላስቲሲዝም ምሁር ተብሎ የሚታወቀው አንስለም (Anselem) የተባለው የካንትርበሪ ጳጳስ ሲሆን "እግዚአብሔር ለምን ሰው ሆነ?" በሚለው መጽሐፉ ላይ "ክርስቶስ ለእግዚአብሔር የከፈለው ቤዛነት በሰው ኃጢአት የእግዚአብሔር ክብር ለመጣሱ የተከፈለ ዋጋ ነው"[57] በማለት "የክፍያ አስተምህሮ" (The doctrine of *satisfaction)* የተባለውን አስተሳሰብ አመጣ፡፡ ይህ ቲዎሪም በኃጢአት እና በሰው ኃጢአተኛነት ላይ ከመጠን ያለፈ ትኩረት ለሚያደርገው አስተሳሰብ ጫፍ የደረሰ መግለጫ ነበር፡፡ በኋላ ላይ ዮሐንስ ቄስሌይ የተባለው ደግሞ "ክርስቶስ የሞተው የእግዚአብሔርን ቁጣ ለመካስ (ለማብረድ) ነው"[58] በማለት ይህን አሳቤ ትንሽ ለወጥ በማድረግ አቀረበው፡፡ ይህ አሳቤ (Theory) በሥነ ሕግ ጽንሰ ሃሳብ ምሕዋር ዙሪያ ሲሽከረከር ለነበረው ሕግ ተኮር ለሆነው በኃጢአትና በቅጣት ላይ ከፍ ያለ ትኩረት ለሚያደርገውና በምዕራባዊው ዓለም በብዛት ይንጸባረቅ ለነበረው አስተሳሰብ ቅርጽ የሰጠና ነገሩን ከዳርቻው ላይ ያደረሰ አሳቤ ነበር፡፡ የክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት ኃጢአተኛ የሆነውን ሰው ሁሉ ወክሎ ለአብ የከፈለው የኃጢአት ዋጋ ነው የሚለውን ከፍ ያለ ትኩረት ይሰጡት ነበር፡፡

በዚህ አሳቤ መሠረት ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ "ተፈጸመ" ሲል ዕዳው ተከፍሏል፣ ዕዳው በመከፈሉም መዳን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተገኝቷል፣ የእያንዳንዱ ሰው የመዳን ጉዳይም ተዘግቷል ይላሉ፡፡ ይህ አሳቤ (The doctrine of *satisfaction)* አብዛኛውን የምዕራቡን ዓለም የነገረ መለኮት ሰዎች አሳቤ በዕለተ ዓርብና በመስቀሉ ዙሪያ ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ በማድረግ የሥጋዌውን ሌሎች ገጽታዎችና ያስገኙትን ጠቀሜታዎች፣ እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስን ሚና ሁሉ እንዲዘነጉ አደረጋቸው፡፡ መዳን አንድ ጊዜ ዕዳችን ሲከፈል በመስቀል ላይ ስለ ተፈጸመ ከዚያ በኋላ ምንም ነገር አያስፈልግም ወደሚል ጽንፍም ወሰዳቸው፡፡ በዚህ አሳቤ መሠረት ስለ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነትና ሚና እንዲሁም የራሱን መዳን ለመፈጸም የእያንዳንዱ ሰው ሚና (ሱታፌ) ሁሉ አላስፈላጊና ፋይዳ ቢስ ሆነ፡፡

## 2.2.3 የትሬንት ጉባኤ (1545 – 1563)

ይህ ከላይ የተገለጸው አሳቤ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን እና የእያንዳንዱን ሰው ሚና አላስፈላጊና ፋይዳ ቢስ ስላደረጋቸው ለእነዚህ ነገሮች (ለምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንና ለምግባር ለትሩፋት) ድርሻ እንዲኖራቸው ለማድረግ በማሰብ በ16ኛው መቶ ዓመት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የትሬንት ጉባኤን አካሄደች፡፡ ጉባኤው በዋናነት ሉተራውያን ተሐድሶዎችን በተመለከተ የተደረገ ጉባኤ ነበር፡፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ጉባኤ ላይም "መጽደቅ" የኃጢአት ሥርየት ብቻ ሳይሆን መቀደስ እና በነጻ ፈቃዱ ጸጋ እግዚአብሔርን በመቀበል የሚገኘው የሰው ውሳጣዊ ባሕርዩ መታደስም ነው አለች፡፡ ለዚህ ደግሞ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንና ምግባር ትሩፋት ሚና አላቸው አለ፡፡

[57] (The recompense that Christ paid to God because his honor had been violated.)
[58] (Christ died to satisfy God's wrath.)

## የፕሮቴስታንቶች አጸፋ

በዚህ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውሳኔ የተበሳጩት ፕሮቴስታንቶች ደግሞ "መዳን ያለ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንና ያለ የመልካም ምግባር ሕይወት በእምነት ብቻ ነው" በማለት ለካቶሊኮች ውሳኔ ያላቸውን ተቃውሞ ገለጹ፡፡ ስለ መዳን በሚያስተምሩት ትምህርትም በሁለት ቃላት መካከል ልዩነት አደረጉ፤ እነዚህም መጽደቅ (Justification) እና መቀደስ (Sanctification) የሚሉት ናቸው፡፡ በእነርሱ አስተምህሮ መሠረት መጽደቅ የሚሉት የኃጢአት ሥርየትን ሲሆን መቀደስ የሚሉት ደግሞ ጸጋ ወደ ሰውነት መምጣቱን (ጸጋን ማግኘትን) ነው፡፡ በእነርሱ ትምህርት መጽደቅ የክርስቶስ የጸጋው ሥራ ብቻ ነው፡፡ እርሱን ለማግኘት የሚያስፈልገው ሁኔታ ወይም መንገድ እምነት ብቻ ነው፤ ሆኖም እምነትም እንደገና የራሱ የእግዚአብሔር የነጻ ስጦታ ስለሆነ የእርሱው ግንዘብ በመሆኑ ሰው ለራሱ መዳን አንዳችም ድርሻ ወይም ሚና የለውም ማለት ነው፡፡

በዚህ እነርሱ በሚሉት መጽደቅ ውስጥ ጥምቀትም ሆነ ምሥጢራት እንዲሁም መንፈሳዊ ተጋድሎና መልካም ምግባራት ምንም ዓይነት ድርሻ የላቸውም፡፡ መልካም ሥራዎች ደግሞ የመዳን ፍሬዎችና ምልክቶች ናቸው እንጂ ለመዳን የሚያስፈልጉ አይደሉም አሉ፡፡ በሌላ በኩል መቀደስም (መጽደቅ ብቻ ሳይሆን) የጸጋው ሥራ ብቻ ነው፤ ምክንያቱም መቀደስም የመጽደቅ ውጤት ነውና፡፡ ያልጸደቀ ስለማይቀደስ፤ መጽደቅ ደግሞ የሚገኘው በእምነት ብቻ ስለሆነ፤ እምነትም ደግሞ የራሱ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ስለሆነ ሰው ለመጽደቅም ሆነ ለመቀደስ የራሱ አንዳችም ድርሻ (ሱታፌ) የለውም ማለት ነው፡፡ ወደ ኋላ ላይ ዮሐንስ ዌስሊይ የተባለው መጽደቅ የክርስቶስ ሥራ ሲሆን መቀደስ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው ብሎ አስተማረ፡፡ ሲጠቀለል ሁሉም ነገር ከጸጋው ብቻ የሚሰጥ ስለሆነ ሰው በእርሱ ላይ የሚሆነውን ነገር ዝም ብሎ መታዘብና መቀበል ብቻ እንጂ አንዳችም የሚያደርገው ሱታፌ የለውም ማለት ነው፡፡

### እነዚህ ነገረ መለኮታዊ እሳቤዎች ሲመዘኑ

የካቶሊኩ ዓለምም ሆነ የፕሮቴስታንቱ ዓለም ሲወዛገቡባቸው የነበሩት ነገረ መለኮታዊ እሳቤዎች የሁለቱም የጋራ መሠረት ከነበረው ከሥነ ሕግ (Legalistic) እሳቤና ድባብ የመነጩ ነበሩ፡፡ ሁለቱም ሲዋኙበት የነበረው ዓለም በፍርድ ቤት ባለው በወንጀል፤ በወንጀለኛ ላይ በሚፈጸመው የወንጀለኛ አቀጣጥና ነጻ አወጣጥ ሂደት፤ በዋስ መውጣት፤ በካሳ ክፍያና በመሳሰሉት ፍርድ ቤታዊና ሕጋዊ ጉዳዮች ዙሪያ በነበሩ የሕግ ግንዛቤዎችና አፈጻጸሞች ላይ የተመሠረተና በዚያ እሳቤ የተቃኙ ነበሩ፡፡ በመልካም ሥራ መዳን የሚለው አስተሳሰብም ሆነ በሌላው ጽንፍ የተነሣው ሰው በራሱ መዳን ላይ ምንም ዓይነት ድርሻ የሌለው ታዛቢ ብቻ የሚያደርገውና መዳኑን የሚያውቀው በእምነት ብቻ ነው የሚለው እሳቤ ሁለቱም ስህተት ነበሩ፡፡ የፕሮቴስታንቶች የመዳን ትምህርት *እግዚአብሔር በእኛ ስላደረገውና ስለሚያደርገው (what He does in us)* ሳይሆን *እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገው ነገር (what God has done for us)* ላይ ብቻ የተወሰነና የተገደበ ነበር፡፡

"ክርስቶስ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው ለማን ነው?" የሚል ጥያቄ ካነሡትና ለመመለስ ከሞከሩት መካከልም የካንተርበሪው አንሰለም "መሥዋዕቱን ያቀረበው ለእግዚአብሔር አብ ነው" አለ፡፡ ይህ የክርስቶስ መሥዋዕትነት ለአብ የቀረበ ነው የሚለው የአንሰለም አስተምህሮ እግዚአብሔር ክብሩና ፍትሑ እንደ ተነካበትና ከዚህም የተነሣ እንደ ተቆጣ፣ ለዚህም መካሻና የቁጣው ማብረጃ ይሆን ዘንድ ተገቢውን ዋጋና ክፍያ እንደ ጠየቀ አድርጎ ያሳያል፡፡ ይህ ግን ለእግዚአብሔር የማይገባ አገላለጽና አስተሳሰብ ከመሆኑም በላይ እግዚአብሔር አብ በልጁ ሰው መሆን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለሰው ልጅ መዳን ያደረገውን የአንዲት የቅድስት ሥላሴ ፈቃድ የሚነጣጥልና የሚቃረን እሳቤ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስን በየራሳቸው ለያይቶ የሚያይ ነው፡፡

የቅድስት ሥላሴ ግን ፈቃዳቸው አንዲት ናት፤ "አሐቲ ይእቲ ሥምረቶሙ ለሥላሴ" እንዲል፡፡ ከቅድስት ሥላሴ ውስጥ አንዱን ተቆጪና ሌላውን ደግሞ መሥዋዕት ይዞ ቀራቢና ቁጣ አብራጅ አድርጎ ማቅረብ ተገቢ አስተሳሰብና አገላለጽ አይደለም፡፡ "ወልድ የሞተው የአብን ቁጣ ለማብረድ ነው" የሚለው በኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ ተቀባይነት የለውም፡፡

ኦርቶዶክሳውያን አባቶች ስለ መሥዋዕቱ ተቀባይ ሲናገሩ የቀረበውና የተከፈለው "ስለ እኛ ሁኔታ ከፈለልን" በሚል፤ እንዲሁም በቅዱስ ባስልዮስ አገላለጽ "ራሱን ለሞት ቤዛ አድርጎ ሰጠ"[59] በሚል ነው፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስም "ቃል የተዋሐደውንና ገንዘቡ ያደረገውን ሥጋ ከበደል ንጹሕ የሆነ መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብና ለሞት በመስጠት ሞትን ከወገኖቹ አስወገደ" ብሎ ነው የወልድን ቤዛነት የገለጸው፡፡ በዚህም ራሱን ለሞት አሳልፎ በመስጠቱ ሞት በእኛ ላይ የነበረው ኃይል ተወግዶ የክርስቶስ ሞት ለሙታን የትንሣኤን በር ከፈተ፡፡ ከዚህ ውጭ ግን ኦርቶዶክሳውያን አበው የወልድ መሠዋት የአብን ቁጣ ለማብረድ የግድ መቅረብ የሚገባው ነገር ነበር የሚለውን የስኮላስቲሲዝም መሠረታዊ መነሻና ማጠንጠኛ አስተሳሰባቸውን አይቀበሉትም፡፡ ስለዚህ የክርስቶስ መሥዋዕትነት ሞትንና ኃጢአትን ድል አደረገ እንላለን እንጂ ለአብ የተነካ ክብር መመለሻና ቁጣ ማብረጃ ተከፈለ እንልም፡፡ አብን ተለማኝ (ተማላጅ)፣ ወልድን ደግሞ ማራቸው ባይ (ለማኝ፣ ማላጅ) አድርጎ የማሰቡ ፕሮቴስታንታዊ ባህል ከዚህ ዓይነቱ የተሳሳተ የአስተሳሰብ እርሾ የመነጨ ነው፡፡

ተሐድሶዎች (ፕሮቴስታንቶች) *"መዳን በእምነት ብቻ"* የሚለውን አስተምህሮ እርሾውን ከተለያዩ ሰዎች የወረሱት ነው፡፡ "የሰው ልጅ መልካም ሥራ ለመሥራት ያለው ነጻነት ለመዳን አስፈላጊ ነው" ብሎ ያስተምር ከነበረው ፔላግዮስ ከተባለው ሮማዊ መነኩስ ጋር በነበረው ውዝግብ አውግስጢኖስ ደግሞ ወደ ሌላኛው ጽንፍ ሄደና "የሰው ነጻነት በአዳም ኃጢአት ጨርሶ የተበላሸና የጠፋ ስለሆነ ሰው በራሱ መዳን ውስጥ እንዳችም ድርሻ የለውም" አለ፡፡ ከአውግስጢኖስ (354 - 430 ዓ. ም.) በኋላ የተነሡ አንዳንድ የምዕራብ ቤተ ክርስቲያን ሰዎችም የሰው መዳን የእግዚአብሔር ብቻ ሥራ ነው ብለው ያስተምሩ ነበር፡፡ የትሬንት ጉባኤም የተካሄደው ለዚህ አጸፋታ የሚሆን - ለምሥጢራትና ለመልካም ሥራ ቦታ ለመፈለግ ነበር፡፡ ከኬልቄዶን ጉባኤ ከአንዲቷ ቤተ ክርስቲያን እምነትና አስተምህሮ የተለዩት ካቶሊካውያን በስህተት ጎዳና መጓዛቸውን በመቀጠላቸው አንዱን ስህተት እናስተካክላለን ሲሉ ሌላ ስህተት እየወለዱ፣ እንደገና የእነርሱን ስህተት እናርማለን የሚሉት ተቃዋሚዎቻቸው (ፕሮቴስታንቶች) ደግሞ ሌላ ስህተት እየፈጠሩ አሁንም በዚያው የስህተት አዙሪት ውስጥ ገብተው እየደከሙ ይገኛሉ፡፡

## ኦርቶዶክሳዊው የመዳን ትምህርት ምን ይላል?

ኦርቶዶክሳዊው የመዳን ትምህርት በካቶሊኮችና በፕሮቴስታንቶች መካከል የነበረው ውዝግብና መምታታት አልገጠመውም፤ የውዝግባቸው አካልም አልነበረም፡፡ ሆኖም የስኮላስቲሲዝም ነገረ መለኮታዊ አስተሳሰብና አስተምህሮ፣ እንዲሁም የትሬንት ጉባኤ አንዳንድ ውሳኔዎች በካቶሊክ ሚሲዮናውያን አማካይነት በተወሰነ መልኩ ዘልቀው ሳይገቡ እንዳልቀሩ የሚገልጹ ሰዎች አሉ፡፡[60] ምንም እንኳ ወደ ታች በዝርዝርና በስፋት የምናየው ዋና ጉዳዮችን ቢሆንም ለንጽጽር እንዲረዳ ኦርቶዶክሳዊውን የመዳን ትምህርት ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ እንመለከታለን፡፡

[59] ('He gave himself as a ransom to death')

[60] Coptic Church Review, A Quarterly of Contemporary Patristic Studies, Volume 16, Number 2, Summer 1995

## ኦርቶዶክሳዊ የመዳን ትምህርት፦

በመጀመሪያ ኦርቶዶክሳዊ የመዳን ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስና በቤተ ክርስቲያን ሕይወት (ትውፊት) ያለውን ስለ መዳናችን የተነገረውን አስተምህሮ እንዳለ በመቀበል ላይ እንጂ ይህን ወደ አንድ ዓይነት አሳቤ (Theory) በመጠቅለል አያምንም፣ እንዲህ ለማድረግም አይሞክርም፡፡ ከሐዋርያት ጀምሮ በየዘመናቱ የተነሡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች መዳንን እግዚአብሔር ለእኛ ካደረገው ከቸርነቱ አንጻር ከተለያየ አቅጣጫ ይመለከቱት ነበር እንጂ ወደ አንድ አሳቤ (Theory) ለማስገባትና በዚያ ውስጥ ለመወሰን አይሞክሩም ነበር፤ መዳን ምንም ዓይነት የሰው ልጅ አሳቤ (Human theory) ወይም ሐተታ ሊገልጸውም ሆነ ሊወስነው የማይችል ጥልቅና ረቂቅ አምላካዊ ድርጊት ነውና፡፡

ኦርቶዶክሳውያን አበው በመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለጸው አንጻር ክርስቶስን እንደ ዳግማዊ አዳም፣ ድል አድራጊ፣ መምህር፣ መሥዋዕት፣ ሊቀ ካህናት ያዩት ነበር፡፡ ሆኖም ግን ምንም ዓይነት አገላለጽ ቢጠቀሙም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌላቸውን ፍልስፍናዊ መንገዶችና ንድፈ ሐሳቦች ላለመጠቀም ይጠነቀቁ ነበር፡፡ ከእነ መርቅያን፣ አርዮስና መምህሮቻቸው ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን ራስ ምታት ሲሆኑ የኖሩት መናፍቃን የእግዚአብሔርን የቸርነት ሥራ በፍልስፍናና በሰው አስተሳሰብ ለመወሰንና ለዚያ ተገዢ ለማድረግ ፍልስፍናዊ አሳቤዎችን በልካቸው ሠርተው ነገረ መለኮታዊውን ድርጊት እዚያ ውስጥ እያስገቡ ለመተንተን መሞከራቸው ነበር፡፡ ይህም ማለት አጽሙን ፍልስፍናዊ አድርገው ያዘጋጁና መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እውነታ አስቀድሞ ላዘጋጁት አጽም ሥጋ ማልበሻ ያደርጉት ነበር፡፡ ኦርቶዶክሳዊ አባቶች ደግሞ መነሻቸውም መድረሻቸውም ራሱ መጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነታ እንጂ ፍልስፍናዊም ሆነ ሥነ ሕግ የሆነው ውጫዊ ልማድና አስተሳሰብ አልነበረም፡፡ የእነ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ተጋድሎም ቤተ ክርስቲያንን ከእንደዚያ ዓይነት ባዕድ ልብ ወለዳዊ አካሄድ ነጻ ማውጣትና ወደ ሐዋርያዊነቷ መመለስ ነበር፡፡ ለዚህ ነው እርሱም "ሐዋርያዊ" የተባለው፡፡

### የኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን የመዳን አስተምህሮ ዋና ዋና ነጥቦች

1. መዳናችንን ክርስቶስ በሥጋዌው በመላ የፈጸመው የእርሱ የማዳን ሥራ ነው እንጂ በመስቀሉ ላይና በዕለተ ዓርብ ድርጊት ዙሪያ ላይ ብቻ የሚወሰን አይደለም፡፡ ለመዳናችን በአባቱ ዕቅፍ ከነበረበት ጀምሮ እስከ ልደቱ፣ ስደቱ፣ ጥምቀቱ፣ መጾሙ፣ ማስተማሩ፣ ተአምራት ማድረጉ፣ ስቅለቱ፣ ሕማማቱ፣ ትንሣኤው፣ ዕርገቱ እና ዳግም ምጽአቱ ሁሉ እንጂ ዕለተ ዓርብና ስቅለቱ ብቻ አይደለም፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ በትምህርቱ የክርስቶስ መላ ሕይወቱ በሙሉ መዳንን ያስገኘልን መሆኑን በአጽንኦት ይገልጻል፡፡ (በእንተ ተሠግዎተ ቃል)

2. መዳን ለክርስቶስ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የአብና የመንፈስ ቅዱስም ሥራ ነው፡፡ የእኛ መዳን ክርስቶስ ሊፈጽመው የመጣው የሰማያዊ አባቱ ፈቃድ ነው (ዮሐ. 4:34 ፤ 5:30 ፤ 6:38; ዕብ. 1:1 ፤ 3:1-6 ፤ 5:4 ፤ 8:2 ፤ 10:5-9)፡፡ እግዚአብሔር አብ በዚህ በመዳናችን መፈጸም ላይ ሕያው የሆነ ሚና አለው (ሉቃ. 23:46 ፤ የሐዋ. 3:26 ፤ ዕብ. 13:20)፡፡ የወልድ ተግባር ከሰማያት ወርዶ የሰውን ባሕርይ ተዋሕዶ መዳናችንን መፈጸምና ወደ አባቱ መመለስ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ አማኒው ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ይሆንና ይዋሐድ ዘንድ ይቀድሰውና ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት እንዲያድግ ይረዳው ዘንድ ከአማኒው ጋር ይኖራል፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ የተገኘው መቀደስ ከመዳን ሊለይ አይችልም፡፡

መንፈስ ቅዱስ በሰው ልጅ ላይ የኖረው ከክርስቶስ ዕርገት በኋላ ነው፤ ጌታችን "እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና" እንዳለ፡፡ ዮሐ. 16፡7 ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ በአርዮሳውያን ላይ በጻፈው ድርሳኑ በዚሁ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ሚና የእርስ በርስ ተመጋግቦት ላይ እንዲህ ሲል ያብራራል፡- "እኛ መንፈስ ቅዱስን እንቀበል ዘንድ ቃል ሥጋችንን ገንዘቡ አደረገው፡፡ የክርስቶስን የማዳን ተግባር ለእያንዳንዳችን የሚፈጽመውና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትና ሱታፌ ይኖረን ዘንድ የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ " ስለዚህ መዳናችን የእግዚአብሔር አብ፣ የእግዚአብሔር ወልድና የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ - የአንድ አምላክ የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድና ስጦታ ነው እንጂ የወልድ ብቻ ተደርጎ ተነጥሎ አይታይም፡፡

3. *መዳን ከኃጢአት ይቅርታ* ባሻገር ብዙ ነገሮችን የያዘ ሰፊና ጥልቅ ነገር ነው፡፡ ስለዚህም አንደኛውንና የመጀመሪያውን ሥጦታ (የኃጢአትን ይቅርት ማግኘትን) ብቻ ሌላውን እስከሚያስረሳ ድረስ ማጉላትና ከዚያ ያለፈ ነገር የሌለ ማስመሰል እግዚአብሔር የሰጠውን ጸጋ ማሳነስና የተጠራንበትን ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን ጥሪ ማስረሳት ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱሳዊውና በአበው ቀደምት አስተምህሮ መሠረት መዳን ስንል ሥርየተ ኃጢአት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን ማወቅን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማግኘትን፣ ብርሃናዊነትን ገንዘብ ማድረግን፣ ከባርነት ነጻ መውጣትን፣ አዲስ ተፈጥሮንና የጸጋ አምላክነትን ገንዘብ ማድረግን ሁሉ የሚጨምር ሰፊና ጥልቅ ነው፡፡

እነዚህ እንዲህ ለያይተን የምንገልጻቸውም በመዳን ያገኘነውን ብዙና ሰፊ ጸጋ በእያንዳንዳቸው አማካይነት ለመረዳትና ለመግለጽ እንዲረዳ በእኛ በሰዎች አረዳድና አገላለጽ ለመተንተን ነው እንጂ ሁሉም እርስ በርስ የተመጋገቡና የተያያዙ ናቸው፡፡ ሌሎቹ እንደሚያደርጉት መነሻንም ሆነ መድረሻን ኃጢአትና ኃጢአት ላይ ብቻ ከማድረግና በዚህ ላይ ከመጠን ያለፈ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ ኦርቶዶክሳዊው የመዳን ትምህርት የእግዚአብሔር ፍቅር ላይ እና ለሰው በተሰጠው በጸጋ እግዚአብሔር እያደገና እየበለጸገ የመሄድ ክሂሎ ክዊን (Potential)[61] ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ቅዱሳን አባቶቻችን ከሐዋርያው ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር "መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን" ወዳለው ታላቅ ነገር አርቀው ይመለከታሉ፡፡ 2 ቆሮ. 3፡18

4. እያንዳንዱ ሰው መዳንን ለራሱ ገንዘብ የሚያደርገው እንዴት ነው? በሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ላይም ኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ ከፕሮቴስታንቱ ፈጽሞ የተለየ ነው፡፡ እግዚአብሔር በአካላዊ ቃል ሰው መሆን ለሁሉም ሰው የሰጠውን መዳን እያንዳንዱ ሰው በራሱ ሕይወት ገንዘብ የሚያደርገው እንዴት ነው? ለሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ፕሮቴስታንቶች መዳን በእምነት ብቻ የሚገኝ ነው ሲሉ ኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን ግን የጸጋው ሥጦታ ነጻ (እንዲሁ) የሚሰጥ መሆኑን በአንድ በኩል፣ የሰውን ነጻ ፈቃድ (ነጻነት) ደግሞ በሌላ በኩል አስተባብረው በመያዝ ለሰው መዳን የሁለቱ መስተጋብር (በግሪኩ *Synergy*) አስፈላጊ መሆኑን በአጽንኦት ያስተምራሉ፡፡ ይህም በቅዱስ ጳውሎስ "ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና" ተብሎ የተገለጸው ነው፡፡ 1 ቆሮ. 3፡9

[61] ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት አባቶቻችን ትምህርት የሰው ልጅ በጸጋ እግዚአብሔር እያደገ ለመሄድ የሚችል የመሆኑን ነገር በተመለከተ ሲገልጹ የተጠቀሙበትን Potential - የሚለውን ቃል "ክሂሎ ክዊን" በሚል ቃል ተርጉሜዋለሁ። ይህም የቃሉን ሃሳብ በተሻለ ይገልጸዋል ብዬ ስላሰብሁ ነው።

ስለዚህ መዳን በአንድ በኩል በሰው ጥረትና ችሎታ ያልተገኘ የእግዚአብሔር ጸጋ (ስጦታ) ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሰው ያለ ራሱ ፈቃድና ሱታፌ እንዲሁ ከውጭ የሚጫንበት "ሸክም" ወይም "ግዴታ" ሳይሆን ራሱ ወድዶና ፈቅዶ ገንዘብ የሚያደርገው ጸጋ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር የሰጠውን መዳን የራሱ ሕይወት የሚያደርግበት መንገድ እንዲሁ የሆነውን ነገር በመቀበል ብቻ (እምነት ብቻ የሚሉት) ሳይሆን ከዚያም ባለፈ መንገድ ነው፡፡ መዳንም ሥርየተ ኃጢአት ብቻ ሳይሆን ከዚያ በላይ ብዙ ነገሮችን የሚይዝ ጥልቅ ጸጋና ሀብት ነው፡፡ ይህን ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ክፍሎች በመጠኑ ሰፋ አድርገን ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡

እዚህ ላይ ከጥንት ጀምሮ የነበረውን የመዳን ትምህርት ታሪካዊ ሂደት መዳሰስ የተፈለገው አንደኛ ስለ መዳን ትምህርት ሊሎች የሚሉት ምን እንደ ሆነና ያም በምን ዓይነት ድባብና ባህል የተፈጠረ እንደ ሆነ መጠነኛ ግንዛቤ እንዲኖር ይረዳል ከሚል ሲሆን፣ ሁለተኛ ደግሞ በእኛ አገር አሁን እለን እያሉ ያሉት ተሐድሶዎች ስለ መዳን የሚያስተምሩት ትምህርት ምንጩ ከየት እንደ ሆነ ግልጽ እንዲሆንና እነርሱ እንደሚሉት እርቶዶክሳዊ ናቸው? ወይስ ፕሮቴስታንታዊ? የሚለውን ለመረዳት እንዲያግዝ በማሰብ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## ኦርቶዶክሳዊ የመዳን ትምህርት (ነገረ ድኅነት)

### መግቢያ

የቤተ ክርስቲያን መሠረቷና ሀብቷ በእግዚአብሔር የተሰጣት ሃይማኖት ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ አካላት ሆነው የተሠሩትንና በመሠራት ላይ ያሉትን ምእመናን አንድ የሚያደርጋቸው ይህ ሃይማኖት ሲሆን አንድነታቸው የሚገለጠው ደግሞ በሱታፌ ምሥጢራት አማካይነት ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከተሰጣት ሃይማኖት ደግሞ ነገረ ድኅነት ከኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ ሥጋዌ ጋር መሠረቷና ጉልላቷ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንን ከሌሎች የእምነት ድርጅቶች በዋናነት የሚለያት የመዳን ትምህርቷ ነው፡፡ የመናፍቃንን ትምህርት የማትቀበለውም የመዳን ትምህርታቸው የተሳሳተና እግዚአብሔር የሰጠንን የመዳን ጸጋ ለማግኘት የማያስችል የስህተትና የጥፋት መንገድ ስለሆነ ነው፡፡

መዳን የሚለው ቃል እንደ አገባቡ የተለያየ መልእክት ወይም ትርጉም ሊኖረው ይችላል፡፡ ለምሳሌ ያህል መዳን የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተለያዩ ዓይነት ችግሮችና ጥፋቶች ስለ መዳንና ነጻ ስለ መሆን ተነግሮ እናገኛለን፡፡ ለምሳሌም፡- ኖኅ ከጥፋት ውኃ መዳኑ (ዘፍ. 6-9)፣ ሎጥ በሰዶምና በገሞራ ላይ ከደረሰው የእሳትና የዲን ቃጠሎ መዳኑ (ዘፍ. 19)፣ ያዕቆብና ልጆቹ ዮሴፍ አስቀድሞ ወደ ግብጽ በመሄዱ ምክንያት በዘመኑ ከነበረው ከባድ ረሃብ መዳናቸው፣ ንዕማን ሶርያዊ ከነበረበት ለምጽ በዮርዳኖስ ወንዝ ታጥቦ መዳኑ፣ ሕዝበ አይሁድ ከሐማ ተንኮል በአስቴርና በመርዶክዮስ ምክር ለሦስት ቀናት ባደረጉት ጾምና ጸሎት መዳናቸው፣ እስራኤላውያን በሙሴ መሪነት ከግብጽ ባርነት ነጻ መውጣታቸውና ከሞተ በኩር መዳናቸው፣ የሶርያ ንጉሥ ወልደ አዴር ከበሽታው መዳኑ (2 ነገ. 8፡7-10)፣ ደቀ መዛሙርቱ በባሕር ላይ ሲጓዙ ሳለ ኃይለኛ ማዕበል በተነሣባቸው ጊዜ "አድኅነነ ከመ ኢንሙት - ጌታ ሆይ አድነን" ብለው መጮኻቸውና ጌታም ማዕበሉን ጸጥ አድርጎ እነርሱን ከጭንቀትና ከጥፋት ማዳኑ (ማቴ. 8፡23-27)፣ ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮም ታስሮ በመርከብ ሲወሰድ ሳለ አብረውት ከነበሩት ሰዎች ጋር ከደረሰባቸው ከባድ አደጋ መዳናቸው (የሐዋ. 27፡31)፣ በአጠቃላይ ከተለያዩ ክፉ ነገሮች መዳን (2 ጢሞ. 4፡18)፤ እነዚህ ሁሉ "መዳን" ተብለው ተገልጸዋል፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌው ከልዩ ልዩ ዓይነት ደዌና ችግር ያዳናቸውና የፈወሳቸው ብዙ ሰዎች ነበሩ፡፡ እነዚህ ሁሉ ከየችግሮቻቸው በጌታችን ቸርነት ተፈውሰዋል፣ ድነዋል፡፡

ሆኖም በነገረ ድኅነት ትምህርት "መዳን" ስንል እነዚህንና መሰሎቻቸውን ማለታችን አይደለም፡፡ እነዚህ ከላይ የተገለጹት ዓይነት መዳኖች ለጊዜው ሲደረጉ መልካምና ጠቃሚ መሆናቸው ባይዘነጋም ነገር ግን ጊዜያዊና በዚህ ዓለም ተወስነው የሚቀሩ ነገሮች ናቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች በአብዛኛው "ፈውስ" ተብለው የሚጠሩ ናቸው፡፡ በነገረ ድኅነት ትምህርት "መዳን" ስንል ግን የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በማፍረሱ ምክንያት የደረሱበትን ተደራራቢ ውድቀቶች፣ ቅጣቶች፣ ከጸጋ መራቆቶችና የባሕርይ መጎሳቆሎች እና ኋላም በእግዚአብሔር ልዩ ምክር በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋዌ በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠውን መዳን ማለታችን ነው፡፡

የመዳን ትምህርት ከትምህርቶች ሁሉ ዋናውና የመጀመሪያው ነው፡፡ ምክንያቱም የክርስትና ሃይማኖት የመዳን ሃይማኖት ስለሆነ ነው፡፡ ከዚሁም ጋር የሰው ልጅ ዘለዓለማዊ ሕይወቱን በተመለከተ የማያቋርጥ ውሳጣዊ ፍለጋና ሕሊናዊ ጥያቄ ያለበት በመሆኑ በመጀመሪያ ሊመልስለትና ሕሊናውን ሊያሳርፍበት የሚገባው ጉዳይም ይኸ በመሆኑ ነው፡፡ የሰው ልጅ የሚኖረው በዚህ ዓለም ላለው ለጥቂቱ ዘመን ብቻ ሳይሆን ከዘመን ውጭ ለሆነው ዘለዓለማዊነት ስለሆንና ሊሆንም ስለሚገባው ነው፡፡ የመዳን ትምህርት (ነገረ ድኅነት) እንዲህ የመኖራችን ዓላማና የክርስትና ምንነትና መሠረት ስለሆነ የትምህርት ሁሉ መዓዝን ነው፡፡ አስተምህሮዎችና አስተሳሰቦች ሁሉ የሚመዘኑትና የሚለኩት በነገረ ድኅነት መለኪያነትና ሚዛንነት ነው፡፡ የመናፍቃን ኑፋቄም ኑፋቄነቱና ጎጂነቱ ግልጽ ሆኖ የሚታየውና ስህተትነቱ የሚጋለጠው በነገረ ድኅነት ሚዛንነት ሲመዘን ቀልሎ ስለሚገኝ ነው፡፡ ስለሆነም ነገረ ድኅነት የአስተምህሮዎችና የአስተሳሰቦች ሁሉ ማንጠሪያና መለኪያ ነው፡፡

## 3.1 መዳን ለምን አስፈለገ?

አንድ ነገር "መዳን" ያስፈልገዋል ሲባል በችግር ላይ የነበረና መዳንን ግና ያላገኘ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለ ሰው ልጅ መዳን ስንናገርም ከሁሉ አስቀድሞ መዳን ለምን አስፈለገው? የሚድነውስ ከምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ማንሣት የግድ ይሆናል፡፡ ሰው ለምን መዳን አስፈለገው? ሲባል መልሱ ሰው በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን እምነት ትቶ ዲያብሎስን አምኖ ሕገ እግዚአብሔርን አፍርሶ ትእዛዙን ጥሶ የተሰጠውን ሕይወት፣ ጸጋና ክብር በራሱ ጥፋት በማጣቱና ከሕይወት ወደ ሞት፣ ከክብር ወደ ኃሳር ወርዶ የነበረ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ለሌሎች ፍጥረታት ያላደረገውን ልዩ ነገር በማድረግ፣ ይኸውም "ንግበር ሰብአ በአርአያ ወበአምሳሊነ - ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" በማለት በራሱ መልክና ምሳሌ ፈጠረው፡፡ እንዲሁም ሰውን በሕያዊት ነፍስ አክብሮ፣ ነጻነት ያለው፣ ክፋውንና በጎውን መለየትና መምረጥ የሚችል፣ አዋቂና አስተዋይ አድርጎ ፈጠረው፡፡ ለዚህም ይረዳው ዘንድ ክፉ እውቀትን ወደ ማወቅ እንዳይሄድና የሚኖረው እውቀት ምን ጊዜም መልካም የሆነ፣ የማይጎዳና የማያስጸጽት ብቻ ይሆንለት ዘንድ "*ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና*" በማለት አዘዘው፡፡ ይህ የሕግ ምልክትም የሰው ልጅ ለፈጣሪው ያለውን ፍቅሩን ይገልጽበት ዘንድ የተሰጠው መንገድ ነበር፡፡ ዘፍ. 2፡16-17 ሆኖም የሰው ልጅ ይኸን ሁሉ ቸርነት ካደረገለት ከእግዚአብሔር ይልቅ ምንም ነገር ያላደረገለትንና ባዶ የሆነ የቃል ተስፋ ብቻ ይዞ የመጣውን ዲያብሎስን በማመን በፈጣሪው በእግዚአብሔር ላይ በማመጽ አምላኩን ካደ፤ በፈጣሪው ላይ ላለው እምነትና ፍቅር መግለጫ የነበረውን ምልክትም አፈረሰ፡፡

የአዳም የመጀመሪያውና ዋናው ኃጢአቱ (በደሉ) ቅጠል ቆርጦ መብላቱና አለመታዘዙ ሳይሆን እግዚአብሔርን አለማመኑ ነበር፡፡ አለመታዘዙ የመጣው ካለማመኑ ነበር፤ ማለትም አዳምን የፈጣሪውን ትእዛዝ ወደ መጣስና ሕጉን ወደ ማፍረስ የወሰደው በእግዚአብሔር ላይ የነበረው እምነት በዲያብሎስ ስብከት ከተለወጠ በኋላ ነበር፡፡ ከመነገር በላይ የሆነውን መልካሙን ሁሉ ያደረገለትን፣ እንዲሁም ለራሱ ሲል "ከዚህ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና እንዳትበላ" ብሎ ያስጠነቀቀውን እግዚአብሔርን ተጠራጠረው፣ ካደው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ምንም መልካም ነገር ያላደረገለትን ዲያብሎስን አመነው፡፡ ዲያብሎስ "ሞትን አትሞቱም፣ ከእርሷ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ፣ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ" በማለት እግዚአብሔርን ክፉ፤ ራሱን ደግሞ አዛኝና ተቆርቋሪ አስመስሎ ሲሰብካቸው በአንድ ጊዜ ግልብጥ ብለው እግዚአብሔርን ተጠራጠሩት፣ ዲያብሎስን ግን አመኑት፡፡ ዘፍ. 3፡4-5

አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ላይ የነበራቸው እምነት ሰለ ጠፋ ፤ አለማመናቸው ሕጉን በማፍረስ ተገለጠ፡፡ የሕግ ምልክት፣ የሃይማኖት ምልክት፣ የሰው መታመን ወካይ ዓርማ የነበረችውን ዛፍ ፍሬዋን ቆርጠው በሉ፡፡ ዲያብሎስን ደግሞ የነገራቸውን በመፈጸም በእርሱ ሰብከት ላይ ያላቸውን እምነት ለእርሱ በመታዘዝና እንዳስተማራቸው ቅጠሏን በመብላት ገለጹ፡፡ በምዕራባውያን አስተምህሮ በአብዛኛው የመጀመሪያው በደል (ኃጢአት) የሚሉት *አለመታዘዝ* (Disobedience) ሲሆን በምሥራቃውያን (በኦርቶዶክሳውያን) አስተምህሮ ግን የመጀመሪያው በደል አለማመን፣ ሕጸተ ሃይማኖት (Disbelief) ነው፡፡ አለመታዘዝ ያለማመን መገለጫና ውጤት ነው፡፡

የሰው ልጅ ፈጣሪውን ማመን ትቶ ዲያብሎስን ባመነ ጊዜና ፈጣሪውን መካዱንም የእምነት ምልክት የነበረችውን ዛፍ ቆርጦ በመብላት ከሐልዮ ወደ ግቢር በማሳደግ በተግባር ባረጋገጠ ጊዜ በዚያው ቅጽበት ከዚያ በፊት በባሕርዩ አብሮት ያልነበረ (ያልተፈጠረበት)፣ ነገር ግን በኃጢአቱ ምክንያት የሕይወት ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር የመለየቱ ውጤት የሆኑ ብዙ ተደራራቢ ነገሮች ደረሱበት፡፡ እነዚህም በዋናነት የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ሞት፣ ሟችነት

ሰው የተፈጠረው ለሕይወት እንጂ ለሞት አልነበረም፡፡ ሆኖም ሰው ሲፈጠር እንደ መላእክት ከመጀመሪያው የማይሞት ተደርጎ አልተፈጠረም፤ ነገር ግን ሕጉን ቢጠብቅ በሕይወት ሲኖር፣ ባይጠብቅ ደግሞ ሊሞት እንዲችል አድርጎ በማዕከላዊ ሁኔታ ነበር እግዚአብሔር የፈጠረው፡፡ ማለትም ወደ ወደደው መንገዝ ይችል ዘንድ በመሞቲነትና በኢመሞቲነት መካከል አድርጎ ፈጠረው፡ ፡ ሕጉን ለተወሰነ ጊዜ (እግዚአብሔር ለሚያውቀው ጊዜ) ቢጠብቅ ወደ ኢመሞቲነት ሊሸጋገር፣ ባይጠብቅ ደግሞ ወደ መሞቲነት ሊወርድ በሙሉ ነጻነት ተፈጠረ፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ቸርነት ነበር፡፡ ምክንያቱም ገና ከመጀመሪያው ኢመዋቲ (ለምሳሌ እንደ መላእክት የማይሞት) ተደርጎ ተፈጥሮ ቢሆን ኖሮ አንደኛ ሊሞት የሚችል ሆኖ ተፈጥሮ እያለ እንኳ እንደዚያ በእግዚአብሔር ላይ የሚያምጽና የሚክድ ከሆነ ከመጀመሪያውኑ የማይሞት ተደርጎ ቢፈጠር ኖሮ ምን ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ከባድ ነው፡፡ *ሁለተኛ* ደግሞ ከመጀመሪያው ኢመዋቲ ሆኖ ተፈጥሮ ቢሆን ኖሮ ኃጢአት ሲሠራ ኃጢአቱ ከባሕርዩ ጋር ተጣብቆ ለዘለዓለም የባሕርዩ አካል ሆኖ ስለሚኖር "የማይሞት ምውት" ሆኖ ይኖር ነበር፡፡ ይህም ባሕርዩ ጎስቋሎ እንደ ኢጋንንት መጨረሻ የሌለው ሞት በሆነበት ነበር፡፡

እግዚአብሔር አዳም ከበደለ በኋላ ከዕፀ ሕይወት እንዳይበላ የከለከለውና ወደዚያ የሚወስደውን መንገድ በመላእክት ያስጠበቀበትም ለዚህ ነበር፤ እንዲህ ሲል፡-

> እግዚአብሔር አምላክም አለ፡- እነሆ አዳም መልካሙንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤ አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ፥ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፥ ለዘላለምም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ ከዔድን ገነት አስወጣው፥ የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ። አዳምንም አስወጣው፥ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በዔድን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ። ዘፍ. 3፡22-24

ሰው መሞት የሚችል ሆኖ በመፈጠሩ ወደ ባሕርዩ ውስጥ ዘልቆ የገባው ኃጢአት የባሕርዩ ዘለዓለማዊ አካል ሳይሆን ከእርሱ የሚወገድበትን መንገድ - ሞትን - አዘጋጀለት፡፡ በበደለ ጊዜ በሰው ላይ ሞትን ማዘዙ በራሱ የእግዚአብሔር የቸርነቱ ሥራ ነበር፡፡ በዚህም ወደ ውስጣችን ዘልቆ የገባው ኃጢአት በሞት ከእኛ ይለያል፤ እግዚአብሔር የፈጠረውና በሐዲስ ተፈጥሮ ያከበረው ሰውነታችን ደግሞ በትንሣኤ በክብር ይነሣል፡፡ እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ኢመዋቲ ያላደረገን በዚህ ቸርነቱ ምክንያት ነበር፡፡ ሆኖም ግን በመጀመሪያ የተሰጠንን ዕድል - ኢመዋቲነትን - ገንዘብ ማድረግ እንችል ዘንድ የሕግን ምልክትነት ሰጠን፡፡ ሆኖም ግን ያን የተሰጠንን መንገድ ራሳችን አበላሽነው፣ ሳንጠቀምበትም ቀረን፡፡

ስለሆነም አባታችን አዳም "በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ" ተብሎ የተነገረውን ማስጠንቀቂያ በማፍረሱ ምክንያት እንዳይደርስበት ይጠነቀቅ ዘንድ አስቀድሞ የተነገረው ሞት በተግባር ደረሰበት፣ ተፈጸመበት፡፡ ከዚያን ጊዜ እንሥቶ ሞት የሰውን ልጆች አንድም ሳያስቀር ቀጥቅጦ ገዛ፡ በሰው ላይ ሠለጠነ፤ "ሞት ነገሠ" ተብሎ እንደ ተገለጸ፡፡ ሮሜ 5፡14 ከእግዚአብሔር የመለየቱን መንፈሳዊ ሞት ራሱ አዳም፣ የነፍስና የሥጋውን የመለየት ሞት ደግሞ ልጁ አቤል በመጀመሪያ ገፈቱን ቀመሱት፡፡ ሞትም ወደ ባሕርያችን ውስጥ ዘልቆ ገባ፤ ከአጥንታችን፣ ከደማችን፣ ከሕዋሳታችንና በአጠቃላይ ከሁለንተናችን ጋር ተዋሐደ፡፡ የሰው ሕይወት በሞት ተዋጠ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰው ኑሮው በራሱ ወደ ሞት የሚደረግ ጉዞ ሆነ፤ ይጠለሻል፣ ያድጋል፣ ያረጃል፣ ከዚያም ይሞታል፡፡ ይህ የሕይወት ሂደት በኃጢአት ምክንያት የመጣ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረም፣ ሞት የኃጢአት ውጤት ብቻ ነው፤ ያን ጎትተን ያመጣነውም እኛው ሰዎች ራሳችን ነን፡፡ ለምሳሌ ብርሃን በነበረበት ስፍራ ላይ ብርሃኑን ሲሰጥ የነበረውን መብራት ቢያጠፉት ጨለማ እንደሚሰፍነው ዓይነት ማለት ነው፡፡ ሐዋርያው ሞትን "የኋለኛው ጠላት" ብሎ የገለጸው ለዚህ ነው፤ ከሰው ተፈጥሮ በኋላ የመጣ በሽታ ስለሆነ፡፡ 1 ቆሮ. 15፡26

## 2. የባሕርይ መጎስቆል ደረሰበት

የሰው ባሕርይ እጅግ ግሩም በሆነ ሁኔታ በክብር የተፈጠረ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ፀሙን ሲፈጥረው ብርሃን አልብሶ በጸጋ አጎናጽፎ በአርአያውና በምሳሌው አስውቦና አክብሮ እንደ ፀሐይ በሚያበራ ብርሃናዊ ጸዳል ይህ ቀረው በማይባል ክብርና ጸጋ ነበር፡፡ ነገር ግን ሕጉን በማፍረሱ ምክንያት ባሕርዩ ጎሰቆለ፣ ተዋረደ፡፡ ጸጋውን ተገፍፎ ራቁቱን ሆኖ ቅጠል ለፍቶ አገለደመ፣ ቁርበት ለበሰ፡፡ ክብሩን በማጣቱ ምክንያት ከእርሱ ላነሱ ሥነ ፍጥረቶች ተገዛ፣ እነርሱን መፍራትና ማምለክም ጀመረ፡፡ "ሰብእሰ እንዘ ክቡር ውእቱ ኢያእመረ ወኮነ ከመ እንስሳ ዘአልቦ ልብ ወተመሰሎሙ - ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አላወቀም፣ አእምሮ እንደ ሌላቸው እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ" እንደ ተባለው ሆነ፡፡ መዝ. 48፡12

በሰውነቱ ላይም እርሱ ለእግዚአብሔር እንዳልታዘዘ ሁሉ ራሱ ለራሱ አልገዛለት አለ፣ የሚፈልገውን መልካም ነገር ትቶ የማይፈልገውን ክፉ ነገር ወደ ማድረግ የሚሳብና የሚሸነፍ ሆነ፡፡ ለእርሱም የማይታዘዙና የማይገዙ ክፉ ፈቃዳትና እኩያት ፍትወታት በውስጡ ሠለጠኑበት፣ አስጨነቁትም፡፡

## 3. ስደተኛ ሆነ

ከቦታው ከገነት ተባረረ፣ የራሱ ኃጢአት አሳደደው፡፡ ቀድሞ የደስታው ምንጭ የነበረው የእግዚአብሔር ድምጽ አሁን ግን አስፈራው፡፡ ስለዚህም ከእግዚአብሔር ሸሸ፣ ለመሸሸግም ሞከረ፡፡ እግዚአብሔር "ወዴት ነህ?" ብሎ በጠራውና በፈለገው ጊዜ "በገነት ድምፅህን ሰማሁ፣ ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፤ ተሸሸግሁም" በማለት እጅግ አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ መለሰ፡፡ ዘፍ. 3፡9-10 እግዚአብሔርም የበደለውን አዳምን ቀናና በመስጠት ከገነት አስወጣው፡፡ "እግዚአብሔር አምላክ ከዔድን ገነት አስወጣው፣ የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ። አዳምንም አስወጣው፣ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በዔድን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ።" ዘፍ. 3፡23-24 ስለዚህም ግዞተኛ ሆኖ ወደ ምድር ተጣለ፡፡

4. ሰላም አጣ፣ ተጨነቀ

የሰው ልጅ የሰላም አምላክ ከሆነው ከእግዚአብሔር በመለየቱ ምክንያት የሚፈራ፣ የሚደነግጥ፣ የሚጨነቅ፣ የሚታወክ ሆነ፡፡ ከመበደሉ በፊት የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት የደስታው ምንጭ ነበር፡፡ "ኃጥእን ሰው ኃጢአቱ ታጠምደዋለች፥ በኃጢአቱም ገመድ ይታሰራል" እንደ ተባለ ሰውን ኃጢአቱ አጠመደው፣ አሰረውም፡፡ ምሳ. 5፥22 የእግዚአብሔርን ድምፅ በሰላም መስማት አልቻለም፣ ድምፁን ሲሰማ ሥራው ትዝ እያለው ይፈራና ይሸሽ ጀመር፡፡ "ለክፉዎች ሰላም የላቸውም" እንደ ተባለ የራሱ ክፋት ሰላሙን አሳጣው፡፡ ኢሳ. 48፥22

5. መንፈሳዊ እድገቱ ተቋረጠ፣ መቋረጥ ብቻም ሳይሆን ጉዞው በተቃራኒ አቅጣጫ ሆነ፡፡

ሰው ሲፈጠር በቅድስናና በጸጋ እያደገ መሄድ እንዲችል ሆኖ ነበር የተፈጠረው፡፡ ከውድቀቱ በኋላ ግን እንደ ተነቀለ ችግኝ ያ ዕድገቱ ተቋረጠ፡፡ መልካም የሆነው የመንፈሳዊ ሕይወቱ ዕድገት መቋረጥ ብቻም ሳይሆን የሕይወቱ አቅጣጫ የሚጓዘው በተቃራኒ አቅጣጫ ሆነ፡፡ ሕይወቱ ወደ ተቃራኒ የጥፋት አቅጣጫ (ወደ አለ መኖርና ወደ ጥፋት አቅጣጫ) መውረድ ጀመረ፡፡ ሂደቱ ከመከራ ወደ መከራ፣ ከውርደት ወደ ውርደት ሆነ፡፡

6. በአጠቃላይ እግዚአብሔር ሲፈጥረው ያዘጋጀለትን ጸጋና ክብር በሙሉ አጣ፡፡

የእግዚአብሔር ልጅነት ጸጋ ሆኖ ተሰጥቶት የነበረው የሰው ልጅ በኃጢአቱ ምክንያት ያ ጸጋ አጥቶ የዲያብሎስ ባርያ የኃጢአት መናኸሪያ ሆ፡፡ በዚህ ዓለም በተሰጠችው ዕድሜ ሲኖርም ሆነ ከሞት በኋላ ሕይወቱ አሳዛኝና ከጥፋት ወደ ጥፋት የሚሸጋገር ሆነ፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ ከዚህ ሁሉ ኃጢአት ካመጣው ፅዳና መከራ የሚያድነው መድኃኒት በእጅጉ ያስፈልገው ነበር፡፡ መፈጠሩና መኖሩ ፅዳ ሆኖበት ሲጨነቅና ሲቃትት ነበር፡፡ በዘመነ ብሉይ የነበሩ ወገኖቻችን ይኸን ፅዳ ተሸክመው መዳንን በመናፈቅና ተስፋ በማድረግ ነበር ወደ መቃብር የወረዱት፡፡

እነ ዳዊት "ወዓዲ በተስፋሁ ኀደረ ሥጋየ እስመ ኢተኃድጋ ውስተ ሲኦል ለነፍስየ - ነፍሴን በሲኦል ውስጥ አትተዋትምና ሥጋየ በተስፋ አደረ" እያሉ በተስፋ ሞቱ፡፡ መዝ. 15፥9-10 ሌሎችም አበውና ነቢያት የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ እያደረጉ ኖሩ፡፡ ሲጠበቅ የነበረውን ተስፋ ሰው ሆኖ የፈጸመው ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው ሲያስተምር *"አብርሃም አቡክሙ ተመነየ ይርአይ ዕለትየ ርእየ ወተፈሥሐ - አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ፥ አየም ደስም አለው"* በማለት የተናገረው አብርሃምና ሌሎችም ነቢያት አካላዊ ቃል ሰው ሆኖ የሚገለጥባትንና የሚያድንባትን የተመረጠች ዕለት በናፍቆት ሲጠብቁ የነበረ መሆኑን በግልጽ የሚያስረዳ ነው፡፡ ዮሐ. 8፥56 ያች የተመረጠች ዘመን ቶሎ ትደርስ ዘንድ ናፍቆታቸውንና ጉጉታቸውንም "ኦ እግዚኦ አድኅነሶ - አቤቱ እባክህ አሁን አድን፣ ኦ እግዚኦ ሠርሕሶ - አቤቱ እባክህ አሁን አቅና" እያሉ አጥብቀው ደጅ ጸኑ፡፡ መዝ. 117፥25

እግዚአብሔርም በፈታሒነቱ በሰው ላይ ቢፈርድበትም በቸርነቱ ደግሞ እንደሚያድነው ወዲያውኑ ገና እንደ በደለና ከእርሱ እንደ ተለየ የሚድንበትን መንገድ ነግሮታል፡፡ እንዲህ በማለት ተስፋውን አስጨብጦታል፤ *"በአንተና በሴቲቱ መካከል፣ በዘርህና በዘሯም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፡፡ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ"* ዘፍ. 3፥15 "የሴቲቱ ዘር" የተባለው ያለ አባት ከእርሷ (ከቅድስት ድንግል ማርያም) ይወለድ ዘንድ ያለው ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱ የዘንዶውን ራስ - ዲያብሎስን - በሥጋዌው እንደሚቀጠቅጠውና የሰውን ልጅ እንደሚያድን ተስፋውን ወዲያውኑ አበሰረው፡፡ ለስሙ አጠራሩ ክብርና ምስጋና ይግባውና ጌታችን "ውእቱ ጊዜ እቤ ነየ መጻእኩ ውስተ ርእሰ መጽሐፍ ተጽሕፈ በእንቲአየ - በዚያን ጊዜ አልሁ፣ በመጻሕፍት

ራስ ስለ እኔ ተጽፏል" ያለው ለዚህ ነበር፡፡ መዝ. 39፥7 ፤ ዕብ. 10፥7 የመጻሕፍት ራስ የተባለው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመጀመሪያ መጽሐፍ የሆነው ኦሪት ዘፍጥረት ነው፡፡ የመዳናችን ተስፋ የታወጀው ገና ከመጀመሪያው ነበር፡፡

ከዚያ ተስፋ የተነሣም አዳም ሞትን ቀርጣ ያበላችውን ሔዋንን "የሞት እናት" በማለት ፋንታ "ሔዋን - የሕያዋን ሁሉ እናት" አላት፡፡ ይህም ዲያብሎስን የሚቀጠቅጠውን ዘር የምታስገኘዋን አማናዊት ሔዋን - እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ገና አስቀድሞ ከርቀት በትንቢት የሚያመለክት ምሥጢር ነበር፡፡ አዳምና ሔዋንም ያን የተስፋ ስንቅ ይዘው ከደረሰባቸው ጉስቁልና ጋር አብረው ተስፋውንም ለልጆቻቸው አወረሱ፡፡ ያ ተስፋም በጉጉት ሲጠበቅ ኖረ፡፡ ታዲያ ያን ተስፋ የሚፈጽመውና ሰውን ከደረሰበት ከዚያ ሁሉ የሞትና የጉስቁልና ማጥ፣ ከጨለማው ሕይወት ሊያድነው የሚችለው ማን ነበር?

## 3.2 ሰውን ሊያድነው የሚችለው ማን ነበር?

ለሰው ልጅ ወደ ባሕርዩ ውስጥ ዘልቆ የገባውን ሞት አስወግዶ ሕይወትን የሚሰጠው፣ ያጣውን ሰላምና ነጻነት የሚመልስለት፣ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን አንድነት ሊመልስለት የሚችለው ማን ነበር?

ሀ) ነቢይ ነበርን?

ነቢያት በየዘመናቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ሰዎች እየተላኩ ሕዝቡ ከኃጢአታቸው በንስሐ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱና በበደላቸው ምክንያት ከሚመጣባቸው ቁጣ እንዲድኑ ሲመክሩና ሲያስተምሩ ኖረዋል፡፡ ነቢያት ሕዝቡንና ነገሥታትን እውነቱን በማስተማራቸውና ስለ ክርስቶስ ትንቢት በመናገራቸው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ካመፁ ሰዎች ብዙ መከራ ተቀብለዋል፡፡ ሆኖም ያ ሁሉ የነቢያት ተጋድሎ በአዳምና በሔዋን ከተፈጸመው በደልና ያ ካደረሰው ተደራራቢ ጉዳት ሊያድኑንና ከሞት ዕዳ ነጻ ሊያወጡን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቁንና ወደ እግዚአብሔር አንድነት ሊመልሱን አልቻሉም፡፡ እነርሱም የችግሩ ወራሾችና ባለ ዕዳዎች ስለ ነበሩ ለእነርሱም መድኃኒት ያስፈልጋቸው ነበር እንጂ እንኳን ለሌላው ሊተርፉ ቀርቶ ራሳቸውንም ማዳን አልቻሉም፡፡

ስለዚህም የነቢያት ዋናው የትንቢታቸው ማዕከል ዓለምን የሚያድነው መድኃኒት ነበር፡፡ ያ መድኃኒት ቶሎ ይመጣ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር አጥብቀው ይጸልዩና ሕዝቡን ደግሞ ያጽናኑ ነበር፡፡ እነርሱም መዳንን በመናፈቅ ይጮኹ ነበር፡፡ ለአብነትም ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ የሰውን ልጆች የመዳን ናፍቆትና የእድነን ጩኸት እንዲህ ሲል አቅርቧል፦

> ሰማዮችን ቀድደህ ምነው ብትወርድ! ተራሮችም ምነው ቢናወጡ! እሳት ጭራሮውን እንደሚያቃጥል፥ እሳትም ውኃውን እንደሚያፈላ፥ ስምህ ለጠላቶችህ ይገለጥ ዘንድ፥ አሕዛብም በፊትህ ይንቀጠቀጡ ዘንድ። . . . እነሆ አንተ ተቈጣህ፥ እኛም ኃጢአት ሠራን፤ ስለዚህም ተሳሳትን። ሁላችን እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል፥ ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው፥ ሁላችንም እንደ ቅጠል ረግፈናል፥ በደላችንም እንደ ነፋስ ወስዶናል። ስምህንም የሚጠራ አንተንም ሊይዝ የሚያስብ የለም፥ ፊትህንም ከእኛ ሰውረሃል፥ በኃጢአታችንም አጥፍተኸናል። አሁን ግን፥ አቤቱ አንተ አባታችን ነህ፥ እኛ ጭቃ ነን፥ አንተም ሠሪያችን ነህ፥ እኛም ሁላችን የእጅህ ሥራ ነን። አቤቱ፥ እጅግ አትቈጣ፥ ለዘላለምም ኃጢአትን አታስብ፥ እነሆ እባክህ ተመልከት፥ እኛ ሁላችን ሕዝብህ ነን። ኢሳ. 64፥1-9

ልበ አምላክ የተባለ ዳዊትም እንዲህ አለ፡-

> ዮሴፍን እንደ መንጋ የምትመራ የእስራኤል ጠባቂ ሆይ፣ አድምጥ፤ በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ ተገለጥ። በኤፍሬምና በብንያም በምናሴም ኃይልህን አንሣ፣ እኛንም ለማዳን ና። አቤቱ መልሰን፤ ፊትህንም አብራ፣ እኛም እንድናለን። የሠራዊት አምላክ አቤቱ፥ በባሪያህ ጸሎት ላይ እስከ መቼ ትቈጣለህ? የእንባ እንጀራን ትመግበናለህ፥ እንባም በስፍር ታጠጣናለህ። ለጎረቤቶቻችን ክርክር አደረግኸን፥ ጠላቶቻችንም በላያችን ተሣለቁብን። የሠራዊት አምላክ አቤቱ፥ መልሰን፤ ፊትህንም አብራ፣ እኛም እንድናለን። መዝ. 79፥1-7

እንዲሁም፡-

> አቤቱ፣ ሰማዮችህን ዝቅ ዝቅ አድርጋቸው፤ ውረድም፤ . . . እጅህን ከአርያም ላክ አድነኝም፣ ከብዙ ውኆች፣ አፋቸውም ምናምንን ከሚናገር፥ ቀኛቸው የሐሰት ቀኝ ከሆነ፣ ከባዕድ ልጆች እጅ አስጥለኝ። መዝ. 143፥5-8

ነቢያት ማድረግ የቻሉት ነገር ቢኖር እግዚአብሔር አስቀድሞ የተናገረው የመዳናችን ተስፋ ዘመኑ ደርሶ እስኪፈጸም ድረስ የሰው ልጆች ተስፋውን ያውቁና ይጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ማጽናናት ለሕዝቡ ማድረስ ብቻ ነበር፡፡ እግዚአብሔር በነቢያት ሕዝቡን እንዲህ እያለ ያጽናና ነበር፡- "አጽናኑ፥ ሕዝቤን አጽናኑ ይላል አምላካችሁ። . . . የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል፣ ሥጋ ለባሹም ሁሉ በአንድነት ያየዋል፣ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሯልና።" ኢሳ. 40፡1-5 ነቢያት የበደለው የአዳም ልጆችም በመሆናቸው፥ ከዚያም በላይ ፍጡራን በመሆናቸው የሰውን ልጅ ማዳን አልቻሉም፤ ፍጡር ፍጡርን ማዳን አይችልምና፡፡ ስለሆነም የሰው ልጅ ከነቢያት የበለጠ ኃይልና ክሂል ያለው መድኃኒት (አዳኝ) ያስፈልገው ነበር፡፡

## ለ) መልአክ ነበርን?

መላእክት "ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?" የተባለላቸው፥ እኛን የሚራዱንና የሚጠብቁን፣ የእግዚአብሔርን ምሕረት ወደ ሰዎች፣ የሰዎችን ጸሎት ደግሞ ወደ እግዚአብሔር የሚያሳርጉ ናቸው፡፡ ዕብ. 1፡14 ፤ ራእ. 5፡8 ፤ 8፡3-4 በአንድ ኃጥእ ንስሐ መግባትና ወደ እግዚአብሔር መመለስም ታላቅ ደስታ ያደርጋሉ፡፡ በአጠቃላይ መላእክት የአንዲቷ ሃይማኖት አካላት ሲሆኑ ለሰው ልጆች በሃይማኖት መንገድ በማገዝና በመራዳት እንደ ታላቅ ወንድም ናቸው፡፡ ዘካ. 1፡12-17 ፤ ሉቃ. 15፡7 ሆኖም ግን መላእክት የሰውን ልጅ ከደረሰበት ነገር ሊያድኑት አይችሉም፡፡ ፍጡራን እንደ መሆናቸው የፈረሰውን የእግዚአብሔርን ቃልና ያስከተለውን ጉዳት መቤዠትና መመለስ አይቻላቸውም፡፡ ይህ ከፍጡራን ዐቅም በላይ ነውና፡፡

## ሐ) መሥዋዕተ ኦሪት ነበርን?

መሥዋዕተ ኦሪት የተሠራው የዲያብሎስን ራስ የሚቀጠቅጠው የሴቲቱ ዘር (ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ) እስኪመጣ ድረስ መቆያ እንዲሆን፣ ለአማናዊው ለመሥዋዕተ ወንጌል ማዘጋጃና ምሳሌ እንዲሆን፣ እስከዚያውም ከአባርና ከቸነፈር ከመሳሰሉ መቅሠፍቶች እንዲታደግ ነበር እንጂ የሰውን ልጅ ለማዳን አልነበረም፡፡ "ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና፣ ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያ መሥዋዕት የሚቀርቡትን ሊፈጽም ከቶ አያችልም። እንደዚህማ ባይሆን፣ የሚያመልኩት አንድ ጊዜ ነጽተው ከዚያ በኋላ በሕሊናቸው ኃጢአትን ስላላወቁ ማቅረብን በተዉ አልነበረምን? ነገር ግን በዚያ መሥዋዕት በየዓመቱ የኃጢአት መታሰቢያ አለ፤ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና" በማለት የሰው ልጅ በኦሪት መሥዋዕት ሊድን የማይቻል መሆኑ ተገልጿል። ዕብ. 10፥1-4

ዋናው የሕገ ኦሪት አገልግሎት ለሕገ ወንጌል የትንቢትና የተምሳሌት ምስክርና ማስረጃ መሆን ነበር፡፡ ስለሆነም መሥዋዕተ ኦሪት የሰውን ልጅ ሊያድነው አይችልም ነበር፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን የሕጉን መሠረታዊ ጭብጥ የሆነውን የክርስቶስን መድኃኒትነትና ሊቀ ካህናትነት ሳይረዱ ገጸ ንባቡን ብቻ ጨብጠው የቀሩትን አይሁድ ለማስረዳት ነበር በዕብራውያን መልእክቱ ስለዚህ ጉዳይ ሰፋና ጠለቅ አድርጎ የጻፈላቸው፡፡ እንዲሁም ሁሉንም ጠቅልሎ "ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና" በማለት ገልጾታል፡፡ ሮሜ 10፥4 "ሕግ" ሲል ብሉይ ኪዳንን በሙሉ ያጠቃልላል፡፡

መ) እግዚአብሔር ነውን?

አዳምን ከዋንቱ የፈጠረውና ሕግን የሰጠው፣ ባጠፋም ጊዜ የፈረደበት፣ በኋላም ተስፋውን የሰጠው ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ስለዚህም በሰው ላይ የደረሰውን ጥልቅና ተደራራቢ ጉዳት እርሱ በሚያውቀው መንገድ ሊያድነው የሚችለው ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነበር፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ከወሰነ ማዳኑ ፍትሐዊም ተገቢም ይሆን ዘንድ አዳምን የሚያድነው መድኃኒት ቢያንስ የሚከተሉትን ነገሮች ማሟላት ይገባው ነበር፤ እነዚህም፡-

1. ሰው መሆን አለበት፣ ምክንያቱም የበደለው ሰው ነውና፤

   የበደለውና የተፈረደበት ሰው ስለሆነ አዳኙም ሰው ካልሆነ ማዳኑና አፈጻጸሙ የተገባጠመ አይሆንም፣ ይዛነፋል፤ ችግሩና መፍትሔው በትክክል አይገጣጠሙም፡፡ የበደለው ሰው ሆኖ ሳለ ሌላ ተገብቶ ቢያድነው አግባብነቱ ሙሉ አይሆንም፡፡

2. መሞት አለበት፣ በበደለኛው ላይ የተፈረደበት ቅጣት ሞት ነውና፤

   በበደለው በሰው ላይ የተፈረደው ፍርድ ሞት ስለሆነ ("በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ" ተብሎ) ያ ዕዳ ካልተከፈለ በስተቀር ሰው ነጻ ሆነ፣ ዳነ ማለት አይቻልም፡፡ ወይም ደግሞ ይህ ፍርድ ሳይፈጸም ቢድን የእግዚአብሔር ቃል ተፈጻሚነት ጉዳይ ችግር ላይ ይወድቅ ነበር፡፡

3. ሞትን ማሸነፍ መቻል አለበት፤

   ሰውን የሚያድነው መድኃኒት መሞት መቻል ብቻ ሳይሆን ሞትንም ማሸነፍ የሚችል መሆን ነበረበት፡፡ አለበለዚያ መሞቱ ብቻ ለሰው ልጅ የሚጠቅመው ነገር አይኖርም ነበር፡፡ ሞትን መቀበል መቻልና መሞት ብቻ ሳይሆን ሞቶ ሞትን ድል ማድረግና ማሸነፍ መቻል አለበት፡፡ ምክንያቱም ሞትን ድል ማድረግ ካልቻለ እንዲሁ ቢሞት የሟቾችን ቁጥር በአንድ ከመጨመር በስተቀር በመሞቱ ብቻ የሚያስገኝልን ጥቅም አይኖርም ነበርና፡፡

4. ንጹሐ ባሕርይ መሆን አለበት፤

   ስለ ኃጢአተኞች ለመካስ ሟቹ ከበደልና ከኃጢአት ዕዳ ንጹሕ መሆን ይኖርበታል፡፡ ራሱ ንጹሕ ካልሆነ ቢሞት እንኳ በራሱ ዕዳ ይሞታል እንጂ ለሌሎች ቤዛ ሊሆን አይችልምና፡፡

የመጀመሪያውን ሁለቱን፣ ማለትም ሰው መሆንን እና መሞትን ሊያሟላ የሚችለው ሰው ነው፤ ምክንያቱም አምላክ በባሕርዩ ሰውም አይደለም፣ ሞትም አይስማማውም፡፡ ሌሎቹን ሁለቱን ደግሞ - ሞትን ማሸነፍን እና ንጹሐ ባሕርይ መሆንን የሚያሟላው ደግሞ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ሰው ብቻውን መሞት ቢችልም ሞትን ማጥፋትና ሞትን ድል ማድረግ ስለማይችል ሁለቱንም - በአንድ በኩል ስለ ሰው ሲል ሰው መሆንን እና ሞትን በፈቃዱ መቀበልን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሞትን ማሸነፍንና በንጹሐ ባሕርይነቱ ቤዛ መሆንን - ማሟላት የሚችለው እግዚአብሔር ስለሆነ ራሱ

መድኃኒት ሆነልን፡፡ ሆኖም ግን እግዚአብሔር በባሕርዩ ሞት ስለሌለበትና ሰውም ስላልሆነ ስለ እኛ ይከስልንና ሞትን ተቀብሎ ያጠፋልን ዘንድ የእኛን ባሕርይ ገንዘብ ማድረግ አስፈለገው፡፡ አለበለዚያ ማዳኑ ውላጣዊና አማናዊ፣ እንዲሁም ፍጹም ፍትሐዊና የተሟላ አይሆንም ነበር፡፡ ስለዚህም አካላዊ እግዚአብሔር ቃል ሰው ሆነ፡፡

ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ የቃልን ሥጋ መሆን በተመለከተ በተናገረበት ድርሳኑ ስለዚህ ሲናገር እንዲህ አለ፡-

> በመሞት ካልሆነ በቀር የሰው ሞት ሊወገድ እንደማይችል እግዚአብሔር ቃል ባየ ጊዜ እርሱ በባሕርዩ የማይሞት ስለ ሆነ ስለ ሁሉም መሞት ይችል ዘንድ የሚሞት የእኛን ባሕርይ ተዋሐደ፡፡ ይህም የእኛ ባሕርይ ከተዋሐደው ከእግዚአብሔር ቃል የተነሣ የማይሞት ይሆን ዘንድ፣ መፍረስና መበስበስም በትንሣኤ ይጠፋ ዘንድ ነው፡፡ ቃል የተዋሐደውንና ገንዘቡ ያደረገውን ሥጋ ከበደል ንጹሕ የሆነ መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብና ለሞት በመስጠት ሞትን ከወገኖቹ አስወገደ፡፡ የሞትን ዕዳ ሞትን በመክፈል ከእኛ አስወገደው፡፡ ሞትና ጥፋት የእኛን ሥጋ ከተዋሐደው ከአካላዊ ቃል የተነሣ እኛን ሊገዙና ሊይዙ አልተቻለውም፡፡ የሁሉ ጌታና መድኃኒት መጥቶ ሞትን ድል ባያደርገው ኖሮ የሰው ዘር ጠፊ ነበር፡፡ (ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ በእንተ ተሠግዎተ ቃል፣ ቁ. 9)

ስለዚህም አስቀድሞ ራሱ ብሥራቱን ለአዳምና ለሔዋን በነገራቸው መሠረት እርሱ ባወቀው ምሥጢር ከሦስቱ አካላት አንዱ የሆነው አካላዊ ቃል ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆነ፡፡ ስለዚህ አምላክ ሰው ሆነ፤ "ቃል ሥጋ ኮነ ወኀደረ ላዕሌነ - ቃል ሥጋ ሆነ፣ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ" ተብሎ የተገለጠው ድንቅ ምሥጢርና ጸጋ ይህ ነው፡፡ ዮሐ. 1፡14 እንደዚሁም "ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ" ተብሎ የተገለጸው ይህ ምሥጢር የመዳናችን ቁልፍ ነው፡፡ 1 ዮሐ. 3፡8

ሰውን ሊያድነው የሚችለው እውነተኛና ዘለዓለማዊ መድኃኒት ራሱ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን፣ እንዲሁም ይኸ ሰውን የማዳን ጉዳይ ከራሱ ከእግዚአብሔር በቀር በሌላ በማንም የማይፈጸምና ለማንም የማይቻል መሆኑን እግዚአብሔር በነቢያቱ አፍ አስቀድሞ ደግሞ ደጋግሞ ተናግሯል፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን እንመልከት፡-

- "እኔ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም።" ኢሳ. 43፡11
- "ይናገሩ ይቅረቡም፣ በአንድነትም ይማከሩ፣ ከጥንቱ ይህን ያሳየ፣ ከቀድሞስ የተናገረ ማን ነው? ያሳየሁም የተናገርሁም እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን? ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ እኔ ጻድቅ አምላክና መድኃኒት ነኝ፣ ከእኔም በቀር ማንም የለም።" ኢሳ. 45፡21
- "አምላካችንና መድኃኒታችን ሆይ፣ እርዳን፤ ስለ ስምህ ክብር፣ አቤቱ ታደገን፥ ስለ ስምህም ኃጢአታችንን አስተሥርይልን።" መዝ. 78፡9
- "የመድኃኒታችን አምላክ ሆይ፣ መልሰን፣ ቍጣህንም ከእኛ መልስ።" መዝ. 84፡4
- "እግዚአብሔር ግን እስራኤልን በዘላለማዊ መድኃኒት ያድነዋል፣ እናንተም ለዘላለም አታፍሩምና አትዋረዱም።" ኢሳ. 45፡17
- "እርሱም፦ በእውነት ሕዝቤ ሐሰትን የማያደርጉ ልጆች ናቸው አለ፤ መድኃኒትም ሆናቸው።" ኢሳ. 63፡8
- ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው።" 1 ጢሞ. 2፡3-4

❖ *ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ . . .”* ቲቶ 3፡4

ይህን ሁሉ አጠቃልሎ በነቢዩ ኢሳይያስ *“አኮ በመልአክ ወአኮ በተንባል አላ ለሊሁ ይመጽእ ወያድኅኖሙ - በመልእክተኛ (በመልአክ) አይደለም፣ በአማላጅም አይደለም፣ እርሱ ራሱ ይመጣል፣ ያድናቸውማል እንጂ”* አለ፡፡ ኢሳ. 63፡9-10

እግዚአብሔር አምላካችን እንዲህ ባለ ሁኔታ መድኃኒት እርሱ ራሱ ብቻ መሆኑን፣ ከእርሱም በቀር ሌላ የሚያድን የሌለ መሆኑን ነግሮናል፡፡ ፍጡር ፍጡርን በተለያየ ሁኔታ እንደ ዓቅሙ ሊረዳው ቢችልም በሰው ልጅ ላይ የደረሰውን ሞት አስወግዶ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ሊሰጠው፣ እግዚአብሔርን መምሰል ሊመልስለት፣ ያጣውን ጸጋ ሊሰጠው ግን አይችልም፡፡ ይህን ማድረግ የሚችለው ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነበር፡፡

በቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ እና በአርዮስ መካከል የነበረው ክርክር ዋና ጭብጥም ይኸው የሰውን ልጅ የሚያድነው መድኃኒት ማንነት ጉዳይ ነበር፡፡ አርዮስ የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ቢክድም አዳኝነቱን (መድኃኒት ነው ማለትን) ግን እቀበላለሁ ባይ ነበር፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ አርዮስን ሲሞግት ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ (እግዚአብሔር) ካልሆነና "ፍጡር" ከሆነ፣ ፍጡር ፍጡርን ሊያድነው ስለማይችል የሰው ልጅ አልዳነም ማለት ነዋ! ይላል፡፡ የሰው ልጅ ካልዳነ ደግሞ የክርስትና ሃይማኖት ትርጉም የለውም ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም የክርስትና ሃይማኖት የመዳን ሃይማኖት ነውና፡፡

ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ አዳኛችን ማን መሆን እንዳለበት ሲያብራራ ሰውን ሊያድነው የሚችለው የኃጢአትን ኃይል ሊያሸንፍ የሚችል፣ ለሰው ልጅ ሞትን አጥፍቶ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ሊሰጠው የሚችል ራሱ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን በአጽንዖት ይገልጻል፡፡ የሰው ልጅ መሠረታዊ ባሕርዩ መዳን የሚያስፈልገው መሆኑ ነው፡፡ ማንም ፍጡር ሌላውን ፍጡር ሊያድነው አይችልም፡፡ ፍጡሩን ሊያድን የሚችለው የፈጠረው ፈጣሪው ብቻ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ካልሆነ ግን እርሱ ራሱ የችግሩ አካል ነው እንጂ መፍትሔው አይደለም ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት እርሱ ራሱ መዳን ከሚያስፈልጋቸው መካከል አንዱ ይሆናል እንጂ አዳኝ (መድኃኒት) ሊሆን አይችልም ማለት ነው ሲል የአርዮሳውያን ክህደት መሠረታዊ ጭብጥ ሰውን መድኃኒት አልባ (ያልዳነ) የሚያደርግ፣ የእግዚአብሔርን ታላቅ ውለታ ከንቱ የሚያደርግ የክህደት ሁሉ ክህደት መሆኑን ፍንትው አድርጎ ያሳያል፡፡

ሰው የዳነ ካልሆነ ሃይማኖትስ፣ አምልኮስ ፋይዳቸው ምንድን ነው? ሃይማኖት ለዘለዓለማዊ ሕይወት ካላበቃና መዳንን የማያስገኝ ከሆነ ፋይዳው ምንድን ነው? ቅዱስ አትናቴዎስ ከአርዮሳውያን ጋር ያን ያህል ትዕግሥት አስጨራሽ የሆነ የግማሽ ክፍለ ዘመን ሁለንተናዊ ተጋድሎ ያደረገው አርዮሳውያን መድኃኒቱን ኢየሱስ ክርስቶስን ፍጡር በማድረግ ያገኘውን መዳንን ሐሰት ለማድረግ ስለ ተነሡበት ነበር፡፡ የቅዱስ አትናቴዎስ እና የአርዮስ መሠረታዊ ክርክር "አዳኙ ማን ነው?" የሚለው ጉዳይ ነበር፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ ፍጡር ፍጡርን ማዳን አይችልም፣ አዳኙ ራሱ እግዚአብሔር ካልሆነ በስተቀር ሲል፤ አርዮስ ደግሞ ፍጡርም ቢሆን ፍጡርን ሊያድነው ይችላል ባይ ነበር፡፡ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከፕሮቴስታንታዊ የተሐድሶ መናፍቃን ጋር ያላት መሠረታዊ ልዩነትም በዚህ በመዳን ትምህርት ላይ ነው፡፡ ቀጥሎ እንደምንመለከተው የተሐድሶዎች አስተምህሮ ዓይነቱ ይለያይ እንጂ እንደ አርዮሳውያን ሰውን ከመዳን መስመር የሚያወጣ የጥፋት ትምህርት ነው፡፡

## 3.3 የሰዉ ልጅ ድኅነት (መዳን) የእግዚአብሔር ዓላማ መሆኑ

እግዚአብሔር ለእኛ ያደረጋቸው የተለያዩ የቸርነት ነገሮች ሁሉ እኛን ለማዳንና ስለ እኛ መዳን የተደረጉ ናቸው፡፡

ሀ. የእግዚአብሔር ሰው መሆን ዓላማው የሰው ልጅ (የእኛ) መዳን ነበር፡፡

እግዚአብሔር አምላክ በቃላት ተከናውኖ ሲነገር ይቅርና በሕሊና እንኳ ታስቦ በማይደረስበት ጥልቅ ፍቅሩ አካላዊ ቃል ሰው ሆኖ የእኛን ባሕርይ ተዋሕዶ ወደ እኛ እስኪመጣ ያደረሰው ዋናው ምክንያት ሰውን ማዳን ነው፡፡ ይህን ራሱ ጌታችን እንዲህ በማለት ነግሮናል፦

> ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ . እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና። ዮሐ. 3፥14-17

እንዲሁም "የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቷልና" በማለት አካላዊ ቃል ሰው የሆነበት ምክንያት የጠፋነውን እኛን ለመፈለግና ለማዳን መሆኑን ተናግሯል፡፡ ሉቃ. 19፥10 ጌታችን የመጣበትን ዓላማ ያልተረዱ ከውጭ ሲያዩዋቸው የተማሩ የሚመስሉ፣ ራሳቸውንም የሕዝቡ መምህራን አድርገው የሚቆጥሩና አዋቂ ነን ይሉ የነበሩ፣ ውስጣቸው ግን ባዶ የነበሩት ጻፎችና ፈሪሳውያን ጌታችንን ቀራጮችና ኃጢአተኞች ሁሉ ሊሰሙት ወደ እርሱ ሲቀርቡ ባዩ ጊዜ "ይህስ ኃጢአተኞችን ይቀበላል፣ ከእነርሱም ጋር ይበላል" ብለው እርስ በርሳቸው አንጐራጐሩበት። በዚያን ጊዜ ጌታችን ድንቅ የሆኑ ሦስት ተከታታይ ምሳሌዎችን መስሎ ነገራቸው፡፡ እነዚህም የጠፋው በግ፣ የጠፋው ድሪም እና የጠፋው ልጅ ናቸው፡፡ ሉቃ. 15 ሦስቱም ስለ ጠፍቶ መገኘት የተነገሩ ናቸው፡፡ ሦስቱም የጠፉት ነገሮች አጠፋፋቸውና የተገኙበትም መንገድ ቢለያይም በመጨረሻ ግን ሁሉም ተገኝተዋል፡፡ አራተኛው የጠፋው ልጅ ታላቅ ወንድም ("ያልጠፋው ልጅ") ግን "ጠፋ" ተብሎ ባይነገርለትም በተግባር ሲታይ ግን በአካል ከአባቱ ቤት ባይጠፋም በአባቱ ቤት የመኖርን ጣዕም ሳያውቅ፣ የአባቱም ዓላማ ሳይገባው በአካል ያለ፣ በመንፈስ ግን የጠፋ የእነርሱ (የጸሐፍትና ፈሪሳውያን) ምሳሌ ነበር፡፡

ጌታችን ስለ ጠፋው በግ ሲናገር እንዲህ አለ፦ "መቶ በግ ያለው ከእነርሱም አንዱ ቢጠፋ፣ ዘጠና ዘጠኙን በበረሃ ትቶ የጠፋውን እስኪያገኘው ድረስ ሊፈልገው የማይሄድ ከእናንተ ማን ነው? ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት በጫንቃው ይሸከመዋል፤ ወደ ቤትም በመጣ ጊዜ ወዳጆቹንና ጐረቤቶቹን በአንድነት ጠርቶ፣ የጠፋውን በጌን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ ይላቸዋል። እላችኋለሁ፣ እንዲሁ ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል። እንደዚሁ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንዲጠፋ በሰማያት ያለው አባታችሁ ፈቃድ አይደለም።" በአጠቃላይ በሦስቱም የጠፉ ነገሮች መገኘት ታላቅ ደስታ ተደርጓል፡፡ ይህን ሲያጠቃልል ጌታችን "እላችኋለሁ፣ እንዲሁ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል" አለ፡፡

- እግዚአብሔር አብ በልጁ ሥጋዌ በመንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኖችን የጠራንና የመረጠን መዳንን እንድናገኝና ዘለዓለማዊ ሕይወትን እንድንወርስ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "እግዚአብሔር ለቍጣ አልመረጠንምና፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ" እንዳለ፡፡ 1 ተሰ. 5፥8-9 እንዲሁም ይኸው ሐዋርያ እንዲህ ይላል፦ "እኛ ግን፣ በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፣ ሁል ጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አለብን፣ እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኵራት መርጧችኋልና፡፡" 2 ተሰ. 2፥13

ሥጋው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ የሥጋዌው ዋና ዓላማ የሰውን ልጅ ማዳን በመሆኑ መልካምና እውነተኛ እረኛነቱን በተናገረበት አንቀጽ፦ "ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ። እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፤ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም" አለ፡፡ ዮሐ. 10፡10፤ 28 ይህ መዳን "የዘለዓለም ሕይወት"፣ "የዘለዓለም ሕይወት ተስፋ" ተብሎም ተገልጿል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በመልእክቱ እንዲህ ይላል፦ "ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን፤ ሕይወትም ተገለጠ፤ አይተንማል እንመሰክርማለን፤ ከአብ ዘንድ የነበረውንም ለእኛም የተገለጠውን የዘላለምን ሕይወት እናወራላችኋለን፤ እርሱም የሰጠን ተስፋ ይህ የዘላለም ሕይወት ነው።" 1 ዮሐ. 1፡1-2 ፤ 2፡25 እንዲሁም "በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፤ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና" ይላል፡፡ 1 ዮሐ. 4፡9

ለ. የነቢያት የትንቢታቸው ዋና ማዕከል የሰው መዳን (ድኅነት) ነበር፡፡

ከጥንት ጀምሮ የተነሡ የተለያዩ አበው ነቢያት የሰው ልጅ መዳን ከመድረሱና ከመፈጸሙ አስቀድሞ ተስፋውን በትንቢት፣ በተምሳሌትና በተለያዩ ነገሮች ይናገሩ ነበር፡፡ ይህም የሰው ሕሊና በተስፋ እንዲጠብቅና እንዲዘጋጅ እንዲሁም ስለ ሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች ነበር፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ይህን የነቢያትን የትንቢት ሠብጥና ተልእኮ ጉዳይ በተመለከተ በመልእክቱ እንዲህ ሲል ገልጾታል፦

> ለእናንተም ስለሚሰጠው ጸጋ ትንቢት የተናገሩት ነቢያት ስለዚህ መዳን ተግተው እየፈለጉ መረመሩት፤ በእነርሱም የነበረ የክርስቶስ መንፈስ፣ ስለ ክርስቶስ መከራ ከእርሱም በኋላ ስለሚመጣው ክብር አስቀድሞ እየመሰከረ፣ በምን ወይም እንዴት ባለ ዘመን እንዳመለከተ ይመረምሩ ነበር። ለእነርሱም ከሰማይ በተላከ በመንፈስ ቅዱስ ወንጌልን የሰበኩላችሁ ሰዎች አሁን ባወሩላችሁ ነገር እናንተን እንጂ ራሳቸውን እንዳላገለገሉ ተገለጠላቸው፤ ይህንም ነገር መላእክት ሊመለከቱ ይመኛሉ። 1 ጴጥ. 1፡10-12

እነ ነቢዩ ኢሳይያስ "ስለ ጽዮን ዝም አልልም፥ ስለ ኢየሩሳሌምም ጸጥ አልልም፤ ጽድቅዋ እንደ ጸዳል መዳንዋም እንደሚበራ ፋና እስኪወጣ ድረስ" እያሉ ስለ መዳናችን ትንቢት ይናገሩ ነበር፡፡ ኢሳ. 62፡1 ነቢዩ ኤርምያስም በትንቢቱ "በእውነት የእስራኤል መዳን በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ ነው" ይል ነበር፡፡ ኤር. 3፡23 የዮሐንስ መጥምቅ አባት ካህኑ ዘካርያስም የመዳናችን ፈጻሚና ራስ የሆነው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ ጠራጊ ይሆን ዘንድ መንፈቅ ተቀድሞ የተላከው ዮሐንስ መጥምቅ በተወለደና ስም በወጣለት ጊዜ ተዘግቶ የነበረው አንደበቱ ሲከፈት በመንፈስ ቅዱስ እንዲህ አለ፦ "እንሆ ለነ ቀርነ መድኃኒትነ እምቤተ ዳዊት ገብሩ በከመ ነበበ በአፈ ነቢያቲሁ ቅዱሳን እለ እመዓለም - ቀድሞ ከጥንት ጀምሮ በነበሩት በቅዱሳን ነቢያት አፍ እንደ ተናገረ፣ በብላቴናው በዳዊት ቤት የመዳን ቀንድን አስነሥቶልናል" በማለት ከጥንት ጀምሮ በየዘመኑ የተነሡ የተለያዩ ነቢያት የትንቢታቸው ዋና ማእከልና ዓላማ የመዳናችን ፈጻሚ የኢየሱስ ክርስቶስ የመገለጥና የመምጣት ጉዳይ የነበረ መሆኑንና ያን ጊዜ ዮሐንስ መጥምቅ ሲወለድ ደግሞ ያ የመዳን ቀን ጊዜው የደረሰ መሆኑን በመንፈስ ቅዱስ እናጋሪነት ተናገረ፡፡ ሉቃ. 1፡69-70

ሐ. የሐዋርያት ተልእኮና ስብከት ዓላማው የሰው መዳን ነው፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መዳናችንን በሥጋዌው ከፈጸመ በኋላ ቅዱሳን ሐዋርያቱን በኃይለ መንፈስ ቅዱስ ቀድሞ የነበረባቸውን ፍርሃትና አለማስተዋል አስወግዶ እንዲህ ሲል ወደ ዓለም ላካቸው፦ "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡" ማቴ. 28፡19-20

እንዲሁም "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ። ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል" አላቸው፡፡ ማር. 16፥15-16

በዚሁ ተልእኮ መሠረት ደቀ መዛሙርቱ በየደረሱበት የመዳንን ቃል ለሕዝቡ ይናገሩ ነበር፡፡ የሰብከታቸውም ዓላማ ሰዎች የመዳንን አስፈላጊነትና እንዴትም እንደሚዳን ተረድተው እንዲድኑ የእግዚአብሔርን የመዳን ጸጋና ጥሪ ለሰዎች ማድረስ ነበር፡፡ ለአብነትም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያው ሐዋርያዊ ጉዞው ከጓደኞቹ ጋር ጳፉ ከተባለው ቦታ ተነሥቶ የጲስድያ ወደምትሆን ወደ አንጾኪያ ደረሱና በሰንበት ቀን ወደ ምኵራብ ገብተው ተቀመጡ። በዚያም ሕግና ነቢያትም ከተነበቡ በኋላ የምኵራቡ አለቆች፡- "ወንድሞች ሆይ፣ ሕዝብን የሚመክር ቃል እንዳላችሁ ተናገሩ" ብለው በላኩባቸው ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስ ተነሣና በእጁ ጠቅሶ እንዲህ አለ፡-

> የእስራኤል ሰዎችና እግዚአብሔርን የምትፈሩት ሆይ፣ ስሙ፤ የዚህ የእስራኤል ሕዝብ አምላክ አባቶቻችንን መርጦ በግብፅ አገር በእንግድነት ሳሉ ሕዝቡን ከፍ ከፍ አደረጋቸው፣ ከፍ ባለችውም ክንዱ ከዚያ አወጣቸው። . . . ከዚህም ሰው ዘር (ከዳዊት) እግዚአብሔር እንደ ተስፋው ቃል ለእስራኤል መድኃኒትን እርሱም ኢየሱስን አመጣ። ከመምጣቱ በፊት ዮሐንስ አስቀድሞ ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ የንስሐን ጥምቀት ሰብኮ ነበር። . . . እናንተ ወንድሞቻችን፣ የአብርሃም ዘር ልጆች ከእናንተ መካከልም እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሆይ፣ ለእናንተ የዚህ የመዳን ቃል ተላከ። የሐዋ. 13፥14-26

ለቆሮንቶስ ምእመናን ስለ ወንጌል ምንነትና ዓላማ በመልእክቱ ሲያስታውሳቸውም እንዲህ አለ፡ - "ወንድሞች ሆይ፥ የሰበክሁላችሁን ደግሞም የተቀበላችሁትን በእርሱም ደግሞ የቆማችሁበትን በእርሱም ደግሞ የምትድኑበትን ወንጌል አሳስባችኋለሁ፡፡" 1 ቆሮ. 15፥1 የሐዋርያት ስብከት ለሚቀበሉትና ለሚጠቀሙበት የሕይወት መንገድ፣ ለማይቀበሉት ደግሞ ያው የመዳን ቃል የሚፈረድባቸው ስለሆነ የሞት መንገድ የሚሆንባቸው መሆኑን ሲናገር፡- "ለእነዚህ ለሞት የሚሆን የሞት ሽታ፣ ለእነዚያም ለሕይወት የሚሆን የሕይወት ሽታ ነን" አለ፡፡ 2 ቆሮ. 2፥16 ቅዱስ ጴጥሮስም "ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኰል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ" በማለት ቃለ እግዚአብሔር ዓላማው መዳን መሆኑን ገልጿል። 1 ጴጥ. 1፥2-3 ቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙሩን ቲቶን ሲመክረው "አንተ ግን ሕይወት ለሚገኝበት ትምህርት የሚገባውን ተናገር" ብሎታል። ቲቶ 2፥21

መ. ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት ለሰዎች የመዳን እውቀትን ለመስጠት ነው፡፡

ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን ሊያጠቃልል ሲል ወንጌሉን የጻፈበትን ዋና ምክንያት እንዲህ ሲል ገለጸ፡- "ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፤ ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፣ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፏል።" ዮሐ. 20፥30-31 ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ትምህርት አስተምሯል፣ ብዙ ተአምራት አድርጓል፡፡ ሆኖም ሁሉም አልተጻፉም፡፡ ቅዱሳን ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ተቃኝተው ከእነዚያ መካከል መርጠው በወንጌል የጻፉልን ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒት መሆኑን አምነን በስሙ ሕይወት ለማግኘት የሚረዳንን ያህል ነው ማለት ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙሩን ጢሞቴዎስን፡- "ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉ ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል" ሲል የጻፈለት ለዚህ ነው፡፡ 1 ጢሞ. 3፥15 ካህኑ ዘካርያስም እንደበቱ በተከፈተ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ በተናገረው ጸሎት ስለ ልጁ ስለ ዮሐንስ መጥምቅ ሲናገር፡- "እንደዚህም የኃጢአታቸው ስርየት የሆነውን የመዳን እውቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ" ያለው ይኸንኑ የሚያስረዳ ነው፡፡ ሉቃ. 1፥77

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት መሠረታዊና ተቀዳሚ ዓላማ በሥነ ፍጥረት ስላለው ነገር ወይም ስለ ሌሎች የተለያዩ ጉዳዮች ጥልቅ እውቀት ለማሳወቅና ለማራቀቅ ሳይሆን ሰው በእግዚአብሔር አምኖ የሚድንበትን የሕይወት መንገድ ለማሳየት ነው፡፡ "የመዳን እውቀት" የሚባለውም እግዚአብሔር በቸርነቱ የሰጠንን ድኅነት አውቀን በዚህ በመዳን መንገድ እንድንጓዝና ዘለዓለማዊ ሕይወትን ገንዘብ እንድናደርግ የሚረዳን እውቀት ነው፡፡ ለመዳን የማይጠቅም እውቀት በእግዚአብሔር ዘንድ ሞኝነት ነው፡፡ ከመዳን የሚያሰናክል እውቀት ደግሞ የተከለከለ "የእውቀት ዛፍ" ነው፡፡ እውቀት ማለት *"የመዳን እውቀት"* ነው፡፡ "የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው" የተባለውም ለዚህ ነው፡፡

## 3.4 መዳን ማለት ምን ማለት ነው?

በኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ መዳን ስንል የኃጢአት ደመወዝ ከሆነው ከሞትና ከቅጣት መዳን ብቻ፣ ወይም ከኩነኔ መዳንና ማምለጥ ብቻ አይደለም፡፡ መዳን የኃጢአት ሥርየትን ማግኘትና ከቅጣት መዳን ብቻ ሳይሆን ከዚያ እጅግ ያለፈ ጥልቅና ሁለንተናዊ ነው፡፡ ይህ መሠረታዊና ዋና ነገር ነው፤ ሆኖም ግን ይህ እንዳለ ሆኖ በዚያ ላይ የተሰጡን ብዙ ጸጋዎችና ሀብታትም አሉ፡፡ጌታችን ያደረገልን የመዳን ቸርነትና ስጦታ ስለ እኛ ተገብቶ የኃጢአታችንን ዕዳ መክፈልና እኛን ነጻ ማውጣት ብቻ አይደለም፤ ከዚያ በላይ የሆነ እጅግ በጣም ብዙና ድንቅ ነገር ነው እንጂ፡፡ ይህን በተመለከተ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ እንዲህ ብሏል፡-

> በአንድ ቃል ለመግለጽ መድኃኒታችን ሰው ሆኖ ለእኛ ያደረጋቸው ነገሮችና የሰጠን ጸጋዎች ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ ሊቆጥራቸው የሚፈልግ ሰው ቢኖር የባሕርን ስፋ አይቶ ሞገዱን ለመቁጠር እንደሚፈልግ ሰው ያለ ነው፡፡ በባሕሩ ላይ ያለውን ሞገድ ሁሉንም በዓይኑ ስፍር ውስጥ ማስገባትና መቁጠር እንደማይችል ሁሉ፣ ምክንያቱም ሞገዱ ወዲህና ወዲያ ሲል ዓይኑ አንዱን ሞገድ ሲከተል ሌላው ሁሉ እያመለጠው ኅሊናውን በተደጋሚ ይይዘዋልና፤ ክርስቶስ በሥጋ ተገልጦ የሰጠንን ጸጋ ሁሉ ለመቁጠርና ለመስፈር የሚፈልግ ሰውም ሁሉንም መዘርዘርና መቁጠር ቀርቶ እንዲሁ በደፈናው ለመገመት እንኳ አይቻለውም፤ አስቤዋለሁ ወይም ቆጥሬዋለሁ ብሎ ከሚያስበው ይልቅ ከኅሊናው ውጭና ከአእምሮው በላይ ሆኖ የሚቀረው እጅግ ብዙ ነውና፡፡ ስለዚህ የተወሰነውን እንኳ በሚገባ መናገርና መግለጽ የማይቻል ከሆነ ሁሉንም ለመናገር አለማሰብ የተሻለ ነው፤ (በእንተ ተሠግዎተ ቃል፤ ቁ. 54)

በአጠቃላይ መዳን ስንል የሚከተሉትን አራት መሠረታዊ የእግዚአብሔር ስጦታዎችን ያጠቃልላል፡፡ እነዚህም፡-

1) *ኃጢአት ካመጣው ፍዳ ሁሉ መዳን፤*
2) *ፈጣሪውን እንዲያውቅ መሆን፤*
3) *ሐዲስ ተፈጥሮ፤ እና*
4) *በቅድስና (እግዚአብሔርን በመምሰል) ማደግ ናቸው፡፡*

ይህ በመቀጠል በኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ "መዳን" ስንል ምን ማለት እንደ ሆነ፣ የእግዚአብሔር ማዳን ምን ምን ነገሮችን (ጸጋዎችን) እንደ ሰጠን መጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በመቀጠልም በቀደምት ቅዱሳን አበው ትምህርት እንመለከታለን፡፡

### 1) ኃጢአት ካመጣው ፍዳ ሁሉ መዳን

አዳምና ሔዋን ምክንያት በባሕርያችን የደረሰብን ጉዳት ሁለት ዘርፍ ያለው ነው፡፡ ይህም በአንድ በኩል ሕጉን በማፍረሳቸውና ቃሉን ባለመጠበቃቸው ምክንያት ሕግ አፍራሾችና ወንጀለኞች ሆንን፤ ከዚህም የተነሣ (ሕጉን በማፍረስ ምክንያት) በሕግ አፍራሾች ላይ የሚደርሰው "የሕግ ርግመት" ደረሰብን፡፡ ስለዚህም ቅጣት የሚገባን ወንጀለኞች፣ ሕጉን በሚተላለፉ ላይ የሚደርሰው

የሕግ ርግመት የደረሰብን ሆንን፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ባሕርያችን በኃጢአት ምክንያት መሰወጥና መነስቆል አገኘው፤ ሕይወትን አጣን፣ ለሞት ተገዛን፡፡ ሞት ወደ ባሕርያችን ዘልቆ ገብቶ ተቆጣጠረን፣ ማርጀትና ማፍጀት፣ መድከምና መዛል፣ መታመምና መቸገር ሁሉ ወደ ባሕርያችን ውስጥ ገቡ፡፡ ስለዚህ መዳናችንም ይህንኑ መንገድ የተከተለ ይሆን ዘንድ ይገባው ነበር፤ በአንድ በኩል በሕጉ ከመጣብን ርግመት ነጻ ያወጣንና ጸጋውን ይመልስልን ዘንድ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በኃጢአት ምክንያት ሙታን የሆንነውን ሕያዋን ያደርገንና ሕይወትን ይሰጠን ዘንድ ያስፈልገን ነበር፡፡

የእግዚአብሔርን ሕግ በማፍረሳችን ያመጣነውን ርግመትና ዕዳ በሞቱ ከፈለልን፤ ካሰልን፡፡ በአዳምና በሔዋን ውድቀት ምክንያት የሰው ልጅ በኃጢአትና በዲያብሎስ ባርነት ሥር ወድቆ ነበር፡፡ ስለዚህ ሰው ለመዳን ይህ ባርነቱና ርግመቱ መወገድ ነበረበት፡፡ ይህንንም የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ገንዘብ ባደረገው በእኛ ባሕርይ በመስቀል ላይ በመሞቱ፣ በመነሣቱ፣ በማረጉና በአብ ቀኝ በመቀመጡ፣ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን ለቅዱሳን ሐዋርያቱ በመላኩ ፈጽሞታል፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፏልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን" በማለት እንደ ገለጸው በመስቀል ላይ በመሞት በእኛ ላይ የነበረውን ርግመትና ዕዳ አስወገደልን፣ ነጻ አወጣን፡፡ እንደዚሁም "በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነው" እንደ ተባለ ጌታችን የእኛን ርግመት በመቀበል ከዚያ የሕግ ርግመት ዋጀን፡፡ ዘዳ. 21፥23 ፤ ገላ. 3፥13 "ኢተረክበ ሐሰት ውስተ አፉሁ - በአንደበቱ ሐሰት አልተገኘበትም" እንደ ተባለ ንጹሐ ባሕርይ የሆነ እርሱ የእኛን በደል ተሸክሞ ከዕዳ ነጻ አረደገን፡፡ ኢሳ. 53፥9 ፤ 1 ጴጥ. 2፥22 "በመስቀል ላይ በመሞቱ በሞት ተይዘው የነበሩትን እንዳዳናቸው ሁሉ ርግመታችንን በመሸከም ደግሞ ከርግመት አዳነን" እንዳለ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ[62]፡፡ ስለዚህም በሰው ልጅ ላይ ተፈርዶበት የነበረው የሞት ፍርድ ተወገደለት፣ ተነሥቶት (ተወስዶበት) የነበረው ሕይወትም ተመለሰለት፡፡

ራሱ መድኃኒታችን በቅዱስ ቃሉ "እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል፣ ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም" በማለት የገለጸው ይህን ማዳኑን ነው፡፡ ማቴ. 20፥28 ሐዋርያውም "ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ" ይላል፡፡ 1 ጢሞ. 2፥6 ቅዱስ ባስልዮስም "እርሱ ራሱ ስለ እኛ ርግመት በመሆን የተረገምን ከመሆን አዳነን፣ የውርደት ሞት የሆነውን ሞት በመቀበል ደግሞ ወደ ከበረው ሕይወት እንደገና መለሰን" ብሏል፡፡[63] ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያም "ዮሐንስ መጥምቅ እንዳለው ጌታችን አማናዊ በግ ነው፤ የዓለምን ኃጢአት ያስወገደና የፍጥረትን እጥፊ ያጠፋ ነው፡፡ ስለ ሁሉ በመሞቱ ሞታችንን ያጠፋ ዘንድና በእኛ ላይ የነበረውን መርገም ያስወግድ ዘንድ አማናዊው በግ፣ ንጹሑ መሥዋዕት እርሱ ወደ መታረድ ተወሰደ፡፡ በዚህም 'አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ' የሚለው ቅጣት ይወገድና ሁለተኛው አዳም ከመሬት ሳይሆን ከሰማይ ይገለጥ ዘንድ ነው" ብሏል፡፡ ዘፍ. 3፥19 ፤ 1 ቆሮ. 15፥47[64]

ጌታችን እኛ ከሞትና ከርግመት እንድን ዘንድ ራሱን የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ፤ "ክርስቶስም ደግሞ እንደ ወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ ሰጠ" እንዲል፡፡ ኤፌ.5፥2 ክርስቶስ የመጣው ከኃጢአት ብቻ ሳይሆን ከሞትም ሊያድነን ነው፡፡ በሞት የደረሰብንን የነፍስና የሥጋ መለያየት ያድን ዘንድ ሥጋችንንና ነፍሳችንን ተዋሐደ፡፡ ለዚህም መድኃኒታችን ነፍሱና ሥጋው በሞት ጊዜ እንዲለያዩ ፈቀደ፡፡ሆኖም መለኮት

[62] St. John Chrysostom, *P.G.* 61:700, cols. 652, 653

[63] *Long Rules*, Question 2.4;*P.G.* 31:916A.

[64] ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፣ ትርጓሜ ወንጌል ዮሐንስ

ከሁለቱም ጋር - ከሥጋውና ከነፍሱ ጋር - የተዋሐደ ስለሆነና ስለማይለይ ሞት ሥጋውንም ሆነ ነፍሱን ይይዛቸው ዘንድ አልቻለም፤ ምክንያቱም መለኮት ከሁለቱም ጋር ተዋሕዷልና፡፡ ከሦስት ቀን በኋላም ቅድስት ነፍሱንና ክቡር ሥጋውን በትንሣኤ እንደገና አዋሓዳቸው፡፡ ስለዚህም ሞትን አጠፋው፡፡

በጌታችን ሞት ሞት ድል ሆነ፣ ሲኦል ተመዘበረ፣ መቃብር ተከፈተ፡፡ ለዚህም ምስክሮችና በኩራት ይሆኑ ዘንድ በኢየሩሳሌም ሞተው ተቀብረው ከነበሩት ቀደምት ወገኖች መካከል የተወሰኑት ከመቃብር በመነሣት ለሰዎች እንዲታዩ አደረጋቸው፡፡ በቅዱስ ወንጌል "ከትንሣኤውም በኋላ ከመቃብሮች ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ ገቡና ለብዙዎች ታዩ" እንደ ተባለ፡፡ ማቴ. 27፥53 በሞቱ ሞትን ሻረው፤ "የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው" የተባለው ለዚህ ነው፡፡ 1 ቆሮ. 15፥26 ስለዚህም "አሁን ነፍሴ ታውካለች ምንስ እላለሁ? አባት ሆይ፥ ከዚህ ሰዓት አድነኝ። ነገር ግን ስለዚህ ወደዚህ ሰዓት መጣሁ" አለ። ይህም ማለት ጌታችን ሰው የሆነውና ወደ ሕማማቱ የገባው ስለ እኛ እስከ ሞትና መቃብር ድረስ የደረሰ መከራን በፈቃዱ ለመቀበል መሆኑን ነው፡፡ ዮሐ. 12፥27 ቆላ. 1፥20፤ የሐዋ. 20፥28 ፤ ሮሜ 5፥9 ፤ ኤፌ. 1፥7 ፤ ቆላ. 1፥14 ፤ ዕብ. 9፥22 ፤ ራእ. 1፥5-6 ፤ ራእ. 5፥9

የሰው ልጅ *"በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ"* ተብሎ አስቀድሞ ተነግሮት የነበረው የሞት ማስጠንቀቂያ በገቢር ተፈጽሞበት፣ በሰውነቱ ላይ ሞት ነግሦበት የሞት ተገዢ ሆኖ ነበር፡፡ ዘፍ. 2:17 በሕይወተ ሥጋ እያለም ኑሮው በጽላሎተ ሞት (በሞት ጥላ ሥር) ውስጥ የወደቀና በሞት ስጋትና ፍርሃት የታጠረ፣ ሲሞትም ነፍሱ በጻዕር ተለይታ ሥጋው ወደ መቃብር ነፍሱ ወደ ሲዖል በመውረድ በጭንቅና በመከራ ይኖር ነበር፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የሚስማማውን የእኛን ሥጋ በመዋሓድ ሞታችንን ሞቶ በሞቱ ሞትን አጠፋልን፣ የእርሱን ሕይወት ለእኛ ሰጠን፣ ሞትን በትንሣኤ ለወጠልን፣ የመቃብርን ይዞ የማስቀረትና ሰውነታችንን የማፍረስና የመለወጥ ኃይል ድል በማድረግ በመቃብር ተይዞ ፈርሶ በስብሶ መቅረትን አጠፋልን፡፡

በብሉይ ኪዳን የነበሩ ወገኖቻችን የሚኖሩት በሞት ፍርሃት ውስጥ ነበር፡፡ ሲሞቱም በጻዕርና በመከራ ነበር፡፡ ነቢዩ ዳዊት ይህን በዚያን ዘመን የነበረውን ፍርሃተ ሞት ሲገልጽ እንዲህ ይላል፦

> ወደንገጸኒ ልብየ በላዕሌየ ወመጽአኒ ድንጋጼ ሞት ፍርሃት ወረዓድ አኃዘኒ ወደፈነኒ ጽልመት ወእቤ መኑ ይሁበኒ ክንፈ ከመ ርግብ እሰርር ወአእርፍ - ልቤ በላዬ ተናወጠብኝ፣ የሞት ድንጋጤም ወደቀብኝ፣ ፍርሃትና እንቅጥቅጥ መጡብኝ፣ ጨለማም ሸፈነኝ፣ በርሬ ዐርፍ ዘንድ እንደ ርግብ ክንፍን ማን በሰጠኝ? መዝ. 54:4-7

ልበ አምላክ የተባለ ዳዊት በመዝሙሩ እንዲህ አድርጎ የገለጸው በዘመኑ እሪት ሰው ሁሉ በሞት ፍርሃትና ጭንቀት ውስጥ የነበረ መሆኑን ነው፡፡ ይህን የሰውን ልጅ ሲያስፈራና ሲያስደነግጥ የኖረውን ሞት ከሥሩ ነቅሎ ያጠፋልንና ያስወገደልን ዘንድ ክብር ምስጋና ለዘለዓለሙ ለእርሱ ይሁንና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆነልን፡፡ ሐዋርያው *". . . እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፣ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፣ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነፃ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ" እንዳለ፡፡ ዕብ. 2:14-15*

ስለሆነም ክርስቶስ በሞቱ ድል ካደረገው ወዲህ ሞት ኃይሉን ያጣ ደካማ፣ የቀድሞ አስፈሪነቱ ቀርቶ በክርስቲያኖች ዘንድ መሳለቂያና ወደማያልፈው ዓለም መሄጃ መንገድ ሆኗል፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ እንደ ገለጸው በዘመነ ክርስትና ሞት ጥፍሩ እንደ ወለቀ፣ ጥርሱ እንደ ረገፈና ኃይሉ እንደ ደከመ፣ ከዚህም የተነሣ የሕፃናት መጫወቻ እንደ ሆነ አንበሳ፤ እንዲሁም መርዙ እንደ ወጣና ምንም ጉዳት ማድረስ እንደማይችል እባብ ሆኗል፡፡

ሞት በሰው (በአዳም) በኩል መጥቶ በሰው ላይ እንደ ነገሠ ሰው በሆነው የእግዚአብሔር ቃል በዳግማዊ አዳም ተወገደ፣ ትንሣኤ ሕይወት ተገኘ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኗልና፡፡ ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና" እንዳለ፡፡ 1 ቆሮ. 15፥21-22

ስለሆነም ከጌታችን ሞትና ትንሣኤ ወዲህ ባለው ዘመን እስከ አሁን ድረስ፣ ወደፊትም እስከ ኅልቀተ ዓለም ድረስ ሰው የሚሞተው *"አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ"* በሚለው በቀደመው ፍርድ ለኩነኔ አይደለም፤ ለትንሣኤ ነው እንጂ፡፡ ከአሁን በኋላ እንደ ቀድሞው ለኩነኔ አንሞትም፤ ነገር ግን ከሞት ተነሥቶ የሁሉን ትንሣኤ እንደሚጠብቅ ሰው በራሱ ጊዜ የሚያደርገውን ትንሣኤ ዘጉባኤን እንጠብቃለን፡፡ ዘፍ. 3:20 ፤ 1 ጢሞ. 6፥15

ቅዱስ ጳውሎስ ይህን *መሠረታዊ* የሆነውን የትንሣኤ ምሥጢር በተመለከተ በቀዳማይ ቆሮንቶስ *መልእክቱ* ላይ ግልጽ አድርጎ አብራርቷል፡፡ *"ነገር ግን ሰው፡- ሙታን እንዴት ይነሣሉ? በምንስ ዓይነት አካል ይመጣሉ? የሚል ይኖር ይሆናል፡፡ አንተ ሞኝ፣ አንተ የምትዘራው ካልሞተ ሕያው አይሆንም"* በማለት ዘር ካልተዘራና በአፈር ውስጥ ካልሞተ ሕያው ሆኖ ለመብቀልና ለማፍራት እንደማይችል ሁሉ የሰው ሞትም እንዲሁ በሐዲስ ሰውነት ለመነሣት *መሆኑን* አስረዳ፡፡ 1 ቆሮ. 15:35-36 *መቃብርም* ለዘለዓለም በዚያው ውስጥ ይዞ የሚያስቀረን ሳይሆን እስከ ትንሣኤ ድረስ የምንቆይበትና ከዚያም የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን፣ የሚሞተው የማይሞተውን ለብሶ የሚነሣበት ነው፡፡ በዚያን ጊዜም በኃጢአት ምክንያት ከሰው ተፈጥሮ በኋላ የመጣው *"የኋለኛው ጠላት" - ሞት"* - ድል ይነሣል፡፡ 1 ቆሮ. 15:26 እሳት የሚኖረው የሚቃጠል ነገር እስካለ ድረስ ብቻ እንደ ሆነ ሁሉ ሞትም ከትንሣኤ በኋላ የሚሞት ሰውነት ስለማይኖር "ይሞታል"፤ ለዘለዓለምም ይጠፋል፡፡ ይህን ነው ሐዋርያው በመልእክቱ እንዲህ በማለት የገለጸው፡-

> . . . *ሙታንም* የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ፤ እኛም እንለወጣለን፡፡ ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ፤ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና፡፡ ዳሩ ግን ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሲለብስ፤ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ በዚያን ጊዜ፡- ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል፡፡ 1 ቆሮ. 15:51-55

በኃጢአት ምክንያት የእግዚአብሔር ልጅነታችንን አጥተን የዲያብሎስ ባሪያ ሆነን ነበር፡፡ ጌታችን ግን በቸርነቱ ያን ባርነታችንን አስወግዶ የልጅነትን ጸጋ ሰጠን፡፡ የጸጋ ልጅነቱንና ክብሩን አጥቶ በባርነት ውስጥ ሆኖና ተዋርዶ ለነበረው የሰው ልጅ ዳግመኛ ከእግዚአብሔር የሚወለድበትንና ልጅነትን የሚያገኝበትን ጥምቀትን ሰጠው፡፡ ይህ የልጅነት ጸጋም ለሌሎች ከእግዚአብሔር ለሚገኙ ጸጋዎች ሁሉ *መሠረት* ነው፡፡ ልጅ ከሆነ ዘንድ የአባቱን ንብረት ለመውረስ ይችላልና፡፡ ይህንም የአባትና የልጅነት ግንኙነት በውስጡ የሚያደርበት መንፈስ ቅዱስ *እንዲመሰክርለት* አደረገ፡፡ *"የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል"* እንዳለ፡፡ ሮሜ. 8:16 እንዲሁም ይኸው ሐዋርያ፡- *"ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ፡፡ ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም"* ይላል፡፡ ገላ. 4:6 ስለሆነም ከእንግዲህ የባርነት መንፈስ ሳይሆን "አባ አባት" ብለን የምንጠራበትን የልጅነት መንፈስ ሰጠን፡፡ ሮሜ 8:15 "አባታችን ሆይ" ብለን እንድንጠራውም ፈቀደልን፡፡

እንዲሁም "ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ ባሪያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፣ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፤ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄያችኋለሁና" በማለት በኃጢአት በተፈጠረ የጠብ ግድግዳ ምክንያት ከምሥጢሩ ርቀን ከአንድነቱ ተለይተን በባርነት እንኖር የነበረውን ሁኔታ አስወግዶ የዕርቅና የልጅነት መገለጫ የሆኑትን ፈቃዱን ማወቅንና ከባርነት ነፃ መውጣትን ሰጠን፡፡ ዮሐ. 15:15 *"የፈቃዱን ምሥጢር አስታውቆናልና"* ያለው ለዚህ ነው፡፡ ኤፌ. 1:9

ስለሆነም መዳን ስንል በመጀመሪያ በሰው ኃጢአት ምክንያት በባሕርያችን ደርሶብን የነበረውን ነገር ሁሉ - ሞትን፣ ርግመትን፣ ጉስቁልናን፣ ባርነትን . . . ሁሉ - አስወግዶልን፣ በአንጻሩ ደግሞ ሕይወትን፣ ልጅነትን፣ ኢመዋቲነትን ሰጠን ማለት ነው፡፡ ይህ ግን አንዱ እንጂ ብቸኛው አይደለም፡፡

2) *ፈጣሪውን እንዲያውቅ መሆን፣*

እግዚአብሔር ሰውን በመልኩና በአርአያው የፈጠረው ሩቅ ያልሆነውንና በእርሱ ዘንድ ያለውን የፈጣሪውን አርአያ እያሰበና እየተመለከተ በፍቅሩ ሆኖ በተዘክሮው ጸንቶ እንዲኖር ነበር፡፡ ሰው ግን የተደረገለትን ታላቅ ነገር ረስቶ በጸጋው መጠቀምን ትቶ በአርኣያውና በመልኩ የፈጠረውን እግዚአብሔርን ረሳ፡፡ መርሳት ብቻም ሳይሆን እርሱን ያገለግሉትና ይጠቀምባቸው ዘንድ የተፈጠሩለትን ከእርሱ በታች ያሉትን የተለያዩ ፍጥረታትንና ቁሳ ቁሶችን አመለካቸው፣ ተገዛላቸውም፡፡ በፈጣሪ ፋንታ ለፍጡር ተንበረከከ፤ ከዚህም በላይ የእግዚአብሔርን ክብር ለዕቃውና ለድንጋዩ፤ ለቁሳቁሱ ሁሉ ሳይቀር ሰጠ፡፡ ከዚህም ወደ ባሰ ሄዶ "ውኃ የሚወስደው ሰው ዐረፋ ይዞ ለመትረፍ ይሞክራል" እንደሚባለው ሆነና የሰው ልጅ ኢጋንንትን እንኳ እስከ ማምለክ ደረሰ፡፡ በጨለማ የተቀመጠ ሰው አገኝ አጣውን እንደሚዳስስ እንዲሁ ሳይመርጥ ያገኘውን ሁሉ የሚያመልክ ሆነ፡፡ ሮሜ 1:19-25 እርሱ ሊገዛቸውና ሊያገለግሉት፣ እንዲሁም የፈጣሪውን ሀልውናና ሥራ ለማወቅ እንዲረዱት ለአንክሮና ለተዘክሮ የተፈጠሩለትን ፍጥረታት አመለካቸው፡፡

ነቢዩ ይህን በተመለከተ በማዘንና በመገረም እንዲህ ይላል፡-

> የዝግባን፣ የዞጲንን፣ የኮምበልንና የጥድን ዛፍ ይተክላል፣ ዝናብም ያበቅለዋል፡፡ ለሰውም ማገዶ ይሆናል፤ ከእርሱም ወስዶ ይሞቃል፣ እንድዶም እንጀራ ይጋግርበታል፤ ከእርሱም አምላክ አበጅቶ ይሰግድለታል፣ የተቀረጸውንም ምስል ሠርቶ በእርሱ ፊት ይንበረከካል፡፡ ግማሹን በእሳት ያቃጥላል፣ ሥጋም ይጠብስበትና ይበላል . . . የቀረውንም እንጨት አምላክ አድርጎ ምስል ይቀርጽበታል፤ በፊቱም ተጎንብሶ ይሰግዳል፣ ወደ እርሱም እየጸለየ፡- አምላክ ነህና አድነኝ ይላል፡፡ ኢሳ. 44:12-17

ሰው እንዲያ ሥነ ፍጥረትን ሲያመልክ በአንጻሩ የራሱን አስገኚና ሥነ ፈጥረትን ሁሉ የፈጠረውን እግዚአብሔርን ግን ረሳው፡፡ የሰው ልጅ በጊዜያዊ ተድላ ደስታና በኢጋንንት ምትሐት በመታለል ራሱን ወደ እውነት መምራት አልቻለም፡፡

ሰው እንዲህ ፈጣሪውን አውቆ እንዲኖር ለክብር ተፈጥሮ ሳለ ከእርሱ በታች ያሉትን እስከ ማምለክ ድረስ ተዋርዶ፣ ፈጣሪውን ማወቅ ተስኖት በነበረበት ሁኔታ እንዲቀር እግዚአብሔር አልፈቀደም፡፡ ይህም ከቸርነቱ የተነሣ ነው፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ሰው በመሆን ሰውን እርሱን እንዲያውቀው አደረገ፡፡ ሰዎች አወቅን፣ ተጠበብን እያሉ ነገር ግን የጥበብ መጀመሪያ የሆነውን ፈጣሪያቸውን ማወቅ ስላልቻሉ፣ የሰው ጥበብና ዕውቀት ሰፊ ጊዜ ተሰጥቶት (ቅድመ ሥጋዌ የነበሩት ብዙ ሺህ ዓመታት) ተፈትኖ ስለ ወደቀ አምላክ በሚታይ ሥጋ በመገለጥ ራሱን ለሰው ገለጠ፡፡ 1 ጢሞ. 3:16 ሐዋርያው *"ዓለም በጥበብዋ እግዚአብሔርን ስላላወቀች በስብከት በሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኗልና"* ያለው ለዚህ ነበር፡፡ 1 ቆሮ. 1:21

ቅዱስ አትናቴዎስ የቃልን ሰው መሆን (በእንተ ተሠግዎተ ቃል) በተናገረበት ድርሳኑ ስለዚህ ጉዳይ ሰፋ አድርጎ በመተንተን እንዲህ ይላል፡-

> ሰዎች እግዚአብሔርን ማሰብ ትተው ለራሳቸው መዋትያን ሰዎችንና አጋንንትን አምላክ አድርገው ማምለካቸውን ባየ ጊዜ ሰውን ወዳጅ የሆነው የዓለም መድኃኒት እግዚአብሔር ወልድ ሥጋን ተዋሐደ፤ እንደ ሰውም በመመላለስ ሰው እርሱን ወደ ማወቅ እንዲመለስ አደረገ፡፡ ፍጥረትን በመፍራት ፍጥረታትን አምላክ ብለው እስኪያመልኩ ከደረሱ የፍጥረቱ ባለቤት ሰው ሆኖ ሲመጣ

> ያምኑ ዘንድ፣ ሐሊናቸው ወደ ሰዎች አዘንብሎ አማልክት ናቸው እስከ ማለት ከደረሱ የእርሱን ሥራውን አይተውና ሌሎች ፍጡራን ካደረጉት ጋር አነጻጽረው ከዚያ በፊት እንደ አማልክት ያከብሯቸው ለነበሩት ሁሉ ጌታቸውና ፈጣሪያቸው መሆኑን አውቀው አምልኮታቸውን ወደ እርሱ እንዲመልሱ፣ ርኩሳን መናፍስትን ወደ መፍራት፣ ማመንና ማምለክ ያዘነበሉትንም እነዚያን ክርስቶስ ሲያባርራቸውና ሲያስወጣቸው አይተው እርሱ ብቻ አምላክ እንደ ሆነና ርኩሳን መናፍስት ግን ምንም አለመሆናቸውን እንዲረዱ ነው፡፡
>
> የሞቱ ሰዎችን (ሙታንን) እንደ ጀግናና እንደ አማልክት የሚያከብሩና የሚያመልኩም ቢሆኑ የጌታን ትንሣኤ አይተው የእነዚያን ሐሰትነትና ጌታችን የፍጡራን ብቻ ሳይሆን የሞት እንኳ ጌታ መሆኑንና ብቸኛው አምላክ እርሱ መሆኑን ያውቁ ዘንድ፡፡ ስለዚህ ምክንያት ጌታችን ሰው በመሆን ተገለጸ፣ የሰዎችን ሥራ ኢምንት የሚያደርግ ሥራ ሠራ፣ ሰውን በማንኛውም መንገድ ቢስት ይመልሰውና ያድነው ዘንድ፣ እውነተኛ አምላክ እርሱ ብቻ መሆኑን ያሳውቀው ዘንድ፡፡ ይህም አምላክ ሰው የሆነበት ሁለተኛው ምክንያት ነው፡፡ (በእንተ ተሠግዎተ ቃል፣ ቁ. 11-16)

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው በመሆን የፈጠረንና የምናመልከው አምላካችን ግን መሆኑን እኛን ሊገባን በሚችለው መጠን ነገረን፡፡ ከትምህርቱና ከተአምራቱ ሁሉ አስቀድሞ ባደረገው በጥምቀቱ እግዚአብሔር አምላካችን በአንድነቱ ውስጥ ያለውን ልዩ ሦስትነቱን ገለጠልን፡፡ አብ በደመና ሆኖ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" ብሎ ሲናገር፣ ወልድ በዮርዳኖስ ተጠምቆ ከውኃው ሲወጣ እና እግዚአብሔር አብ "ልጄ" ብሎ ሲመሰክርለት፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በርግብ አምሳል በጌታችን ራስ ላይ ሲያርፍ ታየ፡፡ ቅዱስ ወንጌል እንዲህ ሲል እንደ ገለጸው፣ - "ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ።" ማቴ. 3፥16-17

ልዩ የሆነ የአካል ሦስትነትን በጥምቀቱ እንደ ገለጠልን ሁሉ፣ "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው . . ." በማለት የስም ሦስትነትንም ገለጠልን፡፡ ማቴ. 28፥19 እንዲሁም ወንጌላዊው "መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው" በማለት ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው በመሆኑ ያገኘነውን ታላቅ ጸጋ ተናገረ፡፡ ዮሐ. 1:18 ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ "ጌታ ሆይ፣ አብን አሳየንና ይበቃናል" ባለው ጊዜ ጌታችን "አንተ ፊልጶስ፥ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቷል፤ እንዴትስ አንተ አብን አሳየን ትላለህ? እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም፤ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል። እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፤ ባይሆንስ ስለ ራሱ ስለ ሥራው እመኑኝ" በማለት ወልድን በማየታችን አብንም ያየነውና ያወቅነው መሆኑን ነገረን፡፡ ዮሐ. 14፥8-11

ይህን ሁሉ አጠቃልሎ ራሱ መድኃኒታችን "ሁሉም ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ተብሎ በነቢያት ተጽፏል፤ እንግዲህ ከአብ የሰማ የተማረም ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል" አለ፡፡ ዮሐ. 6፥45 ይህ ማለት ሰዎች ራሱ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ እንደሚያስተምራቸው አስቀድሞ በነቢያት ተነግሮ ነበር፤ አሁን ያ የተነገረው ተስፋ ደርሶ እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆኖ ስላስተማራቸው ከሌላ ሳይሆን ከራሱ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ የተባለው ትንቢት መፈጸሙን መናገሩ ነበር፡፡ ይህም ማለት እንደ ቀደመው ዘመን (ብሉይ ኪዳን ዘመን) በሥነ ፍጥረትና በአምላካዊ መግቦቱ፣ ኋላም በሕጉና በነቢያት እንዳስተማረው ማስተማር ያለ ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ ስለ ራሱ ያስተማረን መሆኑን ነው፡፡ ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ የጌታችንን ማስተማር ሲጽፍ "አፉንም ከፍቶ አስተማራቸው" ያለው ይህን የሚያመለክት ነው፡፡ ማቴ. 5፥2 ጥንቱንም አንድ ሰው ሲናገር አፉን ሳይከፍት አይናገርም፣ ነገር ግን እዚህ ላይ እንዲህ ማለቱ በነቢያት ወይም በመልእክተኛ ሳይሆን ራሱ አካላዊ ቃል ያስተማረን መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው፣ ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን" ያለው ይህን ምሥጢር ነው፡፡ ዕብ. 1፡1-2 ይህን ሁሉ አጠቃልሎ መድኃኒታችን ይህን ራሱ አምላክ ሰው ሆኖ ያስተማረ መሆኑንና አይሁድ ግን አለመቀበላቸው አሳዛኝ መሆኑን ሲናገር "ሌላ ሰው ያላደረገውን ሥራ በመካከላቸው ባላደረግሁ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን እኔንም አባቴንም አይተውማል፣ ጠልተውማል" አለ፡፡ ዮሐ. 15፡24

ይህ ጸጋ በመዳናችን ውስጥ ያለው ሚና ቀላል አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሰው ፈጣሪውን ሳያውቅ እንዴት ሊድን ይችላል? ያዳነውንስ ካላወቀ ምን ሕይወት ይኖረዋል? ይህን ያደረገለትን አምላክ ካላወቀና ከእርሱ ጋር እንዲኖር የሚረዳውን ትምህርትና ሕይወት ሳይሰጠው እንደ ዘመን ብሉይ በድንግዝግዝ የሚኖር ከሆነ ከኃጢአትና ከቅጣት በመዳኑ ብቻ ምን ይጠቀማል? ምክንያቱም መዳን ስንል ከእግዚአብሔር ጋር መኖር፣ ከእግዚአብሔር ጋር በጸጋ አምላካዊ ኅብረትና ሱታፌ እንዲኖረው መሆን ማለት እንጂ እንዲሁ ከቅጣት እንደ ምንም አንድ ጊዜ ላምልጥ እንጂ ከዚያ በኋላ የራሱ ጉዳይ እንደሚል ወንጀለኛ ዓይነት አስተሳሰብ አይደለምና፡፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ "እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን፣ የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት" ያለው ለዚህ ነው። ዮሐ. 17፡3

ስለዚህ መዳን ስንል እግዚአብሔርን ማወቅም ስለሆነ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካችንን እናወቅ ዘንድ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን፡- ትምህርቱን፣ ተአምራቱን፣ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን መላክን - ያደረገው ለዚህ ነው፡፡ መዳን ማለት በመስቀል ተሰቅሎ የኃጢአታችንን ዕዳ መክፈልና ሞታችንን ማጥፋት ብቻ ቢሆን ኖሮ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ማስተማርና ተአምራት ማድረግ ሳያስፈልገው ሰው እንደ ሆነ ወዲያውኑ ወይም ሠላሳ ዓመት እንደ ሞላው ወዲያውኑ ይህን ማድረግ ይችል ነበር፡፡ ሆኖም ግን እርሱን ማወቅ ለመዳናችን በእጅጉ ያስፈልገን ስለ ነበርና የመዳናችን አካል ስለሆነ ጌታችን ትምህርቱንና የመዳን ተግባሩን ከዚህ እንጻርም አደረገ፡፡

በአጠቃላይ የሰው ልጅ በተሰጠው የመዳን ጸጋ ለመጠቀም ያዳነውን አምላኩን ማወቅ እንዲችል አብርሆት ያስፈልገው ነበር፡፡ አለበለዚያ እግዚአብሔር ሰውን የማዳን ድርሻውን ቢፈጽምም እንኳ ሰው እንደ ጥንቱ በጥፋት መንገድ ከመቀጠል የሚመልሰው ነገር አልነበረም፡፡ ስለዚህም ለሰዎች የተሰጣቸው የመዳን ጸጋ ምን እንደሆነ፣ አዳኙ ማን እንደ ሆነ፣ እንዴት መኖር እንዳለበት፣ ወዘተ ማወቅ ነበረበት፡፡ ጌታችን ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ሳያቋርጥ ደቀ መዛሙርቱን ያስተማረውና እነርሱንም ወደ ዓለም ሁሉ ሂደው እንዲያስተምሩ የላካቸው ለዚህ ነበር፡፡ እግዚአብሔርን ማወቅ ስንልም እንዲሁ ጽንሰ ሃሳባዊ እውቀት ሳይሆን ከእርሱ ጋር መቀራረብን፣ በአባትና በልጅ መካከል እንዳለው መቀራረብና መተዋወቅ ዓይነት ሕይወታዊ እውቀት ነው፡፡

3) ሐዲስ ተፈጥሮ

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው በመሆኑና የእኛን ባሕርይ ገንዘብ በማድረጉ ምክንያት ወድቆና ጎስቁሎ የነበረውን ባሕርያችንን አድሶታል፣ ከወደቀበትም አንስቶታል፣ የረከሰውን ቀድሶታል፣ የደከመውን ጽኑ አድርጎታል፡፡ ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ዲያብሎስ አታልሎትና አሸንፎት የነበረውን ያንኑ የእኛን ባሕርይ ተዋሕዶ በገዳመ ቆሮንቶስ በሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ተፈትኖ ድል አድራጊ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ጌታችን ሰው የሆነበት ዓላማ የኃጢአታችንን ዋጋ በመክፈል እኛን ከዕዳ ነጻ ማድረግ ብቻ ቢሆን ኖሮ ያን ያህል ጊዜ እየተዘዋወረ ማስተማር ሳያስፈልገው ተሰቅሎ በሞቱ ሞታችንን መደምሰስ ይችል ነበር። ነገር ግን ከዚያ ባሻገር በውድቀታችንና ከእርሱ በመለየታችን ምክንያት በባሕርያችን ላይ የደረሰብን ጉስቁልናና ድካም ተወግዶ ባሕርያችን በሐዲስ ተፈጥሮ እንደገና መፈጠርና "አዲስ ሰው" መደረግም ያስፈልገው ነበር ።

በውድቀታችን ባሕርያችን ጨርሶ አልተለወጠም፤ ሌላ ወደ መሆንም አልፈለሰም። ነገር ግን ባሕርያችን ጎስቋሎ፣ የተሰጠን ጸጋና ኃይል ደክሞ፣ ባሕርያችን (ሰብእናችን) ዲያብሎስ በቀላሉ የሚያሸንፈውና ወደ ስሁተት የሚመራው ሆኖ ነበር። ስለዚህም ለመዳናችን ይህ ሁኔታ መስተካከል ስለ ነበረበት መድኃኒታችን ይህን አድርጎልናል። ጌታችንን የቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ ቀርበው፡- "እኛና ፈሪሳውያን ብዙ ጊዜ የምንጦመው፥ ደቀ መዛሙርትህ ግን የማይጦሙት ስለ ምንድር ነው?" ብለው ለጠየቁት ጥያቄ "በአረጀ ልብስ አዲስ እራፊ የሚያኖር የለም፤ መጣፊያው ልብሱን ይቦጭቀዋልና፥ መቀደዱም የባሰ ይሆናል። በአረጀ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር የለም፤ ቢደረግ ግን፥ አቁማዳው ይፈነዳል፥ የወይን ጠጁም ይፈሳል አቁማዳውም ይጠፋል፤ ነገር ግን አዲሱን የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ያኖረዋል፥ ሁለቱም ይጠባበቃሉ" በማለት የመለሰላቸው ለዚህ ነበር። ማቴ. 9፡14-17

በአዲስ ልብስና በአዲስ የወይን ጠጅ የተመሰለው ለእኛ የሚሰጠን የመዳን ጸጋ ሲሆን በአሮጌ ጨርቅና በአሮጌ አቅማዳ የተመሰለው ደግሞ በአዳም ኃጢአት ምክንያት ያረጀውና የጉሰቀለው ባሕርያችንና ሰውነታችን ነው። ባረጀ ልብስና ባረጀ አቅማዳ በተመሰለው በመጀመሪያው አዳማዊ እኛነታችን ሆነን እርሱን ወደ መምሰል የሚወስዱንን ነገሮች ለመፈጸም አንችልም ነበር። ስለሆነም የሰው ልጅ ሁሉ አዲሱን የመዳን ጸጋ መቀበልና በእርሱ መጠቀም የሚችል ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ባሕርዩ በሐዲስ ተፈጥሮ መፈጠርና አዲስ ሰው መሆን፣ መታደስና እንደገና መፈጠር ነበረበት ማለት ነው። ስለዚህ በሚሰጠው የመዳን ጸጋ ለመጠቀም በመጀመሪያ አሮጌው አዳማዊ ሰውነት መታደስና በዳግማዊ አዳም በኢየሱስ ክርስቶስ እንደገና መፈጠር እንዳለበት አስተማረን።

መድኃኒታችን ሰው ሆኖ "ሰው እንደ ገና ካልተወለደ" በማለት ያስተማረው ለሁለተኛ ጊዜ የሚሆን ልደተ ሥጋን ሳይሆን ሰው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል እንደ ገና ካልተወለደና ካልታደሰ ማለቱ ነው። ዮሐ. 3፡3 ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን" በማለት፤ እንዲሁም "ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፏል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል" በማለት ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋዌውና በማዳኑ ሁሉንም ነገር አዲስ ያደረገ መሆኑን ይናገራል። ሮሜ 6፡4 ፤ 2 ቆሮ. 5፡17 ይህን ሐዲስ ተፈጥሮ እያንዳንዱ ሰው ገንዘብ ሊያደርገው የሚገባ ስለመሆኑም ሲናገር፡- "በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት መሆን ይጠቅማል እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና" በማለት ያሳስበናል። ገላ. 6፡15 እንዲሁም "ለእውነትም በሚሆን ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ" ይላል። ኤፌ. 4፡24

ስለሆነም ልዩ ሊቀ ካህናት ሆኖ ኃጢአታችንን ከማሥተሰረዩ ጋር ሁለንተናዊ ማንነታችንን አድሶታል። ይህም ማለት መዳን ስንል ከቅጣት መዳን ብቻ ሳይሆን ሐዲስ ተፈጥሮንም የሚጨምር ነው ማለት ነው። የሰው ልጅ በጌታችን ሥጋዌ ያገኘው መዳን ሐዲስ ተፈጥሮን - አዲስ ፍጥረት መሆንንም ነው።

የመጀመሪያው ፍጥረታችን ራስ ቀዳማዊ አዳም ነበር፡፡ ሆኖም የእርሱ ራስነት በሰብአዊ ባሕርያችን ላይ ብልየትንና ጥፋትን ስላስከተለ በዚያ ሂደት መቀጠል ወደ ሕይወት ሳይሆን ወደ ሞትና ወደ ጥፋት የሚወስድ ነበር፡፡ ስለሆነም ከዚያ ይህን ካስከተለብን ከመጀመሪያው ራሳችን አውጥቶ ወደ ሕይወትና ክብር የሚወስድ አዲስ ራስ ያስፈልገን ነበር፤ ጌታችን ሰው ሆኖ "ዳግማዊ አዳም፣ ወልደ እጓለ እመሕያው" የተባለው ለዚህም ነው፡፡ አሁን ራሳችን የመጀመሪያው አዳም ሳይሆን ዳግማዊ አዳም ክርስቶስ ነው፡፡ ቅዱስ ኢትናቴዎስ "ኀደግነ አበ ቀዳማዌ ዘቦቱ ማሰነ ዘውእቱ አዳም - የተጎዳንበትን የመጀመሪያውን አባታችንን ትተነዋል፤ እርሱም አዳም ነው" ያለው ለዚህ ነው፡፡ በዳግማዊ አዳም በኢየሱስ ክርስቶስ የሐዲስ ተፈጥሮ ሂደት ዳግመኛ ያልተፈጠረ ሰው ለእርሱ ራሱ አሁንም የቀደመው አዳም ስለሆነ ገና በጥፋትና በሞት ውስጥ ያለ አሮጌው ሰው ነው፡፡ በመዳን ጸጋ ውስጥ ይህ ሐዲስ ተፈጥሮ በጣም መሠረታዊ ነገር ነው፡፡

ከላይ እንዳነሣነው ቅዱስ አትናቴዎስ ኃጢአት ሁለት መሠረታዊ ውጤቶችን (ጉዳቶችን) ያስከተለ ስለ መሆኑ ይናገራል፡፡ እነዚህም የሰው ሕይወት መጎስቆል እና ሰው በሞት ላይ መውደቁ ናቸው፡፡ ስለዚህ መዳን እነዚህን ሁለት ችግሮች መፍታት ይገባው ነበር፡፡ ማለትም የኃጢአት ውጤት የሆነውን ሞትንና ቅጣትን ማስወገድ እና የጎሰቆለውን ባሕርያችንን ማደስና በሐዲስ ተፈጥሮ መፍጠር ናቸው፡፡ በባሕርያችን የደረሰውን ለውጥ ለመመለስና እንደገና በሐዲስ ተፈጥሮ ለመፍጠር፣ የማይሞትና ዘለዓለማዊ ለማድረግ እግዚአብሔር ሰብእናችንን (ባሕርያችንን) መዋሐድና የራሱ ገንዘብ ማድረግ ነበረበት፡፡ አለበለዚያ ወደ ሰው ባሕርይ ውስጥ ዘልቀው የገቡት ሞትና ጉስቁልና አፍአዊ በሆነ ሁኔታ ሊወገዱና ሰውም ያጣው ሕይወት ሊመለስለትና ባሕርዩ ሊታደስለት አይችልም ነበር፡፡ መድኃኒታችን በሥጋዌ ምሥጢር ያደረገውም ይህን ነው፡፡ ስለዚህ በጌታችን ሥጋዌ ከሞት ቅጣት ነጻ የሆንን ብቻ ሳይሆን አዲስ ፍጥረቶችም ሆነናል፡፡

ሰው በበደለና ከእግዚአብሔር በተለየ ጊዜ በኃጢአቱ ምክንያት ወድቆና ጎስቁሎ፣ ደክሞና ዝሎ የነበረውን የእኛን ባሕርይ አካላዊ ቃል ስለ ተዋሐደውና የራሱ ገንዘብ ስላደረገው ከዚህ የተነሣ በሰውነቱ ላይ እንደ አረም በቅለው ሠልጥነውበትና ድል አድርገው ያስጨንቁትና ይገዙት በነበሩት በእኩያት ሕሊናትና በፍትወታት ላይ ሙሉ ኃይል አገኘ፡፡ ለኃጢአት ባሪያ ሆኖ መገዛቱ ቀርቶ ኃጢአትን የሚያሸንፍበት ኃይል አገኘ፡፡ ኃጢአትንና ፍትወታት እኩያትን የመቋቋምና የማሸነፍ ኃይልና ሥልጣን አገኘ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ፡- "ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን" በማለት የገለጸው ይህን ነው፡፡ እንዲሁም "አሁን ግን ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ ለእግዚአብሔር ተገዝታችሁ ልትቀደሱ ፍሬ አላችሁ" አለ፡፡ ሮሜ. 6:6 ፤ 20-22 ፤ 7:4-6

እግዚአብሔር በምሥጢራት አማካይነት ውስጣችንን የሚቀድሰውንና የሚያድሰውን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ባይሰጠን ኖሮ ቅድስናን ገንዘብ ማድረግ አንችልም ነበር፡፡ ባሕርያችን ባይታደስና እንደገና በሐዲስ ተፈጥሮ ባይፈጥረን ኖሮ በጎሰቆለውና በወደቀው ባሕርያችን የተቀበልነውን የሥርየተ ኃጢአት ጸጋ ለመጠቀምና በዚያው ለመቀጠልም አንችልም ነበር፡፡

ስለዚህም ባለፈው በደላችን ሥርየትን እንደ ሰጠን ለወደፊቱ ደግሞ በአዲስ ሕይወት እንመላለስ ዘንድ በሐዲስ ተፈጥሮ ፈጠረን፡፡ ከላይ እንደ ተገለጸው መድኃኒታችን በአዲስ እራፊና በአዲስ የወይን ጠጅ መስሎ የተናገረው እርሱ የሚሰጠውን የመዳን ጸጋ ሲሆን ያን መቀበልና መጠቀም ይችል ዘንድ አቁማዳው አዲስ መሆን አለበት ማለቱ ያን ጸጋ እግዚአብሔር መቀበልና መጠበቅ የሚችለው በሐዲስ ተፈጥሮ አዲስ የሆነ ሰውነት ብቻ መሆኑን ሲገልጽ ነው፡፡ ስለዚህ ስለ መዳን ስናስብ ስለ ወይኑ ብቻ ሳይሆን ስለ ወይኑ መያዣም (ስለ አቁማዳው) አዲስ መሆን አስፈላጊነት ነገረን፡፡ አንዱን ጥሎ የተመቸውን ብቻ አንጠልጥሎ መሮጥ አግባብ አይደለምና፤ የመናፍቃን ጠባይ የመሰላቸውን አንዱን ብቻ በማጕኽ ሌላውን መሸፈን ነውና ከዚህ ዓይነቱ ስህተት መራቅና መጠበቅ ይገባል፡፡

ከውድቀት ጋር ተያይዞ የሰው ልጅ ሕዝብና አሕዛብ ተብሎ ተለያይቶ ስለ ነበር ያን ሁሉ አጥፍቶ አንድ አዲስ ሰው የተባለ የራሱ አካል የሆነች ቤተ ክርስቲያንን ፈጠረ፡፡ በመስቀሉ ቤዛነትም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው የጠብ ግድግዳ ፈረሰ፡፡ እንዲሁም በሕዝብና በአሕዛብ የነበረው መለያየትም ተወገደ፤ አንድነትና ሰላም ተመሠረተ፡፡ "እርሱ ሰላማችን ነውና፤ ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ፤ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ" እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ፡፡ ኤፌ. 2፥14-15

ከዚህም ጋር ወደ እግዚአብሔርና ቅዱሳን አንድነት መመለስን ሰጠን፡፡ ሰው ከእግዚአብሔር አንድነት ተለይቶ የተሰፋ ቦታውን አጥቶ ከዓለመ መላእክት ወደ ዓለመ እንስሳት ተጥሎ ነበር፡፡ ክብር ምስጋና ይግባውና አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ ሰው ሆኖ ሰው ወደ ወደቀበት ወደዚህ ዓለም በመምጣትና በእንስሳት በረት በመወለድ የሰውን ልጅ ወደ ራሱ ኅብረትና አንድነት መለሰው፡፡ በዚህም መላእክት ከሰዎች ጋር በአንድነት፡- "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ - ክብር ለእግዚአብሔር በሰማያት ይሁን፤ ሰላምም በምድር፤ ለሰውም በጎ ፈቃድ" በማለት ሰው ወደ እግዚአብሔር በመመለሱ ደስታቸውን ገለጹ፡፡ ሉቃ. 2፥14

በዚህም ከቅዱሳን አንድነት ደመረን፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶስ በመስቀሉ ቤዛነት ጥልን ማስወገዱንና ሰላምን ማድረጉን ከገለጸ በኋላ የዚህን ተከታይ ውጤት ሲናገር እንዲህ አለ፡-

> እምይእዜሰ ኢኮንክሙ ነግደ ወፈላሲ አላ አንትሙ ሰብአ ሀገሪቶሙ ለቅዱሳን ወሰብአ ቤቱ ለእግዚአብሔር - እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮች እና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም፡፡ ኤፌ. 2:19

እንዲሁም በዕብራውያን መልእክቱ ይህንኑ በተመለከተ ማለትም የሰውን ወደ ቅዱሳን አንድነት መመለስ ሲናገር እንዲህ አለ፡-

> ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ተራራ ደርሳችኋል፤ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም፤ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፤ በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር፤ የሁሉም ዳኛ ወደ ሆነ ወደ እግዚአብሔር፤ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፤ የአዲስ ኪዳንም መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ . . . ደርሳችኋል፡፡ ዕብ. 12:22-24

ከመነሻቸው የተሳሳቱትና ከመጀመሪያውም በትክክለኛ መንገድ የማያምኑት ወገኖቻችን ተሐድሶዎች ግን መዳን ሲሉ ከላይ እንደ ተገለጸው በምልዓት ሳይሆን አንዱን ብቻ ነጥለውና አንጠልጥለው ከምንጮቻቸው ባገኙት ሕግ ነክ አመለካከት መሠረት ከእስር ቤት ስለ መውጣትና ከሕግ ቅጣት ስለ ማምለጥ ብቻ ያለውን በመደጋገም ነው፡፡ ለአብነትም እንዲህ የሚሉትን እናስታውስ፡-

◉ "ጽድቅ፤ መጽደቅ፡- ዕዳው የተከፈለለትና በዕዳ ከመጠየቅ የዳነ ለመሆኑ ማስረጃ ያቀረበውን ባለ ዕዳ የነበረ ተከሳሽ ጉዳይ ዳኛው መርምሮ ብይን በመስጠት ነጻ መሆኑን ያውጅለታል፤ ያጸድቀዋል፡ ፡ ዳኛው በባለ ዕዳው ስም የተመዘዘበው ዕዳ ለመከፈሉ የሚቀርበውን ማስረጃ መርምሮ ይቀበለዋል እንጂ አንተ ስላልከፈልከው፤ ሌላ ሰው (ዘመድ) ስላንተ ሆኖ የከፈለልህ በመሆኑ ማስረጃውን አልቀበልም አይልም፡፡ እንደዚሁም በኃጢአት ምክንያት በሕግ ተከሶ ከፍርድ በታች የነበረው ሰው በኃጢአት ዕዳ ከመጠየቅ የዳነ ወይም ነጻ የወጣ ለመሆኑ የሚያቀርበውን ስለ እርሱ የተከፈለውን የኢየሱስ ክርስቶስን የቤዛነት መሥዋዕት የእምነት ማስረጃ ብቁነት በማረጋገጥ 'ከተከሰሰከበት የኃጢአት ዕዳ ነጻ ነህ፤ አያስጠይቅህም' የሚለው ከመንፈስ ቅዱስና ከእግዚአብሔር ቃል ለእማኙ ሕሊና የሚሰጥ የብይን ማረጋገጫ ነው፡፡ ከኃጢአት ዕዳ ተጠያቂነት መዳኑ ሕጋዊነት ያለው ለመሆኑ ከመለኮታዊ ዙፋኑ የሚወጣ በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም የተረጋገጠ የጻድቅነት ውሳኔ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ኃጢአተኛው ከተበየነለት (ከጸደቀ) በኋላ ረታ ይባላል፡፡ ተከሳሽ ግን በዚህ ውሳኔ ተረታ ተፈረደበት ማለት ነው፡፡" (ሙራ ቁ. 11፤ ገጽ 15)

እንግዲህ መዳንን ለመግለጽ የተጠቀሙበት ይህ ሐተታ የፍርድ ቤት ችሎት ቃለ ጉባኤ ይመስል እንደሆነ እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸውን የእግዚአብሔር ማዳን በአግባቡ የሚገልጽ ግን አይደለም፡፡ ይህ የቀዱበት ፕሮቴስታንታዊ ምንጫቸው ሕግ ነክ አስተሳሰብ መገለጫ ነው፡፡ ከላይ የተመለከትነው የቅጣት ምትክ ቲዎሪ (Penal Substitution Theory) እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን መዳን የሚመለከት አይደለም፡፡ አምላካችን ያዳነን ነፍስና ሥጋችንን በመቀደስ፣ ቅድስናንና ፍጹምንትን ገንዘብ እንድናደርግ ክሂልና ኃይልን በመስጠት፣ በአዲስ ተፈጥሮ በመፍጠር፣ ወደ ቅዱሳን እንድነት በመመለስ፣ እርሱ አዲሱ ራሳችን በመሆን ሁሉ - በምልአት - እንጂ በሆነ መንገድ ከእስር እንዳመለጠና ከዚያ በኋላ ግብሩና ጠባዩ ይቀየርም አይቀየርም ጉዳዩ እንዳልሆነ ወንጀለኛ ሰው በሆነ ሁኔታ አይደለም፡፡

እንደዚሁም "ወደ ፍርድ ቀርቤ ይፈረድብኛል የሚል ፍርሃት የለብህም" (ጠማረ ጽድቅ፣ ገጽ 21) በሚለው አባባላቸውም ይህንኑ የመዳንን ትምህርት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግና በፍርድ ቤት ሂደት የማየት አቋማቸው ምን ያህል አስተሳሰባቸውን የገዛው መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ ይህ ቲዎሪ ምን ያህል አጥብቆ የተጠናወታቸው መሆኑን ለማየት የሚከተሉትን እንጨምር፡-

- "በኃጢአትህ ምክንያት ባንተ ላይ ሊያርፍ የነበረው የእግዚአብሔር ፍርድ ባንተ ላይ ማረፉና መፈጸሙ ቀረና ቤዛ ሆኖ በተሰጠህ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ በረፈ፡፡" (ሙራ ቁ፣ 7፣ ገጽ 20-21)
- "ጠበቃችን ተከራካሪና ተሟጋች ወይም አማላጅ ብቻም አይደለም፤ የኃጢአታችን ማስተስረያ ነው እንጂ፡፡ በእርሱ በኩል ለሚቀርብ ተናዛዥ ይህማ እኔ የተወጋሁለት የደማሁለት የቆሰልሁለት በመስቀል ጎዳና ሞትን የተቀበልሁለት መሆኑን ያመነ ኃጢአተኛ ነው፡፡ ስርየት በተሰጠበት ማስተስረያ ሊጠየቅ አይገባውም በማለት የኃጢአት ማስተስረያ የሆነበትን ማስረጃ በማሳየት ይሰፍ ያሰኛል ማለት ነው፡፡" (ሙራ ቁ. 8፣ ገጽ 30)

ይህ አባባል ፕሮቴስታንታዊ እንጂ ኦርቶዶክሳዊ አይደለም፡፡ ተሐድሶዎች እንደሚሉት ያለፈውም፣ የአሁኑም፣ የሚመጣውም ኃጢአታችን በሙሉ ጌታችን በመስቀል ላይ ሳለ ወደ እርሱ የተላለፈበትና ዕዳነቱን የከፈለበት ከሆነ ስለ ኃጢአታችን አንጠየቅም ማለት ነው፤ ምክንያቱም ምትካችን የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመታት አስቀድሞ ከፍሎታልና፡፡ ስለዚህ ኃጢአት አያስጠይቅም ማለት ነው፣ ምክንያቱም ማንኛውም ኃጢአት ገና ከመደረጉ በፊት ምትክ በሆነው በክርስቶስ አስቀድሞ ተከፍሎበታልና፡፡ እንዲህ ከሆነ ከዚህ አስተምህሮ የሚከተለው ድምዳሜ ወይም መላው የሰው ልጅ በሙሉ (አመነም አላመነም፣ ኃጢአት ሠራም አልሠራም) ይድናል የሚለው አስተሳሰብ (Universal salvation) ነው፤ አለበለዚያ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው ለመዳን ለመረጣቸው ለጥቂቶች ብቻ እንጂ ለመላው የሰው ልጅ በሙሉ አይደለም የሚለው አስተሳሰብ (John Calvin's 'limited atonement') ነው፡፡ ሆኖም ሁለቱም አስተሳሰቦች ስህተቶች ናቸው፡፡

የካልቪን ሃሳብ በቀጥታ የምትክ ቲዎሪ ውጤት ነው፡፡ ምክንያቱም የሰው ሁሉ ኃጢአት - ያለፈውም ሆነ የወደፊቱ - አስቀድሞ የተከፈለና ማንም ሰው ስለ ኃጢአቱ ኃላፊነት የሌለበት ከሆነና ለመዳን የራሱ ድርሻ የሌለው ከሆነ ሁሉም የሰው ልጅ በሙሉ (ኃጢአት ሠራም አልሠራም፣ ንስሐ ገባም አልገባም፣ . . .) ይድናል ያሰኛል፡፡ ሆኖም ግን ይህ እንዳልሆነ በተግባር የታወቀ በመሆኑ የሚድኑ[65] (ሁሉም ሰው እንዲሁ ዝም ብሎ ስለማይድን) ካልቪን "የሚድኑት በእግዚአብሔር አስቀድመው ለመዳን የተወሰኑ ወይም የተመረጡ ጥቂቶች ብቻ ናቸው" አለ፡፡

---

[65] የሚድኑትን በተመለከተ በቅዱስ ወንጌል ከተነገረው እውነት የተነሣ እንዲሁ ሁሉም ሰው ይድናል ማለት ስለማይቻል። ለምሳሌም እንዲህ ያለውን ብቻ እናስታውስ፡- "አንድ ሰውም ጌታ ሆይ፣ የሚድኑ ጥቂቶች ናቸውን? አለው። እርሱም እንዲህ አላቸው፥ በጠበበው በር ለመግባት ተጋደሉ፤ እላችኋለሁና፥ ብዙዎች ሊገቡ ይፈልጋሉ አይችሉምም። ባለቤቱ ተነሥቶ በሩን ከቈለፈ በኋላ፣ እናንተ በውጭ ቆማችሁ፦ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ ክፈትልን እያላችሁ በሩን ልታንኳኩ ትጀምራላችሁ። እርሱም መልሶ፦ ከወዴት እንደ ሆናችሁ አላውቃችሁም ይላችኋል።" ሉቃ. 13:23-25 እንዲሁም፡- "በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።" ማቴ. 7:21

ስለሆነም ከላይ የተጠቀሰው የተሐድሶዎች ትምህርት የሉተራውያንና የካልቪኒስቶች እንጂ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት አለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ አንድ "ታዋቂ" የተባለ የ19ኛው መቶ ዓመት የፕሮቴስታንት ሰባኪ ስለዚህ የቅጣት ምትክ አስተምህሮ የተናገረውን ቀጥሎ እንመልከት፡-

> እኛ ከአሁን በኋላ ከኃጢአት ለሚመጣ ቅጣት በሕግ የሞትን ነን፡፡ በኃጢአቴ (በበደሌ) ምክንያት እንድሞት ቢፈረድብኝ፣ ሆኖም በእኔ ፋንታ ሌላ ሰው ተተክቶ ከሞተልኝ፣ በዚያ በሞተልኝ ሰው ውስጥ እኔ ሞቻለሁ፡፡ ሕጉ ለሁለተኛ ጊዜ በእኔ ላይ ክስ ሊያቀርብብኝ፣ በዳኛው ፊት ሊያቀርበኝና ሊፈርድብኝ፣ እንድሞትም ሊያደርገኝ አይችልም፡፡ እንዲህ ያለው አካሄድ ፍትሐዊነቱ የት አለ? በምትኬ አማካይነት አንድ ጊዜ አስቀድሞ ሞቻለሁ፣ ታዲያ እንዴት ሁለተኛ ሙት እባላለሁ? የእግዚአብሔርን ቁጣ በተቀደሰውና በተከበረው ምትኬ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ተሸክሜያለሁ፣ ታዲያ እንዴት እንደገና ተሸክም እባላለሁ? እኔ መልሼ የምጠየቅበት ከሆነ የምትኬ አስፈላጊነት ምን ላይ ነው? ሰይጣን በእግዚአብሔር ፊት ቀርቦ ቢከሰኝ መልሱ "ይኸ ሰው ሞቷል፡፡ ቅጣቱን በምትኩ አማካይነት ከፍሏል፣ ለኃጢአትም የሞት ነው፣ በእርሱ ላይ ሊሰጥ የሚገባው ፍርድ ቀደም ብሎ በክርስቶስ ላይ ተፈጽሟልና" የሚል ነው፡፡
>
> (The Complete Works of Charles Spurgeon - Volume 1, Sermons, "Sin-Bearer.", Kindle Edition)

ይህ ሰው ካስተማረው ትንሽ ጨምረን እንመልከት፡-

> ይህ የእግዚአብሔር ቋንቋ በሰዎች ቃላት ሲገለጽ ነው፤ 'በተወደደው ልጄ ባደረገው መልካም ነገርና ነገር ሁሉ በምሕረት አንቀጽ ልመለከታችሁ እችላለሁ፡፡' በኢየሱስ ብታምኑ፣ ማለትም ብታምኑት፣ ኢየሱስ ያደረጋቸው መልካም ነገሮች ሁሉ የእናንተ መልካም ሥራዎች ይሆናሉ፣ የእናንተ ሆነው ይቆጠሩላችኋል፡፡ የኢየሱስ መከራዎች ሁሉ የእናንተ መከራዎች ሆነው ይቆጠራሉ፡፡ እያንዳንዱ የእርሱ መልካም ድርጊት ሁሉ ለአንተ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በእግዚአብሔር ፊት የምትቆመው ልክ ክርስቶስ እንደ ሆንክ ሆነህ ነው፣ ምክንያቱም ክርስቶስ በእግዚአብሔር ፊት የቆመው ልክ አንተ እንደ ሆንክ ሆኖ አንተን ወክሎ ነውና - እርሱ በአንተ ቦታ፣ አንተ ደግሞ በእርሱ ቦታ፡፡ ምትክነት!. . .
>
> (The Complete Works of Charles Spurgeon - Volume 1, Sermons, "Justification By Faith", Kindle Edition)

እንግዲህ የተሐድሶዎች ትምህርት የፕሮቴስታንቶች መሆኑ ይኸውና! በሙራ መጽሔት ላይ ይህን የቅጣት ምትክ ቲዎሪ ትምህርት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና አስተምህሮ አስመስለው የጻፉት እነ መሠረት ስብሐት ለአብና መሰሎቻቸው ከመምህሮቻቸው ከሚሲዮናውያኑ ከእነ ዳቪድ ስቶክስ ፕሮቴስታንታዊውን ትምህርት ደኅና አድርገው መቅዳታቸውን አስመስክረዋል፡፡ በጣም የሚገርመውና የሚያሳዝነው ግን ይህን ፕሮቴስታንታዊ ትምህርት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ነው ብለው ደፍረው መጻፋቸው ነው፡፡

ሆኖም የእግዚአብሔር ቃል በእርሱ አምነን፣ እርሱ በሚሰጠን ኃይል ሥራ እንሠራ ዘንድ (እንድንጸም፣ እንድንጸልይ፣ እንድንጋደል . . .) ያስተምረናል እንጂ በማመናችን ብቻ የክርስቶስ መልካም ሥራ ሁሉ (መጾሙ፣ መጸለዩ፣ መከራ መቀበሉ፣ ወዘተ) ለእኛ ሆኖ እንደሚቆጠር አይነግረንም፡፡ እንዲሁም በኃጢአታችንም ንስሐ እስካልገባን ድረስ ተጠያቂዎች እንደምንሆን ደጋግሞ ይናገራል፡፡ ለአብነትም "ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስሐ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቍጣ ቀን ቍጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ። እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል" ይላል፡፡ ሮሜ 2፥5-6 እንዲሁም "ሁላችን በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለንና። እንግዲያስ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን" ይላል እንጂ ካመንን ከዚያ በኋላ ኃጢአት ብንሠራም የክርስቶስ ጽድቅ የእኛ ጽድቅ ሆኖ ስለሚቆጠርልን በኃጢአታችን አንጠየቅም አይልም፡፡ ሮሜ 14፥10፥12

እንዲሁም "የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሏልና" በማለት እርሱ መከራ እንደ ተቀበለ እኛም እንድንቀበል፣ በጾምና በጸሎት ከአጋንንት ጋር መጋደልን በተግባር እንዳሳየን እኛም በእርሱ ኃይል እንደ ዓቅማችን በጾም፣ በጸሎት፣ በትዕግሥት፣ . . . እንድንጋደል እርሱ አብነት ሆኖ በተግባር አሳየን፡፡ 1 ጴጥ. 2፡21 ጌታችን የደቀ መዛሙርቱን እግር በትሕትና ካጠበ በኋላ "እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና" በማለት የእርሱን ተግባራዊ መምህርነት ተከትለን እንድናደርግ አስተማረን እንጂ እርሱ የደቀ መዛሙርቱን እግር አጥቧልና ያ የእርሱ ሥራ ለእኔ ሆኖ ይቆጠርልኛል በሉ አልተባልንም፡፡ ዮሐ. 13፡15 እርሱ ምትካችን ሆኖ ጽድቅን ሁሉ ስላደረገ እናንተ ማድረግ አያስፈልጋችሁም፣ የእርሱ ሥራ ለእናንተ ይቆጠርላችኋል አልተባለም፡፡

እንዲህ የማያደርግ ካለም "እንግዲህ ንስሐ ግባ፤ አለዚያ ፈጥኜ እመጣብሃለሁ" ይላል እንጂ ተሐድሶዎች እንደሚሉት "ሥርየት በተሰጠበት ኃጢአት ሊጠየቅ አይገባውም እያለ ይለፍ ያሰጣል" አይልም፡፡ ራእ. 2፡16 ተሐድሶዎች ይህን ለመጽሐፍ ቅዱስና ለቤተ ክርስቲያን ትምህርት ባዕድ የሆነ ፕሮቴስታንታዊ ትምህርት እንደ ወረደ ቀድተው በድፍረት "ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት ነውና ስሙን፤ እመኑን" እስከ ማለት ደርሰዋል፡፡ ስለዚህ ከላይ ያየነው የተሐድሶዎች አባባል ፕሮቴስታንታዊ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት አይደለም፡፡ ዲያብሎስ በሰዎች አድሮ ስለ ቅጣትና ስለ ፍርድ ቤት ማምለጥ አብዝቶ እየተናገረ አምላካችን የሰጠንን ሁለንተናዊ ድኅነት በምልአት እንዳንረዳና እንዳንጠቀምበት፣ ታላቁን ተስፋ እንዳናይ ዓይነ ልቡናችንን ለመሸፈንና በእሞኑ ለማስቀረት እየሠራ ነውና መንቃት ይገባል፡፡ "በሰይጣን እንዳንታለል፤ የእርሱን አሳብ አንስተውምና" የተባለውን የእግዚአብሔር ቃል ማሰቡ ተገቢ ነው። 2 ቆሮ. 2፡11

ከዚህም በተጨማሪ በኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ መዳን ስንል እነዚህን ብቻ ሳይሆን ከዚህ ቀጥሎ የተገለጸው ጉዳይም እጅግ ወሳኝና መሠረታዊ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ጉዳይ በተሐድሶዎች ዘንድ ከነ ቃሉም አይታወቅም፤ ምክንያቱም አባቶቻቸው ፕሮቴስታንቶች ይህን ጉዳይ አያውቁትምና ነው፡፡

4. ሱታፌ አምላካዊ [እግዚአብሔርን በመምሰል ማደግ - (Θέωσις - theosis or divinisation)]

መዳን ስንል ከላይ በተገለጹት ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ከእነዚህም ጋር በኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ መዳን ስንል ወደ እግዚአብሔር መቅረብና ከእርሱ ጋር ፍጹም አንድነትና ኅብረት ለማግኘት የሚደረግ ዕድገት ነው፡፡ በፕሮቴስታንቶች ዘንድ በአብዛኛው መዳን ሲሉ ግን ከኃጢአት ቅጣት ነጻ መሆንን፣ ከእስራት መፈታትን ብቻ ነው፡፡ የመዳን አስተምህሯቸው በአውግስጢኖሳዊ የቅድሚያ ምርጫ (Predestination) እና በጥንተ በደል (አብሶ) (Original sin) አስተሳሰቦች የተቃኘና የተመሠረተ ነው፡፡ የፕሮቴስታንቶችን አስተምህሮ አዲስ አስመስለው እያቀረቡልን ያሉት የአገራችን አዲስ ፕሮቴስታንቶችም (ተሐድሶዎች) የመዳን ትምህርት ብለው የሚገልጹት ይህንኑ ነው፡፡

ኦርቶዶክሳዊ የመዳን ትምህርት ግን ከእነርሱ የመዳን ትምህርት በጣም የተለየ ነው፡፡ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ከእነርሱና ከመሰሎቻቸው የሚለያት ዋናው ጉዳይም ይህ የመዳን ትምህርት መሆኑ ከላይም ተገልጿል፡፡ ሌሎች ጉዳዮች ቢኖሩም መሠረታዊው ልዩነት ግን ስለ መዳን ትምህርት ያለው ልዩነት ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በብዙዎች ዘንድ ልብ ሲባል የሚታይ ባለ መሆኑ አሁንም ሊስተዋል የሚገባው መሆኑን በድጋሚ እናስታውሳለን፡፡ በመዳናችን ውስጥ ከኃጢአት ቅጣት መዳናችን አንዱና የመጀመሪያው ደረጃ ብቻ ነው፡፡ መዳን ግን ከዚያ እጅግ ያለፈ ነው፡፡ ከኃጢአት ቅጣት ነጻ ከመሆን በላይ እግዚአብሔርን መምሰልን ገንዘብ ወደ ማድረግ የሚደረግ የማያቋርጥ ጉዞ ነው፡፡ ይህ ጉዞ ሱታፌ አምላካዊ (በግሪኩ Θέωσις - theosis) ተብሎ የሚታወቀው ነው፡፡

ያዕቆብ ከምድር እስከ ሰማይ ድረስ ተዘርግቶ፣ በላዩም እግዚአብሔር ተቀምጦበት እንዳየው መሰላል የእግዚአብሔር የባሕርዩ መገለጫዎች የሆኑትን ነገሮች በጸጋ ገንዘብ ለማድረግ ከምድር ወደ ሰማይ የሚደረግ ታላቅ መንፈሳዊ ጉዞ ነው፡፡ ዘፍ. 28፡12-13 መንፈሳዊነት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር በመኖር የሚገኘውን ሕይወት ገንዘብ ማድረግ ነው፡፡ መንፈሳዊነት የእግዚአብሔር የባሕርያቱ መገለጫዎች የሆኑትንና ለሰው በፍጥረት ጊዜ የተሰጡትን ጸጋዎች ገንዘብ ማድረግና ወደ ፍጹምነት ማሳደግ ነው፡፡

ይህ በቅድስና እግዚአብሔርን በመምሰል የማደግ ሂደትም ከእግዚአብሔር ቅድስና የመሳተፍ ሱታፌያዊ ሂደት ነው፡፡ የዚህ ትምህርት መሠረቱም መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ "ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ <u>ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን</u>" ይላል፡፡ ታዲያ ይህ ምን ማለት ነው? 2 ጴጥ. 1፡4 የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባሕርይ ፍጡር ገንዘብ ማድረግ ይችላል ማለት ነውን? አይደለም! የእግዚአብሔር ባሕርይ (ουσια - God's essence) ለሌላ ለማንም አይተላለፍም፣ አይመረመርምም፡፡ ነገር ግን ሐዋርያው "<u>ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ</u>፥ <u>በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን</u>" ያለው የባሕርዩ መገለጫና መታወቂያ የሆኑትን ነገሮች - ኃይላተ እግዚአብሔር - (ενεργια - divine energies) - ቅድስና፣ ቸርነት፣ ደግነት፣ ጥበብ፣ እውነተኛነት፣ ገገርነት፣ . . . የመሳሰሉትን ገንዘብ እናደርግ ዘንድ የተሰጠን በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ከፓንቴይዝም እርሾ የጸዳ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሐዋርያዊ ትምህርት ነው፡፡

እነዚህ የእግዚአብሔር ኃይላት በአጠቃላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ መታወቂያዎችና መገለጫዎች የሆኑት (ፈቃዳተ እግዚአብሔር) ናቸው፡፡ ስለሆነም በኃይላተ እግዚአብሔር መሳተፍ በፈቃደ እግዚአብሔር መሳተፍ፣ ትእዛዛቱን ማድረግ ነው፡፡ ትእዛዘተ እግዚአብሔር እግዚአብሔር ፈቃዱን የገለጠባቸው ናቸውና፡፡ የራሳችንን ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የበለጠ እያስማማንና አንድ እያደረግን በሄድን መጠን የበለጠ እግዚአብሔርን እየመሰልን እንሄዳለን፡፡ መድኃኒታችን "ሊከተለኝ የሚወድ ሰው ቢኖር ራሱን ይካድ፣ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ" ያለው ይህን ነው፡፡ ሰው የራሱን ፈቃድ እየተወ በሄደ መጠን ጌታችን በተግባር እንዳስተማረን የራሱን ፈቃድ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያደረገ ይሄዳል፡፡ ያን ጊዜም እግዚአብሔርን መምሰልን ገንዘብ እያደረገ ይሄዳል፡፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል በተጻፈው ትምህርቱ ላይ ለአይሁድ ሲናገር አስቀድሞ በዳዊት "እኔ ግን አማልክት ናችሁ፣ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ አልሁ" የተባለውን በማጽናት "እኔ አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን?" በማለት የተናገረው ይህን ለሰው ልጅ የተዘጋጀውን ጸጋ ሲያስረዳ ነው፡፡ መዝ. 81፡6 ፤ ዮሐ. 10፡34 የጸጋ አምላክነት የተባለውም በባሕርይ ያይደለ ፈቃድን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር አንድ በማድረግና እግዚአብሔርን እየመሰሉ በመሄድ የሚገኝ ክብር ነው፡፡ በዚህም ሰው በባሕርዩ ሊያደርጋቸው የማይችላቸውን ነገሮች በኃይለ እግዚአብሔር አማካይነት ማድረግ እየቻለ ይሄዳል፡፡

አስቀድሞ እግዚአብሔር ሙሴን "ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ" ብሎት ነበር፡፡ ዘጸ. 7፡1 መድኃኒታችንም "እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል" ያለው ለዚህ ነው፡፡ ዮሐ. 14፡12 እንዲህ ባለው የመዳን መንገድ በመጓዝ እግዚአብሔርን ወደ መምሰል በማደግ ላይ ያሉ ሰዎች "ንሕነሰ ሕሊናሁ ለክርስቶስ - እኛስ የክርስቶስ ልብ አለን" እስከ ማለት ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ 1 ቆሮ. 2፡16 እንዲሁም "ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ" እስከ ማለትም ይደርሳሉ፡፡ ፊል. 4፡13 ምክንያቱም ኃይላተ እግዚአብሔርን (Divine energies) ገንዘብ እያደረጉት ይሄዳሉና ነው፡፡

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር "ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ - ሰውን እንደ መልካችን፣ እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" ካለ በኋላ "እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው" ይላል። ይህም ማለት ሰው አርአያ (መልክ) እግዚአብሔር እና አምሳለ እግዚአብሔር (ምሳሌ) ተሰጥተውታል ማለት ነው፡፡ ከእነዚህ የመጀመሪያውን (የእግዚአብሔር መልክ) በፍጥረት ጊዜ (ሲፈጥረው) ሰጥቶታል፤ "እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው" ይላልና። ዘፍ. 1፡26-27 ሁለተኛውን፣ ማለትም "የእግዚአብሔር ምሳሌን" ግን ከተሰጠው ከእግዚአብሔር "መልክ" ተነሥቶ የተሰጠውን ጸጋ በማሳደግ ወደፊት ይደርስበት ዘንድ የተሰጠው፣ ሆኖም ገና ያልደረሰበት ጸጋ ነው፡፡

አርአያ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር መልክ) የተባሉት በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት በእግዚአብሔር ዘንድ በምልአት ያሉት፣ ለሰው ደግሞ እንደ ዓቅሙ መጠን በጸጋ የተሰጡት ሲሆኑ እነዚህም ብዙ ኅብረ መልክእና ገጽታ ያላቸው ናቸው፡፡ ይህም ቅድስና፣ ፍቅር፣ ነጻነትና ኃላፊነት፣ ጥበብ፣ ገዢነት፣ የሰብእና ርቱዕነትና ንጽሕና፣ ክብር፣ ፍትሐዊነት፣ ርኅራኄ፣ ምክንያታዊነት፣ አሳቢነትና አዋቂነት እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ ለሰው በተፈጠረ ጊዜ የተሰጡት በዘርነት (በመነሻነት) ደረጃ ነው፡፡

እነዚህ የእግዚአብሔር መልክ የተባሉት የቅድስና መንፈሳዊ ባሕርያት መገለጫዎች ለሰው የተሰጡት ያሳድጋቸውና ይንከባከባቸው ዘንድ ነው፡፡ እነዚህን የማሳደጉና ወደ ፍጹምነት ደረጃ የመውሰዱ ሂደት ነው መንፈሳዊ ሕይወትና መንፈሳዊነት የሚባለው፡፡ በዚህም ሰው ከተሰጠው የእግዚአብሔር "መልክ" በመነሣት ወደ እግዚአብሔር "ምሳሌ" ያድጋል ማለት ነው፡፡ እነዚህም ተዘክሮተ አምላክና ከእርሱ (ከእግዚአብሔር) ጋር ኅብረት ያለው ሆኖ መኖር፣ የቅድስና ሕይወትንና የመልካም ምግባር ሕይወትን ፍጹም በሆነ ሁኔታ ገንዘብ ማድረግ፣ እና ዘለዓለማዊ ሕይወት ናቸው፡፡ ሐዋርያው ". . . የሥጋችን አባቶች . . . መልካም ሆኖ እንደ ታያቸው ለጥቂት ቀን ይቀጡን ነበርና፣ እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል" በማለት እንደ ገለጸው እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረበት ዋና ዓላማና በየጊዜው በእኛ ላይ የሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ግባቸው እኛን ከቅድስናው እንድንካፈል ማድረግ ነው፡፡ ዕብ. 12፡10 "ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፣ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና" ያለውም ለዚህ ነው። ዕብ. 12፡14

እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ በሁለተኛ ቆሮንቶስ መልእክቱ ላይ ይህን ጉዳይ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡ - "እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ _ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።_" 2 ቆሮ. 3፡18 ስለዚህ የክርስቲያን ዓላማ ቅዱስ ጳውሎስ "ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን" ብሎ የገለጸውን፣ ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ "ከመለኮቱ ባሕርይ ተካፋዮች እንሆን ዘንድ" በማለት የገለጸውን ሱታፌ አምላካዊ ገንዘብ ማድረግ ነው፡፡ ይህም ሂደታዊና የሚያድግ እንጂ በአንድ ጊዜ የሚያልቅ አይደለም፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም ወደፊት ጌታ ሲገለጥ የምንጠብቀው ተስፋ ምን እንደሆነ ሲናገር፡ - "ወዳጆች ሆይ፥ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን" ብሏል። 1 ዮሐ. 3፡2 ቅዱስ ጳውሎስም "ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወሰኗልና" ይላል፡፡ ሮሜ 8፡29

በመቀጠልም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "የዚያንም የመሬታዊውን መልክ እንደ ለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን" ይላል፡፡ 1 ቆሮ. 15፡49 እንግዲህ ይህን መሠረታዊ ጉዳይ ቅዱሳን ሐዋርያት ምን ያህል ደጋግመው በአጽንኦት እንዳስተማሩት መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ጌታችን

በመሠረታዊው የወንጌል ትምህርቱ ላይ የተናገረው ነው፤ እንዲህ ሲል፡- "እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ።" ማቴ. 5፡48 ይህ የማይቻል ቢሆን ኖሮ ጌታችን ሊሆን የማይችል ነገር አይናገርም ነበር፡፡ ሆኖም ግን በቤዛነቱ የዳኑና ሐዲስ ተፈጥሮን ገንዘብ ያደረጉ ሰዎች በቅድስና መንገድ ከተጓዙ ወደዚህ ፍጹምነት ደረጃ መድረስ ይችላሉ ማለት ነው፡፡ "እርሱም ሁሉን እንኳ ለራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሠራር ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል" ተብሎ የተነገረው ለዚህ ነው። ፊል. 3፡21

እስከ ሦስተኛው ሰማይ የደረሰውና ሰው ሊሰማቸው የማይገቡ የተባሉ ነገሮችን ሰማሁ ያለው፣ ስለ ክርስቶስ ምርኮ ዕቃ የሆነውና እጅግ በጣም ብዙ መከራዎችን የተቀበለው ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ "ወንድሞች ሆይ፣ እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቈጥራለሁ፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ" ያለው ይህን ለሰው ልጆች የተሰጠውን እጅግ ታላቅ ነገር ከፊቱ ስለ ተመለከተ ነው። ፊል. 3፡13-14 ታላቁ ሐዋርያ "እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቈጥራለሁ" ለምን አለ? መዳን ማለት ሥርየተ ኃጢአትን ማግኘትና ከቅጣት መዳን ብቻ ቢሆን ኖሮ ቅዱስ ጳውሎስ እነዚህን አላገኘም ነበርን? ወይስ አላመነም ነበረን? ለምንስ "እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቈጥራለሁ፣ . . . በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ" አለ? አዎ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ የተዘጋጀልን የመጥራት ዋጋ "ከፍ ከፍ" ያለ ነው እንጂ ከቅጣት በማምለጥና ከእስር በመፈተታ ብቻ የተገደበና የተወሰነ አይደለም፡፡

ይህን መሠረታዊ ጉዳይ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ቴዎሲስ (*theosis*) ይሉታል፡፡ ይህ የመዳን ጉዳይ በፕሮቴስታንትና በካቶሊካውያን ዘንድ፣ በአጠቃላይ በምዕራባውያን ነገረ መለኮታዊ አስተሳሰብ ዘንድ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አይታወቅም ነበር፡፡ የሚገርመው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከታተሙ ባለ ብዙ ገጽና ሰፌ ጉዳዮችን ከሚዳስሱ መዝገበ ቃላቶቻቸውና ኢንሳይክሎፒዲያዎቻቸው ውስጥ እንኳ ስለዚህ ጉዳይ (ስለ ቴዎሲስ) የሚናገር አንዳችም አንቀጽ የላቸውም ነበር፤ (*theosis*) የሚለው ቃልም አልነበረም፡፡ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ግን አንዳንድ ምዕራባውያን የነገረ መለኮት ምሁራን ይህን ጉዳይ በተመለከተ ከምሥራቃውያን (ኦርቶዶክሳውያን) ሊቃውንት ዘንድ በማግኘታቸው ነገረ ድኅነትን ከዚህ ጽንሰ ሃሳብ አንጻር ለማጥናት የጀመሩና ፍላጎት እያሳዩ ያሉ አሉ፡፡[66] ለዚህም በዚህ የግርጌ ማስታወሻ የተጠቀሱትን መጻሕፍት ማየት ይቻላል፡፡ ለእነርሱ መዳን ሲሉ ከተጠያቂነት ማምለጥንና ከእስር መፈታትን ብቻ ነው እንጂ ከዚያ በኋላ ስላለው ብዙም ጉዳያቸው አይደለም፡፡ የመዳን ጸጋን እንዲህ "ከመለኮቱ ባሕርይ ተካፋይነት" እስከ ተባለው ከፍ ከፍ ያለው የእግዚአብሔር ጥሪ ድረስ አይመለከቱትም ነበር፡፡ ተሐድሶዎችም በየመጣጥፎቻቸው የሚያንጸባርቁት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ከቀዱበት ከምንጫቸው ያለውን ይህንኑ ሃሳብና መንፈስ ነው፡፡ በምሥራቃውያን አባቶች ዘንድ ግን ከመጀመሪያዎቹ ታላላቅ አባቶች ጀምሮ ይህን ሃሳብ ታላቅ ቦታ ሰጥተውት እናገኘዋለን፡፡

[66] (Norman Russell, The Doctrine Of Deification in The Greek Patristic Tradition, Oxford University Press, Incorporated, 2004.; Christensen, Michael J. & Jeffery A. Wittung, Partakers of the Divine Nature: The History and Development of Deification in the Christian Traditions, eds., Grand Rapids: Baker, 2008.; M. David Litwa, '2 Corinthians 3:18 and Its Implications for Theosis.)

ለምሳሌም ታላቁ አባት ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ እንዲህ ይላል፡-

> እግዚአብሔርን በባሕርዩ መገለጫዎች (*In His Energies*) እናውቀዋለን ብለን እስረግጠን መናገር የምንችል ሲሆን በባሕርዩ ግን ሊታወቅና ሊደረስበት የማይቻል ነው፡፡ የሚሰጠን ጸጋዎችና ኃይሉ ወደ እኛ የሚመጣልንና የሚደርሰን ሲሆን ባሕርዩ ግን የማይደረስበትና የማይመረመር ነው፡፡ በእኛ ሊታወቅ የሚቻለውን የእግዚአብሔርን ኃይል እንደ ፀሐይ ጨረር ማሰብ እንችላን፤ ባሕርዩን ደግሞ እንደ ራሷ እንደ ፀሐይ ማሰብ እንችላለን፡፡ እግዚአብሔር በራሱ በባሕርዩ የማይታወቅና እገሌ በሚል ስም የማይጠራ ነው፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ በገለጠባቸው መንገዶች (In His Energies) ግን ይታወቃል፤ ስሙም እግዚአብሔር ይባላል፡፡

(ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ፤ መልእክት ኀበ አምፊሎቅዮስ ጳጳስ)

ይህንም ሐዋርያው "እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም፤ ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን፤ አሜን" በማለት የገለጸው ነው፡፡ 1 ጢሞ. 6፥16

የመዳን የመጨረሻ ዓላማው (ግቡ) ሰውን አዳም በገነት ሳለ ወደነበረበት ደረጃ ለመመለስ ብቻ አይደለም፤ አካላዊ ቃል በተዋሕዶ ባሕርያችንን ከዚያ በእጅጉ ከፍ ወዳለ ደረጃ አድርሶታልና፡፡ በክርስቶስ ሥጋዌ ራሳችን የመጀመሪያው አዳም ሳይሆን ዳግማዊው አዳም (ክርስቶስ) ነውና፡፡ 1 ቆሮ. 15፥22፤ 45-50 ስለዚህ የሰዎች መዳን ስንል የሰው ባሕርይ መክበርና የጸጋ አምላክ መሆንንም (The deification of human nature - *theosis)* ነው፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ ይህን "መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ሕይወት የሚሠራው ሲሆን በጥምቀት የሚጀምርና ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት እማኙ ቀስ እያለ የሚያድገው ሂደታዊ ዕድገትና ወደ እርሱ መቅረብ፤ እርሱን የበለጠ ማወቅና ከእርሱ ጋር መዋሐድ ነው" ሲል ገልጾታል፡፡

በኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ አካላዊ ቃል ወደ እኛ የወረደው እኛን ወደ እርሱ ያወጣን (ከፍ ከፍ ያደርገን) ዘንድ ነው፡፡ በጥምቀት የክርስቶስ አካል ሆኖ መሥራት የጀመረ እያንዳንዱ ክርስቲያንም ወደ እግዚአብሔር በማደግ ላይ ነው፡፡ ይህን የማደግ ሂደት ነው ሱታፌ አምላካዊ (Theosis) የምንለው፡፡ ይህም እያንዳንዱ የክርስቶስ አካል ሆኖ የተሠራ ክርስቲያን ከፍጹምነት ወደ ፍጹምነት፤ ከቅድስና ወደ ቅድስና እያደገና እየተሸጋገረ፤ ወደ እግዚአብሔር የበለጠ እየቀረበና እየተዋሐደ የሚሄድበት መንፈሳዊ የዕድገት ጉዞ ነው፡፡ የሰው ሕይወት ግቡ ከእግዚአብሔር ጋር በፍጹማዊ ሁኔታ መዋሐድ ነው ማለት ነው፡፡ ይህም ከእግዚአብሔር ከባሕርዩ ሳይሆን ከቅድስና ሕይወቱ መሳተፍ ነው፡፡

ይህም ቅዱስ የመሆን ጥሪና ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ያለው ወደ መሆን መጠራት ነው፡፡ ከላይ እንዳነሳነው ሐዋርያው "በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ" ሲል የገለጸው ነው፡፡ ይህ በቅድስና የማደግ ሂደትም እስከ ዳግም ምጽአት ድረስ ቀጣይ ነው፤ በሞትም አይቋረጥም፡፡ በመቅድመ ወንጌል ላይ "ወይትዌሰክ ሎሙ ስን በዲበ ስን - በክብር ላይ ክብር በጸጋ ላይ ጸጋ እየተጨመረላቸው ይሄዳል" ተብሎ የተገለጸው ይኸ መንፈሳዊ የማደግ ሂደት ነው፡፡

ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት መዳን የሚገኘው ከክርስቶስ ጋር በመዋሐድና አንድ በመሆን ነው፡፡ ከእርሱ ጋር በመዋሐድም በሕይወታችን ሁሉ የበለጠ እግዚአብሔርን የምንመስል እየሆንን በማደግ ወደ እግዚአብሔር ምሳሌ እናድጋለን፡፡ ይህ ደግሞ ሂደታዊ እንጂ ቅጽበታዊ አይደለም፤ እንዲሁም የሚያድግና የሚበለጽግ (Dynamic) እንጂ የተወሰነና የተገደበ (Static) አይደለም፡፡ ሱታፌ አምላካዊ (Theosis) ተብሎ የሚገለጸው ይህ ሂደት ነው፡፡ ይህም እግዚአብሔር የሰጠን ታላቅ ጸጋ ነው፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ "የእግዚአብሔር ቃል ሰው

የሆነው እኛ ሰዎች አምላክ እንሆን ዘንድ ነውና"[67] በማለት በተደጋጋሚ የሚገልጸው ይህን ጥልቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ነው፡፡ ይህም በእርሱ ብቻ ሳይሆን ከእርሱ በፊት በነበሩትም፣ ከእርሱ በኋላ በተነሡትም ኦርቶዶክሳውያን ቅዱሳን አባቶች በአጽንኦት የተነገረ ነው፡፡

የክርስትና ሕይወት ዓላማ ከሲኦል ማምለጥ ብቻ አይደለም፣ ወይም ጥሩ ሰው መሆን ብቻም አይደለም፤ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ገንዘብ በማድረግ ደካማና ትሑት የሆነው ሰብእናችን (እኛነታችን) "ከክብር ወደ ክብር" እንዲለወጥና እግዚአብሔርን እስኪመስል ድረስ እንዲከብር ማድረግ ነው እንጂ፡፡ የተጠራንበት ዓላማ ምን ያህል ታላቅና ግናና እንደሆነ እስካልተረዳነው ድረስ የክርስትና ሕይወትን ግብ ልንደርስበት አንችልም፣ "ራእይ ከሌለ ሕዝብ ይጠፋል" የተባለው ለዚህ ነው፡፡ ምሳ. 29፡18 ይህን ዓላማ አለመረዳትና መርሳት ክርስትናን በእጅጉ ያወርደዋል፣ በዚህ ዓለም እንዳሉ እንደ ሥነ ምግባር መመሪያዎች ወይም ደግሞ ከቅጣት ስለ ማምለጥ ብቻ የሚናገር የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ (Criminal Code) ያስመስለዋል፡፡

የሱታፌ አምላካዊነት ጽንሰ ሃሳብ መዳንን አንድ ጊዜ እንደ ተፈጸመና እንደ ቆመ ታሪክ ወይም ደግሞ እግዚአብሔር የጥፋተኛነት መዝገባችንን አስወግዶ ነጻ ናችሁ ብሎ የእስር ቤት በሩን ከፍቶ እንዳስወጣን ወንጀለኞች ብቻ አድርገው ማሰብና መረዳት የለመደባቸውን ሰዎች ያላዩትን አቅጣጫ እንዲያዩ የልቡናቸውን በር በኃይል አንኳኩቶባቸዋል፡፡ መዳን እስከ ሱታፌ አምላካዊነት ድረስ ነው የሚለው ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት ግን በሕማሙና በመስቀሉ የተገኘውን ቤዛነትና ሥርየት ተቀብሎ መስቀሉንና ሕማሙን ከማየት በተጨማሪ ከዚያ ባሻገር ትንሣኤውን፣ ዕርገቱን፣ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ መላኩን፣ ዳግም ምጽአቱን ሁሉ በምልአት ይመለከታል፡፡ ወደ ኋላም እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን የወሰነውን የማይመረመር አምላካዊ ውሳኔ፣ ብሥራትን፣ ፅንሰቱን፣ ልደቱን፣ ጥምቀቱን፣ ዞሮ ማስተማሩን፣ ሁሉ ይመለከታል፡፡ ስለዚህ አምላካችን የሰጠንን የመዳን ጸጋ በምልአትና በትክክል የሚገነዘበውና የሚያስተምረው ኦርቶዶክሳዊ የመዳን ትምህርት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ከላይ እንደ ተመለከትነው በእነ አንሰለም የቀረበው ንድፈ ሃሳብ መዳንን ዕለተ ዓርብ ላይ ብቻ በማንጠልጠል ሌላውን የጌታችንን ሥራ ችላ በማለት ጠባብና ቁንጽል የሆነ የነገረ ድኅነት አስተሳሰብ የምዕራቡን ዓለም በአብዛኛው ተጠናውቶታል፡፡ በዚህ ትምህርት በኢየሱስ ክርስቶስ መሰቀልና መሥዋዕት ሆኖ መቅረብ እግዚአብሔር አብ በሰው ላይ የነበረውን ቁጣ አበረደ፣ የተነካው ክብሩ ተካሰ የሚለው እንግዳ ትምህርት መሠረት ፈውስና መድኃኒት የሚያስፈልገው በኃጢአት የወደቀው የሰው ዘር ከመሆን ይልቅ ክብሩ በመነካቱ የተቆጣው እግዚአብሔር ነው ያሰኛል፡፡

## <u>ሱታፌ አምላካዊ (Theosis) በቅዱሳን አበው ትምህርት</u>

ከላይ እንደ ተገለጸው ይህ ትምህርት በኦርቶዶክሳውያን አባቶች የመዳን ትምህርት ውስጥ ታላቅ ቦታ የሚይዝና መሠረታዊ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ ቀጥሎም ከብዙ አባቶችና ከትምህርታቸው መካከል ለአብነት የሚከተሉትን እንመለከታለን፡፡

1) ቅዱስ ሄሬኔዎስ

- "ቃል የእኛን ባሕርይ የተዋሐደውና ሰው የሆነው ሰዎች የጸጋ አማልክት ይሆኑ ዘንድ ነው፡፡"
- "ከኢፍጹምነት ወደ ፍጹምነት ለማደግ የጌታችን ሥጋዌ መሠረታዊ ነው፡፡ በጌታችን የማዳን ሥራ ከመልክአ እግዚአብሔር (Image) ወደ አርአያ እግዚአብሔር (Likeness) ለማደግ የሚያስችለንና የሚያስፈልገን የነበረው ዓቅምና ችሎታ ተመለሰልን፡፡" (ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ በእንተ መናፍቃን፣ መጽሐፍ 3፣ ምዕ. 18)

[67] ('He [the Word of God] became human so that we could become divine') - በእንተ ተሠግዎተ ቃል፣ ቁ. 54

2) ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ

❖ "የእግዚአብሔር ልጅ ሰው የሆነው እኛ አማልክት ዘበጸጋ እንሆን ዘንድ ነው፡፡" (በእንተ ተሠግዎተ ቃል)[68]

❖ "አካላዊ ቃል ወደ እኛ የመጣውና የወረደው ሰዎችን ለማክበር እንደ መሆኑ የእግዚአብሔር ልጅ የሚለውን ስም በሽልማትነት የተቀበለ አይደለም፤ ይልቁንም እኛን የአባቱ ልጆች እንድንሆን አደረገን፣ ራሱ ሰው በመሆን ሰውን የጸጋ አምላክ ወደ መሆን ክብር ከፍ አደረገው እንጂ፡፡" (ትምህርት በእንተ አርዮሳውያን፣ ትምህርት 1)

❖ " . . . ስለዚህም በመጀመሪያ ሰው ሆኖ ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር የሆነ አይደለም፣ እግዚአብሔር የነበረ ሲሆን ሰው የሆነ ነው እንጂ፣ ይህም እኛን የጸጋ አምላክ አድርጎ ለማክበር ነው፡፡" (ትምህርት በእንተ አርዮሳውያን፣ ትምህርት 2፣ 39)

❖ "እርሱ ሰው የሆነው እኛን አማልክት ዘበጸጋ ያደርገን ዘንድ ነው፡፡ ከሴት፣ ከድንግል የተወለደው በስህተት ላይ የነበረውን ትውልዳችንን ያስቀርልንና ከዚያ ወዲህ የተቀደስን ዘሮች እና የመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች እንሆን ዘንድ ነው፡፡" (መልእክት ቁ. 60 ኀበ ጳጳስ አደልፊየስ)

❖ "ይህን የማያደንቅ ማን ይኖራል? ወይስ ይህ ነገር በእውነት አምላካዊ ስለመሆኑ የማይስማማ ማን ይኖራል? የቃል የአምላክነት ሥራዎች ከእኛ በነሣው ሰውነት ባይደረጉ ኖሮ ሰው የጸጋ አምላክነትን ባላገኘ ነበርና፡፡ እንደ ገናም እንዲህ ባይሆን ኖሮ (ቃል የእኛን ባሕርይ ገንዘብ ባያደርገው ኖሮና ሥራውን በእርሱ ባይሠራ ኖሮ) የትስብእት ገንዘቦች የሆኑት ነገሮች የቃል ገንዘብ ተደርገው ባይነገሩ ኖሮ ሰው ነጻ ባልወጣ ነበር፡፡ . . . እርሱ ሰው ሲሆን በሥጋ የእግዚአብሔር እናት ከሆነች ከድንግል ማርያም በመወለዱ ለሌሎች መወለድንና ሕይወትን የሚሰጠው እርሱ ራሱ ተወለደ ተባለ፡፡ ይህም መነሻችንን (ምንጫችንን፣ መገኛችንን) ወደ እርሱ ይወስደውና ከፍ ከፍ ያደርገው ዘንድ፣ መሬታዊ እንደ መሆናችን ወደ መሬት ተመልሰን በዚያው እንዳንቀር ለማድረግ፣ ይልቁንም ሰማያዊ ከሆነው አካላዊ ቃል ጋር ባሕርያችን አንድ ከመሆኑ የተነሣ በእርሱ (በአካላዊ ቃል) ወደ ሰማይ እንወሰድ ዘንድ ነው፡፡" (ትምህርት በእንተ አርዮሳውን፣ ቁ. 3)

3) ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ

❖ " . . . ክብራችንን እንገንዘብ፣ እንመስለው ዘንድ ያለንን የፍጻሜያችንን አርአያ (መልክ - Archetype) እናክብር፣ የምሥጢሩን ኃይል እንወቅ፣ ክርስቶስ ስለ ምን እንደ ሞተ (የሞተበትን ምክንያት) እናስተውል፡፡ ክርስቶስን እንምሰል፣ ክርስቶስ እኛን መስሏልና፡፡ ስለ እርሱ ስንል አማልክት እንሁን፣ እርሱ ስለ እኛ ሰው ሆኗልና፡፡ ለእኛ ከሁሉ በላይ ታላቅና የተሻለ የሆነውን ነገር ይሰጠን ዘንድ እርሱ ለአምላክነቱ የባሕርይ ክብር ተገቢ ያልሆነውን ዝቅተኛ ነገር ገንዘቡ አደረገ፡፡ በእርሱ ድህነት እኛ ባለጠጎች እንሆን ዘንድ ድሀ ሆነ፤ እኛ ነጻነታችንን መልሰን እናገኝ ዘንድ እርሱ የባሪያን መልክ ያዘ፤ እኛ ከፍ ከፍ እንል ዘንድ እርሱ ወደ ታች ወርዶ መጣ፤ እኛ ድል እናደርግ ዘንድ

[68] ቅድስና ተለይቶት የነበረው የሰው ልጅ የተቀደሰውና ቅድስናን ገንዘብ ማድረግ የቻለው በክርስቶስ ነው። ይህንንም ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ መሆኑን ካስረዳባቸው ነጥቦች አንዱ ነበር፤ እንዲህ በማለት፦ "ወልድ ራሱ እግዚአብሔር ባይሆን ኖሮና የሰው ባሕርይ የተዋሐደው ከፍጡር ጋር ቢሆን ኖሮ ሰው የጸጋ አምላክነትን አያገኝም ነበር" (Orat 2.70).

እርሱ ተፈተነ፤ እኛን ያከብረን ዘንድ እርሱ ተዋረደ፤ እኛን ያድነን ዘንድ እርሱ ሞተ፤ በኃጢአት ምክንያት የመጨረሻ ውርደት ተዋርደን፣ ኃጢአት በሚያመጣው ተዋርዶ ዘቅጠን የነበርነውን እኛን ወደ እርሱ ይወስደንና ያነሣን ዘንድ እርሱ ወደ ላይ ወጣ (ዐረገ)።" (በእንተ ትንሣኤ ወምክንያተ ኅንድዮቱ፣ ትምህርት 1፣ ቁ.4)

❖ "የቸርነቱ ሥጦታ ምንድን ነው? በእኔ (በባሕርየ ሰብእ) ዙሪያ ያለው ምሥጢር ምንድን ነው? በምሳሌው (በአርአያ እግዚአብሔር - the Image) ድርሻ (ሱታፌ) አለኝ፤ እኔ ግን አልጠበቅሁትም፤ ምሳሌውን (አርአያ እግዚአብሔርን) ያድነውና ሰውነትን (ሥጋን) የማይሞት ያደርገው ዘንድ የእኔን ሰውነት ገንዘቡ አደረገው፣ ተዋሐደው። ከመጀመሪያው የበለጠ ታላቅ ክብርና ኅብረት (አንድነት) ሰጠን። በመጀመሪያው መልካም የሆነውን ተፈጥሮ ሰጠ፣ በሁለተኛው (በሥጋዌው) ግን የወደቀውን ባሕርይ የራሱ ገንዘቡ አደረገው። ከመጀመሪያው ድርጊቱ ይልቅ ይኸኛው የበለጠ አምላካዊ ነው፣ አእምሮና መረዳት ባላቸው ሰዎች ዘንድ ሁሉ ይኸኛው እጅግ ታላቅና የከበረ ነው።" [በእንተ ልደተ ክርስቶስ (በእንተ አስተርእዮቱ)፣ ትምህርት ቁ. 38]

❖ "በተዋርዶ ለነበረው ለሰው ባሕርዩ ከእግዚአብሔር ጋር በምሥጢረ ተዋሕዶ ከመዋሐድና አንድ ከመሆን በላይና በዚህ ተዋሕዶም የጸጋ አምላክ ከመሆን በላይ ምን ክብርና ፍጻሜ ሊኖረው ይችል ነበር? . . . ይህን ያደረገልንስ ስለ እኛ ራሱን ካዋረደውና ክብር የሌለው ሆኖ ከተገለጠው፣ ነገር ግን በአምላክነቱ ባሕርይ ጉልበት ሁሉ ሊንበረከክለት የሚገባው ከሆነው ከራሱ ከእግዚአብሔር በቀር ማን ነው?" (ነገረ መለኮታዊ ትምህርቶች፣ ትምህርት ቁ. 30

4) ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ

❖ "እኔ የጸጋ አምላክ ልሆን የተጠራሁ ፍጡር ነኝ።"
❖ "የእግዚአብሔር መልክ (አርአያ እግዚአብሔር) በተፈጥሮ ተሰጥቶናል፣ ስለዚህም አይለወጥም፤ ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ እንዳለ ይኖራል። ምሳሌውን (አምሳለ እግዚአብሔር - The likeness) የምናገኘውና የምንደርስበት ግን በራሳችን ፈቃደኛነትና ከእርሱ ጋር በሚኖረን የፈቃድ ኅብረትና ትብብር ነው። በእኛው ውስጥ የመሆን ክሂሎ ክዋን አለ፣ በመልካም ምግባር ሕይወትና በጥሩ የቅድስና ሕይወት ማደግና ወደ ታሰበው ግብ መድረስ እንችላለን።"

5) ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ

❖ "የእግዚአብሔርን መልክ (አርአያ እግዚአብሔርን) የምንቀበለው አእምሮ ያለን አዋቂ ሆነን በመፈጠራችን ነው፤ አምሳለ እግዚአብሔርን (ምሳሌ - the likeness of God) የምንቀበለው ደግሞ የመልካም ምግባር ሕይወትን ገንዘብ በማድረግ ነው። በመፈጠሬ የእግዚአብሔር መልክ (አርአያ እግዚአብሔር) አለኝ፣ ነጻ ፈቃዴን በመጠቀም ደግሞ በእግዚአብሔር ምሳሌ (In the likeness of God) እሆናለሁ።" (ትምህርት በእንተ ድንግልና)

❖ "ክፉ አኗኗርህን (ምግባርህን) የምትተወውና ወደ እግዚአብሔር የምትመለሰው ቅጣትን ከመፍራት የተነሣና ከቅጣት ለማምለጥ ስትል ብቻ ካልሆነ፣ ወይም ደግሞ የመልካምን ነገር ዋጋ ለማግኘት ብቻ ስትል (እንደ ምንደኛ) ከማድረግና የመልካም ምግባር ሕይወትን በሒሳባዊ ስሌትና ጥቅምን በሚያሰላስል ራስ ወዳድ ሕሊና የምትለውጥና የምትነግድ ከመሆን ነጻ መውጣት - እውነተኛው ፍጹምነት ይህ ነው። ሁሉም ነገር ለእኛ የተዘጋጀና የተጠበቀልን ስለ መሆኑ የተነገረንን ተስፋ አምነህና ተማምነህ

የሚያስጨንቅህና የሚያሳስብህ ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍቅር እንዳትለይ ብቻ ሊሆን ይገባል፤ የሕይወት ታላቁ መዳረሻና የጸርጅ ፍጻሜ ከሆነው በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ከመኖርና በእርሱ የተወደደ ከመሆን የሚበልጥ እንዳችም ነገር የሌለ መሆኑን አስተውለህና ተረድተህ ብትኖር ታላቁ ፍጹምነት ማለት ይህ ነው፡፡" (በእንተ ሕይወቱ ለሙሴ)

- "ኃጢአትና የኃጢአት ግዛት የማያቋርጥ ወደ ሆነ የሞትና የጥፋት ሂደትና ሰንሰለት እየወሰዱን ነበር፡፡ ክርስቶስ ደግሞ ወደ ጥፋትና ወደ አለመኖር እየወሰደን ከነበረው ከዚያ የጥፋት ሠንሰለት አውጥቶ ወደ እግዚአብሔር በሚወስደን፣ ከእርሱ ጋር ከፍ ወዳለ ሱታፌ በሚያደርሰን የድኅነት (የመዳን) መንገድና ሂደት ላይ አስቀመጠን፡፡ የሙሴ ወደ ሲና ተራራ መውጣት የሚያሳየን ይህን ነው፡፡ ሆኖም ይህ መውጣት (ሂደት) ማብቂያ የለውም፡፡ መልካም ነገር ገደብ የሌለው ነው፡፡ ስለዚህም በመልካም ነገር ማደግ መቸም መች አይቋረጥም፡፡ ከሞት በኋላም የሚቀጥለው ይኸው በመልካም ነገር የማደግ ሂደት ነው፡፡ ይህም ፍጡር ለሆነ ነገር ሊሰጠው የሚችለው የመጨረሻው መልካም ነገር ነው፡፡" ((በእንተ ሕይወቱ ለሙሴ)

- "ክርስቶስ በጥምቀትና በሜሮን ከእርሱ ጋር አንድ ሆነን የተዋሐድነው ራሳችን፣ ሙሽራችን ነው፤ እኛ ደግሞ አካላቱ ነን፡፡ ሆኖም ይህ ውሕደት በማያቋርጠው የመንፈሳዊነት ዕድገት ሂደት ውስጥ የመጀመሪያው ደረጃ እንጂ የመጨረሻው (ፍጻሜው) አይደለም፤ እርሱን የማወቅና ከእርሱ ጋር ሱታፌና ኅብረትን ገንዘብ የማድረግ የማያቋርጥና የማያልቅ ሂደት (Infinite process) ነው፡፡ (ትርጓሜ መኃልየ መኃልይ)

- "ሐዋርያው 'ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን' እንዳለ በየቀኑ በሚደረግ መንፈሳዊ ዕድገት ሁል ጊዜ በመሻሻል በፍጹምነት እያደግን በመሄድ የተሻለ ወደ ሆነው ነገር ዘወትር ሳናቋርጥ እንድንለወጥና እንድናድግ እንሁን፤ ሆኖም ከፍጹምነት ወሰን መድረስ ግን መቸም መች አንችልም፡፡ 2 ቆሮ. 3፡18 ፍጹምነት ያለው መልካም በሆነው ነገር ማደግ መቻላችን (ማደግ የመቻል ዕድላችን) የማያቆም (የማያቋርጥ) በመሆኑ ላይ ነውና [እንጂ ከፍጹምነት ጥግ ወይም መጨረሻ ደረጃ ላይ በመድረስ አይደለምና፡፡] (ስለ ፍጹምነት ያስተማረው ትምህርት)

የእስካሁኑ ማጠቃለያ

አካላዊ ቃል ሰው የሆነውና ባሕርያችንን በማይመረመር ድንቅ ምሥጢሩ የራሱ ባሕርይ ያደረገው ከሲኦል ለማውጣትና ከቅጣት ለማዳን ብቻ አይደለም፡፡ ይህ ሳይዘነጋ እንዳለ ሆኖ ነገር ግን በዚህ ላይ ሌሎች ብዙ ሀብታትን አጎናጽፎናል፡፡ ይህ የአካላዊ ቃል ሰው መሆንና እኛን የማዳን ጸጋም በአንዱ ገጽ ላይ ብቻ የሚነበብ ሳይሆን ሁለንተናውን በሚገባ ማንበብ የሚገባው ክቡር ሥጦታ ነው፡፡ ስለሆነም "የሰው ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ዳነ" ስንል አንዱን ነገር ብቻ ነጥሎና አንጠልጥሎ ሌላውን የቸርነት ሥራውንና የመዳናችን ጸጋ የሆነውን ግን ጥሎ መሆን የለበትም፡፡ በኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ መዳን ስንል በኃጢአት ከመጣው ሞትና ቅጣት ማምለጥና ነጻ መውጣት ብቻ ሳይሆን በዚያ ላይ ሐዲስ ተፈጥሮን ገንዘብ ማድረግን፣ እግዚአብሔርን ማወቅን እና በቅድስናና እግዚአብሔርን በመምሰል ከአርአያ እግዚአብሔር ወደ አምሳለ እግዚአብሔር የሚደረግ ዕድገትን - ሱታፌ አምላካዊ (Theosis - የጸጋ አምላክነትን ገንዘብ የማድረግ ሂደትን) የሚይዝ ሰፊና ጥልቅ ነገር ነው፡፡ ይህን መቀደሳችንን እና የጸጋ አማልክት ወደ መሆን የምናደርገውን ጉዟችንን የሚመራንና የሚቀድሰን መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

ሆኖም ይህ የነገረ ድኅነት አስተምህሮ በምዕራባውያን የነገረ ድኅነት ትምህርት ውስጥ፣ በአጠቃላይ በነገረ መለኮታዊ አስተምህሯቸውና አስተሳሰባቸው ውስጥ የለም፡፡ የክርስቶስ ሰው መሆን፣ ሞቱና ትንሣኤው ሥርየተ ኃጢአትንና ጸጋ መንፈስ ቅዱስን እንደሚያስገኝ ቢያምኑም ሰው በቅድስና ሊያድግ እንደሚችልና የእግዚአብሔር አርአያ በሰው ውስጥ እያደገ ወደ አምሳለ እግዚአብሔር ይደርሳል የሚለው ኦርቶዶክሳዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ በእነርሱ ዘንድ በተለይም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ እንደ ተገለጸው በመዝገበ ቃላታቸው ውስጥ እንኳ (Theosis) የሚል ቃል ወይም ይህን የሚወክል ሌላ ቃል እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አልነበረም፡፡ እነዚህ ወገኖች የአውግስጢኖስን የጥንተ አብሶ አስተሳሰብ በመከተል ለሰው ተሰጥቶት የነበረው አርአያ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር መልክ - Image of God) አዳም በበደለ ጊዜ ጨርሶ ጠፍቷል፣ ተደምስሷል ባዮች ናቸው፡፡ ከዚህ የተነሣ ነው ከእግዚአብሔር ምሕረትና ጥልቅና ሰፊ ከሆነው የመዳን ጸጋ ይልቅ ሁል ጊዜ ኃጢአትና ቅጣት ላይ ልዩ ትኩረትና አጽንኦት የሚያደርጉት፡፡ በምዕራፍ አንድ ላይ እንደ ተገለጸው ማርቲን ሉተርን መጀመሪያ ኃጢአተኛነቱን ብቻ እያሰበ ተስፋ ወደ መቁረጥ እንዲደርስ፣ በኋላ ደግሞ ወደ ሌላ ጽንፍ እንዲሄድ ምክንያት የሆነው አንዱ ጉዳይም ይህ ነበር፡፡

በኦርቶዶክሳውያን አባቶች አስተምህሮ ዘንድ ግን አዳም ሲበድል የተሰጠው የእግዚአብሔር መልክ ደከመ፣ ባሕርዩም ጎሰቆለ እንጂ ጨርሶ አልጠፋም የሚል ነው፡፡ ስለዚህም ምሥራቃውያን ኦርቶዶክሳውያን አባቶች ከቅዱስ አትናቴዎስ ጀምሮ የተጠቀሙት ቃል "የባሕርይ መጎስቆል - fallen nature" የሚለውን ነው፡፡ "ጥንተ አብሶ - original sin" የሚለው ቃል ከጥንቱ ሲጀመር አንሥቶ በአውግስጢኖስ የተጀመረና በአብዛኛው ምዕራባውያን የተጠቀሙበት ቃል ነው፡፡ ለኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ቃል ሰው መሆን ወደ ጥንት ክብሩ፣ ከዚያም በላይ መጀመሪያ በተፈጠረ ጊዜ የተሰጠው ከእግዚአብሔር መልክ ወደ እግዚአብሔር ምሳሌ የማደግ ጸጋ ተመለሰለት የሚለው ጉዳይ የነገረ ድኅነት አስተምህሯቸው መሠረትና ማዕከል ነው፡፡ እነ ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ ቅዱስ አትናቴዎስ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ሌሎችም ሁሉ ይህንኑ በአጽንዖት አስተምረዋል፡፡

በቤተ ክርስቲያን አንድነት ውስጥ መኖር፣ ከምሥጢራት መካፈል፣ ራስን መግዛትና መጋደል፣ ወዘተ የሚያስፈልገው ይህን ጸጋ ገንዘብ ለማድረግና ለመጠቀም ነው፡፡ አንድ ዘር በቅሎ፣ አድጎ፣ ፍሬ እንዲሰጥ የተለያዩ እንክብካቤዎችን እንደሚፈልግና ትጉህ ገበሬ ተገቢውን ሥራ በትክክለኛው ጊዜ መሥራት እንዳለበት ሁሉ የእግዚአብሔር ምሳሌ ገንዘብ ለማድረግና ወደዚያ ለማደግ እያንዳንዱ ሰው ተገቢውን መንፈሳዊ ተግባር ማከናወን ይኖርበታል፡፡ መንፈሳዊ ሕይወትና መንፈሳዊ ተጋድሎ የሚባለው ይኼው ሂደት ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን "እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ" ሲል የመከረው ለዚህ ነው፡፡ 1 ጢሞ. 4፥7

ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባትና መምህር ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ይህን ሲያስረዳ መንፈሳዊነት ከአርአያ እግዚአብሔር ወደ አምሳለ እግዚአብሔር (From Image to Likeness) የሚደረግ የማደግ ሂደት ነው ይላል፡፡ ይህ የዕድገት ሂደትም የማያቋርጥና የማያቆም ነው፡፡ በፍጥረት ጊዜ የተሰጠን "አርአያ እግዚአብሔር" እንደ ዘር ሲሆን በመንፈሳዊነት የዕድገት ሂደት ገንዘብ እናደርገው ዘንድ የተሰጠን "አምሳለ እግዚአብሔር" ደግሞ እንደ ዛፍ ነው፡፡ አንድ ዘር ዛፍ ለመሆን የሚያስችለው መሠረታዊ ባሕርይ ሁሉ አለው፤ ሆኖም ሙሉ ዛፍ ሆኖ ለማደግና ለማፍራት የሚያስፈልጉት ብዙ ነገሮች (መትከል፣ ውኃ መጠጣት፣ መኮትኮት፣ የፀሐይ ብርሃን፣ ጊዜ፣ . . .) አሉ፡፡ እነዚህን ካገኘ ዘሩ አድጎ ሙሉ ዛፍ ይሆናል፣ ፍሬንም ይሰጣል፡፡ መንፈሳዊነትም እንደዚያ ነው፤ በተፈጥሮ እንደ ዘር የተሰጠንን አርአያ እግዚአብሔር በቃለ እግዚአብሔር፣ በፍቅረ እግዚአብሔር፣ በትሕትና፣

በምሥጢራትና በተጋድሎ በማሳደግ ወደ እግዚአብሔር ምሳሌ ደረጃ ማሳደግ ነው፡፡ ይህም ማለት እነዚህ ነገሮች በፍጹምነት ያሉት በእግዚአብሔር ዘንድ ሲሆን ሰው ደግሞ የተቻለውን ያህል በጸጋ ገንዘብ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ መንፈሳዊነት የሚባለውም ሰዎች በቅድስና፣ በፍቅር፣ በጥበብ፣ በነጻነትና በመሳሰሉት መንፈሳዊ ባሕርያት እያደጉ መሄድ ነው፡፡ እነዚህም እንደ ዘርና እንደ ቡቃያ ከትንሽ ጀምረው ቀስ በቀስ እያደጉ ሲሄዱ ቅድስናን ፍጹም ወደ ማድረግ ደረጃ እየተሸጋገሩ ይሄዳሉ፡፡ ከክብር ወደ ክብር መሸጋገርን የሚያመጣውም ይኸ ነው፡፡

ይህ መንፈሳዊ የዕድገት ሂደትም ቀጣይ ነው፡፡ ከሞት በኋላም ቢያንስ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ይቀጥላል፡፡ እኛ ኦርቶዶክሳውያን ከዚህ ዓለም በሞት ለተለዩን ወገኖቻችን ጸሎት የምናደርገውና የምናስባቸውም አንዱ ለዚህ ነው፤ መንፈሳዊ የማደግ ሂደት በሞት አይቋረጥም ብለን ስለምናምን፡፡ ሐዋርያው "እንግዲህ ወዳጆች ሆይ፣ የዚህ ተስፋ ቃል ካለን በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንጻ" በማለት የተናገረውም ለዚህ ነው፡፡ 2 ቆሮ. 7፡1

መጽሐፍ ቅዱሳዊው እና ተሐድሶዎች "አባቶቻችን" የሚሏቸው፣ አንዳንድ ጊዜ ሲመቻቸውና የሚደግፏቸው ሲመስላቸው ለማደናገሪያ የሚጠቅሷቸው የቤተ ክርስቲያን ቀደምት አባቶቻችን ሊቃውንት የመዳን ትምህርት እንዲህ በምልዐትና በሰፋት ያለ ሆኖ ሳለ እነርሱ ግን እውነተኛ አባቶቻቸው መናፍቃን በመሆናቸው የነገረ ድኅነት አስተምህሯቸው ጎደሎና ሕጸጽ፣ የተሳሳተም ነው፡፡ ስለሆነም የመዳን ትምህርታቸው ፕሮቴስታንታዊ እንጂ ኦርቶዶክሳዊ አይደለም፡፡ እንደ ፕሮቴስታንቶቹ አስተምህሮ "መዳን" በኃጢአትና በቅጣት፣ ፍርድ ቤት በመቆምና በመከራከር፣ በመታሰርና በመፈታት ዙሪያ ላይ የተወሰነ ሕግ ተኮር (Legalistic) ነው፡፡ ይህም ከላይ በታሪካዊ ዳሰሳው በአጭሩ እንደ ተገለጸው የሂጶው አውግስጢኖስ እና የካንተርበሪው አንሰለም የቀነኑት መሠረተ እሳቤ ቀጣይ ሂደት ነው፡፡

## 3.5 የሚድኑ እነ ማን ናቸው?

በኦርቶዶክሳዊ የመዳን ትምህርት እግዚአብሔር ከመዳን ውጭ ያደረገውና ይህን ጸጋ የነፈገው ማንም ሰው የለም፡፡ ሁሉም የተጠራው ለመዳን ነው፡፡ እግዚአብሔር በአጠቃላይ የሰውን ልጆች በሙሉ ይድኑ ዘንድ ይወዳል፤ ይፈቅዳል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት . . . " ሲል የገለጸው ይህንኑ የሚያስረዳ ነው፡፡ 1 ጢሞ. 2፡3-4

ጌታችንም "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና። በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም" በማለት የተናገረው ቃል በልጁ ሰው መሆን ያመነ ሁሉ መዳን የሚችል መሆኑን በግልጽ የሚያስረዳ ነው፡፡ ዮሐ. 3፡16-18

ስለዚህ መዳን በእግዚአብሔር ቸርነት ለሰው ሁሉ የተሰጠ ጸጋ እንጂ በቅድመ ምርጫና በቅድመ ውሳኔ (Predestination) የሚያምኑ ሉተራውያንና ካልቪኒስቶች እንደሚሉት አስቀድመው ለተወሰኑ ለጥቂቶች ብቻ የተሰጠ አይደለም፡፡ በተግባር ሲታይ የሚድኑት ጥቂቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህ ግን እያንዳንዱ በራሱ ስንፍና ምክንያት ይቀርበታል እንጂ አስቀድሞ ለመዳን የማይችል ሆኖ ስለ ተወሰነበት አይደለም፡፡ በራስ ስንፍና ምክንያት አለመዳንና እንዳይድን አስቀድሞ የተወሰነበት መሆን ፈጽሞ የተለያዩ ነገሮች ናቸውና፡፡ እንደ አንዳንዶች አባባል የሚድኑት አስቀድመው

የተመረጡት ብቻ ከሆኑ የአምላክ ሰው መሆኑ፣ መከራ መቀበሉ፣ ምሥጢራትን መስጠቱ፣ ወንጌል መሰበኩ . . . ይህ ሁሉ ከንቱ ድካም መሆኑ አይደለምን? መዳን በዚህ ዓለም ላሉ ሰዎች ሁሉ እንደ ተዘጋጀ ማዕድ በፊታቸው የቀረበ ነው፣ መጠቀምና አለ መጠቀም ደግሞ የእያንዳንዱ ድርሻ ነው፡፡ ጌታችን ግን እያንዳንዱን "ወደ ሠርጉ ኑ በሏቸው" እያለ እየተጣራ ነው፡፡ ማቴ. 22 እንዲሁም "ልትድን ትወዳለህን?" እያለ እየጠየቀ ነው፡፡

## 3.6 መዳን (ድኅነት) - የእግዚአብሔር ስጦታ? ወይስ የሰው የሥራው ውጤት?

እግዚአብሔር የሰጠን የመዳን ጸጋ የቸርነቱ ስጦታ ነው፡፡ በእግዚአብሔር አብ ፈቃድ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋዌ በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠን መዳን ከሰዎች መልካምነት ወይም ከተጋድሎ የተነሣ የተገኘ አይደለም፤ ከፍጹም ቸርነቱ የተነሣ የተሰጠን ጸጋ ነው እንጂ፡፡ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ሰው የዳነው በእግዚአብሔር ቸርነት (ጸጋ) ነው፡፡ የሰው ድኅነት የእግዚአብሔር የቸርነቱ ስጦታና ለሰው ያለው የማይለወጥ ፍቅር ውጤትና መገለጫ ነው፡፡ ድኅነታችን የተገኘው በእኛ ሥራ መልካምነት አይደለም፡፡ በአንድ በኩል የሰው ልጆችን አጠቃላይ የቀደመ ሁኔታ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር እንዴት እንዳዳነን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ግልጽ በሆነ ሁኔታ እንዲህ ሲል ያስተምረናል፡-

> እኛ ሁላችን ደግሞ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን፡፡ እንደ ሌሎችም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጸጋ ስለሆነ ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን፤ በጸጋ ድናችኋልና፡፡ በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ ከእርሱ ጋር አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን፡፡ ኤፌ. 2:3-8

እንዲሁም ይኸው ሐዋርያ ስለዚሁ ጉዳይ ሲናገር እንዲህ አለ፡-

> እኛ ደግሞ አስቀድመን የማናስተውል ነበርንና፤ የማንታዘዝ፣ የምንስት፣ ለምኞትና ለልዩ ልዩ ተድላ እንደ ባሪያዎች የምንገዛ፣ በክፋትና በምቀኝነት የምንኖር፣ የምንጣላ፣ እርስ በርሳችን የምንጠላላ ነበርን፡፡ ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው ጥምቀትና በመንፈስ መታደስ አዳነን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም፡፡ ቲቶ. 3:3-5

ጌታችንና መድኃኒታችንም እግዚአብሔር ሰውን የወደደውና ያዳነው እንዲሁ በአባታዊ ፍቅሩ መሆኑን ሲገልጽ፡- *"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን (ሰውን) <u>እንዲሁ ወድዷልና</u>"* አለ፡፡ ዮሐ. 3:16 እንዲሁ ማለትም ያለ ምንም ዋጋ ወይም ቅድመ ሁኔታ ማለት ነው፡፡ የወደደን እንዲሁ በቸርነቱ እንጂ እንዲወደን የሚያደርግ መልካም ሥራ ስለ ነበረን ወይም እኛ አስቀድመን ስለ ወደድነው አልነበረም፡፡ ሰውማ እግዚአብሔርን ክዶ ዲያብሎስን ሰምቶ በአምላኩ ላይ ያመጸና ሕጉን በይፋ ያፈረሰ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ጌታችን በጠፋው በግ ምሳሌ እንደ ተናገረው የጠፋውን የሰውን ልጅ ይፈልገውና ወደ ቀደመ ክብሩ ይመልሰው ዘንድ ከሉዓላዊ መንበሩ ወርዶ ፈለገው፤ ባገኘውም ጊዜ ለመፈለግ በደከመው ድካም ሳይቆጣው፣ ሳይገርፈው፣ በእግርህ ሂድ ሳይለው በማግኘቱ ተደስቶ በጫንቃው ላይ ተሸከመው፡፡ እንደ ገናም በጠፋው ልጅ ምሳሌ እንደ ተናገረው ያጠፋውን ጥፋትና የበደለውን በደል አንዱንም ሳያስብ አዘነለት፣ በፍጹም ፍቅር ተቀበለው፣ የሰባውን በማረድ (የራሱን ቅዱስ ሥጋውን በመቀረብና ክቡር ደሙን በማፍሰስ) በዓል አደረገለት፡፡ *"ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኗል፣ ጠፍቶም ነበር ተገኝቷልም፤ ደስ እንዲለን ፍሥሐም እንድናደርግ ይገባናል"* አለ፡፡ ሉቃ. 15:11-32

ቅዱስ ጳውሎስም ይህንኑ ሲገልጽ፦ *"እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፣ በፊት የተለያችሁትን፣ ክፉ ሥራንም በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን በሥጋው ሰውነት በሞት በኩል አስታረቃችሁ"* አለ፡፡ ቆላ. 1፥21-22 እንዲሁም ክርስቶስ ያዳነን ጻድቃን ሆነን ተገኝተን ስለ ነበር ሳይሆን ገና ኃጢአተኞችና ደካሞች ሳለን እንደ ነበር ሲናገር እንዲህ አለ፦ "ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቷልና። ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና፤ ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል። ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቷልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።" ሮሜ 5፥6-8 ይህን ሁሉ አጠቃልሎ "ወሶበ እንዘ ጸሩ ንሕነ ለእግዚአብሔር ተሣሀለነ በሞተ ወልዱ - እግዚአብሔር ጠላቶቹ ሳለን በልጁ ሞት ታረቀን" አለ፡፡ ሮሜ. 5፡10 ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም- "እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፣ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ" በማለት የዳንነው ክርስቶስ በቸርነቱ በተቀበለው ሕማምና መከራ መሆኑን ይነግረናል፡፡ 1 ጴጥ 2፡24

ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስም እንዲህ ይላል፦

> በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፤ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና፡፡ ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን፣ ስለ ኃጢአታችንም ማስተሥረያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም፡፡ 1 ዮሐ. 4፡9-10

የወደቀውንና የሞተውን የሰው ልጅ ያዳነው የእግዚአብሔር ቸርነት እንጂ የሰው የራሱ ሥራ አይደለም፡፡ ሰው በሥራው ብቻ የሚጸድቅ ቢሆን ኖሮ በብሉይ ኪዳን የነበሩ ደጋግ አባቶች ለመዳን ክርስቶስ ባላስፈለጋቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ምንም እንኳ በደጋግ ሥራቸው በኃጥአን ላይ የሚደርሰው መከራ ሙሉ በሙሉ ባይደርስባቸውም ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ በአዳም በደል ምክንያት የተዘጋችውን ገነት እስኪከፍታት ድረስ ከሲኦል መውጣትና ወደ ገነት መግባት አልቻሉም ነበር፡፡ በኃጢአት ምክንያት ከመጣው ፍዳና ዕዳም አንዷንም እንኳ ፈቀቅ ማድረግ አልቻሉም ነበር፡፡ ስለዚህ እኛን ያዳነን የእግዚአብሔር ቸርነት እንጂ ሥራችን አይደለም ማለት ነው፡፡ እንደ ሥራችንማ ቢሆን እግዚአብሔር ሰው ኾኖ ኃጥአን ለሆንነው ለእኛ መከራ ይቀበል ዘንድ የሚያበቃው የትኛው ሥራችን ነበር? በእኛ ሥራ ቢሆንማ ኖሮ እንኳን ይህ ሁሉ ቸርነት ሊደረግልን ቀርቶ ከተደረገልን ቸርነት አንዷንም እንኳን ባላገኘን ነበር፡፡ መዳን ከፍጡር በሚገኝ ነገር ሊገዛ የሚችል አይደለምና፡፡

በኃጢአታችን ሞት የተፈረደብን "የሞት ሰዎች" ሆነን ሳለን ክርስቶስ ከፍጹም ፍቅሩ የተነሣ ስለ እኛ ሰው ሆኖልን፣ ራሱን ቤዛ አድርጎ ሰጠ፣ ሞተልን፤ በሞቱም ከሞት አዳነን፣ ሕይወትን ሰጠን፡፡ ይህ የእርሱ የጸጋ ስጦታ ብቻ ነው፡፡ ኢሳ. 53፡4-6

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህን የመዳን ትምህርት እንደ ዓይኗ ብሌን ትጠብቀዋለች፣ ትመሰክረዋለች፣ ታስተምረዋለች፣ በተግባርም ትኖረዋለች፡፡ የኃጢአተኞች መድኃኒት የተገኘው ሰው በሆነው በሥግው ቃል በኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በትምህርቷ፣ በሥርዓተ አምልኮዋ በሁሉም ነገሯ የምትገልጠው ይህን ነው፡፡ በጸሎተ ሃይማኖቷም ". . . በእንቲአነ ለሰብእ ወበእንተ መድኃኒትነ ወረደ እምሰማያት ተሰብአ ወተሠገወ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል - ስለ እኛ ስለ ሰዎች ስለ መዳናችን ከሰማያት ወረደ፣ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ" እያለች ሁል ጊዜ ትመሰክራለች፡፡

## 3.7 ስመዳን እያንዳንዱ ሰው ምን ማድረግ ያስፈልገዋል?

ለመዳን የሰው ልጅ ድርሻ ለዚህ የእግዚአብሔር ስጦታ በጎ ምላሽ መስጠትና ድኅነትን ያገኘበት ዘንድ በተነገረው መንገድ መሄድና መዳንን ገንዘብ ማድረግ (የራሱ ማድረግ) ነው። በእግዚአብሔር በኩል ሰውን ለማዳን አስፈላጊ የሆነው ነገር ሁሉ - የእግዚአብሔር ድርሻ - ተፈጽሟል፡፡ ስለ እያንዳንዳችን መዳን በእግዚአብሔር በኩል ያልተፈጸመና የቀረ አንድም ነገር የለም፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መዳናችንን በሥጋዌው ፈጽሟል፡፡ አሁን የሚቀረው የእያንዳንዳችን ድርሻ ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሠርጉን ደግሶ የሚያስፈልገውን ሁሉ አዘጋጅቶ "ሁሉም ተዘጋጅቷል፤ ወደ ሠርጉ ኑ በሏቸው" በማለት እየጠራ ነው። ማቴ. 22፡4 የእግዚአብሔርን ጥሪ "እሺ" ብሎ ተቀብሎ የሠርግ ልብስ ለብሶ ወደ ሠርጉ ቤት መግባት ደግሞ የእያንዳንዱ ድርሻ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ የእያንዳንዱ ሰው ድርሻ የእያንዳንዱን ሰው ፈቃድና ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡

በራሱ የመዳን ሂደት ውስጥ እያንዳንዱ ሰው ድርሻ አለው? ወይስ የለውም? ካለውስ ድርሻው ምንድን ነው? እስከ ምንስ ድረስ ነው? በሚሉት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በታሪኳ ውስጥ ሁለት የተሳሳቱ ጽንፎች ገጥመዋታል፡፡ እነዚህም፡-

1. በአንድ በኩል "የሰው ተፈጥሮ በራሱ የመልካም ምግባር ሕይወትን መፈጸምና እያንዳንዱ ሰው ራሱን ለማዳን ይችላል፤ (የሰው ባሕርይ በራሱ መዳንን ገንዘብ ማድረግ ይችላል)፤ የክርስቶስ ሰው መሆንና ሞቱ ጠቀሜታው ሥነ ምግባራዊ ብቻ ነው" የሚለው በ5ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ የተነሣው የአየርላንዳዊው መነኩሴ የፔላጊየስ ኑፋቄ (Pelagian heresy) ሲሆን፤

2. በሌላ በኩል ደግሞ "የሰው ባሕርይ በአዳም ኃጢአት ምክንያት ሙሉ በሙሉ የተበላሸና ነጻ ፈቃዱንም ያጣ ስለሆነ የሰው መዳን የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ውሳኔና ድርሻ ብቻ ነው፤ እግዚአብሔር በመለኮታዊ ውሳኔው ለዘለዓለማዊ ሕይወት የመረጣቸውን አስቀድሞ ወስኗል፡፡ ስለዚህ ማንም ሰው በራሱ መዳን ወይም አለመዳን ላይ ምንም ድርሻ ወይም ሚና የለውም የሚለው የአውግስጢኖስ ትምህርት (The Doctrine of Predestination and Irresistible grace) ነበር፡፡ ይህም ማለት እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር የሚሰጠውን እንደ ግኡዝ ፍጥረት ዝም ብሎ ከመቀበል ያለፈ ሱታፌ የለውም ማለት ነው፡፡ ሁሉም ሰው በአዳም ኃጢአት (Original Sin) ምክንያት ለሞት የተሰጠ ሲሆን እግዚአብሔር በቸርነቱ የተወሰኑትን ሰዎች ብቻ ለዘለዓለማዊ ሕይወት መርጧቸዋል፡፡ ሆኖም ለሕይወት የሚመርጣቸውን ወሳኙ እግዚአብሔር ስለሆነ ከሚድኑትም ሆነ ከማይድኑት መሆን የሰው የራሱ ውሳኔ አይደለም፤ ስለዚህ ሰው በራሱ መዳን ላይ አንዳችም ድርሻ የለውም የሚል ነው፡፡

በመጽሐፍ ቅዱሳዊው የመዳን ትምህርት ሲመዘኑ እነዚህ ጽንፍ የሆኑ አመለካከቶች ሁለቱም ስህተቶች ናቸው፡፡ ሆኖም እነዚህ እንደ ምዕራብና ምሥራቅ ተቃራኒ ጽንፍ የሆኑት የፔላጊዮስና የአውግስጢኖስ አስተሳሰቦች የተለያዩ ሰዎችና ወገኖች ስለ መዳን ባላቸው እምነትና አመለካከት ላይ በተለያየ ሁኔታ የየራሳቸውን አሻራ ማሳረፋቸው አልቀረም፡፡ በተለይም "የእግዚአብሔር ጸጋ ያለ ራሱ ያለ ሰውዬው ፈቃድም ቢሆን ሰውን ያድነዋል፤ ምክንያቱም የሰው ባሕርይ በአዳም ኃጢአት ምክንያት ጨርሶ የተበላሸ ስለሆነ በዚህ ኃጢአታቸው ምክንያት ሞት ከሚገባቸው ከሰው ልጆች መካከል እርሱ ባወቀ ለመረጣቸው ለተወሰኑት መዳንን እና ለመዳን የሚያበቃቸውን ጸጋ አብሮ ይሰጣቸዋል፤ ያን ለመዳን አስቀድሞ የመረጠውንና ይህን ጸጋ የሰጠውን ሰውም ያለ ፈቃዱም ቢሆን ወደ መዳን ይመራዋል" የሚለው የአውግስጢኖስ ትምህርት ኦርቶዶክሳዊው የመዳን ትምህርት ላይ አሉታዊ ጠባሳ አሳድሯል፡፡ ይህም ጸጋውን የተቀበለው ሰው ሊቃወመው የማይችለው "አስገዳጅ ጸጋ"[69] የሚሉት ትምህርት ነው፡፡

[69] (Irressistible grace)

አውግስጢኖስ ይህን አስተምህሮ የፈጠረው እያንዳንዱ ሰው ራሱን ለማዳን በቂ ዓቅም አለው የሚለውንና የክርስቶስን ቤዛነት ከንቱ የሚያደርገውን የፔላግዮስን ትምህርት ለመቃወም ሲል እንደ ነበር ይነገራል፡፡ በርግጥ አውግስጢኖስ ይህ አስተምህሮ ከፔላግዮስ መነሣት በፊትም የደረሰበት አቋሙ እንደ ነበር የሚያሳዩ ሁኔታዎች አሉ፡፡ በተለይም ወደ ክርስትና ከመምጣቱ በፊት የነበረበት የውጣ ውረድ ሕይወት ወደ እንዲህ ዓይነቱ የተሳሳተ ንድፈ ሃሳብ ላይ እንዲደርስ ከፍ ያለ ተጽእኖ እንደ ፈጠረበት የሚያሳዩ ምልክቶች አሉ፡፡ የሆነ ሆኖ ወደ ሌላ የስህተት ጽንፍ ሄደ፡፡ እነዚህ ሁለቱ ጽንፎች በተለያየ ሁኔታ ብዙዎች ላይ ተጽእኖቻቸውን ሲያሳርፉ ኖረዋል፡፡ የፕሮቴስታንቶች የመዳን ትምህርት ከዚህ ከአውግስጢኖስ የተሳሳተ የመዳን ትምህርት የተቀዳ ነው፡፡ እነ ማርቲን ሉተርና ጆን ካልቪን ያስተማሩት የመዳን ትምህርት ይህን የአውግስጢኖስን አስተሳሰብ የበለጠ በመለጠጥና በማጋነን፣ እርሱ በታላቅ ፈሪሃ እግዚአብሔርና ጥንቃቄ ሆኖ የተናገራቸውን ነገሮች እነርሱ በኃይልና በድፍረት በመስበክ ነበር፡፡ አውግስጢኖስ ከነበረው መንፈሳዊነትና አስተዋይነት የተነሣ በብዙ ጥንቃቄና ፈሪሃ እግዚአብሔር አጥሮ ለማስቀመጥ የሞከራቸውን ነገሮች እነ ሉተር ባልተወለደ አንደበታቸው የአውግስጢኖስን አጥሮችና ቅጥሮች በመሰባበር በውስጥ የነበሩትን ፍልስፍናዊ ትምህርቶችና መነሻዎች ወደ ጽንፍና በጣም ሩቅ ወደ ሆነ መደምደሚያ አደረሷቸው፡፡

ኦርቶዶክሳዊው የመዳን ትምህርት ከሁለቱም ጽንፍ ነጻ ነው፡፡ እንደ ፔላግዮስ ሰው ያለ እግዚአብሔር የማዳን ጸጋ በራሱ ይድናል አይልም፤ እንደ አውግስጢኖሳዊው ትምህርትም ሰው ያለ ራሱ ፈቃድና ሱታፌ ይድናል አይልም፡፡ እያንዳንዱ ሰው ለመዳን የራሱ ድርሻ አለው፡፡ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋዌ የፈጸመውን አጠቃላይ መዳን እያንዳንዱ ሰው ለራሱ ገንዘብ የሚያደርገው ይኸን በእምነት በመቀበል ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔርና በሰው መካከል በሚኖረው ሱታፌያዊ ሂደት ነው፡፡ ይህም ማለት ሰው በራሱ ፍላጎትና ጥረት ብቻ ሊድን እንደማይችል ሁሉ እግዚአብሔርም ያለ ሰው ፍላጎትና ከነጻ ፈቃዱ ውጭ በግድ በአፍአዊ ሁኔታ እንዲድን አያደርገውም ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር የማዳን ጥሪ ከሰው ፍላጎትና ለእግዚአብሔር ጥሪ በጎ መልስ ከመስጠት ጋር ሲዋሐዱ ለዚያ ሰው መዳን ይሆንለታል፡፡ ከዚህ ውጭ ድኅነት የለም፡፡

በመዳናችን ላይ የእኛ ድርሻ የልባችንን በር ለሚያንኳኳው ጌታ በራችንን መክፈት፣ ድንጋዩን ከመቃብሩ ላይ ማንሣት ነው፡፡ ዋናው የእግዚአብሔር ነው፤ ሆኖም የሰውን ድርሻ ጨርሶ የሚያጠፋና የሰውን ነጻ ፈቃድ ከንቱ የሚያደርግ "መዳን" በኦርቶዶክሳዊ የመዳን ትምህርት ተቀባይነት የለውም፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለምና፡፡ መዳን በአንድ ሰው ላይ ያለ ፍላጎቱ የሚጫን ግዴታ አይደለም፡፡ በመዳናችን የተመለሰልን አንዱ መሠረታዊ ነገር ጨርሶ ባይጠፋም በውድቀታችን ምክንያት ደክሞና ፈዝዞ የነበረው ነጻነታችን ነውና፡፡ ስለዚህ በጥምቀት የመዳናችን ዘር ይዘራል፤ በሌሎቹ ምሥጢራት እያደገና ፍሬ እያፈራ ይሄዳል፤ ይህም እስከ ዳግም ምጽአት ድረስ ይቀጥላል ማለት ነው፡፡

ስለዚህ በኦርቶዶክሳዊ ትምህርት መዳን በአንድ ቅጽበት ተፈጽሞ ከዚያ በኋላ "ድኛለሁ" እያሉ የሚፎከርበት ሳይሆን ሐዋርያው "ስለዚህ፤ ወዳጆቼ ሆይ፤ ሁል ጊዜ እንደ ታዘዛችሁ . . . በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ" በማለት እንዳስተማረን በፈሪሃ እግዚአብሔርና በተጋድሎ እስከ መጨረሻው በመጽናት የሚፈጸም ነው፡፡ ፊል 2፡12 ቅዱስ ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈላቸው የፊልጵስዩስ ሰዎች ክርስቲያኖች ነበሩ፡፡ ታዲያ መዳናቸው ተፈጽሞ አልቆ የነበረ ከሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ክርስቲያኖች የሆኑትን ምእመናን መዳናቸው ገና ያልተፈጸመ ይመስል "በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ" ለምን አላቸው?

ሰውን ያዳነው የእግዚአብሔር ጸጋ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን ይህን መዳን ለመፈጸምና በተሰጠው የመዳን አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን ከእያንዳንዱ ሰው የሚጠበቅ ነገር አለ፡፡ ሐዋርያው የእግዚአብሔርን የማዳን ነገር ሲገልጽ፡- *"እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው"* በማለት ንጹሐ ባሕርይ የሆነ ክርስቶስ ስለ እኛ ኃጢአት "ኃጥእ" ተብሎ መከራ በመቀበሉ የእኛ ኃጢአት መወገዱንና በእርሱ "ኃጥእ" መባል እኛ "የእግዚአብሔር ጽድቅ" መሆናችንን ገለጸ፡፡ በመቀጠልም *"አብረንም እየሠራን የእግዚአብሔርን ጸጋ በከንቱ እንዳትቀበሉ ደግሞ እንለምናለን"* አለ፡፡ 2 ቆሮ. 5:21 ፤ 6:1 ይህም ማለት እግዚአብሔር ያደረገልንን የማዳን ጸጋ ለመቀበል ከእኛ የሚጠበቀውን ነገር (ምንም እንኳ የምናደርገው ነገር ለጸጋው ምንም የማይመጥንና እዚህ ግባ የሚባል ባይሆንም) ሳናደርግ እንዳንቀር ነው፡፡ ይህም እያንዳንዳችን ማድረግ ያለብን የራሳችን ድርሻ ያለ መሆኑን በግልጽ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ከእርሱ የሚጠበቅበትን ለማይፈጽም ሰው የእግዚአብሔር ሰውን ማዳን ብቻ በራሱ እንዲድን አያደርገውም፡፡

እያንዳንዱ ሰው ለመዳን የሚከተሉትን መፈጸም ይኖርበታል፡፡

### 3.7.1 እምነት (ማመን)

ማመን ማለት በዋናነት እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን በፈቃዱ ያደረገውን ነገር ሁሉ ማመንና መቀበል (እምነት) እና በአጠቃላይ እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት እንዲሁም በሥጋዌው የገለጸውን የእውነት ትምህርት (ሃይማኖት) ሳይቆነጻጽሉና ሳያጎድሉ በምልአት መቀበልና ማመን ነው፡፡

ማመን ስንል እግዚአብሔር አንድ መሆኑን፣ በአንድነቱ ውስጥ ልዩና የማይመረመር ሦስትነት ያለው መሆኑን፣ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካላዊ ቃል ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው መሆኑን፣ ሥግው ቃል ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ከመወለድ ጀምሮ ለሰው ሲል ያደረውን - መጠመቁን፣ ዞሮ ማስተማሩንና ያስተማረውን ቃልና ትእዛዝ ማመንን፣ መከራ መቀበሉን፣ በመጨረሻም በራሱ ፈቃድ ለእኛ ሲል መሞቱን፣ መቀበሩንና በሦስተኛው ቀን መነሣቱን እና በአርባኛው ቀን ወደ ቀደመ ክብሩ ማረጉን . . . ሁሉ ማመን ለመዳን አስፈላጊ ነው፡፡ በአጠቃላይ ሐዋርያዊት የሆነች ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከጌታችንና ከሐዋርያት የተቀበለችውንና የምታምነውን ሁሉ በፍጹም ልብ ማመን ያስፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ያደረገውን ልዩ ቸርነትና እናምነው ዘንድ የገለጠውን እውነት የማያምን ሰው ሊድን አይችልም፡፡

ያዳነን አምላክ ማን መሆኑን እርሱ ራሱ አምላካችን በገለጠልን መጠን ማወቅና ማመን ለመዳን ወሳኝ መሆኑን ጌታችን በትምህርቱ ደጋግሞ ተናግሯል፡፡ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር ሲነጋገር እርሷ "አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ፤ እናንተም ሰው ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ" ባለችው ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አላት፡- ". . . *<u>እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፤</u> እኛ መዳን ከአይሁድ ነውና <u>ለምናውቀው እንሰግዳለን</u>። ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፤ አሁንም ሆኗል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና፤ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ <u>የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል</u>።"* ዮሐ. 4፡20-24 የምናመልከውንና የምንሰግድለትን ማወቅና አምልኳችንም በኑፋቄና በስህተት በተበከለ ትምህርት መሠረት ሳይሆን በእውነተኛ ትምህርት የተመሠረተ እምነት ሊሆን እንደሚገባው አስተማረን፡፡ አስተምህሮው የተሳሳተ እምነት አምልኮው ትክክል ሊሆን አይችልምና፡፡

የምንሰግድለት አምላክ ሰዎች በኑፋቄ ትምህርታቸው በምናባቸው የሣሉትና በሃሳባቸው የፈጠሩት ሳይሆን እኛ በሚገባን መንገድ ራሱን ለእኛ የገለጠውና እንድናውቀው ያደረገን እውነተኛው አምላክ መሆን አለበት፡፡ አለበለዚያ እንደ ሳምራውያን *"እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ"* የሚል ወቀሳን ያስከትላል፡፡ ስለዚህም ነው ጌታችን "እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት" በማለት እውነተኛ አምላክ የሆነውን እርሱን ማወቅ የዘለዓለም ሕይወት መሠረት መሆኑን የተናገረው፡፡ ዮሐ. 17፥ 3 ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ "ሰው በጨለማ ስፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ" በማለት ለመጽሐፍ ቅዱሳዊና ሐዋርያዊው ትምህርት ታላቅና ከባድ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ አስተምሮናል፡፡ 2 ጴጥ. 1፥19 እንደዚሁም ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በራእዩ ማብቂያ ላይ እንዲህ ብሏል፡-

> "በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ፥ ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍቶች ይጨምርበታል፤ ማንም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጎድል፥ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል።" ራእ. 22፥18-19

ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ የሌለው ሰው ከመዳን መንገድ የወጣ ስለሆነ እንዲህ ያለውን ሰው በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ እንዲህ ይላል፡-

> ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ገብተዋልና፥ እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የማያምኑ ናቸው፤ ይህም አሳቹና የክርስቶስ ተቃዋሚው ነው። ሙሉ ደመወዝን እንድትቀበሉ እንጂ የሠራችሁትን እንዳታጠፉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከዚህ አስተምህሮ ለሚወጣ ሁሉ፥ በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖር ሰው አምላክ የለውም፤ በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት። ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት፥ ሰላምም አትበሉት፤ ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና። 2 ዮሐ. 7-11

እግዚአብሔር ያደረገውን ቸርነትና የፈጸመውን ድኅነት ለማያምን ሰው ለእርሱ ልክ የሰው ድኅነት እንዳልተፈጸመና ገና እንዳልዳነ ይሆንበታል፡፡ ይህም ማለት በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምን ሰው አሁን እየኖረበት ያለው ዘመኑ ዘመነ ወንጌል ዓመተ ምሕረት ቢሆንም  እርሱ ግን በዘመነ ኦሪት በዓመተ ፍዳ እንደ ነበሩት ሰዎች ይሆናል ማለት ነው፡፡ በእርግጥ እንዲያውም በዚያ ዘመንም ወደፊት በዘመነ ወንጌል የሚሆነውን በእምነት አሻግረው ያዩና በተስፋ የጠበቁ ደጋግ አበው ነበሩ፡፡ ከዘመኑ ሳይደርሱ እንደ ደረሱ ሆነው ሥጋዌው ከፊታቸው ግልጽ ብሎ እየታያቸው ዕለቱን እንደ ተፈጸመ እያደረጉ ትንቢት የተናገሩ ነቢያትም ነበሩ፡፡ አሁን በዘመነ ወንጌል በዓመተ ምሕረት እየኖረ የማያምን ኢአማኒ ሰው ግን በዘመነ ብሉይ እንደ ነበሩት አሕዛብ ያለ ነው፡፡ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በኢየሱስ ክርስቶስ ያላመነን ሰው ምን እንደሚገጥመው ሲናገር "*<u>በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም</u>*" ያለው ለዚህ ነው፡፡ ዮሐ. 3፥36

ጌታችን በቅዱስ ቃሉ፡- *"እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም"* በማለት ማመን የሕይወት መንገድ መሆኑን አስተምሮናል፡፡ ዮሐ. 5፥24 እንዲሁም *"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና፡፡ . . . በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል"* በማለት በእርሱ ማመን የድኅነት መሠረት ሲሆን አለማመን ደግሞ የፍርድና የሞት መንገድ መሆኑን ቅዱስ ቃሉ ይናገራል፡፡ ዮሐ. 3፥18 ፤ ዮሐ. 4:5 ፤ ዮሐ. 5:10

እንዲሁም *"የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀበሉት፤ ከአንተም ዘንድ እንደ ወጣሁ በእውነት አወቁ፤ አንተም እንደ ላከኸኝ አመኑ"* በማለት እምነት እርሱ የነገረንን ቃል መቀበልና ማመን መሆኑን ተናግሯል፡፡ ዮሐ. 17፥8 በአጠቃላይ እግዚአብሔር እርሱን ማወቅ በምንችለው መጠን እናውቀውና እናምነው ዘንድ፤ ወደ እውነት ይመራን ዘንድ በቅዱስ መጽሐፍ የገለጠውን እውነት መቀበልና ማመን ለድኅነት የግድ ነው፡፡ *"ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ፤ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና"* እንደ ተባለ፡፡ ዕብ. 11፥6

ሃይማኖት የድኅነት መሠረት ነው፡፡ ቤት ያለ መሠረት ሊቆም እንደማይችልና በአየር ላይ ሕንፃ መገንባት እንደማይቻል ሁሉ የዘለዓለማዊ ድኅነት መሠረትም ሃይማኖት ነው፡፡

መዳን ከእግዚአብሔር የተሰጠን ስጦታ (ጸጋ) ነው፡፡ የእኛ ድርሻ ደግሞ በመጀመሪያ ይን የእግዚአብሔርን ስጦታ እሺ ብሎ መቀበልና ለእግዚአብሔር የማዳን ጥሪ በጎ ምላሽ መስጠት ነው፡፡ በዚህ ላይ ይህ እሺ ማለታችንና መዳንን መሻታችን በተግባር የሚገለጽባቸው እና ለሁሉም የሰው ልጅ በአዋጅ የተሰጠውን የመዳን ጸጋ ለእያንዳንዳችን ገንዘብ የምናደርግባቸውንና ራሱ ያዳነን እግዚአብሔር አድርጉ ያለንን ነገሮች መፈጸም ይኖርብናል፡፡ መዳን እንዲሁ "አምኛለሁ" በማለት ብቻ የሚፈጸም አይደለም፤ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ሰው በመሆን በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ማኅፀን ከመፀነስ ጀምሮ ከኃጢአት በስተቀር በእኛ ላይ የሚደርሰውን ነገር ሁሉ እንደ ተቀበለና ብዙ ሂደቶችን እንዳሳለፈ ሁሉ የእኛ መዳንም የሚፈጸመው አዳኛችን የሆነው እርሱ በተግባር ሠርቶ ባሳየንና በተጓዘበት መንገድ ስንጓዝ ነው፡፡

በክርስቶስ ማመን በወንጌል የተነገረውን ከመቀበል ወይም እውነት ነው ብሎ ከመስማማት ያለፈ ነገር ነው፡፡ ማመን መሠረት እንጂ መደምደሚያ፤ መጀመሪያ እንጂ መጨረሻ አይደለም፡፡

## 3.7.2 ለድኅነት መሠረታዊ የሆኑ ምሥጢራትን መፈጸም

ለመዳን ከማመን ቀጥሎ ለድኅነት ወሳኝና አስፈላጊ የሆኑ ምሥጢራትን መፈጸም ይገባል፡፡ እነዚህም በመጀመሪያ ጥምቀት፤ ቀጥሎ ሜሮን እና ከዚያም ቅዱስ ቁርባን ሲሆኑ ከዚያ በኋላ በሕይወት ሂደት ለሚገጥሙ ነገሮች ደግሞ ንስሐ ናቸው፡፡ እነዚህ ምሥጢራት የሚፈጸሙትም በቅድስት ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ነው፡፡ ለድኅነት መሠረታዊ የሆኑት ምሥጢራት ከቤተ ክርስቲያን ውጭ አይፈጸሙም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስን በሚያስደንቅ ሁኔታ ራሱ ጌታችን ተገልጦ ከጠራውና ካነጋገረው በኋላ ለመዳን የሚያስፈልገውን ነገር ያገኝ ዘንድ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲሄድ ነበር ያዘዘው፡፡ የሐዋ. 9 ቆርኔሌዎስንም እንዲሁ ቅዱስ ጴጥሮስን እንዲያስመጣና ለመዳን የሚያስፈልገውን ነገር በቤተ ክርስቲያን በኩል እንደሚያገኝ ነበር የነገረው፡፡ የሐዋ. 10 ይህም ያለ እነዚህ ምሥጢራትና ምሥጢራቱ ከሚፈጸሙባት ከቤተ ክርስቲያን ውጭ እንዲሁ በባዶ ሜዳ "አምኛለሁ" በማለት ብቻ የማይፈጸሙና መዳን የማይቻል ስለሆነ ነው፡፡

### 3.7.2.1 ምሥጢረ ጥምቀት

#### 3.7.2.1.1 የተሐድሶዎች አስተምህሮ ስለ ጥምቀት

ጥምቀትን በተመለከተ የተሐድሶዎች አስተምህሮ እንዲህ የሚል ነው፦

- "ጥምቀት ወደ መንግሥተ ሰማያት ከመግባት ጋር አንዳች ግንኙነት የለውም።" (ጠማሪ ጽድቅ፣ ጥቅምት 1991 ዓ.ም. ገጽ 88)
- "ሐዋርያው ጳውሎስ ከጌታ ከተገናኘ በኋላ በአጋጣሚ ከመጠመቁ በፊት ሞቶ ቢሆን እንኳን ገነት ይገባ ነበር። . . . ጥምቀት ከዓለም አኗኗር ሊኖረን ከሚገባው ውጫዊ ስፍራ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው።" (ጠማሪ ጽድቅ፣ ጥቅምት 1991 ዓ.ም. ገጽ 93)
- "ጥምቀት የኃጢአትን ሥርየት አያሰጥም።" (መሠረታዊ የክርስትና እምነት መግቢያ፣ 2000 ዓ.ም.፣ ገጽ 1)
- "ነገር ግን የምንጠመቀው በሰማያት በክብር ወደ ተቀመጠው ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለም። ይህም ማለት የምንጠመቀው ከጌታ ሞት ጋር ኅብረት ለማድረግ እንጂ አሁን እርሱ በሰማያት ካለው ክብሩ ጋር ኅብረት ለማድረግ አይደለም።" (ጠማሪ ጽድቅ፣ ጥቅምት 1991 ዓ.ም. ገጽ 89)
- "ጥምቀት በውኃ ሲደረግ በውስጥ ለሚሆነው ለሐዲስ ልደት ጸጋ አፍአዊ መግለጫና ሰዎች በክርስቶስ ሞት ምሳሌ ለኃጢአት እንደ መሞት <u>ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ መግባትን የሚያስታውቁበት</u>፣ እንዲሁም ማንኛውም ነገድ ወደ አንዲት ሥጋ በአንድ መንፈስ ሲጠመቅ ዋናው የትምህርቱ ምሥጢር ሆኖ አምላካዊ የጽድቅ ኪዳን ማኅተም ያለበት <u>ሜዳዊ ምልክት ነው</u>።" (ስምዓ ጽድቅ ብሔራዊ፣ ገጽ 159)

ተሐድሶዎች ስለ ጥምቀት ያላቸው አስተምህሮ ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፦

1. "ጥምቀት ወደ መንግሥተ ሰማያት ከመግባት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ምንም ጥቅም የለውም። እንዲህም ስለሆነ (ማለትም ጥምቀት ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ምንም ፋይዳ ስለሌለው) ቅዱስ ጳውሎስ ከጌታ ከተገናኘ በኋላ በአጋጣሚ ከመጠመቁ በፊት ሞቶ ቢሆን እንኳን ገነት ይገባ ነበር።" ይህም ማለት ያልተጠመቀ ሰው ካመነ ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊገባ ይችላል ማለታቸው ነው። እዚህ ላይ በጣም የሚገርመው ይህን ትምህርት ማለትም "ቅዱስ ጳውሎስ ከጌታ ከተገናኘ በኋላ በአጋጣሚ ከመጠመቁ በፊት ሞቶ ቢሆን እንኳን ገነት ይገባ ነበር" የሚለውን ከየት አገኙት? መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ የሚል ቃል ፈጽሞ የለውም። ለክህደትና ለጥፋት ድፍረታቸው እስከዚህ ድረስ ነው።

2. "ጥምቀት ከዓለም አኗኗር ሊኖረን ከሚገባው ውጫዊ ስፍራ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው"። ይህም ማለት የጥምቀት ፋይዳ አንድ ሰው ወደ አንድ ድርጅት አባል ሆኖ ሲገባ የድርጅቱ አባል መሆኑን የሚገልጽ መታወቂያ እንደሚሰጠው ዓይነት ነው ማለት ነው። "ጥምቀት . . . <u>ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ መግባትን የሚያስታውቁበት</u>፣ . . . አምላካዊ የጽድቅ ኪዳን ማኅተም ያለበት <u>ሜዳዊ ምልክት ነው</u>" ያሉት ለዚህ ነው።

ይህን እምነታቸውንና አስተምህሯቸውን ከመጨረሻ ጥግ ድረስ ሲለጥጡት ደግሞ "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ራሱን ከምእመናን ጋር አንድ ለማድረግ ተጠመቀ" አሉ። (ጠማሪ ጽድቅ፣ ጥቅምት 1991 ዓ. ም.፣ ገጽ 88) ይህም ማለት ጌታችን የተጠመቀው እንደዚሁ ራሱን ከምእመናን ጋር አንድ ለማድረግ (ከምእመናን ገብቶ ለመቆጠር) እንጂ የእርሱ መጠመቅ እኛ በጥምቀት የምናገኘውን ጸጋ ለመስጠት የሚችል ለማድረግና ጥምቀትን ለመባረክና ለመቀደስ አይደለም ማለት ነው።

3. ሌላው ደግሞ "ጥምቀት የኃጢአትን ሥርየት አያሰጥም" የሚለው ትምህርታቸው ነው፡፡

ተሐድሶዎች ስለ ጥምቀት ያላቸው እምነትና ትምህርት ይህ ከሆነ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ይህ እምነታቸውና አስተምህሯቸው በመጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ይመዘናል፡፡ ቀጥሎም በጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አባቶች ትምህርት ይመዘናል፡፡

## 3.7.2.1.2 ጥምቀት - በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ

ጥምቀት ለስሙ አጠራሩ ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁሉም ከምሥጢራት ሁሉ አስቀድሞ የፈጸመው ታላቅ ምሥጢር ነው፡፡ ደቀ መዛሙርትን ከመሰብሰቡ በፊት፣ ትምህርትና ተአምራት ከመጀመሩ በፊት፣ ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ሄዶ መጾምና መጸለይ ከመጀመሩ በፊት የመጀመሪያው ሥራው ያደረገው በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ በመጠመቅ ምሥጢረ ጥምቀትን መመሥረትን ነው፡፡ ማቴ. 3፥16-17 በጥምቀቱም ጊዜ አብ በደመና ሆኖ "ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር - የምወደው ልጄ ይህ ነው" አለ፡፡ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ዐረፈ፡፡ በዚህም ምሥጢረ ሥላሴ ተገለጠ፡፡ ይህም ጥምቀት የእግዚአብሔር አንድነትና ልዩ ሦስትነት የተገለጠበት ልዩ ምሥጢር መሆኑን ያስረዳል፡፡ ከዚያ በፊት እንዲያ ባለ ሁኔታ ያልተገለጠ ድንቅ ምሥጢር የተገለጠበት ስለሆነም ነው "ሰማያት ተከፈቱ" የተባለው፡፡

ጌታችን በውኃ በመጠመቅ ለእኛ መዳን ጠቃሚ የሆኑ ብዙ ተግባራትን አደረገልን፡፡ <u>አንደኛ</u> በተግባር በመጠመቅ ጥምቀት ለማንኛውም ሰው አስፈላጊ መሆኑን አሳየን፡፡ <u>ሁለተኛ</u> በውኃ በመጠመቅ ከዚያ በኋላ ለምንጠመቅ ለእኛ ማያት በጸሎት ሲባረኩ ዳግመኛ የምንወለድባቸው ማኅፀኖች እንዲሆኑ ኃይልን ሰጣቸው፣ ቀደሳቸው፡፡ <u>ሦስተኛ</u> እርሱ ሲጠመቅ አብ በደመና ሆኖ ልጅነቱን እንደ መሰከረለት እኛም ስንጠመቅ ከእርሱ ዳግመኛ መወለዳችንና የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ይመሰክርልናል፡፡ <u>አራተኛ</u> እርሱ ሲጠመቅ "ሰማያት ተከፈቱ" እንደ ተባለ በጥምቀቱ አገራችን በሰማይ መሆኑን የአገራችንን በር ከፍቶ አሳየን፤ የምንጠመቀው ያን ሰማያዊ ሀገር ለመውረስ የሚያበቃንን ልጅነት ለማግኘት መሆኑን በተግባር አሳየን፡፡

ስለዚህ ጌታችን የተጠመቀው እነዚህና የመሳሰሉትን ሀብታትና ምሥጢራት ሊሰጠን እንጂ ተሐድሶ ወገኖቻችን "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ራሱን ከምእመናን ጋር አንድ ለማድረግ ተጠመቀ" እንደሚሉት አይደለም፡፡ ይህ መሠረታዊ የሆነውን የጌታችንን ጥምቀት ለማቃለልና ከንቱ ለማድረግ መሞከር ነው፡፡ በጥምቀት የማያምኑ አሕዛብስ ከዚህ የበለጠ ሌላ ምን ይላሉ? ያውም የእነርሱ አቋማቸውና ማንነታቸው የለየላቸው ስለሆነ ግልጽ ነው፤ እነዚህ ግን ወንጌል እናምናለን፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንሰብካለን ይላሉ፤ የሚሉትን ወደ ውስጥ ገብቶ ሲያዩት ደግሞ እንዲህ ያለ ጸረ መጽሐፍ ቅዱስ ሆኖ ይገኛል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደ ተነገረው ጥምቀት የሚከተሉት ዋና ዋና ጠቀሜታዎች አሉት፡-

1. ሥርየተ ኃጢአት፣ መዳን

ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ለማዳን ከፅንሡቱ ጀምሮ እስከ ዕርገቱ ድረስ ያደረገው ነገርና የሰጠው ጸጋ፣ እንዲሁም በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ የቆረሰው ሥጋውና ያፈሰሰው ደሙ፣ ሞትን ድል አድርጎ መነሣቱ ሁሉ ለእያንዳንዳችን የሚደርሰን በጥምቀት አማካኝነት ነው፡፡ ጌታችን በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ሳለ ሐራዊ ጎኑን በጦር በወጋው

ጊዜ ከቅዱስ ጎቦው (ጎኑ) ውኃና ደም እንዲወጣ የፈቀደው ለዚህ ነበር፣ ከጎኑ በተገኘው በውኃውና በደሙ ልጅነትንና ሥርየተ ኃጢአትን እንድናገኝ ነው፡፡ በማየ ገቦው እንጠመቃለን፥ ደሙን ደግሞ በምሥጢረ ቁርባን እንቀበለዋለን፡፡

ቅዱሳን ሐዋርያት በተሰፋ ቃሉ መሠረት ጸጋ መንፈስ ቅዱስን እንደ ተቀበሉ በዓለ ሰዊትን ለማክበር በኢየሩሳሌም ተሰብስበው ለነበሩት አይሁድ ቅዱስ ጴጥሮስ የዘለዓለም ሕይወትን ይወርሱ ዘንድ ማድረግ ስላለባቸው ነገር ሲያስተምራቸው በትምህርቱ ልባቸው ተነክቶ *"ምን እናድርግ?"* ብለው በጠየቁት ጊዜ "ካመናችሁ ይበቃችኋል፥ ሌላ የሚያስፈልጋችሁ ምንም ነገር የለም" አላላቸውም፤ *"ንስሐ ግቡ፣ ኃጢአታችሁም ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ"* በማለት ለመዳንና ሥርየተ ኃጢአትን ለማግኘት መጠመቅ እንዳለባቸው ነገራቸው እንጂ፡፡ የሐዋ. 2፥38 *"ጥምቀት የኃጢአትን ሥርየት አያስገኝም"* የሚሉት ተሐድሶዎች ከዚህ የእግዚአብሔር ቃል ጋር በቀጥታ ሲቃረኑ እናያለን፡፡ እንዲሁም ይድኑ ዘንድ የሐዋርያትን ትምህርት ሰምተው በጌታ አምላክነትና መድኃኒትነት ያመኑ እነ ሊዲያ፣ ቆርኔሌዎስ፣ የወኅኒ ጠባቂው ሁሉ ተጠምቀዋል፡፡ የሐዋ. 10፥47 ፣ 16፥15 ፣ 33 ስለዚህ የሰው ልጅ ይድን ዘንድ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሊጠመቅ ይገባዋል፡፡ ማቴ. 28፥19-20

ጌታችን *"ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል"* በማለት ጥምቀት ለመዳን የግድ አስፈላጊ ምሥጢር መሆኑን በማይታበል ቃሉ አስተምሮናል፥ ማር. 16፥16 ቅዱስ ጳውሎስም፥ - *"ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና (በጥምቀት) በመንፈስ ቅዱስ መታደስ አዳነን"* በማለት ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአትና ለመዳን መፈጸም የሚገባው ፀሳኝ ምሥጢር መሆኑን ጽፎልናል፡፡ ቲቶ. 3፥5

እንዲሁም ጥምቀት ለመዳን አስፈላጊ የሆነ ምሥጢር መሆኑን ቅዱስ ጴጥሮስ ምሳሌውን ተርጉሞ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- "ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቈየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም። <u>ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል</u>፥ የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም፥ ለእግዚአብሔር የበጎ ሕሊና ልመና ነው እንጂ፤ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው፡፡" 1 ጴጥ. 3፥20-21 እንግዲህ ጥምቀት የሚያድን መሆኑን፥ የሰውነትን እድፍ ማስወገድ ሳይሆን ውሳጣዊ እድፍን (ኃጢአትን) ማስወገጃ ምሥጢር መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ይመሰክርልናል፡፡

አስቀድሞ በትንቢትም "ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለሁ፣ እናንተም ትጠራላችሁ፣ ከርኩሰታችሁም ሁሉ ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ" በማለት በውኃ በሚፈጸመው ጥምቀት አማካይነት ከርኩሰት መንጻትና ከኃጢአት ሥርየት የማግኘት ጸጋ እንደሚሰጥ ተነግሮ ነበር፡፡ ሕዝ. 36፥25 ጊዜው ሲደርስ ደግሞ መድኃኒታችን ይህን አማናዊ ምሥጢር አድርጎ ሰጠን፡፡ በሁለተኛው ዓለም አቀፋዊ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በ381 ዓ.ም. በቁስጥንጥንያ የተሰበሰቡት አንድ መቶ ሃምሳው ቅዱሳን አባቶቻችንም በጸሎተ ሃይማኖት ላይ "ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት - ኃጢአት በሚሠረይባት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን" ብለው የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን እምነት የገለጹት ለዚህ ነው፡፡

ስለዚህ *"ጥምቀት የኃጢአትን ሥርየት አያስገኝም"* የሚለው የተሐድሶዎች ትምህርት ከጌታችን ትምህርት ጋር በቀጥታ የሚጋጭ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ የስህተት ትምህርት ሰዎች አምነው በመጠመቅ ሥርየተ ኃጢአትንና መዳንን እንዳያገኙ ዲያብሎስ የሚያሰራጨው የሞት ትምህርት መሆኑን ይኸው መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ይመሰክርባቸዋል፡፡

## 2. የእግዚአብሔርን ልጅነት ማግኘት፡ ዳግም ልደት

ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችን "እውነት እውነት እልሃለሁ፣ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም" በማለት፡ እንዲሁም "እውነት እውነት እልሃለሁ፣ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው" በማለት በጥምቀት ዳግመኛ ያልተወለደ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት የማይችል መሆኑን በአምላካዊ ቃሉ አስተምሮናል፡፡ ዮሐ. 3፡3-6 አንድ ሰው ከእናትና ከአባቱ ሥጋዊ ልደትን እንደሚወለድ ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ ደግሞ በጥምቀት አማካይነት መንፈሳዊ ልደትን ይወለዳል፡፡ በዚህ መንፈሳዊ ልደትም የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል፡፡ በልጅነት ጸጋውም የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ባለ ተስፋ ይሆናል፤ በጊዜው ጊዜም የተዘጋጀለትን የአባቱን መንግሥት ይወርሳል፡፡

"ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ" በማለት የጥምቀትን አፈጻጸም ነገረን፡፡ በሚታየው በውኃው አማካይነት በመጠመቅ መንፈሳዊ ልደትን ከእግዚአብሔር እንወለዳለን፡፡ ጌታችን በጥምቀቱ ማየትን ስለ ቀደሳቸው በጸሎት አማካይነት ማየ ጥምቀቱ ሲቀደስ ተጠማቂዎች በሚታየው በውኃው አማካይነት የማይታየውን ረቂቅ ልደት የሚወለዱበት ማኅፀን ይሆናል፡፡ ይህ በጥምቀት የሚገኘው ዳግመኛ ልደት የማይጠፋና የማያዳግም ዘለዓለማዊ የልጅነት ማኅተም ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ "ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፤ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ" በማለት እንደ ተናገረው ይህን የማይጠፋ ዘለዓለማዊ የልጅነት ጸጋ በጥምቀት የሚገኝ መሆኑን ነው፡፡ 1 ጴጥ. 1፡23 "አንዲት ጥምቀት" የተባለውም ለዚህ ነው፡፡ ሰው ሥጋዊ የሆነውን የመጀመሪያውን ልደት ከእናትና ከአባቱ የሚወለደው አንድ ጊዜ ብቻ እንደ ሆነ ሁሉ መንፈሳዊ (ረቂቅ) የሆነውን ልደት ከእግዚአብሔር በጥምቀት አማካይነት የሚወለደውም እንዲሁ አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ኤፌ. 4፡5

በጥምቀት በምናገኘው ዳግም ልደትና የእግዚአብሔር የልጅነት ጸጋ የመንግሥቱ ወራሾች እንሆናለን፡፡ "ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ፡፡ ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም" የተባለው ይፈጸምልናል፡፡ ገላ. 4፡6-7 እንዲሁም "አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል" የተባለው በጥምቀት ዳግመኛ ለተወለዱና የልጅነትን ጸጋ ላገኙ ክርስቲያኖች ነው፡፡ ሮሜ 8፡15-17 ከዲያብሎስ ባርነት ወጥተን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆንን ጸጋ የምናገኘው በጥምቀት ምሥጢር አማካይነት ነው፡፡ ያለ ጥምቀት የእግዚአብሔር ልጅነት፤ ያለ እግዚአብሔር ልጅነት ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረስ አይቻልም፡፡

ቅዱስ ወንጌል "ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው" ሲል ልጅነት ወደሚገኝበት ወደ ጥምቀት የሚያደርሰው መሠረት በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን መሆኑን የሚገልጽ እንጂ የእግዚአብሔር ልጅነት በማመን ብቻ ይገኛል ማለቱ አይደለም፡፡ ዮሐ. 1፡12 በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ክፍሎች የተነገሩትን የእግዚአብሔር ቃላት አንድ አድርጎ በአንድ መንፈስ አስማምቶ መረዳትና መተግበር ይገባል እንጂ ለራስ ስሜትናአስተሳሰብ የምትስማማ የመሰለችውን አንዲቷን ጥቅስ ብቻ እንጠልጥሎ ከዚያ ላይ የሃይማኖት አስተምህሮ መፍጠር ብዙዎች መናፍቃን ራሳቸውን በራሳቸው ያጠፉበት አደገኛ የስህተት አካሄድ ነው፡፡ ለምሳሌ ጌታችን "ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ፥ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋው አይጠፋበትም" ብሏል። ማቴ. 10፡42

ታዲያ ይህ ማለት አንድ ሰው በእግዚአብሔር ሳያምን፣ ሳይጠመቅ፣ ወዘተ እንዲሁ በደቀ መዝሙር ስም ቀዝቃዛ ውኃ በማጠጣት ብቻ የዘለዓለም ሕይወትን ይወርሳል ማለት ነውን? አይደለም! አንድ ሌላ ምሳሌ ብንጨምር መድኃኒታችን "ነፍሱን በዚህ ዓለም የሚጠላ ለዘላለም ሕይወት ይጠብቃታል" ብሏል፡፡ ዮሐ. 12፡25 ይህ ማለት ግን ሳያምን፣ ሳይጠመቅ፣ ከቅዱስ ሥጋውና ከክቡር ደሙ ሳይቀበል፣ . . . ነፍሱን ስለ ጠላ ብቻ የዘላለም ሕይወትን ይወርሳል ማለቱ አለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህ አንድን የእግዚአብሔርን ቃል ከተነገረበት ዓራ አውጥቶ ያን ጉዳይ በተመለከተ የተነገረውን ሌላውን የእግዚአብሔር ቃል ያልተጻፈ ያህል ረስቶና ትቶ "መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል"፣ "የጌታ ትምህርት ይህ ነው" እያሉ በድፍረት መናገር ትርፉ ለተናጋሪውም ሆነ ለሰሚው ተያይዞ መጥፋት ብቻ ነው፡፡

3. *መንግሥት ሰማያትን መውረስ*

በጥምቀት በምናገኘው የእግዚአብሔር የልጅነት ጸጋ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ የምንችል ባለ ተስፋዎች እንድንሆን ያደርገናል፡፡ ልጅ ያልሆነ ርስት የመውረስ መብት እንደ ሌለው ሁሉ በጥምቀት ዳግመኛ ያልተወለደና የእግዚአብሔርን የልጅነት ጸጋ ያላገኘ ሰውም በራሱ ምግባር ትሩፋት የቱንም ያህል ሰማይ ቢደርስ እንኳ የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረስ አይችልም፡፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት የሚያስችል ምንም ዓይነት የሰው ልጅ ምግባርና ተጋድሎ የለም፣ ሊኖርም አይችልም፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በዚህ ዓለም ገንዘብም ሆነ በሰው ተጋድሎ የምትገዛና የምትዋጅ አይደለችም፡፡ በሰው ጽድቅ ብቻ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት የሚቻል ቢሆን ኖሮ አካላዊ ቃል ሰው መሆንና ያን ሁሉ የማዳን ጉዞ መጓዝ ባላስፈለገው ነበር፡፡ ሰው በራሱ ተጋድሎ ብቻ መጽደቅ ቢችል ኖሮ ሐዋርያው "በከንቱኬ ሞተ ክርስቶስ - እንግዲያ ክርስቶስ በከንቱ ሞቷል!" እንዳለው የክርስቶስ ሞት አላስፈላጊ በሆነ ነበር፡፡ ግን አይደለም፣ እግዚአብሔር የሰጠንን ጸጋ ለመቀበል በጥምቀት የእግዚአብሔር ልጆች ሆነን ካልተወለድን በስተቀር ከእናት ከአባት በተወለድነው ተፈጥሯዊና ሥጋዊ ልደት መንፈሳዊና ሰማያዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ አንችልም፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ጥምቀት የግድ አስፈላጊ ነው፡፡

ለዚህ ነው ጌታችን "*ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም*" በማለት ግልጽና የማያሻማ ጽኑ ዐዋጅ የተናገረው፡፡ እንዲሁም በአጽንዖት በድጋሚ እዚያው ላይ "*እውነት እውነት እልሃለሁ፣ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም*" በማለት ያስተማረን ለዚህ ነው፡፡

ልጅነታችን መንግሥቱን የምንወርስ ለመሆናችን መያዣ (ዐረቦን) ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "*ወወሀበነ ዐረቦነ መንፈሶ - የመንፈሱን መያዣ ሰጠን*" በማለት የገለጸው ይህን ምሥጢር ነው፡፡ 2 ቆሮ. 5፡5 አንድ ሰው አንድን ዕቃ ሲገዛ ወዲያውኑ ሙሉ ዋጋውን በገንዘብ ከፍሎ ካልወሰደው "ዕቃውን እገዛዋለሁ፣ ይቆመጥልኝ" ቢል ያን ዕቃ በእርግጥ የሚገዛውና ተመልሶ መጥቶ ሙሉ ዋጋውን ከፍሎ የሚወስደው መሆኑን ለማረጋገጥ የተወሰነ የመያዣ ገንዘብ ወይም ቀብድ አስቀድሞ ይከፍላል፡፡ ቀብድ ከከፈለ ያን የከፈለውን ገንዘቡን ሜዳ ላይ ትቶ ስለማይቀር ተመልሶ መጥቶ ሙሉ ዋጋውን ከፍሎ ያን ዕቃ እንደሚወስደው ማረጋገጫ ወይም መያዣ ይሆናል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ የእኛንም ጉዳይ የገለጸው እንዲህ ባለ ሁኔታ ነው፡፡

ይህም ማለት ዛሬ ልጅነትን በጥምቀት አግኝተናል፤ መንግሥቱን ግን ገና አልወረስንም፡፡ ታዲያ መንግሥቱን የምንወርስ ስለ መሆናችን ማረጋገጫው ወይም ዋስትናው ምንድን ነው? የሚል ሰው ቢኖር መያዣው በጥምቀት የልጅነትን ጸጋ ማግኘታችን ነው፡፡ በጥምቀት የሚገኘውን የልጅነት ጸጋ እንደ ዐረቦን ስለ ያዝን "ትምጻእ መንግሥትከ - መንግሥትህ ትምጣልን" እያልን ደጅ የምንጠናትን መንግሥቱን ደግሞ በጊዜው ጊዜ ስትገለጥ በቸርነቱ ያወርሰናል ማለት ነው፡፡ "ልጅም ከሆንህ ደግሞ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ" ተብሏልና፡፡ ገላ. 4፡7 እንዲሁም "ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፤ አብረንም ደግሞ እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን" ተብሏል፡፡ ሮሜ 8፡15-17 ስለዚህ ጥምቀት የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ የሚያስችለንን ታላቁን ጸጋ - የእግዚአብሔርን ልጅነት - የምናገኝበት ድንቅ ምሥጢር ነው፡፡

ስለሆነም "ጥምቀት ወደ መንግሥት ሰማያት ከመግባት ጋር አንዳች ግንኙነት የለውም" የሚለው የተሐድሶዎች ትምህርት ባለቤቱ አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማይታበል ቃሉ "እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም፣ እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም" ብሎ ካስተማረው ትምህርት ጋር ተቃራኒ ነው ማለት ነው፡፡ እንዲሁም ጌታችን "ያመነ የተጠመቀ ይድናል" ካለው ትምህርት ጋርም በቀጥታ የሚቃረን ነው፡፡ ጌታችን ለመዳን መጠመቅ አስፈላጊ መሆኑን፣ በጥምቀት ከውኃና መንፈስ ያልተወለደ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ እንደማይችል አስተማረን፡፡ ተሐድሶዎች ደግሞ ጥምቀት ለመዳን ምንም ጥቅም እንደ ሌለው ይነግሩናል፡፡

ተሐድሶዎች "ሐዋርያው ጳውሎስ ከጌታ ከተገናኘ በኋላ በአጋጣሚ ከመጠመቁ በፊት ሞቶ ቢሆን እንኳን ገነት ይገባ ነበር" በማለት የፈጠራ ትምህርታቸውን ሊነዙብን ሞክረዋል፡፡ ይህ ትምህርታቸው ፍጹም እንግዳና ሰው ሠራሽ (ተሐድሶ ሠራሽ) የሆነ ትምህርት እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፡፡ ይህ ሰይጣን በገነት አባታችን አዳምንና እናታችን ሔዋንን "በበላችሁ ቀን ሞትን ትሞታላችሁ" ብሎ እግዚአብሔር የነገራቸውን ቃል ገልብጦ በተቃራኒው "ሞትን አትሞቱም፣ ከእርሷ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ" ብሎ እንደ ነገራቸው ያለ ተቃራኒ ትምህርት ነው፡፡ ዘፍ. 3፡4-5 የሚናገርበት እንደበትና የተሰወረበት ሰውነት ተለየየ እንጂ ያን ጊዜ በእባብ፣ ዛሬ ደግሞ በሥጋ ወንድሞቻችን በሆኑ ሰዎች አድሮ እውነቱን ሐሰት፣ ሐሰቱን እውነት እያስመሰለ በማቅረብ የሚፈትነን ያው ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ ነው፡፡ እንዲህ ያለውን "ልዩ ወንጌል" ደግሞ "ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን። አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፥ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን" ተብሏልና ልንቀበለው አንችልም፣ መቼምም አንቀበለውም፡፡ ገላ. 1፡6-9

የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ እምነት ብቻ ሳይሆን በማመን ላይ ጥምቀት የግድ ከሆነ፣ ተሐድሶዎች ደግሞ ለመዳን መጠመቅ አያስፈልግም የሚሉ ከሆነ እነርሱ "መዳን" የሚሉት ምኑን ይሆን? መዳን የሚሉት ምን ዓይነት መዳን ነው? ይህን ሁሉ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነና ሰዎችን ከመዳን መንገድ በተቃራኒ የሚመራ ትምህርት ይዘው ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የተቆረቆሩ መስለው ለመታየት የሚሞክሩት ተደራሲያቸውን ምን ያህል ቢንቁ ይሆን? ምነው ያውቁብናል፣ ይታዘቡናል ማለት ጠፋ! ለነገሩ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሕሊና ሰውን እንዴት አድርጎ ሊያፍር ይችላል?

### 4. ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን፤ በሞቱና በትንሣኤው መተባበር

ጥምቀት የጌታችንን ሞቱንና ትንሣኤውን ማመናችንን በተግባር የምንመሰክርበትና ከሞቱና ከትንሣኤው የምንሳተፍበት ምሥጢር ነው፡፡ ይህን ምሥጢር ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ገልጾታል፦

> ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፤ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን። ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን ሮሜ 6፡3-5

ጌታችን ስለ እኛ ሲል ሞትን በፈቃዱ ተቀብሎ ከዚያም ወደ መቃብር ወርዶ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ቆየ እኛም ያን ማመናችንን በተግባር ለመመስከር፤ እንዲሁም ከሞቱ ጋር ለመተባበርና ሞቱን እንደ እርሱ ነፍሳችንና ሥጋችን ተለያይተው በተግባር በመሞት ባይሆንም እንኳ በምሳሌ ለመሳተፍ እንጠመቃለን፡፡ ስንጠመቅም ወደ ውኃው ሦስት ጊዜ እየገባን እንወጣለን፡፡ ክርስቶስ ወደ መቃብር ወርዶ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ቆየ እኛም የፈለገ የርዳኖስ አምሳል በሆነው ማየ ጥምቀት ውስጥ ሦስት ጊዜ በመግባት ከሞቱ ጋር እንተባበራለን፤ ማለትም ሞቱን በተግባር እንሳተፋለን፡፡ በመጨረሻም ጌታችን ሞትንና የመቃብርን ይዞ የማስቀረት ኃይል፤ ሰውነትን የማፍረስና የመለወጥ ኃይሉን ድል አድርጎ ዳግመኛ ላይሞት እንደ ተነሣ እኛም ከውኃው እንወጣለን፡፡

በጥምቀት መዳናችን (ድኅነታችን) የተገኘው በጌታችን በሞቱና በትንሣኤው መሆኑን ማመናችንን በተግባር እንመሰክራለን፤ ከሕማማቱና ከትንሣኤው በምሳሌም ቢሆን እንሳተፋለን፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን" በማለት በሞቱ መተባበር በትንሣኤው ለመተባበር ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ገልጿል፡፡ ከክርስቶስ ጋር በሞቱ የምንተባበረውና ከእርሱ ጋር አንድ የምንሆነው ደግሞ በጥምቀት ምሥጢር ነው፡፡ ይህም "ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን?" በማለት የገለጸው ነው፡፡ ወደ ውኃው ውስጥ በመግባት ሞቱን በሚመስል ሞት ክርስቶስ ስለ እኛ ከተቀበለው አማናዊ ሞቱ ጋር እንተባበራለን፤ ሞቱን እንሳተፋለን፡፡ ሞቱን ስንሳተፍ ደግሞ ከዚያ ቀጥሎ የሚገኘውን "ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን" ተብሎ የተነገረውን ተስፋ እናገኛለን፡፡

በምሥጢረ ጥምቀት አማካይነት ሞቱን በሚመስል ሞት ከክርስቶስ ጋር ያልተባበረ (አንድ ያልሆነ) ግን ከዚያ የሚገኘውን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆንን ሊያገኝ አይችልም፡፡ ምክንያቱም "ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ከክርስቶስ ጋር መተባበር" ከዚያ በፊት በሚፈጸመው "ሞቱን በሚመስል ሞት ከክርስቶስ ጋር በመተባበር" ቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነው፡፡ ቅድመ ሁኔታ የሆነው ካልተሟላ በስተቀር ከዚያ ቀጥሎ የሚመጣው ሊኖር አይችልምና፡፡ ስለዚህ በጥምቀት የምሥጢር በር ያላለፈ ማንም ሰው ቢሆን በክርስቶስ የሕይወትና የክብር ትንሣኤ ለመነሣት አይችልም፡፡ በትንሣኤ ዘጉባኤ መነሣቱ ባይቀርም ትንሣኤው ግን የሓሳር እንጂ የክብር አይሆንለትም፡፡

ከዚህም ጋር ሦስት ጊዜ በውኃው ውስጥ መግባታችንና መውጣታችን ስመ አብን ስመ ወልድንና ስመ መንፈስ ቅዱስን ለመመስከርና ምሥጢረ ሥላሴን ለመግለጥ ነው፡፡ ጌታችን "በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው" ብሏልና፡፡ ማቴ. 28፡19 ይህ ለመዳን ወሳኝ ሱታፌ ነው፡፡ እንዲህ በማድረግም ሞቱን በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር በመተባበር በትንሣኤውም እንተባበራለን፤ ማለትም ሞትን በገደለው ሞቱ በመሳተፍ ሕይወትን ያስገኘልንን የከበረች ትንሣኤውን እናገኛለን፤ ዘለዓለማዊ ለሆነው የሕይወት ትንሣኤ እድምተኞች እንሆናለን፡፡

በዚህ ዓይነት ያልተጠመቀ ሰው ከክርስቶስ ጋር ኅብረት የለውም፡፡ ያልተጠመቀ ሰው ክርስቶስ በሞቱ ሞትን ድል ማድረጉን አምኖ ይህን እምነቱን (በጥምቀት) ስላልመሰከረና ሞቱን በሚመስል ሞት (ወደ ውኃ ውስጥ በመግባትና በመጠመቅ) ከክርስቶስ ጋር ስላልተባበረ በትንሣኤው ሊተባበር አይችልም፡፡ ይህም ማለት በክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው የተገኘውን የሕይወት ትንሣኤን ሊያገኝ አይችልም፡፡ ይህ የሞት ድል መነሣት ለእያንዳንዳችን የሚደርሰን ሞቱን በሚመስል ሞት በጥምቀት ውስጥ ስናልፍ ብቻ ነው፡፡ በጥምቀት ከእርሱ ጋር በመተባበር ካልሆነ በስተቀር በሞት ላይ በእዋጅ የተደረገው ሽረትና ድል መንሣት ለማንም ሊደርሰው አይችልም፡፡ ስለዚህ ጥምቀት በሞት ላይ የተገኘውን ድል አድራጊነትና አሸናፊነት፣ እንዲሁም በዕለተ ምጽአት የሕይወት ትንሣኤን ለመነሣት ለሚፈልግ ለእያንዳንዱ ሰው ሁሉ መፈጸም ያለበት ታላቅ ምሥጢር ነው፡፡

የጥምቀት ምሳሌ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ "አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ፣ ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ፤ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ" በማለት በገለጸው መንገድ በደመናና በባሕር ያልተጠመቁ ከሙሴ ጋር መተባበር አይችሉም ነበር፡፡ 1 ቆሮ. 10፡1-2 ከሙሴ ጋር አንድ ሆነው በእርሱ መሪነት ወደ ምድረ ርስት ከነዓን መጓዝ፣ ከሰማይ የወረደውን መና መመገብ፣ ከዓለት የፈለቀውን ውኃ መጠጣት የቻሉት በደመናና በባሕር የተጠመቁት ብቻ ነበሩ፡፡ እንደዚሁም ሁሉ በጥምቀት ምሥጢር ያልተሳተፈ ሰው ከክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን፣ ሥጋውንና ደሙን ለመቀበልና ወደ መንግሥተ ሰማያት ጉዞ ለመጀመር አይችልም፡፡ እንዲህ ያለው ሰው ገና በግብጽ ውስጥ በባርነትና በመከራ እንዳለ ሰው ነው፡፡

## 5. ክርስቶስን ለመልበስ

አሮጌውን አዳማዊ ሰውነታችንንና ማንነታችንን አስወግደን "አዲስ ሰው" የተባለ ዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስን የምንለብሰውም በጥምቀት ነው፡፡ ስለሆነም ጥምቀት ለሕይወት የሆነ አዲስ ሰውነትን ገንዘብ የምናደርግበት ምሥጢር ነው፡፡ *"የተጠመቃችሁ ሁላችሁ ክርስቶስን ለብሳችኋልና"* እንዳለ፡፡ ገላ. 3፡27 ያልተጠመቀ ሰው ገና አሮጌውን ሰውነት (የበደለውንና ከዚህም የተነሣ የተራቆተውን የአዳም ሰውነት) እንደ ለበሰ ነው፡፡ ያለ ጥምቀት በስተቀር ማንም ቢሆን ክርስቶስን ሊለብስና አዲስ ተፈጥሮን ገንዘብ ሊያደርግ አይቻለውም፡፡ የተጠመቁ ምእመናን "አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፣ ... የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል" ተብሎ የተነገረላቸው ናቸው፡፡ ቆላ. 3፡9-10

ተጠማቂ (ሊጠመቅ ያለ ሰው) ወደ ማየ ጥምቀቱ ሲገባ ልብሱን አውልቆ ዕራቁቱን የሚጠመቀውም ለዚህ ነው፡፡ ከመጠመቁ በፊት ያለው ሰውነት ከፈጣሪው ጋር በመጣላቱ የተራቆተውንና ከዚያም የተነሣ ቢቸግረው የበለስ ቅጠል ሰፍቶ ኃፍረቱን ለመሸፈን የሞከረውን የቀደመውን አዳማዊ ሰውነት ይወክላል፡፡ ተጠማቂው ከተጠመቀ በኋላ ከማየ ጥምቀቱ ሲወጣ ደግሞ ነጭ ልብስ ይለብሳል፡፡ ይህም በጥምቀት ንጹሕ መሆኑንና ንጹሐ ባሕርይ ኢየሱስ ክርስቶስን መልበሱን የሚያመለክት ነው፡፡ ከጥንት ዘመን ጀምሮ ክርስቲያኖች ሲጠመቁ ለአንድ ሳምንት ያህል ነጭ ልብስ ይለብሱ እንደ ነበር የሚያስረዱ ትውፊታዊ ታሪኮች አሉ፡፡ ያ ትውፊት በብዙዎቹ ዘንድ ቢጠፋም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግን አሁንም ድረስ አለ፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንሄድና በመንፈሳዊ በዓላትና አገልግሎቶች ጊዜ ቢያንስ ነጭ ነጠላ መስቀለኛ አጣፍቶ የመልበስ ባህል ከዚያ የመጣና እስካሁንም ተጠብቆ ያለ ክርስቲያናዊ ትውፊት ነው፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ምሥጢረ ሃይማኖትን ከነትውፊታዊ ውበቱ ጠብቃ ከዛሬ የደረሰች ናት፡፡ በፕሮቴስታንታዊ የፕሮፓጋንዳ ነፋስ እንደ ገለባ የተወሰዱ ወገኖቻችንም የትዕቢትና የተንኮል ጫማቸውን አውልቀው፣ ባላወቁት ነገር ደርሶ ፈራጅና ነቃፊ መሆንን ትተው በትሕትና ወደ ውስጧ ገባ ብለው በመንፈስ ሕሊና ሆነው ለመረዳት ቢሞክሩ ጥሩ ነበር፡፡

ቀጠማዊ በምሥጢረ ጥምቀት በዕለተ ዓርብ ከጌታችን ጎን በፈሰሰው ማየ ገቦ ልጅነትን፣ ሥርየተ ኃጢአትን፣ አዲስ ሰውነትን ያገኛል፡፡ ባለመታዘዝ ምክንያት ያስጎዳንን የቀደመውን አባታችን ቀዳማዊ አዳምን ትተን ያዳነንን ዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስን እንለብሳለን፡፡ "ወአንትሙሰ እለ ተጠመቅሙ ክርስቶስሃ ለበስክሙ - ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁላችሁ ክርስቶስን ለብሳችኋል" እንደ ተባለ፡፡ ገላ. 3፡27

በአጠቃላይ ጥምቀት ተሐድሶዎች እንደሚሉት ለመዳን ምንም ጥቅም የሌለው፣ እንዲሁ ለይስሙላ ወይንም ለአባልነት መታወቂያ ብቻ የሚፈጸም ሥነ ሥርዓት ወይም "ሚዳዊ ምልክት" ሳይሆን ለመዳን ወሳኝ ምሥጢር ነው፡፡ መድኃኒታችን *"ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል"* በማለት ግልጽ በሆነ ሁኔታ ያለ ጥምቀት ድኅነት የሌለ መሆኑን ተናግሯል፡ ፡ ማር 16፡16፡፡ *"ያላመነ፣ ያልተጠመቀ ይፈረድበታል"* በማለት ፋንታ *"ያላመነ ይፈረድበታል"* ያለው ያላመነ ሰው ለመጠመቅ የሚፈልግበት ምክንያት ስለሌለው ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው የሚጠመቀው የጥምቀትን ጥቅም ሲረዳና ሲያምን ነው፡፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ሐዋርያው ፊልጶስን *"ነዋ ማይ ወመኑ ይክልአኒ ተጠምቆ - እነሆ ውኃ፤ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድን ነው?"* ብሎ የጠየቀው ለመዳን ጥምቀት አስፈላጊ ምሥጢር መሆኑን፣ በአጠቃላይ ለመዳን ምን ማድረግ እንደሚያስፈልገው ያስተማረውን ትምህርት ስላመነ ነበር፡፡ ባያምን ኖሮ ስለ መጠመቅ እንዲያ ብሎ ባልጠየቀ ነበር፡፡

ቅዱስ ፊልጶስም *"ይደልወከ ከመ ትእመን በፍጹም ልቡናከ - በፍጹም ልብህ ልታምን ይገባሃል"* አለው፡፡ እርሱም *"አነ አአምን ከመ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልዱ ለእግዚአብሔር - ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ"* በማለት እምነቱን መስክሮ ተጠመቀ፡፡ የሐዋ. 8፡35-38 የማያምን ሰው መጠመቅ አይፈልግም፣ ሊጠመቅም አይገባውም፣ ቢጠመቅም አይጠቅመውም፤ ይልቁንም የባሰ ዕዳ በደል ይሆንበታል፡፡ ይህ እምነት ወሳኝ ስለሆነ ሕፃናት ሲጠመቁ የክርስትና እናት ወይም አባት ስለ እነርሱ ጸሎተ ሃይማኖትን እንዲደግምላቸውና ሲያድጉም ሃይማኖታቸውን እንዲያስተምሯቸው በእግዚአብሔር ፊት አደራ ይቀበላል፣ ቃልም ይገባል፡፡

ይህ *"ያመነ የተጠመቀ ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል"* የሚለው ቃለ ወንጌል የሕፃናትን ጥምቀት የሚከለክል አይደለም፡፡ ይልቁንም ጥምቀት ለእነርሱም አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳይ ነው እንጂ፡፡ ምክንያቱም ጥምቀት ለመዳን አስፈላጊ እንደ መሆኑ መጠን እነርሱም ይድኑ ዘንድ ሊጠመቁ ግድ ይላልና፡፡ በመሠረቱ ይህ ቃል የተነገረው በተለያየ ምክንያት ሳይጠመቁ ላደጉና ማመን በሚችሉበት ዕድሜ ላይ ለደረሱ ሰዎች ነው እንጂ የሕፃናት ጥምቀትን በተመለከተ የተነገረ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ፡- *"ሊሠራ የማይወድ አይብላ"* ያለው መሥራት እየቻሉ በስንፍና ምክንያት መሥራት የማይወዱትን በተመለከተ እንጂ በዕድሜ ሕፃናት የሆኑትንና በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት የማይችሉትን የሚመለከት አለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ 2 ተሰ. 3፡10

ያውም *"ሊሠራ የማይወድ አይብላ"* አለ እንጂ *"የማይሠራ አይብላ"* አላለም፡፡ *"ያመነ የተጠመቀ ይድናል"* የሚለውም አዋቂዎችን በተመለከተ የተነገረ እንጂ ሕፃናትን በተመለከተ የተነገረ አይደለም፡፡ ሳይጠመቅ ቆይቶ ማመን በሚችልበት ዕድሜ የደረሰ ሰው ግን ከመጠመቁ በፊት የክርስትናን ትምህርት በሚገባ ሊማርና ሊያምን ይገባዋል፡፡ ከክርስቲያን ቤተሰቦች የተወለዱ ሕፃናት ግን በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ወንዶች በተወለዱ በአርባ ቀን፣ ሴቶች ደግሞ በሰማንያ ቀናቸው ይጠመቃሉ፡፡ ከዚያም ትምህርቱን ደግሞ እያደጉ ቢሔዱ ይማራሉ፡፡ ይህ የጥምቀት አፈጻጸም ሥርዓት ነው፡፡ ዋናው መሠረታዊው ነገር ጥምቀት ለመዳን ያለው አስፈላጊነትና ወሳኝ ሚና ነው፡፡ የሕፃናት ጥምቀትም ከጥንት ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ሲሠራበት የኖረ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ትውፊታዊ ነው፡፡ የሐዋ. 16፡33 ፤ 1 ቆሮ. 1፡15

ክርስቶስ ራስ ነው፣ ምእመናን ሁሉ የእርሱ አካላት ናቸው፡፡ በእርሱ እንድንኖር የሚያደርገን፣ የእርሱ አካል የሚያደርገን፣ ክርስቶስን በውስጣችን እንዲሣልብን የሚያደርገን ጥምቀት ነው፡፡ ጥምቀት አዲስ ተፈጥሮ፣ አዲስ ልደት ነው፡፡ በትንሣኤ ዘጉባኤ ለሁሉም ከመሰጠቱና ፍጻሜውን ከማግኘቱ በፊት (አስቀድሞ) ዘለዓለማዊ ሕይወት በምእመናን ዳግም ልደት ይገለጣል፣ ይኸውም የሚሰጠውና የሚከወነው በጥምቀት ነው፡፡ በጥምቀት ምእመናን ከጌታ ጋር የሚያደርጉት ረቂቅ ተዋሕዶ፣ የሚመጣው ሕይወት እና የትንሣኤ ዘር የሚዘራበትና መሠረቱ የሚጣልበት ድንቅ ምሥጢር ነው፡፡ 2 ቆሮ. 3:18 ፤ 4:10፤ 14፤ 5:1፡2

## 3.7.2.1.3 ጥምቀት በጥንት ሲቃውንት ስባቶች ስስተምህሮ

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ታላላቅና ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ስለ ጥምቀት ካስተማሩት ትምህርት መካከል የተወሰኑትን እንመለከታለን፡፡

- "ለማያምኑት አልቅሱላቸው፣ የጥምቀትን ማኅተም ሳያገኙ ለሞቱት አልቅሱላቸው፡፡ እነርሱ ከመንግሥት ሰማያት ውጭ ናቸውና ልናለቅስላቸው ይገባናል፡፡ 'ሰው ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም' ተብሏልና፡፡ (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ፊልጵስዩስ፣ ክፍለ ትምህርት 3)
- "ጥምቀትን ለኃጢአት ሥርየት ሰጠን፣ እንዲሁም በዚሁ በጥምቀት ክፍዳ እንድንድንና መንግሥቱን እንድንወርስ አደረገን፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌለ ማቴዎስ፣ ክፍለ ትምህርት 61፣ ቁ. 2)
- "ጥምቀት ከኃጢአት የሚያነጻ ነው፣ ምስትሥራዬ በደል ነው፣ የመታደስና የአዲስ ልደት ምክንያት ነው፡፡ አዲስ ልደት (ዳግም ልደት) ስንልም በሥጋዊ ዓይን የሚታይ ልደት ነው ብለህ አታስብ፡፡ መንፈሳዊ ነገርን ለመረዳት ዘገምተኛ እንደ ነበረው እንደ አይሁዳዊው ኒቆዲሞስ ትልቁን ሰው ሕፃን ወደ መሆን እንለውጠውምና፣ ያረጀውንና ቆዳው የተሸበሸበውን ሰውም ሰውነቱን ወደ ሕፃንነትና ወጣትነት እንመልሰውምና፡፡ ነገር ግን በአምላካዊት ጸጋ የኃጢአት ጠባሳ የተሸከመውን፣ በክፉ ልማድ የጎለመሰውንና ያረጀውን ሰው ወደ ሕፃናት ይውሀና እንመልሰዋለን እንጂ፡፡ አዲስ የተወለደ ሕፃን ከክስና ከቅጣት ነጻ እንደ ሆነ ሁሉ በጥምቀት ዳግመኛ የተወለደው ሰውም ከኃጢአት ዕዳ ነጻ ስለሚሆን የሚጠየቅበት አበሳ አይኖርበትም፡፡ ... በውኃ ስንታጠብ በጭቃና በቆሻሻ ያደፈ ሰውነታችን ንጹሕ እንደሚሆነው ሁሉ በምሥጢረ ጥምቀትም መንፈሳዊ ንጽሕናንና አብርሆትን ገንዘብ እናደርጋለን፡፡" (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ በእንተ ጥምቀተ ክርስቶስ)
- "ማንም ሰው ካልተጠመቀ በቀር መዳንን አያገኝም፤ በውኃ ሳይሆን በደማቸው ከተጠመቁ ከሰማዕታት በስተቀር፡፡ ጌታችን ዓለምን በመስቀሉ ባዳነ ጊዜ ጎኑን ተወጋ፣ ያን ጊዜም ደም እና ውኃ ከጎኑ አፈለቀልን፡፡ ይህም በሰላም ጊዜ የሚኖሩ ሰዎች በውኃው ይጠመቁ ዘንድ፣ በስደትና በመከራ ጊዜ የሚኖሩ ሰዎች ደግሞ በደማቸው ይጠመቁ ዘንድ ነው፡፡ ሰማዕትነትን ጌታችንም ጥምቀት ብሎታል፤ እንዲህ ሲል፦ 'እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ፣ እኔም የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን?' ሰማዕታት ስለ ክርስቶስ ፍቅር ደማቸውን በማፍሰስና ስለ እርሱ መከራ በመቀበል የእምነታቸውን ምስክርነት በደማቸው ይሰጣሉና፡፡ ማቴ. 20:22 ፤ 1 ቆሮ. 4:9" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ በእንተ ጥምቀት፣ ትምህርት 3፣ ቁ. 10)

ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም እንዲህ አለ፡-

- "... ክርስቶስ ከመስቀሉ በፊታችን ወደሚታየን ወደሚቀበርበት ቦታ [ወደ ጎልጎታ] እንደ ተወሰደ እናንተም [አዲስ ተጠማቂ ምእመናን] ከእነዚህ ነገሮች በኋላ አምሳካዊ የሆነው የጥምቀት ምሥጢር ወደሚፈጸምበት ወደ ተቀደሰው የውኃ መጠመቂያ ገንዳ (ማየ ጥምቀት)[70] እንድትሄዱ ሆናችሁ፡፡ እያንዳንዳችሁም በስመ አብ በስመ ወልድ በስመ መንፈስ ቅዱስ ማመናችሁን ተጠየቃችሁ፡፡ እናንተም ማመናችሁን መሰከራችሁ፣ ወደ መጠመቂያው ውኃም ሦስት ጊዜ እየገባችሁ ወጣችሁ፤ በዚህም ክርስቶስ በመቃብሩ ሦስት ቀን መቆየቱን እየመሰከራችሁ ነው፡፡ መድኃኒታችን በልበ ምድር ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንዳሳለፈ እናንተም መጀመሪያ ወደ ማየ ጥምቀቱ ከገባችሁ በኋላ ከውኃው መውጣታችሁ ጌታችን በመሬት ውስጥ ያሳለፈውን የመጀመሪያውን ቀን ያመለክታል (ይገልጻል)፤ ወደ ውኃው በመግባታችሁ ደግሞ በከርሠ ምድር ያሳለፈውን ሌሊቱን ያመለክታል (ይገልጻል)፤ በሌሊት ያለ ሰው እንደማያይ፣ በቀን ያለ ግን ማየት እንደሚችል እንዲሁም ወደ ውኃው በመውረድ ጊዜ እንደ ሌሊቱ ምንም አላያችሁም፤ ከውኃው በወጣችሁ ጊዜ በቀን የሚመሳሰስ ማየት እንዲችል እናንተም እንደዚሁ ነበራችሁ፡፡

  "እንደዚሁም እንዲያ በምታደርጉበት በዚያው በአንድ ጊዜ እየሞታችሁና እየተወለዳችሁ ነበር፤ ያ የድኅነታችን ውኃም (Water of salvation) በአንድ ጊዜ መቃብራችሁም፣ እናታችሁም ነበር፡፡ ሰሎሞን 'ለመወለድ ጊዜ አለው፥ ለመሞትም ጊዜ አለው' ብሎ ስለ ሌሎች የተናገረው ለዚህ ተስማሚ ሆኖ ይገኛል፡፡ መክ. 3፡2 ሆኖም ይህ ለእናንተ የሚፈጸመው 'ለመሞት ጊዜ አለው፣ ለመወለድም ጊዜ አለው' በሚል በተቃራኒ ቅደም ተከተል ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱም (መሞትና መወለድ) የሚፈጸሙት በአንድ ጊዜ ነው፣ ልደታችሁም ከሞታችሁ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ አብሮ ጎን በጎን የተፈጸመ ነው፡፡"

  (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 20፣ በእንተ ጥምቀት፣ ቁ. 4)

- "እንዴት ያለ እንግዳና ለማሰብ የሚደንቅ ነገር ነው! ለመጠመቅ ወደ መጠመቂያው ውኃ ስንገባ ሞትን በእማናዊ ሁኔታ በተግባር አልተቀበልንም፣ በእውነትም አልተቀበርንም፣ አልተሰቀልንም፣ ሞተንም አልተነሣንም፤ እነዚህን ሁሉ የተካፈልነው በምሳሌ ነው እንጂ፡፡ የምናገኘው መዳን ግን እንደምንሳተፍበት መንገድ ምሳሌያዊ ሳይሆን እማናዊ ነው፡፡ ክርስቶስ በእውነት ተሰቅሏል፣ በእውነት ወደ መቃብር ወርዶ ተቀብሯል፣ ከዚያም በእውነት ተነሥቷል፤ እነዚህን ነገሮች ሁሉ እኛ በምሳሌ ተሳትፈን መዳንን ግን በእውነት እናገኝ ዘንድ በነጻ በቸርነቱ ሰጥቶናል፡፡ ምን ዓይነት ዕፁብ ድንቅ የሆነ ሰውን መውደድና ቸርነት ነው! ክርስቶስ ንጹሐት በሆኑ እጆቹ ላይ በችንካር ተቸነከረ፣ ሕማማትንም ተቀበለ፤ በእኔ ግን ያለ መቸንከር፣ ያለ ሕማምና ያለ ጭንቅ በእርሱ የደረሰው ችንካርና ሕማም ሳይደርስብኝ እንዲሁ ሕማሙን በማመንና በምሳሌ በመሳተፍ ማለትም ወደ መጠመቂያው ውኃ በመግባትና በመውጣት ሞቱንና ትንሣኤውን በመመስከርና በመሳተፍ እርሱ በእውነት ሞቶና ተነሥቶ የፈጸመውን መዳን በነጻ ሰጠኝ፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 20፣ በእንተ ጥምቀት፣ ቁ. 5)

- "ክርስቶስ በስሜት ሕዋሳት ሊመረመሩና ሊታወቁ የሚችሉ ነገሮችን አይደለም የሰጠን፤ በሚታዩ ነገሮች አማካይነት የተሰጡንና የሚፈጸሙ ምሥጢራት ቢኖሩም እንኳ ሁሉንም ምሥጢራት በመንፈስ ሕሊና ሊታሰቡ በሚገባቸው ሁኔታ ነው ያደረገው፡፡ በጥምቀትም እንዲሁ ነው፣ በጥምቀት የሚሰጠው ጸጋ የሚከናወነውና የሚገኘው በሚታየው በውኃ አማካይነት ነው፤ የሚገኘውን የልጅነት ጸጋና ዳግም ተፈጥሮ የምናውቀው ግን በመንፈስ ነው፡፡

[70] (Baptismal font)

“መንፈሳዊና ረቂቅ ሆነህ ቢሆን ኖሮ መንፈሳዊ የሆኑትን ጸጋዎች በግልጽ ሊሰጥህ ይችል ነበር፤ ነገር ግን ነፍስ በሥጋ ውስጥ የተሸፈነች ስለ ሆነች በመንፈስ አእምሮ ልትረዳቸው የምትችላቸውን ነገሮች በሚታዩ ነገሮች አንጻር (አማካይነት) ሰጠህ፡፡ አሁን ካለነው ሰዎች ምነው የጌታችንን ገጹን ባየሁት፣ ልብሶቹን ባየኋቸው፣ በዳሰስኋቸው ብለው የሚመኙ ብዙዎች አሉ፡፡ እርሱን እያያችሁት እኮ ነው፣ እየዳሰሳችሁት ነው፣ እየበላችሁት ነው፡፡ እናንተ ልብሶቹን ለማየት ትመኛላችሁ፣ እርሱ ግን ራሱን የሰጣችሁ እንድታዩት ብቻ ሳይሆን እንድትዳስሱትም፣ እንድትበሉትና በውስጣችሁ እንድትቀበሉትም ጭምር ነው፡፡”

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌል ማቴዎስ፣ ክፍለ ትምህርት 87፣ ቁ. 4-5)

- “ጥምቀት የኃጢአት ሥርየትን ጸጋ የሚያሰጥ ብቻ ወይም ደግሞ የልጅነትን ጸጋ የሚያሰጥ ምሥጢር ብቻ አድርጎ የሚያስብ ማንም ሰው አይኑር፡፡ አዎ፣ ኃጢአታችንን እንደሚያስተሠርይና ንጹሕ እንደሚያደርገን እና የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ እንደሚያድለን እናውቃለን፡፡ ከዚህ ባሻገር ደግሞ ጥምቀት ከክርስቶስ ሕማማት የመሳተፍ ምሥጢር ነው፡፡ ስለዚህም ምክንያት ጳውሎስ ‘ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፣ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን’ እያለ ጮኾ ይናገራል፡፡ ሮሜ 6፡3 ሐዋርያው እነዚህን ቃላት የተናገረው ጥምቀት የሚያሰጠን ጸጋ የኃጢአትን ሥርየትና ልጅነትን ብቻ እንደ ሆነና ከዚያ ባሻገር ግን ከክርስቶስ ሕማማት የመሳተፍ ምሥጢር ጋር ግንኙነት የለውም ብለው የማሰብ ዝንባሌ ለነበራቸው ሰዎች ነበር፡፡” (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 20፣ በእንተ ጥምቀት፣ ቁ. 6)
- “. . . ስፍር ቁጥር የሌላቸውን መልካም ነገሮችን የተመላውን ምሥጢረ ጥምቀትን ሰጠን፣ ቅዱስ ቊርባንን ሰጠን፣ መንግሥተ ሰማያትን ተስፋ አድርጎ ሰጠን፣ እንዲሁም ሊነገሩ የማይችሉትን መልካም ነገሮች ሁሉ ሰጠን፡፡” (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌል ማቴዎስ፣ ክፍለ ትምህርት 66፣ ቁ. 5)
- “አሁን ደግሞ ይህን ነገር ወደ ማስተዋል እንሂድ፡፡ ቅዱስ በሆነው በምሥጢረ ጥምቀት የምናገኘው ምንድን ነው? ከአሁን ወዲያ ሞት በማያገኘው ሕይወት መሳተፍንና ገንዘብ ማድረግን አይደለምን? ክርስቲያን ነኝ ከሚሉ ሰዎች መካከል ማንም ሰው ቢሆን ይህን ይክዳል ብዬ አላስብም፡፡” (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ትምህርት በእንተ መንፈስ ቅዱስ)
- “እነዚህ [ካህናት] በእውነት በጥምቀት የሚገኘውን ዳግም ልደት አደራ የተሰጡና የሚፈጽሙ ናቸው፡፡ በእነርሱ አማካይነት በሚፈጸመው የጥምቀት ምሥጢር ክርስቶስን እንለብሳለን፣ ከእግዚአብሔር ልጅ ጋር አብረን እንቀበራለን፣ የዚያ ቅዱስ ራስ [የኢየሱስ ክርስቶስ] አካላትም (ብልቶች) እንሆናለን፡፡”[71] (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ በእንተ ክህነት፣ መጽሐፍ 3፣ ቁ.. 6)
- “የመጠመቂያውን ውኃ ተራ ውኃ አድርገህ አትመልከተው፣ በውኃው አማካይነት የሚሰጠውን መንፈሳዊ ጸጋ እንጂ፡፡ . . . ውኃው በስመ አብ በስመ ወልድ በስመ መንፈስ ቅዱስ ሲባረክ በመንፈስ ቅዱስ ቀዳሽነት አማካይነት አዲስ የሆነ የመቀደስን ኃይል ገንዘብ ያደርጋልና፡፡” (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ በእንተ ጥምቀት፣ ቁ. 3)

[71] (These verily are they who are entrusted with the pangs of spiritual travail and the birth which comes through baptism: by their means we put on Christ, and are buried with the Son of God, and become members of that blessed Head.)

❖ " . . . ይህን የምለው እኔ ከራሴ አይደለም፣ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እንጂ፤ 'ማንም ቢሆን ከውኃና ከመንፈስ ዳግመኛ ካልተወለደ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም' ብሏልና፡፡ በውኃ የሚጠመቅ ሆኖ ነገር ግን በመንፈስ ዳግመኛ ለመወለድ የተገባ (የበቃ) ሆኖ ያልተገኘ ማንም ቢሆን ፍጹም የሆነውን ጸጋ በምልዓት አያገኝም፤ እንዲሁም የመልካም ምግባር ሕይወት በሚገባ ያለው ደገኛ የሆነ ሰው ቢሆን እንኳ በውኃ አማካይነት በሚፈጸመው ጥምቀት ካልታተመ በስተቀር ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊገባ አይችልም፡፡ ይህ ከባድ አባባል ሊመስል ይችላል፣ ግን የእኔ የራሴ ቃል ሳይሆን ይህን ያወጀው ራሱ ባለቤቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ የዚህ አባባል ማስረጃውና ማረጋገጫውም ከቅዱስ መጽሐፍ አለ፡፡ ቆርኔሊዎስ መላእክትን እስከ ማየት የደረሰ ጻድቅ ሰው ነበር፣ ጸሎቱና ምጽዋቱም ለመልካም ተግባሩ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በሰማያት በእግዚአብሔር ዘንድ ያረገለት ሰው ነበር፡፡ ሆኖም ግን ጴጥሮስ ወደ እርሱ ተልኮ መጥቶ ይድን ዘንድ መጠመቅ እንዳለበት ነገረው፣ እርሱም እንደዚያው አደረገ፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ በእንተ ጥምቀት፣ ትምህርት 3፣ ቁ. 4)

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ስለ ጌታችን ጥምቀት ባስተማረው ትምህርት ላይ ስለ ጥምቀት ሰፋ ባለ ሁኔታ በብሉይ ኪዳን የተነገሩ ትንቢቶችንና የነበሩ ተምሳሌቶችን በመተርጎምና በማመሥጠር በጥልቀት አስተምሯል፡፡ ከዚህ ትምህርቱ ውስጥ የሚከተለውን ብቻ እንመልከት፡-

❖ "ከጌታችን ከስቅለቱ በኋላ የተጻፉት ወንጌላት ብቻ ሳይሆኑ ከሥጋዌው በፊት የተጻፉት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትም እኛ አዲስ ልደትን ስለምናገኝበት ስለ ምሥጢረ ጥምቀት ደግመውና ደጋግመው በተለያየ ሁኔታ በተምሳሊትና በምሳሌያት ጽፈዋል፡፡ ጥምቀት በቃልም በድርጊትም አስቀድሞ ይነገር ነበር፡፡ የአብርሃም አገልጋይ የነበረችው አጋር ከእመቤቷ ከሣራ ጋር ተጣልታ ልጇን እስማኤልን ይዛ በተሰደደች ጊዜ በአቅማዳዋ የያዘችው ውኃ ስላለቀባት (የአይሁድ ምኩራብ ለዘላቂ ሕይወት የሚሆን ውኃን ትሰጥ ዘንድ የማይቻላት ነበርና) ውኃ ከማጣቷ የተነሣ ከልጇ ጋር ከውኃ ጥም የተነሣ ለሞት በተቃረበች ጊዜ መልአክ እግዚአብሔር በድንገት ተገልጦ የሕይወት ውኃ ምንጭን አሳያት፡፡ ከዚያ የውኃ ምንጭ ጠጥታም ራሷንና ልጇን ከሞት አተረፈች፡፡ ተመልከት፣ ይህ የምሥጢራዊው የጥምቀት ምሳሌ እንደ ነበር አስተውል፤ ገና ከመጀመሪያው ከጥንት ጀምሮ በጥፋትና በሞት ላይ ለነበረው ሰው መዳን የመጣለት (የሆነለት) ከዚያ በፊት ያልነበረና እንደ ተአምራዊ ሥጦታ ሆኖ በመልአኩ አማካይነት በተሰጠ የሕይወት ውኃ መሆኑን አስተውል፡፡

". . . እንደ ገናም በኋላ ዘመን በተዳረ ጊዜ [ይስሐቅ] የአብርሃም አገልጋይ ሚስት የምትሆነውን ፈልጎ ያመጣለት ዘንድ በተላከ ጊዜ ርብቃን ያገኛት ከውኃው ጉድጓድ አጠገብ ነበር፡፡ ክርስቶስ የሚገኝበትን ዘር ያስገኘው ጋብቻ መሠረቱ የተጣለውና የመጀመሪያ ቃል ኪዳኑ የተፈጸመው በውኃ ነበር፡፡ ዘፍ. 24 ራሱ ይስሐቅም መንጋውን እየጠበቀ ሳለ በበረሓው የተለያዩ ሥፍራዎች የውኃ ጉድጓዶችን ቆፈረ፡፡ እነዚያን የቆፈራቸውን የውኃ ጉድጓዶችም ጠላቶቹ አስቆሙት፣ ደፈኑበትም፡፡ እነዚህም በኋላ ዘመናት የጥምቀትን ጸጋ የሚቃወሙና የሚያሰናክሉ፣ እውነትን አጽንተው የሚቃወሙ የከፉዎች ሰዎች ምሳሌዎች ናቸው፡፡ እንዲያ ሆኖም ሰማዕታትና ካህናት ጉድጓዶቹን እንደገና መልሰው በመቆፈር የጥምቀትን ጠላቶች ድል አደረጓቸው፤ የጥምቀት ጸጋም መላውን ዓለም አዳረሰ፡፡ ዘፍ. 26፥15-22

"እንዲሁም ያዕቆብ ወደፊት ሚስቱ የምትሆነውን ራሔልን ያገኛት በውኃ ጉድጓድ አጠገብ ነበር፡፡ በዚያም በውኃው ላይ የተገጠመ ብዙ እረኞች በአንድ ላይ ካልሆኑ በስተቀር ሊያንከባልሉትና መንጋቸውን ለማጠጣት የማይቻላቸው ታላቅ ድንጋይ ነበር፡፡ ያዕቆብ ግን ያን ድንጋይ ብቻውን ገለበጠው፣ ለመንጋዎቹም ውኃን አጠጣቸው። ዘፍ. 29 በውኃው ላይ የነበረው ድንጋይ ከክርስቶስ በቀር ሌላ ማን ይሆናል? ስለ እርሱ ኢሳይያስ "እነሆ፣ በጽዮን ድንጋይን ለመሠረት አስቀምጣለሁ፤ የተፈተነውን፣ የከበረውን፣ መሠረቱ የጸናውን የማዕዘን ድንጋይ የሚያምን አያፍርም" ይላልና፡፡ ኢሳ. 28፡16 ነቢዩ ዳንኤል የሰው እጅ ሳይነካው ከተራራ ሲወርድ ያየው ድንጋይም እንበለ ዘርአ ብእሲ በድንግልና የተወለደው የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ዳን. 2፡45 ስለዚህም በውኃው ጉድጓድ ላይ የነበረው መንፈሳዊ ድንጋይ እስኪገለጥና አማናዊ ሆኖ እስኪሰጥ ድረስ ብዙ ዘመናትን የጠየቀውን የጥምቀትን ጸጋና ምሥጢር በጥልቁ ውስጥ የሰወረው ክርስቶስ ነበር፤ ውኃውን ከጉድጓዱ ውስጥ ለማውጣት ገመድ ያስፈልግ እንደ ነበር ሁሉ የጥምቀትን ጸጋ ለመግለጥም የብዙ ዘመናት ማለፍ አስፈልጓል፡፡

"ያዕቆብ ድንጋዩን አንሥቶ ለራሔል በጎች ይጠጡ ዘንድ ውኃን እንደ ሰጣቸው ክርስቶስም የተሰወረውን የጥምቀትን ምሥጢር ገልጦ ለቤተ ክርስቲያን መንጋዎች የሕይወትን ውኃ ሰጠን፡፡ በዚህም ላይ የያዕቆብን ሦስት በትሮች መጨመር እንችላለን፡፡ ዘፍ. 30፡37-43 ያዕቆብ ሦስቱን በትሮቹን በውኃው አጠገብ ካስቀመጠበት ጊዜ ጀምሮ አሕዛባዊው ላባ እየደኸየ፣ ያዕቆብ ደግሞ በበጎችና በከብቶች እየበለጸገ ሄደ፡፡ ላባ የዲያብሎስ ምሳሌ ሲሆን ያዕቆብ ደግሞ የክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ የጥምቀት ምሥጢር በጌታችን ከተገለጠበት ጊዜ አንሥቶ ክርስቶስ የዲያብሎስን መንጋ ሁሉ ወሰደበት፤ ቤተ ክርስቲያንም ከበረች፣ ዲያብሎስ ደግሞ ደኸየ፡፡

"እንደ ገናም ጨካኙ ፈርዖን በዕብራውያን ሕፃናት ላይ ካወጀው አዋጅ የተነሣ ሙሴን በሣጥን ውስጥ አድርገው በወንዝ ዳር አስቀመጡት፤ ሕጉ በሣጥን ይሸፈን ዘንድ የተገባ ነበርና፡፡ ዘጸ. 2 ያስቀመጡትም በውኃ ዳር ነበር፡፡ ምንነታቸውና ፍጻሜያቸው ፍጹምና አስደናቂ በሆነው በምሥጢረ ጥምቀት ግልጽ ሆኖ የሚታዩት ሕጉና (ኦሪት) በዕብራውያን ላይ በየቀኑ ይፈጸሙ የነበሩት የመርጨትና የማንጻት ሥርዓቶች እነርሱ ከጸጋው የራቁ አልነበሩምና (ሙሴ በውኃው አጠገብ እንደ ተጣለ እነዚያም ለጸጋው ፋና ወጊዎችና ዐረቦኖች ነበሩ፣ ከጸጋው የራቁ አልነበሩም ማለት ነው)፡፡

"እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረው ሕዝበ እስራኤል ራሳቸው በቀይ ባሕር መካከል ማለፋቸውና ከግብጽ ባርነት ነጻ መውጣታቸው በውኃ አማካይነት በሚፈጸመው የጥምቀት ምሥጢር የሚገኘውን ድኅነት (መዳን) አስቀድሞ የሚያውጅ ፀዋጅ ነበር፡፡ 1 ቆሮ. 10፡1-4 ሕዝቡ (እስራኤል) በውስጡ በደኅና ሲሻገሩ የግብጹ ንጉሥ ፈርዖን ግን ከነሠራዊቱ ሰጠመ፡፡ በዚህም የጥምቀት ምሥጢር አስቀድሞ ታየ፣ በምሳሌ ተገለጠ፡፡ ዛሬም በጥምቀት ከግብጽ የሚያልፍና የሚሸሽ ማንኛውም ሰው ከኃጢአት ቀንበር ነጻ ይወጣል፣ ይድናልም፡፡ ዲያብሎስ ግን ከነአገልጋዮቹ (ማለትም የክፋት መናፍስት ማለቴ ነው) በጭንቅ ይያዛል፣ ይጠፋልም፤ እርሱ [ዲያብሎስ] የሰዎችን መዳን የእርሱ ጥፋት እንደ ሆነ አድርጎ ይቆጥረዋልና፡፡

"ስለ ጥምቀት ሊኖረን ስለሚገባው ትክክለኛ ትምህርት እነዚህ እስካሁን የተጠቀሱት በቂ ሊሆኑ ቢችሉም ከዚህ ቀጥሎ ያለውንም መዘንጋት አይገባም፡፡ የዕብራውያን ሕዝብ ከብዙ መከራዎችና ውጣ ውረዶች በኋላ አስቸጋሪውን የበረሓ ጉዞ ከፈጸሙ በኋላ መሪያቸው በሆነው በኢያሱ አማካይነት በዮርዳኖስ ወንዝ ከማለፋቸው በፊት ወደ ተስፋዪቱ ምድር አልገቡም፡፡ በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ እንዲያልፉ ያደረጋቸውና የመራቸው፣ እንዲሁም በወንዙ ውስጥ አሥራ ሁለት ድንጋዮችን ያስቀመጠው ኢያሱ ጥምቀትን የሚፈጽሙትን የአሥራ ሁለቱን ሐዋርያት መምጣት አስቀድሞ እያመለከተ ነበር፡፡ ኢያ. 3-4

"እንደ ገናም አስደናቂ የሆነውና የሰውን ሁሉ ሐሊና የሚያልፈው የቴስብያዊው የኤልያስ መሥዋዕት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ያለንን እምነት እና መዳናችንን አስቀድሞ በድርጊት ከማሳየት ውጭ ሌላ ምን ያመለክታል? . . . በጸሎቱ ከሰማይ እሳትን በደረቀው እንጨት ላይ ያወረደ ሳይሆን ተላላኪዎቹን ብዙ ውኃ እንዲያፈስሱበት አዘዛቸው፡፡ 'ሦስት ጊዜ አራት ጋን ውኃ ሙሉ፣ በሚቃጠለው መሥዋዕትና በእንጨቱ ላይ አፍስሱ' ካለ በኋላ ውኃው በመሠዊያው ዙሪያ ፈሰሰ፣ ጉድጓዱንም በውኃ ሞላው። ከዚያም በኋላ በጸሎቱ ያወረደው የእግዚአብሔር እሳት የሚቃጠለውን መሥዋዕቱንም እንጨቱንም ድንጋዮቹንም አፈሩንም ሁሉ የበላ ብቻ ሳይሆን በጉድጓዱም ውስጥ ያለውን ውኃ ላሰው። በዚህም የአምላኩን የእግዚአብሔርን ኃይል ያሳይ ዘንድ ነበር፡፡ 1 ነገ. 18 በዚህም፣ ኤልያስ በዚያ አስደናቂ በሆነው መሥዋዕቱ በኋላ ዘመን የሚገለጠውንና የሚሠራውን የጥምቀትን ምሥጢር በግልጽ አሳየን፡፡ እሳቱ የተቀጣጠለው በላዩ ላይ ሦስት ጊዜ በፈሰሰበት በውኃው ነበር፡፡ በዚህም ምሥጢራዊ የሆነው ማየ ጥምቀት ባለበት በዚያ የማይረባውንና ኢሃይማኖታዊ የሆነውን የሚያቃጥለው፣ ቁረተ ኃጢአትን አስወግዶ ሙቀትን የሚሰጠው፣ ለምእመናን ብርሃንን የሚያድላቸውና ብሩሃን ልቡና የሚያደርጋቸው አስፈሪና ሕይወትን ሰጪ የሆነው መንፈስ ቅዱስ አለና፡፡ . . ."

(ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ በእንተ ጥምቀተ ክርስቶስ)

ቅዱስ ያሬድም "ወብዙኃን" በተባለው መዝሙር ላይ ትንቢቱን ከፍጻሜው ጋር እየተረጐመና እያመሠጠረ በዜማ ገልጾታል፡፡ ቅዱስ ያሬድ በመዝሙሩ እንዲህ ይላል፡-

- "ወብዙኃን ኖሎት መጽኡ ወስእኑ ከሢቶታ ለዕብን እምአፈ ዐዘቅት እስከ ይመጽእ ያዕቆብ ዘክቡት ውስተ ሐቁሁ ዘህሎ ይሠሣ እምሰብእ ከሠተ ወአስተየ መርዔቶ ወከማሁ መጽኡ ብዙኃን ነቢያት ወስእኑ ከሢቶታ ለጥምቀት እስከ ይመጽእ ዐቢይ ኖላዊ እምሰማይ ከሠተ ወአጥመቀ ብዙኃነ አሕዛበ በውስቴታ . . . - ብዙ እረኞች ወደ ውኃው ጉድጓድ መጡ፣ ሆኖም ክርስቶስ ከእርሱ ዘር ሰው የሚሆንበት ያዕቆብ ወደ እነርሱ እስከሚመጣ ድረስ ድንጋዩን ከጉድጓዱ አፍ ላይ ማንከባለልና በጎቻቸውን ውኃ ማጠጣት አልቻሉም፡፡ ያዕቆብ ሲመጣ ግን ድንጋዩን ከጉድጓዱ አፍ ላይ አንስቶ መንጋዎቹን አጠጣቸው፡፡ እንደዚሁም ሁሉ ብዙ ነቢያት ቢመጡም ከሰማይ የሚመጣው ታላቁ እረኛ ክርስቶስ እስከሚመጣና የጥምቀትን ምሥጢር ከፍቶ ብዙ አሕዛብን በውኃ እስከሚያጠምቅ ድረስ የጥምቀትን ምሥጢር ሊገልጧት አልተቻላቸውም፡፡" (ቅዱስ ያሬድ፣ መዝሙር ዘቅበላ)

### 3.7.2.1.4 ስለ ምሥጢረ ጥምቀት - ማጠቃለያ

ተሐድሶዎች ስለ ምሥጢረ ጥምቀት የሚያስተምሩትን ትምህርት መጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምሥጢረ ጥምቀት ከሚያስተምረው ትምህርት አንጻር፣ በመቀጠል ደግሞ ቀደምት ኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን ስለ ጥምቀት ባስተማሩት ትምህርት መሠረት መዘንነው፡፡ ሆኖም በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በአበው ትምህርት ሲመዘን የተሐድሶዎች ትምህርት ፍጹም ተቃራኒ ሆኖ መገኘቱን አንባቢ ሁሉ በቀላሉ የሚመሰክረው ሐቅ ነው፡፡ በአንጻሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ ምሥጢረ ጥምቀት የምታምነው እምነትና የምታስተምረው ትምህርት ደግሞ ሙሉ በሙሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ቅዱሳን አባቶቻችን ሊቃውንት የሚያስተምሩት ትምህርት ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን እምነቷም ትምህርቷም ይኸው በመጽሐፍ ቅዱስ እና በሊቃውንት አባቶች የተገለጸው ነው፡፡ ስለዚህ ተሐድሶዎች በምሥጢረ ጥምቀት ላይ ያላቸው ትምህርት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና ኢኦርቶዶክሳዊ መሆኑን እነርሱው እንቀበላቸዋለን ያሏቸውና የጠቃቀሷቸው መጽሐፍ ቅዱስና ቀደምት አባቶች ተባብረው ይመሰክሩባቸዋል፡፡

## 3.7.2.2 ምሥጢረ ሜሮን

### 3.7.2.2.1 ስለ ምሥጢረ ሜሮን የተሐድሶዎች ትምህርት

ተሐድሶዎች ተጠማቂዎች የሚቀበሉትንና ጸጋ መንፈስ ቅዱስን የሚያገኙበትን ምሥጢረ ሜሮንን በተለመደው የስድብ አፋቸው ይነቅፋሉ፣ ይኰንናሉ፡፡ ለምሳሌም እንዲህ ይላሉ፡-

◉ "... ሆኖም ቤተ ክርስቲያን በሰይጣን ዙፋን ሥር ወድቃ ... መንፈስ ቅዱስ ባይኖራትም መንፈስ ቅዱስ የተመሰለበት ዘይት (ቅባት) በምትኩ ይኖራት ዘንድ ተጠበበች፡፡ ... የእግዚአብሔርን ምሥጢር የምናውቅበት በምእመናን የሚያድረው ቅብዐት ግን የተቀመመ ዘይት ሳይሆን ራሱ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ... ዛሬ መንፈስ ቅዱስን ተክቶ የሚሠራውና የሚሠራበት "ሜሮን" የተባለው ይህ ዘይት ሲሆን ስሙ ከመንፈስ ቅዱስ ይልቅ ይበልጥ የሚታወቅና የሚከበር ሆኗል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ እስካለንበት እስከ 20ኛው ምእት ዓመት መገባደጃ ድረስ መንፈስ ቅዱስ በተጻፉት መጻሕፍት ላይ ስሙ ከመነበቡ በስተቀር በእኑነቱ ሳይታወቅ ኖረ፡፡ ... ዘይት ስፍራውን ነጠቀው እንጂ በየትኛውም ጉባኤ ምእመናን መገኘት የነበረበት መንፈስ ቅዱስ አልነበረምን?" (ጮራ ቁ. 10፣ ገጽ 5-6)

እስኪ ተሐድሶዎች "እንደ እውነቱ ከሆነ እስካለንበት እስከ 20ኛው ምእት ዓመት መገባደጃ ድረስ መንፈስ ቅዱስ በተጻፉት መጻሕፍት ላይ ስሙ ከመነበቡ በስተቀር በእኑነቱ ሳይታወቅ ኖረ" የሚሉት በቤተ ክርስቲያን ያለ መንፈስ ቅዱስ የሚፈጸም ምን ነገር አለና ነው? ገና ጸሎተ ቅዳሴው ሊጀምር ሲል እንኳ መንፈስ ቅዱስን በመጥራት እንዲህ እያለ ነው፡- "ሚ መጠን ግርምት ዛቲ ዕለት ወዕፁብ ዛቲ ሰዓት እንተ ባቲ ይወርድ መንፈስ ቅዱስ እመልዕልተ ሰማያት ወይጼልሎ ለዝንቱ መሥዋዕት ወይቄድሶ ... - ይህች ቀን ምን ያህል የምታስፈራ ናት! ይህችስ ሰዓት ምን ያህል የምታስጨንቅ ናት፣ መንፈስ ቅዱስ ከሰማየ ሰማያት የሚወርድባት፣ ይህን መሥዋዕቱን የሚሰውርባትና የሚያከብርባት ..." (ሥርዓተ ቅዳሴ፣ ገጽ 12) በመቀጠልም "አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" ብሎ ካህኑ በዜማ ስመ አብን ስመ ወልድን ስመ መንፈስ ቅዱስን ይጠራል፡፡ ትንሽ አለፍ እንዳለም ካህኑ "ንስግድ" ሲል ሕዝቡ "ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዘ ሠለስቱ አሐዱ" በማለት በዜማ ተሰጥዖውን ይቀበላል፡፡ "ህበነ ንኅበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ ..." እያለ ካህኑና ሕዝቡ በመቀባበል ይጠሩታል፡፡

በአጠቃላይ በቅዳሴው ሂደት በሙሉ መንፈስ ቅዱስ ይጠራል፡፡ መሥዋዕቱን የሚያከብረውና የሚለውጠው እርሱ ነው፡፡ በምሥጢራቱ ሁሉ አከባሪውና ለዋጩ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ እያንዳንዱ ክርስቲያን ሲያማትብ እንኳ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብሎ ነው፡፡ ታዲያ "መንፈስ ቅዱስ በእኔነቱ ሳይታወቅ ኖረ" የሚሉት ምን ያህል ከእውነት የራቀ ነገር ነው! ጥንቱንስ ቅድስት ሥላሴን ስማቸውን በአምልኮ በጸሎት መጥራት እንጂ ከዚያ አልፎ ባሕርያቸው ሊመረመርና ሊታወቅ ይችላልን? ወይስ "መንፈስ ወረደልን" እያሉ ራሳቸውን እየሳቱ እንደሚንዘፈዘፉትና አልክል ናላውን እንዳዞረው ሰው የሚናገሩትን እንደማያውቁት አሳዛኝ ወገኖቻችን ካልተሆነ በስተቀር መንፈስ ቅዱስ ታወቀ አትሉም? ጥረታችሁ ወደዚያው ለመንተት አይደል!

አሁንም ይኸው የተሐድሶዎች በምሥጢረ ሜሮን ላይ ያላቸው አቋምና ትምህርት መጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ ቀጥሎም በአበው ትምህርት ይመዘናል፡፡

## 3.7.2.2.2 ምሥጢረ ሜሮን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

እግዚአብሔር ሥራውን ሲሠራና ጸጋውን ሲያሳድር በሚታዩ (ቁሳዊ ህልዎት ባላቸው) ነገሮች አማካይነት መጠቀሙንና መሥራቱን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያሳየን እውነታ ነው፡፡ ጥምቀትን በውኃ አማካይነት እንዲከናወን ማድረጉ እግዚአብሔርን አልሠራም ወይም እግዚአብሔር ተረሳ፣ ተዘነጋ ወይም ስፍራውን ውኃ ወሰደበት አያሰኝም፡፡ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብጽ ሲያወጣ በሙሴና በአሮን መሪነት ማድረጉ እግዚአብሔር በቀጥታ ሕዝቡን ማነጋገር ስለማይችል አልነበረም፤ እንዲያ ማድረጉም ሕዝቡን ከግብጽ ያወጣው ራሱ እግዚአብሔር ነው ከመባል አያግደውም፣ አላገደውምም፡፡ "እግዚአብሔር ባሕቲቱ መርሖሙ - እርሱ እግዚአብሔር ብቻውን መራቸው" እንደ ተባለ፡፡ ሆኖም ግን እርሱ ቸር ስለሆነ እርሱ ባወቀ የተለያዩ ነገሮችን ወይም ምክንያቶችን በመጠቀም ሥራውን ይሠራል፡፡ ስለሆነም ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ለማሳደር በጸሎት በከበረ ቅዱስ ቅባት (ሜሮን) መጠቀም መንፈስ ቅዱስን መርሳትና እርሱን ትቶ በተቀመመ ቅባት ላይ መታመን አይደለም፤ ሆኖም አያውቅም፡፡ ይህ እንዲሁ ካለማወቅና ከአጉል ደፋርነት ወይም ደግሞ ከጭፍን ጥላቻ የሚመነጭ አነጋገር ነው፡፡

እግዚአብሔር ሥራውን ሲሠራ ያለ ሥነ ፍጥረት አማካይነት እንዲሁ በቀጥታም ይሠራል፤ እንደዚሁም ደግሞ እርሱ በፈጠራቸው በሥነ ፍጥረታት አማካይነትም ይሠራል፡፡ ለአብነትም እስራኤላውያን ከግብጽ ከወጡ በኋላ በምድረ በዳ በጉዞ ላይ ሳሉ ሱር ወደ ተባለው ምድረ በዳ ወጥተው በዚያ በምድረ በዳው ሦስት ቀን ከተጓዙ በኋላ ውኃ አላገኙም ነበር፡፡ ከዚያም ስለ ሆነው ሲናገር መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

> ወደ ማራም በመጡ ጊዜ የማራ ውኃ መራራ ነበረና ሊጠጡ አልቻሉም፤ ስለዚህ የዚያ ስፍራ ስም ማራ ተብሎ ተጠራ፡፡ ሕዝቡም ምን እንጠጣለን? ብለው በሙሴ ላይ አንጐራጐሩ፡፡ ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፤ እግዚአብሔርም እንጨትን አሳየው፣ በውኃውም ላይ ጣለው፣ ውኃውም ጣፈጠ፡፡ ዘጸ. 15፡23-25

እግዚአብሔር ውኃውን በቀጥታ ራሱ በማጣፈጥ ፋንታ ለሙሴ በውኃው ላይ የሚጥለውና ውኃውን የሚያጣፍጥበት እንጨት ለምን አሳየው? የውኃውን ምሬት ለምን በዚያ እንጨት አማካይነት አጣፈጠው? እንደ ተሐድሶዎች አስተሳሰብ ከሆነ ይህ እግዚአብሔርን ትቶ "እንጨትን መፈለግ"፣ "በእንጨት መታመን" መሆኑ ነበርን?

ነቢዩ ኤልሳዕ የኢያሪኮን ውኃ ሲያጣፍጥ "አዲስ ማሰሮ አምጡልኝ፣ ጨውም ጨምሩበት" በማለት ነበር፡፡ አዲስ ማሰሮ፣ ያውም ጨው ጨምራችሁ አምጡልኝ ማለት ለምን አስፈለገው? ከዚያም ውኃው ወዳለበት ምንጭ ወጥቶ ጨው ጣለበትና "ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፈወስክዎ ለዝንቱ ማይ - እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ይህን ውኃ ፈውሼዋለሁ፣ ከዚህም በኋላ ሞትና ጭንገፋ አይሆንበትም አለ። ኤልሳዕም እንደ ተናገረው ነገር ውኃው እስከ ዛሬ ድረስ ተፈውሷል።" 2 ነገ. 2፡21-22 ታዲያ በማሰሮና በጨው እንዴት ውኃው ተፈወሰ? በእንዲያ ዓይነት ሁኔታ የተፈወሰውን ውኃስ "እኔ ፈወስኩት" ሳይሆን "እግዚአብሔር ፈወሰው" እንዴት አለ? እንደ ተሐድሶዎች አስተሳሰብ ቢሆን ኖሮ የእግዚአብሔርን ሥፍራ ማሰሮና ጨው ነጠቀው ይሉ ነበር፡፡

ራሱ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐዋርያቱ ጋር በአካል አብሯቸው እያለ እንኳ በዘይት እየቀቡ በሽተኞችን እንዲፈውሷቸው ልኳቸው ስለነበር ወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ የዚያን ተልእኮ ውጤት ሲነግረን "ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሷቸው" ይላል፡፡ ማር. 6፡13 ታዲያ ራሱ ጌታችን ድውዮችን ዘይት እየቀቡ እንዲፈውሷቸው ማድረጉ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች *"ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ባይኖራትም መንፈስ ቅዱስ የተመሰለበት ዘይት (ቅባት) በምትኩ ይኖራት ዘንድ ተጠበበች፡፡ . . . የእግዚአብሔርን ምሥጢር የምናውቅበት በምእመናን የሚያድረው ቅብዐት የተቀመመ ዘይት ሳይሆን ራሱ መንፈስ ቅዱስ ነው"* እንደሚሉት መንፈስ ቅዱስ ያለ መኖርና ሌላ ምትክ ወይም አማራጭ መፈለግ ነበረን? በጭራሽ!

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብስ በመልእክቱ "ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት" ለምን አለ? ያዕ. 5፡14 በተቀመመ ዘይት ላይ ጸልዮ ሀብት ሥርየት ማሰጠት እንደ ተሐድሶዎች ትምህርት ከሆነ መንፈስ ቅዱስን መተውና ሌላ ምትክ መፈለግ ስለሆነ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ መንፈስ ቅዱስን ትቶ ሌላ አማራጭ እየፈለገ ነበር ይሆን? በእውነት ጌታችን በመስቀል ላይ እያለ "አባ ሥረይ ሎሙ እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ - አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" እንደ ተባለላቸው ክርስቶስን እንደ ሰቀሉት አይሁድ የሚያደርጉትን አውቀው ታል ይሆን? ቅዱስ ጳውሎስ "የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም" እንዳላቸው እንደ አይሁድ የራሳቸውን "እንግዳ ጽድቅ" ለማቆም ሲሉ የእግዚአብሔርን ጽድቅ እየተቃወሙና እየነቀፉ መሆኑን ማየት አልቻሉም። ሮሜ 10፡3 እብደታቸው ከምን የክህደት ጉድጓድ እንደሚያደርሳቸው መረዳት አልቻሉም ወይም አልፈለጉም፡፡

ብሉይ ኪዳን በሐዲስ ኪዳን ለሚሆነው ነገር አመልካች፣ አዘጋጅና ፋና ወጊ ነበር፡፡ ስለዚህ ጸጋ እግዚአብሔር የሚተላለፍበትን የተቀደሰ ቅባት አዘገጃጀት በተመለከተ ራሱ እግዚአብሔር ለሙሴ በዝርዝር ነግሮታል፤ እንዲህ ሲል፦

> በቀማሚም ብልሃት እንደ ተሠራ ቅመም፥ የተቀደሰ የቅብዓት ዘይት ታደርገዋለህ፣ የተቀደሰ የቅብዓት ዘይት ይሆናል። የመገናኛውንም ድንኳን፣ የምስክሩንም ታቦት፣ ገበታውንም ዕቃውንም ሁሉ፣ መቅረዙንም ዕቃውንም፣ የዕጣን መሠዊያውንም፣ ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆነውን መሠዊያና ዕቃውንም ሁሉ፣ የመታጠቢያውን ሰንና መቀመጫውንም ትቀባበታለህ። ሁሉንም ትቀድሳቸዋለህ፤ ቅድስተ ቅዱሳንም ይሆናሉ፤ የሚነካቸውም ሁሉ ቅዱስ ይሆናል። በክህነትም ያገለግሉኝ ዘንድ አሮንንና ልጆቹን ቅባቸው፥ ቀድሳቸውም። እንተም ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ተናገር፦ ይህ ለልጅ ልጃችሁ የተቀደሰ የቅብዓት ዘይት ይሁንልኝ። በሰው ሥጋ ላይ አይፍሰስ፣ እንደ እርሱም የተሠራ ሌላ ቅብዓት አታድርግ፣ ቅዱስ ነው፤ ለእናንተም ቅዱስ ይሁን። እንደ እርሱ ያለውን የሚያደርግ ሰው፥ በሌላም ሰው ላይ የሚያፈስሰው ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ። ዘጸ. 30፡25-33

እንዲሁም እግዚአብሔር ጸጋውን በጸሎት በሚከብር ዘይት አማካይነት እንደሚሰጥ በተምሳሌታዊ አነጋገር እንዲህ ተብሎ ተገልጸ እናገኛለን፡- "ወይራው ግን፦ እግዚአብሔርና ሰዎች በእኔ የሚከብሩበትን ቅባቴን ትቼ በዛፎች ላይ እንድሰፍፍ ልሂድ? አላቸው።" መሣ. 9:9 ራሳቸውን "ተሐድሶ" ብለው የሚጠሩት ወገኖቻችን እነዚህ የእግዚአብሔር ቃሎች መሆናቸውን ቢያምኑ ኖሮ ከላይ እንደ ጠቀስነው ያለ ድፍረት እንዴት ይጽፉ ነበር? በተለያየ ሁኔታ ለማድበስበስና ለመሸፈን ቢሞክሩም ዋናው ችግራቸው ሙሉ በሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን ማመን ላይ ነው፡፡ መናፍቅ የሚያሰኛቸውም ይህ ነው፡፡ በተለይም ደግሞ ለብሉይ ኪዳን ያላቸው ጥላቻና ንቀት ከመርቅያንና መሰሎቹ ግኖስቲኮች የወረሱት ክፉ እርሾ ነው፡፡

ተሐድሶዎች "ተጠማቂዎችን በቅብዐ ሜሮን ማክበር ጸጋን አያሰጥም" የሚሉት በውኃ አማካይነት የሚፈጸመው ጥምቀትም ልጅነትንና ሥርየተ ኃጢአትን የማያሰጥ እንዲሁ የአባልነት መታወቂያ ነው ከማለታቸው የቀጠለ ክህደታቸው ነው፡፡ ይህም ሥነ ፍጥረትን ከሚጠሉትና ከሚጸየፉት ከእነ መርቅያንና ከእነ ማኒ የምንታዌ ትምህርት አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የቀዱት የክህደት መርዝ ነጸብራቅ ነው፡፡ ይህም በመጀመሪያ እግዚአብሔር ጸጋውን ለማስተላለፍና ሥራውን ለመሥራት ሥነ ፍጥረቱን አይጠቀምም ማለታቸውና በሥነ ፍጥረት አማካይነት የሚተላለፉ ጸጋዎችን (በውኃ የሚፈጸመውን ጥምቀት፣ በቅብዐ ቅዱስ የሚፈጸመውን ሜሮን፣ ወደፊት እንደምናየው ደግሞ በኅብስትና በወይን የሚፈጸመውን ምሥጢረ ቁርባንን) የሚያቃልሉትና አምርረው የሚጠሉት ከላይ በመኃትው ላይ እንደ ተመለከትነው ግኖስቲካዊና መርቅያናዊ እርሾቸው ስለሚስባቸው ነው፡፡ ቅዱስ ሄሬኔዎስ ምሥጢራት የሚፈጸምባቸውን ነገሮች ያቃልሉና ይነቅፉ ስለ ነበሩ ስለ እንደዚህ ዓይነቶቹ መናፍቃን ሲናገር እንዲህ ይላል፡- "ሰዎችን ወደ ውኃ ውስጥ ማስገባትና ማጥመቅ አላስፈላጊ ነው የሚሉ አንዳንዶች አሉ፡፡ . . . እነዚህ የማይታየውና የረቂቁ ኃይል በሚታዩና ቁሳዊ ህልውና ባላቸው ሥነ ፍጥረታት አማካይነት መፈጸም የለበትም ይላሉ፡፡ . . ." (ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ በእንተ መናፍቃን፣ ምዕ. 21. ቁ. 4)

በሁለተኛ ደግሞ በብሉይ ኪዳን በተምሳሌትና በትንቢት የተነገረውን ነገር ሁሉ መጸየፋቸውና አለመቀበላቸው አሁንም የብሉይ ኪዳንን አምላክ "ክፉው አምላክ" እያሉ ይጠሉና ይቃወሙ የነበሩት የመርቅያንና የማኒ ልጆች በመሆናቸው ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ከላይ ዘጸ. 30:25-33 ላይ የተነገረውንና ለዘመነ ወንጌል መርገፍና ፋና ወጊ ሆኖ ያገለገለውን የእግዚአብሔር ትእዛዝ የሚጠሉት ከዚህ መርቅያናዊ እርሾ የተነሣ ነው፤ ዛፍ ከፍሬው ይታወቃልና፡፡

እኛ ግን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያስተምረው በውኃ አማካይነት በሚፈጸም ምሥጢረ ጥምቀት ልጅነትን፣ ሥርየተ ኃጢአትን . . . ይሰጠናል፤ በቅብዐ ሜሮን አማካኝነትም ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ያሳድርብናል፣ ያትመናል ብለን እናምናለን፡፡ በጥምቀት ጊዜ በጸሎት በሚከብረው ማየ ጥምቀቱ (ውኃው) ምክንያት (የሚታይ መሣሪያ) ሲሆን ዳግም የምንወለደው ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ ሁሉ በቅብዐ ሜሮንም የሚቀባው ሰው አካሉ ላይ የተቀደሰው ቅባት (ሜሮን) ሲያርፍ መንፈስ ቅዱስ በዚያ አማካይነት ያከብረዋል፣ ያትመዋል፡፡ ሥነ ፍጥረት እግዚአብሔር የፈጠረውና የከበረ ስለሆነ እግዚአብሔር ጸጋውን በወደደው መንገድ ያስተላልፍበት ዘንድ ይችላል፡፡

ስለዚህ ምሥጢረ ሜሮን ለተጠመቁ ሰዎች ከጥምቀት ቀጥሎ ወዲያውኑ የሚፈጸም ምሥጢር ነው፡፡ ይህም በቅዱስ ቅባት መቀባትን የሚያመለክት ምሥጢር ሲሆን በዚህም ተጠማቂው በመንፈስ ቅዱስ መታተምንና ሀብታተ መንፈስ ቅዱስን ያገኛል፡፡ ሜሮን ለእግዚአብሔር መታተምን ያስገኛል፡፡ በዚህ ምሥጢር መፈጸም ተጠማቂው አባቱን እግዚአብሔርንና ፈቃዱን የሚያውቅበትንና ፍቅሩ በውስጡ የሚሣልበትን ጸጋ ያገኛል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ስለዚህ ምሥጢርና አገልግሎቱ ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

> እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፤ ሁሉንም ታውቃላችሁ፡፡ . . . እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፤ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፡፡ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ፤ እውነተኛም እንደ ሆነ፤ ውሸትም እንዳልሆነ፤ እናንተንም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ፡፡ 1 ዮሐ. 2:20፣21፣27

በአጠቃላይ ይህ ምሥጢር፦ *"እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን"* እንደ ተባለ እያንዳንዱ ክርስቲያን ይሠራበትና ፈጣሪውን ያገለግልበት ዘንድ እንደየ ዓቅሙ የሚችለውንና የሚጠቅመውን ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታ የሚያገኝበት ምሥጢር ነው፡፡ ኤፌ. 4:7 ፤1 ቆሮ. 12:7፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ስለዚህ ምሥጢር፦ *"ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ"* አለ፡፡ ኤፌ. 4:4

## 3.7.2.2.3 ምሥጢረ ሜሮን በአበው ሊቃውንት ትምህርት

*ምሥጢረ ሜሮን ከመጀመሪያዎቹ የሐዲስ ኪዳን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ከቅዱሳን ሐዋርያትና ከተከታዮቻቸው ሊቃውንት ዘመን ጀምሮ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን በአማንያን ለማሳደር አገልግሎት ላይ ይውል የነበረ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢር ነው፡፡ ቀደምት ሊቃውንት ስለ ምሥጢረ ሜሮን ካስተማሩት ትምህርት ለአብነት የሚከተለውን እንመለከታለን፡፡*

- "ልብስህን ባወለቅህና ዕራቁትህን በሆንህ ጊዜ በተቀደሰው ቅባት (በሜሮን - μύρῳ) ተቀባህ፤ ከራስህ ጸጉር እንስቶ እስከ እግርህ ድረስ ተቀባህ፤ በዚህም ከመልካሙ የወይራ ዘይት ዛፍ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሱታፌ ያለህ ሆንህ፡፡[72] ባዕድና ዱር በቀል ከሆነው የወይራ ዘይት ዛፍ ተቆርጠህ መልካም ከሆነው የወይራ ዘይት ዛፍ ላይ ተተከልህ፤ ከእማናዊው የወይራ ዘይት ዛፍ [ከኢየሱስ ክርስቶስ] ከሰፈፈው መልካም ቅባት ተሳታፊ ተደረግህ፡፡ የተቀደሰው ቅባት (ሜሮን - μύρῳ) ብዙ ከሆነው ከክርስቶስ ሀብታት የመካፈል ምልክት ነው፡፡ የቅዱሳን እስትንፋስና የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ልክ በላዒ እንደ ሆነ ኃይለኛ የእሳት ነበልባል ርኩሳን መናፍስትን እንደሚያቃጥላቸውና እንደሚያባርራቸው ሁሉ፤ እንደዚሁም በጸሎት የተባረከው (የከበረው) ቅባት (ሜሮን - μύρῳ) ስመ እግዚአብሔርን በመጥራትና በጸሎት የኃጢአትን ቅሬት ማቃጠልና ማንጻት ብቻ ሳይሆን የክፉውን መንፈስ ረቂቅና የማይታዩ ኃይላት ሁሉ የማባረር ኃይልን ያስገኛል፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፤ ትምህርት 20፤ በእንተ ጥምቀት፤ ቁ. 3)

- "የተጠመቀ ሰው ከመጠመቁ ቀጥሎ በሜሮን ይቀባ ዘንድ አስፈላጊ ነው፡፡ ሜሮንን የሚቀበለውና የሚቀባውም ከእግዚአብሔር የተቀባ ይሆን ዘንድና በውስጡ የክርስቶስ ጸጋ እንዲያድርበት ነው፡፡ ሆኖም መሠዊያ (ምሥዋዕ) እና ቤተ ክርስቲያን የሌለው ቅብዐ ሜሮንን ሊቀድስና ማክበር አይችልም፤ መናፍቃን ይህን የሜሮን ምሥጢር የመፈጸምና የመቀባት ሥልጣን የላቸውም፡፡ በመናፍቃን ዘንድ ዘይቱም ሊከብር፤ የቅዱስ ቁርባን ምሥጢርም ሊፈጸም አይችልም፡፡ ይልቁንም ማንም ከእውነት ውጭ እንዳይሄድና ከመንገድ ወጥቶ እንዳይባዝን 'የኃጢአተኛ ዘይት ግን ራሴን አይቀባ' ተብሎ እንደ ተጻፈ ማወቅና ማስታወስ ይገባናል። መዝ. 140፡5" (ሰማዕቱ ቅዱስ ቆጵርያኖስ፤ መልእክት 69)

[72] ይህ የቅዱስ ቄርሎስ አገላለጽ ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ ምዕራፍ 11 ላይ "ሥሩም ቅዱስ ከሆነ ቅርንጫፎቹ ደግሞ ቅዱሳን ናቸው። ነገር ግን ከቅርንጫፎች አንዳንዱ ቢሰበሩ አንተም የበረሀ ወይራ የሆንህ በመካከላቸው ገብተህ ከእነርሱ ጋር የወይራ ዘይት ከሚወጣው ሥር ተካፋይ ከሆንህ በቅርንጫፎች ላይ አትመካ . . ." ብሎ ከገለጸው ትምህርት አንጻር የቀረበ ማብራሪያ ነው።

በ4ኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ገደማ በኢየሩሳሌም መንበር ላይ ጳጳስ የነበረው ታላቁ አባት ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም አዲስ ለተጠመቁና በሜሮን ምሥጢር ለታተሙ ክርስቲያኖች ባስተማረው ትምህርት ላይ እንዲህ ብሏል፡-

- "ይህ ሜሮን ተራ ቅባት ነው ብለህ እንዳታስብ ተጠንቀቅ፡፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በመሥዋዕቱ ላይ እንደሚወርድና መሥዋዕቱን እንደሚያከብረው፤ በጸሎተ ቅዳሴው ከተጠራና ካከበረው በኋላ የቁርባኑ ኅብስት መጀመሪያ እንደ ነበረው ተራ ኅብስት ሳይሆን የራሱ የክርስቶስ ሥጋ እንደሚሆን ሁሉ ይህ ቅዳ ስ ቅባትም ተራ ቅባት አይደለም፤ በጸሎት ከከበረ በኋላ የክርስቶስን የጸጋ ስጦታ የሚያሳድርና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ጸጋውን ለማሳደር ተገቢ የሆነ መሣሪያ ይሆናል እንጂ፡፡ ይህ ቅባትም በግምባራችን ላይና በሌሎች የሰውነታችን አካላት ላይ ይደረጋል፤ የሚታየው ሰውነት በሚታየው በከበረው ቅባት (በሜሮን) ሲቀባ ነፍስ ደግሞ ቅዱስና ሕይወት ሰጭ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ትቀደሳለች፡፡

"መጀመሪያ ሜሮኑን ከግምባራችሁ ላይ ተቀባችሁ (ታተማችሁ)፤ ሕገ እግዚአብሔርን ያፈረሰው የመጀመሪያው ሰው (አዳም) በየሄደበት ሁሉ ተሸክሞት ይዞር ከነበረው ኃፍረት ነጻ ትሆኑ ዘንድ፤ እንዲሁም *በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያንፀባረቁን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ* (2 ቆሮ. 3፥18)፡፡ ከዚያም በጆሯችሁ ላይ ተቀባችሁ፣ አምላካዊ ምሥጢራትን ለመስማት የፈጠኑ ጆሮዎችን ትቀበሉ ዘንድ፤ ኢሳይያስ 'እግዚአብሔር ሆይ፣ የሚሰማ ጆሮን ሰጠኝ' እንዳለው ያለ እንዲሁም ጌታችን 'ጆሮ ያለው መስማትን ይስማ' እንዳለው ያለ ጆሮን እንቀበል ዘንድ፡፡ ኢሳ. 50፥4 ማቴ. 11፥15 ቀጥሎም አፍንጫህ ላይ ተቀባህ፤ ይህም የተቀደሰውን ቅባት ስትቀባ "በሚድኑቱና በሚጠፉቱ ዘንድ ለእግዚአብሔር የክርስቶስ መዓዛ ነንና" ማለት የምትችል ትሆን ዘንድ ነው፡፡ 2 ቆሮ. 2፥15

"በመቀጠልም ጡታችሁ ላይ ትቀባላችሁ፤ ይህም 'የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ' እንድትችሉ ነው፡፡ ኤፌ. 6፥11፤ 14 ክርስቶስ ከተጠመቀና እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ በላዩ ላይ ካረፈ በኋላ ጠላት ዲያብሎስን ድል እንዳደረገው ሁሉ [ከዚያ በኋላ በቀጥታ ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ሄዶ አርባ ቀንና ሌሊት በመጋደል] እንደዚሁም ከቅዱስ ጥምቀት እና ከምሥጢራዊው ሜሮን በኋላ የመንፈስ ቅዱስን ዕቃ ጦር ሁሉ ለብሰን በጠላት ኃይል ላይ ልንነሣበትና 'ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ' እያልን ድል ልናደርገው ይገባል፡፡[73] ፊል. 4፥13

"በዚህ በተቀደሰው በሜሮን ከመታተማችሁ የተነሣ ክርስቲያኖች ተባላችሁ፣ ይህን ስምም በአዲሱ ልደታችሁ አረጋገጣችሁ፡ ለዚህ ጸጋ ከመብቃታችሁና ይህን ጸጋ ከማግኘታችሁ በፊት ለዚህ ታላቅና የከበረ ስም [ክርስቲያን ለመባል] መብት አልነበራችሁምና፡፡

"በተጨማሪም በብሉይ ኪዳን የዚህ የሜሮን ምሳሌ እንደ ነበረ ታውቁ ዘንድ ይገባል፡፡ ሙሴ ለወንድሙ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሲነግረውና ሊቀ ካህናት ሲያደርገው በውኃ ከታጠበ በኋላ አሮንን ከቅዱሱ ቅባት ቀባው፤ አሮንም የተቀባ (ቅቡዕ) ተባለ፡፡ ይህም በግልጽ ሁኔታ ምሥጢረ ሜሮንን የሚያሳይ ነበር፡፡ እንደዚሁም ሊቀ ካህናቱ ሰሎሞንን ሲያነግሠውና ለመንግሥት ሲቀባው በግዮን ውኃ ካጠበው በኋላ ቅብዐ መንግሥት ቀባው፡፡ 1 ነገ. 1፥39

[73] (For as Christ after His Baptism, and the vis tatic n of the Holy Ghost, went forth and vanquished the adversary, so likewise ye, after Holy Baptism and the Mystical Chrism, having put on the whole armour of the Holy Ghost, are to stand against the power of the adversary. and vanquish it, saying, *I can do all things through Christ which strengtheneth me.)*

ሆኖም ለእነዚያ እነዚህ ነገሮች የተደረጉላቸው በምሳሌ ነው (ምሳሌዎች ናቸው)፤ ለእናንተ የተደረገላችሁ ግን በምሳሌ ሳይሆን በእውነት ነው፤ ምክንያቱም እናንተ በመንፈስ ቅዱስ በእውነት ተቀብታችኋልና፡፡ ክርስቶስ የድኅነታችሁ ጀማሪ ነው፤ እርሱ በእውነት በኩር ነውና፤ እናንተ ደግሞ ብሆው ናችሁ፤ ሆኖም በኩራቱ ቅዱስ ከሆነ ቅድስናው ወደ ብሆው ማለፉና መድረሱ አይቀርም፡፡" ሮሜ 11፥16"

(ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፤ ትምህርት 21፤ በእንተ ሜሮን፤ ቁ.3-7)

- "ሐዋርያዊ በሆነው ትውፊታችን መሠረት በጸሎት የከበረ ሜሮን እንቀባለን፡፡" (ቅዱስ አቡሊዲስ፤ ትውፊት ዘሐዋርያት[74])

- "ተጠማቂውን ዲያቆናት ሙሉ በሙሉ ልብሱን ካስወለቁት በኋላ ካህናቱ የሚቀባውን ቅዱስ ቅባት (ሜሮን) ያቀርባሉ፡፡ ከዚያም ሦስት ጊዜ በስመ ሥላሴ ካማተበበት በኋላ መላ አካሉን ይቀባዋል፡፡ . . . ካህኑ ተጠማቂውን በቅዱስ ሜሮን ካተመው በኋላ ፍጹም ሰማያዊ የሆነውን ቅዱስ ቁርባንን እንዲቀበል ያደርገዋል፡፡" (ቅዱስ ዲዮናስዮስ፤ ክፍል 7)

- ". . . በመቀጥልም አዲስ ተጠማቂውን እንደ ብርሃን ነጭ የሆነ ልብስ ያለብሱታል፡፡ . . . ፍጹም ማኅተም የሆነው የቅብዐ ሜሮን መቀባት አዲሱን ተጠማቂ የክርስቶስ መልካም መዐዛ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡" (ቅዱስ ዲዮናስዮስ፤ ክፍል 8)

- "ከመጠመቂያው ውኃ እንደ ወጣን ወዲያውኑ በተቀደሰው ዘይት (በሜሮን) እንቀባለን፡፡" (ጠርጠሉስ፤ በእንተ ጥምቀት)

## 3.7.2.2.4 ስለ ምሥጢረ ሜሮን - ማጠቃለያ

ምሥጢረ ሜሮን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት ባገኘችው ትምህርትና ትውፊት መሠረት የምትጠቀምበት ምሥጢር ነው፡፡ ተሐድሶዎች ይህን ምሥጢር መንቀፋቸውና መጸየፋቸው ግን ከአባቶቻው ከግስቲኮችና ከእነ መርቅያን የወረሱት ኑፋቄ እንጂ እነርሱ የሚሉት ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ እና በአባቶች ትምህርት አንዳችም ድጋፍና መሠረት የለውም፡፡ ስለዚህም ራሳቸውን "እርቶዶክስ" ብለው ለመጥራት አንዳችም መሠረት የላቸውም፡፡ ይልቁንም ራሳቸውን "መናፍቃን" ወይም "ፕሮቴስታንት" ብለው ቢጠሩ ቢያንስ ማንነታቸውን በእውነት በመናገራቸው እንኳ እውነት መናገር ሊሆንላቸው ይችል ነበር፡፡ ሆኖም ግን ለዚህ እንኳ አልታደሉም፡፡

## 3.7.2.3 ምሥጢረ ቁርባን

### 3.7.2.3.1 ተሐድሶዎች ስለ ምሥጢረ ቁርባን የሚያስተምሩት ትምህርት

ለእውነተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ዘብ ቆመናል የሚሉት ተሐድሶዎች ስለ ምሥጢረ ቁርባን የሚሉትን እንመልከት፡-

- "እውነት ነው፥ ብዙዎች 'የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ፥ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም፡፡ ሥጋዬን የሚበላ፥ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው' የሚለው አንቀጽ ቅዱስ ቁርባንን እንደሚያመለክት ያምናሉ፡፡ ይህ አተረጓጎም ግን ክርስቶስ ከተናገረበት ጊዜ፥ ከአድማጮቹ ሁኔታና ከሰጠው ሌላ ትምህርት ጋር <u>የሚስማማ አይመስልም</u>፡፡ . . . ይህንም አተረጓጎም የማንቀበልበት ዋና ምክንያት ክርስቶስ ሰው የዘላለም ሕይወት የሚያገኘው በእርሱ በማመን እንደሆነ በዚህ አንቀጽ

[74] (Apostolic Tradition)

በማስተማሩ ነው፡፡ ደግሞም "የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፣ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፣ በእኔ የሚያምንም ሁል ጊዜ ከቶ አይጠማም" በማለቱ እምነትን በመብላትና በመጠጣት መሰለው፡፡ ይህ አንቀጽ ቅዱስ ቁርባንን ያመለክታል የሚሉ ወገኖች ስሕተት፣ ክርስቶስ በምሳሌ አገላለጥ መናገሩን እንጂ ቃል በቃል አለማስተማሩን ያለመረዳታቸው ነው፡፡" (ጮራ ቁ. 19፣ ገጽ 8)

- "ወደ እርሱ ወደ ራሱ በመንፈስ በመቅረብ እርሱን ራሱን በመንፈሳዊ መብልነቱ መቀበል፣ በመንፈሳዊ መጠጥነቱ እርሱን ራሱን በመንፈስ መጠጣት ነው፡፡" (ጮራ ቁ. 26፣ ገጽ 10-11)

- " 'ስያሜውን በተመለከተ - ይህ ኅብስት ሥጋዬ ነው፤ እንኩ ብሉ፡፡ ይህ ጽዋ ደሜ ነው፤ እንኩ ጠጡ' ከሚለው ጋር እያይዞ 'ሥጋውንና ደሙን የሚወክል "ኅብስትና ወይን ነው" ለማለት ተፈልጎ የወጣ ስም ሊሆን ይችላል፡፡' ነገር ግን 'በጸሎት ኅብስቱና ወይኑ ተለውጠ፣ በመዓዛውም በጣዕሙም በቀለሙም አማናዊውን ሥጋ ኢየሱስን ይሆናል' በሚል እሳቤ የወጣ ስም ከሆነ ትክክል አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ከሆነ ጊዜ ጀምሮ እንደዚህ ሆኖ ስለማያውቅ ነው፡፡" (ጮራ ቁ. 26፣ ገጽ 12)

- "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብስቱን ቆርሶ ሲሰጣቸው 'ይህ ሥጋዬ ነው' ብሏል፤ እንደዚሁም ከጽዋው እንዲጠጡ ሲሰጣቸው 'ይህ ደሜ ነው' ብሏል፡፡ ይህ ሥጋዬ ነው፤ ይህ ደሜ ነው ያለው ቢለወጥ አይደለምን? የሚል ክርክርም አስነሥቷል፡፡ አንድን ነገር ሊወክል የቀረበው ተወካይ (ምሳሌው) ወካዩን ሆኖ መነገሩ የተለመደ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ካርታ 'ይቺ ኢትዮጵያ ናት'፣ የሰዎችን ፎቶ ወይም ሥዕል 'ይህ እገሌ ነው፣ ይቺ እገሊት ናት' እንደ ማለት ነው፡፡" (ጮራ ቁ. 26፣ ገጽ 14)

- "ምግቡ [ምሥጢረ ቁርባን] በሌላ ጊዜ ከምንመገበው ማዕድ የተለየ ነገር የለውም፡፡ በትንሽ ጉርሻና ጥቂት ጠብታም መወሰን የለበትም፡፡ እንደ ሌላው ኅብስት ይበላል፤ እንደ ሌላውም ወይን ይጠጣል፡፡ ሲዘጋጅም ሆነ ከዝግጅት በኋላ ኅብስቱ እንደ ማንኛውም ኅብስት ነው፤ ወይኑም እንደ ማንኛውም ወይን ነው፡፡" (ጠማሬ ጽድቅ፣ ጥቅምት 1991 ዓ.ም.፣ ገጽ 97)

- "በሚቀርበው የምስጋና ጸሎትም በኅብስቱና በወይኑ ላይ የሚመጣ መለወጥ የለም፡፡ ካህኑ በሚጸልየው ጸሎት ኅብስቱና ወይኑ ወደ እውነተኛ የክርስቶስ ሥጋና ደም ይለወጣል ብለው እንደ . . . የመሳሰሉ የሃይማኖት ድርጅቶች የያዙት እምነት . . . በቅዱሳት መጻሕፍት ምንም ድጋፍ የለውም፡፡" (ጠማሬ ጽድቅ፣ ጥቅምት 1991 ዓ.ም.፣ ገጽ 97)

- "ወደዚህ ገበታ አንዳች ለመቀበል አንመጣም፡፡ የጌታ እራት ጸጋን የምንቀበልበት ምስጢር አይደለም፡፡ . . . በዚህ ስብሰባ ላይ ልዩ ተሰጥኦ ወይም በተለዩ ሰዎች የተያዘ ክህነታዊ ሥልጣን ስፍራ የለውም፡፡" (ጠማሬ ጽድቅ፣ ጥቅምት 1991 ዓ.ም. ገጽ 102)

በምሥጢረ ቁርባን ላይ ያላቸው እምነትና ትምህርታቸው ሲጠቃለል፡-

1. "ሥጋዬን የሚበላ፣ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው" የሚለው አንቀጽ ቅዱስ ቁርባንን አያመለክትም ይላሉ፡፡

2. ሥጋውና ደሙ የተባለው "እምነት" ነው እንጂ አማናዊ የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ አይደለም ይላሉ፡፡

3. ምሥጢረ ቁርባን የተለየ ምሥጢርነት የለውም፣ እንደ ማንኛውም ተራ ምግብ ነው ይላሉ፡፡ እግዚአብሔር ይቅር ይበለንና ወደር በሌለው ክህደትና ድፍረት እንዲህ ይላሉ፡- "ምግቡ በሌላ ጊዜ ከምንመገበው ማዕድ የተለየ ነገር የለውም፡፡ በትንሽ ጉርሻና ጥቂት ጠብታም መወሰን የለበትም፡፡ እንደ ሌላው ኅብስት ይበላል፤ እንደ ሌላውም ወይን ይጠጣል፡፡ ሲዘጋጅም ሆነ ከዝግጅት በኋላ ኅብስቱ እንደ ማንኛውም ኅብስት ነው፤ ወይኑም እንደ ማንኛውም ወይን ነው፡፡" (ጠማሬ ጽድቅ፣ ጥቅምት 1991 ዓ.ም. ገጽ 97)

4. በጸሎተ ቅዳሴ የሚቀርበው ኅብስቱና ወይኑ ወደ ክርስቶስ ሥጋነትና ደምነት አይለወጥም፣ አይከብርም ይላሉ፡፡

- "በሚቀርበው የምሲጋና ጸሎትም በኅብስቱና በወይኑ ላይ የሚመጣ መለወጥ የለም፡፡ ካህኑ በሚጸልየው ጸሎት ኅብስቱና ወይኑ ወደ እውነተኛ የክርስቶስ ሥጋና ደም ይለወጣል ብለው እንደ . . . የመሳሰሉ የሃይማኖት ድርጅቶች የያዙት እምነት . . . በቅዱሳት መጻሕፍት ምንም ድጋፍ የለውም፡፡" (ጠማሪ ጽድቅ፣ ጥቅምት 1991 ዓ.ም. ገጽ 97)
- "ይህ ሥጋዬ ነው ማለቱም የሰጣቸው ሥጋውን ሆኖ አይደለም፣ ኅብስቱ የሥጋው እንደራሴ ሆኖ ነው እንጂ፡፡" (ጠማሪ ጽድቅ፣ ጥቅምት 1991 ዓ. ም. ገጽ 98)
- "በጸሎት ኅብስቱና ወይኑ ተለውጦ፣ በመዓዛውም በጣዕሙም በቀለሙም አማናዊውን ሥጋ ኢየሱስን ይሆናል" በሚል እሳቤ የወጣ ስም ከሆነ ትክክል አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ከሆነ ጊዜ ጀምሮ እንደዚህ ሆኖ ስለማያውቅ ነው፡፡" (ፋኑራ ቁ. 26፣ ገጽ 12)

5. ምሥጢረ ቁርባን አንዳች ነገር ወይም ጸጋ አያስገኝም ይላሉ፡፡ "ወደዚህ ገበታ አንዳች ለመቀበል እንመጣም፡፡ የጌታ እራት ጸጋን የምንቀበልበት ምስጢር አይደለም፡፡" (ጠማሪ ጽድቅ፣ ጥቅምት 1991 ዓ.ም.፤ ገጽ 102)

ከዚህ ቀጥሎ ተሐድሶዎች የሚሉትን ይህን ሁሉ ጉድ በመጽሐፍ ቅዱስ እና በአበው ሊቃውንት ትምህርት መሠረት ወደ መመዘኑ እንሂድ፡፡

## 3.7.2.3.2 ምሥጢረ ቁርባን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

ምሥጢረ ቁርባን መዳናችን የተፈጸመበትና የታተመበት የምሥጢራት ሁሉ ዘውድ (ምሥጢረ ምሥጢራት) ነው፡፡ ይኸን ምሥጢርም እንደ ሌሎቹ ምሥጢራት ሁሉ በቃሉ ትምህርት የነገረን እንዲሁም በተግባር ሠርቶ ያሳየን ለስሙ አጠራሩ ክብር ምስጋና ይግባውና ራሱ ባለቤቱ ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ አስቀድሞ ትምህርቱን በሰፊትና በጥልቀት ካስተማረ በኋላ በጸሎተ ሐሙስ በተግባር ፈጽሞ ያሳየን ምሥጢር ነው፡፡ በየቅዳሴው ጊዜ የሚፈጸመውም ያው ምሥጢር ነው፡፡ የሚደጋገም አይደለም፣ ያው ራሱ የምሴተ ሐሙሱ፣ ጌታ በዕለተ ዓርብ የፈጸመው ምሥጢር ራሱ ነው እንጂ፡፡

ይኼ ምሥጢር መሠረታዊና ጥልቅ ምሥጢር ስለሆነ ጌታችን ደግሞ ደጋግሞ፣ መልሶና መላልሶ ካስተማራቸው ጥልቅ ትምህርቶች አንዱና ዋነኛው ይኸን ምሥጢር በተመለከተ ያስተማረው ትምህርት ነው፡፡ ትምህርቱን ከጥንቱ ከምሳሌው በመጀመር ወደ አማናዊው በማምጣት እንዲህ ሲል አስተማረ፡-

> እንግዲህ አይሁድ ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ ስላለ ስለ እርሱ አንጐራጐሩ . . . ኢየሱስ መለሰ፣ አላቸውም፡- . . . የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ፣ ሞቱም፣ ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው። ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።
>
> እንግዲህ አይሁድ፡- ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል? ብለው እርስ በርሳቸው ተከራከሩ፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፡- እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፣ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ። ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፣ እኔም በእርሱ እኖራለሁ። ሕያው አብ እንደ ላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን፣ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል። ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው፤ አባቶቻችሁ መና በልተው እንደ ሞቱ አይደለም፤ ይህን እንጀራ የሚበላ ለዘላለም ይኖራል፡፡ በቅፍርናሆም ሲያስተምር ይህን በምኩራብ አለ። ከደቀ መዛሙርቱም ብዙዎች በሰሙ ጊዜ ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው፤ ማን ሊሰማው ይችላል? አሉ። ዮሐ. 6፥41-60

ይህ ትምህርት ሲሰጥ በአካለ ሥጋ የነበሩት አይሁድ ጥንት አባቶቻቸው እስራኤላውያን ከግብጽ ሲወጡ ቀይ ባሕር በተአምራት ወዲህና ወዲያ ተከፍሎላቸው በደረቅ ከተሻገሩ በኋላ እግዚአብሔር መና ከሰማይ አውርዶላቸው ምድራዊት ኢየሩሳሌም ከነዓን እስከሚገቡ ድረስ አርባ ዓመት ሙሉ ሲመገቡ ኖረዋል። ምድረ ርስትን ሲረግጡ፣ በዚያ ከበቀለውና ካፈራው ከምድሪቱ ፍሬ ሲመገቡ ግን መናው ቀርቷል። ይህም በዘመን ወንጌል ስለሚሆነው ነገር አስቀድሞ በተምሳሌት የሚያሳይ መስተዋት ነበር። ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ ምሳሌውን ከአማናዊው፣ ሰሙን ከወርቁ ጋር አነጻጽሮ በአንደኛ ቆሮንቶስ መልእክቱ እንዲህ ሲል የገለጸው፡-

> ወንድሞች ሆይ፣ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ፣ ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ፤ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ፤ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ፣ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና፣ ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ። 1 ቆሮ. 10፥1-4

የጥንቶቹ እሥራኤላውያን ከግብጽ መውጣታቸውና ቀይ ባሕርን መሻገራቸው እኛ በጥምቀት ከሞት ወደ ሕይወት ከባርነት ወደ ነጻነት ለመሻገራችን ምሳሌና አመልካች ነበር። እነዚያ ቀይ ባሕርን ከተሻገሩ በኋላ ከሰማይ የወረደ መና አርባ ዓመት ሲመገቡ እና ከዓለት የፈለቀ ውኃ ሲጠጡ መኖራቸው ዓለት ከተባለው ከክርስቶስ ከጎኑ የተቀዳውን ክቡር ደሙን እና መና ምሳሌው የነበረለትን አማናዊውን የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋውን ለመብላታችን አመልካች (ፋና ወጊ) ነበር።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከጥንቱ ከታሪኩ ጠቅሶ ያስተማረው ለዚህ ነበር። በጌታችን ዘመን የነበሩት አይሁድ ሥጋዊነትና ፍቅረ መብልዕ አጥቅቷቸው አባቶቻችን እንደ በሉት ያለ መና አብላን ባሉት ጊዜ ያን መና የበሉት ከሞት እንዳልዳኑና ምድራዊቷን ርስት ከነዓንን እንኳ መርገጥ ሳይችሉ መቅረታቸውን ካስታወሳቸው በኋላ፣ አሁን አማናዊ መብልዕ የሆነውን የእርሱን ሥጋውን የሚበላውንና ደሙን የሚጠጣውን ግን ምድራዊ ያይደለ ሰማያዊ ርስት እንደሚያወርሰውና ከእርሱ ጋር አንድ እንደሚያደርገው ነገራቸው። ይህን ጸጋ ለማግኘት የሚያስችለውን የሥጋውንና የደሙን ምሥጢር በተመለከተም በሰፊው አስተማራቸው።

ትምህርቱን እንዲህ በሚገባ አስቀድሞ ካስተማራቸው በኋላ በተግባር ፈጽሞ የሚያሳይበት ጊዜ ሲደርስ ደግሞ በምሴተ ሐሙስ ለደቀ መዛሙርቱ ምሥጢሩን አሳያቸው። እንዲህም አላቸው፡-

> ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፡- እንካችሁ፣ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው፤ እንዲህም አለ፡- ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው። ማቴ. 26፥26-28

ይህ ጌታችን በምሥጢረ ቁርባን ላይ ያስተማረው ትምህርቱም የሚከተሉትን ዋና ዋና እውነታዎች ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል፡-

1. ከጸሎተ ፈትቶ በፊት ኅብስትና ወይን ብቻ የነበረው እርሱ ሲያከብረው ግን አማናዊ (እውነተኛ) ሥጋውና ደሙ ይሆናል። አስቀድሞ በትምህርቱ "ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው። ሥጋዬ እውነተኛ መብል፣ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና" ብሎ እንዳስተማረው በኋላም በተግባር ምሥጢሩን ፈጽሞ ሲያሳየን ያንኑ ቃል ትምህርቱን "ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ፣ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፡- እንካችሁ፣ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው። ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው፤ እንዲህም አለ፡- ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" በማለት አጸናው።

2. ስለሆነም በምሥጢረ ቁርባን የምንቀበለው ተራ ኅብስትና ተራ ወይን ሳይሆን እውነተኛ የሆነ የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ነው፡፡ "ይህ ሥጋዬ ነው" አለ እንጂ "ሥጋዬን የሚወክል ነው" ወይም "የሥጋዬ ምሳሌ ነው" አላለም፡፡ እንዲሁም "ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" አለ እንጂ "ይህ የደሜ ወካይ ነው"፣ ወይም "የደሜ አመልካች ነው" አላለም፡፡ መድኃኒታችን ኅብስቱን አክብሮና ለውጦ የራሱ ሥጋ ማድረጉን፣ ወይኑንም እንዲሁ አክብሮና ለውጦ የራሱ ደም ማድረጉን "ይህ ሥጋዬ ነው፣ ይህ ደሜ ነው" ከማለት በላይ ሌላ በምን ይገልጸው ዘንድ ይገባ ነበር ይሆን? አማናዊ የራሱ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ስለ መሆኑ ከዚህ በላይ መግለጫ ቋንቋ የለም! በቃና ዘገሊላ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅነት የለወጠው እርሱ አሁን ደግሞ ወይኑንና ኅብስቱን ለውጦ እውነተኛ ሥጋውና ደሙ ያደርገዋል፡፡

3. ምሥጢረ ቁርባን ከሞት የምንድንበትና የዘላለም ሕይወትን የምናገኝበት ድንቅ ምሥጢር ነው፡፡ ይህንንም ጌታችን "አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ሞቱም፤ ሰው ከእርሱ ብልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው። ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው። . . . እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ" በማለት በማያሻማና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ተናግሯል።

4. "ሥጋዬ" እና "ደሜ" ያለው "እምነትን" ሳይሆን አማናዊ የሆነውን ሥጋውንና ደሙን ነው፡፡

ተሐድሶዎች ስለዚህ ጉዳይ የሚያስተምሩት ከላይ የጠቀስነው ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እውነተኛ የሕይወት ምግብ መሆኑን ክደው "እምነት" ብቻ ነው ይላሉ፤ እንዲህ ይላሉ፦

◉ "ክርስቶስ ሰው የዘላለም ሕይወት የሚያገኘው በእርሱ በማመን እንደሆነ በዚህ አንቀጽ በማስተማሩ ነው፡፡ ደግሞም "የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፤ በእኔ የሚያምንም ሁሉ ጊዜ ከቶ አይጠማም" በማለቱ <u>እምነትን በመብላትና በመጠጣት መስለው፡፡ ይህ አንቀጽ ቅዱስ ቁርባንን ያመለክታል የሚሉ ወገኖች ስሕተት፣ ክርስቶስ በምሳሌ አገላለጥ መናገሩን እንጂ ቃል በቃል አለማስተማሩን ያለመረዳታቸው ነው፡፡</u>"

ነገር ግን ይህ የእነርሱ አረዳድና አተረጓጎም ከጌታችን ትምህርት ጋር አንዳችም የማይገናኝ የራሳቸው ፈጠራ ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም እምነት አንድ ነገር ነው፣ ቅዱስ ቁርባን ደግሞ ሌላ ነገር ነው፡፡ እያንዳንዳቸው የየራሳቸው አግባብ አላቸው እንጂ የሚጣፋፉ ወይም አንዱ በአንዱ የሚጠቀለል አይደሉም፡፡ ጌታችን ጥንት ለእሥራኤላውያን ከሰማይ ስለ ወረደው ኅብስት እንሥቶ እውነተኛና ሰማያዊ ኅብስት ስለ ሆነው ስለ ራሱ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ሲያስተምራቸው አይሁድ ነገሩ አማናዊ ስለ ሆነ የሚበላና የሚጠጣ ነገር መሆኑን ስለ ተረዱ ነበር "አይሁድ ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ ስላለ ስለ እርሱ አንጐራጐሩ" የተባለው፡፡ አይሁድ ጥንት አባቶቻቸው የበሉት መና "እምነት" ሳይሆን እግዚአብሔር በኪነ ጥበቡ በደመና አጓጓዥነት እያመጣ በውርጭ ገበታነት (ሳህንነት) እያነጠፈ መልኩ እንደ በረድ ነጭ የሆነ መጠኑ ድምብላል ያክል መና እያወረደላቸው አርባ ዓመት በተግባር እንደ በሉ ስለሚያውቁ ነበር፡፡

ያ አባቶቻቸው ሲበሉት የነበረው መናም ከነዓን ሲገቡ ስለ ቆመ የተደረገው ቸርነት ሲነገራቸው ከቀጣዩ ትውልድ ተረትና ሐሰት ነው ብሎ የሚያስብ ደካማ ሕሊና እንዳይኖር ሕያው ማስረጃ ይሆን ዘንድ አንድ መስፈሪያ ጎሞር ሙሉ መና በመሶበ ወርቅ ተደርጎ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ

እንዲቀመጥና ሕያው ማስረጃ እንዲሆን እግዚአብሔር አዝዞ ነበር፡፡ ጌታችን በዚያ እውነተኛ የሚበላ በነበረው፣ እሥራኤላውያን ጥቂት ቀናት ወይም ወራት ብቻ ሳይሆን 40 ዓመታት በተከተታይ ሲበሉት በኖሩት በመናው አንጻር ምሥጢረ ቁርባንን ያስተማረው ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ "እምነት" ሳይሆን የሚበላና የሚጠጣ ስለሆነ ነበር፡፡

እንደዚሁም አይሁድ "ይህ ሰው ሥጋውን እንበላ ዘንድ እንዴት ይሰጠናል?" ባሉ ጊዜ ጌታችን "እኔ የተናገርሁት ስለሚበላና ስለሚጠጣ ነገር ሳይሆን ስለ እምነት ነው" አላላቸውም፡፡ እንዲህ አላቸው እንጂ፡-

> ኢየሱስ መለሰ፣ አላቸውም፦ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ፣ ሞቱም፤ ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው። ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።

አይሁድ ጌታችን እየነገራቸው ያለው ስለ "ማመን (እምነት)" ሳይሆን ስለ ሥጋውና ደሙ መሆኑን ስለ ተረዱ "እንግዲህ አይሁድ፦ ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል? ብለው እርስ በርሳቸው ተከራከሩ" በማለት መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይነግረናል፡፡ ጌታችን እየተናገራቸው የነበረው ስለ እምነት ቢሆን ኖሮ "ሥጋዬን ብሉ ደሜን ጠጡ" ሲላቸው "ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል?" እስከ ማለት ደርሰው ያን ያህል ምን ያስጨንቃቸው ነበር? ጌታችንም ይህን አረዳዳቸውን ያስተካክለው ነበር፡፡ ነገር ግን ጌታችን አሁንም ትምህርቱን በመቀጠል እንዲህ አላቸው፡-

> እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ። ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።

የፕሮቴስታንት አንጃ የሆኑት ተሐድሶዎቹ ስለ ምሥጢረ ቁርባን ያላቸው እምነትና ትምህርት ሙሉ በሙሉ ጌታችን በመጽሐፍ ቅዱስ ካስተማረው ጋር የሚቃረንና የሚጻረር ነው፡፡ እርሱ ያስተማረውን በተበላሸ አተረጓጎማቸውና አረዳዳቸው ሊያጣምሙትና ክህደት በሆነ በአዲስ ትምህርት ሊተኩት ይሞክራሉ፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በቀጥታ የሚቃረነውን ትምህርታቸውንም በትርጓሜ ለማቃናት ይሞክራሉ፡፡ ለዚሁ ነው እንዲህ ያሉት፡-

- "ብዙዎች 'የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ፣ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም፡፡ ሥጋዬን የሚበላ፣ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው' የሚለው አንቀጽ ቅዱስ ቁርባንን እንደሚያመለክት ያምናሉ፡፡ ይህ አተረጓጎም ግን ክርስቶስ ከተናገረበት ጊዜ፣ ከአድማጮቹ ሁኔታና ከሰጠው ሌላ ትምህርት ጋር <u>የሚስማማ አይመስልም</u>፡፡ . . . ይህ አንቀጽ ቅዱስ ቁርባንን ያመለክታል የሚሉ ወገኖች ስሕተት፣ ክርስቶስ በምሳሌ አገላለጥ መናገሩን እንጂ ቃል በቃል አለማስተማሩን ያለመረዳታቸው ነው፡፡ . . . <u>በአተረጓጎም ያጋጠመ ስህተት ነው፤ ያን ጊዜም እንደ ዛሬው ትምህርቱን ቃል በቃል በመውሰድ የተፈጠረ ስህተት ነው፡፡"</u> (ሙራ ቁ. 19፣ ገጽ 8)

የሚገርመው ነገር ትርጓሜ ለእነርሱ የሚመች እስከሆነ ድረስ ትክክልና አግባብ መሆኑ ነው፡፡ ለሌላው ሲሆን ግን ስህተት ይሆናል፡፡ ይህ አተረጓጎም ሐዋርያው "በእነዚያ ዘንድ ለማስተዋል የሚያስቸግር ነገር አለ፣ ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ሌሎችን መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ <u>እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ</u>" ተብሎ የተነገረባቸው "መጻሕፍትን አጣማሚዎች" ናቸው፡፡ 2 ጴጥ. 3፥16 ጌታችን በግልጽ ደግሞ ደጋግሞ በቃልና በተግባር ያስተማረንንና ሕይወት የሚሰጠውን ታላቅ ምሥጢር ከንቱ የሚያደርግ ትርጓሜ ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳስጠነቀቀን "ማጣመም" እንጂ "መተርጎም" አይደለም፡፡ ስለዚህ በግልጽ የተነገረውን የምሥጢረ ቁርባን አማናዊነት ትምህርት ለመጠምዘዝና ለማጣመም ሲሉ "ቃል በቃል መውሰድ የለብንም" በማለት የራሳቸውን ክህደት በትርጓሜ ሽፋን ለመሹዋን ይሞክራሉ፡፡

5. ጌታችን በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ ስድስት ላይ ያስተማረው ትምህርት ስለ ምሥጢረ ቁርባን ነው፡፡

ምሥጢረ ቁርባንን የሚቃወሙበት ሌላው ነጥብ ጌታችን በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ ስድስት ያለውን ትምህርት ባስተማረበት ጊዜና በጸሎተ ሐሙስ ይህን ምሥጢር በተግባር ፈጽሞ ለደቀ መዛሙርቱ ባሳየበት ጊዜ መካከል ቢያንስ የአንድ ዓመት ያህል ልዩነት በመካከላቸው ስላለ በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ ስድስት ላይ ያስተማረው ስለ ምሥጢረ ቁርባን ሊሆን አይችልም የሚል ነው፡፡ እስኪ ይህን የመቃወሚያ ነጥብ ልብ ብለን እንመልከተው፡፡ በሌሎቹ ምሥጢራት ጌታችን ያደረገው እንዴት ነበር? ትምህርቱንና ተግባሩን ሁለቱንም በአንድ ጊዜ ነበር የፈጸመው? ወይስ ተራ በተራ ነበር? በተራ ከነበረስ እንዴት?

*በምሥጢረ ጥምቀት* - ጌታችን ተግባሩን አስቀድሞ ትምህርቱን በኋላ አደረገ፡፡ *ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ለሐዋርያት መስጠትን* በተመለከተ ደግሞ ትምህርቱ ቀድሞ ተግባሩ ተከተለ፡፡ ይህም እያንዳንዱ ምክንያት ነበረው፡፡ ጥምቀት - የሁሉ ነገር መጀመሪያ ስለ ሆነና ጌታችንም ሳይጠመቅ ሥራ ስለማይጀምር በተግባር መጠመቅን አስቀድሞ ስለ ጥምቀት የሚያስተምረውን ትምህርቱን ደግሞ ወደ ኋላ ላይ አደረገው፡፡ ገዳመ ቆሮንቶስ ከመሄዱና በጾምና በጸሎት ተጋድሎን ከማሳየቱና ከአጋንንት ፈተናን ከመቀበሉ በፊት፣ ደቀ መዛሙርትን ከመሰብሰቡ በፊት፣ በቃና ዘገሊላ ተገኝቶ ተአምራትን ከማድረጉና አምላክነቱን ከመገለጡ በፊት፣ ከሁሉ አስቀድሞ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ፡፡ ይህን ያደረገውም በጥምቀት ልጅነትን ማግኘት ለመንፈሳዊ ህብታትና ተግባራት ሁሉ በርና የመጀመሪያ መግቢያ መሆኑን በተግባር ሊያስተምረን ስለ ወደደ ነበር፡፡ ለሐዋርያት የጸጋ መንፈስ ቅዱስን መስጠት በተመለከተ ደግሞ ይህን ጸጋ የሚሰጣቸው የዚህ ዓለም የማዳን ተግባሩን ፈጽሞ ከሄደ በኋላ ስለሆነ ትምህርቱን አስቀድሞ ካስተማራቸውና ተስፋውን ከሰጣቸው በኋላ ጸጋውን መስጠቱን ደግሞ በኋላ (ባረገ በአሥረኛው በተነሣ በአምሳኛው ቀን) አደረገ፡፡

ምሥጢረ ቁርባንን በተመለከተም አስቀድሞ መጀመሪያ ትምህርቱን፣ ከዚያም ደግሞ ተግባሩን ጊዜው ሲደርስ በጸሎተ ሐሙስ በተግባር አሳያቸው፡፡ አስቀድሞ ትምህርቱን ነግሯቸው ሕሊናቸው እየተዘጋጀ ከቆየ በኋላ ጊዜው ሲደርስ ደግሞ በተግባር ፈጽሞ አሳያቸው፡፡ ሞቱንና ትንሣኤውን በተመለከተም ያደረገው እንዲሁ ነው! ማለትም ትምህርቱንና ተግባሩን በአንድ ጊዜ አድርጎ አላሳያቸውም፡፡ በፈቃዱ ተላልፎ እንደሚሰጥ፣ ስለ እኛ ሲል እንደሚሞትና እንደሚነሣ አስቀድሞ ደጋግሞ አስተምሮ ከዚያ በኋላ ነበር ስለ እኛ በፈቃዱ ሞትን መቀበልንና ድል አድርጎ መነሣትን በተግባር ያደረገው፡፡ ጌታችን ስለ ሞቱና ስለ ትንሣኤው ባስተማረበት ጊዜና ይህን በተግባር በፈጸመበት ጊዜ መካከል የአንድ ዓመት የጊዜ ልዩነት ስላለና ትምህርቱና ድርጊቱ በአንድ ጊዜ ስላልተፈጸመ ስለ ሞቱና ትንሣኤው ያስተማረውና በኋላ ሞቶ የተነሣው አንድ እርሱ አይደለም አያሰኝም፡፡ ፈጽሞ!

ትምህርቱም ተግባሩም በአንድ ጊዜ ካልተደረገና በትምህርቱና በተግባር አፈጻጸሙ መካከል የጊዜ ልዩነት ካለ ትምህርቱና በተግባር የተደረገው ነገር የተለያዩ ናቸው ማለት እንዴት ይቻላል? ጸጋ መንፈስ ቅዱስን መስጠቱን፣ ሞቱንና ትንሣኤውን በተመለከተ ትምህርቱን አስቀድሞ ተግባሩን እንዳስከተለ ሁሉ በምሥጢረ ቁርባንም ያደረገው እንዲሁ ነው፡፡ መጀመሪያ ደጋግሞ ደጋግሞ ካስተማራቸው በኋላ መሥዋዕተ ኦሪት የሚያልፍበትና መሥዋዕተ ወንጌል የሚተካበት ትክክለኛው ጊዜ ሲደርስ ደግሞ በተግባር አሳያቸው፡፡ ስለሆነም ትምህርቱ የተሰጠበት ጊዜና በተግባር የተፈጸመበት ጊዜ የተለያየ ነውና በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ስድስት ላይ የተነገረው ስለ ምሥጢረ ቁርባን የተነገረ አይደለም ማለት ተበድሮ ክህደት ካልሆነ በቀር ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም፡፡

በትምህርቱና በተግባር አፈጻጸሙ መካከል የአንድ ዓመት ልዩነት አለ በማለታቸው ብቻ የተነገረው ትምህርት ስለ ምሥጢረ ቁርባን አይደለም የሚሉ ከሆነ በዘመነ ብሉይ ኪዳን ከብዙ መቶና ሽህ ዓመታት በፊት ስለ ወንጌል የተነገረው ትንቢትና ተምሳሌት የበለጠ ብዙ የዘመን ርቀት ስላለው ስለ ወንጌል የተነገረ አይደለም ይሉ ይሆን? ለምሳሌም "ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፣ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች" የሚለው ትንቢት በተነገረበት ጊዜና ይህ በተግባር ተፈጽሞ በታየበት ጊዜ መካከል የሰባት መቶ ዓመታት ያህል ልዩነት አለ፡፡ ኢሳ. 7፡14 ፤ ማቴ. 1፡22-23 የአንድ ዓመት ልዩነት እንዲህ የሚያስከዳቸው ከሆነ ከሰባት መቶ ዓመታት ልዩነት በኋላ የሆነውን የአማኑኤልን ከእመቤታችን በድንግልና መወለድ እንዴት አድርገው መቀበል ይችላሉ? ተሐድሶዎች ሆይ፣ ኢሳይያስ ከሰባት መቶ ዓመታት በፊት የተናገረውን የጌታችንን ከድንግል ማርያም መወለድ ከዘመናት በኋላ ጊዜው ደርሶ መፈጸሙን ታምናላችሁን? ይህን የማታምኑ ከሆነ ከክርስትና ወገን ምንም ድርሻ የላችሁምና ሚናችሁን ለዩ፡፡ የበግ ለምድ ለብሳችሁ በጎችን ለመንጠቅ አታድቡ፡፡

በመካከሉ የሰባት መቶ ዓመት ልዩነት ያለውን ከተቀበላችሁ ደግሞ በትምህርቱ መነገርና በተግባር ተፈጽሞ በመታየቱ መካከል የአንድ ዓመት የጊዜ ልዩነት (ያውም በእናንተ ስሌት ነው) ያለውን ምሥጢረ ቁርባንን መቀበል ግድ ይላችኋል፡፡ በግልጽ የተነገረውን ምሥጢር ለመካድ ሰበብ ፍለጋ ለምን ትደክማላችሁ? በእውነት ነገራችሁንና ሁኔታችሁን ሁሉ በትክክል ሲመረምሩት ዋናዎቹ የክህደት ፋና ወጊዎችና ፍታውራሪዎች ናችሁ፡፡

6. ተሐድሶዎች "ከሆነ ጊዜ ጀምሮ (ማለትም ምሥጢረ ቁርባን በጌታችን ከተመሠረተ ጀምሮ) እንደዚያ ሆኖ (አማናዊ ሥጋውና ደሙ ሆኖ) አያውቅም" ያሉት ፍጹም ስሁተት ነው፡፡ በመጀመሪያ እንዲያ ሆኖ ማወቅ አለማወቁን እነርሱ በምን አረጋገጡ? "ሆኖ አያውቅም" ብለው ተናገሩ እንጂ ለምን ሆኖ እንደማያውቅ ግን ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ እንዲህ ያለ የክህደት ድፍረት ይገርማል! በወንጌል ራሱ ባለቤቱ የተናገረውን ስለማያምኑ፣ በአበው ትምህርትም የተነገረውን ስለማይቀበሉ፣ በተለያዩ ቅዱሳን ዜና ሕይወት የተፈጸመውንም ስለማያነቡና ስለማይሰሙ ነው እንጂ ይህ ምሥጢር አማናዊ እንደሆነ ከወንጌል ጀምሮ በእነዚህ ሁሉ የተነገረ እውነት ነው፡፡ በተለያዩ የቅዱሳን ሕይወትም እንዴት እንደሚለወጥ አይገለጥላቸውም እንጂ ከተለወጠ በኋላ በጻሕሉ ላይ በአምሳለ ሕፃን፣ በአምሳለ በግዕ ንጹሕ ሆኖ ካህኑ "ህበነ ንኅበር በዘኢአከ መንፈስ ቅዱስ" እያለ ሲፈትት እጁ በደም እየታለለ የታያቸው አሉ፡፡

ለምሳሌም የእስክንድርያ ፓትርያርክ የነበረው ቅዱስ አባ ማቴዎስ ቅዳሴ በሚቀድስበት ጊዜ ጌታችን በመሠዊያው ላይ ይታየው እንደ ነበር የተጻፈውን እናመልከት፡-

> . . . በአንዲት ዕለትም በቁርባን ቅዳሴ ላይ ሲያገለግል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመሠዊያው ላይ ተቀምጦ አየው፡፡ በታናሽ ሕፃን አምሳል በጻሕል ውስጥ ተኝቶ ነበር፡፡ ኅብስቱንም በሚፈትትበት ጊዜ እጆቹን ዘርግቶ ከታላቅ ልቅሶ ጋር ፈጽሞ እያደነቀ በመፍራትም ለረጂም ጊዜ ይቆማል፣ ይህንም ራእይ ለማንም አይናገርም፡፡
>
> መምህሩም ለረጂም ሰዓት ሲቆም ባየ ጊዜ ያደንቅ ነበር፡፡ ይህንንም ይገልጽለት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፡፡ በአንዲትም ዕለት አባ ማቴዎስ እንደ ልማዱ ሊቀድስ ገባ፡፡ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን በሕፃን አምሳል በጻሕሉ ውስጥ ተኝቶ ኅብስትንም መስሎ በአባ ማቴዎስ እጅ ሲቆረስ ለመምህሩ ለአበምኔቱ ታየው፡፡ አበምኔቱም አደነቀ፣ ለእኛ ለሰው ልጆች ይህን ታላቅ ጸጋ የሰጠኸን አቤቱ ለአንተ ምስጋና ይገባል አለ፡፡ . . ."
>
> (ስንክሳር፣ ጥር 5)

ከዜና አበው ደግሞ አንድ እንጨምር፦

አባ ዳንኤል አባ አርሳንዮስ ሕይወቱ ደገኛና መንፈሳዊ የነበረ፣ ሆኖም ግን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የሌለውና እምነቱ ቀላል ስለ ነበረ አንድ በአስቄጥስ የነበረ ገዳማዊ እንደ ነበር ነገረን አለ። ይህ ገዳማዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ያልነበረው ከመሆኑ የተነሣም ተታለለና «በቁርባን ጊዜ የምንቀበለው ቅዱስ ሥጋው የክርስቶስ ሥጋ ሳይሆን ምልክት (ምሳሌ) ነው» ይል ጀመር። ሁለት አረጋውያን ይህ ሰው እንዲህ ማለቱን ሲሰሙ በአኗኗሩ የታወቀና ደገኛ ሕይወትን በመምራት ላይ እንደ ነበር ስለሚያውቁ ይህን ያለው ከክፋት ሳይሆን ካለማወቅ የተነሣ እንደ ሆነ ተገነዘቡ።

ስለሆነም እርሱን ፍለጋ መጡና «አባ፣ የምንቀበለው የክርስቶስ ሥጋ ሳይሆን ምሳሌ ነው የሚል ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ተቃራኒ የሆነ ነገር ሲነገር ሰማን» አሉት። እርሱም «እንዲህ ያልኩት እኔ ነኝ» አላቸው። አረጋውያኑም «አባ፣ እንዲት የሆነችው ዓለም አቀፋዊት ቤተ ክርስቲያን ያስተማረችንን እምነት እንጂ እንዲህ ያለ የተሳሳተ አስተሳሰብ አይኑርህ። እኛ ግን እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን ከመሬት አፈር ወስዶ በአርአያው እንደ ፈጠረው፣ ሆኖም ግን እንደዚያ ሆኖ ባለመታየቱ ምክንያት ማንም የእግዚአብሔር አርአያነቱን እንደማይቃወም ሁሉ በአርአያ ኅብስት የምንቀበለው ፍጹም የሆነ የክርስቶስ ሥጋ መሆኑን እናምናለን፤ ክርስቶስ ኅብስቱን በጸሎት አክብሮ ከለወጠው በኋላ «ይህ ሥጋዬ ነው» ብሏልና» አሉት።

ያ አረጋዊም «እኔ ይህን ነገር በዓይኔ ማየት ካልቻልኩ በስተቀር ሙሉ በሙሉ አምኖ ለመቀበል ይከብደኛል» አላቸው። እነርሱም «ስለዚህ ምስጢር ጉዳይ ይህን ሳምንት በሙሉ ወደ እግዚአብሔር እንጸልይ፣ እግዚአብሔር እንደሚገልጥልን እናምናለን» አሉት። እርሱም ይህን ነገር በደስታ ተቀበለና እንዲህ እያለ ይጸልይ ጀመር፦ «ጌታ ሆይ፣ ይህን ነገር ያመንኩት በክፋትና በተንኮል እንዳልሆነ አንተ ታውቃለህ፣ ስለሆነም ባለማወቁ ምክንያት እንዳልስትና እንዳልጠፋ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ይህን ምሥጢር ግለጥልኝ።» እነዚያኞቹ አረጋውያንም ወደየ በኣታቸው ተመልሰው «ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ያምን ዘንድና የድካሙን ዋጋ እንዳያጣ ይህን ምስጢር ለዚህ አባት ግለጥለት» እያሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልዩ ሰነበቱ።

እግዚአብሔር የሁላቸውንም ጸሎት ሰማቸው። በሳምንቱ መጨረሻ ላይ እሑድ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጡና ያን አረጋዊ በመካከላቸው አድርገው ሦስቱም በአንድ ላይ ተቀመጡ። በጸሎተ ቅዳሴው ጊዜ ዓይናቸው ተከፈተና ኅብስቱ በጻሕሉ ላይ ሲቀመጥ ለእነዚህ ለሦስቱ ብቻ አንድ ትንሽ ሕፃን በዚያ ላይ ታያቸው። ካህኑ ኅብስቱን ለመፈተት እጁን ሲያነሣ ሰይፍ የያዘ መልአክ ከሰማይ ወርዶ የሕፃኑን ደም በጽዋው ውስጥ አፈሰሰው። ካህኑ ኅብስቱን ሲፈትትም መልአኩ ሕፃኑን ቆራረጠው። ይቀበሉ ዘንድ ወደዚህ ቅዱስ ምስጢር በቀረቡ ጊዜም ያ ሽማግሌ ብቻ ደም የታለለ ሥጋ ተቀበለ። ይህን ሲያይ እጅግ ፈራና «ጌታ ሆይ፣ ይህ ኅብስት የአንተ ሥጋ፣ ይህ በጽዋ ያለውም የአንተ ደም እንደ ሆነ አምናለሁ» ብሎ ጮኸ። ወዲያውኑም እንደ ምሥጢሩ አፈጻጸም የተቀበለው በደም የታለለ ሥጋ ኅብስት ሆነ፤ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ተቀበለ። እነዚያ ሁለቱ አረጋውያንም "እግዚአብሔር የሰውን ተፈጥሮ ያውቃል፣ ሰው በዓይኑ በቀጥታ በሥጋና በደም መልክ ሆኖ ቢያየው ለመቀበል እንደማይችል ስለሚያውቅ ነው በእምነት ለሚቀበሉት ሥጋውን በአርአያ ኅብስት፣ ደሙን በአርአያ ወይን እንዲሆን ያደረገው" አሉት። የድካሙን ዋጋ እንዳያጣ አድርጎታልና ስለዚህ አረጋዊም ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረቡ። ሦስቱም እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ወደየ በኣታቸው በደስታ ተመለሱ።

በመጽሐፈ መነኮሳት አረጋዊ መንፈሳዊ ላይም እንዲሁ ቅዳሴ ሲቀድስ አማናዊ መሥዋዕት ሆኖ እንደ ተገለጠለት ይናገራል፡፡ ከተለወጠ በኋላ ለተለያዩ አባቶቻችን እንደ ታያቸውና እነርሱም በእንክሮ እንደ ተደነቁ በተለያዩ አበው ዜና ሕይወት ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ነገር ግን ተሐድሶዎች ለራሳቸው ክህደት ራሳቸውን ምስክር አድርገው በመጥቀስ "ከሆን ጀምሮ እንደዚህ ሆኖ ስለማያውቅ ነው" በሚል ድርቅና ብቻ ሐሳታቸውን እውነት አስመስለው ለማቅረብ ሞክረዋል፡፡ ይህ እንኳን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለውን ድንቅ የጌታ ትምህርት ይቅርና ተራ አመለካከትን እንኳ ለመለወጥ አንዳችም ክብደት የሌለው ባዶ ሃሳብ ነው፡፡

እንዲህ ባለው የዘለዓለማዊ ሕይወት መሠረት በሆነው አምላካዊ ምሥጢር ላይ በስሜት ሕዋሳት ብቻ በመመራት ወደ ድምዳሜ መድረስ፣ ከዚያ በላይ ደግሞ ይህን እንደ እውነታ አድርጎ መጻፍና ለሌሎች ከዚህ ሌላ እውነት የለም፣ እመኑኝ እያሉ ማስተማር በአንድ በኩል ባዶነትንና ያውቁብኛል እንኳ አለማለትን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ያንኑ የክህደት አሳባቸውንም እንኳ ለማስረዳት ምን ያህል ዓቅም ያጠራቸው መሆናቸውን በግልጽ ያሳይባቸዋል። እኛ ግን የእግዚአብሔር ቃል "በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና" በማለት ስላስተማረን የምንመራው በስሜት ሕዋሳቶቻችን ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል ነው። ስለሆነም መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚመሰክረው፣ ከሐዋርያት ጀምሮ የተነሡ ቀደምት ታላላቅ ቅዱሳን አባቶቻችንም እንደሚመሰክሩት የምሥጢረ ቁርባንን አማናዊነት እናምናለን፣ በእርሱም እንኖራለን። 2 ቆሮ. 5፡6

ተሐድሶ መናፍቃን የድፍረታቸው ብዛት ራሱ ባለቤቱ የተናገረውን ቃል ሁሉ ሽምጥጥ አድርገው በመካድ "በጸሎት ኅብስቱና ወይኑ ተለውጦ፣ በመዓዛውም በጣዕሙም በቀለሙም አማናዊውን ሥጋ ኢየሱስን ይሆናል" የሚለው ትምህርት ትክክል አይደለም" ካሉ በኋላ በመቀጠልም ለዚህ ማስረጃ ነው ብለው ያቀረቡት ደግሞ "ምክንያቱም ከሆን ጊዜ ጀምሮ እንደዚህ ሆኖ ስለማያውቅ ነው" የሚል ነው። በመጀመሪያ "በመዓዛውም በጣዕሙም በቀለሙም ይለወጣል" የሚል ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ የለም። ትምህርታችን ጥርት ያለ ነው፤ እርሱም "ውላጤ እንበለ ውላጤ" የሚል ነው።

ማለትም መልኩና ጣዕሙ ከኅብስትነት አይለወጥም፣ በኅብስትና በወይን መልክና ጣዕም የምንቀበለው ግን ጌታችን እንዳስተማረንና እኛም በእምነት እንደ ተቀበልነው "ይህ ሥጋዬ ነው፣ ይህ ደሜ ነው" እንዳለ የእርሱ አማናዊ ሥጋና ደም ነው። ሆኖም አካሄዳቸው በዚህ ተጠግተው የመሥዋዕቱን አማናዊነት ለማሳበል መሆኑ ግልጽ ነው።

እንግዲህ ሰው ይድን ዘንድ እንዲህ መሠረታዊና ቁልፍ ምሥጢር የሆነውን ምሥጢረ ቁርባንን የሚክዱት ተሐድሶዎች ትምህርታቸው ሰውን ከመዳን ወደ አለመዳን የሚወስድ የሞት መንገድ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ተመሰከረ። የእነርሱ እምነትና ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሲመዘንም ቀልሎ ተገኘ። እንዲህ ሰውን ከሚድንበት መንገድ ከቅዱስ ቁርባን፣ ከጥምቀትና ከሜሮን እያለያዩ፣ እነዚህን ጌታችን የሰጠንን የመዳን ጸጋ የምናገኝባቸውን ምሥጢራት ከሐዋርያት ባገኘችው መጽሐፍ ቅዱሳዊና ትውፊታዊ መንገድ እየፈጸመች ልጆቿን በመዳን ጎዳና እንዲጓዙ የምታደርገውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እየወቀሱና እየከሰሱ ለማሳየት የሚያደርጉት ጥረት ውጤቱ ሰዎችን ከዘላለማዊ የሕይወት ጎዳና አውጥቶ ሕይወት በማይገኝበት የሞት ጎዳና እንዲባዝኑና እንዲጠፉ ከማድረግ ውጭ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? መሠረታዊ የሆነውን፣ አካላዊ ቃል ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሰው የሆነበትን፣ መራራ ሞትን የተቀበለበትን፣ በመስቀል መንገድ ያለፈበትን የመዳናችንን ነገር ከንቱ ካደረጉና ከካዱ በኋላ ከዚህ ውጭ የሚሉት እጅግ መልካም የሆነ ነገር ቢኖራቸው እንኳ (እንደ አለመታደል ሆኖ የላቸውም እንጂ) ምንም ረብና ጥቅም ሊኖረው አይችልም። አንድን ቤት መሠረቱን እያፈረሱ ግድግዳውን ወይም ጣራውን ቀለም እንደ መቀባት ወይም ሰውን ገድሎ ስለ አቀባበሩና ስለ አለቃቀሱ እንደ መጨነቅ ዓይነት ነገር ነው።

ስለሆነም ምሥጢረ ቁርባን ስለ ሁላችን ኃጢአት በቀራንዮ የተሠዋውን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አማናዊ ቅዱስ ሥጋውን የምንበላበትና ክቡር ደሙን የምንጠጣበት ድንቅና ግሩም ምሥጢር ነው። ይህን የሰጠንም እርሱን በልተንና ጠጥተን ከእርሱ ጋር እንድንዋሐድና ከእርሱ ጋር እንድንኖር፣ እንዲሁም ለሁላችንም የኃጢአት ይቅርታ እንዲሆነን ነው። የኃጢአት ሥርየት ለማግኘት መክፈል የሚኖርበት ዕዳ አለ። ሰው ኃጢፋው ጥፋት ራሱ መክፈል ያልቻለውን የኃጢአት ዕዳ ጌታችን በተዋሐደው ሥጋ ራሱ ዕዳችንን በመክፈል ነፃ አውጣን፣ ሥርየትን ሰጠን።

ይህን ሥርየት ለማግኘት ስለ እኛ ኃጢአት የተሠዋውን መሥዋዕት መብላትና መጠጣት ይገባል፡፡ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ *"ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያነጽሐነ እምኵሉ ኃጣውኢነ - የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል"* ያለው ለዚህ ነው፡፡ 1 ዮሐ. 1፥7 በቀራንዮ የተሠዋውና በጸሎተ ቅዳሴ በየዕለቱ የምንቀበለው ያው አንዱ ክርስቶስ ነው፡፡ በመሆኑም በየጊዜው ለሚሠራው ኃጢአት ሁሉ ሌላ መሥዋዕት ሳያስፈልግ ያው በዕለተ ዓርብ ራሱን ለኃጢአት ቤዛ አድርጎ ያቀረበውን መሥዋዕት - ክርስቶስን - በመቀበል የኃጢአታችንን ሥርየት የምናገኘው በዚህ መንገድ ብቻ ነው፡፡ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን አምኖ የማይቀበል ሰው ገና በኃጢአቱ ይኖራል፡፡

### 3.7.2.3.3 ምሥጢረ ቁርባን በአበው ትምህርት

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ የነበሩና የተነሡ ታላላቆቹ ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን ስለ ምሥጢረ ቁርባን አማናዊነትና ሕይወትን ሰጪነት፣ ሥጋው የክርስቶስ አማናዊ ሥጋ፣ ደሙም አማናዊ ደም ስለ መሆኑ ካስተማሩት ትምህርት መካከል የተወሰነውን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

- "... [መናፍቃን] ከቅዱስ ቁርባንና ከጸሎት ይርቃሉ፤ ይህን የሚያደርጉበት ምክንያትም በምሥጢረ ቁርባን የሚቀርበው ኅብስት ስለ እኛ ኃጢአት መከራ የተቀበለውና ከሞት የተነሣው የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ መሆኑን ስለማያምኑ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ታላቅ የእግዚአብሔር ጸጋ ላይ [በቅዱስ ቁርባን ላይ] የማይገባ ነገር የሚናገሩ ሰዎች እነርሱ በክርክራቸው መካከል ሞትን በራሳቸው ላይ ያመጣሉ (እየተከራከሩ ሳሉ ይሞታሉ)፡፡ ነገር ግን በአክብሮት ቢመለከቱትና ቢያምኑበት ይሻላቸው ነበር፡፡ ስለዚህ እንደዚህ ካሉት ሰዎች ትርቁ ዘንድ የተገባ ነው፤ ከእነርሱ ጋርም በግልም ሆነ በማኅበር ግንኙነት አይኑራችሁ፡፡" (ቅዱስ አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ፣ መልእክት ወደ ስምርኔስ ክርስቲያኖች፣ ምዕራፍ 7)

- "ጌታችን 'ሥጋዬን የሚበላ ቢኖር እርሱ ለዘላለም ይኖራል' ባለ ጊዜ በአንድ በኩል ቅዱስ ሥጋውን የሚበሉና ክቡር ደሙን የሚጠጡ ሰዎች ሕያዋን መሆናቸው ግልጽ እንደ ሆነ ሁሉ በሌላ በኩል ደግሞ ማንም ሰው ከቅዱስ ቁርባን በመራቁና በመለየቱ ከክርስቶስ ሥጋና ደም የራቀ በመሆኑ ከድኅነት እንዳይርቅ ልንፈራና ልንጸልይ ይገባናል፡፡ እርሱው ራሱ 'እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም' በማለት በማስጠንቀቂያ በአጽንኦት ተናግሯልና፡፡" (ቅ. ቆጵርያኖስ፣ ትምህርት በእንተ ጸሎተ እግዚእነ፣ ክፍል 4)

- "ታላቁ ጸሎትና እስተብቁዖታት ወደ እግዚአብሔር ከተደረገ በኋላ ቃል በኅብስቱና በጽዋው ላይ ይመጣል፣ እነርሱም [በጻሕሉ ላይ ያለው ኅብስትና በጽዋው ውስጥ ያለው ወይን] የእርሱን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ይሆናሉ፡፡" (ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ)

- "በምሥጢረ ቁርባን የሚቀርቡት ኅብስቱና ወይኑ ቅዱስና ንጹና የሆነውን ስመ ሥላሴን ከመጥራታችንና ከመማጸናችን በፊት ተራ ኅብስትና ወይን እንደ ነበሩ ሁሉ፣ ከጸሎተ ቅዳሴው በኋላ ግን ኅብስቱ የክርስቶስ ሥጋ ይሆናል፣ ወይኑም የክርስቶስ ደም ይሆናል፡፡ (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ በእንተ ምሥጢራት፣ ትምህርት 19፣ ቁ. 7)

- "ይህ መብልዕ በእኛ ዘንድ ዩካሪስቲያ (Eὐχαριστία - the Eucharist) ይባላል፡፡ ከዚህ ምሥጢርም የምናስተምረውን ትምህርት እውነትነት የሚያምን፣ ሥርየተ ኃጢአትና ዳግም ልደት የሚገኝበትን ምሥጢረ ጥምቀትን የፈጸመ ሰው ካልሆነ በቀር፣ እንዲሁም ክርስቶስ እንዳኖር ዘንድ እንዳስተማረው ከሚኖር ሰው በስተቀር ማንም ይሳተፍ ዘንድ አይፈቀድለትም፡፡ ይህን

የምንቀበለውም እንደ ተራ ኅብስትና እንደ ተራ መጠጥ አድርገን አይደለም፤ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ሲል ሰው ከመሆኑ የተነሣ ሥጋና ደም ያለው እንደ ሆነ ሁሉ፣ የእኛ ደማችንና ሰውነታችን የሚቀደስበት እርሱ፣ በቃሉ መቀደስ የሚከብረውና የሚቀደሰው ኅብስትና ወይን ሰው የሆነው የአካላዊ ቃል የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውና ደሙ ነው እንጂ፡፡ ሐዋርያት በጻፏቸው በወንጌላት እነርሱ ከጌታ የተቀበሉትን ለእኛ አውርሰውናል፣ አስተላልፈውልናል፤ እንዲህ ሲሉ፡- 'እንጀራንም አንሥቶ አመሰገነ፣ ቆርሶም ሰጣቸውና ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት' አለ። እንዲሁም 'ከእራት በኋላ ጽዋውን አንሥቶ እንዲህ አለ፦ ይህ ጽዋ ስለ እናንተ የሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው' አለ፤ ለእነርሱም ብቻ ሰጣቸው፡፡ ሉቃ. 22፥19-20" (ሰማዕቱ ቅዱስ ዮስጢኖስ፣ የመጀመሪያው መጽሐፍ፣ ምዕራፍ 66)

❖ "መናፍቃን 'የጌታችንን የከበረ ሥጋውንና ደሙን የበላውና የጠጣው የእኛ ሰውነት ወደ መፍረስና መበስበስ ይሄዳል፣ ሕይወትንም ገንዘብ አያደርግም' ለማለት እንዴት ይችላሉ? ስለዚህ ወይ አስተምህሯቸውን ያስተካክሉ (ይለውጡ)፣ አለዚያ ደግሞ ላያምኑበት ይህን ምሥጢር (ምሥጢረ ቁርባንን) እንፈጽማለን እያሉ ከማስመሰል ያቁሙ፡፡" (ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ በእንተ መናፍቃን፣ መጽሐፍ 4፣ ምዕራፍ 18፣ ቁ. 5)

❖ ". . . በራሱ ደም አዳነን፣ ሐዋርያው 'በደሙ መዳንን፣ ሥርየተ ኃጢአትን አግኝተናል' እንዳለ፡፡ ቆላ. 1፥14 የእርሱ የአካሉ ብልቶች እንደ መሆናችን የእርሱን ምግብና የምናገኘው በሥነ ፍጥረት ነው፤ . . . ከሥነ ፍጥረት ተዘጋጅቶ የሚቀርበውንና በጽዋው ውስጥ ያለውን 'የራሴ ደም ነው' ብሎታል፤ ኅብስቱንም (እርሱም ከሥነ ፍጥረት የሚገኝ ነው) 'የራሴ ሥጋ ነው' ብሏል፡፡ በዚህ በሥጋውና በደሙም የእኛ ሥጋና ደም ይበለጽጋል፣ ያድጋል፣ ከእርሱም ጋር ይዋሐዳል፡፡" (ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ በእንተ መናፍቃን፣ መጽሐፍ 5፣ ምዕራፍ 18፣ ቁ. 2)

❖ "ከወይን ግንድ የተቆረጠና በመሬት ውስጥ የተተከለ ቁራጭ በጊዜው ጊዜ ለፍሬ እንደሚደርስ ሁሉ፣ ወይም በመሬት ውስጥ የተዘራና በአፈር ውስጥ የተቀበረ የስንዴ ቅንጣት ከፈረሰ በኋላ ሁሉን በያዘ በእግዚአብሔር መንፈስ እንደገና ብዙ ፍሬ ያለው ሆኖ እንደሚነሣ ሁሉ፣ ከዚያም በእግዚአብሔር ጥበብ ለሰዎች ጥቅም እንደሚያገለግል ሁሉ፤ *ከዚያም መሥዋዕት ሆኖ ሲቀርብ በእግዚአብሔር ቃል (በጸሎተ አኮቴት) አማካይነት የክርስቶስ ሥጋና ደም እንደሚሆን ሁሉ*፤ የእኛም ሰውነት ይህን የክርስቶስን ሥጋና ደም ከመመገቡ የተነሣ በመሬት ውስጥ ተቀብሮ (ተቀምጦ) ከቆየ በኋላና መፍረስና መበስበስ ካገኘው በኋላ እግዚአብሔር እርሱ ባወቀ ለትንሣኤው በቀጠረለት ጊዜ ይነሣል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል መዋቲ ለሆነው ለዚህ ሰውነታችን ትንሣኤን (መነሣትን) እና ኢመዋቲነትን ይሰጠዋል፡፡ . . . ይህም የእግዚአብሔር ኃይል በድካም ስለሚገለጥ፣ እንዲሁም በባሕርያችን ከራሳችን ሕይወት ያለን መስሎ እንዳይሰማንና ሕሊናችን ውስታ ቢስ እንዳይሆን፣ ከዚህም የተነሣ በእግዚአብሔር ላይ ራሳችንን ከፍ ከፍ እንዳናደርግ ነው፡፡" (ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ በእንተ መናፍቃን፣ መጽሐፍ 5፣ ምዕራፍ 2፡2-3)

❖ ". . . እጅግ የተከበርህ ወዳጄ ሆይ፣ አካላዊ የእግዚአብሔር ቃልን በጸሎትህ ስትጠራውና ያለ ሥለት በሆነ ሁኔታ የጌታችንን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን በምትፈትትበት ጊዜ ስለ እኔ መጸለይንና መማለድን አታቋርጥ፡፡"[75] (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ፣ መልእክት ኀበ አምፊሎቅዮስ ጳጳስ ዘኢቆንዮን፣ ቁ. 171)

[75] (. . . But, most reverend friend, cease not both to pray and to plead for me when you draw down the Word by your word, when with a bloodless cutting you sever the Body and Blood of the Lord, using your voice for the glaive.)

ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም ስለ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ካስተማረው ሰፊና ጥልቅ ትምህርት መካከል ደግሞ የሚከተለውን እንመልከት፡-

- "ቅዱስ ጳውሎስ ያስተማረው ትምህርት ብቻ እንኳ እነዚያን እምላካውያት ምሥጢራት በተመለከተ ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች መሆን እንድትችሉ ለማድረግ በራሱ በቂ ነው፡፡ ግልጽ በሆነ ሁኔታ እንዲህ ሲል ሰምታችሁታልና፡- 'ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተላልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፥ ቆርሶም እንካችሁ ብሉ፥ ይህ ሥጋዬ ነው አለ፤ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ ካመሰገነ በኋላ ይህ ደሜ ነው፥ እንካችሁ ጠጡ አላቸው።' 1 ቆሮ. 11፡24-25፤ ማቴ. 26፡26 እንግዲህ እርሱ ራሱ ባለቤቱ ኅብስቱን '*ይህ ሥጋዬ ነው*' ብሎ ከተናገረና ካወጀ ይህን ሊጠራጠር የሚችል ማን አለ? እንዲሁም እርሱው ራሱ ባለቤቱ ጌታችን በማይታበል ቃሉ '*ይህ ደሜ ነው*' ብሎ በግልጽ የተናገረውን፥ 'አይ ይህ የእርሱ ደም አይደለም' ብሎ ሊያመነታና ሊጠራጠር ማን ይችላል?

"አስቀድሞ በቃና ዘገሊላ ውኃውን የደም መሰል ወደ ሆነው ወደ ወይን ጠጅነት ለውጦት ነበር፤ ታዲያ ውኃውን ወደ ወይንነት የለወጠው ከሆነ ወይኑን ወደ ራሱ ደምነት ይለውጠዋል ቢባል የማይታመን ነገር የሚሆነው ምኑ ላይ ነው? ሰብአዊ በሆነው ሠርግ ላይ በተጠራ ጊዜ ያን አስደናቂ ነገር በተአምራት አደረገ፤ ታዲያ በምድራዊው ሠርግ እንዲያ ካደረገ በሙሽራው ሠርግ ላይ (በቤተ ክርስቲያን በሚደረገው ጸሎተ እኩቴት መሥዋዕተ ቁርባን ጊዜ) ኅብስቱንና ወይኑን ለውጦ የራሱ ሥጋና ደም አድርጎ እንደሚሰጥ ሊታመን አይገባውምን? ማቴ. 9፡15

"ስለዚህም በፍጹም እምነትና መተማመን የክርስቶስን ሥጋና ደም እንቀበል፤ በኅብስት አምሳል የምትቀበለው የእርሱን ቅዱስ ሥጋ፥ በወይን አምሳል የምትቀበለው ደግሞ የእርሱን የከበረ ደም ነውና፤ በዚህም ከክርስቶስ ከሥጋውና ከደሙ በመቀበልህ (በመሳተፍህ) ከእርሱ ጋር አንድ ሥጋና አንድ ደም ትሆን ዘንድ ነው፡፡ በዚህም ክርስቶስን እንሸከመዋለን፥ ምክንያቱም ሥጋውና ደሙ በሕዋሳቶቻችን ይሰራጫሉና፤ ቅዱስ ጴጥሮስ እንደ ተናገረው የመለኮቱ ባሕርይ ተካፋዮች የምንሆነው በዚህ ነው፡፡ 2 ጴጥ. 1፡4

". . . በብሉይ ኪዳን የገጽ ኅብስት ነበረ፥ ሆኖም ያ የብሉይ ዘመን ስለነበር ወደ ፍጻሜው መምጣት ነበረበት፡፡ በሐዲስ ኪዳን ግን ነፍስንና ሰውነትን የሚቀድስ ሰማያዊ ኅብስት አለ፥ የመድኃኒት ጽዋም አለ፡፡ ስለዚህ ኅብስቱንና ወይኑን እንዲሁ እንደሚታዩት ተራ ነገር አድርገህ አታስባቸው፥ በጌታችን ቃልና አዋጅ መሠረት የክርስቶስ ሥጋና ደም ናቸውና፡፡ ስሜትህ የሚያየውና የሚነግርህ እንደዚህ ቢሆን እንኳ እምነትህ ያጽናህ፥ ይጠብቅህ፡፡ ከጣዕሙና ከመልኩ አንጻር አትፍረድ፥ ነገር ግን በፊትህ የቀረበልህ የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መሆኑን ያለ መጠራጠር በእምነት ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ሁን፡፡ እነዚህን ነገሮች በመማርና በማስተዋል፥ በኅብስት መልክ የምታየው መልኩና ጣዕሙ እንደዚያ ቢሆንም የራሱ የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋ መሆኑን፥ በወይን አንጻር የምታየውም ጣዕሙ እንደዚያ ቢሆንም የክርስቶስ ደም መሆኑን ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ሆነህ በማመን ቅረብ፡፡ . . . ይህንም ንጹሕ በሆነ ሕሊናህ በመቀበል የጌታን ክብር እንደ መስተዋት መግለጥ ትችል ዘንድና ከክብር ወደ ክብር ትሸጋገር ዘንድ ይሁንልህ። 2 ቆሮ. 3፡18"

ትምህርት 22፥ በእንተ ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ፥ ቁ. 1-9

- "ጌታችን 'ሥጋዬን የሚበላ፥ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ' ብሏል። . . . የመድኃኒታችንን ቅዱስ ሥጋውን የሚበላና ክቡር ደሙን የሚጠጣ ሰው ራሱ ባለቤቱ እንደ ተናገረ ከእርሱ ጋር አንድ ይሆናል፤ እርሱን በሥጋውና በደሙ በመሳተፉ በክርስቶስ ውስጥ የሚገኝ ያደርገዋል፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፥ ትርጓሜ ወንጌል ዮሐንስ)

- "በምሥጢረ ቁርባን የሚቀርቡት ኅብስቱና ወይኑ ቅዱስና ገናና የሆነው ስመ ሥላሴ ከመጠራቱና በእርሱ ከመክበራቸው በፊት ተራ ኅብስትና ወይን ነበሩ፤ ከጸሎተ ቅዳሴው በኋላ ግን ኅብስቱ የክርስቶስ አካል (ሥጋ)፣ ወይኑ ደግሞ የክርስቶስ ደም ይሆናሉ፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 19፣ በእንተ ምሥጢራት 1፣ ለአዲስ ተጠማቂዎች የተሰጠ ትምህርት፣ ቁ. 7)

- "ሥጋውንና ደሙን የሚያቀርቡ ካህናት እነርሱ ራሳቸው አክብረው ለውጠው እርሱን እንደሚሰጡን በልቡናችን እናስብ፡፡ እነርሱ እንደ ተቻላቸው የአገልግሎት ሥራ ይሠራሉ እንጂ ሁሉን የሚፈጽመው ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ለበቁትም ሥጋውን የሚሰጣቸው እርሱ ነው፡፡[76]" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 32)

- "እኛነታችንን በእነዚህ መንፈሳዊ መዝሙራት በመቀደስ መሐሪውን አምላካችንን እግዚአብሔርን በፊቱ ቡተሰየመውና በቀረበው በቁርባኑ ላይ ቅዱስ መንፈሱን እንዲልክልን እንማጸነዋለን፤ ኅብስቱን የክርስቶስ ሥጋ፣ ወይኑን ደግሞ የክርስቶስ ደም ያደርገው ዘንድ፤ መንፈስ ቅዱስ የነካው ሁሉ ይቀደሳል፣ ይለወጣልምና፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 23፣ በእንተ ቅዱስ ቁርባን ወነገረ ቅዳሴ፣ ቁ. 7)

- "ዛሬ የሚያስፈልገንን የዕለት እንጀራችንን ስጠን፡፡ የሚያስፈልገን እንጀራ የተባለው ይህ ምድራዊው እንጀራ አይደለም፣ ይህ ቅዱስ ቁርባን ግን አስፈላጊያችን ነው፣ ለነፍሳችን ምግብ ይሆን ዘንድ የተዘጋጀ ነውና፡፡ ይህ ምድራዊው እንጀራ ወደ ሆድ ከገባ በኋላ ወደ ውጭ ይወጣልና፣ ቅዱስ ቁርባን ግን ለሰውነታችንና ለነፍሳችን ጥቅም ይሆን ዘንድ በመላው ሕዋሳታችን ይሰራጫል፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 23፣ በእንተ ቅዱስ ቁርባን ወነገረ ቅዳሴ፣ ቁ. 15)

- "ከዚህ በኋላ ቀዳስያኑ ከቅዱሳት ምሥጢራት ትሳተፉ ዘንድ 'ጠዐሙ ወታእምሩ ከመ ኄር እግዚአብሔር - እግዚአብሔር ቸር መሆኑን ቅመሱ፣ እወቁ' እያሉ በተቀደሰ የዜማ ድምጽ ይጋብዟችኋል፡፡ በእምነት መነጽር እየተመለከትህ በማይናወጽ እምነት ላይ ቁም እንጂ ሥጋዊ ሰውነትህ በሚነግርህ የጣዕም ስሜት ላይ አትመሥረት፣ በእርሱም አትታመን፡፡ ትቀበል ዘንድ የሚጠሩህ ተራ ኅብስትና ወይን ሳይሆን በዚያ አንጻር የክርስቶስን ሥጋና ደም ነው እንጂ፡፡ ስለዚህ ወደ ቅዱስ ቁርባን ስትቀርብ ጣቶችህ እንደ ተበታተኑ፣ ወገብህ ቀጥ እንዳለ ሆነህ አትቅረብ፤ ንጉሥን ሊቀበል እንዳለው ሰው ግራ እጅህ ለቀኝ እጅህ ማረፊያ ዙፋን እንዲሆነው አድርግ እንጂ [እጆችህን አመሳቅለህ ቅረብ]፡፡ እንዲህ ባለ ሁኔታ ተዘጋጅተህ የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋ "አሜን" ብለህ ተቀበል፡፡ ከተቀበልከውም አንዳች እንኳ እንዳይነጥብብህ አጥብቀህ ተጠንቀቅ፡፡ የሚነጥብብህ ቢኖር ልክ ከአካልህ አንዱ እንደ ጠፋብህ ያህል ነውና፡፡ እስኪ ንገረኝ፣ አንድ የሆነ ሰው የወርቅ አፈር ቢሰጥህ ከእነርሱ አንዷ ቅንጣት እንኳ እንዳትጠፋብህ አድርገህ በታላቅ ጥንቃቄ ተጠንቅቀህ አትይዘውምን? ታዲያ ከወርቅና ከከበሩ ማዕድናት ሁሉ ይልቅ እጅግ የከበረ የሆነውን የክርስቶስን ሥጋና ደም እንዳይነጥብብህ እጅግ ተጠንቅቀህ ልትቀበለው አይገባህምን?" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 23፣ በእንተ ቅዱስ ቁርባን ወነገረ ቅዳሴ፣ ቁ. 20-21)

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

- "... ወደ ሕይወቱ ሞት ለገባበትና ሕይወቱን ለመረዘበት ለሰው ባሕርይ መድኃኒቱና መፍትሔው ምን ነበር? ሞትን ድል ካደረገውና በትንሣኤው የሕይወታችን በኩር ከሆነው

[76] (ወውእቱ ዘይሚጥዎሙ ለእለ ይከውኑ ድልዋን ሎቱ)

ከኢየሱስ ክርስቶስ ሰውነት በስተቀር ሌላ ማንም ሊሆን አይችልም፡፡ ሐዋርያው ትንሽ እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካዋል እንዳለ ከእግዚአብሔር አካላዊ ቃል ጋር ከመዋሐዱና አንድ ከመሆኑ የተነሣ ኢመዋቲነትን ገንዘብ ያደረገውን የክርስቶስን ሰውነት ስንቀበልና በውስጣችን ሲሆን የእኛን መዋቲ ሰውነት ወደ እርሱ ሕያውነት ያሸጋግረዋል፣ ይለውጠዋል፡፡ ኢመዋቲና ሕያው የሆነውን የክርስቶስን አካል የሚቀበል ሰው ከዚህ ከተቀበለው ሕይወት የተነሣ ሕይወትንና ኢመዋቲነትን ገንዘብ ያደርጋል፡፡ ያ አንዱ የክርስቶስ አካል በመላው ዓለም ከጽንፍ እስከ ጽንፍ በየቦታው ያሉ ምእመናን ሁሉ ሲበሉት አያልቅም፣ በእያንዳንዱ ሰውነት ሲገባም በምልዐት ነው እንጂ ሕጸት ወይም ጉደለት የለበትም፡፡ ሥጋውንና ደሙን በእምነት ወደሚቀበሉት ወደ እያንዳንዱ ምእመን ሰውነት በምልዐት ሲገባም እርሱ ከእርሱነቱ ሳይለወጥ በምልዐት ይኖራል፡፡

" . . . በእግዚአብሔር ቃል የሚከብረውና የሚቀደሰው ኅብስት ወደ እግዚአብሔር ቃል ሥጋነት ይለወጣል ብለን ማመናችን ትክክል ነው፡፡ አካላዊ ቃል ራሱ 'ይህ ሥጋዬ ነው' ብሏልና በዚህ ቃል መሠረት ኅብስቱ የእርሱ አካል ወደ መሆን ይለወጣል፡፡ በሥጋ የተገለጠው አካላዊ ቃል መለወጥ የሚስማማውንና መዋቲ የሆነውን የእኛን ሰውነት የተዋሐደውና ገንዘቡ ያደረገው ስለዚህ ነውና፤ ማለትም የእኛ ባሕርይ ከመለኮታዊ ባሕርይ ጋር ከመዋሐዱ የተነሣ የሰው ልጅም የጸጋ አምላክነትን ያገኝ ዘንድ ነው[77]፡፡ ከቸርነቱ የተነሣ ቅዱስ ሥጋውንና ደሙን የሚቀበሉ ምእመናን እርሱን ራሱን እንዲቀበሉት በማድረግና ከሰውነታቸው ጋር አንድ ሆኖ በመዋሐድና በውስጣቸው በመሆን በዚህ ምሥጢር አማካይነት ለዚህ ክብር (የጸጋ አምላክነት) ለማብቃትና ኢመዋቲ ከሆነው ከእርሱ ጋር ከመዋሐዳቸው የተነሣ እነርሱም (የሰው ልጆች) የእርሱን ኢመዋቲነትና ሕይወት ገንዘብ ያደርጉ ዘንድ ለማድረግ ነው፡፡"

(ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ዐቢይ ትምህርተ ክርስትና፣ ምዕ. 37)

❖" . . . ስለዚህ እንዘን፣ የጊዜውንም መከራ እንፍራ፣ እርሱ ደሙን ስለ እኛ ስለ ሁላችን ማፍሰስን ወደ ኋላ አላለምና፣ እንደ ገናም ቅዱስ ሥጋውን እንድንበላና ክቡር ደሙን እንድንጠጣ ፈቅዶልናልና፣ ስለዚህ ስለ እኛ ደኅንነት ከሚያስፈልገው ነገር ሁሉ የማያደርገው ምን ነገር ይኖራል?" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 2፣ ቁ. 25)

[77] (. . . Rightly, then, do we believe that now also the bread which is consecrated by the Word of God is changed into the Body of God the Word. For that Body was once, by implication, bread, but has been consecrated by the inhabitation of the Word that tabernacled in the flesh. Therefore, from the same cause as that by which the bread that was transformed in that Body was changed to a Divine potency, a similar result takes place now. For as in that case, too, the grace of the Word used to make holy the Body, the substance of which came of the bread, and in a manner was itself bread, so also in this case the bread, as says the Apostle, "is sanctified by the Word of God and prayer"; not that it advances by the process of eating to the stage of passing into the body of the Word, but it is at once changed into the body by means of the Word, as the Word itself said, "This is My Body." Seeing, too, that all flesh is nourished by what is moist (for without this combination our earthly part would not continue to live), just as we support by food which is firm and solid the solid part of our body, in like manner we supplement the moist part from the kindred element; and this, when within us, by its faculty of being transmitted, is changed to blood, and especially if through the wine it receives the faculty of being transmuted into heat.

Since, then, that God-containing flesh partook for its substance and support of this particular nourishment also, and since the God who was manifested infused Himself into perishable humanity for this purpose, viz. that by this communion with Deity mankind might at the same time be deified, for this end it is that, by dispensation of His grace, He disseminates Himself in every believer through that flesh, whose substance comes from bread and wine, blending Himself with the bodies of believers, to secure that, by this union with the immortal, man, too, may be a sharer in incorruption. He gives these gifts by virtue of the benediction through which He transelements the natural quality of these visible things to that immortal thing.)

- ". . . ዳግመኛም የሚያድን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውና ደሙ እንደ ሆነ በክብረ ቁርባን እናምናለን፡፡ ቄሱ ሳያከብረው ኅብስትና ወይን የነበረው ቄሱ ባከበረው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በላዩ ይወርዳል፤ ኅብስት ከመሆን የወልደ እግዚአብሔር አማናዊ ሥጋ ወደ መሆን ይለወጣል፡፡ ወይኑም እንዲሁ ወይን ከመሆን የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ አምላካዊ ደም ወደ መሆን ይለወጣል፤ ከሥጋው ጋር አንድ ሆኖ፡፡" (ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 22)

ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያም እንዲህ ይላል፡-

- "'እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ' አለ፣ ከቀድሞ ጀምሮ በተስፋ ሲነገርና ሲጠበቅ እንደ ነበርና በምሳሌ ሲታይ እንደ ነበር፣ አሁን ግን ያን የሰጠሁትን ተስፋ እፈጽም ዘንድ እኔ አለሁ አለ፡፡ 'እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ' አለ፣ ከጊዜያዊ ረሀብ ብቻ የሚያድንና ከረሀብ ከሚመጣው ጥፋት ብቻ ነጻ የሚያወጣ ሳይሆን መላ ሕይወታችንን ለዘላለማዊ ሕይወት እንዲሆን የሚለውጥና በሐዲስ ሁኔታ የሚያዘጋጅ ነው እንጂ፡፡ ለዘለዓለም ሊኖር ተፈጥሮ የነበረውን የሰውን ልጅ ሕይወት ከሞት በላይ የሚያደርግ ነው እንጂ፡፡ በእነዚህ ቃላትም በቅዱስ ሥጋው ለእኛ የሚተላለፍልንን ሕይወትና ጸጋ፣ የአንድያ ልጁ ገንዘብ የሆነው ሕይወት ወደ እኛ የሚደርስበትን መንገድ አመለከተን፡፡

  "ስለዚህም ክርስቶስ ስለ ሁላችን ሕይወት የራሱን ሰውነት ሰጠ፣ በእርሱም ሕይወት በእኛ ውስጥ እንዲኖር (ሕያዋን እንድንሆን) አደረገን፡፡ ይህ እንዴት እንደ ሆነ የቻልሁትን ያህል ለመግለጽ ልሞክር፡፡ ሕይወትን ሰጪ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል የእኛን ሰውነት ገንዘቡ ስላደረገው መልካም ወደ ሆነው ወደ እርሱ ማለትም ወደ ሕይወት ከፍ አደረገው፡፡ በዚህ ሊነገር በማይቻለው የተዋሕዶ ምሥጢር የእኛን ባሕርይ በፍጹም የራሱ ገንዘብ አድርጎ ስለ ተዋሐደውና ከራሱ ጋር አንድ ስላደረገው እርሱ በባሕርዩ ሕይወትን ሰጪ እንደ ሆነው ሁሉ ከእኛ የነሣውን የእኛን ባሕርይም ሕይወትን መስጠት የሚችል (ሕይወትን ሰጪ) እንዲሆን አደረገው፡፡ ስለዚህም የክርስቶስ ሥጋ ለሚቀበሉት ሁሉ ለሁሉም የዘለዓለም ሕይወትን ይሰጣል፡፡"

  (ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፣ ትርጓሜ ወንጌለ ዮሐንስ)

## ወደ ቅዱስ ቁርባን ሲቀርቡ መዘጋጀትና መጠንቀቅ ያስፈልጋልን?

ቅዱስ ቁርባን የክርስቶስ አማናዊ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደሙ መሆኑን ከማስተማር ጋር ወደዚህ ምሥጢር ስንቀርብ ተዘጋጅተን፣ ራሳችንን ለካህን አሳይተን በካህናት ፈቃድ አማካይነት እንጂ እንዲሁ በግድ የለሽነትና በራሳችን ፈቃድ ብቻ ዝም ብለን ሊሆን እንደማይገባው፣ እንዲሁም ይህ ሥርዓት ከጥንት ዘመን ጀምሮ የነበረ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሆኑንም እንዲሁ አባቶቻችን ቅዱሳን ሊቃውንት አስተምረዋል፡፡ ለአብነትም ሰማዕቱ ቅዱስ ቆጵርያኖስ እና ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ያስተማሩትን ትምህርት እንመልከት፡፡

- ". . . ተነሣሕያን በጥቃቅን ኃጢአቶች በታወቀው ቀኖና መሠረት ለተወሰነ (ለታወቀ) ጊዜ ንስሐ ሊገቡና ቀኖና ሊቀበሉ ቢችሉም፣ እንዲሁም እንደ ቀኖናው ሕግ አካሄድ በሕዝብ ፊት ንስሐ ለመግባት ቢመጡም፣ እንዲሁም በጳጳሱና በካህናቱ ይሁንታና ቡራኬ ቅዱስ ቁርባንን የመቀበል ፈቃድ ቢቀበልም የመከራና የስደት ዘመን ካልሆነ በስተቀር ገና በቀኖና ላይ ያለ ተነሣሒ (ቀኖናውን ያልፈጸመ ክርስቲያን) ቅዱስ ቁርባንን ሊቀበል አይገባም፡፡" (ቅዱስ ቆጵርያኖስ፣ መልእክት 9)

* "የጾሙ ጊዜ እያለቀና ወደ ፍጻሜው እየገሰገሰ ነው፤ ስለዚህም በበለጠ ሁኔታ ራሳችንን ለቅድስና ማዘጋጀትና መስጠት ይገባናል፡፡ በውድድር ሜዳ የሚሮጡ ሯጮች ሽልማታቸውን ካጡና የማያገኙ ከሆነ መሮጣቸውና የሜዳውን ዙሪያ ደጋግመው መዞራቸው ምንም እንደማይጠቅማቸው ሁሉ፤ እኛም የተቀደሰውን የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም በንጹሕ ሕሊና ሆነን መቀበል የማንችል ከሆነ ከጾሙ ጋር በተያያዘ ከምናደርጋቸው ዘርፈ ብዙ ድካሞችና ተግባራት ሁሉ ምንም የሚተርፈን ጥቅም አይኖርም፡፡

* ጾም የተሠራውና የጌታችንን ጾም እንድንጾም የተደረገው፣ ይህን ያህል ቀናት ሁሉ ጉባኤያት፣ ጸሎታት፣ ትምህርቶች የሚደረጉት ዓመቱን ሙሉ ከሠራነው ኃጢአት በእነዚህ ሁሉ ነጽተን ከዚያ <u>እንበለ ደም ከሆነው ቅዱስ መሥዋዕት</u> ከሕሊናዊና ውሳጣዊ ወቀሳና ከሰሳ ነጻ ሆነን መሳተፍ እንችል ዘንድ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን፣ መጨረሻው ውጤቱ ከቅዱስ ቁርባን እንድንቀበል የማያደርሰን ከሆነ ግን፣ ያ የደከምነው ድካም ሁሉ እንዲሁ ያለ ምንም ትርፍ በከንቱ ይሆንብናል፡፡
"ስለዚህም እያንዳንዱ ከነበረበት ደካማ ጎን ውስጥ ምን ዓይነት ስሁተቶችን እንዳስተካከለ፣ ምን ዓይነት መልካም ሥራ መሥራት እንደ ቻለ፣ ምን ዓይነት ኃጢአት አሽቀንጥሮ እንደ ጣለ፣ ምን ዓይነት ነውር እንዳነጻ፣ በምን ሁኔታ ከቀድሞው ሕይወቱ የተሻለ እንደ ሆነ ራሱን ይመልከት፡፡ በዚህ ረገድ በጾሙ ያገኘው ትርፍ መኖሩን ካየና በቁስሉ ላይ ያገኘው መፈወስ እንዳለ ከተሰማው ወደዚህ ቁርባን ይቅረብ! አሁንም በግዴለሽነቱ ከቀጠለ፣ እንዲሁ እጾማለሁ ከማለት በቀር ምንም መልካም ነገር ያደረገ ካልሆነ ግን በውጭ ይቆይ! እነዚህን ነውሮችና ጥፋቶች ካስተካከለና ካሰወገደ በኋላ ይግባ፡፡ . . ."

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 20፣ ቁ. 1)

ይህ ቅዱስ አባት ስለዚህ ጉዳይ በስፋት ካስተማራቸው ብዙ ትምህርቶች መካከል የሚከተለውን እንመልከት፦

* "የተቀደሰውን መሥዋዕት ባልታጠቡ እጆችህ ለመንካት መድፈር የለብህም፤ ምንም ያህል እንኳ አስገዳጅና ግድ የሚል ሁኔታ ላይ ብትሆን፡፡ እንዲህ ከሆነ ባልታጠበ ነፍስ አትቅረብ! ይህ ከዚያኛው በእጅጉ የከፋ ነውና፣ የበለጠ ከባድ ቅጣትም ያመጣልና፡፡" (ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 20፡ ቁ. 19)

* "በጥንቃቄና በመረዳት ከሚያደርጉት ይልቅ ብዙዎች የክርስቶስን ሥጋና ደም እንደ ቀላል ነገር እንዲሁ በዘፈቀደ ሲቀበሉ እያለሁ፡፡ የተቀደሰው የጌታችን ጾም ሲፈጸም ወይም የጌታችን በዓለ ኤጲፋንያ (አስርእዮ - መገለጥ) ሲመጣ ሰውዬው ሕይወቱ ምንም ይሁን ምን ከቅዱሳት ምሥጢራት ይሳተፋል፡፡ ሆኖም ግን ወደዚህ ድንቅ ምሥጢር መቅረባችንን ተገቢ የሚያደርገው ጊዜ የጌታችን ጾም ፍጻሜ ቀን መሆኑ ወይም በዓለ ኤጲፋንያ መሆኑ ሳይሆን የነፍስ ንጽሕናና ርትዓተ ልብ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ከሆነ ሁል ጊዜ ቅረቡ፣ ያለዚህ ከሆነ ግን መቼም አትቅረቡ፡፡ . . . በብሉይ ኪዳን ዘመን ከመሥዋዕቱ ይሳተፉ የነበሩት ምን ያህል ተዐቅቦና ጥንቃቄ ያደርጉ እንደ ነበር አስተውል፡፡ ሁል ጊዜ ራሳቸውን ያነጹና ያዘጋጁ ነበርና፡፡ አንተስ ኃያላን መላእክት ወደሚንቀጠቀጡለት ወደዚህ መሥዋዕት ስትቀርብ ካኑን የምትለካው በወቅቶች መፈራረቅ ነውን? የእርሱን አካል በረከሰ ሰውነትህና ከናፍር የምትቀበለው አንተ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ራስህን እንዴት አድርገህ ታቀርባለህ? መቼም አንድን ንጉሥ ንጹህ ባልሆነ አፍ ልትስመው አትደፍርም፡፡ ታዲያ የሰማያትን ንጉሥ ንጹሕ ባልሆነ ነፍስ ትስመዋለህን? ይህ እብደት ነው፣ በጣም የሚያሳዝንና የሚያበሳጭም ነው፡፡ . . .

"ከቅዱሳት ምሥጢራት ለመካፈል እንችል ዘንድ ራሳችንን ሳናዘጋጅ በግዴለሽነት ዝም ብለን እንዲህ አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ እዚህ ለቆምነው ለእኛ ለእያንዳንዳችንም ለሁላችንም በዚህ ቅጽበት የሚናገረን ቃል ይህ ነው፡፡ ከቅዱሳት ምሥጢራት የማይካፈል ሰው እዚህ የቆመው ኀፍረት የለሽ በሆነ ድፍረት ነው፡፡ በኃጢአት የወደቁና በኃጢአት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች፣ <u>ንስሐ ገብተው ቀኖናቸውን ያልፈጸሙ ሰዎች ከሁሉ አስቀድሞ ከዚህ ምሥጢር እንዲርቁ የሚደረገው ስለዚህ ነው፤</u> አንድ ጌታ ወይም ባለ ሥልጣን በማዕድ ላይ ሲቀመጥ እርሱን ያስቀየሙት አገልጋዮች በዚያ በማዕዱ አብረውት ይሆኑ ዘንድ ተገቢ አይደለም፤ እርሱም አይፈቅድላቸውም፡፡ በዚህም እንደዚሁ ነው፤ መሥዋዕቱ ሲሰየም፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር በግ ሲሠዋ፣ ዲያቆኑ "ጸልዩ" ሲል ስትሰማ፣ መጋረጃው ሲገለጥ፣ ሰማያት ከላይ እንዳሉ ወደ መሬት የወረዱ ሲመስልና መላእክት ሲወርዱ በዓይነ ሕሊናህ አስብ!

"ንፁስ ክርስቲያን (ገና ወደ ጥምቀተ ክርስትና ያልገቡ) ከሆኑ አንዳቸውም ሊገኙ አይገባም፤ ክርስቲያኖች ከሆኑት መካከልም በረከሰ ሕይወት ውስጥ የሚኖሩ እነርሱም በዚህ ምሥጢር ሊገኙ አይገባም፡፡ እስኪ ንገረኝ፣ ወደ በዓል የተጋበዘ ሰው ቢኖር፣ እጁን ታጥቦ በማዕዱ ፊት የሚሳተፍ መስሎ ተዘጋጅቶ ከተቀመጠ በኋላ አልበላም አልጠጣም ቢል የጋበዘውን ሰውዬ እየሰደበው አይደለምን? እናንተም አመጣጣችሁ እንደዚሁ ነው፡፡ መዝሙሩን ዘመራችሁ፣ ቅዳሴውን ከሌሎች ጋር አብራችሁ አስቀደሳችሁ፣ ንፁስ ክርስቲያኖች ሲወጡ አብራችሁ ባለመውጣታችሁ ከቅዱሱ ምሥጢር ሊቀበሉ ካላቸው ወገኖች ውስጥ መስላችሁ ታያችሁ፡፡

"ታዲያ የምትቆርቡ መስላችሁ ከቆያችሁ በኋላ ከቅዱሱ ማዕድ የማትሳተፉት ለምንድን ነው? 'እደ እኔ የበቃሁ አይደለሁም' ነው የምትሉት፡፡ በጸሎት አማካይነት ለምታገኙት ቡታፌስ አሁንም የበቃችሁ አይደላችሁም? መንፈስ ቅዱስ የሚወርደውና የሚረበው በመሥዋዕቱ አማካይነት ብቻ ሳይሆን በጸሎቱና በዝማሬውም ነውና፡፡ የእኛ አገልጋዮቻችን በመጀመሪያ ጠረጴዛውን በስፖንጅ ሲያጸዱትና ቤቱን ሲጠርጉት፣ ከዚያ በኋላ ምግቡን ሲያቀርቡ አናያቸውምን? በጸሎታቱ፣ በቅዳሴው፣ በእግዚአታው ሠርኸት ሁሉ የሚደረገውም ይኸው ነው፡፡ እኛም ልክ በስፖንጅ እንደ ማጽዳት ቤተ ክርስቲያንን እናነጻታለን፣ ሁሉም ነገር ንጹሕ በሆነ ቤተ ክርስቲያን ይፈጸም ዘንድ፣ "እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር" እንዳይኖር (ኤፌ. 5፡27)፡፡ ዓይናችን ይህን ለማየት፣ ጆሯችንም ይህን ለመስማት የበቃ አይደለም፡፡ "እንስሳ እንኳ ተራራውን ቢነካ ይወገር" ተብሏልና፡፡ ዘጸ. 19፡13 ስለዚህ ያን ጊዜ በዚያ በተቀደሰው ተራራ ላይ እግራቸውን እንኳ ለመርገጥ የበቁ አልነበሩም፤ እንዲያ ሆኖም ግን ወደዚያ ቀረቡ፣ እግዚአብሔር የቆመበትን ቦታም ተመለከቱ፡፡

"ፍርድህና ፍዳህ የሚጨምርብህ ምክንያት እንዳልሆን ከመምጣት ወደ ኋላ እንድትል ሳይሆን ከዚህ ለመገኘት፣ እንዲሁም ወደ ተቀደሰው ምሥጢር ለመቅረብ ትችል ዘንድ የበቃህ እንድትሆን ራስህን አዘጋጅ ብዬ እማጸንሃለሁ፡፡ እስኪ ንገረኝ፣ አንድ ንጉሥ 'እንዲህ እንዲህ የሚያደርግ ማንኛውም ሰው ከማዕዴ ይሳተፋል' የሚል ዐዋጅ ቢያስተላልፍ ወደ እርሱ ማዕድ ለመቅረብ ትችል ዘንድ ማድረግ የሚቻልህን ማንኛውንም ነገር ሁሉ አታደርግምን? እርሱ [እግዚአብሔር] እኛን ወደ ሰማያት ጋብዞናል፣ ወደ ታላቁና ገናናው ንጉሥ ማዕድ ተጠርተናል፣ ታዲያ እኛ ወደዚያ በመሮጥና በመሽቀዳደም ፋንታ ገና አሁንም ወደ ኋላ እያልን እናመነታለንን? እንዲህ የምናደርግ ከሆነ የመዳናችን ተስፋ ምን ይሆን? በድካማችን ማሳበብ አንችልም፤ በባሕርያችንም ማመካኘት አንችልም፡፡ የማይገባ ያደረገን ባሕርያችን (ተፈጥሯችን) ሳይሆን ስንፍናችንና ግዴለሽነታችን ብቻ ነው፡፡ . . . 'ልጆችህ በማዕድህ ዙሪያ

እንደ ወይራ ቡቃያ ናቸው' ተብሎ በትንቢት እንደ ተነገረው ወደዚህ ሰማያዊ ማዕድ አንድ ላይ ሆነን፣ በአጋጣሚ ሳይሆን፣ በከንቱም ሳይሆን በፍርሃትና በአክብሮት ሆነን ተዘጋጅተን በኅብረት እንቅረብ። *መዝ.* 127፥3"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ *መል*እክት ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ኤፌሶን፣ ክፍለ ትምህርት 3)

- "በየቀኑ <u>*መሥዋዕቱ*</u> *መ*ቅረቡ በከንቱ ነው፣ እኛ በምሥዋው ፊት *መ*ቆማችን ለከንቱ ነው፤ ምክንያቱም ከ*መሥዋ*ዕቱ የሚቀበል ማንም ሰው የለምና። ይህን የምለው እንዲሁ ዝም ብላችሁ ሳትዘጋጁ ለ*መ*ቀበል እንድትቀርቡ አይደለም፣ ራሳችሁን ለ*መ*ቀበል ታዘጋጁ ዘንድ ነው እንጂ። ከዚህ <u>*መሥዋዕት*</u> ለ*መ*ቀበል ብቁ አይደለህምን? እንዲህ ከሆንክ ለ*መ*ቀበል ትችል ዘንድ ራስህን አዘጋጅ" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ *መል*እክተ ኤፌሶን፣ ክፍለ ትምህርት 3)

- "... *መ*ጽአ ወተጠምቀ እምነበ ዮሐንስ ከ*መ* ይፈጽም ኵሎ ጽድቀ ወከ*መ* ይረሲ *ሥጋ*ሁ ቅዱሰ ወቡሩከ ወለነኒ ለእለ *እመ*ነ ይኩነነ ለ*መ*ድኃኒተ ነፍስነ ወነአምን ከ*መ* በአማን ሀሎ *ሥጋ*ሁ ውስተ ዝንቱ ኅብስት ወነአምን ከ*መ* በአማን ሀሎ ደሙ ውስተ ዝንቱ ጽዋዐ ወይን ወይቤሎሙ ዮሐንስ ለሕዝብ አኮ በከ ዘትሬእዩ አላ *መ*ለኮቶ ኅቡዐ ደ*መ*ረ ውስተ *ሥጋ* ዚአነ ወገብረ ለነ ሕይወተ በሞቱ - ጽድቅን ሁሉ ይፈጽም ዘንድ፣ እንዲሁም *ሥጋ*ውን ቅዱስና ቡሩክ አድርጎ ይሰጠን ዘንድና ለምናምን ለእኛም ለነፍሳችን *መ*ድኃኒት ይሆነን ዘንድ ሰው ሆኖ ወደ እኛ *መ*ጣ፣ በዮሐንስ ዘንድም ተጠ*መ*ቀ። *ሥጋ*ው በእውነት በዚህ በኅብስቱ ውስጥ እንዳለ፣ ደሙም በዚህ በጽዋው ባለው ወይን ውስጥ እንዳለ እናምናለን። ዮሐንስ ሕዝቡን የምታዩት እንዲሁ ከንቱ ወይም ተራ ነገር አይደለም፣ *መ*ለኮቱ በምሥጢር የተዋሐደውና ለእኛ *ሥጋ* ሕይወት ይሆን ዘንድ በውስጡ *መ*ለኮቱ ህልው የሆነበት ነው እንጂ አላቸው። በሞቱም ለእኛ ሕይወትን ሰጠን።" (ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘሰንበት)

- "ሀበነ ንንሣእ ወንት*መ*ጠ እምዝንቱ ኅብስት *ሥጋ*ከ ውእቱ ዘወረደ እምሰማያት ዘሐዳስ *ሥ*ርዓት .... - የሐዲስ *ሥ*ርዓት *መሥ*ዋዕት ይሆን ዘንድ ከሰማይ የወረደውንና ቅዱስ *ሥጋ*ህ የሆነውን ይህን ኅብስት እንቀበል ዘንድ *መ*ስጠትን ስጠን" (ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘአቡነ አረጋዊ)

- "... ሀበነ *ሥጋ*ከ ወደ*መ*ከ ዘወሀብኮሙ ለአርዳኢከ ... ኅብስተ ሕይወት ኅብስተ *መ*ድኃኒት ዘወረደ እምሰማያት በዘይሠረይ ኃጢአት .... - ለደቀ *መ*ዛሙርትህ እንደ ሰጠሃቸው ለእኛም ቅዱስ *ሥጋ*ህንና ክቡር ደምህን ስጠን፣ ... ኃጢአት በሚሠረይበት ገንዘብ ከሰማያት የወረደ የሕይወት ኅብስትና *መ*ድኃኒት ነው ..." (ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘቅዱስ ቴዎድሮስ)

- "ዝንቱ ጽዋዕ ዘንትሜጠ ደ*መ* ውእቱ ለክርስቶስ ይኩነነ ለ*ሥ*ርየተ ኃጢአት ወይክፍለነ ምስለ ነፍሰ ጻድቃን - ይህ የምንቀበለው ጽዋዕ የክርስቶስ ደሙ ነው፣ እርሱም ለኃጢአት *ሥ*ርየት ይሁነን፣ ከጻድቃን ነፍሳት ጋርም ይደምረን (አንድ ያድርገን)።" (ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘቅዱስ ቴዎድሮስ)

- "ዝንቱ ጽዋዕ ዘንትሜጠ ደ*መ* ውእቱ ለክርስቶስ ይኩነነ ለ*ሥ*ርየተ ኃጢአት ወይክፍለነ ምስለ ነፍሰ ጻድቃን በጸሎቱ ለእስጢፋኖስ ዘቀደ*መ* ስምዐ ከዊነ - ይህ የምንቀበለው ጽዋዕ የክርስቶስ ደሙ ነው፣ እርሱም ከሁሉ አስቀድሞ ለክርስቶስ ምስክር (ሰማዕት) በሆነ በእስጢፋኖስ ጸሎት ለኃጢአት *ሥ*ርየት ይሁነን፣ ከጻድቃን ነፍሳት ጋርም ይደምረን (አንድ ያድርገን)።" (ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘቅዱስ እስጢፋኖስ ቀዳሚ ሰማዕት)

- "አሚነነ በአብ ኪያሁ ንሰብሕ አሚነነ በወልድ ኪያሁ ነአኵት አሚነነ በመንፈስ ቅዱስ ሎቱ ንሬኢ ስብሐተ እንዘ ንትሜጦ በአሚን እምዝንቱ ኅብስት ሥጋሁ ቅዱስ ለኢየሱስ ክርስቶስ ዘያስተፌሥሕ ልበነ ወይሠሪ ለነ ኃጢአተነ ወያንጽሐነ እምጌጋይነ ወያነሥአነ እምነ ሙታን በዕለተ ሰንበት በዓባይ ዕለት ናዓርግ ለከ እግዚኦ መሥዋዕተ ጽድቅ ዘሐዳስ ሥርዓት - በአብ አምነን እርሱን እናመሰግናለን፣ በወልድ አምነን እርሱን እናመሰግናለን፣ በመንፈስ ቅዱስ አምነን ለእርሱ ምስጋናን እናቀርባለን፤ ልባችንን ደስ ከሚያሰኘውና ኃጢአታችንን ከሚደመስስልን፣ ከበደላችን ከሚያነጻን፣ በታላቂቱ ዕለት በዕለት ሰንበት ከሙታን ከሚያስነሣን፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋው ከሆነው ከዚህ ኅብስት በእምነት እየተቀበልን እርሱን እናመሰግናለን፣ የሐዲስ ሥርዓት የሆነውን እውነተኛ መሥዋዕትም እናቀርብልሃለን፡፡" (ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘአስተምህሮ)

- "ወረደ ወልድ እምሰማያት ወተወልደ በተድላ መለኰት ወቦአ ውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ወቦአ ውስተ ይእቲ ማዕድ ደመረ ሥጋሁ ውስተ ዝንቱ ኅብስት ወከዓወ ደሞ ውስተ ዝንቱ ጽዋዐ መድኃኒት ወዲያቆንሰ ዘንተ ርእዮ አንከረ ሀለው ካህናት ውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ወይቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ እምዝንቱ ኅብስት ወ. ወሀቡ ለሕዝብ እንዘ ትብሉ ሥጋሁ ለክርስቶስ አሜን ይበል ዘይትሜጦ ወ. ዘኒ ጽዋዐ ሀቡ እንዘ ትብሉ ደሙ ለክርስቶስ አሜን አሜን ይበል ካዕበ ዘይትሜጦ ወ. መንክር ግብር ወዕፁብ ዘተገብረ ሥጋሁ ቅዱስ መብልዓ ጽድቅ ለሰብእ ዘረሰዮ ለሥርየተ ኃጢአት . . . - ወልድ ከሰማያት ወረደ፣ በመለኰት ክብር ተወለደ፣ ወደ መጋረጃው ውስጥም ገባ፣ ወደዚህች ማዕድም ገባ፣ ሥጋውን ከዚህ ኅብስት ጋር አንድ አደረገ፣ ደሙንም በዚህ በመድኃኒት ጽዋ ውስጥ አፈሰሰ (ጨመረ)፤ ይህን የተመለከተ ዲያቆንም [ቅዱስ እስጢፋኖስ] አደነቀ፡፡ ካህናት በመጋረጃው ውስጥ አሉ፤ እነርሱንም ጌታችን እንዲህ አላቸው፡- 'ከዚህ ኅብስት ብሉ፣ ለሕዝቡም 'ይህ የክርስቶስ ሥጋ' ነው እያላችሁ ስጡ፤ ሥጋውን የሚቀበለውም 'አሜን' ብሎ ይቀበል፡፡ ይህን ጽዋም (ደሙን) 'ይህ የክርስቶስ ደም ነው' እያላችሁ ስጡ፣ የሚቀበለውም 'አሜን አሜን' ብሎ ይቀበል፡፡ እጅግ በጣም አስደናቂና አስገራሚ ነገር ተደረገ፤ ይኸውም ቅዱስ ሥጋው ለሰዎች እውነተኛ ምግብና የኃጢአታቸው ማስተሥረያ መድኃኒት ሆኖ የመሰጠቱ ነገር ነው፡፡" (ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘቅዱስ እስጢፋኖስ)

ተሐድሶዎች "ቅዱስ ቁርባን አማናዊ የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ደም አይደለም" የሚለውን ክህደታቸውን ይደግፈናል በማለት "<u>ጥንታውያን ድርሰቶች ምን ይላሉ?</u>" ብለው ይጠይቁና ማስረጃ ብለው ከትምህርተ ኅቡአት እንዲህ የሚለውን ጠቅሰዋል፡-

- "ወበእንተዝ ይበል ኖላዊ መፍትው እንከ ነገረ ኅቡአት ከመ ታእምሩ መነሃ ትሳተፉ ለቅድሳት ወለመኑ ትገብሩ ተዝካር በአኮቴት - እረኛው ወይም ቄሱ ምእመናን ከመቁረባቸው በፊት እንዲህ ብሎ ያስረዳ፡- ለክብር ለብፅዕና ከማን ጋር ኅብረት ልትፈጥሩ ነው? የማንንስ መታሰቢያ በምስጋና ልታደርጉ ነው? ምስጢራትን ልታውቁ ልትረዱ ይገባል ይበላቸው፡፡" (ሎሬ ቁ. 26፣ ገጽ 13-14)

"መታሰቢያ" የተባለው ይህ ምሥጢር ሲፈጸም ሁል ጊዜም "ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ ወትንሣኤከ ቅድስተ . . ." እያልን ሞቱንና ሕማሙን፣ ትንሣኤውንና ዕርገቱን የምናስብ ስለ ሆነ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ " . . . <u>ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፣ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና</u>" ብሎ እንደ ገለጸው 1 ቆሮ. 11፡24-26 ምክንቱም ቅዱስ ሥጋው የተቆረሰውና ክቡር ደሙ የፈሰሰው በዕለተ ዓርብ በመልዕልተ መስቀል ላይ በተቀበለው መከራ ነውና፡፡ ያን መከራውን ማሰብና ማለት ግን ሥጋውና ደሙ አማናዊ አይደለም የሚያሰኝ አንዳችም ነገር የለውም፡፡ በየጊዜው የሚቀርበው መሥዋዕቱ ያው በዕለተ ዓርብ የተቆረሰው ቅዱስ ሥጋውና የፈሰሰው ክቡር ደሙ ነው፡፡ ስለዚህ ምሥጢረ ቁርባንን ስንፈጽም ሕማሙንና ሞቱን ማሰብ ብቻ ሳይሆን፣ ዕለተ ዓርብን ማሰብ ብቻ ሳይሆን እዚያው ዕለት ላይ ነን፡፡

"የንታውያን ድሮስቶች ምን ይላሉ?" ብለው ለመጥቀስ ሲሞክሩ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት እነ ቅዱስ ሄሬኔዎስ፥ እነ ቅዱስ አግናጥዮስ፥ እነ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፥ እነ ቅዱስ አትናቴዎስ፥ እነ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፥ እነ ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፥ እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፥ እነ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ ሁሉም በአንዲት ሃይማኖት ተባብረው ኅብስቱ እውነተኛ የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋ፥ ወይኑም እውነተኛ የክርስቶስ ክቡር ደም ይሆናል እያሉ ከተናገሩት ምነው አልጠቀሱም? ከሐዋርያት የተቀበሉትን የሕይወት ቃልና ምሥጢር በጥንቃቄ የያዙና ያስተማሩ፥ ለእኛም ያወረሱ የእነዚህ ቅዱሳን ኦርቶዶክሳውያን አባቶች እምነትና ትምህርት የእናንተን የውሸት ትምህርት ያፈራርስባችኋል! በትምህርቱ ኅቡዓት ላይ የተገለጸውም ከዚሁ የአባቶች ትምህርት ጋር የሚስማማ እንጂ ከዚያ ተቃራኒ አይደለም፥ የእናንተን ክህደትም አይደግፍም።

ይህ የቅዱስ ቁርባን አማናዊ የክርስቶስ ሥጋነትና ደምነት ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ በነበሩና በሂደት በዳበሩ የቅዳሴ ጸሎታት ላይ በግልጽና በአጽንዖት ሲመሰከር የኖረና ያለ መሠረታዊ ነገር ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በምትገለገልባቸው የቅዳሴ ጸሎታት ውስጥ ስለዚህ ከተገለጹት መካከል ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት።

- "ያንተ ሥጋ የሚሆን ይህን ኅብስት እናቀርብልሃለን። ያንተ ደም የሚሆን ይህንም ጽዋ እናሳርግልሃለን።" (ቅዳሴ ዘቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፥ ቁ. 125)

- "አ ወልድ ክላሕ ከመ ዘሐመ ወበል ኤልማስ ላማ ሰበቅታኒ ወእንዘ ሀሎ ውስተ አፉሆሙ በል አባ ወአቡየ መሐር ወተሣሀል እለ በልዑ ሥጋየ ወሰትዩ ደምየ - ወልድ ሆይ፥ እንደ ታመመ ሰው አሰምተህ ተናገር፥ ኤልማስ ላማ ሰበቅታኒ በል። በአፋቸውም ውስጥ ሳለህ አባ አባቴም ሆይ፥ ሥጋዬን የበሉትን ደሜን የጠጡትን ማራቸው ይቅር በላቸው በል።" (ቅዳሴ ዘቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፥ ቁ. 144)

- "ይምጽእ ውእቱ በግዕ እመልዕልተ መልዕልት ንርአዮ በአዕይንት ወንጥብሖ በአእዳው ከመ ንትፌሣሕ ቦቱ - በግዕ እርሱ ከሰማየ ሰማያት ይምጣ፥ በዓይናችን አይተን በእጃችን ሠውተን ደስ እንሰኝበት ዘንድ። ሥጋው ከዚህ ኅብስት ጋር አንድ ይሁን፥ ደሙም ከዚህ ጽዋ ይቀዳ።" (ቅዳሴ ዘቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፥ ቁ. 150-151)

- "ኪያሁ ካዕበ ንስእሎ ከመ ይረስየነ ድልዋነ ለዕርገት ወለተሳትፎ ምሥጢራቲሁ መለኮታዊት እንተ ኢትመውት ሥጋ ቅዱስ ወደመ መሚሑ ክቡር እኅዜ ኩሉ እግዚአብሔር አምላክነ - ሁሉን የያዘ እግዚአብሔር አምላካችን ለዕርገትና የማትሞት መለኮታዊት ምሥጢሩን የመሲሑን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለመሳተፍ የበቃን ያደርገን ዘንድ ዳግመኛም እርሱን እንለምነው።" (ቅዳሴ ዘቅዱስ ባስልዮስ፥ ቁ. 105)

- "አ እግዚአብሔር ዘቀደስከ ዘንተ ቁርባነ ዘሥሩዕ ቅድሜከ በርደተ መንፈስ ቅዱስ ላዕሌሁ አንጽሐነ አ ሲቅነ እምኩሉ አበሳነ ዘኅቡእ ወዘገሀድ - እግዚአብሔር ሆይ፥ በፊትህ የተዘጋጀ ይህን ቁርባን በላዩ በመንፈስ ቅዱስ መውረድ የለወጥህ፥ ከተሰወረውና ከተገለጸው በደላችን ሁሉ አንጻን" (ቅዳሴ ዘቅዱስ ባስልዮስ፥ ቁ. 110)

- "ወበእንተ ዝንቱ መድኃኒነ ይኬልሕ እንዘ ይብል እስመ ሥጋየኒ መብልዐ ጽድቅ ዘበአማን ወደምየኒ ስቴ ሕይወት ዘበአማን ዘበልዐ ሥጋየ ወሰትየ ደምየ ይሄሉ ምስሌየ ወአነሂ ካዕበ እሄሉ ምስሌሁ - ስለዚህ መድኃኒታችን ይጮኻል፥ እንዲህ እያለ፦ ሥጋዬ እውነተኛ የጽድቅ መብል ነው፥ ደሜም እውነተኛ የሕይወት መጠጥ ነውና፤ ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ ከእኔ ጋር ይኖራል፥ ዳግመኛ እኔም ከእርሱ ጋር እኖራለሁ።" (ቅዳሴ ዘቅዱስ ባስልዮስ፥ ቁ. 119)

- ❖ *"ወቀድስ ነፍስየ ወአንጽሕ ሥጋየ ለነሢአ ሥጋከ ማሕየዊ ወለሰትየ ደምከ ደመ ምሥጢር መለኮታዊ - ማሕየዊ የሆነ ሥጋህን ለመቀበል፣ መለኮታዊ ደምህንም ለመጠጣት ነፍሴን ቀድስ ሥጋዬንም አንጻ፡፡"* (ቅዳሴ ዘቅዱስ ጎርጎርዮስ፣ ቁ. 67)

- ❖ *"ዝንቱ ውእቱ ዘንሕነ ንሠውዖ ለመድኃኒትነ በከመ ተሣሀ በቀራንዮ ለሕይወተ ኩሉ ዓለም፡፡ አኮ በከ በከመ ትሬእይዎ ለዝንቱ ኅብስት ምድራዊ ይቡስ ወብሱል ዘይትገሠሥ ወዘይትለከፍ አላ እሳተ መለኮት ውእቱ ዘ.የውኢ ሦከ ኃጢአት፡፡ በላዒ ውእቱ ዘይበልዕ ፀማጽያነ ወውዑይ ውእቱ ዘያውዒ ኃጥአተነ፡፡ - ለዓለሙ ሁሉ ሕይወት ለመሆን በቀራንዮ እንደ ተሠዋ ለደኅንነታችን የምንሠዋው ይህ ነው፡፡ ይህ ኅብስት የበሰለና የደረቀ የሚዳሰስና የሚነካ ሆኖ እንደምታዩት ምድራዊ ኅብስትና የማይጠቅም (ከንቱ) አይደለም፤ የኃጢአትን እሾህነት የሚያቃጥል እሳተ መለኮት ነው እንጂ፤ ዐመጸኞችን የሚያጠፋ በላዒ ነው፣ ኃጥአንንም የሚቃጥል ውዑይ ነው፡፡"* (ቅዳሴ ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ቁ. 85)

- ❖ *"ከመዝ ነአምን ወከመዝ ንትአመን ከመ ዝንቱ ኅብስት ዘንፌትቶ ሥጋ ክርስቶስ ውእቱ ዘነሥአ እምወለቶሙ ለዕብራውያን ወካዕበ ነአምን ከመ ዝንቱ ጽዋዕ ደመ መለኮት ውእቱ ዘውኅዘ እምገቦ በግዑ ለእግዚአብሔር - እንዲህ እናምናለን እንዲህም እንታመናለን፣ ይህ የምንፈትተው ኅብስት ከዕብራውያን ልጅ [ከድንግል ማርያም] የነሣው የክርስቶስ ሥጋ መሆኑን እናምናለን፡፡ ዳግመኛም ይህ ጽዋ የእግዚአብሔር በግ ከሚሆን ከጎኑ የፈሰሰ ደመ መለኮት እንደ ሆነ እናምናለን፡፡"* (ቅዳሴ ዘቅዱስ ቄርሎስ፣ ቁ. 100-101)

## 3.7.2.3.4 ቅዱስ ቁርባን "መሥዋዕት" ይባላልን?

የተሐድሶ ከሃድያን በክህደት መስመራቸው በመቀጠል ቅዱስ ቁርባን "መሥዋዕት ሊባል አይገባም" ይላሉ፡፡ እንዲህ ከሚለው የስህተት ትምህርታቸው መካከልም የሚከተሉትን እንመልከት፡-

- ◉ *"መሥዋዕት ይባላልን? አይባልም፡፡ 'በግዕ ይምጻዕ ንርአዮ በአዕይንት ወንትባበዮ በእዳው - በጉ ይምጣ በዓይናችን እንየው፤ በእጃችን እንረደው' (ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ) የሚባለው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፡፡ ሌላም መሥዋዕት በእርሱ ፋንታ አይቀርብም፡፡"* (ጮራ ቁ. 26፣ ገጽ 13)
- ◉ *"ኅብስቱና ወይኑ 'መሥዋዕት' አለመባላቸውን ልብ ይሏል፡፡"* (ጮራ ቁ. 26፣ ገጽ 13)
- ◉ *"ለኃጢአታችን ሌላ መሥዋዕት ማቅረብ አያስፈልግም፤ አንችልምም፡፡ . . . ይህም አንድ ጊዜ ለዘላለም የተፈጸመ ነውና አይደጋገምም፡፡"* (ጮራ ቁ. 19፣ ገጽ 9)
- ◉ *". . . ዛሬ ስለ ኃጢአቱ መሥዋዕት ሊሠዋ እግዚአብሔርንም ለማስደሰት ቁርባንን ሊያቀርብ የሚያስብ ቢሆን ስለ ዓለም ሁሉ ኃጢአት አንድ ጊዜ በክርስቶስ የተፈጸመውን ተመልክቶ ያው የበቃ መሥዋዕትና ቁርባን መሆኑን በሃይማኖት ያረጋግጣል እንጂ ሌላ ነገር አድርጎ 'ይህ መሥዋዕት ነው' ሲል ማመን ማሰብ እንደማይገባው እናምናለን፡፡"* (ስምዓ ጽድቅ ብሔራዊ፣ ገጽ 116)

  - ➢ የስምዓ ጽድቅ ብሔራዊ መጽሐፍ ጸሐፊው መሠረት ስብሐት ለአብ ይህን ሃሳቡን ይደግፍልኛል ብሎ ከሃሳቡ አስከትሎ የጠቀሳቸው ሁለት ጥቅሶች ግን ሁለቱም እርሱ ያለውን ሃሳብ የሚሉ አይደሉም፡፡ መጀመሪያ የተጠቀሰው ፊልጶስ የተባለው ሲሆን እርሱም ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ራሱን አንድ ጊዜ መሥዋዕት አድርጎ ማቅረቡን ይናገራል እንጂ "ቅዱስ ቁርባን መሥዋዕት አይባልም" አይልም፡፡ ቀጥሎ ከሊቁ ቄርሎስ ተብሎ የተጠቀሰውም ራሱን ያማረ የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ስለ ማሳረጉ እና ከድንግል ማርያም የተወለደው ሰው ብቻ ነው የሚሉትን ንስጥሮሳውያን - ራሳቸውን ተሐድሶዎችን - የተወገዙ ይሁኑ እያለ ቃለ ግዘት ያስተላልፍባቸዋል እንጂ "ቅዱስ ቁርባን መሥዋዕት አይባልም" አይልም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የቅዱስ ቄርሎስና የሌሎቹም የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ትምህርት ምን እንደሚል ከታች እንመለከተዋለን፡፡ በኋላ ላይ በጮራ መጽሔትና በሌሎቹም የተሐድሶ መጻሕፍትና መጣጥፎች የተገለጸው ከፕሮቴስታንቶቹ ከእነ ዳቪድ ስቶክስ የተቀዳውና በመሠረት ስብሐት ለአብ አስቀድሞ "ስምዓ ጽድቅ ብሔራዊ" በተባለው መጽሐፍ የተለፈፈው ነው፡፡

### 3.7.2.3.4.1 የቅዱስ ቁርባን መሥዋዕትነት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

የምሥጢረ ቁርባንን ሁለንተናዊ ምንነት የማያምኑት ራሳቸውን "ተሐድሶ" ብለው የሚጠሩት የዘመናችን የመርቅያንና የማኒ ተወላጆች ይህንኑ ምሥጢር "መሥዋዕት ሊባል አይገባውም" ይላሉ፡፡ በርግጥም ከመሠረቱ ኅብስቱና ወይኑ በጸሎተ ቅዳሴ በመንፈስ ቅዱስ ለዋጭነት ክብሮ "ንሥኡ ብልዑ ዝ ውእቱ ሥጋየ - ይህ ሥጋዬ ነው፤ ብሉ" ብሎ የሰጠውን የክርስቶስን ሥጋ አይሆንም፤ ወይኑም የክርስቶስ ደም ወደ መሆን አይለወጥም" ብለው የካዱ ሰዎች ይህን የካዱትን ምሥጢር "መሥዋዕት አይባልም" ቢሉ አይገርምም፤ የዋናው ክህደታቸው ቀጣይ አካል ነውና፡፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ሆኖ በዕለተ ዓርብ ያቀረበው መሥዋዕት "ልዩ መሥዋዕት" ነው፡፡ እርሱም ካቀረበው ከዚህ ልዩ መሥዋዕት የተነሣ "ልዩ ሊቀ ካህናት" ተብሏል፡፡ ልዩ ሊቀ ካህናት ያሰኙትም የሚከተሉት መሠረታዊ ነገሮች ናቸው፦

1. የአሪቱ ሊቀ ካህናት የሚያቀርበው መሥዋዕት የሌላውን ደም ነበር (የበግ ወይም የወይፈን ደም ነበር)፡፡ ይህም ማለት መሥዋዕት አቅራቢውና መሥዋዕቱ፤ እንዲሁም መሥዋዕቱን ተቀባዩ ሦስቱም የተለያዩ ነበሩ፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን መሥዋዕት አቅራቢውም፤ መሥዋዕቱም፤ መሥዋዕቱን ተቀባዩም ራሱ ነው፡፡ እርሱ ያቀረበው መሥዋዕትም ሌላ ሳይሆን የራሱን ደም ነው፤ "የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም" እንዳለ። ዕብ. 9፡12 ስለሆነም ጌታችን መሥዋዕት አቅራቢውም፤ መሥዋዕቱም፤ እንደ አምላክነቱ መሥዋዕቱን የተቀበለውም እርሱ ራሱ ስለ ሆነ ከአሪቱ ሊቀ ካህናት የተለየ "ልዩ ሊቀ ካህናት" ይባላል፡፡

2. የብሉይ ኪዳኑ ሊቀ ካህናት ያቀርበው የነበረው መሥዋዕት የሚያገለግለው ለአንድ ዓመት ብቻ ነበር፡፡ ስለዚህም በየዓመቱ ያንኑ መሥዋዕት ይዞ እንደ ገና ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ መግባትና ማቅረብ ነበረበት፡፡ ጌታችና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አንድ ጊዜ በዕለተ ዓርብ ያቀረበው መሥዋዕት ለዘለዓለም በቂ ስለሆነ በየዓመቱ በቀራንዮ መሰቀልና መሞት አያስፈልገውም፡፡ በዕብራውያን መልእክት እንዲህ ተብሎ የተገለጸው ይኸው እውነት ነው፦

   ሊቀ ካህናትም በየዓመቱ የሌላውን ደም ይዞ ወደ ቅድስት እንደሚገባ፥ ራሱን ብዙ ጊዜ ሊያቀርብ አልገባም፤ እንዲህ ቢሆንስ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር፤ አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጧል። ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፥ እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሠዋ በኋላ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል። ዕብ. 9፡25-28

   እንዲሁም "በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል . . . እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ" ተብሎ ተገልጿል። ዕብ. 10፡10፤ 12

3. የብሉዩ ሊቀ ካህናት ፍጡር (ሰው) በመሆኑ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ስለሚሞት በሌላ ሰው ይተካ ነበር፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሕያው ባሕርይ ዘለዓለማዊ አምላክ ስለሆነ በሌላ ሊቀ ካህናት አይተካም፤ ሥልጣኑም ለሌላ ለማንም አይተላለፍም፡፡ "አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ - እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ" የተባለው ለዚህ ነው፡፡ መዝ. 109፡4 ፤ ዕብ. 7፡1-3

4. የብሉይ ኪዳኑ ሊቀ ካህናት ያቀርበው የነበረው መሥዋዕት የሚያስጠው ጥቅም ከጊዜያዊ መከራና ከምድራዊ መዓት፣ ከአባርና ከቸነፈር መዳንን እንጂ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን ኃጢአት ያመጣውን የጠብ ግድግዳ አፍርሶ ሰማያዊ ርስትን፣ አማናዊ ሥርየተ ኃጢአትን የሚያሰጥ አልነበረም፡፡ የጌታችን መሥዋዕትነት ግን ይህን ሁሉ የፈጸመ ነው፡፡

ስለሆነም ለስሙ አጠራሩ ክብርና ምስጋና ይግባውና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ልዩ ሊቀ ካህናት" ይባላል፡፡ አንድ ጊዜ በቀራንዮ ባቀረበው ልዩ መሥዋዕት የዘላለም ቤዛነትን አድርጎልናልና፡፡ ከዚያ በኋላ እርሱ ዳግመኛ መከራ መቀበል፣ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በየጊዜው ማቅረብ ሳያስፈልገው በየማነ አብ በዘባነ ኪሩብ ለመቀመጥ "እርሱው ኖላዌ መኳንንት ወይባእ ንጉሠ ስብሐት" እየተባለ ሥግው ቃል በድል አድራጊነት ዐርጓልና፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጓቸዋልና" ያለው ለዚህ ነው፡፡ ዕብ. 10፡14

ታዲያ እንዲህ ከሆነ በየዕለቱ በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ በጸሎተ ቅዳሴ የሚቀርበው መሥዋዕት ከክርስቶስ መሥዋዕትነት ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? በየዕለቱ በየቤተ ክርስቲያኑ የሚቀርበው ቁርባን በዕለተ ዓርብ ከቀረበውና ከተፈጸመው መሥዋዕት ጋር ያለው ግንኙነትና ኅብረትስ ምንድን ነው? ይህን ለመረዳት ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል የጻፈውን በማስተዋል እንመልከት፡-

> ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው መልካም ነገር ሊቀ ካህናት ሆኖ በምትበልጠውና በምትሻለው <u>በእጆችም ባልተሠራች ማለት</u> <u>ከዚህ ፍጥረት ባልሆነች ድንኳን</u> የዘለዓለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም፡፡ ዕብ. 9፡11-12

"<u>ከዚህ ፍጥረት ባልሆነች ድንኳን</u>" ማለት ምን ማለት ነው? ከእግዚአብሔር ውጭ ያለው ነገር ሁሉ ከፍጥረት ወገን የሚመደብ አይደለምን? ታዲያ ይህ "ከዚህ ፍጥረት ያልሆነች" የተባለው ነገር ምንን ያመለክታል? "ከዚህ ፍጥረት ካይደለች ወይም ካልሆነች ድንኳን" የተባለው የሚያመለክተው ጌታችን ልዩ ሊቀ ካህናት ሆኖ ራሱን ቤዛ አድርጎ ያቀረበባት ዕለተ ዓርብ ስትሆን ያች ዕለት ምንም እንኳ በአንድ በኩል በዚህ ዓለም ባለው በተፈጠረው የጊዜ እቀጣጠር የምትመጣና የምትሄድ ብትሆንም በሌላ በኩል ደግሞ ጌታችን የፈጸመባት የማዳን ሥራ ግን የማያልፍና ዘለዓለማዊ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ስለዚህም በዕለተ ዓርብ የተፈጸመው መሥዋዕትነት ጊዜንና ዘለዓለማዊነትን አንድ አድርጎ የሚያገናኝ ልዩ ምሥጢር ነው፡፡ ያች ዕለት የጊዜንና የቦታን ውስንነት ያሸነፈ ልዩ ቤዛነት የተፈጸመባት ናት፡፡

በሥነ ፍጥረት መጀመሪያ ላይ የተፈጠረው ጊዜ የሚያልፍና የሚተካ ነው፡፡ ይህም ጊዜ በግሪኩ κρονος - ክሮኖስ የሚባለው ነው፡፡ ጊዜ ከመፈጠሩ በፊት የነበረው ደግሞ ከጊዜ ጽንሰ ሃሳብና ጊዜን ለመግለጽ ከምንጠቀምባቸው ቃላትና ሐረጎች ውጭ የሆነ ዘለዓለማዊነት ነው፡፡ ይህንም በግሪኩ καιρος - ካይሮስ - ይሉታል፡፡ ስለዚህ ያች ጌታችን ራሱን የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበባት ዕለት (ቅጽበት) ፍጡርና ኃላፊ በሆነውና እኛ በምናውቀው ጊዜ (κρονος - ክሮኖስ) ውስጥ ብትፈጸምም ድርጊቱ (የተፈጸመባት ድርጊት) ግን የማያልፍና ከጊዜ ውጭ ነው፣ ዘለዓለማዊ ነው፣ በጊዜ ውስጥ የማይወሰንና የማይገደብ (καιρος - ካይሮስ) ነው፡፡

ስለሆነም በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ የሚቀርበው መሥዋዕት ሌላ ወይም አዲስ መሥዋዕት ሳይሆን ጌታችን አንድ ጊዜ የፈጸመውና በዕለተ ዓርብ የቆረሰው ሥጋውና ያፈሰሰው ደሙ ነው፡፡ በየጊዜው በየቤተ ክርስቲያኑ በጸሎተ አኰቴት የሚከብረውና የሚለወጠው የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ከዚያች ከዕለተ ዓርብ ጋር የሚገናኝና አንድ የሚሆን ነው ማለት ነው፡፡ የእያንዳንዱ ጸሎተ ቅዳሴ ፈጻሚውና ቀዳሹም ራሱ ጌታችን ነው፡፡ ስለዚህም ቅዱስ ቁርባን መሥዋዕት ይባላል፡፡

ቅዱስ ቁርባን የጌታችን ቅዱስ ሥጋና ደም ምሥጢር በመሆኑ በየጊዜው የሚቀርበው መሥዋዕት በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ የራሱን ሥጋ በመቁረስ ደሙን በማፍሰስ ያቀረበው መሥዋዕት ነው፡፡ ቅዱስ ቁርባን ያን በዕለተ ዓርብ የተሠዋውን የጌታችንን ሥጋና ደም የምንቀበልበት ምሥጢር እንደ መሆኑ፣ ያ በዕለተ ዓርብ ጌታችን ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ማቅረቡ ደግሞ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረቡ በመሆኑና "መሥዋዕት" የሚባል በመሆኑ ቅዱስ ቁርባን መሥዋዕት መባሉ የተገባና ትክክል ነው፡፡

እንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ ላይ "ወብነ ምሥዋዕ - መሠዊያ አለን" ይላል፡፡ ዕብ. 13፥10 መሠዊያ የሚኖረውና የሚያስፈልገው መሥዋዕት ሲኖር ነው፡፡ መሠዊያ ያለ መሥዋዕት፣ መሥዋዕትም ያለ መሠዊያ አይሆንም፡፡ ስለዚህ አስቀድሞ በጸሎተ ሐሙስ ለደቀ መዛሙርቱ "ይህ ሥጋዬ ነው፣ ብሉ፤ ይህ ደሜ ነው፣ ጠጡ" ብሎ የሰጣቸውን ምሥጢር በማግስቱ በቀራንዮ ሥጋውን ቆርሶና ደሙን አፍስሶ ራሱን ልዩ መሥዋዕት አድርጎ አቅርቧል፡፡ እኛም ሌላ ያይደለ ያንኑ መሥዋዕት በመሠዊያው ላይ እናቀርባለን፡፡ ያን ጊዜ በጸሎተ ሐሙስ እንዳደረገው ዛሬም መሥዋዕቱን የሚያከብረውና የሚሰውጠው፣ መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርበውም እርሱው ራሱ ነው፡፡ስለዚህ ሐዋርያዊትና ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከእነ ቅዱስ ጳውሎስ ጋር ወብነ ምሥዋዕ - መሠዊያ አለን" ትላለች፡፡ የቅዱስ ቁርባንን አማናዊ መሥዋዕትነትም ታምናለች፡፡ ሐዋርያውም "መሠዊያ አለን" አለ እንጂ "መሠዊያ ነበር" አላለም፡፡

## 3.7.2.3.4.2 የቅዱስ ቁርባን መሥዋዕትነት በቀደምት አበው ትምህርት

ዕለት ዕለት በጸሎተ ኪዳን የምናቀርበው የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መሥዋዕት እንደሚባል፣ እንዲሁም እያንዳንዱን መሥዋዕተ ቁርባን የሚያከብረውና የሚፈጽመው ምንም እንኳ ተልእኮውን ሲያከናውን የሚታየን ካህኑ ቢሆንም ራሱ ባለቤቱ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በስፋትና በጥልቀት አስተምሯል፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን ትምህርቶቹን እንመልከት፡-

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ቅዱስ ቁርባን መሥዋዕት ስለ መሆኑና መሥዋዕት የሚባል ስለ መሆኑ በአጽንዖትና በተደጋጋሚ አስተምሯል፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን እንመልከት፡-

- "ቅዱስ ቁርባን መሥዋዕት ነው፤ ይህ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ገና ስለሚሰቀል አይደለም፤ በምሥዋዑ (በመሠዊያው) ላይ የቀረበውና የሚሠዋው ሥጋና ደም ያው አንድ ስለሆነ ነው እንጂ፡፡ ምሥዋዑም ሰማያዊው አምላክ በተዋሕደው ሥጋ የተኛበት የጌታችን ቅዱስ መቃብር ነው፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ዕብራውያን፣ ክፍለ ትምህርት፣ ቁ. 6)

- "ይህ እኛ የምናከብረው መሥዋዕት አሁንም ያው በጸሎተ ሐሙስ ጊዜ ጌታችን ራሱ የፈጸመው መሆኑን እመን፤ ይህ ከዚያ [በጸሎተ ሐሙስ ጊዜ ከነበረው] በምንም ምን የተለየ አይደለምና፡፡ ይህን ሌላ ሰው የሚፈጽመው፣ ያን ግን እርሱ ራሱ የፈጸመው አይደለምና፤ ይህም ያም ሁለቱም የእርሱ ሥራዎች ናቸው እንጂ፡፡ ስለዚህ ካህኑ እጁን ዘርግቶ ቅዱስ ቁርባንን ለአንተ ሲያቀብልህ ስታይ ይህን የሚያደርገው ካህኑ ነው ብለህ አታስብ፤ ወደ አንተ የተዘረጋው የራሱ የክርስቶስ እጅ ነው እንጂ፡፡

  "ያን ጊዜ በምሴተ ሐሙስ መሥዋዕቱን አክብሮ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው እርሱ አሁንም መሥዋዕቱን የሚያከብረው እርሱው ራሱ ነው፡፡ እኛ አገልጋዮች ነን፡፡ መሥዋዕቱን የሚቀድሳቸውና የሚለውጣቸው ያው አንድ እርሱው ነው፡፡ ይህ መሥዋዕትም እንደ ጸሎተ ሐሙሱ ያው ነው፤ በአንዳችም ነገር ያነሰና የተለየ ነገር የለውም፡፡ ያን (የጸሎተ ሐሙሱን) ያከበረውና የፈጸመው ክርስቶስ፣ ይኸን የሚፈጽመው ግን ሰው አይደለም፤

ይኽንም የሚያከብረውና የሚለውጠው እርሱ ነው እንጂ፡፡ ይህ (ቤተ ክርስቲያን) ጌታችን ከሐዋርያቱ ጋር እንደ ነበረበት ቤት ነው፡፡ ያን መሥዋዕት ያከበረው ክርስቶስ ይህንም የሚያከብረው እርሱው ነው፡፡ . . . ቆሞ የሚታየውና የሚላላከው ካህኑ ነው፤ ኃይሉና ጸጋው ግን የእግዚአብሔር ነው፡፡

"ታዲያ ይህ ምንድን ነው? በየቀኑ መሥዋዕት አናቀርብምን? አዎ፤ በርግጥም እናቀርባለን እንጂ፤ ሆኖም የምናቀርበው መሥዋዕት ሞቱን በማሰብ ነው፤ ይህ መሥዋዕትም አንድ ነው እንጂ ብዙ አይደለም፡፡ ብዙ ያይደለ አንድ የሚሆነው እንዴት ነው? ያ መሥዋዕት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንደ ተሠዋና ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ እንደ ገባ ይህ በየዕለቱ የምናቀርበው መሥዋዕትም ያን በዕለተ ዓርብ የቀረበውን መሥዋዕት ያንኑ ነው እንጂ ሌላ ወይም አዲስ መሥዋዕት አይደለም፡፡ ሁል ጊዜ የምናቀርበው መሥዋዕት ያው አንድ ነው እንጂ ዛሬ አንድ መሥዋዕት፣ ነገ ደግሞ ሌላ መሥዋዕት አይደለም፡፡ ሁል ጊዜ፤ ዛሬም ነገም አንድ ነው እንጂ፤ ስለዚህም መሥዋዕቱ ያው አንድ ነው፡፡

"እንዲህ ሆኖም ግን አሁንም መሥዋዕቱ በተለያዩ ቦታዎች (አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት) ስለሚቀርብ ብዙ ክርስቶሶች አሉን? በፍጹም! በየትም ቢሆን ክርስቶስ አንድ ነው፤ እዚህም በፍጹም ሙሉነት በእርሱነቱ አለ፤ እዚያም እንዲሁ እርሱው ራሱ እንበለ ሕጸጽ በምልዐት አለ፡፡ ስለሆነም በተለያዩ ቦታዎች ቢሠዋም አንድ አካል ነው እንጂ ብዙ አካል እንዳይደለ ሁሉ፤ እንደዚሁም እርሱ አንድ መሥዋዕት ነው፡፡ እኛን የሚያነጻንን መሥዋዕት ያቀረበው ሊቀ ካህናታችን እርሱ ነው፡፡ እኛ ዛሬ የምናቀርበው መሥዋዕት ያን ጊዜ የቀረበውን መሥዋዕት ነው፤ በየጊዜው ቢቀርብ አያልቅም፡፡ በየጊዜው የምናቀርበው መሥዋዕት ሌላ መሥዋዕት አይደለም፤ ሁል ጊዜ የምናቀርበው መሥዋዕት ያንኑ አንድ ጊዜ የቀረበውን መሥዋዕት ነው እንጂ፡፡"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ዕብራውያን፣ ክፍለ ትምህርት፣ ቁ. 6)

- "መንገድ ጠራጊው የነበረው ዮሐንስ መጥምቅ ለደቀ መዛሙርቱ 'እነሆ የእግዚአብሔር በግ' ባላቸው ጊዜ በዚህ አባባሉ ክርስቶስ ሊሰጠው ያለውን ጸጋ በሙሉ እና ሥርየተ ኃጢአትን የሚሰጥበትን መንገድም ጭምር አሳይቷቸዋል፡፡ "በግ" የሚለው እነዚህን ሁለቱንም በግልጽ ያሳያልና፡፡ እንዲሁም ዮሐንስ 'የዓለምን ኃጢአት ወደፊት የሚያስወግድ' ወይም 'የዓለምን ኃጢአት ያስወገደ' አላለም፤ ክርስቶስ ይህን ሁል ጊዜ የሚፈጽመው በመሆኑ 'የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ' አለ እንጂ፡፡ ኃጢአትን ያስወገደው ያን ጊዜ መከራ በተቀበለ ጊዜ ብቻ አይደለም፤ ከዚያን ጊዜ አንሥቶ እስካሁንም ድረስ ኃጢአትን ያስወግዳል እንጂ፡፡ ይህም ሁል ጊዜ እንደሚሰቀል ሆኖ ሳይሆን (አንድ ጊዜ ለኃጢአት መሥዋዕት ራሱን አቅርቦ ፈጽሟልና) በዚያው በአንዱ መሥዋዕት ኃጢአትን ሁል ጊዜ ሲያስወግድ ስለሚኖር ነው እንጂ፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌል ዮሐንስ፣ ክፍለ ትምህርት 18፣ ቁ. 2)

- "<u>ይህን መሥዋዕት</u> በተመለከተ ስላነሣሁ ወደዚህ ወደ ቅዱስ ቁርባን ምሥጢር ስለምትቀርቡት ስለ እናንተ አቀራረብ ሁኔታ ትንሽ ነገር ለማለት እወዳለሁ፡፡ አንዳንዶች <u>ከዚህ መሥዋዕት</u> <u>የሚቀበሉት</u> በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡ ሌሎች ሁለት ጊዜ፤ ሌሎች ደግሞ ብዙ ጊዜ ይቀበላሉ፡፡ ይህ አሁን የምንለው ቃል እዚህ ላሉት ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ነው፤ በበረሓ ለሚኖሩት ለባሕታውያንም ጭምር ነው፡፡ እነርሱ ከቅዱስ ምሥጢር የሚቀበሉት በዓመት አንድ ጊዜ፤ አልፎ አልፎም በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ ነውና፡፡ ታዲያ ጥሩ ነው ብለን የምናጸድቀው የትኛውን ነው? በዓመት አንድ ጊዜ የሚቀበሉትን? ወይስ ብዙ ጊዜ ደጋግመው የሚቀበሉትን? አንድ ጊዜ የሚቀበሉትንም አይደለም፤ ደጋግመው ብዙ ጊዜ የሚቀበሉትንም አይደለም፤ በጣም አልፎ አልፎ የሚቀበሉትም አይደለም፤ በንጹሕ ሕሊናና በንጹሕ ልብ፣ ነውርና ነቀፋ በሌለበት ሕይወት ሆነው የሚቀበሉትን እንጂ፡፡

"እንደዚህ ያሉት ሁል ጊዜ ወደ ቅዱስ ምሥጢር ለመቀበል ይቅረቡ፤ እንደዚህ ያልሆኑት ግን አንድ ጊዜም እንኳ ቢሆን አይቅረቡ፡፡ ለምን? ብለህ ትጠይቅ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ለራሳቸው ፍርድን፣ ኩነኔን፣ ቅጣትንና ፍዳን ስለሚቀበሉ ነው፡፡ በዚህም አታድንቅ፡፡ በተፈጥሮው ለሰውነት ሕይወት ጠቃሚ የሆነው ምግብ እንኳ የምግብ ፍላጎት በሌለውና ጤነኛ ባልሆነ ሰው ከተወሰደ ሕዋሳቱን እንደሚያናውጸውና በበሽታ ላይ በሽታ የሚጨምርበት ምክንያት እንደሚሆን ሁሉ ገናና እና አስፈሪ በሆኑት ቅዱሳት ምሥጢራትም እንደዚሁ ነው፡፡ መንፈሳዊው ከሆነው ከንጉሡ ማዕድ ከተመገብህ በኋላ እንደገና እንደበትህን መልሰህ በከንቱ ነገር ታረክሰዋለህን? ራስህን በጣፋጩ ዘይት ከቀባህ በኋላ መልሰህ በመጥፎ መዓዛ ታቆሽሻለህን?" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ. ወርቅ፣ ትርጓሜ ዕብራውያን፣ ክፍለ ትምህርት 17፣ ቁ.6-7)

- "ጌታችን ተሠውቶ በምሥዋዑ (በመሠዊያው) ላይ ተኝቶ ስታየው፣ ካህኑ ቆሞ በመሥዋዕቱ ላይ እየጸለየ ስትመለከተው፣ ምእመናን ሁሉ በዚያ በከበረው ደሙ እየተነዘ ስታይ፣ አንተ ገና ከሰዎች መካከል እንዳለህ ታስባለህን? በምድር ላይ ያለህስ ይመስልሃን?" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ. ወርቅ፣ በእንተ ክህነት፡ መጽሐፍ 4)

አሁንም ይኸው ቅዱስ አባት ሕዝቡ ትምህርቱን ሰምተው በተግባር በሕይወታቸው ባለመተግበራቸውና ወደ ቅዱሱ መሥዋዕት ወደ ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል ባለመቅረባቸው እያዘነ እንዲህ ይላል፡-

- "በየቀኑ <u>መሥዋዕቱ</u> መቅረቡ በከንቱ ነው፣ እኛ በምሥዋዑ ፊት መቆማችን ለከንቱ ነው፤ ምክንያቱም <u>ከመሥዋዕቱ የሚቀበል</u> ማንም ሰው የለምና፡፡ ይህን የምለው እንዲሁ ዝም ብላችሁ ሳትዘጋጁ ለመቀበል እንድትቀርቡ አይደለም፣ ራሳችሁን ለመቀበል ታዘጋጁ ዘንድ ነው እንጂ፡፡ ከዚህ <u>መሥዋዕት</u> ለመቀበል ብቁ አይደለህምን? እንዲህ ከሆንክ ለመቀበል ትችል ዘንድ ራስህን አዘጋጅ" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ. ወርቅ፡ ትርጓሜ መልእክተ ኤፌሶን፡ ክፍለ ትምህርት 3)

- "[ካህኑ] መንፈስ ቅዱስን ሲጠራ፣ እና እጅግ <u>አስፈሪ የሆነውን መሥዋዕት ሲሠዋ</u>፣ በየጊዜው የሁላችንን ጌታ በእጁ የሚዳስሰውን እርሱን ምን መዓርግ ነው የምንሰጠው? ምን ያህል ታላቅ ንጽሕናና ምን ያህል እማናዊ የእምነት ሰው መሆንን እንጠብቅበት ይሆን? . . ."[78] (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ. ወርቅ፣ በእንተ ክህነት፣ መጽሐፍ 6፣ ቁ. 4)

ይህን ምሥጢርም በታላቅ ጥንቃቄና ዝግጅት ሆኖ መቀበል እንደሚገባ አባቶቻችን ያስተማሩትን ትምህርት ከላይ የተመለከትን ሲሆን ከተቀበልን በኋላም ለተቀበልነው ታላቅ ጸጋ ተገቢ በሆነ መንገድ መኖርና መጠንቀቅ የሚገባን ስለ መሆኑ መጽሐፍ ቅዱስና የቤተ ክርስቲያን አባቶች በአጽንኦት ያስተምራሉ፡፡

ለአብነትም ከቅዱስ ሥጋውና ከክቡር ደሙ ከተቀበሉ በኋላ ሁሉንም ነገር በጥንቃቄና በአግባብ ማድረግ የሚገባ ስለመሆኑ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዲህ ይላል፡-

- "እነዚህን ነገሮች እኛ ሁላችንም እንስማ፡ ወደዚህ ቅዱስ ምሥዋዕ ከድሆች ጋር በአንድነት እንቀርባለን፣ ነገር ግን ከዚህ ከወጣን በኋላ ከእነርሱ (ከድሆች) ጋር እንኳን ከአንድ ማዕድ የተቀበልን ልንመስል ቀርቶ ፈጽሞ አይተናቸው የምናውቅ እንኳ አንመስልም፡፡ እኛ ከመጠን በላይ እየበላንና እየጠጣን የተራቡትን አይተን እንዳላየናቸው እናልፋቸዋለን፡፡

[78] (And whenever he invokes the Holy Spirit, and offers the most dread sacrifice, and constantly handles the common Lord of all, tell me what rank shall we give him? What great purity and what real piety must we demand of him? For consider what manner of hands they ought to be which minister in these things, and of what kind his tongue which utters such words, and ought not the soul which receives so great a spirit to be purer and holier than anything in the world?)

ይህን የምናደርገው መቼ ነው? ትሉ እንደ ሆነ ሁል ጊዜ ነው፤ በተለይ ግን እንደዚያ ሊደረግ በማይገባባቸው በበዓላት ቀናት ላይ አብዝታችሁ ታደርጉታላችሁ፡፡ በበዓላት ቀናት ከቅዱስ ቁርባን ከተቀበላችሁ በኋላ ድሆችን መናቅ፣ አብዝቶ መብላትና መጠጣት አይታይባችሁምን? ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ከተቀበላችሁ በኋላ በመጠኑ እህል ውኃ ቀምሳችሁ ያገኛችሁትን ጸጋ በማሰብ በተዘክሮ ልትሆኑ ሲገባችሁ እናንተ ግን ራሳችሁን ለወይንና ለዋዛ ለፈዛዛ ለጨዋታ አሳልፋችሁ ትሰጣላችሁ፡፡ እንዲያው በጠዋት በአጋጣሚ በጣም ጥሩ የሆነ ምግብ በልተህ ከሆነ ከዚያ በኋላ ጣዕም የሌለው ሌላ ነገር በልተህ የዚያን የጠዋቱን ምግብ ጣዕም እንዳታጠፋውና እንዳታጣው አትጠነቀቅምን? አሁን በመንፈስ ቅዱስ በዓል አድርገህ ከሰማያዊ ማዕድ ተሳትፈህ ስታበቃ እንደገና ሰይጣናዊ የሆነ ተድላና ደስታን ታደርጋለህ፡፡

"ሐዋርያት ቅዱስ ቁርባንን ከተቀበሉ በኋላ ምን አደረጉ? ወደ ጸሎትና ዝማሬ የሄዱ አይደለምን? ወደ ትጋህ፣ ራስን በመካድ ላይ ወደ ተመሠረተው ወንጌልን የማስተማር ረጅምና ከባድ ሥራ የገቡ አይደለምን? ሊሰቅሉት ያላቸውን ሰዎች ይጠራቸው ዘንድ ይሁዳ ከእነርሱ ተለይቶ ከወጣ በኋላ እነዚያን ታላላቅና ድንቅ የሆኑ ምሥጢራትን ያን ጊዜ አሳይቷቸዋልና፣ ሰጥቷቸዋልና፡፡ ከቅዱስ ቁርባን የተሳተፉት ሦስቱ ሺህ ሰዎች የመብልና የመጠጥ፣ የጨዋታና የዋዛ የፈዛዛ በዓላት በማድረግ ሳይሆን በጸሎትና ቃሉን በመማር እንደ ቀጠሉና እንደ ጸኑ አልሰማህምን? ከዚህ ምሥጢር ለመቀበል እንደ ዓቅማችሁ በተወሰነ መጠን የበቃችሁና የተዘጋጃችሁ ትሆኑ ዘንድ ከመቁረባችሁ በፊት ትጾማላችሁ፤ ይህ መልካምና ተገቢ ነው፡፡ ነገር ግን ከተቀበላችሁ በኋላ የበለጠ ልትጨምሩና ልትሻሻሉ ሲገባችሁ አስቀድሞ የደከማችሁትን ድካምና ያደረጋችሁትን ነገር ሁሉንም መልሳችሁ ገደል ትከቱታላችሁ፡፡ ከመቀበላችን በፊትም ሆነ በኋላ በጥንቃቄና በአግባቡ መኖር ክርስቲያናዊ ኃላፊነታችንና ተግባራችን ነው፡፡ ከመቀበላችን በፊት ለመቀበል የምንችልና የተገባን ሆነን እንቀርብ ዘንድ ነው፣ ከተቀበልን በኋላ ደግሞ ለተቀበልነው ጸጋ ያልበቃንና የማይባን ሆነን እንዳንገኝ ነው፡፡

" . . . ቅዱስ ጳውሎስ 'ቅምጥሊቱ ግን በሕይወት ሳለች የሞተች ናት' በማለት እንዳስተማረን ማንም ሰው በቅንጦትና በቅምጥልነት መኖር የማይገባው ከሆነና ይህ በሌላ በማንኛውም ጊዜ ሲደረግ ጎጂና ገዳይ ከሆነ ከቅዱሳት ምሥጢራት ከተቀበልን በኋላ ሲደረግ ደግሞ በእጅጉ የበለጠ ጎጂና ገዳይ ነው፡፡ 1 ጢሞ. 5፥6 የሕይወትን ምግብ ከተመገብህ በኋላ የሞት ድርጊት ስታደርግ አትፈራምን? አትንቀጠቀጥምን? በድሎትና በቅንጦት ምን ያህል ታላላቅ ክፉ ነገሮች እንደሚመጡ አታውቅምን? ቅጥ የሌለው ሳቅ ስላቅ፣ ዋዛ ፈዛዛ፣ ሌሎች ለመናገር የሚያሳፍሩ እጅግ ብዙ የሆኑ ነገሮች ሁሉ፤ እነዚህን ነገሮች የክርስቶስን ማዕድ ከተሳተፍክ በኋላ፣ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለመቀበልና በምላስህ ለመንካት የተገባህ ሆነህ በተቆጠርህበት በዚያው ዕለት እንደገና እንዲህ ያለውን ነገር ታደርጋለህ፡፡ ታዲያ እነዚህን ነገሮች ለማስቀረት ሊደረግ የሚገባው ምንድን ነው? እጅህን፣ እንደበትህን፣ ከንፈሮችህን አንጻ፡፡ ሐሊናህን ጌታችን ቅዱሱን ምሥጢር ለሐዋርያት ሲሰጣቸው እነርሱ ወደ ነበራቸው ትጋሃ ሌሊትና ጸሎት፣ የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ወደሚቀርብበት ቅዱስ ምሥዋዕ ከፍ አድርገው፡፡ በዓላት የተሠሩት ያለፉ ኃጢአቶቻችንን እንድናስወግድባቸው ነው እንጂ አዳዲስ ኃጢአቶችን እንድናከማችባቸውና ከአግባብ የወጡ ነገሮች እንድናደርግባቸው አይደለምና፡፡"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ቆሮንቶስ ቀዳማዊ፣ ክፍል ትምህርት 27. ቁ.7)

ቅዱስ ቁርባን መሥዋዕት መሆኑንና መሥዋዕትም እንደሚባል ሌሎቹ ቅዱሳን አባቶችም እንዲሁ አስተምረዋል፡፡

- "አሁን ይህ መሥዋዕት [ቅዱስ ቁርባን] የሚቀርበው በኦሪቱ ሕግ መሠረት አይደለም፤ በመንፈስ ቅዱስ በሚደረገው በአዲስ ኪዳን እንጂ፤ እግዚአብሔርን 'በመንፈስና በእውነት እናመልከው' ዘንድ ይገባናልና፡፡ ስለዚህም የቅዱስ ቁርባን መሥዋዕት ሥጋዊ አይደለም፤ መንፈሳዊ እንጂ፡፡ ኅብስቱንና ወይኑን ለመሥዋዕት አዘጋጅተን ስናቀርብ ምድርን ለእኛ ጥቅም ሲል እንደዚህ ያሉ ፍሬያትን ታስገኝ ዘንድ አዝዟታልና እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን፡፡ ከዚያም መሥዋዕቱን አዘጋጅተን ስንጨርስ ኅብስቱን የክርስቶስ ሥጋ፣ ወይኑን ደግሞ የክርስቶስ ደም ያደርገው ዘንድ መንፈስ ቅዱስን እንለምነዋለን፣ ይህም ይህን የሚቀበሉት የኃጢአትን ሥርየትና ዘላለማዊ ሕይወትን ያገኙ ዘንድ ነው፡፡ (ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ በእንተ መናፍቃን፣ መጽሐፍ 5፣ ምዕራፍ 2፣ ቁ. 37)

ቅዱስ ሄሬኔዎስ "ኅብስቱና ወይኑ ተለውጦ የክርስቶስ ሥጋና ደም አይሆንም፣ ጸጋም አያፅጥም" ይሉ የነበሩትን መናፍቃን እንደዚህ የሚሉት እግዚአብሔር የእጁ ሥራ በሆኑት በሥነ ፍጥረታት አማካይነት ሥራውን አይሠራም የሚሉና ለቁሳዊ ፍጥረታት ጥላቻና ንቀት የነበራቸው ግኖስቲካውያን መሆናቸውን በመግለጽ ይገሥጻቸው ነበር፡፡ የቅዱስ ቁርባን መሥዋዕት የአሠራር ምሥጢር እግዚአብሔር ሥራውን በሥነ ፍጥረት አማካይነት እንደሚሠራና ፍጥረት ርኩስ ወይም የተዋረደ አለመሆኑን የሚያስረዳ ነው ይላል፡፡ ምክንያቱም ከምድር ፍሬ ከሆነው ስንዴና ወይን ተለይቶ መሥዋዕት ይሆን ዘንድ ይቀርባል፡፡ ከዚያም ከምድር ፍሬ ከተገኘው ተለይቶ ለእግዚአብሔር የቀረበውን እርሱ ተቀብሎ ይባርከውና ያከብረው ዘንድ፣ ይለውጠውና ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ያደርገው ዘንድ እርሱን ስሙን በጸሎተ ቅዳሴ እንጠራለን፡፡ እርሱም ለሐዋርያት አድርጎ እንዳሳያቸው እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ያንኑ እንደ ተስፋ ቃሉ ሲያደርገው ይኖራል፡፡ ይህን ምሥጢር አይቀበሉ የነበሩትን መናፍቃን ቅዱስ ሄሬኔዎስ ግኖስቲካውያን መሆናቸውን እንደ ነገረን ዛሬም ይህን የእግዚአብሔርን አሠራር የሚንቁና የማይቀበሉ መናፍቃን ግኖስቲካዊ እርሾ ያለባቸው ናቸው፡፡

ይኸው አባት ስለዚህ ድንቅ ምሥጢር እንዲህ ይላል፡-

- "...ስለዚህም የቅዱስ ቁርባን መሥዋዕት ሥጋዊ አይደለም፣ ገናና የሆነ መንፈሳዊና ንጹሕ መሥዋዕት ነው እንጂ፡፡ መሬት እነዚህን ነገሮች ታፈራ ዘንድ አዝዟታልና እግዚአብሔርን እያመሰገንን ኅብስተ በረከትንና ጽዋዐ አኰቴትን ይህን ላደረገው ለአምላካችን መሥዋዕት አድርገን እናቀርብለታለን እንጂ፡፡ መሥዋዕቱን እንደሚገባ አዘጋጅተን በንጽሕናና በጥንቃቄ ካቀረብን በኋላ ኅብስቱን የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋ፣ ወይኑን ደግሞ የክርስቶስ ክቡር ደም ያደርገው ዘንድ መንፈስ ቅዱስን እንጠራዋለን፤ ይህም ሥጋውንና ደሙን የሚቀበሉ የኃጢአት ሥርየትንና ዘለዓለማዊ ሕይወትን ያገኙ ዘንድ ነው፡፡ ይህን መሥዋዕት ጌታን በማሰብ የሚፈጽሙ ሰዎች የጥበብ ልጆች ይባላሉ፡፡" (ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ ቅሪታት፣ ቁ. 37)

- "እስኩኬ ንርአዮ ለዘይመስል እሳተ ለሕርደት መንፈሳዊ ወለጥብሕ ነባቢ ይደመር ላዕለ ዝንቱ አኰቴት ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም፡፡ - እሳት የሚመስል መንፈሳዊና ነባቢ መሥዋዕትን እስኪ እንየው፤ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ በመሥዋዕቱ ላይ ይደር፣ ለዘለዓለሙ፡፡" (ቅዳሴ ዘቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ ቁ. 156)

- "ይህን ንጹሕ ቅዱስ መሥዋዕት በፊትህ እናቀርብልሃለን፡፡ . . ." (ቅዳሴ ዘቅዱስ ቄርሎስ፡ ቁ. 37)

- "አሚነነ በአብ ኪያሁ ንሰብሕ አሚነነ በወልድ ኪያሁ ንአኩት አሚነነ በመንፈስ ቅዱስ ሎቱ ንፌኑ ሰብሐተ እንዘ ንትሜጦ በአሚን እምዝንቱ ኅብስት ሥጋሁ ቅዱስ ለኢየሱስ ክርስቶስ ዘያስተፌሥሕ ልበነ ወይሠሪ ለነ ኃጢአተነ ወያነጽሐነ እምጌጋይነ ወያነሥአነ እምነ ሙታን በዕለተ ሰንበት በዓባይ ዕለት ናዓርግ ለከ እግዚኦ መሥዋዕተ ጽድቅ ዘሐዳስ ሥርዓት - በአብ አምነን እርሱን እናመሰግናለን፣ በወልድ አምነን እርሱን እናመሰግናለን፣ በመንፈስ ቅዱስ አምነን ለእርሱ ምስጋናን እናቀርባለን፤ ልባችንን ደስ ከሚያሰኘውና ኃጢአታችንን ከሚደመስስልን፣ ከበደላችን ከሚያነጻን፣ በታላቂቱ ዕለት በዕለተ ሰንበት ከሙታንም ከሚያስነሣን፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋው ከሆነው ከዚህ ኅብስት በእምነት እየተቀበልን እርሱን እናመሰግናለን፣ የሐዲስ ሥርዓት የሆነውን <u>እውነተኛ መሥዋዕትም</u> እናቀርብልሃለን፡፡" (ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘአስተምህሮ)

## 3.7.2.3.4 ምሥጢራት - ማጠቃለያ

እስካሁን እንደ ተመለከትነው ተሐድሶዎች ስለ ምሥጢረ ቁርባን የሚያስተምሩት ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፣ እንዲሁም በቀደምት ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ትምህርት ሚዛንነት ሲመዘን ፍጹም ተቃራኒና ባእድ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የእነርሱ ትምህርት ፍጹም ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ የለየለት የክህደት ትምህርት ሰዎች እግዚአብሔር በማይነገር ቸርነቱ ልዩ ጸጋ አድርጎ የሰጠውን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን በልተውና ጠጥተው የዘለዓለም ሕይወትን እንዳያገኙ ለማድረግ ሰይጣን ያሰማራቸው የልቡሳነ ሥጋ አጋንንት ተግባር እንጂ የሰው ሥራ ነው ብሎ ለማመን ይከብዳል፡፡ እንዲህ ካልሆኑ በስተቀር ይህን የመሰለ ተቃርኖና ድፍረት እንዴት ሊናገሩ ቻሉ? እምነትን እናተስምራለን፣ ኑፋቄን እንዋጋለን በሚል ሽፋን ይህን ያህል ዓይን ያወጣ የሞት ትምህርትን ይሰብካሉ፤ ያውም "ኦርቶዶክሳውያን ነን" በሚል ድፍረት!

ጥንቱንም ቢሆን መናፍቃን ኑፋቄያቸውን የሚሰብኩትና የሚነዙት እምነትን እንጠብቃለን፣ ኑፋቄን እንቃወማለን በሚል ሽፋን እንደ ነበር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስተምረናል፡፡ ለምሳሌም የሙሴ ሕግ (ኦሪት) እና የብሉይ ኪዳን ትምህርት ከወንጌል ጋር ተቃራኒ ናቸው ብሎ ያምንና ያስተምር የነበረው መርቅያን የተባለውና በሁለተኛው መቶ ዓመት የተነሣው አደገኛ መናፍቅ ቤተ ክርስቲያን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በመቀበሏ አጥብቆ ይወቅሳትና ይወነጅላት ነበር፡፡ መርቅያን "ሐዋርያት ጌታ ያስተማረውን ትምህርትና ሃይማኖት አበላሽተውታል፣ በርዘውታል" እያለ አምርሮ ይቃወማቸው ነበር፡፡ ራሱን እውነተኛውን የክርስቶስ ትምህርት ለመመለስና ቤተ ክርስቲያንን ለማደስ የተላከ አድርጎም ይቆጥር ነበር፡፡

መርቅያንን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አውግዛ ብትለየውም ብሕትውናንና ትህርምትን ይሰብክና እርሱም ጽኑ ባሕታዊና ተሐራሚ ስለ ነበር ብዙ ሞኛ ሞኝ የሆኑ ሰዎችን ለመማረክና ራሱን የቻለ አንጃ ለመመሥረት ችሎ ነበር፡፡ መናፍቃን ከጥንትም ጀምሮ ግብራቸው እንደዚህ ነው፡፡ ጌታችን ፈሪሳውያንን "አሌ ለክሙ አምሕርት ዕውራን እለ ትመለ ትውኅጡ ወጻጹተ ትነጽፉ - እናንተ ዕውሮች መሪዎች፣ ትንኝን የምታጠሩ ግመልንም የምትውጡ" እንዳላቸው እንደ ትንኝ ያነሱ ነገሮችን በማንሣት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን ለመንቀፍና ለማሳጣት የሚሞክሩት እንደ ግመል የገዘፈ ኑፋቄያቸውን አሾልከው ለማስገባትና ዋናውን የመዳንን ነገር ከምእመናን ልቡና ለማስወጣትና ወደ ሞት ጎዳና ይዞ ለመሄድ እንዲያመቻቸው ነው፡፡ ማቴ. 23፡24

በመጽሐፍ ቅዱስ ጌታችን ያስተማረው ትምህርት፣ እንዲሁም ከባለቤቱ የተቀበሉትን እውነተኛ የሕይወት ትምህርት አጽንተው በያዙ በቅዱሳን አባቶቻችን ትምህርት የተገለጠው እውነታ ግን ኅብስቱ ተለውጦ እማናዊ የጌታችን ቅዱስ ሥጋ፣ ደሙም ተለውጦ እማናዊ የጌታችን ክቡር ደም የሚሆን መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የሆነና ይህን የሚቃወም ትምህርት ግን ጠላት የዘራው እንክርዳድ ነው፡፡ የምሥጢረ ቊርባንን እማናዊነት የማይቀበሉና ከላይ የተገለጸውን ያን ሁሉ የማይገባ የክህደት ነገር በቅዱስ ሥጋውና በክቡር ደሙ ላይ የሚናገሩ ተሐድሶዎች ክርስቲያን ተብለው ለመጠራትም አይችሉም፤ የክርስትና መሠረት የሆነውን የጌታችንን መሠረታዊ ትምህርቶችና ምሥጢራትን አይቀበሉምና፡፡ በምሥጢረ ጥምቀት ሥርየተ ኃጢአት፣ ልጅነትና ሌሎቹም ጸጋዎች እንደሚገኙ የማያምኑ፤ ምሥጢረ ሜሮንን አምርረው የሚኰንኑ፤ የምሥጢረ ቊርባንን እማናዊ የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋነትና ክቡር ደምነት የማይቀበሉ፤ መሥዋዕት አይደለም፣ አይባልም የሚሉና መልሰው ሊናገሯቸው የሚዘገንኑ ነገሮችን በድፍረት የሚሉ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ከማይቀበሉ ከአሕዛብ የሚለዩት በምንድን ነው? ሰውን ክርስቲያን የሚያደርጉት እነዚህ ምሥጢራት አይደሉምን?

በእነርሱ የትምህርት መንገድ የሚሄድ ሰው ካለ በጥምቀት፣ በሜሮንና በቊርባን የሚገኘውን ጸጋ እያቃለሉና ለመዳን ጥቅም የሌላቸው መሆናቸውን እየሰበኩ ከእነዚህ የእግዚአብሔር የመዳን ጸጋ ከሚተላለፍባቸው መንገዶች እየለዩ ወደ ሞት ይወስዱታሉ፡፡ ጌታችን በወንጌል እነርሱ በሞት መንገድ ላይ ሆነው ሳለ ሌሎችን ወደ እነርሱው የሞት መንገድ ለመሳብና አጥፍቶ ለመጥፋት ፈሪሳውያን ያደርጉት የነበረውን ሩጫ በተመለከተ "እናንተ ግብዞች ጸፎችና ፈሪሳውያን፣ አንድ ሰው ልታሳምኑ በባሕርና በደረቅ ስለምትዞሩ፤ በሆነም ጊዜ ከእናንተ ይልቅ ሁለት እጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ ስለምታደርጉት ወዮላችሁ" በማለት የተናገረው ወዮታ በእነዚህ አሳሻች ወገኖቻችንም ደረሰባቸው። ማቴ. 23፡15

የተሐድሶዎች ትምህርት ጸረ መጽሐፍ ቅዱስ የሆነ፣ እግዚአብሔር እንድንበት ዘንድ ካሳየን መንገድና ምሥጢራት የሚያለያይና ወደ ሞት የሚመራ ነው፡፡ ከኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያላቸው መሠረታዊ ልዩነትም ይህን የመዳን መንገድ ከንቱ ለማድረግ የሚስተምሩት የስህተትና የፈጠራ ትምህርት ነው፡፡ እስኪ "ወደዚህ ገበታ አንዳች ለመቀበል አንመጣም፡፡ የጌታ እራት ጸጋን የምንቀበልበት ምስጢር አይደለም፡፡" ከማለት በላይ ክህደት ምን ይምጣ? ጌታችን በማይታበል ቃሉ "ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ" ብሎ አስተማረን፤ ሐሳውያን ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ ያስተምራሉ፡፡ ጌታችን "ሰው ከውኃና ከምፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም" ብሎ አስተማረ፡፡ እነርሱ ደግሞ "ጥምቀት ወደ መንግሥተ ሰማያት ከመግባት ጋር አንዳች ግንኙነት የለውም" ብለው ያስተምራሉ፡፡ ታዲያ እነዚህ ክርስቶስን የሚያሳብሉ ሐሰተኞች ክርስቶሶች አይደሉምን? "የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ፣ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ" የተባሉት እነዚህ ካልሆኑ ማን ሊሆን ነው? ማቴ. 7፡15 ራሱ ጌታችን "ምን እንድትሰሙ ተጠበቁ" ብሎ አስጠንቅቆናልና የሚሰማውን መምረጥ የእያንዳንዱ ሰው ድርሻና ኃላፊነት ነው፡፡ ማር. 4፡24

በአጠቃላይ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ቤዛነት የተገኙት የመዳን ጸጋዎች ተጠብቀው የሚገኙባቸውና እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ለሚኖሩ ሰዎች የሚሰጡባቸው መንገዶች ናቸው፡፡ ለስም አጠራሩ ለአምላክነት ክብሩ ምስጋና ይግባውና መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠን መዳን እስከ ዕለተ ምጽዓት ድረስ ለሚኖረው ለእያንዳንዱ ሰው የሚደርስለትና የሚፈጸምለት በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ነው፡፡

ጌታችን ራሱን በእረኛ መስሎ ባስተማረበት ትምህርት *"በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፤ ይገባልም ይወጣልም፣ መሰማሪያም ያገኛል"* ሲል የተናረው ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን እንደሚመለከት መምህራነ ወንጌል ገልጸዋል፡፡ ዮሐ. 10፡9 *"በእኔ ይገባል"* ማለት በምሥጢራት አማካይነት ወደ መዳን - ወደ እርሱ (ወደ ክርስቶስ) አንድነት ይገባል ማለት ነው፡፡ በጥምቀት፣ በሜሮን፣ በቁርባን አማካይነት ወደ መዳን፣ ወደ ሕይወት ይገባል፡፡ *"ይገባልም ይወጣልም"* ማለትም ከዚህ ዓለም ሕይወት ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚሄደውም በእነዚህ ምሥጢራት አማካይነት ነው፡፡

በምሥጢረ ጥምቀት ሥርየተ ኃጢአትን፣ ልጅነትን፣ በክርስቶስ በሞቱ መሳተፍንና ክርስቶስን መልበስን ገንዘብ እናደርጋለን፡፡ በምሥጢረ ሜሮን ደግሞ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ያድርብናል፣ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ቤት እንሆናለን፡፡ በቅዱስ ቁርባን ምሥጢር ለኃጢአታችን መሥዋዕት ሆኖ የቀረበውን የራሱን የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም እንበላለን እንጠጣለን፣ በዚህም የዘለዓለምን ሕይወት እናገኛለን፣ ክርስቶስን እንዋሐዳለን፡፡ በአጠቃለይ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚፈጸሙት ምሥጢራት ዓላማቸውና አፈጻጸማቸው ሁሉ ከመዳናችን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት እንዲህ ይላል፡- "ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ አጠቃላይ የሆነውን የሰውን ልጆች መዳን የፈጸመ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ያን አጠቃላይ ድኅነት እያንዳንዳችን ገንዘብ የምናደርግበትን ሁናቴ የሚሰጠን ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ክርስቶስ በአጠቃላይ ለሁሉም የፈጸመውን ማዳን መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ ይፈጽማል" ይላል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ይኸን ሥራውን የሚፈጽምባቸው መንገዶች ደግሞ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ናቸው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ በጥምቀት አማካይነት በሐዲስ ተፈጥሮ እንፈጠራለን፣ የክርስቶስ አካላት ሆነንም እንሠራለን፡፡ 1 ቆሮ. 12፡12 ፤ ኤፌ. 4፡3-5 ፤ ገላ. 3፡27 ፤ ሮሜ 6፡3 በቅዱስ ቁርባን ደግሞ በሥጋዌው፣ በሞቱ፣ በትንሣኤውና በዕርገቱ ከተገኘው መዳን እንሳተፋለን፡፡

ቀዳማዊና ዘለዓለማዊ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል የእኛን ባሕርይ ተዋሕዶ የራሱ አካልና ባሕርይ ያደረገበት የተዋሕዶ ምሥጢር በእኛነታችን ላይ ያስከተለው ትርጉምና ለእኛ የሰጠን ጸጋ እጅግ በጣም ጥልቅ ነው፡፡ ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ በየዘመናቱ የነበሩት አባቶቻችን ይህን የምሥጢረ ተዋሕዶ አስተምህሮ ከመናፍቃን ብረዛና ሥርዋጽ ለመጠበቅ ብዙ ዋጋ የከፈሉት ያለ ምክንያት አልነበረም፡፡ አካላዊ የእግዚአብሔር ቃል የእኛን ባሕርይ የራሱ አድርጎ መዋሐዱና በተዋሕዶ አንድ አካል፣ አንድ ባሕርይ የሆነ ሥግው ቃል መሆኑ በሰው ልጅ አጠቃላይ የወደፊት ተስፋና መዳንን ገንዘብ አደራረግ መንገድ ሁሉ ጥልቅና ዘላቂ የሆነ አንድምታ አለው፡፡ መዳንን ገንዘብ የምናደርገው እንዲሁ አፍአዊ (ውጫዊ) በሆነ መንገድ ሳይሆን፣ በማመን ብቻ ሳይሆን፣ ከዚህ ያለ መለያየትና ያለ መለወጥ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ከተዋሐደው የሰው ባሕርይ (ትስብእት) ጋር በጥምቀት፣ በሜሮንና በሥጋውና በደሙ በመሳተፍ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ባሕርይ ሆኖ በመዋሐዱ ኃጢአትንና ሞትን ድል ካደረገው ከዚህ ከአዲሱ የሰው ባሕርይ ጋር ስንዋሐድ ነው እኛም ሞትንና ኃጢአትን ድል ማድረግንና ዘለዓለማዊ ሕይወትን ገንዘብ ማድረግ የምንችለው፡፡ መዳንን የምናገኘው እንዲሁ በማመን ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ የልጁ አካል ሆነን እንሠራ ዘንድ ከእርሱ ጋር በሚያዋሕደን መዋሐድ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ያለ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚፈጸም አይደለም፡፡

የማይሞትና ዘለዓለማዊ የሆነው አካላዊ ቃል ሞትና መለወጥ የሚስማማውን የእኛን ባሕርይ ገንዘቡ አድርጎ እስከ መዋሐድ ያደረሰው ምክንያት ይኸው ነው፤ የደከመና በሞት የተያዘ ባሕርያችንን ከራሱ ባሕርይ ጋር አንድ አድርጎ በማዋሐድ የእርሱ የራሱ ገንዘቡ በማድረግ እኛም ከዚህ ከእርሱ ጋር አንድ ከሆነው አዲስ ሰብእና ጋር በሚኖረን ሱታፌና ኅብረት አማካይነት አምላክነቱ ለትስብእቱ የሰጠውን ሕያውነትና ጸጋ ሁሉ እናገኝ ዘንድ ነው፡፡ ዘለዓለማዊ ሕይወት ያለው በዚህ አካል እና በአዲሱ ሰውነት ነው፡፡

ቅዱስ ቄርሎስ ወደ ንስጥሮስ ከላካቸው አሥራ ሁለት ጥልቅ ነገረ ተዋሕዶን የሚገልጹ ቃለ ግዝቶች መካከል አሥራ አንደኛው እንዲህ የሚል ነው፡-

> . . . ሕይወትን ሰጪ የሆነው (ሕይወትን የሚሰጠው) የክርስቶስ መለኮታዊ ባሕርዩ ብቻ አይደለም፣ የእግዚአብሔር ቃል የራሱ ገንዘብ ያደረገውና ከራሱ ጋር አንድ አካልና አንድ ባሕርይ ያደረገው ከመሆኑ የተነሣ የተዋሐደው ትስብእትም ሕይወትን ሰጪ ነው እንጂ፡፡ ይህን የማያምን ቢኖር የተወገዘ ይሁን፡፡[79]

የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ አፍአዊ (ውጫዊ) ሳይሆን ውሳጣዊ (አካላዊና ባሕርያዊ) እንደ ሆነ ሁሉ መዳናችን የሚፈጸመውም እንዲሁ ውጫዊ በሆነ መንገድ ሳይሆን በጥምቀትና በሜሮን እንዲሁም በሥጋውና በደሙ ከዚህ አካላዊ ቃል ገንዘቡ ካደረገው ከአዲሱ ሰው ጋር በመሳተፍና በመዋሐድ (አንድ በመሆን) ነው፡፡ ከዚህ ውጭ እንዲሁ ዝም ብሎ "አምኛለሁ" በማለት ብቻ መዳን አይገኝም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፣ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፣ በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ" በማለት የገለጸው ይህን ድንቅ ምሥጢር ነው፡፡ ኤፌ. 2፡20-22

ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ ስለ ምሥጢረ ተዋሕዶ ሲናገር እንዲህ አለ፡-

> ባሕርየ እግዚአብሔር (አምላክነት) አንድ ነገር ነው፣ ባሕርየ ሰብእ (ትስብእት) ደግሞ ሌላ ነገር ነው፣ እያንዳንዳቸውም የየራሳቸው አኗኗር አላቸው፡፡ በክርስቶስ ግን እኛ ልንረዳው ከምንችለው በላይ በሆነ ልዩ ምሥጢር ያለ መቀላቀል ወይም ያለ መለወጥ ሁለቱም አንድ ሆነው ተዋሕደዋል፡፡ ሆኖም የተዋሕዷቸውን ሁኔታ (ሁለቱ እንዴት አንድ እንደ ሆኑና እንደ ተዋሐዱ) ግን ፈጽሞ ልንረዳው የምንችለው አይደለም፡፡

እኛ በምሥጢራት አማካይነት የምንዋሐደው ከዚህ በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ ከሆነው ሥግው ቃል ጋር ነው፡፡ በጥምቀቱ፣ በሜሮኑ፣ በቁርባኑ ከእርሱ ጋር አንድ ሆነን እንዋሐዳለን፣ አካላዊ ቃል ገንዘቡ ካደረገው የእኛ ባሕርይ ጋር አንድ እንሆናለን፡፡ "ልበስዎ ለሐዲስ ብእሲ - አዲሱን ሰው ልበሱት" የተባለው ይህን ነው፡፡ ይህ ደግሞ እንዲሁ "በእምነት" ብቻ የሚፈጸም አይደለም፤ ማመን የመጀመሪያው መነሻ ሆኖ ከዚያ በኋላ ግን በተግባራዊ ሱታፌና መዋሐድ የሚፈጸም ነው፡፡

ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መንቀፍና ማቃለል ከጥንት ጀምሮ የነበሩ የክርስትና ጠላቶች የመናፍቃን ዋና ግብራቸው ነበር፡፡ አርዮሳውያንና ሌሎችም መናፍቃን በጥምቀት፣ በሜሮንና በቁርባን ምሥጢራት ላይ ይሳለቁ ነበር፡፡ ለአብነትም ዩኖሚየስ የተባለው ጽንፈኛ አርዮሳዊ ስለ ምሥጢራት የጻፈውን ዘለፋና ንቀት ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ በእርሱ ላይ ከጻፈው የመልስ መጽሐፍ እንመልከት፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ የአርዮስን ኑፋቄ እስከ መጨረሻው ጥግ ድረስ ገፍቶ ያደረሰውና ቀንደኛ አርዮሳዊ የነበረው ዩኖሚየስ ለጻፈው መጽሐፍ በጻፈው እጅግ በጣም ጥልቅና ድንቅ በሆነው የመልስ መጽሐፍ ላይ እንዲህ ይላል፡-

> . . . [ዩኖሚየስ] ዳግም የምንወለድበትን ምሥጢረ ጥምቀትን እንደ ከንቱ ነገር ይቆጥረዋል፣ <u>ልዩ መሥዋዕት የሆነውን የቁርባንን ምሥጢር</u> ረብ ጥቅም እንደ ሌለው ነገር ያደርገዋል፣ በእነዚህ ምሥጢራት መሳተፍንም ምንም ዓይነት ጥቅም የሌለው እንደሆነ ሊያስረዳ ይሞክራል፡፡ በዚህም የእኛን የእምነት አስተምህሮ ያዋረድኩ ቢመስለውም ምንኲሴና እርሾው እነ ሞንታነስ፣ እነ መርቅያን፣ እነ ባሲሊዲስና የመሳሰሉት ግኖስቲኮችና መናፍቃን መሆናቸውን ራሱ ይናገራል፡፡

79 (11. Whosoever shall not confess that the flesh of the Lord giveth life and that it pertains to the Word of God the Father as his very own, but shall pretend that it belongs to another person who is united to him [i.e., the Word] only according to honour, and who has served as a dwelling for the divinity; and shall not rather confess, as we say, that that flesh giveth life because it is that of the Word who giveth life to all: let him be anathema.) የቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ 12ቱ ቃለ ግዘቶች

. . . ዩኖሚየስ ዘለፋውን በመቀጠልም 'ቅዱሳንና ብፁዓን ከሆኑ ሰዎች ጋር በአንድነት ሆነን እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር ያለውና የሚገኘው በትምህርት ፍጹምነት እንጂ እናንተ "ምሥጢራት" የምትሏቸውን እነርሱን በመፈጸምና ከእነርሱ በመሳተፍ አለመሆኑን እናረጋግጣለን' ይላል፡፡ እንዲህ ብሎ ሲጽፍ እንዲህ የሚለውን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስን ለሚያውቅ ሰው ከብሉይም ሆነ ከሐዲስ እንዲህ የሚል ትምህርት ከየትኛውም መጽሐፍ የሌለና ከዚያ ያላገኘው የእርሱ የራሱ ፈጠራ ብቻ መሆኑን ያውቃል፡፡

ስለዚህም እርሱ "ቅዱሳንና ብፁዓን የሆኑ ሰዎች" የሚላቸው እነ ማኒን [መነናውያንን]፣ ኒቆላዎስን፣ ኤቲየስን፣ አርዮስንና መሰሎቹ የሆኑትን ሌሎችን እርሱ በክህደቱ አንድ የሆናቸውንና እንደ እርሱ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ፋይዳ ቢስ ናቸው የሚሉትን መናፍቃንን ማለቱ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ እኛ ግን ከክርስቶስ ቃል "ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም" ያለውን፣ እንዲሁም "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው" ያለውን ቃል ከእርሱ ከባለቤቱ ተምረናልና እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር የሚፈጸመውና የሚታተመው መለኮታዊ የሆኑትን ስመ አብን ስመ ወልድን ስመ መንፈስ ቅዱስን በመታመንና መዳናችን የሚጸናውና የሚከወነው ደግሞ ከምሥጢራት በመሳተፍ መሆኑን እናምናለን፡፡ ዮሐ. 6፡51-54 . . .

ዩኖሚየስና መሰሎቹ በቤተ ክርስቲያን ያሉ ክርስቲያናዊ ትውፊቶችና ምሥጢራት ጥቅም የላቸውም ይላሉ፡፡ ጥቅም የላቸውም ከሚሏቸው ትውፊቶችና ምሥጢራት መካከልም በመስቀል ምልክት ማማተብ፣ ጸሎት፣ ጥምቀት፣ ኃጢአትን መናዘዝ፣ ሕጉን ለመጠበቅ በመንፈስ ቅዱስ በተማወቀና በበረታ ልብ መትጋትና መጋደል፣ ራስን መግዛትና በአግባቡ ለመኖር መታገል፣ የትህርምት ሕይወት፣ በውሳጣዊ ፍላጎቶች ላለመነዳትና ላለመሸነፍ ጥረት ማድረግ፣ ለተድላ ደስታ ተገዢ አለመሆን፣ በሥነ ምግባር ፍጽምና ወደ ኋላ አለመቅረትና አለመስነፍ - ከእነዚህ ውስጥ አንዳቸውም የሚጠቅሙትና የሚረዱት ምንም ነገር የለም ይላሉ፡፡ ምሥጢራትም መንፈሳዊ ሀብታትን አያሰጡም፣ በከፉው ጠላት የሚወረወረውን ፍላጻና መዓት አያርቁም ይላሉ፡፡ ክርስቲያኖች በታላቅ አክብሮት የሚጠብቋቸውንና የሚፈጽሟቸውን ምሥጢራት በድፍረትና በይፋ 'ረብ የለሽ፣ ስንፍናና ሞኝነት ናቸው' ይላሉ፡፡ እምነታችን ሊያንቋሽሹ የሚፈልጉ ጣዖት አምላኪ የሆኑ ሰዎችስ በእኛ ላይ ከዚህ የበለጠ ምን ያደርጋሉ? . . . አዲሶቹ የጣዖት አምልኮ አስተማሪዎች የሚያስተምሩት ትምህርት እንግዲህ ይህ ነው፤ እነርሱን የሚከተሏቸውም በሕግ አፍራሾችና በሃይማኖት ለዋጮች ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ግድ የላቸውም፡፡

(ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ለአርዮሳዊው ዩኖሚየስ የጻፈው የመልስ መጽሐፍ፣ መጽሐፍ 11፣ ቁ. 5)

እዚህ ላይ የምናስተውለው ነገር ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ እንደ ተናገረው በአንድ በኩል በጥምቀት ዳግም ልደትና ሌሎችም ጸጋዎች፣ በምሥጢረ ቁርባንም እንዲሁ የምናገኛቸው ጸጋዎች ሁሉ "የሉም፣ ምሥጢራት ፋይዳ የላቸውም" የሚሉት መናፍቃን እንደ አርዮሳዊው ዩኖሚየስ ሁሉ ትምህርታቸውን ከቀደሙት "ቅዱሳንና ብፁዓን የሆኑ ሰዎች ያገኘነው ነው" ማለታቸው ጥንትም የተለመደ ስልታቸውና ልማዳቸው መሆኑን ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ እንደዚህ የምሥጢራትን ፋይዳ የሚያቃልሉ ሰዎች ከጥንትም ጀምሮ አርዮሳውያን መሆናቸውን ናቸው፡፡

ተሐድሶዎች ከላይ ሲታዩ ስለ ክርስቶስ የሚናገሩና የሚቀረቀሩ ይምሰሉ እንጂ ውስጣቸውና አስተምህሯቸው በትክክል ሲፈተሽና ሲመረመር ግን ከአርዮሳዊ ምንጭ የተቀዳና በአርዮስ እርሾ የተለወሰ ዱቄት ነው፡፡ አስተምህሯቸው በመጽሐፍ ቅዱስና በቀደሙት ታላላቅ አባቶቻችን አስተምህሮ ሚዛንነት ሲመዘን እጅግ አድርጎ ቀልሎ የሚገኘው ለዚህ ነው፡፡ እነርሱም ጸረ ክርስቶሶችና ሐሳውያን መሲሐውያን ናቸው፡፡ አባቶቻቸውና ምንጮቻቸው መጽሐፍ ቅዱስና የቀደሙት ሊቃውንት እነ ቅዱስ አግናጥዮስ፣ ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ እነ ቅዱስ አትናቴዎስ፣ እነ ቅዱስ ጎርጎርዮስ፣ እነ ቅዱስ ቄርሎስ፣ እነ ቅዱስ ባስልዮስ፣ እነ ቅዱስ ያሬድ ሳይሆኑ አርዮሳውያኑ እነ ኤቲየስ፣ እነ ዩኖሚየስ፣ እነ ንስጥሮስና እነ ልዮን እንዲሁም ግኖስቲኮቹ እነ መርቅያናንና እነ ማኒ መሆናቸው ከትምህርታቸው ግልጥ ብሎ ይታያል፡፡

## 3.7.3 በተቀበሉት ጸጋ መጽናት፣ መንፈሳዊ ተጋድሎና ክርስቲያናዊ መልካም ሥራ

እስካሁን አንድ ሰው ለመዳን ማድረግ ያለበትን ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን ተመልክተናል፡፡ እነዚህም የመጀመሪያው ማመን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለመዳን አስፈላጊ የሆኑትን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መፈጸም ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ለመዳን አስፈላጊ የሆኑትን ቀሪዎቹን ነገሮች እናያለን፡፡

### 3.7.3.1 የተሐድሶዎች ትምህርት ስለ መጽናት፣ ተጋድሎና ክርስቲያናዊ መልካም ሥራ

ተሐድሶዎች ሰው ባመነበት ቅጽበት ወዲያውኑ ስለሚድንና ከዚያ በኋላ ያለው ሕይወት ምንም ይሁን ምን በመዳኑ ላይ አንዳችም ለውጥ ስለማያመጣ የፈለገውን ኃጢአት ቢሠራም ከመዳን አያግደውም ይላሉ፡፡ በዚህም ሰው ራሱን እንዲገዛና ከኃጢአት ጋር እንዲጋደል ሳይሆን በተቃራኒው ሰው ኃጢአትን እንደ ቀላል ነገር እንዲመለከት፣ እንዲለማመድና እንዲደፋፈር የሚያደርግ ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ያስተምራሉ፡፡ ለምሳሌም የሚከተሉትን ትምህርቶቻቸውን እንመልከት፡-

- "... ይህን ከተረዳን በኋላ ራሳችንን ለማሻሻል ሙከራ አናደርግም፡፡ ... በእኛ ውስጥ ያለውን ኃጢአት ለማሸነፍ መፍጨርጨር የለብንም፡፡ ክርስቲያን እንደዚህ ማድረግ አለበት ተብሎ የተጻፈ አናገኝም፡፡ ዕብራውያን 12፡4 ከኃጢአት ጋር ስለ መጋደል ይናገራል፤ ነገር ግን በዓለም ስላለው ኃጢአት ተናገረ እንጂ በእኛ ውስጥ ስላለው አይናገርም፡፡ ... በእኛ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስም በኃጢአተኛነታችን ወይም በሥጋችን ላይ ራሱ ይዋጋል እንጂ በሥጋ ላይ መዋጋት የእኛ ድርሻ አይደለም፡፡ ..." (ጠማሪ ጽድቅ፣ ጥቅምት 1991 ዓ.ም.፤ ገጽ 27)
- "ቅድስና ... በክርስቶስ መሞት መነሣትም በሚደረግ በሕይወት መንፈስ ሕግና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንጂ በሰው አሳብ ወይም ጥረት የሚሆን አይደለም፡፡" (ሰምዓ ጽድቅ ብሔራዊ፣ ገጽ 108)
- "አማኝ በውስጡ ካለው ኃጢአት ጋር ሲጋደል እድሜ ልኩን ይወስድበታል የሚለው አባባልም ስህተት ነው፡፡" (ጠማሪ ጽድቅ፣ ጥቅምት 1991 ዓ.ም. ገጽ 28)
- "ሰው ያለ መልካም ሥራ መጽደቅ ይችላል፡፡" (ትምህርተ ድኅነ፣ ገጽ 56)
- " 'እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፣ ለእያንዳንዱ እንደ ስራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ፡፡' በዚህና በመሰል ጥቅሶች እየታገዙ ጽድቅ በሥራ እንደሚገኝ የሚሰብኩ ብዙዎች ናቸው፡፡ ጌታ ለፍርድ ሲመጣ ጻድቃንንም ሆነ ኃጥአንን የሚጠይቀው የእምነት ጉዳይ ሳይሆን ሥራን ነውና ስለዚህ ጽድቅ በሥራ ይገኛል ብለው ያምናሉ፡፡ ይህ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ሚዛናዊነትን ያልጠበቀ አመለካከትና መጽሐፍ ቅዱስ ጽድቅ በሥራ ሳይሆን በእምነት ብቻ እንደሚገኝ የተናገረውን ያፈርሳል፡፡" (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 188)
- "ይህ ጽድቅ በእኛ ድካም የሚገኝ ሳይሆን የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ነውና ለእኛ ተቆጥሮልን የምንጸድቅበት በእምነት ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ወደፊት ሳይሆን ሰው ባመነበት ቅጽበት መጽደቁን ያረጋግጣል፡፡ ጽድቅ በሥራችን የሚገኝ ቢሆን ኖሮ አሁን ሊረጋገጥ አይችልም፡፡ በእምነት ብቻ በመሆኑ አሁን ተረጋግጧል፡፡ የእግዚአብሔር ጽድቅ ነጻ ስጦታ እንጂ የድካም ዋጋ (ደመወዝ) ባለመሆኑ በሥራ ላይ ተመሥርቶ የነበረውን ጽድቅና ከንቱ ትምክህት መና አስቀርቷል፡፡ እግዚአብሔር ያፈረሰውን እንደገና እንጻ ጽድቅን በእምነት ሳይሆን በሥራ ለማግኘት መጣር እግዚአብሔር ወዳዘጋጀው ጽድቅ ካለማድረሱም በላይ ከጸጋው ለይቶ ይጥላል፡፡ ቄርሎስ ጽድቅ በእምነት ብቻ የሚገኝ መሆኑን ሲያስረዳ፡- "እመ ፍጻሜሁ ክርስቶስ ለኦሪት ውእቱ ጽድቅኒ ወያጸድቅኒ በሃይማኖት ባሕቲቱ እስመ ዘዚአሁ ውእቱ ክሂል ለአጽድቆ ዘእምእግዚአብሔር - ክርስቶስ ለኦሪት ፍጻሜው ከሆነ እርሱ ጻድቅ ነውና በሃይማኖት (በእምነት) ብቻም ይጸድቃል፡፡ ከእግዚአብሔር የሚሆን የማጽደቅ ችሎታ የእርሱ ገንዘብ ነውና" ብሏል (ሰምዐ ጽድቅ ብሔራዊ ገጽ 94" (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 188-189)

- ◉ "ጽድቅ የእኛ አንዳች አስተዋጽኦ የሌለበት የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ከሆነ ዘንድ በእምነት ከጸደቅን በኋላ ኃጢአት ፈጽመን ብንገኝ እንኳ ከጽድቅ ተለይተን አንከነንም፣ ስለ ኃጢአታችን በተለያዩ ቅጣቶች እንገሠጻለን እንጂ፡፡ (1 ቆሮ. 11፡32 ፤ 3፡15 ፤ 5፡5) ይህ ሳይሆን ቀርቶ ያገኘነው ጽድቅ ኃጢአት ስንሠራ የሚወሰድብን፣ ጽድቅ ስናደርግ ደግሞ የሚመለስልን አድርገን ከቆጠርን የድካማችን ወይም ጥረታችን ውጤት እንጂ ነጻ ስጦታ መሆኑ ይቀራል፡፡ . . . ከዚህ ውጭ ግን በእምነት ጸድቄያለሁና አልከነንም እያለ ሁል ጊዜ ኃጢአትን በተደጋጋሚ የሚፈጽም ክርስቲያን ጸድቄያለሁ በማለት ራሱን ከሚሸንግል አለመጽደቁን ሊያጤነው ይገባል፡፡ (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 189-90)

ይህ የተሐድሶዎች አስተሳሰብና ትምህርት ከዚህ ቀጥሎ በመጽሐፍ ቅዱስ እና በቀደምት አበው ሊቃውንት ትምህርት ስንመዝነው እንደምናየው አንዱን (እምነትን) ብቻ ይዞ ሌላውን ትቶ በስህተት ሜዳ የሚነጉድ ሰው ሠራሽ ሃሳብ ነው፡፡ በመጀመሪያ "ቄርሎስ ጽድቅ የሚገኘው በእምነት ብቻ ነው አለ" ብለው የጠቀሱልን ራሱን ቄርሎስን ሳይሆን የተሐድሶ አባታቸው መሠረት ስብሐት ለአብ የጻፈውን መጽሐፍ ነው (ስምዐ ጽድቅ ብሔራዊ የመሠረት ስብሐት ለአብ መጽሐፍ ነው)፡፡ መሠረት ስብሐት ለአብ ደግሞ በስምዓ ጽድቅ ብሔራዊ መጽሐፉ ላይ "ቄርሎስ እንዲህ ይላል"፣ "ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዲህ አለ" ብሎ አቀረበ እንጂ ያን ጥቅስ ከየት እንዳገኘው ወይም እነዚህ አባቶች ከየትኛው ትምህርታቸው ላይ እንደዚያ እንዳሉ አልገለጸም፡፡

ይህን ደግሞ ምናልባት በስህተት ያደረጉት ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደዚህ ሊሆን ስለሚችል ምንም አይደለም ብለን በቅንነት እንዳናልፈው በተደጋጋሚ ያደረጉት ነገር ሆነብን፡፡ "ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዲህ ይላል" ይሉና ምንጭ አድርገው የሚጠቅሱት ይህንኑ የመሠረት ስብሐት ለአብን መጽሐፍ ነው፡፡ እንደዚሁም "ቄርሎስ እንዲህ ይላል" ይሉና የሚጠቅሱት አሁንም ይህንኑ መጽሐፍ ነው፡፡ ታዲያ ቄርሎስ አለ ካሉ መጥቀስ የነበረባቸው ራሱ ቄርሎስ ያለውን ነበር እንጂ መሠረት ስብሐት ለአብን መጥቀስ ምን ማለት ነው? ከምንጩ ካላገኙት ደግሞ መጀመሪያ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ከውስጧ በመለወጥ ፕሮቴስታንት ለማድረግ የራሷን ዘይቤ የሚያውቁትን ሰዎች እየፈለገ ሲቀስጥ ከነበረውና "ሠራዊተ ክርስቶስ ማኅበር" የተባለውን ድርጅት ካቋቋመው ከአውሮፓዊው የፕሮቴስታንት ሚሲዮን ከዳዊት ስቶክስ ለአንድ ዓመት ፕሮቴስታንታዊ በሆነ መንገድ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮርስ የወሰደው፣ በመቀጠልም በአሜሪካ ሚሽን ትምህርት ቤት አስተማሪ ሆኖ ሲያገለግል የነበረው፣ ከዚያም በመካነ ኢየሱስ ለ30 ዓመታት ሲያስተምር ኖሮ ሲሞትም ከመካነ ኢየሱስ "ጸሎት" ተደርጎለት የተሸኘውን የመናፍቁን የመሠረት ስብሐት ለአብን ትምህርት በታላቁ ኦርቶዶክሳዊ አባት በቅዱስ ቄርሎስ ሽፋን ለማቅረብ መሞከር አታላይነትና አጭበርባሪነት ነው፡፡ (ጮራ ቁ. 14፣ ገጽ 4) እኛ ያቀረብነው ትምህርቱን ከነባለቤቱ፣ እንዲሁም ከሚገኝበት ምንጭ ጋር ስለሆነ ሊሆን የሚገባው በዚህ መልክ ነው፡፡

በዚያውም ላይ ደግሞ "ጌታ ለፍርድ ሲመጣ ጻድቃንንም ሆነ ኃጥአንን የሚጠይቀው የእምነት ጉዳይ ሳይሆን ሥራን ነውና ስለዚህ ጽድቅ በሥራ ይገኛል ብለው ያምናሉ" ያሉት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ለማለት ከሆነ ይህ ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያለ እምነት በሥራ ብቻ ይጸደቃል ብላ አታምንም፣ አታስተምርምም፡፡ ይህ የተለመደ የሌሎችን እምነትና አስተምህሮ ለመንቀፍና ለማሳጣት ያመች ዘንድ የሚደረግ የማጣመም ስልት ነው፡፡ ለመዳን መሠረቱና ዋናው እምነት ነው፣ እምነት ብቻ ግን አይደለም፡፡ እንደ እነርሱ "በእምነት ብቻ" የማይለውን ሁሉ እምነቱንና ትምህርቱን አዛብቶ ማቅረብ ነውር ነው፡፡ እንደዚሁም "ይህ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ሚዛናዊነትን ያልጠበቀ አመለካከትና መጽሐፍ ቅዱስ ጽድቅ በሥራ ሳይሆን በእምነት ብቻ እንደሚገኝ የተናገረውን ያፈርሳል" ያሉትም እንዲሁ ሐሰት ነው፡፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ጽድቅ በእምነት እንደሚገኝ ይናገራል እንጂ "በእምነት ብቻ" ግን አይልም፡፡ ሌላው አባባላቸውም ሁሉ እንዲሁ ውኃ የማይቋጥር ነው፡፡ ይህን ጉዳይ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ክፍል እንመለከተዋለን፡፡

እግዚአብሔር በቸርነቱ የሰጠንን የመዳን ጸጋ ከተቀበልን በኋላ ያን መዳናችንን ለመፈጸም ምን ማድረግ አለብን? የሚለው ጥያቄ መሠረታዊ ነው፡፡ በእምነት መሠረትነት በጥምቀት የእግዚአብሔር ልጅነትን ካገኘን፣ በምሥጢረ ሜሮን የመንፈስ ቅዱስ ቤት ሆነን ከታተምን፣ በምሥጢረ ቁርባን ከእርሱ ጋር ከተዋሐድን በኋላ ማድረግ የሚጠበቅብን ነገር አለ? ወይስ መዳናችን ስለ ተፈጸመ ከዚያ በኋላ የፈለግነውን ብንሆንና ብናደርግም በመዳናችን ላይ ለውጥ አያመጣምን?

በተሐድሶዎቹ አስተምህሮ መሠረት (እንደ አባቶቻቸው እንደ ፕሮቴስታንቶቹ ማለት ነው) መዳን በአንድ ቅጽበት፣ ያውም ምሥጢራትን ሁሉ ሳያካትት፣ እንዲሁ በእምነት ብቻ ይፈጸማል ስለሚሉ ከዚያ ወዲያ ምንም ነገር ማድረግ እንደማያስፈልግ ያስተምራሉ፡፡ "መዳን በእምነት ብቻ ነው፣ ተጋድሎ፣ ጽናት፣ ምግባር ትሩፋት . . . አያስፈልግም" ይላሉ፡፡ እንደ እነርሱ አስተምህሮ አንድ ሰው በክርስቶስ ካመነ ሌላ ነገር - ጥምቀት፣ ሜሮን፣ ቅዱስ ቁርባን፣ እንዲሁም ደግሞ የተቀበለውን ጸጋ ለመጠበቅ መጋደል፣ ጾም፣ ጸሎት፣ ምጽዋት፣ በአጠቃላይ መንፈሳዊ ተጋድሎና ምግባር ትሩፋት የሚባሉ ነገሮች አያስፈልጉም ይላሉ፡፡ ከዚያም አልፎ እንደ እነዚህ ያሉት ነገሮች መሰበካቸው ለሰው መዳን ተቃራኒ ነው ባዮች ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንንም እነዚህን ነገሮች በማስተማሯ አጥብቀው ይጠሏታል፣ ይኮንኗታልም፡፡

ለአብነትም ከዚህ በታች ያለውን ትምህርታቸውን እንመልከት፡-

- "ሰው በምግባሩ በሚያደርገው ጥረት፣ ሰባቱን አጽዋማት በመጾም፣ ምጽዋት በመመጽወት ይጸድቃል ከሚለው ትምህርት ጋር ተደምረው ለሚያምኑ ሁሉ የሆነውንና በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘውን የእግዚአብሔር ጽድቅ ሸፍነውታል፡፡ አማኞች በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት በኩል በእግዚአብሔር ጸጋ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነው ተብሎ መሰበኩ በገድልና በድርሳን ታሪክ ለደነዘዘ ጆሮ ፍጹም ሞኝነት ሆኖ እንዲቆጠር ተደርጓል፡፡" (ኖኅተ ብርሃን፣ 2002፣ ገጽ 18)

- "እርሱን ለማስደሰት የምታደርጉትን ሁሉ ሊቀበል የሚችልበትን መንገድ ባለማወቃችሁ አልተቀበለውም እንጂ ከፍቅሩ የተነሣ የምታደርጉት ሁሉ ከሰው ዐቅም በላይ ነው፡፡ ስለዚህም ያደረጋችሁትን ሁሉ ያልተቀበለበትንና እንዲያውም የተጸየፈበትን ምክንያት ልታውቁት ይገባል፡፡ እርሱን ያስደስትልናል ብላችሁ ብዙ ነገር የሠራችሁበት ባሕርይ ከእግዚአብሔር ጋር የተጣላ አዳማዊ ባሕርይ ነው፣ ኃጢአተኛ ባሕርይ ነው፣ የረከሰ ባሕርይ ነው፡፡ ከዚህ የተነሣ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ሕግን በመሥራት በእግዚአብሔር ፊት አይጸድቅም ተባለ፡፡ እናንተ በሕግ የታዘዘውን ሁሉ በማድረግ ፈጽመናል፤ እንዲያውም በሕግ ከታዘዘው በላይ በመሥራት "ትሩፋትን" አበርክተናልና እንጸድቃለን ብላችሁ ስትጠባበቁ፣ ሕግን በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት አይጸድቅም በማለት የእግዚአብሔር ቃል መንገዱን ዘግቶባችኋል፡፡ ምክንያቱ ግልጽ ነው፡፡ ሥጋ የለበሱ ሁላቸው በኃጢአት ከተበከለው ከአዳምና ከሔዋን ከሥጋቸውና ከባሕርያቸው ተከፍለው የተወለዱ በመሆናቸው ነው፡፡ መዝ. 51፡5 ሕግን ጠብቅን ትሩፋትንም ሠራን የሚሉበት ጠቅላላው አቋማቸው ረክሷል ማለት ነው፡፡ ኢሳ. 1፡5-6 . . ." (ሖሩ ቁ. 10፣ ገጽ 7-8)

- "የወይን ግንድ ቅርንጫፍ ፍሬን የሚያፈራው ከመጨነቅ፣ ከመሞከር የተነሣ እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ ከግንዱ ከሚገኘው መግቦት የተነሣ ለቅርንጫፉ የዕድገቱ የጥንካሬውና ፍሬን የማፍራቱ እንቅስቃሴ ሁሉ ያለ መጨነቅ የሚሠራ ባሕርያዊ ክንውን ይሆናል፡፡ . . . ሌሎች ክፍሎች ደግሞ አባሎቻቸው የወይን ፍሬን ማፍራት ይችሉ ዘንድ ጥብቅ የቅድስና ድንጋጌዎችን በሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ እንደ ሆነ ያስተምራሉ፡፡ ድንጋጌዎቻቸው በከባድ ቅጣት የታጀቡ ስለሆነ ሕግ ተላላፊዎችን በመቅጣት "የወይን ፍሬን" እንዲያፈሩ ለማስደረግ እንደሚቻል የሚያምኑ ይመስላሉ፡፡" (ሖሩ ቁ. 11፣ ገጽ 17)

እነዚህ አባባሎቻቸው በብዙ ስህተቶች የተሞሉ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ሰው ያለ እምነት፣ ያለ ምሥጢራት፣ "ሰው በምግባሩ በሚያደርገው ጥረት፣ ሰባቱን አጽዋማት በመጾም፣ ምጽዋት በመመጽወት" ብቻ ይጸድቃል እንልም፡፡ ይህ የሌሎችን እምነትና ትምህርት አጣምሞ ማቅረብ የተለመደ ስልታቸው ስለሆነ ነው፡፡ እንዲህ የሚያደርጉትም በዚህ ሽፋን "መዳን በእምነት ብቻ" የሚለውን ኑፋቄያቸውን አሾልከው ለማስገባት ነው፡፡ ከላይ በጠቀስናቸው ትምህርቶቻቸው ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ስህተቶቻቸውን በአጭሩ እንመልከታቸው፡-

1. የሰውን ባሕርይ የረከሰ አድርገው ማቅረባቸው

- "እርሱን ያስደሰትልናል ብላችሁ ብዙ ነገር <u>የሠራችሁበት ባሕርይ ከእግዚአብሔር ጋር የተጣላ አዳማዊ ባሕርይ ነው፣ ኃጢአተኛ ባሕርይ ነው፣ የረከሰ ባሕርይ ነው፡፡ . . . ሥጋ የለበሱ ሁላቸው በኃጢአት ከተበከለው ከአዳምና ከሔዋን ከሥጋቸውና ከባሕርያቸው ተከፍለው የተወለዱ በመሆናቸው ነው፡፡</u>"

ይህ አባባላቸው አካላዊ የእግዚአብሔር ቃል የእኛን ባሕርይ መዋሐዱ በእኛ ባሕርይ ላይ ያመጣውን ሁለንተናዊ ነገር ካለማወቅና ካለመረዳት የመጣ ስህተት ነው፡፡ ለዚህ ድጋፍ ወይም ማስረጃ ብለው የጠቀሷቸው ጥቅሶችም ዘመነ (ዓመተ) ፍዳ በነበረው በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረውን የሰው ሁኔታ የሚገልጡ እንጂ ከአምላክ ሰው መሆን ጀምሮ ባለው በዓመተ ምሕረት በሐዲስ ኪዳን ዘመን ያለውን የሰው ሁኔታ በተመለከተ የተነገሩ አይደሉም፡፡ የእኛ ባሕርይ ከአካላዊ ቃል ጋር ከመዋሐዱ የተነሣ በአዳምና በሔዋን ድቀት በአጠቃላይ በምልዓተ ኃጢአት ከደረሰበት ርኩሰት ነጽቷል፣ ተቀድሷል፣ ከድካሙ በርትቷል፣ ከውድቀቱ ተነሥቷል፡፡ ይህንም በጥምቀት የቀደመውን አሮጌውን ሰውነት (አዳም) አስወግደን አዲሱን ሰው ዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስን ለብሰነዋል፡፡ መድኃኒታችን ሰው የሆነውና ራሱን የተቀደሰ መሥዋዕት አድርጎ የሰጠው እኛን ከቀደሙ ርኩሰታችን ለመቀደስ መሆኑን ሲገልጽ "እነርሱም ደግሞ በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ እቀድሳለሁ" አለ፡፡ ዮሐ. 17፡19 እንዲሁም "አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፉችሁታልና" ይላል፡፡ ቆላ. 3፡9

አሁን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ፣ በምሥጢራት የሚሰጠውን ጸጋ እግዚአብሔር አምነው የተቀበሉ ክርስቲያኖች "በኃጢአት ከተበከለው ከአዳምና ከሔዋን ከሥጋቸውና ከባሕርያቸው ተከፍለው የተወለዱ" አይደሉም፡፡ እንደ ማንኛውም ሰው ሥጋዊ ልደትን ቢወለዱም ክርስቲያኖች ግን "ለተቀበሉት ሁሉ ግን፣ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ <u>እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም</u>" ተብሎ እንደ ተነገረው ከእግዚአብሔር በጥምቀት ዳግመኛ የተወለዱ ናቸው፡፡

ስለዚህ በዳግማዊ ልደት ከእግዚአብሔር የተወለዱ ስለሆነ አሁን አባታቸው ተሐድሶዎች "በኃጢአት የተበከለ" ያሉት አዳም ሳይሆን እግዚአብሔር ነው፡፡ ዮሐ. 1፡12-13 ከዚህ ነጻ ለመውጣት ስለሚያስፈልግም ነው ጌታችን "ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፣ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው። ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል" በማለት ያስተማረን። ዮሐ. 3፡6-7 ስለዚህ በጥምቀት ዳግመኛ የተወለዱ ሁሉ ሥጋውያን ሳይሆኑ መንፈሳውያን ናቸው፣ ከደምና ከሥጋ ፈቃድ የተወለዱ ሳይሆኑ ከእግዚአብሔር የተወለዱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ይህ ተሐድሶዎች ያሉት ነገር ፈጽሞ ስህተት ነው፣ እግዚአብሔር ያደረገልንን ነገር ሁሉ ገደል መክተት ነው፡፡

በእግዚአብሔር ቸርነት የተሰጠውን የመዳን ጸጋ ገንዘብ ያደረጉ ክርስቲያኖች ባሕርያቸው ከእግዚአብሔር ጋር የተጣላ አዳማዊ ባሕርይ ሳይሆን የክርስቶስ አካል የሆነ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ "ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደ ሆነ አታውቁምን?" ይላልና፡፡ 1 ቆሮ. 6፡15 ተሐድሶዎች እንደሚሉት "ኃጢአተኛና የረከሰ ባሕርይም" አይደለም፡፡ አሁንም መጽሐፍ ቅዱስ "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፣ ተቀድሳችኋል፣ ጸድቃችኋል" ይላልና፡፡

1 ቆሮ. 6፥11 እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ያደረገው የማዳኑ ሁሉ ዓላማ ሰውን መቀደስና ማክበር መሆኑን "እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፣ በፊት የተለያችሁትን ክፉ ሥራችሁንም በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ" በማለት ይገልጻል። ቆላ. 1:21-22 በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ አዲስ ፍጥረቶች መሆናቸውንም "ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፏል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል" ሲል በግልጽ ይናገራል፡፡ 2 ቆሮ. 5፥17 በአጠቃላይ እነርሱ እንደሚሉት ከሆነና አሁንም ባሕርያችን ያልተቀደሰ፣ የረከሰና በኃጢአት የተበከለ ከሆነማ ሐዋርያው "በከንቱስ ሞተ ክርስቶስ - እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተን" ያሰኛል፡፡ ገላ. 2፡21 ይህም ወደ ዘመነ ፍዳ ወደ ዓመተ ኩነኔ ወደ ዘመነ እሪት መመለስ ነው፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ የሰጠንን ጸጋና ሰው መሆኑ በእኛ ባሕርይና ሕይወት ላይ ያመጣውን ሁለንተናዊ ነገር በሙሉ ሸምጥጦ የሚክድ አረማዊ አስተሳሰብ ነው፡፡ በርግጥ እነርሱ ቅድስና የሚገኝባቸውን መንገዶች - ምሥጢረ ጥምቀትን፣ ምሥጢረ ሜሮንን፣ ምሥጢረ ቊርባንን፣ ጾምን፣ ጸሎትን፣ መንፈሳዊ ተጋድሎን፣ . . . ስለማይቀበሉ "የሰው ባሕርይ የጎሰቆለውና የረከሰው የአዳም ባሕርይ ነው" የሚሉት በእነርሱ ያለውን እንደ አጠቃላይ እውነታ አድርገው አጠቃልለውት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ የተሐድሶዎች አባባል ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን በአግባቡ ካለማወቃቸውና ፕሮቴስታንታዊ የሆነውን አባባል ብቻ እንደ ወረደ ከማውረዳቸው የመጣ ነው፡፡

2. "ስለዚህም ያደረጋችሁትን ሁሉ ያልተቀበለበትንና እንዲያውም የተጸየፈበትን ምክንያት ልታውቁት ይገባል" ብለዋል፡፡

አሁን ደግሞ እግዚአብሔርን ወክለው እየተናገሩ ነው፡፡ በሃይማኖት ሆነው እርሱን ደስ ለማሰኘት በምግባር በተጋድሎ እንደየ ዓቅማቸውና እንደየ ጸጋቸው የሚወጡ የሚወርዱ የልጆቹን አገልግሎት እግዚአብሔር አለመቀበሉን፣ እንዲያውም መጸየፉን ማን ነገራቸው? ማንስ አረጋገጠላቸው? የራሳቸውን ግምት እንደ ተረጋገጠ እውነት አድርገው ደፍረው ሲናገሩ ትንሽ ሐፍረት እንኳ አይሰማቸውም፡፡ እግዚአብሔር ግን በእምነት ሆኖ የሚደረገውን ነገር ሁሉ በአባትነት ፍቅሩ ደስ ብሎት ይቀበለዋል እንጂ አይጸየፈውም፡፡ "እግዚአብሔር ... ያደረጋችሁትን ሥራ፣ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና" ይላልና፡፡ ዕብ. 6፥10

በአንድ በኩል በእምነት ተመሥርተው በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙትን የእግዚአብሔር ሀብታትና ጸጋዎች አግኝተው በዚያ ላይ ቆመው እግዚአብሔርን የሚያስደስት መልካም ምግባር መሥራትን ንቀውና አጥቅተው ያጥላላሉ፤ ይህ የመዳን ጸጋ ተቃራኒ ነው ይላሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ይህን ትምህርት በማስተማሯም ይወቅሷታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መልካም ምግባርና የቅድስና ሕይወት በሀገራችን ጠፋ ብለው ሊያዝኑና ሊተክዙ ይሞክራሉ፡-

- " . . . በተለይም ወደ ሀገራችን ስንመጣ የክርስቲያን ደሴት ተብላ መጠራቷ እምኑ ላይ ነው? ብለን እስከምናስብ ድረስ የሰዎች ምግባረ ብልሹነት ምድራችንን ሸፍኗት ይገኛል፡፡ ለመንግሥት ሕግ አስከባሪዎች የዕለት ተዕለት ሸክም ሆነው ከሚገኙት ምግባረ ብልሹ ዜጋዎች መካከል ከፍተኛውን እጓዝ የያዙት፣ ከእኛ ወዲያ ክርስቲያን ማን አለ ባዮችና በምግባራችን እንጸድቃለን የሚሉ ወገኖቻችን መሆናቸውን ላለማየት ዓይናችንን ከወንጀለኞች እስታቲስቲክስ ላይ ማንሣት ይኖርብናል፡፡ . . . አምልኮ ባዕድን፣ ጠንቋዩን፣ ዛር ቃልቻውን፣ . . . በክርስቲያንነቱ በሚኮራው ሕዝብ መካከል ተስፋፍቶ፣ በከፊልም ከየጋዜጣው እንደምናነበው ከቤተ ክርስቲያን ጋር ተቆራኝቶ ስናይ ምድሪቱን የክርስቲያን ደሴት ብሎ መጥራት የቱን ያህል አሳፋሪ እንደ ሆነ መረዳት አያስቸግርም፡፡" (ሙራ ቁ. 17፣ ገጽ 29)

ሊገርማቸው የሚገባው አያስፈልግም ብለው የሚያስተምሩት ክርስቲያናዊ መልካም ምግባር ባይጠፋና ቢስፋፋ ነበር እንጂ ቢዳከምና ቢጠፋ ለምን ይገርማቸዋል? በአንድ በኩል አያስፈልግም ይላሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ጠፋብን ተዳከመብን እያሉ የአዞ ዕንባ ሊያፈስሱ ይሞክራሉ፡፡ ይኽ ምን ማለት ነው? እያስተማሩና እየሠሩ ያሉት ምግባርና የቅድስና ሕይወት እንዲጠፉ፣ ሕገ ወጥነትና ምግባረ ብልሹነት እንዲስፋፋ አይደለምን? ታዲያ ይህ ምኞታቸው ቢሳካላቸው ደስ ሊላቸው ይገባል እንጂ ለምን ያዝናሉ? "አማኞች ሆነን ኃጢአት ብንሠራ የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን የተሰጠንን መብት አይቀይረውም" (ጠማሪ ጽድቅ፣ ገጽ 60) እያሉ፣ እንዲሁም "ራሳችንን ለማሻሻል ሙከራ አናደርግም፤ በእኛ ውስጥ ያለውን ኃጢአት ለማሸነፍ መፍጨርጨር የለብንም" እያሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሌለ ሰይጣናዊ ትምህርት ማስተማራቸው ዓላማው ሰውን ወደ ኃጢአት ለመግፋትና ለማደፋፈር ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ታዲያ እንዲህ ብሎ ታጥቆ የሚያስተምር ቡድን ኃጢአት በዛ፣ ጽድቅና ቅድስና ጠፋ ብሎ ሊደሰት እንጂ ሊያዝን እንዴት ይችላል? አያውቁብንም የሚል አስመሳይነት ካልሆነ በስተቀር፡፡ በዚያውም ላይ "ይህን ላለማየት ዓይናችንን ከወንጀለኞች እስታቲስቲክስ ላይ ማንሣት ይኖርብናል" በማለት እንዲሁ እመኑን አሉን እንጂ እነርሱ እንደሚሉት ስለመሆኑ አንድም የስታቲስቲክስ መረጃ አቅርበው አላሳዩንም፡፡

እነ ሉተር የመልካም ምግባር ሕይወት፣ የቅድስና ተጋድሎ ወዘተ አያስፈልግም ብለው ተነሥተው ሕዝቡን ኃጢአትን ካደፋፈሩትና ያለ መሳቀቅ እንዲሠራ ካደረጉት በኋላ በሕዝቡ ዘንድ ወንጀል በመበርከቱና የሰው ምግባር በጣም እየተበላሸ በመሄዱ ወደ ኋላ የተነሡት ፕሮቴስታንታውያን "ፓየቲዝም - Pietism" የሚባል አዲስ እንቅስቃሴ ለመጀመር ሞክረው ነበር፡፡ እርሱም ምግባርና መልካም ሥራ ያስፈልጋል የሚል አዲስ እንቅስቃሴ ነበር፡፡ ሉተር የቅዱስ ያዕቆብን መልእክት በሥራና በእምነት ስለ መጽደቅ ስለሚናገር "ገለባ መልእክት" ይለው ነበር፡፡ ሆኖም ነገሩ ጅብ ከሄደ ዓይነት ሆነና ሕዝብ እንደ ቧንቧ ውኃ ሲፈልጉ የሚከፍቱትና ሳይፈልጉ ደግሞ የሚዘጉት ስላልሆነ የሚሰማቸው አላገኙም፡፡ በዚህ ሂደትም አብዛኛውን የአውሮፓ ሕዝብ ዛሬ ከደረሰበት የእምነት አልባነት ደረጃ አድርሰውታል፡፡ ክርስቲያን ነን የሚሉትም ሴትና ሴትን፣ ወንድና ወንድን በ "ቸርቻቸው" "በጸሎት" የሚያጋቡ ከመሆን መዓርግ ደርሰዋል፡፡ ይህ ነው የፕሮቴስታንቲዝም (የተሐድሶ) ውጤት!

እንደዚሁም ደግሞ "መቅደስ የገቡ መናፍቃን" በሚለው መጽሐፋቸው ከገጽ 58-59 ላይ የተፈጸመውን የእግዚአብሔር ማዳን እና በእያንዳንዳችን በኩል ያለውን የመዳን ድርሻና ሚና እደበላልቀውና ባልተረዳ አእምሯቸው አምታትተው ካቀረቡ በኋላ እንደ እነርሱ "ገነት መንግሥተ ሰማያት እንደምንገባ እርግጠኞች ነን" እያሉ የማይፎክሩትን ሰዎች ከእስላሞች ጋር እንዲህ ሲሉ ለማመሳሰል ሞክረዋል፡-

- *". . . መውረድ መወለዱን አታምኑም? ሲሏቸው እናምናለን ይላሉ፡፡ አልተጠመቃችሁም ሲሏቸው ደግሞ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀናል ይላሉ፡፡ ታዲያ እንዴት አልዳናችሁም ሲሏቸው መልሳቸው ስንሞት ነው የምናውቀው ይላሉ፡፡ . . . እንዲያው የቁርዓኑ የመሐመድ መንፈስ ያደረበት ካልሆነ በቀር አምኖ የተጠመቀ ሁሉ ከጸጋው የተነሣ እንደ ጸደቀ አለማመን የጌታ የኢየሱስን ተልእኮ ትርጉም አልባ ማድረግ መሆኑን አልተረዱትም፡፡ መሐመድ ጀነት ትገባለህ ወይ? ቢሉት ምኑን አውቄው አላህ በምሕረቱ ካላየኝ አለ ይላሉ፡፡"* (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 58-59)

እንዲህ በጣም የሚገርመው ግን ይህን እንዳሉ ወዲያውኑ የሚከተለውን ማለታቸው ነው፡፡

- "የአሮን ልጆች ከሰኑ በተቀመጠው ውኃ ሳይታጠቡ ወደ ቅድስት ቢገቡ ይሞቱ እንደ ነበር ሁሉ ክርስቲያኖችም ኃጢአታቸውን ባይናዘዙ ፍጻሜያቸው ሞት እንደሚሆን የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይለናል፦ ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል። ሁል ጊዜ የሚፈራ ሰው ምስጉን ነው፤ ልቡን የሚያጸና ግን በክፉ ላይ ይወድቃል።" ምሳ. 28፡13-14 (መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ ገጽ 59)

ተሐድሶዎች ሆይ፣ ይህ የእግዚአብሔር ቃል የሚመሰክረው ለማን ነው? "ገነት እንደምገባ እርግጠኛ ነኝ" ለምትሉት ለእናንተ ወይስ "እግዚአብሔር አድኖናል፤ ሆኖም ያን መዳን ሙሉ በሙሉ ገንዘብ ለማድረግና ላለመልቀቅ በዚህ ዓለም ሕይወት ስንኖር መጽናት፣ መጋደል ያስፈልገናል" ለምንለው ለእኛ? ቃሉ የሚለው'ኮ "<u>ሁል ጊዜ የሚፈራ ሰው ምስጉን ነው፤ ልቡን የሚያጸና ግን በክፉ ላይ ይወድቃል</u>" ነው እንጂ "ገነት እንደምገባ እርግጠኛ ነኝ፤ እንዳችም ፍርሃትና ስጋት የለብኝም እያለ የሚፎክር ሰው ምስጉን ነው" አይደለም!

ከዚህ ቀጥሎ እነዚህን የተሐድሶዎች አባባሎች በመንፈስ ቅዱስና በሊቃውንት ትምህርት መሠረት እንመዝናቸዋለን፡፡ በዚህም ኦርቶዶክሳዊነት ትምህርት የትኛው መሆኑን ነጥሮ ይወጣል፡፡

## 3.7.3.2 "<u>በእምነት</u>" መዳን እና "<u>በእምነት ብቻ</u>" መዳን

እምነት ለመዳን የመጀመሪያው አስፈላጊ ነገር ስለ መሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ በስፋት የሚያስተምረን እውነት እንደ ሆነ ከላይ ተገልጿል፡፡ መዳን የእግዚአብሔር የቸርነቱ ስጦታ እንጂ የሰው የሥራው ውጤት አለመሆኑም እንዲሁ በመጽሐፍ ቅዱስ በሚገባ የተገለጸና ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምታምነው እውነት ነው፡፡ የተሐድሶዎች አለመረዳትና ስህተት ያለው አንዱን ጥለው አንዱን አንጠልጥለው መሄዳቸው ነው፡፤ ይህም "መዳን በእምነት ብቻ ነው" ማለታቸው ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት የምንድነው በእምነት ነው፤ በእምነት ብቻ ግን አይደለም፡፡ "በእምነት መዳን" እና "በእምነት ብቻ መዳን" በእጅጉ የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡

"በእምነት መዳን" መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ሲሆን "በእምነት ብቻ መዳን" የሚለው ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አይደለም፡፡ ይህ የፕሮቴስታንቶችና የልጆቻቸው የተሐድሶዎች የፈጠራ ትምህርት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ <u>በእምነት ስለ መዳን</u> እንጂ "<u>በእምነት ብቻ</u>" ስለ መዳን አንድም ቦታ አይናገርም፡፡ "ሰው ያለ ሕግ ሥራ <u>በእምነት እንዲጸድቅ</u> እንቆጥራለንና" በሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ላይ "<u>በእምነት ብቻ እንዲጸድቅ</u>" በማለት "<u>ብቻ</u>" የሚለውን አፍራሽ ቃል በራሱ ደፋርነት የጨመረው በ16ኛው መቶ ዓመት የተነሣው ጀርመናዊው ማርቲን ሉተር ነው፡፡ ሮሜ 3፡28 "በእምነት መዳን" በሚለው የእግዚአብሔር ቃል ላይ "ብቻ" የሚል ቃል በድፍረት የጨመረው በሰው መዳን ውስጥ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን፣ የመጽናትንና የተጋድሎን አስፈላጊነት ሁሉ ከንቱ ለማድረግና እንዲሁ "ድኛለሁ" እያሉ በመፎከር እንዳሻቸው ኃጢአትን ለመሥራት ለራሳቸው ይለፍ ለመስጠት የፈጠሩት ሰፊ መንገድ ነው፡፡

ቅዱስ መጽሐፍ መሠረታዊ ነገር ስለ ሆነው በእምነት ስለ መዳን ጉዳይ ደጋግሞ ይናገራል፡፡ ለአብነትም "እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስሪያ አድርጎ አቆመው" ይላል፡፡ ሮሜ 3፡25 እንዲሁም "እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ"፤ "በእርሱም ደግሞ ወደቆምንበት ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል" ፤ "ይህስ ስለ ምንድር ነው? በሥራ እንጂ በእምነት ጽድቅን ስላልተከተሉ ነው" ይላል፡፡ ሮሜ 5፡1፤ 5፡2፤ 9፡30

ቅዱስ ጳውሎስ "ሕግ" እና "የሕግ ሥራ" በማለት የሚገልጠው ሕገ ኦሪትንና በዚያ የነበረውን የመሥዋዕት ሥርዓት ሲሆን "እምነት" የሚለው ደግሞ ወንጌልንና በወንጌል የሚገኘውን የመዳን ጸጋ ነው፡፡ ለምሳሌም "እምነትም ሳይመጣ ሊገለጥ ላለው እምነት ተዘግተን ከሕግ በታች እንጠበቅ ነበር" በማለት "ሕግ" የሚለው ሕገ ኦሪትን ሲሆን እምነት የሚለው ደግሞ ወንጌልን መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ገላ. 3፡23 እንዲሁም "እምነት ግን መጥቷልና ከእንግዲህ ወዲህ ከሞግዚት በታች አይደለንም" ሲል "እምነት" ያለው ወንጌልን መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ገላ. 3፡25

ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክታቱ ደጋግሞ፣ በተለይም ደግሞ በሮሜ መልእክቱ እና በገላትያ መልእክቱ ላይ ሕግንና እምነትን በተመለከተ የተናገረውና ሰው የሚድነው ሕግን በመፈጸም ሳይሆን በእምነት ነው እያለ ያስተማረው ጽድቅ ወይም መዳን የሚገኘው ሕገ ኦሪት የሚያዝዘውን በማድረግ (ግዝረትን፣ የበግና የፍየል ደም መርጨትን፣ የተለያዩ የመንጻት ሥርዓቶችን በመፈጸም፣ የፋሲካውን በግ በመብላት . . .) ነው ብለው ወንጌልን ለመቀበል አምጸው የነበሩትንና ወደ ክርስትና ከገቡም በኋላ መሥዋዕተ ኦሪትን አሁንም ከመሥዋዕተ ወንጌል ጋር አብረን ጎን ለጎን እንፈጽማለን እያሉ ያስቸግሩ ለነበሩት አይሁድና አይሁድ ዘመም ክርስቲያኖች (Judaizing Christians) ነበር፡፡ (ተሐድሶዎች ሆይ፣ እንዲህ ያሉት አይሁድ ዘመም ክርስቲያኖች ደግሞ የኦሪት ልማዳቸው እንዲቀር በኒቅያ ጉባኤ መወሰኑ በክርስትና ታሪክ አሳዛኝ ውሳኔ ነው እያላችሁ የተሟገታችሁላቸው መሆናቸውን አትርሱ)፡፡ በተጨማሪም የሚከተሉትን እንመልከት፡-

- "ትምክህት እንግዲህ ወዴት ነው? እርሱ ቀርቷል። በየትኛው ሕግ ነው? በሥራ ሕግ ነውን? አይደለም፣ በእምነት ሕግ ነው እንጂ።" ሮሜ 3፡27
- "ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለንና።" ሮሜ 3፡28
- "እንግዲህ ሕግን በእምነት እንሽራለንን? አይደለም፣ ሕግን እናጸናለን እንጂ።" ሮሜ 3፡31
- "ከሕግ የሆኑትስ ወራሾች ከሆኑ እምነት ከንቱ ሆኗል፣ የተስፋውም ቃል ተሽሯል" ሮሜ 4፡14
- "ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን አውቀን፣ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል።" ገላ. 2፡16
- "እንግዲህ መንፈስን የሚሰጣችሁ በእናንተም ዘንድ ተአምራት የሚያደርግ በሕግ ሥራ ነውን ወይስ ከእምነት ጋር በሆነ መስማት ነው?" ገላ. 3፡5
- "ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሏልና ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንዳይጸድቅ ግልጥ ነው።" ገላ. 3፡11
- "እንደዚህ ከእምነት የሆኑት ካመነው ከአብርሃም ጋር ይባረካሉ።" ገላ. 3፡9

እንግዲህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በእነዚህ በጠቀስናቸውና በሌላውም ትምህርቱ መዳን የሚገኘው ሕገ ኦሪትን በመፈጸም (በመሥዋዕተ ኦሪት) ሳይሆን መሥዋዕተ ወንጌል በሆነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን መሆኑን በአጽንኦት ይናገራል እንጂ መዳን "በእምነት ብቻ ነው" አላለም፡፡ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ አያስፈልግም፣ ምግባር ትሩፋት አያስፈልግም አላለም፡፡ ስለዚህ በክርስቶስ መሥዋዕትነት የተተካውን የሕገ ኦሪትን መሥዋዕትና ሥርዓት በተመለከተ የተነገረውን ሁሉ "ሕግ" የሚለውን ቃል ብቻ ነጥሎ በመውሰድ በክርስቶስ ያመነ ሁሉ በመንፈሳዊ ሕይወት በመጽናትና በመጋደል ፋንታ አውታሯን እንደ በጠሰች በቅሎ በኃጢአት ሜዳ እንዳሻው እንዲፈረጥጥ ለማድረግ የሚያደርጉት ጥረት ሁሉ የማታለል መንገድ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፡፡

እስኪ ሌላውን ሁሉ እናቆየውና ራሱ ባለቤቱ ጌታችን "ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው፣ የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል፣ እኔም እወደዋለሁ፣ ራሴንም እገልጥለታለሁ" በማለት እርሱን ለመውደዳችን ምልክቱና ማስረጃው ትእዛዛቱን መጠበቅ መሆኑን አልተናገረምን?

ዮሐ. 14፡21 እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ "አውቄዋለሁ የሚል ትእዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው፤ እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም" አይልምን? 1 ዮሐ. 2፡4 እነዚህን ሁሉ ትእዛዛቱን መጠበቅ እንደሚገባን፡ ትእዛዛቱን መጠበቅም ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር የምንገልጥበት የተቀደሰ ነገር መሆኑን ይነግሩናል እንጂ "ካመናችሁ በቃችሁ፤ ኃጢአት ብትሠሩም ችግር የለውም" አይሉም፡፡ ትእዛዛቱን መጠበቅ ሕጉን ማክበር የጽድቅ መሰናክል ናቸውም አይሉም፡፡

እግዚአብሔር የሰጠው ሕግ (ትእዛዝ) የፍቅሩ መገለጫ ነው እንጂ በሰው ላይ የተጫነ ሸክም አይደለም፡፡ በኦርቶዶክሳዊ ክርስትና አስተምህሮ ሕገ እግዚአብሔር ጸጋ እንጂ ጫና ወይም ሸክም አይደለም፡፡ ክላይ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለዚህ ሲያስተምር "ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል፤ እኔም እወደዋለሁ፡ ራሴንም እገልጥለታለሁ" ማለቱን ጠቅሰናል፡፡ ዮሐ. 14፡21 በዚህ የጌታችን ትምህርት መሠረት የእግዚአብሔር ወዳጅ ለመሆን እነዚህ ሁለት ነገሮች ያስፈልጋሉ ማለት ነው፡ ፡ አንደኛው "ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው" እንዳለ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መሰጠትና ያንን አጽንቶ መያዝ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጌታችን "የሚጠብቃትም" እንዳለ ይህን የተሰጠውን ሕጉን መጠበቅ ናቸው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ሕጉን የሰጠን የእርሱ ወዳጆች ለመሆን እንችል ዘንድ ነው እንጂ በእኛ ላይ ገዢነቱን ለማሳየት ወይም ደግሞ ሕጉን በመስጠቱ እርሱ ከእኛ የሚያገኘው እንዳች ነገር ስላለ አይደለም፡፡ ከመጀመሪያውም ለአዳም ሕጉን የሰጠው ለዚሁ ለወዳጅነት ክብር ስላጨው ለዚያ ክብር እንዲበቃ ነበር፡፡

እግዚአብሔርን በእውነት የሚወደውና የእርሱ ፍቅር ያለው ሰው ይህን ፍቅሩን የሚገልጠው የእግዚአብሔርን ሕጉን በመጠበቅ ነው፡፡ ጌታችን ይህን በተመለከተ ሲናገር "የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን፤ በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን። የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም" በማለት ቃሉን መጠበቅ እርሱን የመውደድ፤ ቃሉን አለመጠበቅ ደግሞ እርሱን ያለመውደዱ መገለጫ መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ አስተምሮናል፡፡ ዮሐ. 14:23-24

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ሕግ ስለ መጠበቅ ሲናገር "በመንገዳቸው ንጹሐን የሆኑ፤ በእግዚአብሔርም ሕግ የሚሄዱ ምስጉኖች ናቸው። ... ትእዛዛትህን እጅግ እንጠብቅ ዘንድ አንተ አዘዝህ" ይላል፡፡ መዝ. 118፡1፤4 እንዲሁም እስራኤላውያንን ከግብፅ ምድር አውጥቶ በተለያዩ አሕዛብ ተይዛ የነበረችውን ሀገር ያወረሳቸው ለምን እንደ ሆነ ሲናገር "ሕዝቡንም በደስታ የተመረጡትንም በእልልታ አወጣ። የአሕዛብንም አገሮች ሰጣቸው፤ የወገኖችንም ድካም ወረሱ፡፡ ከመ ይዕቀቡ ሕጉ ወይኅሡ ሥርዓቶ - ሕጉን ይጠብቁ ዘንድ፤ ሥርዓቱንም ይፈልጉ ዘንድ" ይላል፡፡ መዝ. 104፡43-45 ስለዚህ የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅና ሥርዓቱን መሻትና መከተል በእግዚአብሔር ለሚያምኑ ሁሉ የተሰጠ ተግባር እንጂ አምኛለሁና ሕጉና ትእዛዙ አያስፈልገኝም ለማለት የሚያስችል እንዳችም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻ የለም፡፡

በራእየ ዮሐንስ ላይም "የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁት፤ ኢየሱስንም በማመን የሚጸኑት ቅዱሳን ትዕግሥታቸው በዚህ ነው" በማለት ቅዱሳን የተባሉት ኢየሱስን በማመን የሚጸኑት ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁም መሆናቸው ተገልጿል፡፡ ራእ. 14፡12 ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ ላይም በብሉይ ኪዳን በሃይማኖት ስለ ተጋደሉ አባቶችና እናቶች ተጋድሎ በሰፊው ካስታወሰ በኋላ ". . . በነፍሳችሁ ዝላችሁ እንዳትደክሙ፤ ከኃጢአተኞች በደረሰበት እንዲህ ባለ መቃወም የጸናውን አስቡ። ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም" በማለት "ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ" ጽኑ የሆነ ተጋድሎ ገና ከፊታችን ተደቅኖ የሚጠብቀን ሰዎች እንጂ "ጨርሻለሁ" እያልን ልንፎክር የሚገባን እንዳይደለን ጽኑዕ በሆነ ሁኔታ ነገረን፡፡

ይህን ከፊታችን ያለውን ጽኑ ተጋድሎም በትዕግሥት እንሮጥ ዘንድ "የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ" በማለት መክረን፡ አሳሰበን፡፡ ዕብ. 12፡1-4

በመጽሐፍ ቅዱስ ዘለዓለማዊ ሕይወትን እንዴት እንደምናገኝና እንደምንድን ከተነገሩት ብዙ አንቀጾች መካከል የሚከተሉትን እንጨምር፡-

- "እንግዲህ እንደዚያ እንደ አለመታዘዝ ምሳሌ <u>ማንም እንዳይወድቅ ወደዚያ ዕረፍት ለመግባት እንትጋ</u>።" ዕብ. 4፡11
- "በብዙ መጽናት፥ በመከራ፥ በችግር፥ በጭንቀት፥ በመገረፍ፥ በወኅኒ፥ በሁከት፥ በድካም፥ እንቅልፍ በማጣት፥ በመጦም፥ በንጽሕና፥ በእውቀት፥ በትዕግሥት፥ በቸርነት፥ በመንፈስ ቅዱስ፥ ግብዝነት በሌለው ፍቅር፥ በእውነት ቃል፥ በእግዚአብሔር ኃይል፥ ለቀኝና ለግራ በሚሆን በጽድቅ የጦር ዕቃ . . ." 2 ቆሮ. 6፡5-8
- "ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናልና" የሐዋ. 14፡22
- "እንግዲህ ወደ ዕረፍቱ ለመግባት ተስፋ ገና ቀርቶልን ከሆነ፥ ምናልባት ከእናንተ ማንም የማይበቃ መስሎ እንዳይታይ እንፍራ" ዕብ. 4፡1
- "በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ" 2 ፊል 2፡12
- "እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።" ማቴ. 24፡13

ስለዚህ "በእምነት ብቻ መዳን" የሚለውና የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ አላስፈላጊ ነው፥ ለመዳን ሚና የለውም የሚለው የፕሮቴስታንቶችና የልጆቻው የተሐድሶዎች ትምህርት አንዳችም የመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት የለውም፡፡

## 3.7.3.3 በተቀበሉት ጸጋ መጽናት፣ ተጋድሎና ክርስቲያናዊ መልካም ሥራ ለመዳን ያላቸው ሚና፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መዳን የሚያስተምረው ትምህርት ሁለቱንም ማዕከል ባደረገና በጠበቀ መልኩ ነው፡፡ በአንድ በኩል ድኅነትና ዘላለማዊ ሕይወት በሰው ጥረትና ዓቅም የተገኘና የሚገኝ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቸርነት የተሰጠ የነጻ ስጦታ (ጸጋ) መሆኑን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ የመዳን ጸጋ ለመካፈል እያንዳንዱ ሰው ከማመን ጀምሮ ከምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ጋር በዚህ ዓለም ይኖርበት ዘንድ እስከ ተሰጠው እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ መጽናትና መጋደል ያለበት መሆኑን ቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል ያስተምረናል፡፡ ይህን ያልተረዱ ወይም የማይቀበሉ መናፍቃን ግን በአንድ በኩል ድኅነት በሰው ዓቅምና ጥረት ብቻ የሚገኝ አስመስለው በማውራት ወደ ፔላጊየስ ስህተት ያጋድላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መዳን ያለ ሰውዬው ፈቃድና ምርጫ እንደሚጫንበት ሽክም በመቁጠር በእምነትና በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሱታፌ የሚጀመረውንና ከዚያም በዚያ ጸጋ ለመጽናትና በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ መጋደል እንደሚያስፈልግ አስመስለው የሚናገሩ ከእውግስጢኖሳዊ የቅድመ ምርጫና ቅድመ ውሳኔ (Predestination) እና በግዴታ በሰው ላይ የሚጫን ጸጋ እግዚአብሔር (Irresistible grace) እርሾ የቀዱ ሉተራውያንና ካልቪናውያን ፕሮቴስታንቶችና ስማቸው የበዛ ፕሮቴስታንታውያን ተሐድሶዎች ናቸው፡፡

ይህን የተመለከቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃሎችን እንመልከት፡-

ወደ ሕይወት ይመራን ዘንድ የተሰጠን ቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈልን ግን ሁለቱንም ሚዛን በጠበቀ መልኩ ነው፡፡ ለአብነትም የተወሰኑትን እንመልከት፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ መዳን የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ መሆኑን ሲናገር እንዲህ አለ፡-

> ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፥ በጸጋ ድናችኋልና፤ በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለ ጠግነት ያሳይ ዘንድ ከእርሱ ጋር አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን። <u>ጸጋው በእምነት አድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።</u> ኤፌ. 2፥5-10

ይህን ከገለጸ በኋላ ደግሞ ከዚያው ቀጥሎ ወደ ሌላ ነገር ከመሄዱ በፊት "እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን <u>መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን</u>" በማለት መልካም ሥራን መሥራት እንኳን አያስፈልግም ሊባል ይቅርና እንዲያውም የተፈጠርንለት ምክንያት መሆኑን ተናገረ፡፡ ኤፌ. 2፥5-10

- "እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል፤ በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናንና ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል፤ ለዓመፃ በሚታዘዙ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙትና በአድመኞች ላይ ግን ቍጣና መቅሠፍት ይሆንባቸዋል። ክፉውን በሚያደርግ ሰው ነፍስ ሁሉ መከራና ጭንቀት ይሆንበታል፥ አስቀድሞ በአይሁዳዊ ደግሞም በግሪክ ሰው፤ ነገር ግን በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል፡፡" ሮሜ 1፥6-10
- በተጨማሪም <u>"በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና"</u> በማለት ሕግን ማድረግ የሚያጸድቅ ተግባር እንጂ የሚያስወቅስ አለመሆኑን መምህራችን አስተምሮናል፡፡ ሮሜ 2፡13 ስለሆነም እኛ ስለ እምነትና በእምነት ስለሚገኘው ጽድቅ የተናገረውን እናምናለን፤ ስለ መልካም ሥራና ሕግጋተ እግዚአብሔርን ስለ መፈጸም የተናገረውንም እናምናለን፡፡ ሁለቱም የሚጣሉና ወይ ይህን፤ አለዚያ ያንን፤ ከሁለት አንዱ ምረጥ የሚባሉ ሳይሆኑ የሚመጋገቡ መሆናቸውን፤ መልካም ሥራ በእምነት ላይ ተመሥርቶ የሚያድግ መሆኑን እናምናለንና፡፡ ተሐድሶዎች ግን ሉተር የጨመረውን "በእምነት ብቻ" የሚለውን በማንጠልጠል በሕይወታቸው መልካም ፍሬ ለማፍራት የሚያስፈልገውን ተጋድሎ ለመሸሽ ሲሉ ሰው ሠራሽ መንገድ ፈጥረዋል፡፡ "ክፉ በመሥራት ደስ የሚላቸው፤ በጠማማነትም ደስታን የሚያደርጉ፤ መንገዳቸውን የሚጠመዝዙ፤ አካሄዳቸውንም የሚያጣምሙ ናቸው" ተብሎ በመጽሐፍ የተነገረባቸው ናቸው፡፡ ምሳ. 2፡15 ነቢዩም "ወዛቲ ፍኖቶሙ ዕቅፍቶሙ - ይህች መንገዳቸው መሰናከላቸው ናት" ይላቸዋል፡፡ መዝ. 48፡13
- "ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፤ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፤ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ። . . . ስለ ሥጋችሁ ድካም እንደ ሰው ልማድ እላለሁ። ብልቶቻችሁ ዓመፃ ሊያደርጉ ለርኵስነትና ለዓመፃ ባሪያዎች አድርጋችሁ እንዳቀረባችሁ፥ እንደዚሁ ብልቶቻችሁ ሊቀደሱ ለጽድቅ ባሪያዎች አድርጋችሁ አሁን አቅርቡ። አሁን ግን ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ ለእግዚአብሔርም ተገዝታችሁ፤ ልትቀደሱ ፍሬ አላችሁ፥ መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው።" ሮሜ 6፥13-22

ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በላከው የመጀመሪያ መልእክቱ ላይ ጥንት ለእስራኤላውያን የተደረገውን ቸርነት ዘርዝሮ ካስታወሳቸው በኋላ፣ ሆኖም ግን ያ ሁሉ ቸርነት ከተደረገላቸው ከእነርሱ በሚበዙት እግዚአብሔር ደስ እንዳልተሰኘ ገለጸ፡፡ ከዚያም በማያያዝ ይህን ታሪክ በማስታወስ እነዚያን አስታውሶ እርሱ መልእክቱን የሚጽፍበትን ምክንያት ሲያስረዳ እንዲህ አለ፡- "*ይህም ሁሉ እንደ ምሳሌ ሆነባቸው፤ እኛንም የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን ሊገሥጸን ተጻፈ፡፡ ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ፡፡*" 1 ቆሮ. 10፡1-12 እስራኤላውያን ከግብጽ ባርነት ነጻ ሲወጡ የተደረገላቸው ድንቅ ተአምራትና ፀቢይ ቸርነት በሐዲስ ኪዳን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚፈጸመው የምእመናን ከባርነት ወደ ነጻነት መውጣትና ከሞት ወደ ሕይወት መሸጋገር ምሳሌ ነበር፡፡ ሐዋርያው ይህን በማነጻጸር እንዲህ አለ፡-

> *ወንድሞች ሆይ፤ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ፡፡ አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ፤ ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ፤ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ፤ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ፤ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ድንጋይ ጠጥተዋል፤ ያም ድንጋይ ክርስቶስ ነበረ፡፡ እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ በሚበዙት ደስ አላለውም፣ በምድረ በዳ ወድቀዋልና፡፡ ... ይህም ሁሉ እንደ ምሳሌ ሆነባቸው፤ እኛንም የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን ሊገሥፀን ተጻፈ፡፡* 1 ቆሮ. 10፡1-5 ፤ 11

እስራኤላውያን ያን ሁሉ ጸጋ በማግኘታቸው ብቻ እንዳልተጠቀሙ ሁሉ ክርስቲያኖችም በመጠመቃቸውና ከቅዱስ ምሥጢር በመካፈላቸው ብቻ ሕይወታቸው ለዚህ ጸጋ ተስማሚና ተገቢ እስካልሆነ ድረስ እንደማይጠቀሙ ሲገልጽ ለእስራኤላውያን የተሰጣቸውን ጸጋና የተቀጡትን ቅጣት በምሳሌነት በማንሣት አስረዳ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "*ይህም ሁሉ እንደ ምሳሌ ሆነባቸው፤ እኛንም የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን ሊገሥፀን ተጻፈ*" ሲል ምን ማለቱ ይሆን? ለእነርሱ (ለእስራኤላውያን) ጥንት የተደረገው ስጦታ ምሳሌያዊ ሲሆን ለእኛ (ለክርስቲያኖች) የተደረገው ደግሞ አማናዊ ነው፤ ለእነርሱ የተደረገው ጊዜያዊ፣ ለእኛ የተደረገው ቀዋሚና ዘለዓለማዊ፤ ለእነርሱ የተደረገው ምድራዊ፣ ለእኛ የተደረገው ደግሞ ሰማያዊ መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡

ሐዋርያው እንዲህ ማለቱ ነው፡- እናንተ (ክርስቲያኖች) የክርስቶስን ሥጋ እንደምትበሉ እነዚያ (እስራኤላውያን) መና በሉ፤ እናንተ ከጎኑ የፈሰሰውን ክቡር ደሙን እንደምትጠጡ እነዚያ ደግሞ የክርስቶስ ምሳሌ ከሆነው ከዓለት ላይ የፈለቀ ውኃን ጠጡ፡፡ ዓለቱን ሙሴ በበትሩ ሲመታው ጽሩይ የሆነ ውኃ ፈልቆላቸው ይጠጡ እንደ ነበር እኛም በመስቀል ላይ ጎኑ በጦር በተወጋ ጊዜ የፈሰሰውን ሕይወት ሰጪ የሆነውን ክቡር ደሙን እንጠጣለን፡፡ ለእስራኤላውያን በጥንት ዘመን ከግብጽ ሲወጡ ምሳሌያዊ የሆነውን ያን መብልና መጠጥ ያዘጋጀ ክርስቶስ ለእናንተ ደግሞ አማናዊ የሆነውን የራሱን ሥጋና ደም አዘጋጀ፤ እነዚያን በቀይ ባሕር መካከል ውኃውን እንደ ግድግዳ ግራና ቀኝ አቁሞ ያሳለፋቸው እርሱ ለእናንተ ጥምቀትን ሰጠ፡፡ ነገር ግን ይህ ሁሉ በተደረገላቸው በብዙዎቹ ደስ አላለውም፡፡ ምንም ያህል ቸርነቱን ቢያደርግላቸው በበደሉ ጊዜ ግን ከመቅጣት አልተዋቸውም፡፡ በቁጥር ብዙ መሆናቸው፣ ብዙ ጸጋ መሰጠታቸው፣ የአባቶች የቃል ኪዳን ልጆች መሆናቸው ሲያጠፉ ከመቀጣትና ከመቀሠፍ አላዳናቸውም፡፡ "*በምድረ በዳ ወድቀዋልና*" ያለው ለዚህ ነው፡፡

ለእነዚያ (ለእስራኤላውያን) የተደረጉት ስጦታዎች ምሳሌዎች እንደ ነበሩ ሁሉ ቅጣቶቹም እንዲሁ ምሳሌያዊ ናቸው፡፡ እሥራኤላውያን በቀይ ባሕር መካከል ማለፋቸው በሐዲስ ኪዳን ዘመን ክርስቲያኖች በውኃ ለመጠመቃችን ምሳሌ ነበር፡፡ እነዚያ ከሰማይ የሚወርድ መና መመገባቸውና ከዓለት የፈለቀውን ውኃ መጠጣታቸው እኛ አማናዊ የሆነውን ኅብስተ ሕይወት የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም ለመመገባችን ምሳሌ ነበር፡፡

እነርሱ ያገኙት ጸጋ ምሳሌያዊ የነበረ ሲሆን እኛ ያገኘነው ደግሞ አማናዊውን (እውነተኛውን) ነው፡፡ በሐዲስ ኪዳን ዘመን ላለን ለእኛ ስጦታዎቹ አማናዊና ዘለዓለማዊ እንደ ሆኑ ሁሉ ቅጣቱም እንዲሁ አማናዊና ዘለዓለማዊ ነው፡፡ በእሥራኤላውን ሕይወት ምሥጢረ ቁርባን አስቀድሞ ከዓለት በፈለቀው ውኃና ከሰማይ በወረደው መና ምሳሌ፣ ጥምቀት ደግሞ በባሕር መካከል በማለፍ ምሳሌ እንደ ታዩ በዚያው ሳይቀሩ ምሳሌዎቹ እውነተኛና ቀዋሚ በሆነው ማለትም መናው በቅዱስ ሥጋው (ዮሐ. 6፡48-51)፣ ከዓለት የፈለቀው ውኃ ከጎኑ በፈሰሰው ክቡር ደሙ፣ በባሕር መካከል ማለፋቸው በጥምቀት እንደ ተተኩና በምሳሌ ብቻ ታይተው እንዳልቀሩ፣ እንደዚሁም ሁሉ ለምሳሌያዊው ጸጋ ብቁ ባልሆኑት በእነዚያ ላይ ያን ጊዜ የደረሰባቸውና የተፈጸመባቸው ቅጣት ዛሬም አማናዊውን ጸጋ ከተቀበሉ በኋላ ሕይወታቸው ለዚያ ተገቢ በሆነ መንገድ በማይኖሩ ላይ እንዲሁ ይደርሳል ይፈጸማል ማለቱ ነው፡፡

በቸርነትና በጸጋ ስጦታው ምሳሌው ቀድሞ አማናዊው እንደ ተከተለ (በኋላ እንደ መጣ) በቅጣቱም እንዲሁ ነው፡፡ እነዚያ የተሰጡት ጸጋና የተቀጡት ቅጣት ምሳሌያዊ ነው፤ እኛ ደግሞ የተሰጠን ጸጋ አማናዊ እንደ ሆነ ሁሉ ካጠፋን ቅጣቱም እንደዚያው አማናዊ ነው፡፡ አማናዊው ስጦታ ከምሳሌው እንደሚበልጥ ቅጣቱም እንዲሁ ከእነዚያ ቅጣት በዚያው መጠን ይበልጣል፡፡

ምሳሌያዊ የሆነውን ቸርነትና ስጦታ ያቃለሉትና ለዚያ ምሳሌያዊ ጸጋ ተስማሚ ያልሆነ ሕይወትን ያሳዩት እስራኤላውያን እንዲያ ከተቀጡ ለአማናዊው ጸጋ ተስማሚ የሆነ ሕይወት የሌለው ከሆነ ማን ከቅጣት ሊያመልጥ ይችላል? እንዲያውም የሐዲስ ኪዳኑ ስጦታ አማናዊ እንደ መሆኑ መጠን ከብሉይ ኪዳን ምሳሌያዊ ጸጋ ፈጽሞ እንደሚበልጥ ሁሉ አማናዊውን ጸጋ ያቃለለ ቅጣቱም በጸጋው ታላቅነት መጠን ከብሉይ ኪዳኑ ቅጣት ፈጽሞ የበለጠና ዘለዓለማዊ ነው፡፡

በዚህም በዓመጸኛነታቸውና ባለ መታዘዛቸው ምክንያት ከግብፅ ከወጡት ከአንድ ሚሊዮን ሕዝብ በላይ መካከል ከሁለት ሰዎች (ካሌብና ኢያሱ) በስተቀር ሌሎቹ ወደ ተስፋዪቱ ምድር ሳይገቡ በቃዴስ በርኔ በረሓ ወድቀው ወድቀው ቀርተዋል፡፡ ዘጸ 12፡37 ይህንም ሐዋርያው ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

> ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት፣ በማስመረር እንደ ሆነ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ፡፡ ሰምተው ያስመረሩት እነማን ነበሩ? በሙሴ ተመርተው ከግብፅ የወጡ ሁሉ አይደሉምን? አርባ ዓመትም የተቆጣባቸው እነ ማን ነበሩ? ሬሳቸው በምድረ በዳ የወደቀ፣ ኃጢአትን ያደረጉት እነርሱ አይደሉምን? ካልታዘዙትም በቀር ወደ ዕረፍቱ እንዳይገቡ የማለባቸው እነ ማን ነበሩ? ባለማመናቸውም ጠንቅ ሊገቡ እንዳልቻሉ እናያለን፡፡ ዕብ. 3፡15-19

ሐዋርያው አሁንም የዚህን ነገር ክብደት እንዲህ ሲል በአጽንዖት ይገልጻል፡-

> ስለዚህ ከሰማነው ነገር ምናልባት እንዳንወሰድ ለእርሱ አብልጠን ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል፡፡ በመላእክት የተነገረው ቃል ጽኑ ከሆነ መተላለፍና አለመታዘዝም ሁሉ የጽድቅን ብድራት ከተቀበለ እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንል እንዴት እናመልጣለን? ዕብ. 2፡1-3

ስለሆነም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከንጽሕተ ንጹሐን ከቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ሰው ሆኖ ወንጌልን አስተምሮ መከራ ተቀብሎ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ከመሠረተውና በቸርነቱ ከሰጠን የመዳን መንገድ ወጥቶ ለቃሉ ለማይታዘዝና በዓመፅና በኃጢአት ጎዳና ለሚጓዝ ሰው መዳን አይቻለውም ማለት ነው፡፡ እስራኤላውያን የአማናዊው የሐዲስ ኪዳን መዳን ምሳሌና ፋና ወጊ የነበረውን ጸጋ - ከግብጽ መውጣትን (ከሲኦል የመውጣት ምሳሌ ነበር)፣ በበጉ ደም ከቅስፈተ ሞት መዳንን (በክርስቶስ ደም ከሞት ለመዳናችን ምሳሌ ነበር)፣ በባሕር መካከል ማለፍን (የጥምቀት ምሳሌ ነበር)፣ መና ከሰማይ ወርዶ መመገብን (የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋ ምሳሌ ነበር)፣ ውኃ ከዓለት ፈልቆ መጠጣትን (የክቡር ደሙ ምሳሌ ነበር)

- እነዚህን ሁሉ ጸጋዎች ተሰጥተው የነበረ ቢሆንም ከቃሉ ትእዛዝ በወጡና በተለያየ ኃጢአት እግዚአብሔርን ባሳዘኑ ጊዜ ከመቀጣትና ከመጥፋት አልዳኑም፡፡

ከፉ ነገር በመመኘት ባሳዘኑት ጊዜ ተቀጡ፡፡ ስለዚህም ሐዋርያው *"እነዚህም ክፉ ነገር እንደ ተመኙ እኛ ደግሞ እንዳንመኝ ይህ ምሳሌ ሆነልን"* ሲል ያስጠነቅቀናል፡፡ ከዚያ ሁሉ መከራ ያወጣቸውን፣ በጭንቃቸው ጊዜ የደረሰላቸውንና በዘጠኝ ተአምራት፣ በአሥረኛ ሞተ በኩር በአሥራ አንደኛ ሥጦመተ ባሕር ፈርዖንን ያህል ጽኑ ገገር ድል አድርጎ ያወጣቸውንና መና እያወረደ ውኃ እያፈለቀ እየመገባቸው የነበረውን አምላካቸውን እግዚአብሔርን የበሉት የመናውና የጠጡት የውኃው ጣዕሙ ከአፋቸው ሳይጠፋ ካዱት፡፡ ይባስ ብለው አሮንን ሙሴ ከተራራው ሳይወርድ እንደ ዘገየ ባዩ ጊዜ በአንድነት ወደ አሮን ተሰብስበው *"ይህ ከግብፅ ምድር ያወጣን ሰው ሙሴ ምን እንደ ሆነ አናውቅምና ተነሥተህ በፊታችን የሚሄዱ አማልክት ሥራልን"* አሉት። *ከግብጽ ያወጣቸውን እግዚአብሔርን ረስተው "ይህ ከግብፅ ምድር ያወጣን ሰው ሙሴ"* አሉ፡፡ ይኽ እግዚአብሔርን የመካዳቸው መገለጫ ነበር፡፡

ከዚያም አሮን *"በሚስቶቻችሁ በወንዶችና በሴቶች ልጆቻችሁም ጆሮ ያሉትን የወርቅ ቀለበቶች ሰብራችሁ አምጡልኝ"* አላቸው። ሕዝቡም ሁሉ በጆሮዎቻቸው ያሉትን የወርቅ ቀለበቶች ሰብረው ወደ አሮን አመጡለት። አሮንም ከእነርሱ የተቀበለውን ወቅር የጥጃ ቅርጽ ያለው ጣዖት አድርጎ ሠራው፡፡ ከዚያም ሕዝቡ ማልደው ተነሥተው ለጣዖቱ የሚቃጠል መሥዋዕት ሠው፡፡ ሕዝቡም ሊበሉና ሊጠጡ ተቀመጡ፤ ሊዘፍኑም ተነሡ። በዚያ ኃጢአት ምክንያት በዚያ ቀን ከሕዝቡ ሦስት ሺህ ሰዎች ተቀሠፉ። ስለዚህም ነው ሐዋርያው *"ሕዝብም ሊበሉ ሊጠጡም ተቀመጡ፣ ሊዘፍኑም ተነሡ ተብሎ እንደ ተጻፈ ከእነርሱ አንዳንዶቹ እንዳደረጉት ጣዖትን የምታመልኩ አትሁኑ"* ሲል የመከረን፡፡ 1 ቆሮ. 10፡7

እንደ ገናም ወደ ከነዓን በጉዞ ላይ ሳሉ በለዓም የተባለው ጠንቋይ ከመከረው ጥልቅ የሆነ ክፉ የተንኮል ምክር የተነሣ ከምድያማውያን ሴቶች ጋር ባመነዘሩ ጊዜ በአንድ ቀን ብቻ ሃያ ሦስት ሺህ (23,000) ሰዎች በመቅሠፍት ረግፈው አልቀዋል፡፡ በአጠቃላይ መቅሰፍቱ እስከሚከለከል ድረስ ያለቁት ሃያ አራት ሺህ (24,000) እሥራኤላውያን ናቸው፡፡ አሁንም ይህን በማስታወስ ሐዋርያው *"ከእነርሱም አንዳንዶቹ እንደ ሴሰኑ በአንድ ቀንም ሁለት እልፍ ከሦስት ሺህ እንደ ወደቁ አንሴስን"* ሲል ይመክረናል። 1 ቆሮ. 10፡8

አሁንም በቃዴስ በረሃ በመንገድ ላይ ሳሉ ከሖር ተራራ ከኤዶምያስ ምድር ርቀው ሲዞሩ ሳለ የሕዝቡ ሰውነት ከመንገዱ የተነሣ በደከመ ጊዜ ሕዝቡ በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ እንዲህ ብለው ተናገሩ፡- "በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ ከግብፅ ለምን አወጣችሁን? እንጀራ የለም፣ ውኃ የለም፣ ሰውነታችንም ይህን ቀላል እንጀራ ተጸየፈው፡፡" በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ እባቦችን ሰደደ፤ ሕዝቡንም ነደፉ፤ ከእስራኤልም ብዙ ሰዎች ሞቱ።" ዘኍ. 21፡4-6 ስለዚህም ይላል ቅዱስ ጳውሎስ *"ከእነርሱም (ከእስራኤላውያን) አንዳንዶቹ ጌታን እንደ ተፈታተኑት በእባቦቹም እንደ ጠፉ ጌታን አንፈታተን።"* 1 ቆሮ. 10፡10

ምድሪቱን ይሰልሉ ዘንድ የተላኩት ከአሥራ ሁለቱ ሰላዮች መካከል ከሁለቱ (ኢያሱና ካሌብ) በስተቀር አሥሩ *"በኃይል ከእኛ ይበረታሉና በዚህ ሕዝብ ላይ መውጣት አንችልም፤ እኛ ዞረን የሰለልናት ምድር የሚኖሩባትን ሰዎች የምትበላ ምድር ናት"* እያሉ ክፉ ወሬ ለእስራኤል ልጆች አወሩ፡፡ ዘኍ. 14፡31-33 በዚያን ጊዜ የእስራኤል ማኅበር ሁሉ ድምፃቸውን አንሥተው ጮኹ፤ ሕዝቡም በዚያ ሌሊት አለቀሱ። ሙሴንና አሮንንም *"በግብፅ ምድር ሳለን ምነው በሞትን ኖሮ! ወይም በዚህ ምድረ በዳ ምነው በሞትን ኖሮ! እግዚአብሔርም በሰይፍ እንሞት ዘንድ ወደዚች ምድር ለምን ያገባናል? ሴቶቻችንና ልጆቻችን ምርኮ ይሆናሉ ወደ ግብፅ መመለስ አይሻለንምን?"* አሏቸው። እርስ በርሳቸውም "ኑ፣ አለቃ ሾመን ወደ ግብፅ እንመለስ" ተባባሉ።

በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፦

> የሚያጕረመርምብኝን ይህን ክፉ ሕዝብ እስከ መቼ እታገሠዋለሁ? . . . እንዲህ በላቸው፦ እኔ ሕያው ነኝና በጆሮዬ እንደ ተናገራችሁት እንዲሁ በእውነት አደርግባችኋለሁ ይላል እግዚአብሔር፡ - በድኖቻችሁ በዚህ ምድረ በዳ ይወድቃሉ፡፡ የተቈጠራችሁ ሁሉ፣ እንደ ቍጥራችሁ ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ የሆን ሁሉ፣ እናንተ ያጕረመረማችሁብኝ፣ ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብና ከነዌ ልጅ ከኢያሱ በቀር በእርሷ አስቀምጣችሁ ዘንድ እጄን ዘርግቼ ወደ ማልሁላችሁ ምድር በእውነት እናንተ አትገቡም። ምርኮኛ ይሆናሉ ያላችኋቸውን ልጆቻችሁን እነርሱን አገባቸዋለሁ፣ እናንተም የናቃችኋትን ምድር ያውቃሉ። እናንተ ግን በድኖቻችሁ በዚህ ምድረ በዳ ይወድቃሉ።
>
> ልጆቻችሁም በምድረ በዳ አርባ ዓመት ይቅበዘበዛሉ፣ በድኖቻችሁም በምድረ በዳ እስኪጠፋ ድረስ ግልሙትናችሁን ይሸከማሉ። ምድሪቱን በሰላለችሁባት ቀን ቍጥር፣ አርባ ቀን፣ ስለ አንድ ቀንም አንድ ዓመት፣ ኃጢአታችሁን አርባ ዓመት ትሸከማላችሁ፣ ቍጣዬንም ታውቃላችሁ። እኔ እግዚአብሔር፡ በእኔ ላይ በተሰበሰበ በዚህ ክፉ ማኅበር ሁሉ ላይ እንዲህ አደርጋለሁ ብዬ ተናግርሁ፡፡ በዚህ ምድረ በዳ ያልቃሉ፣ በዚያም ይሞታሉ። ምድሪቱንም ሊሰልሉ ሙሴ ልኳቸው የተመለሱት ሰዎች ክፉ ወሬም ስለ ምድሪቱ እያወሩ በእርሱ ላይ ማኅበሩ ሁሉ እንዲያጕረመርሙ ያደረጉ፣ ክፉ ወሬ ያወሩ እነዚያ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት በመቅሠፍት ሞቱ። ዘኁ. 14፥26-37

ቅዱስ ጳውሎስ ይኸን በማስታወስ *"ከእነርሱም አንዳንዶቹ እንዳንጎራጎሩ በሚያጠፋውም እንደ ጠፉ አታንጕርጕሩ"* ሲል መከረን። 1 ቆሮ. 10፥10

እስራኤላውያን ጣዖት ሲያመልኩ፣ ሲያጕረመርሙ፣ ሲያመነዝሩ፣ ሲመኙና ልዩ ልዩ ኃጢአት ሲሠሩ በኃጢአታቸው እንደ ተቀጡ ሁሉ እግዚአብሔር የማይወደውንና የከለከለውን የሚሠራ፣ ያዘዘውን ደግሞ የማያደርግ ማንም ቢሆን ከቅጣት አያመልጥም ማለት ነው፡፡ በተቀበልነው የመዳን ጸጋ ለመጠቀምና ለመጠበቅ ምን ማድረግ እንደሚገባን ሲያስተምረን ራሱ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ፦ "በጠበበው በር ለመግባት ተጋደሉ፤ እላችኋለሁና፣ ብዙዎች ሊገቡ ይፈልጋሉ አይችሉምም።" ሉቃ. 13፥24 እንግዲህ ጌታችን "ለመግባት ተጋደሉ" አለ እንጂ "ድነናልና ከአሁን በኋላ ምንም ነገር አልቀረንም፣ ፈጽመናል፤ እርግጠኞች ነን እያላችሁ ፎክሩ" አላለንም፡፡ ይህ የመናፍቃን ከንቱ ጩኸት ብቻ ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስም በሮሜ መልእክቱ ላይ ከአሕዛብ ወገን በክርስቶስ ያመኑ ወገኖችን በክርስቶስ ባላመኑ አይሁዳውያን ላይ መመካትን ትተው የእግዚአብሔርን ቸርነት እንዲያደንቁና በተሰጣቸው ጸጋ ጸንተው መኖር እንዲገባቸው *"እነርሱ ካለማመን የተነሣ ተሰበሩ፣ አንተም ከእምነት የተነሣ ቆመሃል። ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ። እግዚአብሔር እንደ ተፈጥሯቸው ለነበሩት ቅርንጫፎች የራራላቸው ካልሆነ ለአንተ ደግሞ አይራራልህምና። እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና ተመልከት፤ ጭከናው በወደቁት ላይ ነው፣ በቸርነቱ ግን ጸንተህ ብትኖር የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ላይ ነው፤ ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቆረጣለህ"* በማለት በአጽንኦት ይናገራል፡፡ ሮሜ 11፥20-22 ይህም ማለት በእምነት ባገኙት ጸጋ ጸንተው ካልኖሩ መቆረጥና መሰበር እንደሚገጥማቸው ይናገራል እንጂ አንድ ጊዜ ካመናችሁ በኋላ ከዛፉ (ከክርስቶስ) የሚለያችሁ ምንም ነገር የለም አላለም፡፡ ከዛፉ ላለመቆረጥ "በቸርነቱ ጸንቶ መኖር" የእያንዳንዱ ድርሻ መሆኑን የተናገረው በግልጽ ነው፡፡ ሰው በራሱ ሥራ በግንድ ከተመሰለው ከክርስቶስ ጋር ሊዋሐድ አይችልም፤ ሆኖም በእምነትና በምሥጢራት ከተዋሐደ በኋላ እንዳይቆረጥ መጽናትና መጋደል ግን ይኖርበታል፡፡

ስለሆነም እነዚያ ምሳሌያዊውን ጸጋና መዳን (ከግብጽ መውጣትን) ያገኙት ለእግዚአብሔር ቃልና ለሕጉ ባልታዘዙና በተለያዩ ኃጢአቶች በወደቁ ጊዜ የተለያየ መቅሠፍት እንደ ወረደባቸውና የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ወደ ሆነችው ወደ ከነዓን ሳይገቡ እንዳደሩ ሁሉ እኛም እማናዊ የሆነውን መዳን የተቀበልንና ያገኘን ብንሆንም በዚህ ዓለም ባለንበት የሕይወት ጉዞ በሰውነታችን ላይ እግዚአብሔር የማይወዳቸውን ነገሮች ካደረግን በመዳን መንገድ መጓዝ መጀመራችን ብቻ ከዳር ሊያደርሰን አይችልም፡፡

በሕይወት ጉዟችን መጋደል የሚያስፈልገውም በተቀበልነው የመዳን ጸጋ ጸንተን ወደ ዘለዓለማዊ ክብርና ሕይወት እንድንገባ ነው፡፡ ያ ካልሆነ ግን "እኔ እንዴ ተጠምቄያለሁ፣ ቆርቤያለሁ . . ." በማለት ብቻ ከዚያ በኋላ ባለን ሕይወት በጥንቃቄና እግዚአብሔር ባዘጋጀው የመዳን መንገድ የማንሄድ ከሆነ በእነዚያ የደረሰው እንዳይደርስብን መጠንቀቅ ይገባናል፡፡ *"እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ በሚበዙት ደስ አላለውም፣ በምድረ በዳ ወድቀዋልና"* የተባለው እንዳይደርስብን በፈሪሃ እግዚአብሔርና በጥንቃቄ መኖር ይጠበቅብናል፡፡ የእስራኤላውያን ሕይወት ለእኛ ማሳያና ተግባራዊ ማስተማሪያ ነውና፣ ሐዋርያው *"ይህም ሁሉ እንደ ምሳሌ ሆነባቸው . . . እኛንም የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን ሊገሥጸን ተጻፈ"* ያለው ለዚህ ነውና፡፡ *"የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን እኛን"* ማለቱም የእነዚያ ምሳሌ ሲሆን እኛ ግን ያለነው ምሳሌው የሚፈጸምበት ዘመን ደርሶ በተፈጸመበት በዘመነ ወንጌል የምንኖር መሆናችንን ለመግለጽ ነው፡፡

በተቀበልነው የመዳን ጸጋ መጽናትና ይህንንም እስከ መጨረሻው እስትንፋስ መጠበቅ እንደሚገባን ለስም አጠራሩ ክብርና ምስጋና ይግባውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ደግሞ ደጋግሞ መላልሶ አስተምሮናል፡፡ መሠረታዊ የሆነውን የወንጌል ትመህርት ካስተማረ በኋላ ወደ መደምደሚያው ላይ እንዲህ አለ፡-

> *በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፣ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። በዚያ ቀን ብዙዎች፡- ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፣ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜም፡- ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፣ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ። ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ፥ ጎርፍም መጣ፥ ነፋስም ነፈሰ፥ ያንም ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም። ይህንም ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ፥ ጎርፍም መጣ፥ ነፋስም ነፈሰ፥ ያንም ቤት መታው፥ ወደቀም፥ አወዳደቁም ታላቅ ሆነ። ማቴ.* 7፥21-27

ታዲያ ከዚህ በላይ እንዴት አድርጎ ይንገረን?

ስለዚህም አሁን በዚህ ዓለም ሕይወት ሳለን "ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደምገባ እርግጠኛ ነኝ" እያልን የምንኩራራበት ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቸርነት ደጅ የምንጠናበትና እኛም በእርሱ ቸርነት እስከ መጨረሻው ለመጽናት የምንታገልበት ዘመን ነው፡፡ በእግዚአብሔር በኩል እኛን ለማዳን አስፈላጊ የሆነው ነገር ሁሉ የተፈጸመና አንዳች ነገር ያልቀረ ቢሆንም በእኛ በኩል ግና ግና የተሰጠንን ጸጋ መጠበቅና መጋደል ያለብን ስለሆነ ይህ የእኛ ድርሻ ገና አልተጠናቀቀም፡፡ ለዚህ ነው ጌታችን *"እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል"* ያለው፡፡ ማቴ. 24፡13 መጨረሻ መቼ ነው? ከዚህ ዓለም ሕይወት ወደ ሰማያዊ ሕይወት ስንሸጋገር ነው፡፡

በሕይወተ ሥጋ በዚህ ዓለም ያሉ ምእመናን ገና በጉዞ ላይ ናቸው፡፡ ስለዚህም እስከ መጨረሻው ይጸኑ ዘንድ መጋደል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ካልጸኑና ድል ካላደረጉ በመጀመሪያቸው ብቻ፣ የመዳንን ጸጋ ስላገኙና በድኅነት ሕይወት መጓዝ ስለጀመሩ ብቻ የክብር አክሊል የዘለዓለም ሕይወት አይገኙም፡፡ ጌታችን ለወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በራእዩ እንዲህ ብሎታል፡-

> *በሰምርኔስም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፡- ሞቶ የነበረው ሕያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል፡- . . . እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን፥ የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ። መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ። ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጐዳም። ራእ.* 2፡8-11

ይህ መልእክት የተጻፈለት የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን መልአክ (አለቃ) በክርስቶስ ማዳን ያመነና ለመዳን አስፈላጊ የሆኑትም ነገሮች ሁሉ የፈጸመ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ገና በዚህ ዓለም በተጋድሎ ላይ ስለ ነበረና ከፊቱ ብዙ ፈተናዎች ይጠብቁት ስለ ነበር እነዚያን ካላለፈና ድል ካልነሣ በስተቀር የሕይወትን አክሊል ስለማያገኝ፣ በሁለተኛው ሞት ያለመጎዳትን ጸጋ ገና ስላላገኘ፣ ይህም የሚወሰነው በሚያደርገው ተጋድሎና እስከ ሞት ድረስ የታመነ ሆኖ ጸንቶ በመገኘቱ ላይ ስለሆነ አስቀድሞ በመልእክቱ አሳሰበው፡፡ እንዲያ ባይሆን ኖሮ ይኽ ሁሉ የማሳሰቢያ ቃል ለምን ያስፈልገው ነበር? ይህ ሁሉ ቃል አላስፈላጊ የሆነ ከንቱ ድካም ብቻ በሆነ ነበር!

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ሕይወትን በሩጫ መስሎ ገልጿል፦

> *በእሽቅድምድም ስፍራ የሚሮጡት ሁሉ እንዲሮጡ፣ ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን? እንዲሁም ታገኙ ዘንድ ሩጡ። የሚታገልም ሁሉ በነገር ሁሉ ሰውነቱን ይገዛል፤ እነዚያም የሚጠፋውን አክሊል ሊያገኙ ነው፣ እኛ ግን የማይጠፋውን። ስለዚህ እኔ ያለ አሳብ እንደሚሮጥ ሁሉ እንዲሁ አልሮጥም፤ ነፋስን እንደሚጎስም ሁሉ እንዲሁ አልጋደልም፤ ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ <u>ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ</u>።*
> 1 ቆሮ. 9፡24-

በዚህ ዓለም የውድድር ሜዳ ላይ የተሰለፉና የሮጠ ሁሉ ሽልማት እንደማያገኝ ሁሉ በመንፈሳዊ ሕይወትም እንደዚያው ነው በማለት ቅዱስ ጳውሎስ ነገረን፡፡ የሚጠፋውን የዚህን ዓለም አክሊል ለማግኘት በሩጫ ሜዳ የሚሮጡ ሰዎች ያን ያህል ልምምድ፣ ያን ያህል ላብ ማፍሰስ፣ ያን ያህል ትግልና ውጣ ውረድ እንደሚያሳልፉ ሁሉ የማይጠፋውን ሰማያዊውን አክሊል ለማግኘት የሚሹም እንዲሁ ጸንተው መከራውንና ውጣ ውረዱን ሁሉ ታግሠው እንዲሮጡ እንጂ "አንድ ጊዜ በእምነት ድኛለሁና መጋደል የሚባል ነገር አታንሡብኝ፣ አታሳዩኝ" የሚባልበት አይደለም፡፡

አባታችን ቅዱስ ጳውሎስ በሚገባ መሮጥ እንደሚገባ ካስተማረን በኋላ ስለ ራሱ ሲናገር እንዲህ አለ፣ - *"ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ።"* እንግዲህ ቅዱስ ጳውሎስን ያህል ታላቅ ሐዋርያ "የተጣለ እንዳይሆን" ሥጋውን እየጎሰመ ማስገዛት ካስፈለገው "የፈልግሁትን መሆን እችላለሁ፣ አሁን መንግሥት ሰማያት እንደምገባ እርግጠኛ ነኝ" እያሉ መናገርን ምን አመጣው?

ቅዱስ ጳውሎስ "ታገኙ ዘንድ ሩጡ" ሲል አንድ ሰው የሚድነው በራሱ መሮጥ ላይ ተመሥርቶ ብቻ ነው ማለቱ አይደለም፡፡ ይህን ሲል መዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት የተገኘ መሆኑን ዘንግቶም አይደለም፡፡ ነገር ግን ያ እንዳለ ሆኖ በመንፈሳዊ የትሩፋትና የተጋድሎ መስመር የተቻለውን ያህል መሮጥ የሚገባ ስለሆነ ነው፡፡ ይህን ቃል በራሱ ካየነው መዳንን በራስ ጥረት ላይ ብቻ ያንጠለጠለው ሊመስል ይችላል፡፡ በዚህ ዓለም ባለው ሩጫ ምሳሌ አንጻር የተናገረው ስለ መንፈሳዊ ተጋድሎ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚያምኑ እውነተኛ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች የሚያደርጉት ይኸንኑ ነው፦ ከክፉ ፈቃዳችን፣ ከረቂቃንና ልቡሳነ ሥጋ ከሆኑት አጋንንት (መናፍቃንና መሣሪያዎቻቸው) ጋር መታገል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "ታገኙ ዘንድ ሩጡ" በማለት ገና ምንም ነገር ያላገኙ መሆኑንና ማግኘት አለማግኘታቸው የሚወሰነው እንደ አሯሯጣቸው መሆኑን ሲገልጽና ስለ መንፈሳዊ ተጋድሎ ሲናገር በክርስቶስ የተገኘውን የታመነ ቤዛነትና ድኅነት በመዘንጋት አይደለም፤ በክርስቶስ ቤዛነት በጸጋ የተሰጠውንና በእምነት የሚገኘውን መዳን በተመለከተ ሲናገርም ከሰዎች የሚገባውን መንፈሳዊ ተጋድሎ ዘንግቶ አይደለም፡፡ ትክክለኛ (ኦርቶዶክሳዊ) እምነትና አረዳድ የሚሆነው ለራስ ብቻ የሚስማማውን እያንጠለጠሉ ሌላውን እየጣሉ በመሮጥ ሳይሆን ሁሉንም የእግዚአብሔር ቃል በእምነት በመቀበል ስለ አንዱ ሲነገር ሌላኛውንም በማሰብና በመያዝ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

መናፍቃን ሁል ጊዜም ጠባያቸው ብዙውን የእግዚአብሔር ቃል የሌለ ያህል በመተው አንዱን ወይም ጥቂቱን ቃል ብቻ ይዘው በቅል ውስጥ እንዳሉ ጥቂት የባቄላ ፍሬዎች እነዚያን ብቻ እያንኳኩ መረበሽና ማደንቆር ነው፡፡

ከላይ እንደ ተገለጸው እኛን ለማዳን በእግዚአብሔር በኩል ያስፈልግ የነበረው ነገር ሁሉ የተፈጸመ ቢሆንም በእኛ በኩል ያለው ግን የተጀመረ እንጂ ገና ያልተቋጨ ነው፡፡ ስለዚህም ማድረግ የሚገባንን ሐዋርያው እንዲህ ሲል ይነግረናል፦ "ስለዚህ፥ ወዳጆቼ ሆይ፥ ሁል ጊዜ እንደ ታዘዛችሁ፥ በእናንተ ዘንድ በመኖሬ ብቻ ሳይሆን ይልቁን አሁን ስርቅ <u>በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፡፡</u>" ፊል. 2፡12 የራሳችንን መዳን በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ መፈጸም አለብን ማለት ያለ እምነት፥ ያለ ክርስቶስ ቸርነት በራሳችን ጥረት ብቻ እንድናለን ማለት ነውን? በጭራሽ! ቅዱስ መጽሐፍ አንዱን ሲናገር ሌላውን ጥሎና ንቀሎ ሳይሆን ያን እንዳለ በመቀበል፥ በዚያ ላይ ከዚያ ጋር መያዝና ማድረግ የሚገባንን ነገር የሚጨምር ነው፡፡

በፍርድ ቀን የምንሆነውን ይቅርና ከትንሽ ቅጽበት በኋላ በእያንዳንዳችን ሕይወት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ነገር እንኳ ማወቅ የማንችል ደካሞች መሆናችንን መዘንጋት ግብዝነት ነው፡፡ ይልቁንም ወደ መንግሥቱ ለመግባት እርግጠኞች እንደ ሆኑና በፍርድ ቀን በፊቱ ሲቆሙ እንደማያፍሩ በድፍረት መናገርና መፎከር የኃጥአን ጠባይ ሆኖ እናገኛዋለን፡፡ የጻድቃን ግብር ደግሞ ለዚያ ብቁ አለመሆናቸውን በትሕትና መናገር መሆኑን በቅዱስ መጽሐፍ መስተዋትነት እናያለን፡፡ ለአብነትም ጌታችን በፍርድ ቀን ስለሚሆነው የተናገረውን እንመልከት፡፡ በዚያን ጊዜ ስለሚሆነው ሲናገር በቀኙ የሚቆሙትን ጻድቃንን በበጎች፥ በግራው የሚቆሙትን ኃጥአንን ደግሞ በፍየሎች መስሎ ከተናገረ በኋላ በቀኙ ለሚቆሙት ለጻድቃን፦ "እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ፤ ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥ ታርዤ አልብሳችሁኛል፥ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና" ብሎ ያመሰግናቸዋል፡፡ ጻድቃንም መልሰው ይሉታል፦ "ጌታ ሆይ፥ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ? እንግዳ ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ? ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን?" ብለው ይጠይቁታል፡፡ እርሱም መልሶ "እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት" ይላቸዋል። ስለሆነም ክስቶስን ተርቦ አብልተውት፥ ተጠምቶ አጠጥተውት፥ . . . በቸርነቱ በፊቱ ለመቆም ምክንያት የሚሆን ሥራ ሠርተው ሲያበቁ እነርሱ ግን በትሕትና ሆነው "ጌታ ሆይ፥ ተርበህ መቼ አበላንህ? ተጠምተህስ መቼ አጠጣንህ?. . ." ይላሉ፡፡ ትሕትና የቅዱሳን ግብር ነው፡፡

በአንጻሩ ኃጥአንን ደግሞ ይወቅሳቸዋል፥ እንዲህ ብሎ፦ "በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል፦ እናንተ ርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ። ተርቤ አላበላችሁኝምና፥ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፥ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፥ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፥ ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና።" በዚያን ጊዜ እነርሱም እንዲህ ያለ ነገር ይደርስብናል ብለው የማያስቡ ስለነበሩ ጌታን ሊጠይቁት ይጀምራሉ፦ "ጌታ ሆይ፥ ተርበህ ወይስ ተጠምተህ ወይስ እንግዳ ሆነህ ወይስ ታርዘህ ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ መቼ አይተን አላገለገልንህም?" ይሉታል። እርሱ ግን ያን ጊዜ "እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል። እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።" ማቴ. 25፡31-46

እነዚህ በግራው የሚቆሙ ኃጥአን የተባሉት ባለቤቱ እስኪለያቸውና ከእኔ ራቁ ብሎ እስከሚያባርራቸው ድረስ በቀኝ እንደሚቆሙና ወደ ዘለዓለም ሕይወት እንደሚገቡ እርግጠኞች ስለ ነበሩ ነው "ከእኔ ወግዱ" ሲላቸው ነገሩ ድንገተኛና ያልጠበቁት የሆነባቸው፡፡ ያን ጊዜ በዚህ ዓለም እንደ ለመዱት በማጭበርበርና በቃላት ጨዋታ የሚሆን መስሏቸው "ጌታ ሆይ፣ ተርበህ ወይስ ተጠምተህ ወይስ እንግዳ ሆነህ ወይስ ታርዘህ ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ መቼ አይተን አላገለገልንህም?" ብለው ሊከራከሩ ይጀምራሉ፡፡ ለዚህ ያደረሳቸው በዚህ ዓለም ሳሉ በአጓጉል የራስ መተማመን ተዘልለው የኖሩ በመሆናቸው ነበር፡፡

ጌታችን ስለ ዘለዓለማዊው ፍርድ በተመለከተ ባስተማረው በሌላ ምሳሌም ከአሥሩ ደናግል መካከል አምስቱ ልባሞች፣ ሌሎቹ አምስቱ ደግሞ ሰነፎች ነበሩ፡፡ ልባሞቹ ከማሰሮቻቸው ጋር ዘይት የያዙ የነበሩ ሲሆን ሰነፎቹ ግን ዘይት አልነበራቸውም፡፡ የሚያሳዝነው ሰነፎቹ ደናግል ዘይት ያልነበራቸው መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ከሙሽራው ጋር ወደ ውስጥ ለመግባትና የደስታው ተካፋይ ለመሆን የዘይት አስፈላጊነት አልታሰባቸውም ነበር፡፡ ያለ ዘይት መብራት ማብራትና ወደ ሠርግ ቤት ውስጥ እንዲሁ መግባት የሚቻል መስሏቸው ነበር፡፡ ለዚህ ነበር ዘይት በሌለው በባዶ ማሰሮ ሙሽራውን ለመቀበልና ወደ ውስጥ አብረው ለመግባት የሞከሩት፡፡ ስለዚህ ባዶ ማሰሮ ብቻ ይዞ ከሙሽራው ጋር ወደ ሠርግ ቤት እገባለሁ እያሉ በከንቱ ተስፋ ማድረግ፣ በእምነት ሆኖ የምግባር ፍሬ ሳያፈሩ ያለ ጥያቄ ወደ መንግሥተ ሰማያት እገባለሁ እያሉ ማውራት የሰነፎችና የኃጥአን ግብራቸውና መገለጫቸው ነው፡፡

በአጠቃላይ እንደዚህ ያሉት ጌታችን የተናገረውን ሳይሆን የራሳቸውን መንገድ ተከትለው ከንቱ ተስፋ ሰንቀው የሚኖሩት ሰዎች በመጨረሻ በውጭ ቆመው በሩ ሲዘጋባቸው ለራሳቸው እንደሚገቡ እርግጠኞች ስለ ነበሩ ያ ራሳቸው የፈጠሩት ተስፋቸው ከንቱ ሲሆንባቸውና በውጭ ሲቀሩ "ጌታ ሆይ ክፈትልን" ይሉ ዘንድ ይጀምራሉ፡፡ "ባለቤቱ ተነሥቶ በሩን ከቈለፈ በኋላ፥ እናንተ በውጭ ቆማችሁ፦ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ ክፈትልን እያላችሁ በሩን ልታንኳኩ ትጀምራላችሁ፡፡ እርሱም መልሶ፦ ከወዴት እንደ ሆናችሁ አላውቃችሁም ይላችኋል" ያለው እንደዚህ ላሉት ነው፡፡ ሉቃ. 13፡25 በዚህም ጊዜ አሁንም ያው አብሯቸው የኖረውና ያስረጃቸው የራሳቸው አስተሳሰብ ስለማይለቃቸው "ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን?" ይላሉ፡፡ መድኃኒታችን ግን "የዚያን ጊዜም፦ ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፣ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ" በማለት የሚሰማ ጆሮ ላለው ሁሉ እውነተኛውን ትምህርት አስተማረ፡፡ ማቴ. 7፡22-24

በውጭ ከቀሩ በኋላ እንኳ እውነታውን መቀበል አቅቷቸው "ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ ክፈትልን" እያሉ በሩን ሊያንኳኩ ጀመሩ" ማለቱ የሆነው ነገር እነርሱ ከጠበቁት ተቃራኒ ስለሚሆንባቸው ነው፡፡ አሁንም ያ በቀጥታ ያለ ምንም ጥያቄ እንደምንገባ እርግጠኞች ነን የሚለው ግብዝነታቸው ያልለቀቃቸውና እውነታው የተናነቃቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም "እንደምንገባ እርግጠኞች ነን" እያሉ የራሳቸውን ጩኸት ብቻ ሲያዳምጡና በባዶ ተስፋ ራሳቸውን አሳምነው በከንቱ ሲገበዙ ኖረው በኋላ "ከእኔ ወግዱ" ሲባሉ ያልጠበቁት መዓት ስለሚሆንባቸው ነው፡፡ ሰነፎቹ ደናግልም እንዲሁ ወደ ሠርግ ቤት ያለ ዘይት እንገባለን ሲሉ መብራታቸው ሊጠፋባቸው ባለ ጊዜ "ሰነፎቹም ልባሞቹን መብራታችን ሊጠፋብን ነው፤ ከዘይታችሁ ስጡን አሏቸው"፡፡ ሆኖም ከባልጀሮቻቸው የጠየቁትን ባጡ ጊዜ ፍለጋ ሄደው ሲመለሱ በሩ ስለ ተዘጋባቸው "ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ ክፈትልን" አሉ፡፡ እርሱ ግን "እውነት እላችኋለሁ፣ አላውቃችሁም" አላቸው። ማቴ. 25፡11-13

እንግዲህ በግልጽ ጌታችን እንደ ተናገረው እርሱን በማሰብ ስለ እርሱ የምናደርገው የተራበ ማብላት፣ የታረዘ ማልበስ፣ . . . ሁሉ ዋጋ ያለው ነገር እንጂ ፕሮቴስታንቶቹና አገር በቀል ልጆቻቸው ተሐድሶዎቹ እንደሚሉት ለመዳናችን ምንም ዋጋ የሌለው ነገር አለመሆኑን ለስም አጠራሩ ክብርና ምስጋና ይግባውና ራሱ ባለቤቱ ነገረን፡፡ ከዚህ ወዲያ ማን ይንገረን? እንዲህ ሲባል ግን ከመሠረቱ ጀምሮ (እምነት፣ ምሥጢራት) ቀርተው በዚህ ብቻ ይዳናል ማለቱ እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡

ለመዳን አስፈላጊ የሆኑት እምነት፣ ምሥጢራትን መፈጸም እንዳሉ ሆነው፣ በእነዚያ ላይ ተመሥርቶ ግን የሚያስፈልጉትን ክርስቲያናዊ መልካም ሥራዎችን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላልና፦

> ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፣ መጻሕፍትም ተከፈቱ፤ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ፣ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው፤ <u>ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ</u።። ባሕርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ፣ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፤ <u>እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለ</u>። ራእ. 20፥12-13

የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል *"እንደ እምነታቸው መጠን ብቻ ተከፈሉ" አይልም፤ "ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ። . . . እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለ"* አለ እንጂ፡፡ *ታዲያ ሥራቸው ዋጋ የሌለው ከሆነ* "እንደ *ሥራቸው* መጠን ተከፈሉ" ለምን አለ?

እንደዚሁም ይህንኑ ሲያስተምረን ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ፦

> እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፣ <u>ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ</u>። አልፋና ዖሜጋ፣ ፊተኛውና ኋለኛው፣ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው በደጆችዋም ወደ ከተማይቱም እንዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው። ራእ. 22፥12-15

ታዲያ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ይከፍል ዘንድ አልፋና ዖሜጋ፣ ፊተኛውና ኋለኛው የሆነው እርሱ ሲመጣ ዋጋ ለመቀበል የሚቻለውን ያህል መዘጋጀት ይሻላል? ወይስ ይኼ ሁሉ አያስፈልግምና እንዳሻኝ ልሁን ማለት? ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ እንዲቻለን ልብስ የተባለ ሰውነታችንን በንስሐ ማጠብ? ወይስ "የቀረኝ ነገር የለም፣ ሩጫዬን ጨርሻለሁ" እያሉ በባዶው መኩራራት?

እንደዚሁም ጌታችን "በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ <u>መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ፣ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና</u> በዚህ አታድንቁ" በማለት በዳግም ምጽአቱ ጊዜ የሕይወት ትንሣኤ ለመነሣት መልካም ማድረግ እንደሚጠቅም፣ ክፉ ማድረግ ደግሞ ለፍርድ (ለኩነኔ) ለሆነ ትንሣኤ እንደሚያበቃ በአማናዊ ቃሉ አስተማረን፡፡ ዮሐ. 5፥28-29 መልካም ማድረግ የማይጠቅም፣ ክፉ ማድረግ ደግሞ የማያስጎዳ ቢሆን ኖሮ ራሱ ባለቤቱ ለምን እንዲህ አለ?

በአጠቃላይ እኛ በዚህ ዓለም ያለነው ምእመናን ገና በመሠራት ላይ ያለችው ቤተ ክርስቲያን አባላት ስለ ሆንን የክርስቶስ አካላት ሆኖ መሠራታችን እስኪፈጸም ድረስ ገና ብዙ ሂደቶችን ማለፍ ይጠበቅብናል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል የገለጸው ይህን ነው፦

> እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም። በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፣ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ *በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤ በእርሱም <u>እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ</u>።* ኤፌ. 2፥19-22

ክርስቶስ የማዕዘኗ ራስና ሰብሳቢዋ የሆነችው አንዲትና ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የዚህ ዓለም ጉዟቸውን ፈጽመው የሄዱ ነቢያትና ሐዋርያት፣ እና ሌሎችም የአካሏ የተለያዩ ክፍሎች ሆነው ተሠርተው ፈጽመዋል፡፡

ይህች ቤተ ክርስቲያንም አንድ ሁኔታ ላይ የቆመችና የማታድግ (static) ሳትሆን በየጊዜው በእምነትና በምሥጢራት አካሏ እየሆኑ በሚጨመሩ ምእመናን እያደገች የምትሄድ መሆኗን ሲገልጽ *"በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል"* አለ፡፡ ይህች አካሉ የተባለች ቤተ ክርስቲያን የምታድግባቸው የተባሉ በዚህ ዓለም ገና በተጋድሎ ላይ ያሉ ምእመናን አካል ሆነው መሠራታቸው ስላልተፈጸመ *"በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ"* አለ፡፡

አንድ ሕንፃ ሲሠራ ለግንባታው ሂደት ጠቃሚ ሆኖ የተገኘው በሕንፃው አካል ውስጥ እየገባና እየተካተተ ሲሄድ ጠቃሚ ሆኖ ያልተገኘው ደግሞ ወይ ተጠራርቦና ተበጃጅቶ መግባት የሚችል መሆኑ ይታይና ይገባል፡፡ ያ ካልሆነ ግን ወደ ውጭ ይጣላል፡፡ እየተሠራች ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ በሕንፃ አንጻር የገለጸት የክርስቶስ አካል (የሕንፃው አካል) መሆን ከጀመረ በኋላ በዚያው ካልቀጠለ ወደ ውጭ መጣል ሊገጥመው የሚችል መሆኑን ለማስረዳት ነው፡፡ ከዚያ የመጨረሻ መጣል በፊት ራሱን በማሻሻል ለአካሉ የሚመች መሆን ከቻለ ደግሞ በሕንፃው ማለት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አካል ሆኖ መሠራት ይችላል፡፡ ያ ካልሆነ ግን ጌታችን "ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ወደ ውጭ ጣሉት" የሚለው አካል ሆኖ ሊሠራ ያልቻለውን ነው፡፡ ስለሆነም በእምነት መሠረትነት በምሥጢራት ቀዳሽነትና አክባሪነት የክርስቶስ አካል ሆነው መጋጠምና መሠራት የጀመሩና በዚህ ዓለም በጉዞ ላይ ያሉ ክርስቲያኖች ገና ተሠርተው ሳያበቁ "ተሠርተን ጨርሰናል" የሚሉበት አይደለም፡፡ *"ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ"* እንደ ተባለ ገና በመሠራት ላይ ነንና፡፡

በአጠቃላይ የእግዚአብሔር ቃል ይህን እውነት - ለመዳን ከእምነትና ምሥጢራት ጋር መንፈሳዊ ተጋድሎና በመልካም ሥራ መጋደልና እስከ መጨረሻው መጽናት አስፈላጊ መሆኑን ይነግረናል፡፡ ለማጠቃለልም በዚህ ዙሪያ በሰፋት ከተገለጸው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መካከል የሚከተሉትን ብቻ እንመልከት፡-

- "መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፥ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና።" 2 ቆሮ. 5፡10
- "እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚነበልበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤ የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፥ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።" ኤፌ. 6፡11-17
- "ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቈጥራለሁ፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ።" ፊል. 3፡13-14
- "በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ በእግዚአብሔርም እውቀት እያደጋችሁ፥ ከደስታም ጋር በሁሉ ለመጽናትና ለመታገሥ እንደ ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታችሁ፥ በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን።" ቆላ. 1፡10-12
- "ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና፤ እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁኑና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው ለነገር ሁሉ ይጠቅማል። ይህ ቃል የታመነ ሁሉም እንዲቀበሉት የተገባ ነው፤ <u>ይህን ለማግኘት እንደክማለንና፥ ስለዚህም እንሰደባለን፤</u> ይህም ሰውን ሁሉ ይልቁንም የሚያምኑትን በሚያድን በሕያው አምላክ ተስፋ ስለምናደርግ ነው።" 1 ጢሞ. 4፡8-10

ቅዱስ ጳውሎስ ሲያምን አንድ ጊዜ መዳኑ የተፈጸመና ያለቀ ከሆነና የእርሱ ድርሻ ካልነበረው "ይህን ለማግኘት እንደክማለን" ለምን አለ?

- ❖ "በእምነትና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ፥ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳንዳችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን።" ዕብ. 6፥11-12
- ❖ "አቤቱ ምሕረትም ያንተ ነው፤ አንተ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ፍዳውን ትሰጣለህና።" መዝ. 61፥12

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ በፍቅር የሚሠራ እምነት" በማለት እምነታችን መልካም ሥራ መሥራት የማይችል ምውት ሳይሆን በፍቅር ሆኖ የሚሠራ ሕይወት ያለው መሆኑን ተናግሯል፡፡ ገላ. 5፥6 ጌታችንን አንድ ወጣት ባለጸጋ ወደ እርሱ ቀርቦ፦ *"የዘለዓለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን ላድርግ?"* ብሎ ሲጠይቀው *"ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ትእዛዛትን ጠብቅ"* ብሎታል፡፡ ማቴ. 19:16-18 ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ማመን ብቻ ሳይሆን በተግባርም የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም እንደሚያስፈልግ ሲናገር፦ *"በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም"* አለ፡፡ ማቴ. 7፥21

መናፍቃን መጽሐፍ ቅዱስ ባሕር በመሆኑ ከውስጡ ለእነርሱ የፈጠራ ትምህርት የሚስማማ መስሎ የሚታያቸውን ጥቂት ነገር ብቻ ነጥለው በመጠቃቀስ፣ እነርሱ ሊሆን በሚፈልጉት አቅጣጫ በመተርጎምና ሥጋና ደም ያቀበላቸውን በመናገር የሰው ልጅ ከማመን በቀር ለመዳኑ ምንም ዓይነት ድርሻ የለውም፣ ምንም ነገር አይጠበቅበትም የሚል ሃሳብ ያቀርባሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ሃሳብ ፈጽሞ የተሳሳተ ነው፡፡ እነዚህ "በጸጋው ድነናል" እያሉ የሰው ልጅ ለመዳኑ ምንም እንደማይጠበቅበት በማስመሰል ሰዎችን ወደ ሞት ጎዳና የሚመሩ የጥፋት መንገድ ሰባኪዎች ናቸው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ክርስቶስ በተቀበለው መከራና ባደረገው የማዳን ሥራ ድነናልና ከእኛ የሚጠበቅ ምንም ነገር የለም፣ ምግባር ትሩፋት መሥራት አያስፈልገንም" የሚል የተሳሳተ አመለካከት ለነበራቸውና ለሚኖራቸው ሰዎች ሲጽፍ፦ *"ነገር ግን በክርስቶስ ልንጸድቅ የምንፈልግ ስንሆን ራሳችን ደግሞ ኃጢአተኞች ሆነን ከተገኘን፤ እንግዲያስ ክርስቶስ የኃጢአት አገልጋይ ነዋ!"* በማለት *"በጸጋው ስለ ዳንን ምግባር አያስፈልገንም"* ማለትና በኃጢአት መኖር ክርስቶስን የኃጢአት አገልጋይ ማድረግ መሆኑን ገልጿል፡፡ ገላ. 2፥17

የክርስትና ጥሪ ለማመን ብቻ ሳይሆን መስቀሉን ለመሸከምና መከራ ለመቀበልም ነው፡፡ ፊል. 1:29 ጌታችን መከራ የተቀበለው እኛም የእርሱን እርአያ እንድንከተል ነውና፣ *"የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሏልና"* እንዳለ፡፡ 1 ጴጥ. 2:21 መልካም ምግባር ካልተጨመረበት ከኃጢአት መለየትና መራቅ ብቻም አይበቃም፤ *"ተገሐሥ እምእኩይ - ከክፉ ሽሽ"* ካለ በኋላ *"ወግበር ሠናየ - መልካምንም አድርግ፤ ወትነብር ለዓለመ ዓለም - ለዘለዓለምም ትኖራለህ"* ይላልና፡፡ መዝ. 36:27

ከላይ እንደ ተገለጸው ጌታችን ስለ ፍርድ ቀን ሁኔታ ሲናገር በቀኙ የሚቆሙትን ዘለዓለማዊ መንግሥቱን ሲያወርሳቸው "ተርቤ አብልታችሁኛልና፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና . . ." በማለት መልካም ሥራቸውን መስክሮ ነው፡፡ በግራው የሚቆሙትን ደግሞ "እናንተ ርጉማን፣ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘለዓለም እሳት ከእኔ ሂዱ" የሚላቸው "ተርቤ አላበላችሁኝምና . . ." ብሎ ከወቀሳቸው በኋላ ነው፡፡

ማቴ. 25፥34-36 በዚህ ዓለም ሕይወት ሳሉ ያደረጉት ድርጊት በቀኝ ወይም በግራው ለመቆም እና ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ወይም ወደ ዘለዓለማዊ ቅጣት የሚሄዱበትን መዳረሻ ፍጻሜያቸውን ወሰነ ማለት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ለመዳን መልካም ሥራ አስፈላጊ መሆኑን እንዲህ በግልጽ እየተናገረ ከዚህ በተቃራኒ የሚያስተምሩ መናፍቃንን የሚሰማና በእነርሱ የሚሳሳት ሰው ካለ ለስህተቱ እንዳችም ምክንያት የለውም፡፡

ለመዳን እምነትና ምግባር የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ በግልፅ ጽፏል፡-

> ወንድሞቼ ሆይ፤ እምነት አለኝ የሚል፤ ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን? . . . እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን? አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን? እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ፤ በሥራም እምነት እንደ ተፈጸመ ትመለከታለህን? መጽሐፍም፡- አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት ያለው ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ፡፡ ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ፡፡ እንደዚሁም ጋለሞታይቱ ረዓብ ደግሞ መልእክተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን? ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው፡፡ ያዕ. 2፥14-26

እንግዲህ ይህ የእግዚአብሔር ቃል ለመዳን እምነትና ምግባር ሁለቱም አስፈላጊዎች መሆናቸውን በማያሻማ ሁኔታ ተናግሯል፡፡

ምናልባት መንፈሳዊ ተጋድሎ መጋደል የተሳናቸውና በስም ክርስቲያን ቢባሉም በተግባር ግን የአሕዛብ ዓይነት ሕይወት መኖር የሚሹ ወገኖች ራሳቸውን በማታለያ መጋረጃ ሸፍነው "ድኅነት በጸጋ እንጂ በተጋድሎ አይደለም" በማለት ሰንፈው ለማሳነፍ መንፈሳዊ ተጋድሎን የሚነቅፉ አሉ፡፡ ነገር ግን ይኽ የዲያብሎስ ግብረ አበርነት የሞት መረኅት ነው እንጂ ማንንም የሚጠቅም አይደለም፡፡ ምንም እንኳ በቅማችን እየደከመ ሰማያዊነታችንን እየዘነጋን ምድራዊነታችን እየሳበን ብንቸገርም የእያንዳንዳችንን ጥረትና ፍላጎት ደኅና አድርጎ የሚያውቅ እርሱ የቸርነትና የምሕረት እጆቹን እንዲዘረጋልንና ብርታትንና ድል መንሣትን እንዲሰጠን መማጸኑ ከሁሉም የተሻለ ነው፡፡ መዳን እንዲሁ በማመን ብቻ የሚገኝ ቢሆንማ ኖሮ ሐዋርያው *"እስመ በብዙኅ ጻማ ወሕማም ሀለወነ ንባእ ለመንግሥተ እግዚአብሔር - ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ ድካምና መከራ እንገባ ዘንድ አለን"* ለምን ይል ነበር? የሐዋ. 14፥22 ወደ ሕይወት የሚወስደውን መንገድ ቀጭን ደጁንም ጠባብ ያሰኘው በክርስትና ሕይወት ውስጥ ጽኑ መንፈሳዊ ተጋድሎ በማስፈለጉ አይደለምን? ማቴ. 7፥13-14 በመሆኑም የሰው ልጅ ይድን ዘንድ ሥጋውን የሚጎስምባቸውና ራሱን ለፈቃደ እግዚአብሔር የሚያስገዛባቸው መንፈሳዊ ተጋድሎዎች - ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት፣ ዐቂበ ሕዋሳት፣ ምጽዋት፣ ትዕግሥት፣ ትሕትና . . . ያስፈልጉታል፡፡

"እግዚአብሔር ዓለምን ሁሉ አድኗል" ማለት እኛን ለማዳን የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ተፈጽሟል ማለት ነው፡፡ በዚህ ነገር እሺ ብሎ ለመጠቀም አለዚያም እምቢ ብሎ ለመጎዳት ለእያንዳንዱ ሰው ነጻ ፈቃድ ተሰጥቶታል፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ይገባ ዘንድ በፍቅሩ ይጠራዋል፤ ይመራዋል፤ የተለያየ የቸርነት ሥራውን ይሠራለታል እንጂ ሰውዬው ሳይፈልግ በግድ ጎትቶ አያድነውም፡፡ ይህም "ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ" ባለው ቅዱስ ቃሉ ግልጽ ሆኖ ይታያል፡፡ ዮሐ. 14፥15 ማንም ሰው ትእዛዙን ጠብቆ የመጠቀም፣ ያልፈለገ ደግሞ ባለመጠበቅ የመጎዳት ነጻ ፈቃድና ሙሉ መብት አለው፡፡

ጌታችን አልዓዛርን ከመቃብር ሲያስነሣ የመቃብሩን ድንጋይ ሰዎች እንዲያነሡ ሲያደርግ እርሱ ደግሞ ከሞተ አራት ቀን የሆነውን ጠርቶ አስነሣው፡፡ ይህን ማድረጉ ሰው በድኅነቱ ላይ የራሱ የሆነ ድርሻ እንዳለው ለማሳየት ነው፡፡ ዮሐ. 11፡39-44

ሐዋርያውም "ከወገናችንም ያሉት ደግሞ ፍሬ ቢሶች ሆነው እንዳይቀሩ፣ የግድ ስለሚያስፈልገው ነገር በመልካም ሥራ እንዲጸኑ ይማሩ" በማለት መልካም ሥራ ማድረግ ብቻ ሳይሆን "በመልካም ሥራ መጽናትም" በእጅጉ አስፈላጊ ስለሆነ "የግድ ስለሚያስፈልገው ነገር" በማለት ያሳስባል፡፡ ቲቶ 3፡14 እንደዚሁም ለቲቶ በጻፈው መልእክቱ "ቃሉ የታመነ ነው። እግዚአብሔርንም የሚያምኑት በመልካም ሥራ በጥንቃቄ እንዲጸኑ እነዚህን አስረግጠህ እንድትናገር እፈቅዳለሁ። ይህ መልካምና ለሰዎች የሚጠቅም ነው" በማለት ይህንኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ያገለጻል፡፡ ቲቶ 3፡8 በተጨማሪም "በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን በእናንተ እያደረገ ፈቃዱን ታደርጉ ዘንድ በመልካም ሥራ ሁሉ ፍጹማን ያድርጋችሁ፤ ለእርሱ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን" ይላል፡፡ ዕብ. 13፡21

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መልካም ሥራ አስፈላጊነት ይህን ሁሉ እየተናገረ፣ መልካም ሥራ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በመልካም ሥራ መጽናት፣ እንዲሁም በመልካም ሥራ ፍጹማን ለመሆን መጋደልና መትጋት የሚገባ መሆኑን ደጋግሞ እየተናገረ እያለ "መልካም ሥራ አያስፈልግም" የሚለው የተሐድሶ መናፍቃን አባባል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወይስ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ? "የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ" እንደ ተባለ እኛም የምናመልከውንና የምንሰማውን መምረጥ ግድ ይለናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ትምህርት በአንድ በኩል፣ የመናፍቃን የስህተትና የፈጠራ ትምህርት ደግሞ በሌላ በኩል የቀረበው ለዚህ እንዲረዳ ነው፡፡

በመጨረሻም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ ላይ ያመኑ ምእመናን ምን ያህል ጥንቃቄ እንደሚያስፈልጋቸውና በሰይጣን እንዳይታለሉ ስጋት እንዳደረበት የገለጸውን እንመልከት፡-

> በእግዚአብሔር ቅንዓት እቀናላችኋለሁና፣ እንደ ንጽሕት ድንግል አናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁና፤ ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ። 2 ቆሮ. 11፡2-3

በግልጽ ቃል ሐዋርያው ያስተማረን በዚህ ዓለም ሕይወታችን ሳለን ያገኘነውን የመዳን ጸጋ ድቀት እንዳይገጥመንና ከያዝነው የሕይወት መንገድ እንዳንወጣ ልንሰጋና ልንጠነቀቅ እንደሚገባን እንጂ "ገነት መንግሥተ ሰማያት እንደምገባ እርግጠኛ ነኝ" እያልን በከንቱ ተስፋ ራሳችንን እንድናታልልና በዚህም ተዘልለን በመገኘት ለሰይጣን ፈተናና ማታለል የተመቸን ሆነን እንድንገኝ አይደለም፡፡ ሰይጣን ግን ለእርሱ ወጥመድ ተመቻችተን እንገኝ ዘንድ በመናፍቃን እያደረ ክርስቲያናዊ ተጋድሎንና ምግባር ትሩፋትን የማጥላላትና የማስጠላት ሥራውን ሊሠራብን ይሞክራልና ልናውቅበት ይገባል፡፡ "ውቅያኖሙ ለከለባት ወውቅያኖሙ ለገበርተ እኪት - ውሾችን እወቁባቸው፣ ክፉዎችም ሠራተኞችም ተጠበቁ" ተብለናልና፡፡ ፊል. 3፡2

## 3.7.3.4 መጽናት፣ ተጋድሎና ክርስቲያናዊ ሥራ ስመዳን ያላቸው ሚና በአበው ሊቃውንት ትምህርት

ቅዱሳን አባቶቻችን ለመዳን ከእግዚአብሔር የቸርነት ሥጦታ (ጸጋ) ጋር ክርስቲያናዊ ተጋድሎና መልካም ሥራ የራሳቸው ድርሻ ያላቸው መሆኑን በሰፊው አስተምረዋል፣ ጽፈዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል የተወሰኑትን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

- "እግዚአብሔር እንተን በተመለከተ ፍርዱን የሚሰጠው መልካም ሥራ በሚያደርጉት ሰዎች ነው፤ አንተ እነርሱ የሠሩትን መልካም ሥራ ካልሠራህ ያን ያደረጉት ሰዎች እነርሱ በአንተ ላይ ይፈርዱብሃልና፡፡ ክርስቶስን ተርቦ ያላበሉትና ተጠምቶ ያላጠጡት ሰዎች የተፈረደባቸው ያን መልካም ሥራ ባደረጉት ሰዎች አንጻር ነበርና፡፡ መልካም ሥራ ያላደረጉት ኃጥአን ግን ቁጥራቸው ብዙ መሆኑ እንዳቸው ሌላቸውን ሊረዳቸውና ሊያድናቸው አልቻለም፡፡ የአምስቱ ደናግል ጉዳይም እንዲሁ ዓይነት ነበር፡፡ ከጓደኞነታቸው የተጠቀሙት ነገር የለም፤ ነገር ግን በጥበብ ካደረጉት ከልባሞቹ ደናግል መልካም ሥራ አንጻር ተፈረደባቸው እንጂ፡፡ ስለዚህ እነዚህም (አምስቱ ሰነፎች ደናግልም)፣ እነዚያም (ተርቦ ያላበሉት) ሁለቱም መልካም ሥራ ባለማድረጋቸው ተፈረደባቸው፣ ተቀጡ እንጂ፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 6፣ ቁ. 15)

- "አንድ ጌታ፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ጥምቀት አለ' (ኤፌ. 4:5)፣ በፍጹም ነፍሳችን፣ በፍጹም ልባችንና በፍጹም ኃይላችን የምናምነው ይህንን ነው፡፡ ከኢየሱስ ክርስቶስም በቀር በሌላ በማንም መዳን የለም (የሐዋ. 4:10-12)፡፡ የምናምነውና የምንከተለው ይህንን ነው፡፡ እንዲሁም መልካም ሥራዎች ያለ እውነተኛ ሃይማኖት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንደ ሌላቸውም እናውቃለን፣ እውነተኛ ሃይማኖትም ያለ መልካም ሥራዎች በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም፡፡[80] ክፉና አመንዝራ ለሆነ ሰው እግዚአብሔርን የተመለከቱ አስተምህሮዎችን በሚገባ ማወቅ ብቻውን ምን ይጠቅመዋል? እንደገናም እግዚአብሔርን ለማያውቅና ከእውነተኛው የሃይማኖት ትምህርት ውጭ ለሆነ ሰው ምግባሩና ሥራው ያማረና መልካም መሆኑ ምን ይጠቅመዋል? ስለዚህም እውነተኛ የሆነውን ትምህርተ ሃይማኖት ማወቅ ውድና ክቡር የሆነ ሀብት ነው፡፡ በከንቱ ፍልስፍናና በተለያዩ የማታለል ዘዴዎች የሚያታልሉ ብዙዎች ስላሉ ነፍሳችን ይህን እውነተኛ ትምህርተ ሃይማኖት አዋቂና ጥንቁቅ ትሆን ዘንድ በእጅጉ ያስፈልጋል፡፡

  "አሕዛባዊ የሆኑ አዋቂዎች ነን ባዮች ሰዎችን በለሰለሰ ምላሳቸው ከእውነት መንገድ ያወጧቸዋል፤ 'ከጋለሞታ ከንፈር ማር ይንጠበጠባል' እንደ ተባለ፡፡ ምሳ. 5:3 ከተገረዙት ወገን የሆኑት [አይሁድ] ደግሞ ምንም እንኳ ከልጅነታቸው ጀምሮ በዘመናቸው ሁሉ ቢያጠኗቸውም ቅሉ [ቅዱሳት መጻሕፍትን] ባለማወቅ ስለሚያረጁ ምሥጢራቸውንና ጭብጣቸውን ያልተረዷቸውን ቅዱሳት መጻሕፍትን አጣምመው በመተርጎም ያስቷቸዋል፡፡ የመናፍቃን ልጆች ደግሞ በለሰለሰ ምላሳቸውና መልካም በሚመስል ቃላቸው ልክ መርዝን በማር እንደሚለውሱትና አጣፍጠው እንደሚያቀርቡት ክፉዎች ሰዎች እነርሱም መርዝ ኑፋቄያቸውንና የጥፋት ትምህርታቸውን ማር በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመሸፈን የየዋሃንን ልቡና በእውነተኛው ሃይማኖት ላይ እንዲሸፍትና ወደ ጥርጥርና ክህደት እንዲያዘንብል ያደርጉታል፡፡ እነዚህን ሁሉ በተመለከተ ነው ጌታችን 'ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ' በማለት ያስጠነቀቀን፡፡ አንቀጸ ሃይማኖትን (ጸሎተ ሃይማኖትን)[81] ማስተማርና በእርሱ ውስጥ ያሉትን ትምህርቶች በሚገባ ማስረዳትና መተንተን ያስፈለገበት ምክንያት ይህ ነው፡፡"

  (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት በእንተ አሠርቱ ነገራተ እምነት፣ ትምህርት ቁ. 4)

- "ወደዚህ በረከት ፈጥነህ ደስ እያለህና እየዘለልህ ግባ፣ በዚያም ሁለት ዘርፍ የሆነውን ተጋድሎ ለመጋደል ጀምር፡፡ ይህም በመጀመሪያ ራስህን በማንጻት ለምሥጢረ ጥምቀት ማዘጋጀት ነው፤ በመቀጠልም በጥምቀት ያገኘኸውን ጸጋ ለመጠበቅ መጋደል ነው፡፡ በመጀመሪያ የሌለን የነበረውን በረከትና ድኅነት ማግኘት እና ካገኘነው በኋላ ደግሞ ያን ጸጋ አጽንቶ መያዝና መጠበቅ እኩል ፈታኞችና ተጋድሎን የሚጠይቁ ነገሮች ናቸውና፡፡

[80] (And we recognize that works without true doctrine are not accepted by God, neither is true doctrine without works accepted by God.)

[81] (The Creed)

መጀመሪያ ላይ በነበረ መንፈሳዊ ቅንዓትና ቁርጠኝነት የተገኙ ጸጋዎችን ወደ ኋላ ላይ ስንፍናና ግድ የለሽነት ያጠፋቸዋልና፤ ወደ ኋላ የሚመጣ ስንፍናና ጥርጥር ያሳጣንንና ያጠፋብንን ነገሮች ደግሞ ትጋት መልሶ ያስገኛቸዋል፡፡ የምትፈልገውን ጸጋ ለማግኘትና ያለህን ለማጽናት ትጋሃ ሌሊቶች፣ አጽዋማት፣ መሬት ላይ መተኛት፣ ጸሎታት፣ እንባዕ፣ ለተቸገሩት ማዘንና መመጽወት ታላቅ እገዛና ጠቀሜታ አላቸው፡፡" (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ ትምህርት በእንተ ጥምቀት፣ ቁ. 31)

- "ሁለት ወገን የሆነ ተጋድሎን ለመጋደል ራስህን አዘጋጅ፤ ይኸውም በመጀመሪያ ራስህን የሚያነጻህን ጸጋ ለምትቀበልበት ለጥምቀት አዘጋጅ፡፡ በመቀጠልም በጥምቀት የምታገኘውን ጸጋ ለመጠበቅ ለመጋደል ራስህን አዘጋጅ፡፡ ያልነበረንን መቀደስና ጸጋ ማግኘት እና ከተቀበልነው በኋላ መጠበቅ እኩል ከባዶችና አስቸጋሪዎች ናቸውና፡፡[82] ብዙ ጊዜ ጸጋውን ከማግኘት አስቀድሞ በጉጉትና በናፍቆት የተገኘውን ጸጋ ኋላ ላይ ስንፍናና ግድ የለሽነት ያጠፋዋልና፤ ለሚመለስ ደግሞ ስንፍና ያጠፋውን ትጋት መልሶ ገንዘብ ያደርገዋልና፡፡ በጥምቀት ያገኘኸውን ጸጋ ለመጠበቅና ለዚህ ለምትፈልገው ነገር መገኘት ደግሞ ትጋሃ ሌሊቶች፣ አጽዋማት፣ መሬት ላይ መተኛት፣ ጸሎታት፣ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ማዘንና መመጽወት በጣም ታላቅ ጠቀሜታ ያላቸው ረዳቶችና አጋሮች ናቸው፡፡ ስለዚህ ስለ ተቀበልከው የምታመሰግን ሁን፤ እንዲሁም ለመጠበቅ የምትተጋም ሁን፡፡ የተሰጠህን ጸጋ እንድታስብ የሚረዱህ ብዙ ትእዛዛት አሉና እነርሱንም አትተላለፋቸው፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ በእንተ ጥምቀት፣ ቁ. 31)

- "ሕይወትን የሚሰጠው ማየ ጥምቀት የገሃነምን እሳት እንደሚያጠፋው ሁሉ በምጽዋት እና በጽድቅ ሥራዎችም የኃጢአት እሳት ይጠፋል፡፡ በጥምቀት የኃጢአት ሥርየት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚሰጥ ስለሆነ የጥምቀትን አርአያ በመከተል የማያቋርጥና ቋሚ የሆነ መንፈሳዊ ተጋድሎና መልካም ነገር በማድረግ ጽሙዳን መሆን የእግዚአብሔር ምሕረት በእኛ ላይ እንዲመጣ ያደርገዋል፡፡" (ሰማዕቱ ቅዱስ ቆጵርያኖስ፣ ስለ የጽድቅ ሥራዎችና ስለ ምጽዋት ያስተማረው ትምህርት፣ ቁ. 2)

- ". . . ቅዱስ ጳውሎስ ስለ መልካም ሥራ አስፈላጊነት ከተናገረ በኋላ እንደገና ስለ እግዚአብሔር ጸጋ ወደ መናገር ተመለሰ፡፡ 'በፍቅር አስቀድሞ በክርስቶስ መረጠን' አለ፡ ፡ ይህ መዳናችን የተገኘው ከሰው ተጋድሎ ወይም መልካም ሥራ ሳይሆን ከእርሱ ፍቅር የተነሣ ነውና፤ እንዲህ ሆኖም ግን ከእርሱ ፍቅር ብቻ ግን አይደለም፣ ከእኛ የመልካም ምግባርና የተጋድሎ ሕይወትም ነው እንጂ፡፡ ኤፌ. 4፡4 ከእርሱ ፍቅር ብቻ የተገኘ ቢሆን ኖሮ ሁሉም ሰው መዳን ነበረበት ያሰኛል፤ እንዲሁም ደግሞ ከእኛ የመልካም ምግባር ሕይወትና ተጋድሎ ብቻ የተገኘ ቢሆን ኖሮ የእርሱ መምጣትና ሰው ሆኖ ያደረገው ነገር ሁሉ አላስፈላጊ በሆነ ነበር፡፡ ሆኖም ግን መዳናችን የእርሱ ፍቅር ብቻ ውጤትም አይደለም፣ የእኛ የመልካም ምግባርና የተጋድሎ ሕይወት ውጤትም አይደለም፤ የሁለቱ ተዋሕዶ ውጤት እንጂ፡፡"[83] (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ኤፌሶን፣ ክፍል ትምህርት 1)

[82] (. . . for it is a matter of equal difficulty to obtain a blessing which we have not, and to keep it when we have gained it.)

[83] (Having thus spoken of the good works of these, he again recurs to His grace. "In love," saith he, "having predestinated us." Because this comes not of any pains, nor of any good works of ours, but of love; and yet not of love alone, but of our virtue also. For if indeed of love alone, it would follow that all must be saved; whereas again were it the result of our virtue alone, then were His coming needless, and the whole dispensation. But it is the result neither of His love alone, nor yet of our virtue, but of both.)

- "... በፍርድ ቀን በቀኙ ከሚቆሙት ጋር ትሆን ዘንድ ምን ማድረግ እንዳለብህ መንገዱን ተምረሃል፡፡ ስለዚህ ስለ ክርስቶስ የተነገረህን ትምህርት ጠብቅ፡ በፊራጁ ፊት በቀኙ መቆም ትችል ዘንድ እና ሰማያዊ መንግሥትን ትወርስ ዘንድ በመልካም ሥራ የበረታህና የተጋህ ሁን፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፡ ትምህርት 15፤ "ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ..."፣ ቁ. 33)

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ደግሞ እንዲህ ይላል፦

- "... አሁን ካለንበት አስቸጋሪ ሁኔታ የተነሣ ተስፋ አንቁረጥ፣ አብዝተንም አንጨነቅ፤ መልካም ነገር እንደሚመጣልን በተስፋ እንጠብቅ እንጂ፤[84] አሁን ልንሰማቸው ስላሉት ነገሮችም ልባችንን እንስጥ፡፡ ዛሬም ሞትን መናቅን በተመለከተ እንግራችሁ ዘንድ አለኝና፡፡ ትናንትና ሞትን የምንፈራው እርሱ በእውነት አስፈሪ ስለሆነ ሳይሆን የእግዚአብሔር መንግሥት ፍቅር ወደ እኛ ወደ ውስጣችን ዘልቆ ስላልገባ፡ ሲያልን መፍራትም በውስጣችን ስለሌለ ነው፤ እንዲሁም ከዚህም ጋር ንጹሕ ሕሊና ስለሌለን ነው ብያችሁ ነበር፡፡ ሞትን ለምን እንደምንፈራ እስካሁን ከተናገርኳቸው ምክንያቶች ያላነሰ፡ እንዲያውም የበለጠ እውነተኛ የሆነ ሌላ አራተኛ ምክንያት ልነግራችሁ ትወዳላችሁን? ይህም ለክርስቲያኖች እንደሚገባ ባለ የተጋድሎና የትሀርምት ሕይወት አለመኖራችን ነው፡፡ ይልቁንም በተቃራኒው የስንፍና፣ የተድላና የደስታ እና ስሜታዊነትን የመከተል ሕይወትን መኖርን እንወዳለን፤ ስለሆነም አሁን ካሉ ምድራዊ ነገሮችና ከዚህ ዓለም ሕይወት ጋር የመጣበቅ አኗኗራችን ያመጣው ውጤት ነው፡፡

  "ይህን ሕይወታችንን በጸሎት፡ በትጋሃ ሌሊት፡ መናኛ በሆነ አመጋገብ፡ መጠን አለፍ የሆኑ ፍላጎቶቻችንን ሁሉ ቆርጠን በመጣል፡ በምኞቶቻችን ላይ ማዕቀብ በማድረግ ብንኖር ኖሮ፡ የመልካም ምግባር ሕይወት የሚጠይቀውን ድካም በመቀበል ብንኖር ኖሮ፡ ሰውነታችንን እንደ ቅዱስ ጳውሎስ እየጎሰምን ብናስገዛው ኖሮ (1 ቆሮ. 9፡27)፡ 'አርነታችን ለሥጋ ፍትወት ምክንያትን ባይሰጥ' ኖሮ፡ በጠባቧና በቀጭኗ መንገድ ብንሄድ ኖሮ ስለሚመጣው ዓለም ነገር አብዝተን የምንናፍቅ እንሆን ነበር፤ ከዚህ ዓለም ድካም ለማረፍም እንጓጓ ነበር፡፡ ገላ. 5፡13 ይህ የምለው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ከፈለግህ ወደ ገዳማት ሂድና በዚያ የሚኖሩትን መነኰሳት ተመልከታቸው፡፡ በዚያ ያሉ ገዳማውያን መነኰሳት አንዳንዶቹ ማቅ ለብሰው፡ አንዳንዶቹ በሰንሰለት ሆነው፡ አንዳንዶቹ አብዝተው በመጾም፡ አንዳንዶቹ ደግሞ በኢታቸውን ዘግተው በጨለማ ውስጥ በመጋደል ያሉትን ተመልከታቸው፡፡ እነዚህ ሁሉም ሞትን እንደሚፈልጉትና እንደማይፈሩት፡ ስሙንም ዕረፍት እንደሚሉት ታያለህ፡፡ ...

  "በመልካም ምግባር ሕይወት የሚኖር፣ በተጋድሎና በትሀርምት የሚኖር፡ በጾምና በትጋሃ ሌሊት የሚኖር፡ ሰውነቱን በገድልና በትሩፋት በመቀጥቀጥ የሚኖር ሰው ከዚህ ዓለም ድካሙ ያርፍ ዘንድ፡ የመውደቅ ስጋትና አደጋ ወደ ሌለበት የጸጥታ ወደብ ይደርስ ዘንድና የተዘጋጀለትን የክብር አክሊል በእርግጠኝነት ያገኝ ዘንድ ሞትን ይናፍቀዋል፡፡ እግዚአብሔር በዚህ ዓለም አድካሚና አስቸጋሪ የሆነ ሕይወትን የሰጠን ለዚህ ነው፤ መከራውና አለመመቸቱ፡ የሚመጣውን ዓለም ሕይወትና በረከት እንድንናፍቅ እንዲያደርገን፡፡ እንዲህ ብዙ ሐዘናት፡ አደጋዎች፡ ፍርሃቶች፡ ጭንቀቶች ወዘተ መልተውና ሰፍነው በሁሉም አቅጣጫ ከብበው እያስጨነቁን እያለ እንኳ ከዚህ ዓለም ሕይወት ጋር ይህን ያህል የተጣበቅን ከሆነ የዚህ ዓለም ሕይወታችን ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ ነጻ ሆኖ ቢሆን ኖሮ እንዴት አድርገን

---

84 እንዲህ ያለው ይህን ትምህርት በሚያስተምርበት ጊዜ የአንጾኪያ ከተማ ነዋሪዎች የንጉሡንና የቤተሰቦቹን ሐውልቶች አፈራርሰው በከተማው በመንተት ከቴዎዶስዮስ ቀዳማዊ ጋር ተጣልተው ስለ ነበር ንጉሡ ደግሞ ከተማዋን እበቀላለሁ በማለቱ ሕዝቡ በታላቅ ፍርሃትና ጭንቀት ላይ ስለነበሩ ነው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በዚህ ክስተት ምክንያት ያስተማራቸው ትምህርቶች "Homilies on the Statues - በአንድ ምክንያተ ሐውልታት" ተብለው የተሰየሙት በሐውልቱ መፍረስ በተፈጠረው ችግር ሰሞን ያስተማራቸው ትምህርቶች በመሆናቸው ነው፡፡

ነበር ስለሚመጣው ሕይወት የምንጓጓውና የምንናፍቀው? እግዚአብሔር በዕብራውያን ላይ በግብጽ ሳሉ ጭቃ በማቡካትና ጡብ በመሥራት እንዲጨነቁና ያ ሁሉ ችግር እንዲደርስባቸው የፈቀደው ከጭንቀታቸውና ከመከራቸው ክብደት የተነሣ ግብጽን እንዲጠሉና ወደ ምድረ ርስት ከነዓን የመመለስ ፍላጎት በውስጣቸው እንዲያድርባቸው፣ ስለ መመለሳቸውም ወደ እርሱ ይሥኙ ዘንድ ነበር፡፡"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 6፣ ቁ. 7-8)

- "ሀብትና ንብረት፣ ወርቅና ብር አንዳንዶች እንደሚያስቡት የዲያብሎስ አይደሉም፡፡ እግዚአብሔር በነቢዩ በግልጽ እንዲህ ብሎ ተናግሯል፦ "ብሩ የእኔ ነው፣ ወርቁም የእኔ ነው፣ ለወደድሁትም እሰጠዋለሁ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር" ሐጌ 2፡8 በአግባቡ እስከ ተጠቀምክበት ድረስ ገንዘብ በራሱ ችግር የለበትም፡፡ ነገር ግን መልካም የሆነውን ነገር ያለ አግባብ ስትጠቀምበት የራስህን መጥፎ የአጠቃቀምና የአያያዝ ስህተት ለማመን ፈቃደኛ ካለመሆንህ የተነሣ በድፍረት ችግሩንና ስህተቱን ወደ ፈጣሪህ ልታሳብብ ትፈልጋለህ፡፡ በአግባቡ ከተጠቀመበት ሰው በገንዘቡ ሊጸድቅ ይችላል፡፡ ጌታችን "ተርቤ አብልታችሁኛል" የሚለው ይህ በገንዘብ የሚፈጸም ተግባር መሆኑ ግልጽ አይደለምን? "ታርዤ አልብሳችሁኛል" የሚለውም በእርግጠኝነት ከገንዘብ የሚገኝ ነው፡፡ ስለዚህ ገንዘብ በአግባቡ ከተጠቀሙበት የመንግሥተ ሰማያት በር ሊሆን እንደሚችል አታስተውልምን? ጌታችን "ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሽጠህ ለድሆች ስጥ፣ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ" አላለምን? ማቴ. 19፡21" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 8፣ ቁ. 6)

- "እንደዚሁም ይህን እንደገና እናስበው ዘንድ ይገባል፤ ያለ አግባብ በሆነ ነገር በዚህ ዓለም ሕይወታችን ምንም ዓይነት ግፍና መከራ ቢደርስብን በዚህ ብዙ ኃጢአታችንን እናነጻለን፡፡ ስለዚህም የኃጢአታችንን ቅጣት በዚያኛው ዓለም ከመቀበል ይልቅ በዚህ ዓለም መቀበል ታላቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ ያ ባለ ጸጋ በዚህ ዓለም ምንም ክፉ ነገር አልተቀበለም ነበር፣ ስለዚህም በዚያኛው ዓለም በነበልባል ተቃጠለ፡፡ ባለ ጸጋው በዚያኛው ዓለም ምንም ዓይነት መጽናናት ያላገኘበት ምክንያት ይህ መሆኑንም አብርሃም "ልጄ ሆይ፣ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ፣ ስለዚህም አሁን ትሣቀያለህ" እያለ ሲናገር ሰማው፡፡ ሉቃ. 16፡25 ለአልዓዛር ስለ ተሰጡት መልካም ነገሮች ደግሞ ተጋድሎውና የጽናት ሕይወቱ ብቻ ሳይሆን በዚህ ዓለም ሳለ እጅግ ብዙ መከራ መቀበሉ አስተዋጽኦ እንዳደረገለት ከርእሰ አበው ከአብርሃም ቃል ተማር፡፡ ለባለ ጸጋው "አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ" ካለው በኋላ በመቀጠል "አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ ስለዚህም ምክንያት አሁን እርሱ በዚህ ይጽናናል" አለ፡፡ በመልካም ምግባር ሕይወትና በተጋድሎ እየኖሩ የሚሠቃዩና መከራ የሚቀበሉ ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ እጥፍ ድርብ ዋጋን ይቀበላሉ፤ በኃጢአት ተዘፍቆ እየኖረ መከራ ሳይቀበል የኖረ ደግሞ እጥፍ ድርብ ቅጣት ይቀበላል፡፡"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 6፣ ቁ. 10)

- "የጾሙን ሁለተኛ ሳምንት ፈጽመናል፣ ሆኖም ዋናው ነገር በጾሙ ውስጥ ማለፍ ማለት እንዲሁ በጊዜው ውስጥ ማለፍ ብቻ ሳይሆን በጾሙ ውስጥ ሥነ ምግባራችንንና ድርጊታችንን ማስተካከልም ሲኖር ነው፡፡ ስለዚህ ይህን እናስተውል፣ በጾሙ ውስጥ ለመንፈሳዊ ሕይወትና ለተጋድሎ የበለጠ ትጉሃንና ጠንቃቆች መሆን አለመሆናችንን፣ ከድክመቶቻችን ያሻሻልነው ስለ መኖር አለመኖሩ፣ ኃጢአታችንን ያጠብንና ያስወገድን ስለ መሆን አለመሆኑ ጉዳይ እንመርምር፡፡ በዐቢይ ጾም (በጾመ ኢየሱስ) እያንዳንዱ ሰው እንዴት እንደ ጾሙ መጠየቅ የተለመደ ነው፡፡

ሆኖም ግን በጾማችን ውስጥ ምንም ዓይነት መልካም ሥራዎችን ሳናደርግ ካሳለፍነው መጾማችን ብቻ ጥቅሙ ምንድን ነው? . . . ጾሙን ልናሳልፈው የሚገባው ከሥጋና ከመባልዕት በመከልከል ብቻ ሊሆን አይገባም፣ ከኃጢአትም በመተቃብ ሊሆን ይገባል እንጂ፡፡ እንዲህ አድርገን ብንጾም በመንግሥተ ሰማያት ከምናገኘው ታላቅ ዋጋ በተጨማሪ በዚህ ዓለም ሕይወታችንም የምናገኘው ጥቅም ቀላል አይደለም፡፡ በኃጢአትና በርኩሰት የሚኖር ሰው በሲኦል የሚጠብቀውን ቅጣት ከማግኘቱ በፊት ከራሱ ሕሊና ከሚደርስበት ወቀሳና ውጊያ የተነሣ ገና አስቀድሞ በዚህ ዓለም ቅጣት እንደሚያገኘው ሁሉ፣ በመልካም ሥራዎች ባለ ጸጋ የሆነ ሰውም በሚመጣው ዓለም መንግሥተ ሰማያትን ከማግኘቱ በፊት የተቀደሰ ሰማያዊ ተስፋ ያለው ከመሆኑ የተነሣ ገና አስቀድሞ በዚህ ዓለምም በሐሤትና በደስታ የመሞላትንና የመኖርን ታላቅ ጥቅም ያገኛል፡፡

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 16፣ ቁ. 13)

- ". . . ብቻ አንተ በርታ፣ አይዞህ፣ መሥራት ያለብህን ነገር ሥራ፣ በርትተህ ተጋደል፣ ለእግዚአብሔር ብለህ ከምታደርጋቸው መልካም ነገሮች አንዳቸውም እንኳ እንዲሁ አይጠፉብህም፣ ያለ ዋጋም አይቀሩብህም፡፡ እያንዳንዱ ጸሎትህ፣ የምትዘምረው እያንዳንዱ ዝማሬህ ይመዘገባል፣ እያንዳንዱ ምጽዋትህ፣ እያንዳንዱ ጾምህ ይመዘገባል፣ እያንዳንዱ በአግባቡ የተከበረና የተጠበቀ ትዳር ይመዘገባል፣ ስለ እግዚአብሔር ተብሎ የተኖረና የተጠበቀ ንጽሕና ይመዘገባል፣ ሆኖም በመዝገቡ ውስጥ ቀዳሚው (የመጀመሪያው) አክሊል ለድንግልናና ለንጽሕና ነው፤ እንዲህ [በድንግልና] የምትኖር ከሆነ እንደ መልአክ ልታብራ ይገባሃል፡፡ ነገር ግን መልካም የሆነውን ዜና ደስ ብሎህ እንደ ሰማህ ከዚህ ተቃራኒ የሆነውንም ነገር ሳትሸማቀቅና ሳትደናገጥ ስማ፡፡ እያንዳንዱ የቅንዓትና የምቀኝነት ሥራህም ይመዘገባል፣ እያንዳንዱ የአመንዝራነት ሥራህም ይመዘገባል፣ እያንዳንዱ የሐሰት መሐላህም ይመዘገባል፣ እያንዳንዱ ነቀፋና ስም ማጥፋት፣ መተት፣ ስርቆት፣ ግድያ፣ ሁሉም ይመዘገባል፡፡ ከጥምቀት በፊት ያደረጋችሁት ሁሉ በጥምቀት ተሠርዮላችኋል፤ ከተጠመቃችሁ በኋላ ከዚያ በፊት ታደርጉት እንደ ነበረው የምታደርጉ ከሆነ ግን እነዚህ ነገሮች ሁሉ ይመዘገባሉ፡፡"

(ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ "ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ . . ."፣ ትምህርት 15፣ ቁ. 23)

- "አንድ ሰው ንብረት ስለ ተወሰደበት አዘነ እንበል፣ ነገር ግን ሐዘኑ የተወሰደበትን ንብረት አይመልስለትም፡፡ ሌላ ሰው ደግሞ ልጁ ስለ ሞተበት አዘነ እንበል፣ ሆኖም ሐዘኑ የሞተውን ማስነሣት አይችልም፣ የሞተውንም አይጠቅመውም፡፡ የሆነ ሰው ቢገረፍ፣ ቢመታና ቢሰደብ ያዝናል፡፡ ሆኖም ማዘኑ የደረሰበትን ነገር አይመልስለትም፡፡ የታመመ ሰው ቢያዝንና ቢተክዝ ትካዜው ሕመሙን አይፈውስለትም፣ እንዲያውም ያብስበት ካልሆነ በስተቀር፡፡ በእነዚህ ሁሉ ሐዘን በአንዳቸውም እንኳ ምንም ዓይነት ጠቀሜታ እንደ ሌለው አስተዋልህን? የሆነ ሰው በኃጢአት ወደቀና አዘነ እንበል፡፡ የዚህ ሰው ሐዘን ግን ኃጢአቱን ያስወግድለታል፣ በኃዘኑ ከበደሉ ነጻ ይሆናል፡፡ ይህ በምን ይታወቃል? ብትል በእግዚአብሔር አዋጅ ይታወቃል፡፡ ኃጢአትን ስላደረገ ስለ ሆነ ሰው ሲናገር እንዲህ አለ፡- "ስለ ኃጢአቱ ጥቂት ጊዜ ተቈጥቼ ቀሠፍሁት፣ ፊቴን ሰውሬ ተቈጣሁት፣ እርሱም እንዳዘነ አየሁ፣ ስለዚህም ፈወስኩት" ኢሳ. 57፡17

"ስለዚህም ጳውሎስ ሲናገር 'እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሐዘን ጸጸት የሌለበትን፣ ወደ መዳንም የሚያደርሰውን ንስሐ ያደርጋልና' ይላል፡፡ 2 ቆሮ. 7፡10 ስለሆነም ከላይ እንዳልሁት የሀብት መጥፋት፣ መበደል፣ መገረፍ፣ መሰደብ፣ መታመምም ሆነ ሞት ወይም ሌላ ይህን የመሰለ ነገር በሐዘንና በትካዜ ሊመለስና እንዳልተደረገ ሊሆን አይችልም፡፡ ሐዘን ሊያስወግደውና ሊያነጻው የሚችለው ኃጢአትን ብቻ ነው፤ ሐዘን በዚህ ዓለም እንዲኖር የተደረገበት ብቸኛ ምክንያትም ይኸው ነው፡፡ ስለዚህም ስለ ሀብትና ስለ መሳሰለው የዚህ ዓለም ነገር መታጣት እንዘን፣ ኃጢአት በሠራን ጊዜ ብቻ እንዘን፡፡ በዚህ ዓይነት ጊዜ ከሐዘን የሚገኘው ጠቀሜታ ታላቅ ነውና፡፡ ግፍና በደል፣ ሀብት መወረስና ሌላም ነገር ደርሶብሃልን? አትዘን፡፡ ኃጢአት ሠርተሃልን? እንዲህ ከሆነ ያኔ እዘን፣ ተከዝ፤ ይጠቅምሃልና፡፡ . . .

"ሐዘንና ሞት ኃጢአትን እንደሚያስወግዱ በመጀመሪያ ከሰማዕታት ግልጽ ሆኖ ይታወቃል፡፡ እንደዚሁም ቅዱስ ጳውሎስ ኃጢአት ላደረጉ ሰዎች 'ስለዚህ ምክንያት በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ፣ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል' በማለት ከተናገረው ግልጽ ሆኖ ይታያል። 1 ቆሮ. 11፡30 እንደ በደላችሁ ሁሉ ትሞታላችሁ፣ ከኃጢአታችሁ በሞት ነጻ ትሆኑ ዘንድ፡፡ ስለዚህም በመቀጠል እንዲህ አለ፡- 'ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር፤ ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ ከዓለም ጋር እንዳንኰነን በጌታ እንገሠጻለን።' 1 ቆሮ. 11፡31-32 ትል ከእንጨት ተገኝቶ እንደ ገና መልሶ ያንኑ የተገኘበትን እንጨት እንደሚበላው፣ የሐር ትልም የተገኘበትን ሐሩን መልሶ እንደሚበላው፣ ሐዘንና ሞትም የተወለዱት ከኃጢአት ሲሆን መልሰው ያንኑ ያስገኛቸውን ኃጢአትን ይበሉታል፣ ያጠፉታል፡፡"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 5፣ ቁ. 13)

- "በኃጢአታችን ምክንያት አሁን እየተቀበልን ያለው ሥቃይና መከራ፣ ሎንቀትና ፍርሀት . . . የእግዚአብሔርን ቁጣ አቀጣጥለን የነበረ ከሆነ ይህን ቅጣት በመቀበል እናበርደዋለን፡፡ ለኃጢአታችን ተገቢ የሆነውን ተመጣጣኝ ቅጣት ያሀል የከፈልን ባይሆን እንኳ ምሕረቱን ለማግኘት ግን በቂ ይሆናል፡፡"[85] (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 6፣ ቁ. 3)

- "እንደ ጥንቱ ጠቦቶችንና ጥጆችን ሳይሆን ለእግዚአብሔር በመሠዊያው (በምሥዋዑ) ከሽብሽባና ከአጽሕሶ ጋር የምስጋና መሥዋዕትን እንሠዋ፡፡ ከዚህም ሁሉ እጅግ የበለጠ የሆነውን መሥዋዕት ልናገር፡- ራሳችንን ለእግዚአብሔር እንሠዋ፣ እንዲያውም በእያንዳንዱ ዕለትና ቅጽበት ሁሉ ራሳችንን ለእርሱ መሥዋዕት አድርገን ማቅረባችንን እንቀጥል፡፡ ስለ እግዚአብሔር ስንል ማንኛውንም ነገር እንቀበል፡፡ የተለያዩ መከራዎችን በመቀበል የእርሱን ሕማማት እንካፈል፣ ደማችንን ስለ እርሱ ማፍሰስ እንኳ ቢያስፈልግ ይህንኑ በማድረግ እርሱ ስለ እኛ ያፈሰሰውን ደም እናክብር፣ ደስ እያለን ወደ መስቀሉ እንውጣ፡፡ ችንካሮቹ በጣም የሚያምሙ ቢሆኑም ጣፋጮች ናቸው፡፡ በተድላና በደስታ በምቾትና በድሎት ከመኖር ይልቅ ከክርስቶስ ጋር መከራ መቀበልና ስለ እርሱ መቸገርና መሰቃየት በእጅጉ የበለጠና የተሻለ ነውና፡፡"

(ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ ትምህርት ካልአይ በእንተ ትንሣኤ፣ ቁ. 23)

85 (. . . But now, we have sustained a life more grievous than countless deaths; fearing and trembling during so many days, and being suspicious of our very shadows; and paying the punishment of Cain; and in the midst of our sleep, starting up, through constant agony of mind. So that if we have kindled God's wrath, we have appeased Him in the endurance of such a punishment. For if we have not paid the satisfaction due to our sins, yet it hath been enough to satisfy the mercy of God.)

* "በዘመነ ኦሪት ከነበረው ይልቅ ዛሬ በዘመነ ወንጌል የመልካም ምግባር ሕይወት ቀላል ሆኗል፤ ስለዚህም ነው በበለጠ የክርስቲያናዊ የመልካም ሥራና ተጋድሎ ሕይወት ሕግጋት እንድንኖር የተደረግነው። ያን ጊዜ በዘመነ ኦሪት የነበሩትን ሰዎች ሁኔታና ዛሬ ጸጋ እግዚአብሔር በዝቶ በተሰጠበት በዘመነ ወንጌል ጊዜ ያለውን የሰዎች ሁኔታ ተመልከት። በጥንቱ ዘመን (በዘመነ ኦሪት) ለሰዎች የማይቻሉ ይመስሉ የነበሩ ነገሮች - በድንግልና መኖር፣ ሞትን መናቅ፣ ሌሎችም ከበድ ከበድ ያሉ ስቃያትን መቀበል፣ ዛሬ በመላው የዓለም ክፍል ሁሉ በብዙዎች ሲተገበሩና ሲኖሩ እናያቸዋለን። ይህም በእኛ ዘንድ ባሉት ብቻ ሳይሆን በሲጢያዎችም፣ በትራኪያዎችም፣ በሕንዶችም፣ በፋርሶችም፣ በሌሎች ቀድሞ አረመኔዎች በነበሩ ሕዝቦች ዘንድ ሁሉ ራሳቸውን ለክርስቶስ ሙሽራ ያደረጉ የብዙ ደናግል አንድነት፣ የሰማዕታት ነገድ፣ የመነኰሳት አንድነት ይገኛሉ። እንዲያውም በአንዳንድ አካባቢዎች ደናግሉና መነኰሳቱ ካገቡት ሰዎች በቁጥር እየበዙ ይገኛሉ። በእነዚህ ዘንድም ጽኑ የሆነ ጾምና ትህርምት፣ ሀብትና ንብረትን መተውና ምናኔ ሕይወታቸው ነው።[86]

ነገርም እነዚህ ነገሮች ከአንድ ወይም ሁለት የተለዩ ሁኔታዎች በስተቀር በዘመነ ኦሪት በኖሩ ሰዎች ዘንድ እንኳን ሊያደርጓቸውና ሊኖሩባቸው ቀርቶ በሕልማቸው እንኳ ያላዩዋቸውና ያላሰቧቸው ነገሮች ነበሩ። ስለዚህም በዘመነ ወንጌል የምትኖር አንተ እንዲህ ባለው ታላቅ የጸጋ ዘመን እየኖርክ ራስህን ለመልካም ሥራና ለተጋድሎ ሰነፍና ደካማ አታድርግ። ለክርስቲያናዊ ሥራና ለተጋድሎ ሰነፍ የሆነ ሰው ከእምነት በኋላም እንኳ ሊድን አይችልምና። ትግሉና ተጋድሎው ቀላል የሆነልህ አንተ ታሸንፍና ድል ታደርግ ዘንድ ነው እንጂ እንድትተኛ ወይም የተሰጠህን ጸጋ ታላቅነት ለስንፍናህ ሽፋን አድርገህ በሐኬት እንድታንቀላፋና ራስህን ከመልካም የተጋድሎ ሕይወት ውጭ እንድታደርግ አይደለምና።[87]"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ መልክአተ ሮሜ፣ ትምህርት 13)

* "በወንጌል ያመኑትን ይመረምር ዘንድ እርሱ ሁል ጊዜ ይመጣል፤ ልብሱ አድፎ ያገኘውንም ወዳጄ፤ የሠርግ ልብስ ያልለበስክ ለምን ገባህ? ብሎ ሥራውን ይጠይቀዋል። " (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 4)

* "ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተፈራረቁ የሚሆኑትን መከራዎች እግዚአብሔር እነዚህ ነገሮች እንዲሆኑ ይፈቅዳል (እንዳይሆኑ ከመሆን አያስቀራቸውም፣ አያጠፋቸውም)። ይህም ለእርሱ ጸንተው የሚጋደሉትንና በመከራ የሚጸኑትን አስቀድሞ ነቢያቶቹንና ሐዋርያቶቹን እንዳከበራቸውና የድል አክሊልን እንደ ሰጣቸው ሁሉ እነርሱም በዚህ ዓለም ለጥቂት ጊዜ ደክመውና መከራ ተቀብለው ዘለዓለማዊ የሆነውን ሰማያዊ መንግሥት ይወርሱ ዘንድ ነው። ነቢዩ ዳንኤል እንዲህ ሲል እንደ ተናገረው፦ 'ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደ እርሱ ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል። በዚያም ዘመን በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ እያንዳንዱ ይድናል። በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ፥ እኵሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት፥ እኵሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጕስቍልና።

[86] (The things which aforetime seemed not possible to any one, virginity, and contempt of death, and of other stronger sufferings, are now in full vigor through every part of the world, and it is not with us alone, but with the Scythians, and Thracians, and Indians, and Persians, and several other barbarous nations, that there are companies of virgins, and clans of martyrs, and congregations of monks, and these now grown even more numerous than the married, and strictness of fasting, and the utmost renunciation of property.)

[87] ( . . . Since not even after the faith is it possible for a listless man to be saved! For the wrestlings are made easy that thou mayest strive and conquer, nor that thou shouldest sleep, or abuse the greatness of the grace by making it a reason for listlessness, so wallowing again in the former mire.

ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ፀዳል፥ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ።" ዳን. 12፥1-3 (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 15፣ "ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ . . ."፣ ቁ. 17)

❖ "በአንድ በኩል ስለ ዘለዓለማዊ ሕይወት የተነገረን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ዘለዓለማዊ ፍርድ ለእኛ የተዘጋጀውና የተነገረን ነገር በእውነት እጅግ አስፈሪ ነው፡፡ በፊታችን መንግሥተ ሰማይ ቀርቦልናል፣ ዘለዓለማዊ እሳትም እንዲሁ፡፡ ታዲያ እሳቱን የምናመልጠው እንዴት አድርገን ነው? ወደ መንግሥተ ሰማያት የምንገባውስ እንዴት ነው? የሚሉ ይኖራሉ፡፡ እርሱ ራሱ ነግሮናልና ስለዚህ ነገር ራሱ ባለቤቱ የተናገረውን ተማር፡፡ እዚህ ላይ በግልጽ የተነገረ ስለሆነ ትርጓሜ ወይ ማራቀቅ የሚያስፈልገው ነገር የለም፣ የተባለውን መፈጸም ብቻ ነው፡፡ "ተርቤ ነበር፣ አብልታችሁኛልና፤ ተጠምቼ ነበር፣ አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሆኜ ነበር፣ እናንተ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ ነበር፣ አልብሳችሁኛልና፣ ታምሜ ነበር፣ ጠይቃችሁኛልና፣ ታስሬ ነበር፣ እናንተ ወደ እኔ መጥታችሁ ጠይቃችሁኛልና" ይላል። ማቴ. 25፥35-36 እነዚህን ነገሮች ብታደርግ ከእርሱ ጋር አብረህ ትነግሣለህ፤ እነዚህን ካላደረግህ ደግሞ ትኮነናለህ፡፡ ስለሆነም እነዚህን ነገሮች ማድረግን ከአሁኑ ጀምር፣ በሃይማኖትም ኑር፡፡ እንደ ሰነፎቹ ደናግል ዘይት ከመግዛት ዘግይተህ በሩ እንዳይዘጋብህ እነዚህን ነገሮች ለመፈጸም ተፋጠን፡፡ ማሰሮውን ስለ ያዝክ ብቻ አትተማመን፣ ሁል ጊዜ የበራ እንዲሆን አድርግ እንጂ፡፡ የመልካም ሥራህ ብርሃን በሰዎች ፊት ይብራ፤ ክርስቶስም ከአንተ የተነሣ እንዳይነቀፍብህ ተጠንቀቅ፡፡

❖ "የቆሸሸና ያደፈ ልብስ ለብሰህ ከሆነ በመልካም ሥራ እንዲነጻና እንዲያሸበርቅ አድርገው፣ እንደ መጋቢ (አሳላፊ) ሆነህ ታገለግልበት ዘንድ ከእግዚአብሔር የተሰጠህን ማንኛውም ዓይነት ነገር ቢሆን ጠቃሚ በሆነ መንገድና ሁኔታ አውለው፡፡ የሀብት አደራ ተሰጥቶህ ከሆነም በአግባቡ አውጣው፣ ሰዎችን መግብበት፡፡ በማስተማር ቃል ታገለግል ዘንድ ተሰጥቶህ ከሆነም መልካምና ታማኝ መጋቢ ሁን፡፡"

(ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 15፣ "ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ . . ." ቁ. 26)

ይህን ሁሉ አጠቃልሎ ሲገልጽ ቅዱስ ቄርሎስ እንዲህ ይላል፦

❖ "ዘለዓለማዊ ሕይወትን በተመለከተ ምስክሮቹና ማስረጃዎቹ ብዙዎች ናቸው፡፡ ይህን ዘለዓለማዊ ሕይወት ማግኘት ስንመኝ እርሱን የምናገኝባቸውን መንገዶች ቅዱሳት መጻሕፍት ያሳዩናል፡፡ አንድ ጊዜ ይህ ሕይወት የሚገኘው በእምነት መሆኑን ይነግሩናል፤ 'በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው' ተብሎ ተጽፏልና፡፡ ዮሐ. 3፥36 እንዲሁም 'እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፣ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም' ይላል፡፡ ዮሐ. 5፡24 በሌላ ጊዜ ደግሞ ወንጌልን በመስበክ እንደ ሆነ ይነግረናል፤ እርሱ እንዲህ ብሏልና፦ 'የሚያጭድ ደመወዝን ይቀበላል፣ የሚዘራና የሚያጭድም አብረው ደስ እንዲላቸው ለዘላለም ሕይወት ፍሬን ይሰበስባል' ዮሐ. 4፥36 በሌላ ጊዜ ደግሞ በሰማዕትነትና በክርስቶስ ስም በመታመን እንደ ሆነ ይነግረናል፤ እንዲህ ብሏልና፦ 'ነፍሱን የሚወድ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም በዚህ ዓለም የሚጠላ ለዘላለም ሕይወት ይጠብቃታል።' ዮሐ. 12፥25 እንደ ገናም ክርስቶስን ከዘመድና ከሀብት ንብረት በላይ በመውደድና በመምረጥ እንደ ሆነ ሲናገር፦ 'ስለ ስሜም ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል፣ የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል" ይላል፡፡ ማቴ. 19፥29

"በተጨማሪም ትእዛዛቱንና ሕግጋቱን በመጠበቅም መሆኑን ደግሞ እንዲህ ሲል ነግሮናል፡ - አንድ ሰው ቀርቦ፡- 'መምህር ሆይ፤ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ? ብሎ በጠየቀው ጊዜ 'ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ' ብሎታልኛ፡፡ ማቴ. 19፡16-18 በተጨማሪም በአንድ በኩል ከክፉ ሥራዎችና ነገሮች በመራቅ፥ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔርን በማገልገል ነው፤ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላልና፡- 'እንግዲህ ዛሬ ከምታፍሩበት ነገር ያን ጊዜ ምን ፍሬ ነበራችሁ? የዚህ ነገር መጨረሻው ሞት ነውና። አሁን ግን ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ ለእግዚአብሔርም ተገዝታችሁ ልትቀደሱ ፍሬ አላችሁ፤ መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው።' ሮሜ 6፡21-22"

(ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 18፣ በእንተ አሐቲ ቅድስት ኵላዊት ቤተ ክርስቲያን ወትንሣኤ ሥጋ ወሕይወት ዘለዓለማዊ፡ ቁ. 33)

❖ "የዘብዴዎስ ልጆች እናት ከእናትነት ፍቅሯ የተነሣ ለልጆቿ 'እነዚህ ሁለቱ ልጆቼ አንዱ በቀኝህ አንዱም በግራህ በመንግሥትህ እንዲቀመጡ እዘዝ' አለችው። ጌታችንም መልሶ 'እኔ ልጠጣው ያለውን ጽዋ ልትጠጡ፥ እኔም የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን?' አላቸው። እነርሱም 'እንችላለን' አሉት፡፡ መድኃኒታችንም 'ጽዋዬንስ ትጠጣላችሁ፤ በቀኝና በግራ መቀመጥ ግን ከአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም' አላቸው። ማቴ. 20፡21-23 ታዲያ እንዲህ ከሆነ ሰው ለእግዚአብሔር ብሎ የሚደክመው ድካም ዋጋ የለውም ማለት ነውን? ራሱን ለመግዛት የሚያደርገው ተጋድሎስ ከንቱ ነውን? መንፈሳዊ ፍልስፍናውስ አይጠቅመውምን?[88] ጾሙስ? ትጋሃ ሌሊቱስ? መሬት ላይ መተኛቱስ? እንብዑስ? ሰዎች የሚመረጡትና ጸጋ የሚያገኙትስ ከእነዚህ ነገሮች በአንዳቸውም ሳይሆን እንዲሁ በዕጣ ወይም በዕድል ከእናታቸው ማኅፀን በሚሆን ምርጫ ነውን?

"አንዳንዶች የሁብት ትንቢትን ጸጋ የሚቀበሉትና የሚድኑት፥ ሌሎች ደግሞ የሚኮነኑት ነፍሳት ከሥጋ ጋር አንድ ከመሆናቸው በፊት በራሳቸው ሕይወት እንደ ነበራቸውና ለጸጋም ሆነ ለኩነኔ የሚመረጡት በራሳቸው ውሳኔ ሳይሆን በቅድመ ውሳኔ (Predestination) መሠረት ነው በማለት እንዲህ ያለ ከንቱ የሆነ አስተሳሰብ የሚያስብ እንዳይኖር እሰጋለሁ፡፡ ሆኖም እንዲህ ያለው አስተሳሰብ ባዕድና እብደትም ነው፥ ከቤተ ክርስቲያን ትውፊት ጋርም ተቃራኒ ነው፡፡ ስለዚህም 'ለተሰጣቸው ነው' በሚለው ቃል ላይ 'የተገባቸው ሆነው ለተገኙት' የሚል ማብራሪያ መጨመር ይኖርብናል፤ ይህን ግብር ከእግዚአብሔር አብ የተቀበሉ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ለራሳቸውም የተገባቸው እንዲሆኑ በሕይወታቸው በተግባር ያሳዩና ከዚህ የተነሣም የተቀበሉ ብቻ ሳይሆኑ ለራሳቸውም የሰጡ ናቸው እንጂ፡፡"

(ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፥ ትምህርተ 37፣ በእንተ ቃላተ ወንጌል ዘይቤ "ሶበ ፈጸመ እግዚእ ኢየሱስ ዘንተ ነገረ . . . ማቴ. 19፡1"፣ መልእክት ቁ. 14-15)

❖ ". . . እርምሞ ተዓቅብ ሃይማኖተ ወምግባር ታበጽሕ ሰማያተ . . . - ዝምታ ሃይማኖትን ትጠብቃለች፥ ምግባርም ወደ ሰማያት ታወጣለች፡፡" (ቅዱስ ያሬድ፡ ዝማሬ ዘምኩራብ)

❖ "ጊዮርጊስ ሠናየ ገድለ ተጋደለ ገድሉኒ ሕይወተ ኮኖ ገድሉኒ መድኃኒተ ኮኖ ሠናየ ገድለ ተጋደለ . . . ጊዮርጊስ ሠናየ ገድለ ተጋደለ በእንተ ፍቅረ ክርስቶስ - ጊዮርጊስ መልካም ገድልን ተጋደለ፤ ተጋድሎውም ሕይወት ሆነው፥ ተጋድሎው መድኃኒት ሆነው . . . ጊዮርጊስ ስለ ክርስቶስ ፍቅር መልካሙን ተጋድሎ ተጋደለ፡፡" (ቅዱስ ያሬድ፡ ዝማሬ ዘቅዱስ ጊዮርጊስ)

[88] (Nothing the philosophy?)

- "እንግዲህስ የደስታ ገነት ሆይ፥ ሰላም ላንቺ ይሁን እንበል፤ በመጨከን ነው እንጂ ወደ አንቺ እንገባ ዘንድ የማይቻለን፡፡ የአባታችን የአዳም ኤዶም ገነት ሆይ፣ ሰላም ላንቺ ይሁን፤ በውስጥሽ ደስ ሊለን የማይቻል፡ በዚህ ሥጋችንን ካላደከምን በቀር፡፡ የገነት ምድር ሆይ፥ ሰላም ላንቺ ይሁን፤ በውስጥሽ ልንመላለስ የማይቻል፡ እግሮቻችንን በከንቱ ከማመላለስ ካልከለከልን በቀር፡፡" (ቅዳሴ ዘቅዱስ አትናቴዎስ፡ ቁ. 35-37)

- "የእግዚአብሔርን ጸጋ የተቀባን በእውነት ክርስቲያን የክርስቶስ ወገኖች መሢሐውያን እኛ ግን እንትጋ፣ እንቸኩልም፤ እንቅና፡ ከክብር ወደ ክብር እንገባም ዘንድ እንቅረብ፡፡ አስቀድሞ ሥጋችንን እናስገዛው፡ ሁል ጊዜ አሳባችንን ከመባከን እንሰብስብ፡፡" (ቅዳሴ ዘቅዱስ አትናቴዎስ፡ ቁ. 47)

## ማጠቃለያ

ሰው የሚድነው በእግዚአብሔር ቸርነት የተሰጠውን የመዳን ጸጋ በእምነት ሲቀበል፡ በመቀጠልም ይህን የመዳን ጸጋ በአማናዊ መንገድ የሚያገኝባቸውንና የራሱ የሚደርግባቸውን ምስጢራት - ጥምቀት፡ ሜሮን እና ቅዱስ ቁርባን ሲፈጽም ነው፡፡ ከዚያም ይህን ተቀበለውን የመዳን ጸጋ ለመጠበቅና ወደ ሕይወት ለመግባት መጽናትና መጋደል፡ እንደዚሁም ክርስቲያናዊ መልካም ሥራ መሥራት ይገባዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እና አበው ቀደምት ሁሉም ተባብረውና ተስማምተው የሚነግሩን ይህን እውነተኛ የሕይወት መንገድ ነው እንጂ የራሳቸውን መንገድ ፈጥረው የሚጓዙት ተሐድሶዎች እንደሚሉት መዳን በእምነት ብቻ ነው ብለው አይደለም፡፡

ለምሳሌ ተሐድሶዎች ያሉትን አንዱን ብናስታውስ፡-

◉ "ጽድቅ የእኛ እንዳች አስተዋጽኦ የሌለበት የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ከሆነ ዘንድ በእምነት ከጸደቅን በኋላ ኃጢአት ፈጽመን ብንገኝ እንኳ ከጽድቅ ተለይተን አንከነንም፤ ስለ ኃጢአታችን በተለያዩ ቅጣቶች እንገሠጻለን እንጂ" ይላሉ፡፡

ይህ አባባል ፈጽሞ የተሳሳተ ነው፡፡ ምክንያቱም ካመን በኋላ ኃጢአት ፈጽመን ብንገኝ እንኳ አንከነንም የሚል ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ የሌለ ትምህርት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለን ካመንን በኋላ ኃጢአት ብንሠራ ንስሐ ካልገባን በስተቀር ጽኑ ቅጣት የሚጠብቀን መሆኑን ነውና፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል፡-

> "አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን፡ ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን፡ ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን፡ መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን፡ በኋላም የካዱትን እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው፤ ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና፣ ያዋርዱትማልና።" ዕብ. 6፡4-6

እንዲሁም "<u>የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት</u> አይቀርልንምና፡ የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ" ይላል፡፡ ዕብ. 10፡26-27 እንደገናም "የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርጋችሁ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መጽናት ያስፈልጋችኋልና። . . . ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል፡ <u>ወደ ኋላም ቢያፈገፍግ ነፍሴ በእርሱ ደስ አይላትም</u>። <u>እኛ ግን ነፍሳችውን ሊያድኑ ከሚያምኑቱ ነን እንጂ ወደ ጥፋት ከሚያፈገፍጉት አይደለንም</u>" በማለት በእምነት ከጀመሩ በኋላ ወደ ኋላ ቢያፈገፍጉ የሚጠብቀው ሞት እንጂ አንድ ጊዜ ካመንን በኋላ ኃጢአት ፈጽመን ብንገኝም ችግር የለውም አይልም፡፡ ፈጽሞ! ዕብ. 10፡36-39

ስለዚህ "ከእምነት በኋላ ኃጢአት ብናደርግም ራሱ በተለያዩ ቅጣቶች ይገሥጸናል እንጂ አንኮነንም" የተባለው ስህተት ነው፤ ሰው ራሱ መበደሉን አምኖ ተጸጽቶ ንስሐ መግባት ይኖርበታል እንጂ እኔ አልኮነንም፣ በሆነ ቅጣት መገሠጽና ማጽደቅ የራሱ የእግዚአብሔር ድርሻ ነው ብሎ ራሱን መሸንገልና ማታለል የለበትም፡፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የኃጢአትን ከባድነትና የሚያስከትለውን ቅጣት ሲናገር ሌላው ቀርቶ ወንድሙን መሳደብ እንኳ ምን ያህል ከባድ እንደ ሆነ "እኔ ግን እላችኋለሁ፣ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል" በማለት አስተማረን። ማቴ. 5:22 ስለዚህ ኃጢአት ይሆን ያህል ከባድና ወደ ገሃነም ሊወስድ የሚችል በመሆኑ ወደ ልቡ ተመልሶ መጸጸትና ንስሐ መግባት ይገባል እንጂ ራሱ ይገሥጸኛል እንጂ አይኰንንኝም እያሉ ራስንም ሌሎችንም ማታለል አጥፍቶ መጥፋትና አጥፍ ድርብ ባለ እዳ መሆን ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ከሥራቸው የተነሣ የተፈረደላቸውም ሆነ የተፈረደባቸው መሆኑን የሚናገረውን የእግዚአብሔር ቃል መጋፈጥ ሲሳናቸው ከዚህ አጣብቂኝ ለመውጣት እንዲህ አሉ፡-

> "ከዚህ ውጭ ግን በእምነት ጸድቂያለሁና አልኮነንም እያለ ሁል ጊዜ ኃጢአትን በተደጋጋሚ የሚፈጽም ክርስቲያን ጸድቂያለሁ በማለት ራሱን ከሚሸነግል አለመጽደቁን ሊያጤነው ይገባል፡፡" (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 189-90)

ሰው የሚጸድቀው በእምነት ብቻ ከሆነ እንዲህ ያለው "ክርስቲያን" ለምን ይኰነናል? ተሐድሶዎች ሆይ፣ አቋማችሁን ግልጽ አድርጉ እንጂ ነፋስ ወዲያና ወዲህ እንደሚያደርገው እንደ መቃ መስዬ (ሸምበቆ) አንድ ጊዜ ወደዚህ፣ ሌላ ጊዜ ወደዚያ ማለት ግራ የመጋባትና የመጨነቅ ውጤት ነው፡፡

"ሰው በእምነት ብቻ ይድናል፣ ካልዳነ ግን መጀመሪያውኑም አላመነም ነበር ማለት ነው" የሚለው አባባል በሃሳብ አቀራረብ ውስጥ የአመክንዮ አዙሪት (Circular reasoning) የሚሉት ዓይነት ነገር ነው፡፡ ይህም ማለት የአንድን ሃሳብ መነሻ መልሶ እንደ ማስረጃ አድርጎ የማቅረብ ስህተት ማለት ነው፡፡ በዚያውም ላይ "እምነት ብቻ" የሚለው በራሱ የእምነት ጉድለት ያለበት ሃሳብ ነው፡፡ እንደ ፕሮቴስታንታዊው የተሐድሶዎች ትምህርት ሰው በእምነት ብቻ የሚድን ከሆነ በመጨረሻ ላይ "ተርቤ አላበላችሁኝም፣ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝም፣ ..." ተብሎ ለምን ይፈረድበታል? ወደ ሠርግ ቤት "የሠርግ ልብስ ሳትለብስ ለምን ገባህ?" ተብሎስ ለምን ይፈረድበታል? "የአባቴን ፈቃድ አልፈጸምህም" ተብሎስ ለምን አላውቅህም ይባላል? ተሐድሶዎች ይህን ያፈጠጠ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐቅ "እንዲህ ያለው ሰው ድሮውንም አላመነም ነበር" ብለው ለማምለጥ ይሞክራሉ፡፡ ይህ ግን ስንዝር አያራምድም፡፡ ምክንያቱም ካልዳነ "ጥንቱንም አላመነም ነበር" የሚለውን ብቻ ሳይሆን የሚያመለክተው በእምነት ብቻ መዳን አይቻልም የሚለውንም ሊሆን እንደሚችል ማየት ይገባቸው ነበርና!

ጌታችን በዳግም ምጽአቱ በፍርድ ቀን በግራው የሚቆሙትን "ተርቤ አላበላችሁኝምና፣ . . ." ያለው ይህንኑ ያሳያል፡፡ መዳን በእምነት ብቻ ቢሆን ኖሮ እንዲህ ያለውን ክርስቲያናዊ ሥራ ነክ ጥያቄ ለምን ይጠይቅ ነበር? እንዲህ የተባሉት ሰዎች ማለትም "ተርቤ አላበላችሁኝም . . ." የተባሉት ሰዎች "እናንተ ርጉማን፣ ከእኔ ወግዱ . . ." የተባሉትና ያልዳኑት "ስላላመኑ ነው" ብሎ ጌታችን ሲናገር የተጻፈ አናገኝም፤ መጽሐፍ ቅዱስ መልካም ስላለማድረጋቸው መሆኑን ይግረናል እንጂ፡፡ ስለዚህ ያመኑ ሰዎች በመጨረሻ "ከእኔ ወግዱ፤ አላውቃችሁም" የሚባሉ ከሆነ መጀመሪያውኑ ስላላመኑ ነው ብሎ መደምደም አይቻልም፤ አምነው ሥራ ስላልሠሩ እንጂ፡፡ ጌታችንም "ስላላመናችሁብኝ ነው" አላላቸውም፤ "ተርቤ ስላላበላችሁኝ . . ." አላቸው እንጂ፡፡ የተፈረደባቸው ሰዎችም ሲመልሱ "ጌታ ሆይ፣ ተርበህ ወይስ ተጠምተህ ወይስ እንግዳ ሆነህ ወይስ ታርዘህ ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ መቼ አይተን አላገለገልንህም?" በማለት በእርሱ ያመኑ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ምክንያቱም "ጌታ ሆይ" ያሉት ጌትነቱን የተቀበሉና ያመኑበት ስለሆኑ ነው፡፡ ሆኖም ግን በእምነት ላይ ሆነው ለታናናሾቹቸው መልካም ሥራ ባለመሥራታቸው ተፈረደባቸው፡፡

አሁንም "ቢያምኑ ይሠሩ ነበር፤ ያልሠሩት ስላላመኑ ነው እንጂ" ማለት ከላይ እንዳልነው የአመክንዮ አዙሪት "Circular reasoning" ወይም ደግሞ "Begging the Question" እንደሚባለው ያለ የአስተሳሰብ ችግር ነው፡፡ ያላመኑማ መጀመሪያውኑም ወደፊቱ አይቀርቡም፤ ምክንያቱም ገና ከጥንቱ ባለማመናቸው ምክንያት ተፈርዶባቸዋልና፡፡ ራሱ ባለቤቱ ጌታችን "በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም" ብሏልና፡፡ ዮሐ. 3፡36 እንዲሁም "በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል" በማለት ያላመነ ሰው የሚፈረድበት ገና ወደፊት ሳይሆን በዚህ ዓለም ሳለም ባለማመኑ ምክንያት አሁንም በፍርድ (በኩነኔ) ውስጥ ያለ መሆኑን በግልጽ ነግረን፡፡ ዮሐ. 3፡18

በመዝሙረ ዳዊት ላይም "ወበእንተዝ ኢይትነሥኡ ረሲአን እምደይን ወኢኃጥአን ውስተ ምክረ ጻድቃን - ስለዚህ ክፉዎች በፍርድ፣ ኃጢአተኞችም በጻድቃን ማኅበር አይቆሙም" ይላል። መዝ. 1፡5 ይህም ማለት ክፉዎች የተባሉ ኢአማንያን ከሞት አይነሡም ማለት ሳይሆን ባለማመናቸው ምክንያት ገና በዚህ ዓለም ሳሉ የተፈረደባቸው ስለሆኑ ለፍርድ ወደ ፊቱ አይቀርቡም ማለት ነው፡፡ ወደ ጌታችን ፊት ቀርበው ሥራቸው የሚመረመረውና ለፍርድ የሚቀርቡት ያመኑ ሰዎች ናቸው፡፡ እነዚህ እንደ እምነታቸው ሆነው ተገኝተው መሆን አለመሆኑ፣ ባመኑበት ጸንተው መልካም ፍሬ አፍርተው መሆን አለመሆኑ ይገለጥ ዘንድ በፊቱ ይቀርባሉ፡፡ ጌታችን መንግሥተ ሰማያትን በሠርግ መስሎ ባስተማረበት ትምህርቱ ላይ ወደ ሠርግ ቤት ያልገቡትን ሰዎች አልተቆጣጠራቸውም፤ እነዚያ ሲጠሩ "አልሰማም፣ አላምንም" ብለው በውጭ ቀርተዋልና፡፡ ወደ ሠርግ ቤት የገቡት ማለትም ያመኑትና የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አካላት መሆን የጀመሩትን ግን ባለቤቱ ገብቶ ልብሳቸውን (በሕይወታቸው ያደረጉት ሥራ) ምን እንደሆነ ተመልክቷቸዋል፡፡ እንዲሁም ጌታችን "ምናልባት አንዳች ይገኝባት እንደ ሆነ" ብሎ ፍሬ ሊፈልግ የሄደባት በለስ "ቅጠል ያላት በለስ" ነበረች፡፡ ማር. 11:13 ቅጠል ሃይማኖት ሲሆን ፍሬ ደግሞ ምግባር ነው፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ" ያለው ማመኑ ብቻ የሚበቃ ቢሆንና መልካም ሥራ ላመነ ሰው እንዲሁ በራሱ ጊዜ የሚመጣ ቢሆን ኖሮ የተጣለ እንዳይሆን ለምን ፈራ? ሥጋውን መጎሰምስ ለምን አስፈለገው?

ቅጠል የሌለው በለስ ፍሬ ሊያፈራ እንደማይችል ሁሉ ጌታችንም እምነት ከሌለው ሰው የክርስቲያናዊ መልካም ሥራ ፍሬ ስለማይኖረው ወደዚያ አይሄድም፤ እንዲህ ያሉት ወደ ፊቱም አይቀርቡም፡፡ ቅጠል የተባለ እምነት ያላቸውን ግን ወደ ፊቱ ያቀርባቸዋል፤ ፍሬ ያላቸው መሆን አለመሆናቸው ይገለጥ ዘንድ፡፡ጌታችን ወደ በለሲቷ የሄደው ፍሬ ያላት መሆን አለመሆኗ ጠፍቶት ሳይሆን ይህን ትምህርት ለእኛ ለማስተማር በመሆኑ በፊቱ በቀኝና በግራ አቁሞ የሚያመሰግናቸውንና የዘለዓለም ሕይወትን የሚሰጣቸውንም ሆነ የሚወቅሳቸውንና ወደ ዘለዓለም ቅጣት ሂዱ የሚላቸውን እርሱ በቀኝና በግራ ከመቆማቸው በፊት ግብራቸውን ያውቀዋል፤ ሆኖም ፍርዱን ለሁሉም ግልጥ በሆነ መንገድ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ በእምነት ላይ ቆመውና ጸንተው በእርሱ ቸርነት በእርሱ ቸርነት መልካም ፍሬ አፍርተው የተገኙ ወደ ዘለዓለም ሕይወት ይገባሉ፡፡ በባዶው "ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ" እያሉ ዘመናቸውን ክርስቲያናዊ መልካም ምግባር ሳይሠሩ ቅጠል ብቻ ሆነው የተገኙ ደግሞ ወደ ዘለዓለም ቅጣት ይሄዳሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊውና ኦርቶዶክሳዊው የመዳን ትምህርት ይህ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ያለው ግን የስህተትና የሞት መንገድ ነው፤ በራስ ሕይወት ላይ መቀለድና የቃላት ጨዋታ መጫወት ነው፡፡

ስለዚህ "መዳን በእምነት ብቻ"፣ "ክርስቲያናዊ መልካም ሥራ አያስፈልግም"፣ "ካመንን በኋላ ኃጢአት ሠርተን ብንገኝ እንኳ አንኰነንም"፣ . . . የሚለው የተሐድሶዎች ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱም ሆነ በአበው ሊቃውንት ትምህርት የሌለ የፈጠራ ትምህርት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እና አባቶቻችን ሊቃውንት የሚያስተምሩን ለመዳን ሰው በእምነት ላይ ሆኖ ክርስቲያናዊ መልካም ሥራ መሥራትን መጋደል ያለበት መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ተቃራኒ የሆነውን የተሐድሶዎች የስህተት ትምህርት ግን ጌታችን "ሑር እምድኅሬየ ሰይጣን - አንተ ሰይጣን፣ ከእኔ ወግድልኝ" እንዳለው እኛም እንዲሁ ሰይጣን ሆይ፣ የሞት ትምህርትህን ይዘህ ከእኛ ወግድልን እንለዋለን፡፡ ማቴ. 4፥10

# ምዕራፍ አራት

## ጾም፣ ምጽዋት እና ቀኖና

በዚህ ምዕራፍ ስለ ጾም፣ ምጽዋት እና ቀኖና ምንነትና አስፈላጊነት እንመለከታለን፡፡ ከላይ እንዳየነው ተሐድሶዎች ዋጋ የለሽና ጥቅም አልባ ናቸው ብለው የፈጠራ ትምህርታቸውን ከሚናገሩባቸው ክርስቲያናዊ ተግባራት መካከል ጾም፣ ምጽዋት እና ቀኖና ይገኙባቸዋል፡፡ ስለሆነም በዚህ ምዕራፍ በመጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በመቀጠልም በአበው ሊቃውንት ትምህርት መሠረት እነዚህን በተመለከተ ያለውን እውነተኛ ክርስቲያናዊ አስተምህሮ እንመለከታለን፡፡

## 4.1 ጾም

ጾም በመንፈሳዊ ሕይወት የማደጊያና ልብላ ልጠጣ የሚለውን የሰውነት መሻትና ፍላጎት ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ማቅረቢያ መንገድ ነው፡፡ ጾም ማለት ከሆነ ነገር መከልከል ማለት በመሆኑ ጾም ለአዳም የተሰጠው የመጀመሪያው ትእዛዝ ነው፡፡ "ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፣ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና" ብሎ ያዘዘው ትእዛዝ ይህ ነውና፡፡ ዘፍ. 2፥17 አዳም ማድረግ ይችል የነበረውን ነገር (ከዚያ ዛፍ መብላትን) ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ብሎ እንዲተው ነበር የታዘዘው፡፡ ጾምም አንድ ሰው ለማድረግ መብት እያለው ነገር ግን ከዚያ በላይ ፈጣሪውን አስቦ ያን ነገር በመተው ከፈቃዱ መሥዋዕት አድርጎ የሚያቀርብበት መንገድ ነው፡፡ አባታችን ዳዊት "ዘእምፈቃድየ እሠውእ ለከ - ከፈቃዴ እሠዋልሃለሁ" ያለው ይህን ነው፡፡ መዝ. 53፥6

### 4.1.1 ጾም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጾም አስፈላጊነትና ጠቀሜታ አበክሮ ይናገራል፣ ያስተምራል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጾም የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

#### 4.1.1.1 የጾም አስፈላጊነትና ጠቀሜታ

1) ጾም እግዚአብሔርን የመፍራትና ፊትን ወደ እርሱ የማዞር ምልክትና የእግዚአብሔርን ገጸ ምሕረት መለመኛ መንገድ ነው፡፡

ኢዮሣፍጥ የተባለው የእሥራኤል ንጉሥ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ፣ እግዚአብሔርን ከመተው እርሱን ወደ ማምለክ ፊቱን ባቀና ጊዜ ይህን መልካም የሆነ መንፈሳዊ ጉዞውን የጀመረው በጾም ነበር፤ "ኢዮሣፍጥም ፈራ፤ እግዚአብሔርንም ሊፈልግ ፊቱን አቀና፣ በይሁዳም ሁሉ ጾም አወጀ" እንዲል። 2 ዜና 20፥3 እንዲሁም ካህኑ ዕዝራ እስራኤላውያን በኃጢአታቸው ምክንያት ተማርከው ባቢሎን ወርደው ሰባ ዓመት በኖሩበት ዘመን ሲናገር እንዲህ ይላል፦ "በአምላካችን ፊት ራሳችንን እናዋርድ ዘንድ፣ ከእርሱም የቀናውን መንገድ ለእኛና ለልጆቻችን ለንብረታችንም ሁሉ እንለምን ዘንድ በዚያ በአኅዋ ወንዝ አጠገብ ጾም አወጅሁ።" ዕዝ. 8፥21 በዚያ በጾማቸው ስላገኙት ጥቅም ሲናገር ደግሞ "ስለዚህም ነገር ጾምን፣ ወደ እግዚአብሔርም ለመንን፣ እርሱም ተለመነን" በማለት ጾም እግዚአብሔርን መለመኛና ጸሎታችን እንዲሰማ የሚያደርግ መልካም መሣሪያ መሆኑን በተግባር ካገኙት ነገር በመነሣት ይመሰክራል፡፡ ዕዝ. 8፥23

2) ጾም ሐዘንን እና ችግርን ለእግዚአብሔር መንገሪያና ጭንቀታችንን ሁሉ በፊቱ ማፍሰሻ መንገድ ነው፡፡

የኢየሩሳሌም ከተማ ቤተ መቅደሷ ፈርሶ ቅጥሮቿ ሁሉ ተቃጥለውና ጠፍተው ስለ ነበር ነህምያ ያን ባሰበ ጊዜ በጾምና በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ሐዘኑን ገለጸ፣ እንዲህ ሲል፡- "ይህንም ቃል በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስሁ፣ አያሌ ቀንም አዝን ነበር፤ በሰማይም አምላክ ፊት እጾምና እጸልይ ነበር" ነህ. 1፡4 በጾሙና በጸሎቱም እግዚአብሔር በማረካቸው ንጉሥ ፊት ሞገስን ሰጠው፣ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ቅጥሮቿን እንደገና እንዲሠራ ፈቃድ ሰጠው፡፡ ነህ. 2 ልበ አምላክ የተባለ ዳዊትም "እኔስ እነርሱ በታመሙ ጊዜ ማቅ ለበስሁ፣ ነፍሴንም በጾም አደከምኋት"፤ እንደዚሁም "ነፍሴን በጾም አስመረርኋት፣ ለስድብም ሆነብኝ" በማለት ስለ ሌሎች ወገኖቻችን ችግር መጾም ተገቢ መሆኑን፣ እንዲሁም ጾም ማለት ሰውነት እስኪደክምና ረሃብ እስኪሰማው ድረስ የሚፈጸም መሆኑን ይናገራል፡፡ መዝ. 34፡13 ፤ 68፡10

ነቢዩ ኢዮኤልም "ጾምን ቀድሱ፣ ጉባኤውንም አውጁ፣ ሽምግሌዎችንና በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ቤት ሰብስቡ፣ ወደ እግዚአብሔርም ጩኹ" በማለት ጾም የሚታወጅ መሆኑን፣ እንዲሁም ወደ እግዚአብሔር መጮኺያ መንገድ መሆኑን ተናግሯል፡፡ ኢዮ. 1፡14 ራሱ ባለቤቱ እግዚአብሔርም በጾም ወደ እርሱ እንመለስ ዘንድ "አሁንስ ይላል እግዚአብሔር፣ በፍጹም ልባችሁ፣ በጾምም፣ በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ። በጽዮን መለከትን ንፉ፣ ጾምንም ቀድሱ፣ ጉባኤውንም አውጁ" በማለት ነግሮናል፡፡ ኢዮ. 2፡12

3) ጾም የትውልድ ስብራት የሚጠገንበትና መልካም የሆነ ትውልድ የሚታነጽበት መሣሪያ ነው፡፡

እግዚአብሔር ምን ዓይነት ጾም እንደሚያስደስተውና በዚያ መንገድ ብንጾም ምን በረከትና ጥቅም እንደምናገኝ ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

> እኔስ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን? የበደልን እስራት ትፈቱ ዘንድ፣ የቀንበርንስ ጠፍር ትለቅቁ ዘንድ፣ የተገፉትንስ አርነት ትሰድዱ ዘንድ፣ ቀንበሩንስ ሁሉ ትሰብሩ ዘንድ አይደለምን? እንጀራህንስ ለተራበ ትቈርስ ዘንድ፣ ስደተኞቹን ድሆች ወደ ቤትህ ታገባ ዘንድ፣ የተራቈተውንስ ብታይ ታለብሰው ዘንድ፣ ከሥጋ ዘመድህ እንዳትሸሸግ አይደለምን? የዚያን ጊዜ ብርሃንህ እንደ ንጋት ይበራል፣ ፈውስህም ፈጥኖ ይበቅላል፣ ጽድቅህም በፊትህ ይሄዳል፣ የእግዚአብሔርም ክብር በኋላህ ሆኖ ይጠብቅሃል። የዚያን ጊዜ ትጠራለህ፣ እግዚአብሔርም ይሰማሃል፣ ትጮኻለህ፣ እርሱም፡- እነሆኝ ይላል፡፡ . . . ብርሃንህ በጨለማ ይወጣል፣ ጨለማህም እንደ ቀትር ይሆናል። እግዚአብሔርም ሁል ጊዜ ይመራሃል፣ ነፍስህንም በመልካም ነገር ያጠግባል፣ አጥንትህንም ያጠናል፣ አንተም እንደሚጠጣ ገነት፣ ውኃውም እንደማያቋርጥ ምንጭ ትሆናለህ። <u>ከዱሮ ዘመን የፈረሱት ስፍራዎች ይሠራሉ፣ የብዙ ትውልድም መሠረት ይታነጻል</u>፣ አንተም ሰባራውን ጠጋኝ፥ የመኖሪያ መንገድን አዳሽ ትባላለህ። . . . የእግዚአብሔር አፍ ተናግሯልና። ኢሳ. 58፡6-14

እግዚአብሔር አምላካችን "<u>ከዱሮ ዘመን የፈረሱት ስፍራዎች ይሠራሉ፤ የብዙ ትውልድም መሠረት ይታነጻል</u>" በማለት በግልጽ እንደ ተናገረው ያለፉ ስህተቶቻችንና በሀገርና በወገን ላይ ያሳደሯቸው አሉታዊ ጠባሳዎች፣ ያፈረሷቸው ስፍራዎችና መልካም ነገሮች ሁሉ የሚጠገኑትና ተመልሰው የሚሠሩት በጾም ነው፡፡ ያለፈው ብቻ ሳይሆን የሚመጣው ትውልድም በጥሩ መሠረት ላይ የሚመሠረተው እንዲሁ በጾም ነው፡፡ ከዚህም ጋር በአግባቡ የሚጾመውን ሰው "አንተም ሰባራውን ጠጋኝ ትባላለህ" እንደ ተባለ ጾም የተሰበረው የሚጠገንበት ታላቅ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፡፡ የስብራት መጠገን ሲባል ደግሞ በዋናነት ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት በኃጢአት ምክንያት ተሰብሮ ከነበረ የሚጠገንበት መንገድ ጾም መሆኑን ራሱ እግዚአብሔር ባለቤቱ ነገረን፡፡

እንደዚሁም ጾም የመልካም ነገር ሞዜግና መጥቅዕ ስለ መሆኑ ሲናገር እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የአራተኛው ወር ጾም፣ የአምስተኛውም፣ የሰባተኛውም፣ የአሥረኛውም ወር ጾም ለይሁዳ ቤት ደስታና ተድላ፥ የሐሤትም በዓላት ይሆናል፤ ስለዚህም እውነትንና ሰላምን ውደዱ።" ዘካ. 8፡19

4) ጾም የአምልኮ መንገድ ነው።

በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን የነበሩት ነቢያትና መምህራን ጌታን ካመለኩበት መንገድ አንዱ ጾም ነበር። ይህንንም ቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ ይነግረናል፦

> በአንጾኪያም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ፤ እነርሱም በርናባስ ኔጌር የተባለው ስምዖንም፥ የቀሬናው ሉክዮስም፥ የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄሮድስ ባለሟል ምናሔ፥ ሳውልም ነበሩ። እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ፦ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ። በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም እጆቻቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቷቸው።

የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን መምህራንና ነቢያት እግዚአብሔርን ሲያመልኩ እየጾሙ ነበር። እውነተኛ አምልኮ ከጾም ርቆና ተለይቶ እንደማይሆን በተግባር አስተማሩን። በጾምና በአምልኮ ላይ ሳሉም "መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ" አላቸው። ይህን "በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ" የሚለውን የመንፈስ ቅዱስ የጥሪ ድምፅ የሰሙት እየጾሙ ሳሉ ነበር። የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ለመስማት ከመብላት ይልቅ መጾምን መምረጥ ጠቃሚም ተገቢም መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይነግረናል። መንፈስ ቅዱስ ለሥራ የጠራቸውን በርናባስንና ሳውልን ያሰናበቷቸውም እንዲሁ በጾምና በጸሎት ነበር፤ "በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም እጆቻቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቷቸው" እንዲል። የሐዋ. 13፡1-2

እንዲሁም ጾም ለእግዚአብሔር ከሚደረጉ አገልግሎቶች አንዱና ዋናው ነው። ከአሴር ወገን የነበረችውና ሰማንያ አራት ዓመት በባልቴትነት በቤተ መቅደስ እግዚአብሔርን ስታገለግለው ስለ ነቢይቱ ሐና ሲናገር መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "እርሷም ሰማኒያ አራት ዓመት ያህል መበለት ሆና በጣም አርጅታ ነበር፤ በጾምና በጸሎትም ሌሊትና ቀን እያገለገለች ከመቅደስ አትለይም ነበር።" ሉቃ. 2፡37 የሐና አገልግሎት ጾምና ጸሎት ነበር። ጾም ታላቅ አገልግሎት ነውና።

5) ጾም አጋንንትን የሚያወጣቸው፣ ርኩሳን መናፍስትን የምንዋጋበት መሣሪያ ነው።

በተለይም ጸበል በመጸበልና መስቀል በመታሸት ብቻ በቶሎ የማይወጡና "አሳድጌ አሳድጌ አሁን የት ልሂድ?" እያሉ የሚያስቸግሩ ርኩሳን መናፍስት የሚወጡት ከውስጥ በሚሆን የጾም ተጋድሎ ነው። ይህንም ጌታችን ደቀ መዛሙርቱ ማውጣት አቅቷቸው የነበረውን ጋኔን እርሱ ካወጣው በኋላ ወደ እርሱ ቀርበው "እኛ ልናወጣው ያልቻልን ስለ ምን ነው?" ብለው በጠየቁት ጊዜ ስለ እምነታቸው ማነስ መሆኑን ከነገራቸው በኋላ ከዚያው ቀጥሎ "ይህ ወገን በጸሎትና በጦም ካልሆነ በምንም ሊወጣ አይችልም" አላቸው። ማር. 9፡29

ስለሆነም ያለ ጾምና ጸሎት አጋንንትን ማውጣት አይቻልም። ጾምን እየነቀፉና እያጥላሉ፥ እንዲሁም በተግባር ሳይጾሙ አጋንንትን እናወጣለን ማለት የአጋንንት መዘባበቻና መጫወቻ መሆን ነው። እንዲህ ያለውን ሰው አጋንንት የወጡ እየመሰሉ የበለጠ ይጫወቱበታል። እንዲህ ባሉት ሰዎች ርኩሳን መናፍስት ይወጡልኛል ብሎ የሚያምነውንም ሰው አጋንንት ከድጡ ወደ ማጡ ይወስዱታል። ቅዱሳን ሐዋርያት እንኳ ያለ ጾም ማውጣት ያልቻሉ ከሆነ የጾም ጠላት ሆኖ ጾምን እየነቀፉና እየተሰቀቁ አጋንንትን ማውጣት እችላለሁ የሚል እርሱ ማን ነው? ከሐዋርያት ይበልጣልን? ከጌታ ቃልስ ይበልጣልን?

አንድ ሊቅ "ጸሎትና ጾም በሌለበት ሰው ውስጥ ሰይጣን አለ ብለን ማሰብ እንችላለንን?" ብሎ ይጠይቅና ሲመልስ "አዎ፣ አጋንንት ወደ ሰው ውስጥ ሲገቡ መግባታቸውን በግዛድ አያሳውቁም፣ መግባታቸው እንዳይታወቅባቸው ለማድረግ ሲሉ ራሳቸውን ይደብቃሉ እንጂ፤ ሆኖም የገቡበትን ያን ሰው ክፉውን ነገር ሁሉ በስውር ከውስጥ ያስተምሩታል፣ መልካም የሆነውን ነገር ደግሞ ያስጠሉታል፡፡ ያ ሰው የሚፈጽመው የጠላትን ፈቃድ ሆኖ ሳለ እርሱ ግን እርሱ ራሱ እያደረገው እንደሆነ ያስባል፡፡ ጠላት ትቶህ የሚወጣውና ሊላ መመለሻ አጋጣሚ እስኪያገኝ ድረስ ከአንተ ርቆ የሚጠባበቀው ጸሎትና ጾምን ስትታጠቅ ብቻ ነው፡፡ ጸሎትና ጾም ከተተው ግን እንደገና ተመልሶ ይመጣል" ይላል፡፡

ስለሆነም ጾምና ጸሎት በተተውበትና በሌሉበት ሕይወት ዘንድ ኦርቶዶክሳዊነት ሽታውም አለ ማለት አይቻልም፡፡ ጾም የሌለበት ሰውነት የአጋንንት መሥሪያ ቤት እንጂ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አይሆንም፡፡ በተሐድሶዎችና በመሰሎቻቸው እያደረ "ዘመናዊ" ወይም "ሊበራል" በሚል ሽፋን ሰይጣን የሚሰብከውን "ጾም የለሽ" "ክርስትና" ወይም "እምነት" ልብ እንበል፣ እንወቅበትም! ኦርቶዶክሳዊነት በባሕርዩ ትህርምታዊ (Ascetic) ነው፡፡ ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ሕዝቡንም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ጠርቶ እንዲህ አላቸው፦ በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ፣ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ" ያለው ለዚህ ነው፡፡ ማር. 8፡34 ሆድን ወድዶ ጾምን ጠልቶ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆን አይቻልም፡፡ እንዲህ ያሉት "ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ሆነው ይመላለሳሉና፤ ብዙ ጊዜ ስለ እነርሱ አልኋችሁ፣ አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ፤ መጨረሻቸው ጥፋት ነው፣ ሆዳቸው አምላካቸው ነው፣ ክብራቸው በነውራቸው ነው፣ አሳባቸው ምድራዊ ነው" የተባሉት ናቸው። ፊል. 3፡18-19

6) ጾም ታላቅ የመንፈሳዊ ተጋድሎ መንገድ ነው፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው የሥራው ሁሉ መጀመሪያ ጾምን ያደረገው ለዚህ ነበር፡፡ መድኃኒታችን በገዳመ ቆሮንቶስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት የጾመው ጾም የመንፈሳዊ ተጋድሎ ሁሉ መጀመሪያና በር መሆኑን በተግባር ለማሳየትና ለማስተማር ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም የጌታውን አርአያ በመከተል "በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፣ በራብና በጥም፣ <u>ብዙ ጊዜም በመጦም</u>" ይላል፡፡ 2 ቆሮ. 11፡27

ቅዱስ ጳውሎስ ከተጋደለባቸው መንገዶች አንዱ ጾም ነበር፡፡ ይህንም በሁለተኛ ቆሮንቶስ መልእክቱ ለእኛ ትምህርት ይሆን ዘንድ እንዲህ ሲል ገልጾታል፦ "ነገር ግን በሁሉ እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳችንን እናማጥናለን፤ በብዙ መጽናት፣ በመከራ፣ በችግር፣ በጭንቀት፣ በመገረፍ፣ በወኅኒ፣ በሁከት፣ በድካም፣ እንቅልፍ በማጣት፣ <u>በመጦም</u>፣ በንጽህና፣ በእውቀት፣ በትዕግሥት፣ በቸርነት፣ በመንፈስ ቅዱስ፣ ግብዝነት በሌለው ፍቅር፣ በእውነት ቃል . . . " 2 ቆሮ. 6፡4-6

4.1.1.2 ጾም የታወቀ ጊዜ ያለው መሆኑ

ጾም የታወቀ ጊዜ አለው፡፡ በተለይም የአዋጅ አጽዋማት የሚጀምሩበትና የሚወጡበት ጊዜ የታወቀ ነው፡፡ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ በሚገባ ተገልጿል፡፡ ለአብነትም በትንቢተ ኤርምያስ እንዲህ ይላል፦

> አንተ ግን ሂድ፣ ከአፌም የጻፍኸውን የእግዚአብሔርን ቃል <u>በጾም ቀን</u> በእግዚአብሔር ቤት በሕዝቡ ጆሮ በክርታሱ አንብብ፣ ደግሞም ከከተሞቻቸው በሚወጡ በይሁዳ ሰዎች ሁሉ ጆሮ እንብበው። እንዲህም ሆነ፣ በይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአቄም በአምስተኛው ዓመት በዘጠነኛው ወር <u>በኢየሩሳሌም የተቀመጡ ሕዝብ ሁሉ ከይሁዳም ከተሞች ወደ ኢየሩሳሌም የመጡ ሕዝብ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት</u> <u>ለመጾም አዋጅ ነገሩ</u>፡፡ ኤር. 36፡6-9

"በጾም ቀን" ማለቱ የታወቀ የጾም ቀን ስለ ነበር ነው፡፡ እንዲሁም "በኢየሩሳሌም የተቀመጡ ሕዝብ ሁሉ ከይሁዳም ከተሞች ወደ ኢየሩሳሌም የመጡ ሕዝብ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ለመጾም አዋጅ ነገሩ" የተባለው በዐዋጅ ተነግሮ በኅብረት የሚጾም ጾም ያለ በመሆኑ ነበር፡፡ የኅብረት ጸሎት እንዳለ ሁሉ የኅብረት ጾም እንዳይኖር የሚያግድ ምን ምክንያት አለ? በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አሥራ ሦስት ላይ ከላይ እንዳየነው በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ጌታን ሲያመልኩና ሲጾሙ የነበረው በኅብረት (በአንድነት) ነበር፡፡ ስለዚህም በዐዋጅ የሚታወቅ የኅብረት ጾም አለ፡፡ ነቢዩ ኢዮኤልም "ጾምን ቀድሱ፥ ጉባኤውንም አውጁ፥ ሽምግሌዎችንና በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ቤት ሰብስቡ፥ ወደ እግዚአብሔርም ጩኹ" በማለት ጾም የሚታወጅ መሆኑን፣ እንዲሁም ወደ እግዚአብሔር መጮኺያ መንገድ መሆኑን ተናግሯል፡፡ ኢዮ. 1፥14 ነቢዩ ዘካርያስም "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ የአራተኛው ወር ጾም፥ የአምስተኛውም፥ የሰባተኛውም፥ የአሥረኛውም ወር ጾም ለይሁዳ ቤት ደስታና ተድላ የሐሤትም በዓላት ይሆናል" ዘካ. 8፥19 ይህም ጾም ያለባቸው (የሚጾምባቸው) ወራት ተለይተው ይታወቁ እንደ ነበር በግልጽ ያስረዳናል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም "ብዙ ጊዜም ካለፈ በኋላ፥ የጦም ወራት አሁን አልፎ ስለ ነበረ . . ." በማለት የታወቀ የጾም ጊዜ ያለ መሆኑን ተናግሯል፡፡ የሐዋ. 27፥9

ጌታችን ስለ ጾም ባስተማረበት አንቀጽ "አንተ ግን ስትጦም በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደ ጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ፥ ፊትህንም ታጠብ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል" ያለው በአጠቃላይ አንድ ሰው ሲጾም በሕሊናው ለታይታና መጾሙን ሰው እንዲያውቅለትና ጾመኛ እንዲለው ከመሻት እንዳይሆን የተሰጠ ትምህርት ነው፡፡ ማቴ. 6፥17-18 ወሳኙ ጉዳይ ሰው ማየት አለማየቱ ሳይሆን የሰውዬው ሕሊና ነው፡፡ በጸሎት ጊዜ በኅብረት ስንጸልይ ሰው ያየናል ብለን "በማኅበር ባርክዎ ለእግዚአብሔር - እግዚአብሔርን በጉባኤ በአንድነት አመስግኑት" የተባለውን እንደማንተው ሁሉ በጾምም መጾማችን ይታወቃል ብለን በታወቀ ጊዜ በሕዝበ ክርስቲያኑ ሁሉ በአንድነት የሚጾሙ አጽዋማትን አንተውም፡፡

ጌታችን "ቀኝህ የምታደርገውን ግራህ አትወቅ" ሲል ከአንድ የሰውነት አካል ውስጥ አንዱ የሚሠራውን ሌላው ለማወቅ የማይችል ሆኖ አይደለም፡፡ ነገር ግን በዚህ ቃሉ ሊያስገነዝበን የፈለገው የምንሠራውን መንፈሳዊ ሥራ ሁሉ ልክ እኛው ራሳችን እንኳ የማናውቀው እስኪሆን ድረስ መርሳት (ይህን አድርጌያለሁ እያሉ አለማስታወስ) የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ አሥራ ስምንት ላይ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዶ ሲጸልይ የነበረውን ፈሪሳዊ የነበሩትን መልካም ነገሮች ያጠፋበትና ባዶውን ያስቀረው እነዚያኑ ዘርዝሮ መናገሩም ነበርና፡፡ ስለዚህ ዋናው ጉዳይ ሕሊናዊ እንጂ አፍአዊ አይደለም፡፡ በዚህም ላይ መናፍቃን "ስንጾም መታየት አንፈልግም" የሚለው አባባላቸው ሽፋኑ እንጂ እውነታው ጾምን መጥላትና ሆድን መውደድ ነው፡፡ ሐዋርያው "መብል ለሆድ ነው፥ ሆድም ለመብል ነው፤ እግዚአብሔር ግን ይህንም (መብልንም)፥ ያንም (ሆድንም) ያጠፋቸዋል" የተባለውን የእግዚአብሔር ቃል እኛ ኦርቶዶክሳውያን እናምናለን፥ እንኖርበትማለን፡፡ 1 ቆሮ. 6፥13 ስለዚህ ያልሆነ ምክንያት እየፈጠሩ ለመብላት ከማድላት ይልቅ እውነተኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ተቀብሎ ለጾም ማድላት የተሻለ መሆኑም ግልጽ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ "ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው እንጂ በመብል አይደለም፤ በዚህ የሚሠሩባት አልተጠቀሙምና" ይላልና፡፡ ዕብ. 13፥9

እንደዚሁም ክርስቲያኑ ሁሉ አንድ ሆኖ በሚጾምባቸው አጽዋማት ጊዜ መጾም ለአንድ ክርስቲያን እንደ ክርስቲያናዊ ግዴታው የሚታይ እንጂ እንደ ልዩ ነገር ተቆጥሮ ውዳሴ ከንቱን የሚያመጣበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ አንድ ወታደር አገሩን ለመጠበቅ የገባውን ግዳጅ ቢወጣ ግዳጁን ተወጣ ይባላል እንጂ እንደ ተለየ አዲስ ነገር አይቆጠርለትም፡፡ አንድ መምህርም የተሰጠውን የትምህርት ዓይነት በተመደበለት ክፍለ ጊዜ እየገባ ተማሪዎቹን ቢያስተምር ይህ ሊሠራው የሚገባውን ሥራውን ሠራ ይባላል እንጂ ልዩ ነገር አደረገ ተብሎ አያስመሰግነውም፡፡

አንድ ክርስቲያንም መጾም ባለበት ጊዜ መጾሙ እንዲሁ ነው፡፡ ክርስቲያን የአንዲቷ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አካል እንደ መሆኑ በኅብረት የሚሠሩ መንፈሳዊ ተግባራት በጋራ ይሠራሉ፡፡ እነ ቅዱስ ጳውሎስ፡ ነቢያትና ሐዋርያት የታወቀ የጾም ወቅት ከነበራቸው እኛ እነርሱን እንከተላለን እንጂ ከእነርሱ የተለየ ሌላ መንገድ አንከተልም፡፡ ኦርቶዶክሳዊነት ማለት ጌታ ለሐዋርያት የሰጣቸውንና እነርሱ ደግሞ ያስተማሩንንና ያወረሱንን እንዳለ መጠበቅና በእርሱ መኖር ነውና፡፡

### 4.1.1.3 በጾም ወቅት የማይበሉ ምግቦች ስለ መኖራቸው

ጾም ሰውነትን በተወሰነ መጠን የሚያደክምና በልቶ ጠጥቶ የሚገኘውን ርካታ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ በመተው የሚቀርብ መሥዋዕት ነው፡፡ ስለሆነም በሌላ ጊዜ ከሚበሉ መባልዕት መካከል በጾም ጊዜ የማይበሉ የምግብ ዓይነቶች አሉ፡፡ ይህም እነዚያ ምግቦች የረከሱ ስለ ሆኑ ሳይሆን ጾሙን እውነተኛና የፍቅር መገለጫ ይሆን ዘንድ ሰውነትን ደከም የሚያደርግ እንዲሆን ነው፡፡ ይህ ከቀደምት አበው ጀምሮ የነበረ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሕይወት ነው፡፡ ነቢዩ ዳዊት እንዴት እንደ ጾመ ሲናገር "ወአሕመምክዋ በጾም ለነፍስየ - ነፍሴንም በጾም ቀጠኋት አደከምኋት)" አለ፡፡ መዝ. 34፥13

እንደዚሁም "ወቀጻእክዋ በጾም ለነፍስየ ወኮነኒ ጽእለተ - ነፍሴን በጾም አስመረርኋት፣ ለስድብም ሆነብኝ" በማለት ጾም በተወሰነ መልኩም ቢሆን ሰውነትን ማስመረር (መራብና መጠማት) እንዳለበት ይናገራል፡፡ መዝ. 68፥10 እንዲሁም "ጕልበቶቼ በጾም ደከሙ፣ ሥጋዬም ቅቤ በማጣት ከሳ" በማለት ጾም ጉልበትን እንደሚያደክምና በጾም ጊዜም ቅቤ እንደማይበላ ይናገራል፡፡ ንጉሥ ዳዊት "ሥጋዬም ቅቤ በማጣት ከሳ" ያለው በጾም ጊዜ ቅቤ ስለማይበላ እንጂ ዳዊትን ያህል ገናና ንጉሥ ቅቤ ቸግሮት አልነበረም፡፡ መዝ. 108፥24

ነቢዩ ዳንኤልም እንዴት እንደ ጾመ ሲናገር "ማቅ ለብሼ፣ በአመድም ላይ ሆኜ ስጾም እጸልይና እለምን ዘንድ ፊቴን ወደ ጌታ ወደ አምላክ አቀናሁ" በማለት በጾም ወቅት ማቅ ለብሶ አመድ ነስንሶ መጾም ቢቻል ጾሙ የበለጠ እንደሚሆን ይናገራል፡፡ ዳን. 9፥3 እንዲሁም ሦስት ሳምንት በጾመ ጊዜ እንዴት እንደ ጾመ ሲናገር እንዲህ አለ፡- "በዚያም ወራት እኔ ዳንኤል ሦስት ሳምንት ሙሉ ሳዝን ነበርሁ። <u>ማለፊያ እንጀራም አልበላሁም፣ ሥጋና ጠጅም በአፌ አልገባም፣ ሦስቱም ሳምንት እስኪፈጸም ድረስ ዘይት አልተቀባሁም</u>።" ዳን. 10፥1-3 ስለሆነም በጾም ጊዜ ሥጋና ቅቤ፣ በአጠቃላይ የእንስሳት ተዋጽኦዎች ይተዋሉ ማለት ነው፡፡ ጾም መተው ነውና፡፡

### 4.1.1.4 ጾም በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ ያለው ስለ መሆኑ

እግዚአብሔር ባዘዘውና ኋላም ሥጋው ቃል መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አርአያ ሆኖ ባሳየው መንገድ የሚፈጸም ጾም ከእርሱ ዘንድ ታላቅ ዋጋ አለው፡፡ ጌታችን ራሱ ጾሞ ጾምን በተግባር ካሳየን በኋላ እንዴት መጾም እንዳለብን ሲያስተምረን እንዲህ አለ፡-

> ስትጦሙም እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፤ ለሰዎች እንደ ጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፋሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፣ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ስትጦም በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደ ጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ ፊትህንም ታጠብ፤ <u>በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል</u>። ማቴ. 6፥16-18

ጌታችን እንዴት መጾም እንዳለብን እንዲህ ያስተማረን ጾም በእርሱ ዘንድ ታላቅ ጥቅምና ዋጋ ያለው በመሆኑ ነው፡፡ በተለይ ጾምን ከውዳሴ ከንቱና ለሰዎች ለመታየትና ጾመኛ ለመባል ብሎ ከማድረግ መጠበቅ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ጌታችን "<u>በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል</u>" ያለው ጾም ታላቅ ዋጋ ያለው በመሆኑ አይደለምን? ጾምን ለውዳሴ ከንቱ ሊታይ የሚያደርጉት

ሰዎች "ዋጋቸውን ተቀብለዋል" ማለቱም እንዲህ ያሉት ሰዎች የሚጾሙት ከእግዚአብሔር ዘንድ በጾም የሚገኘውን ዋጋ ለማግኘት ሽተውና ተስፋ አድርገው ሳይሆን እንዲሁ ሰዎች እንዲያመሰግኗቸውና "ጾመኛ" እንዲሏቸው ብለው ስለሆነ ያንኑ የፈለጉትን ዋጋ ከሰዎች ስለ ተቀበሉ ሌላ ዋጋ ከእግዚአብሔር ዘንድ የላቸውም ማለት ነው፡፡ ከሰዎች ውዳሴን በመፈለግ ሳይሆን በእውነትና በአግባብ የሚጾሙ ሰዎች ደግሞ ከእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ዋጋ አላቸው፡፡ ራሱ ባለቤቱ በማይታበል ቃሉ "በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል" ብሏልና፡፡

ጌታችን ጾም ይህን ያህል ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገው ያስተማረን ጥቅም ለሌለው ነገር አይደለም፡፡ ጾምን በአግባቡ ለሚጾሙት ክርስቲያኖች ይህን በሰጠን በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ዋጋ አላቸው፡፡ የመጾም ዋጋቸውንም በትንሣኤ ዘጉባኤ በግልጥ ይከፍላቸዋል፡፡

ካህኑ ዕዝራስ "ስለዚህም ነገር ጾምን፣ ወደ እግዚአብሔርም ለመንን፣ እርሱም ተለመነን" በማለት ጾም ታላቅ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን አልተናገረምን? ዕዝ. 8፥23 እንዲሁም ራሱ እግዚአብሔር "አሁንስ፡ ይላል እግዚአብሔር፡ በፍጹም ልባችሁ በጾምም በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ። በጽዮን መለከትን ንፉ፣ ጾምንም ቀድሱ፣ ጉባኤውንም አውጁ" በማለት የተናገረው ጾም ጥቅምና ዋጋ ስላለው አይደለምን? ኢዮ. 2፥12-15

## 4.1.2 ጾም በቅዱሳን አባቶች ትምህርት

ስለ ጾም ጠቃሚነትና አስፈላጊነት፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ሰማያዊ ዋጋ ያለው ስለ መሆኑ፣ በጾም ጊዜ የእንስሳት ተዋጽኦዎች (ዓሣን ጨምሮ) እንደማይበሉ፣ እና በመሳሰሉት ጾምን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ቅዱሳን አባቶቻችን አስተምረዋል፡፡ ከእነዚያ መካከል የተወሰኑትን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

- "... ትምህርታችንን እንደሚከተለው ማጠቃለል ተገቢ ነው፤ የተፈጠርነው በሐሤትና በደስታ እንድንኖር ነበር፡፡ ስንፈጠር ደስተኞች ተደርገን ነበር የተፈጠርነው፡፡ ኅትትን የተሰጠነው በሕይወት እየኖርን ሐሤትን እንድናደርግ ነበር፡፡ ሕግን የተሰጠነውም እርሱን በመጠበቅ መልካም ስምና ክብር ይሆንልን ዘንድ ነበር፤ እግዚአብሔር ምን እንደሚሆን (ሕጉን እንደምናፈርስ) ስለማያውቅ ሳይሆን የነጻ ፈቃድን ሕግ ያስቀመጠ ስለሆነ ነበር፡፡ ከኅትት የተባረርነውም ሕጉን ስላፈረስን ነበር፡፡ የእውቀት ዛፍ በተባለችው ተሸንፈን መጾምን እምቢ በማለታችንና ጾምን በማፍረሳችን ከዚያ በኋላ በደረሰብን መከራ በግድ ጾምን፡፡ የጾም ሕግ ጥንታዊና ቀዳማዊ ነውና፣ ከእኛ መፈጠር ጋርም አብሮን የነበረ ሕግ ነውና፡፡ የጾም ሕግ አስቀድሞ የተሰጠንም ለነፍሳችን ትምህርት፣ ለድሎትና እርሱ ለሚያመጣው ዕጻ አርቆ ማጠሪያና መጠበቂያ እንዲሆነን ነበር፡፡ ስለዚህም ዛሬ ከጥንቱ ከመጀመሪያው የጾምን ሕግ ባለመጠበቃችን ምክንያት ያጣነውን ነገር መልሰን እናገኝ ዘንድ ጾምን እንድንጾምና ለጾም እንድንገዛ አደረገን፡፡"

 (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ፣ ትምህርት ካልአይ በእንተ ትንሣኤ፤ ቁ. 28)

- "በጾማችን የነፍሳችንን ክፉ ልማዶች ካላስወገድን ከሥጋ መከልከላችን ብቻውን ምን ይጠቅመናል? ስንጾም ውስን ጾም ከመግባቱ በፊት እንመገበው የነበረውን ምግብ ለውጠን መናኛ የሆነ የጾም ምግብ በማዕዳችን አቀረብን፣ ሆኖም ግን በጾሙ የምንመገበውን ምግብ እንደ ለወጥን ክፉ ግብራችንን እና ሕይወታችንንስ አብረን ለውጠናል ይሆን? በእውነት እኔ ግን እንዲህ ያደረጋችሁ አልመስለኝም፡፡

እንዲህ ከሆነ መጾማችሁ ጥቅሙ ምንድን ነው? ስለዚህ ከጾማችሁ ጋር ልማዳችሁንና ሕይወታችሁን ወደ መልካምነት ትቀይሩ ዘንድ በተከታታይ እንድታስቡበት አደርጋችሁ ዘንድ ስለዚህ ነገር እናንተን ማስተማርንና መገሠጽን አላቋርጥም፡፡ በጾማቸው መንፈሳዊ ፉክክር የሚፎካከሩ እንዳሉ ሁሉ፤ በዚህም አስደናቂ የሆነ ተጋድሎን የሚጋደሉ እንዳሉ ሁሉ፤ ሁለት ሙሉ ቀናትን በተከታታይ ምንም ነገር ሳይቀምሱ የሚጾሙ አንዳንዶች አሉና፡፡ ሌሎች ደግሞ በጾም ጊዜ ወይን እና ዘይትን መተው ብቻ ሳይሆን ሌላውን ነገር ሁሉ ትተው መላውን ዐቢይ ጾም በደረቅ ዳቦና በውኃ ብቻ የሚጾሙ አሉና፡፡ . . ." (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፤ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 4፤ ቁ. 12)

- "ጾም ምን እንደሚያደርግ ተመልከት፤ ደዌን ይፈውሳል፤ አጋንንትን ያባርራቸዋል፤ ክፉ ሃሳቦችን ያስወግዳቸዋል፤ ልብን ንጹሕ ያደርጋል፡፡ በርኩስ መንፈስ የተያዘ ሰው እንኳ ቢኖር በጌታ ቃል መሠረት 'እንዲህ ያለው መንፈስ ያለ ጾምና ጸሎት በስተቀር እንማይወጣ' ይወቅ፡፡ ማ. 17፡21" (ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ)

- "ራሳችንን ፍሬ በሌለው መንገድ በከንቱ እንዳናደክም ጥቂት ነገሮችን እንበል፡፡ በርግጥ አሁን የምታደርጉት ነገር - ጾማችሁና መሬት ላይ መተኛታችሁ - በጣም የተመሰገነ ተግባር ነው፡፡ ሆኖም ከእነዚህ ጋር ሌሎች በጾም ጊዜ ሊፈጸሙ የሚገባቸው ተግባራት ካልተጨመሩ በስተቀር ከጾም የምናገኘውን ዋጋ ያሳጡናል፡፡ እግዚአብሔር ኃጢአትን እንዴት ይቅር እንደሚል አሳይቶናል፡፡ በጥንት ዘመን የነነዌ ሰዎች ኃጢአትን ባደረጉ ጊዜ በኃጢአት ቁስላቸው ላይ ጽኑ የሆነ የጾምን መድኃኒት አድረጉ፡፡ መሬት ላይ በመተኛት ማቅና ዓመድ ለበሱ፤ ልቅሶንና ሐዘንን በኃጢአት ቁስላቸው ላይ መድኃኒት አድርገው አፈሰሱ፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ከዚህ ሁሉ ጋር ደግሞ ሕይወታቸውን ከክፉ ወደ መልካም ለወጡ፡፡ ከዚህ ሁሉ ጋር እግዚአብሔር በምን ምክንያት እንደ ማራቸው ሲናገር 'እግዚአብሔርም ከክፉ መንገዳቸው እንደ ተመለሱ ሥራቸውን አየ፤ እግዚአብሔርም ያደርግባቸው ዘንድ በተናገረው ክፉ ነገር ተጸጸተ አላደረገውም' ይላል። ዮና. 3፡10 ስለዚህ ከመጾም ጋር ከክፉ መመለስንና ከክፉ ነገር መጾምንም እንፈጽም ዘንድ መዘንጋት የለብንም፡፡"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፤ ትርጓሜ ቆሮንቶስ ቀዳማዊ፤ ክፍለ ትምህርት 4. ቁ. 6)

- "ቅዱስ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ የጌታችንን ጽዋ ከጠጣበትና ቅዱስ ሥጋውን ከበላበት ከጸሎተ ሐሙስ ማታ አንሥቶ ጌታችንን ከሞት ተነሥቶ እስኪያየው (እስከ ትንሣኤው) ድረስ ምንም ነገር እንደማይቀምስ ለራሱ ቃል ገባ፡፡[89] ስለዚህም መድኃኒታችን እንደ ተነሣ ወዲያውኑ ለያዕቆብ ተገለጠለትና እንዲመገብ አዘዘው፡፡ 1 ቆሮ. 15፡8" ቅዱስ ጀሮም

- "አመጋገብን በተመለከተ የምትከተሉት መመሪያችሁ ይህ ይሁን፤ በጾም ጊዜ ከሚመገቡት የምግብ ዓይነት የተነሣም ብዙዎች ይሰናከላሉና፡፡ . . . ከሥጋና ከወይን በመከልከልና እነዚህን በመተው የምንጾመው የረከሱ ነገሮች ናቸው ብለን በመጸየፍ አይደለም፤ ነገር ግን እነዚህን የሚታዩትን ቁሳዊ ነገሮች በመናቅና በመተው መንፈሳዊና ሰማያዊ ተድላ ደስታን እናገኝ ዘንድ ተስፋ በማድረግ ነው እንጂ፡፡ በጾማችን ሥጋንና ወይንን የምንተወው ሰማያዊ ዋጋን ከእግዚአብሔር ዘንድ እናገኝ ዘንድ ተስፋ ስለምናደርግ ነው፤ *በልቅሶ ዘርተን በደስታ እናጭድ ዘንድ ነው እንጂ* መዝ. 125፡5 . . . ከእነዚህ ነገሮች ራሳችሁን ስትከለክሉና ስትታቀቡ የተጠሉና የረከሱ ነገሮች እንደሆኑ አድርጋችሁና አስባችሁ መሆን የለበትም፤ እንደዚህ የምታስቡ ከሆነ ጾማችሁ ምንም ዋጋ የለውም፡፡ ነገር ግን ሥጋና ወይን በተፈጥሯቸው መልካም ነገሮች ቢሆኑም በፊትህ ስለ ተዘጋጁልህ የበለጡ መንፈሳዊ ነገሮች ስትል በጾም ጊዜ እነርሱን ተዋቸው፡፡"

(ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፤ ትምህርት 4፤ ቁ. 27)

[89] በቤተ ክርስቲያናችን "አክፍሎት" የምንለው ጾም ማለት ነው፡፡

- "ብዙ ሰዎች አንዳቸው ለሌላቸው 'የጾሙ ግማሽ አለፈ፣ ግማሹን ጾም ፈጽመናል' ሲባባሉ እመለከታለሁ፡፡ እኔ ግን እንዲህ ያሉት ሰዎች የጾሙ ግማሽ በማለቁ በዚህ እንዳይደሰቱ እመክራቸዋለሁ፡፡ ከዚህ ይልቅ በጾማቸው የኃጢአታቸው ግማሽ ተወግዶ ስለ መሆኑ እንዲያስቡና በእርግጥ በጾማቸው እንደዚህ ዓይነት ጥቅም አግኝተው ከሆነ ያን ጊዜ ቢደሰቱ መልካም ይሆናል፡፡ ልናስብበት የሚገባው ነገር ይህ ነውና፤ ጾሙን ስንጨርስ ልክ ስንጀምር እንደ ነበርነው ዓይነት ሰዎች ሆነን ሳይሆን ከኃጢአታችን የነጻን ሰዎች ሆነን እንድንጨርሰው መሆንን ነው፡፡ . . . የክረምት ጠቀሜታው የበለጠ የሚታወቀው ወቅቱ ካለፈ በኋላ ነውና፡፡ ያን ጊዜ የአበባዎች ማበብ፣ የአዝመራው ማፍራት፣ የዛፎች መለምለም፣ እነዚህ ሁሉ በመታየታቸውና በመውጣታቸው ከክረምቱ ያገኙትን ጠቀሜታ በግልጽ ይናገራሉ፡፡ በእኛም እንዲሁ ይሁን፡፡ በጾም ወራት ያገኘነው መንፈሳዊ ጥቅም ጾሙ ካለፈ በኋላ በእኛ ላይ በሚያፈራው መልካም ፍሬ ጠቀሜታው ግልጽ ሆኖ እንዲታይ ይሁን፡፡ እንዲህ ካደረግን ጾሙ እንደገና ተመልሶ ሲመጣ በደስታ እንቀበለዋለን፡፡ . . . ከጾም የሚገኘውን ጥቅም በትክክል የተረዳነውና በጾማችን ወቅት ያንን ጠቀሜታ የምንቀስመው ሆነን ቢሆን ኖሮ ጾሙ በየቀኑ እንዲመጣ በተመኘን ነበር፡፡ እንዲህ ሆኖም የጾሙን መምጣት መናፈቃችንንና ለጾም ያለንን ጉጉትና ናፍቆት መቀነስ የለብንም፣ እርሱን በማሰብ መፍራትና መጨነቅም አይኖርብንም፡፡"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 18፣ ቁ. 1-2)

- "በጣም ከዓቅማችሁ በላይ የሆኑ ምሳሌዎችን መከተል ምን ያደርግላችኋል? በምግባር ስትሰማሩ በዓቅማችሁ መጠን እንጂ ለራሳችሁ ታደርጓቸው ዘንድ የማይመከሩና ከዓቅማችሁ በላይ የሆኑ ነገሮችን ባታደርጉ መልካም ነው፡፡ በአፈጻጸም ደረጃ በወንጌል የተፈጸሙ ታሪኮች ዛሬ አፈጻጸማቸው ከዚያን ጊዜው ለየት ያሉ ነገሮች አሉና፡፡ ለአብነትም ክርስቶስ የጾመው ከመፈተኑ ጥቂት አስቀድሞ ነበር፣ እኛ ደግሞ ከትንሣኤ በፊት እንጾማለን፡፡ የጾሙን የጊዜ ርዝመት በተመለከተ ቀናቱ ያው [አርባ ቀናት] ናቸው፣ የጾሙን ዘመን በተመለከቶ ግን ልዩነት አለ፡፡ ለእኛ ጾሙ ከክርስቶስ ጋር ለመሞታችን አምሳል ነው፣ ጾማችን ራሳችንን ለትንሣኤው በዓል ለማዘጋጀት የምናነጻበትና የምንቀድስበት መሣሪያ ነው፡፡ እንዲሁም ጌታችን ለአርባ ቀናት በተከታታይ ጾመ፣ እርሱ እግዚአብሔር ነውና፡፡ እኛ ግን ስንጾም በተከታታይ ሳይሆን እስከ ተወሰነ ሰዓት እየጾምን እንደ ዓቅማችን መጠን እናደርጋለን፤ ምንም እንኳ አንዳንዶች ለጾም ካላቸው ልዩ ፍቅርና ቅንዓት የተነሣ ጾማቸውን ረዘም ላሉ ሰዓታትና ቀናት ቢያራዝሙም፡፡ እንደ ገናም ለደቀ መዛሙርቱ ምሥጢረ ቁርባንን የሰጣቸው በደርብ ፎቅ ላይና ከራት በኋላ፣ ከስቅለቱ አንድ ቀን አስቀድሞ ነበር፡፡ እኛ ግን ምሥጢረ ቁርባንን የምንፈጽመው በቤተ ክርስቲያን፣ ከምግብ በፊት እና ከትንሣኤ በኋላ ነው፡፡ እርሱ ያደረጋቸው ነገሮች ከእኛና እኛ ከምናደርጋቸው የተለዩ አይደሉም፤ ሆኖም ግን አፈጻጸማቸውን በተመለከተ ከጊዜና ከሁኔታዎች ጋር ፍጹም የሆነ ተመሳሳይነትና አንድነት የሌለባቸው ነገሮች አሉ፡፡ ሆኖም ለእኛ የተላለፉልን ማድረግና መፈጸም ለሚገባን ነገሮች አርአያና መሠረት እንዲሆኑን ነው፡፡[90]"

(ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ ትምህርት በእንተ ጥምቀት፣ ቁ. 30)

---

90 (. . . But matters which have to do with Him are neither abruptly separated from us, nor yet yoked together with those which concern us in point of time; but they were handed down to us just so far as to be patterns of what we should do, and then they carefully avoided an entire and exact resemblance.)

- "በመብልና በሆዳምነት የዛገውንና የደነዘውን ሰውነትህን በጾም ሳለው፣ ወልውለው፣ ሰንግለው፡፡ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚወስደውን መንገድ ያዝ፣ መንገዱ ጠባብና የማይመች ቢሆንም አንተ ግን በዚህ መንገድ ለመሄድ ምረጥና ተጓዝበት፡፡ ይህን ማድረግ የምትችለው እንዴት ነው? ሰውነትህን በማስገዛትና በቁጥጥር ስር እንዲውልና እንዲገዛ በማድረግ ነው፡፡ መብልና ሆዳምነት ትልቅ መሰናክል ናቸውና፡፡ በዚህ ሁሉ የሕይወት ተጋድሎ ጾም ታላቅ መሠረትና መምህር ሆኖ ያገለግለናልና፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 3፣ ቁ. 7)

ይኸው አባት ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ "ስለ ሆድህና ስለ በሽታህ ብዛት ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ እንጂ ወደ ፊት ውኃ ብቻ አትጠጣ" (1 ጢሞ. 5፥23) ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የጻፈለትን ምክር ጠቅሶ በዚያ ላይ ባስተማረው ትምህርት ላይ እንዲህ ይላል፡-

- ". . . እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ከመጀመሬ በፊት ስለ ጢሞቴዎስ የተጋድሎ ሕይወት እና ስለ ጳውሎስ አባታዊ የፍቅር አሳቢነቱና እንክብካቤው ትንሽ ነገር እንድል ፍቀዱልኝ፡ ፡ እንደዚያ ባሉ ብዙ አስቸጋሪና ፋታ በሚነሱ ሁኔታዎች ውስጥና ሩቅ ከሆነ ቦታ ላይ ሆኖ እያለ እንኳ ስለ ደቀ መዝሙሩ ጤና ያን ያህል እንደሚያስበውና እንደሚጨነቀው፣ እናም የጤናው ችግር የሚስተካከልበትን ነገር እንደ ጻፈው እንደዚህ አባት ያለ ርህሩኅና አሳቢ ማን አለ? የጢሞቴዎስን የተጋድሎ ሕይወት የሚያህልስ ምን አለ? ከትህርምቱ ጽናትና ከጾሙ ብዛት የተነሣ ሕመም ላይ እስከሚወድቅ ድረስ ድሎትንና ተድላ ሥጋን ናቀ፣ የላመና የጣመ ምግብ ያለበትን ማእድ ከእርሱ አራቀ፡፡ ጳውሎስ ያለው 'ትንሽ ወይን ጠጣ' ብቻ ሳይሆን አስቀድሞ 'ወደ ፊት ውኃ ብቻ አትጠጣ' ካለው በኋላ ነው ወይን እንዲጠጣ የመከረው፡፡ ይህ 'ወደ ፊት ውኃ ብቻ አትጠጣ' የሚለው አባባል እስከዚያ ጊዜ ድረስ የሚጠጣው ውኃ ብቻ የነበረ መሆኑንና ከዚህም ከትኅርምት ብዛት የተነሣ ሆዱ መታመሙን የሚያሳይ ነውና፡፡ . . ." (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት፣ ክፍለ ትምህርት 1፣ ቁ. 8)

- "እኔ አሁን የምናገረው እንዲሁ ብዙ ሰዎች ጾምን ስለሚሉት ጾም አይደለም፣ ስለ እውነተኛው ጾም ነው እንጂ፡፡ እውነተኛው ጾም ከሥጋ መከልከል ብቻ አይደለም፣ ከኃጢአትም መራቅ ነው እንጂ፡፡ ጾም የሚጠቅመውና ሊያስገኝልን የሚችለውን ጥቅም የሚያስገኘው ልንጾምበት እንደሚገባው ሕግ መሠረት ሆነን ስንጾመው ነውና፡፡ 'ደግሞም በጨዋታ የሚታገል ማንም ቢሆን እንደሚገባ አድርጎ ባይታገል የድሉን አክሊል አያገኝም' ተብሏልና፡፡ ስለዚህም በጾም ድካም ውስጥ ካለፍን በኋላ የጾማችንን ዋጋ እንዳናጣ እንዴትና በምን ዓይነት ሁኔታ መጾም እንዳለብን መረዳት ይገባናል፡፡ 2 ጢሞ. 2፥5 . . . ጾም መድኃኒት ነው፤ ሆኖም ግን መድኃኒት አጠቃቀሙን የሚያውቅ ሰው ይፈልጋል፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 3፣ ቁ. 8)

በጾም ወቅት እንኳን ሌላ ዓሣ እንኳ የማይበላ እንደ ነበር ታላቁ አባትና መምህር ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በትምህርቱ ውስጥ ገልጾት እናገኛለን፡-

- "ስንጾም እንደበታችንም ከማይገቡ ንግግሮችና ከነቀፋዎች ይጹም፡፡ እንዲህ ካላደረግን <u>ከሥጋና ከዓሣ መጾማችን</u> ብቻ ምን ይጠቅመናል?" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 3፣ ቁ. 12)

- "... ከሕዝቡ ሁሉ ጋር በጾም፣ በትጋት፣ እና በጸሎት የበረታንና የተጋን እንሆን ዘንድ ለአፍታም እንኳ መዘንጋት አይገባንም። በማያቋርጥ ሐዘንና ልቅሶ እና ዘወትር በሚሆን ጸሎት ጽሙዳን በመሆን የበረታንና የተጋን እንሁን። ጽንተን እንድንቆም የሚያደርጉን እነዚህ ናቸው። የሚጠብቁንና የሚጋርዱን መንፈሳዊ መከላከያዎቻችንና አምላካውያት መሣሪያዎቻችን እነዚህ ናቸው። (ቅዱስ ቆጵርያኖስ፡ ለሮማው ጳጳስ ለቆርኔሌዎስ ከጻፈው መልእክት፣ መልእክት 56፡ ቁ. 5)

- "ልዩ በምትሆን በአርባዕቱ ቀን በሚደረገው ትሩፋትና በጾም የሚገኝ በጎ መድኃኒት አለ፡ ፡" (ቅዱስ አቡሊዲስ፡ ሃይማኖተ አበው፡ ቁ. 22)

- "... ኢክርስቲያናዊና ተገቢ ያልሆነን ነገር እንደ ልማድ አድርገው የያዙ ሰዎች ከዚያ ወጥተው መልካሙን ነገር ልማድ ማድረግ ይቻላቸዋል። ለምሳሌ ከምግብ ተከልክሎ መቆየት ቀላል ባይሆንም ጾም ሲለመድ ግን ልማድ ይህን ከባዱን ነገር ለማድረግ የማያስቸግር ቀላል ያደርገዋል። ስለዚህም የጾሙ ጊዜ ሲመጣ ወይን ይጠጣ ዘንድ ወይም በጾም ጊዜ እንዳይበሉ ከተከለከሉ ምግቦች አንዱን ይበላ ዘንድ ሺህ ጊዜ እንኳ የሚመክረውና የሚዘበዝበው ሰው ቢኖር እንኳ ጾምን ልማድ ያደረገ ሰው በጾም የተከለከለውን ነገር ከሚነካ የሚመጣበትን መከራ ቢቀበል ይመርጣል። አንድ ጊዜ ልምድ ካደረግነው ከዚያ በኋላ ልናደርገው የማይገባውን ነገር ከሕሊናችን የተነሣ እንኳ እንጸየፈዋለን።" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 6፡ ቁ. 17)

- "በከመ ይቤ እግዚእነ በወንጌል ኢትዝግቡ መዝገበ ዘበምድር አንትሙሰ ዝግቡ ለክሙ መዝገበ ዘበሰማያት ኀበ ኢይበሊ ወኢይማስን ... ሡዐ ለእግዚአብሔር መሥዋዕተ ሰብሐት በጾም ወበጸሎት በኂሩት ወበተፋቅሮ ወበርትዕት ሃይማኖት ሡ. በጾም ወበጸሎት ዳንኤል ድኅነ እም አፈ አናብስት ሶስና ድኅነት እምእደ ረበናት ሡ. በጾም ወበጸሎት አበው ቀደምት ድኅኑ እመንሡት ዓደው እሞት ውስተ ሕይወት ሡ ... - ጌታችን በወንጌል እንደ ተናገረ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፤ የማይበላሽና የማይጠፋ ሰማያዊ መዝገብን ሰብስቡ (አከማቹ) እንጂ ... በጾምና በጸሎት፣ በደግነትና እርስ በርስ በመፋቀር፣ በእውነተኛ ሃይማኖት ሆነህ ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕትን ሠዋ፣ ... በጾምና በጸሎት ዳንኤል ከአንበሶች አፍ ዳነ፣ በጾምና በጸሎት ሶስና ከረበናት እጅ ዳነች፣ በጾምና በጸሎት የቀደሙ አባቶቻችን ከፈተና ዳኑ፣ በጾምና በጸሎት ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገሩ።" (ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘመዛግብት)

- "አኃውየ ንጹም ጾመ ወናፍቅር ቢጸነ ወንትፋቀር በበይናቲነ እስመ ከማሁ አዘዘነ አኃውየ ፈድፋደ ናፍቅር ቢጸነ እስመ ሙሴኒ በሲና ጾመ ወኢያሱኒ በይእቲ ጾም ድኅነ በገባዖን ፀሐየ አቀመ እ. ጾመ እግዚእነ በእንቲአነ አርአያሁ ከመ የሀበነ ... - ወንድሞቼ ሆይ፣ ጾምን እንጹም፣ ወንድሞቻችንንም እንውደድ፤ እርስ በርሳችንም እንፋቀር፣ እንዲህ እናደርግ ዘንድ አዝዞናልና ወንድሞቼ ሆይ፣ ወንድሞቻችንን አብዝተን እንውደድ፤ ሙሴ በሲና ጾሟልና፣ በዚህች ጾም ኢያሱ በገባዖን ዳነ፣ ፀሐይንም አቆመ፤ ጌታችንም ለጾም አርአያ ይሆነን ዘንድ ስለ እኛ ጾመ ..." (ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘምኩራብ)

- "... ሥርዐ ለነ ጾመ ለንስሐ እስመ ጾም በቋዒት ባቲ ክርስቶስ ጾመ በእንቲአነ አርዓያሁ ከመ የሀበነ - ለንስሐ ይሆነን ዘንድ ጾምን ሠራልን፣ ጾም ብዙ ጥቅም ያለባት ጠቃሚ ናትና፣ ክርስቶስም ምሳሌውን ይሰጠን ዘንድ ስለ እኛ ጾመ።" (ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘመጻጉዕ)

- "... ንጹም ጾመ ወናፍቅር ቢጸነ ንንግእ ወንትመጦ እሚነነ እምዝንቱ ኀብስት ርእዩ ዕበየ ወክብራ ለጾም ኃዘን ለአብዳን ወፍሥሐ ለጠቢባን ን. ብፁዕ ብእሲ ዘይትዔገሥ ለሥርዓትየ ይንግእ ትእዛዝየ እነ ሎቱ ሥምረቶ እገብር ን. እንተ ባቲ ተመጠወ ሙሴ ሕገ እግዚአብሔር ወባቲ ጾመ ለሊሁ መድኃኒነ ን. ወበይእቲ ጾም ኤልያስ ዐርገ ውስተ ሰማያት ወዳንኤል ድኅነ እም አፈ አናብስት ... - ጾምን እንጹም፣ ወንድሞቻችንንም እንውደድ፣ ከዚህ ኅብስትም እምነን [የክርስቶስ ሥጋ መሆኑን] እንቀበል፡፡ የጾምን ታላቅነትና ክብር ተመልከቱ፤ ጾም ለሰነፎች ሐዘን ስትሆን ለጥበበኞች ደግሞ ደስታ ናት፡፡ ትእዛዜን ግንዘብ ያደርግ ዘንድ ሥርዓቴን የሚታገግት ሰው ምስጉን ነው፤ እንዲህ ለሚያደርግ ሰው እኔም ፈቃዱን እፈጽምለታለሁ፡፡ ሙሴ የእግዚአብሔርን ሕግ የተቀበለው በእርሷ [በጾም] ነው፤ መድኃኒታችንም እንዲሁ ጾመ፡፡ በዚህች ጾም ኤልያስ ወደ ሰማያት ዐረገ፤ ዳንኤልም ከአንበሶች አፍ ዳነ ..." (ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘገብር ኄር)
- "ጾም ልጓም ፍሬሃ ጥዑም ትሁተ ኢናምስላ ለጾም - ጾም ልጓም ናት፣ ፍሬዋም ጣፋጭ ነው፤ ስለዚህም ጾምን ታናሽ (ቀላል) አናስመስላት፡፡" (ቅዱስ ያሬድ፣ ጾመ ድጓ ዘቅድስት፣ ዘረቡዕ)
- "እስመ ጾም ዐቢይ በቁዔት ባቲ ታግዕዘከሙ ነፍስክሙ እምኃጢአት ትሜህሮሙ ለወራዙት ጽሙና ዛቲ ጾም ጾም ቅድስት ትፈሪ ሰላመ ወተዓሥዮሙ ትፍሥሕተ - ጾም ታላቅ ጠቀሜታ አላት፣ ነፍሳችሁን ከኃጢአት ነጻ ታወጣታለች፤ ለወጣቶችም ዕርጋታንና ራስን መግዛትን ታስተምራቸዋለች፡፡ ይህች ጾም ቅድስት ናት፤ ሰላምን ታፈራለች፤ ለሚያደርጓት ሰው ደስታን ትሰጠዋለች፡፡" (ቅዱስ ያሬድ፣ ጾመ ድጓ ዘቅድስት፣ ዘሐሙስ)
- "እስመ ዛቲ ጾም ወሀበቶ ሞገሰ ለሙሴ ብእሴ እግዚአብሔር - ጾም ለእግዚአብሔር ሰው ለሙሴ ሞገስን ሰጠችው፡፡" (ቅዱስ ያሬድ፣ ጾመ ድጓ ዘቅድስት፣ ዘሐሙስ)

ቅዱሳን አበው ሊቃውንት ቀደምት ስለ ጾም ያስተማሩትን ትምህርት ማር ይስሐቅ ጾምን በተመለከተ ግሩም በሆነ ሁኔታ እንዲህ ሲል በገለጸው እናጠቃልል፡-

- "እስመ ጾም ይትባየፃ ለኩሉ ምግባር ትሩፍ - ጾም የትሩፋትን ሥራ ሁሉ ይስማማዋልና
  ወጥንት ለኩሉ ገድል - የሥራ መጀመሪያ ናት
  አክሊሎሙ ለጽሙዳን - የጽሙዳን ክብራቸው ናት
  ወስኖሙ ለድንግልና ወለቅድስና - የድንግልናና የንጽሕና ጌጣቸው ናት
  ወጥንታ ለፍኖት መሢሐዊት - የወንጌል ሥራ መጀመሪያ ናት
  እማ ለጸሎት - የጸሎት እናት ናት
  ወነቅዓ ለአንብዕ - የዕንባ መገኛ ናት
  ወመንቅሒት ላዕለ ኩሉ ገድል ውዱስ - ለበጎ ሥራ ሁሉ ታነቃቃለች ...
  ወዘአስተሐቀረ ኪያሃ ናሁ አሰሰለ እምላዕለ ነፍሱ ኩሎ ሠናያተ - ጾምን የናቀ ያቃለለ በጎውን ነገር ሁሉ ከራሱ አራቀ
  እስመ ዛቲ ትእዛዝ ተወድየት ውስተ ጠባይዒነ እምትካት ለዓቂብ ወለተጸውኖ - እኛ እሷን ልንጠብቃት እሷ እኛን ልትጠብቀን ይህች ጾም ከቀድሞ ጀምሮ በባሕርያችን ታዝዛለችና (አዳምን ዕፀ በለስ አትብላ ባለው ጊዜ)
  ወዝየ ወድቀ ጥንተ ተልሕኮትነ - ባለመጾም የባሕርያችን ጥንት የሚሆን አዳም ድል ሆነ ወበእንተ ዝንቱ እምኀበ መጽአ ኀትል ቀዳማዊ እምኔሁ ባሕቲቱ መጽኡ መስተጋድላን ኀበ ፈሪሀ እግዚአብሔር ሎቱ ስብሐት - ስለ በላ ጥፋት (ኃጉል) ካመጣበት ከሙብል

ጀምረው ነቢያት ድል እየነሡ ወደ ፈሪሃ እግዚአብሔር መጡ፣ በመብል ጥፋት ከመምጣቱ የተነሣ ወደ ጾም መጡ፡፡

ሶበ ተደለው ለዓቂበ ትእዛዛቲሁ - ሕጉን ሊጠብቁ በተዘጋጁ ጊዜ

ወመድኅኒነ ሎቱ ስብሐት እመ አስተርአየ በዓለም በውስተ ዮርዳኖስ በዝየ ወጠነ - ክብር ይግባውና ጌታም በዚህ ዓለም በዮርዳኖስ በተገለጠ ጊዜ ሥራውን በጾም ጀመረ፡፡

ወኩሎሙ እለ ወጽኡ ለተሊዎ ዓሡሩ በዛቲ አርአያ ረበዩ ቀንተ ገድሎሙ - በሥራ እርሱን ለመምሰል የወጡ ሁሉ ሥራቸውን በጾም ጀመሩ፡፡

እስመ ውእቱ ንዋየ ሐቅል ዘተገብረ እምእግዚአብሔር ልዑል - ከልዑል እግዚአብሔር የተሰጉደ ማለት የተሰጠ ጋሻ ነውና፡፡

ወዘአስተሐቀረ ኪያሁ በእፎኬ ዘኢየሐምይዎ - ጾምን የናቀን ያቃለለን ሰው እንደምን አይነቅፉት!

እመሰኬ ሠራዒ ሕግ ናሁ ጾመ መኑ እንከ እምእለ ያበድሩ ዐቂበ ሕግ ዘኢይፈቅዳ ለጾም - ሕግን የሠራ ያዘዘ ጌታ ከጾመ ሕግን መጠበቅ ከሚወዱ ሰዎች ወገን ጾምን የማይወድ ማን ነው?

. . .

ወእምከመ ርእዮ መስተቃርን ጸራዊ እኩይ ለዝንቱ ንዋየ ሐቅል ኅዕለ ኢሐዱ እምሰብእ ይፈርህ ሶቤሃ - ክፉ ባላጋራ ሰይጣን ከሰው አንዱን ጾም ሲጾም ያየው እንደሆን (ባየው ጊዜ) ይፈራል፡፡

ወይዜክሮ ፍጡነ ለጉፋሬሁ ወለተመውዖቱ ውስተ ገዳም እምኀበ መድኃኒነ ሎቱ ስብሐት - ክብር ይግባውና ጌታ በገዳም ያሳፈረውን ማፈሩን፣ የነሣውን ድል መነሣቱን ያስበዋል፡፡

ወትነድድ ኃይሉ በንዋየ ሐቅል ዘተውህበ ለነ እምኀበ ሊቀ ሠራዊትነ - የካህናት አለቃ ከሚሆን ከጌታ በተሰጠን በጾም ኃይሉ ትደክማለች፡፡"

(ማር ይስሐቅ፣ አንቀጽ ራብዕ፣ ምዕራፍ 6)

እንግዲህ ጾም በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በቅዱሳን አባቶቻችን ትምህርት ይህን ያህል የተብለለት ታላቅ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው፡፡ አባቶቻችን ጾምን "ለአዳም የተሰጠው ጥንታዊው ሕግ"፣ "ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰማያዊ ዋጋ የምናገኝበት"፣ "በልቅሶ ተዘርቶ በደስታ የሚታጨድበት"፣ "ጸንተን እንድንቆም የሚያደርገን፣ ከክፉ የሚጠብቀንና የሚጋርደን መንፈሳዊ መከላከያችንና አምላካዊ መሣሪያችን"፣ "መድኃኒት"፣ "ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰማያዊ ዋጋ የምናገኝበት"፣ ወዘተ እያሉ ገልጸውታል፡፡ ስለዚህ ምናልባት በተለያየ ምክንያት መጾም ያልቻለ ሰው ቢኖር መፍትሔው ጾምን መንቀፍና መተቸት አይደለም፡፡ እንዲህ ማድረጉ ሁለት በደል ይሆንበታል፡፡ አንደኛው መጾም ሲገባው ባለመጾሙ ሲሆን ሁለተኛውና የባሰው ደግሞ እግዚአብሔር ለጥቅማችን የሰጠንን ጾም በመንቀፉ ነው፡፡ እኛ ስለ ነቀፍነንና ስላልተቀበልነው የእግዚአብሔር ሐሳብ አይለወጥምና፡፡ ስለዚህ ቢቻለን መጾም፣ ከከበደን ደግሞ እንዲያስችለን እርሱን መለመንና ባለመቻላችን ማዘን ይገባል እንጂ ከዚያ አልፎ መሄድ መጠንን አለማወቅና በኃጢአት ላይ ኃጢአት መጨመር ስለሆነ መቼም ቢሆን አይጠቅምም፡፡

ከዚህም ጋር አሁን አሁን አንዳንድ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ጾምን "ዓባይን ገድበን እንዳንጠቀም ግብጻውያን የጫኑብን ሸክም ነው፣ በግብጻውያን የተጣለብን የተንኮል መሣሪያ ነው" ሲሉ ከተደመጡ ውሎ አድሯል፡፡ እንግዲህ ይህ አስተሳሰብ ቢያንስ ሁለት መሠረታዊ ስህተቶች ያሉበት የፈጠራ አስተያየት ነው፡፡ <u>በመጀመሪያ</u> ጾም ግብጻውያን በኢትዮጵያውያን ላይ የጫኑት ሸክም ወይም የወሰኑት ውሳኔ ሳይሆን ከላይ እንደ ተመለከትነው ከጥንቱ ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ በእግዚአብሔር

ብሚያምኑ ወገኖች ዘንድ የነበረ የአምልኮ መግሪያ ነበር፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን ደግሞ ግብጻውያን እንኳን በሌላው ላይ ጾምን ሲጭኑ ይቅርና ራሳቸውም ገና በአምልኮ ጣዖት ወድቀው በግብረ ኃጢአት ተይዘው የነበሩበት ዘመን ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ግን በዘመኑ አሪትም እግዚአብሔርብን ታመልክ የበረች ሀገር ነበረች፡፡ ለዚህም ምስክሩ ሰው ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ለምሳሌም ሙሴ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ከማያውቁና ከማያመልኩ ሰዎች ወገን ጋር እንዳይጋቡ የከለከለ ሲሆን እርሱ ያገባት ሚስቱ ግን ኢትዮጵያዊት ነበረች፤ ምክንያቱም ኢትዮጵያውያን በዘመኑ ሕገ ልቡናም እግዚአብሔርን ያመልኩ የነበሩ ሕዝቦች ናቸውና፡፡ ዘኁ. 12 ይህን ያልተረዱት የሙሴ ወንድም አሮንና እኅቱ ማርያም ሙሴን በመንቀፋቸው እግዚአብሔር በጽኑ ሁኔታ ገሥጿቸዋል፡፡ እንደዚሁም ራሱ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን "የእስራኤል ልጆች ሆይ፤ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?" በማለት ኢትዮጵያውያንን አብነት አድርጎ ተናግሯቸዋል፡፡ አሞ. 9፡7

በሐዲስ ኪዳንም ኢትዮጵያ ክርስትናን የተቀበለችው በትንቢቱና በተስፋው መሠረት ስትጠብቀው የነበረ በመሆኑ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በሐዋርያው በቅዱስ ፊልጶስ መምህርነት በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አማካይነት ነው እንጂ ክርስትናን ከግብጽ አልተቀበለችም፡፡ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ በሐዋርያት ሥራ በምዕራፍ ስምንት ላይ በግልጽ ተጽፎ የሚገኝ እውነት ነው፡፡ ስለዚህ የግብጽ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊትና ቅድስት የሆነችው የአንዲቷ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አካላት እንደ መሆናቸው ሁለቱም በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትምህርትና በሐዋርያዊ ትውፊት መሠረት ክርስቲያናዊ ጾምን ይጾማሉ እንጂ አንዱ በሌላው ላይ ጫኑ የሚባል ነገር የለም።

_ሁለተኛ_ ደግሞ ክርስቲያናዊ ጾም ያለው በኢትዮጵያና በግብጽ ክርስቲያኖች ዘንድ ብቻ አይደለም፡፡ ጾም በሌሎች ኦሬንታልና ኦርቶዶክስ እና በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትም ያለ ክርስቲያናዊ ሕይወት ነው፡፡ ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ በሌሎች ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ያሉትን አጽዋማት እንመልከት፡፡

ሀ) ኦሬንታል ኦርቶዶክስ[91] አብያተ ክርስቲያናት (የኢትዮጵያ፣ የግብጽ፣ የኤርትራ፣ የሶርያ፣ የአርመን እና የሕንድ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት)[92]

- ጾመ ነቢያት
- ዐቢይ ጾም
- ረቡዕ እና ዓርብ
- ጾመ ገሃድ
- ጾመ ሐዋርያት
- ጾመ ማርያም (ጾመ ፍልሰታ)
- ጾመ ነነዌ

[91] ኦሬንታል ኦርቶዶክስ (Oriental Orthodox) አብያተ ክርስቲያናት የሚባሉት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ ከላይ የተዘረዘሩት ሲሆኑ የኬልቄዶንን ጉባኤ የማይቀበሉት ናቸው። የሚቀበሏቸው ዓለም አቀፋዊ ጉባኤያት የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ (የኒቅያ፣ የቁስጥንጥንያ እና የኤፌሶን ጉባኤ) ብቻ ናቸው። የምሥራቅ ኦርቶዶክስ (Eastern Orthodox) አብያተ ክርስቲያናት የሚባሉት ደግሞ የኬልቄዶንን ጉባኤ የሚቀበሉ ሆነው ከምዕራቡ ክፍል የሮማ ካቶሊክ በ1054 ዓ. ም. የተለያዩ ናቸው።

[92] የአንዳንዶቹ አጽዋማት የሚጀምሩበት ጊዜና አጠቃላይ የሚሸፍኗቸው የቀናት ብዛት አልፎ አልፎ ሊለያይ ይችላል።

ለ) የምሥራቅ ኦርቶዶክስ (የግሪክ፣ የሩሲያ፣ ሰርቢያ፣ ወዘተ) ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት[93]

- ዐቢይ ጾም
- ጾመ ነቢያት
- ረቡዕ እና ዓርብ
- ጾመ ማርያም (ጾመ ፍልሰታ)
- ጾመ ሐዋርያት
- የጥምቀት ዋዜማ (ገሃድ)
- የቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ አንገቱ የተሰየፈበት ዕለት
- በዓለ ቅዱስ መስቀል

ማንም ሰው ማየት እንደሚችለው ከዚህ ሁሉ መረዳት የሚቻለው ጾም በኢትዮጵያ እና በግብጽ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ሐዋርያዊ ትውፊት ባላቸው በኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ ያለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስቲያናዊ ሕይወት መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ጾም በግብጻውያን የተጫነብን ሸክም ሳይሆን መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠንና አባቶቻችን ቅዱሳን ሐዋርያት ተቀብለው ኖረውበትና ተጠቅመውበት ያወረሱን ክርስቲያናዊ መሣሪያና ሀብት ነው፡፡

## 4.2 ምጽዋት

የሐሳዊ መሢሕ መንገድ ጠራጊነታቸውን ቃላቸውና ተግባራቸው የሚያጋልጥባቸው ወገኖች የሚቃወሙትና ዋጋ ቢስ የሚያደርጉት ሌላው ነገር ምጽዋት ነው፡፡ አሁንም እንደ ሌሎቹ ጉዳዮች ሁሉ ምጽዋትንም መጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል፣ በመቀጠልም በአባቶቻችን ትምህርት የተጻፈውን በመመልከት የእነዚህን ተቃዋሚዎች ትምህርት እንመዝነዋለን፡፡

### 4.2.1 ምጽዋት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

ምጽዋት አንድ ሰው ፍቅረ እግዚአብሔርን መሠረት በማድረግ ለሌሎች ሰዎች የሚያደርገውን መልካም ነገር ሁሉ የሚያጠቃልል ሰፊ ነገር ነው፡፡ አንድ ሰው ለተቸገረና በሐዘን ላይ ላለ ወገኑ በመጀመሪያ የሚያደርገው ምጽዋት ችግሩንና ሐዘኑን በመንፈስ መጋራትና አብሮ መካፈል ነው፡፡ "ከእነርሱ ጋር እንደ ታሰረ ሆናችሁ እስረኞችን አስቡ፣ የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ" በማለት የተነገረው ቃል ይህን ሁኔታ የሚስረዳ ነው፡፡ ዕብ. 13፡3 ስለዚህ ምጽዋት ሲባል የግድ ገንዘብ መስጠትን ብቻ ሳይሆን ከሁሉም በላይ ልቡናን መስጠትንና በችግራቸው አብሮ መካፈልን የሚያካትት፣ ከዚያ በመነሣትም የተቻለውን ነገር ሁሉ እስከ ማድረግ የሚዘልቅ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለችግረኞች ስለሚያስቡና መልካም ስለሚያደርጉ ሰዎች ምን እንደሚያገኙና እርሱም ምን እንደሚያደርግላቸው ሲናገር እንዲህ ይላል፦

> "ብፁዕ ዘይሌቡ ላዕለ ነዳይ ወምስኪን እምዕለት እኪት ያድኅኖ እግዚአብሔር እግዚአብሔር የዐቅቦ ወያሐይዎ ወያበጽዖ ዲበ ምድር ወይረድኦ ውስተ ዐራተ ሕማሙ ወኢያበውኦ ውስተ እደ ጸላኢሁ - ለችግረኛና ለምስኪን የሚያስብ ምስጉን ነው፣ እግዚአብሔር ከክፉ ቀን ያድነዋል። እግዚአብሔር ይጠብቀዋል፤ ሕያውም ያደርገዋል፤ በምድር ላይም ያስመሰግነዋል፤ በጠላቶቹም እጅ አያሳልፈውም። እግዚአብሔር በደዌው አልጋ ላለ ይረዳዋል፤ መኝታውን ሁሉ በበሽታው ጊዜ ያንጥፍለታል።" መዝ. 40፡1-3

[93] Kallistos Ware, The Orthodox Church, New Edition, New York: Penguin Books USA, 1997

ነቢዩ ዳንኤል በዘመኑ ገናና የነበረው የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ያየውን ራእይ ከተረጎመለት በኋላ ምን እንደሚደርስበት ሲነግረው እንዲህ አለው፡-

> ልቡሉም በሰዎች መንግሥት ላይ እንዲሠለጥን፣ ለሚወድደውም እንዲሰጠው እስኪታውቅ ድረስ ከሰዎች ተለይተህ ትሰደዳለህ፤ መኖሪያህም ከምድር አራዊት ጋር ይሆናል፤ እንደ በሬም ሣር ትበላ ዘንድ ትገደዳለህ፤ በሰማይም ጠል ትረሰርሳለህ፤ ሰባት ዘመናትም ያልፉብሃል። ዳን. 4፡25

ከእግዚአብሔር ዘንድ የታዘዘበትን ያን ከባድ ቅጣት - ከሰው ሁሉ ተለይቶ ከቤተ መንግሥቱ ወጥቶ እንደ በሬ ሣር እየበላ ከምድር አራዊት ጋር ሰባት ዓመት እንዲኖር የተፈረደበት መሆኑን - ከነገረው በኋላ ከዚያ ፍርድ የሚድንበትን መንገድ ሲያመለክተው እንዲህ አለው፡- *"ንጉሥ ሆይ፤ ስለዚህ ምናልባት የደኅንነትህ ዘመን ይረዝም እንደ ሆነ ምክሬ ደስ ያሰኝህ፣ ኃጢአትህንም በጽድቅ በደልህንም ለድሆች በመመጽወት አስቀር።"* ዳን. 4፡27 እንግዲህ ያን ያህል ከባድ ፍርድ እንዲፈረድበት ያደረገውን የናቡከደነፆርን ኃጢአትና በደል ሊያስቀር እስከሚችል ድረስ የሆነው ምጽዋት ምን ያህል ኃይል ያለውና ገናና ቢሆን ይሆን?

እግዚአብሔር ለተራበ ለሚያበላና ለተቸገረ ለሚሰጥ ምን እንደሚያደርግለትና ምን እንደሚያገኝ ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

> እንጀራህንስ ለተራበ ትቈርስ ዘንድ፣ ስደተኞቹን ድሆች ወደ ቤትህ ታገባ ዘንድ፣ የተራቈተውንስ ብታይ ታለብሰው ዘንድ፣ ከሥጋ ዘመድህ እንዳትሸሸግ አይደለምን? የዚያን ጊዜ ብርሃንህ እንደ ንጋት ይበራል፤ ፈውስህም ፈጥኖ ይበቅላል፤ ጽድቅህም በፊትህ ይሄዳል፤ የእግዚአብሔርም ክብር በኋላህ ሆኖ ይጠብቅሃል። የዚያን ጊዜ ትጠራለህ፣ እግዚአብሔርም ይሰማሃል፤ ትጮኻለህ እርሱም፡- እነሆኝ ይላል። ከመካከልህ ቀንበርን ብታርቅ፣ ጣትህንም መጥቀስ ብትተው፣ ባታንጐራጕርም፣ ነፍስህንም ለተራብ ብታፈስስ፣ የተጨነቀውንም ነፍስ ብታጠግብ ብርሃንህ በጨለማ ይወጣል፤ ጨለማህም እንደ ቀትር ይሆናል። እግዚአብሔርም ሁል ጊዜ ይመራሃል፤ ነፍስህንም በመልካም ነገር ያጠግባል፤ አጥንትህንም ያጠናል፤ አንተም እንደሚጠጣ ገነት፣ ውኃውም እንደማያቋርጥ ምንጭ ትሆናለህ። ኢሳ. 58፡7-11

በአንጻሩ ለድሆችና ለችግረኞች አለማሰብና ማድረግ የሚገባውን ነገር አለማድረግ ደግሞ ኃጢአት መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ደጋግሞ ይናገራል፡፡ ለምሳሌም "ሰባተኛው ዓመት የዕዳ ምሕረት ዓመት ቀርቧል ብለህ ክፉ አሳብ በልብህ እንዳታስብ፤ ለድሀውም ወንድምህ አንዳች የማትሰጥ እንዳትሆን፣ ዓይንህም በእርሱ ላይ ክፉ እንዳይሆን፣ እርሱም ወደ እግዚአብሔር በአንተ ላይ እንዳይጮህ፤ ኃጢአትም እንዳይሆንብህ ተጠንቀቅ" በማለት ያስጠነቅቃል፡፡ ዘዳ. 15፡9 ለችግረኛ በማሰብ መልካም ስለሚያደርጉት ደግሞ እንዲህ ይላል፡- "በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት እንዲህ በል፡- የተቀደሰውን ነገር ከቤቴ ወስጄ ለሌዋዊው ለመጻተኛውም ለድሀ አደጉም፣ ለመበለቲቱም እንዳዘዝኸኝ ትእዛዝ ሁሉ ሰጥቻለሁ፤ ትእዛዝህን ምንም አላፈረስሁም፣ አልረሳሁምም፡፡" ዘዳ. 26፡13

ለተቸገሩ ለድሆች ምጽዋት መስጠት በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ ያለው ስለ መሆኑም እንዲህ ይላል፡- "ለድሀ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል፤ በጎነቱንም መልሶ ይከፍለዋል።" ምሳ. 19፡17 ለድሀ የሚራራ እንደሚባረክም "ርኅሩህ የተባረከ ይሆናል፣ ከእንጀራው ለድሀ ሰጥቷልና" ይላል፡፡ ምሳ. 22፡9

ምጽዋት የእውነተኛ አምልኮ አካል መሆኑንም ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ እንዲህ ሲል ይናገራል፡- "ንጹሕ የሆነ፣ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፤ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ፣ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነቱን መጠበቅ ነው።" ያዕ. 1፡27 እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ "ነገር ግን መልካም ማድረግን፣ ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና" በማለት ምጽዋት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት መሆኑን ይናገራል፡፡ ዕብ. 13፡16

ምጽዋት ታላቅ የሆነ ሰማያዊ ዋጋ ያለው መሆኑንም ራሱ ባለቤቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማይታበል ቃሉ "ያላችሁን ሸጡ፥ ምጽዋትም ስጡ፤ ሌባ በማይቀርብበት ብልም በማያጠፋበት በሰማያት የማያልቅ መዝገብ የሚሆኑትን የማያረጁትንም ኮረጆዎች ለራሳችሁ አድርጉ" በማለት አስተምሯል፡፡ ሉቃ. 12፡33 እንዲሁም ጌታችን ወደ እርሱ መጥቶ ስለ ዘለዓለማዊ ሕይወት ጉዳይ የጠየቀውን ጎልማሳ ባለ ጸጋ ሕግጋትን ስለ መጠበቅ ሲነግረው ወጣቱ ባለ ጸጋ "ይህንማ ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄያለሁ፤ ደግሞስ የሚጐድለኝ ምንድር ነው?" ብሎ በጠየቀው ጊዜ እንዲህ ነበር ያለው፡- "ኢየሱስም፦ ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፤ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፤ መጥተህም ተከተለኝ አለው።" ማቴ. 19፡16-21

እንዲሁም ጌታችን መሠረታዊ ትምህርት ካስተማረባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ምጽዋት ነበር፡፡ በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ ስድስት ላይ በመጀመሪያ ያስተማረው ምጽዋትን በተመለከተ ነበር፤ እንዲህ በማለት፡-

> ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤ ያለዚያ በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም። እንግዲህ ምጽዋት ስታደርግ ግብዞች በሰው ዘንድ ሊከበሩ በምኩራብ በመንገድም እንደሚያደርጉ በፊትህ መለከት አታስነፋ፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ፤ <u>በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል</u>። ማቴ. 6፡1-4

ምጽዋት ዋጋ የሌለው ቢሆን ኖሮ ለውዳሴ ከንቱ ብለው በሰው ፊት የሚያደርጉትን ሰዎች ከእርሱ ዘንድ ያገኙ የነበረውን ዋጋ ማጣታቸውን በመግለጽ "ዋጋቸውን ተቀብለዋል" ለምን አለ? በስውር የሚያደርጉት ዋጋ የሌላቸው ከሆነስ ለምን ስለ አፈጻጸሙ ጥብቅ የሆነ ትምህርትን አስተማረ? ራሳችሁን "ተሐድሶ" ብላችሁ የምትጠሩ ወገኖቻችን ሆይ፥ እናንተ "የጸደቀ ዛፍ ፍሬ እንደሚያፈራው ሁሉ ያመነም ሰው የምግባር ፍሬ የግድ አብሮት ይከተለዋል" እንደምትሉት ቢሆን ኖሮ ስለ ምጽዋት ለምን ማስተማር አስፈለገው? ምክንያቱም እንደ እናንተ አባባል አንድ ሰው ካመነ ምጽዋት መመጽወትም የግድ አብሮት ይከተለዋል፤ በአንድ በኩል ምጽዋት ዋጋ የሌለው ነው በማለት፥ በሌላ በኩል ደግሞ ያውም ቢሆን ላመነ ሰው የግድ ተከትሎት የሚመጣ ፍሬ ነው እንጂ ጥረትና ጥንቃቄ አያስፈልገውም እያላችሁ ሰዎች በጌታችን የተሰጠውን ትምህርት በንጹሕ ልባቸው ተቀብለው በምጽዋት አማካይነት ዋጋ እንደሚገኝ በእነዚህ ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት የተነገረውን መልካም ነገር እንዳያገኙ መሰናክል መሆን ምን ይጠቅማችኋል? የራሳችሁ መጎዳት አንሶ ሌሎችን ይዛችሁ ለመጥፋት ይህን ያህል ድካም መድከማችሁ በእውነቱ ያሳዝናል፡፡

ምጽዋት ታላቅ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ቅንነቱና ማስተዋሉ ላለው ሰው በቆርኔሌዎስ ሕይወት ብቻ እንኳን ማየትና መረዳት ይቻላል፡፡ ስለ ቆርኔሌዎስ ሲናገር መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

> በቂሣርያም ኢጣሊቄ ለሚሉት ጭፍራ የመቶ አለቃ የሆነ ቆርኔሌዎስ የሚሉት አንድ ሰው ነበረ። እርሱም ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር እግዚአብሔርን የሚያመልክና የሚፈራ፥ ለሕዝብም እጅግ ምጽዋት የሚያደርግ ወደ እግዚአብሔርም ሁል ጊዜ የሚጸልይ ነበረ። ከቀኑም ዘጠኝ ሰዓት ያህል፦ ቆርኔሌዎስ ሆይ የሚለው የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ ሲገባ በራእይ በግልጥ አየው። እርሱም ትኵር ብሎ ሲመለከተው ደንግጦ፦ ጌታ ሆይ፥ ምንድር ነው? አለ። መልአኩም አለው፦ ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን አረገ። አሁንም ወደ ኢዮጴ ሰዎችን ልከህ ጴጥሮስ የሚባለውን ስምዖንን አስመጣ።" የሐዋ. 10፡1-5

ቆርኔሌዎስ አሕዛብ የነበረ ቢሆንም፥ ያደረገው ጸሎትና ምጽዋት በእግዚአብሔር ፊት መድረሱንና ከንቱ ሆኖ አለመቅረቱን ከእግዚአብሔር የተላከ መልአክ ነገረው፡፡ ከዚያም ለመዳን የሚያስፈልገውን ነገር የሚነግረውንና ምሥጢራትን የሚፈጽምለትን ቅዱስ ጴጥሮስን ልኮ እንዲያስጠራ መንገዱን አሳየው፡፡ የምጽዋት ጥቅም እንዲህ አሕዛብ የነበሩትን እንኳ በቅን ልቡናና እውነትን በመፈለግ እስካደረጉት ድረስ ወደ እውነትና ወደ መዳን መንገድ የሚመራ ታላቅ ነገር ነው፡፡

## 4.2.2 ምጽዋት በስበው ትምህርት

❖ "መልካም ማድረግ የምትችሉበት ሁኔታ ላይ ስትሆኑ ለሌላ ጊዜ አትግፉት (አታሸጋግሩት)፣ ምክንያቱም ምጽዋት ከሞት ታወጣለችና፡፡" (ቅዱስ ፖሊካርፐስ፣ መልእክት ኀበ ሰብአ ፊልጵስዩስ፣ ምዕራፍ 10)

"ቅዱስ ጳውሎስ በመከራ ላይ ሳለ የፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች ያደረጉለትን መልካም ስጦታ በተመለከተ ሲናገር ለእግዚአብሔር የቀረበ መሥዋዕት ነው ብሎታል፤ እንዲህ ሲል፡- 'በተሰሎንቄ እንኳ ሳለሁ አንድ ጊዜና ሁለት ጊዜ ያስፈለገኝን ለዳችሁልኝ ነበርና። . . . የመዓዛ ሽታና የተወደደ መሥዋዕት የሚሆነውን . . . ለእግዚአብሔርም ደስ የሚያሰኘውን ስጦታችሁን ከአፍሮዲጡ ተቀብዬ ተሞልቼዋለሁ። አምላኬም እንደ ባለጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል።' ፊል. 4፡16-19 አንድ ሰው ለድሀ ባዘንና መልካም ባደረገ ቁጥር ለእግዚአብሔር ማበደሩ ነው፣ ለታናሾች የሚሰጥ ሰውም የሰጠው ለእግዚአብሔር ነው፡፡ እንዲህ ያለው መሥዋዕት ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መዓዛው የተወደደ መንፈሳዊ መሥዋዕት ነው፡፡" (ሰማዕቱ ቅዱስ ቆጵርያኖስ፣ ትምህርት በእንተ ጸሎተ እግዚእነ፣ ቁ. 33)

❖ "እግዚአብሔር ብዙ መንገዶችን የከፈተልን ስለዚህ ነው፡፡ 'በአንድነትም ሆነን እንፋረድ፣ ትጸድቅም ዘንድ ኃጢአትህን ተናገር' ይላልና። ኢሳ. 43፡26 እንደ ገናም 'ኃጢአቴን ለአንተ አስታውቅሁ፣ በደሌንም አልሸፈንሁም፣ ለእግዚአብሔር መተላለፌን እነግራለሁ አልሁ፡፡ አንተም የልቤን ኃጢአት ተውህልኝ' ይላል። መዝ. 31፡5 ኃጢአትን ሳያቋርጡ ሁል ጊዜ ማሰብና ራስን መውቀስ ብዛታቸውንና ዕዳነታቸውን ለመቀነስ ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ አለውና፡፡ ከዚህም የበለጠ ደግሞ ሌላ መንገድ አለ፤ እርሱም በእኛ ላይ በደል ባደረሱብን ሰዎች በአንዳቸውም እንኳ ቂም አለመያዝ፣ የበደሉንን ሁሉ በደላቸውን ይቅር ማለት ነው፡፡ ሌላ ሦስተኛ መንገድ ማወቅ ትፈልጋለህ? ነቢዩ ዳንኤል እንዲህ ሲል ስማው፡- "ንጉሥ ሆይ፣ ኃጢአትህንም በጽድቅ፣ በደልህንም ለድሆች በመመጽወት አስቀር።" ዳን. 4፡27 እንደዚሁም ጾምንም ለሌሎች ከመራራትና ከምጽዋት ጋር ካደረግነው ከሠራነው ኃጢአት ሥርየትንና መጽናናትን እንድናገኝ፣ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቁጣ በማብረድ ረገድ ያለው ጠቀሜታ በጣም ታላቅ ነው፡፡ 1 ጢሞ. 2፡1 'ውኃ የሚንበለበለውን እሳት እንደሚያጠፋው፣ ኃጢአትም በምጽዋት ይሠረያል፡፡'" ሲራ. 3፡29 (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌል ዮሐንስ፣ ክፍለ ትምህርት 7፣ 2)

❖ "ከጥምቀት በኋላ የሚሠሩ ኃጢአቶችን ማስወገጃና ማጠቢያ መንገድ ማግኘት መቻል ምን ያህል ታላቅ ነገር መሆኑን ልብ በል! ምጽዋት መስጠት ምን ያህል ታላቅ ዋጋ እንዳለው አስተውል፡፡ እርሱ ምጽዋት ስጡ ባይለን ኖሮ፣ 'ገንዘብ መስጠትና ከሚመጣው ክፉ ነገር በምጽዋት አማካይነት መዳን የሚቻል ቢሆን ኖሮ እንዴት ጥሩ ነበር' የሚሉ ስንት ሰዎች በኖሩ ነበር! ነገር ግን አሁን እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ቸርነት የተነሣ በምጽዋት አማካይነት ከሚመጣው ክፉ ነገር መዳን የምንችልበትን ዕድል ስለ ሰጠንና ይህን የሚቻል ስላደረገልን እንደገና ብዙዎች ተመልሰው ግድ የለሾች ሆነው ይታያሉ፡፡ አይ፣ እኔ ምጽዋት እሰጣለሁ እኮ ትል ይሆናል፡፡ ይህ ምንድን ነው? ሆኖም ግን መቀነቷን ፈትታ ሁለት ሣንቲሞችን እንደ ሰጠችው ሴት ያህል አልሰጠህም፡፡ እረ የእርሷን ግማሽ ያህል፣ እርሷ ከሰጠችው ጥቂቱን ያህል እንኳ አልሰጠህም፡፡ ካለህ ገንዘብ ብዙውን ክፍል ጥቅም በሌለው ነገር ላይ ታባክነዋለህና፡፡ በመጠጥ፣ በመባልዕት፣ ቀጥ ባጣ አባካኝነት እያዋልክ ራስህን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም እንደ አንተ እንዲያባክኑና ገንዘባቸውን በማይጠቅማቸውና ተገቢ ባልሆነ ነገር ላይ እንዲያጠፉት ፈተና ትሆንባቸዋለህና፡፡

በዚህም ቅጣትህ እጥፍ ድርብ ይሆንብሃል፤ የራስህ ጥፋት እንሶህ ሌሎችንም ወደ ጥፋት መርተሃቸዋልና፣ የኃጢአት ምክንያት ሆነህባቸዋልና፡፡ (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌል ማቴዎስ፣ ክፍለ ትምህርት 67፣ ቁ. 5)

❖ ". . . በተለይም ደግሞ የከፉዎች መናፍቃንን ጉባኤዎች ተጸየፋቸው፣ ከእነርሱ ጋር ኅብረት እንዳይኖርህ ተጠንቀቅ፡፡ በማንኛውም መንገድ ቢሆን በጾም፣ በጸሎት፣ በምጽዋት፣ የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቃል በማንበብ ነፍስህን ንጹሕ እንድትሆን አድርጋት፤ በሥጋ ትኖርበት ዘንድ በተሰጠህ በቀሪው ዕድሜህ በኦርቶዶክሳዊ ነገረ ሃይማኖትና በማስተዋል በመኖር ከጥምቀት የሚገኘውን መዳን ታገኝ ዘንድ፣ እግዚአብሔር ከሰማያውያን ሠራዊት ጋር አንድ አድርጎ ይደምርህና ይቆጥርህ ዘንድ፣ በዚህም በኢየሱስ ክርስቶስ ለሰማያዊ የክብር አክሊል የበቃህ ትሆን ዘንድ፣ ለእርሱ ክብርና ምስጋና ለዘለዓለሙ ይሁን አሜን፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 4፣ በእንተ አሠርቱ ነገራተ እምነት፣ ቁ. 37)

❖ "በዓመፃ ገንዘብ ለራሳችን ወዳጆችን እንግዛበት፤ 'እኔም እላችኋለሁ፣ የዓመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘላለም ቤቶች እንዲቀበሏችሁ፣ በእርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ' ተብሏልና። ሉቃ. 16፡9 ይህም ማለት ያን እሳት እናጠፋው ዘንድ፣ በዚያን ዕለት ድፍረት እናገኝና በፊቱ ያለ ኃፍረት መቆም እንችል ዘንድ ምጽዋትን እንስጥ፣ ንብረታችንን ሁሉ እንዳለ በእነርሱ ላይ እናፍስሰው ማለት ነው፡፡ በዚያ የሚቀበሉን እነርሱ አይደሉም፣ የራሳችን ሥራ ነው እንጂ፤ ሊያድነን የሚችለው እንዲሁ ዝም ብሎ እነርሱ የእኛ ወዳጆች መሆናቸው ብቻ አይደለም፡፡ ይህንም ቀጥሎ ከተባለው ታገኘዋለህ፦ "በዘላለም ቤቶች እንዲቀበሏችሁ በእርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ" ካለ በኋላ እንዴት እንደምንወዳጃቸው ሲናገር "በዓመፃ ገንዘብ" አለን፡፡ ወዳጆች የምናደርጋቸው በገንዘባችን መሆኑን አሳየን፡፡ መልካም ሥራ እስከ ሌለን ድረስ፣ በዚህ ዓለም ያገኘነውን ገንዘብ በጽድቅ ሥራ ላይ እስካላዋልነው ድረስ እንዲሁ እነርሱን መወዳጀት ብቻ ሊረዳን እንደማይችል ነገረን፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ዕብራውያን፣ ክፍለ ትምህርት 1)

❖ "በእግዚአብሔር ዘንድ ክብርን ለማግኘት እንደ ምጽዋት የሚጠቅም ነገር የለም፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌለ ዮሐንስ፣ ክፍለ ትምህርት 33፤ 3)

❖ "ይህ ሰውነታችን እንኳ የዕለት ምግብ ያስፈልገዋል፣ ነፍሳችንም እንዲሁ፤ ይልቁንም ነፍሳችን የበለጠ ያስፈልጋታል፡፡ ነፍሳችን በየዕለቱ የሚያስፈልጋትን ምግብ ካላገኘች ግን ደካማና ከፉ እየሆነች ትሄዳለች፡፡ ስለሆነም እየጠፋችና እየከሰመነች፣ መራራም እየሆነች ስትሄድ ዝም ብለን አንያት፡፡ በየቀኑ ብዙ የሚያቆስሉ ነገሮችንና የሚያደሙ ፍላጻዎችን ትቀበላለች፤ በመመኘት፣ በመቆጣት፣ በስንፍና፣ በመንቀፍ፣ በብቀላ፣ በቅናት፣ በእነዚህ ሁሉ ትቆስላለች፡፡ ስለዚህም ለእነዚህ ቁስሎች የሚሆኑ መድኃኒቶችን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፤ ለዚህም ምጽዋት በእያንዳንዱ ቁስል ላይ ሁሉ ሊደረግ የሚችል ታላቅ ፈዋሽነት ያለው መድኃኒት ነው፡፡ "ካላችሁ ነገር ምጽዋት ስጡ፣ እነሆም ሁሉ ንጹሕ ይሆንላችኋል" ይላልና፡፡ ሉቃ. 11፡41 ስግብግብነት ሳይሆን ምጽዋት ስጡ፣ ከስግብግብነት የሚመጣን ነገር ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ ብትሰጠውም የሚጠቅመው ነገር የለም፡፡ ምጽዋት የሚባለው ከማንኛውም ግፍና ዓመፃ ነጻ የሆነ ነገር ነው፡፡ እንዲህ ያለው ምጽዋት ሁሉንም ነገር ንጹሕ ያደርገዋል፡፡ እንዲህ ያለው ምጽዋት ነፍስን ብርህት ያደርጋታል፣ በጸጋ እንድታንጸባርቅና ጽንዕት እንድትሆን ያደርጋታል፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌለ ዮሐንስ፣ ክፍለ ትምህርት 81፤ 3)

- " ሁለት ወገን የሆነ ተጋድሎን ለመጋደል ራስህን አዘጋጅ፤ ይኸውም በመጀመሪያ ራስህን የሚያነጻህን ጸጋ ለምትቀበልበት ለጥምቀት አዘጋጅ፡፡ በመቀጠልም በጥምቀት የምታገኘውን ጸጋ ለመጠበቅ ለመጋደል ራስህን አዘጋጅ፡፡ ያልነበረንን መቀደስና ጸጋ ማግኘት እና ከተቀበልነው በኋላ መጠበቅ እኩል ከባዶችና አስቸጋሪዎች ናቸውና፡፡[94] ብዙ ጊዜ ጸጋውን ከማግኘት አስቀድሞ በጉጉትና በናፍቆት የተገኘውን ጸጋ ኋላ ላይ ስንፍናና ግድ የለሽነት ያጠፉዋልና፤ ለሚመለስ ደግሞ ስንፍና ያጠፋውን ትጋት መልሶ ግንዘብ ያደርገዋልና፡፡ በጥምቀት ያገኘኸውን ጸጋ ለመጠበቅና ለዚህ ለምትፈልገው ነገር መገኘት ደግሞ ትጋሃ ሌሊቶች፣ አጽዋማት፣ መሬት ላይ መተኛት፣ ጸሎታት፣ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ማዘንና መመጽወት በጣም ታላቅ ጠቀሜታ ያላቸው ረዳቶችና አጋሮች ናቸው፡፡ ስለዚህ ስለ ተቀበልከው የምታመሰግን ሁን፤ እንዲሁም ለመጠበቅ የምትተጋም ሁን፡፡ የተሰጠህን ጸጋ እንድታስብ የሚረዱህ ብዙ ትእዛዛት አሉና እነርሱንም አትተላለፋቸው፡፡"

(ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ በእንተ ጥምቀት፣ ቁ. 31)

- "ምጽዋትን የማድረግ ሕይወት ታላቅ የተጋድሎ ሕይወት ነው፤ ይህም ምጽዋቱ ከንጹሕ መዝገብ የወጣ ሲሆን ነው፡፡ ንጹሕ ካልሆነ መዝገብ የሚወጣ ምጽዋት የጭቃ ወንዝ እንደሚያፈልቅ ምንጭ ነው፡፡ በአግባብ ከተገኘ መዝገብ ሲወጣ ደግሞ በገነት እንዳለ ንጹሕና ጥርት እንዳለ፣ በጠራራ ፀሐይ ላይ ጥም ላቃጠለው ሰው ሲሰጥ እንደሚያረካና ደስ እንደሚያሰኝ ኮለል ያለ የምንጭ ውኃ ነው፡፡ ምጽዋት እንዲህ ነው፡፡ በምጽዋት ከእግዚአብሔር ጋር መወዳጀት በሰዎች ዘንድ መወደድንና መከበርን እና ከሁሉም ዘንድ በጎ እይታን የሚያስገኝ ሲሆን ከሁሉም በላይ ደግሞ እግዚአብሔር የሚከብርበት ተግባር ነው፡፡ እንዲሁም ምጽዋት ኃጢአትን ያስተሠርያል፡፡ . . . ምጽዋት የእሳትን ባሕር ያጠፋል፣ ያን የማያንቀላፋውን ትልም እፉን ይዘጋዋል፡፡ ማር. 9፡44 ምጽዋት ያለው ጥርሱን አያፋጭም፡፡" *(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ግብረ ሐዋርያት፣* ክፍለ ትምህርት 22)

- "ሕይወትን የሚሰጠው ማየ ጥምቀት የገሃነምን እሳት እንደሚያጠፋው ሁሉ በምጽዋት እና በጽድቅ ሥራዎችም የኃጢአት እሳት ይጠፋል፡፡ በጥምቀት የኃጢአት ሥርየት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚሰጥ ስለሆነ የጥምቀትን አርአያ በመከተል የማያቋርጥና ቋሚ የሆነ መንፈሳዊ ተጋድሎና መልካም ነገር በማድረግ ጽሙዳን መሆን የእግዚአብሔር ምሕረት በእኛ ላይ እንዲመጣ ያደርገዋል፡፡ ጌታችን ይህን በወንጌል አስተምሯል፡፡ ደቀ መዛሙርቱ እጃቸውን ሳይታጠቡ በመብላት በተከሰሱ ጊዜ ሲመልስ "ነገር ግን በውስጥ ያለውን ምጽዋት አድርጋችሁ ስጡ፤ እነሆም ሁሉ ንጹሕ ይሆንላችኋል ብሏል፡፡ ሉቃ. 11፡41" (ሰማዕቱ ቅዱስ ቆጵርያኖስ፣ ስለ የጽድቅ ሥራዎችና ስለ ምጽዋት ያስተማረው ትምህርት፣ ቁ. 2)

- "እግዚአብሔር ሀብትህን ለሌላ እንድትሰጠው አንተን ያዘዘበት ምክንያት የአንተ ይሆን ዘንድ ነው፡፡ የአንተ በሆነ መጠን የአንተ አይደለምና፡፡ ለሌላ ስትሰጠው ግን ያን ጊዜ የራስህ አድርገህ ተቀብለኸዋል፡፡ ታዲያ እንደዚህ ደስ የሚያሰኝ ነገር ምን አለ? እርሱ ራሱ ለጠላቶቹ ደሙን አፈሰሰ፤ እኛ ግን መልካሙን ሁሉ ላደረገልን ለእርሱ ገንዘብ እንኳ አንሰጥም፡፡ እርሱ በራሱ ደም እንዲህ አደረገ (ደሙን ሰጠ)፤ እኛ ግን የእኛ ባልሆነው ገንዘብ እንኳ እንዲህ አናደርግም፡፡ እርሱ ከሁላችንም በፊት አስቀድሞ አደረገ፤ እኛ ደግሞ የእርሱን አርአያነት ተከትለን እንኳ አናደርገውም፡፡ እርሱ ለእኛ መዳን ሲል አደረገው፤ እኛ ግን ለራሳችን ጥቅም ስንል እንኳ አናደርገውም፡፡ እኛ ለሰዎች ከምናደርገው መልካም ነገር እርሱ የሚጠቀመው አንዳችም ነገር የለም፤ እንዲያ ከማድረጋችን የሚገኘው ጥቅም ሁሉ ለእኛ ይደረግልናል፤ ይጠቅመናልም እንጂ፡፡

[94] (. . . for it is a matter of equal difficulty to obtain a blessing which we have not, and to keep it when we have gained it.)

"እንደ ሌባ ወይም ቀማኛ ያለ ከአንተ እንዳይወስድብህ፡ ወይም ደግሞ እነዚህን ሁሉ ብታመልጥ እንኳ ሞት ከንብረትህ ይለይሃልና ከዚህ ሁሉ አስቀድመህ ለሚያስፈልገው ስጠው አለሁ፡፡ ገንዘቡን አንተ እስከ ያዝከው ድረስ አስተማማኝ የሆነ ባለቤትነት የለህም፡፡ በድሆች አማካይነት ለእኔ ብትሰጠው ግን ሁሉንም እንዳለ ያለ አንዳች ጉድለት ለአንተ እጠብቅልሃለሁ፤ በትክክለኛው ጊዜም ከብዙ ትርፍ ጋር ለአንተው ለራስህ እመልስልሃለሁ ይልሃል፡፡ እኔ ከአንተ የምቀበልህ ልወስድብህና ላስቀርብህ አይደለም፤ ማንም ሊያበድርህ ወይም ሊያዝንልህ በማይችለው በዚያ ሰዓት ላይ ያለ ችግር ትሆን ዘንድና ለዚያ የችግር ጊዜ ይሆንህ ዘንድ፡ ብዙ ይሆንልህም ዘንድ ነው እንጂ ይልሃል፡፡

"ታዲያ ከዚህ ሁሉ የአምላካችን ቃል መግባት በኋላ ለእርሱ ለማበደር አለምሯችን የማይወስን ከሆነ ከዚህ በላይ ልበ ደንዳናነት ምን ይኖራል? እም፣ በእርሱ ፊት ራቁታችንንና ባዷችንን ድሆች ሆነን የምንሄደው ገንዘባችንን ከማንም በላይ በጥንቃቄ በሚጠብቅልንና በሚያስቀምጥልን በእርሱ ዘንድ ስለማናስቀምጥ ነው፡፡ ይህን ባለማድረጋችንም በጽኑ ልንቀጣ ይገባናል፡፡ . . . ኃላፊና ጠፊ የሆነውን፣ የራሳችን ያልሆነውን ገንዘብ ምጽዋት አድርገን ለእርሱ አለመስጠት፣ እጥፍ ድርብ አድርጎ ዘለዓለማዊ ዋጋ ለሚሰጠን ለእርሱ አለመስጠት ታላቅ በደል ነው፡፡"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ መልእክት ሮሜ፣ ክፍል ትምህርት 7)

- "ዳንኤል ለናቡከደነፆር ያለውን አስታውስ፦ 'ንጉሥ ሆይ፣ ስለዚህ ምናልባት የደኅንነትህ ዘመን ይረዝም እንደ ሆነ ምክሬ ደስ ያሰኝህ፤ ኃጢአትህንም በጽድቅ፣ በደልህንም ለድሆች በመመጽወት አስቀር።' ዳን. 4፥27 ... ምን ማለትህ ነው? እንዲህ ላለው በጣም ከባድ ኃጢአትም በምጽዋት ይቅርታ ማግኘት ይቻላል ማለት ነውን? አዎ! ምጽዋት ሊያስተሠርየውና ሊያጠፋው የማይችል ምንም ዓይነት ኃጢአት የለም፤ ሁሉም ኃጢአት ከእርሱ በታች ነው! ለእያንዳንዱ ቁስል የሚስማማ ፈዋሽ መድኃኒት ነው፡፡ ሥራው ሁሉ ግፍን የተመላ ከሆነው ከቀራጭ የከፋ ምን አለ? እንዲያ ሆኖም ግን ምጽዋት የዘኬዎስን ያን ሁሉ ኃጢአቱን አጠበለት፡፡ ይህንንም ክርስቶስ ሰዎች ከሚያመጡት መካከል የተወሰነ በማቆየት እንዲያዝ በማድረጉ ተመልከት፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም "ድሆችን እናስብ ዘንድ ብቻ ለመኑን፣ ይህንም ደግሞ ላደርግ ተጋሁ" አለ፡፡ ገላ. 2፥10 በሌላም ቦታ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለዚህ ጉዳይ አብዝተው ይናገራሉ፡፡ "ለሰው ነፍስ ቤዛው ሀብቱ ነው" ይላል፡፡ ምሳ. 13፥8 ይህም የተባለው በእውነት ነው፤ ክርስቶስ "ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፣ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፤ መጥተህም ተከተለኝ" ብሎታልና፡፡ ማቴ. 19፥21 ይህ የፍጹምነት ወሳኝ አካልና እርምጃ ነውና፡፡

"ሆኖም ምጽዋት በገንዘብ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ሊደረግ ይችላል፡፡ ለምሳሌም አንዱ ሌላውን ሰው ለመታደግና ለመርዳት ከጎኑ ሊቆምለት ይችላል፤ ሌላው ደግሞ በችግሩ ጊዜ የእርዳታ እጁን ሊዘረጋለት ይችላል፡፡ በተግባር የተደረገ አገልግሎትና ምጽዋት ብዙውን ጊዜ በገንዘብ ከተደረገው በላይ ጠቃሚ ሲሆን ይታያል፡፡ ስለዚህም የተለያዩ ዓይነት የሆኑ ምጽዋቶችን ለማድረግ እንነግ፡፡ በገንዘብ ምጽዋት ማድረግ ትችላለህን? ታዲያ አትሳነፍ፤ ቶሎ አድርገው፡፡ በቢሮህ ሰዎችን በመልካም ሁኔታ በማስተናገድ ምጽዋት ማድረግ ትችላለህን? እኔ ገንዘብ ስለሌለኝ ይህ ምንም ጥቅም የለውም አትበል፡፡ ይህ ታላቅ ነገር ነው እንጂ፣ ወርቅ እንደ ሰጠህ አድርገህ ቁጠረው፡፡ ጊዜህንና መልካም ፈቃድህን[95] በመስጠት ምጽዋት ማድረግ ትችል ከሆነም ይህንም አድርግ፡፡

---

[95](kind attentions - θεραπείας)

"ለአብነትም ሐኪም ብትሆን እውቀትህን መጽውት፤ ይህም ታላቅ ነገር ነውና፡፡ አማካሪ መሆን ትችላለህ? ይህ አገልግሎት ከሁሉም በላይ ነው፤ ይህ ምጽዋት ከሁሉም የተሻለ ነው፡፡ እንዲህ በማድረግህ የምታርቀውና የምታስቀረው ረሃብን ሳይሆን ክፉ ሞትን ነውና፡፡ ሐዋርያት ከመጠን በላይ አብዝተው አትረፍርፈው ያፈሰሱት ይህን ዓይነት ምጽዋት ነው፡፡ የገንዘቡን አስተዳደርና አሰጣጥ በተመለከተ ኃላፊነቱን ለሌሎች የሰጡት ለዚህ ነበር፤ እነርሱ በቃለ እግዚአብሔር የሚሆነውን ምጽዋት ይሰጡ ዘንድ፡፡ ለጠፋችና ለባዘነች ነፍስ፤ በጥፋት አፋፍ ላለችና በሚያቃጥል ትኩሳት ውስጥ ላለች ነፍስ ከበሽታዋ ነጻ እንድትሆን ማድረግ መቻል ቀላል ምጽዋት ነው ብለህ ታስባለህን? ለምሳሌ በገንዘብ ፍቅር የተያዘ ሰው ብታይ አዘንለት፡፡ በፍቅረ ንዋይ የእሳት ጭስ ሊታፈን ቀርቧልን? እንዲያ ከሆነ እሳቱን አጥፋለት፡፡ 'አልሰማኝ ቢልና ባይቀበለኝስ?' ትል ይሆናል፡፡ አንተ የምትችለውን ያህል የድርሻህን አድርግ፤ ስለ ሌላው ሰው ግዴለሽ አትሁን፡፡"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፤ ትርጓሜ ግብረ ሐዋርያት፣ ክፍለ ትምህርት 25)

❖ "ሁሉንም ነገር እንዲሆን ያደረገው፣ ዓለምን የፈጠረው፣ መላእክትን የፈጠረው፣ ከቸርነቱ የተነሣ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ቸርነቱ የተነሣም ወደ ሲኦል በመውረድ ያስፈራራናል፤ ይገሥጸናል፤ ይህም በቸርነቱ መንግሥቱን እንድንወርስ ለማድረግ ነው፡፡ እግዚአብሔር አንድ ብቻውን ሲሆን ይህን ሁሉ ለምን ፈጠረ? በቸርነቱ ምክንያት አይደለምን? ሰውን ከመውደዱ የተነሣ አይደለምን? ይህ ነገር፣ ወይም ያ ነገር ለምን ሆነ? ብለህ ብትጠይቅ ሁል ጊዜም መልሱን የምታገኘው በቸርነቱ ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ ለእኛም ምሕረት እንዲደረግልን እኛም ለወገኖቻችን ምሕረትን እናድርግላቸው፡፡ የእሳት ነበልባል በነደደ ጊዜ የሚያጠፋው ውኃ ለሌሎች የምናደርገው የምሕረት ዘይት ነው፤ ይህ ለእኛም ብርሃንን ያበራልናል፡፡ ስለሆነም በምጽዋት አማካይነት ከሲኦል እሳት እንድናለንና ምጽዋትን እናድርግ፡፡"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ፊልጵስዩስ፤ ክፍለ ትምህርት 4)

❖ "ዘራዕ ምጽዋተ በትሕትና - ምጽዋትህን በትሕትና መጽውት፤
ወተዓርር ምሕረተ በጊዜ ፍዳ - በፍርድ ቀን ይቅርታን ታገኛለህ፡፡"

(ማር ይስሐቅ፣ አንቀጽ ካልዕ፣ ምዕ. 2)

በዚህ ምዕራፍ እንደ ተመለከትነው ምጽዋት በመጽሐፍ ቅዱስ እና በአባቶቻችን ትምህርት ታላቅ ጠቀሜታ ያለው መሆኑ በሰፊው የተነገረለት ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ምጽዋት "ለእግዚአብሔር ማበደር"፣ "የፍጹምነት መንገድ"፣ "ከእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ መቀበያ"፣ ከክፉ ቀን የሚያድን"፣ "እግዚአብሔርን በጠሩት ጊዜ ፈጥኖ እንዲሰማና እነሆኝ እንዲል የሚያደርገው" ወዘተ መሆኑ ተገልጿል፡፡

በአባቶቻችን ትምህርትም እንዲሁ ምጽዋት "ከሞት የሚያወጣ"፣ "ከሠራነው ኃጢአት ሥርየትንና መጽናናትን የምናገኝበት"፣ "ከሚመጣው ክፉ ነገር መዳን የምንችልበት መንገድ"፣ "በዚያን ዕለት ድፍረት እናገኝና በፊቱ ያለ ኃፍረት መቆም እንችል ዘንድ የሚያደርግ"፣ "በእግዚአብሔር ዘንድ ክብርን ለማግኘት የሚጠቅም"፣ "ከሲኦል እሳት የሚያድን"፣ "ለእያንዳንዱ ቁስል የሚስማማ ፈዋሽ መድኃኒት"፣ "ኃጢአትን የሚያስተሠርይ"፣ "የእሳትን ባሕር የሚያጠፋ፣ የማያንቀላፋውን ትልም አፉን የሚዘጋ" ወዘተ እያሉ ገልጸውታል፡፡

ተሐድሶዎች ጾምንና ምጽዋትን የሚነቅፉት በአንድ በኩል ሁለንተናቸውን የሠረጻቸው የቅጣት ምትክ ትምህርት አንድ ጊዜ ጌታ በእኔ ምትክ ተሰቅሎ እኔን ከእስራት ስላስፈታኝ ከዚያ በኋላ የፈለግኩትን ብሆን ምንም ችግር የለውም፣ መብቴ ነው ከሚለው የተሳሳተ ትምህርት የተነሣ ነው፡፡ ከዚህም ጋር በሌላ በኩል ደግሞ መዳን ሲባል ከቅጣት ማምለጥና ከእስራት መፈታትን ብቻ እንጂ ከዚያ ያለፈ እስከ ሱታፌ አምላካዊ ድረስ ያለውን ጸጋ እግዚአብሔር ስለማያውቁት በዚህ ሂደት አስፈላጊና ጠቃሚ የሆኑትን ጾምንና ምጽዋትን፣ ትጋሃ ሌሊትን . . . ሁሉ ይነቅፋሉ፡፡ ይህም በሃይማኖት ሽፋን ጾምን በመንቀፍ ሰው እንደ እንስሳት ጊዜያትንና ሰዓታትን ሳይለይ አገኘ አጣውን እንዲበላና ከመብል በቀር ሌላ የማያውቅ ተመጋቢ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ለሚደረገው ፕሮቴስታንታዊ ዓለም አቀፋዊ ዘመቻ መጋቢ ተልእኮና የዚያ አካል ላለመሆኑ ምን ዋስትና አለ? ምጽዋትን በመንቀፍም የእነርሱን የስህተት ትምህርት የሚሰማ ቢኖር ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚገኘውን ጸጋና ዋጋ ማሳጣታቸው እንዳለ ሆኖ እርስ በእርሱ የማይተዛዘን አውሬ የሆነ ትውልድ ለማምጣት የሚደረገው ጉዞ አካል ላለመሆኑስ ምን ማረጋገጫ አለ?

## 4.3 ለካህን መናዘዝና እና ቀኖና መቀበል ለምን?

ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ማንኛውም ሰው ይፈጽመውና ይመላለስበት ዘንድ ከታዘዙት ነገሮች አንዱ ንስሐ ነው፡፡ ንስሐ ሲባል በውስጡ የተለያዩ ተግባራትን አጠቃልሎ የያዘ ታላቅ ነገር ነው፡፡ ከእነዚህም መካከል በደለኛነቱን አምኖ ማዘንና መጸጸት፣ ኃጢአትን ለእግዚአብሔር መናዘዝ፣ ኃጢአትን ለካህን መናዘዝ፣ ኃጢአትን ለበደሉት ሰው መናዘዝን እና ከዚህም ጋር በካህን (ንስሐ አባት) አማካይነት ቀኖና መቀበልን ያጠቃልላል፡፡

ተሐድሶዎች "እንግዳ ትምህርት" ከሚሏቸውና ከሚቃወሟቸው ነገሮች መካከል አንዱ "ለንስሐ አባት መናዘዝ" እና "ቀኖና መቀበልን" ነው፡፡ ይህን ሲነቅፉና ሲቃወሙ ከተናገሯቸው መካከልም፡- "ኃጢአትን ለንስሐ አባት ተናግሮ የሚወስንበትን ቅጣት መቀበል የኃጢአት ሥርየት ያስገኛል መባሉ" ከቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮና አሠራር መካከል አንዱ ትልቅ ችግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡ (ኖኅተ ብርሃን፣ መጋቢት 2002፣ ገጽ 18) እንዲሁም ደግሞ ወደ ምሥጢረ ቁርባን ሲቀረብ ንስሐ ገብቶ ቀኖና ተቀብሎ መቅረብ እንደማያስፈልግ ይናገራሉ፡፡ ምንም ዓይነት ዝግጅትና ቀኖና መፈጸም የሚባል ነገር አያስፈልግም ባዮች ናቸው፡፡ በርግጥ ዋናውን ጉዳይ - የምሥጢረ ቁርባንን አማናዊ የክርስቶስ ሥጋና ደምነት፣ መሥዋዕትነቱን፣ በዚያ የሚገኘውን ሥርየተ ኃጢአትና የዘለዓለም ሕይወት የካዱ ስለሆነ እንዴት መቅረብ እንደሚገባ ያለውን ጥንቃቄ ቢክዱ አይገርምም፡፡ ስለሆነም እዚህ ላይ የምናየው ኃጢአትን ለንስሐ አባት መናዘዝን እና ቀኖና መቀበልን በተመለከተ ይሆናል፡፡ ከዚያ በፊት ግን ተሐድሶዎች ይህን ጉዳይ በተመለከተ ያላቸውን ትምህርት እንመልከት፡፡

### 4.3.1 የተሐድሶዎች ትምህርት ለካህን ስለ መናዘዝና ቀኖና ስለ መቀበል

◉ ". . . ነገሩ እነርሱ እንደሚሉት ይሁን እንኳ ቢባል አፈጻጸሙ በጣም አስቸጋሪ መሆኑ እርግጥ ነው፡፡ ሰው ንስሐ የሚገባው በበደለ ሰዓት በመሆኑ ኃጢአት የሠራው ሰው በበደለ ሰዓት መናዘዝ ቢፈልግ እንኳ ቄሱን የግድ ማግኘት ስለሚኖርበት እሱን ፍለጋ መሄዱ አይቀርም፡፡ ከሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣ በወቅቱ ሊያገኘው ባይችል ደግሞ ለንስሐ ቀጠሮ ለመያዝ ይገደዳል፡፡ ወይም ደግሞ ቢገናኙ በተነሳሒው ልብ ውስጥ ቄሱ እንደሱው ያለ ሰው መሆኑ ስለሚታወቅ የሚናዘዘው ኃጢአቱን በከፊል አሊያም የሆነውን ትቶ ኃጢአት ያልሆነውን ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ሰው የሆነው ቄስ በስሩ ከሚገኙት ብዛት ያላቸው የንስሐ ልጆች አንጻር ለስንቱ ሊበቃ ነው?" (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 151)

- "ኃጢአትን ለእግዚአብሔር መናዘዝ እንደሚገባ የብሉይ ኪዳን ሰዎች ሳይቀር ስለ ተረዱ ብዙ ጊዜ ኃጢአታቸውን ለእግዚአብሔር በቀጥታ ይናዘዙ ነበር፡፡" (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 152)

- "ለቄስ ካልተናዘዙን በቀር ስርየት የለም የሚለውን እንግዳ ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን አስርገው ያገቡት ሰዎች በእነርሱ ሥርዓት መሰረት ንስሐ ለሚገባ ሰው ቀኖና (ስለ ኃጢአቱ የሚከፈል ዋጋ ወይም የሚቀጣው ቅጣት ጾም፣ ስግደት . . .) እንዲኖር ደንብ ደንብተዋል፡፡ ክርስቶስ በሊቀ ካህንነቱ የገዛ ደሙን የኃጢአት ማስተስረያ አድርጎ እንዳቀመ እነርሱም ራሳቸውን በእርሱ ስፍራ አስቀምጠዋልና ሌላ የኃጢአት ማስተስረያ መፈለጋቸው ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን "ሰውስ ስለነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል? ሲል ነፍስን ከኃጢአት አንጽቶ ለማዳን የሚበቃ ዋጋ አለመኖሩን ይመሰክራል፡፡ ማር. 8፡37 ቄርሎስም ይህንኑ ሲያረጋግጥ "ወአኮ ክርስቶስ በካልዕ ዘየኀድግ ኀጢአተ ወይስእሮ ለሞት ዘእንበለ በደሙ - ክርስቶስም ኃጢአትን ይቅር የሚለው ሞትንም የሚሽረው በደሙ ነው እንጂ በሌላ አይደለም፡፡ (ስምዐ ጽድቅ ብሄራዊ)" (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 153)

- ". . . በዚህም መሠረት በሠራው ኃጢአቱና በበደለው በደሉ ተጨንቆ ሲናዘዝ ኃጢአተኛ መሆኑን ያስታውቅ እንጂ የሰው ክፋት በሙሉ ከሚያውቅ ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአተኛው ራሱ እንኳ የሠራውን ወይም የሚሠራውን በሙሉ ሊያውቅ እስከማይችል ድስ ልቡ በውድቀት ዕውረት የተሸፈነ ነውና ማንም ሊቆጥረውና ሊያስተውለው በማይችል የኃጢአት ብዛት ዘርዝሮ ይናገር ዘድ አስፈላጊ አይደለም፡፡" (ስምዓ ጽድቅ ብሔራዊ፣ ገጽ 156)

## በዚህ ጉዳይ ላይ የተሐድሶች መሠረታዊ ስህተቶች

### 1) ኃጢአትን ለካህን መናዘዝ ማለት ለእግዚአብሔር አለመናዘዝ ወይም ለእግዚአብሔር መናዘዝን እንደሚተካና እንደሚያስቀር አስመስለው ማቅረባቸው፤

አንድ ተነሣሒ ለካህኑ የሚናዘዘው ካህኑን እንደ እግዚአብሔር መልእክተኛ፣ እግዚአብሔርን ደግሞ ዳኛ አድርጎ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ "ካህኑ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነውና" ይላልና፡፡ ሚልክ. 2፡7 ለንስሐ አባቱ ሲናዘዝም ሆነ ከዚያ በኋላ፣ ኃጢአቱን እንደ ሠራና ወደ ንስሐ አባቱ ሳይመጣም፣ ሁል ጊዜም በኃጢአቱ የሚጸጸተውና አንተን ብቻ በደልሁ እያለ ንስሐውን የሚያፈስሰው ምን ጊዜም ለእግዚአብሔር ነው፡፡ ይህ ግን ለካህን መናዘዝን አያስቀርም፣ ለካህን መናዘዝም ለእግዚአብሔር የመናዘዙ አካል እንጂ ያን የሚተካ አይደለም፡፡ ነገሮችን በሆኑበትና በራሳቸው ምንነት ሳይሆን ፊደል መቁጠር ያልለየ ሕፃን የተለያዩት ፊደሎች አንድ መስለው እንደሚታዩትና እንደሚደባለቁበት ነገሩን ሁሉ በየምንነቱ ከማየት ይልቅ ማደባለቅና ማምታታት መለያ ጠባያቸው መሆኑ ያሳዝናል!

### 2) ተነሳሒ የሚቀበለው ቀኖና "ስለ ኃጢአቱ የሚከፍለው ዋጋ ወይም የሚቀጣው ቅጣት ነው" ማለታቸው፤

ማንም ተነሳሒ ሰው የተወሰነ ጾም መጾምና መስገድ . . . ይቅርና መላ ዘመኑን በሙሉ እናቱን ወደ ታች ዘቅዝቆ ከባሕር ውስጥ ጠልቆ መጸለይ ቢችል እንኳ ወይም እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ባለ ሁኔታ መላ ዕድሜውን ቢጋደል እንኳ ለኃጢአቱ ዋጋ ሊሆነው አይችልም፡፡ የአዳም ኃጢአት ምን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለ ይታወቃልና፡፡ ስለዚህ ለተነሳሒ የሚሰጠው ቀኖና ተግሣጻዊና ወደ መስመር ማስገቢያ፣ ወደ ቅዱስ ምሥጢር ለመቅረብ መዘጋጃ እንዲሆን እንጂ ለኃጢአቱ ተመጣጣኝ ክፍያ ነው ተብሎ አይደለም፡፡ "መጽሐፍ ቅዱስ ግን 'ሰውስ ስለነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?' ሲል ነፍስን ከኃጢአት አንጽቶ ለማዳን የሚበቃ ዋጋ አለመኖሩን ይመሰክራል" እያሉ የደረደሯቸው ጥቅሶች አለቦታቸው የገቡና ባልተባለ ነገር ላይ ለማስረዳት የተጠቀሱ ስለሆነ "የባከኑ ጥቅሶች" ናቸው፡፡

ምክንያቱም ንስሐ መግባትና ቀኖና መቀበል ማለት ስለ ነፍሱ ቤዛ የሚሆን ዋጋ መክፈል ነው የሚል አርቶዶክሳዊ አስተምህሮ የለምና፡፡ ያልተረዱትን ነገር አበላሽቶ መተርጎምና በዚያው ባልተረዱት ነገር በመቀጠል መገስገስ ከራሱ ጋር ብቻ እንደሚወዳደር ሯጭ መሆን ነው፡፡ ወይም ቅዱስ ጳውሎስ "ነፋስን እንደ መጐሰም" ብሎ እንደ ገለጸው ያለ ባዶ ድካም ነው፡፡ ስለዚህ ባልሆነው መውቀስና መክሰስ ዋናው ስልታቸው ስለሆነ ካዋጣቸው ይቀጥሉበት፡፡

እንዲሁም በተደጋጋሚ "ክርስቶስ በሊቀ ካህንነቱ የገዛ ደሙን የኃጢአት ማስተስረያ አድርጎ እንዳቆመ እነርሱም ራሳቸውን በእርሱ ስፍራ አስቀምጠዋልና ሌላ የኃጢአት ማስተስረያ መፈለጋቸው ነው" የሚለው አጉል ውንጀላ ብቻ ነው፡፡ ካህናት የተነሳሕያንን ኑዛዜ የሚሰሙትና ቀኖና የሚሰጡት ተነሳሕያን ለኃጢአታችን ፈውስና ሕይወት ሆኖ ወደ ተሰጠን የክርስቶስ አማናዊ የሆነ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ ለማድረግ እንጂ እነርሱ በራሳቸው "ለእኔ ተናዝዘሃልና በቃህ፣ ኃጢአትህን እኔ እሥተስርዬልሃለሁ" ሊሉ አይደለም፡፡ ሲናዝዙ እንኳ "እግዚአብሔር ይፍታሕ - እግዚአብሔር ይቅር ይበልህ" ብለው ነው እንጂ "እኔ ፈታሁህ፣ ይቅር አልኩህ" ብለው አይደለም፡፡ ከላይ እንደ ተገለጸው ካህናት የእግዚአብሔር መልእክተኞች ናቸውና፡፡ እንዲሁም ራሱ ባለቤቱ ጌታችን "ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል" ብሏቸዋልና፡፡ ዮሐ. 20:23

ንስሐ መግባትና ቀኖና መቀበል ወደ ቅዱስ ቁርባን ለመቅረብ የሚደረግ የዝግጅት አካል ነው፡፡ ሆኖም ይህ ትምህርት የሚገባቸው በቅዱስ ቁርባን አማናዊነት ለሚያምኑ ነው፡፡ ይህን ለማይቀበሉና "እንደ ማንኛውም ምግብ ይበላል፤ እንደ ማንኛውም መጠጥ ይጠጣል፤ ወደዚህ ስንቀርብም የተለየ ዝግጅት አያስፈልግም እያሉ በራሳቸው ላይ ለሚቀልዱ ተሐድሶዎች አይደለም፡፡ ይህ ከእርሱ የተሰወረ ነው፡፡

3) አፈጻጸሙ አስቸጋሪ ሊሆን ከመቻሉ የተነሣ ያቀረቡት፣

እነዚህም አንደኛ ተነሳሒው ካህኑን ንስሐ መግባት በፈለገበት ጊዜ ባያገኘውስ? የሚል ሊሆን ሌላኛው ደግሞ ኃጢአቱን መናዘዝ ትቶ ኃጢአቱ ያልሆነውን ሊናዘዝ ይችላል የሚል ነው፡፡ እንዲሁም ሦስተኛው ደግሞ ካህኑ በሥሩ ካሉት ብዙ የንስሐ ልጆች አንጻር ለስንቱ ሊበቃ ነው? የሚል ነው፡፡

የመጀመሪያውን ስንመለከት በማንኛውም በዚህ ዓለም በጊዜና በቦታ በሚፈጸሙ ምሥጢራት አፈጻጸም ውስጥ (ችግሩ እናንተ አታምኑባቸውም እንጂ) ጊዜያትንና ቦታዎችን ማመቻቸት የግድ ነው፡፡ ለምሳሌ ሊጠመቅ ያለ ሰው ቢኖር ወይም ሊቆርብ ያለ ሰው ቢኖር ይህን አፈጻጸም በተመለከተ ከካህናቱ ጋር መነጋገርና በዚያው መንገድ አገልግሎቱን ማግኘት ይችላል፡፡ ነገር ግን ያ ሰው ሊጠመቅ በፈለገበት ጊዜ ካህን ባያገኝስ? ቤተ ክርስቲያን በሌለበት ቦታ ቢሆንስ? ቅዳሴ በማይቀደስበት አካባቢ ቢሆንስ? ... በማለት እነዚህ ነገሮች ይቅሩ ሊባል አይቻልም፤ ሊሆኑ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንጂ፡፡ በንስሐም እንዲሁ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ የሚወስደው ለካህን መናዘዝ ይቅር ወደ ማለት ሳይሆን ካህናትና ተነሳሕያን በአግባቡ ሊገናኙ የሚችሉበትን ሁኔታ ወደ ማመቻቸት እንሂድ ወደሚል ነው፡፡

ተነሳሒው በልቡ ውስጥ ያለውን ሙሉውን ሳይሆን በከፊል፣ ወይም ኃጢአቱን መናዘዝ ትቶ ኃጢአቱ ያልሆነውን ሊናዘዝ ይችላል የሚለው ደግሞ እውነተኛ ተነሳሒ እስከ ሆነ ድረስ ይህን አያደርግም፤ በራሱ ላይ የሚቀልድ ጤነኛ ሰው የለምና፡፡ ይህ አባባል የተነሳሒው ንስሐ ተቀባይነት የሚወሰነው ካህኑ በተነሳሒው ውስጥ ያለውን ኃጢአት ሙሉ በሙሉ በማወቁ ላይ ነው የሚል ሃሳብ በውስጡ አለው፡፡ ይህ ግን ትክክል አይደለም፡፡ ካህኑ መርማሪ ፖሊስ አይደለምና፡፡

እንዲሁም ሦስተኛው ካህኑ በስሩ ካሉት ብዙ የንስሐ ልጆች አንጻር ለስንቱ ሊበቃ ነው? የሚል ነው፡፡ የንስሐ አባቶች የሆኑ ካህናት ሙሉ ጊዜያቸውን በዚሁ አገልግሎት ላይ እንዲያውሉ የሚደረገው ለዚህ ነው፡፡ የሆነ ሆኖ በዚህ ዙሪያ ክፍተት ቢኖር እንኳ መፍትሔው ይህን ለመሙላት ተገቢውን ሥራ መሥራት ነው እንጂ ለንስሐ አባት መናዘዝን ማጥፋት አይደለም፡፡

## 4.3.2 ለንስሐ አባት መናዘዝና ቀኖና መቀበል

### በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

አንድ ሰው ኃጢአት ሲሠራ በመጀመሪያ ኃጢአት ማድረጉን ለእግዚአብሔር ይታመናል፡፡ እንዲህ በማለት በደሉን በእግዚአብሔር ፊት ይናዘዛል፡-

> ተሣሃለኒ እግዚኦ በከመ ዐበየ ሣሕልከ ወበከመ ብዙኃ ምሕረትከ ደምስስ ኃጢአትየ ኅጽበኒ ወእንጽሐኒ እምኃጢአትየ ወእምአበሳየኒ እንጽሐኒ እስመ ለልየ አአምር ጌጋይየ ወኃጢአትየኒ ቅድሜየ ውእቱ በኩሉ ጊዜ ለከ ለባሕቲትከ አበስኩ ወእኩየኒ በቅድሜከ ገበርኩ -

> አቤቱ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ፡ እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ። ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፡ ከኃጢአቴም አንጻኝ፡ እኔ መተላለፌን አውቃለሁና፡ ኃጢአቴም ሁል ጊዜ በፊቴ ነውና። አንተን ብቻ በደልሁ፡ በፊትህም ክፉትን አደረግሁ፡፡" መዝ. 50፡1-3

ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር የምንናዘዘው ስለማያውቀው ለመንገር ሳይሆን እርሱን መበደላችንን በመታመን ይቅርታውንና ምሕረቱን ለመማጸን ነው፡፡ የአባትነት ፍቅሩን ማሳዘናችንን ለመግለጽና የተሰማንን ጸጸት በፊቱ ለማፍሰስ ነው፤ "ወከዐው ልበክሙ ቅድሜሁ - ልባችሁን በፊቱ አፍስሱ" እንደ ተባለ፡፡

ከዚህ ጋር ደግሞ ኃጢአትን ለንስሐ አባት መናዘዝ ተገቢም፡ አስፈላጊም ነው፡፡ ይህ የታዘዘበት ብዙ ምክንያቶች አሉት፡፡ ከዚያ በፊት ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ምን እንደሚል እንመልከት፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ከጌታችን መንፈቅ ተቀድሞ ሕዝቡን ለክርስቶስ የሚያዘጋጅ የንስሐ ጥምቀት ያጥምቅ ነበር፡፡ ያን ጊዜ ሕዝቡ ወደ እርሱ እየመጡ የንስሐ ጥምቀት ከመጠመቃቸው በፊት ኃጢአታቸውን ለእርሱ ይናዘዙ ነበር፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ ስለዚህ ሲናገር እንዲህ ይላል፡- "ያን ጊዜ ኢየሩሳሌም ይሁዳም ሁሉ፤ በዮርዳኖስም ዙሪያ ያለ አገር ሁሉ፤ ወደ እርሱ ይወጡ ነበር፤ <u>ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር</u>።" ማቴ. 3፡5-6

ሕዝቡ የንስሐ ጥምቀትን ለመጠመቅ ይችሉ ዘንድ ንስሐ ሲገቡ ኃጢአታቸውን ለመጥምቁ ዮሐንስ ይናዘዙ እንደ ነበረ ሁሉ ምእመናንም ወደ ቅዱሳት ምሥጢራት ከመቅረባቸው በፊት ኃጢአታቸውን ለንስሐ አባቶቻቸው ይናዘዛሉ፡፡ ዮሐንስ መጥምቅ ይናዘዙ የነበሩትን ሰዎች "ግበሩ ፍሬ ዘይደሉ ለንስሐ - ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ፤ በልባችሁም፡- አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ አይምሰላችሁ፤ እላችኋለሁና ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት እግዚአብሔር ይችላል። አሁንስ ምሳር በዛፎች ሥር ተቀምጧል፤ እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል፡ ወደ እሳትም ይጣላል" ብሎ ምክርና ተግሣጽ እንደ ሰጣቸው የንስሐ አባቶችም ከተነሣሒው ሕይወትና ሁኔታ አንጻር መዝነው ተገቢ ነው ያሉትን ምክርና ቀኖና ይሰጣሉ፡፡ ማቴ. 3፡8-10

እስራኤላውያን ዮርዳኖስን ተሻግረው መጀመሪያ ከወረሷት ከኢያሪኮ ምንም ነገር እንዳይወስዱ እርም ነውና አትንኩ ተብለው በእግዚአብሔር ታዝዘው ነበር፡፡ ነገር ግን ከመካከላቸው አካን የተባለው አንድ ሰው ከተከለከለው ነገር ሰርቆ በመውሰዱ ምክንያት በሕዝቡ ዘንድ ከደረሰው ነገር የተነሣ ተጣርቶ በመጨረሻ ያን ያደረገው ሰው ተገኘ፡፡

**በዚያን ጊዜም ኢያሱ አካንን እንዲህ አለው፡-**

> ኢያሱም አካንን፦ ልጄ ሆይ፥ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ክብር ስጥ፥ ለእርሱም ተናዘዝ፥ ያደረግኸውንም ንገረኝ፥ አትሸሽገኝ አለው። አካንም መልሶ ኢያሱን፦ በእውነት የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን በድያለሁ፥ እንዲህና እንዲህም አድርጌአለሁ። በዘረፋ መካከል አንድ ያማረ የሰናዖር ካባ፥ ሁለት መቶም ሰቅል ብር፥ ሚዛኑም አምሳ ሰቅል የሆነ ወርቅ አይቼ ተመኘኋቸው፥ ወሰድኋቸውም፤ እነሆም፥ በድንኳኔ ውስጥ በመሬት ተሸሽገዋል፥ ብሩም ከሁሉ በታች ነው አለው። ኢያ. 7፡21-23

ኢያሱ አካንን "ልጄ ሆይ፥ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ክብር ስጥ፥ ለእርሱም ተናዘዝ፥ ያደረግኸውንም ንገረኝ፥ አትሸሽገኝ" እንዳለው ሁሉ አንድ ሰው ለንስሐ አባቱ የሚናዘዘው ለእግዚአብሔር የመናዘዙ አካል ነው፡፡ አካን ለኢያሱ ሲናዘዝ ለእግዚአብሔር መናዘዙ ነበር፡፡ ለዚህ ነው "ለእርሱም ተናዘዝ፥ ያደረግኸውንም ንገረኝ፥ አትሸሽገኝ" ያለው፡፡ አካንም ኢያሱን "እኔ ኃጢአቴን ለእግዚአብሔር ብቻ እነግራለሁ እንጂ ለአንተ አልናዘዝም" አላለውም፡፡ ተነሣሒ ለንስሐ አባቱ ሲናዘዝ እግዚአብሔርን ሰሚና ዳኛ አድርጎ ነውና፡፡

በሐዲስ ኪዳንም ጌታችንን አንድ ለምጽ የነበረበት ሰው ቀርቦ "ጌታ ሆይ፥ ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ" እያለ እየሰገደ በጠየቀው ጊዜ እጁን ዘርግቶ ዳሰሰውና "እወዳለሁ ንጻ" አለው፡፡ ወዲያውም ለምጹ ነጻ። ከዚያ በመቀጠል ግን ወዲያውኑ ጌታችን ያን እርሱ ያነጻውን ለምጻም የነበረውን ሰው እንዲህ የሚል ትእዛዝ አዘዘው፡- "ኢየሱስም፦ ለማንም እንዳትናገር ተጠንቀቅ፥ ነገር ግን ሂደህ ራስህን ለካህን አሳይ፥ ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ሙሴ ያዘዘውን መባ አቅርብ አለው።" ማቴ. 8፡2-4 ምንም እንኳ ያን ለምጻም ራሱ ጌታችን ያገኘውና የፈወሰው ቢሆንም፥ በጌታችን ፈውስ ላይ ሌላ የሚያስፈልግ እንዳችም የቀረ ተጨማሪ ነገር ባይኖርም፥ ነገር ግን ራሱ ባለቤቱ ጌታችን ያን ያነጻውን ሰው "ሂደህ ራስህን ለካህን አሳይ" ሲል አዝዞታል፡፡

ይህን የንስሐ አባትና ልጅ ግንኙነት በንጉሥ ዳዊትና በነቢዩ በናታን ግንኙነትም ማየት እንችላለን፡፡ ዳዊት ቤተ መቅደስ ስለ መሥራት ሲያስብ ጉዳዩን ያማከረውና ወደ እግዚአብሔር እንዲያመለክትለት የነገረው ነቢዩን ናታንን ነበር፡፡ ነቢዩ ናታንም ወደ እግዚአብሔር እየጸለየ ከአምላኩ ያገኘውን መልስ ለዳዊት ይነግረው ነበር፡፡ በኋላ ላይ ዳዊት የኃጢአት መሰናክል ባገኘው ጊዜም እግዚአብሔር ዳዊትን ከኃጢአት ዕንቅልፍ ይቀሰቅሰውና ንስሐ ይገባ ዘንድ የላከው ያንኑ ነቢዩ ናታንን ነበር፡፡ ናታንም ሂዶ በጥበብና በብልሃት ለዳዊት ኃጢአቱን ነገረው፡፡ ያን ጊዜ ዳዊት ጥፋቱን አመነ፥ ተጸጸተ፥ ንስሐም ገባ፡፡ የንስሐ አባት የሚያስፈልግበት አንዱ ምክንያት እያንዳንዱን ሰው እንዲህ ቀስ አድርጎ በፈሊጥ ውድቀቱን እንዲገነዘብና ንስሐ እንዲገባ ለማድረግ ነው፡፡ ይህ በዐውደ ምሕረት በሚደረግ ስብከት ብቻ የሚያልቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ ዳዊት ስለ በደለው ባለ ጸጋ ግፍ ነቢዩ ናታን በምሳሌ አድርጎ ሲነግረው ያ የሚባለው ሰው እርሱ ራሱ መሆኑን አላወቀም ነበር፡፡ ኃጢአት ሲጫጫን አእምሮን ያደነዝዛል፥ ልቡናን ያጨልማልና፡፡ ሆኖም ነቢዩ ናታን ቀስ እያደረገ በምሳሌና በጥበብ ስላስረዳው የኃጢአቱን ክብደት ለመረዳት ቻለ፥ ንስሐም ገባ፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱን ሰው እንደየ ድክመቱና ጥንካሬው በመንፈሳዊ ሕይወቱ የሚመራ፥ የሚመክር፥ ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ በጸሎቱ የሚረዳ መንፈሳዊ አባት አስፈላጊ ነው፡፡

ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የንስሐ አባትነትን ተግባርና አፈጻጸም በተግባርም አሳይቶናል፡፡ በሕይወቷ ከደረሰባት ውስብስብ ውጣ ውረድ የተነሣ ልቧ ቆስሎ ውስጧ ተጎድቶና ሰው ጠልቶ የነበረችውን ሳምራዊቷን ሴት ብቻዋን አግኝቶ አናገራት፡፡ ለዚህም ሲል ደቀ መዛሙርቱን ቀደም አድርጎ "ምግብ ግዙ" ብሎ ላካቸው፡፡ እርሷ ሰዎች ልቧን ያቆሰሏት በመሆኑ የዚያ አካባቢ ሴቶች ውኃ የሚቀዱት አየሩ ቀዝቀዝ ሲል በጠዋትና በማታ ስለ ነበር ሰው በማይገኝበት ሰዓት ለመቅዳት ስትል በጠራራ ፀሐይ በቀትር ወደ ውኃው ጉድጓድ ሄደች፡፡

ጌታችን የስድስት ሰዓት ያህል መንገድ በሰማርያ ሞቃታማ መንገድ የተጓዘው ለዚህ ነበር፡፡ ከዚያም ልትቀዳው በመጣችው በውኃ በመጀመር ቀስ በቀስ ከምድራዊ ነገር ወደ ሰማያዊ፣ ከጊዜያዊ ወደ ዘለዓለማዊ ነገር ከፍ ከፍ አደረጋት፣ አሸጋገራት፡፡ ከዚያም ጌታችን "ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነዪ" አላት። ይህን ያላት በውስጧ ያለውን ኃጢአቷን እንድትናዘዝ በሩን እየከፈተላትና መንገዱን እያሳያት ነበር፡፡ እርሷም መልሳ፡- "ባል የለኝም" አለችው። ከዚያም ጌታችን "ባል የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ፤ አምስት ባሎች ነበሩሽና፣ አሁን ከአንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም፤ በዚህስ እውነት ተናገርሽ" በማለት እርሷ ልትናገረው የፈራችውን በመናገር እርሱ ሁሉንም ሕይወቷን የሚያውቅ አምላክ መሆኑን እንድትረዳ አደረጋት፡፡ ዮሐ. 4፥1-42

ጌታችን ይህን በተግባር ያሳየን የንስሐ አባት እያንዳንዷን ነፍስ ማነጋገርና የምትፈወስበትን መንገድ መፈለግ ያለበት ብዙ ሰው በተሰበሰበበት በአደባባይ ስብከት ሳይሆን ለብቻው ቀስ አድርጎ፣ ጥብብና ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ መሆን እንዳለበት ለማስተማር ነው፡፡ ምክንያቱም የአንዱ ስብራት ከሌላው ጋር ላይገጥም ይችላል፤ የአንዱ ደካማ ጎን ለሌላው ምንም ላይሆን ይችላል፡፡ በዚህ ዓለም ሐኪም ቤት እንኳ የአንዱ በሽታ ከሌላው የተለየ ነው፤ ለአንዱ የሚታዘዘው መድኃኒት ለሌላው ላይሆነው ይችላል፡፡ ለዚህ ነው ሐኪሞች እያንዳንዱን ታማሚ ለየብቻው የሚያናግሩት፣ የሚመረምሩትም፡፡ ሥጋዊ በሆነው የታማሚዎች ምርመራና ሕክምና እንኳ ይህን ያህል ጥንቃቄ የሚያስፈልግ ከሆነ ረቂቅና መንፈሳዊ ስለሆነውማ ምን ያህል ያስፈልግ ይሆን? ስለዚህ የንስሐ አባትና የንስሐ ልጅ ግንኙነት እንዲህ ያለ ምሥጢራዊና እግዚአብሔር ብቻ ምስክሩ የሆነ በሁለቱ መካከል ብቻ የሚኖር ምሥጢራዊ ግንኙነት ነው ማለት ነው፡፡

የንስሐ አባቶች በእነርሱ አባትነት ሥር ላለው ለእያንዳንዱ ሰው ነፍስ ኃላፊነትና ተጠያቂነት አለባቸው፡፡ እግዚአብሔር በነቢዩ አማካይነት "ኃጢአተኛውን፦ ኃጢአተኛ ሆይ፣ በእርግጥ ትሞታለህ ባልሁ ጊዜ ኃጢአተኛውን ከመንገዱ ታስጠነቅቅ ዘንድ ባትናገር ያ ኃጢአተኛ በኃጢአቱ ይሞታል፤ ደሙን ግን ከእጅህ እፈልጋለሁ። ነገር ግን ከመንገዱ ይመለስ ዘንድ ኃጢአተኛውን ብታስጠነቅቀው እርሱም ከመንገዱ ባይመለስ በኃጢአቱ ይሞታል፣ አንተ ግን ነፍስህን አድነሃል" በማለት የተናገረው ጠንካራ ማሳሰቢያ ይህን ከባድ አደራ ነው፤ ሕዝ. 33፥8-9 ለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው ይህንኑ በደስታ እንጂ በኃዘን እንዳያደርጉት፡ . . . ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ" በማለት በዕብራውያን መልእክቱ ያሳሰበው። ዕብ. 13፥17 እነዚህ "ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ" የተባሉት የንስሐ አባቶች ናቸው፡፡ ለነፍሳት ቢተጉ የመልካም እረኞች ጌታ መልካም ዋጋቸውን ይሰጣቸዋል፤ "የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ" ተብለዋልና፡፡ 1 ጴጥ. 5፥4 የተጣለባቸውን አደራ ባይወጡ ደግሞ ስለ በጎቹ ነፍሱን አሳልፎ የሰጠው እውነተኛው እረኛ ይጠይቃቸዋል፤ "ደሙን ከእጅህ እፈልጋለሁ" ይላልና፡፡

### 4.3.2.1 ለካህን መናዘዝና ቀኖና መቀበል

በአንቀጸ ንስሐ አግባብ መሠረት ቀኖና መቀበል ማለት አንድ ሰው ከሃይማኖት ወይም ከተግባራዊ የክርስትና የሕይወት መንገድ በተለያየ ደረጃና ሁኔታ ወጣ ብሎ ወይም አፈንግጦ ከነበረ ወደ መስመር እንዲመለስና ሃይማኖታዊውን የሕይወት ጉዞ በትክክለኛው ጎዳና እንዲጓዝ መርዳትና ማድረግ ነው፡፡ ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር መጠኑና ዓይነቱ ይለያያል እንጂ ውጣ ውረድና ስህተት ስለማይጠፋ ንስሐ ሲገባ የሰውዬውን የተለያዩ ሁኔታዎች ባገናዘበ ሁኔታ የንስሐ አባቱ ቀኖና ይሰጠዋል፡፡

አንድ ምእመን በኃጢአት ሲሰነካከል እንደ ድቀቱ ስፋትና ጥልቀት ፍቅርና ማጽናኛ ሊለየው ከማይገባ መጠነኛ ተግሣጽና ምክር እንሥቶ ለተወሰነ ጊዜ ከማኅበረ ምእመናን እስከ መለየት የሚያደርስ ጽኑ ቀኖና ሊሰጠው ይችላል፡፡ ይህም በቅዱሳት መጻሕፍት በስፋት ተገልጾ የምናገኘው ነገር ነው፡፡ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ በሕይወታቸው በጣም ከባድ የሆኑ ኃጢአቶች ውስጥ ገብተው የነበሩ አንዳንድ ምእመናን ነበሩ፡፡ ሆኖም የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን እነዚያን በኃጢአት የተሰነካከሉ ሰዎች ተገቢውን ቀኖና በመስጠት ፋንታ ይልቁንም የተወሰኑ ሰዎች በቲፎዞነት መንፈስ በዙሪያቸው ተሰልፈው እነርሱን እያጽናኑ እንጂ ፈጥረው ነበር፡፡ በአጠቃላይ በዚያን ዘመን በቆሮንቶስ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን እንደዚያ ዓይነት ሰዎችን በተመለከተ ልትወስድ ይገባት የነበረውን ቀኖናዊ ተግባር ሳትፈጽም ምንም ነገር ያልተፈጠረ ይመስል በውስጧ አቅፋ ይዛቸው ነበር፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ያ ዓይነት ሁኔታ ትክክል አለመሆኑንና ምን ሊደረግ እንደሚገባው በመልእክቱ እንዲህ ሲል ጽፎላቸዋል፡-

> በእጭር ቃል በእናንተ መካከል ዝሙት እንዳለ ይወራል፣ የዚያም ዓይነት ዝሙት በአሕዛብስ እንኳ የማይገኝ ነው፡፡ የአባቱን ሚስት ያገባ ሰው ይኖራልና፡ እናንተም ታብያችኋል፣ ይልቅስ እንድታዝኑ አይገባችሁምን? <u>ይህን ሥራ የሠራው ከመካከላችሁ ይወገድ</u>። እኔ ምንም እንኳ በሥጋ ከእናንተ ጋር ባልሆን፥ በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝ፥ ከእናንተም ጋር እንዳለሁ ሆኜ ይህን እንደዚህ በሠራው ላይ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሁን ፈርጀበታለሁ፤ እናንተና መንፈሴም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ጋር ተሰብስበን <u>መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው</u>። 1 ቆሮ. 5፡1-5

በመጀመሪያ እንደዚህ ዓይነት አሳፋሪ ኃጢአት የሠራው ሰው ከምእመናን መካከል ሊወገድ እንደሚገባ *"ይህን ሥራ የሠራው ከመካከላችሁ ይወገድ"* በማለት አዘዘ፡፡ እንደዚሁም ይህ ቀኖናዊ ውሳኔ መሆኑን ሲገልጽ ደግሞ "ከእናንተም ጋር እንዳለሁ ሆኜ ይህን እንደዚህ በሠራው ላይ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሁን ፈርጀበታለሁ" አለ፡፡ በመቀጠልም እንዲህ ዓይነቱ ቀኖና የሚሰጥበት ዓላማ ሰውዬውን ለማጥፋት ሳይሆን ለማዳን፥ ለመርዳት ካሉን ለመጥቀም መሆኑን ደግሞ *"መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው"* በማለት ተናገረ፡፡ ስለዚህ ቀኖና የሚሰጥበት ዓላማ ሰዎች ነፍሳቸው በፍርድ ቀን ትድን ዘንድ ለመርዳት ነው፡፡

ጥፋተኛው እንዲህ ጽኑ ቀኖና እንዲሰጠው ካዘዘ በኋላ ደግሞ ያ ቀኖና የተሰጠው ሰው ተስፋ እንዳይቆርጥና በብዙ ሐዘን እንዳይዋጥ ከተወሰነ የቀኖና ጊዜ በኋላ ምሕረትንና ሐዘኔታን ማሳየት እንዲገባ በሁለተኛው የቆሮንቶስ መልእክቱ እንዲህ ብሏቸዋል፡-

> በብዙ መከራና ከልብ ጭንቀት በብዙም እንባ ጽፌላችሁ ነበርና፤ ይህም እናንተን አብዝቼ የምወድበትን ፍቅር እንድታውቁ እንጂ እንዳሳዝናችሁ አይደለም። ነገር ግን ማንም አሳዝኖ ቢሆን፥ እንዳልከብድባችሁ በከፍል ሁላችሁን እንጂ እኔን ያሳዘነ አይደለም። <u>እንደዚህ ላለ ሰው ይህ ከእናንተ የምትበዙት የቀጣችሁት ቅጣት ይበቃዋልና እንደዚህ ያለው ከልክ በሚበዛ ኀዘን እንዳይዋጥ፥ ይልቅ ተመልሳችሁ ይቅር ማለትና ማጽናናት ይገባችኋል። ስለዚህ ከእርሱ ጋር ፍቅርን እንድታጸኑ እለምናችኋለሁ</u>፡፡ 2 ቆሮ. 2፡4-11

ሰይጣን በአንድ በኩል ቀኖና አያስፈልግም በማለት በድፍረትና በግድ የለሽነት እንደሚፈትን ሁሉ በሌላ በኩል ደግሞ በጽኑ ቀኖና ሂደት በማስጨነቅና ተስፋ በማስቆረጥ ከክርስቶስ ለመለየት ይፈትናልና መጠንቀቅ የሚገባ መሆኑን አሳሰበ፡፡ ስለዚህም ያን አስቀድሞ "ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው" በማለት ጽኑ ቀኖና ይሰጠው ያለውን ሰው ከተወሰነ የቆኖና ጊዜ በኋላ ደግሞ ይቅር ብለው ከማኅበረ ምእመናን እንዲቀላቅሉትና ፍቅር እንዲሳዩት ያዘዘበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ ሲገልጽ "በሰይጣን እንዳንታለል፤ የእርሱን አሳብ አንስተውምና" አለ፡፡

የመጀመሪያዎቹ ሰዎች አዳምና ሔዋን በበደሉ ጊዜ እግዚአብሔር የማዳን ተስፋውን ቢሰጣቸውም ያለ ቀኖና ግን አልተዋቸውም፡፡ ለእያንዳንዳቸው እርሱ ባወቀ ተገቢ የሆነውን ቀኖና ሰጥቷቸዋል፤ እንዲህ ሲል፡-

> ለሴቲቱም አለ፡- በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ፤ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፤ እርሱም ገዥሽ ይሆናል። አዳምንም አለው፡- የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና፣ ከእርሱ እንዳትበላካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርሷ ትበላለህ፤ እሾህንና አሜከላን ታበቅልብሃለች፣ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ። ወደ ወጣህበት መሬት እስከትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤ አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህና። ዘፍ. 3፡15-19

ይህ ለአዳምና ለሔዋን በአንድ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት ይቅር እስኪላቸውና እስከሚያድናቸው ድረስ ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን የተሰጠ ቀኖና ነበር፡፡ ጌታችን ሰው ሆኖ ካዳነን ወዲህ ያ የተሰጣቸው ቀኖና አብቅቷል፡፡ እንዳንድ የማስታወሻ ቅሬቱ ቢኖርም እንደ ብሉይ ኪዳኑ ዘመን የቀኖና (የቅጣት) መሆኑ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት ተቀግዷል፡፡ "ወሠዐረ መርገመ በዲበ መስቀል - መርገምን በመስቀል ላይ ሻረ፤ አስወገደ" እንዳለ፡፡ ሐዋርያውም "ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው" እንዳለ፡፡ ኤፌ. 2፡16 እንዲሁም "በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዷልና" በማለት የገለጸው ይህን ነው። ቆላ. 1፡19-20

ከዚህም ጋር እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ሰጥቷቸው ከነበረው ክብር አስወጥቷቸዋል፤ ወደዚያ እንዳይመለሱም በኪሩቤልና በምትገለባበጥ የነበልባል ሠይፍ አጥሮባቸዋል፡፡ እንዲሁም ከዕፀ ሕይወት እንዳይበላ አድርጎታል፡፡

መድኃኒታችንና አምላካችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የቀኖና ጉዳይ ከየት ጀምሮ እስከ ምን ደረጃ ሊደርስ እንደሚችል እንዲህ የሚል መመሪያና ትምህርት ሰጥቶናል፡-

> ወንድምህም ቢበድልህ፤ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው። ቢሰማህ ወንድምህን ገንዘብ አደረግኸው፤ ባይሰማህ ግን በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር ውሰድ፡፡ እነርሱንም ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፡፡ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ። እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል። ማቴ. 18፡15-18

ከቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል ያጠፋን ሰው በመጀመሪያ ለብቻው መምከር ይገባል፡፡ በዚህ የማይመለስ ከሆነ በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች መንገርና ተገቢውን ቀኖና መስጠት ይቀጥላል፡፡ ሆኖም ለቤተ ክርስቲያን ከተነገረ በኋላ አሁንም የማይመለስ ከሆነ ግን እንደ አረመኔና ቀራጭ ይሆናል፡፡ ማለትም አረመኔ የሆነ ኢጥሙቅ ከቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት መሳተፍ እንደማይችለው ሁሉ ተመክሮ ተዘክሮ አልመለስም ያለ ምእመንም ከቤተ ክርስቲያን እስከ መለየት (እስከ መወገዝ) ሊደርስ ይችላል ማለት ነው፡፡

#### 4.3.2.2 ቀኖና የሚሰጥባቸው ምክንያቶች

ለተነሣሒያን ምእመናን ቀኖና መስጠት የሚያስፈልገው ስለ ተለያዩ፤ ግን ተደጋጋሚ ስለ ሆኑ ብዙ ምክንያቶች ነው፡፡ ከእነዚህም መካከል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

1) ንስሐ ሳይገቡና ቀኖና ሳይቀበሉ በኃጢአት በቆሸሸ ሰውነት ወደ ምሥጢራት መቅረብ ስለማይገባ፣

እግዚአብሔር አምላክ አዳምና ሔዋን በበደሉ ጊዜ ከላይ እንዳየነው ተገቢ የሆነውን አባታዊ ተግሣፅ (ቀኖና) ሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፦

> እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ ... አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ፣ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፣ ለዘላለምም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ ከዔድን ገነት አስወጣው፤ የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ። አዳምንም አስወጣው፣ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በዔድን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ። ዘፍ. 3፥22-24

አዳም ከበደለና ባሕርዩ በኃጢአት ከጎሰቆለ በኋላ እግዚአብሔር ለምን ከሕይወት ዛፍ እንዳይበላ ከለከለው? ለምንስ ከዔድን ገነት አስወጣው? እግዚአብሔር አዳምን በበደለ ጊዜ ከዚህ ሁሉ ጸጋው የከለከለውና ከገነት ያስወጣው ከቸርነቱ የተነሣ ነበር እንጂ እነርሱን ለመጉዳት ወይም ለመበቀል አልነበረም፡፡ አዳም ባሕርዩ በኃጢአት እንደ ጎሰቆለ ከነኃጢአቱ ሳለ ዕፀ ሕይወትን በልቶ ኃጢአቱ ከባሕርዩ ጋር ለዘላለም ተጣብቆ እንደ ዲያብሎስ የማይሞት ምውት ሆኖ እንዳይኖር ለማድረግ ነበር፡፡ አዳም በጎሰቆለ ባሕርዩ ከዕፀ ሕይወት በልቶ ቢሆን ኖሮ እንደ ሰይጣናት የማይሞት (ነፍሱና ሥጋው የማይለያዩ)፣ ግን ከእግዚአብሔር ቅድስናና ሕይወት የተለየ ዘለዓለማዊ ምውት ይሆን ነበር፡፡ ስለዚህ ከሕይወት ዛፍ እንዳይበላ የከለከለውና ከገነት ያስወጣው ቀኖናውን ፈጽሞ የባሕርዩ መጎስቆል አካላዊ ቃል ባሕርዩን ሲዋሐድ በሚያገኘው ከኃጢአትና ከጉስቁልና ነጻ መሆን ተፈውሶ ለሕይወት ተስማሚ በሆነ ሁኔታ ሆኖ ወደ ሕይወት እንዲቀርብ ለማድረግ ነበር፡፡

በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቀኖና የሚሰጥበት *መሠረታዊ ምክንያትም* ይኸው ነው፤ ማንም በማይገባ ሕይወት ወደ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ቀርቦ እንዳይጎዳ ለመጠበቅ ነው፡፡ እግዚአብሔር አዳም በጎሰቆለ ባሕርዩ ከዕፀ ሕይወት ወስዶ እንዳይበላ የከለከለው ሰው በኃጢአት እንደ ወደቀና እንደ ጎሰቆለ በዚያ ሁኔታ እያለ ሕይወትን ሰጪ ወደ ሆኑት ወደ ምሥጢራተ እግዚአብሔር መቅረብ የሌለበት መሆኑን ለማስተማርም ነው፡፡ ለዚህ ነበር እግዚአብሔር አምላክ *"አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ፣ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፣ ለዘላለምም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር"* በማለት የከለከለውና ከገነት ያስወጣው፡፡ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ በኪሩቤልና በምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍ ያስጠበቃት ለዚህ ነበር፡፡ ስለዚህ ያ ለአዳምና ለሔዋን የተሰጣቸው ቀኖና ለሰው ጥቅም ነበር ማለት ነው፡፡ ይልቁንም የሰው ልጅ ለዘለቄታው ይጎዳ የነበረው ያ ቀኖና ባይሰጠው ነበር ማለት ነው፡፡

ወደ ቅዱስ ቁርባን ምሥጢር በመቅረብና በመሳተፍ ጊዜ ምን ሊደረግ እንደሚገባውና ያን ጥንቃቄ ካለመጠበቅ የተነሣ ቀኖናዊ ሂደቱን ባልጠበቁት ላይ ምን እንደ ደረሰባቸው ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያው የቆሮንቶስ መልእክቱ እንዲህ ሲል ይናገራል፦

> ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፣ ይጠጣልምና። ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ፤ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል። ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር፤ ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ ከዓለም ጋር እንዳንኰነን በጌታ እንገሠጻለን። 1 ቆሮ. 11፥29-32

ስለሆነም በእነዚያ የደረሰው እንዳይደርስበት የሚፈልግ ሁሉ ወደ ቅዱሳት ምሥጢራት ከመቅረቡ በፊት በንስሐ ራሱን መመርመርና አስፈላጊ የሆኑ ቀኖናዊ ሂደቶችን መፈጸም ይኖርበታል። መቼም ቢሆን የሰው ዝግጅት በራሱ የእግዚአብሔርን ምሥጢራት ለመቀበል የሚያበቃው ሊሆን እንደማይችል ይታወቃል። የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመቀበል የማንም ሰው የቅድስና ደረጃ በራሱ ብቁ ሊሆን አይችልም፤ እግዚአብሔር እርሱ ባወቀ በቸርነቱ የሚሰጠው ነው እንጂ። ስለዚህም ነው "ጸጋ" የሚባለው። የቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅን ያህል የቅድስና ሕይወት፣ የመላእክትን ያህል ንጽሕና ያለው ሰው ቢኖር እንኳ ከቅዱስ ቁርባን ለመቀበል ብቁ አያደርገውም። ስለዚህ የምንቀርበው በቅትን ሳይሆን ተዘጋጅተን ነው። ሆኖም ግን "መቼም ቢሆን እኔ ለቅዱስ ቁርባን ልበቃ አልችልም፣ በቸርነቱ እንጂ" በማለት ደግሞ እንዲሁ በተነሳቀለና በኃጢአት ባደፈ ሰውነት ሆኖ መቅረብም አይገባም። ማንኛውም ምእመን የተቻለውን ያህል ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሠርግ ቤት ተገኝቶ በዚያ የታደሙትን እያንዳንዳቸውን በተመለከታቸው ጊዜ በዚያ የሠርግ ልብስ ያልለበሰ አንድ ሰው አየና፦ "ወዳጅ ሆይ፣ የሠርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ?" ብሎ ጠይቆታል። ያን ጊዜ "እርሱም ዝም አለ" ይላል። በመቀጠልም "በዚያን ጊዜ ንጉሡ አገልጋዮቹን፦ እጁንና እግሩን አስራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል አለ" ይላል። ማቴ. 22፡11-13 የሠርጉ ባለቤት ለምን በዚያ የተቀመጡትን ስለ ለበሱት ልብስ መቆጣጠር አስፈለገው? ለምንስ "የሠርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ?" ብሎ ጠየቀው? ይህ የሚያስተምረን ወደ ቅዱሳት ምሥጢራት ስንቀርብ ልብስ የተባለ ሰውነታችንን በንስሐ አጥበን ቀኖናችንን ፈጽመን መቅረብ የሚገባ ስለመሆኑ አይደለምን? እንዲህ ሳያደርጉ እንዲሁ በዘፈቀደ የሚቀርቡ ምን እንደሚጠብቃቸውም "እጁንና እግሩን አስራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል" በማለት በማያወላውል ሁኔታ ነገረን። ታዲያ እንዲያው ምንም ይሁን ምን ቢያንስ ዓላማው ከዚህ "ወዳጅ ሆይ፣ የሠርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ?" ከሚለው ጽኑ ወቀሳ ለመዳንና ከሚያስከትለው ወደ ውጭ የመጣል ከባድ ቅጣት ለመዳን የሆነ ሰው ንስሐንና ቀኖናን እንዴት ሊቃወም ይችላል? እንዲሁም "ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው በደጆቿም ወደ ከተማይቱም እንዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው" ተብሏል። ራእ. 22፡14

2) የኃጢአት ደመወዝ ሞት መሆኑን ለማስታወስ፤

ተነሣሒ ምእመን በቀኖና ሂደት-የሚያልፍበት ሌላው ምክንያት የኃጢአት ደመወዝ ሞት መሆኑን ለማስታወስና እግዚአብሔርም ተነሣሒውን ከዚያ ዓይነት ከባድ ሁኔታ ያወጣው መሆኑን ለማዘከር ነው። ሐዋርያው "የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና" ብሎ በግልጽ እንደ ተናገረው። ሮሜ 6፡23 እንዲሁም እግዚአብሔር "ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርሷ ትሞታለች" ብሏል። ሕዝ. 18፡4 ስለዚህ ንስሐ የሚገባ ሰው ይህን በኃጢአቱ ይደርስበት የነበረውን ዘለዓለማዊ ቅጣትና የሞት ደመወዝ እንደ ቀረለትና ከዚያ ዓይነት ሁኔታ እንደ ወጣ አዘካሪ ይሆነው ዘንድ በቀኖና ሂደት ውስጥ ያልፋል።

3) ኃጢአት ቅጣት ያለው መሆኑ እንዳይረሳ፤

ቀኖና የሚያስፈልግበት ሌላው ምክንያት ደግሞ ኃጢአት ቅጣት ያለው መሆኑ እንዳይረሳ ነው። ነቢዩ ዳዊት በሠራው ኃጢአት ምክንያት ንስሐ እንደ ገባ ወዲያውኑ በነቢዩ በናታን አማካይነት "እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልሃል፣ አትሞትም" በማለት ይቅር ያለው ቢሆንም ያለ ቅጣት ግን አልተወውም። በናታን አማካይነት እንዲህ አለው፦ "ነገር ግን በዚህ ነገር ለእግዚአብሔር ጠላቶች ታላቅ የስድብ ምክንያት አድርገሃልና ስለዚህ ደግሞ የተወለደልህ ልጅ ፈጽሞ ይሞታል።" ቀኖናዊ ቅጣቱም ወዲያውኑ ጀመረ። "እግዚአብሔርም የኦርዮ ሚስት ለዳዊት የወለደችውን ሕፃን ቀሠፈ" ይላል። 2 ሳሙ. 12፡13-15

የዳዊት ቀኖና በዚያ በድቀት በተወለደው ልጅ መሞት ብቻ አላበቃም፡፡ የታላቅ ሰው ፈተናውም ጽኑና ታላቅ በመሆኑ የዳዊት ድቀት ከባድ ስለ ነበር ቀኖናውም ከበድ ያለ ነበር፡፡ ኃጢአቱን ገና በመጀመሪያው "እግዚአብሔርን በድያለሁ" ባለ ጊዜ "እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልሃል" በማለት ይቅር ያለው ቢሆንም በዚህ ዓለም በነበረው በቀሪ የሕይወት ዘመኑ ግን ብዙ ተከታታይ ቀኖናትን ተቀብሏል፡፡ በልጁ መሞት የተጀመረው ቅጣት በመቀጠል ልጁ የሆነው አምኖን እኅቱን ትእማርን ከክብር አሳነሳት፣ አስነወራት፡፡ ከዚያም የተነሣ አቤሴሎም ለእኅቱ ለትእማር በመቆርቆር ቀንና ኢጋጣሚ ጠብቆ ወንድሙን አምኖንን ገደለው፡፡ በመቀጠልም የራሱ ልጅ አቤሴሎም ከቤተ መንግሥቱ አሳደደው፡፡ በኋላም አቤሴሎም በጦርነት ላይ እያለ ተገደለ፡፡ ዳዊት ምንም ከመንግሥቱ ያባረረውና ችግር የፈጠረበት የነበረ ቢሆንም የአባትነት አንጀቱ አላስችል ብሎት ለአቤሴሎም "ልጄ አቤሴሎም ሆይ፣ ልጄ፣ ልጄ አቤሴሎም ሆይ፣ በአንተ ፋንታ ሞቼ ኖሮ ቢሆን፣ ልጄ አቤሴሎም፣ ልጄ ሆይ" እያለ ሲያለቅስ እንኳ ሐዘኑን በነጻነት ለመግለጽ አልቻለም፡፡ የጦር አበጋዞቹ እነ ኢዮአብ ወደ እርሱ መጥተው እንዲህ ብለውታልና፡-

> ኢዮአብም ወደ ንጉሡ ወደ ቤት ገብቶ እንዲህ አለ፡ ዛሬ ነፍስህንና የወንዶችና የሴቶች ልጆችህን ነፍስ የሚስቶችህንና የቁባቶችህን ነፍስ ያዳኑትን የባሪያዎችህን ሁሉ ፊት ዛሬ አሳፍረሃል፣ አንተ የሚጠሉህን ትወድዳለህ፡ የሚወድዱህንም ትጠላለህ። መሳፍንትህንና ባሪያዎችህን እንዳታስብ ዛሬ ገልጠሃል፡፡ ዛሬ ሁላችን ሞተን ቢሆን ኖሮ፣ አቤሴሎምም ድኖ ቢሆን ኖሮ ደስ ያሰኝህ እንደ ነበረ ዛሬ አያለሁ። አሁን እንግዲህ ተነሥተህ ውጣ፣ ለባሪያዎችህም የሚያጽናናቸውን ነገር ተናገራቸው፡፡ ያልወጣህ እንደ ሆነ ግን አንድ ሰው ከአንተ ጋር በዚህች ሌሊት እንዳይቀር በእግዚአብሔር እምላለሁ፣ ይህም ከብላቴናነትህ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ካገኘህ ክፉ ነገር ሁሉ ይልቅ ታላቅ መከራ ይሆንብሃል። ንጉሡም ተነሥቶ በበሩ ተቀመጠ፡፡ ሕዝቡም ሁሉ ንጉሡ በበሩ እንደ ተቀመጠ ሰማ፣ ሕዝቡም ሁሉ ወደ ንጉሡ ፊት መጣ። እስራኤልም እያንዳንዱ ወደ ድንኳኑ ሸሽቶ ነበር። 2 ሳሙ. 18፡33-19፡8

ዳዊት እንዲህ በግድ የመጣበትን ቀኖና ከተቀበለ እኛ በፈቃዳችን ቀኖና መቀበል የለብንምን? ወይስ በግድ ካልተጫነብን በስተቀር በፈቃድ ራስን ለእግዚአብሔር ማቅረብ አይሆንልንም? ቅዱስ ጳውሎስም እግዚአብሔር በቸርነቱ የቀደመ በደልን ይቅር የሚል መሆኑን ሳንዘነጋ በሌላ በኩል ደግሞ ያን የቀደመ ስህተታችንን ጨርሶ መዘንጋት እንደማይገባ ሲያስታውስ "እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና፣ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ ነኝ" ይላል፡፡ 1 ቆሮ. 15፡9

ጋለሞታ የነበረችውና በእምነት ኢያሱ የላካቸውን ሁለቱን ሰላዮች በመቀበሏ እግዚአብሔር ከታላቅ ቸርነቱ የተነሣ በኢየሱስ ክርስቶስ የሥጋዌ የዘር ሐረግ ገብታ እንድትቆጠር ያደረጋትን ረዓብን (ራኬብን) ሲጠቅሷት ቅዱስ ጳውሎስ እና ቅዱስ ያዕቆብ እምነቷንና መልካም ሥራዋን ተባብረው ሲመሰክሩላት የቀድሞ ግብሯን ከማስታወስ ጋር እንዲህ በማለት ነበር፡- "ጋለሞታይቱ ረዓብ ሰላዮችን በሰላም ስለ ተቀበለቻቸው ከማይታዘዙ ጋር በእምነት አልጠፋችም፡፡" ዕብ. 11፡31 "እንደዚሁም ጋለሞታይቱ ረዓብ ደግሞ መልእክተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን?" ያዕ. 2፡25 እንዲሁም ለምጻም የነበረውንና ጌታችን የፈወሰውን ስምዖንን መድኃኒታችን በቤቱ በተገኘ ጊዜ "እርሱም በቢታንያ በለምጻሙ በስምዖን ቤት በነበረ ጊዜ . . ." በማለት ወንጌላውያን የቀደመ ሁኔታውን በማዘከር ገልጸውታል፡፡ ማር. 14፡3 ይህም በአንድ በኩል የቀደመ ግብራቸው (የረአብ ዘማነቷ፣ የስምዖን ለምጻምነቱ) ወደ እግዚአብሔር ከመመለስና ጸጋውን ከማግኘት እንዳላገዳቸው እንዲታወቅ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የቀደመ ግብራቸው መጠቀሱ እኛም እግዚአብሔር በምሕረቱና በቸርነቱ በደላችንን ይቅር ሲለንና ጸጋውን ሲሰጠን የቀደመ ማንነታችንን መርሳት የሌለብን መሆኑን የሚያሳስብ ነው፡፡

ለተነሳሕያን ቀኖና የሚሰጥበት አንደኛው ምክንያትም ይህ ነው፣ ምንም እንኳ እግዚአብሔር ይቅር ባይ ቢሆንም የቀደመ በደላችንን ደግሞ መርሳትና ምንም ያላደረግን ጻድቃንና ንጹሐን እንደ ሆንን ማሰብ የማይገባ መሆኑን፡ ኃጢአትም ቅጣት ያለው መሆኑን በተግባር እንድንረዳ ነው፡፡ አባታችን ዳዊት ኃጢአቱን እግዚአብሔር ይቅር ካለው በኋላም እንኳ "ወኃጢአትየኒ ቅድሜየ ውእቱ በኩሉ ጊዜ - ኃጢአቴ ሁል ጊዜ በፊቴ ነው" እያለ ያዝንና ይጸጸት ነበር፡፡ መዝ. 50፡4 ኃጢአት ሠርቶ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ ከባድ ነገር ነው፤ ቅዱስ ጳውሎስ "እስመ ጽኑዕ ወዲቅ ውስተ እደ እግዚአብሔር ሕያው - በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው" ያለው ለዚህ ነው፡፡ ዕብ. 10፡31 የአዳምና የሔዋን ኃጢአት ምን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለ ስናስበው ኃጢአት ምን ያህል ከባድ፣ ውጤቱም መራር መሆኑን እናያለን፡፡ ቀኖና የዚህ እውነታ መገለጫም፣ ማስጠንቀቂያም ነው፡፡

## 4) ለወደፊቱ ወደ ኃጢአት የመሄድን ዝንባሌ ገታ ለማድረግ፣ ለመርዳት

ምንም እንኳ ይህ ዋና ምክንያት ነው ባይባልም አንድ ሰው ኃጢአት ከሠራ በኋላ ንስሐ ሲገባ የተወሰነ ቀኖና መቀበሉ ለወደፊቱ ያን ዓይነት ተመሳሳይ ኃጢአት ወደ መሥራት በቀላሉ እንዳይሄድ ሊረዳው ይችላል፡፡ እግዚአብሔር ነገሮችን የሚሠራልን ሰዎች ከመሆናችን አንጻር ድክመታችንን በሚያግዝ መልኩ ነው እንጂ ሁሉ ነገር የተሰጠው ፍጹማን እንደ መሆናችን አይደለም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም የቆሮንቶስ ምእመናንን በመልእክቱ እንዲህ ብሏቸዋል፡- "እኔም፣ ወንድሞች ሆይ፣ የሥጋ እንደ መሆናችሁ፣ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም። ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤ ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም።" 1 ቆሮ. 3፡1-3 ይህም ማለት ለሕፃናት የሚሰጠው ጠንካራ ምግብ ሳይሆን ዓቅማቸውን የሚመጥን ወተትና ቀላል ምግብ እንደሆነ ሁሉ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንደ ሕፃናት ለሆኑም ሕግና ሥርዓት የሚሠራው እንደ ዓቅማቸው እነርሱን ለመርዳት ነው፡፡

እግዚአብሔር ሕግ የሠራውም የሰውን ድካም ለማገዝና ለመርዳት ነበር፡፡ "ወወሀበ ሕገ ለረድኤት - ሕግን ለዕርዳታ ሰጠ" እንደ ተባለ፡፡ ኢሳ. 8፡20 ስለዚህ ቀኖና ኃጢአት እንደ ውኃ መንገድ እንዳይሆን እንደ ሥነ ልቡናዊ ማዕቀብ (Psychological deterrent) ሆኖ ሊያገለግልና ሊያግዝ ይችላል፡፡ ወደ ኃጢአት የሚገፋፋ ሁኔታ ቢገጥመው ነገ ንስሐ መግባት አለበትና የሚቀበለውን ቀኖና ሲያስበው ከፊቱ የተደቀነው ኃጢአት ከሚያስገኘው ግብታዊ ዕርካታ ይልቅ ያ (የቀኖናው) የበለጠ ከባድ ሆኖ ስለሚታየው ለመጠበቅ ሊረዳው ይችላል፡፡ እንዲህ ባለ ሁኔታ ትርፍና ኪሳራን ማስላት ተገቢ መሆኑም በቅዱስ መጽሐፍ ተመልክቷል፡፡ ሉቃ. 14፡28-32 ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ በትክክል የሚረዱትና የሚያውቁት ደግሞ በክርስትና ሕይወት በተግባር የሚኖሩበት ሰዎች እንጂ በክርስትና ላይ የሚቀልዱት ዋዘኞችና ጸረ ክርስትና መንፈስ የሚያናውዛቸው ሰነፎች ሰዎች አይደሉም፡፡

በዚህ ሁሉ ልብ ሊባል የሚገባው መሠረታዊ ነጥብ አለ፡፡ እርሱም ይህ ሁሉ የሚሠራው ኃጢአት ከባድ መሆኑን በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረውን የጌታችንን ትምህርት በሙሉ አምኖ ለሚቀበል ሰው ነው እንጂ "ላመነ ሰው ኃጢአት ቢሠራም የሚያስከትልበት ችግር የለም"፣ "ኃጢአት ብንሠራም ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት ላይ ለውጥ አያመጣም" እያለ የክህደት ቃል ለሚናገርና በዚህ መንገድ ለሚኖር አለመሆኑ ነው፡፡ እንዲህ ላሉት መጀመሪያ ሊሰበክላቸው የሚገባው መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ በሙሉ ስለ መቀበል ጉዳይ ነው፡፡

## 4.3.3 ንስሐ ስባትና ቀኖና - በስበው ትምህርት

ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲክዱና ለጣዖት እንዲሰግዱ በሚል ከአላውያን ነገሥታትና መኳንንት መከራ በመጣባቸው ጊዜ ለህብትና ለንብረታቸው እንዲሁም ለምድራዊ ደኅንነታቸው አድልተውና መከራውን ተሰቅቀው ክርስቶስን ከካዱ በኋላ ንስሐ ስለ ገቡና ስለ ተመለሱ ተነሳሕያን ሰዎች ቀኖና በተመለከተ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሰማዕቱ ቅዱስ ቆጵርያኖስ እርሱ በአላውያን በተነሣው መከራ ምክንያት በስደት ላይ ሆኖ እንዲህ የሚል መልእክት ላከላቸው፡-

- "የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ እግዚአብሔርን በመፍራት ልቡናችሁ ዝግጁ የሆነ እናንተ፣ ክርስቶስን ክዳችሁና በኃጢአት ወድቃችሁ የነበረ ቢሆንም አሁን አእምሯችሁ ጥፋቱንና በደሉን በማሰብና በመጸጸት ላይ ያላችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ በንስሐና በሐዘን ሆናችሁ የኃጢአታችሁን ከብደት አስተውላችሁ ተመልከቱ፡፡ የሕሊናችሁን የኃጢአት ጥልቀት እወቁ፣ ታመኑ፤ ዓይነ ልቡናችሁን ኃጢአታችሁን ለመረዳት ክፈቱት፡፡ ይህም በአንድ በኩል በእግዚአብሔር መሐሪነት ተስፋ ሳትቆርጡ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ ጊዜ ፈጥናችሁ ይቅር ይለናል ብላችሁ ሳትሳነፉ ነው፡፡ እግዚአብሔር እንደ አባትነቱ ባለው ፍቅር ሁል ጊዜ ይቅር ባይና ደግ ነው፤ በዚሁ መጠን ደግሞ የዳኝነቱ ግርማና ፍርድ ሊፈራ ይገባዋል፡፡ አብዝተን እንደ መበደላችን መጠን አብዝተን ልናለቅስና ልናዝን ይገባናል፡፡ ከባድና ጥልቅ ለሆነ ቁስል ረዘም ያለና ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ሕክምና ያስፈልገዋል፤ ንስሐው ከኃጢአቱ ያነሰ ሊሆን አይገባውም፡፡

  "እምነት የለሽ በሆነ አነጋገራችሁና ቃላችሁ የካዳችሁት እግዚአብሔር፣ ከእርሱ ይልቅ ምድራዊ ሀብት ንብረታችሁን የመረጣችሁትን፣ ቤተ መቅደሱን (ሰውነታችሁን) ለረከሱ ጣዖታት በመሠዋት ያረከሳችሁበት እርሱ እንዲሁ በቀላሉ ይቅር የሚላችሁ ይመስላችኋልን? 'አምላካችን አይደለም' ብላችሁ በዐዋጅ የካዳችሁት እርሱ በቀላሉ ምሕረት የሚያደርግላችሁ ይመስላችኋልን? በጸሐቀ ልቡና ሆናችሁ መጸለይና መማጸን ይኖርባችኋል፣ ቀኑን በሐዘን ማሳለፍ ይገባችኋል፤ ሌሊቱን በትጋሃ ሌሊትና በልቅሶ ልትደክሙ ይገባችኋል፡፡ ጊዜያችሁን ሁሉ በሰቆቃ ዕንባ ማሳለፍ አለባችሁ፤ በትተኙም መሬት ላይ፣ ያውም አመድ ላይ፣ ማቅና መናኛ ልብስ ለብሳችሁ ይሁን፡፡ የክርስቶስን ልብስነት እርሱን በመካዳችሁ ራሳችሁ ልብሳችሁን ካጣችሁ በኋላ ምንም ልብስ እንዳይኖራችሁ መሆንን መቀበል አለባችሁ፣ የዲያብሎስን ማዕድ ከበላችሁ በኋላ መጾምን መምረጥ አለባችሁ፡፡ ኃጢአት የሚሠረይባቸውን የጽድቅ ሥራዎች በመሥራት ጽኑዓን ሁኑ፣ ነፍሳት ከሞት የሚድኑበትን የምጽዋት ሥራ አዘውትራችሁ የምትሠሩ ሁኑ፡፡ . . . መልካም ሥራዎችን ያለ መዘግየት በብዛት የምትሠሩ ሁኑ፡፡ ሀብታችሁ ቁስላችሁን በመፈወስ ተግባር ላይ ይዋል፣ ሀብታችንና ንብረታችንን እኛን ለሚፈርደን ለጌታ እናበድረው፡፡"

  (ሰማዕቱ ቅዱስ ቆጵርያኖስ፣ ከሃይማኖት አድጠው ስለ ነበሩና ስለ ተመለሱ ተነሣሕያን (On the Lapsed) የተሰጠ ትምህርት፣ ቁ. 35)

ነባቤ መለኮት ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ ከዚህ በታች የምናገኘውን መልእክት የጻፈበት ምክንያት ቴዎዶር የተባለው የቲያና ጳጳስ ጊዮርጊስ የተባለውን አንድ ምእመን ስለ አንድ ጉዳይ እንዲያስረዳለትና እንዲያሳምንለት ወደ እርሱ ልኮት ስለ ነበር ነው፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ ለጊዮርጊስ እንዲያስረዳውና እንዲያሳምነው ጳጳሱ ቴዎዶር የፈለገው ኃጢአትና ስህተትም ጊዮርጊስ የተባለው ምእመን በአንደበቱ ሳይናገር በጽሑፍ ብቻ የማለውን አንድ መሐላ ማፍረሱን "ኃጢአት ነው" ብሎ ጳጳሱ ቴዎዶር ሊያስረዳው ቢሞክርም ጊዮርጊስ ግን "በጽሑፍ ብቻ ጻፍኩት እንጂ በቃሌ ስላልተናገርኩት መሐላ እንደ ማፍረስ ሆኖ አይቆጠርብኝም" እያለ ጳጳሱን ቴዎዶርን ሊሰማው ባለመቻሉና በማስቸገሩ ነበር፡፡

ቅዱስ ጎርጎርዮስም በቃል አለመነገሩ በጽሑፍ እስከ ማለ ድረስ ያው መሐላ መሆኑንና ይህን ማፍረሱም ኃጢአት መሆኑን በሚገባ አሳምኖና አስረድቶ፣ ከዚያም ወደ ጳጳሱ ቴዎዶር ጾን ቀኖና እንዲሰጠውና የቀኖና ጊዜው ርዝመትም እንደ በሁዳው መመለስና የልቡ የመሰበር ሁኔታ እንዲታይ የሚል መልእክት አስይዞ መልሶ ልኮታል፡፡

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ ወደ ጳጳሱ ወደ ቴዎዶር የላከው መልእክት ሙሉ ቃልም እንደሚከተለው ነው፦

- **"እግዚአብሔር አንተን ለቤተ ክርስቲያን የሰጣት ለእኛ ክብር እንድትሆንንና ብዙዎችን እንድትጠቅም ነው፤ ስለ መንፈሳዊ ነገሮች አንተ ራስህ እጅግ ጠንቃቃ እንደ ሆንከው ሁሉ ከአንተ በዕድሜ ትንሽ ቀደም ትላላችሁ የምንባለውን እኛንም እንደ አንተ ጠንቃቃዎችና አስተዋዮች ታደርገን ዘንድ ነውና፡፡ ሆኖም ግን በአንተ መንፈሳዊ አገልግሎትና ድካም ውስጥ እኛንም ተሳታፊዎች ታደርገን ዘንድ (የፓስፓሱሱ ጊዮርጊስ - George of Paspasus - ስለ ማለው መሐላ በተመለከተ ማለቱ ነው) ስለ ፈለግህ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚከተለውን እንላለን፦**

  **"ለእኔ እንደሚመስለኝ በጣም ብዙ ሰዎች በአንደበት በመናገርና በቃል በመግለጽ የተነገሩ መሐላዎችን እውነተኛ መሐላዎች እንደ ሆኑ፣ ነገር ግን በጽሑፍ ብቻ የተቀመጡትንና በአንደበት ያልተነገሩትን መሓላዎች ግን የእውነት መሐላዎች አይደሉም እያሉ ራሳቸውን ያታልላሉ፡፡ በጽሑፍ ያለ የብድር ዕዳ በቃል ካለ ይልቅ የበለጠ አስገዳጅና ግዴታዊ ሆኖ ሳለ በጽሑፍ ያለ መሐላ ግን መሐላ ሳይሆን ሌላ ነገር ነው ማለት እንዴት እንችላለን? . . . ወንድማችንን ጊዮርጊስን ኃጢአቱን ለመሸፈን ሰበብና ምክንያት ከመፈለግ ይልቅ፣ እንዲሁም በደሉን ለመከላከል የክርክር ጉዳይ ወደ መፈለግና ራሱን ከበደል ንጹሕ አስመስሎ ለማሳየት ወደ መድከም እንዳይሄድና በጽሑፍ የገባው መሐላ እውነተኛ መሐላ መሆኑን እንዲቀበል አሳምኜዋለሁ፡፡**

  **"ስለዚህ ምንም እንኳ አስቀድሞ የተለየ አመለካከት የነበረውና ራሱን እያታለለ የነበረ ቢሆንም አሁን ግን ስለ ኃጢአቱ በእግዚአብሔርና በብፁዕነትህ በአንተ ፊት እንዲያዝንና እንዲጸጸት አሳምኜዋለሁ፡፡ ከእርሱ ጋር የተስማማነው ይኸን ነው፡፡ በዚህም ላይ አንተ እርሱን በጥንቃቄ ብታነጋግረው ንስሐውንና ጸጸቱን የበለጠ ሥር እንዲሰድድና ጥልቅ እንዲሆን ትረዳዋለህ፤ አንተ የነፍሳት ታላቅ ፈዋሽ ነህና፡፡ እንደዚሁም በቀኖናው መሠረት አንተ ተገቢ ነው ለምትለው ጊዜ ያህል ቀኖና ስጠው፡፡ በምትሰጠው የቀኖና ጊዜ ውስጥም ንስሐው ምን ያህል እውነተኛ እንደ ሆነና እምነት የሚጣልበት ስለ መሆኑ ሁኔታውን በሚገባ ታየዋለህ፡፡ የሚሰጠውን የንስሐ ጊዜ የሚወስነውም ስለ ኃጢአቱ የሚያደርገው ንስሐና የልቡ መጸጸት እውነተኛነት መሆን አለበት፡፡"**

  (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ መልእክት ኀበ ጳጳስ ቴዎዶር ዘቲያና (Theodore of Tyana)፣ ቁ. 163)

- *"ቅንጦትንና ድሎትን በመተው ራስን ወደ መግዛትና በመጠን ወደ መኖር እንሂድ፡፡ ይህ ጊዜ በእውነት ገና ላልተጠመቁትም[96] ሆነ ለተጠመቁት የንስሐ ጊዜ ነውና፡፡ ይህም የተጠመቁት ንስሐ ገብተውና ቀኖናቸውን ፈጽመው ከቅዱሳት ምሥጢራት ይሳተፉ ዘንድ ነው፤ ለእነዚያ ደግሞ ኃጢአታቸውን በጥምቀት ካጠቡ በኋላ ወደዚህ ምሥጢር በንጹሕ ሕሊና ይቀርቡ ዘንድ ነው፡፡ ስለሆነም ይህን የለሰለሰና የቅምጥልነት የአኗኗር ልማድ እንተው፡፡ ንስሐ መግባትና ቀኖና መቀበልን እና በድሎት መኖርን ሁለቱንም በአንድ ጊዜ ማድረግ አይቻልምና፡፡ ይህንም ዮሐንስ [መጥምቅ] በልብሱ፣ በምግቡ፣ በመኖሪያው ያስተምርሀ፡፡ እንዲህ ያለ ተጋድሎና*

[96] (The uninitiated)

አኗኗር እንድንኖር ታዝዘናለህን? ትለኝ ይሆናል፡፡ ቢሆን ጥሩ ነው ብዬ እነግራችኋለሁ፣ እመክራችኋለሁ እንጂ እንደ ትእዛዝስ አላዝዛችሁም፡፡ ሆኖም ይህ የማይቻልህ ከሆነ ቢያንስ ቀኖና በመቀበል ንስሐ ግባ፤ የእግዚአብሔር ፍርድ በደጅ ደርሷልና፡፡ ፍርዱ ገና ቢሆን እንኳ የእያንዳንዱ ሰው ሕይወት የራሱ ፍጻሜ ነውና ገና ነው ብሎ ልብን ማደንደንና ተዘልሎ መቀመጥ አይገባንም፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌለ ማቴዎስ፣ ክፍለ ትምህርት 10፣ ቁ. 6)

- "ከቅዱሳት ምሥጢራት ለመካፈል እንችል ዘንድ ራሳችንን ሳናዘጋጅ በግዴለሽነት ዝም ብለን እንዲህ አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ እዚህ ለቆምነው ለእኛ ለእያንዳንዳችንም ለሁላችንም በዚህ ቅጽበት [እግዚአብሔር] የሚናገረን ቃል ይህ ነው፡፡ ከቅዱሳት ምሥጢራት የማይካፈል ሰው እዚህ የቆመው ኀፍረት የለሽ በሆነ ድፍረት ነው፡፡ በኃጢአት የወደቁና በኃጢአት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች፣ ንስሐ ገብተው ቀኖናቸውን ያልፈጸሙ ሰዎች ከሁሉ አስቀድሞ ከዚህ ምሥጢር እንዲርቁ የሚደረገው ስለዚህ ነው፤ አንድ ጌታ ወይም ባለ ሥልጣን በማዕድ ላይ ሲቀመጥ እርሱን ያስቀየሙት አገልጋዮች በዚያ በማዕዱ አብረውት ይሆኑ ዘንድ ተገቢ አይደለም፣ እርሱም አይፈቅድላቸውም፡፡ በዚህም እንደዚሁ ነው፣ መሥዋዕቱ ሲሰዋ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር በግ ሲሠዋ፣ ዲያቆን "ጸልዩ" ሲል ስትሰማ፣ መጋረጃው ሲገለጥ፣ ሰማያት ከላይ እንዳሉ ወደ መሬት የወረዱ ሲመስልና መላእክት ሲወርዱ በዓይን ሕሊናህ እስብ!" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ኤፌሶን፣ ክፍለ ትምህርት 3)

- "ከመጀመሪያ መልካም የሆነውን ነገር አለመምረጥ ክፉ ነገር ነው፣ መልካም ባልሆነው መንገድ መሄድ ከጀመሩ በኋላ አለመመለስ ደግሞ የበለጠ ክፉና የከበደ ዕዳ ነው፡፡ ሰውን ክፉና ብልሹ የሚያደርገው ከማንኛውም ነገር በላይ ይህ ነው፡፡ ሆኖም ማንም ሰው እንዲህ አይሁን፣ ምንም ዓይነት የመጨረሻ ጥልቅ በሆነ የኃጢአት ጉድጓድ ውስጥ ቢገባ እንኳ ከዚያ ሊወጣና ወደ መልካም ሊቀየር የሚችል ስለ መሆኑ ተስፋ አይቁረጥ፡፡ ከኃጢአት የመጨረሻ ጥልቅ ደረጃ እንኳ ቢሆን መነሣት ቀላል ነገር ነውና፡፡ በነውሯና በኃጢአቷ ከሁሉም በላይ የነበረችው ያች አመንዝራ በተጋድሎዋና በመንፈሳዊነቷ ሁሉንም እንዳስናቀቻቸው አልሰማችሁምን? በወንጌል የተነገረችውን አመንዝራ ሴት ማለቴ አይደለም፣ በእኛ ዘመን ያለችውንና የመጨረሻ ብልሹ ከሆነው ከተማ ከፊንቄ የመጣችውን ማለቴ እንጂ፡፡ እርሷ ቀድሞ አመንዝራ የነበረች፣ በመድረክ ትወና በጣም ታዋቂና ስመ ጥር የነበረች፣ ስሟም በእኛ ከተማ ብቻ ሳይሆን በኪልቅያና በቀጰዶቅያ ሁሉ ይታወቅ ነበርና፡፡ ብዙ ትዳሮችን አፍርሳለች፣ ብዙ ቤተሰብ በትናለች፣ በጥንቆላና በምትሃት የሚከሷትም ብዙዎች ነበሩ፡፡ ይህን ሁሉ የምታደርገው በውበቷ ብቻ ሳይሆን በመድኃኒቶቿ (በመተቷ) ጭምር ነው ይሏት ነበር፡፡ ይህቺ አመንዝራ የንግሥቲቱን ወንድም እስከ ማሸነፍ ደርሳ ነበር፤ የእርሷ ወጥመድነት ታላቅ ነበርና፡፡

"ነገር ግን እጅግ አስገራሚ በሆነ ሁኔታ በአንድ ጊዜ ያን ሁሉ ነገር እርግፍ አድርጋ በመተው የዲያብሎስን ጓዝና ጣጣ ሁሉ አሽቀንጥራ በመጣል የእግዚአብሔር ጸጋ በእርሷ ላይ እንዲመጣ አደረገች፣ ወደ ሰማይ ወጣች፡፡ በመድረክ ላይ ስትተውን ከእርሷ የከፋ ሌላ ብልሹ ሰው አልነበረም፡፡ ሆኖም በኋላ ግን በንጽሕናዋና በትህርምቷ፣ የሚኮሰኩስ ማቅ በመልበስ ብዙዎችን በለጠቻቸው፣ በመንፈሳዊ ተጋድሎም አልፋቸው ሄደች፡፡ ቀሪ ሕይወቷን ሁሉ እንዲህ ባለ ትህርምትና ተጋድሎ ኖረች፡፡ ከዚች ሴት የተነሣ አገረ ገዢው በግድ ወደ መድረክ ትወናዋ ይመልሷት ዘንድ ወታደሮችን ቢያዝዝም ወደ መድረኩ ያወጧት ዘንድ ኃይል ግን አልነበራቸውም፣ እርሷን ከተቀበሏትና አብራቸው ከምትኖራቸው ከደናግል መካከልም ለይተው ሊወስዷት አልተቻላቸውም፡፡

"ይህች ሴት ከማይነገሩት ድንቅ የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት ምሥጢራት ለመሳተፍ የበቃች ሆና፣ እንዲሁም ለተቀበለችው ጸጋ ተገቢና ተስማሚ በሆነ ትጋትና ተጋድሎ ኖራ ሕይወቷን እንዲህ ባለ አስደናቂ ሁኔታ ፈጸመች፡፡ ከተጠመቀች በኋላ ታላቅ በሆነ ራስን መግዛትና ትህርምት ኖረች፡፡ በራሷ ላይ ዘግታ ብዙ ዓመታትን ብቻዋን በመሆን በእስር ቤት እንደ መኖር ያለ በሆነ ሁኔታ ኖረች፡፡ ስለዚህም "ኋለኞች ፊተኞች ይሆናሉ" እንደ ተባለው ሆነ፡፡ በመሆኑም በማንኛውም ጉዳይና ሁኔታ ጽኑና ቀናዒ የሆነ ልቡና ያስፈልገናል፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅና ምስጉን ከመሆን የሚያግደን ምንም ነገር የለምና፡፡ በኃጢአት ከሚኖሩ ማናቸውም ቢሆን ተስፋ አይቁረጥ፣ በመልካም ምግባር ሕይወት የሚኖር ማንም ደግሞ አይዘናጋ፡፡ በመልካም ምግባር ሕይወት የሚኖረውም ቢሆን እርግጠኛ አይሁን፣ አይተማመን፣ አመንዝራ የነበሩ ሊያልፉት ይችላሉና፡፡ ሌላውም ተስፋ አይቁረጥ፣ ከኋላ ተነሥቶ ፊተኞችን እንኳ ሳይቀር ሊያልፋቸው ይችላልና፡፡"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌለ ማቴዎስ፣ ክፍለ ትምህርት 67፣ ቁ. 3-4)

❖ "ክርስቶስ በስሜት ሕዋሳት ሊመረመሩና ሊታወቁ የሚችሉ ነገሮችን አይደለም የሰጠን፣ በሚታዩ ነገሮች አማካይነት የተሰጡንና የሚፈጸሙ ምሥጢራት ቢኖሩም እንኳ ሁሉንም ምሥጢራት በመንፈስ ሕሊና ሊታሰቡ በሚገባቸው ሁኔታ ነው ያደረገው፡፡ በጥምቀትም እንዲሁ ነው፣ በጥምቀት የሚሰጠው ጸጋ የሚከናወነውና የሚገኘው በሚታየው በውኃ አማካይነት ነው፤ የሚገኘውን የልጅነት ጸጋና ዳግም ተፈጥሮ የምናውቀው ግን በመንፈስ ነው፡፡ መንፈሳዊና ረቂቅ ሆነህ ቢሆን ኖሮ መንፈሳዊ የሆኑትን ጸጋዎች በግልጽ ሊሰጥህ ይችል ነበር፤ ነገር ግን ነፍስ በሥጋ ውስጥ የተሸፈነች ስለ ሆነች በመንፈስ አእምሮ ልትረዳቸው የምትችላቸውን ነገሮች በሚታዩ ነገሮች አንጻር (አማካይነት) ሰጠህ፡፡ አሁን ካለነው ሰዎች ምነው የጌታችንን ገጹን ባየሁት፣ ልብሶቹን ባየኋቸው፣ በዳሰስኋቸው ብለው የሚመኙ ብዙዎች አሉ፡፡ እርሱን እያያችሁት እኮ ነው፣ እየዳሰሳችሁት ነው፣ እየበላችሁት ነው፡፡ እናንተ ልብሶቹን ለማየት ትመኛላችሁ፣ እርሱ ግን ራሱን የሰጣችሁ እንድታዩት ብቻ ሳይሆን እንድትዳስሱትም፣ እንድትበሉትና በውስጣችሁ እንድትቀበሉትም ጭምር ነው፡፡

"ስለዚህም ማንም ሰው እንዲሁ በግድ የለሽነትና ያለ ጥንቃቄ፣ እንዲሁም በዛለ ልቡናና መንፈስ ሆኖ አይቅረብ፤ በሚቃጠል መንፈስ፣ ከፍ ከፍ ባለ ልቡና ሆኖ እንጂ፡፡ አይሁድ እንኳ የፋሲካውን በግ በበሉ ጊዜ ቆመው፣ ጫማቸውን ተጫምተው፣ በትራቸውን በእጃቸው ይዘው በችኮላ የበሉ ከሆነ፣ እናንተ ከዚያ እጅግ በበለጠ ሁኔታ በጥንቃቄና በፍርሃት ልትቀርቡ ይገባችኋል፡፡ እነርሱ (እስራኤላውያን) ወደ ምድረ ፍልስጥዔም ለመጓዝ ያን ያህል ዝግጅትና ጥንቃቄ ካስፈለጋቸው፣ ስለዚህም ነበር የመንገደኛ ልብስ የለበሱት፤ እናንተ ግን የምትጓዙት ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደ መሆኑ ከእነዚያ የበለጠ ዝግጅት ያስፈልገናል፡፡ ስለሆነም በሁሉም ነገር ጠንቃቆችና አስተዋዮች መሆን ይገባናል፤ ራሳቸውን በንስሐ ሳያዘጋጁና በቀኖናው መሠረት የሚገባውን ቀኖና ተቀብለው ሳይፈጽሙ ከዚህ ምሥጢር ለሚካፈሉ ሰዎች የተዘጋጀላቸው ቅጣት ከባድ ነውና፡፡"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌለ ማቴዎስ፣ ክፍለ ትምህርት 87፣ ቁ. 4-5)

❖ "ነቢዩ ናታን ንጉሥ ዳዊትን ኃጢአቱን ከነገረው በኋላ ወዲያውኑ ኃጢአቱን እንዳመነ አጽናንቶት ነበር፡፡ ሆኖም ብፁዕ ዳዊት ግን ምንም እንኳ 'እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልሃል፣ አትሞትም' (2 ሳሙ. 12፥13) የሚለውን የነቢዩን ቃል የሰማ ቢሆንም 'ንስሐ ከመግባት ግን አልተመለሰም፡፡ ንጉሥ የነበረ ቢሆንም በልብሰ መንግሥት ፋንታ አመድ ለበሰ፣ በወርቅ ዙፋን ላይ በመቀመጥ ፋንታ በመሬት ላይ፣ ያውም በአመድ ላይ ተቀመጠ፡፡

በአመድ ላይ የተቀመጠ ብቻ ሳይሆን አመድንም ምግቡ አደረገ፣ እርሱ ራሱ "አመድን እንደ እህል ቅሜያለሁና፣ መጠጤንም ከእንባዬ ጋር ቀላቅያለሁና" (መዝ. 101፥9) ብሏልና፡፡ ወደ ኃጢአት የተመለከተው ዓይኑ በዕንባ እስኪሟሟ ደረሰ፤ "ሌሊቱን ሁሉ አልጋዬን አጥባለሁ፣ በዕንባዬም መኝታዬን አርሳለሁ፤ ዓይኔ ከቍጣ ዕንባ የተነሣ ታወከች" እንዳለ፡፡ መዝ. 6፡ 6-7 መኳንንቱ እህል እንዲቀምስ በለመኑት ጊዜ እንኳ አልሰማቸውም፡፡ ጾሙን እስከ ሰባት ሙሉ ቀናት አራዘመ፡፡ ንጉሥ የነበረው እርሱ እንዲያ ባለ ሁኔታ ንስሐ ከገባ ተራ ግለሰብ የሆንከው አንተ ንስሐ ልትገባና ልትናዘዝ አይገባህምን?" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 2፡ በእንተ ንስሐ ወሥርየተ ኀጢአት፣ ቁ. 12)

- ❖ "በንስሐ ስለ ዳኑ ሰዎች አስታውስህ ዘንድ ከእኔ ጋር እንዲህ ወዳለው ጉዳይ በመንፈስ ና፡፡ ምናልባት ከሴቶች መካከልም አንዳንዶች 'እኔ በዝሙት ወድቄያለሁ፣ ሰውነቴን በሁሉም የኃጢአት ዓይነት አሳድፌያለሁ፤ ታዲያ እኔ መዳን እችላለሁን?' የሚሉ ይኖሩ ይሆናል፡፡ እንዲህ የምትሉ ሴቶች ካላችሁ፣ ዓይናችሁን ወደ ረአብ (ራኬብ) መልሱ፡፡ በይፋ በአደባባይ አመንዝራ የነበረችው እርሷ እንኳ በንስሐ የዳነች ከሆነ፣ በሆነ ክስተት ወይም ሁኔታ የወደቀች ብትኖር በንስሐ እና በጾም አትድንምን? እርሷ እንዴት እንደ ዳነች እናስተውል፤ *'የእናንተ አምላክ በሰማይም በምድርም ያለው ገናና አምላክ እርሱ ነውና'* አለች፡፡ ከሕይወቷ የነሰቀለ መሆን የተነሣ የእኔ አምላክ ለማለት አልደፈረችም፡፡ እርሷ የዳነች ስለ መሆኗ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምስክር ከፈለግህ በመዝሙር ላይ ተጽፎ ታገኘዋለህ፡- "እዜክሮን ለረአብ ወለባቢሎን እለ የአምራኒ - የሚያውቁኝን ረዓብንና ባቢሎንን አስባቸዋለሁ" ተብሎ፡፡ መዝ. 86፥4 የእግዚአብሔር ሰውን መውደዱና ደግነቱ ምን ያህል ድንቅ ነው! አመንዝራዎችን እንኳ ሳይቀር በቅዱሳት መጻሕፍት መጥቀሱና ስለ እነርሱ መናገሩ፤ 'ረዓብንና ባቢሎንን አስባቸዋለሁ' ብቻ አይደለም ያለው፣ "የሚያውቁኝን - ከሚያውቁኝ መካከል" አለ እንጂ፡፡ ስለዚህም ለወንዶችም ለሴቶችም በንስሐ የሚገኘው ሕይወት የተዘጋጀ ሆኖ አለ፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 2፤ በእንተ ንስሐ ወሥርየተ ኃጢአት ወጸላኢ፣ ቁ. 9)

የዛሬን አያድርገውና ጠንካራ የክርስትና መዲና የበረችው የሰሜን አፍሪካዋ የቅርጣግና (ካርቴጅ - የዛሬዋ ቱኒዚያ ውስጥ) ጳጳስ የነበረው ሰማዕቱ ቅዱስ ቆጵርያኖስ በዘመኑ ከገጠሙት ጉዳዮች አንዱ በቤተ ክርስቲያን ላይ በተነሣው መከራ ምክንያት የታሠሩና ሰማዕትነትን የተቀበሉ ጽኑዓን ክርስቲያኖች እንደ ነበሩ ሁሉ ከፍርሃትና ከሥጋ ድክመት የተነሣ ክርስቶስን የካዱና ራሳቸው በቀጥታ ለጣዖት ባይሠውም ነገር ግን መሥዋዕት እንዳቀረቡ የሚገልጽ የምስክር ወረቀት የተቀበሉ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን አመላለሳቸውና ወደ ምሥጢረ ቁርባን አቀራረባቸው ጉዳይ ነበር፡፡ ንስሐ ሲገቡ ወደ ቤተ ክርስቲያን አመላለሳቸውና ወደ ምሥጢራት አቀራረባቸው ጉዳይ ለተወሰኑ ዘመናት ውዝግቦችን ፈጥሮ ነበር፡፡ በፊት ክርስቶስን ከካዱትና በኋላ መመለስ ከሚፈልጉት ሰዎች መካከል ቀኖና ሳንቀበል እንዲሁ ዝም ብለን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንቀላቀል፤ ወደ ምሥጢራት ከመቅረብም አንከልክል እያሉ የሚያስቸግሩ አንዳንዶች ነበሩ፡፡ አንዳንድ ካህናትና ዲያቆናትም እነዚያን ሰዎች በወንጌልና በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ተገቢውን ቀኖና ሳይቀበሉና ሳይፈጽሙ እንዲሁ ዝም ብለው ሊቀበሏቸው የሚሞክሩ ነበሩ፡፡

ስለዚህም ጳጳሱ ቅዱስ ቆጵርያኖስ ዐላውያን ባስነሡት መከራ በስደት ላይ ካለበት ሆኖ እንዲህ የሚል መልእክት ላከላቸው፡-

- "... የእያንዳንዳቸውን የኃጢአታቸውን ዓይነትና ምንነት መመርመርና ማስተዋል ይኖርባችኋል፡፡ አለበለዚያ እንዲሁ ሳንመረምር ዝም ብለን ብንቀበላቸው ቤተ ክርስቲያናችን ሌላው ቀርቶ በአሕዛብ ዘንድ እንኳ ትንቀፍብናለች፣ ታፍርብናለችም፡፡ እንዲሁ ዝም ብሎ "እነ እገሌ ከጓደኞቻቸው ጋር ይመለሱ፣ ተቀበሏቸው" የሚል ደብዳቤ መስጠት የማይመለከታቸው ሰዎች አብረው ሾልከው እንዲገቡ ሰፊ በር መክፈት ነውና፡፡ ስለዚህም ምክንያት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመለሱትንና ወደ ምሥጢራት እንዲቀርቡ የምትፈቅዱላቸውን ሰዎች እናንተው ራሳችሁ በሚገባ ያያችኋቸውን፣ ያወቃችኋቸውን፣ ንስሐቸውንና ቀኖናቸውን አፈጻጸማቸው ወደሚፈለገው ደረጃ የቀረበ የሆኑትን ብቻ እንዲሆን እለምናችኋለሁ፡፡"

(ሰማዕቱ ቅዱስ ቆጵርያኖስ፣ መልእክት ቁ. 14)

እንዲሁም ቀኖናቸውን ሳይፈጽሙ ወደ ምሥጢራት እንዲቀርቡ ማድረግ ታላቅ ስሁተት መሆኑን ይኸው አባት በአሥረኛው መልእክቱ በአጽንኦት ያስረዳል፡፡ ይህን ሊያደርጉ የደፈሩ አንዳንድ ካህናት ነበሩና እንዲህ ይላል፡-

- "... በፈተናው ጊዜ ክርስቶስን ክካዱት መካከል ለአንዳንዶቹ የመከራው ጊዜ እንዳለቀ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመለሱ ይፈቀድላቸው ዘንድ የሚጠይቁ ደብዳቤዎችን ልካችሁልኛል፡፡ መከራው ቆም ሲል ከካህናቱ ጋር ጉባኤ እናደርጋለን፡፡ ሆኖም ግን እነዚያ ካህናት ከወንጌል ሕግ ተቃራኒ በሆነ መንገድ የካዱት ሰዎች ቀኖናቸውን ሳይጨርሱ፣ እጅግ ከባድና አስቃቂ የሆነውን የኃጢአታቸውን የንስሐ ጊዜ ሳይፈጽሙ፣ በተነሣሒው ላይ ጳጳሳትና ካህናት እጃቸውን ሳይጭኑለትና ሥርየትን ሳይሰጡት፣ እንዲሁም ወደ ምሥጢራት እንዲቀርብ ሳይፈቅዱለት ቅዱስ ቁርባንን ሊያቀብሏቸው ይደፍራሉ፡፡ ይህ ግን 'ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት' ተብሎ በቅዱስ መጽሐፍ የተጻፈ ሆኖ ሳለ የእነርሱ ድርጊት ግን ቅዱሱን የጌታችንን ሰውነት አለማክበርና ማቃለል ነው፡፡ 1 ቆሮ. 11፥27"

(ሰማዕቱ ቅዱስ ቆጵርያኖስ፣ መልእክት ቁ. 10)

- "እናንተ ከክፉ ግብራችሁ ስለ መመለሳችሁና ስሁተታችሁን ስለ ማረማችሁ ለማረጋገጥ እያንዳንዳችሁን በግላችሁ ሳገኛችሁ ከዚህ ስሁተቱ ያልተመለሰና ያልታረመ ማንንም ሰው ካገኘሁ ከቅዱሳት ምሥጢራት ለጊዜው በመከልከል እቀጣዋለሁ፡፡ ይህም ሁል ጊዜ ተከልክለው እንዲቀሩ ሳይሆን ራሳቸውን አስተካክለው በንጹሕ ሕሊና ወደ ቅዱሱ ምሥጢር ይቀርቡና ይቀበሉ ዘንድ ነው፤ እውነተኛ የሆነ ከቅዱስ ቁርባን መቀበል ማለት ይህ ነውና፡፡ አገልግሎቱን በሚፈጽሙት አባቶቻችን ጸሎት፣ በሁሉም ቅዱሳን ጸሎት፣ እነዚህንና ሌሎችንም ድክመቶቻችንን አስተካክለን መንግሥተ ሰማይን እንወርስ ዘንድ ነው ..." (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 20፣ ቁ. 24)

- "እኛ ግን ከሕጉ ብንለይ ትእዛዙንም ብናፈርስ መኖሪያችን እሳቱ በማይጠፋበት ትሉ በማያንቀላፋበት በዘላለም ኩነኔ ውስጥ ይሆናል፡፡ . . . ጌታ ሕጉን መጠበቃችንን ነው እንጂ ከእኛ ከባድ ሥራ አልፈለገም፤ ብንበድልም ልባችንን እናጽና፣ ፊጥንን ወደ ንስሐ እንመለስ እንጂ . . . የካህኑን ትእዛዙን ተግሣፁን እንሰቀቅ፤ ነፍስን የሚያድን ባለ መድኃኒት ነውና፡፡ . . ." (ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 1-3)

## 4.3.4 ማጠቃለያ

ተሐድሶዎች በተለመደው የማደባለቅና የማጭበርበር ተግባራቸው ንስሐ መግባትንና ቀኖና መቀበልን በራሱ አዳኝ መንገድ እንደ ሆነና የክርስቶስን መድኃኒትነት ትቶ ሌላ የመዳኛ መንገድ እንደሆነ አስመስለው ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ ለዚህም እንዲህ ያሉትን እንመልከት፡-

- "ያነጻን የደሙ መፍሰስና የእኛም ይህን አምኖ መቀበል እንጂ ሌላ በዓይነ ሥጋ የሚታይ አፍአዊ ሥርዓት መፈጸም አለመሆኑን የተረዳው ኤፍሬም ሶርያዊ ፡- "ብውኂዘ ደሙ ቅዱስ አንጽሖሙ ለመሃይምናን ወለሕዝብ ንጹኃን - በክቡር ደሙ መፍሰስ ያመኑትንና ንጹሐን የሆኑትን ወገኖች አነጻቸው" ብሏል፡፡ (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 149)

በመጀመሪያ ያነጻን የክርስቶስ የደሙ መፍሰስና የሥጋው መቆረስ መሆኑን የተረዳው ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያን ቅዱሳን አባቶቻችን ናቸው፡፡ በቅዱሳን መካከልም ክፍፍል ለመፍጠር አስበው ይሆን? በንስሐ ሂደት ውስጥ በንስሐ አባት የሚሰጠውን ቀኖና በተመለከተ እነ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ "የካህኑን ትእዛዙን ተግሣፁን አንሰቀቅ፣ ነፍስን የሚያድን ባለ መድኃኒት ነውና" በማለት፣ እነ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት የአንድን ተነሣሒ ክርስቲያን ቀኖና በተመለከተ "በቀኖናው መሠረት አንተ ተገቢ ነው ለምትለው ጊዜ ያህል ቀኖና ስጠው፡፡ በምትሰጠው የቀኖና ጊዜ ውስጥም ንስሐው ምን ያህል እውነተኛ እንደ ሆነና እምነት የሚጣልበት ስለ መሆኑ ሁኔታውን በሚገባ ታየዋለህ፡፡ የሚሰጠውን የንስሐ ጊዜ የሚወስነውም ስለ ኃጢአቱ የሚያደርገው ንስሐና የልቡ መጸጸት እውነተኛነት መሆን አለበት" በማለት፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ደግሞ "ቀኖና በመቀበል ንስሐ ግባ" በማለት፣ እንዲሁም "ንስሐ ገብተው ቀኖናቸውን ያልፈጸሙ ሰዎች ከሁሉ አስቀድሞ ከዚህ ምሥጢር [ከቅዱስ ቁርባን] እንዲርቁ የሚደረገው ስለዚህ ነው" እያለ፣ ሰማዕቱ ቅዱስ ቆጵርያኖስ ደግሞ "ስለዚህም ምክንያት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመለሱትንና ወደ ምሥጢራት እንዲቀርቡ የምትፈቅዱላቸውን ሰዎች እናንተው ራሳችሁ [ካህናቱን] በሚገባ ያያችኋቸውን፣ ያወቃችኋቸውን፣ ንስሐቸውና ቀኖናቸውን አፈጻጸማቸው ወደሚፈለገው ደረጃ የቀረበ የሆኑትን ብቻ እንዲሆን እለምናችኋለሁ" እያሉ ማስተማራቸው ድኅነት የሚገኘው ከክርስቶስ ውጭ በሚፈጸም አፍአዊ ሥርዓት ነው ማለታቸው ኖሯልን? ይቅር ይበላቸው!

ይልቁንም እነዚህና ሌሎቹም በዚህ ያልጠቀስናቸው ኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን አንድ ሰው በኃጢአት ሲደናቀፍ ንስሐ እንዲገባ፣ ንስሐ ሲገባም ለእግዚአብሔር እንደሚናዘዘው ሁሉ ለንስሐ አባቱ በመናዘዝ ተገቢውን ቀኖና ተቀብሎ ከካህናት እጅ ሥርየትን ተቀብሎ በንጹሕ ሕሊና ወደ ቅዱስ ቁርባን እንዲቀርብ ያስተማሩት አንደኛ ከቅዱሳን ሐዋርያት የተቀበሉት ሥርዓት እንዲህ በመሆኑ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ቅዱስ ቁርባኑ አማናዊ የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መሆኑን ስለሚያምኑ ነው፡፡ ተሐድሶዎች ግን የቅዱስ ቁርባንን አማናዊነት ስለማያምኑ ሊላው ክህደታቸው ሁሉ ከዚሁ ዐቢይ ክህደት የሚፈልቅ ክህደት ነው፡፡

እዚህ ላይ ተሐድሶዎች ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ አለ ብለው የጠቀሱትን ነገር እንመልከት፡-

- "መፍትው ለነ ናዑቅ እበሳነ አኮ በልሳንነ ባሕቲቱ አላ በሕሊናነሂ ምስለ ገዐር ወክዒወ ልብ እንዘ ናዜክር ኩሎ ኃጣውኢነ በበገጹ ወአኮ ዘእብለከ ከመ ትክሥት ርእሰከ ወኢከመ ትሕምያ ለንበ ካልዓን አላ ተአዘዝ ለነቢይ ዘይቤ "ክሥት ለእግዚአብሔር ፍኖተከ" ወተአመን ባቲ ወንበ መኮንን አይድዕ ጌጋየከ እንዘ ትስእል ወታስተበቍዕ፡፡ ትርጉም - ከጭንቀትና ልብን ከማፍሰስ ጋር ኃጢአታችንን ሁሉ በየሲማው (በየመልኩ) እያሳሰብን በአንደበታችን ብቻ ሳይሆን በመላው አሳባችን በደላችንን እናስታውቅ ዘንድ አግባብ ነው፡፡ ይህንም ስልህ ራስህን ለማናቸውም እንድትገልጥ ወይም በሌሎች ዘንድ ነፍስህን ሊሐሜት አሳልፈህ እንድትሰጥ ማለቴ አይደለም፡፡ ነገር ግን "መንገድህን ለእግዚአብሔር የተገለጸ አድርግ" ለሚለው ለነቢይ ቃል ታዘዝ፡- በእርስዋም እምነህ ተዳኝ (ተናዘዝ)፡፡ በልመናና በምልጃም በደልህን ለጻድቁ ፈራጅ ተናገር፡፡ (መዝ. 36፡5) (ስምዐ ጽድቅ ብሔራዊ፣ ገጽ 157-158) (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 152)

በዚህ የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ነው ተብሎ በቀረበው ጥቅስ ላይ ብዙ ነገሮችን እንመለከታለን፡፡ እነዚህም

1) ጥቅሱ የቀረበው የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ነው ተብሎ ነው፤ ምንጭ ተደርጎ የቀረበው ግን "ስምዐ ጽድቅ ብሔራዊ" የተባለው የጮራ መጽሔት አዘጋጅና የተሐድሶ አቀንቃኝ የነበረው የመሠረት ስብሐት ለአብ መጽሐፍ ነው፡፡ ታዲያ የጥቅሱ ባለቤትና የጥቅሱ ምንጭ መች ተገጣጠመ! ወይ መሠረት ስብሐት ለአብ አለው በሉ! አለበለዚያ በታላቁ ቅዱስ አባት ስምና ሽፋን የፕሮቴስታንቱን የመሠረት ስብሐት ለአብን ሃሳብ ለማስተላለፍ አትሞክሩ፡፡ የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ከሆነም ከምንጩ ፈልጎ መጥቀስ ይገባል እንጂ እንደ ልማዳችሁ ከተሐድሶ ምንጮች እየጨለፉ ማደፍረስ ተገቢ አይደለም፡፡

2) ሌላው ደግሞ ግእዙ ወደ አማርኛ ሲተረጎም የአተረጓጎም ሸፍጥ ያለበት መሆኑ ነው፡፡ በግእዙ "ወኢኮ ዘእብለከ ከመ ትክሥት ርእሰከ ወኢከመ ትሕምያ ለኀበ ካልዓን" የሚለው ወደ አማርኛ የተመለሰው "ይህንም ስልህ ራስህን ለማናቸውም እንድትገልጥ ወይም በሌሎች ዘንድ ነፍስህን ለሐሜት አሳልፈህ እንድትሰጥ ማለቴ አይደለም" ተብሎ ነው፡፡ "ወኢኮ ዘእብለከ ከመ ትክሥት ርእሰከ ወኢከመ ትሕምያ ለኀበ ካልዓን" የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉሙ "ይህንም የምልህ ራስህን ትገልጥ ዘንድ ወይም በሌሎች ትወቀሳትና ትከሰሳት ዘንድ አይደለም" ነው፡፡ በዚህ ትክክለኛ መንፈሱ ሲታይ ለካህን ንስሐ መግባትንና መናዘዝን የሚነቅፍ ወይም የሚከለክል አይደለም፡፡ ምክንያቱም አንደኛ ተነሣሒ ለካህኑ የሚናዘዘው ለእግዚአብሔር የመናዘዙ አካል ነው እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ ሁለተኛም "ወኢከመ ትሕምያ ለኀበ ካልዓን" ሲል ካህኑ የእግዚአብሔር መልእክተኛ እንደ መሆኑ ለካህኑ መንገር ለሌሎች ሰዎች እንደ መንገር አይደለምና ለካህኑ አትናዘዝ ማለት ነው አያሰኝም፡፡

3) ጥቅሱ የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ትምህርት ነው ቢባልም እንኳ ችግር የለውም፡፡ ምክንያቱም እዚህ ላይ ሊቁ ማተኮር የፈለገው ኃጢአተኛነትን ስለ መታመንና ለእግዚአብሔር ስለ መናዘዝ ነው እንጂ ለካህን መናዘዝንና ቀኖና መቀበልን መንቀፉ ወይም መከልከሉ አይደለም፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በዚህ ጉዳይ ላይ ያስተማራቸውን ብዙ ትምህርቶች ስናስታውስ ከእነዚያ ጋር የሚቃረን ሌላ ትምህርት ማስተማሩ እንዳልሆነ እንረዳለንና፡፡ ለዚህ እንዲረዳን ከላይ የጠቀስናቸውን አጠር አጠር አድርገን እናስታውሳቸው፡-

- " . . . ይህ ጊዜ በእውነት ገና ላልተጠመቁትም[97] ሆነ ለተጠመቁት የንስሐ ጊዜ ነውና፡፡ *ይህም የተጠመቁት ንስሐ ገብተውና ቀኖናቸውን ፈጽመው ከቅዱሳት ምሥጢራት ይሳተፉ ዘንድ ነው፤* ለእነዚያ ደግሞ ኃጢአታቸውን በጥምቀት ካጠቡ በኋላ ወደዚህ ምሥዋዕ በንጹሕ ሕሊና ይቀርቡ ዘንድ ነው፡፡ ስለሆነም ይህን የለሰለሰና የቅምጥልነት የአኗኗር ልማድ እንተው፡፡ ንስሐ መግባትና ቀኖና መቀበልን እና በድሎት መኖርን ሁለቱንም በአንድ ጊዜ ማድረግ አይቻልምና፡፡ . . . ቀኖና በመቀበል ንስሐ ግባ፤ የእግዚአብሔር ፍርድ በደጅ ደርሷልና፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌለ ማቴዎስ፣ ክፍለ ትምህርት 10፥ ቁ. 6)

[97](The uninitiated)

- "ቅዳሳት ምሥጢራት ለመካፈል እንችል ዘንድ ራሳችንን ሳናዘጋጅ በግዴለሽነት ዝም ብለን እንዲህ አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ እዚህ ለቆምነው ለእኛ ለእያንዳንዳችንም ለሁላችንም በዚህ ቅጽበት የሚናገረን ቃል ይህ ነው፡፡ . . . በኃጢአት የወደቁና በኃጢአት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች፣ ንስሐ ገብተው ቀኖናቸውን ያልፈጸሙ ሰዎች ከሁሉ አስቀድሞ ከዚህ ምሥጢር እንዲርቁ የሚደረገው ስለዚህ ነው፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ኤፌሶን፣ ክፍለ ትምህርት 3)

- ". . . አሁን ካለነው ሰዎች ምነው የጌታችንን ገጹን ባየሁት፣ ልብሶቹን ባየኋቸው፣ በዳሰስኋቸው ብለው የሚመኙ ብዙዎች አሉ፡፡ እርሱን እያያችሁት እኮ ነው፣ እየዳሰሳችሁት ነው፣ እየበላችሁት ነው፡፡ እናንተ ልብሶቹን ለማየት ትመኛላችሁ፣ እርሱ ግን ራሱን የሰጣችሁ እንድታዩት ብቻ ሳይሆን እንድትዳስሱትም፣ እንድትበሉትና በውስጣችሁ እንድትቀበሉትም ጭምር ነው፡፡ ስለዚህም ማንም ሰው እንዲሁ በግድ የለሽነትና ያለ ጥንቃቄ፣ እንዲሁም በዛለ ልቡናና መንፈስ ሆኖ አይቅረብ፤ በሚቃጠል መንፈስ፣ ከፍ ከፍ ባለ ልቡና ሆኖ እንጂ፡፡ ... ራሳቸውን በንስሐ ሳያዘጋጁና በቀኖናው መሠረት የሚገባውን ሳይፈጽሙ ከዚህ ምሥጢር ለሚካፈሉ ሰዎች የተዘጋጀላቸው ቅጣት ከባድ ነውና፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌለ ማቴዎስ፣ ክፍለ ትምህርት 87፣ ቁ. 4-5)

ስለዚህ ይህ ታላቅ አባት ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ንስሐ ገብቶ ቀኖና ተቀብሎ፣ የተቀበሉትን ቀኖናም ፈጽሞ አማናዊ ወደ ሆነው ቅዱስ ቁርባን መቅረብ የሚገባ መሆኑን እንዲህ በአጽንኦት ደግሞ ደጋግሞ አስተምሯል፡፡ ትምህርቱም ከነምንጩ እንዲህ ቀርቧል፡፡ ስለዚህ የቅዱሱ አባት እውነተኛ ትምህርት ይህ ነው እንጂ አንድ ምንጭ ላይ ብቻ፣ ያውም ከዳራው አውጥቶ ለመተርጎም በተደረገ ጥረት፣ በዚያውም ላይ ምንጩን ባለማሳየት እንዲሁ ይላል በማለት ብቻ በማቅረብ እውነተኛውን የመጽሐፍ ቅዱስና የአባቶቻችንን ትምህርት ለማስካድ መታገል የጥፋት ሠራተኛነት ነው፡፡ ስለሆነም ኃጢአትን ለካህን መናዘዝና ቀኖና መቀበል በመጽሐፍ ቅዱስ እና በቀደምት አበው ሊቃውንት ትምህርት በግልጽ ሁኔታ የተቀመጠ ትምህርት ነው፡፡ ይህን ትምህርት የሚቃወሙ ተሐድሶዎች ተቃውሟቸው እንዳችም መጽሐፍ ቅዱሳዊና የቀደምት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ድጋፍ የለውም፡፡

## 4.4 ማጠቃለያ - የክፍል አንድ

በክፍል አንድ ውስጥ ባሉት ሦስት ምዕራፎች ውስጥ በዋናነት ስለ መዳን ትምህርት ተመልክተናል፡፡ በዚህም ከተሐድሶ መናፍቃን ጋር ያለን መሠረታዊውና ዋናው ልዩነት በመዳን ትምህርት ላይ መሆኑን አይተናል፡፡ የሰውን ልጅ መዳን በተመለከተ በተሐድሶዎች በኩል ያሉት መሠረታዊ የስህተት ትምህርቶች ብዙ መሆናቸውንና እያንዳንዳቸውም ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቀደምት ኦርቶዶክሳውያን አባቶች አስተምህሮ አንጻር ተመዝነው ፍጹም ተቃራኒዎችና አፍራሾች ሆነው መገኘታቸው በመጽሐፍ ቅዱስና በቀደምት አበው ትምህርት ከበቂ በላይ (Beyond reasonable doubt) ተረጋግጧል፡፡

ለማጠቃለል በመዳን ትምህርት ዙሪያ የተሐድሶዎች ስህተቶችና ችግሮች በጣም ብዙ ቢሆኑም በሦስት ነጥቦች ዙሪያ ሊጠቀለሉ ይችላሉ፡፡ ይህም አንደኛው መዳንን ከኃጢአት ቅጣት ማምለጥ ብቻ አድርጎ የሚወስድና በመካከለኛው ዘመን ከነበረው የወንጀለኞች መቅጫ ሕግ አንጻር የተቃኘና በዚያ የተመሠረተ መሆኑ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ግን መዳን ከዚያ ባለፈ "ከመለኮቱ ባሕርይ ተካፋይ" እስከ መሆን የሚደርስ እጅግ ሰፊና ጥልቅ ነው፡፡ ኦርቶዶክሳዊ የመዳን ትምህርት "መዳን" ሲልና ፕሮቴስታንት መራሾቹ ተሐድሶዎች "መዳን" ሲሉ በውስጡ ያለው ነገር እጅግ የተለያየ መሆኑን አይተናል፡፡

ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ እያንዳንዱ ሰው ለመዳን ምን ማድረግ አለበት? በሚለው ጉዳይ ላይ ነው፡፡ እንደ ተሐድሶዎች ትምህርት ሰው የሚድነው "በእምነት ብቻ" ነው የሚሉ ሲሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ግን ሰው ለመዳን እምነት መጀመሪያ እንጂ መጨረሻ ነገር አለመሆኑን፣ "በእምነት ብቻ መዳን" የሚል ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሌለና መናፍቃን የፈጠሩት ሰው ሠራሽ ትምህርት መሆኑን፤ እንዲሁም መጀመሪያ ማመን፣ ቀጥሎም መጠመቅ፣ ከዚያም የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መቀበል ለመዳን የግድ አስፈላጊ ነገሮች መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ደጋግሞ በአጽንኦት የሚያስረዳን መሠረታዊ ትምህርት መሆኑን በሰፋት አይተናል፡፡ ከዚህ በኋላም በአንድ በኩል የተቀበሉትን የመዳን ጸጋ ለመጠበቅ፣ በሌላ በኩል ደግሞ "ለመዳን <u>በእርሱ እንድታድጉ</u> . . ." እንደ ተባለው መዳን ሕያው እንደ መሆኑ በሱታፌ አምላካዊነት ማደግም ስለሆነ በጾም፣ በጸሎት፣ በመንፈሳዊ ትጋት፣ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሱታፌ መጋደልን ይጠይቃል፡፡ "እስከ መጨረሻው የጸና እርሱ ይድናል" የተባለውን፣ እንዲሁም "እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን፣ የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ" የተባለውንና ይህን የመሰሉትን ሌሎችም ብዙ አምላካዊ ቃላት እናምናለንና፡፡

በመጨረሻም ክርስትና የመልካም ምግባር ሕይወትን ለመያዝና በዚያ ለማደግ የሚደረግ የዕድሜ ልክ ሂደት ነው፡፡ ክርስትና ጌታ በወንጌል "መንግሥተ ሰማያት በእርሻ ውስጥ የተሰወረውን መዝገብ ትመስላለች፤ ሰውም አግኝቶ ሰወረው፣ ከደስታውም የተነሣ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠና ያን እርሻ ገዛ" ብሎ የገለጸው ነው፡፡ የክርስትና ምንነት የገባው ሰው በእርሷ ውስጥ የተሰወረውን ክቡር ነገር ለማግኘት ሲል ደስ እያለው ያለውን ሁሉ እስኪሸጥ ድረስ ይደርሳል፡፡ ያለውን ሁሉ ሳይሸጥ ግን ያን የተሰወረ መዝገብ መግዛት አይችልም፡፡ ይህም በጥምቀት ተጀምሮ ከዚያ በኋላ በሚደረግ ተጋድሎ በሂደት የሚደረግ መንፈሳዊ ዕድገት ነው፡፡ ግቡም ከእግዚአብሔር ጋር መኖርና እርሱ "የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ" ብሎ የተናገረውን ፍጽምና ገንዘብ ማድረግ ነው፡፡ የክርስትና ሕይወት ዓላማው እግዚአብሔር በባሕርዩ ያሉትን ለእኛ ደግሞ በጸጋ ገንዘብ እናደርጋቸው ዘንድ በቸርነቱ የሰጠንን መልካም ነገሮች ለማግኘት ከሰው የሚጠበቀውን ነገር ሁሉ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ በኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ የቅድስናና የመልካም ምግባር ሕይወትን ገንዘብ ለማድረግ መጋደል መሠረታዊ ነገር ነው፡፡

ስለሆነም ክርስትናን ከመንፈሳዊ ተጋድሎ ነጥሎ ማየት አይቻልም፡፡ በብሉይ ኪዳን ከግብጽ ከወጡት እስራኤላውያን መካከል የተቆጠሩትና ብዛታቸው ይህን ያህል ነው ተብሎ በቁጥር መጽሐፍ (በኦሪት ዘኍልቁ) የተነገረን እድሜያቸው ከሃያ ዓመት በላይ የሆኑ ወንዶች ብቻ፣ ከእነዚያም መካከል ወደ ጦርነት መሄድና ከጠላት ጋር መዋጋት የሚችሉ ጤነኞችና አካለ ሙሉዎች፣ እንዲሁም ያልሸመገሉና ያልደከሙ ሰዎች ብቻ ነበሩ፡፡ በኦሪት ዘኍልቁ በምዕራፍ ሁለት ላይ "*ከእስራኤል ልጆች በየአባቶቻቸው ቤቶች የተቈጠሩ እነዚህ ናቸው፣ ከየሰፈሩ በየሠራዊቶቻቸው የተቈጠሩ ሁሉ ስድስት መቶ ሦስት ሺህ አምስት መቶ አምሳ (603,550) ነበሩ*" ይላል፡፡ ዘኍ. 2፡32 ሆኖም ከግብጽ የወጡት የአጠቃላይ የሕዝቡ ቁጥር ግን ቢያንስ የእነዚያን ያህል ሴቶች (ሚስቶቻቸውን)፣ ሕፃናትን፣ ሽማግሌዎችንና ደካሞችን ስንጨምርበት ከአንድ ሚሊዮን በላይ ይሆናል፡፡ ሆኖም የተቆጠሩት ግን ወደ ጦር መዝመትና ከጠላት ጋር መዋጋት የሚችሉት ብቻ ነበሩ፡፡ ያ ለክርስትና ሕይወት ምሳሌ ነበር፡፡ የክርስትና ሕይወትም ክርኩሳን መናፍስትና ከእኩያት ፍትወታት ጋር የሚደረግ ረቂቅና መንፈሳዊ ውጊያ መሆኑን አመልካች ነበር፡፡ ያን ጊዜ ተቆጥረው በኦሪት ዘኍልቁ የተጻፉት የሚዋጉት ብቻ እንደ ነበሩ ሁሉ ዛሬም በእግዚአብሔር ፊት የሚቆጠሩትና በሕይወት መጽሐፍ የሚጻፉት መንፈሳዊ ተጋድሎ የሚጋደሉ ብቻ ናቸው፡፡ ክርስትና ከመንፈሳዊ ተጋድሎ ተነጥሎ ሊታይ አይችልምና፡፡

ክርስትና በየዕለቱ ከክፉ ፍላጎቶችና ከክፉ መናፍስት ጋር የሚደረግ የዕድሜ ልክ ተጋድሎ ነውና፡፡ ለስም አጠራሩ ምስጋና ይግባውና ጌታችንና አምላካችን መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስም "ለሁሉም እንዲህ አላቸው፡- በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ፣ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ" ያለው ለዚህ ነው፡፡ ሉቃ. 9፡23 ክርስትና የአንድ ሰሞን ሳይሆን የዕለት ተዕለት መስቀል መሸከም (ተጋድሎ መንፈሳዊ) ነውና፡፡ ክርስትና የየዕለት ሰማዕትነት የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል የገለጸው ይህንኑ ነው፡-

> የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፤ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፣ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ። እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፤ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤ የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። ኤፌ. 6፡11-17

ሆኖም ይህ የመንፈሳዊ ተጋድሎ ሕይወት በመጻን ውስጥ ያለው ሚና በፕሮቴስታንቱ ዓለም አላስፈላጊና ለክርስቶስ የማዳን ጸጋ እንደ ተቃራኒ ተደርጎ በይፋ ይለፈፋል፡፡ በመሆኑም ክርስትናን ከመሠረታዊ ባሕርዩና ማንነቱ ነጥለው ስሙን ብቻ እንደ ማስታወቂያ ይዘው ውስጡን ግን አራቁተውታል፡፡ ተሐድሶዎች አንደኛው መሠረታዊ ችግራቸው ይህን አለመረዳታቸው ነው፡፡ የዚህ ዋናውና መሠረታዊው ምክንያትም ከትንሣኤ በኋላ በሚገኘው ዘለዓለማዊ ክብርና ሕይወት በሚገባ አለማመናቸው ነው፡፡ ምዕራባዊው ዓለም የክርስትና መሠረት የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነትና የትንሣኤውን አማናዊነት ለማመን እየተቸገረ ያለበት ሁኔታ በመሆኑ ከሞት በኋላ ስለሚገኘው ሕይወትና ክብር ሲሉ አሁን ባለው ዓለም የሚገኘውን ተድላና ጣዕም ለመተውና ራስን በመግዛት ለመጋደል ፍላጎቱም እምነቱም በእጅጉ እየራቃቸው ሄዷል፡፡

ክርስቲያናዊ ተጋድሎንና የዚህን ዓለም ተድላ ደስታ ችላ እያሉ ለሰማያዊ ክብርና ጸጋ ሲሉ ራስን መግዛትንና ይህን ዓለም መናቅን በተለያዩ መንገዶች የሚያጥላሉትና የሚያቃልሉት ከዚህ ውስጣዊ የእምነትና የአረዳድ ችግራቸው የተነሣ ነው፡፡ ከዚያም አልፎ እግዚአብሔር ለሰዎች ተስፋ አድርጎ የሰጠው መልካም ነገር በዚህ ዓለም በሚደረግ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገትና ያ በሚያመጣው የኑሮ መሻሻልና ብልጽግና እውን ሊሆንና ሊፈጸም ይችላል እያሉ እንደ ፍልፈል ምድር ለምድር እየቆፈሩ ይገኛሉ፡፡ "ሐሳባቸው ምድራዊ ነው" ተብለው የተገለጹት ዓይነት ናቸው፡፡ የተሐድሶዎች ችግርም ይህን ከክርስትና መንፈስ ባእድ የሆነ ባህልና ፍልስፍና እንዳለ አፍሰው መጋታቸው ነው፡፡ ከእነዚህም የተወሰኑት በየዋህነት መልካምና እውነት መስሏቸው፤ ሌሎቹ ደግሞ እያወቁ እንደ ይሁዳ ለጥቂት ገንዘብ ሲሉ ለማጥፋት ነው፡፡

ለማጠቃለል እስካሁን የተመለከትናቸውን ዋና ዋና ጉዳዮች ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ እንያቸው፦

| | ነገረ ሃይማኖታዊ ጉዳይ | መጽሐፍ ቅዱስ | የቀደምት አበው ትምህርት | ፕሮቴስታንት | ተሐድሶ | ምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያን | ኦሬንታል ኦርቶዶክስ (የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ጨምሮ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ም. ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት፣ ለልጅነት፣ መ/ስማያትን ለመውረስ፣ በክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው ለመሳተፍ፣ በአጠቃላይ ለመዳን አስፈላጊ መሆኑን | ይመሰክራል | ይመሰክራል | አያምኑም | አያምኑም | ያምናሉ | ያምናሉ |
| 2 | ም. ቁርባን አማናዊ የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መሆኑን | ይመሰክራል | ይመሰክራል | አያምኑም | አያምኑም | ያምናሉ | ያምናሉ |
| 3 | የም. ቁርባንን መሥዋዕትነት | ይመሰክራል | ይመሰክራል | አያምኑም | አያምኑም | ያምናሉ | ያምናሉ |
| 4 | ወደ ም. ቁርባን ሲቀርቡ በንስሐ ተዘጋጅቶ ሊሆን እንደሚገባ | ይመሰክራል | ይመሰክራል | አያምኑም | አያምኑም | ያምናሉ | ያምናሉ |
| 5 | ም. ሜሮን ጸጋ እግዚአብሔር የሚሰጥበት ምሥጢር መሆኑን | ይመሰክራል | ይመሰክራል | አያምኑም | አያምኑም | ያምናሉ | ያምናሉ |
| 6 | ጸሎትና ምጽዋት ኃጢአትን ለማስተሥረይና ለመሳለሉት ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑን | ይመሰክራል | ይመሰክራል | አያምኑም | አያምኑም | ያምናሉ | ያምናሉ |
| 7 | ለካህን መናዘዝና ቀኖና መቀበል የሚገባ ስለ መሆኑ | ይመሰክራል | ይመሰክራል | አያምኑም | አያምኑም | ያምናሉ | ያምናሉ |

- ተሐድሶና ፕሮቴስታንት የሚጋሯቸው - 7/7 = 100%
- ተሐድሶና ኦርቶዶክስ የሚጋሯቸው - 0/7 = 0%

ተሐድሶ በእነዚህ መሠረታዊ በሆኑት ሰባት ነጥቦች ሲመዘን ሙሉ በሙሉ (100%) የሚመሳሰለው፣ መመሳሰል ብቻም ሳይሆን አንድ የሚሆነው ከፕሮቴስታንት ጋር ነው፡፡ ከኦርቶዶክሳውያን ጋር ግን ለመዳን መሠረታዊ ከሆኑት ከእነዚህ ነገረ ሃይማኖታዊ ነጥቦች መካከል በአንዱም እንኳ የሚያገናኛቸው ጉዳይ የለም፡፡ ታዲያ "እኛ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ልጆች ነን" የሚሉት ለምንድን ነው? ተመሳስሎ ለማታለል ካልሆነ በቀር የማያምኑበትን እምነት በስሙ ልጠራበት ማለት ምን ማለት ነው?

በመሆኑም የተሐድሶዎች የመዳን ትምህርታቸውና አጠቃላይ ግንዛቤያቸው ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊውና ከቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሊቃውንት ትምህርትና መንፈስ ፍጹም ተቃራኒ የሆነ የሞት መንገድ ነው፡፡ ከተሐድሶዎች ጋር ያለን መሠረታዊ ልዩነትም እነርሱ መዳን የሚሉትና ስለ መዳን የሚያስተምሩት ነገር ሁሉ ስህተት በመሆኑና እግዚአብሔር ወደ ሰጠን ሕይወት ሳይሆን ወደ ሞት የሚወስድ በመሆኑ ላይ ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ባሉት የተለያዩ ጉዳዮች ላይ የምናየው ስህተታቸውም ከዚህ ከመሠረቱ በመዳን ትምህርት ላይ ያላቸው የተሳሳተ ግንዛቤና አስተምህሮ መገለጫና ቀጣይ አካል ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

## በእንተ ወላዲተ አምላክ

## ምዕራፍ አምስት

## እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

### 5.1 በእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ውስጥ የሰው ሱታፌ

እግዚአብሔር ሰውን ሲያድን ማዳኑን የፈጸመው እጅግ በጣም ልዩ በሆነ ሁኔታ ነው፡፡ ይህም ገናናነቱን ከእኛ ታናሽነት ጋር አዋሕዶ፣ ከሃሊነቱን ከእኛ ነጻነት ጋር አስማምቶ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ማለት ምን ማለት ነው? ሊያድነን ሲነሣ እንዲሁ በማንኛውም መንገድ ቢያድነን ታላቅ ቸርነትና ደግነት ሆኖ ሳለ፣ እርሱ ግን ከዚያም በላይ በሆነ መንገድ እኛኑ አሳትፎ፣ ፈቃዳችንን ተቀብሎ አስፈቅዶና አስወድዶ ነው ያዳነን፡፡ እርሱ ሁሉን ማድረግ ስለሚችል ብቻ ያለ እኛ ፈቃድና ሱታፌ እንዲሁ አፍአዊ በሆነ ሁኔታ እና ያለ ፈቃዳችን አላዳነንም፡፡ ባሕርያችንን ሲዋሐድም ያለ እኛው ፈቃድና ሱታፌ አላደረገውም፡፡ የሚጠቅመንን የመዳናችንን ነገር ሲፈጽም እኛን አስወድዶና አሳትፎ ነው፡፡ አካላዊ የእግዚአብሔር ቃል እኛን ለማዳን ከሰማየ ሰማያት ሲወርድ መከራ ተቀብሎ እኛን የሚያድንበትን መሣሪያ የወሰደው ከእኛው መዳኑ ከሚያስፈልገንና ከሚደረግልን ከሰዎች ነበር፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ ሰዎችን የሚወክልና እኛን ሁሉ ወክሎ የሚሳተፍ አንድ ሰው ያስፈልግ ነበር፡፡

እግዚአብሔር አምላክ እንደሚያድነን አስቀድሞ በነቢያት በግልጽ ሲያናግር እንደ ነበረ ሁሉ ያ የሚያድንበት ዕለት ደርሶ ሊያድነን ወደ እኛ ሲመጣም እንዲሁ በግልጽ ተናግሮ ነው የመጣው፡፡ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ወደ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የእግዚአብሔር ወልድን ሰው የመሆን ነገር መልካም ዜና (ብሥራትን) አስይዞ ላከው፡፡ ዘለዓለማዊው አምላክ ሰው ሊሆን፣ የእነ ዳዊት የእነ አብርሃም ፈጣሪ የእነርሱ ልጅ ሊባል፣ ጊዜና ቦታ የማይወስነውና እነርሱን የፈጠረው እርሱ በጊዜና በቦታ ሊገለጥ፣ ልዩ የሆነ እንግዳ ምሥጢር ሊፈጽም እርሱ ባወቀ ወስኗልና አሁን ያን ውሳኔ ለእመቤታችን በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል በኩል እንዲነገራት አደረገ፡፡ የምሥራቹ መልእክትም እንዲህ የሚል ነበር፦

> በስድስተኛውም ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ፣ ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ፣ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ። መልአኩም ወደ እርሷ ገብቶ፦ ደስ ይበልሽ፣ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፣ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት። እርሷም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ በጣም ደነገጠችና፦ ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች። መልአኩም እንዲህ አላት፦ ማርያም ሆይ፣ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ። እነሆም ትፀንሻለሽ፣ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፣ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ። እርሱ ታላቅ ይሆናል፣ የልዑል ልጅም ይባላል፣ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለላም ይነግሣል፣ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም።

ይህን ልዩ ነገር፣ ከዚያ በፊት ማንም ሰምቶት የማያውቅ፣ ከዚያ በኋላም ሌላ ማንም ሊሰማው የማይችል ነገር በሰማች ጊዜ ተገረመች፡ ሁኔታውም ግራ አጋባት፡፡ በዚህ ጊዜ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምና መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል የተነጋገሩት እንዲህ የሚል ነው-

> ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው። መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፡ መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፡ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። እነሆም ዘመድሽ ኤልሳቤጥ እርሷ ደግሞ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፣ ለእርሷም መካን ትባል ለነበረችው ይህ ስድስተኛ ወር ነው፤ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና። ማርያምም፡- እነሆኝ የጌታ ባሪያ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች። ሉቃ. 1፡26-38

በዚህ የእግዚአብሔር መልእክት እና የእመቤታችን መልስ ለእግዚአብሔር ሰውን የማዳን ሂደት ታላቅ በር የከፈቱና መሠረት የሆኑ ቢያንስ ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን እንመለከታለን፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡-

1) የእመቤታችን እምነት

እግዚአብሔር "ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ - እንደ ቃልህ ይሁንልኝ" የሚለውን የእመቤታችንን የእምነት መልስ ከእርሷ መስማት ባይፈልግ ኖሮ የዚህን መልእክት ቃል አስቀድሞ ወደ እርሷ መላክ ለምን አስፈለገው? ለምን እንዲሁ ዝም ብሎ በማኅፀኗ አልተፀነሰም? እግዚአብሔር አምላካችን ኃይል ሲሰማውና ዓቅም ሲያገኝ ደስ ያለውን እንደሚያደርግ አምባ ገነን ባለ ሥልጣን አይደለም፡፡ እግዚአብሔር እንዲሁ ማድረግ ስለሚችልና ከኃሊ ስለሆነ ብቻ እንዳችም ነገር አያደርግም፤ ድርጊቱም፤ የሚያደርግበት መንገድም እርሱ ባወቀ አግባብነት ያለው ሲሆን ብቻ እንጂ፡፡ "እስመ ርቱዓት ፍናዊሁ ለእግዚአብሔር - የእግዚአብሔር መንገድ ሁሉ ቅን ነው" እንደ ተባለ፡፡ ሆሴ. 14፡9 እንዲሁም "ኩነኔሁ ለእግዚአብሔር ፍትሕ ወርትዕ ኅቡረ - የእግዚአብሔር ፍርድ እውነትና ቅንነት በአንድነት ነው" እና እንደገናም "ሣህል ወርትዕ ተራከባ ጽድቅ ወሰላም ተሰዐማ - ምሕረትና እውነት ተገናኙ፣ ጽድቅና ሰላም ተስማሙ" የሚለው ይህን የእግዚአብሔር ድንቅና ረቂቅ አሠራር የሚገልጽ ነው፡፡ መዝ. 18፡9 ፤ 84፡10

ስለሆነም እግዚአብሔር ለእመቤታችን መልእክቱን በመልአኩ አማካይነት የላከበት መሠረታዊ ምክንያት ነበር፡፡ የሰው ልጅ በመጀመሪያ የበደለው በደል፣ ከፈጣሪው ጋር የተለየበት ዋና ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት በዲያብሎስ ስብከት መነሻነት በራሱ ክህደት በማጣቱ ነበር፡፡ ሞት ወደ ሰው ልጆች ሕይወት የገባው በመጀመሪያ በሃይማኖት ጉድለት ነበር፡፡ አዳምና ሔዋን መጀመሪያ ያጡት እምነታቸውን ነበር፤ ሕጉን ያፈረሱት እምነታቸውን ካፈረሱ በኋላ ነበር፡፡ ሕግ ማፍረሳቸው፣ ቅጠል ቆርጠው መብላታቸው ሁሉ የእምነታቸው መፍረስ መገለጫና ውጤት ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሊፈልጋቸው የት ናችሁ? ምን ሆናችሁ? እያለ ጥፋታቸውን እንዲያምኑና ንስሐ እንዲገቡ መንገዱን ከፊታቸው ሲጠርግላቸው እንኳ ሌላ ሰበብ በመስጠት ላይ የነበሩት በእግዚአብሔር ላይ የነበራቸው እምነት ስለ ደከመ ነበር፡፡

እግዚአብሔር ያ የቀደመውን የሞት መንገድ ሊያፈርስና ወደ ሕይወት መንገድ ሊመልሰን ሲመጣ በዚያው ሞት መጀመሪያ በገባበት መንገድ ያስወጣው ዘንድ ከሰው ልጅ ጠፍቶ የነበረውን እምነት እንደ ገና በመፈለግና በዚያ በመመሥረት መንገዱን አንድ ብሎ መጀመር ወደደ፡፡ ለዚህም ነበር ከሁሉ አስቀድሞ ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም መልእክቱ የተነገራት፡፡ ሔዋን ሰውን ወደ ሞት ይወስደው ዘንድ በተንኮሉ ያቀደውን የዲያብሎስን ቃል ሰምታ እግዚአብሔርን ከዳ ለሰይጣን ታምና ነበር፤ ይህ የመጀመሪያው ኃጢአትና የቀደመው የሞት መንገድ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሰይጣንን ሳይሆን ከእግዚአብሔር የተላከውን መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ሰምታ ቃሉን በእምነት ተቀበለች፡፡

መልአኩ "ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና" ሲላት እርሷም "ነየ አመቱ ለእግዚአብሔር ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ - እነሆኝ የጌታ ባሪያ፡ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ" በማለት በእግዚአብሔር ላይ ያላትን ፍጹም የሆነ እምነት ገለጸች፡፡ በሔዋን ክህደት የተጀመረው የሞት መንገድ አሁን ደግሞ በዳግማዊት ሔዋን በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም እምነት ሊሰበርና አቅጣጫው ሊቀየር፡ አዲስ የሕይወት መንገድም ሊጀመር ሆነ፡፡ ይህ የእመቤታችን የእምነት መልስ አኳላዊ ቃል በእምነት መንገድ ወደ ባሕርያችን ይገባ ዘንድ በሩን የከፈተ ታላቅ ቁልፍ ነበር፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ያን የእግዚአብሔር የማዳን ጉዞ የመጀመሪያ ምዕራፍ በእምነት ባትቀበል ኖሮ ምን ይፈጠር ነበር? ብንል በነገረ ሃይማኖት ባልተፈጸመ (ባልሆነ) ነገር ላይ ተንሥቶ ሃሳብ መስጠት አይቻልም፤ የምናውቀው የተነገረንንና የሆነውን ብቻ ስለሆነ፡፡ ለምሳሌ "አብርሃም ልጁን ይስሐቅን ቢሠዋው ኖሮ . . ." ብሎ መጠየቅ ትርጉም የለውም፡ አልሠዋውምና፡፡

ስለሆነም እመቤታችን የሰውን ልጆች ሁሉ በሙሉ (ከአዳም እስከ መጨረሻ ሰው ፍጥረት ያለውን በሙሉ) ወክላ የእግዚአብሔርን የማዳን የጥሪ መልእክት በእምነት መቀበሏ እግዚአብሔር ባሕርያችንን በእኛ ይሁንታና እሺታ በእርሷ አማካይነት እንዲዋሐድና ቃል ሥጋ እንዲሆን በማድረግ የሰውን ሁሉ ድርሻ ተወጥታለች፡፡ የሔዋን እግዚአብሔርን ክዶቶ ዲያብሎስን ማመን የሰውን ልጅ በሙሉ እንደ ጎዳውና ሞትን ከፍቶ ወደ ውስጣችን እንዳስገባው ሁሉ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም እምነትና የእምነት ቃል ደግሞ ሞትን የሚገድለውና ሕይወትን የሚሰጠው የእግዚአብሔር ልጅ ወደ እኛ እንዲገባ በሩን ከፍቷል፡፡

የሔዋን እምነት ማጣት በሰው ልጆች ላይ በሙሉ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን የሚያምን ሁሉ የእመቤታችን እምነት ደግሞ ለሰዎች በሙሉ ታላቅ ጠቀሜታ የነበረው መሆኑን መቀበል የግድ ይለዋል፡፡ የሔዋን እግዚአብሔርን መጠራጠርና ወደ ዲያብሎስ ማዘንበል ሞትን ማምጣቱን የሚያምን ሁሉ የእመቤታችን በእግዚአብሔር ላይ የነበራት ፍጹም እምነት ደግሞ ሕይወት ወደ ዓለም (ወደ ሰው ሁሉ) እንዲገባ በር መክፈቱን ማመን ግድ ይለዋል፡፡ ይህን አለማመን ኢ.ምክንያታዊም ኢ.ፍትሐዊም ነው፡፡ ምክንያቱም ክፉ ክፉውን የሚያምንና የሚቀበል (የሔዋንን ክህደትና ያስከተለውን ሞትና ችግር)፡ መልካም መልካሙን ደግሞ የሚክድ (የእመቤታችን እምነትና ያመጣውን መልካም ነገር) መሆን ይሆንበታልና፡፡ ስለ እግዚአብሔር ሰው መሆንና ማዳን ስንናገር ይህን የመጀመሪያውን ምዕራፍ ትተንና አልፈን ሊሆን አይችልም፡ አይገባምም፡፡ ክርስትና እንደ ቡፌ ላይ ምግብ ደስ ያለንንና የፈለግነውን ብቻ እየመረጥን የምናነሣበት አይደለምና፡፡

2) የእመቤታችን መታዘዝና ራሷን ለእግዚአብሔር መስጠት

የሔዋን ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ከእምነቷ መጉደል የተነሣ፣ ለሰይጣን መታዘዟ ደግሞ እምነቷን ወደ እርሱ በማዞሯ ምክንያት የመጣ እንደ ነበረ ሁሉ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ለእግዚአብሔር መታዘዝም በእግዚአብሔር ላይ ከነበራት ፍጹም እምነት የተነሣ የተገኘ ነበር፡፡ ምንም እንኳ በመልአኩ አማካይነት የተነገራት መልእክት ማንም ሰው ሰምቶት የማያውቅ በጣም ልዩና እንግዳ የሆነ ነገር ቢሆንም እርሷ ግን በእምነት ተቀበለችው፡፡ እርሷ "ይኩነኒ - ይሁንልኝ" ብላ የተቀበለችውን መልእክት ይቅርና ካህንና አረጋዊ የነበረው ዘካርያስ እንኳ በታወቀው መንገድ ያው መልአክ ቅዱስ ገብርኤል "ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች" ብሎ ሲነግረው ተጠራጥሮ ነበር፡፡

እንግዲህ ዘካርያስ በመጀመሪያ መጻሕፍትን የሚያውቅና እድሜ የጠገበ አረጋዊ ካህን ነበር፡ እመቤታችን ግን ገና የአሥራ አምስት ዓመት ብላቴና ነበረች፡፡ ሁለተኛ ዘካርያስ "ሚስትህ ትወልዳለች" የተባለው በታወቀው በዘር በሩካቤ መንገድ ነበር፤ ለእመቤታችን የተነገራት ግን ከዚያ ፍጹም ልዩ በሆነ ሁኔታ በኀቱም ድንግልና ስለ መፅነሥና ስለ መውለድ ነበር፡፡

ሦስተኛ ለዘካርያስ እግዚአብሔር ከፈቀደ በእርጅና ዘመንም ልጅ መውለድ እንደሚቻል ሊያስረዱት የሚችሉ ከእርሱ በፊት የተፈጸሙ የእነ አብርሃምና ሣራ፣ የእነ ማኑሄና እንትክይ (የሶምሶን ወላጆች)፣ የሐና እመ ሳሙኤልና የመሳሰሉት ብዙ ታሪኮች ነበሩ፡፡ ለእመቤታችን ግን በድንግልና ፀንሶ በድንግልና ስለ መውለድ ምሳሌ ሊሆናት የሚችል አንድም ታሪክ አልነበረም፡፡ እንደዚሁም ዘካርያስ ትወልዳለህ የተባለው ፍጡር የሆነ ሰውን ነበር፤ እመቤታችን ግን ትወልጃለሽ የተባለችው በሥጋ የሚገለጠውን የእግዚአብሔር ቃልን ነው፡፡ ሆኖም ዘካርያስ በዚያ ሁሉ ሁኔታ እያለ እንኳ ሲጠራጠር እመቤታችን ግን በዚያ ዓይነት ከባድ ሁኔታ የተነገራትን ቃል "ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ - እንደምትለኝ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ፣ እኔ የእግዚአብሔር አገልጋዩ ዝግጁ ነኝ፣ እነሆኝ አለሁኝ" ብላ በፍጹም ታዛዥነት ተቀበለች፡፡ አካላዊ የእግዚአብሔር ቃል በማኅፀኗ እንዲፀነስና ሰው እንዲሆን ያበቃው ይህ መታዘዟ ነበር፡፡ እርሷ "ይሁንልኝ፣ እነሆኝ አለሁኝ" ብላ በፈቃዷ ባትታዘዝ ኖሮ እግዚአብሔር በግድ የእርሷን ባሕርይ ይዋሐድ ነበረን? እንዲያ ባይሆን ኖሮስ ከዚያ ቀጥሎ ምን ሊሆን ይችል ነበር? የሰው መዳን ሁኔታስ እንዴት ይሆን ነበር? ብለን ብናስብ ከጥያቄ በቀር መልስ አናገኝም፡፡ የሔዋን አለመታዘዝ ሞትን እንደ ፀነሰና እንደ ወለደ፣ የእመቤታችን መታዘዝ ደግሞ ሕይወትን ፀነሰ፣ ሕይወትን ወለደ፡፡ ይህ የእመቤታችን መታዘዝና የመታዘዟ ሚና ሊሸፋፈንና ሰምቶ እንዳልሰሙ ሊታለፍ የሚገባው ነገር አይደለም፡፡

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መለኮታዊ ፈቃድን በፈቃዷ ተቀበለች፣ በእዎንታ እሺ ይሁንልኝ ብላ መለሰች፣ ፈቃዷን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር አስተባበረች፣ በነጻነት ታዘዘች፡፡ ይህ የሰው ልጆችን በሙሉ ወክላ መለኮታዊ ፈቃድን መቀበሏና መታዘዟ ወሳኝ ነገር ነበር፡፡ የእመቤታችን መታዘዝ የሔዋንን አለመታዘዝ ካሠው፡፡ የመጀመሪያውን አዳም ስህተት የቤዠው ልጇ ዳግማዊ አዳም ሲሆን እርሷ ደግሞ ዳግማዊት ሔዋን ናት፡፡ ቅዱስ ሄሬኔዎስ የዚህን የእመቤታችንን "ይሁንልኝ" ብላ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የመቀበሏን ነገር ሚና በተመለከተ ሲናገር "ድንግል ማርያም ከእግዚአብሔር ሰውን የማዳን መለኮታዊ አሠራር ጋር ተባበረች[98]" ብሏል፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ እንዲሁ ዝም ብሎ በኃይልና በግድ ያለ ፍላጎትና ስምምነት የሚጫንብን ወይም አለ ፈቃዳችንና ሱታፌያችን ዛፍ ላይ እንደሚበቅል ተቀጽላ የሚለጠፍብን ነገር አይደለምና፡፡ ያ እንዳይሆን የእመቤታችን ይሁንታና መታዘዝ ልዩ ሚና ነበረው፡፡

እንዲሁም እመቤታችን ነጻነት ማለት ምን ማለት እንደ ሆነም በትክክል በተግባር አሳየች፡፡ ነጻነት ማለት ለእግዚአብሔር አለ መታዘዝና ሞትን መምረጥ ሳይሆን ለእግዚአብሔር በራስ ፈቃድና ውሳኔ "እነሆኝ፣ አለሁኝ" ማለትና ሕይወትን መምረጥ መሆኑን በተግባር አሳየች፡፡ በአዳምና በሔዋን የታየው የተሳሳተ የነጻነት ግንዛቤና አተገባበር በእርሷ ተስተካከለ፡፡ ሕይወትን መጥላትና ሞትን መምረጥ ነጻነት ሳይሆን እብደት ነው፡፡ አዳምና ሔዋን ያበላሹትን ያን የነጻነት ጸጋ እመቤታችን በአግባቡ ተጠቀመችበት፡፡ በዚህም በተሳሳተ ነጻነት አጠቃቀም የገባውን ሞት የሚያስወግደውና ሕይወትን መልሶ የሚሰጠው ሕይወት ወደ ዓለም እንዲገባ በር ሆነች፡፡ ነጻነትን መጠቀም ማለት ምን ማለት እንደ ሆነም ለሰው ልጆች ሁሉ አርአያ ሆነች፡፡

አዳም ሞትን ቆርጣ ያበላችውን ሔዋንን ስም ሲያወጣላት "የሞት ምክንያት" ወይም "የሞት እናት"፣ ወይም ልጆቿ እነ አቤልና ቃየን ሲጋደሉና ሲሞቱ አይቶ "የሙታን እናት" በማለት ፋንታ "የሕያዋን እናት" ለምን አላት? እንደ ግብሯ ከሆነ ለሔዋን ሊያወጣላት ይገባ የነበረው ስም እንዲያ ዓይነት ነበር፤ እርሱ ግን ከፈጸመችውና ካመጣችው ውጤት በተቃራኒ "የሕያዋን እናት" አላት፡፡ የዚህ ምክንያቱ ሞትን ባመጣችው በመጀመሪያዋ ሔዋን አንጻር ከእርሷ የምትገኘውንና ሕይወትን የምትወልደውን ዳግማዊት ሔዋን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ከርቀትም ቢሆን በጸጋ እግዚአብሔር ስለ ተመለከተ ነበር፡፡

98 "Mary *cooperating* with the economy". St. Irenaeus, *Adv. Haeres.*, 111, Book 3.21, 7)

## 5.2 በእግዚአብሔርና በሰዎች ግንኙነት ሂደት ውስጥ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ቦታ

ለአዳምና ለሔዋን እግዚአብሔር ስለ ጥፋታቸው ለእያንዳንዳቸው ተገቢውን አባታዊ የምሕረት ቀኖና ከሰጣቸው በኋላ ተስፋውን እንዲህ ሲል ነግሯቸዋል፦ "በአንተና በሴቲቱ መካከል፣ በዘርህና በዘሯም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፣ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።" ዘፍ. 3፡15 የዲያብሎስን ራስ የሚቀጠቅጠውና "በዘሯ" የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ያን ዘር የምታስገኘው "ሴት" ደግሞ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ነበረች፡፡ ለልማዱ ዘር ከወንድ እንጂ ከሴት አይደለም፤ በጌታችን ሥጋዌ ግን እንበለ ዘርእ ብእሲ በድንግልና ከእመቤታችን ስለሚወለድ "የሴቲቱ ዘር" ተባለ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "ወአመ በጽሐ ጊዜሁ ፈነወ እግዚአብሔር ወልዶ ወተወልደ እምብእሲት - የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ፣ ከሴትም ተወለደ" በማለት የገለጸው "የሴቲቱ ዘር" ተብሎ የተሰጠው ተስፋ የደረሰና የተፈጸመ መሆኑን ለመግለጽ ነበር፡፡ ገላ. 4፡4

ሔዋን እስከ ልጅ ልጆቿ በዘር በሩካቤ ካስገኘቻቸውና በዚህ መንገድ ሲወለዱ ከኖሩ "ዘሮቿ" መካከል ዲያብሎስን የቀጠቀጠው ማንም የለም፡፡ ስለዚህ የዲያብሎስን እናት በመስቀል የሚቀጠቅጠው ያ "ዘር" ጌታችንና መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ሴቲቱ ደግሞ እመቤታችን ናት፡፡ ስለሆነም በፈቃዱ መታዘዟ ለእግዚአብሔር አሠራር ታላቅ ሚና ነበረው፡፡ እመቤታችንን ትቶና ረስቶ ዘልዬ ወደ ሌላው ልሂድ ማለት ይህን ድንቅ ምሥጢር ከመሠረቱ ከመረዳት ያግዳል፡፡ ከመሠረቱ ያልጠራና ያልጀመረ ነገር ደግሞ ጥራዝ ነጠቅ የመሆንና ወደ ስህተት የማምራት ዕድሉ ሰፊ ነው፡፡ ይህንንም ከሐዋርያት ዘመን ቀጥሎ የተነሡት ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች በትምህርታቸው በሰፊው ያስተማሩትና ያመሰጠሩት ጉዳይ ነው፡፡ ይህን በቀደምት አበው ትምህርት በሚለው ክፍል እናገኘዋለን፡፡

የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን እናት በተመለከተ ያለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮና ጥልቅ ምሥጢር አይመለከተኝም ማለትና አልፎ መሄድ ልጇን ኢየሱስ ክርስቶስን በተመለከተ እናውቅ ዘንድ የተገለጸውን ማወቅ አለ መፈለግና አልፎ መሄድ ነው፡፡ ሲጀመር እመቤታችንን ያወቅናት በሰው መዳን ሂደት ውስጥ ነው፡፡ ለአዳምና ለሔዋን በምሥጢር የዲያብሎስን እናት የሚቀጠቅጠውን ዘር የምታስገኘው "ሴቲቱ" ተብላ የተነገረችው የመዳናቸው ነገር ሲነገራቸው ነበር፡፡ መንፈስ ቅዱስ በነቢያት ስለ ልጁ ትንቢት ሲያናግርም እርሷን ትቶና ዘንግቶ አልነበረም፡፡ ለምሳሌም ነቢዩ ኢሳይያስ "ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ - እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፣ ወንድ ልጅም ትወልዳለች" ብሎ ልደተ ወልድን ብቻ ሳይሆን ሰው ሲሆን የምትወልደውንም ጨምሮ "ድንግል ትወልዳለች" ብሎ ነው የተናገረው፡፡

ከዚህም ጋር አማናዊት ምልክት መሆኗን "ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል" በማለት ይህ የድንግል በድንግልና መውለድ ለአምላክ ሰው መሆን ዋና ምልክት መሆኑን እግዚአብሔር በነቢዩ አማካይነት አስቀድሞ ነግሮናል፡፡ ኢሳ. 7፡13-14 ምክንያቱም አካላዊ ቃል ሰው ሲሆን እንደ ማንኛውም ሰው በዘር በሩካቤ ተወልዶ ቢሆን ኖሮ ከሌሎች ሰዎች ተለይቶ ዓለምን ለማዳን የመጣው ሰው የሆነው አምላክ እርሱ መሆኑ በምን ይታወቅ ነበር? ዓለምን የሚያድነው አምላክ ሰው መሆኑና በሥጋ መገለጡ በማያሻማ ሁኔታ የታወቀው ከድንግል በመወለዱ ነበር፡፡ ስለዚህ ድንግል ማርያም የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛው መድኃኒት መሆኑን አጥርቶ ለማወቅ ዋናዋ ምልክት ናት፡፡ ይህቺን ምልክት በሚገባ ያልተረዱ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን በተመለከተም በተለያየ ዓይነት ኑፋቄ ውስጥ ወድቀዋል፡፡ ዶሴቲኮች፣ ግኖስቲኮች፣ ንስጥሮሳውያን ወዘተ የዚህ ተግባራዊ ማሳያዎች ናቸው፡፡

ነቢዩ ሕዝቅኤልም ሲናገር "ወደ ምሥራቅም ወደሚመለከተው በስተ ውጭ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ፣ ተዘግቶም ነበር። እግዚአብሔርም፦ ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፣ ሰውም አይገባበትም፣ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል" በማለት ስለ ገባው እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ስለ ገባባት *የመቅደስ በርም* ተናግሯል። ሕዝ. 44፡1-2 ሳይከፍት እንደ ተዘጋ የገባባት የመቅደሷ በር በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ በኅቱም ድንግልና የተወለደባት እመቤታችን ናት፡፡ ይህ ትንቢት እመቤታችን አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ስለ መውለዷና ከዚያም በኋላ ዘለዓለማዊት ድንግል ሆና ስለ መኖሯ የተነገረ ትንቢት መሆኑንም ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ የተረዳችበት መንፈስ ነው፡፡ እንዲሁም ቀደምት ኦርቶዶክሳውያን አባቶች የገለጹትና የተረጎሙትም እንደዚሁ ነው፡፡ ሌሎች ነቢያትም እንዲሁ ሰው ሆኖ ስለሚገለጠው ጌታ ብቻ ሳይሆን ስለሚገለጥባት ስለ ድንግል ማርያምም ተናግረዋል፡፡

እዚህ ላይ ከነቢዩ ከኢሳይያስ በቀር ሌሎቹ ድንግል አላሉም ወይም ስሟን አልገለጹም የሚል ይኖር ይሆናል፡፡ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሰው መሆን በተመለከተም'ኮ ነቢያት ሲናገሩ አብዛኛዎቹ ኢየሱስ ክርስቶስ እያሉ ስሙን እየጠቀሱ አልነበረም፡፡ እርሱን በትንቢት በገለጹበት መንገድ አንጻር ግን እርሷንም በትንቢት አመልክተዋታል፡፡ ለአብነት ያህልም ነቢዩ ዳንኤል ጌታችንን "እጅ ሳይነካው ከተራራ ተፈንቅሎ በወረደ ድንጋይ" ሲመስለው እርሷን ደግሞ "ድንጋዩ በተገኘበት ተራራ" መስሏታል፡፡ ዳን. 2:45 ነቢዩ ሚልክያስ ደግሞ ጌታን "እናንተም የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል" በማለት "ወደ መቅደሱ በሚመጣ" ሲገልጸው እርሷን ደግሞ ይህ ጌታ በሚገኝባት "መቅደስ" መስሏታል፡፡ ሚልክ. 3፡1

ነቢዩ ኢሳይያስ ደግሞ "ትወጽእ በትር እምሥርወ እሴይ ወየዐርግ ጽጌ እምጉንዱ - ከእሴይ ግንድ በትር ትወጣለች፣ ከሥሩም ቊጥቋጥ ያፈራል" በማለት ከዳዊት ወገን ስለምትገኘው ዛፍ ስለ እመቤታችንና ከዛፉ ስለሚገኘው ፍሬ ስለ ጌታችን ተናግሯል፡፡ ኢሳ. 11፡1 እንዲሁም "በፊቱ እንደ ቡቃያ ከደረቅም መሬት እንደ ሥር አድጓል" በማለት እርሱን በቡቃያና በሥር ሲመስለው እርሷን ደግሞ ቡቃያውንና ሥሩን ያለ ርጥበት (እንበለ ዘርእ ወሩካቤ) ባበቀለችው "ምድር ጽምዕት - ደረቅ መሬት" መስሏታል፡፡ ኢሳ. 53፡2 ይህ ሥርም "እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ" ብሎ የተናገረው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ራእ፣ 22፡16

ስለሆነም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በትክክል ልንረዳትና ልናውቃት የምንችለው በነገረ ክርስቶሳዊ ዳራና ድባብ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ እርሷን አለመረዳት ልጇን መድኃኒታችንና ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን፣ እንዲሁም በአጠቃላይ ነገረ ሥጋዌን በትክክል አለመረዳት ነው፡፡ እግዚአብሔር ወልድ ሰው የሆነባትን እመቤታችንን አልፎ ነገረ ሥጋዌን መናገር አይቻልም፡፡ ከብሉይ ኪዳን ወደ ሐዲስ ኪዳን ስንሸጋገር የማድ መሃል ላይ የምናገኛት እርሷ ናት! ሰማያዊውን አካላዊ ቃል እኛን ሁሉ ወክላ በእምነት በመታዘዝ የእኛን ባሕርይ ለእርሱ በፈቃዷ አበርክታ በእኛ ባሕርይ ተወልዶ እንድናየው ያደረገችው እርሷ ናት! የማይጨበጠውንና የማይታየውን ወልዳ በቤተ ልሔም በግርግም ተኝቶ እንድናየው ያደረገችው እርሷ ናት! ሰው ሆኖ ሲወለድም መላእክት ያመሰገኑት፣ ሰብአ ሰገል የሰገዱለት ከእርሷ ተወልዶ በእናትነቷ ታቅፋው ነዋ! ይሄን ሁሉ ክዶ ክርስትና ከየት ይመጣል?

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከፍጥረት ሁሉ የተለየ ልዩ ቦታ አላት፡፡ ይህ ለእርሷ የተሰጣት ልዩ ቦታ ደግሞ ከእርሷ በፊትም ሆነ በኋላ ለማንም ያልሆነና መቼም መች ሊሆን የማይችል ልዩ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ እርሷ "ምልእተ ጸጋ - ጸጋን የተመላሽ ነሽ" የተባለ አንድም ፍጥረት አልሰማንም፡፡ ሰዎች እንደየ ጸጋቸውና ተጋድሏቸው ከተለያየ የቅድስና መዓርግ ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ሰላደረገ ተወሰደ ተብሎለታል፣ ኤልያስ በእሳት ሠረገላ ዐርጓል፣ ቅዱስ ጳውሎስ እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ መሄድ ችሏል፡፡ ሆኖም ከእነዚህም ሆነ ከሌሎች ብዙ ቅዱሳን አንዳቸውም "ጸጋን የተመላህ ነህ" አልተባሉም፡፡

ከፍጥረታት ወገን ፈጣሪዋን የፀነሰችና የወለደች ከእርሷ በፊትም አልነበረም፣ ከእርሷ በኋላም አይኖርም፡፡ ፈጣሪዋን "ጌታዬና አምላኬ" ያለችም፣ "ልጄ" ያለችም እርሷ ብቻ ናት፡፡ ሌሎች ሴቶች "አምላኬ"፣ "መድኃኒቴ" ማለት እንጂ "ልጄ" ማለት አይችሉም፡፡ ፈጣሪዋን ጡት ያጠባችው እርሷ ብቻ ናት፣ ያዘለችው እርሷ ብቻ ናት፣ ሠላሳ ዓመት ሆኖት በጉባኤ ትምህርትና ተአምራት ከመጀመሩ በፊት ያን ሁሉ ጊዜ አብራው የኖረችውና ይናገር የነበረውን ነገር፣ ሁኔታውን ሁሉ ለማየትና ለመስማት የታደለችው እርሷ ብቻ ናት፡፡ ቅዱሳን ሐዋርያትም ሆኑ ሌሎች ሰዎች እርሱን ያወቁትና ትምህርቱን መስማት የጀመሩት ሠላሳ ዓመት ከሆነውና ካደገ በኋላ ነው፡፡ አንድ ጊዜ ገና በአሥራ ሁለት ዓመቱ እንኳ በቤተ መቅደስ ተገኝቶ በአይሁድ መምህራን መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸውና ሲጠይቃቸው የሰሙት ሁሉ በማስተዋሉና በአነጋገሩ እንደ ተገረሙ በወንጌል ተጽፏል፡፡ ሉቃ. 2፥46-47 ይህ እንደ ቅምሻ የተጻፈልን ነው፡፡ እርሷ ግን አንድ ቀን ሳይሆን ሠላሳ ዓመት ሙሉ እነዚያን የሚያስደንቁ ነገሮች በየዕለቱ ስትሰማቸው ኖራለች፡፡ ሆኖም እርሷ እንደ ቀደመችው ሔዋን አይደለችምና ያን ሁሉ ምሥጢር ግን አውጥታ አልተናገረችም፤ "ወትወድዮ ለኩሉ በውስተ ልባ - እናቱም ይህን ነገር ሁሉ በልቧ ትጠብቀው ነበር" እንደ ተባለ በልቧ መዝገብነት ጠበቀችው እንጂ፡፡ ቅዱስ ያሬድም ከዚህ በመነሣት "ማርያምሰ ሀለወት ተዐቅብ ዘንተ ኩሎ - ማርያም ግን ይህን ሁሉ ምሥጢር ትጠብቀው ነበር" ሲል ምሥጢርን ከዜማ ጋር ባዋሐደው ሰማያዊ ድርሰቱ በአድናቆት ተናግሯል፡፡

ሐዋርያት እንኳ አብረውት የኖሩት ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ብቻ ነው፡፡ እርሷ ግን ሐዋርያት ከመጠራታቸው በፊት አብራው ነበረች፡፡ በምሴተ ሐሙስ ማታ ላይ ደቀ መዛሙርቱ (ከዮሐንስ በቀር) ጥለውት ሲሸሹም እርሷ እስከ መስቀሉ እግር ድረስ አብራው ሄዳለች፡፡ በራሱ ፈቃድ ነፍሱን ከሥጋው እስኪለይ ድረስም አብራው ነበረች፡፡ የማዳን ተልእኮውን ፈጽሞ ወደ ቀደመ ክብሩ ወደ ጥንት አኗኗሩ ሲያርግም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብራ ነበረች፡፡ ታዲያ ለመድኃኔ ዓለም ከእርሷ በላይ የቀረበ፣ ከእርሷ በላይስ የሚያውቀው ማን ሊኖር ይችላል? በምንስ ሂሳብ? በየትኛው ስሌት?

ንጽሕተ ንጹሐን ቅድስተ ቅዱሳን እመቤታችን ድንግል ማርያም እርሱ እግዚአብሔር ባወቀ ባዘጋጀው ሰውን የማዳን መለኮታዊ ዓቅድ ውስጥ ከጥንቱ ከዘለዓለሙ የታሰበችና የተዘጋጀች ምርጥ ዕቃ ነበረች፡፡ የአምላክ ሰው የመሆን ምሥጢር እንዲሁ በድንገት የተወሰነና የተከሠተ ሳይሆን እኛ ልንደርስበት በማንችለው ረቂቅ መለኮታዊ ሃሳብና ዓቅድ ውስጥ የታወቀ ነበርና፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ከዘላለም ዘመንም የተሰወረው፣ አሁን ግን የታየው፣ በነቢያትም መጻሕፍት የዘላለም እግዚአብሔር እንደ አዘዘ ለእምነት መታዘዝ ይሆን ዘንድ ለአሕዛብ ሁሉ የታወቀው ምሥጢር እንደ ተገለጠ መጠን" በማለት የገለጸው ይህን ነው፡፡ ሮሜ 16፥25-26 እንዲሁም "ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለ ጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ፣ ሁሉንም በፈጠረው በእግዚአብሔር ከዘላለም የተሰወረው የምሥጢር ሥርዓት ምን እንደሆነ ለሁሉ አገልጥ ዘንድ ይህ ጸጋ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለኔ ተሰጠ" ያለለት ድንቅ ምሥጢር ይህ ነው፡፡ ኤፌ. 3፥8-9 ስለሆነም ለዚህ በልበ ሥላሴ ታስቦ ይኖር ለነበረው ዘለዓለማዊ ምሥጢር የተዘጋጀች መሣሪያ ሆና መመረጧ ሌላው ልዩ የሚያደርጋት ነገር ነው፡፡ ከሥጋዌው መፈጸም በፊትም እንኳ በእግዚአብሔር ልዩ በሆነ መንገድ፣ ለልዩ ዓላማ ተለይታ የተቀመጠች ነበረች፡፡

እግዚአብሔር በቸርነቱ ከአሳዳጅነት የጠራውን ቅዱስ ጳውሎስን እንኳ ይህን ምሥጢር ይሰብክ ዘንድ ብዙ መከራ እንደሚቀበል በመግለጽ "ይህ በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ *የተመረጠ ዕቃ ነው"* ካለው፣ ገና ከመጀመሪያው በቃል ሥጋ መሆን ምሥጢር የተሳተፈች፣ ከሁሉ በፊት "እነሆኝ የጌታ ባሪያ" ብላ ራሷን በፈቃዷ ለእግዚአብሔር ያቀረበች፣ ሥጋዋንና ነፍሷን ሁለንተናዋን ለእግዚአብሔር ወልድ ተዋሕዶ የሰጠች፣ ሥግው ቃልን ዘጠኝ ወራት በማኅፀኗ የተሸከመችው፣ ጡቷን ያጠባችው፣ በእጆቿ ያቀፈችው፣ አዝላው ወደ ምድረ ግብጽ የተሰደደችው፣ በቃና ዘገሊላ በተአምራቱ ቦታ፣ በሚያስተምርበት ቦታ፣ በመስቀሉ እግር ሥር

ሁሉ ያልተለየችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም "ምርጥ ዕቃ" መባል ይበዛባታልን? የሐዋ. 9፡15-16 ምን ብለን ብንጠራትስ በትክክል እንደሚገባ አድርጎ ሊገልጻት ይችል ይሆን?

ቃል ሥጋ ከሆንና ዓለምን ካዳነ በኋላ ይህን የመዳን መንገድ የሰበኩትና ያስተማሩት እነ ቅዱስ ጳውሎስና ደቀ መዛሙርቱ የቆሮንቶስ ምእመናንን "እኛ ለደስታችሁ ከእናንተ ጋር የምንሠራ ነን" ካሉ ገና ከመጀመሪያው ለዚህ ምሥጢር ራሷን በእምነትና በመታዘዝ ለእግዚአብሔር የሰጠችና ይህ ሁሉ እንዲሆን በሩን የከፈተች እመቤታችንን ምን እንበላት? 2 ቆሮ. 1፡24 በእውነቱ ጠላት ዲያብሎስ በእርሻ ልቡናችን ላይ ከሚዘራው እመቤታችንን የማስጠላት እንክርዳድ ራስን መጠበቅ ይገባል፡፡ እመቤታችንን መጥላት ክርስቶስን የመውደድና ለእርሱ ዘብ የመቆም ምልክት እያስመሰለ ሞኞችን እየሰበከ ይገኛልና ከዚህ የዲያብሎስ ዘመቻ መንቃትና ራስን መጠበቅ ይገባል፡፡ "ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ብፁዕ ነው" ተብሏልና፡፡ ራእ. 16፡15

ጌታችን በምሴተ ሐሙስ በስምዖን ቤት ሳለ ዋጋው እጅግ የበዛ ሽቱ የሞላው የአልባስጥሮስ ብልቃጥ አምጥታ በጌታችን ራስ ላይ ባፈሰሰች ጊዜ በይሁዳ ተንኮል ተገፋፍተው ሌሎቹ ደቀ መዛሙርቱም "ይህ ጥፋት ለምንድር ነው? ይህ በብዙ ዋጋ ተሽጦ ለድሆች ሊሰጥ ይቻል ነበርና" እያሉ በተቆጡ ጊዜ ጌታችን እንዲህ አላቸው፡-

> መልካም ሥራ ሠርታልኛለችና ሴቲቱን ስለ ምን ታደክሟታላችሁ? ድሆች ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና፤ እኔ ግን ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም፤ እርሷ ይህን ሽቱ በሰውነቴ ላይ አፍስሳ ለመቃብሬ አደረገች። እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በማናቸውም ስፍራ በሚሰበክበት እርሷ ያደረገችው ደግሞ ለእርሷ መታሰቢያ እንዲሆን ይነገራል። ማቴ፥ 26፡7-13

ይህች ሴት አንድ ቀን መጥታ በጌታችን ራስ ላይ ዋጋው ውድ የሆነ ሽቱ በማፍሰሷ እንዲህ ከተባለላት ሥጋዋንና ነፍሷን ለሰጠች፣ መላ ሕይወቷን ለአካላዊ ቃል ተዋሕዶ ላቀረበች ለቅድስት ድንግል ማርያም ከዚህች ሴት በበለጠ ያደረገችው ሊነገር አይገባውምን? ማርያም እንተ ዕፍረት ለተነሳሕያን አብነት ትሆን ዘንድ "እርሷ ያደረገችው ደግሞ ለእርሷ መታሰቢያ እንዲሆን ይነገራል" ከተባለላት ከመጀመሪያው ጀምሮ በንጽሕናና በቅድስና ለሚኖሩና እንዲህ ዓይነት ሕይወት ስለመኖር አብነት የምትሆነው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እርሷ ያደረገችው ይነገርላት ዘንድ የተገባ አይደለምን? በጌታችን መዋዕለ ሥጋዌ መጨረሻ ላይ የመጣችው ማርያም እንተ ዕፍረት እንዲያ ከተባለላት ከመጀመሪያው ጀምሮ፣ ሰው ሆኖ በማኅፀኗ ሲፀነስ ጀምሮ ሥግው ቃልን የምታውቀውና ወደዚህ ዓለም ከመግባቱ እንሥቶ እስከ ዕርገቱ ድረስ ያልተለየችውና አብራው የኖረችው ቅድስተ ቅዱሳን ንጽሕተ ንጹሐን ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ቢነገርላት ምን ይደንቃል?

የሰውን ልጅ ከወደቀበት ጥልቅ ሊያወጣው ሰው የሆነው አምላክ የሰውን ሥጋና ነፍስ በሙሉ የወሰደው ከእርሷ ነው፡፡ የአካላዊ ቃል ሰው መሆን በሰው መጸእ ሕይወትና መዳረሻ ላይ አዲስ መንገድ የቀየሰ ነበር፡፡ በሥጋዌው "አዲስ ሰው" ተወለደ፡፡ "ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፏል፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ" የተባለው ከእርሷ በነሣው ባሕርይ ነው፡፡ 1 ቆሮ. 15፡45

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ የሚያምኑ ስለሚያገኙት ልዩ ልደት ሲናገር "ለተቀበሉት ሁሉ ግን፣ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው" ካለ በኋላ የዚህን አዲስ ልደት ሁኔታ ሲናገር ደግሞ "እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም" አለ፡፡ ዮሐ. 1፡12-13 እርሱ የተወለደው ከእመቤታችን ማኅፀን ነው፣ የእመቤታችን የማኅፀኗ ፍሬ ነው፡፡

እርሱ መወለድን ሳይንቅ "ወኢእምሥምረተ ብእሲ ወብእሲት - ከወንድና ሴት ፈቃድ ውጭ" በሆነ በፍጹም ድንግልና መወለዱ እኛም ለምንወለደው ከወንድና ከሴት ፈቃድ ላልሆነው ለመንፈሳዊው ልደት በር ከፋችና ፀረቦን ነበር፡፡ የእርሱ ከእርሷ መንፈሳዊ በሆነ ሁኔታ መወለድ ምእመናን ለሚያገኙት መንፈሳዊ ልደት መሠረትም አርአያም፣ ፀረቦንም ነው፡፡

እንዲሁም እመቤታችን የእግዚአብሔር አንድነትና በአንድነቱ ውስጥ ያለው ልዩ ሦስትነት (ምሥጢረ ቅድስት ሥላሴ) የተገለጸባት ናት፡፡ "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፣ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" ተብላለችና፡፡ በዚህም መንፈስ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ፣ ሦስቱም በእመቤታችን ላይ ተገልጠዋል፡፡ "በአንቺ ላይ ይመጣል" የተባለው መንፈስ ቅዱስ፣ "የልዑል ኃይል ይጸልልሻል" የተባለው እግዚአብሔር አብ፣ እና "ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ" የተባለው እግዚአብሔር ወልድ በእርሷ ላይ ተገልጠዋል፡፡ ይህ የሆነውም በዮርዳኖስና በደብረ ታቦር ከተፈጸመው የቅድስት ሥላሴ የመገለጥ ምሥጢር አስቀድሞ ነው፡፡ ነቢዩ ዳዊት "ወያስተርኢ አምላከ አማልክት በጽዮን - የአማልክት አምላክ በጽዮን ይታያል" ብሎ የተናገረው ትንቢት ተፈጽመ፣ ፡ መዝ. 83፡7 ደራሲውም "በላዕሌኪ ወበዮርዳኖስ ወበታቦር ሥልስ ጊዜያተ፣ ለውሉደ ሰብእ ያርኢ ዘሥላሴሁ ግጻተ፣ ዘአልቦ ተውላጠ ወአልቦ ኅጸተ ..." በማለት የገለጸው ይህን ምሥጢር ነው፡፡

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋርና በሕዝቡ መካከል ለመኖሩ ምልክቱና ምስክሮቹ የቃል ኪዳኑ ታቦት እና በዚያ ላይ የተሣሉት ኪሩቤል ነበሩ፡፡ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ እግዚአብሔር ባሕርያችንን ባሕርዩ አድርጎ ከእኛ ጋር አንድ አካል አንድ ባሕርይ ለመሆኑ - አማኑኤል ለመሆኑ ምልክቷና ምስክሯ እመቤታችን ናት፡፡ በታቦቱ ውስጥ የነበረው በእግዚአብሔር ጣቶች ፀሐርቱ ትእዛዛት የተጻፉበት ጽላቱ እንደ ነበር በእመቤታችን ማኅፀን ደግሞ አካላዊ ቃል በግብረ መንፈስ ቅዱስ ከእርሷ በማኅፀኗ ሰው ሆኗል፡፡ ምስለ ፍቁር ወልዳን - የእመቤታችን ሥዕል ከተወዳጅ ልጇ ጋር - የሐዲስ ኪዳን የሥጋዌ ምልክት አድርገን የምንጠቀመው ለዚህ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የእኛን ባሕርይ ነሥቶ ሰው ለመሆኑ ቋሚ ምስክሯ እርሷ ናትና፡፡

ከዶሴቲኮች ስህተት የሚጠብቀው ከእርሷ ባሕርይዋን ባሕርዩ አድርጎ ሰው መሆኑንና መወለዱን መረዳት፣ ማመንና መቀበል፣ ይህንም መማርና ማስተማር ሲኖር ነው፡፡ ይህን ችላ ማለት "ከእርሷ ምንም ነገር አልነሣም፣ ውኃ በቧንቧ ውስጥ እንደሚያልፍ እንዲሁ ዝም ብሎ ወጣ" የሚሉትን የዶሴቲኮችን[99] ክህደት በይፋም ሆነ በስውር መጋራትና ማራመድ ነው፡፡ እነዚህ መናፍቃን "ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነ መስሎ በምድር ላይ ተመላለሰ እንጂ በእውነት ሰው አልሆነም" ብለው ደፍረው የሚናገሩ ነበሩ፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ማሰብና ማስታወስ ግን የእግዚአብሔር ቃልን ሰው መሆን (የሥጋዌውን) እማናዊነት እፍ እውጥቶ የሚናገር ሕያው ምስክርና ከዶሴቲኮች ዓይነት ስህተትም የሚጠብቅ አጥር ቅጥር ነው፡፡ የሰው መዳን ይህን ድልድይ ዘልሎ፣ ይህን ችላ ብሎ ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ ወደ ዶሴቲኮችና ግኖስቲኮች፣ እንዲሁም ወደ ንስጥሮሳውያን ስህተት ይወስዳል፡፡

ከላይ በመኃትው ላይ እንዳየነው ግኖስቲኮች "የከፉው አምላክ ፍጥረት ስለሆነ የሰው ሥጋ ርኩስ ነው" ይሉ ነበር፡፡ ዶሴቲኮችም እንደ ግኖስቲኮቹ ቁስ አካላዊ ህልዎት ያለውን ነገር በሙሉ፣ የሰውን ሥጋ ጨምሮ፣ ርኩስ አድርጎ ይቆጥር የነበረው የዚሁ የፕላቶናዊው የግሪክ ፍልስፍና አማኞች ስለነበሩ ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ሥጋዋንና ነፍሷን ነሥቶ ሰው ሆነ የሚለውን የክርስትና መሠረታዊ ትምህርት አይቀበሉም ነበር፡፡ በእነርሱ እምነትና አስተምህሮ መሠረት ለአምላክ ሥጋን መዋሐድ ይቅርና መንካት እንኳ መርከስ ነበር፣ የማይታሰብ ነበር፡፡

[99] "Docetæ" - Docetism, from the Greek 'dokeo' - to seem, to appear.

ስለዚህም እነዚህ መናፍቃን አካላዊ የእግዚአብሔር ቃል ከእመቤታችን ሰው ሆኖ ተወለደ የሚለውን ትምህርት አጥብቀው ይቃወሙና አምርረው ይጠሉ ነበር፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በእውነት ሰው የመሆን ምልክትና ዓርማም ናትና የእግዚአብሔር ቃልን በእውነት ሰው መሆን የሚክዱ ሁሉ እርሷንም ይክዳሉ፣ ይጠላሉ፡፡ የእመቤታችን ነገር በነገረ ሥጋዌ ሲነሣ የማይወዱና እንደ ሌላ ነገር ቆጥረው ሊያልፉት የሚፈልጉ ሁሉ የግኖስቲኮችና የዶሲቲኮች ተረፈ ፕላቶናዊ ፍልስፍና እርሾ ያቦካቸው ሊጦች ናቸው፡፡ "ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ እንዲያቦካ አታውቁምን? ተብሏልና፡፡ 1 ቆሮ. 5፥6

## 5.3 እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም "ወላዲተ አምላክ" ትባላለችን? ለምን?

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ላይ መዝመትን እንደ ዓላማቸው ያደረጉት ተሐድሶዎች ከሚቃወሙት ጉዳይ አንዱ የእመቤታችንን "ወላዲተ አምላክ" መባል ነው፡፡ "ወላዲተ አምላክ አትባልም" ይላሉ፡፡ ለአብነትም "በውኑ በማርያም ማመን ይገባሃልን?" የተባለ መጽሐፋቸው ላይ ስለ እመቤታችን መቼም እምነት አለኝ የሚል ሰው ይቅርና በማንኛውም ሰው ክቡርነት የሚያምን ሰው እንኳ ሊናገራቸው የሚዘገንኑ ቃላትንና አባባሎችን በመጠቀም ጽፈዋል፡፡ በእውነቱ ሲታይ ክርስትና ማለት እመቤታችንን መስደብ፣ ወይም ክርስቶስን ማክበር ማለት እናቱን ማቃለልና ቅዱሳንን መናቅ ነው ተብሎ የተሰበከላቸው ይመስላሉ፡፡ በዚህ መጽሐፋቸው ላይ ተሐድሶዎች ስለ እመቤታችን ወላዲተ አምላክ መባል አለመባል ጉዳይ እንዲህ ብለዋል፡-

- "ማርያምን ወላዲተ አምላክ ብንላት ኑፋቄ ሊሆን ይችላልን?" ብሎ ይጠይቅና ራሱ ሲመልስ "ማርያምን የአምላክ እናት ወይም ወላዲተ አምላክ ማለት ኑፋቄ ነው" ይላል፡፡

"በውኑ በማርያም ማመን ይገባሃልን?" የተባለ፣ ጸሐፊው ራሱን "መጋቤ ጥበብ ሰሎሞን ዘሀገረ ጊሸን ደብረ ክርቤ ማርያም" ነኝ የሚል የተሐድሶ መጽሐፍ፣ ገጽ 78-80

ሳሙኤል ጎባት የተባለው አውሮፓዊ የፕሮቴስታንት ሚስዮን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ፕሮቴስታንት ለመለወጥ የተሻለው ዘዴ ቀስ በቀስ ከካህናቱና ከቤተ ክርስቲያኒቱ የአመራር አካላት ጋር መቀራረብን በመፍጠርና እነርሱን በመያዝ ነው ብሎ ያምን ነበር፡፡ እንደ እርሱ አረዳድና አባባል እንዲህ ባለ መንገድ ቤተ ክርስቲያኒቱን በአቋራጭ ወደ ፕሮቴስታንትነት መለወጥ ይቻላል የሚል ሃሳብ ነበረው፡፡ ስለሆነም ይኸው ሚሲዮናዊ ከእጨጌውና ከካህናቱ ጋር በፈጠረው የተንከል ቅርርብ የእርሱን እምነትና አመለካከት ለዕጨጌው ሲያስረዳ እንዲህ ብሎ ነበር፡-

- ". . . ከሴቶች ሁሉ የተመረጠች ብፅዕት ሴት እንደ መሆኗ መጠን ለእርሷ ካለኝ ታላቅ አክብሮት ሌላ በበኩሌ ማርያምን የእግዚአብሔር እናት ብሎ መጥራት ትልቅ ስሕተት ነው እላለሁ፡፡ ነገር ግን ሐዋርያት ሲጠሯት እንደ ነበረው የኢየሱስ እናት ብለን ብንጠራት በቂ መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡" (ሳሙኤል ጎባት፣ 1834፣ ዶናልድ ክረሚ፣ 1972)

ተሐድሶዎች "መጋቤ ጥበብ ዘሀገረ ግሸን ደብረ ክርቤ ማርያም" በሚል ለምድ ተከላነታቸውን ሸፍነው የሚያቀርቡልን ክህደት ቀደም ሲል የእነ ንስጥሮስ፣ ኋላም የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያኑ የእነ ሳሙኤል ጎባት ክህደት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን ልብ ሊባል የሚገባው ነገር ቤተ ክርስቲያኒቷን እናድሳለን በሚል ሽፋን እነ ሳሙኤል ጎባት ፕሮቴስታንታዊ ኑፋቄያቸውን ለማስረጽ የሞከሩበት አካሄድና ስልት ከምን ደረጃ ላይ እንደ ደረሰ ነው፡፡ ማለትም በፊት የባእድ አገር የፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን በራሳቸው አፍ ይጮኹት የነበረውን ጩኸት አሁን ግን ሀገር በቀል ባንዳዎችን መልምለው አሳድገው በእነርሱ አፍ ጩኸታቸውን ከማሰማት ደረጃ መድረሳቸው ነው፡፡

ይህም ምን ያህል ሥራ እንደ ሠሩብን ያሳያል፡፡ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክነት የሚቃወሙት ተሐድሶዎች ጩኸታቸው የእነ ሳሙኤል ጎባትና የአዝማቾቻቸው ጩኸት መሆኑንም ልብ ማለት ተገቢ ነው፡፡ ለዚህም ከላይ የተገለጹትን ሀገር በቀሎቹ ተሐድሶዎች በእመቤታችን ላይ የሚሉትንና አውሮፓዊው ሚሲዮን ሳሙኤል ጎባት የተናገረውን ማነጻጸር ነው፡፡ ሳሙኤል ጎባት ደግሞ አውሮፓዊ ፕሮቴስታንት እንጂ ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን አልነበረም፡፡ ስለዚህ የፕሮቴስታንቶችን እምነት ይዘው የሚጮኹ ተሐድሶዎችም እንደ አባታቸው እንደ ሳሙኤል ጎባት ፕሮቴስታንቶች እንጂ ኦርቶዶክሳውያን አለመሆናቸው ይኸው ከራሳቸው ተገለጠ፡፡

## 5.4 "<u>ወላዲተ አምላክ</u>"

### 5.4.1 የቃሉ ትርጉም

"ወላዲተ አምላክ" የሚለው ቃል ምንጩ (ጥንት የት መጣው) ግሪክ ሲሆን በግሪኩ (በጽርዑ) ቴዎቶክስ (Θεοτόκος - theotokos) የሚል ሲሆን ትርጉሙም "የእግዚአብሔር እናት"፣ "የአምላክ እናት"፣ "አምላክን የወለደች" ማለት ነው፡፡ "ወላዲተ አምላክ" የሚለው የሁለት ቃላት ጥምረት የሚገልጸው ዋና ሃሳብ ከንጽሕተ ንጹሐን ከቅድስተ ቅዱሳን ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ሰው የሆነውና በእኛ ባሕርይ (ከኃጢአት በስተቀር) ተወልዶ የተገለጠው ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው የሚለውን መሠረታዊ የሆነውን የክርስትና እምነትና ትምህርት ነው፡፡

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ናት፣ አምላክን ወልዳለች ስንል እግዚአብሔር በባሕርየ መለኮቱ የተገኘው ከእርሷ ከተወለደ በኋላ ነው ለማለት አለመሆኑ ግልጽ ቢሆንም መታወስ ግን ይኖርበታል፡፡ እግዚአብሔር በባሕርዩ ጥንትና ኋላ የለበትም፣ አስገኚና መነሻም የለውም፤ እርሱ ከጊዜ ጽንሰ ሃሳብ ውጭ የሆነ ዘለዓለማዊ አምላክ ነውና፡፡ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ያለ ነው፡፡ ለዚህ ነው ሙሴ "የአባቶቻችሁ አምላክ ወደ እናንተ ላከኝ ባልሁ ጊዜ ስሙስ ማን ነው? ባሉኝ ጊዜ ምን እላቸዋለሁ?" ብሎ በጠየቀው ጊዜ "ዘሀሎ ወይሄሉ - I AM THAT I AM - ያለና የሚኖር ወደ እናንተ ላከኝ በላቸው" በማለት ራሱን የገለጠው በዘለዓለማዊ ህላዌው ነው፡፡ ዘጸ. 3፡13-14 ስለዚህ እግዚአብሔር ሰው ሆነ፣ ተወለደ ስንል በሥጋዌ ምሥጢር ስለ ተፈጸመው ነገር ማለታችን መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡

እግዚአብሔር ስንል አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ማለታችን እንደ መሆኑ ሰው የሆነውና በእኛ ባሕርይ የተወለደው ከሦስቱ አካላት አንዱ የሆነው እግዚአብሔር ቃል በተለየ አካሉ ነው፡፡ ቅዱስ ወንጌል "በመጀመሪያው ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ" በማለት ስለ ቃል ቀዳማዊነትና እግዚአብሔርነት ከተናገረ በኋላ ዘመን ከተፈጠረ በኋላ ስለሆነው ነገር ሲናገር ደግሞ "ቃልም ሥጋ ሆነ፣ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ" በማለት የቃልን ሰው መሆን ይነግረናል፡፡ ስለዚህ አካላዊ ቃል ሰው ሲሆን በማኅፀኗ የፀነሰችውና በድንግልና የወለደችው እመቤታችን ናት፡፡ ስለዚህ እርሷን ወላዲተ አምላክ ያሰኛት ከእርሷ የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ስለሆነ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ " . . . ወእምኔሆሙ ተወልደ ክርስቶስ በሥጋ ሰብእ ዘውእቱ አምላክ ቡሩክ - ከእነርሱም [ከእስራኤላውያን] ክርስቶስ በሥጋ መጣ፣ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው" እንዳለ። ሮሜ 9፡5

ይህ "ወላዲተ አምላክ" የሚለው ቃል ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ "ቃል ሥጋ ሆነ" ሲል የገለጸውንና ቅዱስ ሉቃስ ደግሞ "የጌታዬ እናት" በማለት የገለጸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት በአንድ ላይ ጠቅልሎ የሚይዝ ቃል ነው፡፡ ዮሐ. 1፡14 ፤ ሉቃ 1፡43 "ቃል ሥጋ ሆነ" ማለትም አካላዊ የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር ቃል ከእመቤታችን የራሱ ገንዘብ አድርጎ ፈጥሮ የተዋሐደው የእኛ ባሕርይ በማኅፀነ ድንግል ማርያም አንድ አካል ሆነዋል፣ በምሥጢረ ተዋሕዶ ያለ መጠፋፋትና ያለ መቀላቀል፣ ያለ መለያየትና ያለ መከፋፈል አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነዋል ማለት ነው፡፡

ተዋሕዶውም አካላዊ ብቻ ሳይሆን ባሕርያዊም ስለሆነ እመቤታችን የወለደችው ብቻ ሳይሆን የፀነሰችውም ሥግው ቃልን - በባሕርዩ አምላክ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው፡፡ ስለዚህ ይህ "ወላዲተ አምላክ" የሚለው ቃል የእመቤታችንን የወላዲተ አምላክነት ክብር ከሚናገረው በላይ የክርስቶስን ማንነት በተመለከተ ሊኖረን የሚገባውን መጽሐፍ ቅዱሳዊና ኦርቶዶክሳዊ እምነት ጠቅልሎ የሚይዝ መሠረታዊ ቃል ነው፡፡

## 5.4.2 የቃሉ ነገረ መለኮታዊ ፋይዳ

ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕርዩ ከአብ ጋር አንድ መሆኑ (ὁμοούσιον - homoüsion - ዋሕደ ባሕርይ ምስለ አብ - Consubstantial with the Father) እና የባሕርይ አምላክ መሆኑ ራሱ ጌታችን የገለጠው እውነትና ያስተማረው ትምህርት መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ይህም በቅዱስ ወንጌል በሰፊውና በግልጽ የተጻፈ እውነት ነው፡፡ ሆኖም አርዮስና መሰሎቹ በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ላይ ያነሡት ኑፋቄና ጥያቄ በ325 ዓ.ም. በኒቅያ ጉባኤ ላይ በማያዳግም ሁኔታ ግልጽ ሆኖ ተብራርቷል፡፡ ይህ ማለት ይህን ትምህርት የተቃወሙትና እንግዳ ነገር ያመጡት አርዮስና መሰሎቹ ስሀተታቸው በዓለም አቀፋዊ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በይፋ በአደባባይ ተገልጦ ተነገረ ለማለት ነው እንጂ በኒቅያ ጉባኤ አዲስ ነገር ተወሰነ ማለት አለመሆኑም ግልጽ ነው፡፡ ጉባኤያት (ሲኖዶሳት) የቤተ ክርስቲያንን እምነት ይጠብቃሉ፣ ያስጠብቃሉ እንጂ አዲስ እምነት ሊፈጥሩ ወይም ሊሠሩ አይችሉም፤ እምነት ሰው ሠራሽ የአቋም መግለጫ አይደለምና፡፡

በኒቅያ ጉባኤ ላይ የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት የቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት መሆኑ፣ ከዚህ ውጭ ያለው የአርዮስ ኑፋቄ ደግሞ ባእድና ቤተ ክርስቲያን የምትጸየፈው መሆኑ ቢገለጽም ቅሉ አርዮሳውያን በቤተ ክርስቲያን ላይ ያደርሱ የነበረው የወረራ ዘመቻ ወዲያውኑ ተቋርጦ እፎይታ ተገኘ ማለት ግን አይደለም፡፡ አርዮሳውያን ጳጳሳትና መኳንንት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን እስከ 381 ዓ. ም. ድረስ ቀጣዩን ግማሽ ምእት ዓመት መፈንጫና መጫወቻ አድርገዋት ነበር፡፡ ሆኖም ግን ሐሰት ቢነግሥም ፀሐይ እስኪወጣ ድረስ እንደሚሰፍን እንደ ማለዳ ጤዛ ለተወሰነ ጊዜ ስለሆነ በኋላ ላይ እየከሰመና እንደ እክክ እየረገፈ መጥቷል፡፡ ሆኖም አርዮሳዊ እርሾና ውስጠ ነገሩ መልኩን እየለዋወጠ ቤተ ክርስቲያንን ማስቸገሩና ፈተና መሆኑ ግን ዛሬም ድረስ አልቀረም፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በሚያምኑት ወገኖች ውስጥ ደግሞ የመለኮታዊ ባሕርዩን እና የትስብእቱን ተዋሕዶ በተመለከተ ጥያቄና ውዝግብ መነሣት ጀመረ፡፡ ይህን ምሥጢር በመረዳትና በማብራራት ሂደት በዋናነት ሁለት ዓይነት አረዳዶችና አተረጓጎሞች ይታዩ ጀመር፡፡ አንደኛው የአንጾኪያ ትምህርት ቤት ሰዎች አረዳድና አተረጓጎም ሲሆን የእነርሱም የቴዎዶር ዘሞፕሰስቲያን አስተሳሰብ የተከተለና ክርስቶስን የሁለት ሰዎች ጥምረት አድርጎ የሚያስብ ነበር፡፡ በእነርሱ አስተምህሮ በባሕርይ እና በአካል ደረጃ ጥምረት (*Conjunction)* እንጂ ውሳጣዊና ባሕርያዊ ተዋሕዶ (*union)* የለም፡፡ ተዋሕዶ አለ የሚሉት በውጫዊ መገለጫው ደረጃ (Prosopic union) ነው፡፡ በመለኮታዊ ባሕርዩ እና በትስብእቱ መካከል የሚያደርጉት የልዩነት ድንበር ክርስቶስን ሁለት የተለያዩ ሰዎች (መለኮታዊ ልጅ እና ሰብእዊ ልጅ) በአንድ የገጽ (የፊት - prosopon) መገለጫ ላይ ብቻ ሲጣመሩ ዓይነት ሆኖ እንዲታይ አደረጉት፡፡ በእነርሱ እምነት ከእመቤታችን የተወለደው በኋላ ላይ አካላዊ ቃል ያደረበት - የቃል ማደሪያ - እንጂ ቃል የተዋሐደውና የራሱ አካል ያደረገው ሥግው ቃል አይደለም፡፡ ስለዚህም እመቤታችንን "ወላዲተ ሰብእ" - (Anthropotokos) ይሏት ነበር፡፡

በዚያን ዘመን የአንጾኪያ ትምህርት ቤት አስተምህሮ ተደርጎ ወደ መወሰድ ደረጃ ደርሶ የነበረውን ይህን ዓይነቱን አመለካከት ያራምድ የነበረው ንስጥሮስ የተባለው መነኩሴ ከሶርያ ገዳማት በአንዱ ይኖር የነበረ ሲሆን እንደበተ ርቱዕ ከመሆኑ የተነሣ በቀጥታ በንጉሡ ተመርጦ በ428 ዓ. ም. በቁስጥንጥንያ መንበር ላይ ፓትርያርክ ተደርጎ ተሾመ፡፡ እርሱም ችኩልና ስሜታዊነት የሚታይበት ስለ ነበር ገና መንበሩን እንደ ያዘ ወዲያውኑ እመቤታችን ወላዲተ አምላክ ናት የሚለውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በግልጽ መቃወም ጀመረ፡፡ ከዚያ በፊት በአንጾኪያ ይባል የነበረውን "ወላዲተ ሰብእ" - (Anthropotokos) የሚለውን አሻሻልኩ ብሎ "ወላዲተ ክርስቶስ - Christotokos - ክርስቶስን የወለደች" ልትባል እንጂ ወላዲተ አምላክ ልትባል አይገባም ይል ጀመር፡፡ በይፋ "ማንም ሰው ማርያምን የእግዚአብሔር እናት ሊላት አይገባም" አለ፡፡ ከእርሱ ጋር የማይስማሙትንም ማስፈራራትና መዛት ጀመረ፡፡ ይህን ትምህርቱን የያዙ መጣጥፎችን እየጻፈ ማሰራጨቱንም ተያያዘው፡፡ የራሱን ትምህርትም ሥልጣኑን ተጠቅሞ በቤተ ክርስቲያን ላይ በኃይልና በግድ ለመጫን ፈለገ፡፡ አንድ አናስጣስዮስ የተባለ የአንጾኪያ ቄስ በንስጥሮስ ላኪነትና ደጋፊነት በቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሕረት ላይ "ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ አትባልም" እያለ ማስተማሩን ተያያዘው፡፡ ንስጥሮስንም በቁስጥንጥንያ የነበሩ መነኰሳትና ምእመናን መናፍቅ ነህ እያሉ በግልጽ ይቃወሙት ጀመር፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሁከት እየተፈጠረ በመንበረ ፓትርያርኩ የነበረው የቅዳሴ አገልግሎት ብዙ ጊዜ እየተቋረጠ እንደ ገና እየቀጠለ በዚያ ዓይነት ሁኔታ ይካሄድ ነበር፡፡

ይህ ነገርም ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ከቅዱስ ቄርሎስ ዘንድ ደረሰ፡፡ በመጀመሪያ ቅዱስ ቄርሎስ የንስጥሮስን ስም ሳያነሳ በጉዳዩ ላይ ትምህርት የሚሰጥ አጠር ያለ ጽሑፍ ለግብጽ መነኰሳትና ለምእመናን የሚሆን መግቢያ ዓይነት መልእክት አዘጋጀ፡፡ በመቀጠልም ንስጥሮስ ከያዘው አቋሙና ያንኑ ከማስፋፋት ወደ ኋላ የማይል መሆኑ ግልጥ እየሆነ ሲሄድ ጠንከር ያለ ነገረ ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው ሁለተኛ መልእክት አዘጋጀ፡፡ ይህም "ሁለተኛው የቅዱስ ቄርሎስ መልእክት ወደ ንስጥሮስ" ተብሎ የሚታወቀው ነው፡፡ በዚህ መልእክቱም ቅዱስ ቄርሎስ ወላዲተ አምላክ የሚለው ቃል በቤተ ክርስቲያን እምነት ላይ ጥልቅና መሠረታዊ አንድምታ ያለው መሆኑን ንስጥሮስ እንዲረዳውና እንዲያስተውለው ለማድረግ ሞከረ፡፡ዘለዓለማዊ የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ በድንግል ማርያም ማኅፀን ሲፀነስ ባሕርየ ትስብእትን የራሱ አድርጎ የተፀነሰ ስለሆነ እርሷ የወለደችው ሥጋው ቃልን ነው፣ ስለዚህም ነው ወላዲተ አምላክ የምትባለው በማለት ቅዱስ ቄርሎስ ጻፈለት፡፡

ቅዱስ ቄርሎስ "ስለዚህ እርሷ ወላዲተ አምላክ ናት፣ ይህ ቃልም እውነተኛና ትክክለኛ ለሆነ ነገረ ክርስቶስ መሠረት ነው" በማለት ለማስረዳት ሞከረ፡፡ ንስጥሮስ ግን "አንተ አታስተምረኝም" በሚል መንፈስ በእምቢታው ጸና፡፡ እንዲያውም ቅዱስ ቄርሎስን ኑፋቄ እያስተማረ ነው ብሎ ይከስሰው ጀመረ፡፡ ንስጥሮስ ከአቋሙ ፍንክች የማይል መሆኑ ግልጽ እየሆነ በሄደ ጊዜ ቅዱስ ቄርሎስ አሥራ ሁለት ቃለ ግዝት ያለበት መልእክት ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር ላከለት፡፡ ይህም ወደ ንስጥሮስ የተላከው የቅዱስ ቄርሎስ ሦስተኛው መልእክት ነው፡፡ ንስጥሮስ የማይመለስ በመሆኑ በ431 ዓ.ም. በኤፌሶን ጉባኤ ላይ እርሱ ከነ ትምህርቱ ተወገዘ፡፡

ንስጥሮስ አርዮስን በጽኑ የሚቃወም ሰው ነበር፡፡ "ክርስቶስ ዕሩቅ ብእሲ (ሰው ብቻ) ነው" በሚሉት አርዮሳውያን ላይ የሚከለክል ሕግ እንዲወጣ የዘመኑን መንግሥት እስከ ማሳመንና ማስፈጸም ደርሶም ነበር፡፡ ሆኖም ግን በእመቤታችን ማኅፀን የተፀነሰውና ከእርሷ የተወለደው ክርስቶስ አምላክ መሆኑን አልቀበልም አለ፡፡ ንስጥሮስ ወላዲተ አምላክ የሚለውን መቃወሙ የክርስቶስን ተዋሕዶ ከመቃወሙና ካለማመኑ የተነሣ የመጣ ነበር፡፡ክርስቶስን በውጫዊ ሁኔታ ብቻ በአንድ ቆዳ እንደ ተጠቀለሉ የሁለት ሰዎች ውጫዊ መገናኘት አድርጎ ነበር የተረዳው፡፡ ይህ አስተምህሮም የአምላክን ሰው መሆን (ሥጋዌውን) ምትሐት፣ ሐሰት እና ባዶ ቃላት ብቻ ያስመስለዋል፡፡ ይህን ቃል መቃወሙ ለእመቤታችን የሚገባውን ክብር አለመስጠቱ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ከዚያ በላይ በዋናነት ግን የመዳናችንን መሠረትና ክርስትናን በአጠቃላይ ከመሠረቱ ከንቱ የሚያደርግ አደገኛ ኑፋቄ ነበር፡፡

## 5.4.3 የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክነት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

"ወላዲተ አምላክ" የሚለው ስያሜ በአጽንዖት የሚገልጸው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የወለደችው ሕፃን "ዕሩቅ ብእሲ" አለመሆኑንና እንድያ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ነው፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ቃልን ሁለት ልደት የሚገልጽ ነው፤ መጀመሪያ ከአብ ያለ እናት የባሕርይ ልደት፣ ሁለተኛ ደግሞ ከእመቤታችን ያለ አባት በፈቃዱ የተፈጸመው ልደት ነው፡፡ ስለዚህም ከእመቤታችን የተወለደው ሌላ ማንም ሳይሆን ከእኛ የአእምሮ መረዳትና የቋንቋ የመግለጽ ዓቅም ውጭ የሆነውን ቀዳማዊ ልደት ከአብ በባሕርዩ የተወለደው ራሱ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ነው፡፡ ይህም የኦርቶዶክሳዊ እምነት መሠረትና ዓምድ ነው፡፡

ሁለተኛ ልደት የሚባለውም ሥጋዌው (ሰው መሆኑ) ነው፡፡ እመቤታችን በመፅነሷና በመውለዷ ሂደት የተገኘው አዲስ "ወልድ" አይደለም፤ ያው ዘለዓለማዊውና ቀዳማዊው የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ አካላዊ ቃል የሰውን ባሕርይ ገንዘቡ አድርጎ ራሱ ሰው ሆነ እንጂ፡፡ የእመቤታችን የአምላክ እናትነት ምሥጢር ያለው እዚህ ምሥጢር ውስጥ ነው፡፡ ከእርሷ የተወለደው እርሱ ሥግው ቃል (ሰው የሆነ አምላክ) ከሆነ እርሷ ደግሞ የእርሱ እናት መሆኗ ግልጽ ነው፡፡ እርሱ አምላክ እንደ መሆኑ እርሷ ደግሞ እርሱን የወለደች እንደ መሆኗ ወላዲተ አምላክ መባሏ የግድ ነው፡፡ ከእርሷ የተፀነሰውና የተወለደው ከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ ነው፡፡ ሥጋዌውን በትክክል ለመረዳት በእመቤታችን ማኅፀን የተፀነሰው አካላዊ ቃል የእኛን ባሕርይ ከእርሷ ነሥቶ (የራሱ አድርጎ) መሆኑን በሚገባ መረዳትና መገንዘብ የአምላክን ሰው የመሆን ምሥጢር እንዲሁም ምክንያቱንና ያገኘነውን ጸጋ በሚገባ ለመረዳት ቁልፍ ነው፡፡

በአምላክ ሰው የመሆን ምሥጢር የእግዚአብሔርን ፈቃድና መንሻ ብቻ ይዞ በእንጻሩ ከእመቤታችን ባሕርይዋን ገንዘብ አድርጎ ስለ መወለዱና ስለዚህ መሠረታዊ ነጥብ ፋይዳ ግድ የለሽ መሆን ወይም ይህን እውነታ እንደ ሌለ መቁጠርና ቦታ አለመስጠት ወይም ማቃለልና መንቀፍ ቢያንስ ሁለት መሠረታዊ ስህተቶችን ያመለክታል፡፡ አንደኛው የእግዚአብሔር ቃል ከእመቤታችን የተወለደው በእውነት ባሕርይዋን ነሥቶ ነው የሚለው ይዘንጋና "በእርሷ ውስጥ ያለፈው ውኃ በቧንቧ ውስጥ እንደሚያልፈው ነው፤ ከእርሷ ምንም ነገር አልነሣም" ወደሚለው ዶሴቲኮች የሚባሉት መናፍቃን ይሉት ወደ ነበረው ኑፋቄ ይወስዳል፡፡ የአምላክ ሰው የመሆን ምሥጢር (ምሥጢረ ሥጋዌ) ስንል ይህ የተፈጸመው በእመቤታችን በኩል መሆኑን የሚናገረውን መጽሐፍ ቅዱስን ሽምጥጦ ሳይክዱ ይህን መካድ ደግሞ አይቻልም፡፡

ስለዚህ የአምላክን ሰው የመሆን ምሥጢር (ሥጋዌውን) ከዶሴቲኮች ዓይነት ኑፋቄ የሚጠብቀውና የሚያርቀው፣ እንዲሁም ሰው ሆነ ስንል በእውነት የእኛን ባሕርይ ገንዘቡ አድርጎ የተዋሐደው መሆኑን የሚገልጸው ሥጋዌውን ስናስብ ክርስቶስ ባሕርይዋን ባሕርዩ አድርጎ ከነሳባትና ከተወለደባት ከእናቱ ከድንግል ማርያም ጋር ማሰብ ስንችል ብቻ ነው፡፡ ከጥንት ጀምሮ በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ የእመቤታችን ሥዕል ሲሣል በዋናነት የሚሣለው የሥጋዌው ሥዕል (ምስለ ፍቁር ወልዳ - እመቤታችን ከተወዳጅ ልጇ ጋር) የሆነው ለዚህ ነው፡፡ከልጇ ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሆና ነው የምትሣለው፡፡ የጌታችን ሰው የመሆን ሥዕል ያለ ድንግል እናቱ እንዴት ሊሣል ይችላል? አለበለዚያ ይህ ወደ ዶሴቲኮች ኑፋቄ ላለመውሰዱ ወይም የእነርሱ እርሾ የሌለበት ለመሆኑ ምንም ዓይነት ዋስትና የለውም፡፡

ሌላው ሁለተኛው ደግሞ ሥጋዌው (ሰው መሆኑ) በእኛ በሰዎች ሁለንተናዊ ሕይወትና ማንነት ላይ ያመጣው አዎንታዊ ለውጥ፣ እንዲሁም ሰብአዊ አንድምታዎቹና ነጸብራቆቹ ይሸፈናሉ፡፡ በፅንሡቱና በልደቱ እርሱ የእኛን ባሕርይ ገንዘብ አድርጎ ሰው በመሆኑ እኛን ወደ እርሱ ከፍ ከፍ ያደረገን መሆኑ፣ ለእኛ የእርሱን ልጅነት የማግኘት ጸጋ መንገዱ የተከፈተልን በዚህ መሆኑ ይዘነጋል፡፡

ቃል ሥጋ የሆነው እኛን ወደ እርሱ ከፍ ለማድረግ ነው፡፡ የሥጋዌው መላ ውጤትና በእኛ ሁለንተናዊ ሕይወት ላይ ያመጣው ለውጥ በሙሉ ወደ አንድ ጠርዝ ላይ ብቻ ይሰበሰባል፡፡ የሥጋው ቃል ሰው የመሆን ምክንያትና የሰጠን ጸጋ ሁሉ ሁለንተናዊ አንድምታው ይዘነጋና አንድ የሆነ ነጠላ ሃሳብ ላይ (የእግዚአብሔር ቁጣ ወይም ፍቅር፣ ፍርድ ወይም ይቅርታ፣ ወዘተ) የሚሉ ነገሮች ላይ ብቻ እንዲንጠለጠል ያደርገዋል፡፡ ይህም ከላይ በነገረ ድኅነት ክፍል እንዳየነው በዚህ መስመር የሚያስቡትን ሰዎች መዳንን ገድበውና ወስነው ከቅጣት ማምለጥና ከፍርድ መዳን ላይ ብቻ እንዲያተኩር አድርገው እንዲረዱት አድርጓቸዋል፡፡ ስለዚህ መዳንን በትክክለኛ መልኩ ለማየትና ሁለንተናዊ የሆነውን የመዳን ጸጋ ለመረዳት አምላክ ሰው ሲሆን ከመጀመሪያው የመጣበትን መንገድ ከብሥራቱና ቀጥሎም በፅንሠቱ ከማኅፀን ድንግል ጀምሮ ያደረገውን ባሕርያችንን የራሱ አድርጎ መንሣቱን በሚገባ ከማስተዋልና ከማድነቅ መጀመር ይገባል፡፡ አለበለዚያ ከመነሻው የተሳሳተ አስተሳሰብ ወደ ትክክለኛ ድምዳሜና ፍጻሜ ያደርሳል ብሎ ማሰብ ከባድ ነው፡፡

አምላክ የእኛን ባሕርይ ከእመቤታችን ነሥቶ ሰው ሲሆን በእኛ ላይ አማናዊና ዘላቂ፣ እንዲሁም ቋሚ የሆነ መሠረታዊና ታላቅ ለውጥ መጥቷል፡፡ ይህም ማለት ባሕርያችን ከጥንተ ተፈጥሮው ተለውጧል ማለት ሳይሆን በፊት ያልነበረውን ልዩ ክብርና ጸጋ አግኝቷል ለማለት ነው፡፡ የእኛ ባሕርይ እንደ ቀድሞው (አካላዊ ቃል ገንዘቡ አድርጎ ሳይዋሐደው ከዚያ በፊት እንደ ነበረው) የወደቀና ዲያብሎስና ኃጢአት የሚሜወቱበት መሆኑ ቀርቶ አካላዊ ቃል ከራሱ አካልና ባሕርይ ጋር አንድ አድርጎ ስለ ተዋሐደው ቀዳማዊ ባሕርዩን ሳይለቅና ሳይለወጥ በተዋሕዶ ርስት ኃጢአትንና ዲያብሎስን የቀጠቀጠና ሞትን ድል ያደረገ፣ በየማነ አብ በዘባነ ኪሩብ የሚቀመጥ አምላክ ሆኗል፡፡ ይህ የሥጋዌው ድንቅ ውጤትና ሥጦታ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በሰው ሕይወትና ክብር ላይ ያመጣው ለውጥ እጅግ ጥልቅና ድንቅ ነው፡፡ እኛ ሰዎች አጥተነው የነበረው ነገር ተመልሶልን የታሪካችን አቅጣጫ መቀየር የጀመረው ከዚህ ነው፡፡ ስለዚህ ይህን መሠረት ትቶና ዘንግቶ ሮጦ ከቅጣት ወይም ከፍርድ መዳን ላይ ብቻ መንጠልጠል ባሕርያችን ያገኘውን ልዩና ሁለንተናዊ የሆነ ታላቅ ክብር ይሸፍነዋል፡፡ ቃል ሥጋ የሆነውና በእኛ መካከል ያደረው ለዚህም ነውና፡፡

ስለዚህ የእመቤታችንን ወላዲተ አምላክነት መረዳትና ማመን አካላዊ ቃል በእርሷ ሰው ሆኖ በመፀነሱና የእኛን ባሕርይ የእርሱ ገንዘብ አድርጎ በመዋሐዱ ያገኘነውን ከመታሰብና ከመነገር በላይ የሆነውን ጸጋ ለመረዳት ቁልፍ ነው፡፡ እንዲያ ካልሆነ ግን ክርስትናን እንዲሁ ስሙን ብቻ መጥራት እንጂ ውስጡን በሚገባ ለማወቅ አይቻልም፡፡ የክርስትና ቁልፍ ያለው የእግዚአብሔር አካላዊ ቃል በማይመረመር ጥበቡ በማኅፀነ ድንግል ማርያም የእኛን ባሕርይ የራሱ ባሕርይ አድርጎ ከመንሣቱ (ከመዋሐዱ) ላይ ነውና፡፡ ልደቱ፣ ስደቱ፣ ጥምቀቱ፣ ማስተማሩ፣ . . . ሞቱ፣ ትንሣኤው፣ ዕርገቱ ሁሉ ከዚህ መሠረት የቀጠሉ ናቸውና፡፡ ተሐድሶዎች ከላይ በክፍል አንድ እንዳየነው በአካላዊ ቃል ተዋሕዶ የእኛ ባሕርይ ያገኘውን ይህን ታላቅ ጸጋና ክብር ካለመረዳታቸው የተነሣ ነው የሰውን ባሕርይ "የረከሰ ባሕርይ ነው፣ ከእግዚአብሔር ጋር የተጣላ አዳማዊ ባሕርይ ነው፣ ኃጢአተኛ ባሕርይ ነው፣ ..." እያሉ የተናገሩት፡፡ አዎ፣ ከመሠረቱ ያልተረዱትን ኋላ ከየት ያምጡት?

በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ተጽፎ እንደምናገኘው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ሲያበሥራት ከእርሷ የሚወለደው ማን መሆኑን የተናገረው በግልጽ ነው፤ እንዲህ በማለት፦ "እነሆም ትፀንሻለሽ፣ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፣ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ። እርሱ ታላቅ ይሆናል፣ የልዑል ልጅም ይባላል፣ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሣል፤ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም።" ሉቃ. 1:31-33 በመቀጠልም "መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፦ መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" በማለት በማያሻማ ሁኔታ እመቤታችን ድንግል ማርያም የምትወልደው ሌላ ሳይሆን ራሱን "ቅዱሱን

የእግዚአብሔር ልጅ" መሆኑን ተናግሯል፡፡ ሉቃ. 1፡35 ከእርሷ የተወለደው "ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ" ከሆነ ታዲያ እርሷ ወላዲተ አምላክ አትባልም የሚባልበት ምን ምክንያት ሊኖር ይችላል? ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይስ ማን ይናገር?

የዮሐንስ መጥምቅ እናት ኤልሳቤጥም እመቤታችን በፈቃደ አምላክ በብሥራተ መልአኩ ሥግው ቃልን ፀንሳ ሳለ፣ ግን ከትሕትናዋ ብዛት የተነሣ ልትጠይቃት ወደ እርሷ በመጣች ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት "<u>የጌታዬ እናት</u> ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?" በማለት እመቤታችን የጌታ እናት መሆኗን ገና ሥግው ቃል በማኅፀን ሳለ መስክራለች፡፡ ሉቃ. 1፡43 ስለዚህ ከተወለደ በኋላ ብቻ ሳይሆን ሲፀነስ ጀምሮ እርሱ ባሕርያችንን ገንዘብ አድርጎ በሥጋ ርሰት ሰው የሆነ አምላክ ነው፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ የኤልሳቤጥ ምስክርነት ከማን መሆኑን በግልጽ እናውቅ ዘንድ "በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት" በማለት የተናገረችው ቃል - "የጌታዬ እናት" የሚለው - የሰው ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት መሆኑን እንድናውቅ አድርጎናል፡፡ ሉቃ. 1፡41

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች <u>የተወለደውን ልጁን ላከ</u>" በማለት ከእመቤታችን የተወለደው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ግልጽ በሆነ ሁኔታ ተናግሯል፡፡ ገላ. 4፡4 ምክንያቱም እግዚአብሔር የላከውና ከእመቤታችን የተወለደው ያው አንዱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ይላልና፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ ሌላ፣ ከድንግል ማርያም የተወለደው ግን ሌላ አይደለምና፡፡ እንዲሁም "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ" በማለት ከእመቤታችን የእኛን ባሕርይ ገንዘብ አድርጎ የተወለደውና ስለ እኛ ደሙን ያፈሰሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ሥግው ቃል - እግዚአብሔር እንደሚባል በግልጽ አስተማረን፡፡ የሐዋ. 20፡28 ስለሆነም "ወላዲተ አምላክ" የሚለው ቃል የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ማጠንጠኛ መሠረታዊ ቃል ነው፡፡ ይህን የካደ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን የማይቀበልና የካደ ነው፤ ክርስቲያን ተብሎ ለመጠራትም አይበቃም፡፡ ነገረ ሥጋዌንና መጽሐፍ ቅዱስን፣ እንዲሁም የቃሉን ባለቤት እግዚአብሔርን የማይቀበል ነውና፡፡

"የአዳም ልጅ፣ የእግዚአብሔር ልጅ" ተብሎ የተገለጠው ያው አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ሉቃ. 3፡38 የአዳም ልጅ (ከእመቤታችን የተወለደው) ሌላ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ደግሞ ሌላ አይደለም፤ ከዘመንና ከምንም ነገር በፊት፣ ልደት ቀድምናን ሳያስቀርበት ከአብ ባሕርይ የተወለደው እርሱ በኋላም በፈቃዱ ከቅድስት ድንግል የተወለደው ያው አንዱ እርሱ ነው እንጂ፡፡ እግዚአብሔር አብም ስለ ባሕርይ ልጁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመሰክር መጀመሪያ በዮርዳኖስ፣ ኋላም በደብረ ታቦር "ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር - የምወደው ልጄ ይህ ነው" አለ እንጂ "በዚህ በምታዩት ሰው ውስጥ ያደረው እርሱ ልጄ ነው" አላለም (ይቅር ይበለንና)፡፡ ማቴ. 3፡17 ፤ 17፡5 አስቀድሞ በትንቢትም እንዲህ ተብሎ ተነግሯል፡- "ሕፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፣ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፣ ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፣ ለሰላሙም ፍፃሜ የለውም፡፡" ኢሳ. 9፡6-7 በተዋሕዶ ምሥጢር ከእመቤታችን ሰው ሆኖ የተወለደው ሕፃን "ሥግው ቃል የባሕርይ አምላክ" ካልሆነ በስተቀር "አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፣ ስሙም ድንቅ፣ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል" ሊባል እንዴት ይቻላል? ለፍጡር "ድንቅ መካር ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት" መሆን አይቻለውምና፡፡ በምሥጢረ ሥጋዌ ሕፃን ሆኖ ከእመቤታችን የተወለደው እርሱ ድንቅ መካር ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ነው፡፡

ከእመቤታችን በፈቃዱ በተወለደው ልደት ሕፃን ሆኖ ቢወለድም፣ አንድ ዓመት ሁለት ዓመት ... ሠላሳ ዓመት ሆነው እየተባለ ዘመን ቢቆጠርለትም እርሱ ዘለዓለማዊና የዘላለም አባት ነው፡፡ ስለዚህም በምሥጢረ ተዋሕዶ ከእመቤታችን የተወለደው ሥግው ቃል (God Incarnate) ስለሆነ እርሷም ወላዲተ አምላክ ትባላለች፡፡ ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ ግልጽ እውነት ነው፡፡ ይህን አለመቀበል መጽሐፍ ቅዱስን በአዋጅ መካድ ነው፡፡

እመቤታችን ወላዲተ አምላክ አትባልም የሚሉት ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት የማያምኑ ሰዎች ናቸው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ መሆኑን፣ የተወለደውና ሰው የሆነውም ከእመቤታችን ከቅድስት ደንግል ማርያም መሆኑን የሚያምን ሰው እርሷ ወላዲተ አምላክ መሆኗን ከመቀበል ውጭ መሆን እንዴት ይችላል? ጌታችን በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ሳለ ካደረጋቸውና ከተናገራቸው ነገሮች ስለ አንደኛው ሲናገር ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ "ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን አንቺ ሴት፣ እነሆ ልጅሽ አላት" አለ፡፡ ጌታችን ራሱ "እናቴ" ካላት፣ ወንጌላዊውም "እናቱ" ካላትና እርሱ ደግሞ አምላክ ከሆነ እርሷ ወላዲተ አምላክ መባሏ የተገባ ነው፡፡ ዮሐ. 19:26-27

ነገር ግን ከላይ የጠቀስናቸው እነ ሳሙኤል ኀብትና ሀገር በቀል ተከታዮቻቸው ተሐድሶዎች "እርሷ እንደ መጽሐፉ ቃል የኢየሱስ እናት ብቻ መባል ይበቃታል፣ የአምላክ እናት መባል መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም" የሚሉት የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ስለማያምኑ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ "ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" የሚለው ቃል፣ እንዲሁም "የጌታዬ እናት" . . . የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈው እንቀበለዋለን እናምንበታለን በሚሉት መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ስለዚህ "የአምላክ እናት መባሏ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም" የሚሉት ወይ መጽሐፍ ቅዱስን አለማወቅ ነው፣ አለዚያ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን ያለማመን ችግር ነው፡፡ እርሷ እነርሱም እንዳመኑት የኢየሱስ እናት ከሆነችና ኢየሱስ ደግሞ አምላክ ከሆነ እርሷ የአምላክ እናት መባሏ የግድ ነው፡፡ ነገር ግን እርሷን ወላዲተ አምላክ አትባልም ማለት የወለደችው ኢየሱስ አምላክ አይደለም ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ አርዮሳዊና ንስጥሮሳዊ ጣምራ ኑፋቄ ነው፡፡

ከእርሷ የተወለደው "ኢየሱስ" ተብሏል፡፡ "ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ" እንደ ተባለ። ማቴ. 1:21 "ኢየሱስ" ማለትም ትርጉሙ በመልአኩ እንደ ተነገረው ሕዝቡን ሁሉ ከኃጢአት የሚያድን መድኃኒት ማለት ነው፡፡ ይህ ከእርሷ የተወለደው ኢየሱስ መለኮት የተዋሐደው ሥግው ቃል ካልሆነ በስተቀር፣ ከእርሷ የተወለደው ሰው ብቻ ቢሆን ኖሮ ሕዝቡን ሁሉ የሚያድን መድኃኒት መባል እንዴት ይቻለዋል? መድኃኒት መባል የተገባው፣ መድኃኒት የሆነንም ከእርሷ የተወለደው ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) ሳይሆን የእግዚአብሔር አካላዊ ቃል በተዋሕዶ - ሥግው ቃል - ስለሆነ ነው፡፡ ስለዚህም እርሷ የሥግው ቃል እናት፣ ወላዲተ አምላክ ትባል ዘንድ በእውነት የተገባ ነው፡፡

ይህን ሁሉ ያስተዋለ አንድ ሊቅ በመገረም እንዲህ አለ፡- "ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊውን አምላክ መውለዷን፣ ማጥባቷን፣ እንደ ሕፃን በዕቅፏ ማቀፏን ስናስበው ይህን ድንቅ ምሥጢር ለመረዳትና ለማሰላሰል እንኳ ከአእምሯችን በላይ ይሆንብናል፡፡ ፍጡር የሆነች እርሷ ወደ መለኮታዊ ባሕርይና ክብር ይህን ያህል የቀረበችና የከበረች የመሆኗን ነገር ማሰብስ የሚያስከትለው ምን ዓይነት አግራሞትንና ፍርሃትን ይሆን?" ይህም ቅዱስ ኤፍሬም "አይ ልቡና ወአይ ኅሊብ ወአይ ሰሚዕ ዘይክል አእምሮ ዝንቱ ምሥጢር መንክራት ዘይትነበብ ላዕሌሃ - ስለ እርሷ ድንቅ ሆኖ የሚነገረውን ይህን ምሥጢር ማወቅ የሚቻለው ምን ልቡ ነው! መናገር የሚቻለው ምን አንደበት ነው! መስማት የሚቻለውስ ምን ጆሮ ነው!" ብሎ ከገለጸው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ (ውዳሴ ማርያም ዘሐሙስ)

በአጠቃላይ ንስጥሮስና ንስጥሮሳውያን እና ሀገር በቀል ልጆቻቸው ተሐድሶዎች ወላዲተ አምላክ የሚለውን መግለጫ ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም መስጠት አይገባም ማለታቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ፣ እንዲሁም ከነገረ ድኅነት ትምህርት ጋር ፍጹም ተቃራኒ ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የእመቤታችንን ወላዲተ አምላክ መባል በተመለከተ የአበው ቀደምትን ትምህርት እንመልከት፡፡

## 5.4.4 የእመቤታችን ወላዲተ አምላክነት - በቀደምት አበው ትምህርት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክ ብሎ መጥራት ከቅዱሳን ሐዋርያትና ከእነርሱ ዘመን ጀምሮ በነበረው ዘመን ሁሉ የነበረ ነገር ነው፡፡ ከመጀመሪያው ዘመን ሳይኖር ቆይቶ ወደ ኋላ በሆነ ዘመን ላይ ብቅ ያለ ነገር ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታ እንደ መሆኑ ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን የነበረ ነው፡፡ ይህ የእመቤታችን ወላዲተ አምላክነት በተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ትምህርቶች ላይ የምናገኘው እውነታ ነው፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን እንመለከታለን፡፡

ቅዱስ ቄርሎስ ንስጥሮስ "ወላዲተ አምላክ" የሚለውን መቃወሙ በነገረ ክርስቶስና በነገረ ድኅነት ላይ የሚያስከትለው ነገር መሠረታዊ የሆነ ኑፋቄ መሆኑን በሚገባ አስረድቷል፡፡ እነዚህን ነገሮችም እንደሚከተለው በሚገባ ለይቶ አውጥቷቸዋል፡-

1. ከድንግል ማርያም የተወለደው አካላዊ ቃል የእኛን ባሕርይ ነሥቶ (ተዋሕዶ) ሥጋው ቃል ካልሆነና ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) ከሆነ መዳናችን አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡ ምክንያቱም ክርስቶስ የተቀበላቸው ሕማማትና መከራዎች የሥጋው ቃል (ሥጋን የተዋሐደውና የእኛን ባሕርይ ባሕርዩ አድርጎ ሰው ሆኖ በሥጋ የተገለጠው አካላዊ የእግዚአብሔር ቃል) ሕማማትና መከራዎች ሳይሆኑ የዕሩቅ ብእሲ (የሰው ብቻ) ይሆናሉና፡፡ ፍጡር በሆነ በሰው ብቻ መዳን አይቻልምና ስለዚህ ድነናል ማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ ወላዲተ አምላክ የሚለውን ቃል መካድ የአምላክን ሰው የመሆን ምሥጢር (ምሥጢረ ሥጋዌን) እና የሰውን መዳን መካድ ነው፡፡

2. እንደዚሁም አካላዊ ቃል አዲሱን ሰው ዳግማዊ አዳምን ለመፍጠር አካላዊ ቃል ከእኛ ባሕርይ ጋር ሊያደርግ የሚያስፈልገው ተዋሕዶ፣ ንስጥሮስ እንዳለው ዓይነት አፍአዊና የጉርብትና ዓይነት ዝምድና ሳይሆን፣ ውሳጣዊና ባሕርያዊ የሆነ ጥብቅ እና አማናዊ የሆነ ተዋሕዶ ያስፈልገው ነበር፡፡ ይህ አይደለም ከተባለ የባሕርያችን መታደስ፣ በሐዲስ ተፈጥሮ የመዳናችን ነገር ሁሉ ከንቱ ይሆናል፡፡

3. ከዚህም ሁሉ ጋር ንስጥሮስ ዘላለማዊ ሕይወት የሚገኝበትን ምሥጢረ ቁርባንን ሕይወት የመስጠት ኃይል የሌለው በማድረግ ከዚህ ምሥጢር መካፈልን ወደ ሰው በላነት (Cannibalism) ደረጃ አውርዶታል፡፡ ምክንያቱም በእርሱ እምነትና አስተምህሮ በመሠዊያው ላይ የሚደረገውና ምእመናን የሚበሉት ሥጋ አካላዊ ቃል የተዋሐደውና የራሱ አካልና ባሕርይ ያደረገው ሳይሆን ፍጡር የሆነ የሰው ሥጋ ብቻ ነውና፡፡ "ዕሩቅ ብእሲ - ሰው ብቻ" መብላት ደግሞ ሕይወትና መድኃኒት ሊሆን አይችልም፡፡

ቅዱስ ቄርሎስ በሚገባ እንዳመለከተው ከድንግል ማርያም የተወለደው መለኰት የተዋሐደው ሥግው ቃል ካልሆነ በስተቀር መዳን የማይታሰብ ነው፡፡ መለኰት ያልተዋሐደውና ዕሩቅ ብእሲ (ሰው ብቻ) የዓለምን ኃጢአት ለመሸከምና ለማስወገድ፣ የተረገመውን ለመቀደስ፣ እና ለሰው ልጆች መዳንን ለመስጠት ዓቅምም ሥልጣንም አይኖረውም፡፡ በተጨማሪም ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን የተዋሐደ የባሕርይ አምላክ ካልሆነ በስተቀር፣ ለራሱ ፍጡር የሆነ ነገር እኛን ወደ እግዚአብሔር ሊመልሰንና ከጠፋንበት ፈልጎ ሊያገኘን አይችልም፤ ምክንያቱም ፍጡር እንኳን ሌላውን ሊያድን ይቅርና እርሱ ራሱ ሌላ መድኃኒትና መሪ ያስፈልገዋልና፡፡ ፍጡር ሊያድን አይችልምና፡፡ ፍጡር ማዳን ቢችልማ ኖሮ አምላክ ሰው መሆን ለምን ያስፈልገው ነበር? ስለሆነም እኛ እንድን ዘንድና ወደ እግዚአብሔር ተመልሰን ከእርሱ ጋር ሱታፌ ያለን እንሆን ዘንድ ባሕርያችን አፍአዊ በሆነ ደረጃ ሳይሆን አማናዊና ውሳጣዊ የሆነ ተዋሕዶን ይፈልግ ነበር፡፡

ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ይህን መሠረታዊ ጉዳይ በአርዮሳውያን ላይ በጻፈው ጥልቅና ሰፊ ትምህርቱ ላይ እንዲህ ሲል ያብራራዋል፡-

> ቃል ፍጡር ቢሆን ኖሮ ይህ [የእኛ መዳን] ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም ነበር፤ ፍጡር ቢሆን ኖሮ ዲያብሎስም ራሱ ፍጡር ስለሆነ ትግሉን ይቀጥልበት ነበር፤ ሰውም በሁለቱ መካከል ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር የሚዋሐድበትና ከፍርሃት ነጻ የሚወጣበት መንገድ አጥቶ ሕይወቱ ሁል ጊዜ በአደጋ ውስጥና በጥፋት ላይ እንደ ሆነ ይቀጥል ነበር፡፡ . . . ስለዚህም በእውነት የእኛ የሆነውን ሰውነትና ባሕርይ ነሣ (ገንዘብ አደረገ)፣ ይህም ባሕርያችንን እርሱ ፈጣሪውና አስገኚው እንደ መሆኑ በእርሱ በራሱ ያከብረው ዘንድ፣ በዚህም በእርሱ መሪነትና አርአያነት ወደ መንግሥተ ሰማያት ያገባን ዘንድ ነው፡፡[100] የሰው ባሕርይ (ትስብእት) የተዋሐደው ከፍጡር ጋር ቢሆን ኖሮ፣ ወይም ወልደ እግዚአብሔር እውነተኛ እግዚአብሔር ባይሆን ኖሮ የእኛ ባሕርይ የጸጋ አምላክነትን አያገኝም ነበር፤ የእኛን ሥጋ የለበሰው የእርሱ [የእግዚአብሔር] እውነተኛና የባሕርይ ልጁ ባይሆን ኖሮ ሰው ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ከፍ ከፍ ሊልና ሊቀርብ አይችልም ነበር፡፡ (ትምህርት በእንተ አርዮሳውያን፣ ትምህርት 2፣ ቁ. 43)

አካላዊ ቃል ሰው የሆነው ለመዳናችን ባሕርያችንን መለኰት ፍጹም በሆነ በአማናዊ ተዋሕዶ ገንዘቡ ያደርገው ዘንድ ያስፈልገው ስለ ነበር ነው፡፡ ስለዚህም በማይመረመር ምሥጢር ባሕርያችንን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ነሥቶ የተወለደው ሥግው ቃል አምላክ ወልደ አምላክ ነው፡፡ እርሷም ወላዲተ አምላክ ትባላለች፡፡ ይህ ካልሆነ መዳናችንን ከንቱ ማድረግ ይሆናል፡፡ ስለሆነም የእመቤታችንን ወላዲተ አምላክነት መቀበልና ማመን እግዚአብሔር በቸርነቱ የሰጠንን የመዳን ጸጋ መቀበልና ማመን ነው፤ ይህን አለመቀበልና መካድ ደግሞ የወልደ እግዚአብሔርን ሥጋዌና የሰዎችን መዳን እንደማያምኑ እንደ አሕዛብ መሆን ነው፡፡ ምክንያቱም ዋናው ጉዳይ እርሷ የወለደችው የእግዚአብሔርን ቃል በሥጋ መሆኑን ማመኑ ላይ ነው እንጂ ይህን ካላመኑማ አርዮሳውያንም፣ ንስጥሮሳውያንም፣ ከዚያም ባሻገር መሐመዳውያንም ሳይቀሩ በድንግልና መወለዱንና ከሌሎች ሰዎች ላቅ ያለ ሰው መሆኑንማ እነዚህ ሁሉ ያምናሉ፡፡

---

[100](For therefore did He assume the body originate and human, that having renewed it as its Framer, He might deify it in Himself, and thus might introduce us all into the kingdom of heaven after His likeness)

ችግሩ እንዲህ ዓይነቱ ከእውነታው ተቃራኒ የሆነ የሰዎች አስተሳሰብ በመሆኑ ጥቅም አልባ ብቻ ሳይሆን የሚያስፈርድም መሆኑ ነው እንጂ፡፡ የመሐመድ አስተማሪ ባሂራ (ባሀራኒ) የተባለ ግኖስቲካዊ እርሾ የነበረው ንስጥሮሳዊ መነኩሴ ነበር ተብሎ ይነገራል[101]፡፡ ስለዚህ የእመቤታችንን ወላዲተ አምላክነት የማያምኑ ሰዎች በምሥጢረ ሥጋዌና አምላክ የሰውን ልጅ ለማዳን ያደረገውን ድንቅ ምሥጢር የማያምኑ በመሆናቸው ከክርስቲያንነት ይልቅ ወደ መሐመዳዊነት የቀረቡ ናቸው፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ሌሎች አባቶች ካስተማሯቸው ትምህርቶች የተወሰኑትን እንመለከታለን፡፡

- ❖ "ድንግል ማርያም ሥጋን በወለደች ጊዜ ቃልን ወለደችው፡፡ ቃልንም በሥጋ ስለ ወለደች በእውነት ወላዲተ አምላክ ናት፡፡" (ቅዱስ አቡሊዲስ፡ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 4)

- ❖ ". . . ገብርኤል ለዘካርያስ እንደ ነገረው፣ እንዲሁም ለወላዲተ አምላክ ለድንግል ማርያም እንደ ነገራት . . ." (ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ ትምህርት በእንተ አርዮሳውያን፣ ክፍል 3፣ ቁ. 14)

- ❖ "ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መሆኗን የማያምን ሰው ካለ ከእግዚአብሔር የተለየ ነው፡፡ . . . ትስብእት መጀመሪያ ተፈጥሮ ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ቃል አደረበት የሚል ቢኖር እርሱም የተወገዘ ነው፡፡" (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ መልእክት ኀበ ካህን አቅላንድዮስ በእንተ አቡሊናርዮስ፡ መልእክት 101)

- ❖ "የማምነውና ተስፋ የማደርገው በምትሐት ወይም በማስመሰል ሳይሆን ስለ እኔ በእውነት ሰው በሆነውና በሞተው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ሐሰት የሆነ ነገር ለእውነት አስጸያፊ ነውና፡፡ ስለሆነም የማምነው ድንግል ማርያም የፀነሰችውና የወለደችው እግዚአብሔር ቃል የተዋሐደውን ሥግው ቃልን ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃልም የእኛን ባሕርይ ገንዘቡ አድርጎ በእውነት ከድንግል ማርያም ተወልዷል፡፡ ሰዎችን ሁሉ በማኅፀን የሚፈጥረውና የሚቀርጸው እርሱ ራሱ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ በድንግልና በማኅፀኗ ተፀንሶ ኖሯልና፡፡" (ቅዱስ አግናጥዮስ፡ መልእክት ኀበ ሰብአ ጥራልያን፣ ምዕ. 10)

- ❖ "ሰይጣን በአንዳንዶች መስቀሉን ይክዱ ዘንድ በእነርሱ ላይ ሥራውን ይሠራል፣ የጌታችንን ሕማማቱንና ሞቱን እንዲያፍሩበትና ምትሐት ነው እንዲሉ በውስጣቸው ይሠራባቸዋል፣ ከድንግል መወለዱንና ሥጋ መልበሱን፣ እንዲሁም የእኛን ባሕርይ ርኩስ እንደ ሆነ አድርጎ ይነቅፋል፡፡ ከአይሁድ ጋር ደግሞ ሰዎች መስቀሉን እንዲክዱ ቤተ ክርስቲያንን ይዋጋታል፣ ከአሕዛብ ጋር ደግሞ ድንግል ማርያምን ይነቅፋል፣ ያክፋፋል፣ ክርስቶስ ከእርሷ ባሕርይዋን ገንዘቡ አድርጎ እንዳልተወለደ አድርገው ይናገራሉ፡፡ የክፋት ሁሉ መሪና ፍታውራሪ የሆነው ዲያብሎስ አሠራሩ ብዙ ዓይነት ነውና፣ እርሱ የሰዎች ፈታኝና አታላይ እንደ መሆኑ ሰዎችን በተለያዩ መንገዶች ከእውነት ይለያቸው ዘንድ ይፈትናቸዋልና፡፡" (ቅዱስ አግናጥዮስ፣ መልእክት ኀበ ፊልጵስዮስ፣ ምዕ. 4)

- ❖ "ቅዱስ ጴጥሮስም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን መስክሯል፡፡ እርሱም የቅዱስ ጴጥሮስ ምስክርነት እንደሚገልጸው ከድንግል ማርያም የተወለደው ያው እርሱው የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡" (ቅዱስ አግናጥዮስ፣ ምዕ. 12)

---

[101] Watt, W. Montgomery, 1964, Muhammad: Prophet and Statesman, Oxford University Press.

- "... ይህ የሆነው እግዚአብሔር በነቢዩ 'እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል፥ ይህም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለት ነው' ተብሎ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ነው፡፡ ይህም በአንድ በኩል ለአባቶቻችን የተሰጠው ተስፋ መፈጸሙን የሚያሳይ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔር ልጅ ከድንግል መወለዱን ግልጽ በሆነ ሁኔታ የሚያስረዳ ነው፡፡ እንዲሁም መናፍቃን እንደሚሉት ድንግል ማርያም የወለደችው ዕሩቅ ብእሲን ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል የተዋሐደውን ኢየሱስ ክርስቶስን መሆኑን በግልጽ ይናገራል፡፡" (ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ በእንተ መናፍቃን፣ መጽሐፍ 3፣ ምዕ. 16፣ ቁ. 2)

- "ኢየሱስ አንድ፣ ክርስቶስ ደግሞ ሌላ ነው ብለን ማሰብ የለብንም፤ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ነው እንጂ፡፡ እንደ ገናም መልአኩ ለድንግል ማርያም ቃለ ብሥራትን ይዞላት በመጣ ጊዜ "እርሱ ታላቅ ይሆናል፣ የልዑል ልጅም ይባላል፣ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል" ብሏታል፡፡ ሉቃ. 1፡32 በዚህም የልዑለ ባሕርይ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ የሆነው እርሱ፣ የዳዊት ልጅ የሆነውም ያው አንዱ እርሱ መሆኑን መሰከረ፡፡ ዳዊትም በመንፈሰ ትንቢት የአካላዊ ቃልን በሥጋ መምጣት ተረድቶ፣ ያ የሚመጣውም በሁሉም በሕዋንና በሙታን ላይ ገዢ የሆነ መሆኑን አውቆ 'ጌታ ጌታዬን በቀኜ ተቀመጥ አለው' በማለት 'ጌታዬ' ብሎ ጠራው፤ ጌታው መሆኑን መሰከረ፡፡ መዝ. 109፡1 ኢየሱስ ክርስቶስን ሳያየው እንደማይሞት ከመንፈስ ቅዱስ ተስፋ የተሰጠው ስምዖን አረጋዊ የድንግል ማርያምን የበኩር ልጅ ታቅፎ እግዚአብሔርን አመሰገነ፣ እንዲህም አለ፦ 'ጌታ ሆይ፣ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ፤ ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና፤ ይህም ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን ለሕዝብህም ለእስራኤል ክብር ነው።' ሉቃ. 2፡29-32 በዚህም በእቅፉ የያዘው ሕፃን የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ መሆኑን መሰከረ፡፡" (ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ በእንተ መናፍቃን፣ መጽሐፍ 3፣ ምዕ. 16፣ ቁ. 2-4)

- "... ስለዚህም አንድ ክርስቶስ አንድ ገዢ እንደሆነ እናምናለን፣ ያለ መቀላቀልም ይህን ተዋሕዶ እናስተምራለን፡፡ ቅድስት ድንግልም እግዚአብሔርን የወለደች እንደ ሆነች እናምናለን፤ የእግዚአብሔር ቃል ሥጋን ተዋሕዶ ሰው ሆኗልና፤ ከእርሷ የነሣውንም ሥጋ ከተፀነሰበት ቀን ጀምሮ ከእርሱ ጋር አንድ ባሕርይ አድርጎታልና፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 25)

- "አማኑኤል የባሕርይ አምላክ እንደ ሆነ፣ ንጽሕት ድንግልም አምላክን የወለደች እንደ ሆነች፣ ሰው የሆነ የእግዚአብሔርንም ቃል እንደ ወለደች የማያምን ሰው ቢኖር ውጉዝ ይሁን፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 44)

- "... አምላክን የወለደች ንጽሕት ድንግልንም የእግዚአብሔር እናት እንላታለን፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 8)

- "አምላክን የወለደች ናት ብንልም ንጽሕት ድንግል ከሥጋ የተለየ መለኮትን እንደ ወለደች አድርጋችሁ መጠራጠር በልባችሁ አይደር፡፡ ሥጋን ነፍስን የተዋሐደ የእግዚአብሔር ቃልን ወለደች እንጂ፡፡ በዚህ በተዋሕዶ ምሥጢር ብቻ እንጂ በሌላ አምላክን ወለደች አንልም፡፡ ሰው ሆነ ብለን ማመናችንም ሰው የሆነበትን ጥንተ መሠረት ያለ ጥርጥር ያስተምረናል፡፡ እንደ እኛ ነፍስን ሥጋን በመዋሐዱ አንድ ክርስቶስን ድንቅ በሚያሰኝ ልደት በወለደችው ጊዜም ንጽሕት ድንግል ቴዎቶኮስ መሆኗን እናምናለን፤ ይኸውም እግዚአብሔርን የወለደች ማለት ነው፡፡ . . . ከልባችን ባነቃነው ነገር ተዋሕዶን ልንነቅፍ አይገባም፤ ማርያም እግዚአብሔርን የወለደች አይደለችም አንበል፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 37፣ 40)

- "ከድንግል ማርያም የተወለደው እርሱው ራሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ እርሱ እንዲህ ብሏልና፡- 'የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል፣ ከሽማግሌዎችም ከካህናት አለቆችም ከጻፎችም ሊጣል፣ ሊገደልም ከሦስት ቀንም በኋላ ይነሣል፡፡' ማር. 8፡31 በቅዱስ ወንጌል የተጻፈውና የተነገረው ስለ ሌላ ክርስቶስ ሳይሆን ከድንግል ማርያም ስለ ተወለደው፣ መከራ ስለ ተቀበለውና ሞትን ድል አድርጎ ስለ ተነሣው የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ነው፡፡" (ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ በእንተ መናፍቃን፣ መጽሐፍ 3፣ ምዕ. 16፣ ቁ. 4)

- "የሁላችን መሠረት አዳም የተገኘው ካልታረሰችና ድንግል ከነበረች መሬት እንደ ነበር (እግዚአብሔር አምላክ በምድር ላይ አላዘነበም ነበርና፣ ምድርንም የሚሠራባት ሰው አልነበረም፣ ዘፍ. 2፡5) እንዲሁም በእግዚአብሔር እጅ፣ ማለትም በእግዚአብሔር ቃል የተፈጠረ እንደ ነበር ሁሉ፣ ሁሉ የሆነው በእርሱ ነውና፤ እግዚአብሔርም ከምድር አፈር ወስዶ እንዳበጀው ሁሉ፣ ያው የእግዚአብሔር ቃል ዳግማዊ አዳም ሆኖ ሲወለድም ድንግል ከሆነች ከቅድስት ማርያም ተወለደ፡፡" *(ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ በእንተ መናፍቃን፣ መጽሐፍ 3፣ ምዕ 22፣ ቁ. 10)*

- "በእግዚአብሔር የማዳን ዓቅድ ሂደት ድንግል ማርያም ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዥ ሆና ተገኘች፤ 'እነሆኝ የጌታ ባሪያ፣ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ' አለች፡፡ ሉቃ. 1፡38 ሔዋን ግን የማትታዘዝ ነበረች፤ ድንግል ሳለች ለእግዚአብሔር ቃል አልታዘዘችም ነበርና፡፡ . . . ካለመታዘዟም የተነሣ ለራሷም፣ ለመላው የሰው ዘርም የሞት ምክንያት ሆነች፤ ድንግል ማርያም ግን ራሷን ለእግዚአብሔር በመስጠቷና ለቃሉ በመታዘዟ ለራሷም ለመላው የሰው ዘርም የመዳን ምክንያት ሆነች፡፡ . . . የሔዋን ለእግዚአብሔር ቃል ባለመታዘዝ ምክንያት ያገኛት የኃጢአት ማሰሪያዋ በድንግል ማርያም ተፈታ፡፡ ድንግል የነበረችው ሔዋን እግዚአብሔርን ባለማመኗ ምክንያት በሰው ልጅ ላይ ያመጣችውንና በጽኑ ማሰሪያ ያሰረችውን ድንግል ማርያም በእምነቷ ፈታችው፡፡" (ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ በእንተ መናፍቃን፣ መጽሐፍ 3፣ ምዕ 22፣ ቁ. 4)

- "የመለኮትንና የትስብእትን ተዋሕዶ በእምነት የማይቀበሉት ኢቢዮናውያን[102] ከንቱዎች ናቸው፡፡ እነርሱ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም የተወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ሊረዱና ሊቀበሉ አይፈልጉም፡፡ እርሱ እንዲህ ያደረገው በቀደመው አዳም ልደት ሞትን እንደ ወረስን አዲስ በሆነው በጌታችን ልደት ደግሞ ሕይወትን እንወርስ ዘንድ ነው፡፡" (ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ መጽሐፍ 5፣ ምዕ 19፣ ቁ. 3)

- "ለወንድ ታጭታ የነበረችው ድንግሊቷ ሔዋን በዲያብሎስ በሐሰት ነገር ተታልላና ወደ ሞት መንገድ ተወስዳ እንደ ነበር ሁሉ የዚያ ካሳ ይሆን ዘንድ በመልአኩ ገብርኤል አማካይነት ለቅድስት ድንግል ማርያም እውነተኛ የሆነውን ነገር የምሥራቹን ቃል አበሠራት፡፡ ሔዋን በመልአክ ቃል (ዲያብሎስ በተፈጥሮው መልአክ ስለሆነ) እንደ ተሳሳተች፣ እንዲሁም ቃሉን ስትጥስ ከእግዚአብሔር እንደ ሸሸች፤ ድንግል ማርያም ደግሞ ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዥ በመሆኗ ምክንያት እግዚአብሔር ከእርሷ ጋር እንደ ሆነ የሚናገረውን ደስ የሚያሰኝ ቃል ብሥራት ከመልአክ ተቀበለች፡፡ ሔዋን እግዚአብሔርን ባትታዘዝ ድንግል ማርያም ለእግዚአብሔር ታዛዥ ሆና ተገኘች፤ ይህም ድንግል ማርያም ድንግል ለነበረችው ለሔዋን ጠበቃዋና ካሳዋ ትሆን ዘንድ ነው፡፡ ስለሆነም የሰው ዘር በመጀመሪያ በድንግል አማካይነት ሞት እንደ ነገሠበትና ሞትን እንደ ወረሰ ሁሉ ዳግመኛ ደግሞ በድንግል አማካይነት ከዚህ ዕዳ ነጻ ወጣ፡፡ በዚህም ድንግልናዊ አለመታዘዝ ፍጹም በሆነ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ በድንግልናዊ መታዘዝ ተካሰ፣ ተስተካከለ፡፡ በዚሁ በተመሳሳይ ሁኔታ መጀመሪያ የተፈጠረው ሰው ኃጢአት በኩር በሆነው በጌታችን ተካሠ፣ ተስተካከለ፤ የእባብ መምጣትም በርግብ ይውህና ድል ተነሣ፡፡

[102](Ebionists)

ወደ ሞት የተወሰድንባቸው ማሰሪያዎች በእነዚያው በታሰርንባቸው ገመዶች ተፈቱ፡፡" (ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ በእንተ መናፍቃን፣ መጽሐፍ 5፣ ምዕ 19፣ ቁ. 1)

❖ "ቅዱሳት መጻሕፍት ክርስቶስን በተመለከተ የሰው ልጅ መሆኑን እንደሚነግሩን ሁሉ እርሱው ሰው ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል እና እግዚአብሔር መሆኑንም ይነግሩናል፡፡ በዘመኑ ፍጻሜ ከድንግል ማርያም እንደ ተወለደ ከእግዚአብሔር አብ በቅድምና ተወልዷል፡፡ እንደ ተራብ ሁሉ ሌሎችን አጥግቧል፤ እንደ ተጠማ ሁሉ ከጥንት አይሁድን ጥማቸውን አርክቷል፣ 'ይከተላቸው ከነበረው መንፈሳዊ ዓለት ጠጡ፣ ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ" እንደ ተባለ፡፡" 1 ቆሮ. 10፡4 (ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ ቅሬታት፣ 52)

❖ "ማርያም የወለደችው ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ እንደሆነ፣ ከአብ ጋርም አንድ እንደሆነ፣ ሥጋን በመዋሐድ የማይለወጥ፣ በመለኮትም የማይታመም ቀዳማዊ አምላክ እንደ ሆነ የማያምን ቢኖር ውጉዝ ይሁን፡፡" (ቅዱስ አቡሊዲስ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 18)

❖ "ከድንግል የተወለደው ታሞ ሞቷልና እርሱ አዳነን፤ ድንግልም አምላክን በወለደች ጊዜ ለዓለም ሕይወትን አስገኘች፡፡ . . . ድኅነት ከእግዚአብሔር ከተገኘ፣ ከሌላ ካልተገኘ፣ ዳግመኛ ዓለምም በእርሱ ከታደሰ የተወለደው የተሰቀለው መከራ የተቀበለው መድኅን ነው፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የወለደችው ከመለኮት የተለየ ዕሩቅ ብእሲ አይደለም፤ አይሁድም የሰቀሉት ዕሩቅ ብእሲን አይደለም፤ ከድንግል በሥጋ የተወለደ አምላክ ነው እንጂ፡፡" (ቅዱስ አቡሊዲስ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 18፣ 20)

❖ ". . . ጊዜው ሲደርስም ስለ እኛ የአምላክ እናት ከሆነች ከድንግል ሥጋን ነሣ (ገንዘብ አደረገ)፣ ሰውም ሆነ" (ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ ትምህርት በእንተ አርዮሳውያን፣ ክፍል 3፣ ቁ. 29 )

❖ ". . . እንዲሁም ዮሐንስ ገና በማኅፀን ሳለ የእግዚአብሔርን እናት የድንግል ማርያምን ድምጽ በሰማ ጊዜ በደስታ ዘለለ . . . " (ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ ትምህርት በእንተ አርዮሳውያን፣ ክፍል 3፣ ቁ. 33)

❖ "ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ነው፡፡ እርሱም የባሕርይ አምላክ ነው፤ መለኮት ቢያድርበት በጸጋ የከበረ አይደለም፡፡ ሥጋን በመንሣት ሰው የሆነ እርሱ ብቻ ነው፡፡ በመለኮት የእግዚአብሔር ልጅ ነው፣ አምላክም ነው፣ እርሱ ወልድ አንድ ብቻ ነው፡፡" (ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 6)

❖ "ዳግመኛም ከሰው ባሕርይ በነሣው በሥጋ ሥርዓት አምላክን በወለደች በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም እናምናለን፡፡" (ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 15)

❖ "ከእስራኤል ፈጣሪ በቀር ሰው እንዳልገባባት ነቢዩ ሕዝቅኤል እንዳያት ምኅት ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ ተወለደ፡፡" (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 13)

❖ " . . . በዚህ በክብሮ ታሪክ ድንግልናን የሚያመላክት ነገር አለው፤ ይህም መጀመሪያ በሙሴና በአሮን እኅት በማርያም የታየ ሲሆን . . . ይህም የእግዚአብሔር እናት የድንግል ማርያም ምሳሌ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡" (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ በእንተ ድንግልና፣ ምዕ. 19)

- "... የእግዚአብሔር እናት በሆነችው በማርያም ዘመን እንደ ሆነው . . ." (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ በእንተ ድንግልና፣ ምዕ. 13)

- "ከድንግል በተወለደ ጊዜ ድንግልናዋን ያለ መለወጥ አጸናው፣ ቀድሞም ሔዋን ድንግል ነበረችና፣ ዲያብሎስ አሳታት እንጂ፣ ድንግል ማርያምን ግን ገብርኤል አበሠራት፡፡ ሔዋንን ዲያብሎስ አሳታት፣ የሞት ምክንያት የሚሆን ቃየልንም ወለደች፣ ማርያም ግን መልአክ በአበሠራት ጊዜ ሁሉን ወደ ዘለዓለም ሕይወት የሚመራ አካላዊ ቃልን በሥጋ ወለደች፡፡ . . . ዳግመኛም ድንግልናዋ እንዳልተለወጠ ጽኑዕ መለኮት ከባሕርዩ አልተለወጠም፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 3-4፣ 7)

እዚህ ላይ መታወስ ያለበት ነገር እነዚህ አባቶች ሁሉም ንስጥሮስ ከመነሳቱና "እመቤታችን ወላዲተ አምላክ አትባልም" የሚለውን ኑፋቄ ከማስራጨቱ በፊት (ከ428 ዓ. ም.) የነበሩ አባቶች መሆናቸው ነው፡፡ ይህም ማለት የእመቤታችን ወላዲተ አምላክ መባል አዲስ ነገር ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን አባቶች የታወቀና ኦርቶዶክሳዊ ትውፊትና ትምህርት ነበር ማለት ነው፡፡ ይህም እንግዳው ባህል የንስጥሮስ ተቃውሞ የነበረ መሆኑን በግልጽ ያሳየናል፡፡

- "ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መባል የሚገባት ስለ መሆን አለ መሆኑ ግራ የሚገባቸውና በጥርጥር ላይ ያሉ ሰዎች የመኖራቸው ነገር ይገርመኛል፣ ያስደንቀኛልም፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ከሆነ በሥጋ የወለደችው ቅድስት ድንግል ማርያም እንዴት ወላዲተ አምላክ አትባልም?" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፣ መልእክት 1፣ ለግብጽ መነኩሳት የተላከ መልእክት)

- "እግዚአብሔር ወልድ ከሴት በመወለድ እንደ እኛ ሆነ፡፡ ድንግል ማርያም ያስገኘችው የእኛን ባሕርይ (ትስብእትን) ቢሆንም አካላዊ ቃል ከእኛ የነሣው ትስብእት ከቃል ጋር ከመዋሐዱ በፊት ቀድሞ ስላልተፈጠረና የራሱ የሆነ ህልውና ከጀመረ በኋላ ቃል የተዋሐደው ስላልሆነ፣ ህልዎቱን አንድ ብሎ የጀመረው ከአካላዊ ቃል ጋር ተዋሕዶ በመሆኑ እርሷ የወለደችው ሥግው ቃልን ነው፤ ስለዚህም እርሷ ወላዲተ አምላክ ናት፡፡" (ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ)[103]

- "ሰማያውያንን ምድራውያንን ፈጥሮ መግዛት ገንዘቡ ነው፡፡ ስለ እኛ ነፍስን ሥጋን ነሥቶ ያለ መለወጥ ሰው ሆነ፣ ከእሴይ ከዳዊት ባሕርይ ተወልዶ በሥጋ ተገለጠ፣ አምላክን የወለደች ንጽሕት ድንግል ማርያም ከእነርሱ ተወልዳለችና ሐዋርያ፣ የምናምንበት ሊቀ ካህናት ተባለ፡፡" (ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 3)

- "አምላክን የወለደች ማርያም ለዘላለሙ ድንግል እንደ ሆነች መውለዷም የማይመረመር ድንቅ እንደ ሆነ፣ ከወለደችም በኋላ በድንግልና ጸንታ እንደ ኖረች አስረዳን፡፡ . . ." (ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 14)

በንስጥሮስ ውዝግብ ጊዜ ላይ የአንጾኪያ መንበር ጳጳስ የነበረውና በተለያዩ ምክንያቶች ከቅዱስ ቄርሎስ ጋር የመጣላትና ከንስጥሮስ ጎን የመቆም አዝማሚያ ያሳይ የነበረው ጳጳስ ዮሐንስ (John of Antioch)[104] እንኳ ሳይቀር የእመቤታችንን ወላዲተ አምላክነት ያምን ነበር፡፡

---

[103] St. Severus of Antioch

[104] በኋላ ከቅዱስ ቄርሎስ ጋር በ433 ዓ.ም. ታርቀዋል

ይህንም ለንስጥሮስ በላከለት አንድ ጦማሩ ላይ እንዲህ ብሏል፦

- "ይህን መጠሪያ ክብር (ወላዲተ አምላክ የሚለውን) ያልተጠቀመበትና ያልተናገረው ማንም የቤተ ክርስቲያን አባትና መምህር የለም፡፡ ይህን ቃል የተጠቀሙበትም ብዙዎችና የታወቁ አባቶች ናቸው፡፡ ያልተጠቀሙበት ቢኖሩ እንኳ የተጠቀሙበትን አልተቃወሟቸውም፣ ስህተት ነውም አላሉም፡፡" (ዮሐንስ ጳጳስ ዘአንጾኪያ፣ በእንተ ጉባኤ ኤፌሶን፣ ክፍል 1፣ ምዕራፍ 25)

- " . . . ንስጥሮስ ሆይ፣ ባልታረመና ጸያፍ በሆነ አንደበትህ ከሐዋርያት ጀምሮ ሳይቋረጥ ተጠብቆ የመጣውን ኦርቶዶክሳዊ እምነት የጠበቁና የያዙ ካህናትን ትሰድባቸዋለህ፡፡ . . . ታዲያ አንተ አሁን የቀደሙ ጳጳሳትን አራሚና አስተካካይ መሆንህ ይሆን? አንተ ከጎርጎርዮስ የተሻልክ ነህ? ከዮሐንስ አፈ ወርቅስ ትበልጣለህ? እንዲሁም ከሌሎቹ በምሥራቅ መናብርት ከነበሩትና እንደ ጠቀስኳቸው አባቶች ያህል ስማቸው የገነነ ባይሆንም እንኳ ከእነርሱ ጋር አንዲት እምነት ከነበራቸው ከሌሎች ጳጳሳት ሁሉ አንተ ትበልጣለህ? . . ." (ቅዱስ ዮሐንስ ካዝያን[105]፣ በንስጥሮስ ላይ በእንተ ሥጋዌ የጻፋቸው ሰባት መጻሕፍት)

ኦርቶዶክሳውያን አባቶች ሁሉ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክነትና ስለ ክብሯ በሰፊው አስተምረዋል፣ ጽፈዋል፡፡ ኦርቶዶክሳውያን ቀደምት አበው ስለ እመቤታችን ካስተማሩት ትምህርት መካከል ሁለት ባሕርይ ባዮች ከሆኑት ኬልቄዶናውያን ጋር ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ተዋሕዶና አንድ ባሕርይነት ጽኑ ተጋድሎ ያደረገውና ከዚህም የተነሣ በ538 ዓ. ም. በኬልቄዶናውያን ከአንጾኪያ መንበሩ እንዲሳደድና ብዙ ዘመኑን በግብጽ በስደት እንዲያሳልፍ የተደረገው ቅዱስ ሳዊሮስ ዘንጾኪያ ስለ እመቤታችን ካስተማረው ትምህርት አንዱን እንደ ማሳረጊያ ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

(1) "በቃላት የተዋበና የተቀመረ ምስጋና ለቅዱሳን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ተገቢም ትክክልም ነው፡፡ ስለዚህም ጌታቸውን በእውነት እንዳገለገሉና የመዳናችን ነገር አማናዊነቱ እንዲገለጥ የድርሻቸውን እንደ ተወጡ እንደ በጎ አገልጋዮች ተገቢ በሆነ ክብራቸውን በሚገልጥ በምስጋና ስብከትና በዓላቸውን በማድረግ እናመስግናቸው፡፡[106] በአንድ በኩል ድንቅ የሆነውን ታላቁን እግዚአብሔርን የመምሰልን ምሥጢር (1 ጢሞ. 3፥16) ከዘመኑ አስቀድመው ለመስበክ የቻሉትን ነቢያትን እናመስግናቸው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ይህን ምሥጢር ያስተማሩ ሐዋርያትን እናመስግናቸው፡፡ በመቀጠልም ደግሞ የነቢያትን ትንቢትና የሐዋርያትን ስብከት በደማቸው ያረጋገጡ ሰማዕታትን እናመስግናቸው፤ አንድን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ የሆነ ነገር፣ ወይም በሌላ መንገድ ማረጋገጥ የማይቻልን ነገር በቃላቸው ምስክርነት እውነትነቱን የሚያሳዩ ሰዎች 'ምስክሮች' ይባላሉና፡፡

(2) የክርስቶስ ሰማዕታት ድምጻቸው (የምስክርነት ቃላቸው) የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደው *የእግዚአብሔር በግ* (ዮሐ. 1፥29) *ያፈሰሰውን* የመጀመሪያውንና የመለኮታዊውን ደም ተከትሎ የፈሰሰው ደማቸው ነው፤ እርሱ ከእነዚህ ከሰማዕታት አስቀድሞ ስለ ራሱ ምስክር ሆኗልና፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ተናገረ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ፊት መልካሙን መታመን የመሰከረ እርሱ (1 ጢሞ. 6፥13) በእውነት ሌላ ምስክር አይፈልግምና (አያስፈልገውምና)፡፡ እርሱ ራሱ እውነት ለሆነ ለእርሱ ከእርሱ የበለጠ እውነተኛና ተአማኒነት ያለው ሌላ ምስክር ከየት ሊገኝ ይችላል? ነገር ግን እርሱ የአገልጋዮቹን በጎ ፈቃድና እርሱን የማገልገል ተምኔታቸውን የሚቀበል ቸር ስለ ሆነ የእርሱ በሆነው በዚህ መዓርግ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ፈቀደላቸው፣ ሰማዕታት ተብለው እንዲጠሩም አደረጋቸው፡፡

[105] St. John Cassian

[106] ("It is fitting and just that we should offer praise composed of words to all the saints: and let us honour them with laudatory sermons and with festivals as those who have truly served their Lord and have contributed faithfully towards the dispensation of our redemption.")

(3) "*ታዲያ የእግዚአብሔርን እናት፣ በእውነት ቅድስት እና ዘለዓለማዊት ድንግል የሆነችውን ድንግል ማርያምን ሰው ሁሉ እንደ ነቢዪት፣ እንደ ሐዋርያ፣ እና እንደ ሰማዕት ሊያከብራት እንዴት አይገባም? እንደ ነቢዪት ልትከበር የሚገባት ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ እርሷ እንዲህ ብሎ በተናገረው ትንቢት መሠረት ነው፡- 'ወደ ነቢዪቱም ቀረብሁ፣ እርሷም ፀነሰች፣ ወንድ ልጅንም ወለደች። እግዚአብሔርም፦ ሕፃኑ አባቱንና እናቱን መጥራት ሳያውቅ የደማስቆን ሀብትና የሰማርያን ምርኮ በአሦር ንጉሥ ፊት ይወስዳልና ስሙን፦ ምርኮ ፈጠነ፣ ብዝበዛ ቸኰለ ብለህ ጥራው አለኝ።'* ኢሳ. 8፥3-4

(4) "በቅዱሳት *መጻሕፍት 'ምርኮ ፈጠነ፣ ብዝበዛ ቸኰለ'* ተብሎ የተነገረለትንና አባቱንና እናቱን *መጥራት* ሳያውቅ ኃያላኑን የሚማርካቸውን ልጅ የወለደችው የእግዚአብሔር እናት ከሆነችውና ገና እንደ ተወለደ የደማስቆን ሀብትና የሰማርያን ምርኮ በመውሰድ ዲያብሎስን ያናወጸውን አማኑኤልን ከወለደችው ከድንግል በቀር ሌላ ማን ነው?

(5) እነዚህ *ቃላቶች* በዘይቤያዊ አገላለጽ የጣዖታትን አምልኮ የሚያመላክቱ ናቸውና፡፡ በአንድ በኩል ደማስቆ ማለት በደም የታለለ (Bloody) ተብሎ ይተረጎማልና፡፡ በሌላ በኩል ሰማርያ ደግሞ ከወርቅ የተሠራ የጥጃ ምስል አቁሞ ከሕዝቡ ዘንድ የእውነተኛውን አምላክ አምልኮና አገልግሎት ያራቀና ያስቀረ ነው (1 ነገ. 12፥26-28)፡፡ ስለሆነም በእነዚህ በሁለቱ ነገሮች በተለይ የጣዖታት አምልኮ የሚገለጥ መሆኑ ለሰዎች ሁሉ የታወቀ ነው፡፡ ስለዚህም አማኑኤል በሥጋ እንደ ተወለደ ወዲያውኑ ምርኮውን ከእነዚህ ወሰደ፡፡ የመጀመሪያው በግርግም ተኝቶ በጨርቅ ተጠቅልሎ ሳለ ሰብአ ሰገል መጥተው እንዲያመልኩት ባደረገ ጊዜ ሲሆን ሌላው ደግሞ ወደ ግብጽ በሄደ ጊዜና ኢሳይያስ በትንቢቱ እንደ ተናገረ በዚያ የነበሩትን ጣዖታት ባናወጻቸው ጊዜ ነበር (ኢሳ. 19፥1)፡፡ ይህን ያደረገውም በአሦር ንጉሥ ፊት ነው፤ ትንቢቱ ዲያብሎስን በብዙ ቦታ የአሦር ንጉሥ እያለ ይጠራዋልና፤ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጠራም በነቢያት ዘንድ ተደጋግሞ ተነግሮ ይገኛል (ኢሳ. 10፥12-)፡፡

(6) "ነቢዪቷ ድንግል ማርያም ለእኛ የወለደችልን ልጅ ይህ ነው፤ ገና ከሕፃንነቱ ጀምሮ፣ ወዲያውኑ እንደ ተወለደ የዲያብሎስን ምሽግ ማፍረስና ግዛቱን ማናወጽ የጀመረውን ይህን ነው፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስም 'ሕፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፣ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፣ ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል' ይላልና (ኢሳ. 9፥6)፡፡ . . .

(7) "ስለዚህም ምክንያት ድንግል እና እናት የሆነችው እርሷ፣ እንዲህ ያለውን የነቢያት ጌታ የወለደችው እርሷ ከኤልሳቤጥ ሰላምታ በኋላ እንዲህ ባለች ጊዜ ትንቢት እየተናገረች ነበር፡- 'የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቷልና። እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጓልና፤ ስሙም ቅዱስ ነው፣ ምሕረቱም ለሚፈሩት እስከ ትውልድና ትውልድ ይኖራል' (ሉቃ. 1፥48-50)፡፡

(8) "እንደዚሁም እርሷን ሐዋርያ ብለን፣ ሐዋርያ ብቻም ሳይሆን ከሁሉም ሐዋርያት በላይ ብለንም ልንጠራት በእውነት እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ከመጀሪያው እርሷ ራሷ ከሐዋርያት ጋር ተቆጥራለችና፤ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንዲህ ሲል እንደ ጻፈልን፡- 'እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር' (የሐዋ. 1፥14)። ከዚህም ጋር እነርሱን ሐዋርያት ያሰኛቸው ከጌታችን የሰሙት 'ሒዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ' የሚለው ቃል ከሆነ፣ ዝም ብላ ሳለ እንዲህ ባለ ድንቅና ልዩ በሆነ ሁኔታ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን የወለደችልን ከመሆኗ የተነሣ፣ እንዲሁም የወንጌል ትምህርት ምንጭና እናት ካደረጋት በፍጹም ደንግልና ከመፅነሷና ከመውለዷ የተነሣ እርሷ ያላስተማረችውና እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ ያላመጣችው ሕዝብ የትኛው ነው?

(9) "ከዚህም ጋር እርሷ ሰማዕት ናት ብሎ ለመናገር ወደ ኋላ የሚልና የሚያመነታ አይኑር፡፡ እርሷ በብዙ ረገድ ሰማዕት ናትና፤ የሴፍ ከእርሷ የሚወለደው በመንፈስ ቅዱስ ምሥጢር መሆኑን ከመልአኩ ሰምቶ እስኪረዳ ድረስ በሁኔታዋ ግራ መጋባቱን በጽንዓት ተቀብላለችና፡፡ እንዲሁም ደግሞ ከሄሮድስ ቁጣ የተነሣ ወደ ግብጽ በተሰደደች ጊዜ፣ እንዲሁም ከግብጽ በተመለሰች ጊዜና የአርኬላዎስን ፍርሃት በተሸከመች ጊዜና ወደ ናዝሬት በሄደች ጊዜ፣ እንዲሁም ያን ሁሉ ጊዜ ከአይሁድ ነፍስ ገዳዮች ጋር በኖረችና እያንዳንዱን ቀን ለሞት የቀረበ ሕይወት በኖረች ጊዜ ሁሉ እርሷ ሰማዕት ናትና፡፡

(10) "ታዲያ የጻድቃን ነፍሶች በዚህች ሰዓት የሚያመሰግኗትን ይህችን ሴት እኛ ተገቢ የሆነ እውነተኛ ክብር እናከብራት ዘንድ እንዴት አይገባንም? በአንድ በኩል አበው ቀደምት ከጥንት ዘመን ጀምሮ ሲጠበቅ የነበረውን ተስፋ እንዲፈጸም ያደረገችልን፣ እና ዓለም የሚባረክበትን የአብርሃምን ዘር (እርሱም ክርስቶስ ነው) ያስገኘችልን ብለው ያከብሯታል፡፡ በሌላ በኩል ነቢያት ደግሞ ትንቢታቸውን እንዲፈጸምና ብሩህ እንዲሆን ያደረገችላቸው፣ የተሰወረውን ምሥጢርና ያልታወቀ የነበረውን ነገር ሁሉ የገለጠውን እውነተኛውን ፀሐይ (ሚልክ. 4፡2) የወለደችልን ናት በማለት ያመሰግኗታል፣ ያከብሯታልም፡፡ እንደ ገናም ሐዋርያት ደግሞ የስብከታቸው መጀመሪያ ብለው ያከብሯታል፡፡ ሰማዕታት ደግሞ የተጋድሏቸውንና የድል አድራጊነታቸውን አርአያና መጀመሪያ ያመጣችልን ብለው ያመሰግኗታል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና የክርስቶስ አማናዊ መንጋ ጠባቂዎች ደግሞ የኑፋቄን አፍ የዘጋችልንና መልቶ ተርፎ የሚወርድ፣ ከንጹሕ ምንጭ የሚፈስስና የሚቀዳ የኦርቶዶክሳዊ ትምህርት መገኛ ብለው ያመሰግኗታል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ የመናፍቃንን [107]ጨለማ ያራቀችልን ይሏታል፡፡

(11) "የእግዚአብሔር ቃል ከእርሷ እንበለ ውላጤ (ያለ መለወጥ) ሰው በሆነ ጊዜ እኛን የፈጠረንና የሠራን እርሱ አንድ እንደ ሆነ አስረዳ፡፡ እነዚያ ሰዎች [መናፍቃን] እንደሚሉት የድፍረትና የጽርፈት አባባል ቢሆን ኖሮ፣ ማለትም በአንድ በኩል ነፍስን የፈጠራት ደግ አምላክ ቢሆንና በሌላ በኩል ደግሞ ሥጋን የፈጠሩት ክፉው አምላክና ጨለማ ቢሆኑ ኖሮ 'በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ' (ዕብ. 2፡14) ተብሎ እንደ ተጻፈ የአብ ልጅና ደግ አምላክ እንዴት የእኛን ሥጋ ተዋሕዶ ሰው ሆኖ ይገለጥ ነበር? . . .

(15) "በሌላ በኩል ደግሞ ድንግል የአምላክ እናት የንስጥሮስን እብደት አትታገሥም፡፡ ኃያል አምላክ፣ ድንቅ፣ መካር፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ የሆነውን ወልድን የወለደች እርሷ የአምላክ እናት እንዴት አትባልም? ቡተቃራኒው ንስጥሮስ 'እግዚአብሔርን ትወልድ ዘንድ የሴት ባሕርያዊ ተፈጥሮ አይደለም' ይላል፡፡ እንዲህ ስትል ሥጋ ያልለበሰውንና ሰው ያልሆነውን እግዚአብሔርን ማለትህ ከሆነ ይህን እኔ ራሴም እንደ አንተ የማረጋግጠው ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን ሥጋ የለበሰውንና ሰው የሆነውን ማለትህ ከሆነ ግን ስለ ተደረገው አምላካዊ ተአምር አትጠራጠር፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ሴት ከሥጋ ጋር ካልተዋሐደ በስተቀር ነፍስን ብቻ ትወልድ ዘንድ አትችልምና፤ ነገር ግን ነፍስ ከሥጋ ጋር ሲዋሐድና በአንድ ቅጽበት ተዋሕዶ አንድ ፍጥረት ሲሆን[108] ከሥጋ ጋር በአንድ ጊዜ ይወለዳል፡፡ እርሷም [እናት የምትሆን ሴት] የሥጋ ብቻ እናት የምትባል ሳይሆን ሕይወትና እውቀት ያለው የሰው እናት ትባላለች፡፡ አማኑኤል በሥጋ ስለ ተወለደው ልደትም ይህን ተመሳሳይ ነገር ተመልከት፣ ቅዱስ መጽሐፍ ይህን በምሥጢር እንዲህ ሲል ይነግረናል፡- 'እንግዲህ ልጆቹ በሥጋናበደም ስለሚካፈሉ፣ እርሱ ደግሞ . . . በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ፡' ዕብ. 2፡14

[107] (Manicheans)

[108] (. . . but when it is joined with a body and becomes a single unit in one simultaneous creation)

(16) "እግዚአብሔር ቃል መለኮታዊ ባሕርዩንና ህልዎቱን ያገኘው ከማርያም አይደለምና፤ እርሱ መጀመሪያ የሌለው ዘለዓለማዊና የጊዜያትና የዘመናት ሁሉ ፈጣሪና አስገኚ ነውና። ሆኖም ግን የእኛን ባሕርይ ገንዘብ ማድረግንና ሰው መሆንን በወደደ ጊዜ ባሕርይዋ የሆነውን ነገር ድንግል ለእርሱ ሰጠችው፤ በዚህም በተዋሕዶው ከእርሷ የሆነው ገንዘብ ሁሉ በአንድ ጊዜ ወደ እርሱ ገባ፡ ከመለኮታዊ አካሉና ባሕርዩ ጋር በአንድ ጊዜ ተዋሐደ። ፅንሰቱ እንበለ ዘርአ ብእሲ በመሆኑ መንፈስ ቅዱስ ፅንሰቱ እንዲፈጸምና እንዲከወን አደረገ፡ ልደቱንም እንዲሁ ከፍጻሜ አደረሰ። ስለዚህ እግዚአብሔር ቃል እርሱ ራሱ ከእርሷ በተፀነሰና በሥጋ በተወለደ ጊዜ እግዚአብሔር ቃልን በሥጋ የወለደችው ድንግል ማርያም የእግዚአብሔር እናት መሆኗን አሳየ።

(17) "ስለዚህም የተወለደው አንዱ እርሱ አማኑኤልም ተብሏል፤ ከሁለት ባሕርያት - ከመለኮታዊና ከሰብአዊ ባሕርያት - የተገኘ፣ ያለ መለያየትና ያለ መከፋፈል በተዋሕዶ አንድ ነውና። ይህ አንድ የሆነ እርሱ የማይከፋፈሉና ልዩ የሆኑ ነገሮች ገንዘቡ የሆኑለት እርሱ ነው፤ እነዚህም ከአብ የሆነው ቀዳማዊና ዘመን የማይቆጠርለት ዘለዓለማዊ ልደቱ (ከአብ የተወለደው እርሱ ብቻ ነውና፣ ከአምላክ የተወለደ አምላክ እርሱ ብቻ ነውና) እና ከድንግል ማርያም የተወለደው ልደቱ (ወንድ ካላወቃት ድንግል የተወለደ እርሱ ብቻ ነውና፣ እርሷም ሌላ የሚመስላት የሌለ ብቸኛ ናትና)። እርሱ ሲለወድ የእናቱን ድንግልና አልለወጠም፤ ታዲያ ሊገለጽ ከማይችለው ምሥጢራዊ ተዋሕዶ በኋላ የንስጥሮስን የሞኝነት ትምህርት የተከተለው የኬልቄዶን ጉባኤ እንደ ወሰነው ወደ ሁለትነት ሊከፈልና ወደ ምንታዌ ባሕርያት ሊበታተን የሚቻለው እንዴት ብሎ ነው?

(18) ቅድስት የአምላክ እናት እና ዘለዓለማዊት ድንግል የሆነችውን ድንግል ማርያምን ከምንም በላይ በሆነ እጅግ ታላቅ ክብር የምናከብራት ስለዚህ ነው። እርሷ ከሌሎች ቅዱሳን ሁሉ በላይ ስለ እኛ ጸሎትንና ምልጃ የምትቃርብልን ናትና፣ እኛም እርሷን የባሕርያችን መመኪያና ጌጥ ሆና አግኝተናታልና እርሷን እንመካባታለን። ዳግማዊ አዳም ራሱን በሥጋ ያስገኘባትና የተወለደባት ነባቢትና ሕያዊት ምድር፣ እግራችንን በደረጃዎቹ ላይ አጽንተን ከተገኘን እኛም ወደ ሰማይ እንወጣበት ዘንድ ሰማያዊው መሰላል ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ በሥጋ የተዘጋጀባት የድንግልና ተክል፣ በጭጋግና በጢስ ያልተሸፈነችና የምትታይ ደብረ ሲና፣ ይልቁንም በእውነተኛው ፀሐይ የምታብራ እና የዐሥርቱን ትእዛዛት ሕግ ብቻ የምትሰጥ ሳትሆን በምድር ላይ የታየውንና ከሰዎች ጋር የተመላለሰውን ሕግ ሠሪውን ራሱን የምትሰጥ የሕግ መገኛ፣ እንዲሁ ከእርሷ የተገኘውም እንደ ቀድሞው ሕግ አሰጣጥና ሁኔታ እንደ ሕዝብ እስራኤልን ብቻ ሳይሆን በወንጌል ትምህርቱ አማካይነት ሁሉንም ሕዝብና የሰው ዘር ወደ መረቡ የሳበውን እርሱን ያስገኘች ናት።

(19) "ታዲያ ለእግዚአብሔር እናት የምንሰጣት ክብር ምን ዓይነት ክብር ነው? ለነፍሳችን ድኅነት ከእርሷ ለተወለደው ለእግዚአብሔርስ? . . ."

(ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ፣ ክፍለ ትምህርት 14፣ ቁ. 1-19)

## 5.5 ማጠቃለያ

ወላዲተ አምላክ የሚለው ለእመቤታችን የሚሰጠው መጠሪያ ቅጽል መጽሐፍ ቅዱሳዊና ኦርቶዶክሳዊ የሆነውን የምሥጢረ ተዋሕዶና የነገረ ክርስቶስ ትምህርት አንድ አድርጎ የሚጠብቅና የሚገልጽ ድንቅ ቃል ነው፡፡ ቀዳማዊና ዘላለማዊ የሆነው የእግዚአብሔር አካላዊ ቃል ሰው የሆነው ባሕርየ ትስብእትን (የእኛን ባሕርይ) በማኅፀነ ድንግል ማርያም ፈጥሮና የራሱ ገንዘብ አድርጎ ተዋሕዶ ነው፡፡ ቃል የሚዋሐደውን ትስብእት ሲፈጥረውና ሲዋሐደው አንድ ጊዜ ነው፡፡ ቀድሞ ፈጥሮ ከዚያ በኋላ የተዋሐደው አይደለም፣ ይህ ኅድረትን ያመጣልና፡፡

ትስብእት የአካላዊ ቃል ገንዘብ ሳይሆን በራሱ ጊዜ የኖረበት የመጨረሻ ትንሽ የሚባል የጊዜ ሽራፊ ወይም ቅንጣቢ እንኳ የለም፡፡ ስለዚህ ቅድስተ ቅዱሳን ንጽሕተ ንጹሐን የባሕርያችን መመኪያ እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የፀነሰችውና የወለደችው በተዋሕዶ ምስጢር ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ የሆነውን ሥግው ቃልን ነው፡፡ ስለሆነም እርሷ የወለደችው ከተፈጠረ በኋላ በማኅፀኗ ቃል የሚያድርበትን ወይም ከተወለደ በኋላ የቃል ማደሪያ የሚሆነን ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) ሳይሆን፣ ከመጀመሪያው ህልውናው ጀምሮ ቃል ትስብእትን የራሱ ገንዘብ አድርጎ ሲፈጥረውና ሲዋሐደው የጊዜ ልዩነት ስለሌለ እርሷ የወለደችው አንዱን የእግዚአብሔር ልጅ ሥግው ቃል የባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው፡፡ ስለሆነም እርሷ ወላዲተ አምላክ መባሏ የተገባና ትክክለኛ የሃይማኖት መግለጫ ነው፡፡

ይህን ቃል ለእመቤታችን መቀጸል የጀመርነው እኛ አይደለንም፣ ከላይ እንዳየነው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጀምሮ በሐዋርያትና በየዘመኑ በተነሱ ቅዱሳን አባቶች ሲነገር የነበረ ክርስቲያናዊ እውነታ ነው፡፡ እኛ ይህን በማለታችን ለእመቤታችን የምንጨምርላት፣ ባለማለታችን ደግሞ የምናስቀርባት እንዳች ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ይህን የማያምኑ ሰዎች ራሳቸውን ከእውነተኛው የቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ከወንጌል ድኅነት ውጭ ያደርጋሉ፡፡ ወላዲተ አምላክ የሚለው መግለጫ ቃል ነገረ ክርስትናንና ምሥጢረ ሃይማኖትን በሙሉ እንደ ሽማ ጠቅልሎ እንደ ወርቅ አንከብሎ የሚይዝ ቃል ነው፡፡ ስለሆነም ወላዲተ አምላክ የሚለው ቃል የአንድን ትምህርት ኦርቶዶክሳዊ መሆን አለመሆን በቀላሉና በአጭሩ ለመመዘንና ለመለየት የሚያስችል አጭር መንገድ ነው፡፡

ብዙውን ጊዜ የእመቤታችንን ወላዲተ አምላክነት መቀበል የሚከብዳቸው ወይም በግልጽ የሚቃወሙ ሰዎች በመነናውያንና በዶሲቲኮች፣ በአርዮሳዊነትና በንስጥሮሳዊነት በሽታ የተለከፉ መናፍቃን መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ ነገረ ሥጋዌንና የመዳንን ምሥጢር የሚቃወሙ የንስጥሮስ ተከታዮች ኑፋቄያቸውን እመቤታችንን በመቃወም ሊሸፍኑ የሚሞክሩበት ምክንያት አንዳንዶቹ በቀጥታ ነገረ ክርስቶስ ውስጥ ገብተው ነገረ ተዋሕዶ ላይ ያለውን ነገር መቃወምና ማስረዳት ስለሚያቅታቸው ነው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ንስጥሮሳዊነታቸው በይፋ እንዳይታወቅባቸው ለመሸፈንና ስለ ክርስቶስ ክብር የተቆረቆሩና የእመቤታችን መከበር የክርስቶስን ክብር ሸፍኖታል በማለ ሽፋን ቢገቡ ኑፋቄያቸውን በቀላሉ ለማስረጨትና ተከታይ ለማግኘት የተሻለ አማራጭ ስለሚመስላቸው ነው፡፡ ስለዚህም "ማርያም ወላዲተ አምላክ አትባልም"፣ "ለእርሷ የሚሰጠው ክብር በዝቷል" በሚል የአዛኝ ቅቤ አንጓች ዓይነት የጩኸት ጭምብል ውስጥ ኢክርስቲያናዊ የሆነውን ንስጥሮሳዊ ኑፋቄያቸውን ሰውረው ለመንቀሳቀስ ይሞክራሉ፡፡

በርግጥም አስቀድሞ በነቢዩ "ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች" ተብሎ እንደ ተነገረ እርሷ ለኦርቶዶክሳዊ ነገረ ክርስቶስ (Christology) መለዩና መለኪያ (Canon - ቀኖና) ሆና የተሰጠችን ምልክት ናት። ንስጥሮስ ወላዲተ አምላክ የሚለውን የተቃወመው ለድንግል ማርያም የተለየ ጥላቻ ስለ ነበረው አልነበረም፤ ነገረ ክርስቶሳዊ እምነቱና አስተምህሮው የተሳሳተ ስለ ነበር እንጂ።

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችንም ከተለያዩ መናፍቃን ጋር ያላት መሠረታዊ ልዩነት ምናልባት ለብዙ ሰዎች በነገረ ቅዱሳን ላይ ያተኮረ ሊመስላቸው ይችል ይሆናል እንጂ ዋናውና መሠረታዊ ልዩነት ያለው ነገረ ክርስቶስ (Christology) ላይ እና የመዳን ትምህርት (Soteriology) ላይ ነው። በሌላው የተለያየነው በመሠረቱ በነገረ ክርስቶስ ስለ ተለያየን ነው።

ስለሆነም *"ወላዲተ አምላክ"* የሚለው ቃል በነገረ ክርስቶስ ላይ ያለንን ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ የሚገልጥና የሚጠብቅ ዕንቁአችን ነው። በነገረ ድኅነት ትምህርት ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ማንነት፤ ሚና እና ወላዲተ አምላክነት ያለን አስተምህሮ ለኦርቶዶክሳዊ እምነት መጠበቅ ወሳኝ ነው። የእርሷን ወላዲተ አምላክነት የተቃወሙትን ንስጥሮሳውያን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በ431 ዓ.ም. አውግዛ የለየቻቸው ለዚህ ነው። ያን ኑፋቄ እንደ አዲስ ይዘው ብቅ ያሉ የዘመናችን መናፍቃንም ከእንዲት፥ ሐዋርያዊት፥ ጉባኤያዊትና ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አንድነት በራሳቸው ኑፋቄ የተለዩ ናቸው። የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክነት የሚቃወሙ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ እና በኦርቶዶክሳውያን አባቶች ትምህርት ሚዛንነት ሲመዘኑ ባዶ ሆነው ቀልለው ተገኝተዋል። ስለሆነም "ኦርቶዶክሳውያን ነን" እንደሚሉት መሆን ይቅርና የኦርቶዶክሳዊ ክርስትና ሽታው ሲያልፍም አልነካቸው።

# ክፍል ሦስት

## በእንተ ቅዱሳን

## ምዕራፍ ስድስት

### 6.1 ስለ ቅዱሳን መማርና ማስተማር ለምን አስፈለገ?

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የእምነቷ መሠረት አንድ አምላክ በሆነ፣ በአንድነቱ ውስጥ ልዩ ሦስትነት ባለው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ማመን ነው፡፡ ከዚህም ጋር እኛን ለማዳን ሲል በራሱ ፈቃድ፣ በአባቱ ፈቃድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ በተለየ አካሉ ሰው በሆነው በአካላዊ ቃል በእግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆን (ሥጋዌ) ታምናለች፡፡ በአጠቃላይ የእምነቷ መሠረትና ጉልላት በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠው እውነትና ትምህርት ነው፡፡ በዚህም መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ቅዱሳን ታስተምራለች፡፡ ግን ለምን?

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ቅዱሳን የምታስተምረው በራሷ ፈቃድ ወይም ፍላጎት ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ በመሆኑና ከሐዋርያት ጀምሮ የተነሡ የቅዱሳን አባቶቻችንን ፈለጋቸውን የምትከተል ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን በመሆኗ ነው፡፡ ሆኖም ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን መንቀፍንና ያልሆነ መልክ መስጠትን ሥራዬ ብለው የያዙት ተሐድሶዎች ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚነቅፉበትና የሚወቅሱበት አንዱ ጉዳይ "ለምን ስለ ቅዱሳን ታስተምራለች? ስለ ቅዱሳን ማስተማር ክርስቶስን ይሸፍናል፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊም አይደለም . . ." ወዘተ እያሉ የሚቃወሙት ተቃውሞ ነው፡፡ ስለ ቅዱሳን ማስተማርን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የፈጠረችው እንግዳ ነገር ነውን? ቅዱሳንስ ክርስቶስን ይሸፍናሉ? ወይስ ይገልጣሉ? ስለ ቅዱሳን መናገርና ስማቸውን እንደ አግባቡ ማንሣትስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው? ወይስ አይደለም? ጉዳዩ እነርሱ (ተሐድሶዎቹ) እንደሚሉት ነው? ወይስ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን እንደምታምነውና እንደምታስተምረው? አሁንም በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ነገር ምን እንደሚል እንመለከታለን፡፡

ስለ ቅዱሳን መማርና ማስተማር አስፈላጊ የሆነባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1) መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚናገርና ስለሚያስተምረን

የቤተ ክርስቲያናችን መሠረቷና መመሪያዋ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከተለያዩ አባቶች ጋር ያደረጋቸውን ግንኙነቶች፣ የተናገራቸውን ነገሮች፣ የሰጣቸውን ቃል ኪዳኖች . . . የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡ ለአብነት ያህልም ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አራት ዘፍጥረትን፣ አራት ዘጸአትን፣ አንደኛና ሁለተኛ ሳሙኤልን፤ ከሐዲስ ኪዳን ደግሞ አራቱ ወንጌላትን እና የሐዋርያት ሥራን ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡

### ኦሪት ዘፍጥረት

| የተጠራው አባት | ኖኅ | አብርሃም | ይስሐቅ | ያዕቆብ | ዮሴፍ | 5ቱ አበው የተጠቀሱበት ጊዜ ድምር | እግዚአብሔር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሰበት ጊዜ ብዛት (ቁጥር) | 39 | 169 | 74 | 163 | 142 | 587 | 291 |

ከመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት መጀመሪያ ላይ የምናገኘው መጽሐፍ ኦሪት ዘፍጥረት እነዚህን አምስት አባቶች፤ ማለትም ኖኅን፣ አብርሃምን፣ ይስሐቅን፣ ያዕቆብን እና ዮሴፍን ያነሣበት ጊዜ ብዛት 587 ሲሆን እግዚአብሔርን ያነሣው ደግሞ 291 ጊዜ ነው፡፡ ታዲያ ይህ በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን አባቶች ከእግዚአብሔር አስበልጧል ተብሎ ሊወቀስ ነውን? በጭራሽ! እንዲህ ያለውን ክፉና ብልሹ አስተሳሰብ ከእኛ ያርቅልን!

### ኦሪት ዘጸአት

| የተጠራው አባት | ሙሴ | አሮን | ዮሴፍ | 3ቱ አበው የተጠቀሱበት ጊዜ ድምር | እግዚአብሔር |
|---|---|---|---|---|---|
| የተጠቀሰበት ጊዜ ብዛት (ቁጥር) | 262 | 109 | 4 | 375 | 375 |

ከመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ሁለተኛ ላይ የምናገኘው የኦሪት ዘጸአት መጽሐፍ እነዚህን ሦስት አባቶች - ሙሴን፣ አሮንን እና ዮሴፍን ያነሣበት ጊዜ ብዛት ድምር (375) ሲሆን ይህም መጽሐፉ እግዚአብሔርን ከጠራበት ጊዜ ጋር (375) እኩል ነው፡፡ ታዲያ ይህ በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ፍጡራንን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሏል ይባላልን? በፍጹም! አሁንም እንዲህ ያለውን ክፉ አስተሳሰብ ከእኛ ያርቅልን፡፡ ይህ መጽሐፍ ቅዱስን ከስሙ በቀር ውስጡን የማያውቁት ሰዎች አስተሳሰብ ብቻ ነው፡፡

### 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል

| | ሐና | ሳሙኤል | ዳዊት | ድምር | እግዚአብሔር |
|---|---|---|---|---|---|
| 1ኛ ሳሙኤል | 12 | 108 | 290 | 410 | 283 |
| 2ኛ ሳሙኤል | | | 284 | | 1,220 |

### አራቱ ወንጌል

| | ዮሐንስ መጥምቅ | ድንግል ማርያም | ቅ.ጴጥሮስ | ኢየሱስ |
|---|---|---|---|---|
| ማቴዎስ | 26 | 8 | 24 | 161 |
| ማርቆስ | 25 | 1 | 20 | 90 |
| ሉቃስ | 31 | 11 | 19 | 96 |
| ዮሐንስ | 19 | 3 | 32 | 242 |

አራቱ ወንጌልም ከጌታችን ስም ጋር እንደ አስፈላጊነቱ የተጠቀሱ የእመቤታችንንና የሌሎችንም ስሞች ይዘዋል፡፡

ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አንዱ የሆነው "የሐዋርያት ሥራ" መጽሐፍ በአጠቃላይ የሚናገረው ስለ ሐዋርያት ነው፡፡ ሐዋርያት ጸጋ መንፈስ ቅዱስን መቀበላቸውን፣ ከዚያም ኃይል መንፈሳዊ አግኝተው ትምህርትና ተአምራት መጀመራቸውን፣ በኋላም ሳውል ይባል የነበረው ቅዱስ ጳውሎስ መጠራቱን፣ በሐዋርያት የደረሰውን ልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራና እግዚአብሔር በእነርሱ እያደረ የሠራውን ድንቅ ሥራ የሚናገር መጽሐፍ ነው፡፡

## የሐዋርያት ሥራ

| | ኢየሱስ ክርስቶስ | ቅዱስ ጳውሎስ |
|---|---|---|
| የተጠቀሱበት (የተጠሩበት) ጊዜ ብዛት | 69 | 160 |

ይህን ቁጥር በማየት ብቻ የሐዋርያት ሥራ ስለ ኢየሱስ ከሚናገረው ይልቅ ስለ ጳውሎስ አብዝቶ ይናገራል ሊባል ይቻላልን? በጭራሽ! መጽሐፉ ቅዱስ ጳውሎስን የሚጠራው (የሚያነሣው) ኢየሱስን ለመስበክና ከመስበኩ ጋር በተያያዘ ነውና፡፡ ስለ ቅዱሳን ስንናገርም እግዚአብሔርን ለማገልገል የወጡትንና የወረዱትን ነገር እንጂ ስለ ሌላ ጉዳይ - ስለ ፖለቲካዊ ሥልጣን ጉዳይ፣ ወይም ስለ ንግድ ወይም በሌላ ጉዳይ አላወቅናቸውም፡፡ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሰደዱ፣ እውነቱን ሲመሰክሩ፣ መከራ ሲቀበሉ፣ ሲራቡ፣ ሲጠሙ፣ ሲነቀፉ፣ ሲሰየፉ፣ ሲታሰሩ፣ ሲደበደቡ፣ ሌሎች ደግሞ ዓለምንና ፍላጎቷን እርግፍ አድርገው በመተው የሚመጣውን ዓለም አኗኗር ገና በዚህ ዓለም ለመኖር ሲታገሉና ሲጋደሉ፣ ይህንና ይህን በተመለከተ ነገር ነው ያወቅናቸው፡፡ ዜና ሕይወታቸውም የሚያጠነጥነው በዚህና ይህን በመሳሰለው ዙሪያ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሎ ሲናገር ስለ ራሱ መስበኩ አልነበረም፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ስለ ደረሰበት እንጂ፦

> እንደ እብድ ሰው እላለሁ፤ እኔ እበልጣለሁ፤ በድካም አብዝቼ፣ በመገረፍ አብዝቼ፣ በመታሰር አትርፌ፣ በመሞት ብዙ ጊዜ ሆንሁ። አይሁድ አንድ ሲጎድል አርባ ግርፋት አምስት ጊዜ ገረፉኝ። ሦስት ጊዜ በበትር ተመታሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወገርሁ፤ መርከቤ ሦስት ጊዜ ተሰበረ፤ ሌሊትና ቀን በባሕር ውስጥ ኖርሁ። ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄድሁ፣ በወንዝ ፍርሃት፣ በወንበዴዎች ፍርሃት፣ በወገኔ በኩል ፍርሃት፣ በአሕዛብ በኩል ፍርሃት፣ በከተማ ፍርሃት፣ በምድረ በዳ ፍርሃት፣ በባሕር ፍርሃት፣ በውሸተኞች ወንድሞች በኩል ፍርሃት ነበረብኝ፤ በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፣ በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም፣ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ። 2 ቆሮ. 11፥23-27

እንግዲህ ከመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት አንዱ የሆነው ይህ የሐዋርያት ሥራ ተብሎ የሚታወቀው መጽሐፍ መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን የሚጠራው 69 ጊዜ ሲሆን ቅዱስ ጳውሎስን የሚያነሳው ደግሞ 160 ጊዜ ነው፡፡ ይህም ማለት ጳውሎስ ጌታችን ከተጠራበት ከእጥፍ ጊዜ በላይ ተጠርቷል ማለት ነው፡፡ ታዲያ ለምን እንዲህ ሆነ? "ጌታን መስበክ" ማለት አንዳንዶች (ፕሮቴስታንቶች፣ ተሐድሶዎችና በእነርሱ እርሾ የተለከፉ መሰሎቻቸው) እንደሚሉት ያለ ርእስ ጉዳዩና ያለ አገባቡ ሁሉ እንዲሁ አእምሮውን እንዳጣ በሽተኛ እየተንዘፈዘፉ ስሙን ብቻ መጥራት ነውን? እንዲያ ከሆነ ታዲያ ቅዱስ ጳውሎስ ጌታን አልሰበከም ማለታቸው ይሆንን?

በተለያዩ ዘመናት ከጠላት ጎን ተሰልፈው አገራቸውንና ወገናቸውን የወጉ ብዙ ያልታደሉ ባንዳዎች ነበሩ፣ ተሐድሶዎችም በመጽሐፍ ቅዱስ ሲመዘንና ሲለካ እንዲህ እንዱም መያዣና መጨበጫ የሌለውን ነገር በጥላቻ መንፈስ አስርጸው በሃይማኖት ሽፍነው በጥቅስ አለባብሰው የላኳቸው የእነዚያው ልጆች ናቸው፡፡ይህን የምንለው ደግሞ ዝም ብለን ሳይሆን በመረጃ ነው፡፡

ለምሳሌም "WORLD WATCH LIST" የተባለው ድርጅት "Open Doors, Serving persecuted Christians worldwide" ከተባለ በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ "ሥራዎችን" ከሚሠራለትና መረጃ ከሚሰበስብለት አካል ጋር በ2013 (እ. ኤ. አ) ባወጣው ሪፖርት ላይ እንዲህ ብሏል፡-

> የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በውስጧ ወደሚካሄደው የተሐድሶ እንቅስቃሴ የሚገቡትን ሰዎች ለዘመናት በጽኑ ስታሳድዳቸው ኖራለች፡፡ ቤተ ክርስቲያኗ ዕብሪት የተጠናወታት ናት፡፡ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ለሚካሄደው የተሐድሶ እንቅስቃሴ ዋናው ስጋት ማኅበረ ቅዱሳን የተባለው አክራሪ ቡድን ነው፡፡ . . . ክርስቲያኑም ሆነ እስላሙ ሳይቀር ፕሮቴስታንት ቸርቾችንና ተሐድሶዎችን የ ሲ አይ ኤ (CIA) ወኪሎች ናቸው እያሉ ይከሷቸዋል፡፡[109]

በአፄ ሱስንዮስ ዘመን፣ በአድዋ ጦርነት፣ በማይጨው ጦርነት፣ ወዘተ ለባዕዳን ተቀጥረው አገራቸውን የወጉት ሰዎች አገራቸውን እየጎዱ መሆኑን ብዙዎቹ ልብ አይሉት እንደ ነበረ ሁሉ እነርሱም ለጊዜው ልብ ላይሉት ቢችሉና ይሄ እውነታ ባይታያቸው አይገርምም፤ ከታሪክ ተምረናልና እንደነቅም፤ ለእነርሱ ግን በእግዚአብሔርም፣ በትውልድም አጥፊነታቸውና ተወቃሽነታቸው ከባድ ነው፡፡ እንዲያ ባይሆንማ ኖሮ ያደረሰችው ጥፋት ተነግሮና ተዘርዝሮ የማያልቀውንና ሀገሪቱም ሆነ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከዘጠነኛው መቶ ዓመት በፊት የነበራቸውን ታሪክና ቅርስ አቃጥላና ቀጥቅጣ ያወደመችውንና ያጠፋችውን ዮዲት ጉዲትን ባላሞካሹት ነበር፡፡ እንዲህ ብለዋልና፡-

- "... መቼም ከጥንት ጀምሮ የሀገራችን ታሪክ ጸሐፊዎች የመንግሥት ባለ ሥልጣኖችና ክርስቲያኖች እንደ መሆናቸው መጠን፣ ለወገን ባያደሉ ኖሮ ቁንጅናዋን፣ ዘዴዋን፣ ታዋቂነቷን፣ ፈጣንነቷን . . . ለዓላማዋ ግብ መምታት እንዴት እንደ ተጠቀመችበት ጽፈው ቢሆን ኖሮ እንደ ግብጽዋ ክሊዎፓትራ የምትቆጠር በሆነች ነበር፡፡" (ሙራ ቁ. 13፤ ገጽ 17)

ታዲያ እንዲህ አይሁዳዊቷን ዮዲትን ከግብጻዊቷ ክሊዎፓትራ ጋር ለማነጻጸር የሚገዳደሩና ስሟ ጠፋ ብለው የሚቆጩ ከሆነ የሀገርና የትውልድ ጠላት ለሆኑት አጋሮችና አድናቂዎች ናቸው ማለት ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ተሐድሶዎች "ኦርቶዶክሳውያን ነን" እያሉ ተቆርቋሪነታቸውና ወገንተኝነታቸው ግን ለሀገሪቷና ለቤተ ክርስቲያኒቷ ጠላቶች መሆኑን ነው፡፡ ታላቁ አባት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ እንዲህ ያሉት ለዚህ ነበር፡-

> የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በራሷ ቋንቋ የምትመሰክረው ከራሷ ማንነት (Identity) ጋር የሚመሳሰል እምነት እያላት እንደ ሌላት በመቁጠር የገዛ ልጆቿን ከጉያዋ እየነጠቁ እየወሰዱ በሷ እንዲነሡባት የጥላቻን ትምህርት የሚያስተምሩ አያሌ ናቸው፡፡ ታዲያ ይህ ተንኮል ያልገባው የኔ አገር ልጅ እውነት የሚናገሩ እየመሰለው እንደ ጠፍ ከብት ወደ ነዱት ይሄዳል፡፡ እነሱ ግን ዓላማቸው የእግዚአብሔር መንግሥት አይደለም፣ የላኩቸውም እግዚአብሔር አይደለም፡፡ (የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣ መቅድም)

በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ የብዙ አባቶችንና ቅዱሳንን ሥራ የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡ ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነገረ ሕይወታቸው ከተጠቀሰውና ከተጻፈው አባቶች መካከል የሚከተሉትን

ለአብነት መመልከት ይቻላል፡-በብሉይ ኪዳን፡-

- የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ ታሪክ - ዘፍ. ምዕ. 12 – 18 ፤ ምዕ. 20-35
- የዮሴፍ ታሪክ - ዘፍ. ምዕ. 39-50
- የነቢዩ የኤልያስና የኤልሳዕ ታሪክ - 1 ነገ. ምዕ. 17 - 22 ፤ 2 ነገ. ምዕ. 1-9
- የዳዊት ታሪክ - 1 ሳሙ. 16 - 1 ነገ. ምዕ. 2 ድረስ፡፡ 1 ዜና ምዕ. 11-29
- የኢዮብ ታሪክ - መጽሐፈ ኢዮብ በሙሉ

[109] WORLD WATCH LIST, 2013 Report, pp. 28-32

በሐዲስ ኪዳን፡-

- ❖ የነቢዪት የሐና ታሪክ - ሉቃ. 2:36-38
- ❖ የኤልያስ ሥራ - ያዕ. 5:17፤ ሮሜ 11:2-4
- ❖ ስለ መልከ ጼዴቅ - ዕብ. 7:1-10
- ❖ የሐዋርያት ሥራ - የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በሙሉ

"ግብረ ሐዋርያት" የሐዋርያትን ታሪክ የያዘ መጽሐፍ መሆኑ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ መጽሐፍ ሆኖ ከመቆጠር አላገደውም፡፡ የሐዋርያት ታሪክ የክርስትና ታሪክ፣ የወንጌል ታሪክ ነውና፡፡ "ሂዱና አስተምሩ"፣ "ምስክሮቼ ትሆናላችሁ"፣ "በጨለማ የምነግራችሁን በብርሃን ተናገሩ፤ በጆሮም የምትሰሙትን በሰገነት ላይ ስበኩ" እያለ የነገራቸውን የአምላካቸውን ትእዛዝ ለመፈጸምና ጨለማውን ዓለም በወንጌል ብርሃን ለማብራት የተደረገውን መንፈሳዊ ተጋድሎ የሚናገር መጽሐፍ ነውና፡፡ የቅዱሳን ሐዋርያትን ዜና ሕይወት ቅዱስ ሉቃስ ጽፎ እንዳቆየልን ሁሉ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችንም የቅዱሳን አበውን ሥራቸውን፣ ሕይወታቸውንና ተጋድሏቸውን እንዲሁም እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ አድሮ የሠራውን ሥራ ለትውልድ ታቆያለች፡፡ የሐዋርያት ሥራ ባይጻፍ ለእኛ ሊደርስና ምክርና ትምህርት ልናገኝበት አንችልም ነበርና፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሯችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፤ የኑሯቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሏቸው" ይላል፡፡ ዕብ. 13፡7 ከእነዚህ ቅዱስ ጳውሎስ "የኑሯቸውን ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሏቸው" ካላቸው አበው ጋር በአንድ ዘመን የኖሩና ጊዜ ያገናኛቸው ሰዎች በአካል እያዩ ከሕይወታቸውና ከትሩፋታቸው በመማር እነርሱን አብነት አድርገው ሥራ ለመሥራት ሊነሳሱና ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ አባቶች የዚህ ዓለም ሥራቸውን ጨርሰው ወደ ፈጣሪያቸው ከተወሰዱ በኋላ የሚነሣው ትውልድ የእነዚህ አባቶቻችን ዜና ሕይወታቸውና ገድላቸው ካልተጻፈ በስተቀር የኑሯቸውን ፍሬ እንዴት አድርጎ ሊመለከትና እነርሱን ሊመስል ይችላል? ስለዚህ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተማርነው ስለ ቅዱሳን እንማራለን፣ እናስተምራለን፡፡

2) እግዚአብሔር ሥራውን የሠራው፣ የሚሠራውም በቅዱሳን ስለ ሆነ

እግዚአብሔር ስለ ሠራቸው የተለያዩ ድንቅ ድንቅ ሥራዎች ስናስብ በእነዚያ የእግዚአብሔር ሥራዎች ውስጥ የተለያዩ ሰዎችን እናገኛቸዋለን፡፡ ሕዝቡን ከግብጽ ሲያወጣ፣ በፈርዖን ፊት ዘጠኙን ተአምራት፣ አሥረኛውን በኲረ ሞት ሲያደርግ በሙሴና በአሮን አማካይነት ነበር፡፡ ዓለሙ የሚባረክበትን ኪዳን ሲያቆም ደግሞ ከአብርሃም ጋር ነበር፤ "እባርክሃለሁ፣ ስምህንም አከብረዋለሁ፣ ለበረከትም ሁን፣ የሚባርኩህንም እባርካለሁ፣ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፣ <u>የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ</u>" በማለት፡፡ ዘፍ. 12፡1-3

እግዚአብሔር ምሥጢሩን የሚገልጠው ለወዳጆቹ ለቅዱሳን ነው፡፡ "በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም" እንደ ተባለ፡፡ አሞ. 3፡7 "ለቅዱሳን እለ ውስተ ምድር ተሰብሐ ኲሉ ሥምረትከ በላዕሌሆሙ - ፈቃድህ ሁሉ በምድር ባሉ ቅዱሳንህ ላይ ተገለጠ"፤ እንዲሁም "ተዐውቀ እግዚአብሔር በይሁዳ ወዐብየ ስሙ በእስራኤል - እግዚአብሔር በይሁዳ ታወቀ፣ ስሙም በእስራኤል ከፍ ከፍ አለ" በማለት ቅዱሳን የእግዚአብሔር ፈቃዱ የተገለጠባቸውና ስሙ ከፍ ከፍ ያለባቸው መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ መዝ. 15፡2 መዝ. 75፡1

በዘመኑ ዓለምን እንቀጥቅጦ የገዛውን የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆርን ያሸነፈውና የእግዚአብሔርን ኃያል አምላክነት እንዲያውቅና እንዲያደንቅ ያደረገው የሦስቱ ወጣቶች ጽንዓትና ተጋድሎ ነበር፡፡

> ናቡከደነፆርም መልሶ፦ መልአኩን የላከ፥ ከአምላካቸውም በቀር ማንንም አምላክ እንዳያመልኩ ለእርሱም እንዳይሰግዱ ሰውነታቸውን አሳልፈው የሰጡትን፥ የንጉሡንም ቃል የተላለፉትን በእርሱ የታመኑትን ባሪያዎቹን ያዳነ፥ የሲድራቅ፥ የሚሳቅና የአብደናጎም አምላክ ይባረክ፡፡ እነም እንደዚህ የሚያድን ሌላ አምላክ የለምና . . . ዳን. 3፥28-29

እንዲሁም ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ በሽተኛ የነበረው ሰው በቅዱስ ጴጥሮስና በቅዱስ ዮሐንስ አማካይነት ሲፈወስ "እግዚአብሔርን እያመሰገነ ከእነርሱ ጋር ወደ መቅደስ ገባ" ይላል፡፡ የቅዱሳንን ተጋድሎዎች የሚናገሩ መጻሕፍት የሚነግሩን እግዚአብሔር በእነርሱ አማካይነት የሠራቸውን ድንቅ ሥራዎችና በእነዚያ ሥራዎች አማካይነት እግዚአብሔርን እያወቁ የነበሩ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መቅረባቸውን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን ሰዎች እግዚአብሔርን ግወቃቸውንና እግዚአብሔርን እንዲያውቁ ማድረጋቸውን እንጂ እግዚአብሔርን መሸፈናቸውን አይነግረንም፡፡ የሐዋ. 3፥8

ጌታችን ቅዱሳን ሐዋርያቱን "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፡፡ መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ" ያለውም ይህን እውነታ ነው፡፡ ማቴ. 5፥14-16 እግዚአብሔር ከቀድሞ ጀምሮ ሥራውን በነቢያት አማካይነት መሥራቱን ሲገልጽ "እግዚአብሔርም በነቢይ እጅ እስራኤልን ከግብጽ አወጣ፥ በነቢይም እጅ ጠበቀው" በማለት ተናግሯል። ሆሴ. 12፥14 ስለሆነም የእግዚአብሔርን ሥራ ለመናገር ስንፈልግ ሥራውን የሠራባቸውን የተለያዩ ቅዱሳን ሰዎች ነጥለንና አውጥተን ሊሆን አይችልም፡፡ ለምሳሌ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብጽ ስለ ማውጣቱ ስንናገር ሙሴንና አሮንን አለማንሣት ይቻላልን? እግዚአብሔር በአክአብና በኤልዛቤል ላይ ስላደረገው ስንናገር ኤልያስን አለማንሣት፥ በነቢያት ዘመን ስለሆነው ስንናገር እነ ኢሳይያስንና ኤርምያስን፥ እነ ሕዝቅኤልንና ዳንኤልን፥ እንዲሁም ሌሎቹን ነቢያት አለማንሣት ይቻላልን?

ወንጌል በዓለም የተሰበከበትን ሁኔታ ስናስብስ ቅዱሳን ሐዋርያት የተቀበሏቸውን እነዚያን ለመናገር እንኳ የሚከብዱ ጽዋትወ መከራዎች አለማንሣት እንዴት ይቻላል? ቅዱሳን ሰማዕታት ለአራዊት መጣላቸውን፥ ለእሳትና ለሰለት መዳረጋቸውን፥ ደማቸውን ማፍሰሳቸውን፥ የተለያዩ የመከራ ዓይነቶች ሁሉ የተሞከሩባቸው መሆኑን መዘንጋት ይቻላልን? ለክርስቲያን ይህን ማድረግ አይቻልም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "አሁን በመከራዬ . . . ስለ አካሉም ማለት ስለ ቤተ ክርስቲያን በሥጋዬ በክርስቶስ መከራ የጎደለውን እፈጽማለሁ" ያለውን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ልትዘነጋ አትችልም፡፡ የቅዱሳን መከራ ሐዋርያው "በመከራዬ በክርስቶስ መከራ የጎደለውን እፈጽማለሁ" እንዳለው የቤተ ክርስቲያን የዕድገቷና የእድገቷ ክፍል ነውና፡፡ ራሱ ጌታችንም በትምህርቱ ነቢያትን ብዙ ጊዜ ደጋግሞ አነሳስቷቸዋል፡፡ ለምሳሌም "አብርሃምንና ይስሐቅን ያዕቆብንም ነቢያትንም ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት ባያችሁ ጊዜ" ብሎ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ መሆናቸውን ተናግሮላቸዋል፡፡ ሉቃ. 13፥28

### 3) የእግዚአብሔር ቸርነት የሚገለጥበት መንገድ ስለ ሆነ

እግዚአብሔር በባሕርዩ ቸር ነው፡፡ ሆኖም ይህ ቸርነቱ በተግባር የተገለጠውና እኛም ማየትና መመስከር የቻልነው ጸጋውን ለሰዎች አብዝቶ በመስጠቱ ነው፡፡ እግዚአብሔር ከሰው ወገን ቅዱሳን ይሆኑ ዘንድ መፍቀዱ የዚህ ቸርነቱ ውጤትና መገለጫ ነው፡፡ ለምሳሌም፦ ለሙሴ የጸጋ አምላክነትን በፈርዖን ላይ ሰጠው (ዘጸ. 7፥1)፤ ለኤልያስ ሙት ማንሣትን፥ ዝናም እንዳይጥል ሰማይን ማገድን፥ ኋላም መክፈትን፤ ዮርዳኖስን መክፈልን፥ በእሳት ሠረገላ ማረግን ሰጠው፡፡

ለኤልሳዕ ደግሞ የተሰወረውን ከርቀት ማየትን፣ ሙት ማንሣትን ወዘተ ሰጠው፡፡ የቅዱስ ጴጥሮስ ጥላው፣ የቅዱስ ጳውሎስ የልብሱ ቁራጭ አጋንንትን እንዲያስወጣ፣ ድውያንን እንዲፈውስ (የሐዋ. 5:15፥16 ፤ 19:11-12)፤ ለሐዋርያት ሙት ማንሣትን፣ አጋንንትን ማስወጣትን፣ ሥልጣነ ክህነትን፣ ወዘተ ሰጥቷቸዋል፡፡ ይህ ሁሉ ለቅዱሳን የሰጠው ጸጋ የእግዚአብሔርን ቸርነት በተግባር የገለጠልንና ያሳየን መስተዋት ነው፡፡

እዚህ ላይ ተሐድሶዎች ስለዚህ ያሉትን እናንሣ፤

- "... ብዙ ጊዜ የሚጠቀሱት እግዚአብሔር ሙሴን እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ፡፡ ወንድምህም አሮን ነቢይ ይሆንልሃል" (ዘጸ. 7:1) ያለውን ነው፡፡ ይህን መለኮታዊ ቃል በእግዚአሔር መንፈስ ለመረመረው ሰው በፈርዖን ዘንድ እንደ አምላክ ይመስካል ወይም ደረጃው ዝቅ ያለ ትንሽ አምላክ ይሆናል ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ . . . ሌላው ከዚሁ ጋር አብሮ የሚጠቀሰው (መዝ. 81፥ 6) "እኔ ግን አማልክት ናችሁ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ" ተብሎ የተጻፈው ነው፡፡ ቃሉ የእግዚአብሔር ቃል ስለመጣላቸው የእስራኤል አለቆችና መሪዎች የተነገረ ቢሆንም (ዮሐ. 10፥ 35) እንደ እግዚአብሔር አምላክ መሆንን ወይም መመለክን ከቶ አያሳይም፡፡ ይልቁንም "አማልክት ናችሁ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ" በማለት ትክክለኛ ማንነታቸውን እዚያው ላይ ይገልጻል (ቁ. 7) (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 48-49)

የሚገርም ነው! ሰውን በማይለው መከራከር ምን ይባላል? የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን የጸጋ አማልክት ናቸው የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል የምትረዳውና የምትተረጉመው እንደ አምላክ ይመለካሉ ብላ አይደለም፡፡ ወይም ደረጃቸው ዝቅ ያለ ትናንሽ አምላኮች ብላም አይደለም፡፡ እንደ እግዚአብሔር አምላክ ይሆናሉ ወይም ይመስካሉም አትልም፡፡ ታዲያ "ይህን መለኮታዊ ቃል በእግዚኤሔር መንፈስ ለመረመረው ሰው በፈርዖን ዘንድ እንደ አምላክ ይመስካል ወይም ደረጃው ዝቅ ያለ ትንሽ አምላክ ይሆናል ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ . . . እንደ እግዚአብሔር አምላክ መሆንን ወይም መመለክን ከቶ አያሳይም" እያሉ ተርጓሚና አብራሪ ለመሆን መሞከር ምን ማለት ነው? እስካሁንም ሆነ ወደፊት በተደጋጋሚ እንዳየነውና እንደምናየው ተሐድሶዎች የሚናገሩት ቤተ ክርስቲያኗ የማትለውን እንደምትል፣ የማታምነውን እንደምታምን እያስመሰሉ ጥላሸት በመቀባት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሆነውን መቃወም ሲያቅት ጥቅም ላይ የሚውል ስልት ነው፡፡

በአጠቃላይ ስለ ቅዱሳን ስናነሣና እነርሱን ስናስብ በአእምሯችን የሚመጣውና የሚታየን በእነርሱ የተገለጠው የእግዚአብሔር ቸርነት ነው፡፡ ለአንዳንዶቹ ጻድቃን በበረሐ ዛፍ እንዲያፈራላቸው፣ ቶራ እንድትታለብላቸው፣ መራራው ቅጠል እንዲጣፍጣቸው ሲያደርግላቸው፣ እንዲሁም ለሰው ከባድ የሆኑትን ግርማ ሌሊቱን ድምፀ አራዊቱን ሲያስታግሥላቸው፣ ለገድልና ለትሩፋት ሲያበረታቸው ቸርነቱና ደግነቱ አካል ገዝቶና ጎልቶ ይታያል፡፡ በከሃድያንና በሐሳውያን ፊት እውነቱን ለሚመሰክሩ ለሰማዕታት ደግሞ ነበልባለ እሳት እያበረደ፣ እንዲበሏቸው የሚላክባቸውን አንበሳ እያስገደ፣ በመሳሰለው ኃይል ያጸናቸዋል፣ ያስታግሣቸዋል፡፡ በነቢዩ "መንክር እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ - እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ነው" የተባለው የሚገለጠው በዚህ ሁኔታ ነው፡፡ መዝ. 67፥35

እግዚአብሔር ሥራውን ሲሠራ በቀጥታ (ያለ ምንም ነገር ምክንያትነት) ይሠራል፣ እንዲሁም ደግሞ በምክንያት (በሥነ ፍጥረት አማካይነት) ይሠራል፡፡ ለምሳሌም እስራኤላውያን ከግብጽ ወጥተው ወደ ከነዓን እየተጓዙ በምድረ በዳ ላይ ሳሉ መራራ የነበረውን የማራን ውኃ እግዚአብሔር በእንጨት አማካይነት ማጣፈጡን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ ዘጸ. 15፥23-25 ባሕረ ኤርትራን ሲከፍል በአሮን በትር አማካይነት፣ ኤልሳዕ የኢያሪኮን ውኃ ሲያጣፍጥ በማሰሮ ውስጥ ጨው ጨምሩ በማለት አደረገ፡፡ 2 ነገ. 20-22 ለዓይነ ስውሩ ዓይን ሲፈጥር "ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ" በማለት ነበር፡፡ ዮሐ. 9፥7 እግዚአብሔር እንዲህ በተለያዩ ግኡዛን በሆኑ ሥነ ፍጥረታት

አማካይነት እንኳ ሥራውን የሚሠራና ኃይሉን የሚገልጥ ከሆነ በእርእያውና በአምሳሉ አክብሮ በሕያዊት ነፍስ አሳምሮ ከፈጠራቸው ወገን በሆኑና ፈቃዱን በመፈጸም ደስ ባሰኙት በወዳጆቹ በቅዱሳን አማካይነት ቢሠራ እንግዳ ነገር የሚሆነው ምኑ ይሆን?

እርሱ ባለቤቱ ከቸርነቱ ብዛት የተነሣ በእርሱ ለሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ማድረግ የሚችሉት ነገርና ከሃሌ እስከ ምን ድረስ እንደ ሆነ ሲናገር እንዲህ አለ፦ "እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል።" ዮሐ. 14፥12 ይህ ማለት በእርሱ የሚያምኑ ቅዱሳን ራሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም በሥጋ በተመላለሰባቸው ጊዜያት - በዘመነ ሥጋዌው - ከሠራቸው ሥራዎች የበለጡ ተአምራትን ማድረግ ይችሉ ዘንድ ጸጋውን በቸርነቱ ሰጥቷቸዋል።

ጌታችን "ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል" ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህ ማለት <u>አንደኛ</u> ጌታችን በዘመነ ሥጋዌው ያደረጋቸው ተአምራት በጊዜው የነበሩ ሕሙማን፣ ርሁባን፣ ጽኑሳን ወዘተ ከነበረባቸው ችግር አንጻር የተሰጡ ተአምራታዊ መፍትሔዎች ነበሩ። ነገር ግን በየዘመናቱ የየሰዎች ችግርና ፈተና ዓይነቱ ብዙና ውስብስብ ስለሆነ በየጊዜው የሚነሱ ቅዱሳን ለሚኖሩበት ዘመን ችግር ተገቢና አስፈላጊ የሆነ መፍትሔ በተአምራት መስጠት የሚችሉ መሆኑን የሚያስረዳ ነው። እንዲሁም ጌታችን የሰጠው ጸጋ እርሱ በዘመነ ሥጋዌው ባደረጋቸው የተአምራት ዓይነቶች ብቻ የሚገደብ አለመሆኑን የሚገልጽ ነው። ለምሳሌ እርሱ ያስነሳቸው ሙታን የዕለት ሬሳ የኢያኢሮስን ልጅ፣ ሊቀበር ተገንዞ ሲወሰድ የነበረውን የመበለቲቱን ልጅ፣ እና ከተቀበረ አራት ቀናት ሆኖት የነበረውን አልዓዛርን ነበር። ቅዱሳን ግን ከሞቱ ብዙ ዘመናት የሆናቸውን ማስነሣት ችለዋል። ጌታችን በመዋዕለ ሥጋዌው ፀሐይ የማቆም፣ ዝናም የማዝነም ተአምራትን አላደረገም (ይህን ያላደረገበት ምክንያትም ያደረጋቸው ተአምራት ያን ጊዜ ሁኔታዎች የተአምራቶቹን መደረግ ለሰዎች ጥቅም አስፈላጊ ያደረጓቸውን ብቻ ነበር እንጂ ማድረግ የሚችለውን ሁሉ ስላልሆነ ነው። ለእርሱ የሚሳነው ነገር ስለሌለ ሁሉን ማድረግ ቢችልም ያደረጋቸው ተአምራት ግን እርሱ ባወቀ አስፈላጊ የሆኑትን ብቻ ነበር)፤ ቅዱሳን ግን ፀሐይ አቁመዋል፣ ዝናም አዝንመዋል፣ ከሞቱ ብዙ ዘመናት የሆናቸውን ሙታ አሥነስተዋል፤ . . . ሌሎችም ብዙ አስደናቂ ተአምራትን አድርገዋል።

<u>ሁለተኛው</u> "ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል" ያለበት ምክንያት ደግሞ እርሱ አምላክ ስለ ሆነ ምንም ነገር ቢያደርግ በባሕርዩ ሁሉን ነገር ማድረግ የሚችል ከሃሌ ኩሉ ስለ ሆነ አይደንቅም። እነርሱ ግን ፍጡራን ሆነው ሳለ እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርጋቸው የሚችሉትንና ለፍጡራን መቸም መች በባሕርያቸው ሊደረጉ የማይቻሉትን ነገሮች ማድረግ የሚችሉ መሆናቸውን የሚገልጽ ነው። እርሱ በአምላክነቱ የሚያደርጋቸውን እነርሱ ግን ፍጡራን ሆነው ሳለ ማድረጋቸው አስደናቂ መሆኑን የሚያሳይ አገላለጽ ነው። እነርሱ በደዌ የሚያዙ ሆነው ሳለ ድውያንን መፈወሳቸው፣ የሚራቡ ሆነው ሳለ (እየተራቡም) ሌሎችን መመገባቸው፣ ድሆች ሆነው ሳለ ሌሎችን በጸጋ እግዚአብሔር ማበልጸጋቸው፣ ሞት የሚያገኛቸው ሆነው ሳለ ሙታንን ማስነሣታቸው፣ በሥጋቸው ደካሞች ሆነው ሳለ በመንፈስ ሌሎችን ማበርታታቸው፤ ... ሁሉ አስገራሚና አስደናቂ ነውና። ይህም ሐዋርያው "አሳቾች ስንባል እውነተኞች ነን፤ ያልታወቁ ስንባል የታወቅን ነን፤ የምንሞት ስንመስል እነሆ ሕያዋን ነን፤ የተቀጣን ስንሆን አንገደልም፤ ኀዘንተኞች ስንሆን ዘወትር ደስ ይለናል፤ ድሆች ስንሆን ብዙዎችን ባለ ጠጎች እናደርጋለን" ብሎ የገለጸው ነው። 2 ቆሮ. 6፥8-10 ስለዚህ ስለ ቅዱሳን መማር ይህን ድንቅ የእግዚአብሔር ቸርነት መገለጥ በተግባር ማየትና መማር ነው።

### 4) የቅዱሳን ጽናትና ድል አድራጊነት የእግዚአብሔር ኃይልና ድል አድራጊነት መገለጫና ምስክር ስለሆነ

ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ ሞትን ድል ማድረጉና የሞትን ኃይልና አስፈሪነት ማጥፋቱ ለሰዎች ከተገለጠበትና ለዓለምም ከሚገለጥበት አንደኛው መንገድ ቅዱሳን ሰማዕታት ሞትን መናቃቸውና ፊት ለፊት መጋፈጣቸው፤ ጻድቃን ሰውነታቸውን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ መሥዋዕት አድርገው በማቅረብ ገርማ ሌሊቱን ጸብአ አጋንንቱን ድምፀ አራዊቱን ታግሠው መጋደላቸውና ድል ማድረጋቸው፤ እንዲሁም እውነተኛ ክርስቲያኖች በአጠቃላይ የዚህን ዓለም ጣዕምና ተድላ ደስታ ችል ብለው ለሰማያዊው ሕይወት መኖራቸው ነው፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምኑ ያመኑ አሕዛብ እንደ ጦር የሚፈሩትን ሞት፤ እንዲሁም ሌት ተቀን የሚጨነቁለትን የዚህን ዓለም ሕይወት በክርስቶስ ትንሣኤ ያመኑ ክርስቲያን ሰማዕታት ሲንቁትና ፊት ለፊት ሳይፈሩ ስለ ክርስቶስ ፍቅር ሲሉ ሲጋፈጡት ሲያዩ ብዙዎች ከሞት በላይና ባሻገር ስላለው ሕይወትና እውነት በሰማዕታት ጽናትና ብርታት አማካይነት ተምረዋል፡፡ ከአሕዛብ ወገን፣ ሰማዕታቱን ይገድሉና ያሠቃዩ ከነበሩት ከወታደሮችም ሳይቀር በዚሁ ተስበው ለሰማዕትነት የበቁት በጣም ብዙዎች ናቸው፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እርሱ በዚህ ዓለም ሕይወቱ የተቀበለው መከራ ፋይዳው ምን እንደ ሆነ ሲገልጽ "አሁን በመከራዬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል፤ ስለ አካሉም ማለት ስለ ቤተ ክርስቲያን <u>በሥጋዬ በክርስቶስ መከራ የጎደለውን እፈጽማለሁ</u>" ይላል፡፡ ቆላ. 1፥24 እስኪ ይህ አባባል ምን ማለት እንደ ሆነ ቆም ብለን እናስብ፡፡ "<u>በሥጋዬ በክርስቶስ መከራ የጎደለውን እፈጽማለሁ</u>" ሲል በክርስቶስ መከራ የጎደለ ነገር አለ ማለቱ ይሆን? ያን የጎደለውንስ ነገር እርሱ (ቅዱስ ጳውሎስ) የሚቀበለው መከራ ሊሞላው ይችላል ማለቱ ይሆን? በጭራሽ! ሐዋርያው እንዲህ ያለው ቅዱሳን በሰውነታቸው የሚቀበሉት መከራ በአንድ በኩል ክርስቶስ ስለ እኛ ሲል የተቀበለው መከራ ቀጣይ አካል መሆኑንና በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ የጌታችን መከራና በመከራው የተገኘው ድል አድራጊነት ሕያውና አማናዊ ምስክርና ማስረጃ መሆኑን ሲናገር ነው፡፡ ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስ የሚቀበሉት መከራና የሚጋደሉት ተጋድሎ የክርስቶስ የመከራው አካል ነው፡፡ ጌታችን የኋላውን ቅዱስ ጳውሎስ የቀደመውን ሳውል በሚያስደንቅ ሁኔታ ሲጠራው "ሳውል ሳውል ለምን ታሳድደኛለህ? አለው፡፡ እርሱም "ጌታ ሆይ ማን ነህ?" ባለው ጊዜ "አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ" ያለው ይህን የሚገልጽ ነው፡፡ የሐዋ. 9፥3-5 ጌታችን የክርስቲያኖችን ስደትና መከራ የራሱ አድርጎ "ለምን ታሳድደኛለህ? አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ" አለው እንጂ "ለምን ታሳድዳቸዋለህ?" አላለውም፡፡ ስለሆነም ቅዱሳን በየተሰማሩበት የተጋድሎ አቅጣጫ በእርሱ ቸርነት ያፈሩት ፍሬና የተጋደሉት ተጋድሎ የክርስቶስ መከራ አካል ነው፤ የዚያ ምልአት አካል ነው፡፡ የሰውነት የአካል ክፍሎች የሚሠሩት ሥራ የራስ ሥራ አካል ነውና፡፡

እንደዚሁም ደግሞ ክርስቶስ ሞትን ድል ባያደርገው ኖሮ ሰማዕታትም ሞትን መጋፈጥና መናቅ ባልቻሉ ነበር፡፡ ጻድቃንም የዚህን ዓለም ጣዕምና ፍቅር ድል ማድረግና መተው (መመነን) ባልቻሉ ነበር፡፡ ስለዚህ የቅዱሳን ሰማዕታት፣ የጻድቃንና በአጠቃላይ እግዚአብሔርን በሕይወታቸው ደስ ያሰኙ የክርስቲያን ሰዎች ዜና ሕይወታቸው በቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚነገረው ያ ድል አድራጊነታቸውና የሕይወታቸው ፍሬ የእግዚአብሔር ድል አድራጊነትና ኃይል አካል እና እርሱም የተገለጠበት ስለሆነ ነው፡፡ የእነርሱ ተጋድሏቸው፣ መከራቸውና ድል አድራጊነታቸው የመስቀሉ ድል፣ የትንሣኤው ኃይል ቀጣይ አካልና ሕያው ምስክር ነው፡፡

ይኸው ሐዋርያ "እኔ የኢየሱስን ማኅተም በሥጋዬ ተሸክሜያለሁ" ይላል፡፡ ገላ. 6፥17 እንዲሁም "ይህ ናፍቆቴ ተስፋዬም ነውና፣ በአንድ ነገር እንኳ አላፍርም፡፡ ነገር ግን በሕይወት ብኖር ወይም ብሞት፣ ክርስቶስ በግልጥነት ሁሉ እንደ ወትሮው አሁን ደግሞ በሥጋዬ ይከብራል" ሲል የገለጸውም ይህንኑ የሚያስረዳ ነው፡፡ ፊል. 1፥20 ቅዱሳን በዚህ ዓለም ሳሉ በእግዚአብሔር ኃይልና ጸጋ የተጋደሉት ተጋድሎና ያደረጉት ድል የእግዚአብሔር ድል ነው፤ ኃይላቸው እርሱ ነውና፡፡ ስለዚህ ስለ ቅዱሳን መናገርና መማር እግዚአብሔር በእነርሱ የሠራውን ሥራ መናገርና መማር ነው፤ <u>ቅዱስ ጳውሎስ "በክርስቶስ መከራ የጎደለውን መፈጸም" ብሎ የገለጸው የቤተ ክርስቲያን አካል ነው፡፡</u>

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ ላይ ስለ ደረሰበት መከራ ከገለጸ በኋላ "ነገር ግን፣ ወንድሞች ሆይ፣ ይህ የደረሰብኝ በእውነት ወንጌልን ለማስፋት እንደ ሆነ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ" ይላል፡፡ ፊል. 1፡12 ቅዱሳን አባቶቻችን ወንጌልን ለመስበክና ለማስፋፋት የተቀበሉትን መከራና ያደረጉትን ተጋድሎ፣ እንዲሁም በእነርሱ ላይ የተገለጠውን የእግዚአብሔር ድል አድራጊነት ቤተ ክርስቲያን ትዘነጋ ዘንድ አትችልም፡፡ የእነርሱ ጽናትና ተጋድሎ፣ ፍሬያቸውና ሥራቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል ያደረገው መሆኑን፣ በእግዚአብሔር ያመነ ሰው የሚሳነው ነገር የሌለ መሆኑን በተግባር የሚመሰክሩ ምስክሮች ናቸውና፤ "ምስክሮችህ ድንቆች ናቸው፣ ስለዚህም ነፍሴ ፈለገቻቸው" እንደ ተባለ፡፡ ቅዱሳን ሰማዕታት "ሰማዕታት - ምስክሮች፣ መስካሪዎች" የተባሉትም ለዚህ ነው፡፡ መዝ. 118፡129 ስለዚህም ገድላቸውን ዜና ሕይወታቸውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትናገራለች፣ ታስበዋለች፡፡

## 5) የቅዱሳን ሕይወት ሕያው ወንጌል ስለ ሆነ

በወንጌል የምናገኘው በአብዛኛው እናደርገው ዘንድ የተነገረ ትእዛዝን ሲሆን ይህ ቃለ ወንጌል በተግባር ተፈጽሞ ያየነውና የምናየው ደግሞ በቅዱሳን ሕይወት ነው፡፡ ለምሳሌም ለስም አጠራሩ ክብርና ምስጋና ይሁንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ የሚረግሟችሁንም መርቁ፣ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ፣ ስለሚያሳድዱችሁም ጸልዩ" ብሎ አስተምሮናል፡፡ በመስቀል ላይ ሆኖ ለሰቀሉት ሳይቀር "አባ ሥረይ ሎሙ እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ - የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" በማለት ይህንኑ በተግባር ፈጽሞም አሳይቶናል፡፡ ማቴ. 5፡44-45 ከሰዎች ወገን ደግሞ ይህን የጌታችንን ትምህርት በተግባር በመፈጸም እኛም ልናደርገው የምንችል መሆኑን በተግባር ያስተማሩን ቅዱሳን ናቸው፡፡ ለአብነትም ሊቀ ዲያቆናት ቀዳሚ ሰማዕት የሆነው ቅዱስ እስጢፋኖስ በድንጋይ እየወገሩት ለነበሩት ክፉዎች አይሁድ "ጌታ ሆይ፣ ይህን ኃጢአት አትቍጠርባቸው" ብሎ በታላቅ ድምፅ በመጮኸ ወደ እግዚአብሔር ምሕረትንና ይቅርታን ለመነላቸው። በወንጌል "ለሚያሳድዱችሁ ጸልዩ" የተባለውን በተግባር ፈጸመ፡፡ የሐዋ. 7፡60 በዚህ የቅዱስ እስጢፋኖስ ጸሎትም በእርሱ መወገር ዋና ተዋናይ የነበረው ሳውል የኋላው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲሆን ረድቶታል፡፡

ሌሎችን የአምላካችንን ትእዛዛት፣ በሰው ዓቅምና ኃይል ለመፈጸም የማይቻሉ ወይም በጣም የሚከብዱ የሚመስሉትን ሳይቀር በሕይወታቸው በመፈጸም የአምላካችን ትእዛዛት ሊፈጸሙ የሚችሉ መሆናቸውን በተግባር ያሳዩንና የሕይወት መምህራን የሆኑን በየዘመናቱ የተነሡ ቅዱሳን ናቸው፡፡ ጌታችን በቅዱስ ወንጌል "ቀኝ ዓይንህ ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት" ያለውን ቃል በአሥረኛው መቶ ዓመት በግብጽ አገር ብዙ ምግባር ትሩፋቶችን በስውር ይሠራና ጫማ በመስፋት ይኖር የነበረው ስምዖን የተባለው ምእመን በተግባር ፈጽሞታል፡፡" ማቴ. 5፡29 "እግርህ ብታሰናክልህ ቆርጠህ ጣላት" የተባለውን ደግሞ አባ መርትያኖስ የተባለ ተጋዳይ የነበረ መነኩሴ ፈጽሞታል፡፡ ማቴ. 18፡8

በአጠቃላይ የቅዱሳን ሕይወት ተግባራዊ የሕይወት ትምህርት ቤት ነው፡፡ ሐዋርያው "የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሯችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፣ የኑሯቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነት ምሰሏቸው" ያለው ለዚህ ነው፡፡ ዕብ. 13፡7 ዜና ሕይወታቸው ካልተነገረ በስተቀር እነዚያን ከእኛ በፊት የነበሩትንና የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩንን ዋኖቻችንን ማሰብ፣ እንዲሁም የኑሯቸውንም ፍሬ እየተመለከትን በእምነት ልንመስላቸው የምንችለው እንዴት አድርገን ነው? ሁሉም ትውልድ በአንድ ዘመን ላይ አይኖርምና! አዎ፣ የኑሯቸውን ፍሬ መመልከትና እነርሱን ለመምሰል እንበረታታ ዘንድ፣ ተግባራዊ የሕይወት ትምህርት እናገኝ ዘንድ በክርስቶስ የሆነውን መንገዳቸውን ከዜና ሕይወታቸው ልንማርና ልናውቅ ይገባናል፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መልእክትን ከጻፈላቸው በኋላ ከዚያ በተጨማሪ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሆነውን ተግባራዊ ሕይወቱን በተመለከተ በስፋት ይነግራቸው ዘንድ ደቀ መዝሙሩን ጢሞቴዎስን እንደሚልክላቸው ሲናገር "ስለዚህ የምወደውንና የታመነውን በጌታ ልጄ የሆነውን ጢሞቴዎስን ልኬላችኋለሁ፥ እኔም በየስፍራው በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንደማስተምር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚሆነውን መንገዴን እርሱ ያሳስባችኋል" አላቸው፡፡ 1 ቆሮ. 4፡17 ስለሆነም በአባቶቹ ያሕይወትና የተጋድሎ መንገድ ለመሄድ የሚፈልግ ሁሉ የአባቶቹን "በክርስቶስ ኢየሱስ የሆነውን መንገዳቸውን" ያስብና ያስታውስ ዘንድ ግድ ይለዋል፡፡ ከቅዱሳን አባቶቻችን ካልተማርንስ ከማን እንማር? ከእነርሱ ሕይወት መማር የምንችለው ደግሞ ሕይወታቸው ሲነገር ነው፡፡ ስለዚህም ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆነውን የቅዱሳንን መንገዳቸውን ትናገራለች፡፡

6) የክርስትና ዓላማው ሰዎችን ቅዱሳን ማድረግ ስለሆነ

የክርስትና ዓላማውና ግቡ ሰዎችን ወደ ቅድስና መምራትና ቅዱሳን እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ወንጌልን ያስተማረውና መዳናችንን የፈጸመው ለሰዎች የቅድስና ሕይወትን ለመስጠት፥ ወደዚህ ሕይወት የሚደረስበትን የጉዞ መስመር ለማሳየትና በቅድስና መስመር ተጉዘው ቅዱሳን እንዲሆኑ ለማድረግ ነው፡፡ "እነርሱም ደግሞ በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ እቀድሳለሁ" እንዳለ ጌታችን። ዮሐ. 17፡19

እግዚአብሔር አምላካችን "ኑኑ ቅዱሳን እስመ አነሂ ቅዱስ አነ - እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ" በማለት ሁላችንንም ለቅድስና ጠርቶናል፡፡ ዘሌ. 19፡2 ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን ጽፎ ለሚሰድድላቸው ክርስቲያኖች በመልእክታቱ መጀመሪያ ላይ "በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠራችሁ በሮሜ ላላችሁት ሁሉ..." ፤ "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት . . ." እያለ ይህን የክርስትና ዓላማ ያስታውሳቸውና ያሳስባቸው የነበረው ለዚህ ነው፡፡ ሮሜ 1፡7 1 ቆሮ. 1፡2 ስለዚህ ዓላማችንን እናውቅና ከግባችን መድረስ እንችል ዘንድ በእጅጉ የሚያስፈልገን በመሆኑ ስለ ቅድስናና በዚህ መንገድ ከእኛ በፊት ስለ ተጓዙ ስለ ቅዱሳን ሕይወት መማር የግድ ይለናል፡፡

7) መጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳንን እንድናውቅ፥ ወደ እነርሱ እንድንመለከት ስለሚያዝዘን

መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ቅዱሳን አባቶቻችንና እናቶቻችን እንድንመለከት ያዝዘናል፥ ያስተምረናል፡፡ ለአብነትም በነቢዩ በኢሳይያስ ሲናገረን "ወደ አባታችሁ ወደ አብርሃም፥ ወደ ወለደቻችሁም ወደ ሣራ ተመልከቱ" ይለናል፡፡ ኢሳ. 51፡2 ነቢዩ ኢሳይያስ በነበረበት ዘመን (ከክርስቶስ ሥጋዌ በፊት 700 ዓመታት ገደማ) አብርሃምና ሣራ በዚህ ዓለም ላይ በሕይወተ ሥጋ አልነበሩም፡፡ አብርሃምና ሣራ የነበሩት ከክርስቶስ ልደት በፊት 2,000 ዓመት ገደማ ነበር፡፡ ስለዚህ ነቢዩ ኢሳይያስ "ወደ አባታችሁ ወደ አብርሃም፥ ወደ እናታችሁም ወደ ሣራ ተመልከቱ" ብሎ ይህን የእግዚአብሔር ቃል ሲጽፍ አብርሃምና ሣራ ከዚህ ዓለም ሕይወት ካረፉ (ከሞቱ) 1,300 ዓመታት ገደማ ሆኗቸው ነበር ማለት ነው፡፡ ታዲያ በራሱ በነቢዩ በኢሳይያስ ዘመን የነበሩና ከዚያም በኋላ የሚነሡት ትውልዶች አብርሃምንና ሣራን ሊመለከቱ የሚችሉት እንዴት አድርገው ነው? የእነዚህን ጻድቃን ሰዎች እምነታቸውን፥ ታዛዥነታቸውን፥ ወዘተ ከመጻሕፍት በመማር ካልሆነ በስተቀር በአካለ ሥጋ ሊያዩዋቸው አይችሉምና! ስለሆነም ከእኛ በፊት የነበሩ ቅዱሳን አባቶቻችንንና እናቶቻችንን ገድላቸውንና ዜና ሕይወታቸውን በማንበብ እናያቸውና እናውቃቸው ዘንድ የእግዚአብሔር ቃል ያዝዘናል፡፡መናፍቃን ደግሞ ወደ ቅዱሳን አትመልከቱ ይሉናል፡፡ የምንሰማውን መምረጥ ደግሞ የእያንዳንዳችን ድርሻና ኃላፊነት ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስም "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ" በማለት ክርስቶስን የለበሱና ክርስቶስ በውስጣቸው የኖረባቸውንና የተገለጠባቸውን የቅዱሳንን ሕይወት መመልከት ክርስቶስን መመልከት እንደሆነ፣ እኛንም የክርስቶስ አማናዊ ማደሪያዎችና ዙፋኖች እንድንሆን የሚያንሳሳንና የሚመራን መሆኑን አስተማረን፡፡ 1 ቆሮ. 11፥1 ቅዱስ ጴጥሮስና ዮሐንስም በቤተ መቅደስ አጠገብ ሲለምን የነበረውን በሽተኛ "ወደ እኛ ተመልከት" ብለውታል፡፡ የሐዋ. 3፥4 በሽተኛውም ወደ እነርሱ ሲመለከት ያገኘው የኢየሱስ ክርስቶስን የፈውስ ኃይልና ተአምራት ነበር፡፡ ከተወለደ ጀምሮ ሌሎች ሰዎች ሲያደርጉት ማየት እንጂ እርሱ ግን አንድም ቀን አድርጎት አያውቅ የነበረውን እንደ ልቡ መራመድና ጸንቶ መሄድ እርሱም አግኝቶ ደስ ብሎታል፡፡ እርሱም፣ የእርሱን ሁኔታ ያዩ ሌሎችም ብዙዎች እግዚአብሔርን አመሰገኑ፡፡ ለዚያ በሽተኛ በቅዱሳን ሐዋርያት አማካይነት ከተደረገለት ተአምር የተነሣም አምስት ሺህ ያህል ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አምነዋል፡፡ የሐዋ. 4፥4 ወደ ቅዱሳን መመልከት ይህን ሁሉ የእግዚአብሔርን ሥራ ለማየት በር ከፋችና ፋና ወጊ ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ መጨረሻ ላይ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መልካም ሱታፌ የነበራቸውን የተለያዩ ሰዎችን ከጠቃቀሰ በኋላ "<u>እንግዲህ እንደነዚህ ያሉትን እወቋቸው</u>" ይላል። ሮሜ 16፥18 አዎ፣ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት እንዲህ ያሉትን ቅዱሳን ማወቅ ይገባናልና መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ያሉትን ቅዱሳን አበውና እማት እናውቃቸው ዘንድ ያስተምረናል፡፡ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ሐዋርያዊት በመሆኗና መጽሐፍ ቅዱስን እንደ መናፍቃን የተወሰነውን ብቻ መርጣና ቆርጣ ሳይሆን እንዳለ በሙሉ የምትቀበልና የምታምንበት በመሆኗ እንደነዚህ ያሉትን ቅዱሳን እናውቃቸው ዘንድ ታስተምራለች፡፡

## 6.2 ቅዱሳን ከሞት በኋላ ስለሚኖራቸው ማወቅ/አለማወቅ ጉዳይ

### 6.2.1 የተሐድሶዎች ትምህርት በዚህ ጉዳይ ላይ

ተሐድሶዎች ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ በዚህ ዓለም ስለሚሆነው ነገር ምንም አያውቁም ባዮች ናቸው፡፡ ለዚህም ማሳያ ይሆነናል ብለው በማሰብ በቅዱሳት መጻሕፍት ያሉትን አንዳንድ ጥቅሶች የግድ ጎትተውና ጠምዝዘው እነርሱ ለሚሉት ደጋፊና ምስክር አድርገው ለማቅረብ ብርቱ ጥረት አድርገዋል፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን እንመልከት፡-

- "በ1ኛ ቆሮ 13፡2ን በእውዱ መሠረት ለመተርጎም ብንሞክር ቅዱሳን በሞት ወደዚያኛው ዓለም ሲሸጋገሩ ሁሉን ዐዋቂ ይሆናሉ ከሚል መደምደሚያ ላይ አያደርሰንም፡፡ ጥቅሱ የሚያስረዳው አሁን ያለው እውቀት ውሱን እና ከፊል መሆኑን ነው፡፡ በዚያ ጊዜ ደግሞ ከከፊል እውቀት ወጥተን እኛ ራሳችን በእግዚአብሐር መታወቃችንን ዛሬ በእምነት ከተቀበልነው በላይና ፍጹም በሆነ እውቀት እናረጋግጣለን ማለት ነው፡፡ . . . 'በዚያን ጊዜ' የሚለው ወደፊት የሚመጣን አንድን ጊዜ የሚጠቁመው ሐረግ የሚያመለክተው ከሞት በኋላ ያለውን ጊዜ ሳይሆን ከጌታ ዳግም ምጽአት በኋላ ያለውን ዘመን ነው፡፡ ስለዚህ በዐጸደ ነፍስ ሆኖ በዚህ ምድር ያለውን ስለ ማወቅ ነው ብሎ ማሰብ፣ መጻፍና መናገር የወዲያኛውን ዓለም ክብርና ታላቅነት ዝቅ አድርጎ መመልከት ይሆናል፡፡ ቅዱሳን በዐጸደ ነፍስ ሆነው በዚህ ምድር ላይ የሚሆነውንና አንዳንዶቹም በዐጸደ ሥጋ ሳሉ እግዚአብሔር ገልጾላቸው ያወቁትን ደግመው ያውቃሉ ማለት፣ ቅዱሳን በሰማይ ከቀድሞው የተለየ ሕይወትም ሆነ እውቀት የላቸውም እንደ ማለት ይቆጠራል፡፡ (ጮራ ቁ. 38፣ ገጽ 17)

- "በሉቃስ 16 ከቁጥር 19 ጀምሮ የተገለጸውን ታሪክ ግርነት የማያደርጉትን ባለ ጠጎች ለመውቀስና ለማስተማር <u>ምሳሌ ሆኖ የቀረበ እንጂ በትክክል የተፈጸመ ታሪክ ነው ለማለት አይቻልም</u>። . . . <u>ታሪካዊ መሠረት የሌለውና ለማስተማር የቀረበ ነው</u>። ይሁንና እነርሱ በሚሉት ትርጉም መሠረት ብንሄድ አብርሃም በዐጸደ ነፍስ ሆኖ በምድር ላይ የተደረገውንና ከእርሱ ማንቀላፋት በኋላ የተነሡትን ያውቀው በዐጸደ ነፍስ ስላለ ሳይሆን እግዚአብሔር እንዲያውቅ ስላደረገው ነው ማለት እንችል ይሆናል፡፡ እንዲህ ያለውን ከአንድ ሰው እውቀት ውጭ የሆነውንና የተሰወረውን ነገር መግለጥ የእግዚአብሔር ሥራ ነው እንጂ የሰው ነፍስ በራሷ ልትደርስበት የምትችለው እውቀት አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ግን አብርሃም በዐጸደ ነፍስ ሳለ ከእርሱ በኋላ የመጡትን ዘሮቹን እስራኤላውያንን እንደማያውቃቸው ተጽፏልና (ኢሳ. 63፥16) አብርሃም በዐጸደ ነፍስ ባለበት ሁኔታ በምድር የሚደረገውን ሁሉ ያውቃል ማለት የሚታመን ቀርቶ የማይመስል ነው፡፡" (ሙራ ቁ. 38 ገጽ 17)

- "ጌታችን ስለ አብርሃም ሲናገር አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤትን አደረገ፤ አየም፤ ደስም አለው ብሏል፡፡ (ዮሐ. 8፥56) ጌታችን በተወለደ ጊዜ አብርሃም በአካለ ሥጋ አልነበረም፤ ታዲያ እንዴት አድርጎ አይቶ ደስ አለው? በዐጸደ ነፍስ ሆኖ ስላወቀ ነው እንጂ ስለ ተባለው፦ ጌታ ስለ አብርሃም የተናገረው ይህ ቃል አብርሃም ከሞተ በኋላ በዐጸደ ነፍስ ሳለ የተከናወነና ከጌታ ልደት ጋር የተያያዘ ስለ መሆኑ የሚጠቁም ፍንጭ በጥቅሱ ውስጥ ፈጽሞ አይገኝም፡፡ . . . ከዚህ ይልቅ ጥቅሱ አብርሃም ከሞተ በኋላ ሳይሆን በዐጸደ ሥጋ ሳለ የተከናወነን ድርጊት የሚገልጽ መሆኑን በቃሉ መሠረት ማስረዳት ይቀላል፡፡" (ሙራ ቁ. 38 ገጽ 17)

እነዚህ አባባሎቻቸው ከዚህ ቀጥሎ እንደምንመለከተው በመጽሐፍ ቅዱስ እና በአበው ትምህርት መሠረትና ድጋፍ የሌላቸው የራሳቸው ግምቶችና የፈጠራ አባባሎች ናቸው፡፡ ይህን ለመረዳትም በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ስለ ሰጠው ጸጋ ወሰንና ዳርቻ በማየት እንጀምር፡፡

ወደዚያ ከመሄዳችን በፊት ግን ከላይ ከጠቀስናቸው ትምህርቶቻቸው መካከል ጎላ ጎላ ያሉት አሳዛኝም አስቂኝም የሆኑትን በአጭሩ ዳስሰናቸው እንለፍ፡፡

(1) "ቅዱሳን በሞት ወደዚያኛው ዓለም ሲሸጋገሩ ሁሉን ዐዋቂ ይሆናሉ ከሚል መደምደሚያ ላይ አያደርሰንም፡፡ . . . አብርሃም በዐጸደ ነፍስ ባለበት ሁኔታ በምድር የሚደረገውን ሁሉ ያውቃል ማለት የሚታመን ቀርቶ የማይመስል ነው" የሚሉ ነገሮችን እንደ አዲስ ግኝት አቅርበዋል፡፡ ሲጀመር ማን እንዲህ አለ? የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያረፉ ቅዱሳን ሁሉን አዋቂ ይሆናሉ ብላ አታስተምርም፡፡ ሁሉን አዋቂ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የምትለው ቅዱሳን ከዐረፍታቸው በኋላ እውቀታቸው አይጠፋም፤ ጸጋና እውቀት እየተጨመረላቸው ይሄዳል ነው፡፡ እንዲሁም በዚህ ዓለም ስለሚሆነው ነገር አንዳች አያውቁም የሚሉት የፕሮቴስታንቶች ትምህርት ስህተት ነው ትላለች እንጂ ሁሉን አዋቂ ይሆናሉ አትልም፤ ብላም አታውቅም፡፡ ይህ ከላይም በተደጋጋሚ እንዳየነው በሐሰት የመወንጀል አካሄድ፤ የውሸት ክስ ነው፡፡

(2) ሌላው ደግሞ የ1ኛ ቆሮ 13፥2 ትክክለኛው ትርጓሜ ነው ብለው የገለጹት እንዲህ ብለው ነው፦ "በዚያ ጊዜ ደግሞ ከከፊል እውቀት ወጥተን እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር መታወቃችንን ዛሬ በእምነት ከተቀበልነው በላይና ፍጹም በሆነ እውቀት እናረጋግጣለን ማለት ነው፡፡" እኛ በእግዚአብሔር የመታወቃችንን ነገር ከመሞታችን በፊት አሁን በዚህ ዓለም እያለንም ቢሆን የማያጠራጥር እውነት መሆኑን አያምኑም ማለት ነው? በእግዚአብሔር መታወቃችንን በሚገባ እናምናለን፤ እናውቃለንም፡፡ ስለዚህ ይህን ለማወቅ የግድ መሞት አያስፈልግም፡፡ ራሱ ጌታችን "ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ያለ አባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም። የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቈጥሯል" በማለት እስከ ምን ድረስ እንደሚያውቀን አስተምሮናልና ይህን የጌታን ቃል በእምነት ለተቀበለ ሰው እንዲህ ያለውን እውቀት ለማግኘት እስከሚሞት ድረስ መጠበቅ የለበትም። ማቴ. 10፥29-30 እንዲሁም "እኛን

በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖቹ ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ፣ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለምና" ተብሎ በግልጽ የተነገረ ነገር ነውና፤ ዕብ. 4:13 አሁን ያለን የእውቀት ውሱንነትና በኋላ ሙሉ የሚሆነው እኛ በእግዚአብሔር መታወቃችን ስለመሆኑ ነው ያሉት አተረጓጎም የእግዚአብሔር ቃል የማይለውን እነርሱ ግን የራሳቸውን ሃሳብ በግድ ጫኑበት፡፡[110] በእውነት እግዚአብሔር ሁለንተናውን እንደሚያውቀው የማያምን ሰው ካለ ከሃዲ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡

(3) "ቅዱሳን በዐጸደ ነፍስ ሆነው በዚህ ምድር ላይ የሚሆነውንና አንዳንዶቹም በዐጸደ ሥጋ ሳሉ እግዚአብሔር ገልጾላቸው ያወቁትን ደግመው ያውቃሉ ማለት፣ ቅዱሳን በሰማይ ከቀድሞው የተለየ ሕይወትም ሆነ እውቀት የላቸውም <u>እንደ ማለት ይቆጠራል</u>" የሚለው አባባል ደግሞ ምንም የማይገናኝ አባባልና ትርጉም የለሽ ዐረፍተ ነገር ነው፡፡ ይህ "እንደ ማለት ይቆጠራል" የሚለው ግምታዊ አካሄድ የተሐድሶዎች የተለመደ አካሄድ ነው እንጂ ምንም ጭብጥ የለውም፡፡ ቅዱሳን በዚህ ዓለም ስላለውም ሆነ ከዚያ ውጭ ስላለው ነገር እርሱ ባወቀ የሚገልጥላቸውን ነገር ያውቃሉ ማለት በዚህ ዓለም ሳሉ ከነበራቸው እውቀትም ሆነ ሕይወት የተለየ የላቸውም የሚያሰኝ አንዳችም ነገር የለውም፡፡ የማይገናኝ ነገር ነው፡፡ ከታች በክፍሉ እንደምናየው ከዕረፍታቸው በኋላ በዚህ ዓለም ስለተፈጸሙ ነገሮች ያወቁ ብዙዎች አሉ፡፡ ያ ማለት ግን በዚህ ዓለም ያለውን ነገር ስለገለጠላቸው በዚህ ዓለም ሳሉ ከነበራቸው ሕይወትም ሆነ እውቀት የተለየ ነገር የላቸውም ወደሚል ድምዳሜ የሚወስድ አንዳችም ገር የለም፡፡

(4) "እንዲህ ያለውን ከአንድ ሰው እውቀት ውጭ የሆነውንና የተሰወረውን ነገር መግለጥ የእግዚአብሔር ሥራ ነው እንጂ የሰው ነፍስ በራሷ ልትደርስበት የምትችለው እውቀት አይደለም" ያሉት ደግሞ ሌላው ነው፡፡ ይህም ቅዱሳን ከዕረፍታቸው በኋላ ያውቃሉ ማለትን ነፍስ እግዚአብሔር ሳይገልጥላት በራሷ ኃይል ወይም ፈቃድ ታውቃለች ማለት አስመስለው አቅርበዋል፡፡ ይህም ስህተት ነው፡፡ የባሕርይ እውቀት ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ከዚያ ውጭ ግን ነፍስም ሆነች መላእክት የሚያውቁት እውቀት ከእግዚአብሔር በጸጋ የተሰጣቸውን ያህል ብቻ ነው፡፡ ይህን ከታች በ6.2.2 እንመለከተዋለን፡፡

(5) ሌላው ስህተታቸው ደግሞ "በሉቃስ 16 ከቁጥር 19 ጀምሮ የተገለጸው ታሪክ ቸርነት የማያደርጉትን ባለ ጠጎች ለመውቀስና ለማስተማር <u>ምሳሌ ሆኖ የቀረበ እንጂ በትክክል የተፈጸመ ታሪክ ነው ለማለት አይቻልም</u>፡፡ . . . <u>ታሪካዊ መሠረት የሌለውና ለማስተማር የቀረበ ነው</u>" ያሉት ነው፡፡ ይህ የራሳቸው የፈጠራ ትምህርት ነው እንጂ በሉቃስ ወንጌል ላይ የምናገኘው የባለ ጸጋውና የአልዓዛር ታሪክ ምሳሌ ሳይሆን እውነተኛ የሆነና የተፈጸመ ታሪክ ነው፡፡ ይህንም ከታች በክፍሉ እናየዋለን፡፡

## 6.2.2 እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው የጸጋ መጠን ወሰንና ዳርቻ

እግዚአብሔር በአጠቃላይ ለሰው ልጆች የሰጠውን ጸጋ መረዳት ቅዱሳን ሊደርሱባቸውና ግንዛብ ሊያደርጓቸው ስለሚችሏቸው ጸጋዎች፣ ሀብታትና ምሥጢራት መሠረት ነው፡፡ ምክንያቱም ቅዱሳን የደረሱበት ጸጋ አስቀድሞ ሰው ሲፈጠር ወደፊት በጊዜው ጊዜ ይደርስበት ዘንድ ያልተዘጋጀለትንና ያልተሰጠ አዲስ ነገር የፈጠሩ ሳይሆን ያን ለሰው የተሰጠውን የመሆን ክሂለ ከዊን (potential) የተጠቀሙ፤ በተግባር የገለጡም ናቸው፡፡

[110] (This is imposition, not exposition)

ለሰው ልጅ ትልቁ ጸጋው የሚመነጨውና የሚቀዳው "ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ" ካለው ልዩ አምላካዊ ዐዋጅ ነው፡፡ ዘፍ. 1፡26 ከዚህም ጋር ከራሱ ከእግዚአብሔር ለሰው የተሰጠችው ሕያዊት ነፍስ ናት፡፡ "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፣ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፣ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ" እንደ ተባለ፡፡ ዘፍ. 2፡7 እንግዲህ በእነዚህ በሁለቱ፣ ማለትም "የእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ" እና ሕያዊት የሆነች ነፍስ በመሰጠቷ ውስጥ የሰው ልጅ የክብር መነሻዎችና መድረሻዎች፣ በሂደቱም ውስጥ ያሉት ነገሮች ተመልክተዋል፡፡ ሰው እግዚአብሔርን እስከ መምሰል ድረስ ልዩ የሆነና ለሌላ ለማንም ፍጥረት ያልተሰጠ ጸጋ ተሰጥቶታል ማለት ነው፡፡

ሰው የተሰጠችው ነፍስ ሕያዊት (የማትሞት)፣ ለባዊት (አዋቂ) እና ነባቢት (ሃሳብ ያላትና ያንንም መግለጽ የምትችል) ናት፡፡ ስለዚህ የሰው አዋቂነት መነሻው ይህ ነው፡፡ ሰው በባሕርዩ (በራሱ) አዋቂም ሕያውም አይደለም፡፡ ይህ ከእግዚአብሔር በጸጋ (በስጦታ) የተሰጠው ነው፡፡ የነፍስ እውቀቷም ሕያውነቷም ከእግዚአብሔር በጸጋ የተሰጣት እንጂ የራሷ የባሕርይዋ አይደለም፡፡ ከእግዚአብሔር ውጭ ያለው ነገር በሙሉ ፍጥረት እንደ መሆኑ መጠን ሕይወቱም ሆነ እውቀቱ፣ ኃይሉም ሆነ ሌላ ማንኛውም ነገር ሁሉም የተሰጠና ሊነሣ የሚችል ነው፤ ምክንያቱም የባሕርይ ሳይሆን የተሰጠ (የጸጋ) ነውና፡፡ ሕይወት፣ እውቀት፣ ኃይል . . . የባሕርዩ የሆነ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ሰው ይህን ስጦታ እውን ማድረግና ማሳደግ፣ ወደ ተሰጠው የጸጋ ከፍታና ዳርቻ መንዝና ማደግ የሚችለው ከሰጪና ከምንጩ ከእግዚአብሔር ጋር ባለው የግንኙነት መስመር ነው ማለት ነው፡፡ ከእግዚአብሔር የተለየ ሰው ከጸጋው እየራቀ ሲሄድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖርና በመንፈስ እየቀረበ የሚሄድ ደግሞ በተሰጠው ጸጋ የበለጠ ተጠቃሚ እየሆነ ይሄዳል ማለት ነው፡፡

የመጀመሪያው ሰው አዳም የተሰጠውን ይህን የእግዚአብሔር መልክ በኃጢአት ምክንያት ቢያደበዝዘውም በዘመነ ብሉይ ኪዳንም እንኳ አንዳንድ አባቶች ራሳቸውን ከኃጢአት ለማራቅና ሰውነታቸውን ለማንጻት፣ ወደ ቅድስና ለማደግ ባደረጓቸው ጥረቶች እግዚአብሔር እርሱ ባወቀ የብሉይ ኪዳን አጠቃላይ ሁኔታ እንዳለ ሆኖ፣ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ሊያገኙ የሚችሉትን ጸጋውን አልከለከላቸውም፡፡ ለአብነትም ከአዳም ሰባተኛ የሆነው ሄኖክ ከክፋትና ከኃጢአት በመራቅ ሕይወቱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጉ እስካሁን ድረስ ከሞት ፊት ተሰውሮ እንዲቆይ አድርጎታል፡፡ "ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም፤ እግዚአብሔር ወስዶታልና" ተብሎ እንደ ተጻፈለት። ዘፍ. 5፡24 ይህንም ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ "በአቤል አፍርሆሙ ወበሄኖክ አንቅሆሙ - በአቤል አስደነገጣቸው፣ በሄኖክ ደግሞ አነቃቃቸው፣ አጽናናቸው" ብሏል፡፡ ይህም ማለት ኃጢአት በመሥራት ሞት መኖሩን አቤል ሲሞት "ሞት" ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በተግባር አሳያቸው፣ ሰዎችም ሞትን በተግባር ሲያዩት ደነገጡ፡፡ ከኃጢአት ርቀው ንጽሕ ጠብቀው እግዚአብሔርን ቢያገለግሉ ደግሞ ከሞት ፊት እስከ መሰወር ድረስ ታላቅ ጸጋ መኖሩን ሄኖክን ከገጸ ሞት በመሰወር አሳያቸው፣ ጨርሶ ተስፋ እንዳይቆርጡ አበረታታቸው ማለቱ ነው፡፡

በመቀጠልም በአባቶች በእነ ኖኅና በእነ አብርሃም፣ በእነ ይስሐቅና በእነ ያዕቆብ ከእነርሱ ጋር በመነጋገር ለሰው ያለውን የጸጋ መጠን በዐረፍተ ነገርና በተምሳሌትም ቢሆን አሳየን፡፡ ለሙሴ ደግሞ ወደ ሲና ተራራ እንዲወጣና በዚያ አርባ ቀንና ሌሊት እንዲቆይ በማድረግ ከዚያ ሲወርድ ፊቱ የጸጋ ብርሃን እንዲሳልበት አደረገ፡፡ ከዚያ በፊቱ ላይ ይታይ ከነበረው የጸጋ ብርሃን የተነሣ ሕዝበ እስራኤል ፊቱን ማየት የማይቻላቸው በመሆኑ "ተገልበብ ለነ ሙሴ - ሙሴ ሆይ፤ አባክህ ፊትህን ተሸፈንልን" ብለውት ሙሴ መላ ዘመኑን ፊቱን ሸፍኖ ይኖር ነበር፡፡ በዘመነ ነገሥት የነበሩት ታላላቆቹ ነቢያት ኤልያስና ኤልሳዕም የዚህን ጸጋ ምንነት በሕይወታቸው አይተዋል፣ ገልጠዋልም፡፡ ኤልያስ በሕይወት ዘመኑ አንድ ሙት አስነሥቷል፣ በጸሎቱ ሰማይ ዝናም እንዳይጥል ገዝቷል፣ ኋላም ጸልዮ እንዲዘንም አድርጓል፡፡ በመጨረሻም ሞትን ሳያይ በእሳት ሠረገላ ተሰውሯል፣ እስካሁንም ነፍሱና ሥጋው ሳይለያዩ በሕይወት ይኖራል፡፡ በደብረ ታቦር ከሙሴ ጋር ሲገለጡም ሁለቱም በክብር ሆነው ነበር፡፡

ነቢዩ ኤልሳዕም በሕይወቱ ሳለ እንድ ሙት፣ ከሞተ በኋላ ደግሞ በአጽሙ ሌላ ሙት አስነሥቷል፡፡ እንዲሁም እርሱ በምድረ እሥራኤል ሆኖ ከብዙ ኪሎ ሜትሮች ርቀት ላይ በምድረ ሶርያ ንጉሡ በቤተ መንግሥቱ ከጥቂት የምሥጢር ሰዎቹ ጋር ብቻ እልፍኙን ዘግቶ ይመክር የነበረውን ምክርና የሚደረገውን ነገር ይመለከትና ያውቅ ነበር፡፡ እንዲሁም ደቀ መዝሙሩ ግያዝ ንዕማን ሶርያዊን ተከትሎ ሲሄድ በመንፈስ አይቶታል፣ ያደረገውንም ሁሉ በጸጋ አውቆበታል፡፡ 2 ነገ. 6፥8-13፤ 2 ነገ. 5፥20-27 ሌሎች ነቢያትም እንዲሁ እግዚአብሔር በተለየየ መገለጥና ጸጋ ጎብኝቷቸዋል፡፡ ለነቢዩ ኢሳይያስ በዙፋኑ እንደ ተቀመጠ ንጉሥ ሆኖ ተገልጦለታል፡፡ ለነቢዩ ለሕዝቅኤል በኮቦር ወንዝ ሳለ በኪሩቤል ላይ የእግዚአብሔርን ክብር ምሳሌ አይቷል፡፡ ሕዝ. 1 እንዲሁም ወደ ቤተ መቅደስ በሚገባ ጎልማሳ ታይቶታል፡፡ ለነቢዩ ዳንኤል ደግሞ ከረጂም ተራራ ማንም ሳይፈነቅለው በወረደ ድንጋይ አምሳል ታይቶቷል፡፡ ይህን ሁሉ አጠቃልሎ ነው ሊቁ "እስመ በአንጽሖ መንፈስ ርእይዎ ነቢያት ለእግዚአብሔር ወተናጸፉ ገጸ በገጽ - ነፍስን ንጹሕ በማድረግ ነቢያት እግዚአብሔርን አዩት" በማለት የገለጸው፡፡ ያዩትም ባሕርዩን ሳይሆን እነርሱ በሚገባቸውና ሊያዩት በሚችሉበት መንገድ በተገለጠላቸው ሁኔታ ነው፤ ባሕርዩ የማይመረመርና የማይደረስበት ነውና፡፡

እንግዲህ እነዚህ ነገሮች ለሰዎች ስለ ተሰጠው አምላካዊ ጸጋ መጠን ምንነት አመልካቾች ናቸው፡፡ ሰውራሱን ለእግዚአብሔር ካስገዛና የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስነቱን ከጠበቀ በእግዚአብሔር ጸጋ ማድረግ የማይችለው ነገር እንደ ሌለ ራሱ ባለቤቱ ጌታችን "ለሚያምን ሁሉ ይቻላል" በማለት በማይታበል አምላካዊ ቃሉ አስተምሮናል፡፡ ማር. 9፥23 እንዲሁም ደቀ መዛሙርቱ ሊያወጡት ያቃታቸውን ጋኔን ካወጣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን ወደ እርሱ ቀርበው "እኛ ልናወጣው ያልቻልን ስለ ምን ነው?" ባሉት ጊዜ የሰጣቸው መልስ እንዲህ የሚል ነበር፡- "ኢየሱስም፦ ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው፤ እውነት እላችኋለሁ፣ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፣ ይህን ተራራ ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል፤ የሚሳናችሁም ነገር የለም።" ማቴ. 17፥19-20

እግዚአብሔር በእርሱ ለሚያምኑ ሰዎች የሚሰጠው ጸጋ ከዚህ እስከዚህ ተብሎ የሚገደብና የሚወሰን አይደለም፡፡ ለእብነትም ደመና ጠቅሰው ካሰቡት ቦታ ወዲያውኑ መድረስ የሚችሉ አሉ፡፡ ይህ ማለት ወደ አንድ ቦታ እንሂድ ብለው ባሰቡ ጊዜ ወዲየውኑ ደመና ጠቅሰው በዚያ ተጭነው ካሰቡት ይደርሳሉ፡፡ ነቢዩ ኤልያስን የእሳት ሠረገላ መጥቶ ከወሰደው በኋላ የነቢያት ልጆች ኤልሳዕን "የእግዚአብሔር መንፈስ አንሥቶ ወደ አንድ ተራራ ወይም ወደ አንድ ሸለቆ ጥሎት እንደ ሆነ ሄደው ጌታህን ይፈልጉት ዘንድ እንለምንሃለን" ያሉት ኤልያስ በዚህ ዓለም ሳለ በደመና እየተጫነ ከአንዱ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ ይሄድ ስለነበረ ነው፡፡ 2 ነገ. 2፥16 ነቢዩ ኤልያስ ለአብድዩ ተገልጦ "ሄደህ ለጌታህ ኤልያስ ተገኝቷል በል" ሲለው አብድዩ ግን "አሁንም እነሆ፡- ሂድ ኤልያስ ተገኘ ብለህ ለጌታህ ንገር ትለኛለህ፡፡ እኔም ከአንተ ጥቂት ራቅ ስል የእግዚአብሔር መንፈስ አንሥቶ ወደማላውቀው ስፍራ ይወስድሃል፣ እኔም ገብቼ ለአክዓብ ስናገር ባያገኝህ ይገድለኛል" አለ፡፡ ይህም ከላይ የሚያስረዳው እንደ የተገለጸው ኤልያስ ከአንዱ ስፍራ ወደ ሌላው ስፍራ በመንፈስ እግዚአብሔር ይነጠቅና ይሄድ የነበረ መሆኑን ነው፡፡ 1 ነገ. 18፥7-12 ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ያስተምረውና ያጠምቀው ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ የተላከው ቅዱስ ፊልጶስም ተልእኮውን ከፈጸመ በኋላ "የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው" ይላል፡፡ በጋዛ የነበረው ፊልጶስ በመንፈስ እግዚአብሔር ተነጥቆ ወዲያውኑ በአዛጦን ተገኘ፡፡ የሐዋ. 8፥26፤ 39-40 ስለሆነም ቅዱሳን የእግዚአብሔር ባለሟሎች በደመና መንኮራኩርነት፣ በእሳት ሠረገላነት ወዘተ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ይጓጓዛሉ፣ ካሰቡት ቦታ ወዲየውኑ ይደርሳሉ፡፡ ይህን የመሰሉ ታሪኮችን በቅዱሳን ገድሎች እናገኛለን፡፡

እንዲሁም የእግዚአብሔር ባለሟሎች የሆኑ ቅዱሳን በጥላቸውና በልብሳቸው ዘርፍ ሳይቀር ተአምር የማድረግ ጸጋ ሁሉ ይሰጣቸዋል፡፡ ቅዱሳን ከክርስቶስ ጋር ከመዋሐዳቸው የተነሣ መላ ሰውነታቸውና ሁለንተናቸው የእግዚአብሔር አካል ስለሚሆን ጥላቸውና የልብሳቸው ዘርፍ ሳይቀር ተአምር ይሠራል፡፡ የቅዱስ ጴጥሮስ በሚያልፍበት ቦታ ጥላው፣ የቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ የልብሱ ቁራጭ አስደናቂ ተአምር ያደርግ እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡

ስለዚህ ጴጥሮስ ሲያልፍ ጥላው ቢሆን ከእነርሱ አንዱን ይጋርድ ዘንድ ድውያንን ወደ አደባባይ አውጥተው በአልጋና በቃሬዛ ያኖሯቸው ነበር፡፡ ደግሞም በኢየሩሳሌም ዙሪያ ካሉችው ከተማ ድውያንንና በርኩሳን መናፍስት የተሠቃዩትን እያመጡ ብዙ ሰዎች ይሰበሰቡ ነበር፤ ሁሉም ይፈወሱ ነበር፡፡ የሐዋ. 5፡15-16

እንዲሁም "እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ የሚያስገርም ተአምራት ያደርግ ነበር፡፡ ስለዚህም ከአካሉ ጨርቅ ወይም ልብስ ወደ ድውዮች ይወስዱ ነበር፤ ደዌያቸውም ይለቃቸው ነበር፤ ክፉዎች መናፍስትም ይወጡ ነበር" ይላል፡፡ የሐዋ. 19፡11-12

ከዚህም በላይ ረቂቅ የሆነውንና በሌላው ሰው ልብ ውስጥ ያለውን ነገርና ሃሳብ ማወቅ እስከ መቻል የደረሰ ጸጋ ይሰጣቸዋል፡፡ በሰው ውስጥ ያለውን ሃሳብ የሚያውቀው ራሱ ባለቤቱ (ሰውዬው) እና እግዚአብሔር ብቻ ናቸው፡፡ ሰይጣን እንኳ ይህን ማወቅ አይችልም፡፡ "በሰው ልቡና ያለውን የሚያውቅ ሰው ማነው? በእርሱ ያለችው መንፈሱ ናት እንጂ" እንደ ተባለ፡፡ 1 ቆሮ. 2፡11 እግዚአብሔር ልብ ያሰበውንና ኩላሊት ያጤሰውን የሚያውቅ በባሕርዩ ሁሉን አዋቂ ነው፡፡ ቅዱሳንም የተሰወረውን የሚያውቅ አምላካቸው በሚሰጣቸው የጸጋ እውቀት በሌላው ሰው ልብ ውስጥ ያለውን ሃሳብ ሊያውቁ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌም መጥምቁ ዮሐንስ ሕዝቡን በክርስቶስ ለማመን በሚያዘጋጅ ጥምቀት እያጠመቀና እያስተማረ በነበረበት ጊዜ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን አልባሌ መስለው ተራ ልብስ ለብሰው ከሕዝቡ ጋር ተቀላቅለውና ራሳቸውን ሰውረው ወደ ጥምቀቱ መጡ፡፡ መጥመቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ግን ባያቸው ጊዜ ማንም ነጋሪ ሳያስፈልገውና ከሕዝቡ ጋር ተመሳስለው መምጣታቸው ሳያሳስተው ለይቶ አወቃቸው፤ እንዲህም አላቸው፡- ". . . እናንተ የእፉኝት ልጆች፤ ከሚመጣው ቍጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ?" ማቴ. 3፡7 ዮሐንስ መጥምቅ በጸጋ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ተቀላቅለው ራሳቸውን ሰውረው የመጡትን ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ማንነታቸውን ለይቶ ስውር ሥራቸውን አውቆ ሳለፈው ከገሠጻቸው በኋላ ለሚመጣው እንዲጠበቁ መከራቸው፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም ሐናንያና ሰጲራ የተባሉት ባልና ሚስቶች ንብረታቸውን ሁሉ ከሸጡ በኋላ ከፍለው በማስቀረት ከማኅበረ ሐዋርያት ለመግባት በመጡ ጊዜ መዋሸታቸውንና ከፍለው ማስቀረታቸውን አውቆባቸዋል፡፡ "ጴጥሮስም፡- ሐናንያ ሆይ፤ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ? ... እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም አለው፡፡ ሐናንያም ይህን ቃል ሰምቶ ወደቀ፤ ሞተም"፡፡ የሐዋ. 5፡1-11 ቅዱሳንን መዋሸት ሰውን ሳይሆን በእነርሱ አድሮ ያለ መንፈስ ቅዱስን መዋሸት ነው፡፡ ሐናንያና ሰጲራ ሲማከሩና ከሽያጩ ገንዘብ ሲደብቁ ቅዱስ ጴጥሮስ በአካል አብሯቸው አልነበረም፤ ሌላ የነገረው ሰውም አልነበረም፡፡ ባልና ሚስቱም ምክራቸውን ከእነርሱ ውጭ ለማንም አልተናገሩም ነበር፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ስለ ገለጠለት ቅዱስ ጴጥሮስ የሆነውን ሁሉ አወቀ፡፡ ቅዱሳን ያውቃሉ ስንል ይህ እውቀታቸው ከራሳቸው ከባሕርያቸው ነው አንልም፤ ብለንም እናውቅም፤ እግዚአብሔር በሚሰጣቸው ጸጋ ያውቃሉ እንላለን እንጂ፡፡ በባሕርዩ አዋቂ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ይህ የታወቀ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ነው፡፡

በእምነትና በቅድስና ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖሩ ሰዎች የሚኖሩት ሕይወት የራሳቸው መሆኑ እየቀረ በእነርሱ የሚኖረው እግዚአብሔር እየሆነ ይሄዳል፡፡ የእነርሱ ሕይወት በኢየሱስ ክርስቶስ እየተሰወረ እንደ ብሩህና ንጹሕ መስተዋት የሚያሳዩት ራሳቸውን ሳይሆን እግዚአብሔርን እየሆነ ይሄዳል፡፡ ይህም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት የገለጸው የሕይወት ደረጃ ነው፡- "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።" ገላ. 2፡20 ወደዚህ ደረጃ ሲደርሱ "ተመስሉ ኪያየ በከመ አነ እትሜሰሎ ለክርስቶስ - እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እናንተም እኔን ምሰሉ" ከማለት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ፡፡ 1 ቆሮ. 11፡1 እነርሱነታቸው በክርስቶስ እየተሰወረ በውስጣቸው ያለው ክርስቶስ እየተገለጠ ይሄዳልና እነርሱን ስናይ የምናየው ክርስቶስን ይሆናል፡፡

እግዚአብሔር እርሱን ለሚያምኑትና ለተከተሉት ፍጹም ቸር ነው፡፡ ዳዊትም የእግዚአብሔርን ፍጹም ደግነትና ቸርነት እንዲህ ሲል ያደንቃል፦ "ጥቀ ኄር እግዚአብሔር ለእስራኤል ለርቱዓነ ልብ - ልባቸው ለቀና ለእስራኤል እግዚአብሔር እንዴት ቸር ነው?" ይላል፡፡ እግዚአብሔር ብቁ ሰውነት ካገኘ ወሰን የሌለው ጸጋውን ያጎናጽፋል፡፡ ዮሐንስ ወንጌላዊ ይህን ሲያስረዳ "እስመ አኮ በመስፈርት ዘይሁብ እግዚአብሔር መንፈሶ - እግዚአብሔር ጸጋውንና ሀብቱን የሚሰጠው በመስፈሪያ (ለክቶ) አይደለምና" ይላል፡፡ ዮሐ. 3፡34 ከቸርነቱ የተነሣም እግዚአብሔር ለወዳጆቹ የሚሰጣቸው ጸጋ በቁጥርና በስፍር ሊወሰን የማይችል ነው፡፡

## 6.2.3 ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ ስለሚኖራቸው ዕዋቂነት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

በዚህ ጉዳይ ላይ ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ትምህርት ከመግባታችን በፊት በመጀመሪያ ተሐድሶዎች ስለዚህ ጉዳይ የሚሉትን በመጥቀስ እንጀምር፡፡

- "የእግዚአብሔርን ቃል ለተሳሳተ አመለካከታቸው መሸፈኛነት መጥቀስ የለመዱት ወገኖች <u>ፍጡራንን ከፈጣሪ ጋር ለማስተካከል</u> ብዙ ጊዜ የሚጠቅሱት ይህን ክፍል (1 ቆሮ. 12፡13ን) ሲሆን በዚህ ጥቅስ ሽፋንነት የሚሰበከው ትምህርት ቅዱሳን በአፀደ ሥጋ ሳሉ እውቀታቸው ውሱን እንደሆነና በአፀደ ነፍስ ግን እንደ ፈጣሪያቸው በሰማይ ሆነው በምድር የሚደረገውን እያንዳንዱን ነገር ያውቃሉ የሚል ነው፡፡" (የተቀበረ መክሊት፡ ገጽ 161)
- "ለዚህ ማስረጃነት የሚያቀርቡት በሉቃ. 16፡19-31 በተጻፈው ታሪክ ውስጥ ባለጠጋው ሰው በሕይወተ ሥጋ ያሉት ዘመዶቹ እርሱ ወዳለበት ስቃይ ቦታ እንዳይመጡ በማሰብ አልዓዛርን እንዲልክና እንዲመሰክርላቸው አብርሃም በለመነው ጊዜ የሰጠውን ምላሽ ነው፡፡ . . . ስለሆነም አብርሃም የሞተው አስቀድሞ ነውና ከብዙ ዘመናት በኋላ የተነሡትን ሙሴንና ነቢያትን (የሙሴንና የነቢያትን መጻሕፍት) እንዴት ሊያውቃቸው ቻለ? <u>ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ በምድር ላይ የሚሠራውን ሁሉ አንድ በአንድ ስለሚያውቁ አይደለምን? ይላሉ</u>" (የተቀበረ መክሊት፤ ገጽ 161)
- "ስለዚህ ቅዱሳንም ተፈጥሯዊ ባሕርያቸው ከሚፈቅደው በላይ ያለውንና ለእነርሱ ሰውር የሆነውን ነገር የሚያውቁት እግዚአብሔር ሲገልጥላቸው ብቻ ነው፤ ከዚህ በቀር በአፀደ ነፍስም ቢሆን ሁሉን ማወቅን የራሳቸው ሊያደርጉ አይችሉም፤ ይወቁም ቢባል ባሕርያዊ ውሱንነታቸው ይወስናቸዋል፤ ተራራ፤ ገደል፤ የአገር ርቀት ... ይከለክላቸዋልና አይችሉም፡፡ እንግዲህ ሙሴንና ነቢያትን በአፀደ ነፍስ ሳለ ማወቁ በዚህ መንገድ ስለተገለጸለት ብቻ እንጂ እንደ እግዚአብሔር በምድር የምትሠራዋን ሁሉ አንድ በአንድ ልቅም አድርጎ ስለሚያውቅ ነው ተብሎ በተሳሳተ መንገድ መወሰድ የለበትም፡፡ ምክንያቱም በሌላው ስፍራ በአፀደ ነፍስ ባለበት ሁኔታ አብርሃም የማያውቀው ነገርም እንዳለ ተጽፏልና (ኢሳ. 63፡16)" (የተቀበረ መክሊት፤ ገጽ 166)

እነዚህ አባባሎቻቸው እንደ ተለመደው በሐሰትና አርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የማትለውን እንደምትል አስመስሎ በማቅረብ ለመከራከር የቀረቡ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ "የእግዚአብሔርን ቃል ለተሳሳተ አመለካከታቸው መሸፈኛነት መጥቀስ የለመዱት ወገኖች <u>ፍጡራንን ከፈጣሪ ጋር ለማስተካከል</u>" የሚለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፍጡራንን ከፈጣሪ ጋር አታስተካክልምና እንዲያው ለማደናገሪያ የቀረበ ባዶ ክስ ነው፡፡ ሰውን በሚለው መከራከር ሲያቅት የማይለውን ግድ በል ወይም ትላለህ በማለት ልከራከር ማለት ነውር ነው፤ ያስነውራልም፡፡ ቅዱሳን እግዚአብሔር በሰጣቸው የጸጋ እውቀት ያውቃሉ ማለት ፍጡራንን ከፈጣሪ ጋር ማስተካከል የሚሆነው እንዴት ብሎ ነው? እንዲያው ስለ ቅዱሳን የሆነ ነገር በተባለ ቁጥር ምን እንደሚያስደነግጣቸውና አእምሯቸውን እንደሚያስታቸው ይገርማል! እግዚአብሔር ለቅዱሳን እርሱ ባወቀ የወደደውንና የሚጠቅማቸውን ያህል የጸጋ እውቀት ቢሰጣቸው የእርሱ ለጋስነትና ቸርነት ይገለጣል፤ ይመሰገናልም እንጂ ከእርሱ ጋር መስተካከል የሚሆነው በምን ሂሳብ ይሆን?

በዚያው ላይ ደግሞ "... ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ በምድር ላይ የሚሠራውን ሁሉ አንድ በአንድ ስለሚያውቁ አይደለምን? ይላሉ" ማለት በእውነቱ የሚገርም ነገር ነው፡፡ ቅዱሳን እውቀታቸው የባሕርያቸው ሳይሆን የጸጋ እንደ መሆኑ መጠን እግዚአብሔር በሚሰጣቸው ጸጋ መሠረት እርሱ የገለጠላቸውን ያህል ሊያውቁ ይችላሉ እንላለን እንጂ "ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ በምድር ላይ የሚሠራውን ሁሉ አንድ በአንድ ያውቃሉ" እንልም፡፡ በእውነቱ አባባላቸውንና አስተሳሰባቸውን በሙሉ ሲያዩት ከጤነኛ ሰው የሚወጣ ነው ለማለት በእጅጉ ይከብዳል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "በሃይማኖት ጤናሞች እንዲሆኑ በብርቱ ውቀሳቸው" ያለው እንደዚህ ላሉት በሃይማኖት ለታመሙት ወገኖች ኖሯል! ቲቶ 1፡13-14 በእውነት እግዚአብሔር ይማራቸው፡፡

የዚህ ዓለም ተጋድሏቸውን በእግዚአብሔር ቸርነት በድል ፈጽመው ያጠናቀቁና ወደ ሰማያዊ ሀገር የሄዱ ቅዱሳን ስለሚኖራቸው እውቀት ለመረዳት ከላይ በዚሁ ክፍል መግቢያ ላይ ያነሣነውን እግዚአብሔር ለሰው የሰጠውን የጸጋ መጠን ስፋትና ጥልቀት መገንዘብ ወሳኝ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው በጸጋው አዋቂ እንዲሆን እንጂ ጠቃሚ ከሆነው እውቀት እንዲለይ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር የከለከለው ክፉውን ወይም የማይጠቅመውን እውቀት ብቻ ነው፡፡ እርሱ የሚሰጠው እውቀት፣ እናውቅ ዘንድ የፈቀደልንና የሚሰጠን እውቀት ግን የመዳን እውቀት ነው፡፡ ሉቃ. 1፡77

መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር በሚገኘው መልካም እውቀት እናድግ ዘንድ ደግሞ ደጋግሞ ያስተምረናል፡፡ "ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ" ይላል፡፡ 2 ጴጥ. 3፡18 እንደዚሁም "በበጎነትም እውቀትን፣ በእውቀትም ራስን መግዛት፣ ራስንም በመግዛት መጽናትን፣ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፣ . . . ጨምሩ" ይላል፡፡ 2 ጴጥ. 1፡ 6 ቅዱስ ጳውሎስም "በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ በእግዚአብሔርም እውቀት እያደጋችሁ ... በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን" ይላል፡፡ ቆላ. 1፡10-12 የተከለከለው "ጢሞቴዎስ ሆይ፣ በውሸት እውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቅህ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ" ተብሎ በሐዋርያው የተገለጠው የማይጠቅመውና የ"ውሸት እውቀት" ነው፡፡ 1 ጢሞ. 6፡20

በመቀጠልም ተሐድሶዎች እንዲህ ያሉትን ወደ ማየት እንሂድ፡-

- "በቤተ ክርስቲያናችን ቅዱሳን በአጸደ ነፍስ ያማልዳሉ በሚለው ትምህርት ላይ አንድ ወጥ የሆነ ትምህርት እንደሌለ ይታወቃል፡፡ ከላይ የተመለከትናቸውና የዚህ አስተምህሮ ደጋፊዎች የሆኑ ብዙ ክፍሎችና ተከታዮቻቸው በአፀደ ነፍስ አሁንም በእግዚአብሔር ፊት ቆመው በማማለድ ላይ እንደሚገኙ ሲያምኑ፣ ይህን የማይቀበሉ ወገኖች ደግሞ "በአፀደ ነፍስ አያማልዱም፣ ነገር ግን የቀደመውና በሕይወተ ሥጋ ሳሉ የነበረው ልመናቸውና የተገባላቸው ቃል ኪዳን ሲያማልድ ይኖራል ማለት ነው" ይላሉ፡፡ መርሐ ጽድቅ ባሕለ ሃይማኖት የተሰኘው መጽሐፍ የመጀመሪያውን አመለካከት ውድቅ በማድረግ ሁለተኛውን ደግፎ እንዲህ ይላል፡- "ቅዱሳን ጻድቃን ያማልዳሉ ስለተባለ ግን እላይ እንጻልነው በሕይወተ ሥጋ ሳሉ እግዚአብሔርን አገልግለው የተቀበሉት ቃል ኪዳናቸው እስከ ዕለተ ምጽአት ሲያማልድ ይኖራል ማለት ነው እንጂ እንደገና በአካለ ነፍስ መውጣት፣ መውረድ፣ መስገድ፣ መጸለይ፣ መለመን አለባቸው ማለት አይደለም፡፡ . . . እንግዲህ ይህ አንድ አቋም ያልተያዘበት ትምህርት . . . ፈራሽ ይሆናል፡፡" (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 182-3)

ይህ ኢምክንያታዊ ክርክር ነው፡፡ ምክንያቱም <u>በመጀመሪያ</u> ይህ ልዩነት ተብሎ የሚጠራ አይደለም፡፡ ቁም ነገሩ ቅዱሳን ከዕረፍታቸው በኋላ ያማልዳሉ የሚለው ነገር ነው፡፡ በዚህ ላይ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ልዩነት የላቸውም፡፡ ከዚያ በመቀጠል "የሚማልዱት እንዴት ነው?" በሚለው ጉዳይ ላይ የገለጹትም ልዩነት የሌላቸውና ሃሳባቸው ተመሳሳይ የሆኑ አገላለጾች ናቸው፡፡ በተሐድሶዎቹ "የሁለቱም ወገኖች" ተብለው የተገለጹት ሃሳቦች መሠረታዊ ተቃርኖ የላቸውም፡፡የአንደኛው ያሉት "በአፀደ ነፍስ አሁንም በእግዚአብሔር ፊት ቆመው በማማለድ ላይ እንደሚገኙ ሲያምኑ"

*የተባለው ሲሆን የሁለተኛዎቹ ያሉት ደግሞ "ይህን የማይቀበሉ ወገኖች ደግሞ በአፀደ ነፍስ አያማልዱም፤ ነገር ግን የቀደመውና በሕይወተ ሥጋ ሳሉ የነበረው ልመናቸውና የተገባላቸው ቃል ኪዳን ሲያማልድ ይኖራል ማለት ነው እንጂ እንደገና በአካለ ነፍስ መውጣት፣ መውረድ፣ መስገድ፣ መጸለይ፣ መለመን አለባቸው ማለት አይደለም" ይላሉ ያሉት ነው፡፡ እነዚህ "ሁለቱም"* የተባሉት ሃሳቦች ቅዱሳን ከዕለተ ዕረፍታቸው በኋላ እንደሚያማልዱ የሚስማሙ ናቸው፡፡ ስለዚህ "ሁለት" የተለያዩ ሃሳቦች ሳይሆኑ አንድ ሃሳብ ናቸው፡፡ ከዚህም ጋር "ይህን የማይቀበሉ ወገኖች ደግሞ <u>በአፀደ ነፍስ አያማልዱም</u> ይላሉ" ብለው ተሐድሶዎቹ የገለጹት ሐሰት ነው፡፡ በዚህ ዓለም ሳሉ ያደርጉ እንደ ነበረው ለመማለድ በዓጸደ ነፍስ መውጣት መውረድ የለባቸውም ይላሉ እንጂ "<u>በአፀደ ነፍስ አያማልዱም</u>" አይሉም፡፡ ይህን የሚሉት ተሐድሶዎችና አባቶቻቸው ፕሮቴስታንቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ ይህ የራስህን ክህደት አርቶዶክሳውያ አባቶችም የሚሉት አስመስሎ ለማቅረብ የተደረገ ከንቱ ጥረት ነው፡፡ የራስን ክህደት ሌሎችም የሚሉትና የሚደግፉት አስመስሎ ማቅረብ ነውር ነው!

በዚህም ላይ የሁለተኛዎቹ የተባለውም ሆነ የመጀመሪያዎቹ የተባለው ሃሳብ ቅዱሳን ከዕረፍታቸው በኋላ በዚህ ዓለም ያደርጉት እንደ ነበረው መውጣትና መውረድ፣ መከራ መቀበልና መስገድ አለባቸው አይሉም፡፡ ስለዚህ "በቤተ ክርስቲያናችን ቅዱሳን በአጸደ ነፍስ ያማልዳሉ በሚለው ትምህርት ላይ አንድ ወጥ የሆነ ትምህርት እንደሌለ ይታወቃል" ያሉት ሐሰት ነው፡፡ አርቶዶክሳውያን ሁሉ ቅዱሳን ከዕረፍታቸው በኋላ በአፀደ ነፍስ እንደሚያማልዱ ያምናሉ፡፡ እንደዚሁም በዚህ ዓለም ሳሉ ያደርጉት እንደ ነበረው ሰጊድ፣ ውጣ ውረድ፣ ተወክፎተ መከራ ... እንደ ሊለባቸው ያምናሉ፡፡ ስለዚህ ተሐድሶዎች ያቀረቡት ሃሳብ ስህተት ነው፡፡ እንደዚሁም የማያምኑባትን ቤተ ክርስቲያን "ቤተ ክርስቲያናችን" ማለታቸው ለማስመሰልና ለማታለል ካልሆነ በስተቀር በምንም መንገድ አርቶዶክሳዊነት የሌላቸው መሆኑ እስካሁን ካየነው ግልጽ ነው፡፡

*<u>በሁለተኛ</u>* ደረጃ ደግሞ ይህ ልዩነት ነው ሊባል የሚበቃ አይደለም እንጂ ነው ቢባል እንኳ ስለ አንድ ነገር ቁርጥ ያለ እውቀት አለመኖር ማለት ያ ነገር የለም ወይም ሙሉ በሙሉ ትክክል አይደለም ማለት ሊሆን አይችልም፡፡ ለምሳሌ ሰዎች ስለ መሬት ቅርጽ ብዙ ሲወዛገቡ ኖረዋል፡፡ ለብዙ ዘመናት "ጠፍጣፋ ናት"፣ "ክብ ናት" እየተባባሉ ሲወዛገቡ ነበር፡፡ ይህ ማለት ግን መሬት የለችም ማለት አይደለም፡፡ እንደዚሁም "መሬት በፀሐይ ዙሪያ ትዞራለች" በሚለውና "ፀሐይ በመሬት ዙሪያ ትዞራለች" በሚለውም የብዙ ዘመናት ውዝግብ ነበር፡፡ ይህ ማለት ግን በዚህ ዙሪያ ላይ ሰዎች እርግጠኛውን ስለማያውቁና ስለሚወዛገቡ ይህ ውዝግብ የመጣው ፀሐይም ሆነ መሬት ስለሌሉ ነው አያሰኝም፡፡ እንዲያውም ስለ አንድ ነገር ውዝግብ መኖሩና ጥርት ያለ እርግጠኛ ነገር አለመኖሩ የሚያስረዳው ያ ነገር አለመኖሩን ሳይሆን መኖሩን ነው፡፡ ምክንያቱም ነገሩ ባይኖር ኖሮ ከጥንቱንም የውዝግቡ መነሻ አይኖርም ነበርና፡፡

እንደዚሁም ሁሉ ቅዱሳን ከዕረፍታቸው በኋላ በአጸደ ነፍስ የሚማልዱት እንዴት እንደሆነ በእርግጠኛነት አለመታወቁ ስለማያማልዱ ነው ከሚል መደምደሚያ ሊያደርስ አይችልም፡፡ ቅዱሳን ከዕረፍታቸው በኋላ እንደሚያማልዱ እንጂ እንዴት እንደሚማልዱ በእርግጠኛነት አለመታወቁም ተፈጥሯዊና አግባብ ነው፡፡ ምክንያቱም ከሞት በኋላ ስላለው ነገር በዚህ ዓለም ያለን ሰዎች በእርግጠኝነት አናውቅምና፡፡ ዛሬ የምናውቀው እውቀት በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናውቀው ያህል ነው የተባለውም ለዚህ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚያማልዱ ይነግረናል እንጂ እንዴት እንደሚያማልዱ በዝርዝር አይነግረንም፡፡ ለምሳሌ ከሞት በኋላ ሕይወት እንዳለ እናውቃለን፤ ሆኖም የዚያ ሕይወት አኗኗር በትክክል ምን እንደሚመስል አሁን በዚህ ዓለም ያለን እኛ ሙሉ በሙሉ አናውቀውም፡፡ ይህ ግን ከሞት በኋላ ሕይወት የለም አያሰኝም፤ የሚሆነው ነገር በእኛ ማወቅ አለማወቅ ላይ የተመሠረተ አይደለምና፡፡ ይህን ጉዳይ (የቅዱሳንን አማላጅነት በአጸደ ነፍስ) ከዚህ በታች በሰፊው እንመለከተዋለን፡፡

በመሆኑም እግዚአብሔር ከሚሰጠው ጸጋ አንዱ እውቀት (አዋቂነት) ነው፡፡ ይህ ጸጋም በዚህ ዓለም ይጀመርና እያደገ ይሄዳል፡፡ በዚህ ዓለም ሳሉ የሚያውቁት እውቀት በመጠኑ ነው፡፡ ያ እውቀታቸው በሂደት እያደገ ይሄዳል፣ ሆኖም በዚህ ዓለም ሕይወት ብቻ የተገደበና የተወሰነ ግን አይደለም፡፡ ይህም በመዳን ትምህርት በክፍል አንድ ላይ እንደ ተገለጸው እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ እያደገ የሚሄድ ነው፡፡ ተሐድሶዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ያለባቸው የእውቀትና የአስተሳሰብ ችግር በመዳን ትምህርት ላይ ያለባቸው ችግርና ስህተት ውጤትና ነጸብራቅ ነው፡፡ ይህም መዳንን ቁንጽል አድርገው ከእስር ቤት ከመውጣትና ከቅጣት ከማምለጥ አንጻር ብቻ ስለሚረዱት ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ይህን እንዲህ ሲል ገልጾታል፦

> ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር ነበር፣ እንደ ልጅም አስብ ነበር፣ እንደ ልጅም እቈጥር ነበር፤ ጎልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሽሬያለሁ። ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን፤ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ። 1 ቆሮ. 13፡9-12

ማንም ሰው ቢሆን በዚህ ዓለም ባለው ሕይወቱ የሚያውቀው እውቀት አንድ ሰው በሕፃንነት ዕድሜው እንደሚያውቀው ዓይነት እውቀት ነው፡፡ እውቀቱ ውስንና ተከፍሎ ያለበት ነው፡፡ አንድ ሰው ስለ አንድ ነገር በጎደሎ መረጃ ወይም እንዲሁ በምናቡ የሚሥለው ሥዕል በአእምሮው አብሮት የሚቆየው ትክክለኛ የሆነውን ነገር እስከሚያውቅ ድረስ ነው፡፡ ያን ጊዜ እውነቱ ሲገለጥ ባለማወቅ ወይም በጎደሎ እውቀት ላይ ተመሥርቶ በምናብ ተፈጥሮ የነበረው ሥዕል ይጠፋል፤ ፍጹም የሆነው እውቀት መጥቷልና ቦታውን ይለቅቃል፡፡ ይህን ነው "ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና፣ ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና፤ ፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን ተከፍሎ የነበረው ይሻራል" ያለው መምህራችን ቅዱስ ጳውሎስ፡፡ በሚመጣው ዓለም ሕይወት የሚኖረው ሕይወትና አኗኗር ግን "ዓይን ያላየችው፣ ጆሮም ያልሰማው፣ በሰው ልብም ያልታሰበው፣ እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው" ተብሎ እንደ ተገለጸው አሁን አይታወቅም፡፡ 1 ቆሮ. 2፡9

ቅዱሳን ተጋድሏቸውን ፈጽመው ከዚህ ከቁሳዊው ዓለም ወደ መንፈሳዊው ዓለም ሲሄዱ እውቀታቸውም መንፈሳዊና ከፍ ያለ እየሆነ ይሄዳል እንጂ በዚህ ዓለም ሳሉ ያውቁት ከነበረው ወደ ታች የሚወርድ አይሆንም፡፡ በዚህ ዓለም ሳሉ እንኳ በሕገ ተፈጥሮ ሊታወቅ ከሚችለው ሁኔታ ውጪና በላይ ያወቁ ቅዱሳን ነበሩ፡፡ ለምሳሌም ከላይ እንደ ተገለጸው ነቢዩ ኤልሳዕ እስራኤል ምድር ውስጥ ሆኖ እርሱ ከነበረበት ቦታ ብዙ ርቀት ላይ ባለው በሶርያ አገር፣ ያውም ንጉሡ እልፍኝ ዘግቶ የሚያደርገውን ነገር፣ የሚመክረውን ምክር ሁሉ ያውቅበት ነበር፡፡ 2 ነገ. 6፡8-12 ደቀ መዝሙሩ የነበረውን ግያዝንም በአካል አብሮት ሳይሆን፣ ነገር ግን በመንፈስ ተከትሎት ሄዶ ከንዕማን ጋር እንደ ተገናኘና ምን እንዳደረገ አውቆበታል፤ አይቶታል፡፡ 2 ነገ. 5፡20-25

ቅዱስ ጴጥሮስ ሐናንያና ሰጲራ የተባሉት ባልና ሚስት መሬታቸውን ሸጠው ሙሉ በሙሉ ለመስጠትና ከሐዋርያት የአንድነት ማኅበር ለመግባት ወስነው ሲያበቁ እንደገና ከሽያጩ ከፍለው አስቀርተው ሳለ ያን ነገራቸውን ደብቀው በፊቱ በቆሙ ጊዜ ያደረጉትን ነገር ሁሉ አውቆባቸዋል፡፡ ከላይ እንደ ተገለጸው ባልና ሚስቱ ሲማከሩ ቅዱስ ጴጥሮስ አብሯቸው አልነበረም፡፡ ታዲያ ይህን የእነርሱን ስውር ምክር ማን ነገረው? መንፈስ ቅዱስ ለቅዱስ ጴጥሮስ የተፈጸመውን ነገር ስለ ነገረው ነው፡፡ ስለዚህ የቅዱሳን እውቀታቸው የሚገኘው ከመንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በሚሰጣቸው እውቀት በሕገ ተፈጥሮ በሥጋዊ አእምሮ ሊታወቅ የማይችለውን ነገር ቦታና ጊዜ ሳይገድባቸው ይገልጥላቸዋል፤ እነርሱም ያውቃሉ፡፡

እዚህ ላይ የእውነት ለዋጮች የሆኑት ተሐድሶዎች ያሉትንና ከላይ ከጠቀስናቸው መካከል አንዱን እንመልከት፡-

- "እንዲህ ያለውን ከአንድ ሰው እውቀት ውጭ የሆነውንና የተሰወረውን ነገር መግለጥ የእግዚአብሔር ሥራ ነው እንጂ የሰው ነፍስ በራሷ ልትደርስበት የምትችለው እውቀት አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ግን አብርሃም በዐጸደ ነፍስ ሳለ ከእርሱ በኋላ የመጡትን ዘሮቹን እስራኤላውያንን እንደማያውቃቸው ተጽፏልና (ኢሳ. 63፡16) አብርሃም በዐጸደ ነፍስ ባለበት ሁኔታ በምድር የሚደረገውን ሁሉ ያውቃል ማለት የሚታመን ቀርቶ የማይመስል ነው፡፡" (ጮራ ቁ. 38፤ ገጽ 17)

ይህ ዓይነቱ የመናፍቃን አባባል ቢያንስ <u>ሦስት</u> መሠረታዊ ስህተቶችን ያሳየናል፡፡ የመጀመሪያው "እንዲህ ያለውን ከአንድ ሰው እውቀት ውጭ የሆነውንና የተሰወረውን ነገር መግለጥ የእግዚአብሔር ሥራ ነው እንጂ የሰው ነፍስ በራሷ ልትደርስበት የምትችለው እውቀት አይደለም" የሚለው አባባላቸው ነው፡፡ ጥንቱንም ቢሆን እውቀት የባሕርይ ገንዘብነቱ የእግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ የሰው ነፍስም ሆነች መላእክት በራሳቸው በባሕርያቸው እውቀት የላቸውም፡፡ ስለዚህ ነፍስ አዋቂ ናት የምንለው እግዚአብሔር በሰጣት የማወቅ ጸጋ መሠረት እንጂ በራሷ በባሕርይዋ ነው ብላ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አስተምራ አታውቅም፤ ጤና ያለው ማንም ሰውም እንዲህ አያስብም፡፡ ስለዚህ ይህን ነገር ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውና የምታምነው ሆኖ ሳለ አብርሃም በአጸደ ነፍስ ሳለ ያወቀውን ነገር ለመካድ የማይችሉበት አጣብቂኝ ውስጥ ሲገቡ እንዲህ በሚል ማምታታት ለማምለጥ መሞከር ከእውነት ጋር ድብብቆሽ መጫወት ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ሁል ጊዜም የምታስተምረው ሰው ከእግዚአብሔር በተሰጠው ጸጋ ከብዙ ክብርና እውቀት መድረስ ይችላል የሚል ነው እንጂ በራሱ ኃይል ወይም ባሕርይ አዋቂ ነው ብላ አይደለም፡፡ እነርሱ ግን እንዲህ የሆኑት የቤተ ክርስቲያኒቷን ትምህርት ሳይማሩ ጠላት በልቡናቸው ላይ የዘራው እንክርዳድ ስለ በቀለባቸውና ክፉ ፍሬ ስላፈራባቸው ነው፡፡

ሊላው <u>ሁለተኛው</u> መሠረታዊ ስህተት ደግሞ "<u>በሌላ በኩል ግን አብርሃም በዐጸደ ነፍስ ሳለ ከእርሱ በኋላ የመጡትን ዘሮቹን እስራኤላውያንን እንደማያውቃቸው ተጽፏል</u> (ኢሳ. 63፡16)" ያሉት ነው፡፡ በመጀመሪያ ማስረጃ ብለው የጠቀሱት የእግዚአብሔር ቃል ምን እንደሚል እንመልከት፡-

> <u>አብርሃም ባያውቀን፥ እስራኤልም ባይገነዘበን</u> አንተ አባታችን ነህ፤ አቤቱ፥ አንተ አባታችን ነህ፥ ስምህም ከዘላለም ታዳጊያችን ነው። ኢሳ. 63፡16

"<u>አብርሃም ባያውቀን</u>" ማለት "<u>አብርሃም አያውቀንም</u>" ማለት ነውን? በምን አገባብ ነው እንዲህ የሚሆነው? እንዲህ አድርጎ የተረጎመውስ ማን ነው?

ይህን ቃል ለመረዳት በመጽሐፍ ቅዱስ በዚህ መልኩ የተገለጹ ሌሎች ነገሮችን እንመልከት፡፡ ንጉሥ ናቡከደነፆር እርሱ ላቆመው ምስል እንሰግድም ያሉትን ሠለስቱ ደቂቅን ጠርቶ "አሁንም የመለከቱንና የእንቢልታውን የመሰንቆውንና የክራሩን የበገናውንና የዋሽንቱን የዘፈኑንም ሁሉ ድምፅ በሰማችሁ ጊዜ ተደፍታችሁ ላሠራሁት ምስል ብትሰግዱ መልካም ነው፤ ባትሰግዱ ግን በዚያ ጊዜ በሚነድድ እሳት እቶን ውስጥ ትጣላላችሁ፡፡ ከእጄስ የሚያድናችሁ አምላክ ማን ነው?" ብሎ አስፈራራቸው፡፡ እነርሱ ሲመልሱለት ደግሞ እንዲህ አሉ፡-

> ናቡከደነፆር ሆይ፥ በዚህ ነገር እንመልስልህ ዘንድ አስፈላጊያችን አይደለም። የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል፤ ከእጅህም ያድነናል፤ ንጉሥ ሆይ! ነገር ግን፥ ንጉሥ ሆይ፥ <u>እርሱ ባያድነን</u>፥ አማልክትህን እንዳናመልክ፥ ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ አሉት። ዳን. 3፡15-18

ሠለስቱ ደቂቅ *"እርሱ ባያድነን"* ማለታቸው "እግዚአብሔር አያድነንም" ማለታቸው ኖሯልን? በእነርሱ አተረጓጎም ከሄድን እነዚያን የእምነት አርበኞችና የጨለማ ዘመን ከዋክብት በእግዚአብሔር አዳኝነት የማያምኑ ሊያደርጓቸው ነውን? ይልቁንም *"እርሱ ባያድነን"* የሚለው አባባላቸው የእምነታቸውን ጽናትና ቁርጥ ውሳኔያቸውም የመጨረሻ ደረጃ የደረሰ መሆኑን የሚያመለክት ነበር፡፡ እነርሱ ራሳቸውን ለአምላካቸው አሳልፈው ለመስጠትና ወደ እሳት ውስጥ ለመጣል የቆረጡት እግዚአብሔር በእሳቱ ከመሞት በማዳኑ ወይም ባለማዳኑ ላይ ተመሥርተው ሳይሆን ለእርሱ ካላቸው ጥልቅ ፍቅርና ቀናዒነት የተነሣ ነበር፡፡ ስለዚህ ከእሳቱ ማዳንም ሆነ በእሳቱ ተቃጥለው ሞተው ለእውነት ሰማዕታት (ምስክሮች) እንዲሆኑ ማድረግ የእነርሱ ድርሻና እውቀት ሳይሆን የእግዚአብሔር ብቻ እውቀትና ውሳኔ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚያ የእምነት አርበኞች የሆኑ ሠለስቱ ደቂቅ "ከእሳቱ ቢያድነንም፣ ባያድነንም እኛ ግን ላቆምከው ምስል አንሰግድም" በማለት ለአምላካቸው ያላቸውን ቁርጥና የማያወላውል ተአማኒነት በተግባር መሰከሩ፡፡ ስለዚህ "እርሱ ባያድነን" ማለት "አያድነንም" ማለት አይደለም፡፡

እንደዚሁም ሁሉ *"አብርሃም ባያውቀን፣ እስራኤልም ባይገነዘበን አንተ አባታችን ነህ"* የሚለው ቃል አብርሃምና እስራኤል (ያዕቆብ) ሰዎች እንደ መሆናቸው ልጆቻቸውን ከማሰብና ስለ እነርሱ ከማሳሰብ ቢደክሙ እንኳ፣ እግዚአብሔር ግን የሁሉም ዘለዓለማዊ አባት፣ የማይረሳና የማይተኛ ትጉህ እረኛ ስለሆነ መቼም መች የማይረሳቸው መሆኑን የሚያስረዳ አንጻራዊ (ንጽጽራዊ) አገላለጽ እንጂ በግድ ጠምዝዘው የማይለውን ይላል ለማለት እንደ ሞከሩት እንደ መናፍቃኑ ያለ ሃሳብ የሚናገር አይደለም፡፡ አብርሃምንማ ወደፊት ጊዜያቸውን ጠብቀው የሚመጡትን ልጆቹን ሁሉ "ወደ ሰማይ ተመልከት፣ ከዋክብትንም ልትቈጥራቸው ትችል እንደ ሆነ ቍጠር አለው፤ ዘርህም እንደዚሁ ይሆናል" በማለት አስቀድሞ አሳይቶት የለምን? ዘፍ. 15፡5 እንዲሁም "ለብዙ አሕዛብም አባት ትሆናለህ። ከዛሬም ጀምሮ እንግዲህ ስምህ አብራም ተብሎ አይጠራ፣ ነገር ግን ስምህ አብርሃም ይሆናል፤ ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና። እጅግም አበዛሃለሁ፣ ሕዝብም አደርግሃለሁ፣ ነገሥታትም ከአንተ ይወጣሉ" በማለት ነግሮታል፡፡ ዘፍ. 17፡4-10 ልጆቹ ተለይተው የሚታወቁበት ምልክት ይሆነው ዘንድም ግዝረትን ሰጥቶታል፡፡

እስራኤል የተባለ ያዕቆብንም እንዲሁ ከእርሱ ስለሚወጡት ልጆቹ ነግሮታል፡፡ ያዕቆብ የነገዶች ሁሉ አባቶች ለሆኑት ለአሥራ ሁለቱ ልጆቹ ለእያንዳንዳቸው ወደፊት በየዘመናት ሁሉ ስለሚሆኑት በምርቃት ዓይነት መልኩ የነገራቸው ልጆቹን ስለማያውቃቸው ነውን? መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላልና፡- "ያዕቆብም ልጆቹን ጠርቶ እንዲህ አለ፡- በኋለኛው ዘመን የሚያገኛችሁን እንድነግራችሁ ተሰብሰቡ። እናንተ የያዕቆብ ልጆች ተሰብሰቡ፣ ስሙም፣ አባታችሁ እስራኤልንም አድምጡ። . . . " ዘፍ. 49፡1-28 ለዚህ ነበር በየዘመናቱ የተነሡት ልጆቻቸው ወደ እግዚአብሔር ሲጸልዩ "የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብም አምላክ" እያሉ እግዚአብሔርን ይጠሩትና ይጸልዩ የነበረው፡፡

ሌላው ሦስተኛው ዶጋማው የሚሉት ስህተት ደግሞ *"አብርሃም በዐጸደ ነፍስ ባለበት ሁኔታ በምድር የሚደረገውን ሁሉ ያውቃል ማለት የሚታመን ቁርቶ የማይመስል ነው"* የሚለው ነው፡፡ በምድርም ይሁን በሰማይ፣ አብርሃምም ይሁን ማንም የሚደረገውን ነገር ሁሉ የሚያውቅ ፍጡር የለም፡፡ ሁሉን ማወቅ የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘብ ብቻ እንጂ የፍጡራን ችሎታ አይደለም፡፡ ስለዚህ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ብላ አላስተማረችም፡፡ አንድን ሰው የሚለውን ሃሳብ ትቶ በማይለው ሃሳብ ለመሞገት መነሣት በሥነ አመክንዮ ካሉት ስህተቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህም ያ አካል የሚለውን ሃሳብ ለመሞገት ያለመቻል መገለጫ ነው፡፡ ሰዎችም ሆኑ መላእክት የሚያውቁት ምን ጊዜም እግዚአብሔር ያውቁ ዘንድ የገለጠላቸውን መጠንና ያህል ብቻ ነው፡፡ ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሌሎች የነገሯቸውን ብቻ እንጂ ውስጧ አለመኖራቸውንና ምን ያህል እንደማያውቋት ይህ ሁሉ ይመሰክርባቸዋል፡፡

ወደ እግዚአብሔር የሄዱ ቅዱሳን ከዚህ ዓለም ዕረፍታቸው በኋላም በዚህ ዓለም ስለሚሆነው ነገር እግዚአብሔር በገለጠላቸው መጠን እንደሚያውቁ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች እንመልከት፡፡

### ሀ) ሙሴና ኤልያስ በደብረ ታቦር

ከዚህ ዓለም ከሞተ ቅድመ ሥጋዌ አንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመታት ገደማ የሚሆነው ሙሴ እና ነፍሱና ሥጋው ሳይለያዩ ያለው ኤልያስ ሁለቱም በደብረ ታቦር ተገልጠዋል፣ ተገናኝተዋል፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ እንደሚል፡-

> ሲጸልይም የፊቱ መልክ ተለወጠ፤ ልብሱም ተብለጭልጮ ነጭ ሆነ። እነሆም ሁለት ሰዎች እነርሱም ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ይነጋገሩ ነበር፤ በክብርም ታይተው በኢየሩሳሌም ሊፈጽም ስላለው ስለ መውጣቱ ይናገሩ ነበር። ሉቃ. 9፥29-31

ይህ የእግዚአብሔር ቃል ቅዱሳን ከዕረፍታቸው በኋላ እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ መጠን ስለሚኖራቸው አዋቂነት ብዙ ነገሮችን ያስተምረናል፡፡

1) አንድ ሰው ከዚህ ዓለም ከሞተ በኋላ በዚህ ዓለም ስለሚሆነው ነገር የማያውቅ ቢሆን ኖሮ፣ ሙሴ ከሞተ ከአንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመታት በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣቱንና በሥጋዌ መገለጡን እንዴት አወቀ? ኤልያስስ ከዚህ ዓለም ከተወሰደ ከብዙ ዘመን በኋላ ጌታችን በዚህ ዓለም መወለዱን እንዴት ሊያውቅ ቻለ?

2) ሙሴና ኤልያስ ጌታችን ሰው ሆኖ እስከ ተገለጠበት እስከዚያ ጊዜ ድረስ ብቻ ሳይሆን ወደፊት ስለሚሆነው ነገርስ እንዴት ማወቅ ቻሉ? ምክንያቱም "በኢየሩሳሌም ሊፈጽም ስላለው ስለ መውጣቱ ይናገሩ ነበር" ተብሏልና፡፡ "በኢየሩሳሌም ሊፈጽመው ያለው መውጣቱ" የተባለው በዚያ (በኢየሩሳሌም) ለድኅነተ ዓለም የሚፈጽመው ስቅለቱና ሞቱ፣ እንዲሁም ትንሣኤው ነውና፡፡ ሙሴና ኤልያስ እስከዚያ (በደብረ ታቦር እስከ ተገለጠበት) ጊዜ ድረስ ብቻ የሆነውን - ሰው መሆኑንና በዚህ ዓለም መገለጡን (ኃላፍያትን) - ብቻ ሳይሆን ገና ወደፊት የሚሆነውን (መጻእያትን) (ስቅለቱንና ትንሣኤውን) እንዴት ማወቅ ቻሉ?

እንግዲህ በዓጸደ ነፍስ ያሉ ቅዱሳንም ሆኑ በአጠቃላይ ከእኛ ጋር በሥጋ አብረውን የማይኖሩ ቅዱሳን የቦታና የጊዜ ውስንነት ሳይገድባቸው እግዚአብሔር በሚገልጥላቸው መጠን በዚህ ዓለም ስለ ሆኑትና ወደፊትም ስለሚሆኑት ነገሮች የሚያውቁ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ አድርጎ በግልጽ ነግሮናል፡፡

### ለ) አብርሃም፣ ባለ ጸጋውና አልዓዛር

ይህን በተመለከተ ጌታችን የተናገረው ቅዱስ ቃሉ እንዲህ ይላል፡-

> ቀይ ልብስና ቀጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበረ፤ ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር። አልዓዛርም የሚባል አንድ ድሀ በቍስል ተወርሶ በደጁ ተኝቶ ነበር፤ ከባለ ጠጋውም ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር፤ ውሾች እንኳ መጥተው ቍስሎቹን ይልሱ ነበር። ድሀውም ሞተ፤ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት፤ ባለ ጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ። በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ፤ አልዓዛርንም በእቅፉ። እርሱም እየጮኸ፡- አብርሃም አባት ሆይ፣ ማረኝ፣ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ ምላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ።

አብርሃም ግን፦ ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ፥ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል፥ አንተም ትሣቀያለህ። ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጓል አለ። እርሱም፦ እንኪያስ አባት ሆይ፥ ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ፤ አምስት ወንድሞች አሉኝና፤ እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸው፡፡ አብርሃም ግን፦ ሙሴና ነቢያት አሏቸው፤ እነርሱን ይስሙ አለው። እርሱም፥ አይደለም፥ አብርሃም አባት ሆይ፥ ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው ንስሐ ይገባሉ አለ። ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ ከሙታንም አንዱ እንድ ቢነሣ አያምኑም አለው። ሉቃ. 16፡19-31

ይህ የእግዚአብሔር ቃል ብዙ መሠረታዊ እውነታዎችን ይገልጥልናል፡፡ በመጀመሪያ ይህ የጌታችን ትምህርት የሆነ (የተፈጸመ) ታሪክ ነው እንጂ ምሳሌ አይደለም፡፡ ምክንያቱም አብርሃም በእውነት በምድራችን ላይ የነበረ ሰው እንጂ ያልነበረ (ምናባዊ) ሰው አልነበረም፡፡ ባለ ጸጋውም እንዲሁ በምድራችን ላይ በአንድ ወቅት የኖረና የነበረ ሰው ነበር፡፡ እንዲሁም ድሀው አልዓዛር በስሙ ተጠቅሷል፡፡ አልዓዛር ከሞተም በኋላ አብርሃም "ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ፥ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ" በማለት ባለ ጸጋ የነበረውም ሰው፥ ድሀው አልዓዛርም በምድራችን ላይ በአንድ ወቅት ዘመን ገጠም ሆነው የኖሩ ሰዎች መሆናቸውን ይመሰክራል፡፡

ከዚህም ጋር ባለጸጋው "እንኪያስ አባት ሆይ፥ ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ፤ አምስት ወንድሞች አሉኝና፤ እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸው፡፡ አብርሃም ግን፦ ሙሴና ነቢያት አሏቸው፤ እነርሱን ይስሙ አለው፡፡ እርሱም፦ አይደለም፥ አብርሃም አባት ሆይ፥ ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው ንስሐ ይገባሉ አለ። ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ ከሙታንም አንዱ እንድ ቢነሣ አያምኑም አለው" የሚሉት ነገሮች ሁሉ ስለ እውነተኛ ታሪክ የተነገረ ስለ መሆኑ ከበቂ በላይ አስረጂዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ተሐድሶዎች "በሉቃስ 16 ከቁጥር 19 ጀምሮ የተገለጸውን ታሪክ ቸርነት የማያደርጉትን ባለ ጠጎች ለመውቀስና ለማስተማር <u>ምሳሌ ሆኖ የቀረበ እንጂ በትክክል የተፈጸመ ታሪክ ነው ለማለት አይቻልም</u>፡፡ . . . <u>*ታሪካዊ መሠረት የሌለውና ለማስተማር የቀረበ ነው*</u>" ያሉት ሃሳብ እንዲህ በቃሉ መሠረት ሲመዘን ቀልሎ ይገኛል፤ ስሁትነቱም ግልጥ ነው፡፡

ከዚህም ሌላ ጌታችን የሚናገረው ነገር ምሳሌ ሲሆን ስም ሳይጠቅስ እንዲሁ ጉዳዩን በሚያስረዳ መልኩ ነው ያስተማረው፡፡ ለአብነትም ስለ ጠፋው ልጅና ስለ አባቱ ሲናገር "አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት" በማለት ነበር፡፡ ሉቃ. 15፡11 እንደዚህ ዓይነት አጠቃላይ ጉዳዮችን በምሳሌ ያስተማረባቸው ብዙ ምሳሌያዊ ትምህርቶች አሉ፡፡ ለአብነት ያህልም፦ "ነገር ግን ምን ይመስላችኋል? አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት፤ ወደ አንደኛው ቀርቦ፦ ልጄ ሆይ፥ ዛሬ ሂድና በወይኔ አትክልት ሥራ አለው" የሚለው (ማቴ. 21፡28)፤ የተለያየ መክሊት የተሰጣቸው ሦስት ዓይነት ሰዎች (ማቴ. 25)፤ "በምሳሌም ይነግራቸው ጀመር። አንድ ሰው የወይን አትክልት ተከለ፥ ቅጥርም ቀጠረለት፥ መጥመቂያም ማሰለት፥ ግንብም ሠራና ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ" (ማር. 12፡1)፤ "ለአንድ አበዳሪ ሁለት ተበዳሪዎች ነበሩት፥ በአንዱ አምስት መቶ ዲናር ነበረበት፥ በሁለተኛውም አምሳ" እያለ እገሌ ብሎ ስም ሳይጠቅስ ጉዳይ ተኮር አድርጎ አስተምሯል፡፡ ሉቃ. 7፡41

ስም፥ ቦታ፥ ጊዜና ሁኔታን በመጥቀስ ያስተማራቸው ትምህርቶች ግን እውነተኛ ታሪኮች ናቸው፡፡ ለምሳሌም የደጉ ሳምራዊና በመንገድ ላይ ሽፍቶች የደበደቡት ሰው ታሪክ፥ የሳምራዊቷ ታሪክ፥ አንድ ሰው ቀርቦ ጌታችንን "መምህር ሆይ፥ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን ላድርግ?" ብሎ የጠየቀው ጥያቄ (ማቴ. 19፡16)፥ ስለ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ "በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን ከአብያ ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበረ፤ ሚስቱም ከአሮን ልጆች ነበረች፥ ስምዋም ኤልሳቤጥ ነበር" ተብሎ የተነገረው (ሉቃ. 1፡5)፥ እና የመሳሰሉት እውነተኛ የተፈጸሙ ድርጊቶችና ታሪኮች ናቸው፡፡ ከዚህም ጋር ሊዘነጋ የማይገባው ነጥብ ጌታችን ያስተማረባቸው ምሳሌዎችም ቢሆን ተግባራዊና ተዘውትረው

የሚሆኑ ስለ ሆኑ እንደ ምሳሌ ተደረጉ እንጂ በተግባር የማይሆኑና ያልሆኑ ስለሆኑ አይደለም፡፡ "በሆነ ምሳሌ አስተማራቸው" የምንል ለዚያ ነው፡፡ ይልቁንም ምሳሌያዊ መሆናቸው ቀዋሚ እውነታነታቸውን ያጎላዋል እንጂ አይቀንሰውም፤ ከእውነታ የራቁም አያደርጋቸውም፡፡

ተሐድሶዎች "ይህ ታሪክ ሳይሆን ምሳሌ ነው" ካሉ አብርሃምም ታሪክ መሆኑ ሊቀር ነዋ! ስለ ሲኦል የተነገረውም እንዲሁ እውነት መሆኑ ሊቀር ነዋ! አጠቃላይ አካሄዳቸው ሁሉ ከእምነት ወደ ክህደት የሚወስድ ነው፡፡ ተሐድሶዎች "በሉቃስ 16 ከቁጥር 19 ጀምሮ የተገለጸውን ታሪክ "ቸርነት የማያደርጉትን ባለጠጎች ለመውቀስና ለማስተማር ምሳሌ ሆኖ የቀረበ እንጂ በትክክል የተፈጸመ ታሪክ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ... ታሪካዊ መሠረት የሌለውና ለማስተማር የቀረበ ነው" በማለት የተናገሩት ግልጽ ስህተት ነው፡፡ ይህ አባባላቸው የሚያሳየን የእግዚአብሔር ቃል እነርሱ ከያዙት አቋም ጋር የሚቃረንና ልብ ወለድ ፍልስፍናቸውን የሚያፈርስባቸው ሲሆንባቸው እውነቱን እንዳለ ከመቀበል ይልቅ ወደ ራሳቸው አመለካከት ለመጠምዘዝ የተደረገ ያልተሳካ (ሊሳካም የማይችል) የማስገደድ ሙከራ ነው፡፡

እግዚአብሔር አምላካችን በዚህ ቅዱስ ቃሉ ከዚህ ዓለም ሕይወት በኋላ ስለሚሆኑ ነገሮች ገና በዚህ ዓለም ሕይወታችን ልናውቃቸው የሚያስፈልጉንን ብዙ መሠረታዊ እውነታዎችን አስተምሮናል፡፡ ከእነዚህም መካከል አንዱ ትምህርት ቅዱሳን ከሞቱ (ካረፉ) በኋላ በዚህ ዓለም ስለሚሆነው ነገር የሚያውቁ መሆናቸውን ነው፡፡

ይህም በሚከተሉት ነጥቦች ግልጽ ሆኖ ይታያል፡-

1) አብርሃም ከዚህ ዓለም ወደዚያኛው ዓለም ከሄደ ከብዙ ዘመናት በኋላ በዚህ ዓለም አልዓዛር የሚባል ሰውና ያ ባለ ጸጋ የነበሩና የኖሩ መሆናቸውን በማወቁ፤

2) እንዲሁም አብርሃም አልዓዛርንና የባለ ጸጋውን መኖራቸውን ብቻ ሳይሆን አኗኗራቸውንም ጭምር እንዴት እንደ ነበር ማወቁን ("አብርሃም ግን፡- ልጄ ሆይ፤ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ፤ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል፤ አንተም ትሣቀያለህ" ያለው ይህን ያስረዳልና)፤

3) አብርሃም የነበረው የኦሪትን ሕግ ከእግዚአብሔር ተቀብሎ የሠራው ሙሴ እና ከእርሱ በኋላ የተነሡ ሌሎች ነቢያት ከመምጣታቸው በፊት (ለምሳሌ ከሙሴ ከአምስት መቶ ዓመታት ገደማ በፊት) የነበረ ቢሆንም በዚህ ምድር ላይ ሙሴ የሚባል ሰው የነበረ መሆኑን፤ ሙሴም ሕግ ከእግዚአብሔር መቀበሉንና የጽሑፍ ሕግም ለሕዝቡ መስጠቱን፤ ነቢያት መነሣታቸውንና መጻሕፍትን መጻፋቸውን፤ ወዘተ ሁሉ አብርሃም አውቋል፡፡ ከዚህ ዓለም ከሄዱ (ከሞቱ) በኋላ በዚህ ዓለም ስለሚሆነው ነገር የማያውቁ ከሆነ አብርሃም ይህን ሁሉ ነገር እንዴት ሊያውቅ ቻለ? ይህን የምትቃወሙ ሰዎች ሆይ፤ ከላይ እንዳላችሁት "እግዚአብሔር ስለ ገለጠለት ነው" ልትሉን ይሆን? አሁንም እንዲህ ካላችሁ ደግሞ ድሮውንስ ቢሆን እኛስ የምንለው ቅዱሳን እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ ይህን ሁሉ ያውቃሉ አልን እንጂ ከእግዚአብሔር ውጭ በባሕርያቸው ያውቃሉ ማን አላችሁ? ስለዚህ ጌታችን "የመጽሐፉ ቃል ሊሻር አይቻለውምና" እንዳለ ከእውነት ጋር ከመዋጋት ይልቅ እልህን ትቶ መመለሱ ይጠቅማችኋል እንጂ አይጎዳችሁምና እባካችሁ ስህተትን ነክሶ አልለቅም ከማለት እልህ ትወጡ ዘንድ በታላቅ ትሕትናና በእግዚአብሔር ፍቅር እንማልዳችኋለን፡፡

4) አብርሃም ብቻ ሳይሆን ባለ ጸጋውም እንኳ ከሞተ በኋላ በዚህ ዓለም ወንድሞች የነበሩት መሆኑን፤ እነዚያ ወንድሞቹም አምስት መሆናቸውን፤ ከአብርሃም ጋር እየተነጋገረ በነበረበት በዚያ ጊዜ ላይ እነዚያ ወንድሞቹ በዚህ ዓለም ላይ በሕይወተ ሥጋ ያሉ መሆናቸውን፤ እንዲሁም ንስሐ ያልገቡ መሆናቸውን አውቋል፡፡

ታዲያ "ቅዱሳን ካረፉ በኋላ ምንም አያውቁም" የሚለው የተሐድሶዎች ነገር በዚህ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ፊት ሊቆም እንዴት ይቻለዋል? ሲጀመርስ በነገረ ሃይማኖት "አብርሃም በዐጸደ ነፍስ ባለበት ሁኔታ በምድር የሚደረገውን ሁሉ ያውቃል ማለት የሚታመን ቀርቶ የማይመስል ነው" ማለትን ምን አመጣው? የምናምነው የሚመስለንን አይደለምና፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ "በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስም" ያለው ለዚህ አይደለምን? የሚመስለው ሁሉ አይታመንም፣ ስለማይመስልም አይካድም፡፡ የእምነት መለኪያው የሰው አእምሮ ወይም መምሰሉና አለመምሰሉ አይደለምና፡፡ እነርሱ ግን እምነታቸው ከራሳቸው የመነጨ ስለሆነ የሚያምኑት የሚመስላቸውን በመሆኑ እንዲያ ማለታቸው ማንነታቸውን ከሚያሳብቅባቸው በስተቀር በነገረ ሃይማኖት ግን ቦታ የለውም፡፡ እነርሱ ግን ከእምነት ውጭ ሆነው በይሆናል አይሆንም ግምት እና በመሰለኝ እየተጓዙ ይገኛሉ፡፡ የሚገርመውና የሚያሳዝነው ደግሞ ገና ለራሳቸው ሳይሆን ለሌሎች አስተማሪዎችና መሪዎች እንሁን እያሉ መግለጻቸው ነው፡፡ ነገሩ ጌታችን በወንጌል "ዕውር ዕውረ ለእመ መርሐ ክልኤሆም ይወድቁ ውስተ ግብ - ዕውርም ዕውርን ቢመራው ሁለቱም ወደ ጉድጓድ ይወድቃሉ" ብሎ የተናገረው ነው፡፡ ማቴ. 15፥14

ሐ) ነፍሳት ሰማዕታት

ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ እግዚአብሔር በገለጠለት ሰማያዊ ራእዩ እንዲህ ይላል፦

> አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ። በታላቅ ድምፅም እየጮኹ፦ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፣ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም? ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም? አሉ። ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው፣ እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቍጥር እስኪፈጸም ድረስ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸው። ራእ. 6፥9-11

እነዚህ ስለ ክርስቶስ መስክረው በሰማዕትነት ያረፉ ቅዱሳን ካረፉ በኋላ በአካለ ነፍስ ሆነው እግዚአብሔር ደማቸውን የተበቀለላቸው መሆን አለመሆኑን ባያውቁ ኖሮ "ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፣ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም? ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም?" ብለው መጠየቅ ይችሉ ነበረን? በግፍ ያሠቃዩዋቸውና የገደሏቸው ሰዎች ተገቢውን ፍርድ ማግኘት አለማግኘታቸውን የማያውቁ ቢሆን ኖሮ በመጀመሪያ የሚጠይቁት ጥያቄ "ጌታ ሆይ፣ ፈርደህባቸዋል? ወይስ ገና ነህ? ደማችንን ተበቅለህልናል? ወይስ ገና አልተበቀልሃቸውም?" የሚል ይሆን ነበር እንጂ "እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም?" የሚል ባልሆነ ነበር፡፡ ስለዚህም ሰማዕታት ከሞቱ በኋላ በዓጸደ ነፍስ ሆነው በዚህ ዓለም ስለነበረው ሁኔታ አውቀዋል ማለት ነው፡፡ መቼም የሚያውቁት እውቀት እግዚአብሔር በገለጠላቸው መጠን ነው እያልን በየቦታው እንደ አዝማች መደጋገም አይጠበቅብንም፡፡

መ) ነቢዩ ሳሙኤልም ከሞተ በኋላ ለንጉሥ ሳዖል የሚሞትበትን ቀን ነግሮታል፡፡ እንዲህ ይላልና፣ - "ሳሙኤልም በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ነው፣ እናመሰግነው፤ ትንቢት የሚናገር ነው፡፡ . . . ከሞተም በኋላ ትንቢት ተናገረ፤ የንጉሡንም (የሳኦልን) ሞት ተናገረ፣ ከመቃብርም ተነሥቶ ነገር ተናገረ፡፡" ሲራ. 46፥20

ሠ) የራሔል ልቅሶ

ንጉሥ ሄሮድስ ጌታችንን በሕፃንነቱ ለመግደል በማሰብ በቤተ ልሔምና አካባቢዋ ዕድሜያቸው እስከ ሁለት ዓመት ድረስ የሆናቸውን ሕፃናት በተንኮል በመሰብሰብ አስፈጃቸው፡፡ ቤተ ልሔምና አካባቢው የያዕቆብ ሚስት የነበረችው ራሔል የተቀበረችበት ቦታ በመሆኑ፣ እንዲሁም ከሁለቱ ልጆቿ መካከል የአንደኛው የብንያም ነገድ ርስት በመሆኑ ስለ ተገደሉት ሕፃናት እርሷ በተለየ ሁኔታ አዝናለች፡፡ ለዚህ ነው ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ ስለዚህ ጉዳይ የተነገረውን ትንቢት ከነፍጻሜው

እንዲህ በማለት የተናገረው፦ "ያን ጊዜ በነቢዩ በኤርምያስ፦ ድምፅ በራማ ተሰማ፣ ልቅሶና ብዙ ዋይታ፤ ራሔል ስለ ልጆቿ አለቀሰች፣ መጽናናትም አልወደደችም፣ የሉምና የተባለው ተፈጸመ።" ማቴ. 2፥16-18ራሔል በሕፃናቱ ላይ የደረሰው ግፍ ካልተሰማት በስተቀር "ራሔል ስለ ልጆቿ አለቀሰች፣ መጽናናትም አልወደደችም፣ የሉምና" ተብሎ እንዴት ተነገረ? ገና አስቀድሞ ድርጊቱ ሳይሆን (ሕፃናቱ ሳይገደሉ) አታለቅስም፣ ምክንያቱም ግፉ ገና አልሆነም፣ አልተፈጸመምና፡፡ ራሔል የነበረችው ይህን ትንቢት የተናገረው ነቢዩ ኤርምያስ ከመነሣቱ ከአንድ ሺህ ዓመታት በፊት ነበር፡፡ እንዲሁም ተፈጸመ የተባለው ሄሮድስ ባስገደላቸው ጊዜ ነው እንጂ ትንቢቱ በተነገረበት ጊዜ አይደለም፤ ለዚህ ነው ቃሉ "ያን ጊዜ በነቢዩ በኤርምያስ፦ ድምፅ በራማ ተሰማ፣ ልቅሶና ብዙ ዋይታ፤ ራሔል ስለ ልጆቿ አለቀሰች፣ መጽናናትም አልወደደችም፣ የሉምና የተባለው ተፈጸመ" በማለት ትንቢቱን ጠቅሶ "ተፈጸመ" የሚለውን ግን አሁን ለድርጊቱ ሰጥቶ የተናገረው፡፡ ስለዚህ ራሔል ልጆቿ በሄሮድስ ሲጨፈጨፉ በአካለ ነፍስ አውቃ መከራቸው ተሰምቷት አብራቸው በመንፈስ አልቅሳለች፣ አዝናለች፡፡በዚህም እንደምታለቅስ የተነገረው ትንቢት ተፈጽሟል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በአካለ ነፍስ ያሉ ወገኖቻችን በዚህ ዓለም ስለሚሆነው ነገር ምንም አያውቁም ማለት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የስህተት ትምህርት ነው፡፡ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ሊገልጠው ስለሚችለው እውቀትና ሊሰጣቸው ስለሚችለው ጸጋ ያልተረዳና የእግዚአብሔርን ነጻነት ገዳቢ የሆነ አስተሳሰብ ነው፡፡

## 6.3 የቅዱሳን አማላጅነትን በተመለከተ

### 6.3.1 ተሐድሶዎች የሚያነሷቸው የተሳሳቱ አባባሎችና ድምዳሜዎች

◉ *"ለብዙ ዘመናት በሰይጣንና በአዋልድ ደራስያን ጥበብ የተሰበከና በደማቸው ጠልቆ ገብቶ የተዋሐዳቸውን የቅዱሳን አማላጅነት ትምህርት መቃወምን መዳን እያስፈልጋችሁም የማለትን ያህል ይቆጥሩታል፡፡"* (ኖኅተ ብርሃን፣ መጋቢት 2002፣ ገጽ 7)

"ለማማለድ (አማላጅ ለመሆን) የሚያበቁ መስፈርቶች" በሚል ርእስ ሥር የሚከተሉትን አስቀምጠዋል፦

◉ *"ሀ. <u>ወንጀለኛ ያልሆነ /ከወንጀል የጸዳ/</u> . . . በሰው ልጆች የዘር ሐረግ ከወንጀል የጸዳ ሰው የለም፡፡ ለምሳሌ አብርሃም የተሰፋው ቃል ኪዳን የተሰጠው ነበር፡፡ ሆኖም የሰው ልጅ ሁሉ ከወንጀል የጸዳ ባለመሆኑ አብርሃም የሠራው ስህተት ለዛሬዎቹ ፍልስጥኤምና እስራኤላውያን ግጭት መነሻ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ . . . ለዘሮቹ እንኳንስ ሊያማልድላቸው ቀርቶ በራሱ ማንነት የሠራው ኃጢአት በሥጋ ከእርሱ የተወለዱትን እስካሁን ሰላማቸውን ነሥቷቸው ይገኛል፡፡ ስለሆነም አብርሃም የማማለድ መስፈርቶችን የማያሟላ ነበር፡፡"* ("መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ ገጽ 21-22)

➢ አጭር ማስታዎሻ፦ ይህ የተሳሳተ መነሻ፣ የተሳሳተ ድምዳሜም ነው፡፡ ሲጀመር አንድ ሰው ስለ ሌላው ሰው ለመጸለይ ከኃጢአት ሁሉ ንጹሕ መሆን አለበት የሚለው መሥፈሪያ እነርሱ የፈጠሩት እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደዚያ የሚል ነገር የለም፡፡ በዚያውም ላይ ከዚህ ቀጥሎ እንደምንመለከተው አብርሃም በነበረበት ሕይወት ሆኖ፣ ሌላ ሰው መሆን ሳያስፈልገው ስለ ሌሎች ሰዎች ማልዷል፡፡ ይህን በቦታው ላይ እናየዋለን፡፡

➢ ሌላው ስሁተታቸው ደግሞ "አብርሃም የሠራው ስህተት ለዛሬዎቹ ፍልስጥኤማውያንና እስራኤላውያን ግጭት መነሻ ነው፣ የሠራው ኃጢአት በሥጋ ከእርሱ የተወለዱትን እስካሁን ሰላማቸውን ነሥቷቸው ይገኛል" ማለታቸው ነው፡፡ ይህ የታሪክ አላዋቂነት ችግር ነው፡፡ ባላዋቂነት ላይ ደግሞ ድፍረት የተጨመረበት ድርብ ስህተት ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ስለዚህ ጉዳይ ታሪካዊ ትንታኔ የሚሰጥበት ባለመሆኑ ወደ ዝርዝሩ አንገባም፡፡ ሆኖም ቢያንስ ሁለት

> ነገሮችን በአጭሩ ማስታወስ ግን ይገባል፡፡ በመጀመሪያ ፍልስጥኤማውያን እና እስራኤላውያን አንድ ዘር አይደሉም፡፡ ፍልስጥኤማውያን የካም ዘር ሲሆኑ አብርሃምና ከእርሱ በይስሐቅና በያዕቆብ በኩል የተገኙት እስራኤላውያን ደግሞ የሴም ዘር ናቸው፡፡ ዘፍ. 10፥6-14፤ 10፥21-11፥32 1 ዜና 1፥8-31 ስለዚህ ፍልስጥኤማውያን የአብርሃም ዘር አይደሉም፡፡ የፍልስጥኤማውያን የዘር ሐረግ የት መጣ ጉዳይ በታሪክ ብዙ ያመራመረ ነው፡፡ እንዲሁም ደግሞ አሁን ያለው የሁለቱ ሕዝቦች ግጭት ሌሎች ብዙ ፖለቲካዊ፣ መልክአ ምድራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ዓለም አቀፋዊ ገጽታ ያለው ውስብስብ ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ጉዳይ በሚገባ ባልተረዳ አእምሮ ታላቁ የእግዚአብሔር ሰው አብርሃም ላይ መለጠፍ ከታሪካዊ ጭብጥም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታም አንጻር ምንም መሠረት የለውም፡፡ እንዲህ የእግዚአብሔርን ሰዎች መንቀፍና ያለ ግብራቸው ግብር መስጠት ይህን ያህል የተካኑበት ግብራቸውና መገለጫቸው መሆኑ ግን በጣም ያሳዝናል፡፡

ይልቁንም ቅዱስ ጳውሎስ ይህን በተመለከተ በገላትያ መልእክቱ እንዴት አድርጎ እንደ ጻፈ እንመልከት፡-

> እናንተ ከሕግ በታች ልትኖሩ የምትወዱ፥ ሕጉን አትሰሙምን? እስኪ ንገሩኝ። አንዱ ከባሪያይቱ አንዱም ከጨዋይቱ የሆኑ ሁለት ልጆች ለአብርሃም እንደ ነበሩት ተጽፏልና። ነገር ግን የባሪያይቱ ልጅ እንደ ሥጋ ተወልዷል፥ የጨዋይቱ ግን በተስፋው ቃል ተወልዷል። ይህም ነገር ምሳሌ ነው፤ እነዚህ ሴቶች እንደ ሁለቱ ኪዳኖች ናቸውና። ከደብረ ሲና የሆነችው እንዲቱ ለባርነት ልጆችን ትወልዳለች፥ እርሷም አጋር ናት። ይህችም አጋር በዓረብ ምድር ያለችው ደብረ ሲና ናት፤ አሁንም ያለችውን ኢየሩሳሌምን ትመስላለች፥ ከልጆቿ ጋር በባርነት ናትና። ላይኛይቱ ኢየሩሳሌም ግን በነጻነት የምትኖር ናት፥ እርሷም እናታችን ናት። ... እኛም ወንድሞች ሆይ፥ እንደ ይስሐቅ የተስፋ ቃል ልጆች ነን። ነገር ግን እንደ ሥጋ የተወለደው እንደ መንፈስ የተወለደውን በዚያን ጊዜ እንዳሳደደው ዛሬም እንዲሁ ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ምን ይላል? የባሪያይቱ ልጅ ከጨዋይቱ ልጅ ጋር አይወርስምና ባሪያይቱን ከልጇ ጋር አውጣት። ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፥ የጨዋይቱ ልጆች ነን እንጂ የባሪያይቱ አይደለንም። ገላ. 4፥21-31

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን የአብርሃምን ታሪክና በሕይወቱ ዙሪያ የነበረውን ነገር አመስጥሮ ለወንጌልና ለአሪት፣ ለምድራዊውና ለሰማያዊው ሕይወት፣ ለመንፈሳዊ ተጋድሎና ፈተና ምሳሌ አድርጎ በስምና በወርቅ አራቅቆ ተርጉሞት እናገኘለን እንጂ ተሐድሶዎች እንደሚሉት አብርሃምን ሊወቅስና ሊከስ አናገኘውም፡፡

- "ለ. ከእዳ ነጻ የሆነ መሆን አለበት"፣
- "ሐ. ለዋስትና የሚበቃ /ብቃት ያለው ዋስ/ መሆን አለበት፡፡" ("መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ ገጽ 21-26)
- "ከዚህም በተጨማሪ አማላጅ የሚሆነው አካል በአንድ ጊዜ በሁሉም ቦታ የሚገኝ (ምሉእ በኩለሄ) መሆን እና ሁሉን ቻይ መሆን አለበት" የሚል ተጨማሪ መስፈርት አስቀምጠዋል፡፡ (መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ ገጽ 26-28)

በዚህ ሁሉ አማላጅነትን በተሳሳተና በተበላሸ መነጽራቸው ካዩትና የሌለ ልብ ወለዳዊ መስፈርት አስቀምጠው ከለኩት በኋላ ነገራቸውን ሲያጠቃልሉ እንዲህ አሉ፡-

- "... እናም ቤተ ክርስቲያናችን ወደ ጥንት ማንነቷና አስተምህሮዋ የማትመለስ ከሆነ ከእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ወጥታ በራሷ ፍልስፍና የምትመራ፥ እንዲሁም ከአኃት አብያተ ክርስቲያናት ራሷን አግልላ ክርስቲያንና ቤተ ክርስቲያን የሚለውንም ስያሜ ልትተው ይገባታል፡፡" (መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ ገጽ 28)

ይህ አባባልም አኃት አብያተ ክርስቲያናት በቅዱሳን አማላጅነት የማያምኑ ለማስመሰልና ይህን የምትቀበለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብቻ እንደ ሆነች አስመስሎ ለማሳየት የተደረገ ሙከራ መሆኑ ነው፡፡ እስኪ አሁን በዚህ ዘመን የሚኖር ሰው ይህን በቀላሉ አጣርቶ ማወቅ አይችልም ብሎ ማሰብ ምን ዓይነት ሞኝነት ነው? ምናልባት ቀደም ባሉት ዘመናት ቢሆን ኖሮ የአኃት አብያተ ክርስቲያናትን እምነት ምንነት ከራሳቸው ከምንጩ ለማወቅ ቀላል አልነበረም፡፡ ዛሬ ግን የፈለገ በኢንተርኔት መደበኛ ድረ ገጻቸው ላይ፣ ወይም ቤተ ክርስቲያናቱ በይፋ ከጻፏቸው መጻሕፍት ላይ፣ የፈለገና የቻለ ደግሞ አገራቸው በአካል ሄዶ ሊያየውና ሊረዳው ይችላል፡፡ በየትኛውም መንገድ ቢሆን ግን የቅዱሳንን አማላጅነት አኃት አብያተ ክርስቲያናት አይቀበሉም ማለት ውሸታቸው ወይም አላዋቂነታቸው መጠን የሌለው መሆኑን በማሳየት ከታላቅ ትዝብት ላይ ይጥላቸዋል እንጂ የሚጠቅማቸው አንዳችም ነገር የለም፡፡

የፕሮቴስታንት ሚሲዮን የነበረው ሳሙኤል ጎባት "የቅዱሳን የማማለድ እምነት በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተደገፈ ልምድ ነው"[111] በማለት በዘመኑ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትን ለመከራከርና ለማሳመን ጥረት አድርጎ ነበር፡፡ በአገራቸው ያሉ አብያተ ክርስቲያናት እየተዘጉ ወደ ፊልምና መጠጥ ቤትነት እየተለወጡና እየተከራዩ፣ ወደ ሙዚየምነት እየተቀየሩ፣ ሕዝባቸውም በኢአማኒነት መንፈስ በእጅጉ እየተወሰደ እያለ እነ ሳሙኤል ጎባትና ከዚያም ወዲህ በየዘመኑ ወደ አገራችን መጥተው ቤተ ክርስቲያኒቷን እናድሳት እያሉ ብዙ ገንዘብ የሚያፈስሱ አካላት ይህን የሚያደርጉት በእውነት ለሰዎች መዳን አስበው ከሆነ በመጀመሪያ በአገራቸው ያሉትን በእግዚአብሔር መኖር አናምንም እያሉ ያሉትን ሕዝባቸውን ለምን እነርሱን አይሰብኩም? ፈሪሃ እግዚአብሔር የራቀውንና ወንድና ወንድ ሴትና ሴት "ባርኮ" እስከ ማጋባት የደረሰውን ብልሹ አገራቸውን ትተው ፈሪሃ እግዚአብሔር ያልተለየውን ሕዝብ እንስበክ ብለው መምጣታቸው ዓላማው ወንጌልን መስበክና ማጽደቅ ነው ብሎ ለማመን እንዴት ያስችላል?

እነ ሳሙኤል ጎባት በቀጥታ ራሳቸው መጥተው ሊያሳኩት ያልቻሉትን ቤተ ክርስቲያኒቱን ወደ ፕሮቴስታንትነት የመለወጥ ዘመቻ ለማሳካት ያሰለጠኗቸው አገር በቀል ሠራተኞች ከዛሬ መቶ ዓመት በፊት የፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን ሲሙኙት የነበረውን ጩኸት "የቅዱሳን አማላጅነት በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተደገፈ ነው" ብለው ደፍረው እስከ መጻፍ ደርሰዋል፡፡ ያውም ደግሞ ይህ የቅዱሳን አማላጅነት ጉዳይ በአኃት አብያተ ክርስቲያናት የማይታመንና የሌለ ስለሆነ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ብቻ ይህን መቀበሏ ከእነርሱ የተለየች ብቸኛ ያደርጋታል በሚል ደረቅ ሐሰት አጅበው ለማቅረብ ሞክረዋል፡፡

ለነገሩ እውነት የሚለካው በተቀባዩ ብዛትና ማነስ አይደለም እንጂ የቅዱሳንን አማላጅነትስ እንኳን በሃይማኖት ከእኛ ጋር አንድ የሆኑት አኃት አብያተ ክርስቲያናት (ኦሬንታል ኦርቶዶክስ) ይቅርና ምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያንም፣ ካቶሊኮችም ጭምር የሚቀበሉት እውነት ነው፡፡ ይህን የማይቀበሉት እንደ ጅራት ከኋላ ብቅ ያሉት ፕሮቴስታንቶች ብቻ ናቸው፡፡ የፕሮቴስታንት የውስጥ አርበኛ ሆኖ እየሠራ ያለው ተሐድሶ ደግሞ ይህን የስህተት ትምህርታቸውን እንደ አዲስ ግኝት ተቀበሉ ሊለን ይሞክራል፡፡ ስለዚህ እንዲህ ባለ የሐሰት ወሬ ከእውነት አስወጥቶ ወደ ራሳቸው የስህተት ጎራ ለመውሰድ መድፈራቸው በአንድ በኩል ምናልባት ባለማወቅ ከሆነ የአላዋቂነታቸውን መጠን ያሳያል፡፡ እያወቁ ከሆነ ደግሞ ሰዎችን ከእውነት መንገድ ለማውጣት ደረቅ ሐሰትን መጠቀም ዋና የስልታቸው አካልና መሣሪያቸው መሆኑን ያሳያል፡፡

111 (ዶናልድ ክራሚ፣ 1972፣ ገጽ 33)

ሌሎች አባባሎቻቸውን እንጨምር፡-

- "በዐጸደ ነፍስ ያሉ ማለት ምድራዊ ሩጫቸውን ጨርሰው በአካለ ነፍስ ወደ ገነት የተወሰዱ ቅዱሳን እንደ እነርሱ ሩጫቸውን ጨርሰው በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ለገቡ ነፍሳት ይማልዳሉን? ወይም ያማልዳሉን? ቢባል መልሱ አያማልዱም፣ አይማልዱም የሚል ነው።" (ሙራ ቁ. 8፣ ገጽ 31)

- "በዐጸደ ነፍስ ያሉ የቅዱሳን ነፍሳት በአጸደ ሥጋ ላሉት ይማልዳሉን? ያማልዳሉን? የለም አያማልዱም፣ አይማልዱም።" (ሙራ ቁ. 8፣ ገጽ 31)

- ". . . የእርቁን አዋጅ ስሙና ኑ ታረቁኝ እያለ እግዚአብሔር በወንጌላውያን በኩል እየማለደ ሳለ፣ እይ ልጅህ በፈጸመው ሥራ አልታረቅም፣ ሌላ አስታራቂ እፈልጋለሁ ለሚል ሰው ኧረ ምን መፍትሔ ይገኛል?" (ሙራ ቁ. 8፣ ገጽ 32)

- "እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታረቀ ሆኖ ሳለ፣ በማስታረቅ አገልግሎት የተመደቡ መልእክተኞችም ወደ ዓለሙ ሁሉ በመሔድ የዕርቁን ቃል እየሰበኩ ሳለ፣ እስካሁን ድረስ ገና እግዚአብሔርን በጠላትነት ለሚያዩ፣ አስታራቂ ፍለጋ በዱር በገደል ለሚንከራተቱና አስታራቂ ያጡ መስሏቸው ተስፋ ለቆረጡ ሁሉ . . ." (ሙራ ቁ. 11፣ ገጽ 5)

- "ክርስቲያን ወደ ሞቱ ሰዎች ነፍሳትና ወደ ልዩ ልዩ መናፍስት ሊጸልይ ይገባዋልን? የሞቱ ዘመዶቻችንን ነፍሳት ብንጠራቸው ይሰሙናልን? የምንጠይቃቸውን የመፈጸም ችሎታ አላቸውን? ሊጸልይ አይገባውም፣ ይህ የአረማውያን ልማድ ነው። ምድራዊ ተልእኳቸውን ጨርሰው ያንቀላፉትን (የሞቱትን) ሰዎች ነፍሳት በሥጋ ሕይወት ያለነው እኛ ብንጠራቸው አይሰሙም፣ የምንጠይቃቸውንም ለመፈጸም አይችሉም። ሞትን ተሻግረው ወደ ዓጸደ ነፍስ የተሻገሩ ሰዎች በዓጸደ ሥጋ ያሉ ተወላጆቻቸው ቢከብሩ ወይም ቢዋረዱ የማወቅ ወይም የማየት ችሎታ የላቸውም ይላል ቃሉ። ኢዮብ 7፡9-10፣ 14፡1-22 መክ. 9፡4-6" (ሙራ ቁ. 3፣ ገጽ 23-24)

- "መናፍስትን እንዳንጠራ ከተከለከልን መናፍስት በምን ሁኔታ ወደ ሰው ይመጣሉ? በመናፍስትነት የምናውቃቸው መላእክት እና የወደቀው ሰይጣንና ተከታዮቹ ናቸው። የወደቁትንም ሆነ ያልወደቁትን መናፍስት (መላእክትን) እንድንጠራ አልተፈቀደም። ዘዳ. 18፡9-12 መናፍስትንና የሞቱ ሰዎችን ነፍሳት መጥራት ማሟረት ነው። ሙታን በሕይወተ ሥጋ በነበሩበት ጊዜ ይፈጽሙት የነበረውን እስነዋሪ ተግባር ያልሞቱ ዘመዶቻቸው እንዳይሠሩ ለመምከር እንኳ አይችሉም። ሉቃ. 23፡42-43 ራእ. 6፡9-11 ሉቃ. 16፡22 — 30" (ሙራ ቁ. 3፣ ገጽ 23-24)

- "በቤተ ክርስቲያኖቻቸው ስለ ቅድስና የሚወጡትን ድንጋጌዎች ለማክበር ጥረት የሚያደርጉ ምእመናን እንዳሉ ይታወቃል። በእግዚአብሔር የተደነገጉትን ሕጎች ለመጠበቅ በሚደረግ ሙከራ የሚጋደሉም አሉ። በየዕለቱ በመውደቅና በመነሳት በሚደረግ ተጋድሎ ቅድስናን ለመፈጸም የሚታየው የምእመናን ልባዊ ጥረት በሰውም በእግዚአብሔርም ዘንድ የተወደደ መሆኑ አያጠራጥርም። ዳሩ ግን እንደዚህ በመሰለ ሁኔታ ራስን ለማግዛት በሚደረግ ጥረት ውስጥ ያለው ቅድስና በሰው ዐቅም የሚፈጸምና መለኪያውም ሰብአዊ መሆኑን ልንዘነጋ አይገባም፣ እግዚአብሔር የሚፈልግብን ቅድስና ከዚያ በላይ ነውና፣ 'እኔ ቅዱስ እንደ ሆንኩ ቅዱሳን ሁኑ' ይለናልና። . . . እንዲሁ በሌላው ሕይወት ተለክቶ የተሻለ ሆኖ መገኘትን በቂና ፍጹም አድርጎ አይመዘግብልንም። በመውደቅና በመነሣት ውስጥ ከሚያልፍ ሕይወት የተገኘ ቅድስና፣ በሰዎች መካከል በሚፈጠር መመጻደቅና ማነጻጸር እገሌ ጻድቅ ነው፣ አንተ ቅዱስ ነህ ለመባባል ቢያበቃ እንጂ በእግዚአብሔር ቅድስና ተለክቶ ፍጹምነትን አያስገኝም፣ አያሰጥም።" (ሙራ ቁ. 12፣ ገጽ 22)

- "በሰዎች ዘንድ ቅዱሳን ናቸው ከተባሉት መካከል በእግዚአብሔር ዘንድም ቅዱሳን ሆነው የተገኙትም ሆነ ሌሎቹ ሁሉ ምድራዊ ሩጫቸውን ጨርሰው ሲሞቱ ከዚያ በኋላ ምን ይሆናሉ? ለሚለው ጥያቄ "የመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያን መልስ ለመስጠት ሞክረዋል። . . . እንደኛው ወገን እንዲህ ይላል፡- ሰዎች ሲሞቱ ሥጋቸው ወደ መቃብር ነፍሳቸው ወደ እግዚአብሔር ይሄዳሉ። ከዚያም በዳግም ምጽአቱ በሕይወት ሥጋ በነበሩበት ጊዜ ለፈጸሙት ሁሉ ብድራታቸውን እስኪሚቀበሉበት ቀን ድረስ በየተወሰነላቸው መቆያ ይጠበቃሉ።"

በመቀጠልም የሞቱ ሰዎች በዚህ ዓለም ስለላው ነገር ምንም እንደማያውቁ ያትታል፡፡ ከዚህ በመቀጠልም እንዲህ ይላል፡-

- "ከዚህም በቀር በሕይወተ ሥጋ በነበረበት ጊዜ የሚያውቀውን እውቀት ነፍሱ ይዛ እንደምትኖርና እስከ ዳግም ምጽአተ ክርስቶስ በዚሁ እውቀት እንደምትቆይ ታውቋል" በማለት ፍጹም ፕሮቴስታንታዊ የሆነ ሃሳቡን ይገልጻል፡፡ (ሙራ ቁ. 12፣ ገጽ 22-23)
- "የሁለተኛው ወገን ትምህርት ደግሞ እንዲህ ነው፡- ቤተ ክርስቲያን በቅዱስነት የመዘገበቻቸው ምእመናን ነፍሳት ሁሉ ቅዱሳን ናቸው፡፡ ከትንሣኤና ከፍርድ ጊዜ በፊት በአሁን ሰዓት በአካለ ነፍስ እንዳሉ ዋጋቸውን ተቀብለዋል፡፡ በአሁን ሰዓት በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል በኢየሱስ ክርስቶስ የተያዘውን የማስከላዊነት፣ የአስታራቂነት፣ የአማላጅነት ሥራ ያከናውናሉ፡፡ ደህንነትም የኢየሱስ ክርስቶስን ቤዛነት በመቀበል ሳይሆን ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ናቸው በምትላቸው ነፍሳት አማላጅነት በመማፀን ሆኗል፡፡ በእግዚአብሔር የማያምን ቢሆን በእነርሱ ክተማጸነ የሚድንበት ቃል ኪዳን ለቅዱሳን ነፍሳት ተሰጥቷል፣ ይህም ቃል ኪዳን እግዚአብሔር በልጁ በኩል በዚህ በመጨረሻው ዘመን ያቋቋመውን "ሐዲስ ኪዳንን" የሚተካ ነው የሚል ነው፡፡ ቅዱሳን ያልሆኑ ነፍሳት ይድኑ ዘንድ በሕይወተ ሥጋ ያሉ ወገኖቻቸው እንዲጸልዩላቸውና የሚጸልዩላቸው ሰዎች ሥርየትን እንዲገዙላቸው በውሳኔው ተያይዞ ተላለፈ፡፡" (ሙራ ቁ. 12፣ ገጽ 23-24)
- "ሰው ይድንበት ዘንድ ለሰው የተሰጠ ብቸኛ መድኃኒት ጌታ ኢየሱስ ነው፡፡ እርሱን የሚመስልና የሚያህል ሌላ የለም፡፡ ቅዱሳን የምንላቸው በእርሱ አዳኝነት የዳኑትን ሁሉ ነው፡፡ እነዚህም ቅዱሳን ሲባሉ የበቁት በሥራቸው ሳይሆን ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ከኢጋው የተነሣ ስለ ቀደሳቸው ብቻ ነው፡፡ በእርሱ የዳኑትን ከአዳኛቸው ጋር በእኩል ማስቀመጥ ካለማወቅና ካለማስተዋል የሚነሳ ስህተት ነው፡፡ . . . በተጨማሪም ጌታ ኢየሱስ የሁሉ ፈጣሪና እውነተኛ አምላክ ነው፡፡ በሙሉ ሕይወታቸው ሊነግሡ ሲገባቸው በሥጋ በመገለጡ ብቻ ከፍጡራን እኩል በልብ ውስጥ ትንሽ ጎጆ በክፍያ እንዲደርሰው ያደርጋሉ፡፡" (ሙራ ቁ. 16፣ ገጽ 7)

> ተሐድሶዎች፣ በአንድ በኩል "ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነቱን ብቻ ያጎላሉ፣ እንደ እኛ ፍጹም ሰው መሆኑን ዘንግተውታል" በማለት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው፣ ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ ዘዕሩይ ምስሌነ በትስብእቱ ብላ ማምለኳን ይነቅፋሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ "በሥጋ በመገለጡ ብቻ ከፍጡራን እኩል በልብ ውስጥ ትንሽ ጎጆ በክፍያ እንዲደርሰው ያደርጋሉ" በማለት ከፍጡራን እኩል አድርጋችሁ አያችሁት ይላሉ፡፡ የሁለቱን ሃሳቦች ተቃርኖ እነርሱ ራሳቸው ባይረዱት ነው? ወይስ የሚያውቅብን አይገኝም ብለው ይሆን?

- "የኦተቤ ምእመናን እንደ ማንኛውም ሰው ኃጢአተኞች መሆናቸውን ያምናሉ፣ ቅዱስ በሆነው በእግዚአብሔር የፍርድ ዙፋን ፊት ለመቆም ብቃት እንደ ሌላቸውም ይረዳሉ፡፡ ስለሆነም ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቃሉ (አማላጆች ይሆናሉ) የተባሉትን ይማጸኑ ዘንድ ይገደዳሉ፡፡ ታዲያ ለብዙ ዘመናት በሰይጣንና በአዋልድ ደራስያን ጥበብ የተሰበከና በደማቸው ውስጥ ጠልቆ ገብቶ የተዋሐዳቸውን የቅዱሳን አማላጅነት ትምህርት መቃወምን መዳን ኢየስፈልጋችሁም የማለትን ያህል ይቆጥሩታል፡፡" (ኖኅተ ብርሃን፣ ገጽ 7)

## ተሐድሶዎች በቅዱሳን አማላጅነት ዙሪያ የሚያነሷቸው ውሸቶችና ስህተቶች

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት የተሐድሶዎች ትምህርቶች ላይ ያሉ ዋና ዋና ውሸቶችና ስህተቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

### 1) የክርስቶስን ቤዛነትና አዳኝነት ከቅዱሳን አማላጅነት ጋር ማምታታትና ማደባለቅ፤

ሐሰትና ማምታታት የተለመደ ስልታቸው መሆኑ በየጉዳዩ ፍጥጥ ብሎ ይታያል፡፡ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን መሠረተ እምነት ላይ የሚነቅፉትና በተጨባጭ የሚታቀርቡት ስህተት ከማጣታቸው የተነሣ ቤተ ክርስቲያኒቱ የማትለውን እንደምትል፣ የምታምነውን ደግሞ እንደማታምን አስመስለው በውሸት ማቅረቡ ዋናው ስልታቸው መሆኑ ከመጀመሪያ ጀምሮ እስካሁን ስናያቸው በመጣናቸው ጉዳዮች ላይ ሁሉ ግልጽ ሆኖ የሚታይ ነገር ነው፡፡ ደጋግመው የሚያቀነቅኑት እንዲህ እያሉ ነውና፦

- "ደግሞስ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅና ማማለድ ከቻሉ ለምን ኢየሱስ ክርስቶስ መውረድ መወለድ አስፈለገው?" (መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ ገጽ 43)
- "ፍጡር ለመዳንና ገነት መንግሥተ ሰማያት ለመግባት መታመንም ሆነ መመካት ርጉም መሆኑን ነቢዩ ኤርምያስ ተናግሯል፡፡" (መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ ገጽ 49)
- "የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ መሠዋትና መሞት በውርስ ከአዳም ለመጣ ኃጢአት ብቻ ነው ይላሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ዕለት ዕለት ስለሚሠሩት ኃጢአት ከኢየሱስ ክርስቶስ የተለየ አዳኝ ወይም ከኃጢአት የሚያነጻ ሌላ ኃይል ይፈልጋሉ፤ ያበጃሉ፡፡" (ሙራ ቁ. 6 ፣ገጽ 6)፣ (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 30)
- ". . . የእርቁን አዋጅ ስሙና ኑ ታረቁኝ እያለ እግዚአብሔር በወንጌላውያን በኩል እየማለደ ሳለ፣ አይ ልጅህ በፈጸመው ሥራ አልታረቅም፤ ሌላ አስታራቂ እፈልጋለሁ ለሚል ሰው ኸረ ምን መፍትሔ ይገኛል?" (ሙራ ቁ. 8 ገጽ 32)
- "ሰው የሆነበትን ዓላማ ዘንግተው ስለ ቀድሞው ኃጢአታችን ከሞተልን በኋላ አሁን ለምንሠራው ኃጢአት በክርስቶስ ሳይሆን በሌሎች ነው የምንታረቀው ብለው ሌላ አዲስ መሠረት መሥርተዋል፡፡ ነገር ግን ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ አዲስ መሠረት ሊመሠርት አይችልም፤ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡" (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 30)
- "አንባቢ ሆይ፣ በክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ከታረቅንና ከዳንን በኋላ ኃጢአት ሠርተን ብንገኝ ስለ ኃጢአታችን ከክርስቶስ በቀር ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት መንገድም ሆነ የሚቀርብልን መስዋዕት አለመኖሩን አስተውል!" (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 32)
- "እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታረቀ ሆኖ ሳለ፣ በማስታረቅ አገልግሎት የተመደቡ መልእክተኞችም ወደ ዓለሙ ሁሉ በመሔድ የዕርቁን ቃል እየሰበኩ ሳለ፣ እስካሁን ድረስ ገና እግዚአብሔርን በጠላትነት ለሚያዩ፣ አስታራቂ ፍለጋ በዱር በገደል ለሚንከራተቱና አስታራቂ ያጡ መስሏቸው ተስፋ ለቆረጡ ሁሉ . . ." (ሙራ ቁ. 11፣ ገጽ 5)
- "በአሁኑ ሰዓት በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል በኢየሱስ ክርስቶስ የተያዘውን የማስከላዊነት፣ የአስታራቂነት፣ የአማላጅነት ሥራ ያከናውናሉ፡፡ ደህንነትም የኢየሱስ ክርስቶስን ቤዛነት በመቀበል ሳይሆን ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ናቸው በምትላቸው ነፍሳት አማላጅነት በመማፀን ሆኗል፡፡ በእግዚአብሔር የማያምን ቢሆን በእነርሱ ከተማጸነ የሚድንበት ቃል ኪዳን ለቅዱሳን ነፍሳት ተሰጥቷል፤ ይህም ቃል ኪዳን እግዚአብሔር በልጁ በኩል በዚህ በመጨረሻው ዘመን ያቋቋመውን "ሐዲስ ኪዳንን" የሚተካ ነው የሚል ነው፡፡" (ሙራ ቁ. 12፣ ገጽ 23-24)
- "ሰው ይድንበት ዘንድ ለሰው የተሰጠ ብቸኛ መድኃኒት ጌታ ኢየሱስ ነው፡፡ እርሱን የሚመስልና የሚያህል ሌላ የለም፡፡ ቅዱሳን የምንላቸው በእርሱ አዳኝነት የዳኑትን ሁሉ ነው፡፡ በእርሱ የዳኑትን ከአዳኛቸው ጋር በእኩል ማስቀመጥ ካለማወቅና ካለማስተዋል የሚነሳ ስህተት ነው፡፡" (ሙራ ቁ. 16፣ ገጽ 7)

ቅዱሳን ጸሎታቸው ይጠቅማል፣ ያማልዳሉ ማለትን ኢየሱስ ክርስቶስ ከፈጸመው እርቅና መዳን ጋር አምታትተውና አዘበራርቀው በማቅረብ ሰዎችን ግራ ለማጋባት ሞክረዋል፡፡ ይህም "ማሳመን ካልቻልክ ቢያንስ ግራ አጋባ"[112] እንደሚሉት ዓይነት ስልት መሆኑ ነው፡፡ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነትና በአጠቃላይ ስለ መዳን ያለን አስተምህሮና እምነት ከላይ ይህን በተመለከተው ክፍል የተገለጸው ስለሆነ እነርሱን ይመስል አንድን ጉዳይ በየቦታው አሥር ጊዜ አንደጋግምም፡፡ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እነርሱ እንደሚሉት እግዚአብሔርን በጠላትነት አታይም፡፡ እግዚአብሔርን "አባታችን፣ አምላካችን፣ መድኃኒታችን፣ ተስፋችን" እያለች በልጅነት መንፈስ ትጠራዋለች፣ ታከብረዋለች እንጂ ጠላት አትለውም፡፡ "መካር ከእናትና ከልጅ መካከል ይገባል" እንደሚባለው ቤተ ክርስቲያኒቷ ከእግዚአብሔር ጋር ባላት ግንኙነት ገብተው በኑፋቄ በቆሸሸና ባልታጠበ እጃቸው እንፈትፍት ሲሉ ትንሽ እንኳ ፍርሃትና ሲጋት አይሰማቸውምን? ልጆቿም አስታራቂ ፍለጋ በዱር በገደል አይንከራተቱም፣ አስታራቂ ያጡ መስሏቸውም ተስፋ አልቆረጡም፡፡ የራሳቸውን የመንፈስ መንከራተትና ተስፋ መቁረጥ ለምን የሌሎች አስመስለው ለማቅረብ ይሞክራሉ? ከአንዱ የፕሮቴስታንት ዲኖሚኔሽን ወደ ሌላው እየተንከራተቱና የተሻለ ጥቅማ ጥቅም ወደሚገኝበት እየተገለባበጡ አሥር ጊዜ በየድርጅቱ "እየተጠመቁ" ያሉት ራሳቸው መሆናቸው የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡ ለዚህም "ትሪኒቲ" በተባለው የፕሮቴስታንት መጽሔት ላይ የወጣው ሙሴ የተባለው ግለሰብ ለዚህ ምስክር ነው፡፡ ብሶታቸውን መግለጽ ካስፈለጋቸው በሌሎች ሳያሳብቡ መናገር ይችላሉ፡፡

እስኪ እዚህ ላይ ተሐድሶ ወገኖቻችንን አንድ ጥያቄ እንጠይቃቸው፡፡ ቅዱሳን ጸሎታቸው ይረዳል፣ ያማልዳሉ ማለት "ሌላ አዳኝ ፍለጋ"፣ "ሌላ የመዳኛ መንገድ ፍለጋ" ነው ካሉ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የፊልጵስዩስ ምእመናንን "ወደ ፊትም ደግሞ ደስ ይለኛል፤ <u>ይህ በጸሎታችሁና በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ መሰጠት ለመዳኔ እንዲሆንልኝ አውቃለሁና</u>" ሲል ከክርስቶስ ውጭ ሌላ የመዳኛ መንገድ መፈለጉ ኖሯልን? ፊል. 1፥19 እንዲሁም የተሰሎንቄ ክርስቲያኖችን "<u>ወንድሞች ሆይ፣ ስለ እኛ ጸልዩ</u>" ማለቱስ ሌላ አዳኝና መሥዋዕት መፈለጉ ኖሯልን? 1 ተሰ. 5፥25 እንዲሁም "ወንድሞች ሆይ፣ ስለ እኔ ወደ እግዚአብሔር እየጸለያችሁ ከእኔ ጋር ትጋደሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ፍቅር እለምናችኋለሁ"፣ "እናንተም ደግሞ ስለ እኛ እየጸለያችሁ አብራችሁ ስትረዱን. . ." እያለ ደጋግሞ መናገሩ "ሌላ የመዳኛ መንገድ ፍለጋ" ኖሯል ሊሉን ይሆን? ሮሜ 15፥30፤ 2 ቆሮ. 1፥10 ይህን የመሰለ ብዙ ቃል በቅዱስ ጳውሎስ መልእክታትም ሆነ በሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እናገኛለን፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብስ በመልእክቱ "ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች" ብሎ የጻፈልንና ያስተማረን "ሌላ ፈዋሽ ፍለጋ" ኖሯልን? ያዕ. 5፥16 አንዱ ለሌላው መጸለይ ማለት፣ እንዲሁም ቅዱሳን ስለ እኛ በጸሎታቸው ይረዱናል፣ አማላጅነታቸው ይጠቅመናል ማለት፣ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ "ስለ እኔ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩልኝ" ማለት ከክርስቶስ ውጭ፣ ያለ ክርስቶስ አስፈላጊነት ያድኑናል ማለት ነው ብሎ የነገራችሁ ማን ነው? በጣም አሳዛኝ የሆነ የተጣመመ አስተሳሰብ ነው!

የኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነትና የቅዱሳን አማላጅነት ግን በየፈርጁ የሚታይ እንጂ የሚደባለቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ ማዳን የእግዚአብሔር ነው፤ ምልጃ ደግሞ የፍጡራን ተግባር ነው፡፡ እግዚአብሔር አብ በአንድ ልጁ በኩል በመንፈስ ቅዱስ የፈጸመውን መዳን ቅዱሳን ወደ እርሱ ከሚያቀርቡት የምልጃ ጸሎት ጋር ማደባለቅና ማምታታት ወይ እነዚህን ነገሮች ለይቶ ለማወቅ አለመቻል ነው፤ አለዚያም ደግሞ ሆን ብሎ ሰዎችን ለማታለል የሚያደርጉት ተንኮል ነው፡፡ ይህንም በሚቀጥሉት ርእሰ ጉዳዮች በተከታታይ እናየዋለን፡፡

---

[112] (If you cannot convince, at least confuse)

2) በቅዱሳን አማላጅነትና ጸሎት መታመንን በክርስቶስ አዳኝነት አለማመን አስመስሎ ማቅረብ፣

ሲጀመር በቅዱሳን አማላጅነት የሚታመኑ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት የሚያምኑት ናቸው እንጂ በክርስቶስ ያላመኑ አረመኔዎች አይደሉም፡፡ በመጀመሪያ በጸሎታቸው ይረዱናል የምንላቸው ቅዱሳን "ቅዱሳን" የሆኑት በክርስቶስ ነው፡፡ እነዚህ ቅዱሳንም የሚማልዱት ሌላ ማንንም ሳይሆን እግዚአብሔርን ነው፡፡ እግዚአብሔር ግን ጸሎትና ምልጃ ሁሉ የሚቀርብለት አባትና ፈራጅ እንጂ ማላጅ (አማላጅ) አይደለም፡፡ ስለዚህ እንደ እነርሱ የፈጣሪንና የፍጡራንን ተግባር አናዘበራርቅም፡፡ እነርሱ ግን እንደ እነርሱ ሳያዘበራርቅ ለይቶና አጥርቶ የሚያምን ሁሉ የተሳሳተ ይመስላቸዋል፡፡

3) ቅዱሳን ያማልዳሉ ማለትን እግዚአብሔር ሰዎች ካልነገሩት የማይሰማ፣ እስኪሚነግሩት ድረስም የሚጠብቅ ነው ማለት እንደሆነ ማስመሰል፣

◉ "ደግሞስ እግዚአብሔር እንደ ምድራዊ ንጉሥ በአንድ ወንበር ላይ ጉች ብሎ የሚቀመጥ፣ መልእክተኞች እስካላደረሱለት ድረስ የማይሰማ፣ የማያይ አምላክ ነውን? መላእክት እስኪነግሩት ድረስ ጸሎታችንንም ወደ እርሱ እስኪያደርሱለት ድረስ የሚጠብቀው?" ("መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ ገጽ 29)

◉ "መላእክት ከእግዚአብሔር ወደ ሰው የሚላኩ መልእክተኞች እንጂ ከሰው ወደ እግዚአብሔር የሚላኩ አይደሉም፡፡ እግዚአብሔር ልብ ያሰበውን ኩላሊት ያመላለሰውን ያውቃል ብለን ነው የምናስተምረውና፡፡" (መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ ገጽ 50)

*በመጀመሪያ፦* እግዚአብሔር አንዱ ስለ ሌላው እንዲጸልይ ማዘዙ እርሱ ካልነገሩት ስለማይሰማ ኖሯልን? ራሱ እግዚአብሔር አቤሜሌክ ንጉሡ ጌራራን "ነቢይ ነውና ስለ አንተም ይጸልያል፣ ትድናለህም" ያለው አብርሃም ስለ አቤሜሌክ እስኪነግረው ድረስ የማያውቅ አምላክ ስለሆነ ነበረን? እንዲሁም መድኃኒታችን ደጋግሞ "ወደ ፈተና እንዳትገቡ ጸልዩ" እያለ ያስተማረን እኛ ካልነገርነው ስለማያውቅ ነበርን? ጌታችን በማይታበል ቃሉ "ለምኑ፣ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፣ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፣ ይከፈትላችሁማል" ያለውስ እኛ ካልተናገርን የሚሰጠንን ስለማያወቅ ነውን? ማቴ. 7፥7 ይቅር ይበለን! በነቢዩም "እናንተም ትጠሩኛላችሁ፣ ሄዳችሁም ወደ እኔ ትጸልያላችሁ፣ እኔም እሰማችኋለሁ". ይላል፡፡ ኤር. 29፥12 እንግዲህ ይህ ሁሉ የሚያስረዳን እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ከመሆኑ አስቀድሞ፣ ከመሆኑ ብቻም ሳይሆን ከመታሰቡ አስቀድሞ የሚያውቅ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም ነገር ግን እኛ እንድንለምነውና በልመናችን መሠረት ሊሰጠን ቃል የገባ መሆኑን ነው፡፡ ይህም ለምነነው ስንቀበል ያ የተቀበልነውን ነገር ያገኘነው ከእርሱ መሆኑን እንድናውቅና በዚህም ሰጪያችንን እርሱን አውቀን እንድናመሰግነው፣ የእርሱ ፍቅር እንዲያድርብንና ለልቡናችን የተረዳ እንዲሆን ለእኛው ጥቅም ሲል ነው፡፡ የእኛ ምስጋና ለእርሱ የሚጠቅመውና የሚጨምርለት አንዳችም ነገር የለም፣ ስጦታውንና ቸርነቱን አውቀን ብናመሰግን ጥቅሙ ለእኛ ለራሳችን ብቻ ነው፡፡ እንዲህ ሆኖም ሳንለምነው የሚሰጠን ብዙ ነገር መኖሩም የታወቀ ነው፤ "ወዘእንበለ ንስእሎ ይሁብ ፍትወተነ - ሳንለምነው የሚያስፈልገንን ይሰጠናል፣ ያደርግልናል" እንዲል፡፡ ለማያውቁትና ለማያምኑት ሁሉ በአምላክነቱ ፀሐይን እያወጣ ዝናምን እያዘነመ ማያትን እያፈሰሰ አየሩን እያፈነሰ . . . ይመግባል፡፡

ታዲያ እኛ በጸሎት እግዚአብሔርን መጠየቃችን ካልነገርነው በስተቀር የማያውቅ ስለሆነ ሳይሆን በጸሎት ጠይቀን ማግኘት የሚገባንና የሚጠቅመን በመሆኑ ምክንያት ከሆነ ቅዱሳን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡት የምልጃ ጸሎት ከዚህ የተለየ "እግዚአብሔርን ካልነገሩት የማይሰማ፣ እስኪሚነግሩት ድረስም የሚጠብቅ" የሚያሰኘው ምን ነገር ተገኘበት? መላእክት ወደ እርሱ ጸሎታችንን እስኪያደርሱለት ድረስ ይጠብቃል የሚያሰኝ አንዳችም ነገር የለም፡፡

ሁለተኛ፦ "መላእክት ከእግዚአብሔር ወደ ሰው የሚላኩ መልእክተኞች እንጂ ከሰው ወደ እግዚአብሔር የሚላኩ አይደሉም፡፡ እግዚአብሔር ልብ ያሰበውን ኩላሊት ያመላለሰውን ያውቃል ብለን ነው የምናስተምረውና" የሚለው አባባል በተሳሳተ መነሻ ላይ ተነሥቶ ከተሳሳተ ድምዳሜ ላይ የደረሰ ሃሳብ ነው፡፡ ቅዱሳን መላእክት ከእግዚአብሔር ወደ ሰው የሚላኩ ብቻ ሳይሆኑ ከሰውም ወደ እግዚአብሔር ይላካሉ፡፡ ሲጀመር እግዚአብሔር መላእክትን ወደ ሰዎች የሚልከው የግድ መላእክት አስፈልገውት አይደለም፡፡ እርሱ ያለ መላእክት ሰውን ማነጋገር የማይችል ወይም የማይፈልግ አይደለምና፡፡ ሆኖም ግን እግዚአብሔር በባሕርዩ ቸርና ፍጥረቱን በሥራው ውስጥ አሳታፊ አምላክ ስለሆነ ቅዱሳን መላእክትን ወደ ሰዎች ይልካቸዋል፡፡ ሰዎችን እንዲጠብቁም ያደርጋቸዋል፤ ሆኖም እግዚአብሔር እኛን ለመጠበቅ የግድ መላእክት አያስፈልጉትም፡፡ ነገር ግን እነርሱን በጠባቂነትና በተራዳኢነት፤ እኛን ደግሞ በተጠባቂነት አንድ ማኅበር እንድንሆን አደረገ፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ ይህን ሲገልጽ ". . . መላእክት . . . ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?" ይላል፡፡ ዕብ. 1፥14

እንዲሁም ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔርን መልእክት ወደ ሰዎች ይዘው የሚመጡ ብቻ ሳይሆኑ የሰዎችን ጸሎትም ወደ እግዚአብሔር ያሳርጋሉ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ተብሏልና፦

> ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ፤ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሠዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው። <u>የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ</u>። ራእ. 8፥3-4

እንግዲህ ይህ ቃል በግልጽ እንደሚነግረን የቅዱሳን ሰዎች ጸሎት በመልአኩ አማካይነት ወደ እግዚአብሔር መውጣቱን (ማረጉን) ነው፡፡ እንዲሁም "አራቱ እንስሶችና ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በበጉ ፊት ወደቁ፤ እያንዳንዳቸውም በገናንና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ" ይላል፡፡ ራእ. 5፥8 ስለዚህ "መላእክት ከእግዚአብሔር ወደ ሰው የሚላኩ መልእክተኞች እንጂ ከሰው ወደ እግዚአብሔር የሚላኩ አይደሉም" የሚለው አባባል ስሁተት ነው፡፡ ከዚያ በመቀጠል "እግዚአብሔር ልብ ያሰበውን ኩላሊት ያመላለሰውን ያውቃል ብለን ነው የምናስተምረውና" የሚለው አባባላቸው ቅዱሳን መላእክት የሰዎችን ጸሎትና ልመና ወደ እግዚአብሔር ያሳርጋሉ ማለትን እግዚአብሔር መላእክት ወስደው ካልነገሩት በስተቀር አያውቅም አይሰማም እንደ ማለት አስመስሎ ማቅረብ ወይ ፍጹም አላዋቂነት ነው፤ አለዚያም አስመሳይነትና ተንኮለኛነት ነው፡፡

4) "የቅድስና መለኪያውና መመዘኛው ሰዎች ናቸው" ማለታቸው፤

- "አንዱ በሌላው ሕይወት ተለክቶ የተሻለ ሆኖ መገኘትን በቂና ፍጹም አድርጎ አይመዘግብልንም፡፡ በመውደቅና በመነሣት ውስጥ ከሚያልፍ ሕይወት የተገኘ ቅድስና፤ በሰዎች መካከል በሚፈጠር መመጻደቅና ማነጻጸር እገሌ ጻድቅ ነው፤ አንተ ቅዱስ ነህ ለመባባል ቢያበቃ እንጂ በእግዚአብሔር ቅድስና ተለክቶ ፍጹምነትን አያስገኝም፤ አያሰጥም፡፡" (ሙራ ቁ. 12፤ ገጽ 22)

- "ቤተ ክርስቲያን በቅዱስነት የመዘገበቻቸው ምእመናን ነፍሳት ሁሉ ቅዱሳን ናቸው፡፡" (ሙራ ቁ. 12፤ ገጽ 23-24)

ይህ ከአላዋቂነት አለዚያም ያልሆነ መልክ ለመስጠት ከማሰብ የተወለደ ስሁተት ነው፡፡ በመጀመሪያ ቅድስና ራሱ ልዑለ ባሕርይ ቅዱስ እግዚአብሔር "እኔ ቅዱስ እንደ ሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ" ብሎ በከፈተው የቅድስና በር መሠረት የሚገኝ እንጂ በሰው ፈጠራ ወይም ምኞት ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡ ስለዚህ የቅድስና መለኪያው የሰዎች ሕይወት ሳይሆን እግዚአብሔር የሰጠው የቅድስና ጸጋ ነው፡፡ አንዱ ከአንዱ እየተለካ እገሌ ከእገሌ ይበልጣል ወይም ይሻላል እየተባለ የሚሰጥ ቅድስና በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ የለም፤ ኖሮም አያውቅም፡፡ "በሰዎች መካከል በሚፈጠር መመጻደቅና ማነጻጸር እገሌ ጻድቅ ነው፤ አንተ ቅዱስ ነህ ለመባባል ቢያበቃ እንጂ . . ."

ያሉት ጨርሶ በቤተ ክርስቲያናችን የሌለ ነገር ነው፡፡ ቅዱሳን ራሳቸውን እንኳን ቅዱሳን አድርገው ሊቆጥሩና እንዳቸውን ከሌላቸው ሊያወዳድሩና ደረጃ ሊያወጡ ይቅርና ሁል ጊዜም ኃጢአተኛነታቸውን እያሰቡና የእግዚአብሔርን ገጸ ምሕረት እየተማጸኑ የኖሩና የሚኖሩ ናቸው፡፡

ራሳቸውን እንደ ጻድቅ አድርገው እንዲቆጥሩ የሚያሳስብ ሃሳብ ሲመጣባቸው እንኳ ያን ሃሳብ የሚቆጥሩት እንደ ከባድ ፈተና ነበር፡፡ ታላቁ ቅዱስ እንጦንዮስ እንኳ በአንድ ወቅት "አቤቱ ፈጣሪዬ ሆይ፣ እኔ ኃጢአተኛና የማልረባ ሰው ስሆን እንደ ጻድቅ አድርገው ከሚያስቡኝ ሰዎች አድነኝ" ብሏል፡፡ እንኳንስ "እኔ ቅዱስ ነኝ፣ ደረጃዬ ይሄ ነው" ሊሉ ይቅርና ሰይጣን ተገልጦ "በትሕትናህ አሸነፍከኝ" ሲላቸው እንኳ እንዲህ ያለውን ሃሳብ ሳይቀር ሲጋደሉና ሲጠነቀቁ የኖሩ ናቸው፡፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቅዱሳን ራሳቸውን "ጭንጋፍ"፣ "ትል"፣ "ከሁሉ የማንስ"፣ ወዘተ ይላሉ እንጂ ራሳቸውን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ነገር አይሉም፡፡ ራሳቸውን በእውነት የሚያዋርዱትን ቅዱሳን አገልጋዮቹን ራሱ ባለቤቱ እግዚአብሔር ደግሞ "ምርጥ ዕቃ"፣ "እንደ ልቤ የሆነ"፣ "ሴቶች ከወለዷቸው ከእርሱ የሚበልጥ የሌለ" ወዘተ እያለ ያከብራቸዋል፣ ክብራቸውንም ይገልጣል፡፡

እንዲሁም በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን እገሌ ጻድቅ ነው፣ እገሌ ኃጥእ ነው ብሎ የመፈረጅና የመወሰን ባህል የለም፡፡ ይህ የቤተ ክርስቲያን ባሕርይዋም ሥልጣኗም አይደለምና፡፡ የቤተ ክርስቲያን ድርሻዋና ተልእኮዋ ሰዎች የእግዚአብሔርን ጸጋ ያገኙ ዘንድ ማስተማር፣ ከዚያም ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መፈጸምና ተጋድሏቸውን ፈጽመው ወደ መንፈሳዊው ዓለም እስኪሄዱ ድረስ መምራትና መርዳት እንጂ "ኃጥእ"፣ "ጻድቅ" እያለች መፈረጅና ደረጃ መመደብ አይደለም፡፡ ይህ ዓይነቱ ባህል በተለይም ከሞቱ በኋላ ለሰዎች የብፅዕና (beatification)፣ ከዚያም የቅድስና መዓርግ የመስጠት ቀኖና (*canonization*) ያለው በካቶሊካውያን ዘንድ ነው፡፡[113]

በእኛ ዘንድ ግን የሃይማኖት ተጋድሏቸው የጎላና ሕይወታቸውና ትምህርታቸው እንደ አጥቢያ ኮከብ ደምቀው እንዲታዩ ያደረጋቸው፣ እግዚአብሔር እርሱ ባወቀ ለትምህርትና ለአብነት እንዲሆኑን ጎልተው እንዲታወቁ ያደረጋቸውን ቅዱሳን ስማቸው በጸሎተ እኩቴት ጊዜ የሚጠራና በአማላጅነታቸው እንዲያስቡን የምንለምናቸው የተወሰኑ ቅዱሳንን እናውቃለን እንጂ የቅዱሳን ሁሉ ስምና ቁጥር በቀኖና የሚዘረዘርና የሚወሰን አይደለም፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ኮከብ እምኮከብ ይኄይስ ክብሩ - የአንዱ ኮከብ ክብር ከሌላው ይበልጣል" በማለት በምሳሌ እንደ ገለጸው በጣም ጎላ ያሉት የተወሰኑ ቅዱሳን ብቻ ይታወቃሉ፡፡ በቤተ ክርስቲያንም በዘመናት ውስጥ በተጋድሏቸውና በሕይወታቸው ጎላ ላሉና ለአርአያ ለሚሆኑ አንዳንድ ቅዱሳን ልዩ ልዩ እውቅና ሊሰጣቸው ይችል ይሆናል፡፡ ከዚያ ውጭ ግን "ወበኀቤየሰ ፈድፋደ ክቡራን አእርክቲከ እግዚአ ወፈድፋደ ጸንዐ እምቀደምቶሙ እኊልቆሙ እምኆፃ ይበዝሁ - ወዳጆችህ በእኔ ዘንድ እንደ ምን እጅግ የተከበሩ ናቸው! ቊጥራቸውም እንደ ምን በዛ! ብቈጥራቸው ከአሸዋ ይልቅ ይበዛሉ" ተብሏልና ቅዱሳን ወዳጆቹን እነ ማን እንደ ሆኑና የት እንዳሉ የሚያውቃቸው ባለቤታቸው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ መዝ. 138፥17-18

የቅዱሳን ክብራቸው የሚወሰነውም በዚህ ዓለም ባሉ ሰዎች ዘንድ በመታወቃቸውና ባለመታወቃቸው የተመሠረተ እንዳልሆነ እናውቃለን፡፡ ስለሆነም "ቤተ ክርስቲያን በቅዱስነት የመዘገበቻቸው ምእመናን ነፍሳት" ያላችሁት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የማይመለከት ልማድ ነው፣ ሐሰት ነው፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በጎቹንና ፍየሎቹን ለይቶ የሚያውቀው እውነተኛው እረኛ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ታውቃለችና፡፡

---

[113] Catholic Encyclopedia, www.catholic.org/encyclopedia.

ከዚሁም ጋር እግዚአብሔር የሚሰጠው ይህ ቅድስና ሰዎች በነጻ ፈቃዳቸው ከሚሆን ምርጫቸውና ፍላጎታቸው ጀምሮ በጥምቀት ካገኙት ጸጋ በመነሣት በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሱታፌና የተለያዩ መንፈሳዊ ተጋድሎዎችን በመጋደል በሂደት የሚያገኙት እንጂ እንዲሁ እንደ ተሐድሶዎች ዝም ብለው "አንድ ጊዜ ድኛለሁ" እያሉ በማውራት ብቻ ከመሬት ላይ የሚታፈስ አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ከአንዱ ምግባር ወደ ሌላው እያደግንና ከፍ እያልን እንሄድ ዘንድ ያስተምረናል እንጂ እንዲሁ ተዘልለን እንድንቀመጥ አይነግረንምና፡፡ ለአብነትም እንዲህ የሚለውን ቅዱስ ቃል እንመልከት፡-

> *ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፤ በበጎነትም እውቀትን፤ በእውቀትም ራስን መግዛት፤ ራስንም በመግዛት መጽናትን፤ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፤ እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፤ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ። እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ሆነው ቢበዙ፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ሥራ ፈቶችና ፍሬ ቢሶች እንዳትሆኑ ያደርጓችኋልና፤ እነዚህ ነገሮች የሌሉት ዕውር ነውና፤ በቅርብም ያለውን ብቻ ያያል፤ የቀደመውንም ኃጢአቱን መንጻት ረስቷል። ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፣ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ፤ እነዚህን ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉምና።* 2 ጴጥ. 1፡5-10

እነዚህን ለማግኘት ትጋት ያስፈልጋል ተብሎ እንጂ እንዲሁ ራሳቸው በራሳቸው ጊዜ ወደ እናንተ ይመጣሉ፤ እናንተ ግን እንዲሁ ዝም ብላችሁ ተኙ አልተባልንም፡፡ ይህ የአሳናፊው የዲያብሎስ ክፉ ምክር ብቻ ነው፡፡

### 5) ቅዱሳንን እና መላእክትን መጥራትን ርኩሳን መናፍስትን ከመጥራት ጋር አንድ አስመስሎ ማቅረብ

- *"መናፍስትን እንዳንጠራ ከተከለከልን መናፍስት በምን ሁኔታ ወደ ሰው ይመጣሉ? በመናፍስትነት የምናውቃቸው መላእክት እና የወደቀው ሰይጣንና ተከታዮቹ ናቸው፡፡ የወደቁትንም ሆነ ያልወደቁትን መናፍስት (መላእክትን) እንድንጠራ አልተፈቀደም፡፡ ዘዳ. 18፡9-12 መናፍስትንና የሞቱ ሰዎችን ነፍሳት መጥራት ማሟረት ነው፡፡ ሙታን በሕይወተ ሥጋ በነበሩበት ጊዜ ይፈጽሙት የነበረውን አስነዋሪ ተግባር ያልሞቱ ዘመዶቻቸው እንዳይሠሩ ለመምከር እንኳ አይችሉም፡፡ ሉቃ. 23፡42-43 ራእ. 6፡9-11 ሉቃ. 16፡22-30"* (ሎሌ ቁ. 3፤ ገጽ 23-24)
- *"በአምልኳቸው ውስጥ የእግዚአብሔር ስም አልፎ አልፎ ቢጠራም የአምልኳቸው ከፍተኛው ክፍል መናፍስትንና የሙታንን ነፍሳት በመጥራትና በማጠን የድንጋይ፣ የእንጨት፣ የብረታ ብረት ሥዕሎችን ምስሎችንና ቅርጾችን በመሳለም ለየተራራዎችና ኮረብታዎች ለቅርሳ ቅርስ ሥራዎችም አምልኮ ስግደትና ልመና በማቅረብ የተያዘ ነው፡፡ ከአረማውያን የተወረሰ አምልኮ ባዕድን ከክርስትና መሰል ባህለ ሃይማኖት ጋር ቀላቅለው ፍናፍንት ለሆነ የአምልኮ ሥርዓት ይገዛሉ፡፡"* (ሎሌ ቁ. 6፤ ገጽ 6)

አሁንም እንደ ተለመደው በሐሰት ፍረጃ ግራ ለማጋባትና ለማሳሳት ሞክረዋል፡፡ ይህም በአንድ በኩል "መናፍስትን መጥራት ስህተት ነው" በማለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ "መናፍስት" የሚለውን ቃል ከርኩሳን መናፍስት ጋር ብቻ በማቆራኘትና ክፉ መልክ በመስጠት፤ እንዲሁም "በመናፍስትነት የምናውቃቸው መላእክት እና የወደቀው ሰይጣንና ተከታዮቹ ናቸው" በማለት ነው፡፡

እኛን ሰዎችን ቅዱሳን አትበሉ፤ አታክብሩ፤ ሰዎችን ማክበር እግዚአብሔርን ክብር መዘንጋትና ፍጡር ማምለክ ነው ይሉናል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት ደግሞ እነርሱም በእኛ መንገድና ዓላማ ሄደውልናል ብለው ለሚያስቧቸው ሰዎች ይህንኑ ያለ ገደብ ያሸርጎደጉዱላቸዋል፡፡ ለአብነትም በሎሌ መጽሔት ቁጥር 18 የሽፋን ገጽ ላይ "<u>ብፁዕ ወቅዱስ ዓምደ ሃይማኖት ማኅቶተ ቤተ ክርስቲያን አብ እስጢፋኖስ</u>" ብለው አሞካሽተውታል፡፡እንዲሁም እንዲህ የተለያዩ መዓርጎችን

ከደራረቡለት ከዚሁ ሰው ገድል ነው ከተባለው መጽሐፍ ላይ በመጥቀስ እንዲህ ይላሉ፡- "ወይቤሎ ቅዱስ አንሰ ኢይሰግድ . . . ቅዱሱ (አባ እስጢፋኖስ) እንዲህ አለው . . . " (ጮራ ቁጥር 18) ለሌላ ሲሆን ስህተት፣ ለራስ ሲሆን ልክ! ይህ ሁለት ምላስ (Double standard) የሚባለው ኢአመክንዮአዊ አካሄድ ነው፡፡

ይህን ነጥብ በሚገባ ለመፈተሽ በመጀመሪያ "መንፈስ" የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን ለማለትና ምንን ለማመልከት ጥቅም ላይ እንደ ዋለ ማየት ይኖርብናል፡፡ በመቀጠልም "መናፍስት" ወደሚለው ቃል ምንነት እንሄዳለን፡፡ ምክንያቱም "መንፈስ" የሚለው ነጠላ ቃል ሲሆን "መናፍስት" የሚለው ደግሞ መንፈስ የሚለው ሲበዛ (ብዙ ቁጥር ሲሆን) ስለሆነ ነው፡፡ ስለሆነም መንፈስ የሚለውን ቃል ከተረዳን መናፍስት የሚለው ቃል የያዘውን ሃሳብ ብዙ ቁጥር የማድረግ እንጂ ሌላ እንግዳ ወይም ተቃራኒ ትርጉም ወይም ሐሳብ ሊያመጣ አይችልም፡፡

## በመጽሐፍ ቅዱስ "መንፈስ" የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለበት አገባብ

በመጽሐፍ ቅዱስ "መንፈስ" የሚለው ቃል የሚከተሉትን ነገሮች ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሎ እናገኘዋለን፡-

ሀ) የእግዚአብሔርን መንፈስ፣ መንፈስ ቅዱስን ያመለክታል፡-

- "ምድርም ባዶ ነበረች፣ አንዳችም አልነበረባትም፣ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፣ *የእግዚአብሔርም መንፈስ* በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር።" ዘፍ. 1፡2
- *"የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ፥* ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወት ሰጠኝ።" ኢዮ. 33፡4
- *"ከመንፈስህ* ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ?" መዝ. 138፡7
- "በእናንተ የሚናገር *የአባታችሁ መንፈስ* ነው እንጂ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁምና።" ማቴ. 10፡20
- "እኔ ግን *በእግዚአብሔር መንፈስ* አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች።" ማቴ. 12፡28

ለ) እግዚአብሔር የሚሰጠውን ጸጋ፣ እውቀት ያመለክታል

- "አንተም ካህን ሆኖ እንዲያገለግለኝ አሮን ቅዱስ ይሆን ዘንድ ልብስ እንዲሠሩለት *የጥበብ መንፈስ* ለሞላሁባቸው በልባቸው ጥበበኞች ለሆኑት ሁሉ ተናገር።" ዘጸ. 28፡3
- "በሥራ ሁሉ ብልሃት በጥበብም በማስተዋልም በእውቀትም የእግዚአብሔርን *መንፈስ* ሞላሁበት፡፡" ዘጸ. 31፡3
- "ሙሴም እጆቹን ስለ ጫነበት የነዌ ልጅ ኢያሱ *የጥበብን መንፈስ* ተሞላ፤ የእስራኤልም ልጆች ታዘዙለት፣ እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው አደረጉ።" ዘዳ. 34፡9

ሐ) ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ልዩ ኃይል

- "የእግዚአብሔርም መንፈስ በጌዴዎን ገባበት፣ እርሱም ቀንደ መለከቱን ነፋ፣ የአቢዔዝርም ሰዎች ተጠርተው በኋላው ተከተሉት።" መሳ. 6፡34

- "ወደ ሌሒ በመጣ ጊዜም ፍልስጥኤማውያን [ሶምሶንን] እልል እያሉ ተገናኙት። የእግዚአብሔርም መንፈስ በኃይል ወረደበት፣ ክንዱም የታሰረበት ገመድ በእሳት እንደ ተበላ እንደ ተልባ እግር ፈትል ሆነ፣ ማሰሪያዎቹም ከእጁ ወደቁ።" መሳ. 15፡14
- "ወደዚያም ኮረብታ በደረሰ ጊዜ [ሳኦልን] እነሆ የነቢያት ጉባኤ አገኙት፡፡ የእግዚአብሔርም መንፈስ በኃይል ወረደበት፣ በመካከላቸውም ትንቢት ተናገረ።" 1 ሳሙ. 10፡10

መ) ላመኑ የሚሰጥ፣ ላላመኑ ደግሞ የማይሰጥ ወይም የሚነሣ ጸጋ (ረድኤት) እግዚአብሔር

- "የእግዚአብሔርም መንፈስ ከሳኦል ራቀ" 1 ሳሙ. 16፡14
- "አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ፣ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፣ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ፣ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ።" ሕዝ. 36፡26

ሠ) በቅዱሳን ላይ ያደረ ጸጋ እግዚአብሔር

- "ኤልያስ ኤልሳዕን፦ ከአንተ ሳልወሰድ አደርግልህ ዘንድ የምትሻውን ለምን አለው፡፡ ኤልሳዕም መንፈስህ በእኔ ላይ ሁለት እጥፍ ይሆን ዘንድ እለምንሃለሁ አለ።" 2 ነገ. 2፡9
- "ከኢያሪኮም መጥተው በአንጻሩ የነበሩት የነቢያት ልጆች ባዩት ጊዜ፦ የኤልያስ መንፈስ በኤልሳዕ ላይ ዐርፏል አሉ። ሊገናኙትም መጥተው በፊቱ ወደ ምድር ተደፉ።" 2 ነገ. 2፡15

ረ) የሰው ሕይወት (ነፍስ)

- "የሕያዋን ሁሉ ነፍስ፣ የሰውም ሁሉ መንፈስ በእጁ ናት፡፡" ኢዮ. 12፡10
- "ወጥቶ የማይመለስ መንፈስ፣ ሥጋም እንደ ሆኑ አሰበ።" መዝ. 77፡39
- "መንፈስን ለማስቀረት በመንፈስ ላይ ሥልጣን ያለው ሰው የለም፣ በሞቱም ቀን ሥልጣን የለውም፣ በሰልፍም ሰንበቻ የለም፣ ኃጢአትም ሠሪውን አያድነውም፡፡" መክ. 8፡8
- "መንፈስም የፈጠርሁትም ነፍስ ከፊቴ እንዳይዝል ለዘላለም አልጣላም፣ ሁል ጊዜም አልቈጣም።" ኢሳ. 57፡16
- "በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም።" 1 ቆሮ. 2፡11

ሰ) የእግዚአብሔር አገልጋዮች፣ ቅዱሳን መላእክት

- "መላእክቱን መንፈስ የሚያደርግ፣ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል።" መዝ. 103፡4
- "ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?" ዕብ. 1፡14

ከዚሁም ሁሉ ጋር ራሱ እግዚአብሔር "መንፈስ" ተብሏል፡፡ ባለቤቱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል" እንዳለ። ዮሐ. 4፡24 ቅዱስ ጳውሎስም "ጌታ ግን መንፈስ ነው" ብሏል፡፡ እንዲሁም "መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ" ይላል፡፡ 2 ቆሮ. 3፡17-18

በሌላ በኩል ደግሞ መንፈስ የሚለው ቃል ርኩሳን መናፍስትን ለመግለጽም ተደጋግሞ ጥቅም ላይ ውሎ እናገኛለን፡፡

ስለዚህ መንፈስ የሚለው ቃል ራሱን እግዚአብሔርን፣ ቅዱስ የሆነውን የእግዚአብሔርን መንፈስ (መንፈስ ቅዱስን)፣ እንዲሁም እርሱ የሚሰጠውን ጸጋና ረድኤት፣ አገልጋዮቹ የሆኑ ቅዱሳን መላእክትን፣ የሰውን ሕይወት ወዘተ ሁሉ እንደየ አገባቡና እንደየ አጠቃቀሙ የሚገልጽ ነው እንጂ እንዲሁ ከርኩሳን መናፍስትና ከክፉ ኃይላት ጋር ብቻ የተቆራኘ ቃል አይደለም፡፡ ስለሆነም መንፈስን ቅዱስ ይሁን ርኩስ መንፈስ መለየት እንደሚገባን ቅዱስ መጽሐፍ ያስጠነቅቀናል፣ እንዲህ ሲል፦

> ወዳጆች ሆይ፣ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፣ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና። የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደ መጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፤ ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል፤ አሁንም እንኳ በዓለም አለ። 1 ዮሐ. 4፡1-3

መንፈስ የሚለው ቃል በዋናነት እነዚህን ያየናቸውን ነገሮች ሁሉ ሊገልጽ ይችላል፡፡ ግን የትኛውን ለመግለጽ ጥቅም ላይ እንደ ዋለ የምንለየው በአገባቡ ነው፡፡ መንፈስ ለሚለው ቃል ብዙ ቁጥር የሆነው "መናፍስት" የሚለው ቃልም ከዚህ የተለየ አገባብ የለውም፡፡ አንድ ነገር በነጠላና በብዙ ሲገለጽ የነገሩን መጠን (ብዛት) ይገልጻል እንጂ ከዚህ የተነሣ መሠረታዊ ሃሳቡ አይለወጥምና፡፡

ለአብነትም መንፈስ የሚለው ቃል በብዙው (መናፍስት በሚለው) ለክፉዎች መናፍስት መጠሪያነት ሲውል ከሚያሳዩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መካከል የተወሰኑትን እንመልከት፦

- ❖ "ወደ መናፍስት ጠሪዎችና ወደ ጠንቋዮች አትሂዱ፤ እንዳትረክሱባቸውም አትፈልጓቸው፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ።" ዘሌ. 19፡31
- ❖ "መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችንም በሚከተል፣ በሥራቸውም በሚያመነዝር፣ በዚያ ሰው ላይ ፊቴን አከብዳለሁ፣ ከሕዝቡም መካከል ለይቼ አጠፋዋለሁ።" ዘሌ. 20፡6
- ❖ "አስማተኛም፣ መተተኛም፣ በድግምት የሚጠነቍልም፣ መናፍስትንም የሚጠራ፣ ጠንቋይም፣ ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ።" ዘዳ. 18፡11
- ❖ "አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲያወጧቸው በርኩሳን መናፍስት ላይ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣቸው።" ማቴ. 10፡1
- ❖ "... በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል" 1 ጢሞ. 4፡1-2

መናፍስት የሚለው ቃል ቅዱሳን ለሆኑ የእግዚአብሔር አገልጋዮች መጠሪያነትና መግለጫ ሲውል ደግሞ

- ❖ "የነቢያትም መናፍስት ለነቢያት ይገዛሉ" 1 ቆሮ. 14፡32 እዚህ ላይ "መናፍስት" ያላቸው ምንድን ናቸው? መናፍቃን እንደሚሉት ወይ ርኩሳን መናፍስት አለዚያም መላእክት ናቸውን? ርኩሳን መናፍስት ናቸው የሚሉ ከሆነ ነቢያትን ምን እያሏቸው እንደ ሆነ ራሳቸው ይወቁ፡፡ አይ አይደለም፣ መናፍስት የተባሉት መላእክት ናቸው ካሉ ደግሞ "የነቢያት መላእክት ለነቢያት መላእክት ይገዛሉ" እንደ ማለት ይሆንባቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ ያልተጻፈ ማንበብ ነው፡፡

* "ስለ መላእክትም፡- መላእክቱን መናፍስት አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ ከቶ ለማን ብሏል?" ዕብ. 1፥7

* "ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?" ዕብ. 1፥14

እግዚአብሔር ራሱ "የመናፍስት አባት" ተብሎ ተጠርቷል፤ "ከዚህም በላይ የቀጡን የሥጋችን አባቶች ነበሩን እናፍራቸውም ነበር፤ እንዴትስ ይልቅ <u>ለመናፍስት አባት አብልጠን ልንገዛና በሕይወት ልንኖር በተገባን</u>?" ዕብ. 12፥9

## በእግዚአብሔር ዙፋን ያሉት መናፍስት ተብለዋል፤

"ዮሐንስ በእስያ ላሉት ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት፤ ካለውና ከነበረው ከሚመጣውም፥ <u>በዙፋኑም ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት</u>፥ ከታመነውም ምስክር ከሙታንም በኵር የምድርም ነገሥታት ገዥ ከሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን፥ በሰርዴስም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፡- <u>ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስትና</u> ሰባቱ ከዋክብት ያሉት እንዲህ ይላል . . ." ራእ. 1፥4-5

እንዲሁም "ከዙፋኑም መብረቅና ድምፅ ነጎድጓድም ይወጣል፤ በዙፋኑም ፊት ሰባት የእሳት መብራቶች ይበሩ ነበር፤ እነርሱም <u>ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት</u> ናቸው" ይላል፡፡ ራእ. 4፥5 ከዚህም ጋር "በዙፋኑና በአራቱ እንስሶች መካከልም በሽማግሌዎችም መካከል እንደ ታረደ በግ ቆሞ አየሁ፣ ሰባትም ቀንዶችና ሰባት ዓይኖች ነበሩት፣ እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ የተላኩ <u>የእግዚአብሔር መናፍስት</u> ናቸው" ይላል፡፡ ራእ. 5፥6

የእግዚአብሔርን ቃል ለውንጀላና ለክሰሳ ለመጠቀም የሚደክሙትን እነዚህን ወገኖቻችንን እስኪ እንጠይቃቸው፤ እነዚህ "ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት" የተባሉት እነ ማን ናቸው?

<u>ስለዚህ እስካሁን ባየነው መሠረት በዋናነት የሚከተሉትን ነገሮች እናስተውላለን</u>፡-

1. "በመናፍስትነት የምናውቃቸው መላእክት እና የወደቀው ሰይጣንና ተከታዮቹ ናቸው" ያሉት በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ትክክል አለመሆኑን ቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ ደጋግሞ ይመሰክርባቸዋል፡፡

2. በመቀጠልም "መናፍስትን እንዳንጠራ ከተከለከልን መናፍስት በምን ሁኔታ ወደ ሰው ይመጣሉ?" ያሉት መናፍስት አትጥሩ የተባለው ሟርትንና መተትን በተመለከተ እንጂ ያረፉ ሰዎችን ነፍሳት በጸሎት ለማስታወስና የቅዱሳንን ስም መጥራት በተመለከተ አይደለም፡፡ ለዚህ ማስረጃ ብለው የጠቀሱት ጥቅስ አሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 18 ቁጥር 9-12 እነርሱ ያሉትን ሃሳብ የሚደግፍ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ጭራሽ ካነሱት ሃሳብ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ ቃሉ የሚለው እንዲህ ነው፡-

> እነርሱም፥ ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት? አሉት። እርሱም፦ በድንኳኑ ውስጥ ናት አላቸው። እርሱም፦ የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ በእውነት እመለሳለሁ ሚስትህ ሣራም ልጅን ታገኛለች አለ። ሣራም በድንኳን ደጃፍ በስተ ኋላው ሳለች ይህንን ሰማች። አብርሃምና ሣራም በዕድሜያቸው ሸምግለው ፈጽመው አርጅተው ነበር፣ በሴቶች የሚሆነውም ልማድ ከሣራ ተቋርጦ ነበር። ሣራም በልቧ እንዲህ ስትል ሳቀች፥ ካረጀሁ በኋላ በውኑ ፍትወት ይሆንልኛልን? ጌታዬም ፈጽሞ ሸምግሏል። ዘፍ. 18፥9-12

ታዲያ ማስረጃ ብለው የጠቀሱት ይህ የእግዚአብሔር ቃል እነርሱ ከሚሉት መናፍስትን መጥራት አለመጥራት ጉዳይ ጋር ምን ግንኙነት አለው? ሰው አያውቅብንም ብሎ ለማታለል መሞከር ሲታወቅ ያሳፍራልና ትንሽ ያውቁብኛልንም መጨመር ቢቻል ጥሩ ነበር፡፡

እንኳን የፍጡራንን ስም ይቅርና የእግዚአብሔርንም ስም ስንጠራ እንኳ በአግባቡና ተገቢውን ክብር በሚሰጥ ሁኔታ እንጂ እንዲሁ መጥራት ብቻውን በራሱ ተገቢ አይደለም፡፡ ከዚያም በላይ ይህ ጉዳይ ከአሥሩ ትእዛዛት መካከል አንዱ ሆኖ "የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና" በሚል ሕግ ሆኖ ተነግሯል። ዘጸ. 20፡7 የሌሎችን ስም ስንጠራም አግባብ ወይም አላግባብ የሚያደርገው መጥራቱ ሳይሆን አጠራሩና የምንጠራበት ሁኔታ ነው፡፡

እነርሱ እንደሚሉት ከእኛ በፊት የነበሩና ያረፉ ሰዎችን ስም መጥራት መናፍስት መጥራት ከሆነና ይህም በእግዚአብሔር ዘንድ የተከለከለ ከሆነ ሊቀ ነቢያት ሙሴ አባቶቹን አብርሃምን፣ ይስሐቅንና ያዕቆብን እያነሣ ሲጸልይ እግዚአብሔር ለምን ሰማው? ለምንስ አልተቆጣውም? ሙሴ ከሲና ተራራ ሲወርድ የጥጃ ምስል ሠርተው እያመለኩ ባገኛቸው ጊዜ እግዚአብሔር እነርሱን ላጥፋቸው ሲለው ሙሴ ወደ እግዚአብሔር "ከመዓትህ ተመለስ፣ ለሕዝብህም በክፋታቸው ላይ ራራ። ዘራችሁን እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛለሁ፣ ይህችንም የተናገርኋትን ምድር ሁሉ ለዘራችሁ እሰጣታለሁ፣ ለዘላለምም ይወርሷታል ብለህ በራስህ የማልህላቸውን ባሪያዎችህን አብርሃምንና ይስሐቅን እስራኤልንም አስብ" በማለት ተማጸነ። በዚያን ጊዜም "እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፋት ራራ" ይላል። ዘጸ. 32፡12-14 ተሐድሶዎች፣ እነርሱ እንደሚሉት ያለፉ አበውን ስም መጥራትና ማንሣት "የተከለከለ" እና "ማሟረት" ከሆነ እግዚአብሔር ሙሴን በመገሠጽ ፋንታ ለምን ጸሎቱን ሰማው? እንዲህ ያለውን የሙሴን ጸሎት የሰማውን እግዚአብሔርንስ የስህተት ተባባሪ ማድረጋቸው አይደለምን?

እንደዚሁም ይኸው የእግዚአብሔር ሰው ሊቀ ነቢያት ሙሴ ከአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ አንዱ የሆነውንና ከሞተ ብዙ ዓመታት ያለፈውን ሮቤልን ዐጽሙን ከግብጽ ይዞ ሲወጣ "ሮቤል በሕይወት ይኑር፣ አይሙት፣ ሰዎቹም በቍጥር ብዙ ይሁኑ" ብሎ የሮቤልን ስም አንሥቷል፣ ጸልዮለታልም፡፡ ዘዳ. 33፡6 ታዲያ ሙሴ የሞተውን የሮቤልን ስም መጥራቱ እንዳንጠራቸው የተከለከሉ መናፍስትን መጥራቱ ኖሯልን? በፍፁም! ከእኛ በፊት ያረፉ ወገኖቻችንን በጸሎት ጊዜ ስማቸውን መጥራት በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አልተከለከለም፡፡ የተከለከለው ርኩሳን መናፍስትን መጥራት ነው፡፡ ስለዚህ የሁለቱን ልዩነት ሳይረዱ ሌላውን አስተምራለሁ ማለት ትርፉ መድኃኒታችን በወንጌል "ዕውር ዕውርን ቢመራው ሁለቱም ወደ ጉድጓድ ይወድቃሉ" ብሎ የተናገረው ቃል መፈጸሚያ መሆን ብቻ ነው፡፡ ማቴ. 15፡14

እንደዚሁም ለእግዚአብሔር ቀናዒ የነበረው ታላቁ ነቢይ ኤልያስ በሕዝቡ ሲመለክ የነበረውን በኣል የተባለውን ጣዖት ሐሰትነትና የካህናቱን ግብዝነት በአደባባይ ለሕዝቡ ሁሉ ካሳየና ካስመሰከረ በኋላ እርሱ መሥዋዕቱን አዘጋጅቶ ሲጸልይ እንዲህ ብሎ ጸለየ፡-

> መሥዋዕተ ሠርክ በሚቀርብበት ጊዜ ነቢዩ ኤልያስ ቀርቦ፡- አቤቱ፣ የአብርሃምና የይስሐቅ የእስራኤልም አምላክ ሆይ፣ አንተ በእስራኤል ላይ አምላክ እንደ ሆንህ፣ እኔም ባሪያህ እንደ ሆንሁ፣ ይህንም ሁሉ በቃልህ እንዳደረግሁ ዛሬ ይገለጥ። አንተ፣ አቤቱ፣ አምላክ እንደ ሆንህ፣ ልባቸውንም ደግሞ እንደ መለስህ ይህ ሕዝብ ያውቅ ዘንድ ስማኝ፣ አቤቱ፣ ስማኝ አለ።

ከዚያ ቀጥሎ ስለ ሆነው ሲናገር ደግሞ፦ "የእግዚአብሔርም እሳት ወደቀች፣ የሚቃጠለውን መሥዋዕቱንም እንጨቱንም ድንጋዮቹንም አፈሩንም በላች፤ በጕድጓዱም ውስጥ ያለውን ውኃ ላሰች" በማለት ጸሎቱን እግዚአብሔር እንደ ተቀበለውና ይህም በጠላትም ፊት የተመሰከረ እውነታ መሆኑን ይነግረናል፡፡ 1 ነገ. 18፥36-38 ታዲያ እግዚአብሔር ኤልያስን "ለምን የሞቱ ሰዎችን ነፍሳት ትጠራለህ? ይህ ሟርት ነው" ለምን አላለውም? ተሐድሶዎች እንዲህ "ሟርት ነው" የሚሉትን ነገር እነ ሙሴ ካደረጉት፣ እነ ኤልያስ ካደረጉት፣ እንዲሁም የእነርሱ አምላክ ነገሩን የተቀበለው ከሆነ ማን ጋር እየተጣሉና ማንን እየተቃወሙ እንደ ሆነ ይገባቸዋል ይሆን? በእውነት ከልብ እንዲህ እንላቸዋለን፦ እባካችሁ ወንድሞቻችን፤ እስኪ እልኩን ተውትና ሰከን ብላችሁ ለማሰብ ሞክሩ፡፡

ያረፉ ሰዎችን ስም የጠሩት እነ ሙሴና ኤልያስ - ሰዎች - ብቻ አይደሉም፣ ራሱ እግዚአብሔርም እንጂ፡፡ እግዚአብሔር ራሱን ለሙሴ ሲገልጥ "እኔ የአባትህ አምላክ፣ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅም አምላክ፣ የያዕቆብም አምላክ ነኝ" ብሎ ነበር፡፡ ዘጸ. 3፥6 ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በዘመነ ሥጋዌው በትምህርቱ ላይ በብሉይ ኪዳን የነበሩ ብዙ ሰዎችን ጠርቷቸዋል (ስማቸውን አንሥቷል)፡፡ ለምሳሌም "አብርሃምንና ይስሐቅን ያዕቆብንም ነቢያትንም ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት ባያችሁ ጊዜ ..." በማለት፣ እንዲሁም "ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ መቅደስና በመሠዊያው መካከል እስከ ገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቅ ደም ሁሉ ይደርስባችሁ ዘንድ ..." በማለት ከአቤል ጀምሮ እስከ ዘካርያስ ድረስ የሞቱትን ሁሉ ጫፍና ጫፉን በመያዝ (ስለ ጽድቅ በግፍ በመሞት የመጀመሪያውን ሟች አቤልን እና ከጌታችን ሞት በፊት የመጨረሻውን ሰማዕት ዘካርያስን) አንሥቷቸዋል። ሉቃ. 13፥28 ፤ ማቴ. 23፥35

ስም ከመጥራት በላይም ጌታችን ከሞተ ብዙ ዘመን የሆነውን ሙሴን በአካለ ነፍስ ጠርቶ በደብረ ታቦር እንዲገኝ አድርጎታል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ እንደሚል፦ "እነሆም፣ ሁለት ሰዎች፣ እነርሱም ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ይነጋገሩ ነበር፤ በክብርም ታይተው በኢየሩሳሌም ሊፈጽም ስላለው ስለ መውጣቱ ይናገሩ ነበር።" ሉቃ. 9፥30-31 ታዲያ የሞቱ ሰዎችን ጌታችን በአካለ ነፍስ እስኪጠራቸው ከደረሰ ስማቸው መጠራቱ ስህተትነቱና ሟርትነቱ ከቶ ምን ላይ ይሆን?

እንዲሁም ጌታችን ክብር ምስጋና ይግባውና ስለ እኛ ሲል በፈቃዱ በተቀበለው በሞቱ ጊዜ ከተፈጸሙት ተአምራት መካከል አንዱ የመቃብራት መከፈትና ቀድመው ዐርፈው ከነበሩት ቀደምት አበውና እማት መካከል ወደ አምስት መቶ የሚያህሉት ነፍሳቸው ከሥጋቸው ተዋሕዳ ተገልጠው በኢየሩሳሌም መታየታቸው ነበር፡፡ ቅዱስ ወንጌል ስለ እነዚህ ሲናገር እንዲህ ይላል፦ "መቃብሮችም ተከፈቱ፤ ተኝተው ከነበሩትም ከቅዱሳን ብዙ ሥጋዎች ተነሡ፤ ከትንሣኤውም በኋላ ከመቃብሮች ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ ገቡና ለብዙዎች ታዩ፡፡" ማቴ. 27፥52-53 ከእነዚያ መካከል ወዲያውኑ ተመልሰው ያንቀላፉ አሉ፤ ለብዙ ጊዜያት የቆዩም አሉ፡፡ ቢያንስ ቅዱስ ጳውሎስ የመጀመሪያ የቆሮንቶስ መልእክቱን እስከ ጻፈበት እስከ 50 ዓ. ም. ገደማ ድረስ ነበሩ፡፡ ሐዋርያው "ከዚያም በኋላ [መድኃኒታችን ከትንሣኤው በኋላ] ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነርሱም የሚበዙቱ እስከ አሁን አሉ፤ አንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል" በማለት የገለጻቸው እነዚህ ናቸው፡፡ 1 ቆሮ. 15፥6

3. "ሙታን በሕይወተ ሥጋ በነበሩበት ጊዜ ይፈጽሙት የነበረውን አስነዋሪ ተግባር ያልሞቱ ዘመዶቻቸው እንዳይሠሩ ለመምከር እንኳ አይችሉም" ያሉት ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ በዚህ ዓለም ስለሚሆነው አያውቁም ለማለት ከሆነ ከላይ ይህን በተመለከተ መልስ ተሰጥቶበታል፡፡ ደግሞም ቅዱሳን በሕይወተ ሥጋ በነበሩበት ጊዜ አስነዋሪ ተግባር የሚፈጽሙ ሳይሆኑ በእግዚአብሔር ጸጋ መልካም ሥራ ሲሠሩና መሰናከል ሲገጥማቸውም ፈጥነው ንስሐ ሲገቡ የኖሩ ናቸው እንጂ እንደ ተሐድሶዎች "ኃጢአት ብሠራም ከእግዚአብሔር ጋር ባለኝ ግንኙነት ላይ አንዳችም ለውጥ አያመጣም" በሚል የስህተት ትምህርት ተመርተው በኃጢአት ሚዳ ሲጋልቡና የክፋት ሠራተኞች ሆነው ሲያገለግሉ የኖሩ አይደሉም፡፡

ወይም ደግሞ ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ ከመሞታቸው በፊት ያደርጉት እንደ ነበረው በዚህ ዓለም በማስተማር ሥራ ሊሰማሩ (ሊቀጥሉ) ይገባቸው ነበር ለማለት ከሆነ ይኸ በአንድ በኩል ከድካማቸው እንዳያርፉ ለማድረግ ይሆን? በዘመናቸው የታገሉትና የደከሙት አንሶ አሁንም እነርሱን ከመሰሉ ልቡሳነ ሥጋ ጋር ለምን ሲታገሉ ይኖራሉ? ችሩ አባታቸው ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ ጠርቷቸዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በአካለ ነፍስ እየመጡ ማስተማር ነበረባቸው ለማለት ከሆነ እግዚአብሔር ይህን የከለከለው ለጥቅማችን ነው፡፡ ምክንያቱም ታላቁ መምህር ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ባለ ጸጋው ወደ ወንድሞቹ ቤት ከሙታን አንዱ ተልኮ ያስተምራቸው ዘንድ በጠየቀ ጊዜ ለምን እንደ ተከለከለ የሚናገረውን ቃለ ወንጌል በተረጎመበት ክፍለ ትምህርቱ ከሙታን መካከል በአካለ ነፍስ እየተላኩ ማስተማር ቢፈቀድ ኖሮ ርኩሳን መናፍስትም በአካለ ነፍስ የሚላኩ ቅዱሳንን በመምሰል ብዙዎችን የስህተት ትምህርት ለማስተማርና ወደ ጥፋት ለመውሰድ ሰፊ እድል ባገኙ ነበር፤ ስለዚህም እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን ነገር አስቀረልን ይላል፡፡ ሰይጣን እንኳን በር አግኝቶ ይቅርና እንዲያውም ፈታኝ ነው፤ "ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና" ተብሏልና። 2 ቆሮ. 11፥14

ሌላው እንደ ማስረጃ አድርገው የጠቀሱት ጥቅስ ሉቃ. 23፥42-43 ነው፡፡ ይህ ቃል የሚለው እንዲህ ነው፦

> ኢየሱስንም፦ ጌታ ሆይ፥ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ አለው። ኢየሱስም፦ እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው።

ታዲያ ይህ የእግዚአብሔር ቃል እነርሱ ከሚሉት ኑፋቄ ጋር ዝምድናው ምንድን ነው? ተሐድሶዎች እንደሚሉት ያረፉ ሰዎችን ነፍሳት በጸሎት ጊዜ አትጥሩ አይልም፡፡ ራእ. 6፥9-11 ብለው የጠቀሱት ቃልም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማዕትነት የሞቱ ሰዎች ነፍሳት በመሠዊያው በታች ፍርድ ሲካሰሱ መታየታቸውን ይናገራል እንጂ ያረፉ ነፍሳትን በጸሎት ለማሰብም ሆነ እንዲያስቡን መጥራት፣ እግዚአብሔርም ስለ እነርሱ ብሎ ይቅር እንዲለን ማለትን "ሿርት ነው"፣ "የተከለከለ ነው" አይልም፡፡ እንዲህ እነርሱ ከሚሉት ሃሳብ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ጥቅሶች የሚደረድሩት ሰው መጽሐፍ ቅዱስ የማያነብ መስሏቸው ነው? ወይስ ደግሞ እንዲህ ጥቅሱ ሲደረደር ውሸታችንን እውነት አስመስሎ ያሳይልናል ብለው ይሆን?

## 6) ቅዱሳንን ማክበርን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል እንደ ማድረግ አስመስሎ ማቅረብ፣

- "ሰው ይድንበት ዘንድ ለሰው የተሰጠ ብቸኛ መድኃኒት ጌታ ኢየሱስ ነው፡፡ እርሱን የሚመስልና የሚያህል ሌላ የለም፡፡ ቅዱሳን የምንላቸው በእርሱ አዳኝነት የዳኑትን ሁሉ ነው፡፡ እነዚህም ቅዱሳን ሊባሉ የበቁት በሥራቸው ሳይሆን ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ከጸጋው የተነሣ ስለ ቀደሳቸው ብቻ ነው፡፡ በእርሱ የዳኑትን ከአዳኛቸው ጋር በእኩል ማስቀመጥ ካለማወቅና ካለማስተዋል የሚነሳ ስህተት ነው፡፡ . . . በተጨማሪም ጌታ ኢየሱስ የሁሉ ፈጣሪና እውነተኛ አምላክ ነው፡፡ በሙሉ ሕይወታቸው ሊነግሡ ሲገባቸው በሥጋ በመገለጡ ብቻ ከፍጡራን እኩል በልብ ውስጥ ትንሽ ጎጆ በክፍያ እንዲደርሰው ያደርጋሉ፡፡" (ሶሙራ ቁ. 16፣ ገጽ 7)

መሠረታዊ የቤተ ክርስቲያኒቷ እምነት የሆነውን ይኸን ጉዳይ እንደ አዲስ አሁን ሊሰብኩን ይሆን? ምናልባት ሰዎች ካለመማራቸው የተነሣ የሚያደርጉትንና የሚሉትን ሁሉ የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮና መሠረተ እምነት እንደ ሆነ እያስመሰሉ ማቅረብ ተገቢ አይደለም፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አዳኝና ጌታ ማን መሆኑን፣ ቅዱሳን ደግሞ ማን መሆናቸውን በሚገባ የምታውቅና ለይታም የምታስተምር በመሆኗ ይህን እንደ አዲስ ግኝት እናስተምር ማለት "ምጥ ለእናቷ" ዓይነት ነው፡፡ ወይም ደግሞ እነርሱ ይህን የቤተ ክርስቲያኒቷን መሠረታዊ ትምህርት "እግረ ተማሪ" ሆነው "ሌላውን" ሲቃርሙ ሳይማሩት ኖረው ኋላ ይህን ነገር መጀመሪያ የሰሙት ከቤተ ክርስቲያኒቷ ጠላቶች አፍ ስለሆነና እነርሱም ይህን እነርሱ እንጂ ሌላ እንደማያውቀውና እንደማያስተምረው አስመስለው ሲነግሯቸው ሞኝና ወረቀት ሆነና እንዳለ ተቀበሉት፡፡

"በእርሱ የጻኑትን ከአዳኛቸው ጋር በእኩል ማስቀመጥ ካለማወቅና ካለማስተዋል የሚነሳ ስህተት ነው" ያሉት ሃሳቡ እውነት ነው፤ ስህተት የሚሆነው በአንድ በኩል ቤተ ክርስቲያኒቱ የማታውቀውና የማታስተምረው አስመስለው ማቅረባቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ ተንደርድረው "በእርሱ የጻኑትን ከአዳኛቸው ጋር በእኩል ማስቀመጥ ካለማወቅና ካለማስተዋል የሚነሳ ስህተት ነው" በማለት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፍጡርና ፈጣሪ እኩል የምታደርግ አስመስለው ማቅረባቸው ነው፡፡ እንደዚሁም የሆነ ሰው ተናገረው ያሉትን ነገር እንደ መደበኛ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሠረተ እምነት (Doctrine) እና አስተምህሮ አድርጎ መውሰድ ፍጹም ስህተት ነው፡፡ ነገረ ሃይማኖታዊ ጉዳይን በተመለከተ ይቅርና በዚህ ዓለም ያለ ሥነ ሕይወታዊ፣ ሥነ ልቡናዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ . . . እሳቤ (ፍልስፍና) በተመለከተ እንኳ እንዲሁ ያ ጉዳይ ባልገባቸውና ባልተረዱት ሰዎች እውቀትና አገላለጽ ደረጃ ሊወሰድ አይገባም፡፡

7) የቅዱሳንን አማላጅነት ከሙስና ጋር ማመሳሰል፤

◉ *". . . ሙስናን በእግዚአብሔር መንግሥት የሚሠራበት ሕግ አስመሰለው በሃይማኖታቸው አስተምህሮ ውስጥ ሰፊ የትምህርት ምዕራፍ የሰጡ ቡድኖች እንዳሉ አስተውላችሁ ታውቃላችሁን? <u>በመላእክት፣ በጻድቃን፣ በሰማዕታት ስሞች የተደረሱ ገድላት፣ ተአምራት፣ ድርሳናት ወዘተ በመላ የሚታወቁት መንፈሳዊ መሰል መጻሕፍት ሁሉ ሙስና በእግዚአብሔር መንግሥት የተፈቀደ ሕጋዊ ሥርዓት እንደ ሆነ አስመስለው ይናገራሉ</u>፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ጻድቅና ቅዱስ በሆነው፣ አድልዎም በሌለበት በእግዚአብሔር መንግሥት ዕድል ፈንታ የላቸውም የሚላቸው ነፍስ ገዳዮች፣ አመንዝራዎች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ ሌቦች፣ ቀማኞች በጠቅላላው ሕገ እግዚአብሔርን የሚያፈርሱ ወንጀለኞች በእግዚአብሔር ባለሟሎች በኩል ከቅጣት ሊያመልጡ እንደሚችሉ ድርሳናትና ገድላት ይሰብካሉ፡፡ እንዲህ የሚያደርግ ሰው ሕገ እግዚአብሔርን ማፍረስ ብቻም አይደለ፣ ሥላሴን ቢክድ እንኳ በተከፈተው የሙስና መንገድና የስርቆሽ በር አልፎ ገነት መንግሥተ ሰማያት ይገባል ይሉናል፡፡ 78 ሰዎችን የገደለ ሥጋቸውን የበላና ሥላሴን የካደ በላዔ ሰብእ በማርያም አማላጅነት ከእግዚአብሔር የቅጣት ፍርድ ማምለጡን ተአምረ ማርያም ይተርክልናል፡፡ መጠቆም የምንፈልገውም ሙስናን ከሀገራችን ማጥፋት የሚቻለው በእግዚአብሔር መንግሥት ሙስና የተፈቀደና የሚሠራበት ሕግ አስመስለው የሚሰብኩት መጻሕፍት በቅድሚያ ሲወገዙ ነው፡፡" (ሎራ ቁ. 30፣ ገጽ 1-2)*

በእውነቱ በዚህ አባባላቸው ላይ ምንም ነገር ባንልና ለአንባቢ ሕሊና ብንተወው ሳይሻል የሚቀር አይመስለኝም፡፡ ይኸ እንዲህ ይሁንና በትንሹ ሁለት መሠረታዊ ስህተቶቻቸውን ብቻ እናውጣቸው፡፡ እነዚህም፡-

አንደኛው፡- *". . . ሙስናን በእግዚአብሔር መንግሥት የሚሠራበት ሕግ አስመሰለው በሃይማኖታቸው አስተምህሮ ውስጥ ሰፊ የትምህርት ምዕራፍ የሰጡ ቡድኖች እንዳሉ አስተውላችሁ ታውቃላችሁን? በመላእክት፣ በጻድቃን፣ በሰማዕታት ስሞች የተደረሱ ገድላት፣ ተአምራት፣ ድርሳናት ወዘተ በመላ የሚታወቁት መንፈሳዊ መሰል መጻሕፍት ሁሉ ሙስና በእግዚአብሔር መንግሥት የተፈቀደ ሕጋዊ ሥርዓት እንደ ሆነ አስመሰለው ይናገራሉ"* የሚለው ነገራቸው ነው፡፡

በአንዱ ጸሎትና ቃል ኪዳን ሌላው መጠቀሙና መዳኑ ሙስና ከሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ በአንዱ ጸሎት ሌላው የዳነባቸውና የተጠቀመባቸው ነገሮች ሁሉ እነርሱ እንደሚሉት "ሙስና" ናቸው ማለት ነው? ራሱ እግዚአብሔር በሕዝቅያስ ዘመን ኢየሩሳሌምን ከማጥፋት ለምን እንዳዳናት ሲናገር "<u>ስለ እኔም፣ ስለ ባሪያዬም ስለ ዳዊት ይህችን ከተማ አድናት ዘንድ እጋርዳታለሁ</u>" ማለቱ ምን ሊባል ነው? 1 ነገ. 19፡34 ኢየሩሳሌምንና በዘመኑ የነበሩትን ሰዎች፣ እንዲሁም ንጉሡን ሕዝቅያስን ከሰናክሬም እጅ ያዳናቸው ከእነርሱ በፊት ቀድሞ ስለ ነበረውና በዚያን ዘመን በምድር ላይ ስላልነበረው ስለ ባሪያው ስለ ዳዊት ብሎ ነውና፡፡ በአንዱ ደግነት ሌላው መጠቀሙና መዳኑ ሙስና ነው ከተባለ የእግዚአብሔርን ቸርነት ሁሉ ሙስና ሊያደርጉት ምን ቀራቸው?

ቃል ኪዳን በመስጠት ያሳየው ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ እግዚአብሔር ዐሥሩን ትእዛዛት ሲሰጥ ከኢ.ታምልክ ቀጥሎ እንዲህ ብሏል፦ "በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፤ ለሚወድዱኝ፣ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና።" ዘጸ. 20፡5-6 ነገረ እግዚአብሔርን ከፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን በወረሱት ሕግ ነክ መነጽር ማየት የተጠናወታቸው እነዚህ ሰዎች፣ እግዚአብሔር "በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ነኝ" በማለቱ የአባታቸውን ኃጢአት በልጃቸው ላይ፣ ያውም በአንድ ትውልድ ሳይወሰን እስከ ሦስትና አራት ትውልድ ድረስ ማምጣቱ "ኢፍትሐዊነት ነው"፣ "ግፍ ነው"፣ ወዘተ ሊሉት ይሆን? በአንጻሩ ደግሞ "ለሚወድዱኝ፣ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን አደርጋለሁ" ስላለ እንዴት በአንዱ ሰው ምክንያት እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ያሉት ለምን ይጠቀማሉ? ይህ ፍትሐዊ አይደለም ሊሉት ይሆን? ዋናው ችግራቸው ነገረ እግዚአብሔርን የሚረዱበት እይታቸው የተበላሸ መሆኑ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን የሚጠቀሙበት የራሳቸውን አስተሳሰብ ተጠቅመው ማምረት ለሚፈልጉት ምርት የሚስማማቸውን ጥሬ ዕቃ ለመውሰድ ብቻ ነው፡፡

እግዚአብሔር የኢዮብን ሦስቱን ጓደኞቹን እንዲህ ብሏቸው ነበር፦

> እግዚአብሔርም ይህን ቃል ለኢዮብ ከተናገረ በኋላ እግዚአብሔር ቴማናዊውን ኤልፋዝን፦ እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅንን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና ቍጣዬ በአንተና በሁለቱ ባልንጀሮችህ ላይ ነድዷል። አሁን እንግዲህ ሰባት ወይፈኖችና ሰባት አውራ በጎች ይዛችሁ ወደ ባሪያዬ ወደ ኢዮብ ዘንድ ሂዱ፣ የሚቃጠልንም መሥዋዕት ስለ ራሳችሁ አሳርጉ፣ ባሪያዬም ኢዮብ ስለ እናንተ ይጸልያል፣ እኔም እንደ ስንፍናችሁ እንዳላደርግባችሁ ፊቱን እቀበላለሁ፣ እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና። ኢዮ. 42፡7-8

ታዲያ በኢዮብ ጸሎት ሦስቱን የኢዮብ ጓደኞች ይቅር ማለቱ በተሐድሶዎች አባባልና አተረጓጎም'ኮ ደግሞ ለመናገር የሚቀፍ ነገር (ሙስና ...)መሆኑ ነው፡፡ እንዲህ ያለው አስተሳሰብና አባባል እንኳን ሃይማኖት አለኝ ከሚል ሰው ቀርቶ ጤነኛ ከሆ ከማንኛውም ሰው የሚጠበቅ አይደለም፡፡ እነርሱ ግን ከምን ያህል የክህደት አዘቅት ውስጥ እንደ ገቡ ነገራቸውና ሥራቸው በተግባር ያሳያል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ፦ "መጽሐፍ ቅዱስ ጻድቅና ቅዱስ በሆነው፣ አድልዎም በሌለበት በእግዚአብሔር መንግሥት ዕድል ፈንታ የላቸውም የሚላቸው ነፍስ ገዳዮች፣ አመንዝራዎች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ ሌቦች፣ ቀማኞች በጠቅላላው ሕገ እግዚአብሔርን የሚያፈርሱ ወንጀለኞች በእግዚአብሔር ባለሟሎች በኩል ክቅጣት ሊያመልጡ እንደሚችሉ ድርሳናትና ገድላት ይሰብካሉ" የሚለው ነው፡፡

"በእግዚአብሔር መንግሥት ዕድል ፈንታ የላቸውም የሚላቸው ነፍስ ገዳዮች፣ አመንዝራዎች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ ሌቦች፣ ቀማኞች በጠቅላላው ሕገ እግዚአብሔርን የሚያፈርሱ ወንጀለኞች" የሚላቸው'ኮ ንስሐ ለማይገቡና ለማይመለሱ ኃጢአተኞች ነው እንጂ ከጥንቱ በእምነትና በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚገኘውን ጸጋ አግኝተው ከዚያ በኋላ በተለያየ ኃጢአት ሲሰነካከሉ በቅዱሳን ጸሎት ለሚማጸኑ፣ ለመዳን የሚቻላቸውን ጥረትና የራሳቸውን ድርሻ ለማድረግ የሚጋደሉትን አይደለም፡፡ ገድላትና ድርሳናት የሚሉትም እንዲህ ያሉትን ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ደግሞ ተአምር በባሕርዩ ለየት ያለና ከተለመደው ወጣ ያለ ነገር ስለሆነ "ሊሆን አይችልም" ብሎ መከራከር የእግዚአብሔርን ነጻ መሆን መዘንጋትና የማይመረመር ምሥጢሩን አውቃለሁ እንደ ማለት ነው፡፡ ይህም አርዮሳዊ እርሾ ነው፡፡ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረው የመዳን መንገድ በወንጌል የተነገረውን ነው፤ እርሱም ከላይ በክፍሉ ተገልጿል፡፡ በቅዱሳን ጸሎት ሊጠቀሙ የሚችሉ ሰዎችም በመዳን መንገድ መጓዝ የጀመሩት እንጂ እንዲሁ በክህደትና በአረመኔነት የኖሩት ናቸው አይደሉም፡፡

እስኪ ሳያምን፣ ሳይጠመቅ፣ ከምሥጢረ ቁርባን ሳይሳተፍ፣ ንስሐ ሳይገባ "ዳነ" የተባለ ሰው ማን ነው? እነርሱ ግን አሥር ጊዜ ይህንኑ በመደጋገም እኛንም እንደ እነርሱ "ደጋሚዎች" እንድንሆን ሊያደርጉን ይፈልጋሉ፡፡ ነገራቸው ሁሉ እንዲህ ጭብጥ የሌለው ጉንጭ አልፋ ነው፡፡

ተሐድሶዎች ሆይ፣ እንዲያው ለነገሩ ነፍሰ ገዳዮች፣ አመንዝራዎች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ ሌቦች፣ ቀማኞች በጠቅላላው ሕገ እግዚአብሔርን የሚያፈርሱ ወንጀለኞች ይድናሉ እያለ ያለው እኛ ነን ወይስ እናንተ? ሰው ካመነ በኋላ ኃጢአት ቢሠራም ያገኘውን የእግዚአብሔር ልጅነት አያሳጣውም፣ ከመዳን ውጭ አያደርገውም፣ ችግር የለውም የምትሉት እናንተ አይደላችሁምን? ቤተ ክርስቲያናችን ግን በኃጢአት የተሰናከለ ሰው ቢኖር ንስሐ ገብቶ ለኃጢአት ሥርየት የተሠዋውን የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም በልቶ ይድናል ትላለች፡፡ ወደዚህ መዳን እንዲቀርብ ደግሞ የቅዱሳን ጸሎት ይረዳዋል ብላ ታስተምራለች እንጂ እንደ እናንተ የፈለገውን ኃጢአት ቢሠራም ችግር የለውም፣ መዳን በእምነት ብቻ ነው አትልም፡፡ ሕገ እግዚአብሔርን መጠበቅ አያስፈልግም፣ ለመዳንም ጥቅም የለውም የምትሉት እናንተ አይደላችሁምን? ስለዚህ ይህ ክስ የሚመለከተው ራሳችሁን ነው፡፡ ገድላትና ድርሳናትም ቢሆኑ የእግዚአብሔር ባለሟሎች ጸሎታቸውና ምልጃቸው እንደሚጠቅም ይናገራሉ እንጂ ንስሐ ሳትገቡ፣ ቅዱስ ቁርባን ሳትቀበሉ እንዲሁ በተባለው ጻድቅ ወይም ሰማዕት ስም ትድናላችሁ አይሉም! ይልቁንስ ምሥጢራትን እያስፈለጉም እያላችሁ በሞኝነት የሚሰማችሁ ካለ እንደዚያ ዓይነቱን ሰው ከመዳን መንገድ የምታሰናክሉ እናንተ አይደላችሁምን? ደግሞ ከመቼ ወዲህ ለሕገ እግዚአብሔር ተቆርቋሪ መስላችሁ ለመቅረብ ጀመራችሁ?

*"በእግዚአብሔር ባለሟሎች በኩል ከቅጣት ሊያመልጡ እንደሚችሉ ድርሳናትና ገድላት ይሰብካሉ"* ያሉችሁትስ በእግዚአብሔር ሳያምኑ፣ ከጥንቱ በመዳን መንገድ መጓዝ ሳይጀምሩ፣ ኋላም በቅዱሳኑ ጸሎት ወደዚህ የመዳን መንገድ ሳይመጡ እንዲሁ "ዳኑ" የሚል ትምህርት ከማን ነው የሰማችሁት? እስኪ ሳይጠመቅ እንዲሁ በሚባል ጻድቅ አማካይነት ገነት ገባ የሚል ገድል አምጡ! እንዲህ የሚል የለም እንጂ ካለም ገድል ተብሎ አይቆጠርም፡፡ እንዲያው ሰሚም ይታዘባልና እባካችሁ አትዋሹ፡፡ ቅዱሳን ሌላ መንገድ ሳይሆኑ ወደ አንዱ መንገድ ወደ እግዚአብሔር እንመጣ ዘንድ በጸሎታቸውና በቃል ኪዳናቸው የሚያስቡንና የሚረዱን ናቸው፡፡ በእግዚአብሔር ባታምኑም፣ ባትጠመቁም፣ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ባትቀበሉም፣ . . . ችግር የለም፣ በእኔ በኩል ትድናለህ የሚል ወይም ያለ ጻድቅ የለም፣ ኖሮም አያውቅም፡፡ ቅዱሳን ኃጥአንን ይምራቸው ዘንድ ጸሎታቸውን የሚያቀርቡት ፈራጅና ዳኛ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ነው እንጂ ማጽደቅም ሆነ መኮነን የእነርሱ ሥልጣን አለመሆኑን ያውቃሉ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር የቅዱሳንን ልመና ተቀብሎ ኃጢአተኞችን ለምን ይቅር ይላቸዋል? የሚል ተቃውሞ ውስጣችሁን ተዋርሶታል፡፡

ጥያቄው እግዚአብሔር ለምን በዚህ መንገድ ሰዎችን ይቀበላል? ለምን ይምራል? ከሆነ ይህ የእግዚአብሔርን ዓላማ መዘንጋት ነው፡፡ ጥንቱንስ እግዚአብሔር ሰው የሆነው ኃጢአተኞችን ሊያድን አይደለምን? ገነት ቀድሞ የገባውስ ሰው ሲገድል፣ ደም ሲያፈስ፣ ሲቀማና ሲያሰቃይ የኖረው ሽፍታ መሆኑን ተሐድሶዎች አልሰሙም እንዴ? ከደጋጎቹ ከእነ ኖኅ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ . . . አስቀድሞ ለምን ገነት አስገባው? እግዚአብሔር ለሚመለሱ ኃጥአን ቸርና መሐሪ መሆኑን ለሁላችንም ለማስተማር አይደለምን? ቅዱስ ጳውሎስስ ከመመለሱ በፊት የቅዱስ እስጢፋኖስ ዋና ገዳይ፣ የቤተ ክርስቲያን አፍራሽ አልነበረምን? "ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው፤ ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ፤ ስለዚህ ግን የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት በእርሱ ያምኑ ዘንድ ላላቸው ሰዎች ምሳሌ እንድሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ዋና በምሆን በእኔ ላይ ትዕግስቱን ሁሉ ያሳይ ዘንድ ምሕረትን አገኘሁ" ያለው ለከንቱ ነውን? 1 ጢሞ. 1፥15-16 ታዲያ እነዚህ ሁሉ ሊድኑ አይገባቸውም ነበርን? እንዲህ ባለው የእግዚአብሔር ቸርነት ደስ ሊለን ይገባል እንጂ መበሳጨትንና ማዘንን ምን አመጣው? ይህ ከሰዎች ጠላት ከሰይጣን ካልሆነ በስተቀር ከሰው ልጅ የሚጠበቅ አይደለም፡፡

የእግዚአብሔርን ጸጋ ማንም ሰው ተገብቶት ሊያገኝም አይቻለውም፡፡ የእግዚአብሔር የማዳኑ ቸርነት "ጸጋ" (ስጦታ) የሚባለውስ ለዚህ አይደለምን? ኢየሱስ ክርስቶስ የወደደንና የሞተልን ጻድቃን ሆነን አግኝቶን ሳይሆን ኃጢአተኞችና በበደላችን ሙታን በነበርንበት ጊዜ ነበር፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ተባብረው የሚመሰክሩት ይኸንኑ ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ ላይ እንዲህ ሲል ይናገራል፡-

> ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቷልና። ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና፤ ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል። ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቷልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል። ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቍጣው እንድናለን፡፡ ሮሜ 5፡6-9

እንዲሁም

> በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም፣ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ በፊት ተመላለሳችሁባቸው። በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን፤ እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቍጣ ልጆች ነበርን። ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለ ሆነ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፤ በጸጋ ድናችኋልና፡፡ ኤፌ. 2፡1-5

እንዲሁም በቆላስይስ መልእክቱ "እናንተም በበደላችሁና ሥጋችሁን ባለመገረዝ ሙታን በሆናችሁ ጊዜ፥ ከእርሱ ጋር ሕይወትን ሰጣችሁ። በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ" ይላል። ቆላ. 2፡13 ይህን ሁሉ አጠቃልሎ "ወሶበ እንዘ ጸሩ ንሕነ ለእግዚአብሔር ተማሃለነ በሞተ ወልዱ - እግዚአብሔር ጠላቶቹ ሳለን በልጁ ሞት ይቅር አለን" በማለት በአንድ በኩል ሕጉን ያፈረስንና ከእርሱ ይልቅ ዲያብሎስን የመረጥን ጠላቶቹ የነበርን መሆናችንን፤ በሌላ በኩል ደግሞ እኛ ጠላቶቹ ሆነን ሳለ አንድ የባሕርይ ልጁን ስለ እኛ ለኩነተ ሥጋና ለሕማም ለሞት አሳልፎ በመስጠት እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ፍቅርና ይቅር ባይነት በተግባር መግለጡን አጠቃልሎ ተናገረ፡፡ ሮሜ 5፡10

ስለዚህ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ለማዳን ቸር ሲሆን "ኃጢአተኞች ለምን ዳኑ? ለምን ይቅርታ አገኙ?" እያሉ መቆጨትና መበሳጨት የሰው ልጅ ሥራ ሳይሆን የዲያብሎስ ሥራ ነው፡፡ መድኃኒታችን በወይኑ አትክልት በተለያዩ ሰዓቶች በተቀጠሩትና አንድ ዲናር ባገኙት ሠራተኞች ምሳሌ ባስተማረው ትምህርት ላይ ከጧት ጀምረው ሲሠሩ የዋሉት በአሥራ አንደኛው ሰዓት ለተቀጠሩት ሠራተኞች ከእነርሱ ጋር እኩል አንድ ዲናር ሲሰጣቸው ባዩ ጊዜ ተበሳጩ፤ ተቆጡ፡፡ "እነዚህ ኋለኞች አንድ ሰዓት ሠሩ፤ የቀኑንም ድካምና ትኩሳት ከተሸከምን ከእኛ ጋር አስተካከልሃቸው" ብለው በባለቤቱ ላይ አንጐራጐሩ። የወይኑ አትክልት ባለቤትም መልሶ ከእነርሱ ለአንዱ እንዲህ አለው፡- "ወዳጄ ሆይ፤ አልበደልሁህም፤ በአንድ ዲናር አልተስማማኸኝምን? ድርሻህን ውሰድና ሂድ፤ እኔ ለዚህ ለኋለኛው እንደ አንተ ልሰጠው እወዳለሁ፤ በገንዘቤ የወደድሁትን አደርግ ዘንድ መብት የለኝምን? ወይስ እኔ መልካም ስለ ሆንሁ ዓይንህ ምቀኛ ናትን?" ማቴ. 20፡11-15 ለራሱ የተስማማበትና የተቀጠረበት ዋጋ እንዳችም ሳይቀርበት ተሰጥቶት እያለ "ሌላው ለምን እኔ ያገኘሁትን ያህል ያገኛል? ሌላው ለምን እንደ እኔ እኩል አይደክምም ነበር?" እያሉ ማጉረምረም ምቀኝነት ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የዲያብሎስ መለያ ግብሩ ነው፡፡ የዲያብሎስ ዋና ተምኔት ሌላውም እንደ እርሱ ተራቁቶና ከእግዚአብሔር ርቆ ማየት ነውና፡፡

ስለዚህ እንዲህ የሚያስቡ ሰዎች በተፈጥሯቸው የአዳም ልጆች (አዳማውያን) ቢሆኑም በተግባራቸው ግን የዲያብሎስ ልጆች ናቸው፡፡ ጌታችን በትውልድ የአብርሃም ልጆች ቢሆኑም በተግባራቸው ግን የዲያብሎስ ልጆች የሆኑትን አይሁድ "እኔ በአባቴ ዘንድ ያየሁትን እናገራለሁ፤ እናንተም ደግሞ በአባታችሁ ዘንድ ያያችሁትን ታደርጋላችሁ" ባላቸው ጊዜ መልሰው "አባታችንስ አብርሃም ነው" አሉት። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም፦ *"የአብርሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር። ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኋችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ፤ አብርሃም እንዲህ አላደረገም። እናንተ የአባታችሁን ሥራ ታደርጋላችሁ"* አላቸው። እነርሱ ግን እንደ ተሐድሶዎች እውነተኛ ማንነታቸውን ለመቀበል የማይፈልጉ ግብዞች ስለ ነበሩ መልሰው "እኛስ ከዝሙት አልተወለድንም፣ አንድ አባት አለን፤ እርሱም እግዚአብሔር ነው" አሉት። በዚያ ጊዜ ነበር ጌታችን እውነተኛ የግብር አባታቸውን እንዲህ ሲል የነገራቸው፡ - "እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ፥ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና።" ዮሐ. 8፥38-44 ተሐድሶዎችንም "እኛ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ልጆች ነን" ቢሉም ግብራቸው ግን "አይደለም፣ እናንተማ የዲያብሎስ ልጆች ናችሁ" ይላቸዋል፡፡

በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያን ስለ መዳን የምታስተምረው ትምህርት በክፍል አንድ የተገለጸው ነው፡፡ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰውን ኃጢአት እየሠራህ፣ ነፍስ እየገደልህ፣ እየቀማህ . . . ኑር፤ በኋላ በቅዱሳን አማላጅነት ወይም በጸሎተ ፍትሐት ትድናለህ ብላ አታስተምርም፤ እንደዚያ ብላ አስተምራም አታውቅም፡፡ ለዚህ ነው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያልተጠመቁ እንዲጠመቁ፣ የተጠመቁት በቅዱስ ቁርባን እንዲኖሩ፣ ንስሐ እንዲገቡ፣ መልካም የቅድስና ሥራ እንዲሠሩና በሥጋቸው እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ፣ ከኃጢአት ጋር ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ እንዲጋደሉ አጽንታ የምታስተምረው፡፡ ከዚያ ውጭ ያሉት ነገሮች የእግዚአብሔር የተአምራቱና የቸርነቱ ሥራዎች ናቸው፡፡ ለተአምርና ለቸርነት ሥራው ደግሞ እንዴት እንደሚሆንና ለማን እንደሚሆን ወሳኙና አዋቂው ባለቤቱ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ዓይነት ተአምራት ተደርገዋል፡፡ እነዚያ ተአምራት ግን በተፈጥሮ በታወቀው መንገድ ወይም በተቀመጠ ሕግ የሚዳኙና የሚመዘኑ አይደሉም፤ አለዚያማ ተአምርነታቸው ምኑ ላይ ነው? እጅግ ብዙ ከሆኑት በመጽሐፍ ቅዱስ ከተመዘገቡት ተአምራት መካከል ለአብነት በጣት የሚቆጠሩትን ብቻ እናስታውስ፡፡ እስራኤላውያን የቀይ ባሕር ተከፍሎላቸው፣ ውኃው እንደ ግድግዳ በቀኝና በግራ ቆሞላቸው በመካከሉ አልፈዋል፡፡ ይኽ በምን ሕግ ሊመዘን ይችላል? እንዲሁም በኢያሱ መሪነት የዮርዳኖስ ወንዝ ከላይ ቆሞላቸው ሕዝቡ በደረቅ ተሻግረዋል፡፡ ኢያ. 3 የሎጥ ሚስት ወደ ኋላ አትመልከቺ የተባለችውን ትእዛዝ በማፍረሷ ምክንያት የጨው ሐውልት ሆና ቀርታለች፤ "የሎጥም ሚስት ወደ ኋላዋ ተመለከተች፥ የጨው ሐውልትም ሆነች" ይላልና፡፡ ዘፍ. 19፥26 ታዲያ የዮርዳኖስ ወንዝ መቆም፣ የሰው የጨው ሐውልት መቆም ሊብራራ ሊታተት የሚችለው እንዴት ብሎ ነው?

ጌታችን ከእነ ኖኅ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ ኢዮብ፣ ዳዊት፣ ነቢያት ሁሉ አስቀድሞ ገነት እንዲገባ ያደለው ፈያታይ ዘየማን ሽፍታና ወንበዴ የነበረውን፣ ከወንጀለኛነቱ ብዛት የተነሣ ለእስረኞች ምሕረት በሚደረግበት በአይሁድ በፋሲካቸው ቀን የተሰቀለውን ክፉ ወንበዴ ነበር፡፡ ይህ በምን ሕግ ሊመዘን ይችላል? እንደዚሁም ሁሉ በአንዳንድ ቅዱሳን ገድላትና ተአምራት ላይ ኃጢአተኞች የነበሩ ሰዎች ቅዱሳኑ ወደ እግዚአብሔር ያቀረቡላቸውን ምልጃ ተቀብሎ ማራቸው ቢባል ይህ ሊሆን አይችልም ብሎ መከራከር እንዴት ይቻላል? መጠራጠር ይቻል ይሆናል፣ ምክንያቱም ተአምር በእምነት የሚቀበሉት እንጂ እንደ ቁሳዊ ነገር ቤተ ሙከራ ውስጥ አስገብተው

የሚፈትሹት አይደለምና፡፡ ፈጽሞ አይሆንም ብሎ መካድ ግን አይቻልም፣ በእግዚአብሔር ሀልውና እንዲሁም በከሃሊነቱ የማያምን ከሃዲ ካልተሆነ በስተቀር፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስም በእምነት ካልሆነ በስተቀር በሌላ ሊብራሩ የማይችሉ ከላይ እንደ ጠቀስናቸው ያሉ ሌሎች ብዙ ተአምራት አሉ፡፡ የተአምር ጠባዩ እንዲህ ነውና፡፡

ከዚህ አንጻር በላኤ ሰብእን (የቀድሞ ስሙ ስምዖን ነበር) እግዚአብሔር የእመቤታችንን ምልጃ ተቀብሎ ማረው ቢባል የሚያስጨንቀው ነገር ምኑ ነው? ፈያታዊ ዘየማንኮ ስንት ሰው እንደ ገደለ ስላልተጻፈ እንጂ ዕድሜ ልኩን ደም ሲያፈስ ሰው ሲገድልና ሲቀማ የኖረ ጸጉ ሽፍታ ነበር፡፡ ዳዊት ኦርዮን በግፍ ካስገደለው በኋላ ነበር እግዚአብሔር ይቅር ያለው፡፡ ምናሴ የተባለው የይሁዳ ንጉሥ በዘመኑ በግፍ ያፈሰሰው ደምና ያጠፋው ሕይወት መጠን አልነበረውም፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ "ደግሞም <u>ምናሴ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ይሠራ ዘንድ ይሁዳን ካሳተበት ኃጢአት ሌላ ከዳር እስከ ዳር ኢየሩሳሌምን እስኪሞላት ድረስ እጅግ ብዙ ንጹሕ ደም አፈሰሰ</u>" ይላልና፡፡ 2 ነገ. 21፡16 በኢየሩሳሌም በነበረው ቤተ መቅደስ ውስጥ የጣዖት መሠዊያዎች እስከ መሥራት የደረሰ ክፉ ንጉሥ ነበር፤ "እግዚአብሔርም፦ ስሜን በኢየሩሳሌም አኖራለሁ ባለው በእግዚአብሔር ቤት መሠዊያዎችን ሠራ። በእግዚአብሔርም ቤት በሁለቱ ወለሎች ላይ ለሰማይ ሠራዊት ሁሉ መሠዊያዎችን ሠራ" እንዲል፡፡ እንዲሁም ምናሴ የራሱን ልጅ እንኳ ሳይቀር ለጣዖት የሠዋ ሰው ነበር፤ "ልጁንም በእሳት አሳለፈ፥ ሞራ ገላጭም ሆነ፥ አስማትም አደረገ፥ መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችንም ሰበሰበ፥ ያስቈጣውም ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ክፉ ነገር አደረገ" ይላል፡፡ 2 ነገ. 21፡4-6

ሆኖም ምናሴ በመጨረሻ ዘመኑ ላይ እግዚአብሔር በመከራ ስለ ጎበኘው ተመልሶ ንስሐ ስለ ገባ እግዚአብሔር ምሮታል፣ ይቅር ብሎታል፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ ይህንም እዲህ ሲል ይነግረናል፦

> እግዚአብሔርም ምናሴንና ሕዝቡን ተናገራቸው፥ ግን አልሰሙትም። ስለዚህም እግዚአብሔር የአሦርን ንጉሥ ሠራዊት አለቆች አመጣባቸው፤ ምናሴንም በዛንጅር ያዙት፥ በሰንሰለትም አስረው ወደ ባቢሎን ወሰዱት። በተጨነቀም ጊዜ አምላኩን እግዚአብሔርን ፈለገ፥ በአባቶቹም አምላክ ፊት ሰውነቱን እጅግ አዋረደ፥ ወደ እርሱም ጸለየ፥ እርሱም ተለመነው፤ ጸሎቱንም ሰማው፥ ወደ መንግሥቱም ወደ ኢየሩሳሌም መለሰው፤፡ ምናሴም እግዚአብሔር እርሱ አምላክ እንደ ሆነ አወቀ። 2 ዜ. 33፡10-13

በላኤ ሰብእም በመጀመሪያ እግዚአብሔርን የሚፈራና እንግዳ ተቀባይ ነበር፡፡ ኋላ ግን ሰይጣን በተንኰሉ ገባበትና ሰው እንዲበላ አደረገው፡፡ የኋላ ኋላ ግን የእመቤታችንን ስም ሲሰማ ወደ ልቡ ተመለሰ፤ ንስሐም ገባ፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ እንኳ ጌታን ሦስት ጊዜ በተከታታይ ከካደው በኋላ ወደ ልቡ ተመልሶ እንዲጸጸትና እንዲያለቅስ የዶሮ ጩኸት ምክንያት የሆነው ከሆነ ለበላኤ ሰብእ የእመቤታችን ስም ወደ ልቡ እንዲመለስ ምክንያት ቢሆነው ምን ይገርማል? ከዚያም እግዚአብሔር በላኤ ሰብእን ማረው፡፡ የቅዱስ ጴጥሮስ ጥላው ሕሙማንን ይፈውስ ከነበረ የወላዲተ አምላክ የቅድስት ድንግል እመቤታችን ምልጃዋና ጥላዋ በላኤ ሰብእን የእግዚአብሔርን ምሕረት እንዲያገኝ ረዳው ቢባል ይህ ሊሆን አይችልም ሊያሰኝ የሚችል አንዳችም መሠረት የለም፡፡ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚል ካለ እኛም የጴጥሮስ ጥላ ድውያንን መፈወስ ኢጋንንትን ማውጣት እንዴት ቻለ? ወንበዴው ፈያታይ ዘየማን ስንት ነቢያትን፣ አበውና ደጋግ ሰዎችን ቀድሞ እንዴት ገነት ገባ? ብለን እንጠይቃቸዋለን፡፡

እንደዚሁም ከነቢያት ልጆች አንዱ እንጨት ሲቆርጥ ምሳሩ በዮርዳኖስ ውኃ ውስጥ በወደቀበት ጊዜ ነቢዩ ኤልሳዕ እንጨት ቆርጦ ምሳሩ ወደ ወደቀበት ጣለው፥ ብረቱም ተንሳፈፈ። የወደቀበቱም ሰውዬ በውኃው ላይ የተንሳፈፈውን ምሳሩን በእጁ ወሰደው፡፡ 2 ነገ. 6፡1-7 ታዲያ በባሕርዩ የማይሰጥመው እንጨቱ ሰጥሞ በውኃ ላይ የማይንሳፈፈው ብረቱ እንዴት ተንሳፈፈ? ሁሉን እናውቃለን የሚሉና ይህ ልክ ነው፥ ይህ አይደለም እያሉ ራሳቸውን ብይን ሰጪዎች ያደረጉ ተሐድሶዎች፣ እስኪ ይህ እንዴት ሊሆን እንደሚችል ያስረዱን!

የቤተ ክርስቲያን አፍራሽና ነፍሰ ገዳይ የነበረውን ሳውልንስ ለምን ጠራው? ጌታችን ሳውልን ራሱ ሳውል ተጸጽቶ ንስሐ ገብቶ አይደለም የጠራው፣ ክርስቲያኖችን ለማሰርና የበለጠ ለማሰቃየት ወደ ደማስቆ እየሄደ በመንገድ ላይ ሳለ ተገልጦ ጠራው እንጂ፡፡ የሐዋ. 9፡1-6 ስለዚህ ቸርነቱን አመስግነና አምኖ መቀበል ሲገባ እንመርምረው ካልን ግን መውጫ ከሌለው ከባድ የስህተት አዘቅት ውስጥ እንገባለን፡፡ በባሕ ሰብእ እግዚአብሔርን ስለ ካደ እመቤታችን ልትጸልይለት አይገባም ነበር የሚል ካለ ሙሴ በዚያ ሁሉ ተአምራት ከግብጽ ምድር ያወጣቸውንና መና እየመገባቸው የነበረውን እግዚአብሔርን ክደው የጥጃ ምስል ሠርተው ጣዖት እያመለኩ ለነበሩት ለእስራኤላውያን ማራቸው ብሎ ለምን ለመነላቸው? ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶስን አለማመን ብቻ ሳይሆን ለሰቀሉትና መራራ ክርቤ ባፉ ላደረጉለት ለክፉዎች ለአይሁድ "እኔ ራሴ የተረገምሁ ልሁን" እስኪል ድርሶ ለምን ጸለየላቸው? አብርሃምስ ግብራቸው አስጸያፊ ለሆኑት ለሰዶማውያንና ለገሞራውያን ሰዎች ማራቸው እያለ ለምን ማለደላቸው? እመቤታችን ለበባሕ ሰብእ እግዚአብሔርን ለመነችለት የሚለውን ልክ አይደለም ብለው የሚቆሩ ሰዎች እስኪ እነዚህን ነገሮች ከራሳቸው የፈጠራ አስተሳሰብ ጋር የሚያስታርቋቸው እንዴት አድገው ይሆን?

በዚህም ላይ ዋናው ነገር ይህ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የመዳኛ መንገድ ብላ የምታስተምረው አይደለም፤ ተአምር እንጂ፡፡ ይህም ማለት እንደ በባሕ ሰብእ ሰው እየበላችሁ ብትኖሩም ችግር የለውም፣ የኋላ ኋላ እመቤታችን እየማለደች ታድናችኋለችና ብላ ቤተ ክርስቲያን አታስተምርም፡፡ ይህ ተአምር ብቻ ነው፡፡ ተአምር ደግሞ ለማን፣ መቼና እንዴት እንደሚደረግ የሚያውቀው የተአምራት ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ኢያሱ ፀሐይን አቁሟል፡ ግን ማንም እየተነሣ ፀሐይን በየጊዜው አቆማለሁ ቢል አይሆንም፤ እግዚአብሔር እርሱ ባወቀ አልፎ አልፎ ለሚፈቅድላቸው ቅዱሳን ብቻ እንጂ፡፡ ዳዊትና ከእርሱ ጋር የነበሩትም በተራበ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ቤት ገብቶ ካህናትም ብቻ እንጂ እርሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት ሊበሉት ያልተፈቀደውን የመሥዋዕቱን ኅብስት በልተዋል፡፡ ይህ ግን ያን ጊዜ ዳዊትና አብረውት የነበሩት ሰዎች ከነበሩበት ሁኔታ አንጻር የተፈቀደላቸው እንጂ ከዚያ በኋላ እንደ ሕግ ሆኖ አልቀጠለም፡፡ 1 ሳሙ. 21፡1-7፤ ማቴ. 12፡3-4 ኤልሳዕ በእንጨት መስጠም ብረቱን እንዲንሳፈፍ ያደረገው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፤ ከዚያ በኋላ ያደረገው መሆኑ አልተጻፈልንም፡ ፡ በአጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉ ብዙ ተአምራት አሉ፤ ሆኖም እነዚያ ተአምራት በየጊዜው የሚደጋገሙ አይደሉም፤ እንዲያማ ከሆነ ተአምርነታቸው ይቀራል፡፡ ብረት ሁል ጊዜ በውኃ ላይ የሚንሳፈፍ ከሆነ መንሳፈፉ ተአምር የሚያሰኘው ነገር አይኖርም፤ ፀሐይም ለማንም ሰው የምትቆም ከሆነ ኢያሱ ያደረገው ተአምር አይሆንም ነበር፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ለበባሕ ሰብእ ያደረገው ነገር ሁሉን የሚያውቅ አምላክ እርሱ ባወቀ ያደረገው ተአምር እንጂ ሕግ ስላልሆነ ቤተ ክርስቲያን ይህን በተአምርነቱ ትገልጸዋለች እንጂ እንደ ሕግ አድርጋ በእርሱ መንገድ ሂዱ ብላ አታስተምርም፡፡ ተአምር ደግሞ በእምነት የምንቀበለው እንጂ እኛ መዝነን የምንጥለውና የምናሳልፈው አይደለም፡፡

## 6.3.2 የቅዱሳን አማላጅነት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

"ምልጃ" ጸሎች ነው፡፡ ይህም አንዱ ስለ ሌላው የሚያቀርበው ጸሎት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ጸሎትም በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ነገር ነው፡፡ እግዚአብሔር ስለ ራሳችን ከምንጸልየው ጸሎት በበለጠ ስለ ሌላው ሰው የምንለምነውን ልመና ይሰማል፡፡ ምክንያቱም ስለ ሌላው መጸለይ ከራስ ወዳድነት ያለፈ፣ የፍቅርን መሠረተ ሃሳብ የተረዳና ለሌላው ወገናችን ያለንን ፍቅር በተግባር የምንገልጥበት ስለሆነ ነው፡፡ መድኃኒታችን ስለ ራሱ ሳይሆን ስለ ሌሎች፣ ማለትም ስለ እኛ ራሱን አሳልፎ እስከ መስጠትና እስከ መስቀል ሞት ድረስ ከደረሰ እኛ ለሌሎች ወገኖቻችን መሞት እንኳ ባንችል መጸለይ እንዴት ይበዛብናል? ስለሆነም ስህተት የሚሆነው አንዱ ስለ ሌላው የምልጃ ጸሎት ባያደርግ እንጂ ቢያደርግ አይደለም፡፡

ለአንዳንዶች የቅዱሳን አማላጅነት የእግዚአብሔርን መሐሪነት የሚያሳንስ፣ ወይንም ደግሞ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰዎችን የበለጠ ርህሩኆችና ደጎች ማድረግ መስሎ የሚታያቸው አሉ፡፡ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ፈታሒነት አንጻር የማይሄድ የሚመስላቸውና በአጠቃላይ ጉዳዩ የሚጸንናቸው ሰዎች ይኖራሉ፡፡ ሆኖም ግን የቅዱሳን አማላጅነት የእግዚአብሔርን መሐሪነት ይበልጥ የሚገልጥና የሚያጎላ እንጂ የሚሸፍን አይደለም፡፡ ይህን ጉዳይ ከዚህ ቀጥሎ እንመልከት፡፡

## 6.3.2.1 የቅዱሳን አማላጅነት አግባብነት

1) ከእግዚአብሔር ርኅራኄና መሐሪነት አንጻር

◉ "... በዘረጋሃውና በከፈትከው ብቸኛ መንገድ በክል ካንተ ጋር በቀጥታ እንዳንገናኝ፣ በአንተና በእኛ መካከል ጣልቃ ገብተው ራሳቸውን ካንተ ይልቅ ርኅሩኃን፣ ቸሮች፣ ገሮች፣ በምሕረትና በፍቅር የተሞሉ አስመስለው የቀረቡንን፣ አባቶቻችን ግን ያለወቋቸውን መናፍስት በመማጠን ዓመታትን አሳልፈናል፡፡ በአረማውያን ጣዖታት ስም ተጽፈው የነበሩትን የጥንት ተረቶችና ወጎች በቅዱሳን መላእክትህ፣ የልጅህንም ፍጹም አዳኝነት ሲመሰክሩ በሞቱልህ ሰማዕታትህ ስም በመለወጥ የጻፍናቸውን ድርሳናት፣ ተአምራትና ገድላት ሰብከናል፤ በዚህም ሥራችን የዋሃንን በማሳሳት አርክሰናል፤ በድለናል፡፡" (ሥራ ቁ. 13 ገጽ 5)

ቅዱሳን ያማልዳሉ ሲባል ተሐድሶዎች ባልተረዳ አእምሯቸው እንደሚሉት እግዚአብሔር ጨካኝ፣ ቅዱሳን ደግሞ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሰዎች የሚያዝኑ ደጋጎችና ርህሩኃን ሆነው አይደለም፡፡ እንደ እግዚአብሔር ያለ ቸርና ርህሩኅ ማንም የለም፤ ከእርሱ የተሻለ ርህሩኅ አለ ማለት ይቅርና እንዲህ ብሎ ማሰብም አይቻልም፣ አይገባምም፡፡ የቅዱሳን አማላጅነት ድንቅና ጥልቅ የሆነው የእግዚአብሔር ቸርነት የሚሠራበት (የሚገለጥበት) አንድ መንገድ ነው፡፡ ለምሳሌም እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ትተው አሮንን ጣዖት አሠርተው ላቆሙት የጥጃ ምስል በሰገዱ ጊዜ እግዚአብሔር ያጠፋቸው ዘንድ ሙሴን ተወኝ አለው፡፡ ሙሴና እግዚአብሔር እንዲህ ተነጋገሩ፡-

> እኔ ይህን ሕዝብ አየሁት፣ እነሆም አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው፤ አሁንም ቁጣዬ እንዲቃጠልባቸው እንዳጠፋቸውም ተወኝ፤ አንተንም ለታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ አለው፡፡ ሙሴም በእግዚአብሔር በአምላኩ ፊት ጸለየ፣ አለም፡- አቤቱ ቁጣህ በታላቅ ኃይልና በጽኑ እጅ ከግብፅ ምድር ባወጣኸው በሕዝብህ ላይ ስለ ምን ተቃጠለ? ... ከመዓትህ ተመለስ፤ ለሕዝብህም በክፋታቸው ላይ ራራ፡፡ ዘራችሁን እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛለሁ፣ ይህችንም የተናገርኋትን ምድር ሁሉ ለዘራችሁ እሰጣታለሁ፣ ለዘለዓለምም ይወርሷታል ብለህ በራስህ የማልህላቸውን ባሪያዎችህን አብርሃምን ይስሐቅንና እስራኤልንም አስብ፡፡ እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፋት ራራ፡፡ ዘጸ. 32፡7-14

እዚህ ላይ ሲታይ እግዚአብሔር "ተወኝ፣ ላጥፋቸው" ባይ፣ ሙሴ ደግሞ "እባክህ ራራላቸው" ባይ ሆነው ይታያሉ፡፡ ታዲያ ሙሴ "ከመዓትህ ተመለስ፤ ለሕዝብህም በክፋታቸው ላይ ራራ" እያለ እግዚአብሔርን ሲለምን፣ እግዚአብሔር ደግሞ "እኔ ይህን ሕዝብ አየሁት፣ እነሆም አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው፤ አሁንም ቁጣዬ እንዲቃጠልባቸው እንዳጠፋቸውም ተወኝ" ሲል ሙሴ ከእግዚአብሔር የበለጠ "መሐሪና ገር፣ በፍቅር የተሞላና ርህሩኅ" መሆኑ ኖሯልን? በጭራሽ! ጥንቱንም ሙሴ ስለ ሕዝቡ ይማልድላቸውና ይታገሣቸው ዘንድ፣ በአጠቃላይ በሁሉም ነገር እንደ ሞግዚት ሆኖ ይንከባከባቸውና ይመራቸው ዘንድ አደራ ብሎ የሰጠው እግዚአብሔር ነበር፡፡ ስለ ሕዝቡ እንዲራራና እንዲማልድላቸው ይህን ሥልጣንና አደራ ለሙሴ በምሥጢር የሰጠው ራሱ እግዚአብሔር ነበር፡፡ ሙሴ ይህን በደብረ ሲና በቆየባቸው አርባ ቀናት እግዚአብሔር በምሥጢር የነገረውን ነገር ኋላ ላይ ነገሩ ሲከብደው ወደ እግዚአብሔር ባቀረበው አቤቱታው ላይ ገልጾታል፤ እንዲህ ሲል፡-

> ሙሴም ሕዝቡ በወገኖቻቸው፤ ሰው ሁሉ በድንኳኑ ደጃፍ ሲያለቅስ ሰማ፤ የእግዚአብሔርም ቁጣ እጅግ ነደደ፤ ሙሴም ተቆጣ፡፡ ሙሴም እግዚአብሔርን አለው፡- ለምን በባሪያህ ላይ ክፉ አደረግህ? ለምንስ በፊትህ ሞገስ አላገኘሁም? ለምንስ የዚህን ሕዝብ ሁሉ ሸክም በእኔ ላይ አደረግህ? አንተ ለአባቶቻቸው ወደ ማልህላቸው ምድር አደርሳቸው ዘንድ፡- ሞግዚት የሚጠባውን ልጅ እንድታቅፍ በብብትህ እቀፋቸው የምትለኝ በውኑ ይህን ሕዝብ ሁሉ እኔ ፀንሼዋለሁን? ወለድሁትንስ? በፊቴ ያለቅሳሉና፤ የምንበላውን ሥጋ ስጠን ይላሉና ለዚህ ሕዝብ ሁሉ የምሰጠው ሥጋ ከወዴት አገኛለሁ? እጅግ ከብዶኛልና ይህን ሁሉ ሕዝብ ልሸከም አልችልም፡፡ እንዲህስ ከምታደርግብኝ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ በእኔ ላይ የሚሆነውን መከራ እንዳላይ እባክህ ፈጽሞ ግደለኝ፡፡ ዘኊ. 11፥10-15

የሙሴ ለሕዝቡ መራራትና "እባክህ ማራቸው፡ ራራላቸው" እያለ መማለዱ ከእግዚአብሔር የተሰጠና የተገኘ ነበር ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ምልጃ የሚደረገው ሰዎች ከእግዚአብሔር የበለጠ ርኅሩኅና ደጎች ስለ ሆኑ አይደለም፤ እንዲህ ሊታሰብም አይችልም፡፡ ምልጃ በእግዚአብሔር ሥልጣን ጣልቃ መግባትም አይደለም፡፡ እግዚአብሔር እንደ እምባ ጠባቂ መሪዎች "ምን አገባችሁ?" ባይ አይደለምና፡፡ እርሱ ራሱ አንዱ ስለ ሌላው እንዲጸልይና እንዲለምን ያሳሰበ፡ ሳይለምኑት ሲቀሩ ሳይሆን ሲለምኑት ደስ የሚለው ቸር አምላክ ነውና፡፡

ሲለምኑት ደስ የሚለው ብቻ ሳይሆን እኛ ስለ ራሳችንም ሆነ ስለ ሌሎች ወገኖቻችን ስንለምነው ለእኛው ለራሳችን ዋጋ የሚሰጥ ፍጹም ደግ አባት ነው፡፡ "ጸልዩ፤ ለምኑ ይሰጣችኋል፡ በር አንኳኩ ይከፈትላችኋል" ያለው ራሱ ነውና፡፡ "እኔ የምሰጣችሁን ብቻ ወይም ከእኔ የሚወጣውን ፍትሕ ብቻ ዝም ብላችሁ ጠብቁ፤ ከዚያ ውጭ የሚያገባችሁ ነገር የለም" እንደሚል እንደ እምባ ገነን ወይም ለሥልጣኑ እንደሚፈራ ምድራዊ ባለ ሥልጣን አይደለምና፡፡ ይልቁንም ከእርሱ የባሕርይ አምላክነት የተነሣ ፍጡራን የጸጋ አማልክት እስኪሆኑ ድረስ የሚሰጥ ቸር ነውና፡፡ ይህም የባሕርይ ቸርነቱን ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ማሠልጠንና ማክበር የማያስጋው ዘለዓለማዊ የባሕርይ አምላክነቱን ይመሰክራል፡፡

አሮጌውን የፕሮቴስታንት ትምህርት በአዲስ እራፊ ጠቅልለው አዲስ አስመስለው ብቅ ለማለት የሞከሩት ተሐድሶዎች በዚህ ዙሪያ እንዲህ ብለዋል፡-

◉ "የሙሴ የልመናው መሠረት እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ የገባውን ቃል ኪዳን መሠረት ያደረገ ነበር እንጂ በራሱ ማንነት ተመሥርቶ አልለመነም፡፡ ሁል ጊዜ ቅዱሳን በራሳቸው ማንነት ተመሥርተው ስለ እኔ ብለህ አይሉም፤ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ርህራኄ መሠረት አድርገው እንጂ፡፡" (መቅደስ የገቡ መናፍቃን፤ ገጽ 40)

በመጀመሪያ መታመን ያለበት እግዚአብሔር አንዱ ስለ ሌላው የሚያቀርበውን የምልጃ ጸሎት የሚሰማና የሚቀበል መሆን ነው፡፡ ሙሴ ስለ ሕዝቡ እግዚአብሔርን በምልጃ ጸሎት ጠይቆ እግዚአብሔርም የሰማውና ልመናውን የተቀበለው መሆኑን ማመን የመጀመሪያው ደረጃ ነው፡፡ የሙሴ የልመናው መሠረት ይህ ነው፤ ያ ነው ወደሚል መሄድ ከተገባም ወደዚያ መሄድ የሚቻለው ከዚህ በኋላ ነው፡፡ መሠረቱን ለማፍረስ ወይም ለማስረሳት መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ወዳልተናገረው ነገር ዘልሎ መግባት ከንቱ ድካም ነው፡፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሚያስተምረን በሙሴ ጸሎት እግዚአብሔር ሳጥፋቸው ተወኝ ሲላቸው የነበሩትን ሕዝብ ይቅር ማለቱንና መማሩን፤ ይህ የሙሴ አማላጅነትም የራሱ የእግዚአብሔር ቸርነት መሆኑን (መጀመሪያ ስለ እነርሱ እንዲጸልይላቸውና እንዲንከባከባቸው በምሥጢር አደራ የሰጠው በመሆኑ፤ በሁለተኛ ደግሞ ሲያጠፉ ሲማልድላቸው ምልጃውን በመቀበሉ) ነው፡፡ ይህንም ልበ አምላክ ዳዊት "ሰበ አኮ ሙሴ ኅሩዩ ቆመ ቅድሜሁ አመ ብድብድ ከመ ይሚጥ መቅሠፍተ መዓቱ ወከመ ኢይሥርዎሙ - እንዳያጠፋቸው ቍጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠው ሙሴ በመቅሠፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ"

ብሎ በድጋሚ በአጽንኦት ገልጾታል፡፡ መዝ. 105፡23 ስለዚህ መጀመሪያ ቅዱሳን የሚያቀርቡትን ምልጃ እግዚአብሔር እንደሚቀበልና ይቅርታና ምሕረትን እንደሚሰጥ ይመኑ፡፡ ከዚያ በኋላ ወደ ቀጣዩ ጉዳይ መሸጋገር ይቻላል፡፡ አለበለዚያ ግን ከእውነት ጋር ድብብቆሽ ለመጫወት መሞከር ነው፡፡

ተሐድሶዎች ሆይ፡ "የሙሴ የልመናው መሠረት እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ የገባውን ቃል ኪዳን መሠረት ያደረገ ነበር እንጂ በራሱ ማንነት ተመሥርቶ አልለመነም" ማለት ምን ማለት ነው? ማንጠልጠያ እንደ ሌለው ቅል ያለ አባባል ነው፡፡ ታዲያ ድሮውንስ ምልጃ ምንድን ነው? እግዚአብሔር ከእነርሱ በፊት ለነበሩ አበው የገባውን ቃል እያሰቡ ምሕረት እንዲያደርግ መለመን ነው እንጂ ሌላ ምንድን ነው ሲባል ሰምታችሁ ኖሯል? የምትቃወሙትን ነገር እንኳ ቢያንስ መጀመሪያ በደንብ ተረድታችሁ ቢሆን ኖሮ እንዲህ ወዳለ ዝብርቅርቅ ያለ ነገር ውስጥ አትገቡም ነበር፡፡ እንዲሁም "ሁል ጊዜ ቅዱሳን በራሳቸው ማንነት ተመሥርተው ስለ እኔ ብለህ አይሉም፣ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ርህራኄ መሠረት አድርገው እንጂ" ማለታችሁ ድሮውንስ ቅዱሳን "ማርልኝ" ይላሉ እንጂ ራሳቸውን አግዝፈውና ቦታ ሰጥተው "እኔ" አይሉም፡፡

እንዲያውም "እኔ" የሚለው ቃል የራሱ የልዑል እግዚአብሔር መጠሪያ ስም መሆኑን ቅዱሳን አሳምረው ያውቃሉ፡፡ እግዚአብሔር ለሙሴ ራሱን ሲገልጥ "ያለና የሚኖር እኔ ነኝ - I AM THAT I AM" ብሎ ነውና፡፡ በሐዲስ ኪዳንም "እኔ የወይን ግንድ ነኝ፣ መልካም እረኛ እኔ ነኝ፣ እኔ ነኝ፣ አትፍሩ፣ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፣ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፣ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፣ . . . " እያለ ራሱን "እኔ" ብሎ የጠራው እርሱ ነውና፡፡ ስለዚህ ይህ አባባላችሁ ከመነሻው ባዶ ነው፡፡ እግዚአብሔርን በምልጃ የሚጠይቁትም ቸርነቱን መሠረት አድርገው መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ታዲያ እንደ አዲስ ነገር "የእግዚአብሔርን ቸርነትና ርህራኄ መሠረት አድርገው እንጂ" ያላችሁት እኛስ ምን አልን? ቅዱሳን በባሕርያቸው ወይም በሥልጣናቸው ማድረግ ይችላሉ ስንል ሰማችሁን? ወይስ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የምትለው ነገር ሁሉ ስለማይዋጥላችሁ በእናንተ አፍ ካልተባለ በቀር ስህተት ነው ማለት ነው? በአንድ በኩል ምልጃ የለም ትላላችሁ፣ መኖሩን መጽሐፍ ቅዱስ ሲመሰክርባችሁና መሄጃ ስታጡ ደግሞ ሃሳቡን በውል ማስረዳትና ማቅረብ የማይችል ሕፃን ልጅ ይመስል መያዣና መጨበጫ የሌለው መላ ቢስ ነገር ትላላችሁ፡፡ በእውነቱ በነገረ ሃይማኖት ላይ ይህን ያህል ጨዋታ መጫወታችሁ በእጅጉ ያሳዝናል፡፡

## 2) ከእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት አንጻር

ቅዱሳን ያማልዳሉ ሲባል እግዚአብሔር የማያውቀው ነገር ኖሮ ሌላ ነጋሪ፣ ወይም የሚረሳ ሆኖ ሌላ አስታዋሽ የሚያስፈልገው ሆኖ አይደለም፣ ይህ ከእርሱ ይራቅ! እግዚአብሔር እንደ ምድራውያን ባለ ሥልጣናት የሚነግረው ወይም የሚያስታውሰው አያስፈልገውም፤ እርሱ ሁሉን ነገር ከመደረጉ ብቻ ሳይሆን ከመታሰቡ በፊት ልክ እንደ ተደረገ ያህል (ከተደረገ በኋላ እንደሚታወቀው አድርጎ) ያውቀዋልና፡፡ ስለዚህ የቅዱሳን አማላጅነት ከእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት አንጻር የሚጣላ አይደለም፡፡ ጸሎት የምንጸልየው እግዚአብሔርን እንደ ሰው ስለሚረሳ ለማስታወስ አይደለምና፡፡ ወይም ደግሞ የምንፈልገውን መሻታችንን ካልነገርነው ስለማያውቅ እንደ አዲስ ለመንገር አይደለም፡፡ እንደዚሁም ሁሉ በምልጃ ጸሎት አንዱ ለሌላው መጸለዩና መማለዱ ከእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት አንጻር የሚጣላ አንዳችም ነገር የለውም፡፡

## 3) ከሰዎች ፍጹም መሆን አለመሆን አንጻር

የእግዚአብሔርን ቸርነት ደጅ ለመጥናትና አንዱ ስለ ሌላው ለመማለድ የግድ ፍጹም መሆን አይጠበቅም፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ክፍሎች እንደምንመለከተው በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ስለ ሌላው የጸለዩና ያማለዱ ሰዎች የግድ የፍጹምነት ደረጃ ላይ ስለ ደረሱ አልነበረም፡፡

## 6.3.2.2 እማላጅነት ለምን?

1) የፍቅር መንገድና መገለጫ ነው፡፡

አንዱ ስለ ሌላው የሚያደርገው ልመና (እስተብቁዖት) ለሌላው ያለውን ፍቅር በተግባር የሚገልጽበት መንገድ ነው፡፡ ሙሴ "እነርሱን ከምታጠፋ እኔን ከሕይወት መጽሐፍ ደምስሰኝ" ብሎ፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ስላላመኑ አይሁድ ወገኖቼ "ስለ ወንድሞቼ ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንድሆን እጸልይ ነበርና" እስከ ማለት ደርሰው ለወገኖቻቸው ጸልየውላቸዋል፡፡ ሮሜ 9፡3 እስከዚህ ደርሰው የጸለዩላቸው ለወገኖቻቸው ከነበራቸው ፍቅር የተነሣ ነበር፡፡ ሊቀ ነቢያት ሙሴ በብዙ ተአምር ከግብጽ ባርነት ያወጣቸውን እግዚአብሔርን ረስተው "ከግብጽ ምድር ያወጣን ሙሴ" ሲሉት፣ ጣዖት አቁመው ሲሰግዱ ለነበሩት እስራኤላውያን እግዚአብሔር ይምራቸው ዘንድ ከለመነላቸው፡ ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ክርስቶስን ለሰቀሉት አይሁድ እንኳ "ራሴ የተረገምሁ ልሁን" እስከ ማለት ደርሶ ከጸለየላቸው በኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒትነት ላመኑ ወገኖቻችን ብንጸልይላቸው ጥፋቱ ምን ላይ ነው? ለሌሎች የሚደረግን የምልጃ ጸሎት የሚቃወሙ ሰዎች የቤተ ክርስቲያን የአንድነት መንፈስ ያልገባቸውና ከራሳቸው በስተቀር ለሌላው የማያስቡ ራስ ወዳዶች ብቻ ናቸው፡፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም" በማለት የእውነተኛ ፍቅር መገለጫው ራስን ለሌላው አሳልፎ እስከ መስጠት መድረስ መሆኑን በቃሉም አስተምሮናል፤ በተግባርም አሳይቶናል፡፡ ዮሐ. 15፡13 ታዲያ እኛ ራሳችንን ስለ ሌላው ወንድማችን አሳልፈን መስጠት ቢያቅተን እግዚአብሔርን ስለ እነርሱ መለመን ሊበዛብን ይገባልን? ቅዱሳን ያደረጉት ይህን ነው፡፡ ስለ ሌላው ወንድማቸው መዳን ሲሉ በጸሎትና በልመና እግዚአብሔርን ተማጸኑ፤ ይማጸናሉም፡፡ ይህ ተገቢ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተግባር እንጂ አንዳችም የሚያስነቅፍ ነገር የለውም፡፡ ይህ የሚነቀፍ ከሆነም የሚነቀፈው በኢአማንያንና በአሕዛብ ዘንድ ነው፡፡

2) የቤተ ክርስቲያን የባሕርይዋና የመንፈስ አንድነት መገለጫ ነው፡፡

"ወኩሉ ቦቱ ቆመ ወውእቱ ርእሳ ለቤተ ክርስቲያን - ሁሉ በእርሱ ተጋጥሟል፣ እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፡፡" ቆላ. 2፡18 ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል እንደ መሆኗ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ደግሞ የአካል ክፍል ነው፡፡ ለሌላው የአካል ክፍል የማያስብና ብቻዬን እኖራለሁ የሚል የአካል ክፍል የለም፣ ካለም ጤነኛ አካል አይደለም፡፡ ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን አካላት የሆንን እና በክርስቶስ አንድ አካል የሆንን ሁላችን አንዳችን ስለ ሌላው አካል ማሰብና መጸለይ ይገባናል፡፡ አንዱ ለሌላው የሚያደርገው የምልጃ ጸሎት የዚህ የቤተ ክርስቲያን የመንፈስ አንድነትና ምንነት መገለጫና ውጤትም ነው፡፡ መድኃኒታችን እንዲህ ብሎ አስተምሮናልና፡- "አንተ አባት ሆይ፣ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፣ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ። እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፣ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ" ዮሐ. 17፡20-22

"በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ" የተባልነው ለዚህ ነው፡፡ ኤፌ. 6፡18 ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክታቱ ደጋግሞ ምእመናንን ጸልዩልኝ ይል የነበረበት ምክንያት አንዱ ይህ ነበር፡፡ "ወንድሞች ሆይ፣ ስለ እኛ ጸልዩ"፤ "ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ። ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው" ተብሎ የተገለጸው ይህ ነው፡፡ 1 ተሰ. 5፡25፤ 1 ጢሞ. 2፡1-4

3) አንዱ ሰው ለሌላው ሰው የሚጸልይለት ጸሎት የሚጠቅመው ስለሆነ

በመጽሐፍ ቅዱስ ራሳቸው ጸልየው ወይም ወደ ጌታ ቀርበው ሳይሆን ሌሎች ሰዎች በጸለዩላቸው ጸሎትና ወደ ጌታችን ቀርበው በለመኑላቸው ልመና የተጠቀሙ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 8 የተገለጸው የመቶ አለቃ የታመመውን ልጁን በቤት ትቶ ወደ ጌታችን መጥቶ በለመነው ልመና ልጁ ተፈወሰለታል፡፡ ከነዓናዊቷ ሴትም የታመመችውን ልጇን ይዛ ሳይሆን እርሷ ብቻ መጥታ ጌታችንን በመማጸኗ የታመመችው ልጇ ድናላታለች፡፡ ማቴ. 15፡22-28 ሰዎች በአልጋ ተሸክመው ከሰው ብዛት የተነሣ መግባት ስላልቻሉ ጌታችን የነበረበትን የቤቱን ጣራ አንስተው ያስገቡትን በሽተኛም እንዲሁ ጌታችን አድኖታል፡፡ ቅዱስ ወንጌል ስለዚህ ሲናገር "እነሆም በአልጋ የተኛ ሽባ ወደ እርሱ አመጡ። ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን፡ - አንተ ልጅ፥ አይዞህ፥ ኃጢአትህ ተሠረየችልህ አለው" ይላል። ማቴ. 9፡2 "እምነታቸውን አይቶ" የሚለው ቃል በሽተኛውን በአልጋ ተሸክመው ያድነዋል ብለው ወደ ጌታችን ያመጡትን ሰዎች እምነት ነው፡፡ "እምነቱን አይቶ (የበሽተኛውን ብቻ) አላለም፤ "እምነታቸውን አይቶ" አለ እንጂ፡፡ የበሽተኛው እምነት "እምነታቸውን አይቶ" የሚለው ውስጥ ተካትቷል ቢባል እንኳ ጌታችን ያየው የበሽተኛውን እምነት ብቻ ሳይሆን ወደ እርሱ ተሸክመው፣ ከዚያም በላይ ጣራውን አንስተው ወደ ጌታ እስኪያቀርቡት ያደረሳቸው ጽኑ እምነት የነበራቸውን የአምጭዎቹን ሰዎች እምነት አብሮ እንዳየና በዚህም በሽተኛውን እንደ ፈወሰው በቅዱስ ወንጌል ተጽፏል፡፡ ለዚያ በሽተኛ መፈወስ የአምጭዎቹ እምነት ታላቅ ሚና ነበረው፤ ለዚህ ነው ጌታችን "እምነታቸውን አይቶ ሽባውን፡- አይዞህ፥ ኃጢአትህ ተሠረየችልህ" ያለው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ "በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ የጌታ ቃል እንዲሮጥ በእናንተም ዘንድ ደግሞ እንደሚሆን እንዲከበር፥ እምነትም ለሁሉ ስለማይሆን ከዓመፀኞችና ከክፉዎች ሰዎች እንድንድን ስለ እኛ ጸልዩ" ያለውም ለዚህ ነው። 2 ተሰ. 3፡1-2 እንዲሁም "በእግዚአብሔር ፈቃድ በደስታ ወደ እናንተ መጥቼ ከእናንተ ጋር እንዳርፍ፣ በይሁዳ ካሉት ከማይታዘዙ እድን ዘንድ፥ በኢየሩሳሌምም ያለኝ አገልግሎቴ ቅዱሳንን ደስ የሚያሰኝ ይሆን ዘንድ ጸልዩ" ይላል፡፡ ሮሜ 15፡31-32

እንደ ገናም "በዚያን ጊዜም ስለ እርሱ ደግሞ የታሰርሁበትን የክርስቶስን ምሥጢር እንድንናገር እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትልን ዘንድ ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ። ልናገር እንደሚገባኝ ያሀል እገልጠው ዘንድ ጸልዩልኝ" ይላል፡፡ ቆላ. 4፡3-4 ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ እንኳ ሌሎቹን ምእመናን ይሆን ያህል ደጋግሞ "ጸልዩልኝ" ካለ እኛማ ሌሎችን፥ ይልቁንም ደግሞ ቅዱሳንን "ጸልዩልን" ልንል ምን ያህል ይገባናል?

አንዱ ክርስቲያን ለሌላው የሚጸልየው ጸሎት (ምልጃ) እንዲህ ዋጋ ያለው ከሆነ በጸጋ ያደጉ በተጋድሎ የጸኑ ጻድቃን ቅዱሳን የሚያደርጉት ጸሎት ደግሞ የበለጠ ኃይልና ጠቀሜታ አለው፡፡ ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ "የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች፥ ግዳጅም ትፈጽማለች" በማለት እንዳስተማረን፡፡ ያዕ. 5፡16 ስለዚህ ምልጃ አግባብ የሚሆነው ከዚህም አንጻር ነው፡፡

4) እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ያለውን ፍቅርና አክብሮት የሚገልጥበት መንገድ ነው፡፡

እግዚአብሔር አምላክ ተፈትነው የወጡና ታማኝ የሆኑ ወዳጆቹን ለሌሎች የሚያስተዋውቅበትና ክብራቸውን የሚገልጥበት አንዱ መንገድ ሌሎች ሰዎችን እነርሱ እንዲጸልዩላቸው በማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌም እግዚአብሔር የወዳጁን የአብርሃምን ማንነትና ክብር የጌራራ ንጉሥ ለነበረው ለአቤሜሌክ ሲገልጥ እንዲህ አለ፡- "ነቢይ ነውና [አብርሃም] ስለ አንተም ይጸልያል፥ ትድናለህም።" ዘፍ. 20፡7

እንዲሁም የኢዮብን ክብርና ማንነት ለጓደኞቹ ሲገልጥ በወደደ ጊዜ ወደ ኢዮብ እንዲሄዱና እርሱ ስለ እነርሱ እንዲጸልይላቸው አዘዛቸው፡- "እግዚአብሔርም ይህን ቃል ለኢዮብ ከተናገረ በኋላ እግዚአብሔር ቴማናዊውን ኤልፋዝን፦ እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅንን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና ቍጣዬ በአንተና በሁለቱ ባልንጀሮችህ ላይ ነድዷል። አሁን እንግዲህ ሰባት ወይፈኖችና ሰባት አውራ በጎች ይዛችሁ ወደ ባሪያዬ ወደ ኢዮብ ዘንድ ሂዱ፤ የሚቃጠልንም መሥዋዕት ስለ ራሳችሁ አሳርጉ፤ ባሪያዬም ኢዮብ ስለ እናንተ ይጸልያል፤ እኔም እንደስንፍናችሁ እንዳላደርግባችሁ ፊቱን እቀበላለሁ፤ እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና፡፡" ኢዮ. 42፥7-8

5) እግዚአብሔር ከኃጥአን ይልቅ የጻድቃንን ጸሎት የበለጠ ስለሚሰማ ነው፡፡

እግዚአብሔር ወደ እርሱ የሚቀርብን ልመና ሁሉ ይሰማል፤ እርሱ የሁሉ አባት ነውና፡፡ ይልቁንም ደግሞ ጻድቃን ለኃጥአን ወገኖቻቸው የሚለምኑት ልመና በእግዚአብሔር ዘንድ ተወዳጅና ተሰሚ ነው፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ምንም እንኳን ኃጥአንን በክፉ ሥራቸው ቢያዝንባቸውም በቸርነቱ የሚምርበት ምክንያት ይፈልጋልና የቅዱሳንን ምልጃ ለዚሁ ቸርነቱ መንገድ ያደርገዋል፡፡ "የኃጥአን መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው፤ የቅኖች ጸሎት ግን በእርሱ ዘንድ የተወደደ ነው" ተብሏልና፡፡ ምሳ. 15፥8

6) ምልጃ የእግዚአብሔር ትእዛዝና ፈቃድ ነው፡፡

- "ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰው ቀጥተኛ መንገድ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ አገልግሎቱን እንዳይሰጥ ለምእመናን ዝግ ከሆነ በኋላ ሌሎች አቋራጭ የሚመስሉ ነገር ግን ዙሪያ ጥምጥም የሆኑ፤ ይህም ሆኖ ከቶ ወደ አብ የማያደርሱ ብዙ አዳዲስ መንገዶች ተጠርገዋል፡፡" (የተቀበረ መክሊት፤ ገጽ 47)

- ". . . የኢየሱስ ክርስቶስን መንገድነት በመዝጋት በምትኩ ሌሎች መንገዶችን ያዘጋጁ ወገኖች የእግዚአብሔርን ትክክለኛ አድራሻ በማጥፋት ያደረሱት በደል ይህ ነው አይባልም፡፡ በጥቅሉ ሲታይ ግን እንደ ሕዝበ እስራኤል አንድ ብቻ ሳይሆን ሁለት ክፉ ነገሮችን አድርገዋል፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ብቸኛ መንገድነት መዝጋት የመጀመሪያው ጥፋት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለአዳዲሶቹ መንገዶች የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ፣ የእርሱነቱ ብቻ መጠሪያ የሆኑ ስሞቹን ለእርሱ ብቻ ሊቀርብ የሚገባውን ምስጋናና አምልኮ በመስጠት የእግዚአብሔርን ቅዱሳን ማክበር ሳይሆን ወደ ማምለክ መሸጋገር ነው፡፡" (የተቀበረ መክሊት፤ ገጽ 48)

- ". . . በቤተ ክርስቲያናችን የአምላክ ክብርና ስፍራ በተለያዩ ልብ ወለድ ድርሰቶች ለፍጡራን ተሰጥቷል፡፡ ሆኖም ይህ ከብዙኃኑ ሕሊና የተሰወረ ምሥጢር ነው፡፡ በየዐውደ ምሕረቱ "ለቅዱሳን የሚገባውን ክብር እንሰጣቸዋለን እንጂ እናመልካቸውም" ተብሎ የሚነገረው ትክክለኛ አባባል ቢሆንም ወደ ተግባራዊነቱ ግን ጉዳዩን የተገላቢጦሽ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡" (የተቀበረ መክሊት፤ ገጽ 49)

በእነዚህ አባባሎቻቸው ውስጥ ያሉ መሠረታዊ ስህተቶች፡-

1) የቅዱሳንን ምልጃ ሌላ መንገድ አስመስለው ማቅረባቸው

መንገዱ አንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ቅዱሳን በዚች መንገድ የኖሩና የተጓዙ ናቸው፡፡ ቅዱሳን ሌላ መንገድ አይባሉም፤ ከክርስቶስ መንገድነት አማራጭ መንገዶችም አይደሉም፡፡ ቅዱሳን ክርስቶስን ማራቸው ይቅር በላቸው ብለው ይጸልያሉ፤ ይማልዳሉ እንጂ እኛ ራሳችን እናድናችኋለን አይሉም፤ አላሉም፤ ቤተ ክርስቲያናችንም አላለችም፡፡ በእውነቱ እንዲህ ያለውን የወረደ አሉባታቸውን መልስ ባንሰጥበት ይመረጥ ነበር፤ ነገር ግን እንዲህ ያለ የወረደ አባባላቸው እኛንም በዚያው ደረጃ መልስ መስጠት ግዴታ ውስጥ ያስገባን መሆኑ አሳዛኝ ነው፡፡

2) "ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰው ቀጥተኛ መንገድ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዳይሰጥ ተዘግቷል፤ የእግዚአብሔርን ትክክለኛ አድራሻ አጥፍተውታል" ማለታቸው፤

ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰው መንገድ እምነት፤ በጥምቀት የሚገኘው ሥርየት ኃጢአትና ልጅነት፤ አዲስ ሰውነትና በክርስቶስ በሞቱ በመሳፍ የሚገኝ ተስፋ ትንሣኤ፤ በቅዱስ ሥጋውና በክቡር ደሙ የሚገኘው ዘላለማዊ ሕይወት፤ በተቀበሉት ጸጋ መጽናትና መጋደል፤ በክርስቲያናዊ መልካም ሥራ ነው፡፡ ወደ እግዚአብሔር እንደርስ ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ይህን ነው፡፡ ታዲያ እነዚህን ሁሉ ጸጋዎች አያስፈልጉም፤ እንዲሁም በእምነት ብቻ ድኛለሁ እያለ የዘጋቸው ማን ነው? ተሐድሶዎች ወይስ እኛ? እግዚአብሔር የሚገኘው በንጹሕ ልብ በመፈለግ፤ በምሥጢራት በሚሰጠው ጸጋ፤ በጾም በጸሎት፤ . . . እንጂ እንዲሁ በአፈ ጮሌነት ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በማለት፤ ሌሎች የማይሉትን እንደሚሉት እያስመሰሉ በማቅረብና በማሳጥት ነውን? ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኙ ነገሮችን ሁሉ አያስፈልጉም እያሉ የዘጉቸው ራሳቸው ተሐድሶቹ እንጂ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም፡፡

3) "ሁለተኛው ጥፋት ደግሞ ለአዳዲሶቹ መንገዶች የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር፤ የእርሱነቱ ብቻ መጠሪያ የሆኑ ስሞቹን ለእርሱ ብቻ ሊቀርብ የሚገባውን ምስጋናና አምልኮ በመስጠት የእግዚአብሔርን ቅዱሳን ማክበር ሳይሆን ወደ ማምለክ መሸጋገር ነው" ማለታቸው፤

ይህ ቢያንስ ሁለት መሠረታዊ ስህተቶችን የያዘ ነው፡፡ አንደኛው ቤተ ክርስቲያናችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ሊቀርብ የሚገባውን ምስጋናና አምልኮ ለቅዱሳን አትሰጥም፡፡ ይህ የተለመደ ሐሰትና ተንኰል ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ቅዱሳንን አምላክ ናቸው፤ ይመለኩ ልትል ቀርቶ አስባውም አታውቅም፤ ባሕርይዋ አይፈቅድላትምና፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ቅዱሳንን ማክበርን ማምለክ አድርገው መረዳታቸውና መውሰዳቸው ነው፡፡ ለእግዚአብሔር የሚነገሩ ቃላት ለሰዎችም የሚነገሩበት አግባብ አለ፡፡ ይህንም መጽሐፍ ቅዱስ በሚገባ ያስተምረናል፡፡ ለምሳሌ እግዚአብሔር "ቅዱስ" ይባላል፡፡ እንደዚሁም ሰዎችም "ቅዱስ" ይባላሉ፡፡ ይህን ደግሞ ራሱ እግዚአብሔር እንጂ ሰዎች የፈጠሩት አይደለም፡፡ እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፡- "ለእስራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ እንዲህ በላቸው፦ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ።" ዘሌ. 19፡1-2 ስለዚህ ሰዎችም ቅዱሳን ይሆኑ ዘንድና እንዲህ ተብለው ይጠሩ ዘንድ ጥሪውን ያቀረበው ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡

ሌሎች ምሳሌዎችን ብንጨምር "ብርሃን" የሚለው ቃል ለእግዚአብሔር ተነግሮ እናገኘዋለን፡፡ "ደግሞም ኢየሱስ፦ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ" ብሎ፤ እንዲሁም "እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም" ተብሎ ተግሯል፡፡ ዮሐ. 8፡12 ፤ 1 ዮሐ. 1፡5 ራሱን "ብርሃን" ያለው አምላካችን ደቀ መዛሙርቱን "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ" ብሏቸዋል፡፡ ማቴ. 5፡14 እግዚአብሔር "ጻድቅ" እንደሚባል ሰዎችም "ጻድቅ" ተብለዋል፡፡ እግዚአብሔር "ፍጹም" እንደሚባል ሰዎችም "ፍጹም" ተብለዋል፡፡ ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ ኖኅን "ኖኅም በትውልዱ ጻድቅ ፍጹምም ሰው ነበረ" ብሎ ይገልጸዋል፡፡ ዘፍ. 6፡9 ይህ ማለት ግን ሰዎችና እግዚአብሔር እኩል ቅዱስ፤ እኩል ብርሃን፤ እኩል ጻድቅ . . . ናቸው ማለት እንዳልሆነ ጤነኛ አእምሮ ላለው ሁሉ ግልጽ ነው፡፡ የእግዚአብሔር የባሕርዩ ሲሆን የሰዎች ደግሞ ከእርሱ በጸጋ የተሰጣቸው ነውና፡፡ ይህን በተመለከተ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዲህ ይላል፡-

- "ለእግዚአብሔር እና ለሰዎች ተመሳሳይ አገላለጾችን እንጠቀማለን፤ ሆኖም ግን ለእግዚአብሔር ስንናገር የሚኖረን አረዳድና ለሰዎች ስንናገር የሚኖረን አረዳድ የተለያየ ነው፡፡ ምንም እንኳ ቃሉና አገላለጹ አንድ ዓይነት ቢሆንም ስለ እኛ የሚነገረውን ስለ እግዚአብሔር ከሚነገረው ጋር አንድ ዓይነት አድርገን ልንረዳው አይገባም፤ ስለ እግዚአብሔር ሲነገር ለእርሱ እንደሚገባ አድርገን መረዳት ይገባናል፡ አለበለዚያ ከታላቅ ስህተት ላይ እንደወድቃለን፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ቆሮንቶስ ቀዳማዊ፣ ክፍል ትምህርት 26)

ስለዚህ ተሐድሶዎች የሚያቀርቡት ክስ ሐሰትና ስህተት ነው ማለት ነው፡፡

4) "በቤተ ክርስቲያናችን የአምላክ ክብርና ስፍራ በተለያዩ ልብ ወለድ ድርሰቶች ለፍጡራን ተሰጥቷል" ያሉት፤

ይህም ሐሰት ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን የአምላክ ክብርና ስፍራ ለፍጡራን አልተሰጠም! እንዲህ የሚያደርጉ ድርሰቶች አሉ የሚሉትንና "በተለያዩ ልብ ወለድ ድርሰቶች" እያሉ የሚያነሷቸውን በተመለከተ ለመነጋገር ግን አንድ መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታ አለ፡፡ እርሱ ምንድን ነው? በመጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረውን፣ ከሐዋርያትና ከእነርሱ ቀጥሎ ከነበረው ዘመን አንሥቶ በነበሩት ቅዱሳን አበው ሊቃውንት የተነገረውን መሠረታዊ ትምህርት - ስለ መዳን፣ ስለ ምሥጢረ ጥምቀት፣ ስለ ምሥጢረ ሜሮን፣ ስለ ምሥጢረ ቁርባን፣ ስለ ጾም፣ ስለ ምጽዋት፣ ስለ ተጋድሎ፣ ስለ ክርስቲያናዊ መልካም ሥራ፣ ስለ ቅዱሳን አማላጅነት፣ ... የተነገረውን ትምህርት ይመኑ፣ ይቀበሉ፡፡ በመጀመሪያ ይህን ካደረጉ ከዚያ በኋላ ስለሚሏቸው መጻሕፍትና ስለ ይዘታቸው መነጋገር ይቻላል፡፡ ሆኖም መሠረቱን ካላመኑ ግን ወደ ቀጣዩ መሄድ አይቻልም፡፡ ትልቁና ዋናው ምዕራፍ ሳያልቅ ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ መሸጋገር አይቻልም፡፡ ስለዚህ አሁንም በድጋሚ በአጽንዖት እንዲህ እንላቸዋለን፡- ከሁሉ በፊት በመጽሐፍ ቅዱስና በቀደምት አበው ቅዱሳን ሊቃውንት የተነገረውን እምነትና ትምህርት እመኑ፣ ከዚያ በኋላ ስለምታነሡት ስለ ማንኛውም ጉዳይ መነጋገር ይቻላል፡፡ ከዚህ ውጭ መሠረቱን ትቶ ጫፍ ለጫፍ እሄዳለሁ ማለት ግን ተቀባይነት የለውም፣ አስመሳይነትና የማታለል ሥልት (ስትራቴጂ) ነውና፡፡

ከዚህ በመቀጠል ምልጃ እንዴት እንደ ተጀመረ ወደ ማየት እንሂድ፡፡ ተሐድሶዎች እንደሚያወሩት ምልጃ በሰው ፈቃድ የተጀመረና የተደረገ አይደለም፤ ራሱ እግዚአብሔር ሰዎች እንዲፈጽሙት ያዘዘውና የፈቀደው ነገር እንጂ፡፡ ይህንም ከዚህ ቀጥሎ ከተገለጹት መረዳት ይቻላል፡፡

1. አብርሃም ወደ ጌራራ ተሰዶ ሳለ የሀገሩ ንጉሥ አቤሜሌክ ሚስቱን ሣራን ባለማወቅም ቢሆን ወስዶ ሚስቱ ሊያደርጋት ባለ ጊዜ እግዚአብሔር ሌሊት በሕልም ሣራን እንዲመልስለት ካዘዘው በኋላ "ነቢይ ነውና ስለ አንተ ይጸልያል፣ ትድናለህም" ብሎታል፡፡ ራሱ እግዚአብሔር አቤሜሌክን፡- "አንተ ወደ እኔ በቀጥታ ጸልይ፣ ሚስቱን ግን መልስ" ማለት ሲችል "ነቢይ ነውና ስለ አንተ ይጸልያል" ለምን አለው? አቤሜሌክን ወደ አብርሃም እንዲሄድና እርሱ (አብርሃም) እንዲጸልይለት የነገረው ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ዘፍ. 20፡1-7 "ራሳችን በቀጥታ እንጸልያለን፣ አማላጅ መፈለግ መንገድ ማብዛት ነው" የሚሉ ሰዎች አካሄዳቸው ልብ ወለድና የድፍረት አካሄድ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዳልሆነ ልብ ማለት ይገባል፡፡ እግዚአብሔርን የምናገኘው እርሱ ባሳየን መንገድ እንጂ እኛን በሚመስለንና ሥጋና ደም በሚያሳስበን መንገድ አይደለም፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን "ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች፣ ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው" ያለው እንደዚህ ያሉ እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚያስቡ ሰዎች የሚሄዱበትን መንገድ ነው፡፡ ምሳ. 14፡12

የክርስትና ሕይወትና መንገድ እግዚአብሔር የገለጠው እውነታ በመሆኑ እርሱ እንደ ገለጠልንና እንዳስተማረን የምንመላለስበት መንገድና ሕይወት ነው እንጂ እንዲሁ በሰዎች መላ ምትና ፈቃድ የተፈጠረ የይሆናል መንገድ አይደለም፡፡ ለዚህ ነው የክርስትና ሃይማኖት "የአምላክ መገለጥ ሃይማኖት"[114] የሚባለው፡፡

2. ኢዮብን ሊጠይቁት የመጡትን ሦስቱን ጓደኞቹን "እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅንን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና ቁጣዬ በአንተና በሁለቱ ባልንጀሮችህ ላይ ነድዷል፡፡ ... ባሪያዬ ኢዮብ ስለ እናንተ ይጸልያል፣ እኔም እንደ ስንፍናችሁ እንዳላደርግባችሁ ፊቱን እቀበላለሁ" አላቸው፡፡ ራሱ እግዚአብሔር ተገልጦ እያነጋገራቸው እያለ "ብቀጥታ ወደ እኔ ጸልዩ፣ ይቅር እላችኋለሁ" አላለም፡፡ ተፈትኖ የወጣውና እንደ ወርቅ የነጠረው ወዳጁ ኢዮብ ክብሩ ይገለጥ ዘንድ ስለ እነርሱ እንዲጸልይላቸው ወደ እርሱ እንዲሄዱ አዘዛቸው እንጂ፡፡ በዚሁም መሠረት እንደ ታዘዙት ሲያደርጉ ኢዮብ ስለ እነርሱ ጸለየላቸው፣ እርሱም በኢዮብ ጸሎት ይቅር አላቸው፤ "እግዚአብሔርም የኢዮብን ፊት ተቀበለ" እንዲል፡፡ "የኢዮብን ፊት ተቀበለ" ማለቱ ኢዮብ ስለ ሦስቱ ጓደኞቹ ያቀረበውን ምልጃ ተቀበለ ማለት ነው፡፡ ኢዮብ 42፡7-9

3. ቅዱስ ጳውሎስ አማላጅነት የቅዱሳን ሥራ መሆኑን ሲገልጽ "በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ" ብሏል፡፡ 2 ቆሮ. 5፡19-20 እግዚአብሔር ወዳጆቹ ቅዱሳን ስለ ደካሞች እንዲለምኑት በእነርሱ የማማለድ ጸጋና ቃል አኖረ፡፡ እንዲሁም፦ "በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ" ይላል፡፡ ፊልጵ. 4፡6

ቅዱስ ጳውሎስ የቆሮንቶስ ምእመናንን "እርሱም ይህን ከሚያህል ሞት አዳነን፣ ያድነንማል፤ እናንተም ደግሞ ስለ እኛ እየጸለያችሁ አብራችሁ ስትረዱን፥ በብዙ ሰዎች በኩል ስለ ተሰጠን ስለ ጸጋ ስጦታ ብዙዎች ስለ እኛ ያመሰግኑ ዘንድ፣ ወደ ፊት ደግሞ እንዲያድን በእርሱ ተስፋ አድርገናል።" በማለት እነርሱ ስለ እርሱ እና ስለ ሌሎችም የሚያደርጉት ጸሎት የረዳውና የጠቀመው መሆኑን ገልጿል፡፡ 2 ቆሮ. 1፡11

ስለዚህ ምልጃ ራሱ እግዚአብሔር ያሳየው መንገድ ነው፡፡ አማላጅነት የእግዚአብሔር የቸርነቱ ጸጋ (ስጦታ) ነው፡፡ ምክንያቱም ምግባራቸው የደከመና ጸሎታቸው ገና እንደ እርሱ ፈቃድ ያልሆነ ተነሳሒያን ኃጥአን የእርሱን ፈቃድ በሚያውቁና በሚፈጽሙ በምግባር በትሩፋት በበለጸጉ ጻድቃን ጸሎት እንዲደገፉ ማድረጉ የቸርነቱ መግለጫ ነው፡፡ "በእምነት የደከመውን ተቀበሉት" ተብሏልና፡፡ ሮሜ 14፡1 እንዲሁም "ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም፣ እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ" ተብለናልና፡፡ ገላ. 6፡2 ክርስትና በጸሎት ወደ እግዚአብሔር በመማለድ የበረቱት የደከሙትን እየደገፉ የሚኖሩበት እንጂ እንደዚህ ዓለም ስግብግብነት የሌላውንም ጭምር እየቀሙ የሚኖርበት ሕይወት አይደለምና፡፡ ራሱ እግዚአብሔር "የደከሙትን እጆች አበርቱ፣ የላሉትንም ጉልበቶች አጽኑ" ይላልና፡፡ ኢሳ. 35፡3 እንዲሁም "እኔ ጻድቃንን ሳይሆን ኃጢአተኞችን ልጠራ መጥቻለሁና" ብሏልና፡፡

ስለሆነም ምልጃ የእግዚአብሔርን ፈታሒነት (ፈራጅነት) የሚጋፋ ሳይሆን ቸርነቱን የሚገልጽ ነው፡፡ ከአባታዊ ደግነቱ የተነሣ በጻድቃን ጸሎት ተነሳሒያን ኃጥአን እንዲጠቀሙ አደረገ፡፡ ሐዋርያዊትና ኦርቶዶክሳዊት ቅድስት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳንን አማላጅነት የምታምነውና የምታስተምረው ከአበው ሕይወትና ከቅዱሳት መጻሕፍት ባገኘችው መሠረት ነው፡፡ይህን ራሱ እግዚአብሔር የወደደውንና የፈቀደውን የአማላጅነት ነገር የሚቃወም ቢኖር ክርክሩ ከባለቤቱ ከእግዚአብሔር ጋር እንጂ ከሰው ጋር አለመሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ በነቢይ "ሂድ፣ ይህን ሕዝብ፡ መስማትን ትሰማላችሁ አታስተውሉምም፣ ማየትንም ታያላችሁ አትመለከቱምም በላቸው።

[114] (Revealed Religion)

በዓይናቸው እንዳያዩ፣ በጆሮቻቸውም እንዳይሰሙ፣ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፣ ተመልሰውም እንዳይፈወሱ፡ የዚህን ሕዝብ ልብ አደንድን፣ ጆሮቻቸውንም አደንቊር፣ ዓይናቸውንም ጨፍን አለኝ" ተብሎ የተነገረው እንዳይደርስብን መጠንቀቅና ማስተዋል ይገባል። ኢሳ. 6፥9-10

እስካሁን የተመለከትነው በአጠቃላይ ምልጃ ከእግዚአብሔር ቸርነትና መሐሪነት ጋር የሚስማማ መሆኑን፣ የፍቅር ውጤትና መግለጫ መሆኑን፣ እንዲሁም ራሱ እግዚአብሔር ያዘዘውና ያሳየው መንገድ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የቅዱሳን ምልጃ በዚህ ዓለም ሕይወታቸውና ከዚያ በኋላ ብለን ከፍለን እንመለከታለን፡፡

### 6.3.2.3 <u>የቅዱሳን አማላጅነት በሕይወተ ሥጋ</u>

ቅዱሳን በሕይወተ ሥጋ ሳሉ እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ሲል ምሕረትንና ይቅርታን እንደሚያደርግ በነቢዩ በኢሳይያስ ሲናገር እንዲህ ይላል፡- "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ወይን በዘለላው በተገኘ ጊዜ፡- በረከት በእርሷ ላይ አለና አታጥፏት እንደሚባለው ሁሉን እንዳላጠፋ ስለ ባሪያዎቼ እንዲሁ አደርጋለሁ፡፡" ኢሳ. 65፥8 ስለ ወደጆቹ ሲል እንደሚምር ራሱ እግዚአብሔር እንዲህ ምሳሌውን መስሎና ተርጉሞ አስረድቷል፡፡ ከወይን ዛፍ ላይ ዘለላ ፍሬ በተገኘ ጊዜ ሊቀረጥ የነበረው ዛፍ ስለ ተገኘበት ትንሽ ፍሬ ሲባል ይቆይ ተብሎ ከመቆረጥ እንደሚድን ሁሉ ቅዱሳን ያሉበትን ሕዝብና ሀገርም እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ሲል ከማጥፋት እንደሚታገሥ ራሱ እግዚአብሔር ተናገረ፡፡ ለምሳሌም የሚከተሉትን መመልከት ይቻላል፡፡

1. እግዚአብሔር ለአብርሃም ስለ ሰዶምና ገሞራ ጥፋት በነገረው ጊዜ ይምራቸው ዘንድ ደጋግሞ ለመነ፡፡ "አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር" የሚለው ኃይለ ቃል የሚያስረዳው ለእግዚአብሔር ፊትና ኋላ ኖሮት ሳይሆን አብርሃም የእግዚአብሔርን ገጸ ምሕረት እየለመነ የነበረ መሆኑን ነው፡፡ ዘፍ. 18፥22 አብርሃም እግዚአብሔርን ሲለምነው "በእኔ ፍርድ ውስጥ ምን አገባህ?" አላለውም፡፡ ይልቁንም ልመናውን ተቀብሎታል፡፡ "ሃምሳ ጻድቃን በከተማይቱ ውስጥ ቢገኙ በውኑ ሁሉን ታጠፋለህን? ከተማይቱንስ በርሷ ስለሚገኙ አምሳ ጻድቃን አትምርምን?" ብሎ በለመነው ጊዜ "እግዚአብሔርም በሰዶም በከተማይቱ ውስጥ አምሳ ጻድቃን ባገኝ ስፍራውን ሁሉ ስለ እነርሱ እምራለሁ" ብሎታል፡፡ ሆኖም ግን በሰዶምና ገሞራ አምሳ ቀርቶ አሥር ጻድቃን እንኳ ስላልተገኙ ሀገሪቱ በእሳት ተቃጥላ ጠፍታለች፡፡

ለሰዶምና ለገሞራ ጥፋት ምክንያቱ የራሳቸው የሰዎቹ ኃጢአት ቢሆንም በከተማይቱ አሥር ጻድቃን ቢገኙ ኖሮ እግዚአብሔር ስለ እነዚያ አሥር ጻድቃን ሲል ይምራቸው እንደ ነበር ራሱ በማይታበል ቃሉ <u>"ስለ አሥሩ አላጠፋትም"</u> ብሏል፡፡ ነገር ግን እነዚያ አሥር ጻድቃን ባለመገኘታቸው ከተማይቱ ጠፍታለች፡፡ በአብርሃም ጸሎትና በአሥር ጻድቃን መኖር በሰዶም የነበሩ ኃጥአን ሊማሩ ይችሉ ከነበረ እግዚአብሔር ስለ ጻድቃን ሲል ኃጥአንን እንደሚምር በግልጽ ታወቀ፣ ተረዳ፡፡ ደጋግ አበው በኃጢአት ስለሚኖሩ ደካሞች የሚያቀርቡት የምልጃ ጸሎትም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሆኑን ይኸው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በግልጥ የሚመሰክረው እውነት ነው፡፡ በዘመነ ፍዳ በዓመተ ኩነኔ የነበሩትና የኃጢአታቸው ጥልቀትና ስፋት እጅግ ከባድ የነበሩት ሰዶምና ገሞራ እንኳ በአብርሃም ምልጃ የሚድኑ ከሆነ በዘመነ ወንጌል በዓመተ ምሕረት ያሉ ተነሣሒያን በቅዱሳን ምልጃ መዳናቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

2. ሙሴ ከደብረ ሲና አሠርቱ ቃላት የተጻፈበትን ጽላት ይዞ ሲወርድ እስራኤላውያን አምልኮ ጣዖት ጀምረው ስለ ነበር እግዚአብሔር ተቆጥቶ "ቁጣዬ እንዲቃጠልባቸው እንዳጠፋቸውም ተወኝ፤ አንተንም ለታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ" አለው፡፡ ሙሴም "በእግዚአብሔር በአምላኩ ፊት ጸለየ፤ አለም፦ . . . ከመዓትህ ተመለስ፤ ለሕዝብህም በክፋታቸው ላይ ራራ፡፡" በዚህ ጊዜ ተቆጥቶ ሊያጠፋቸው የነበረ የሙሴን ምልጃ ተቀብሎ "እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፋት ራራ" ይላል፡፡ ዘጸ. 32፥10-14

ይህን ሙሴ በኦሪት ዘዳግም እንዲህ ገልጾታል፦ "ስለ ሠራችሁት ኃጢአት ሁሉ፣ እርሱንም ለማስቆጣት በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን ነገር ስላደረጋችሁ እግዚአብሔር ሊያጠፋችሁ ከተቆጣችሁ ከቁጣውና ከመዓቱ የተነሣ ስለ ፈራሁ፤ እንደ ፊተኛው በእግዚአብሔር ፊት አርባ ቀንና ሌሊት ወደቅሁ፤ እንጀራም አልበላሁም ውኃም አልጠጣሁም፡፡ <u>እግዚአብሔርም በዚያን ጊዜ ደግሞ ሰማኝ</u>፡፡" ዘዳ. 9፥18-19 ዳዊትም በመዝሙሩ "እንዳያጠፋቸው ቁጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠው ሙሴ በመቅሠፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ" ብሏል፡፡ "በፊቱ ባይቆም ኖሮ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ" ማለቱ ሙሴ በአማላጅነት በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ስለ እነርሱ እግዚአብሔርን ባይለምንላቸው ኖሮ ያጠፋቸው ነበር ማለቱ ነው፡፡ መዝ. 105፥23

3. አቤሜሌክ ንጉሠ ጌራራ የአብርሃምን ሚስት ሣራን ሊወስድ ባለ ጊዜ እግዚአብሔር በሕልሙ ሣራን እንዲመልስና ስለ ኃጢአቱም አብርሃም እንዲጸልይለት "ነቢይ ነውና ስለ አንተ ይጸልያል፤ ትድናለህም" ሲል ነግሮታል፡፡ ዘፍ. 20፥7 በአብርሃም ጸሎት አቤሜሌክ ዳነ፡፡ ምልጃ ይህ ነው፦ በነቢያት፣ በሐዋርያት፣ በጻድቃንና በሰማዕታት ጸሎት እንደ አቤሜሌክ ያሉ ምግባረ ደካሞች፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ሊቆጣቸው በኃጢአታቸው ደንግጠው የእግዚአብሔርን ገጸ ምሕረት የሚናፍቁ ሰዎች በቅዱሳን ጸሎት የሚረዱበትና የሚጠቀሙበት ነው፡፡

4. ኢዮርብዓም የተባለ የእስራኤል ንጉሥ ጣዖት በማምለኩ ምክንያት ይገሥጸውና ይመክረው ዘንድ እግዚአብሔር ወደ እርሱ የላከውን ነቢይ ለመያዝ በትዕቢት የዘረጋው እጁ ስለ ደረቀ ጨነቀውና መልሶ ያንኑ የእግዚአብሔር ነቢይ "አሁን የአምላክህን የእግዚአብሔርን ፊት ለምን፤ እጄም ወደ እኔ ትመለስ ዘንድ ስለ እኔ ጸልይ" አለው፡፡ ያም ነቢይ "እግዚአብሔርን ለመነ፤ የንጉሡም እጅ ወደ እርሱ ተመለሰች፣ እንደ ቀድሞም ሆነች፡፡" በነቢየ እግዚአብሔር ጸሎት ደርቆ የነበረው የንጉሡ እጅ ዳነ፡፡ 1 ነገ. 13፥1-10

5. እስራኤላውያን በኃጢአታቸው ምክንያት መከራ በከበባቸው ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በአንድነት ቀርበው ነቢዩ ኤርምያስን እንዲህ አሉት፦ "ዓይኖችህ እንዳዩን ከብዙ ጥቂት ቀርተናልና ልመናችን እባክህ በፊትህ ትድረስ፤ አምላክህም እግዚአብሔር የምንሄድበትን መንገድና የምናደርገውን ነገር ያሳየን ዘንድ ስለ እኛ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ፡፡" ነቢዩ ኤርምያስም "እኔ እንደ ቃላችሁ ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ" አላቸው፡፡ ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ነቢዩ ኤርምያስ ስለ ሕዝቡ የጸለየውን ጸሎት ሰምቶ በእርሱ አማካይነት ለሕዝቡ እንዲህ የሚል የሚያጽናና የምሕረት መልእክት ላከ፦ "ስላደረግሁባችሁ ክፉ ነገር ተጸጽቻለሁና በዚህች ምድር ብትቀመጡ እሠራችኋለሁ እንጂ አላፈርሳችሁም፣ እተክላችኋላሁ እንጂ አልነቅላችሁም፡፡ ከምትፈሩት ከባቢሎን ንጉሥ አትፍሩ፣ አድናችሁም ዘንድ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝና አትፍሩ ይላል እግዚአብሔር" ኤር. 42፥2-3፤9-11

ከተሐድሶዎች ብዙዎቹ ምልጃን የሚቃወሙና የማይቀበሉ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ጨርሶ መካዱ እንደማያዋጣ ሲረዱት ያመኑና የተቀበሉ መስለው ነገር ግን ለማድበስበስና ለማታለል ይሞክራሉ፡፡ ለምሳሌም እንዲህ ያሉትን መመልከት እንችላለን፦

- "ስለዚህ ምልጃ ሲነሳ ቅዱሳን ሰዎች የቀመሱትን የእግዚአብሔር ፍቅር ለሌሎች ማድረስን በዚያም እንዲኖሩ ስለ ሌሎች መለመንን የሚያሳይ ነው፡፡ ቅዱሳን ሰዎች ስለ ወንድሞቻቸው /ስለ ወገኖቻቸው/ይጸልያሉ ይማልዳሉ ሲባል ከጊዜያዊ የሥጋ ቅስፈት ለመታደግ የሚያቀርቡት ልመና ማለት ነው፡፡" (መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ ገጽ 34)

እነዚህ አባባሎች ምርቅና ፍትፍት ናቸው፡፡ ምክንያቱም "ስለዚህ ምልጃ ሲነሳ ቅዱሳን ሰዎች የቀመሱትን የእግዚአብሔር ፍቅር ለሌሎች ማድረስን በዚያም እንዲኖሩ ስለ ሌሎች መለመንን የሚያሳይ ነው" የሚለው እውነታ ያለው ቢሆንም "የእግዚአብሔር ፍቅር" የሚለው ያካትተዋል ካልተባለ በስተቀር የቅዱሳን ምልጃ የሚያስገኘው ጥቅም በዚህና በዚያ ተብሎ ገደብ የሚበጅለት አይደለም፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ያሉት "ቅዱሳን ሰዎች ስለ ወንድሞቻቸው /ስለ ወገኖቻቸው/ይጸልያሉ ይማልዳሉ ሲባል <u>ከጊዜያዊ የሥጋ ቅስፈት ለመታደግ የሚያቀርቡት ልመና ማለት ነው</u>" የሚለው ግን ትክክል አይደለም፡፡ ምክንያቱም የቅዱሳን የምልጃ ጸሎት የሚያሰጠው ነገር ከጊዜያዊ ቅስፈት በመታደግ ብቻ የተወሰነና የተገደበ አይደለምና ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ያለ ገደብ አላስቀመጠም፡፡

ስለዚህ ይህ አባባላቸው ሰው ሠራሽ አሳብና እውነቱን ሙሉ በሙሉ በመካድ ሳይሆን ተመሳስሎ ገብቶ ለማሳሳት የተደረገ ጥረት ነው፡፡ በቅዱሳን ጸሎት የሚገኘው ጥቅም በዚህ ዓለም ከጊዜያዊ የሥጋ መቅሠፍት እንደሚታደግ ከታመነ ከነፍስ መቅሠፍት አይታደግም ለማለት የሚያስችል ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለም፡፡ እግዚአብሔር በቅዱሳን ምልጃ ከሥጋ ቅሥፈት የሚታደግ ከሆነ የበለጠ ከሆነው ከነፍስ መቅሥፈትስ ለምን አይታደግም? የእግዚአብሔር ጸጋስ በሰዎች ሊገደብ ይችላልን?

በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፈው የምናገኛቸው አንዱ ስለ ሌላው በሚያደርገው የምልጃ ጸሎት ከእግዚአብሔር የተሰጡ ነገሮች ከሥጋ መቅሠፍት መዳንን ብቻ አይደለም፤ ታላቅ ጸጋ የሆነውን ሥርየተ ኃጢአትንም ነው እንጂ፡፡ ከእነዚህም ጥቂቶቹን ብቻ እንመልከት፡-

> እነሆም አንድ ሽባ በአልጋ ተሸክመው አመጡ፤ አግብተውም በፊቱ ሊያኖሩት ይሹ ነበር። ስለ ሕዝቡም ብዛት እንዴት አድርገው እንዲያገቡት ሲያቅታቸው ወደ ሰገነቱ ወጡ፤ የጣራውንም ጡብ አሳልፈው በመካከል በኢየሱስ ፊት ከአነ አልጋው አወረዱት። እምነታቸውንም አይቶ፡- <u>አንተ ሰው፤ ኃጢአትህ ተሠረየችልህ</u> አለው። ጻፎችና ፈሪሳውያንም፡- ይህ የሚሳደብ ማን ነው? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአት ሊያስተሠርይ ማን ይችላል? ብለው ያስቡ ጀመር። ኢየሱስም አሳባቸውን እያወቀ መልሶ፡- በልባችሁ ምን ታስባላችሁ? ኃጢአትህ ተሰረየችልህ ከማለት ወይስ ተነሣና ሂድ ከማለት ማናቸው ይቀላል? ነገር ግን በምድር ላይ ኃጢአት ሊያስተሰርይ ለሰው ልጅ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ ብሎ ሽባውን፡- አንተን እልሃለሁ፥ ተነሣ፤ አልጋህን ተሸክመህ ወደ ቤትህ ሂድ አለው። ሉቃ. 5፥18-24

የኃጢአት ሥርየት የሥጋ ምሕረት ነው ወይስ የነፍስ? ከእግዚአብሔር የሚለየው ታላቁ ነገር ኃጢአት ነው፡፡ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፡- "እነሆ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም፤ ጆሮውም ከመስማት አልደነቈረችም፡፡ ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፥ እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል፡፡" ኢሳ. 59፥1-2 ስለዚህ ይህ ታላቁ ነገር - ኃጢአትን ይቅር መባል - በሥጋ መቅሠፍት ወሰን የሚገደብ ሳይሆን የሰውን ሁለንተናዊ ምሕረት የሚገልጽ ነው፡፡ ያ በሽተኛ ይህን ታላቅ ጸጋ - ሥርየተ ኃጢአትን - ያገኘው በራሱ ወደ ጌታችን ሂዶ፤ ይቅር በለኝ ብሎ ለምኖ አልነበረም፡፡ ቅዱስ ወንጌል እንደሚነግረን ወደ ጌታችን የወሰዱት ሌሎች ሰዎች ነበሩ፡፡ የእነዚያ ሰዎች እምነትና ለዚያ በሽተኛ መዳን ያደረጉት አስተዋጽኦ እንዲታወቅ ነበር መድኃኒታችን "እምነታቸውንም አይቶ፡- አንተ ሰው፥ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ" ያለው፡፡

ስለሆነም በአንዱ አድራጎት ሌላው ሊያገኘው የሚችለው ነገር ከሥጋ መቅሠፍት በመዳን ብቻ የሚገደብ ሳይሆን የኃጢአትን ይቅርታ እስከ ማግኘት የሚደርስ ሁለንተናዊ ነው፡፡ ለዚህ ነበር ጌታችን ያ በሽተኛ ሥጋውን ከመፈወሱ በፊት የነፍሱን በሽታ - ኃጢአቱን - ይቅር ያለው፡፡

በመቀጠልም "እሊ.ጋህን ተሸክመህ ሂድ" በማለት ሥጋውንም የፈወሰው መሆኑን አሳየ፡፡ ስለዚህ በቅዱሳን ጸሎት የሚገኘው ጥቅም ከሥጋ ቅሥፈት ለመታደግ ብቻ ነው የሚለው አባባል ፈጽሞ የተሳሳተ ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ በሐዋርያዊ አገልግሎቱ ስለ ገጠሙት ነገሮች ከተናገራቸው አንዱ ሄኔሲፎሩ የተባለው ሰው ስላደረገለት መልካም ነገር ሲሆን ለእርሱም እንዲህ ሲል ጸልዮለታል፡-

> ጌታ ለሄኔሲፎሩ ቤተ ሰዎች ምሕረትን ይስጥ፣ ብዙ ጊዜ አሳርፎኛልና፤ በሰንሰለቴም አላፈረበትም፣ ነገር ግን በሮሜ ባደረ ጊዜ ፈልጎ ፈልጎ አገኘኝ፤ _በዚያን ቀን ከጌታ ምሕረትን እንዲያገኝ ጌታ ይስጠው፤_ በኤፌሶንም እንዴት እንዳገለገለኝ አንተ በደንና ታውቃለህ። 2 ጢሞ. 1፥16-18

ቅዱስ ጳውሎስ በአገልግሎቱ ለረዳው ለሄኔሲፎሩ የለመነለት ከሥጋዊ መቅሠፍት እንዲድን አይደለም፤ "በዚያን ቀን ከጌታ ምሕረትን እንዲያገኝ ጌታ ይስጠው" አለ እንጂ፡፡ ይህ ምን ማለት ነው? ከሥጋዊ መቅሠፍት ብቻ ታደገው ማለት ነውን? አይደለም፡፡ "በዚያን ቀን" የተባለው የቱ ቀን ነው? "በዚያም ቀን" ተብሎ የተገለጸው ጌታችን ለፍርድ የሚመጣበት ዕለተ ዳግም ምጽአት ነው፡፡ ለምሳሌም ቅዱስ ጴጥሮስ "የጌታው ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል፤ _በዚያም ቀን_ ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፤ . . ." በማለት ጌታ የሚመጣባትን ቀን "በዚያም ቀን" በማለት ገልጾታል፡፡ 2 ጴጥ. 3፥10 "በዚያን ቀን ጌታ ምሕረት ይስጠው" በማለት በአስፈሪው የፍርድ ቀን እግዚአብሔር ያን አገልግሎቱን አስቦ ምሕረት እንዲሰጠው የምልጃ ጸሎት አቀረበለት፡፡ ስለዚህ የቅዱሳን የምልጃ ጸሎት የሚያስገኘው ጥቅም በሥጋ የተወሰነና የተገደበ አይደለምና እንዲህ የሚለው የተሐድሶዎች ነገር ስህተት ነው፡፡

ይህን በተመለከተ አንድ ነገር ብቻ እንጨምር፡፡ ጌታችን በደብረ ዘይት ባስተማረው ትምህርቱ ላይ ስለሚሆነው ከባድና ተከታታይ መከራ ሲናገር ". . . በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያልሆነ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናልና። _እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር፤_ _ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለ ተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ_" አለ፡፡ ማቴ. 24፥21-22 እነዚያ የመከራ ቀኖች ስለ ተመረጡት ሰዎች ሲሉ ማጠራቸው የሥጋ ነው ወይስ የነፍስ ጥቅም? እነዚያ አስጨናቂ ቀኖች ማጠራቸው የሥቃዩ ጊዜ እንዲያጥር፣ እንዲሁም ከሐሳውያንና ከአላውያን ብዛትና ተንኮል የተነሣ መከራውንም በመሰቀቅ ከእግዚአብሔር እንዳይወጡና ወደ ክህደት እንዳይወድቁ ይረዳቸዋል፡፡ ይህ ከሥጋ መቅሠፍት መዳን ብቻ ተብሎ የሚገደብ ሳይሆን ሁለንተናዊ የሥጋና የነፍስ ጥቅም ነው፡፡

ሰው የነፍስና የሥጋ ውሕድ እንደ መሆኑ አንዱን ሰው በሕይወቱ የሚሆነውን ነገር ከፋፍሎ ይህ የሥጋ ነው፤ ይህ የነፍስ ነው ማለት ከግኖስቲኮችና ከልዮናውያን የመጣ የምንታዌ አስተምህሮ ነው፡፡ ሰው አንድ እንደ መሆኑ ያለው ሕይወት አንድ ነው፤ እርሱም ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ሕይወት ነው፡፡ በዚህ ሕይወቱ መልካም ነገር ሲሆንለት ለሰውዬው መልካም ይሆንለታል፤ ክፉ ሲሆንበት ደግሞ ክፉ ይሆንበታል እንጂ ይህ የሥጋው ይህ የነፍሱ እያሉ እንደ ሁለት ሰዎች ለማከፋፈል መሞከር (ምንታዌ) ቦታ የለውም፡፡

◉ "ቅዱሳን አንድን ሰው ኃጢአተኛ ይሆን አይሆን ሊያውቁት አይችሉም፡፡ ኃጢአተኛ መሆን አለመሆኑን ሳያውቁ ደግሞ ሊጸልዩለት አይችሉም፡፡" (መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ ገጽ 40)

እስኪ በመጀመሪያ ኃጢአት የሌለበት ሰው አለ ወይ? ቅዱስ መጽሐፍ "ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም" ይላልና። 1 ዮሐ. 1፥8 ታዲያ እንዲህ ከሆነ "ቅዱሳን አንድን ሰው ኃጢአተኛ ይሆን አይሆን ሊያውቁት አይችሉም" የሚለው አባባል ምን መሠረት አለው? እንዲሁም "ኃጢአተኛ መሆን አለመሆኑን ሳያውቁ ደግሞ ሊጸልዩለት አይችሉም"

የሚለውም ፍሬ ቢስ አባባል ነው፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያ ሰው መጠኑና ዓይነቱ ይለያይ እንጂ በሥጋ እስካለ ድረስ ከኃጢአት ብናኝ ሙሉ በሙሉ ነጻ አይሆንምና ነው፡፡ እንዲሁም ደግሞ ጸሎት የግድ ኃጢአተኛ ከመሆን አለመሆን ጋር ብቻ የተያያዘ አይደለም፡፡

ተሐድሶዎቹን እንዲህ የሚያሰኛቸው ከላይ በክፍል አንድ እንደ ተገለጸው መዳንን ከኃጢአት ከሚመጣ ቅጣት ማምለጥ እንደሆነ ብቻ አድርገው የሚረዱና ከዚያ ውጭ ስላለው እስከ ሱታፌ አምላካዊነት ድረስ ያለውን የእግዚአብሔር ጸጋ ከማያውቁት ከፕሮቴስታንቶቹ ሳይገባቸው የቀዱት አስተሳሰብ ስለሆነ ነው፡፡ ጸሎት የምንጸልየው ግን ከቅጣት ከማምለጥ አንጻር ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ብዙ ምክንያቶች አሉ፡፡ አንድ የሰውነት ክፍል ስለ ሌላው አካል የሚያስበው የግድ ሲታመምና ችግር ሲኖርበት ብቻ አይደለም፡፡ የአንድ ሰውነት አካል በመሆናቸው ብቻ ሕዋሳትና አካላት እርስ በርስ ይተሳሰባሉ፡፡ እንደዚሁም በክርስቶስ ራስነት የአንዲቷ ቤተ ክርስቲያን አካላት የሆኑ ሁሉ እርስ በርስ መተሳሰቡ ተፈጥሯዊ ነው፤ የግድ ኃጢአተኛ ከመሆን ካለመሆን ጋር ብቻ የተጣበቀ አይደለም፡፡

ከዚህም ጋር ቅዱሳን አንድን ሰው ኃጢአተኛ መሆን አለመሆኑን አያውቁም የሚለው አባባል በራሱ ትክክል አይደለም፡፡ ከላይ በ6.2.3 እንደ ተገለጸው እግዚአብሔር በሚሰጣቸው ጸጋ በሰዎች ውስጥ ያለውን እስከ ማወቅ ድረስ ይችላሉ፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ሐናንያና ሰጲራ ኃጢአት አላወቀምን? ኤልሳዕ የግያዝን ኃጢአት አላወቀምን? ቅዱስ ጳውሎስ የበርያሱስን ኃጢአት አላወቀምን? "ጳውሎስ የተባለው ሳውል ግን መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ ትኵር ብሎ ሲመለከተው፡- አንተ ተንኰል ሁሉ ክፋትም ሁሉ የሞላብህ፣ የዲያብሎስ ልጅ፣ የጽድቅም ሁሉ ጠላት፣ የቀናውን የጌታን መንገድ ከማጣመም አታርፍምን? አሁንም እነሆ የጌታ እጅ በአንተ ላይ ናት፣ ዕውርም ትሆናለህ፣ እስከ ጊዜውም ፀሐይን አታይም አለው። ያን ጊዜም ጭጋግና ጨለማ ወደቀበት፣ በእጁም የሚመራውን እየዞረ ፈለገ።" የሐዋ. 13፥9-11 እነዚህ ያወቁት እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው ነው ካላችሁ እኛም በባሕርያቸው ያውቃሉ አላልንም፣ እግዚአብሔር በሚሰጣቸው እውቀት ግን ያውቃሉ ነው እኛም የምንለው፡፡

በመቀጠል እንዲህ አሉ፡-

- "እስራኤላውያን ወደ ነቢዩ የሄዱት የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት መልካም እንዲሆንልን ወደ አምላክህ ጸልይልን አሉት እንጂ ስለ አንተ ሲል ምሕረት እንዲያደርግልን እባክህ አማልደን አስታርቀን አላሉትም፡፡ እርሱም ቢሆን ስለ እኔ ምሕረት ይደረግላችኋል፣ ተማልጄ አማልዳችኋለሁ አላለም፣ የእግዚአብሔርን ሀሳብ እነግራችኋለሁ አለ እንጂ፡፡" (መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ ገጽ 41)

ይሄ ማምታታት ወይም መደባለቅ ይባላል፡፡ ይህ እስራኤላውያን ነቢዩ ኤርምያስን የለመኑትን ልመና የተመለከተ ነው፡፡ "እስራኤላውያን ወደ ነቢዩ የሄዱት የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት መልካም እንዲሆንልን ወደ አምላክህ ጸልይልን አሉት እንጂ ስለ አንተ ሲል ምሕረት እንዲያደርግልን እባክህ አማልደን አስታርቀን አላሉትም" ማለታቸው ድሮውንስ መጸለዩ ለምን ኖረል? የጸሎት ፋይዳውስ ምንድን ነው? የእርሱ ጸሎት ለእነርሱ እንደሚጠቅማቸው ካመኑ "ስለ አንተ ሲል ምሕረት እንዲያደርግልን እባክህ አማልደን አስታርቀን አላሉትም" የሚሉት የቃላት ጨዋታ ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም ወደ ነቢዩ ወደ ኤርምያስ ሄደው ጸልይልን ያሉት ጥቅም ስለሚያገኙ ነበር እንጂ በከንቱ አልነበረም፡፡ እንዲያ ባይሆን ኖሮ "ራሳችን እንጸልያለን እንጂ ለምን ወደ ነቢዩ ኤርምያስ እንሄዳለን" ባሉ ነበር፡፡ እንደ ተሐድሶዎቹ "እኛው ራሳችን በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር እንጸልያለን እንጂ በዙሪያ መንገድ አንሄድም" አላሉም፡፡ ወደ ነቢዩ ሄደው እንዲጸልይላቸው ለመኑት እንጂ፡፡ ከእነርሱ ይልቅ ነቢዩ ኤርምያስ ቢጸልይላቸውና እግዚአብሔርን ቢጠይቅላቸው የበለጠ እንደሚጠቅማቸው ስለ ተረዱ ነበር ወደ እርሱ ሄደው ልመናቸውን የነገሩት፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊው መንገድ እንዲህ ያለ የትሕትና መንገድ ነውና፡፡

እንዲሁም "እርሱም ቢሆን ስለ እኔ ምሕረት ይደረግላችኋል፣ ተማልጆ አማልዳችኋለሁ አላለም" ያሉት ከጥንቱም የእግዚአብሔር ሰዎች እንዲህ ያለ የትዕቢት ሃሳብና ዕብሪት የለባቸውም፡፡ የራሳቸውን ኃጢአት እያሰቡ እግዚአብሔርን ማራቸው፣ ይቅር በላቸው እያሉ ይማጸናሉ እንጂ ትዕቢታዊ በሆነ ሁኔታ "ስለ እኔ ምሕረት ያደርግላችኋል" አይሉም፡፡ ይህ ዓይነት አባባል በሌለ ነገር መመዘን ነው፡፡ ሐዋርያው "ያለ አሳብ መሮጥ፣ ነፋስን መጎሰም" ብሎ የገለጸው ዓይነት ነገር ነው፡፡ 1 ቆሮ. 9፥26 ሌሎች "ጸልዩልን፣ አማልዱን" ይሏቸዋል እንጂ እነርሱ ራሳቸው "ወደ እኔ ኑ፣ እኔ እማልድላችኋለሁ" አይሉም፡፡ ይህን የሚሉት ፕሮቴስታንታዊ ክፉ መንፈስ ያደረባቸው ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡ እንዲህ ያሉት ሰዎች ቅዱሳንን አያማልዱም እያሉ ራሳቸው ግን "ኑ እንጸልይላችሁ" ይላሉ፡፡ ቅዱሳን ግን "እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር" የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል ያውቃሉና እንደዚህ አይሉም፡፡ ፊል. 2፥3

እግዚአብሔር ስለ እገሌ ብሎ ምሕረት የሚያደርግ መሆኑ በቅዱስ መጽሐፍ የተነገረ ነገር ነው እንጂ የሌለ ነገር አይደለም፡፡ ለአብነትም ከላይ የተገለጸው "ወይን በዘለላው በተገኘች ጊዜ በረከት በእርስዋ ላይ አለና አታጥፉት እንደሚባለው፣ ሁሉን እንዳላጠፉ <u>*ስለ ባሪያዎቼ* እንዲሁ</u> *አደርጋለሁ"* ብሏል፡፡ ኢሳ. 65፥8 በሰዶምና በገሞራም "<u>ስለ አሥሩ አላጠፋትም</u>" ብሏል፡፡ ዘፍ. 18፥ 32 በእነ ኤርምያስ ነቢይ ዘመን በኢየሩሳሌም አንድ ደግ ሰው ቢገኝ ስለ እርሱ ሲል ይቅር ይላት ዘንድ እንዳለው ሲናገር "በኢየሩሳሌም መንገድ እየተመላለሳችሁ ሩጡ፣ ተመልከቱም፣ እወቁም፣ በአደባባይዋም ፈልጉ፣ <u>ፍርድን የሚያደርገውን እውነትንም የሚሻውን ሰው ታገኙ እንደ ሆነ ይቅር እላታለሁ</u>" አለ፡፡ ኤር. 5፥1 እንዲሁም ጌታችን በቅዱስ ወንጌል ስለ ተናገረው በመጨረሻው ጊዜ ስለሚሆነው አስጨናቂ ነገር ሲናገር "እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር፤ ነገር ግን እነዚያ ቀኖች <u>*ስለ ተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ*</u>" ብሏል፡፡ ማቴ. 1፥22 ስለዚህ እግዚአብሔር ስለ ደጋግ ሰዎች ሲል ምሕረትን እንደሚያደርግ እንዲህ ተደጋግሞ የተነገረ ነው፡፡

በዚህም ላይ እግዚአብሔር በነቢዩ በኤርምያስ ጸሎት ለሕዝቡ የሚጠቅማቸውን ነገር የሚነግራቸው መሆኑን ካመኑ የቅዱሳን ምልጃ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳለውና ለሚጠቀሙበት ሰዎች እንዲህ ያለ ጥቅም ያለው መሆኑን ተቀብለዋል ማለት ነው፡፡ ይህ ያስመሰግናቸዋል እንጂ አያስነቅፋቸውም፡፡ ይህን ካመኑ "ወደ አምላክህ ጸልይልን አሉት እንጂ ስለ አንተ ሲል ምሕረት እንዲያደርግልን እባክህ አማልደን አስታርቀን አላሉትም፤ እርሱም ቢሆን ስለ እኔ ምሕረት ይደረግላችኋል፣ ተማልጄ አማልዳችኋለሁ አላለም፣ የእግዚአብሔርን ሀሳብ እነግራችኋለሁ አለ እንጂ" ማለታቸው ቅዱሳን ምን ጊዜም የሚነግሩን የእግዚአብሔርን ቃል እንድንሰማና መልካም እንዲሆንልን ነው እንጂ ከዚህ በተቃራኒ አይደለም፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ያለችው "የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ" ነው፡፡

በመቀጠል ግን "ስለ አንተ ሲል ምሕረት እንዲያደርግልን እባክህ አማልደን አስታርቀን አላሉትም" ያሉት በዚህ በኤርምያስና በእስራኤላውያን መካከል እንዲህ አልተባለም ማለት በሌሎች ቅዱሳንና ምልጃቸውን በሚጠይቁት ሰዎች መካከል ሊባል አይችልም ከሚል መደምደሚያ አያደርስም፡፡ ይህ በችኮላ መደምደም (Hasty generalization) የሚባለው ዓይነት ስህተት ነው፡፡ በቅዱስ መጽሐፍ "በእንተ አብርሃም ፍቁርከ ወበእንተ ይስሐቅ ቁልኤከ ወበእንተ እስራኤል ቅዱስከ - ስለ ወዳጅህ ስለ አብርሃምና ስለ ወዳጅህ ስለ ይስሐቅ፣ ስለ ቅዱስህ ስለ እስራኤልም ብለህ . . . ይቅር በለን" ብለው የጸለዩት አሉ፡፡ ለመጥቀሱስ ይህንኑ ቃል በቀጣዩ ገጽ ላይ ጠቅሰውት ነበር፤ ግን እምነትና ማስተዋል የሌለበት አካሄድ ምን ዋጋ አለው? እንዲህ ሲልባቸው ጊዜ መልሰው "እነዚህ የተጠሩት ሰዎችስ እንኳን ሊለምንባቸው የሚለመንላቸው እንደ ሆኑ የጀርባ ታሪካቸውን ማየቱ በቂ ነው" ብለው መልሰው አፈረሱት፡፡ (መቅደስ የገቡ መናፍቃን፣ ገጽ 42)

## 6.3.2.4 የቅዱሳን አማላጅነት በዓጸደ ነፍስ

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሞት እጅግ በጣም ይፈራ ነበር፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "በሕይወታቸው ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ" ብሎ እንደ ገለጸው ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ወዲህ ግን የሞት አስፈሪነት ቀርቷል፡፡ ዕብ. 2፥14-16 እንዲያውም እነ ቅዱስ ጳውሎስ "ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? ሲዖል ሆይ ድል መንሳትህ የት አለ?" እያሉ ሲንቁትና ሲያቃልሉት እናያለን፡፡ 1 ቆሮ. 15፡55

ቅዱሳን በዚህ ዓለም የተሰጣቸው የማማለድ ጸጋና ሥልጣን ከዕረፍታቸው በኋላ በዓጸደ ነፍስ አይነሳቸውም፡፡ የሚከተሉት ኃይለ ቃሎችና ጥቅሶች ይህንኑ ያረጋግጣሉ፡፡

1. ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በሁለተኛ መልእክቱ በምዕራፍ አንድ ላይ ለክርስቲያኖች ከወጣኒነት እስከ ፍጹምነት ድረስ በእግዚአብሔር ዘንድ ተዘጋጅቶ ያለውን ክብር ዘርዝሮ ካስረዳ በኋላ እንዲህ አለ፡-

> ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ምንም ብታውቁ በእናንተ ዘንድ ባለ እውነት ምንም ብትጸኑ ስለ እነዚህ ዘወትር እንዳሳስባችሁ ቸል አልልም፡፡ ሁል ጊዜም በዚህ ማደሪያዬ ሳለሁ በማሳሰቤ ላነቃችሁ የሚገባኝ ይመስለኛል፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመለከተኝ ከዚህ ማደሪያዬ መለየቴ ፈጥኖ እንዲሆን አውቃለሁና፡፡ ከመውጣቴም በኋላ እነዚህን ነገሮች እንድታስቡ በየጊዜው ትችሉ ዘንድ እተጋለሁ፡፡ 2 ጴጥ. 1፥13-15

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ጴጥሮስ በምን ዓይነት ሞት እንደሚሞት ሲያመለክተው "ጴጥሮስ፣ - አንተ ጎልማሳ ሳለህ ወገብህን በገዛ ራስህ ታጥቀህ ትሄድ ነበር፤ ነገር ግን በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ፤ ሌላውም ያስታጥቅሃል፣ ወደማትወደውም ይወስድሃል አለው፡፡ በምን ዓይነት ሞት እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዳለው ሲያመለክት ይህን አለ" ይላል፡፡ ዮሐ. 21፥18-19 አሁን ቅዱስ ጴጥሮስ ያ ጌታ ያመለከተው፣ ከዚህ ማደሪያው ማለትም በሥጋ በዚህ ዓለም ከመኖር የሚለይበት ጊዜ እንደ ደረሰ ማወቁን ከገለጸ በኋላ "ከመውጣቴም በኋላ እነዚህን ነገሮች እንድታስቡ በየጊዜው ትችሉ ዘንድ እተጋለሁ" በማለት በሞት መለየቱ በዚህ ምድር ያሉ ምእመናን ልጆቹ ለጸጋና ለክብር እንዲበቁ ለማሳሰብ ከመትጋት እንደማይከለክለው አስረዳ፡፡

ምንም እንኳ ቅዱሳን ከዕረፍታቸው በኋላ በዚህ ዓለም ያደርጉት እንደ ነበረው ዓይነት ድካምና ተጋድሎ ያለበት ጾምና ጸሎት፣ ስግደት እንዲሁም ልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራ መቀበል ባይኖርባቸውም በዚህ ዓለም ሳሉ በሠሩት ሥራና ባገኙት ጸጋ ያን እያሳሰቡ በጸሎታቸው የሚታመኑትንና ስማቸውን የሚጠሩትን ሰዎች ሲረዱበት ይኖራሉ፤ "ሥራቸው ይከተላቸዋል" ተብሏልና፡፡ ራዕ. 14፥13

ቅዱስ ጴጥሮስ እንደ ተናገረው ከመውጣታቸው በኋላም በአፀደ ነፍስ ሆነው በዚህ ዓለም ስላሉ ወገኖቻቸው ይተጋሉ፡፡ በአጸደ ነፍስ ያሉ የእግዚአብሔር ቅዱሳን በዚህ ዓለም ስላሉ ወገኖቻቸው አይጸልዩም ብሎ ማሰብ ስለ ነፍስ ሕያውነትና ከሞት በኋላ ሕይወት ያለ መሆኑን ከማያምን ሰው የሚመነጭ አስተሳሰብ ነው እንጂ ይህን ለሚያምን ሰው በአካለ ነፍስ ሕያዋን የሆኑ ቅዱሳን ስለ ሌሎች ሊጸልዩ አይችሉም ከሚል የክህደት አስተሳሰብ አይደርስም፡፡

2. ታሪኩና ሐተታው ከላይ በ6.2.3 እንደ ተገለጸው አብርሃም በአካለ ነፍስም ሆኖ እንደ ተለመነ ጌታችን ተናግሯል፡፡ ይህም ከላይ እንደ ተገለጸው ምሳሌ ሳይሆን እውነተኛ ታሪክ ነው፡፡ እውነተኛ ታሪክ በመሆኑም የአብርሃምንና የአልዓዛርን ስም በመጥቀስ ተናግሯል፡፡ ይኸውም ምንም እንኳ ከላይ እንደ ተገለጸው ባለ ጸጋው ከእርሱ መሟላት ያለበትን ነገር ባለ ማድረጉ በአብርሃም አባትነትና አማላጅነት ለመጠቀም ባይበቃም በዓፀደ ነፍስ ምልጃና ልመና መኖሩን ግን በተግባር አሳይቷል፡፡ በአካለ ነፍስ ምልጃና ልመና ባይኖር ኖሮ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ትምህርት ባላስተማረ ነበር፡፡

## 6.3.3 የቅዱሳን አማላጅነት - በቀደምት አበው ሲቃውንት ትምህርት

- "ቅዱሳን ሐዋርያትን፣ ነቢያትን፣ እና ሰማዕታትን እቀበላቸዋለሁ፤ ወደ እግዚአብሔር እንዲማልዱልኝም እለምናቸዋለሁ፡፡ ይህም እግዚአብሔር በእነርሱ በኩል ማለትም በእነርሱ አማላጅነት መሐሪው አምላክ ለእኔ ይራራልኝና ይቅር ይለኝ ዘንድ፣ የኃጢአቴ ፍጻም ይከፈልና ያበቃ ዘንድ ነው፡፡[115] . . . እንደዚሁም የሰማዕታት ዓጽም ላላቸውና ለጠበቁት ሰዎች መከላከያና ጠባቂ ነው፡፡" (ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ፣ መልእክት ኀበ ቅዱስ አምብሮስ፣ ቁ. 197)

- "ድል ያደረጋችሁ ሰማዕታት ሆይ፣ ስለ አምላካችሁና መድኃኒታችሁ ፍቅር ስትሉ መከራን በፈቃዳችሁ የተቀበላችሁ ሰማዕታት ሆይ፣ እናንተ ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር ድፍረቱ አላችሁ፡፡ ቅዱሳን የሆናችሁ እናንተ፣ የማንረባ ኃጢአተኞችና ስንፍናንና ሐኬትን የተመላን ለሆንን ለእኛ የእግዚአብሔር ጸጋ ይኅበናን ዘንድ ስለ እኛ ጸልዩልን፡፡" (ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፣ በእንተ ሰማዕታት)

- "የቅዱሳን ሰማዕታት ጸሎት ጠቀሜታው ብዙ ነው፤ የእነርሱን ጸሎት መጠየቅም ተገቢ ነው፡፡ ሃይማኖተኛ የሆኑ ሰዎች ስለ ልጆቻቸው ደኅንነት፣ ከቤት ስለ ወጣ የቤተሰባቸው አባል በደኅና መመለስ! ስለ ታመሙት መዳን በጸሎታቸው ይራዷቸው ዘንድ ይጠይቃሉ፡፡ ስለዚህ ጸሎታችሁ ከሰማዕታት ጋር አብሮ ይሁን፡፡" (ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ፣ ገብቶ ወጥ በነበረው በንጉሥ ዑልያኖስ[116] ላይ የጻፈው ትምህርት፣ መልእክት 360)

- "... ካህኑ አባታችን [ጳጳስ መላጥዮስ] የሃይማኖታችን ራስና ፈጻሚ የሆነው ሊቀ ካህናታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ገባበት ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ገባ እንጂ ከእኛ የተወሰደ አይደለም፡ ፡ የሥጋን መጋረጃ ከኋላው ትቶ ወደ ውስጥ ገብቷል፡፡ በዚያ በሰማይም በዚህ ምድር ላይ ሳለ እንደ ነበረው ዓይነት በምሳሌው ወይም በጥላው እንደ ነበረው ዓይነት ጸሎት የሚጸልይ አይደለም፣ የእነዚህን ነገሮች ራሳቸውን ያያቸዋል እንጂ፡፡ እግዚአብሔርን የሚማልደው አይደለም፣ በዚህ ዓለም ሳለ እንደ ነበረው በመስተዋት በድንግዝግዝ አይደለም፤ ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት ስለ እኛ ይማልድልናል እንጂ፤ ስለ ሕዝቡ ኃጢአትና መተላለፍም ይማልዳል እንጂ፡፡"[117] (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ትምህርት በእንተ ዕረፍቱ ለጳጳስ መላጥዮስ)

- "... በተሰጠው ትምህርት መሠረት ማን ማድረግ እንደሚገባው እንደሚያደርግና ማን ደግሞ እንደማያደርግ ማወቅ እችል ዘንድ ይህ ጉባኤ ሲያበቃ ከእያንዳንዳችሁ ጋር ረዘም ያለ ውይይት ለማድረግ የሚቻለኝን ያህል እሞክራለሁ፡፡ አሁንም ግን የሚምል ሰው ካገኘሁ መሐላ መማልን አስወግደው በተስተካከሉት ሰዎች ሁሉ ፊት አቀርበዋለሁ፤ ይህም በሰው ሁሉ ፊት በመገሠጹና በመወቀሱ ከዚህ መጥፎ ልማድ ፈጥኖ ነጻ እንዲወጣ እንረዳው ዘንድ ነው፡፡ በኃጢአቱ ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ በኖሩ በመላው ሰዎች ዓይን ፊት በሚገለጥበት በዚያን ቀን ከሚያፍርና ከሚቀጣ እዚህ ተገሥጾ ቢስተካከል ይሻለዋልና፡፡ ሆኖም በዚህ ጉባኤ ካለነው መካከል እንዲህ ያሉ ነገሮች ደርሰውበት በዚያን ቀን በእግዚአብሔር ፊት በኃፍረትና በቅጣት የሚቆም አንድም ሰው እንዳይኖር እግዚአብሔር

[115] ( I also receive the holy apostles, prophets, and martyrs, and call on them to supplication unto God, that through them, that is, through their mediation, the merciful God may become propitious to me, and a ransom of my sins may be made and granted.) To Julian the Apostate, Ep. 360.)

[116] ዩልያኖስ (To Julian the Apostate)

[117] (No longer through a glass darkly does he intercede with God, but face to face he intercedes with Him: and he intercedes for us, and for the "negligences and ignorances" of the people.)

ይህን ከእኛ ያርቅልን! በቅዱሳን አባቶቻችን ጸሎት ስህተቶቻችንን ሁሉ አስተካክልንና በደሎቻችንን ሁሉ አስወግደን፣ የመልካም ምግባር ሕይወትን ፍሬ አብዝተን አፍርተን ከዚህ ሕይወት ስንሄድ በፊቱ ለመቆም የሚሆነንንና እንደናፍር የሚያደርገንን መልካም ነገር ይዘን ለመሄድ እንችል ዘንድ እርሱ ይርዳን፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 6፣ ቁ. 14)

- "… እግዚአብሔር እርሱ ባወቀ ከሁለታችን መካከል ወደ እርሱ ይሔድ ዘንድ ቀድሞ የሚጠራውና የሚሞተው ወደ ኋላ ለሚቀረው ይጸልይለት ዘንድ ይገባዋል፣ ከዚህ ዓለም ሕይወት ብንወሰድም ለወንድሞቻችንና ለእህቶቻችን በእግዚአብሔር መንበር ፊት ገጸ ምሕረቱን የመለመን ጸሎታችን አይቋረጥም፡፡"[118] (ቅዱስ ቆጵርያኖስ፣ ዘመን ገጠም ለነበረው ለሮማው ጳጳስ ለቆርኔሌዎስ የጻፈው መልእክት፣ መልእክት 56፣ ቁ. 5)

- "ከእኛ በፊት ቀድመው ያረፉትን በጸሎታችን እናዘክራቸዋለን፡፡ በመጀመሪያ አበውን፣ ነቢያትን፣ ሐዋርያትን፣ ሰማዕታትን እንጠራቸዋለን፡፡ ይህም በጸሎታቸውና በምልጃቸው እግዚአብሔር ልመናችንንና አስተብቁዖታችንን ይቀበልልን ዘንድ ነው፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ በእንተ ምሥጢራት፣ ትምህርት 5፣ ቁ. 6)

- "እኛን ይጠብቁን ዘንድ የተሰጡን ቅዱሳን መላእክት ስለ እኛ ይማልዱልን ዘንድ ልንለምናቸው ይገባል፡፡ ቅዱሳን ሰማዕታትንም ልንማጸናቸው ይገባል፣ የራሳቸውን ኃጢአት (ከነበረባቸው ማለቱ ነው) በደማቸው ያጠቡ እነርሱ ስለ እኛ ኃጢአት ሊጸልዩልን ይችላሉና፡፡ ስለ ድካማችን ይጸልዩልን ዘንድ እነርሱ አማላጆቻችን ለማድረግ አንፈር፣ አሁን ድል አድርገው ያለፉትን የሥጋን ድካም ቀድሞ ያውቁታልና፡፡"[119] (ቅዱስ አምብሮስ፣ በእንተ ብእሲተ ማውታ፣ ምዕ. 9)

- "የተቀደስክና በአምላካዊ ጸጋ የከበርህ አባታችን አንተ ቅዱስ ባስልዮስ ሆይ፣ ከላይ ሆነህ ወደ ታች ተመልከተን፣ በምልጃህም በሥጋችን ሆኖ እየወጋን ያለውን እሾህ አስወግድልን፣ አለዚያም ደግሞ በትዕግሥትና በጽናት እንሸከመው ዘንድ አስችለን፡፡"[120] (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ ትምህርት በእንተ ዕረፍቱ ለቅዱስ ባስልዮስ)

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ደግሞ እንዲህ ይላል፦

- "ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ በዚህ ዓለም ሳሉ ብቻ ሳይሆን ከሞቱ በኋላ እንኳ እንዲያበሩና እንዲሠለጥኑ አድርጓቸዋል፡፡ እስኪ ንገረኝ፣ የእስክንድር [የታላቁ] መቃብር የታለ? የት እንዳለ ታውቅ እንደሆነ፣ እንዲሁም የሞተበትን ቀን እስኪ ንገረኝ፡፡ የክርስቶስ አገልጋዮች ግን መቃብራቸው እንኳ ሳይቀር የተከበረ ነው፣ ያረፉበት ቀንም በሚገባ የታወቀ ነው፣ ዕለተ ዕረፍታቸውም በዓለሙም ሁሉ የበዓል ቀን ሆኖ ይከበራል፡፡የተሰቀለው የክርስቶስ አገልጋዮች መቃብሮቻቸው ከነገሥታት ቤተ መንግሥታት ይልቅ የተከበሩና የተወደዱ ናቸው፣ ይህም ከስፋታቸውና ከውበታቸው ሳይሆን ከዚህ በላይ በሆነው በሚገበኟቸው ሰዎች

---

118 ( . . . if any one of us, by the swiftness of divine condescension, shall go hence the first, our love may continue in the presence of the Lord, and our prayers for our brethren and sisters not cease in the presence of the Father's mercy.)

119 ("The angels are to be entreated for us, who are given us for our guard; the martyrs are to be entreated, whose patronage we may in a manner claim by the pledge of their bodies. They can pray for our sins, who have washed in their own blood their own sins, if such they had. Let us not be ashamed to take them as intercessors for our weakness, for they themselves knew the weaknesses of the body, even when they overcame."St. Ambrose, Concernig Widows, ch. 9.)

120 ("But do thou, O divine and sacred head, look on us from above, and either remove by the intercessions the thorn in the flesh that chastises us, or persuade us to bear it with fortitude.")

ጽኑ የሆነ ፍቅርና የሚቃጠል የመንፈስ ቅንዓት ነው፡፡ ልብሰ መንግሥት የለበሰውና ዘውድ የደፋው ንጉሡ ራሱ ወደ እነዚያ የቅዱሳን መቃብራት ሄዶ በእግዚአብሔር ፊት ጠበቃዎች እንዲሆኑትና እንዲረዱት ይለምናቸው ዘንድ የክብር ልብሱን አውልቆ በዚያ ይቆማል፡፡ ልብሰ መንግሥት ያለው እርሱ በሥጋ የሞቱ ቢሆኑም ረዳቶቹ ይሆኑ ዘንድ ድንኳን ሰፊዎችንና ዓሣ አጥማጆችን ይማጸናል፡፡ ታዲያ ከሞቱ በኋላ እንኳ የዚህ ዓለም ነገሥታት ረዳቶችና ጠባቂዎች የሆኑትን የእነዚህን አምላክ እግዚአብሔርን 'የሙታን አምላክ ነው' ልትለው ትደፍራለህን? እስኪ ንገረኝ!

"ሆኖም ወርቅ ለብሶ ዘውድ ደፍቶ፣ የጦር አዛዦቹና መሳፍንቱ፣ መኳንንቱና ሹማምንቱ እግረኛውና ፈረሰኛው ሠራዊቱ ዙሪያውን ከብበውት ቆመው ንጉሥን ማየት ደስ ያሰኛል'ከ የሚል ይኖራል፡፡ ነገር ግን ይህ የእኛ የሆነው ከዚህ ይልቅ እጅግ የከበረና ግርማ ያለው ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይም በዚህ ዓለም ያለው ክብር ሁሉ የልጆች ጨዋታና የመድረክ ላይ ትርዒት ብቻ ነው የሚመስለው፡፡ የቅዱሳን አጽማቸው ያረፈበትና መቃብራቸው ያለበት ቦታ ስትሄዱ ገና ከቦታው ስትደርሱ ቦታው ሐሳባችሁን ወደ ላይ ወደ ሰማይ ያወጣዋል፡፡ በዚያ (በሰማይ) ወዳለው ሰማያዊ ንጉሥና ወደ ሠራዊተ መላእክት፣ ሉዐላዊ ወደ ሆነው ዙፋንና ሰው ሊደርስበት ወደማይችለው መለኮታዊ ክብር ይወስዳችኋል፡፡

"በርግጥ በዚህ ዓለም ያሉ መሪዎችም አንዱን ማሰር ሌላውን መፍታት ይችላሉ፤ የቅዱሳን ዐጽም ያለው ሥልጣን ግን እንዲህ ያለ ተራና መናኛ ሥልጣን ሳይሆን ከዚህ በእጅጉ የበለጠ ነው፡፡ እነርሱ [የቅዱሳን ዐጽም] አጋንንትን ያዝዟቸዋል፣ ያስሯቸዋል፣ ይቀጧቸዋል፣ በእነርሱ የታሠሩትንም ይፈቷቸዋል፡፡ ከዚህ ሁኔታ የበለጠ የሚገርም ምን ነገር አለ? የሚያያቸው ማንም ሰው ባይኖርም፣ አጋንንቱን ሲገርፉቸው በዓይን የሚታይ ነገር ባይኖርም እነርሱ [አጋንንቱ] ግን ያለቅሳሉ፣ ይጮኻሉ፣ ይሠቃያሉ፡፡ ይህም የሚሆነው ከቅዱሳኑ ዐጽም የሚወጣውን ድንቅ ኃይል መቋቋም ስለማይችሉ ነው፡፡

"በዚህ ዓለም ሳሉ ሥጋ ለባሾች የነበሩት እነርሱ አሁን ሥጋ በሌላቸው ኃይላት ላይ ድል አድራጊዎች ሆኑ፡፡ የእነርሱ ዐጽም፣ አመዳቸው፣ አፈራቸው የማይታዩትን ረቂቃን ኃይላት አስጨንቆ ያባርራቸዋል፡፡ ከዚህም የተነሣ የነገሥታትን አብያተ መንግሥታት ለማየት አገር አቋርጠው ወደ ሩቅ ቦታ ከሚሄዱት ሰዎች ይልቅ እንደዚህ ያሉ ተአምራት የሚፈጸሙባቸውን የቅዱሳን ዐጽም ያረፈባቸውን ቦታዎች ለማየት የሚሄዱት ሰዎች ብዙ ናቸው፡፡ የቅዱሳን ዐጽም ያረፈባቸውና በስማቸው የታነጹ አብያተ ጸሎታት የሚመጣውን ፍርድ በጨረፍታ የሚያሳዩ ናቸውና፤ ይህም አጋንንት ይሠቃዩባቸዋል፣ ሰዎች ደግሞ ይገሠጹባቸዋል፣ ነጻም ይወጡባቸዋልና ስለዚህ ነው፡፡

"የቅዱሳንን ኃይል ከሞቱ በኋላ እንኳ አየህን? የኃጥአንን ደካማነት ደግሞ በሕይወት እያሉ እንኳ አየህን? ከደካማነት ራቅ፣ በእነርሱ ላይ ኃይል ይኖርህ ዘንድ፤ የመልካም ምግባር ሕይወትን ባለህ ዓቅም ሁሉ ተከተል፡፡ በዚህ ዓለም እንዲህ ከሆነ በሚመጣው ዓለም ምን ሊሆን እንደሚችል አስብ፡፡ ሁለንተናህ በዚህ ፍቅር የተቃኘና የተገዛ ይሁን! ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ባለው ፍቅር እናገኘዋለን ብለን ተስፋ የምናደርገውን ዘለዓለማዊ ሕይወትን አጥብቀህ ያዝ፣ ምስጋና ለእርሱ ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ከአባቱና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ይሁን፣ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ቆሮንቶስ ካልእ፣ ክፍለ ትምህርት 26፣ ቁ. 5)

ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

❖ "መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው በነፍሱ ብሩህና አዋቂ ይሆናል፣ ሰው በተፈጥሮ ሊያየው ከሚችለው ውጭ የሆኑ ነገሮችን ያያል፤ ቀድሞ አያውቃቸው የነበሩ ብዙ ስውርና ረቂቅ ምሥጢራትን ያውቃል፤ ሰውነቱ በዚህ ዓለም ላይ ሆኖ ነፍሱ ሰማያትን ታያለች፣ በዚያ የሚሆነውን ነገር ትመለከታለች፣ ታውቃለች፡፡ እንዲህ ያለው በመንፈስ ቅዱስ አዋቂ የሆነ

ሰው 'እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት' እስኪል ደርሶ እንደ ኢሳይያስ ያያል (ኢሳ. 6፥1)፣ እንደ ሕዝቅኤል በኪሩቤል ራስ ላይ የሚቀመጠውን ያያል (ሕዝ. 10:1)፣ እንደ ዳንኤልም እልፍ አእላፋት መላእክት በፊቱ ቆመው ያያል (ዳን. 7:10)።።በአካሉና በዕድሜው ትንሽ የሆነው ሰው የዓለምን መጀመሪያና አፈጣጠር ያያል፣ የዓለምን ፍጻሜም ያውቃል፣ በመካከል ያሉትን ዘመናትም ያያል፡፡ የነገሥታትን መፈራረቅና አተካክ ይረዳል፣ ምንም ያልተማራቸውን ነገሮች ያውቃል፡፡ እውነተኛው እውቀትን ገላጭና ነፍስን ብርሀት የሚያደርጋት መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ጋር አብሮት አለና፡፡ ሰውዬው በቤት ግድግዳዎች ውስጥ ተወስኖ እያለ የእውቀቱ ኃይል ግን በጊዜና በቦታ ከዚያ ካለበት እጅግ በጣም አልፎ ይሄዳል፤ ሌሎች ሰዎች የሚያደርጉትን እንኳ እስከ ማየት ይደርሳል፡፡

"ጴጥሮስ ንብረታቸውን በሸጡ ጊዜ ከሐናንያና ከሰጲራ ጋር አብሯቸው አልነበረም፤ ሆኖም በመንፈስ ግን አብሯቸው ነበር፡፡ 'ሐናንያ ሆይ፣ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ?' ያላቸው ለዚህ ነበር፡፡ የሐዋ. 5፥3 ከሳሽና ምስክር አልነበረም፣ ታዲያ ምን እንደ ተደረገ በምን አወቀ? 'ሳትሸጠው የአንተ አልነበረምን? ከሸጥኸውስ በኋላ በሥልጣንህ አልነበረምን? ይህን ነገር ስለ ምን በልብህ አሰብህ? እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም' ብሎታልና፡፡ የሐዋ. 5፥4 የዚህ ዓለም ትምህርት ያልነበረው ጴጥሮስ (የሐዋ. 4፥13) ፈላስፎችና አዋቂቆች የሚባሉት እንኳ ሊያውቁት የማይችሉትን እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ አወቀ፡፡

"በኤልሳዕም እንደዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ነገር እናገኛለን፡፡ ንዕማንን ያለ ምንም ገንዘብ በነጻ ከፈወሰው በኋላ ግያዝ ከንዕማን ገንዘብ ተቀብሎ የተቀበለውን ሁለት መክሊት ብርና ልብስ በሰወረው ጊዜ ያ ነገር ከኤልሳዕ ግን የተሰወረ አልነበረም፡፡ በተመለሰ ጊዜም ጴጥሮስ እንደ ጠየቃቸው እርሱም "ግያዝ ሆይ፣ ከወዴት መጣህ?" ብሎ ጠየቀው፡፡ 2 ነገ. 5፥25 እንዲያ ብሎ የጠየቀውም ካለማወቅ ሳይሆን በጨለማ እንደ ሰወረው ወደ ጨለማ እንደሚሄድ ሲነግረው ነበር፤ የለምጻሙን ፈውስ እንደ ሸጥህ ለምጹ የአንተ ሀብት ይሆናል ሲለው ነበር፡፡ እኔ በነጻ የተቀበላችሁትን በነጻ ስጡ የተባለውን ፈጽሜያለሁ፣ አንተ ግን ይህን የእግዚአብሔር ጸጋ ሸጠሃል፣ ስለዚህ አሁን የሽያጭህን ዋጋ ተቀበል ሲለው ነበር፡፡ ኤልሳዕ "ያ ሰው ከሰረገላው ወርዶ ሊቀበልህ በተመለሰ ጊዜ ልቤ ከአንተ ጋር አልሄደምን?" አለው፡፡ 2 ነገ. 5፥26 'በሥጋዬ እዚሁ ተወስኜ ተቀምጬ ነበር፣ ከእግዚአብሔር የተሰጠኝ መንፈስ ግን ከዚህ ርቀው የሚሆኑ ነገሮችን ያያል፣ ስለዚህም ምን እየተደረገ እንደ ነበር በግልጽ አሳይቶኛል' አለው፡፡ መንፈስ ቅዱስ አላዋቂነትን የሚያርቅ ብቻ ሳይሆን እውቀትን እንደሚሰጥና ኃላፍያትንና መጻእያትን እንደሚያሳውቅ አየህን? የሰዎችን ነፍስ ምን ያህል በእውቀት ብሩህ እንደሚያደርግ ተረዳህን?"

(ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 16፣ በእንተ መንፈስ ቅዱስ፣ ቁ. 16-17)

❖ "እግዚአብሔር ሙሴን 'እኔ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብም አምላክ ነኝ' አለው፤ ይህ ማለት እነዚህ አባቶች በሕይወት ያሉና ሕይወታቸው ያልተቋረጠ (በሞት ያልጠፋ) ስለ መሆናቸው የተነገረ መሆን አለበት፡፡ አብርሃም በሥጋ ሲሞት መኖር አከትሞለት ቢሆን ኖሮ፣ ይስሐቅና ያዕቆብም እንዲሁ በሞታቸው ሕይወታቸው ተቋጭቶ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ሕይወት የሌላቸው የሙታን አምላክ በሆነ ነበር፡፡ አንድ ንጉሥ የሌሉትን ወታደሮች እኔ የወታደሮች ንጉሥ ነኝ ብሎ የሚያውቀው መቼ ነው? የሌለውን ንብረት የእኔ ነው ብሎ የሚያሳይስ ማን ነው? ስለዚህም እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ ይሆን ዘንድ አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ በሕይወት ያሉ ሕያዋን መሆን አለባቸው፤ እርሱ 'የእነርሱ አምላክ ነኝ' አለ እንጂ 'አምላካቸው ነበርሁ' አላለምና፡፡

(ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 18፣ በእንተ አሐቲ ቅድስት ሁላዊት ቤተ ክርስቲያን ወትንሣኤ ሥጋ ወሕይወት ዘለዓለማዊ፣ ፡ ቁ. 11)

❖ "ስለ ኤልያስና ከሞት ስላስነሣው ስለ መበለቷ ልጅ፣ እንዲሁም ስለ ኤልሳዕና ሙታንን ሁለት ጊዜ፡ አንዱን በሕይወት ዘመኑ፣ ሌላውን ደግሞ ከሞተ በኋላ ማስነሣቱን እናገራለሁ። ኤልሳዕ በሕይወተ ሥጋ ሳለ የሞተውን ማስነሣትን በራሱ አደረገ። የቅዱሳን ነፍሳቸው ብቻ ሳትሆን ሥጋቸውም ኃይለ እግዚአብሔር ያደረበትና ጸጋ እግዚአብሔር የማይለየው መሆኑ ይታወቅና ይታመን ዘንድ የኤልሳዕ ሥጋው ባረፈበት መቃብር ላይ የተጣለው አስከሬን የነቢዩን የሞተ ሰውነት በነካ ጊዜ ወዲያውኑ ተነሣ። ሞቶና ተቀብሮ ያለው የነቢዩ ሰውነት ለምውቱ ሕይወትን ሰጠ፤ ሆኖም እርሱ (የኤልሳዕ ሰውነት) ለሞተው ሕይወትን ሰጥቶ ቢያስነሣውም እርሱ ግን ከሙታን ጋር በመቃብሩ መኖርን ቀጠለ። ለምን እንዲያ ሆነ? ኤልሳዕም አብሮ ቢነሣ ኖሮ የሞተውን የማስነሣቱ ሥራ ለኤልሳዕ ሰውነት ሳይሆን ለነፍሱ ብቻ ተደርጎ እንዳይወሰድ ነበር፤ እውነተኛ የሆነች ነፍሳቸው ገንዘቧ ስላደረገችውና እግዚአብሔርን ማገልገያ መሣሪያ አድርጋ የተጠቀመችበት፣ ኋላም ተዋሕዳው የምትነሣው ስለሆነ ነፍስ አብራ ባትኖርም እንኳ የቅዱሳን ሰውነታቸው ክብርና ኃይል የማይለየው መሆኑ እንዲታወቅ ነው። እንዲህ ያለውንም ነገር እንዳልሆነና እንዳልተፈጸመ በመቁጠር በስንፍና አንጠራጠር። ከሰውነት ውጭ የሆኑ የልብስ ዘርፎች የበሽተኞችን ሰውነት ሲነኩ ሕሙማንን ከፈወሱ የነቢዩ የራሱ አካሉ የሆነው ሰውነቱማ እንዴት ከሞት ማንሣት ያቅተዋል?"

(ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፡ ትምህርት 18፤ በእንተ አሐቲ ቅድስት ዙላዊት ቤተ ክርስቲያን ወትንሣኤ ሥጋ ወሕይወት ዘለዓለማዊ፣ ቁ. 16)

በ374 ዓ. ም. ቫሌንስ (ዋሊጦስ) የተባለው አርዮሳዊ የነበረው የምሥራቁ የሮማ ግዛት ንጉሥ አርቶዶክሳውያን አባቶችን ከየመናብርታቸውና ሀገረ ስብከታቸው እያሳደደ በቦታቸው አርዮሳውያንን እየተካ ነበር። አርዮሳዊው ቫሌንስ ካሳደዳቸው ኦርቶዶክሳውያን ጳጳሳት መካከል አንዱ የነበረው አውሳብዮስ የተባለው አባት ወደ ትራኪያ እንዲሰደድ በተደረገ ጊዜ ወደ ግዞቱ የሄደው በቀጰዶቅያ አድርጎ ነበር። በዚያም ቅዱስ ባስልዮስን በአካል አገኘው። ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ ግን በጣም ታምሞ ስለነበር ወጥቶ ሊገናኘው አልቻለም ነበር። ስለዚህም ለጳጳስ አውሳብዮስ የሚከተለውን መልእክት ላከለት፦

❖ "ብፁዕነትህ አባቴ በእኛ ሀገር እያለፍክ በነበረ ጊዜ ከነበርኩበት ቤት ወደ ውጭ እንኳ መመልከት አልችል በነበረበት ሁኔታ በጠና ታምሜ ነበር። ምንም እንኳ ሕመሜ ክፉ ከሚያሳስብ ደረጃ የደረሰ የነበረ ቢሆንም በጣም ያዘንኩት ግን ከሕመሜ ይልቅ የአንተን ቅድስናና ደግነት በአካል ማግኘት ባለመቻሌ ነው። የአንተን የተወደደ ገጽህን (ፊትህን) ለማየት የነበረኝ ናፍቆትና ጉጉት ልክ ከመንፈሳዊ ቁስሉ ለመፈወስ የሚፈልግና ያንም ከአንተ ለማግኘት ያሰበ ሰው የሚኖረው ጉጉት ዓይነት ነበር። ነገር ግን ያን ጊዜ አንተን በአካል ለማግኘት የነበረኝ ምኞት ከኃጢአቴ የተነሣ ባይሳካልኝም አሁንም በአንተ ጸሎት ለችግሬ መፍትሔ አገኝ ዘንድ እችላለሁ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ባለው ጸሎትህ እኔን ለማሰብ ፈቃድህ ቢሆንልኛና ራስህን ወደ እኔ ደረጃ ዝቅ አድርገህ በጸሎትህ ለመታሰብ የበቃሁ አድርገህ ብትቆጥረኝ በዚህ ዓለም ሕይወቴም ሆነ በሚመጣው ዘመን ይህ ለእኔ ከእግዚአብሔር ለሚገኝ በረከት ሁሉ መዝገብና ምንጭ ይሆንልኛል።ስለ ወንጌል እምነት እንዲህ የምትጋደልና መከራን የምትቀበል፤ ይህ ሁሉ ስደት የሚደርስብህና መከራን ሁሉ እየተጋፈጥህ ያለህ አባቴ አንተ - እንዲህ ያለ ሰው በጸሎቱ እኔን ቢያስበኝ የማገኘው ጥቅምና ብርታት ከቅዱሳን ሰማዕታት ከአንዳቸው ከማገኘው ጸሎትና ምልጃ ያነሰ እንዳልሆነ እምናለሁና። ስለዚህ የአንተ የሆነውን ጎርጎርዮስን ስለ ማንኛውም ነገር ሁሉ በጸሎትህ ታስበው ዘንድ እማልድሃለሁ።"

(ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፡ መልእክት ቁ. 64)

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ከእርሱ በፊት በ373 ዓ. ም. ላረፈው ለቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ እንዲህ ብሎ ጸልዮአል፡-

- "ከላይ ከሰማይ ሆነህ እባክህ እኛን በምሕረትና በፍቅር ዓይን ተመልከተን፡፡ ይህን ሕዝብም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ፣ አንድ አምላክ ብለን በምናመልከው በቅድስት ሥላሴ ያለውን ማመንና አምልኮ በፍጹም እምነትና ጽናት እንዲጠብቅ አድርገው፣ እንደዚሁም እኔንም የእረኝነት ተልእኮዬን በሰላም እንድፈጽም እርዳኝ፡፡ ተልእኮዬ በውጣ ውረድና በመከራ የታጀበ ከሆነም ደግሞ አጽናኝ፤ አለዚያም ደግሞ ወደ አንተ ውሰደኝ፣ በዚያም ከአንተ ጋር እና አንተን ከመሰሉ ጋር እኖር ዘንድ አድርገኝ፡፡"[121] (በእንተ ቅዱስ አትናቴዎስ፣ ትምህርት 21፣ ቁ. 37)

- "ንፋቄንና ስህተትን በጽኑ ተዋግቶና ኃይሉን አድክሞ፣ ከብዙ ተጋድሎዎችና መከራዎች በኋላ በመልካም ሽምግልና የዚህን ዓለም ሕይወት ፈጽሞ የሄደው ታላቁ ቅዱስ አትናቴዎስ አሁን ከላይ ሆኖ ወደ እኛ እንደሚመለከተን በሚገባ አውቃለሁ፡፡ እርሱ ከዚህ ዓለም ድካምና ውጣ ውረድ ነጻ የሆነና ያረፈ በሆነ መጠን አሁን በዚህ ዓለም ሕይወት ለእውነት የሚደክሙትን ይረዳቸዋልና፡፡" (በእንተ በጺሖተ ግብጻውያን፣ ትምህርት 34፣ ቁ. 3)

- "እርሱ ከእኛ ጋር ሳለ እኔን ለጓደኛ እንደሚገባ፣ ከዚያም በላይ ደግሞ ከፍ ያለና ሉዐላዊ ስለ ሆነው መንፈሳዊ ሕግ ሲል በብዙ ነገሮች ያርመኝና ያስተካክለኝ እንደ ነበረ ሁሉ፣ እርሱ ለእኛ ለሁላችን የመልካም ምግባር ሕይወት ቀኖናችን ነበርና ይህን ስል አላፍርም፡፡ አሁንም ከላይ ወደ ታች ወደ እኔ እየተመለከተ በርኅራኄና በሐዘኔታ ይመለከተኛል፣ ያስበኛልም፡፡" (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ ትምህርት በእንተ ዕረፍቱ ለቅዱስ ባስልዮስ፣ ቁ. 2)

- "... የእኔን የወደፊት ሁኔታ በተመለከተ እግዚአብሔር እርሱ ወደ ወደደውና ደስ ወዳለው መንገድ ይምራው፣ ስለ እርሱ [የቅዱስ ባስልዮስ] ምልጃ ቀሪ ሕይወቴን የተሻለ ያደርግልኝ ዘንድ እግዚአብሔር ፈቃዱ ይሁንልኝ፡፡" (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ ትምህርት በእንተ ዕረፍቱ ለቅዱስ ባስልዮስ፣ ቁ. 25)

- "እርሱ [ቅዱስ ባስልዮስ] ሥጋው ከድካምና መከራ ሊያደርሱበት ይፈልጉ ከነበሩት ሁሉ በመጨረሻ ነጻ በመሆንና በማምለጥ ከእርሱ በፊት የነበሩት አባቶች በሄዱበት መንገድ ሄዷል፣ ወደ አባቶቹ መቃብር ወርዷል፣ ሊቀ ካህናቱ እርሱ ወደ ካህናት ወገን ተደምሯል፡፡ አሁንም በጆሮዬ እያቃጨለብኝና እየተሰማኝ ያለው ያ ኃይለኛና ግሩም የነበረው ድምፁ ስለ ክርስቶስ ወደ መሰከሩ የምስክሮች ማኅበር ሄዷል፣ ሰማዕቱ ወደ ሰማዕታት ተደምሯል፡፡[122] አሁን እርሱ በሰማይ ነው፡፡ እርሱ በዚያ ስለ እኛ መሥዋዕት እያቀረበልን ነው፣ ስለ ሕዝቡ እየጸለየልን ነው፡፡ እርሱ በሥጋ ከእኛ ተለይቶ የሄደ ቢሆንም ፈጽሞ አልተለየንምና፡፡ ግማሽ ምውት የሆንኩት እኔ ጎርጎርዮስ ታላቅ ከነበረው የእርሱና የእኔ አንድነታችን ከተለየሁ በኋላ ሽካራ በሆነ የዚህ ዓለም የሕማምና የመከራ ሕይወት ሰንሰ መሪዬ የነበረውን እርሱን በማጣቴ የሕይወቴ ፍጻሜ እንዴት እንደሚሆን አላውቅም፡፡ አሁንም ማድረግ ከሚገባኝ ነገር ሳጓድል በሌሊት ራእዮች ይገሥጸኛል፣ ማድረግ ያለብኝንም ይመራኛል፡፡

---

121 (And mayest thou cast upon us from above a propitious glance, and conduct this people in its perfect worship of the perfect Trinity, which, as Father, Son, Holy Ghost, we contemplate and adore. And mayest thou, if my lot be peaceful, possess and aid me in my pastoral charge, or if it pass through struggles, uphold me, or take me to thee, and set me with thyself and those like thee (though I have asked a great thing) in Christ Himself, our Lord, to whom be all glory, honour, and power for evermore. Amen.)

122 (. . . the high priest being added to the priests, the mighty voice which rings in my ears to the heralds, the martyr to the martyrs. And now he is in heaven, where, if I mistake not, he is offering sacrifices for us, and praying for the people, for though, he has left us, he has not entirely left us.)

"አሁን ይህን ስናገር ዓላማዬ ሐዘንን ከምስጋና ጋር ማቀላቀል አይደለም፣ ወይም የእርሱን የቅድስና ሕይወት ታላቅነት ማሳየት አይደለም፡፡ ለሁሉም አብያተ ክርስቲያናትና ነፍሳት የእርሱን ታላቅ ሕይወት እንደ ሕያው ሕግ አድርገው እንዲያዩትና ሕይወታችን እርሱ በተጓዘበት መንገድ ይሆን ዘንድ አርአያነቱን እንድናዘክር፣ እንዲሁም ክርስቲያኖች የሆናችሁ ሁላችሁ እርሱም እንደሚያያችሁና እናንተም እንደምታዩት ሰው ዓይናችሁን በእርሱ ላይ እንድታደርጉና ከዚህም የተነሣ በመንፈስ ቅዱስ ፍጹማን እንድትሆኑ ነው እንጂ፡፡[123]"

(ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ ትምህርት ፀእንተ ዕረፍተ ለቅዱስ ባስልዮስ፣ ቁ. 80)

- "አባቴ ሆይ፣ ምን ትላለህ? አንተ ስለ እኔ መማር ለተቀበልከው መከራና ለደከምከው ድካም ሁሉ ይህ እኔ ለአንተ መታሰቢያ የተናገርሁት የምስጋናና የውዳሴ ንግግር በቂ ነውን? . . . አንተ በርግጥ እንዲህ ስለ አንተ መናገሬ እንደማያስደስትህና እንድናገር እንደማትፈቅድልኝ አውቃለሁ፡፡ ሆኖም ባይሆን ይህን እንድናገርስ ፍቀድልኝ፡፡ በምን ዓይነት የክብር ሁኔታ ላይ እንዳለህ እና ስለ ክበበህ የጸጋ ብርሃን እኛ እንድናውቅ አድርገን፣ በአባትነትህ የሚያምኑትን ሁሉንም አንተ ወዳለህበት የክብር ቦታ ተቀበላቸው፣ ከዚህ ዓለም መከራና ውጣ ውረድ ለመለየት ብዙም ያልቀረኝን እኔንም እንዲሁ ተቀበለኝ፡፡ አንተ ወዳለህበት ሰማያዊ የክብር ቦታ ከመድረሴ (ከመምጣቴ) በፊትም በዚህ ዓለም ተቀበለኝ፡፡" (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ ትምህርት በእንተ ዕረፍተ አቡሁ፣ ቁ. 40)

- "በፊት ከእኛ ጋር በአካል በሕይወተ ሥጋ ሳለ ይነግረን ከነበረው ትእዛዛት በበለጠ አሁን ባለበት ሆኖ የሚያደርግልን የእርሱ ጸሎትና ምልጃ የበለጠ እንደሚጠቅመን እርግጠኛ ነኝ፡፡ ምክንያቱም እርሱ አሁን የበለጠ ወደ እግዚአብሔር ቀርቧልና፣ የሰውነቱን ድካምና ማሠሪያ አራግፏልና፣ ልቡናውንም ከሸፈነው ከሸክላ መዝገብ ነጻ አድርጓልና፣ ንጹሐ ባሕርይ ከሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ግልጽ በግልጽ ይነጋገራልና፣ አሁን ወደ መላእክት ደረጃ ከፍ ብሏልና፡፡" (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ ትምህርት በእንተ ዕረፍተ አቡሁ፣ ቁ. 40)

- "በእውነት ጻድቅ ሰው እንደ አንበሳ ጀግና ነው፤ አንበሳ በክፉ አውሬ ፊት ሳይፈራ ጸንቶ እንደሚቆም እርሱም [ኤልያስ] በንጉሡ ዘንድ በጥብዓት ቆሟልና፡፡ ንጉሡ [አክአብ] ልብሰ መንግሥት ቢለብስም ኤልያስ ደግሞ ከዚያ ይልቅ የከበረ ከበግ ጸጉር የተሠራ ፀጉፍ ነበረው፡፡ ያ ልብሰ መንግሥት ያመጣው ያን ጽኑ ረሀብ ነበር፤ ፀጉፉ ግን ከዚያ ረሀብ ነጻ መሆንን አመጣ! ያ ፀጉፍ የዮርዳኖስን ወንዝ ወዲያና ወዲህ ከሁለት ከፈለ! ኤልሳዕን ሁለት እጥፍ የሆነ ኤልያስ አደረገው! የቅዱሳን ትሩፋታቸው ምን ያህል ታላቅ ነው! ቃላቸው ብቻ ሳይሆን፣ ሰውነታቸው ብቻ ሳይሆን፣ ልብሳቸው እንኳ ሳይቀር በሥነ ፍጥረቱ ሁሉ በእጅጉ ይከበራል፡፡ የኤልያስ ከበግ ቆዳ የተሠራ መጎናጸፊያ ዮርዳኖስን ከፈለ! የሦስቱ ወጣቶች ነጠላ ጫማ እሳቱን ጠቀጠቀው! የኤልሳዕ ቃል ውኃውን ለወጠ፣ ብረቱንም በውኃው ላይ እንዲንሳፈፍ አደረገው! የሙሴ በትር የቀይ ባሕርን ከፈለ፣ ዓለቱንም መታ! የጳውሎስ ልብሶች ሕማማትን ያሳድዱ ነበር! የጴጥሮስ ጥላ ሞትን ያባርር ነበር! የሰማዕታት ዐጽሞችና የሰውነታቸው ቅሬት አጋንንትን ያሳድዳቸዋል! ኤልያስ እንዳደረገው ሁሉንም ነገር በሥልጣን ያደርጋሉ፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 18፣ ቁ. 3)

[123](And my present object is not so much to mingle lamentations with my praises, or to portray the public life of the man, or publish a picture of virtue common to all time, and an example salutary to all churches, and to all souls, which we may keep in view, as a living law, and so rightly direct our lives as to counsel you, who have been completely initiated into his doctrine, to fix your eyes upon him, as one who sees you and is seen by you, and thus to be perfected by the Spirit.)

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ስለ ሰማዕቱ ቅዱስ ቴዎዶሮስ ሲናገር ምልጃውን መለመን እንዲገባ በተደጋጋሚ ይናገራል፡፡ እንዲህም ብሏል፦

* "ቅሬተ ዐጽሙን (Relics) መንካት፣ ምናልባት ይህን ለማድረግ ዕድል የሚገጥመው ሰው ካለ፣ መታደል ነው፡፡ . . . ከዚያም በከበሩት በእነዚያ ቅሬተ አካሎቹ ላይ ለሰማዕቱ ለራሱ እንደሚያቀርቡ በማሰብ ከፍቅርና ከእምነት የሚወጡ ዕንባዎችን በማፍሰስ ይማልድላቸው ዘንድ ልመናቸውን ያቀርባሉ፡፡ እርሱ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ ያገኘ እንደ መሆኑ ገጸ ምሕረቱን ይመልስላቸው ዘንድ እንዲማልድላቸው ይማጸኑታል፡፡" (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ስለ ሰማዕቱ ቅዱስ ቴዎዶሮስ ካስተማረው ትምህርት)

ይኸው ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ በሌሎች ትምህርቶቹም ቅዱሳን ሰማዕታት ይረዱት ዘንድ ይማጸናል፡፡ እንዲሁም በጻፈው በቅዱስ ኤፍሬም ዜና ሕይወት ወደ መጨረሻው ላይ ቅዱሱን "እኛን ሁላችንንም አስበን፣ ስለ ኃጢአታችን ሥርየትን ለምንልን" በማለት ይማጸነዋል፡፡ እንዲሁም በከባድ አደጋ ጊዜ እርዳታውን ስለ ተማጸነ አንድ ሰውና ስላገኘው ውጤት ይናገራል፡፡

* ". . . ወአንተሰ ብእሲ መምህርነ አባ ገሪማ ጸሊ በእንቲአነ - . . . አባ ገሪማ ሆይ፣ አንተ መምህራችን ነህና ስለ እኛ ጸልይልን" (ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘአባ ገሪማ)

* " . . . ዳዊትኒ ይቤ እገኒ ለከ እግዚኦ በውስተ ማኅበር ዐቢይ ወእሴብሐከ በውስተ ሕዝብ ክቡድ ማኅበራኒክ ቅዱሳኒክ እለ እምዓለም አሥመሩከ እለ ጽሑፍ አስማቲሆሙ በሰማያት ይብጽሐነ ወትረ ጸሎቶሙ ለ፫፻ ፲ቱ ወ፰ ማኅበረ በኩር . . . - ዳዊትም በታላቅ ጉባኤ ውስጥ እገዛልሃለሁ፣ በክቡድ ሕዝብ ውስጥም አመሰግንሃለሁ ይላል፤ ከጥንት ጀምሮ ፈቃድህን የፈጸሙና ደስ ያሰኙህ ቅዱሳንህና ማኅበርህ፣ ስሞቻቸው በሰማያት የተጻፈ፣ የ318ቱ ማኅበረ በኩር ጸሎታቸው ሁል ጊዜ ይድረሰን፣ ይደረግልን" (ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘማኅበር)

* "አንተ አጽናዕኮሙ ለአድባር በኃይልከ ወቅኑታን እሙንቱ በኃይል ኅብስተ እምሰማይ ወሀቦሙ አድባረ ድኍኃን ይሰመይ ነፍሳቲሆሙ ለጻድቃን ኀ. አድባረ ድኍኃን ዘይቤ በእንተ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ ወኩሎሙ ቅዱሳን ኀ. መንክር እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ ኀ. ትብል ቤተ ክርስቲያን መዓዛሆሙ ለቅዱሳን ዘአንተ ወሀብከነ - ተራሮችን አንተ በኃይልህ አጸናሃቸው፣ በኃይልም ታጥቀዋል፣ ኅብስትን ከሰማይ ሰጣቸው፡፡ የጻድቃን ነፍሳት የቅመም ተራራዎች ይባላሉ፤ የቅመም ተራራዎች የሚለውም ስለ አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ ነው፡፡ እግዚአብሔር በቅዱሳን ላይ ድንቅ ነው፣ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳንን መዓዛቸውን አንተ ሰጠኸን ትላለች፡፡" (ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘያዕቆብ)

* "ኅብስተ እምሰማይ ወሀቦሙ ሃሌ ሉያ ለመላእክት ሚካኤል ሊቆሙ ሃሌ ሉያ ለሐዋርያት ጽጌ ምድሮሙ ኃረዮሙ ወጸውኦሙ ወባረኮሙ ይብጽሐነ ወትረ ጸሎቶሙ - ኅብስትን ከሰማይ ሰጣቸው፣ ሃሌ ሉያ፣ ለመላእክት ሚካኤል አለቃቸው ነው፣ ሃሌ ሉያ፣ ለሐዋርያት ጌታ መሠረታቸው ነው፡፡ እርሱ መረጣቸው፣ ጠራቸውም፣ ባረካቸውም፣ ጸሎታቸው ሁል ጊዜ ይድረሰን፡፡" (ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ ዘቅዱስ ሚካኤል)

- "ዮሐንስ ሰማዕት ሰባኪ መድኃኒት ጸሎትከ ትኩነነ ፀወነ እመንሱት - ሰማዕት የሆንክና መድኃኒትን የምትሰብክ ዮሐንስ ሆይ፣ ጸሎትህ ከፈተና መጠጊያና መዳኛ ትሁነን" (ቅዱስ ያሬድ፣ መዋሥዕት ዘቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ)

- "ሃሊ ሉያ ዮሐንስ ጸሊ በእንቲአነ እስመ ለዓለም ምሕረቱ - ሃሌ ሉያ፣ ዮሐንስ ስለ እኛ ጸልይ፣ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና፡፡" (ቅዱስ ያሬድ፣ መዋሥዕት ዘተክዚ)

- "ዓውደ ዓመት በጽሐ ለዘፍኖቶ ጼሐ ወንህነኒ ንሴፎ ከመ በጸሎቱ ንድኃን - የጌታን መንገድ የጠረገው የዮሐንስ መጥምቅ ዓውደ ዓመቱ ደረሰ፣ እኛም በጸሎቱ እንድን ዘንድ ተስፋ እናደርጋለን፡፡" (ቅዱስ ያሬድ፣ መዋሥዕት ዘዘካርያስ)

- "ኃላፊተ ምድረ ዘመነነ መድኃኒተ ነፍሱ ዘዴገነ እስጢፋኖስ ሰማዕት አስተምሀር በእንቲአነ - ኃላፊ የሆነውን ዓለም የናቅህ፣ የነፍስህን መድኃኒት የተከተልህ ሰማዕቱ እስጢፋኖስ ሆይ፣ ስለ እኛ ለምንልን፣ ማልድልን" (ቅዱስ ያሬድ፣ መዋሥዕት ዘቅዱስ እስጢፋኖስ)

- "መነነ ዘንተ ዓለመ አቅደመ ሰምዐ ክዊነ እስጢፋኖስ ጸሊ በእንቲአነ ጸሎትከ ወትረ ይብጽሐነ - ይህን ዓለም መነነ፣ ከሊሳው ሁሉ ቀድሞ ሰማዕት ሆነ፣ እስጢፋኖስ ስለ እኛ ጸልይ፣ ጸሎትህም ሁል ጊዜ ይድረሰን፡፡" (ቅዱስ ያሬድ፣ መዋሥዕት ዘቅዱስ እስጢፋኖስ)

- "እስጢፋኖስ ሰማዕት ዜናከ መድኃኒት ጸሎትከ ወትረ ትኩነነ ጸወነ እመንሱት - ሰማዕቱ እስጢፋኖስ ሆይ፣ ዜናህ መድኃኒት ነው፣ ጸሎትህ ሁል ጊዜ ከፈተና መጠጊያና መዳኛ ትሁነን፡፡" (ቅዱስ ያሬድ፣ መዋሥዕት ዘቅዱስ እስጢፋኖስ)

- "ብፁዕ አባ ዮሐኒ ብፁዕ አባ ዮሐኒ ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ ሣሕልከ ይኩን ላዕሌነ - ንዑድ ክቡር የሆንክ አባ ዮሐኒ ሆይ፣ ምሕረትህ በእኛ ላይ ይሆን ዘንድ ስለ እኛ ጸልይ፡፡" [ቅዱስ ያሬድ፣ መዋሥዕት ዘአባ ዮሐኒ (ምልጣን)]

- "ሚናስ ኅሩይ በታዕካ ሰማይ ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ - በሰማያዊ ማደሪያ የተመረጥክ ሚናስ ሆይ፣ ስለ እኛ ጸልይልን፣ ማልድልን" (ቅዱስ ያሬድ፣ መዋሥዕት ዘቅዱስ ሚናስ)

- "ሊባኖስ ክቡር ፍቁሩ ለልዑል ዘሰመየከ መልአከ ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ - የልዑል ወዳጁ የሆንክና ከፍ ከፍ ያደረገህ፣ መልአክ ብሎ የሰየመህ ክቡር ሊባኖስ ሆይ፣ ስለ እኛ ለምንልን፣ ጸልይልንም፡፡" (ቅዱስ ያሬድ፣ መዋሥዕት ዘቅዱስ አባ ሊባኖስ)

- "ጠለ ገዳም ረሰይከ ሲሳየከ አጋንንተ ተዘርው በጸሎትከ ዮም በምድር ተዝካርከ ይብጽሐነ ወትረ ጸሎትከ - ምግብህን የምድረ በዳ ጤዛ ያደረግህ፣ አጋንንት በጸሎትህ የተበታተኑ [አባ ሊባኖስ ሆይ]፣ ዛሬ በምድር መታሰቢያህ ነው፣ ጸሎትህ ሁል ጊዜ ይድረሰን" (ቅዱስ ያሬድ፣ መዋሥዕት ዘቅዱስ አባ ሊባኖስ)

- "ያድኅነነ እመዓቱ አመ ዳግም ምጽአቱ በጸሎቱ ለብፁዕ ሊባኖስ ብእሴ እግዚአብሔር - ንዑድና ክቡር በሆነው በእግዚአብሔር ሰው በሊባኖስ ጸሎት በዳግም ምጽአቱ ከቁጣው ያድነን፣ " (ቅዱስ ያሬድ፣ መዋሥዕት ዘቅዱስ አባ ሊባኖስ)

የሚላኑ ጳጳስ የነበረው ቅዱስ አምብሮስ ከእርሱ በፊት ጳጳስ የነበረውንና በቀጰዶቅያ በ374 ዓ. ም. በሰማዕትነት የሞተውን የቅዱስ ዲዮናስዮስን ዐጽም ይልክለት ዘንድ ይዘው ከሚመጡ ሰዎች ጋር ወደ ቅዱስ ባስልዮስ መልእክትን በላከለት ጊዜ ቅዱስ ባስልዮስ ዐጽሙን እንዲህ ከሚል መልእክት ጋር ላከለት፡-

❖ "ስለ ብፁዕ ጳጳስ ስለ ዲዮናስዮስ ባሳየኸው ጽኑ ቅንዓትና ፍቅር ያሳየኸውና ያስመሰከርከው ነገር ቢኖር ለጌታችንና ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ያለህን ታላቅ ፍቅር፣ ከአንተ በፊት ለነበሩት አባቶች ያለህን ክብርና ፍቅር እና ለእውነተኛዋ ሃይማኖት ያለህን ቅንዓት ነው፡፡ እግዚአብሔርን ላገለገሉ ወዳጆቹ የሚኖረን አመለካከትና ፍቅር እነርሱ ያገለገሉትን እግዚአብሔርን ማፍቀር ነውና፡፡ ስለ ሃይማኖት የተጋደሉ ሰዎችን የሚወዳቸው ሰው እርሱም እንደ እነርሱ ያለ መንፈስና ዓላማ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ . . . የላክሃቸው ልዑካንም ካህናቱና ዲያቆናቱ እንዲሁም ሌሎች ብዙ ምእመናን በተገኙበት የሰማዕቱን ዐጽም እጅግ ታላቅና ተገቢ በሆነ አክብሮት ከተቀበረበት ተቀበሏቸው፡፡ እነዚህን የከበሩ ዐጽሞች ከዚህ ወደ አንተ የላኳቸውና ሲለያቸው ያዘኑት ምእመናን ከተሰማቸውና ካዘኑበት ታላቅ ሐዘን ጋር ተመጣጣኝ በሆነ ደስታና ሐሜት ተቀበላቸው፡፡ አሁን አንተ ይኸውና ያ ድል አድራጊ ሰማዕት አለህ፣ እርሱ ወደ አንተ መጣልህ፡፡

"በተጋድሎው ጊዜ ከተባረከችው ነፍሱ ጋር አብረው የተሳተፉት እነዚህ ዐጽሞች በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቁ ናቸው፡፡ እነዚህን ዐጽሞች ከነፍሱ ጋር 'መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና' ተብሎ እንደ ተጻፈ እርሱ ለጻድቃን ዋጋቸውን ይሰጥ ዘንድ ባዘጋጀው እውነተኛ የፍርድ ቀን የክብር አክሊልን ያቀዳጃቸዋል፡፡ 2 ቆሮ. 5፥10 ለእርሱም ለሰማዕት ተገቢ የሆነ (የሚገባ) ክብር ተደርጎለታል፡፡ በዚያ ሰማዕትነትን በመቀበሉና በመቀበሩ ደስ ተሰኝተው የነበሩት ክርስቲያኖች አሁን ዐጽሙ ሲወሰድባቸው ግን አባቱን እንዳጣ ልጅ አዝነዋል፡፡ ሆኖም የአንተን ደስታ ከእነርሱ መጽናናት በፊት በማስቀደም የሰማዕቱን ዐጽም ወደ አንተ ልከውልሃል፡፡"

(ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ፣ መልእክት ኀበ ቅዱስ አምብሮስ፣ መልክእት 197፣ ቁ. 2)

## ማጠቃለያ

በዚህ ክፍል ውስጥ ብዙ ጉዳዮችን ተመልክተናል፡፡ ቅዱሳን ከሞታቸው (ዕረፍታቸው) በኋላ አዋቂዎች መሆናቸውንና በዚህ ዓለም ስለሚደረገው ነገር እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ መጠን እንደሚያውቁ፣ ቅዱሳን በዚህ ዓለም ሳሉም ሆነ ከዕረፍታቸው በኋላ እንደሚያማልዱ፣ የቅዱሳንን ስም መጥራት ተሐድሶዎች እንደሚሉት የተከለከለ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ እነ ሙሴ፣ እነ ኤልያስ፣ እንዲሁም ራሱ ጌታችን በትምህርቱ ያደረገውና ያሳየን መሆኑን ተመልክተናል፡፡

እንዲሁም የቅዱሳንን አማላጅነት አግባብነት ከእግዚአብሔር መሐሪነትና ሁሉን አዋቂነት አንጻር ለምን እንደሚያስፈልግ አይተናል፡፡ እነዚህንና መሰል ጉዳዮችን በመጽሐፍ ቅዱስና በቀደምት አበው ሊቃውንት ትምህርት ብዙ ምስክሮችን ጠቅሰን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ትክክለኛና እውነተኛ መሆኑን በበቂ ሁኔታ አሳይተናል፡፡ በአንጻሩ ተሐድሶዎች በእነዚህ ነጥቦች ላይና ዙሪያ ያቀረቧቸው ተቃውሞዎች፣ የማስመሰያና የማደናገሪያ አባባሎች ደግሞ ሁሉም ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ትምህርት በተቃራኒ የቆሙ ስህተቶች መሆናቸውን በስፋት ተመልክተናል፡፡

# 6.4 ቤተ ክርስቲያንን በቅዱሳን ስም መለየምና መጥራት

## 6.4.1 የተሐድሶዎች ትምህርት

የተሐድሶዎች ተቃውሞ በዚህ ትምህርት ላይ የሚከተለውን ነው፡-

- "ለሞቱ ቅዱሳን በመታሰቢያ ስም ብዙ ነገሮች እንደ ተከሄዱና እየተከሄዱ እንዳለ ሁሉም ያውቀዋል፡፡ ለዚህ እንግዳ ትምህርት ድጋፍ ይሆን ዘንድ የሚጠቀሰው ኢሳ. 56፡4-5 የተነገረው ስለ መጻተኞችና ስለ ጃንደረቦች መሆኑን በቅድሚያ ማወቁ ለሌላ ከመስጠትና በእውነት ስም ቆሞ ሐሰትን ከመናገር ያድናል፡፡ መጻተኛ ማለት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ አገሬ የሚለውን ምድር ትቶ በምድረ እስራኤል የሚኖር፣ እስራኤላዊ ዝርያ የሌለው የሌላ አገር ተወላጅ ሲሆን ጃንደረባ ደግሞ ጾታ መለያ አካሉ የተቆረጠበት ወይም የተኀዳበት እስራኤላዊ ወይም የእስራኤላዊነት መብት የተሰጠው ማለት ነው፡፡ ጃንደረባ ሲሳም ሁለተኛ ፍቺ እንዳለው ይታወቃል፤ ይኸውም ከፍ ባለ ማዕረግ የሚገኝ ጠባቂ ማለት ነው፡፡ በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ግን በመጀመሪያው ትርጉም የሚገኘውን ጃንደረባ ነው፡፡ . . .
- "ደግሞም <u>በመጻተኞችና በጃንደረቦች ላይ ተደርጎ የነበረው ሕግ የሚሠራው በዚያው በብሉይ ኪዳን ዘመን ብቻ እንጂ በአዲስ ኪዳን እንዳልሆነ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል</u>፡፡ እግዚአብሔር "ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ይባላል" (ኢሳ፣ 56፡7) ባለው መሠረት ምንም ዓይነት ዘር፣ የቀለምና የአካል ልዩነት ሳይደረግ አይሁዳውያንና አረማውያን በሙሉ የክርስቶስ አካል በሆነችው አንዲት ቤተ ክርስቲያን በማጠቃለል በፊት የነበረውን ልዩነት ጨርሶ ደምስሷል፡፡ . . . ቃሉን በትክክል አንብበው ሳያጤኑ ለመናገር የሚቸኩሉና የእግዚአብሔርን ቃል በትክክለኛው መንገድ ሳይሆን ለግል አመለካከታቸው ድጋፊ እንዲሆን የሚጠቅሱት ወገኖች ይህ የኢሳ. 56 ክፍል ለቅዱሳን በስማቸው የተለያዩ መታሰቢያዎችን እድናደርግላቸው የሚናገር ነው ሲሉ ጥቂት እንኳን ቅር አይላቸውም፡፡ ቃሉ የሚናገርላቸውን ክፍሎች ይዘን በእርሱ አተረጓጎም እንሂድ ቢባል እንኳ ከቃሉ አንጻር እስራኤላዊ ዝርያ ያላቸው ቅዱሳን ለምሳሌ ድንግል ማርያም፣ ቅ/ጳውሎስና ቅ/ጴጥሮስ በዚህ ውስጥ ተሳታፊነት አይኖራቸውም፡፡ እነርሱ መጻተኞች ወይም ጃንደረቦች አይደሉምና፡፡" (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 127-130)

### የተሐድሶዎች ዋና ዋና ስህተቶች

1) ለንደኛ ለመጻተኛ የሰጡት ትርጉም ከፊሉን ይዞ ከፊሉን ግን የዘነጋ ወይም የተወ መሆኑ ነው፡፡ እንዲህ ብለዋልና፡- <u>"መጻተኛ ማለት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ አገሬ የሚለውን ምድር ትቶ በምድረ እስራኤል የሚኖር፣ እስራኤላዊ ዝርያ የሌለው የሌላ አገር ተወላጅ ነው</u>፡፡"

በመጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ "መጻተኛ" የተባሉት እነማን እንደሆኑ እንመልከት፡፡ አንደኛውን ትርጉም እነርሱም የተቀበሉት ስለሆነ ያንን እንደግመውም፡፡ እነርሱ የዘነጉትን የሚመለከተውን ብቻ እንመልከት፡፡

#### መጻተኛን በተመለከተ

- "አቤቱ፣ ጸሎቴን ስማ፣ ጩኸቴንም አድምጥ፣ ልቅሶዬንም ቸል አትበለኝ፤ <u>እኔ በምድር ላይ መጻተኛ ነኝና</u>፥ <u>እንደ አባቶችም እንግዳ ነኝና</u>።" መዝ. 38፡12-13
- "እግዚአብሔርም ዘሩ በሌላ አገር <u>መጻተኞች</u> እንዲሆኑ አራት መቶ ዓመትም ባሪያዎች እንዲያደርጓቸው እንዲያስጨንቋቸውም እንዲህ ተናገረ፤ <u>ሙሴም ከዚህ ነገር የተነሣ ሸሽቶ በምድያም አገር መጻተኛ ሆኖ ኖረ</u>፤ በዚያም ሁለት ልጆች ወለደ፡፡" የሐዋ፣ 7፡6፣ 29

- "ለእንግዶች እንደሚሆን በተስፋ ቃል በተሰጠው አገር በድንኳን ኖር፣ ያን የተስፋ ቃል አብረውት ከሚወርሱ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር እንደ መጻተኛ በእምነት ተቀመጠ፤ እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ፣ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አላገኙምና፤ ዳሩ ግን ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት፥ በምድሪቱም እንግዶችና መጻተኞች እንዲሆኑ ታመኑ" ዕብ. 11፥9፤13
- "የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ጴጥሮስ፣ እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው በመንፈስም እንደሚቀደሱ፣ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ ለተመረጡት፣ በጳንጦስና በገላትያ በቀጰዶቅያም በእስያም በቢታንያም ለተበተኑ መጻተኞች፤ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።" 1 ጴጥ. 1፥1-2
- "ወዳጆች ሆይ፣ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት ትርቁ ዘንድ እንግዶችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ እለምናችኋለሁ" 1 ጴጥ. 2፥11

በመጽሐፍ ቅዱስ እነ ዳዊት፣ እነ አብርሃም፣ እነ ሙሴ፣ እነ ያዕቆብና የክርስቶስን መገለጥ በእምነትና በተስፋ እየጠበቁ የኖሩት አባቶች ሁሉ "መጻተኛ" ተብለዋል፡፡ እነዚህ አባቶቻችን ምድራዊ ኑሯቸውንና ያላቸውን ነገር ሁሉ ንቀው የበለጠውን ሰማያዊ ጸጋና ሕይወት ይናፍቁና ይጠብቁ ስለ ነበር "መጻተኞች" ተብለዋል፡፡ ዳዊት ንጉሥ ነበር፤ ሆኖም ግን አኗኗሩ ሰማያዊውን ነገር በመናፈቅ ስለ ነበር ራሱን "እኔ በምድር ላይ መጻተኛ ነኝና፣ እንደ አባቶችም እንግዳ ነኝና" አለ፡፡ ታዲያ ዳዊት ተሐድሶዎች "መጻተኛ ማለት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ አገሬ የሚለውን ምድር ትቶ በምድረ እስራኤል የሚኖር፣ እስራኤላዊ ዝርያ የሌለው የሌላ አገር ተወላጅ ነው" ያሉትን ትርጉም ያሟላል? እነ አብርሃም፣ ያዕቆብ፣ ሙሴ፣ ዳዊት መጻተኛ የተባሉትስ እስራኤላዊ ዝርያ የሌላቸው ስለሆኑ ነበርን?

ሲጀመር እስራኤላውያን "እስራኤላውያን" የተባሉት እግዚአብሔር ያዕቆብን "ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል" ካለው ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ታዲያ ራሱ ያዕቆብ እስራኤላዊ ካልሆነ እስራኤላዊ ዝርያ ያለው ማን ነበር? ዘፍ. 32፥28 ይህ የተሐድሶዎች አተረጓጎምስ ከላይ ያየናቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይገልጻል? መጻተኛ የተባሉት እነ አብርሃም፣ እነ ሙሴ፣ እነ ዳዊት እስራኤላዊ ዝርያ የሌላቸው ነበሩ?

እንዲሁም ደግሞ መጻተኛ የሚባለው "አገሬ የሚለውን ምድር ትቶ በምድረ እስራኤል የኖረ" ያሉትስ ሙሴን ይገልጸዋል? ምክንያቱም ሙሴ ምድረ እስራኤልን ሊኖርባት ቀርቶ ለአንድ ጊዜም እንኳ በሕይወት ዘመኑ አልረገጣትም፡፡ ይልቁንም ይህ የተሐድሶዎች አተረጓጎም ለእነ ሙሴ የሚሠራው በተቃራኒው ነው፡፡

እንደዚሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ክርስቲያኖችን "መጻተኞች" ብሏቸዋል፡፡ ታዲያ እነዚያ ክርስቲያኖች በሙሉ እስራኤላውያንና በእስራኤል ምድር ብቻ የሚኖሩ ነበሩን? "በጳንጦስና በገላትያ በቀጰዶቅያም በእስያም በቢታንያም ለተበተኑ መጻተኞች" አለ እንጂ በምድረ እስራኤል ለሚኖሩ አላለም! ጳንጦስ፣ ገላትያ ቀጰዶቅያ እና እስያ ደግሞ በእስራኤል ምድር ውስጥ ሳይሆኑ በዚያን ጊዜዋ ታናሽ እስያ (የዛሬዋ ቱርክና አካባቢዋ) ውስጥ ነበሩ፡፡ እነዚህ ቦታዎች በታሪክ የእስራኤል ግዛት ሆነውም አያውቁም፡፡

ተሐድሶዎች ለፈጠሩት እንግዳ ትምህርት እንዲመች ለማድረግ ሲሉ ይህን ያህል መዋሸት ምን ይጠቅማቸው ይሆን? እንዲህ እንደምናየው ለሐሰት ትምህርታቸው መነሻቸውም ሆነ ምንጫቸው የራሳቸው ፈጠራ ብቻ ነው፡፡

2) ሁለተኛ ለጃንደረባ የሰጡት ትርጉምም መሠረታዊ የሆነውን ነጥብ እንደሌለ አስመስለውና ለማታለል በሚያመቻቸው መልኩ ሸፍነው ነው፡፡ እንዲህ ይላሉና፡-

◉ "ጃንደረባ ደግሞ ጾታ መለያ አካሉ የተቆረጠበት ወይም የተኰላበት እስራኤላዊ ወይም የእስራኤላዊነት መብት የተሰጠው ማለት ነው፡፡"

## መጽሐፍ ቅዱስ ጃንደረባን በተመለከተ ምን ይላል?

በመጽሐፍ ቅዱስ አገባብ ጃንደረባ አራት ነገሮችን ሊገልጽ ይችላል፡፡ እነዚህም ሦስቱ በማቴዎስ ወንጌል የተገለጹት ሲሆን አራተኛው ደግሞ ጃንደረባ ሲባል ባለ ሥልጣን ማለትም ነው፡፡ ለምሳሌም ዮሴፍን በቤቱ ያገለግለው ዘንድ የገዛው የግብጽ ንጉሥ የፈርዖን የዘበኞቹ አለቃ የነበረው ጲጥፋራ ሚስት የነበረችው ሲሆን "ጃንደረባ" ተብሎ ተገልጿል፡፡ ዘፍ. 39፥1-7 ጌታችን ባረገበት ዓመት የኢትዮጵያ ንግሥት የነበረችው የህንደኬ የገንዘብ አዛዥና በጅሮንድም እንዲሁ ጃንደረባ ተብሎ ተገልጾ እናገኛለን፡፡ የሐዋ. 8፥27 አሁን ወደ ዋናው ጉዳዮቻችን እንሂድ፤ ይህን እነርሱም አልካዱምና፡፡

ተሐድሶዎች የካዱት መሠረታዊ ነጥብ ጌታችን ባስተማረውና በማቴዎስ ወንጌል ላይ ተመዝግቦ በምናገኘው ትምህርት ላይ ጃንደረባነትን በተመለከተ የተናገረውን ሦስተኛውን ነጥብ ነው፡፡ ቃሉ እንዲህ ይላል፡-

❖ "በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፣ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፣ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ። ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው አላቸው።" ማቴ. 19፥11-12

አሁን ይህን የጌታችንን ትምህርት ከተሐድሶዎች ትምህርት ጋር እናነጻጽረው፡፡ ተሐድሶዎች ጃንደረባን የተረጎሙት እንዲህ ብለው ነው፡- "ጃንደረባ ማለት ደግሞ የጾታ መለያ አካሉ የተቆረጠበት ወይም የተኰላበት እስራኤላዊ ወይም የእስራኤላዊነት መብት የተሰጠው ማለት ነው፡፡"

የዘነጉትን ወይም ሆን ብለው የዘለሉትን ዋና ጉዳይ ልብ አልን? ይኸውም "ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ። ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው አላቸው" ብሎ ያስተማረውን ትምህርት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ጃንደረባነት ተሐድሶዎቹ እንዳሉት "የጾታ መለያ አካሉ የተቆረጠበት ወይም የተኰላበት እስራኤላዊ ወይም የእስራኤላዊነት መብት የተሰጠው ማለት ነው" ከሚለው ጋር ፈጽሞ የሚገናኝ አይደለም፡፡ ጌታችን ከእናታቸው ማኅፀንም ይሁን ከተወለዱ በኋላ ብቻ በምንም ይሁን በምን የጾታ አካላቸው ስለ ተኰላባቸው ጃንደረቦች በመጀመሪያው በሁለቱ ዓይነት ጃንደረባነት ከተናገረ በኋላ ሦስተኛው ዓይነት ጃንደረባነት ግን ከጾታ አካል መኰላት ጋር የተገናኘ ሳይሆን በፈቃድ የሚደረግ ጃንደረባነት መሆኑን ተናገረ፡፡ ይኸውም "ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ" በማለት ነው፡፡ ይህም ማለት ተፈጥሯዊ የሆነው የጾታ አካላቸው እያለ ነገር ግን ስለሚበልጠው ነገር ሲሉ፣ ስለ መንግሥተ ሰማያት ሲሉ፣ በፈቃዳቸው ማግባትንና መጋባትን ስለሚተውትና ራሳቸውን እውነተኛ የክርስቶስ ሙሽሮች አድርገው ስለሚያቀርቡ በድንግልና ለመኖር ለሚወስኑና በዚህ ሕይወት ፈጣሪያቸውን ለሚያገለግሉ ሰዎች ነው፡፡ ይህ በማንም ሰው ላይ በግዴታ የሚጫን ሳይሆን ከራስ የውስጥ ፍላጎት ብቻ ሊመጣ የሚገባና በእግዚአብሔር ቸርነት ይህን መርጠው ለሚገቡበት ብቻ እንደሆነ ሲያስተምረንም "ይህ ነገር ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም፤ . . . ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው አላቸው" ይላል።

ስለዚህ ወገኖቻችን ተሐድሶዎች ስለ ጃንደረባ የሰጡት ትርጉም ዋናውንና መሠረታዊውን ጉዳይ የዘለለ ነው፡፡ በዚህም ላይ ጃንደረባ ማለት "እስራኤላዊ ወይም የእስራኤላዊነት መብት የተሰጠው ማለት ነው" በማለት የግድ በጉልበት ከእስራኤላዊነት ጋር ሊያስተሳስሩት ተጣጥረዋል፤ ሆኖም ይህም ሐሰት ነው፡፡ ራሳቸውን በፈቃዳቸው ስለ መንግሥተ ሰማያት ሲሉ ጃንደረቦች ያደረጉትና የሚያደርጉት በትውልድ እስራኤላውያን የሆኑ ወይም ደግሞ የእስራኤላዊነት መብት የተጣቸው ብቻ አይደሉም፡፡ ይህም ሌላው ስህተት ነው፡፡

በመሆኑም ስለ ጃንደረባ የሰጡት ትርጉም ሆን ብሎ ስለ መንግሥተ ሰማያት ሲሉ ራሳቸውን ጃንደረቦች ያደረጉና ማግባትን ንቀው ሳይሆን ጋብቻን እያከበሩ ግን ለበለጠው ነገር ሲሉ በእግዚአብሔር ቸርነት የዚህን ዓለም ሁኔታ የታገሡትን የደናግልና የመነኰሳትን ነገር ከጨዋታ ውጭ ለማድረግ እንዲመቻቸው ነበር፡፡ ከምንኩስና ሕይወትና ከመነኰሳት ጋር ይህን ያህል ጠብና ጦርነት ማድረግ ምን ይጠቅማችኋል? ምንስ አደረጓችሁ?

3) ሦስተኛው ደግሞ እንዲህ ያሉት ነው፦ "<u>በመጻተኞችና በጃንደረቦች ላይ ተደርጎ የነበረው ሕግ የሚሠራው በዚያው በብሉይ ኪዳን ዘመን ብቻ እንጂ በአዲስ ኪዳን እንዳልሆነ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል</u>፡፡ እግዚአብሔር "ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ይባላል" (ኢሳ፡ 56፥7) ባለው መሠረት ምንም ዓይነት ዘር፣ የቀለምና የአካል ልዩነት ሳይደረግ አይሁዳውያንና አረማውያን በሙሉ የክርስቶስ አካል በሆነችው አንዲት ቤተ ክርስቲያን በማጠቃለል በፊት የነበረውን ልዩነት ጨርሶ ደምስሷል፡፡"

እግዚአብሔር "ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ይባላል" ያለው ትንቢት የተፈጸመው በብሉይ ኪዳን ሳይሆን በሐዲስ ኪዳን መሆኑን መናገራቸው ጥሩ ነበር፡፡ ግን ምን ይሆናል፤ ይህን የተናገሩበት መነሻውና መድረሻው ከዚህ ሃሳብ ጋር የማይሄድ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ይህን ያሉበት ከመነሻው ላይ ለተናገሩት ሐሰት ማዋዋጫና ማረሳሻ ለማድረግ መሆኑ ነው፡፡ ምክንያቱም አንደኛ ከላይ እንዳየነው ለመጻተኛና ለጃንደረባ የሰጡት ትርጉም የተሳሳተ በመሆኑ በዚያ ከተሳሳተ መነሻ ላይ ተንደርድራችሁ የደረሳችሁበት ወይም የዚያ መደምደሚያ አስመስላችሁ ለማቅረብ የሞከራችሁት ነገር ስህተት በመሆኑ ነው፡፡ የመነሻዎቹ ሃሳቦች ስህተቶችና ውሸቶች ስለሆኑ መደምደሚያቸውም ማለትም "በመጻተኞችና በጃንደረቦች ላይ ተደርጎ የነበረው ሕግ የሚሠራው በዚያው በብሉይ ኪዳን ዘመን ብቻ እንጂ በአዲስ ኪዳን እንዳልሆነ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል" ያሉየሚለው ነው፡፡ ይህም ስህተት ነው፡፡

በዚያውም ላይ ደግሞ መጻተኞች ተብለው የተነገሩት በአጠቃላይ የዚህን ዓለም ሕይወት ጊዜያዊነትና አላፊነት ተረድተው ሰማያዊውን ሕይወት ተስፋ እያደረጉ በዚህ ዓለም ሲኖሩ እንግዶችና መጻተኞች ሆነው የሚኖሩ ክርስቲያኖች ሁሉ ናቸው እንጂ በብሉይ ኪዳን ከሌላ አገር ወደ እስራኤል ምድር መጥተው በጥገኝነት ይኖሩ የነበሩት ብቻ አይደሉም፡፡ ይህ ኋለኛው ዓይነት ብቻ ቢሆን ኖሮ አዎ አልፎል ሊያሰኝ ይችል ነበር፡፡ ግን መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን እነ ዳዊትን፣ እነ አብርሃምን፣ እነ ሙሴን፣ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ክርስቲያኖች በሙሉ መጻተኞች ይላቸዋል፡፡ እንደዚሁም ጃንደረቦች የተባሉትም ከጾታ አካል ጋር በተገናኘ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ራስን ስለ መንግሥተ ሰማያት ሲሉ በፈቃድ በድንግልና የሚኖሩ ደናግል መነኰሳትም ናቸው፡፡ ስለዚህ "<u>በመጻተኞችና በጃንደረቦች ላይ ተደርጎ የነበረው ሕግ የሚሠራው በዚያው በብሉይ ኪዳን ዘመን ብቻ እንጂ በአዲስ ኪዳን እንዳልሆነ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል</u>" ያሉት ሃሳብ ታላቅ ስህተትና ሐሰት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

4) አራተኛው ደግሞ በእነዚሁ እነርሱው ለራሳቸው ዓላማ እንዲመቻቸው አድርገው ባውሸለሸሏቸው መነሻዎቻቸው መሠረት እንዲህ ብለዋል፦ "ቃሉ የሚናገርላቸውን ክፍሎች ይዘን ·በእነርሱ ኢተረጓጎም እንሂድ ቢባል እንኳ ከቃሉ አንጻር <u>እስራኤላዊ ዝርያ ያላቸው ቅዱሳን ለምሳሌ ድንግል ማርያም፣ ቅ/ጳውሎስና ቅ/ጴጥሮስ በዚህ ውስጥ ተሳታፊነት አይኖራቸውም፡፡ እነርሱ መጻተኞች ወይም ጃንደረቦች አይደሉምና</u>፡፡"

መጻተኛና ጃንደረባ ለሚለው የሰጡት የተሳሳተ ትርጉም ወደዚህ የተሳሳተ ድምዳሜ አደረሳቸው፡፡ ስለ መጻተኛና ጃንደረባ ለሚለው የሰጡት የተሳሳተ ትርጉም ወደዚህ... መጻተኞችና ጃንደረቦች በመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠው ትርጉም እነርሱ እንዳሉት ስላልሆነ ይህ የእነርሱ የተሳሳተ መደምደሚያ እንዳችም መሠረት የለውም፡፡ "ነየ አመቱ ለእግዚአብሔር - የእግዚአብሔር አገልጋይ እነሆኝ" ብላ ራሷን ለእግዚአብሔር የሰጠች ቅድስት ቅዱሳን ንጽሕተ ንጹሐን ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም፣ እነ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስም እንዲሁ መጻተኞችና ጃንደረቦች በሚለው አይካተቱም ማለት እያሳዘነ የሚያስቅ ነው! ምእመናንን "እንግዶችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ" እያለ የጻፈላቸው ቅዱስ ጴጥሮስ፣ "ላላገቡና ለመበለቶች ግን እላለሁ። እንደ እኔ ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው" እያለ ያስተማረ ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ውስጥ አይካተቱም ማለትን ምን እንበለው? 1 ቆሮ. 1፥7 በእውነት ልብ ይስጣችሁ!

ይህን ለማጠቃለል ተሐድሶዎች እንዲህ ያሉትን እናስታውስ፦

- "ቃሉን በትክክል አንብበው ሳያጤኑ ለመናገር የሚቸኩሉና የእግዚአብሔርን ቃል በትክክለኛው መንገድ ሳይሆን ለግል አመለካከታቸው ደጋፊ እንዲሆን የሚጠቅሱት ወገኖች ይህ የኢሳ. 56 ክፍል ለቅዱሳን በስማቸው የተለያዩ መታሰቢያዎችን እድናደርግላቸው የሚናገር ነው ሲሉ ጥቂት እንኳን ቅር አይላቸውም፡፡"

በሰውነታችሁ ወንድሞቻችን የሆናችሁ ተሐድሶዎች ሆይ፣ እስኪ ስለ እውነት፣ ይህ ራሳችሁ የተናገራችሁት አባባል የሚስማማው ለእኛ ነው ወይስ ለእናንተ? የራሳችን አመለካከት ደጋፊ ለማድረግ ስንል ስለ መጻተኛና ስለ ጃንደረባ ያልሆነ ትርጉም የሰጠነው፣ የማይመች የመሰለንን እየተውንና እየዘለልን የምትመቸንን የጠቀስነው፣ ከተሳሳተ መነሻ ላይ ተነሥተን ካልሆነ መደምደሚያ ላይ የደረስነው እኛ ነን ወይስ እናንተ? እንደዚሁም "በቃላት መዋጋትንና ክርክርን እንደ በሽተኛ የሚናፍቁት የዚህ አዲስ ትምህርት አራማጆች መሠረታዊ የሆነ ስህተታቸውን ትክክል ለማስመሰል የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ሽፋን መጠቀማቸው በአንዳንድ መድረኮች ይደመጣል" (የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 48) ያላችሁትስ የሚስማማው ለእኛ ነው ወይስ ለእናንተ? አንብበን ሳናጤን ለመናገር የምንቸኩለውስ እኛ ወይስ እናንተ? ይህን እናንተም፣ አንባቢም ይፍረድ፡፡

## 6.4.2 ቤተ ክርስቲያንን በቅዱሳን ስም መሰየምና መጥራት

## በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ጥንት የት መጣው ከዕብራይስጡ "ካሃል" ከሚለው እና ከግሪኩ "ኤክሌሲያ" ከሚለው ሲሆን ትርጉሙም "የእግዚአብሔር ጉባኤ" ማለት ነው፡፡ በመሠረታዊ አጠራር ቤተ ክርስቲያን ሲባል የምትታሰበው እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ የመሠረታት አንዲት የአማንያን (የምእመናን) ኅብረት (ጉባኤ) ናት፡፡ ስለዚህም በሐዲስ ኪዳን በተደጋጋሚ "የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን" ተብላ ተጠርታለች፡፡

ቤተ ክርስቲያን የምትባለው በመሠረታዊነት በቅድስት ሥላሴ እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒትነት አምነው በክርስቶስ ራስነት ያሉ አካላት ናቸው፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ረቂቅ የክርስቶስ አካል (Mystic Body of Christ) ናት፡፡ቤተ ክርስቲያን ስንል በዋናነት የምናስበውም ይህችን የክርስቶስ መንፈሳዊት አካል ነው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ከዚህም በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ምእመናን ለአምልኮ በአንድነት የሚሰበሰቡበትንና ይህ አንድነታቸው የሚገለጥባትን፣ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበትንና ለመዳናችን ወሳኝ የሆኑ ምሥጢራት የሚፈጸሙባትን ለዚህ የተለየና የተዘጋጀ ቦታ - ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንንም ያመለክታል፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ጉባኤ፣ የክርስቶስ አካል መሆኗ የታወቀ ነው፡፡ እንዲሁም እርሱ የሚመለክበትና ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚፈጸሙበት የተቀደሰ ስፍራም የተቀደሰ ነው፡፡ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ የተነገረ ነገር ነው፡፡ ለአብነትም "ቤተ መቅደስህ ቅዱስ ነው፣ በጽድቅም ድንቅ ነው"፣ እንዲሁም "ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ" ተብሏል፡፡ መዝ. 64፡5 መዝ. 137፡2 እንዲሁም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ መቅደሱ ይሸጡና ይለውጡ የነበሩትን ከዚያ በማባረር ከመቅደሱ አስወጥቷቸዋል፡፡ በመቀጠልም "የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት" ብሏቸዋል፡፡ ዮሐ. 2፡14-17 ስለዚህ የእግዚአብሔር ስም የሚጠራበት አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጸምበት ሕንፃ ቤተ መቅደስ የእግዚአብሔር ቤት እንደሚባል ራሱ ባለቤቱ ጌታችን አስተምሮናል፡፡

ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሚመለክበት የተለየ (የተቀደሰ) ስፍራ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን የነበረው የአምልኮ ስፍራ እስከ ባቢሎን ምርኮ ድረስ በኢየሩሳሌም የነበረው አንድ ቤተ መቅደስ ብቻ የነበረ ሲሆን ከዚያ በኋላ ግን እስራኤላውያን በየሀገሩ ተበታትነው በዝርወት ይኖሩ ስለ ነበር ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚያነቡበትና የሚማሩበት፣ ከመሥዋዕተ ኦሪት በስተቀር ያለውን ሌላውን አምልኮ የሚፈጽሙበት ምኩራብ (ሲናጎግ) የሚባል አዲስ ነገር አመጡ፡፡

የብሉይ ኪዳኑ የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ የሚመለክበት እግዚአብሔር መሆኑ የታወቀ ሲሆን ሲጠራ ግን በሠራው በንጉሥ ሰሎሞን ስም "የሰሎሞን ቤተ መቅደስ" እየተባለም ይጠራ ነበር፡፡ የቤተ መቅደሱ ደጅም እንዲሁ በንጉሥ ሰሎሞን ስም ይጠራ ነበር፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ላይ፣ እንዲሁም በሐዋርያት ሥራ ላይ እንዲህ ተብሎ ተገልጾ እናገኛለንና፡- "ኢየሱስም በመቅደስ በሰሎሞን ደጅ መመላለሻ ይመላለስ ነበር።" ዮሐ. 10፡23 የሐዋ. 3፡11 እንዲሁም "በኢየሩሳሌም ያለው መቅደስ" እየተባለም ይጠራ ነበር፡፡ መዝ. 67፡29 ዕዝ. 5፡15

ምኩራቦቹ ግን እንደ ቤተ መቅደሱ በኢየሩሳሊም የተወሰኑ ሳይሆኑ በየቦታው የተስፋፉና በቁጥርም ብዙ ስለነበሩ አንዳቸው ከሌላቸው ተለይተው የሚታወቁበት ስያሜ አስፈለጋቸው፡፡ በመሆኑም አንዳንዶቹ ምኩራቦች የተለየ የመጠሪያ ስም ነበራቸው፡፡ ለምሳሌም በኢየሩሳሊም ከነበሩት ምኩራቦች አንዱ "የነፃ ወጪዎች ምኩራብ" ተብሎ ይጠራ ነበር፡፡ የሐዋ. 6፡9

ክርስትናም በዓለም እየተስፋፋ ሲሄድ የእግዚአብሔር ጉባኤ እየሰፋ፣ አብያተ ክርስቲያናትም በየቦታው እየታነጹ ሲሄዱ አንዱ ከሌላው ተለይተው የሚታወቁበት መጠሪያ አስፈላጊ ሆኖ የመገኘቱን ነገር መረዳት አእምሮ ላለው ሰው ሁሉ የተሰወረ ነገር ሊሆን አይችልም፡፡ ይህችን የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ሲጠሩና እርሷን በተመለከተ ሲናገሩ ቅዱሳን ሐዋርያት አንዳንድ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ባለችበት በቦታው፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በዋናነት ቤታቸውንና ሕይወታቸውን ለቤተ ክርስቲያን በሰጡ በምእመናን ስም ይጠሯት ነበር፡፡

ለአብነትም የሚከተሉትን እንመልከት፡-

1) *ቤተ ክርስቲያንን ባለችበት ቦታ ሲጠሯት፡-*

- "የእስያ አብያተ ክርስቲያናት ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።" 1 ቆሮ. 16፡19
- "በክንክራኦስ ባለች ቤተ ክርስቲያን . . . በክርስቶስ ኢየሱስ አብረውኝ ለሚሠሩ ለጵርስቅላና ለአቂላ ሰላምታ አቅርቡልኝ . . ." ሮሜ 16፡1-5
- "ጳውሎስና ስልዋኖስ ጢሞቴዎስም፥ በእግዚአብሔር አብ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም ወደምትሆን ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን . . ." 1 ተሰ. 1፡1
- "ከእናንተ ጋር ተመርጣ በባቢሎን ያለች ቤተ ክርስቲያን፥ ልጄም ማርቆስ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።" 1 ጴጥ. 5፡13

2) *ራሳቸውን ለቤተ ክርስቲያን በሰጡ ክርስቲያኖች ሲጠሯት*

- "በሎዶቅያ ላሉቱ ወንድሞችና ለንምፉን በቤቱም ላለች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልን።" ቆላ. 4፡15
- "አቂላና ጵርስቅላ በቤታቸው ካለች ቤተ ክርስቲያን ጋር በጌታ እጅግ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።" 1 ቆሮ. 16፡19
- ". . . በክርስቶስ ኢየሱስ አብረውኝ ለሚሠሩ ለጵርስቅላና ለአቂላ ሰላምታ አቅርቡልኝ፤ . . . በቤታቸውም ላለች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልኝ።" ሮሜ 16፡1-5
- "ለእኅታችንም ለአፍብያ፥ ከእኛም ጋር አብሮ ወታደር ለሆነ ለአርክጳ፥ በቤትህም ላለች ቤተ ክርስቲያን . . ." ፊል. 1፡2

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት ስትሆን በውስጧ የሚመሰገነው እግዚአብሔር፥ የሚሠዋው መሥዋዕት ደግሞ በቀራንዮ የተፈተተው የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙ ነው፡፡ ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን ባለችበት ቦታም ሆነ ራሳቸውን ለቤተ ክርስቲያን በሰጡ ሰዎች ስም ብትጠራ በእምልኮቷና በመሥዋዕቷ ላይ አንዳችም የሚለውጠው ነገር የለም፡፡ "የተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን" ወይም "በባቢሎን ያለች ቤተ ክርስቲያን" ተብላ መጠራቷ ከክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንነት ያገዳት ወይም ያወጣት አንዳችም ነገር የለም፡፡ በተሰሎንቄ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ሌላ፥ በባቢሎን ያለችው ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሌላ አይደለም፤ ሁሉም ተለይተው ይታወቁ ዘንድ ባሉበት ቦታ ተጠሩበት እንጂ የአንድ የክርስቶስ አካላት የሆኑ ክርስቲያኖች ምሥጢራት ቤተ ክርስቲያንን የሚፈጽሙባቸው ናቸው፡፡

ከዚህም የተነሣ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ባከበራቸው በቅዱሳን ስም ይሰየማል፥ ይጠራል፡፡ በየቦታው የታነፁና የሚታነፁ አብያተ ክርስቲያናት በቅዱሳን ስም ካልተጠሩ በማን ስም ይጠሩ? እንደ ፕሮቴስታንቶቹ "የፓስተር እገሌ ቸርች" እየተባለ እንዲጠራ ነው የሚፈለገው? ወይስ እንደ ንግድ ድርጅቶች "የእገሌና ቤተሰቡ ፒ ኤል ሲ" እየተባለ በግለሰብ ስም እንድትጠራ ለማድረግ ነው? ወይስ ቁጥር 1፥ ቁጥር 2፥ ወዘተ እየተባለች እንድትጠራ? በአውሮፓ በእነ ሉተር ስም የተሰየሙ ብዙ የፕሮቴስታንቶች የጸሎት ቤቶችም አሉ፡፡ ተከታዮቻቸውን ቤተ ክርስቲያንን በቅዱሳን ስም መሰየም አይገባም ብለው ሰብከው በራሳቸው ስም ወደ መሰየም አመጡት፡፡

እነ ሉተር የምዕራቡን ዓለም ቅዱሳን አያስፈልጉህም እያሉ ሁሉንም ነገር አጣጥለውና አጥላልተው ያደረሱት ዛሬ ካለበት ግብረ ሰዶማዊነትና እግዚአብሔር የለሽነት ነው፡፡ እምነት አለን የሚሉትም “የፓስተር እገሌ ቸርች” እየተባሉ እንደ ንግድ ሱቆች ወይም ድርጅቶች በግለሰቦች ስም ነው የሚጠሩት፡፡ በሀገራችው ያረረባቸው ፕሮቴስታንቶች የሚያሠለጥኗቸውና በከፍተኛ የገንዘብ ኃይል የሚያሰማሯቸው የተሐድሶዎች የፍጻሜ መዳረሻና ዓላማም እኛንም ወደዚህ “የብቃት ደረጃ” ለማድረስ ነው፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን እግዚአብሔር ባከበራቸው በቅዱሳን ስም መጥራት አስቀድሞ በትንቢት የተነገረና በሐዲስ ኪዳን በተግባር የተፈጸመ ነው፡፡ ከላይ የተገለጸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይትበሃልም በዚሁ የቀጠለ ነው፡፡ ይኸውም እንዲህ የሚለው የትንቢት ቃል ነው፡-

> እግዚአብሔር ሰንበቴን ስለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘኝንም ነገር ስለሚመርጡ ቃል ኪዳኔንም ስለሚይዙ ጃንደረቦች እንዲህ ይላልና፡- በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ፤ የማይጠፋም የዘለዓለም ስም እሰጣቸዋለሁ፡፡ . . . በጸሎቴም ቤት ደስ አሰኛቸዋለሁ፡፡ ኢሳ. 56፥4-7

እግዚአብሔር አምላክ በራሱ ቤት ወዳጆቹ ቅዱሳን እንዲታሰቡበት በዚህ ቃሉ መሠረት አስቀድሞ ተናግሯል፡፡ እግዚአብሔር ይህን ቃል ኪዳን የገባው ለጃንደረቦች ነው፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጃንደረባነትን ዓይነትና ሁኔታ ከላይ እንደ ተመለከትነው በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 19 ቁጥር 10-12 እንዲህ አስተምሮናል፡- “ይህ ነገር ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም፤ በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፤ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፤ <u>ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ</u>፡፡ ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው፡፡” ስለዚህ እግዚአብሔር “በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ” ብሎ የተናገረላቸው ስለ መንግሥተ ሰማያት ሲሉ ፈቃደ ሥጋቸውን የታገሡትንና በንጽሕና የኖሩትን ደናግል መነኰሳትን ነው፡፡

እነዚህ ጃንደረቦች (ደናግል መነኰሳት) ምድራዊ የሆነ የስም ማስጠሪያ ልጅ መውለድን ስለ መንግሥተ ሰማያት ብለው ስለ ተውት አምላካቸው ደግሞ ሥጋውያን ልጆች ሊያስጠሩ ከሚችሉት ስምና ከሚያስገኙት መታሰቢያ የበለጠ የስም ማስጠሪያ እንዲህ ሲል ሰጣቸው፡-

> ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ፤ የማይጠፋም የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ፡፡

ሥጋውያን ልጆች ስም ቢያስጠሩ እስከ ተወሰነ ትውልድ ድረስ ነው፡፡ ለቅዱሳን የተሰጣቸው ስም ግን የማይጠፋና ዘለዓለማዊ ነው፡፡ ስለሆነም ቅዱሳን ስማቸው የማያልፍ፤ ሁል ጊዜ የሚዘከርና የማይጠፋ እንደ ሆነ ራሱ እግዚአብሔር በማይታበል ቃሉ ተናገረ፡፡ <u>“በጸሎቴም ቤት ደስ አሰኛቸዋለሁ</u>” ማለቱም ስማቸው የሚዘከረውና የሚጠራው በቤቱና በቅጥሩ ውስጥ በመሆኑ ነው፡፡ ራሳቸውን ስለ እርሱ ፍቅር ሲሉ ጃንደረቦች ያደረጉት የወዳጆቹ የቅዱሳን ስም በራሱ ቤት ማለትም በቤተ ክርስቲያን እንዲጠራ ቅዱስ ፈቃዱ መሆኑን ራሱ እግዚአብሔር እንዲህ አስረግጦ ነግሮናል፡፡ ታዲያ ይህን መቃወም ምቀኝነት ነው? ወይስ ምን እንበለው?

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው የመጨረሻ ሰዓት ላይ ሽቱ ይዛ መጥታ የቀባችውን ሴት ደቀ መዛሙርቱ ገና በጸጋ ያልበለጸጉ ስለነበሩ ነገሩ ስላልተረዳቸውና በይሁዳ ቀስቃሽነት ድርጊቷን መንቀፍና ማጣጣል በጀመሩ ጊዜ እንዲህ አላቸው፡- “መልካም ሥራ ሠርታልኛለችና ሴቲቱን ስለ ምን ታደክሟታላችሁ? እርሷ ይህን ሽቱ በሰውነቴ ላይ አፍስሳ ለመቃብሬ አደረገች።

እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በማናቸውም ስፍራ በሚሰበክበት እርሷ ያደረገችው ደግሞ ለእርሷ መታሰቢያ እንዲሆን ይነገራል።" ማቴ. 26፡7-13 ሽቱ ላፈሰሰችለት ሴት "ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በማናቸውም ስፍራ በሚሰበክበት እርሷ ያደረገችው ደግሞ ለእርሷ መታሰቢያ እንዲሆን ይነገራል" ካለ ሽቱ ሳይሆን ደማቸውን ላፈሰሱለትና መላ ሕይወታቸውን ለሰጡለት ለሰማዕታትና ለቅዱሳን ወንጌል የሚሰበክባት ቤተ ክርስቲያን ስማቸው ቢጠራና ቢታሰቡ ወንጀሉ ምን ላይ ነው? በኃጢአት ከኖረች በኋላ በሕይወቷ ወደ ኋላ ጊዜ ላይ በንስሐ የተመለሰችው ማርያም እንተ ዕፍረት ወንጌል በሚሰበክበት በዓለም ሁሉ በማናቸውም ስፍራ መታሰቢያዋ እስኪነገር ድረስ ይህን ያህል ክብር የሰጣት ከሆነ መላ ዘመናቸውንና ሕይወታቸውን ለእርሱ የሰጡ ቅዱሳን አባቶቻችንና እናቶቻችን ይህ ክብር ይበዛባቸዋልን?

ስለዚህ ቅድስትና ሐዋርያዊት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቤት በቅዱሳን ስም የምትሰይመው ይህን የፈጣሪዋን ትእዛዝ ይዛ እንጂ እንዲሁ ባለ ማወቅ ወይም በልብ ወለድ አይደለም። ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ቅዱሳን ስም ቢሰየምም በውስጡ የሚፈጸመው አገልግሎት ማኅሌቱ፣ ቅዳሴው፣ መሥዋዕቱ ሁሉ አንድ ነው። የሚመሰገነው እግዚአብሔር ሲሆን የሚሠዋውም አንድ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው። መታሰቢያነቱ ለቅዱሳን እንዲሆን ያዘዘው የቤቱ ባለቤት እግዚአብሔር ነው። ይህን እግዚአብሔር ለወዳጆቹ የሰጠውን ክብር የሚቃወም ካለ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ "በገንዘቤ የወደድኩትን አደርግ ዘንድ አይገባኝምን? ወይስ እኔ ቸር ስለ ሆንኩ ዓይንህ ምቀኛ ናትን?" ይለዋል። ማቴ. 20፡15

## 6.4.3 ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳን ስም እንደሚሰየም የቀደምት አበው ሊቃውንት ትምህርት

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ወደ አንድ ቦታ ሄዶ በዚያ ስለ ነበረው የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ሲናገር እንዲህ ይላል፦

- *"ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ስንገባ በግራ በኩል ያለው በሰማዕታት ስም የታነፀው ቤተ መቅደስ ነበር፤ ፊት ለፊታችን ያለው ቅርጽ የተሠራበት ጥበብ በጣም የሚያስደንቅ ነበር። አንዱ ክፍል የተሠራበት አሠራር ሌላው ክፍል ከተሠራበት አሠራር ረቂቅ በሆነ ጥበብ ይለይ ነበር . . . "* (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ መልእክት ኀበ አደልፊየስ፣ ቁ. 15)

- *"በእግዚአብሔር ቸርነት የሰማዕታቱ ቤተ ክርስቲያን ሥራ በጥሩ ሁኔታ እየሄደ እንደ ሆነ ተገንዝቤያለሁ። የጀመርነውና በእጃችን ላይ ያለው ይህ ሥራ ሁሉን ማድረግ በሚችልና ፈቃዱ ሲሆን ሐሳቡ ሁሉ በቅጽበት ወዲያውኑ ተግባር (ድርጊት) በሚሆን በእግዚአብሔር ኃይል ይፈጸማል። ሐዋርያው 'በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼያለሁና' ያለውን በማሰብ በዚህም ታላቁን ቅዱስ ጳውሎስን ትመስለውና ለጀመርነውና እጃችን ላይ ላለው ለዚህ በሰማዕታት ስም ለሚሠራው የቤተ ክርስቲያን ሥራ በቂ የሚሆን የሰው ኃይል ትልክልን ዘንድ እጠይቅሃለሁ። ፊል 1፡ 6"* (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ መልእክት ኀበ አምፊሎቅዮስ ጳጳስ፣ ቁ. 16)

- *" . . . የቅዱሳን ዐጽም ያረፈባቸውና በስማቸው የታነጹ አብያተ ክርስቲያናት የሚመጣውን ፍርድ በጨረፍታ የሚያሳዩ ናቸው። ይህም አጋንንት ይሠቃዩባቸዋል፣ ሰዎች ደግሞ ይገሠጹባቸዋል፣ ነጻም ይወጡባቸዋልና ስለዚህ ነው። . . ."* (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ቆሮንቶስ ካልእ፣ ክፍለ ትምህርት 26፣ ቁ. 4)

እውነት እላችኋለሁ፣ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በማናቸውም ስፍራ በሚሰበክበት እርሷ ያደረገችው ደግሞ ለእርሷ መታሰቢያ እንዲሆን ይነገራል።" ማቴ. 26፥7-13 ሽቱ ላፈሰሰችለት ሴት "ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በማናቸውም ስፍራ በሚሰበክበት እርሷ ያደረገችው ደግሞ ለእርሷ መታሰቢያ እንዲሆን ይነገራል" ካለ ሽቱ ሳይሆን ደማቸውን ላፈሰሱለትና መላ ሕይወታቸውን ለሰጡለት ለሰማዕታትና ለቅዱሳን ወንጌል የሚሰበክባት ቤተ ክርስቲያን ስማቸው ቢጠራና ቢታሰቡ ወንጀሉ ምን ላይ ነው? በኃጢአት ከኖረች በኋላ በሕይወቷ ወደ ኋላ ጊዜ ላይ በንስሐ የተመለሰችው ማርያም እንተ ዕፍረት ወንጌል በሚሰበክበት በዓለም ሁሉ በማናቸውም ስፍራ መታሰቢያዋ እስከነገር ድረስ ይህን ያህል ክብር የሰጣት ከሆነ መላ ዘመናቸውንና ሕይወታቸውን ለእርሱ የሰጡ ቅዱሳን አባቶቻችንና እናቶቻችን ይህ ክብር ይበዛባቸዋልን?

ስለዚህ ቅድስትና ሐዋርያዊት አርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቤት በቅዱሳን ስም የምትሰይመው ይህን የፈጣሪዋን ትእዛዝ ይዛ እንጂ እንዲሁ ባለ ማወቅ ወይም በልብ ወለድ አይደለም። ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ቅዱሳን ስም ቢሰየምም በውስጡ የሚፈጸመው አገልግሎት ማኅሌቱ፣ ቅዳሴው፣ መሥዋዕቱ ሁሉ አንድ ነው። የሚመሰገነው እግዚአብሔር ሲሆን የሚሠዋውም አንድ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው። መታሰቢያነቱ ለቅዱሳን እንዲሆን ያዘዘው የቤቱ ባለቤት እግዚአብሔር ነው። ይህን እግዚአብሔር ለወዳጆቹ የሰጠውን ክብር የሚቃወም ካለ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ "በገንዘቤ የወደድኩትን አደርግ ዘንድ አይገባኝምን? ወይስ እኔ ቸር ስለ ሆንኩ ዓይንህ ምቀኛ ናትን?" ይለዋል። ማቴ. 20፥15

## 6.4.3 ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳን ስም እንደሚሰየም የቀደምት አበው ሊቃውንት ትምህርት

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ወደ አንድ ቦታ ሄዶ በዚያ ስለ ነበረው የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ሲናገር እንዲህ ይላል፦

- "ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ስንገባ በግራ በኩል ያለው በሰማዕታት ስም የታነፀው ቤተ መቅደስ ነበር፣ ፊት ለፊታችን ያለው ቅርጽ የተሠራበት ጥበብ በጣም የሚያስደንቅ ነበር። አንዱ ክፍል የተሠራበት አሠራር ሌላው ክፍል ከተሠራበት አሠራር ረቂቅ በሆነ ጥበብ ይለይ ነበር . . ." (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ መልእክት ኀበ አደልፊየስ፣ ቁ. 15)

- "በእግዚአብሔር ቸርነት የሰማዕታቱ ቤተ ክርስቲያን ሥራ በጥሩ ሁኔታ እየሄደ እንደ ሆነ ተገንዝቤያለሁ። የጀመርነውና በእጃችን ላይ ያለው ይህ ሥራ ሁሉን ማድረግ በሚችልና ፈቃዱ ሲሆን ሐሳቡ ሁሉ በቅጽበት ወዲያውኑ ተግባር (ድርጊት) በሚሆን በእግዚአብሔር ኃይል ይፈጸማል። ሐዋርያው 'በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼያለሁና' ያለውን በማሰብ በዚህም ታላቁን ቅዱስ ጳውሎስን ትመስለውና ለጀመርነውና እጃችን ላይ ላለው ለዚህ በሰማዕታት ስም ለሚሠራው የቤተ ክርስቲያን ሥራ በቂ የሚሆን የሰው ኃይል ትልክልን ዘንድ እጠይቅሃለሁ። ፊል 1፥6" (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ መልእክት ኀበ አምፊሎቅዮስ ጳጳስ፣ ቁ. 16)

- " . . . የቅዱሳን ዐጽም ያረፈባቸውና በስማቸው የታነጹ አብያተ ክርስቲያናት የሚመጣውን ፍርድ በጨረፍታ የሚያሳዩ ናቸው። ይህም አጋንንት ይሠቃዩባቸዋል፣ ሰዎች ደግሞ ይገሠጹባቸዋል፣ ነጻም ይወጡባቸዋልና ስለዚህ ነው። . . ." (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ቆሮንቶስ ካልእ፣ ክፍለ ትምህርት 26፥ ቁ. 4)

- "... በቅዱሳን ሰማዕታት ስም ወደ ታነጸው ወደዚህ ቤተ መቅደስ እንድትመጡ ጠራኋችሁ፣ ፣ ... ደም አልባ የሆነውን መሥዋዕት በምናቀርብበት በጸሎተ ቅዳሴው ጊዜም ቅዱሳን ሰማዕታትን እንዘክራቸውና ስማቸውን እንጠራ ዘንድ የተገባ ነውና፡፡ ... ቅዱሳን ሰማዕታን በማዘከር በዓል ማድረግና በበዓሉ መንፈሳዊ ደስታ መደሰት ከመንፈስ ቅዱስ ሥርዓት ውጭ የሆነ ነገር አይደለምና፡፡ አማናዊውን ተስፋ ማለትም የክርስቶስን ትንግኤ ከመቀበላችን በፊት ሞት በእውነት ሞት ነበር፣ እርሱን ተከትሎ የሚመጣው ሐዘንም መራርና መጽናናት ያልነበረው ከባድ ነበር፡፡ ..." (ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ፣ ክፍለ ትምህርት 18)

ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በሞተ ጊዜ (337 ዓ. ም.) የመጀመሪያዎቹን ሦስት መቶ ዓመታት እስከ አራተኛው አጋማሽ ገደማ ድረስ ያለውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጽፎ ያቆየልን አውሳብዮስ ዘቂሣርያ ሥርዓተ ቀብሩን በተመለከተ እንዲህ ይላል፡-

- "ቈንስጣንድዮስ [ልጁ] ከወታደራዊ ኃይሉ ጋር ከአስከሬኑ ፊቀቅ ብሎ በቆመ ጊዜ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ካህናቱ ከመላው ሕዝበ ክርስቲያን ጋር ወደ ፊት ቀርበው ለእንዲህ ዓይነት ጊዜ ተገቢ የሆነውን ሥርዓተ አምልኮ በጸሎት አከናወኑ፡፡ መላው ሕዝበ ክርስቲያን በሙሉ ከካህናቱ ጋር አንድ በመሆን ከዕንባ ጋር ስለ ነፍሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎትን አቀረቡ፡፡ ... <u>ከዚህም ጋር በሕይወቱ ሳለ ይመኝ እንደ ነበረው በቅዱሳን ሐዋርያት ስም በተሰየመው ቤተ ክርስቲያን</u> በመቀበሩና ሰውነቱ በዚያ በማረፉ ከእነርሱ ከስማቸው ክብር ጋር ለመሳተፍና ከእግዚአብሔር ቅዱሳን ከሐዋርያት ጋር ሱታፌ በሚያገኝበት ሁኔታ በማረፉ ነው፡፡ በተደረገለት ጸሎተ ፍትሐትና ሥርዓተ አምልኮ በክብረ ሁኔታ ተሸኘ፣ በቅዱሳን ሐዋርያት በተሰየመው ቤተ ክርስቲያን በመቀበሩም በቅዱሳን ጸሎት ሱታፌን አገኘ፡፡" (አውሳብዮስ ዘቂሣርያ፣ ዜና ሕይወቱ ለቆስጠንጢኖስ፣ መጽሐፍ 4፣ ምዕ. 71)

ይህ የሚያስረዳን በዚያን ጊዜም፣ ከዚያ በፊት እንደ ነበረው ሥርዓት ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት በቅዱሳኑ ስም - በሐዋርያት፣ በሰማዕታት ... ይሰየሙ የነበረ መሆኑን እንረዳለን፣ ቆስጠንጢኖስ የተቀበረበት ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳን ሐዋርያት ስም የተሰየመ ነበርና፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያንን በቅዱሳን ስም መሰየም ከጥንት የነበረ የቤተ ክርስቲያን ትውፊት እንጂ በኋላ ዘመን የመጣ አይደለም፡፡

## 6.5 ስለ ቅዱሳን መጻፍ መቼ ተጀመረ?

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ተቃዋሚዎች ስለ ቅዱሳን መናገር፣ ስለ እነርሱ የሚናገሩ መጻሕፍትም መጻፍ የጀመሩት ወደ ኋላ ዘመን ላይ፣ እንዲያውም ከ15ኛው መቶ ዓመት ጀምሮና ከዚያ ወዲህ የተጀመረ ልማድ እንጂ በመጀመሪያው የክርስትና ዘመን ያልነበረ እንደ ሆነ የሚናገሩ አሉ፡፡ ተሐድሶዎች ስለ ቅዱሳን መጻፍን በዓፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እንደ መጣ ለማስመሰል ይሞክራሉ፡፡ ለአብነትም እንዲህ ያሉትን እንመልከት፡-

- "ከአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በኢትዮጵያ እያደገ የመጣውንና መላእክትና ያንቀላፉ ቅዱሳን ሰውን ለማዳን በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በቃል ኪዳን የተሰጠ ድርሻ እንዳላቸው ተደርጎ በገድል፣ በድርሳን በተአምርና በተለያዩ የሰላምታ ድርሰቶች ተስፋፍቶ የሚነገረውን ሁሉ ሊቁ አባ ስብሐት ለአብ አልተቀበሉትም፡፡" (ሙራ ቁ. 24፣ ገጽ 16)

ስለ ቅዱሳን ዜና ሕይወት፣ ስለ ተጋድሏቸው ... መጻፍ የተጀመረው ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ እንጂ በኋላ ዘመን፣ ያውም ተሐድሶዎች እንደሚሉት በኢትዮጵያና እርሱም ደግሞ በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን አልነበረም፡፡ ስለዚህ ይህ አስተሳሰብ ወይ አለማወቅ፣ አለበለዚያም ደግሞ አውቆ ማታለል ካልሆነ በስተቀር ነገሩ እንዲህ አይደለም፡፡ ከላይ እንዳየነው ስለ ቅዱሳን በመናገር ምንጩ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ አፄ ዘርዐ ያዕቆብ የነገሠው በ15ኛው መቶ ዓመት (ከ1434-1468 ዓ. ም.)

ሲሆን የቅዱሳንን ሕይወት በተመለከተ መጻፍ የተጀመረው ግን ከእርሱ ከአንድ ሺህ እና ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ከዘመነ ሐዋርያትና ቀጥሎም ከዘመነ ሊቃውንት አንሥቶ ነው፡፡ ከዚያም በመቀጠል ከመጀመሪያው የክርስትና ዘመን ጀምሮ የተነሡ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ስለ ቅዱሳን የተለያዩ ድርሰቶችን ጽፈዋል፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን እንመለከታለን፡፡

ከላይ እንደ ተመለከትነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የብዙ ቅዱሳንን ዜና ሕይወት የያዙ ክፍሎች መኖራቸውን አይተናል፡፡ ለምሳሌ ያክልም፡-

- አሪት ዘፍጥረት - የእነ ኖኅን፣ አብርሃምን፣ ይስሐቅን፣ ያዕቆብን፣ ዮሴፍን . . . ዜና ሕይወት በተመለከተ በሰፊው የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡

- መጽሐፈ ኢዮብ - "ዖፅ በሚባል አገር ስሙ ኢዮብ የተባለ አንድ ሰው ነበረ፡፡ ያም ሰው ፍጹምና ቅን፥ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፥ ከክፋትም የራቀ ነበረ" ብሎ ይጀምርና ከዚያ በኋላ ኢዮብ ከሰይጣን ስለ ደረሰበት ከስና ተደራራቢ ከባድ ፈተና፣ እርሱ ደግሞ ፈተናውን እንዴት እንደ ቀወጣውና በመጨረሻም እግዚአብሔር በምሕረት እንደ ጎበኘውና ሀብቱንና ጤናውን እጥፍ አድርጎ እንደ መለሰለት የሚናገር በኢዮብ አጠቃላይ ሕይወት ዙሪያ የሚያጠነጥን የገድል ዓይነት ጠባይ ያለው መጽሐፍ ነው፡፡ የሌሎች ቅዱሳን ዜና ሕይወቶችም (ገድላት) የሚጻፉት በዚሁ ዓይነት መልክ ነው፡፡

- መጽሐፈ ነገሥት - በውስጡ ስለ ታላቁ ነቢይ ስለ ኤልያስ፣ ስለ ኤልሳዕ ዜና ሕይወት በሰፋት የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡

- ግብረ ሐዋርያት - ስለ ሐዋርያት በዓለም መሰማራትና ከዚያ ቅዱስ ጳውሎስ ስላደረጋቸው ሐዋርያዊ ጉዞዎችና በዚያም ስለ ገጠሙት የተለያዩ ነገሮች የሚያስረዳ መጽሐፍ ነው፡፡

- መልእክታት - ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቶቹ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ስለሚያውቃቸው የተለያዩ ሰዎች ማንነትና ሁኔታ ገልጿል፡፡

## ገድለ ሰማዕታት

ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ በየቦታው በሰማዕትነት የሞቱትን ቅዱሳን ሰማዕታት አባቶችና እናቶች አሟሟታቸውን፣ ተጋድሏቸውንና ሰማዕትነት ከመቀበላቸው ጋር ተያያዥ የሆኑ ነገሮችን በዓይናቸው ያዩ ክርስቲያኖች ጽፈው ያስቀምጡ ነበር፡፡ ከዚያም ያ ሰማዕት ሰማዕትነትን በተቀበለበት ቀን በየዓመቱ ሰማዕትነት በተቀበለበት ቦታ ወይም እንደ አመቺነቱ ምእመናን እየተሰበሰቡ የሰማዕቱን ዜና ገድል ያነቡ፣ ወንጌልን ይማማሩና ቀድሰው ይቆርቡ ነበር፡፡ እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅና ሌሎች የቤተ ክርስቲያን መምህራንም በቅዱሳን ዓመታዊ መታሰቢያ ቀናት በአብያተ ክርስቲያናት እየተዘዋወሩ ያስተምሩ ነበር፡፡

ቀስ በቀስም በአንድ አካባቢ ብቻ ይታወቁ የነበሩ ሰማዕታት ዜና ገድላቸው በሌሎችም እየታወቀ፣ ምስክርነታቸውን የፈጸሙበት ቀን የሚታሰብበት ዓውድም ሰፋ እያለ መጣ፡፡ በየአካባቢው የነበሩ የቅዱሳን ሰማዕታትን ዜና ሕይወት በአንድ ላይ በማሰባሰብና ወጥ አድርጎ በመጻፍ ለትውልድ እንዲተላለፍ ያደረገው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊው አውሳብዮስ ዘቂሣርያ ነው፡፡ አውሳብዮስ ከዘመነ ሐዋርያት አንሥቶ እስከ ቆስጠንጢኖስ ዘመን የነበሩትን ሰማዕታት ዜና ሕይወት አሥር መጽሐፍ አድርጎ በጻፈው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መጽሐፉ ትቶልን አልፏል፡፡

ታላቁ አባት ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ከጻፋቸውና ትቶልን ከሄዳቸው ትምህርቶቹ መካከል በዘመኑ ስለ ነበሩ ቅዱሳን ተጋድሎና ዜና ሕይወት የጻፋቸው ይገኙባቸዋል፡፡ እነዚህም አምስት ትምህርቶች ሲሆኑ ትምህርቶቹ በአጭሩ የሚከተሉት ናቸው፡-

(1) ኢየሉጣ (ዩሊታ - Julitta)[124] ስለ ተባለች ሰማዕት (ትምህርት - Homily 5)

የቂሣርያ ነዋሪ የነበረች ሴት ስትሆን በ306 ዓ. ም. በሰማዕትነት የተገደለች ታላቅ ሰማዕት ናት፡፡ በዘመኑ የነበረ ዐላዊ ባለ ሥልጣን ሀብቷንና ንብረቷን በሙሉ ከቀማት በኋላ ክርስቲያንነቷን እንድትክድ ባላት ጊዜ ክርስቶስን በጭራሽ አልክድም አለች፡፡ ያን ጊዜም በእሳት ተቃጥላ ተገደለች፡፡ ይህች ቅድስት ሰማዕትም ሴቶችም እንደ ወንዶች ሁሉ በእግዚአብሔር አርአያ የተፈጠሩ ናቸው ብላ መናገሯና ስለ ክርስቶስ ለመመስከርና በጽናት መከራ ለመቀበል ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በእርሱ ኃይል ይችላሉ ብላ እንደ ተናገረች ይነገርላታል፡፡ ቅዱስ ባስልዮስ በዚህ ክፍለ ትምህርቱ ሰማዕቷን ቅድስት ኢየሉጣን በብዙ አመስግኗታል፡፡

(2) ባርለዓም ስለ ተባለ ሰማዕት (ትምህርት - Homily 17)

በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን ሰማዕትነትን የተቀበለ ነው፡፡ አሠቃዮቹ እጅግ የተለያዩ ዓይነት የማሠቃያ መንገዶችን በመጠቀምና ሌሎች አዳዲስ ሥቃያትን እየፈጠሩ ለጣዖታቸው እንዲሠዋ ለማድረግ ብዙ አሠቃዩት፡፡ ዕጣንን በእጁ ላይ አቃጥለው ከዚያም ወደ ጣዖቱ መሠዊያ ላይ እንዲሄድ በግድ በማስገደድ ለጣዖታቸው በግድ እንዲሠዋ ለማድረግ ተጠበቡ፡፡ ሆኖም እሳቱ በተጋዳዩ ሰማዕት እጅ ላይ ኃይል አልነበረውም፤ እንዳሰቡትም አልሆነላቸውም፡፡ ቅዱስ ባርለዓም በቃለ ዳዊት "ቀኝ እጄንም ያዝከኝ፤ በአንተ ምክር መራኸኝ፤ ከክብር ጋር ተቀበልኸኝ" በማለት እሳቱ እጁ ላይ ቢነድድም ኃይል ግን አጣ፡፡ መዝ. 72፡23-24 ስለዚህ ሰማዕት የጻፈው የቅዱስ ባስልዮስ ትምህርት ዜና ገድሉን የሚደመድመው እንዲህ በሚል ቃል ነው፡-

> የሰማዕታትን ተጋድሎዎች በሥዕላት የምትገልጡ ሠዓልያን ሆይ፤ የዚህን ከሠራዊታችን መካከል የነበረ ሰማዕት በተጋድሎ ሥቃያትን የተቀበለ ፊቱን በጥበባችሁ አስውቡት፤ እኔ የዚህን የድል አድራጊ ሰማዕት ብዙም ያን ያህልም ያልሆነ ሥዕል ነው የሣልሁት፡፡ ጥበባችሁንና ያሏችሁን ቀለማት ሁሉ ስለ ክበሩ ተጠቀሙ፡፡

(3) ጎርዲየስ (Gordius) ስለ ተባለ ሰማዕት (ትምህርት - Homily 18)

የመቶ አለቃ የነበረ ሲሆን ሊቅዮኖስ ክርስቲያኖችን ከሠራዊቱ ሲያስወጣ እርሱንም ከመዓርጉ ሻረው፡፡ ከዚያም ጎርዲየስ ሥራውን በፈቃዱ ለቅቆ ወደ በረሓ በመሄድ በዚያ የብሕትውና ሕይወትን ጀመረ፡፡ ከዕለታት በአንድ ወቅት በቂሣርያ የማርስ (Mars) ክብረ በዓል ነበር፡፡ እጅግ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት በዚያ የጣኦት በዓል ላይ በበረሓና በተራራ ብዙ ጊዜ በብሕትውና የተጋደለው ጎርዲየስ ስለ ክርስቶስ መስክሮ ሰማዕትነትን ይቀበል ዘንድ በዚያ በገዢው ፊት ቀረበ፡፡ ገዢውም ያሉ የማሠቃያ ዓይነቶችንና መንገዶችን ሁሉ ይፈጽሙበት ዘንድ አዘዘ፡፡ ገዢውም "ይህ ርጉም ክፉ ሰውዬ የሚሞተው አንድ ጊዜ ብቻ መሆኑ እንዴት ዕድለኛ ነው!" አለ፡፡ ቅዱስ ጎርዲየስም "ስለ ክርስቶስ ደግሜ ደጋግሜ ብዙ ጊዜ መሞት የምችል አለመሆኔ ምንኛ አሳዛኝ ነገር ነው!" አለው፡፡ በመስቀል ምልክት ሰውነቱን ካማተበ በኋላ ራሱን ለሚገድለው ሳይሆን ለመልአክ እጅ አሳልፎ የሚሰጥ በሚመስል ሁኔታ በፍጹም መረጋጋትና በደስታ ሆኖ ከባለ ወጉ ፊት ቀረበ፤ ሰማዕትነቱንም በዚያ ፈጸመ፡፡

---

124 የነሐሴ 6 ስንክሳር ላይ ያነሣታል፡፡ ይህቺ ኢየሉጣ የቅዱስ ቂርቆስ እናት ሳትሆን ሌላ ኢየሉጣ ናት፡፡

(4) ስለ አርብአ ሐራ ሰማዕታት (ትምህርት - Homily 19)

በሴባስቴ ስለ ነበሩት አርባ ወታደር ሰማዕታት ተጋድሎ የሚናገር ነው፡፡ በሉቅያኖስ ባለ ሥልጣናት ለጣዖትት መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ሲታዘዙ እምቢ በማለታቸው በከተማው ውስጥ በነበረ አንድ በረዷማ የውኃ ኩሬ ላይ ጣሏቸው፡፡ ከዚያ ከተጣሉበት በረዷማ ኩሬ ፊት ለፊት ደግሞ ለመታጠቢያነት ተስማሚና ምቹ የሆነ የፍል ውኃ መታጠቢያ ነበር፡፡ ከአርባው መካከል አንደኛው ከቅዝቃዜው ጽናት የተነሣ እውጡኝ እለና ወዲያውኑ እየሮጠ በሙቅ ውኃው መታጠቢያ ለመታጠብ ሄደ፡፡ ወዲያውኑ እንደ ገባም ሰውነቱ ብስክስክ ብሎ ሞተ፡፡ የእነዚያን ተጋዳይ ወታደሮች ሥቃያቸውን ሲከታተሉ ከነበሩት አስፈጻሚ ወታደሮች መካከል አንደኛው ራሱን በፍል ውኃው እያሞቀ ይህን እንግዳ ነገር እየተመለከተ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜም መላእክት ከሰማያት ወርደው ለአርባው ተጋዳዮች አክሊል ሲያቀዳጇቸው የአንደኛው አክሊል ግን ተንጠልጥሎ በአየር ላይ ሲቀር ተመለከተ፡፡ የአርባው ቁጥር በአንዱ መውጣት ለጊዜውም ቢሆን በጎደለ ጊዜ ያ ወታደር በወጣው ሰው ቦታ ገብቶ በክርስቶስ ታምኖ የሰማዕትነት አክሊልን ተቀበለ፡፡

ቅዱስ ባስልዮስ እነዚህን ቅዱሳን ሰማዕታት ጸሎታቸው ጠቃሚ መሆኑንና ክርስቲያኖች በእነርሱ ጸሎትና ምልጃ ይጠቀሙባቸው ዘንድ በትምህርቱ እንዲህ ብሎ ገልጿል፦

> ወደ እግዚአብሔር የሚጸልይላችሁ አንድ ሰው ለማግኘት ምን ያህል ትደክሙ ነበር ይሆን? በአንድ ቃል ሆነው የሚጸልዩ አርባ ቅዱሳን ሰማዕታት (አርብአ ሐራ ሰማዕታት) እዚህ አሉላችሁ፡፡ በጌታ ስም ሁለት ወይም ሦስት ከተሰባሰቡ እርሱ ባለቤቱ በመካከላቸው አብሯቸው አለ፡፡ ታዲያ በአርባው መካከል መኖሩን የሚጠራጠር ማን ይሆን? የተቸገሩ ሰዎች ወደ አርባው ሰማዕታት ይሄዳሉ፤ ደስ ያላቸውም ወደ እነርሱ ይገሰግሳሉ፡፡ እነዚያ (ያዘኑትና የተቸገሩት) ከችግራቸው ይላቀቁና መፍትሔ ያገኙ ዘንድ ሲሆን እነዚኞቹ (ደስ ያላቸው) ደግሞ ያገኙት በረከት እንዲጠበቅላቸው ነው፡፡ በእምነቷ ምስጉን የሆነች እናት ስለ ልጆቿ ትማጸናቸዋለች፤ ከቤት የወጣ ባሏ በደኅና እንዲመለስላት የምትለምንም አለች፤ ታሞም ከሆነ ለጤንነቱ ትለምናለች፡፡ ስለዚህም ልመናችሁንና ምልጃችሁን ወደ እግዚአብሔር ስታቀርቡ ከሰማዕታት ጋር አብሮ ይሁን፡፡ (ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ፤ ክፍለ ትምህርት 19)

(5) ስለ ቅዱስ ማማስ

ስለ ቅዱሳን ተጋድሎና ክብር ከጻፋቸው አምስት ትምህርቶች አምስተኛው (ትምህርት - Homily 22) ስለ ቅዱስ ማማስ የተጻፈ ነው፡፡ በግሪኮች ሴፕቴምበር 2፤ በላቲኖች ደግሞ አገስት 17 ይታሰባል፡፡ እረኛ የነበረና ቂሣርያ ላይ በ274 ዓ. ም. በቄሣር ኦሬሊያን የመከራ ዘመን ሰማዕትነትን የተቀበለ ነው፡፡ ቅዱስ ባስልዮስ በዚህ ትምህርቱ ላይ ቅዱሱ ሰማዕት በአማላጅነቱ እንዲያስበን እንለምነው ዘንድ ያሳስባል፡፡ እንዲሁም ሰማዕቱ በራእይ የተገለጠላቸው ሰዎች ሁላቸውም፤ በጸሎታቸውና በሕይወታቸው የተረዳቸው ሁሉም እርሱን ያስቡት ዘንድ ይጠይቃል፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነበቤ መለኮትም የዚህ ቅዱስ ሰማዕት ዓመታዊ በዓል በሚከበርበት ቀን ያስተማረው ትምህርት አለ (ትምህርት - Oration - 44)፡፡ የዚህ ሰማዕት ዓመታዊ በዓል በናዚያንዘስ አካባቢ በታላቅ ድምቀት ይከበር ነበር፡፡

ለአብነት የቅዱስ ባስልዮስን አነሣን እንጂ ሌሎች ብዙ አባቶችም በየዘመናቸው በቅዱሳን ዙሪያ ላይ ብዙ ትምህርቶችን ያስተማሩና የጻፉ ስለሆነ ወደ ዝርዝሩ ሳንገባ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡

## 6.6 ስለ ቅዱሳን የጻፉ ኦርቶዶክሳዊ አባቶች

| የጻፈው አባት | የጻፈው ድርሰት |
|---|---|
| ቅዱስ አትናቴዎስ | • ገድለ ቅዱስ እንጦንስ<br>• ገድለ ቅዱስ ጳኩሚስ |
| ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት | • ስለ ቅዱስ ማማስ |
| ቅዱስ ባስልዮስ | • ስለ ሰማእታቱ ስለ ኢየሉጣ፣ ስለ ባርለዓም፣ ስለ ጎርዲየስ፣ ስለ አርብአ ሐራ፣ ስለ ማማስ |
| ቅ. ዮሐንስ አፈ ወርቅ | • ስለ ቅ. አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ፣<br>• ስለ ቅ. በረላም፣<br>• ስለ ቅ. ኤዎስጣቴዎስ፣<br>• ስለ ቅ. ባቢላስ፣<br>• ስለ ቅድስት ጲላጊያ፣ ስለ ቅድስት ዶምኒያ እና ስለ ሁለቱ ሴቶች ልጆቿ፣<br>• ስለ ሌሎችም ብዙ ቅዱሳን አስተምሯል፤ ጽፏል፡፡ |
| ጳላድዮስ | • ዜና መነኮሳት |
| ጀቱ መነኮሳት ዘፍልስጥዔም | • ዜና አበው |
| አውሳብዮስ ዘቂሣርያ | • ዜና ሰማዕታት |
| ቅ. ጀሮም | • ገድለ ጳውሊ (ርእሰ ባሕታውያን)<br>• ገድለ ቅ. ሂላርዮን<br>• ማልክስ ስለ ተባለ ተጋዳይ መነኩሴ ሕይወት |
| አባ በብኑዳ | • ገድለ ቅዱስ መቃርዮስ (ታላቁ) |
| አባ ባምዋ | • ገድለ ቅዱስ ኪሮስ |
| ቅ. ዞሲማስ | • ገድለ ብፁዓውያንን |
| ጳጳስ ሳፍሮኒዮስ | • ገድለ ማርያም ግብጻዊት<br>• ገድለ ዞሲማስ |
| ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ | • ስለ አርብአ ሐራ ሰማዕታት |
| ቅዱስ ያሬድ | • አዝቂርና ኪርያቅ፣ ቴዎቅሪጦስ፣ እስጢፋኖስ፣ አባ ገሪማ፣ አባ ሊባኖስ፣ ወዘተ የመሳሰሉ ቅዱሳንን በድጓው፣ በዝማሬና መዋሥዕቱ ያነሣቸዋል፡፡ |

በቅዱሳን ዓመታዊ መታሰቢያ በዓላት ላይ ስለ ቅዱሳን ይሰጡ የነበሩ ትምህርቶችን በተመለከተ ደግሞ ለአብነት እንዲሆነን ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ስለ ቅዱስ አግናጥዮስ ካስተማረው ትምህርት ውስጥ የተወሰነውን ብቻ አለፍ አለፍ እያልን እንመልከት፡-

የታላቋ አንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ ስለ ሆነው፣ ወደ ሮም ተወስዶ በዚያ ሰማዕትነትን ስለ ተቀበለው፣ በኋላም ወደ አንጾኪያ እንዲመጣ ስለ ሆነው እና ጸዋሬ እግዚአብሔር[125] ስለ ተባለ፣ ስለ ሰማዕቱ ቅዱስ አግናጥዮስ፡-

[125](Theophoros – God-bearer)

1. በህብት የከበሩና ተድላ ደስታን የሚያዘወትሩ ሰዎች ለሚጋብዟቸው ሰዎች ቀዋሚና ተደጋጋሚ የሆነ ግብዣን ያደርጋሉ፤ ይህም በአንድ በኩል ሀብታቸውን ለማሳየት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለወዳጆቻቸው መልካም ነገርን ለማድረግ ነው፡፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ለእኛም እንዲሁ ኃይሉንና ክኀሊነቱን ሊያስረዳንና ሊያረጋግጥልን፣ እንደዚሁም ለእግዚአብሔር ወዳጆች መልካም የሆነ ቸርነቱን ሊያሳየን ወዶ በተከታታይና በዘላቂነት የሰማዕታትን በዓል ማዕድ በፊታችን አዘጋጀልን፡፡ ለምሳሌ ከትንሽ ቀን በፊት ድንግሏና ወጣቷ ብላቴና፣ ቅድስቷ ሰማዕት ጲላጊያ[126] በብዙ ደስታ ደስ አሰኘችን፡፡ ዛሬ ደግሞ እንደገና ይህ ቅዱስና የከበረ ሰማዕት አግናጥዮስ ከእርሷ በዓል ቀጥሎ መጣልን፡፡ ሰዎቹ የተለያዩ ናቸው፤ ማዕዱ ግን ያው አንድ ነው፡፡ የተጋድሏቸው ዓይነት (መስመር) የተለያየ ነው፤ አክሊላቸው ግን አንድ ነው፡፡ ውድድራቸው ዘርፈ ብዙ ነው፤ ሽልማታቸው ግን አንድ ነው፡፡ . . .

ስለዚህ አሁን ጊዜው ስለዚህ ቅዱስ ሰማዕት ታላላቅ ሥራዎች እንናገር ዘንድ ይጠራናል፡፡ ነገር ግን እጅግ ብዙ የሆኑ ነገሮች በብዙ አቅጣጫ የእርሱን ሥራ እንድንናገር ይጠሩናልና የትኛውን መጀመሪያ፤ የትኛውን ሁለተኛ፣ የትኛውን ሦስተኛ እንደምንናገር ግራ ተጋብተናል፡፡ አንድ ሰው ወደ አበቦች መስክ ሄዶ በዚያ እጅግ የተለያዩ፣ ነገር ግን እያንዳንዳቸው የተለያየና የእያንዳንዱ በየራሱ ሲያዩት ደስ የሚል ኅብረ ቀለም ያላቸውን አበባዎች ከመመልከቱ የተነሣ የትኛውን መጀመሪያ የትኛውን ደግሞ ከዚያ በኋላ እንደሚመለከት ግራ እንደሚገባው ሰው ዓይነት፤ የሚያየው ሁሉ እያንዳንዱ መጀመሪያ እይታውን እርሱ ላይ እንዲያሳርፍ ይጋብዘዋልና፡፡ ይህም እንደዚያ ዓይነት ሁኔታ ነው፡፡ እኛም ድንቅ ወደ ሆነው የቅዱስ አግናጥዮስ የተጋድሎ መንፈሳዊ መስክ መጥተን በዚያም በአበባ ወራት የሚፈነዱ አበባዎችን ሳይሆን ብዙና የተለያዩ የሆኑ መንፈስ ቅዱስ በዚህ ሰው ላይ ያፈራቸውን ፍሬዎች ስናይ መጀመሪያውን ትኩረት ወይም ቅድሚያ መስጠት ያለብን ለየትኛው መሆኑን ለማወቅ ባለ መቻላችን ግራ ተጋብተናል፡፡

የምናየው ነገር ሁሉ እያንዳንዱ እርሱን እንድናይ ዓይነ ነፍሳችንን ወደዚያ ይጠራዋል፣ ይማርከዋልና፡፡ እስኪ አስተውሉ! ቤተ ክርስቲያንን በእኛ መካከል[127] በግሩም ሁኔታ፣ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያኑን የማስተዳደር ኃላፊነት የሚቀበሉ ሰዎች ሊኖራቸው በሚፈልገው የጥንቃቄና የትጋት መጠን አስተዳደረ፡፡ ክርስቶስ የኤጲስ ቆጶስነት ኃላፊነት ከፍተኛ መለኪያና መመሪያ እንደ ሆነ የተናገረውን እርሱ በተግባር ፈጽሟልና፡፡ ክርስቶስ "መልካም እረኛ ሕይወቱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ይሰጣል" (ዮሐ. 10፡11) ያለውን ቃል ሰምቶ በፍጹም ጀግንነት ራሱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ሰጥቷልና፡፡

እርሱ ከሐዋርያት ጋር እውነተኛ ነገርን የተነጋገረና ጥሩ ምንጮች ከሆኑት ከእነርሱ መንፈሳዊ መጠጥን የጠጣ ነው፡፡ ከእነርሱ እግር ሥር ያደገ፣ ከእነርሱ ጋር ሲነጋገር የኖረና ሊናገሯቸው የሚገቡና የማይገቡ ምሥጢራትን ከእነርሱ የሰማ፤ እነርሱም ደግሞ እንዲህ ላለው እጅግ ታላቅ ክብር የተገባ ሆኖ ያገኙት እርሱ ምን ዓይነት ሰው ቢሆን ይሆን? ኋላም ቁርጥ ውሳኔን የሚጠይቅ የሰማዕትነት ጊዜ መጣ፡፡ እርሱ የአሁኑን ዓለም ነገር የናቀ፣ በመለኮታዊ ፍቅር የሚቃጠል እና ከሚታየው ነገር ይልቅ የማይታየውን ዓለም ሕይወትና ክብር የተገነዘበና ያስቀደመ በመሆኑ አንድ ሰው ልክ ልብሱን በቀላሉ እንደሚያወልቅ ዓይነት ሰውነቱን ለሰማዕትነት አሳልፎ ሰጠ፡፡

---

126 (Pelagia) - ጲላግያ ዘአንጾኪያ የአሥራ አምስት ዓመት ድንግል የነበረችና በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን በአደባባይ ለጣዖት እንድትሠዋ በወታደሮች በኃይል ብትታዘዝም ይህን ባለመቀበሏና በኢየሱስ ክርስቶስ ባላት ሃይማኖት በመጽናቷ ሰማዕትነትን የተቀበለች ናት።

127 ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ይህን ስብከት የሰበከው ወደ ቁስጥንጥንያ ተወስዶ ፓትርያርክ ከመደረጉ በፊት በአንጾኪያ ሳለ ነው።

ታዲያ መጀመሪያ ስለ የትኛው እንናገር? በሙላ የሕይወቱ ዘመን በቃልና በተግባር ስለ መሰከረውና ስላረጋገጠው የሐዋርያት ትምህርት ነው? ወይስ ለዚህ ዓለም ሕይወት ግድ የሌለውና እንደ ቁም ነገር የቆጠረው ስላለመሆኑ? ወይስ ቤተ ክርስቲያንን በታላቅ ጥንቃቄና ጥበብ ላስተዳደረበት ጥብቅና ጽኑዕ የተጋድሎ ሕይወቱ? መጀመሪያ የትኛውን እናስብ? ሰማዕቱን ወይስ ጳጳሱን ወይስ ሐዋርያውን? የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ከሦስት ዓይነት የሆነ አክሊል፤ ለነገሩ ከሦስት ዓይነት ብቻ ሳይሆን ከብዙ ወገን የተሠራ ኅብረ ብዙ የሆነ አክሊል ታትቶ በተቀደሰ ራሱ ላይ አስቀምጦለታልና፡፡ እያንዳንዳቸውን በጥንቃቄ ለሚመለከታቸው ሰው ሁሉንም አክሊላት ከሌላው አክሊል ጋር ለእኛ እያበሩና እያሸበረቁ ያገኛቸዋልና፡፡

2. እንግዲህ ፈቃዳችሁ ይሁንና መጀመሪያ የጵጵስናውን ክብር በተመለከተ ወደ መነጋገር እንምጣ፡፡ ይህ አንድ አክሊል ብቻ ይመስላችኋልን? እስኪ ዘርዘር አድርገን እንመልከተው፡፡ ከእርሱ ሁለት፣ ሦስት ከዚያም በላይ ብዙዎች አክሊሎች ሲገኙ ታያላችሁና፡፡ እርሱ ለዚህ ታላቅ ኃላፊነት የበቃ ሆኖ ስለመገኘቱ ብቻ አልደነቅም፤ ይህን ኃላፊነት ከእነዚያ ቅዱሳን (ከሐዋርያት) የተቀበለ በመሆኑም፣ የተቀደሱት የሐዋርያት እጆች የከበረች ራሱን የነኩት በመሆኑም እንጂ፡፡ ይህም ስለ እርሱ ክብር በተመለከተ የሚነገር ቀላል ነገር አይደለም፡፡ ብዙ ጸጋን ከላይ ያገኘ በመሆኑም ብቻ ሳይሆን፣ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ በዝቶ እንዲወርድ ስላደረጉ ብቻም ሳይሆን በሰዎች ያለ የመልካም ተጋድሎ ሕይወት እያንዳንዱ በእርሱ ያለ መሆኑን ስለ መሰከሩለትም ነው እንጂ፡፡

ሆኖም ዲያብሎስ ይህን ክፉ ነገር ብቻ ያደረገ አይደለም፤ ከዚህ ያላነሰ ሌላም አደረገ እንጂ፡፡ ይህም እንዲህ ነው፦ ጳጳሳቱ በሚያስተዳድሯቸው ከተሞች ውስጥ ብቻ እንዲታረዱ ያደረገ አይደለም፤ ወደ ሌላ ባዕድና ሩቅ አገር እንዲወሰዱና በዚያ እንዲገደሉ አደረገ እንጂ፡፡ ይህን ያደረገውም ከጓደኞቻቸውና ከሚያውቋቸው ሰዎች ተለይተው ብቻቸውን ሲሆኑ በጭንቀትና በፍርሃት ለመያዝ፣ ከመንገዱ ርቀት የተነሣ ደግሞ ለማዳከምና በሁሉም አቅጣጫ ኃይላቸውን በማሟጠጥ ድል ለማድረግ በማሰብ ነበር፡፡ በዚህ ቅዱስ ላይ ያደረገውም ይህንኑ ነው፡፡ ከከተማችን አውጥቶ ወደ ሮም እንዲሄድ አድርጎታልና፣ መንገዱን እጅግ የራቀ በማድረግ ሕሊናውን በመንገዱ ርቀትና በቀኑ ርዝመት ለማዳከም በማሰብ ነው፡፡ . . .

በመንገዱ የነበሩት ከተሞች ከሁሉም አቅጣጫ በአንድነት እየተሯሯጡ ወደ እርሱ በመምጣት አትሌቱን ያበረታቱትና የፍቅራቸው መግለጫ የሆኑ ብዙ ስጦታዎችን ያቀርቡለት ነበር፤ በጸሎታቸውና በምልጃቸውም ከተጋድሎው ተሳትፈዋል፡፡ ሰማዕቱን እንዲያ ባለ ዝግጁነትና ጥብዓት በሰማይ ወዳለ የመንግሥት ክብር ለሚጠራ ሰው እንደሚገባ በሐሤት ወደ ሞት ሲገሰግስ ባዩት ጊዜ፣ በዚያ ታላቅ ሰው ዝግጁነትና ደስታ፣ እርሱ ይገሰግስ የነበረው ወደ ሞት ሳይሆን ከዚህ ዓለም ለመውጣትና ረዘም ያለ ጉዞ የመንዝ ጉዳይና ወደ ሰማይ የማረግ ነገር መሆኑን የሚያስረዳ ከሆነው ከሕይወቱ ያገኙት መጽናናትና ጥቅም ቀላል የሚባል አልነበረም፡፡ በየደረሰበት ከተማም በንግግሩም ሆነ በድርጊቱ ይህንኑ እያስተማረ ሄደ፡፡ አይሁድ ጳውሎስን አስረው ወደ ሮም በላኩት ጊዜ እነርሱ ወደ ሞት ሰደድነው ብለው ቢያስቡም የሆነው ግን ከእነርሱ አሳብ በተቃራኒ በዚያ ለነበሩ አይሁድ መምህር እየላኩላቸው ነበር፡፡ በእግናጥዮስም የሆነው ይህ በበለጠ ሁኔታ ነው፡፡

እርሱን ለማመንና ስለ እርሱ ለመመስከር ሲሉ ሕያዋን ሰዎች አገራቸውን፣ ቤታቸውንና ዘመዶቻቸውን፣ ወዳጆቻቸውንና ሕይወታቸውን እንኳ ሳይቀር እንዲንቁ፤ ከአሁኑ ተድላ ደስታ ይልቅ መገረፍን፣ መከራንና ሞትን እስኪመርጡ ድረስ የተሰቀለውና የሞተው ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞቱ በኋላ ማሳመን መቻሉ በእውነትም የትንሣኤዉና የሕያውነቱ ታላቁ ማስረጃና ማረጋገጫ ነው፡፡ እነዚህ የሞተ ሰው ተግባራትና ውጤቶች አይደሉምና፡፡ በመቃብር የቀረ ሰው መገለጫዎችና ሥራዎችም አይደሉም፤ ከሞት የተነሣና የሕያው ተግባራት እንጂ፡፡ . . .

5. በሮም ይኖሩ የነበሩ ሁሉ ይህ ዝሃዳዊ እውነታ መሆኑን ያውቁ ዘንድ ቅዱሱ በዚያ ፍጹም ይሆን ዘንድ[128] እግዚአብሔር ፈቀደ፡፡ ሰማዕትነትን ከተቀበለ በኋላ ደግሞ ወደ እኛ[129] መለሰልን፡፡ ሰማዕቱን ለከተማዎች አከፋፈለው፡፡ ሮም ደሙ ሲንጠባጠብ ተቀበለች፣ እናንተ ደግሞ በአጽሙ መምጣት ደስ ተሰኛችሁ፡፡ እናንተ በጵጵስናው መንበርና አባትነት ደስ ተሰኛችሁ፣ እነርሱ ደግሞ በሰማዕትነቱ ደስ ተሰኙ፡፡ እነርሱ በውጊያ ላይ ሆኖ በዚያም ድል አድርጎ ሲሸለምና የሰማዕትነት አክሊል ሲደፋ አዩት፣ እናንተ ደግሞ የሁል ጊዜ አብሮነቱ አለላችሁ፡፡ ለጥቂት ጊዜ እግዚአብሔር ከእናንተ አራቀው፤ በታላቅ ክብር እንደገና መልሶ ለእናንተው ሰጣችሁ፡፡ ገንዘብ የሚበደሩ ሰዎች የወሰዱትን ገንዘብ ከወለድ ጋር እንደሚመልሱ ሁሉ እግዚአብሔርም እንዲሁ ይህን የእናንተን ዋጋው እጅግ የከበረ መዝገብ ለትንሽ ጊዜ በመውሰድ ለዚያች ከተማ ወስዶ ካሳየው በኋላ በበለጠ ክብር መልሶ ለእናንተው ሰጣችሁ፡፡ *ጳጳስ ላካችሁ፤ ሰማዕት ተቀበላችሁ፤ በጸሎት ሸኛችሁት፤ በክብር ተቀበላችሁት፡፡* ይህም እናንተ ብቻ ሳትሆኑ በመካከል ያሉ ከተሞች ሁሉ ናቸው፡፡

የከበረ ሰውነቱ (አጽሙ) በተመለሰላቸው ጊዜ ምን እንደ ተሰማቸውና እንዴት የተቀበሉት ይመስላችኋል ይሆን? ምን ዓይነት ደስታ ተፈጠረ? እንዴት ተደሰቱ? ድል አድራጊውን ሰማዕት በሁሉም አቅጣጫ በምን ዓይነት ሐሤት፣ እልልታና ደስታ ተቀበሉት? ተፎካካሪዎቹን ሁሉ ድል አድርጎ ከሩጫው ሜዳ በድል አድራጊነት የሚወጣን አትሌት ተመልካቹ በክብር እንደሚቀበሉትና መሬት እንዲረግጥ የሚተውት ሳይሆን በትካሻቸው ተሸክመው ወደ ቤት እንደሚወስዱትና በብዙ ዓይነት ምስጋና እንደሚያሞግሱት ሁሉ፣ ይህን ቅዱስ የተቀበሉት ከተማዎችም ከሮም ጀምሮ እስከዚች ከተማ ድረስ ተራ በተራ በትካሻቸው በመሸከም ድል አድራጊውን ሰማዕት በመዝሙር እያከበሩ በምስጋና እያጀቡ ተቀበሉት፡፡

ዲያብሎስ ደግሞ በሰማዕቱ ላይ አስቦ ያደረገው ተንኰልና ክፋት ለእርሱ (ለቅዱስ አግናጥዮስ) ክብር ጠቃሚ ሆኖ ዲያብሎስ ካሰበው በተቃራኒ ሆኖ ውጤቱ ተገልብጦበታልና በእርሱ ላይ ደግሞ በነገሩ ከንቱነት እየተሳለቁ ድል አድራጊውን ሰማዕት አጅበው ከዚህ ከተማ አደረሱት፡፡ ስለዚህም በእውነት ሁሉንም ከተማዎች ጠቀማቸው፣ አበረታታቸው፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ይህችን ከተማ አበልጽጓታል፡፡ ልክ ዘለዓለማዊ እንደ ሆነና ከውስጡ በየቀኑ ቢያወጡበትና ቢወስዱበት የማያልቅ መዝገብ ቢኖር በየጊዜው ከእርሱ የሚወስዱትን ሰዎች የበለጠ ባለ ጸጎች እንደሚያደርጋቸው ሁሉ ይህ የከበረ ቅዱስ አግናጥዮስም ወደ እርሱ የሚመጡትን ሁሉ በበረከት፣ በጀግንነት፣ በመንፈስ ጠንካራነት፣ በብዙ ልበ ሙሉነትና ቆራጥነት ሞልቶና አከብሮ ወደ ቤታቸው ይመልሳቸዋል፡፡ . . .

ስለዚህ መንፈሳዊ ፍሬዎችን ከእርሱ እናገኝ ዘንድ ዛሬ ብቻ ሳይሆን ሁል ጊዜ ወደ እርሱ እንሂድ፡፡ ወደዚህ በእምነት የሚመጣ የብዙ መልካም ነገሮችን ፍሬ ለመሰብሰብ ይችላልና፡፡ የቅዱሳን ሰውነታቸው ብቻ ሳይሆን መቃብራቸውም በመንፈሳዊ ጸጋ የተመላ ነውና፡፡ በኤልሳዕ ይህ የተፈጸመ ከሆነ፤ የሞተ ሰው አስከሬን መቃብሩን በነካ ጊዜ የሞትን ማሰሪያ በጥሶ እንደገና ወደ ሕይወት ተመልሷልና (2ኛ ነገ. 13፡21)፤ አሁን ጸጋ እግዚአብሔር በዝቶ በተሰጠበት፣ ኃይለ መንፈስ ቅዱስ የበለጠ ሥራ በሚሠራበት ዛሬ ደግሞ ከዚያ በበለጠ ሁኔታ በእምነት መቃብር የሚነካ ቢኖር የበለጠ ኃይል ያገኛል፡፡ ስለዚህ ምክንያት እግዚአብሔር የቅዱሳን አጽም በእኛ ዘንድ እንዲኖር ፈቀደልን፤ ይህም በእነርሱ እኛንም እነርሱን ወደ መምሰል እንነሣ ዘንድ እና ሁል ጊዜ ከሚደርሱብን ክፉ ነገሮች እንደ መጽናኛ ወደብ ይሆኑን ዘንድ ነው፡፡

128 ሰማዕትነትን ይቀበል ዘንድ፣ የሰማዕታትን ሞት ይሞት ዘንድ (In order then that all who dwell in Rome might learn that these things are a reality, God allowed that there the saint should be perfected . . .)

129 ወደ አንጾኪያ

ስለዚህ ሁላችሁንም እማጸናችኋለሁ፤ ማንም ተስፋ በመቁረጥ ሁኔታ ውስጥ ቢሆን፣ የታመመ ቢኖር፣ በስድብና በነቀፌታ ውስጥ ያለ ቢሆን፣ በሌላ በማንኛውም ዓይነት የዚህ ዓለም ሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ያለ ቢሆን፣ በኃጢአት ጥልቅ ውስጥ የወደቀም ቢሆን፣ በእምነት ወደዚህ ይምጣ፡፡ እነዚያን ነገሮች ሁሉ ወደ ጎን ይጥላቸዋል፤ ከማየቱ ብቻ ሽክሙ ቀሎት ሕሊናው ደስ ብሎት በብዙ ደስታ ይመለሳል፡፡

ከዚህም በላይ ደግሞ በችግር ውስጥ ያሉ ብቻ አይደሉም ወደዚህ ሊመጡ የሚያስፈልጋቸው፡፡ ነገር ግን በደስታ፣ በሥልጣን፣ በክብር፣ በኃይል ላይ ያለም ቢሆን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት አስተማማኝ ሊባል በሚችል ሁኔታ ላይ ያለም ቢሆን ከዚህ የሚገኘውን ጥቅም አያቃልል፡፡ ወደዚህ መጥቶ ይህን ቅዱስ በመመልከትና የእርሱን ግናና ሥራዎች በማዘከር ነፍሱን የተረጋጋችና ጭምት እንድትሆን በማሳመን እና ካደረጋቸው ታላላቅ ነገሮች የተነሣ ሕሊናው ራሱን ከፍ ከፍ ወደ ማድረግ ከንቱ ነገር እንዲሄድ ባለማሰናበት እነዚህን የያዛቸውን ሀብታት አጽንቶ መያዝና መጠበቅ ይችላልና፡፡ በብልጽግና ላሉ ሰዎች ባገኙት ነገር ራሳቸውን አለማስታበይና ከፍ ከፍ አለማድረግ፣ ነገር ግን ብፅላቸውን በትዕግሥትና ራስን በመግዛት እንዴት በመጠን እንደሚኖሩ ማወቅ ቀላል ነገር አይደለም፡፡

ባለ ጸጋዎችም ሀብታቸው ለሁሉም መገልገያ ሆኖ፣ ቤታቸው ለደከሙ ማረፊያ ሆኖ እነርሱም ሀብታት ከሚያመጡት ፈተናዎች ያመልጡ ዘንድና ብፅላቸው ተጠብቆ ይዘልቅላቸው ዘንድ፣ የታመሙት ደግሞ ይድኑ ዘንድ፣ ጤነኞችም ወደ በሽታ እንዳይወድቁ የሚጠቅማቸው ነው፡፡ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ግምት ውስጥ በማስገባት ጊዜያችንን በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ማሳለፍን እንምረጥ፡፡ ከእነርሱ ጋር አብረን በፍጹም ደስታና ሐሤት በመደሰት በማደሪያቸውም ሆነ በክብር ቤታቸው በሁለቱም ከቅዱሳን ጋር አብረን ተሳታፊዎች እንሆን ዘንድ፣ በራሳቸው በቅዱሳኑ ጸሎት፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰውን መውደድ፣ ከእርሱ ጋር ክብርና ምስጋና ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን፣ ዛሬም ዘወትርም እስከ ዘለዓለሙ ድረስ አሜን፡፡

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ - ምዕራፍ ስድስት (6) ውስጥ በቅዱሳን ዙሪያ የሚነሡ ብዙ ጉዳዮችን ዳስሰናል፡ ፡ ያነሣቸውን ጉዳዮችም በመጽሐፍ ቅዱስ እና በቅዱሳን አበው ሊቃውንት ትምህርት መሠረት ትክክለኛው አስምህሮ ምን እንደሆነ በሰፋት ተመልክተናል፡፡ ተሐድሶዎች በቅዱሳን ዙሪያ የሚያነሷቸውና የሚሏቸው ነገሮች አንዳንዶቹ ደረቅ ሐሰቶች፣ አንዳንዶቹ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌላቸውና እንዲሁ አገኝ አጣውን የተነገሩ ነገሮች፣ አሁንም አንዳንዶቹ ከእውቀት ማነስ ይሁን ሆን ብሎ ከማጥፋት ያልተባለውን እንደ ተባለ፣ የሚታመነው እንደ ሌለና እንደማይታወቅ አስመስሎ ለማቅረብ የተደረጉ ሙከራዎች ናቸው፡፡ ቀሪዎቹና በጣም ብዙዎቹ ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቅዱሳን አበው ሊቃውንት ትምህርት ጋር በቀጥታ የሚቃረኑ የስህተት ትምህርቶች መሆናቸውን በግልጽና በሰፋት አይተናል፡፡

ስለሆነም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምታምነው እምነቷና የምታስተምረው ትምህርቷ በመጽሐፍ ቅዱስ ያለውን እውነትና በቅዱሳን አበው ሊቃውንት የተብራራውንና የተመሠጠረውን ሕይወት ነው፡፡ ተሐድሶዎች ግን "እኔ የወይን ግንድ ነኝ፣ እናንተ ደግሞ ቅርንጫፎች ናችሁ" ካለው ከቅዱሳን አምላክ ከግንዱ ከክርስቶስ በክህደታቸው ራሳቸውን ቆርጠው ጥለዋል፡፡ ስለዚህም ከአንዱ የወይን ግንድ ከኢየሱስ ክርስቶስ ከበቀሉ ቅርንጫፎች ቅዱሳን ጋር ኅብረት የላቸውም፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከአበው ሊቃውንት ጋር የሚቃረነው የራሳቸው የፈጠራ ትምህርታቸው ሁሉ ከአምላክ ቅዱሳን ከኢየሱስ ክርስቶስና ከቅዱሳን አንድነት የተለዩ መሆናቸውን ይመሰክርባቸዋል፡፡

# ክፍል አራት

## በእንተ ምንኩስና ወሕይወት ገዳማዊ

## ምዕራፍ ሰባት

## ምንኩስና እና ገዳማዊ ሕይወት

እግዚአብሔር የተናገረውንና ቤተ ክርስቲያን የተቀበለችውን ነገር ሁሉ የመቃወምና የማፍረስ አባዜ የተጠናወታቸው ተቃዋሚዎች መሠረታዊ የሆነውን የመዳን ትምህርት ትክክል ባልሆነ ስኮላስቲካዊና ሉተራዊ አስተሳሰብ የለወጡ እንደ መሆናቸው በሌሎች ነገረ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸው እምነትና ትምህርትም የተበላሸ ነው። እስካሁን ለማየት እንደ ሞከርነው እግዚአብሔር ጸጋውን የምናገኝባቸውና የምንድንባቸው መንገዶች አድርጎ የሰጠንንና የሠራልንን ነገሮች፣ ከምሥጢረ ጥምቀት ጀምሮ ያሉትን ሁሉ ተሐድሶዎች አላስፈላጊ ነገሮች ማድረጋቸውን ራሳቸው ከጻፉት ማስረጃ እየጠቀስን ተመልክተናል። በመዳን ትምህርት ላይ ያላቸው የተበላሸና የተሳሳተ አስተሳሰባቸውና ትምህርታቸው በሌሎች ነገረ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይም የራሱን ጥላ ማጥላቱ አልቀረም፣ ሊሆንም የግድ ነው። ምክንያቱም ከመሠረቱ የተበላሸ ቤት የጸና መኖሪያ ሊሆን አይችልምና።

በዚህ ክፍል የምንመለከተው ደግሞ ተሐድሶዎች ከጥንት አንዳንድ መናፍቃን፣ በዋናነት ግን ከሉተር በወረሱት ወይም ሁሉም ከአባታቸው ከዲያብሎስ በወረሱት መሠረት ነገሮችን ባልተረዳ አእምሯቸው አንዱን ከአንዱ እያደባለቁ ሲያበለሿቸውና እግዚአብሔር የሰጠውን፣ አባቶቻችን ደግሞ የተቀበሉትንና የኖሩበትን የምንኵስናና ገዳማዊ ሕይወት በተመለከተ የሚያነሷቸውን ተቃውሞዎች ነው። እነዚህን ጉዳዮች እስካሁን በሌሎቹም እንዳደረግነው መጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት፣ በመቀጠልም በቅዱሳን አበው ሊቃውንት ትምህርት መሠረት እንመዝናቸዋለን። ከዚያም ተቃውሟቸውና ነቀፋቸው እውነት መሆን አለመሆኑ ግልጥ ይሆናል ማለት ነው።

### 7.1 በምንኵስናና በገዳማዊ ሕይወት ላይ ተቃዋሚዎች የሚያነሷቸው ነገሮች

ተሐድሶዎች በምንኵስናና ገዳማዊ ሕይወት ዙሪያ የሚያነሷቸውን ጉዳዮች ራሳቸው ከጻፉት እየጠቀስን እንመልከት። በመጀመሪያ የምናየው እነርሱ የሚሉትን ይሆናል፡ ከዚያ በኋላ በእያንዳንዱ ተቃውሟቸው ላይ ተገቢውን መልስ እንመለከታለን።

1) ምንኵስናና ገዳማዊ ሕይወትን "የስብከተ ወንጌል እንቅፋት ነው"፣ "ሰይጣን ያዘጋጀው ወጥመድ ነው" ማለታቸው፣

- "... በእጥሩ አነጋገር የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም ከተማ ገዳማዊ አኗኗር መሥርተው ለመኖር የወሰኑ መሰሉ፡፡ ... ሆኖም በሌላ በኩል እንደ ጌታ መመሪያ ወደ ዓለም ሁሉ የመሔድና ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ የማዳረስ ተልእኳቸውን የዘነጉ፣ በኢየሩሳሌም ተከማችተው በመቁነን (በድርጎ) ለመኖር <u>የወሰኑ የሚያስመስላቸው</u> አዝማሚያ በምእመናኑ ታይባቸው ነበር፡፡ ... *<u>ሥርዓቱ የጌታን ዓላማ የሚጻረር ስለ ነበረ</u>*፣ * አገልጋዮቹ ወደ ዓለም ሁሉ ይወጡና ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ይሰብኩ ዘንድ በኢየሩሳሌም የተከማቸውን ጉባኤ ምእመናን ጌታ መበተን ነበረበት፡፡ ... <u>የመጀመሪያዪቱን ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በሥርዓተ ገዳም አፍኖ ለማኖር፣ የዓለምም ሕዝብ ወንጌልን እንዳይሰማና እንዳይድን ለማድረግ ጠላት ያወጣውን እቅድ ያን ጊዜ ጌታ ባያፈርሰው ኖሮ ወንጌል ባልተሰበከ ነበር</u>*፡፡" (ሙራ ቁ. 11፣ ገጽ 28)

- "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ" በሚል ዋና ርእስ ሥር "ክርስትናን የሚያዳክሙ ተጨማሪ ነገሮች" በሚል ንኡስ ርእስ ለወንጌል መስፋፋት ችግር ከነበሩና ለክርስትና መዳከም ምክንያት ነበሩ ብለው ከዘረዘሯቸው ነገሮች አንዱ "ምንኩስና ነው" ይላሉ፡፡ (ጥንተ ብርሃን መጋቢት 2002፣ ገጽ 7-8)

ሆኖም ምንኵስናና ገዳማዊ ሕይወት በሰይጣን የተመሠረተ ሳይሆን ለስም አጠራሩ ክብርና ምስጋና ይግባውና በራሱ በጌታችንና በአምላካችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተ ነው፡፡ እንደ ገናም ምንኵስናና ገዳማዊ ሕይወት የወንጌልን መሰበክ ያደናቀፉ ሳይሆን ያስፋፉ፣ የስብከተ ወንጌል ጸር ሳይሆኑ ታላቅ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያደረጉ ናቸው፡፡ ይህን ወደፊት በ7.8 ላይ እናየዋለን፡፡

2) ወደ አንዳንድ የወንዶች ገዳማት ሴቶች እንዳይገቡ ክልክል (ግዝት) መሆኑን አጣምመው በመተርጎም ከቅድስናና ከብቃት ጋር ለማዛመድና የሴቶች ተቆርቋሪዎችና አዛኝ ቅቤ አንጓች ለመምሰል መሞከራቸው፣

- "በአንዳንድ ገዳማት ሴቶች ምእመናት ገብተው እንዳይሳለሙ እንዳይሳለሙም በግዝት ታግደዋል፡፡ በአጼ ዓምደ ጽዮን ልጅ በአጼ ሰይፈ አርዕድና በግብጻዊው ጳጳስ በአቡነ ሰላማ ግልሳይ '... እመቦ ዘአብአ አንስተ ውስተ ዝንቱ መካነ መጣዕ ... - አባ መጣዕ በመሠረቱት ደብረ ሊባኖስ በተባለው ገዳም ሴቶች እንዲገቡ ያደረገ ማንም ቢሆን ተወግዟል' በማለት ታወጀ፡፡" (ሙራ ቁ. 17 ገጽ 18)

- "በሀገራችን ሴቶች ቢገቡባቸው እንደሚያረክሷቸው እየተቆጠረ ለመግባት የተከለከሉባቸው ገዳማት ቁጥር ብዙ ነው፡፡ መቼም ወንዶች ምእመናንም ሆኑ ሴቶች ምእመናት ክርስቶስን እኩል የለበሱ በመሆናቸው በክርስቶስ እኩል የሚታወቁ ሆነው ሳለ ይህን በመሰለ ሁኔታ አንዱን የክርስቶስን አካል በመገነጣጠል ይኸኛው የአካልህ ክፍል ርኩስ ነው፣ ይኸኛው ቅዱስ ነው ማለት ለሕሊና የሚዘገንን ስድብ ነው፡፡ ... ሴቶች ምእመናት ግን ወደ ምድራዊ ጉባኤ ይቅርና ወደ መንግሥተ ሰማያት እንኳ ከወንዶች ጋር እኩል ይገባሉ፡፡" (ሙራ ቁ. 17፣ ገጽ 19)

- "በ5ኛው ምእት ዓመት ወደ ሀገራችን የገባው ሥርዓተ ምንኩስና ሥር እየሰደደ ሲሄድ በግልጽ የሚፈጸመው ቅዱሱ የጋብቻ ሥርዓት ተነወረ፤ በአንዳንድ ገዳማት የተቀደሰ ጋብቻ የመሠረቱ ቀሳውስት እንዳይቀድሱ መደረጉ ሳያንስ፣ ሴቶች ምእመናት ገብተው እንዳይሳለሙ እንዳይሳለሙም በግዝት ታግደዋል፡፡" (ሙራ ቁ. 17፣ ገጽ 18)

*በመጀመሪያ ያነሡት ነጥብ* - የሴቶች ወደ አንዳንድ ገዳማት እንዳይገቡ መከልከልን በተመለከተ ነው፡፡ ሴቶች ወደ አንዳንድ ገዳማት እንዳይገቡ የተከለከሉት በኢትዮጵያ ብቻ አይደለም፡፡ ይህ ባህል ኦርቶዶክሳውያን በሆኑ ምሥራቃውያን ዘንድም ያለ ጥንታዊ ባህል ነው፡፡ ስለዚህ በመጀመሪያ በኢትዮጵያ ብቻ የተፈጠረ ነገር አስመስለው ለማቅረብ መሞከራቸው ትክክል አይደለም፡፡ ይህ ሥርዓተ ገዳም የተጀመረውም በኢትዮጵያ ሳይሆን እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ "በዚህ ሥርዓት

መሠረት ወደ አንተ የሚመጡ መነኰሳት ገዳማውያንን በአንድነት ሰብስበህ አስተዳድራቸው" ብሎ በሰጠው ሥርዓት መሠረት የአንድነት ገዳማትን በመመሥረትና በማስፋፋት በሚታወቀው በትውልድ ግብጻዊ በሆነው በቅዱስ ጳኩሚስ (ከ296 – 346 ዓ. ም.) ነበር፡፡[130] ቅዱስ ጳኩሚስ በሕይወት ዘመኑ 9 የወንዶችና 2 የሴቶች ገዳማትን መሥርቶ ነበር፡፡ ወደ ወንዶቹ ገዳማት ሴቶች፣ ወደ ሴቶቹ ገዳማት ደግሞ ወንዶች አይገቡም ነበር፡፡ ይህ ሥርዓተ ገዳምም በፍልስጥኤም፣ በታናሽ እስያና በሌሎችም አካባቢዎች ይተገበር የነበረ ሥርዓተ ገዳም ነበር፡፡

ሴቶች ወደ ወንዶች ገዳም፣ ወንዶችም ወደ ሴቶች ገዳም እንዳይገቡ የተከለከለበት መሠረታዊ ምክንያት የገዳማዊ ሕይወት ዓላማና ባሕርይ ሴትና ወንድ ተደባልቆ ከመኖር ጋር የማይሄድ ከመሆኑ የተነሣ ነው፡፡ ገዳም ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ያጩና ከዚህ ዓለም ምኞትና ፍትወት ራሳቸውን ለማራቅና በብቸኝነት ሆነው ሰውነታቸውን ብቻ ሳይሆን መንፈሳቸውንና ሁለንተናቸውንም ለእግዚአብሔር ለመቀደስ በራሳቸው የወሰኑና የመረጡ ሰዎች በአት ነው፡፡ ስለሆነም ገዳማት የአባቶችና የእናቶች መነኰሳትና መነኮሳዪያት የጸሎት ቦታ እንደ መሆናቸው አንድ ላይ መደባለቁ ለመንፈሳዊ ሕይወት ረብህ (ጥቅም) ስለ ሌለው ነው እንጂ የጽድቅና የኃጢአት ወይም የአድልዎ ጉዳይ አይደለም፡፡ ጌታችን *"እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ወደ ሴት ያየ ሁሉ፣ የተመኘትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል"* ያለውን ትምህርት ለሚያምን ሰው ይህ ሥርዓት አግባብነቱ እንጂ አላግባብነቱ አይታየውም። ማቴ. 5፡28

ከዚያም በመቀጠል መድኃኒታችን "ቀኝ ዓይንህም ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት፤ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻልሃልና። ቀኝ እጅህም ብታሰናክልህ ቆርጠህ ከአንተ ጣላት፤ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻላል" በማለት የሚያሰናክሉ ነገሮችን እስከ ምን ድረስ ማራቅና መጨከን እንደሚገባ አስተምሮናል፡፡ ማቴ. 5፡29-30 ታዲያ ይህን አምላካዊ ቃል ለሚያምን ሰው በገዳማት ለምን ሴቶችና ወንዶች ተደባልቀው አይኖሩም? ሴቶችስ ለምን ወደ ወንዶች ገዳም እንደ ልባቸው አይገቡም? ብሎ መከራከር ይገባዋልን? ሆኖም ይህ ጉዳይ ተሐድሶዎችን አያሳስባቸውም፡፡ ምክንያቱም በእነርሱ ዘንድ ያመነ ሰው የፈለገውን ኃጢአት ቢሠራም መንግሥተ ሰማያት ከመግባት የሚያግደው ስላልሆነ፣ ጽድቅም ሆነ ኃጢአት ቢሠራም ከመዳኑ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም ባዮች ስለሆኑ ነው፡፡ ይህ "መንፈሳዊ ለሆነ ሰው በሰውነቱ ምንም ዓይነት ኃጢአት ቢሠራ ችግር የለውም፣ ጉዳትም አያስከትልበትም" የሚለው አስተሳሰብ መፍቀርያነ ፍትወት (Licentious) የነበሩት የግኖስቲኮች ቡድን እምነትና ፍልስፍና መሆኑን መጀመሪያ ላይ በመኃትው ላይ አይተናል፡፡

በጥንት የግብጽ ገዳማት (በተለይ በቅዱስ ጳኩሚስ ገዳማት) ወደ ሴቶቹ ገዳማት ወንዶች አይገቡ ስለ ነበር ከሴቶቹ ገዳማት ሰው ሲሞት እንኳ ሴቶቹ መነኰሳዪያት አዘጋጅተው ከገዳማቸው አውጥተው ነበር ለወንዶቹ መነኰሳት የሚያቀብሏቸው፡፡ ከዚያ በኋላ ወንዶቹ ተቀብለው ጸሎተ ፍትሐት አድርሰው ይቀብሩሉ፡፡ ስለሆነም እንደዚህ ዓይነት ሥርዓት ባላቸው ገዳማት አንዱ ወደ ሌላው ተላልፎ አይገባም፡፡ ወደ ሴቶች መነኮሳዪያት ገዳምም ወንዶች መነኰሳት አይገቡም፡፡ ከወንዶች መነኰሳት መካከል ወደ ሴቶቹ መነኮሳዪያት ገዳም የተወሰኑት ብቻ ተመርጠው እንዲገቡ የሚደረገው በራሳቸው በሴቶቹ ሊከናወን የማይችለውን የቅዳሴ አገልግሎት ለመፈጸም ብቻ ሲሆን እነዚያውም በመልካም ሕይወታቸው የተመሰከረላቸውና በእድሜም ገፋ ያሉ አረጋውያን አባቶች ብቻ ተመርጠው ነው፡፡

130 ገድለ ቅዱስ ጳኩሚስ

እንግዲህ ራሳቸው መነኰሳቱና መነኰሳዪያቱ እንኳ ገዳማቸው ተለይቶ አንዳቸው ወደ ሌላቸው ገዳም የማይገቡባቸው ገዳማት ያሉ ከሆነ፣ ሴቶች መነኰሳዪያት እንኳ ወደ ወንዶች መነኰሳት ገዳም መግባት የተከለከለ ከሆነ፣ ከዓለም ለጉብኝትና ለመሳለም የሚሄዱ ሴቶች ወደ ወንዶች ገዳማት እንዳይገቡ ቢሆን የሚገርመው ምን ነው? ገዳማት የተመሠረቱት ከዓለም ተለይተው ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሰጥተው ፈጣሪያቸውን በተከተተ ልቡና ለማገልገል ለሚፈልጉ ሰዎች እንዲሆኑ እንጂ በአሁኑ ዘመን በአንዳንዶች ዘንድ እንደሚታየው አስተሳሰብ ለጉብኝት (ለቱሪዝም) አይደለም፡፡
ስለዚህ ይህ ሥርዓት ከመደበላለቅና ከመቀላቀል የሚመጣን ነገር አርቆ ለማጠር የተደረገ እንጂ ከርኩሰት ወይም ከቅድስና ጋር የሚያገናኘው አንዳችም ነገር የለም፡፡ በመሆኑም ተሐድሶዎች *"በሀገራችን ሴቶች ቢገቡባቸው እንደሚያረክሷቸው እየተቆጠረ ለመግባት የተከለከሉባቸው ገዳማት ቁጥር ብዙ ነው፡፡ መቼም ወንዶች ምእመናንም ሆኑ ሴቶች ምእመናት ክርስቶስን እኩል የለበሱ በመሆናቸው በክርስቶስ እኩል የሚታወቁ ሆነው ሳለ ይህን በመሰለ ሁኔታ አንዱን የክርስቶስን አካል በመገነጣጠል ይኸኛው የአካልህ ክፍል ርኩስ ነው፤ ይኸኛው ቅዱስ ነው ማለት ለሕሊና የሚዘገንን ስድብ ነው"* በማለት ወደ ገዳም የሚገባ ቅዱስ፣ የማይገባ ደግሞ ርኩስ ነው እንደሚባል አስመስለው ያቀረቡት ደረቅ ሐሰት ነው፡፡ እንዲያው እግዚአብሔር እንደ ምድራውያን ሰዎች በሐሰት ስለ ከሰሱለትና እያስመሰሉ በማውራት ቤተ ክርስቲያኒቷን ስላሳጡለት "መልካም አደረጋችሁልኝ፣ አበጃችሁ" የሚላቸው ይመስላችዋልን? የማይባለውን እንደሚባል፣ ያለውን እንደ ሌለ እያስመሰሉ መጻፍና መናገር እንዲያው ከምራቸው እግዚአብሔርን ያስደስተዋል ብለው አምነውበት ነው? ሆኖም እንዲህ ባለ አካሄድ ለምድራዊ ዓላማቸው መሳካት ያሰማሯቸውን ሰዎች ካልሆነ በስተቀር እግዚአብሔርስ ሊደሰት እንደማይችል የታወቀ ነው፡፡ እርሱ ከሐሰትና ከዓመፃ መንገድ ሁሉ የራቀና ንጹሕ ነውና!

እርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሴቶችን ርኩስ አትልም፣ እንዲህ ያለ ነገር ከእርሷ የራቀ ነው፡፡ ይልቁንም ከፍጥረታት በላይ ከፈጣሪ በታች "ምልእተ ጸጋ" ተብላ የከበረችው፣ ንጽሕተ ንጹሐን ቅድስተ ቅዱሳን ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም ሴት መሆኗን እናውቃለን፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም እግዚአብሔር ሴቶችንም ወንዶችንም እኩል እንደሚወድና ይህንም በተግባር የገለጠ መሆኑን ታውቃለች፣ ታስተምራለችም፡፡ ለዚህም ዋናው ማሳያ እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሲሆን ሴት ከሆነች ከእመቤታችን በመወለድ ሴቶችን እንደሚወድድ አሳየ፣ ወንድ ሆኖ በመወለድ ደግሞ ወንዶችንም እንደሚወድድ አሳየ፡፡ ከዚህ በላይ የሴትነት ቅድስናና ክብር መገለጫ ከየት ይምጣ? ሴቶችን በእውነት ቢያከብሩማ ኖሮ የግድ ወደ ወንዶች ገዳም ካልገቡ እያሉ ነገሮችን ውጥንቅጣቸውን ለማውጣት ከመታገል ይልቅ የሴትነት ምንነት አክሊልና መገለጫ የሆነችውን ቅድስት ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክ ብለው ባከበሯት ነበር፡፡ በእርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ግን ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ ቅዱሳን ሴቶች ሰማዕታትም፣ ነቢያትም፣ ጻድቃን ገዳማውያንና ባሕታውያንም ነበሩ፣ ይኖራሉም፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም የብዙ ቅዱሳት እናቶችን ቅድስናና ተጋድሎ ታስባለች፡፡ ስለዚህ ወደ ሆነ ገዳም የመግባትና ያለመግባት ጉዳይ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ይጠቀሙናል መስሏቸው ካልሆነ በስተቀር ከቅድስናና ከርኩሰት ጋር የሚያገናኘው አንዳችም ነገር የለም፡፡

ይህ ትውፊትና ሥርዓትም በሌሎች ምሥራቃውያን የእርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትም ከጥንት ጀምሮ የነበረና ዛሬም ያለ ሥርዓት ነው፡፡ ለምሳሌ ግሪኮች "የአቶስ ተራራ - Mount Athos" የተባለ ሴቶች የማይገቡበት በጣም ጥንታዊ የሆነ ታሪካዊና ታላቅ ገዳም አላቸው፡፡ ይህ ገዳምም በግሪክ በጣም ታላቁ ገዳም ሲሆን በግሪክ ምሥራቃዊ ግዛት ባሉ የተያያዙ የተራራ ሰንሰለቶች የባሕሩን ጥግ ተከትሎ ያለ ታላቅ የገዳማት ሰንሰለት ነው፡፡ የአቶስ ተራራን "ቅዱሱ ተራራ" ይሉታል፡፡ የአቶስ ተራራ ግዛት ሰፊ ሲሆን ሙሉ በሙሉ የሚተዳደረውም በገዳማውያኑ ነው፡፡ ለግሪኮች የአቶስ ተራራ ማለት ከህልውናቸውና ከማንነታቸው ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ነው፡፡ ሆኖም ወደዚህ ገዳም ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ ሕፃናት ወንዶችም እንኳ አይገቡም፡፡

ሴቶች ወደ ገዳሙ እንዲገቡ ለማድረግ ይህ ዓይነት ነገር የማይገባቸውና ሊገባቸውም የማይፈልጉ ለሰብአዊ መብት ተቆርቋሪዎች ነን የሚሉ ግለሰቦችና ቡድኖች በሴቶች መብት ተቆርቋሪነት ሽፋን ኦርቶዶክሳዊና ምሥራቃዊ የሆነውን ይህን ሥርዓት ለማጥፋት ብዙ ተጽእኖ ለማሳደር ቢሞክሩም ገዳማውያኑና ሀገሪቱ ግን ለማንም ባለ መንበርከክ ትውፊታቸውን እስከ ዛሬም ጠብቀው ይዘው ይገኛሉ፡፡ አንድ የሃይማኖት ማኅበረሰብ "ይህ ጉዳይ ለእኔ ይጠቅመኛል፣ የእኔ ትውፊት ነው" እያለው ያለውን ነገር በዚያ ሃይማኖት የማያምንና በውስጡ ያልኖረበት ሌላ አካል በማያምንበት ጉዳይ ላይ ተነሥቶ "ይህ ይቅርባችሁ" የማለት የሕሊና ስንብትም ሆነ የሞራል አግባብነት እንዴት ሊኖረው ይችላል? ስለማያውቁትና ስላልኖሩበት ሕይወት ማውራት ነውርም አሳፋሪም ነው፡፡ እንዲህ ያለው "እኔ አውቅላችኋለሁ" የማለት ግብዝነት ነው፡፡

እስኪ እዚህ ላይ ተሐድሶ ነን ባዮቹን እንዲህ ብለን እንጠይቃቸው፡- "ሴቶች ለምን ወደ ወንዶች ገዳም መግባት ተገለከሉ?" ብላችሁ የሴቶች መብት ተሟጋች ለመምሰል የምትሞክሩ ተሐድሶዎች፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ "ሴቶች በማኅበር ዝም ይበሉ፤ ሕግ ደግሞ እንደሚል እንዲገዙ እንጂ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውምና። ለሴት በማኅበር መካከል መናገር ነውር ነውና፡ ምንም ሊማሩ ቢወዱ በቤታቸው ባሎቻቸውን ይጠይቁ" የሚለውን ቃል ታምኑበታላችሁ ወይ? 1 ቆሮ. 14፥34-35 እንደዚሁም "ሴት በነገር ሁሉ እየተገዛች በዝግታ ትማር፤ ሴት ግን በዝግታ ትኑር እንጂ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሰለጥን አልፈቅድም። አዳም ቀድሞ ተፈጥሯልና፣ በኋላም ሔዋን ተፈጠረች" የሚለውንስ ታምናላችሁ? 1 ጢሞ. 2፥11-13 ምናልባት የምታምኑበት ከሆነ ለምን እንዲህ ተባለ? ሴቶች በጉባኤ ሊያስተምሩ አይገባም መባሉ አንዱን የክርስቶስን አካል መገነጣጠል ኖሯልን? ሴቶችን ዝቅ ማድረጉና ማኩሰሱስ ኖሯልን? ባልተረዳ አእምሮና በጠማማ መንፈስ ለሚያየው ሊመስለው ይችል ይሆናል፤ የእግዚአብሔር ቃል ሃሳብ ግን እንደዚያ አይደለም፡፡ እንደ ክርስትና ሴቶችን የሚያከብር በዚህ ምድር ላይ አንዳችም ነገር የለም፤ ግን ለገባውና ላመነበት ነው፡፡ ሆኖም ለበለጠ ነገር ሲባል የሚሠሩ ሥርዓቶችን የማይረዱና ሥር መሠረቱ ሳይገባቸው የሰሟቸውን "መብት፣ እኩልነት" ወዘተ የሚሉ ቃላትን እንደ ገደል ማሚቶ መልሰው በሚያስተጋቡ ሰዎች ዘንድ ግን ይህ የተሰወረ ነው፡፡

እንዲያው ለነገሩ "ሴቶች ገብተው እንዳይሳለሙ ለምን ተከለከሉ?" ብላችሁ የምትቆረቆሩት ገዳማትን በመሳለም በረከት እንደሚገኝ አምናችሁ ያ በረከት ቀረባቸው ብላችሁ ነው? ወይስ እንዲያው ቤተ ክርስቲያኒቱን ለመንቀፍና ለማሳጣት፣ ሰዎችም እንዲጠሏት ለማድረግ ይጠቅማል የምትሉትን ነገር ሁሉ ከመጠቀም ስልት የመጣ ነው? በአንድ በኩል ገዳማትን መሳለም እንደማይገባ ትናገራላችሁ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች ገዳማትን ገብተው እንዳይሳለሙ ተከለከሉ ትላላችሁ፡፡ ነገራችሁ ሁሉ የሚገርም ነው! ገብቼ እንዳልሳለም ተከለከልሁ ማለት ያለበት ሰው (ማለት እንኳ ቢኖርበት) ወደ ገዳማት መሄድና መሳለም ተገቢ አይደለም እያለ የሚከራከር እንደ እናንተ ዓይነት ሰው ነውን?

"በአጼ ዓምድ ጽዮን ልጅ በአጼ ሰይፈ አርዕድና በግብጻዊው ጳጳስ በአቡነ ሰላማ ግልሳይ ' . . . እመቦ ዘእብእ አንስተ ውስተ ዝንቱ መካነ መጣዕ . . . - አባ መጣዕ በመሠረቱት ደብረ ሊባኖስ በተባለው ገዳም ሴቶች እንዲገቡ ያደረገ ማንም ቢሆን ተወግዟል' በማለት ታወጀ" ያላችሁት ጉዳይ ገዳሙ ሲመሠረት የወንዶች ገዳም ሆኖ የተመሠረተ ስለ ሆነ በገዳሙ ሥርዓት መሠረት ሴቶች ወደ ወንዶቹ ገዳም እንዳይገቡ ቢደረግ ነውሩ ምን ላይ ነው? ለቅድስና መጠንቀቅና የኃጢአት በር እንዳይሰፋ አርቆ ማጠር ይሻላል? ወይስ በሩን ወለል አድርጎ መክፈት? እንደ ተሐድሶዎቹ ከሆነ የሚሻለው ይህን ሥርዓት ማጥፋት ነው፡፡ ምክንያቱም ከሚፈጠረው ችግር ገዳማትን ለማዳከምና መንፈሳዊ ሕይወትን ለመሸርሸር፣ ብሎም ኦርቶዶክሳዊውን ትውፊት በማጥፋት በሀገሪቱ ላይ ለላኳቸው አካላት ተስማሚ የሆነ እምነትንና ባህልን ለማስፈን ለተያያዙት ዘመቻ በሰፊው ይረዳቸዋልና ነው፡፡ በዚያውም ላይ መንፈሳዊ ተጋድሎና የአንድ ሰው ሥራው ምንም ዋጋ የላቸውም እያሉ በማስተማር ሕዝቡን ከመዳን መንገድ ውጭ እንዲሆን ለያዙት ዘመቻ ገዳማትን ደግሞ በማደበላለቅ ቅድስና እንዲጠፋና ርኩሰት እንዲስፋፋ ይረዳናል ብለው ነው፡፡

ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ ወደ ጉባኤ መግባት አለመግባትን ወደ መንግሥተ ሰማያት ከመግባት አለመግባት ጋር አዋርሰው ማቅረባቸው ነው፡፡ ወደ ጉባኤ መግባት አለመግባትና ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት አለመግባት የተለያዩ ናቸው፡፡ በብሉይ ኪዳን እስራኤላውያን ሴቶችም ወንዶችም የጉባኤ አባላት ነበሩ፤ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚገባው ግን አንድ ሰው ብቻ - ሊቀ ካህናቱ - ነበር፡፡ ያውም እርሱም የሚገባው በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ ካህናቱና ሌዋውያኑ እንኳ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ መቼም መች አይገቡም ነበር፡፡ ሌላው ሕዝብ ሴቶቹ ብቻ ሳይሆኑ ወንዶቹም፤ ሌዋውያኑና ካህናቱም ጭምር ወደ ቤተ መቅደስ አይገቡም ነበር ማለት ግን የእስራኤል ጉባኤ አባል አልነበሩም ማለት አልነበረም፡፡ ስለዚህ ሴቶች የቤተ ክርስቲያን አካል መሆናቸው አንድ ነገር ነው፤ ወደ ወንዶች ገዳም መግባትና አለመግባት ግን ሌላ ነገር ነው፡፡ ስለዚህ እንዲህ ያለ ሥርዓት ባላቸው ገዳማት ዘንድ ሴቶች መነኩሳዪያትም ሆኑ ምእመናት ወደ ወንዶች መነኩሳት ገዳም አለመግባታቸው፤ ወንዶች መነኩሳትም ወደ ሴቶች መነኩሳዪያት ገዳም አለመግባታቸው የአንዲቷ ቤተ ክርስቲያን አካል አይደሉም አያሰኝም፡፡

ከላይ እንዳነሣነው ቅዱስ ጳውሎስ ሴቶች በጉባኤ ዝም ይበሉ ስላለ የአንዲቷ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ አባል አይደሉም ማለቱ አልነበረም፡፡ ይኸው ሐዋርያ በሌላ መልእክቱ ላይ "... ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና" ብሏልና፡፡ ገላ. 3፡28 ስለዚህ በቆሮንቶስ መልእክቱ እና ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክቱ ላይ ያን ያለበት ተግባራዊ ምክንያት ስለ ነበረው እንጂ አንዲቷን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለመነጣጠል አልነበረም ማለት ነው፡፡ እንደዚሁም ሴቶች ወደ አንዳንድ የወንዶች ገዳማት አይግቡ የተባለበት ምክንያቱ ተግባራዊ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ ስለዚህ "ሴቶች ምእመናት ግን ወደ ምድራዊ ጉባኤ ይቅርና ወደ መንግሥተ ሰማያት እንኳ ከወንዶች ጋር እኩል ይገባሉ" ያሉት ነገር ምንም ግንኙነት የሌለው ባዶ ሃሳብ መሆኑን ስናስታውሳቸው በትሕትና ነው፡፡

ተሐድሶዎች እንዲያው በእውነት የተቆረቆሩት ለምን ሴቶች ወደ ገዳም ገብተው በረከት እንዳያገኙ ወይም ወደ ገዳሙ ገብተው በምናኔ እንዳይኖሩ ተከለከሉ ብለው ነው? ወይስ ለምን ገዳም የሚባል ነገረ ኖረ ብለው? በአንድ በኩል ምንኩስና የሚባል ነገር ለምን ኖረ? ጸረ ወንጌል ነው፤ ... እያሉ ይከሳሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለምን ለሴቶች ወደ ወንዶች ገዳማት እንዳይገቡ ተከለከሉ? ይላሉ፡፡ ሙሴ ሰባውን ሽማግሌዎች ወደ ሲና ተራራ ይዟቸው ሲወጣ ኤልዳድና ሙዳድ የተባሉትን ሁለቱን ከታች ትቷቸው የወጣበት ምክንያት የመብቃትና ያለመብቃት ጉዳይ መሆኑ አልተጻፈልንም፡፡ ጌታችንም ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ መካከል ወደ ደብረ ታቦር ይዟቸው የወጣው ሦስቱን ደቀ መዛሙርት (ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን) ብቻ ነበር፡፡ ለምን እንደዚያ እንዳደረገ የሚያውቀው ግን እርሱ ራሱ ብቻ ነው፡፡

ነገር ግን እንዲህ እርሱ ባወቀ የሚሠራቸውን ነገሮች ሁሉ በዘመነ ተሐድሶ የተነሡና አሁን ከክርስትና ጋር ዓይንና ዐፈር የሆኑ የተለያየ ርእዮት አራማጅ የሆኑ ሰዎች በሚያዩበት የተበላሸና የዛገ መነጽር እያየን ሁሉንም ነገር ከመብትና ከይገባኛል አንጻር አናይም፡፡ ለምሳሌ መብቱ ነው ተብሎ ሁሉም ሰው በአንድ ጊዜ ልናገር ካለ መደማመጥ እንዴት ይቻላል? ወይም በስብሰባ አንዱ ሰው ብቻ መላውን ጊዜ ከወሰደው ሌሎች ተሳታፊዎች ሃሳባቸውን የመግለጽ ዕድል እንዴት ያገኛሉ? ስለዚህ ለሁለንተናዊ ጠቀሜታና ለበለጠ ነገር ሲባል የሚገደቡ መብቶች መኖራቸው ግልጽ ነው፡፡ "መብት" እና "እኩልነት" የተባሉ ነገሮች በራሳቸው ክፉት ባይኖራቸውም አሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ በትላልቅ ቻናሎች ሳይቀር እየተራገቡና እየተቀነቀኑ ያሉበት ሁኔታ ግን በእውነትና በቅንነት ላይ የተመሠረተ የመሆኑ ነገር አሳሳቢ፤ አጠያያቂም ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ነገሮች ሰዎች ለምን ተልእኮ ማሳኪያነት ሊጠቀሙባቸው እንደሚፈልጉና ከጥንቱ የተጀመሩበትንና ያደጉበትን የት መጣና ነባራዊ ሁኔታ ከመሠረቱ መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡

ስለዚህ ተሐድሶ ወገኖቻችን ሆይ፣ በማታውቁት ነገር ገብታችሁ የራሳቸው ስውር ዓላማ ያላቸው ሰዎች ለዓላማቸው መሳካት የዘረጉትን ረጂም ገመድ እንዘላለን ብላችሁ እንዳትጠለፉ ቆም ብላችሁ ብታስቡበት ጥሩ ይመስለናል፡፡ እንዲህ የምንለው ግን ከመካከላችሁ ለእውነት ልቡን የሚሰጥና ከተጫነበት ጉዳይ ወጣ ብሎ ማየት የሚችል ነጻ ሰው ካለ ነው፡፡

3) ምንኵስናና ገዳማዊ ሕይወት የሕንዳውያን ፍልስፍና ነው ማለታቸው

◉ "ምንኩስና ሥርዓተ መላእክት?" በሚል መጠይቃዊ ርእስ ይጀምርና ሲቀጥል እንዲህ ይላል፦ "በተባሕትዎና በገዳማዊ ሕይወት መወሰን ራስን ለመግዛትና ወደ ከፍተኛ መዓርገ ጽድቅ ለመድረስ መሰላል ነው የሚለው የቀድሞ ሕንዳውያን ፍልስፍና ከቦታ ወደ ቦታ በመሸጋገር መልኩንም በመለዋወጥ ወደ ክርስትና ተሸጋገረ፡፡ መካከለኛውን ምሥራቅም አቋርጦ ወደ ግብጽ ገባ፤ በገዳመ አስቄጥስ ስሙንና መልኩን እንደገና በመለወጥ 'ሥርዓተ ምንኩስና' ተሰኝቶ ወደ ሌላው ክፍለ ዓለም ተዛዋወረ፡፡ በተሰዓቱ ቅዱሳን አማካይነትም ወደ ኢትዮጵያ ገባና የነዋሪነት ፈቃድ ተሰጠው፡፡ ምንኩስና ከአረማውያን ፍልስፍና የሆነውን ይህን ሥርዓት . . . ሥርዓተ መላእክት ነው ይሉታል፡፡ ምንኩስናን በወንጌል ቀቅለ ለመቀባበት የምትደረገዋን ማመሳሰል ግን ምሁራት "ይቺ፣ ይቺ . . . ናት" ይሏታል፤ አልተቀበሏትም፡፡ አንዳንዶቹ ምሁራንማ ላላወቀሽ ታጠኚ ብለዋታል፡፡" (ጮራ ቁ. 15፣ ገጽ 30-31)

ይህን ነጥብ ወደፊት በ 7.6 ላይ እንመለከተዋለን፡፡

4) አንድ ሰው ሲመነኩስ የሚፈጽመውን ሥርዓትና የሚገባውን ብጽዓት በኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘውንና ገንዘብ ያደረገውን መዳን መካድና ሌላ ተቃራኒ ባእድ ነገር አስመስለው ለማሳየት መሞከራቸው፤

◉ "ከክርስቶስ ጋር በመሞትና በመነሣት የሚያሳትፈኝ ጥምቀትና ለዚህም ያበቃኝ እምነት ወደ ፍጹም መዓርገ ጽድቅ እያደረሰኝም" ብለው ይክዳሉ፡፡" ይላሉ፡፡ ከዚህም ጋር በምንኩስና ራስን ለዚህ ዓለም ምውት ማድረግን ራስን በራስ ማዳን ብለውታል፤ "ራሴን በማስጨነቅ መዳንንና መጽደቅን ገንዘብ ማድረግ አለብኝ፤ እኔ ለራሴ በራሴ ሞትን በሚመስል ሞት እሞታለሁ" በማለት ለሁለተኛ ሞት ራሳቸውን ይገንዛሉ፣ ያስገንዛሉ፡፡ ትንሣኤና ሕይወት የሌለበት ሞት መሆኑ ነው!!" (ጮራ ቁ. 6፣ ገጽ 7)

➢ በአንድ በኩል ጥምቀት እንደ አባልነት መታወቂያ ነው እንጂ ሌላ ጥቅም የለውም ይላሉ፡፡ እዚህ ላይ ደግሞ "ከክርስቶስ ጋር በመሞትና በመነሣት የሚያሳትፈኝ ጥምቀት" ይላሉ፡፡ የተሐድሶዎች አንዱ ችግር ይህ ነው፡፡ ቋሚ የሆነ የመሠረተ እምነት አስተምህሮ ስለ ሌላቸው ደስ እንዳላቸው መናገር ልማዳቸው ነው፡፡ ይህ የፕሮቴስታንቲዝም አንዱና ዋናው ችግሩ ነው፡፡ ሐዋርያት ከጌታችን ተቀብለው ለቀጣዮቻቸው ያወረሷቸውና እነዚያም ለቀጣዮቻቸው እያወረሱ ከእኛ ዘንድ የደረሰው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አረዳድ ስለሌላቸው እያንዳንዳቸው እንዳሻቸው ይናገሩበታል፡፡

◉ "ሥርዓተ ምንኩስና ግን በጌታ የተገኘውንና በእግዚአብሔር ጸጋ በወንጌል የተገለጠውን የሰውን ደኅንነት በማናናቅ "እጸድቅ ያለ መንኩሶ፣ እካስ ያለ ታማሞ" ያሰኘ ልዩ ወንጌል ነው፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ካልሆነ በቀር በሌላ በማንም ደኅንነት እንደሌለ የሚያውቅ ሰይጣን፣ የግብር ልጆቹ የሆኑ ሰዎች ከእጁ እንዳይወጡ በማሰቡ ዓይነ ልቡናቸውን ከኢየሱስ ክርስቶስ ላይ አንስተው እርሱ በፈጠረው ሥርዓተ ምንኩስና ላይ እንዲያሳርፉ አደረገ፡፡ ይልቁንም በክርስትናቸው መጀመሪያ ላይ ከክርስቶስ ጋር መሞታቸውን መነሣታቸውን ያወጁበትን የጥምቀት ቃል ኪዳን በማስካድ ለሥርዓተ ምንኩስና በግል መሞትን የሚያሳይ ሥርዓትን እንዲፈጽሙ አደረጋቸው፡፡ <u>እንደ እውነቱ ከሆነ ምንኩስና ከዚህ ባሕርዩ የተነሣ አዲስ እምነት፣ ልዩ ወንጌል መሆኑን በይፋ አሳውቆ ቢሆን ኖሮ</u> . . . በክርስትና ጃንጥላ ሥር ተጠልሎ አሁን ያደረሰውን ጉዳት ያህል ሊያደርስ ባልቻለ ነበር፡፡" (ጮራ ቁ. 18 ገጽ 19-20)

በመቀጠልም ስለ ምንኵስና ሐተታቸውን በማራዘም እንዲህ ይላሉ፦ "... ምንኩስና ለአገልግሎት ወይም ለኑሮ የእግዚአብሔር ጥሪ አይደለም፡፡ "ጽድቅ በክርስቶስ የቤዛነት ሥራ በማመን ብቻ የሚገኝ እግዚአብሔር ስጦታ ነው" የሚለውን በመቃወም "ጽድቅ በሥርዓተ ምንኩስና ውስጥ ገብቶ በመጋደል ይገኛል" የሚል ፍልስፍና ነው፡፡" (ጥንተ ብርሃን፣ መጋቢት 2002፣ ገጽ 7-8)

- "ተሰዓቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ሰው በሥርዓተ ምንኩስና ፍጹም ወደ ሆነው መዓርገ ጽድቅ ይደርሳል የሚል ስብከት አስፋፍተው ከሰበኩበት ከስድስተኛው ምእት ዓመት ጀምሮ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በሰው ኃጢአት የመጣ ዕዳ ሞት የተከፈለ መሆኑን መገንዘብና ማመን ከተራው ሰው ይቅርና ከቤተ ክርስቲያን መምህራን እንኳ ተሰውሮ ነበር፡፡ ሰው በሚያደርገው ተጋድሎ በኃጢአቱ ሊቀበለው የሚገባውን ዕዳ ሞት ለመክፈል ዕውር ድንብሩን የሚቅበዘበዝበት ጨለማ በቤተ ክርስቲያን ሰፍኖ ነበር፡፡ ጎድገ እንበሳም (የኋላው አባ እስጢፋኖስ) ለመጽደቅ ሲል ወደ ቆየጻ ገዳም ገባ፣ በዚያ መንኩሶ አባ እስጢፋኖስ የሚል አዲስ ስም ወጣለት፡፡" (ሙራ ቁ. 18፣ ገጽ 19-20)

በሌላ በኩል ደግሞ፦

- "ኦርቶዶክሳውያን በእምነታቸው ምክንያት የሁለት ባሕርይ ባህለ ሃይማኖት ተከታዮች (ካቶሊኮች) ከሚደርስባቸው ጭቆና ለመሸሽ በየአቅጣጫው በሚሰደዱበት ጊዜ ዘጠኝ መነኰሳት ከሮም ግዛት በመነሣት ወደ ኢትዮጵያ ገቡ፡፡ ... የአንድ ባሕርይ ባህለ ሃይማኖት ተከታይ ወደ ሆነችው ወደ ኢትዮጵያ መጡ፡፡ ኢትዮጵያም ለአንድ ባሕርይ ባህለ ሃይማኖት ለተሠዋው ለዲዮስቆሮስ ትምህርት ታማኝ በነበረችው በእስክንድርያ መንበረ ሊቀ ጵጵስና ሥር "ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ" በሚል እምነት የጸናች ነበረችና የመነኰሳቱን እምነት ከንጉሡ ጋር የመረመረውና የተቀበለው ጳጳስ ያው እንደ ተለመደው እስክንድርያዊ እንደ ነበረ ጥርጥር የለውም፡፡ ... ይህ ታሪክ ሲጠቀስ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው በኢትዮጵያ ጳጳሱም፣ ንጉሡም፣ ምእመናኑም እንግዶቹ ዘጠኙ መነኰሳት ጭምር ከመንበረ እስክንድርያ ያላፈተለኩ፣ ከአንድ ባሕርይ ባህለ ሃይማኖት ዝንፍ ያላሉ መሆናቸውን የሚያመለክት ሌላው ማስረጃ እንደ ሆነ በማመን ነው" በማለት ለምስክር ገድለ ገሪማን፣ ገድለ ቅዱስ ያሬድን እና ስንክሳርን ጠቅሰዋል፡፡ (ሙራ ቁ. 11፣ ገጽ 21-22)

- ልብ ወለዳዊ ትረካ በሚመስል መልኩ "አባ እገሌ የሚባል መነኩሴ እንዲህ ... እንዳደረገ እገሌና እገሊት ለሚባሉ ባልና ሚስቶች ጉዳን ሁሉ ዘርዝሮ ተናገረ" በማለት መነኰሳትን ወንጀለኞች አድርገው ለመሳል ሞክረዋል፡፡ የጸፉትን እጅግ ጸያፍ የሆነውን ነገር እንተወውና ወደ ማጠቃለያው ካለው ትንሽ እንጥቀስ፦
  - "... ግን እኛ እኮ ከሰው በምን እንለያለን? ሰው የሚያደርገውን ነው የምናደርገው፡፡ በእኛ ላይ ሲሆን ለምን ይገንብናል? <u>ቆቡ እንደ ሆነ ለመኖር ስንል የምንጭነው ነው</u>፣ ተለውጠን እንደ መላእክት አንሆን፡፡ ኅብረተሰቡ የተቀበለውና ያመነበት ስለሆነ ለመኖር ስንል በዚህ መንገድ መቅረብ ተገደድን፣ እያሉ የቆጥ የባጡን ዘላበዱ፡፡ ... ከዚያም [እነዚያ ባልና ሚስቶቹ] ቤተ ክርስቲያናቸው የክርስትና መልክ (ቅርጽ) እንጂ ይዘት የሌላት መሆኑን ተማመኑበት፡፡" (ሙራ ቁ. 20፣ ገጽ 24-25)

ተሐድሶዎቹ በምንኵስናና በገዳማዊ ሕይወት ዙሪያ የሚያነሷቸውን ነገሮች ካየን አሁን ደግሞ እነዚህን ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስና በአበው ትምህርት መሠረት ወደ መመዘኑ እንሂድ፡፡

## 7.2 ምንኵስናና ገዳማዊ ሕይወት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

### 7.2.1 የምንኵስና እና የገዳማዊ ሕይወት ምንነት

የምንኩስና ሕይወት ማለት ራስን ለእግዚአብሔር ብቻ በመስጠት መኖር ማለት ነው፡፡ በዚህ ዓለም ካሉ ነገሮች መካከል ማንኛውም ክርስቲያን ሊርቃቸውና ሊተዋቸው የሚገቡ ነገሮች እንዳሉ ሁሉ ሊያደርጋቸው የተፈቀዱና ኃጢአት ያልሆኑ ነገሮችም አሉ፡፡ በምንኩስና ሕይወት ለመኖር የሚወስን ሰው ግን ማንኛውም ክርስቲያን ሊርቃቸው ከሚገቡ ነገሮች ብቻ ሳይሆን ለሌላው ክርስቲያን ከተፈቀዱት ነገሮችም በራሱ ምርጫና ውሳኔ ስለሚበልጠው ነገር ሲል ራሱን ይከለክላል፡፡ከዚህም አንዱ ጋብቻ ነው፣ እርሱ ብቻ ግን አይደለም፡፡

ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋብቻን ታከብራለች፡፡ በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ጋብቻ ከምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን መካከል አንዱ መሆኑ ይህን የተሰጠውን ታላቅ ቦታ የሚያመላክት ነው፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ጠላት ከነገራቸው ክፋትና ከውጭ ሆነው በልማድ ሲመለከቱት ከኖሩት ነገር በስተቀር ወደ ውስጧ ገብተው እውነተኛ ማንነቷን የማያውቋት ተሐድሶዎችና መሰሎቻቸው እንደሚሉት ጋብቻን አቃልላና ነቅፋ አታውቅም፤ አታቃልልምም፤ አትነቅፍምም፡፡ ምንኩስናና ገዳማዊ ሕይወት ክቡር ነው ማለት ጋብቻ ክቡር አይደለም ማለት አይደለም፤ ስለ ምንኩስና ክብር መናገር ጋብቻን ማቃለል አይደለም፡፡ ጌታችን በበረሓ አርባ ቀንና ሌሊት ከተጋደለ በኋላ የመጀመሪያውን ተአምር ያደረገውና የተገኘው በቃና ዘገሊላ ሠርግ ላይ ነበር፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ በቅዳሴ ሰዓት "እኛስ ጋብቻ ክቡር እንደ ሆነ፣ ልደትም ርኩሰት እንደ ሌለበት . . . እናምናለን" እያለች ትመሰክራለች፡፡ ስለዚህ የአንዱ መኖር ሌላውን ያከብረዋል እንጂ አያቃልለውም፡፡ የግድ አንዱን ለማክበር ሌላውን ማቃለል ወይም ይጥፉ ማለት ተገቢ አይደለም፡፡ ሁሉንም በየአግባቡ መረዳት እንጂ ማደባለቅና ግራ ተጋብቶ ግራ ማጋባት ትክክል አይደለም፡፡

የምንኩስና ሕይወት መሠረታዊ ምክንያቶችና ጠባያት በዋናነት የሚከተሉት ናቸው፡፡

1) ክርስቶስን በሄደበት ሁሉ መከተል

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተጠመቀ የማስተማር አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት የመጀመሪያ ተግባሩ ያደረገው ነገር ቢኖር ወደ በረሓ (ምድረ በዳ) መሄድን ነበር፡፡ ቅዱስ ወንጌል *"ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው፣ አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ ተራበ"* ይላል፡፡ ማቴ. 4፥1-2 ወደ በረሓ የሄደውም በመንፈስ መሆኑ የተጻፈልን ያለ ምክንያት አይደለም፤ *"ወዲያውም መንፈስ ወደ ምድረ በዳ አወጣው"* ይላልና፡፡ ይህም ማለት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተግባር ባሳየው አብነት መሠረት ለመንፈሳዊ ተጋድሎ ወደ ምድረ በዳ (በረሓ) የሚሄዱ ሰዎች ድርጊታቸው ከመንፈስ ቅዱስ መሆኑን የሚያስተምር ነው፡፡ እንዲሁም ጌታችን በዚያ በበረሓው አርባውን ቀናት እንዴት እንዳሳለፈ ሲናገር *"በምድረ በዳም ከሰይጣን እየተፈተነ አርባ ቀን ሰነበተ፤ ከአራዊትም ጋር ነበረ"* ይለናል፡፡ ማር. 1፥12-13

ገዳማዊ ሕይወት፣ ወደ በረሓ ሄዶ በጾምና በጸሎት መጋደል የማያስፈልግና የማይገባ ቢሆን ኖሮ ጌታችን ከማስተማሩ በፊት እንደ ተጠመቀ ለምን ወደ በረሓ ሄደ? ለምንስ በዚያ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከሰይጣን መፈተን አስፈለገው? ለምንስ በዚያ "ከአራዊት ጋር ነበር" ተባለ? እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈልን ለእኛ ጥቅም በመሆኑ ይህን በሙሉ ልብ ማመንና በጥንቃቄ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ ወደ በረሓ መሄዱ ሌላ ቦታ አጥቶ ወይም እንዲሁ ያለ ምክንያት ያደረገው ድርጊት አልነበረም፡፡ ይህ ብዙ ጥልቅ ምክንያቶች ነበሩት፣ ያስከተለው ውጤትም እንዲሁ ድንቅና መጠነ ሰፊ ነው፡፡

ከዚያም በኋላ ጌታችን በመዋዕለ ሥጋዌው በፍልስጥዔም ምድር ባሉ በረሓዎችና ተራራዎች ብዙ ጊዜያትን አሳልፏል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ብቻውን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እኛን ለማስተማርና አርአያ ለመሆን ወደ ምድረ በዳ ይሄድ ነበር፡፡ በቅዱስ ወንጌል ስለዚህ ጉዳይ ከተጻፉት የተወሰኑትን እንመልከት፡-

- "ማለዳም ተነሥቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ፤ ወደ ምድረ በዳም ሄዶ በዚያ ጸለየ።" ማር. 1፥35
- "ነገር ግን እርሱ ወደ ምድረ በዳ ፈቀቅ ብሎ ይጸልይ ነበር።" ሉቃ. 5፥16

- "ሐዋርያትም ተመልሰው ያደረጉትን ሁሉ ነገሩት። ከእርሱ ጋርም ወስዷቸው ቤተ ሳይዳ ከምትባል ከተማ አጠገብ ወደ ምድረ በዳ ለብቻው ፈቀቅ አለ።" ሉቃ. 9፡10
- "በእነዚህም ወራት ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ፤ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ።" ሉቃ. 6፡12

በዘመነ ወንጌል ብቻ ሳይሆን በብሉይ ኪዳንም እግዚአብሔር ብዙ ታላላቅ ተአምራትን ያደረገውና ምሥጢራቱን የገለጠው በምድረ በዳ ነበር፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን እናስታውስ፡-

- ሕዝበ እስራኤል መና ከሰማይ እየወረደላቸው ውኃ ከዓለት እየፈለቀላቸው ሲመገቡ የኖሩት በምድረ በዳ ነበር፤ "በግብፅ ምድርና በኤርትራ ባሕር *በምድረ በዳም* አርባ ዓመት ድንቅና ምልክት እያደረገ አወጣቸው።" የሐዋ. 7፡36

- ለሙሴ ሐመልማል ከነበልባል ተዋሕዶ የታየው ድንቅ ምሥጢር የተገለጠለት በምድረ በዳ ነበር፤ "አርባ ዓመትም ሲሞላ የጌታ መልአክ በሲና ተራራ *ምድረ በዳ* በቍጥቋጦ መካከል በእሳት ነበልባል ታየው።" የሐዋ. 7፡30

- በውስጡ የምስክሩ ጽላት እና የምስክሩ የቃል ኪዳኑ ታቦት ያለበት የምስክሩ ድንኳን የነበረው በምድረ በዳ (በገዳም) ነበር፡፡ ". . . *ወደ ብተራ ስምእ እንተ ነበረት በገዳም - የምስክር ድንኳን ከአባቶቻችን ዘንድ በምድረ በዳ ነበረች -*" የሐዋ. 7፡44

- ለጌታችን ሞትና እኛን ለማዳኑ ምሳሌ የነበረው የነሐስ እባብ የተሰቀለው በምድረ በዳ ነበር፤ "ሙሴም *በምድረ በዳ* እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል።" ዮሐ. 3፡14-15

እነዚህን ለምሳሌ አነሣን እንጂ እግዚአብሔር በምድረ በዳ የገለጣቸው ሌሎችም ብዙ ታላላቅ ምሥጢራት አሉ፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በብሉይ ኪዳን ስለ ነበሩ የተለዩ የእግዚአብሔር ሰዎች ተጋድሎ ሲናገር "በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፤ ተፈተኑ፣ በመጋዝ ተሰነጠቁ፤ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ፤ ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ፤ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ፣ በዋሻና በምድር ጕድጓድ ተቅበዘበዙ" ብሏል። ዕብ. 11፡37-38 እነዚያ ቀደምት አበው በምድረ በዳና በተራራ እንደ ተጋደሉ፣ ጌታችንም ወደዚህ ዓለም መጥቶ በረሓውንና ምድረ በዳውን ለጸሎትና ለተጋድሎ እንደ ባረከው ሁሉ ከጥንት የነቢያትን፣ ከኋላ ደግሞ የባለቤቱን የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ተግባራዊ የሕይወት ትምህርት መመሪያና መሪ አድርገው ከዚህ ዓለም ተለይተው ወደ በረሓ ወደ ገዳም ሄደው በተመስጦና በተዘክሮ ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ለመኖርና እርሱን ብቻ ለማገልገል ከራሳቸውና ከርኩሳን መናፍስት ጋር ቢጋደሉ በእግዚአብሔር በሚያምኑና መጽሐፍ ቅዱስን በሚቀበሉ ሰዎች ዘንድ በእጅጉ የሚያስመሰግንና በእግዚአብሔርም ዘንድ የተወደደ እንጂ መቸም መች የሚነቀፍ ነገር ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ የሚነቀፍ ሊሆን የሚችለው በአንድ ወገን ብቻ ነው፡- በአጋንንትና በመሰሎቻቸው፡፡ አጋንንት እንደ መነኰሳትና ገዳማውያን አምርረው የሚጠሉት የላቸውም፡፡

በዜና አበው ይህን የሚያስታውሰን አንድ ነገር አለ፡፡ የመነኰሳት ሁሉ አባት የሆነው ታላቁ ቅዱስ እንጦንስ በአንድ ወቅት ሰይጣን ለመነኰሳት ያለውን ጥላቻና ፍራቻ እንዲሁም የመነኰሳት ልብስ ያለውን ኃይል ለማየት ፈለገ፡፡ ለዚህም አንድ ባዶ ተመስሎ ነገር ወስዶ የመነኰሳት ልብስ (ቆሚስና ቆብ) በላዩ ላይ አደረገበት፡፡ ያን ጊዜ አጋንንት ከሩቅ ሆነው ፍላጻቸውን ወደዚያ ልብሱ ወደ ተደረገበት ተመስሎ ነገር ሲወረውሩበት አያቸው፡፡ እርሱም የአጋንንቱን ጅልነት አይቶ ውስጡ ሰው ያይደለ ባዶ ነገር (ተመስሎ) መሆኑን ነገራቸው፡፡ አጋንንቱም "ያስፈራንና ያስቀጣን፣ እንዲህ እንድናደርግ ያደረገንኮ ልብሶቹን ስናይ መነኩሴ መስሎን ነው" አሉት ይላል፡፡

ከጥንት ዘመን ጀምሮ የነበሩ የተለያዩ አባቶችና እናቶች ከዓለም ወጥተው ወደ በረሓ፣ ወደ ምድረ በዳ፣ ወደ ገዳም ሄደው በዚያ በእግዚአብሔር ኃይል ከርኩሳን መናፍስትና ከእኩያት ፍትወታት ጋር ሲጋደሉ የኖሩት ይህን የጌታቸውን ተግባራዊ ትምህርት አርአያ አድርገው የመድኃኒታቸውን ፈለግ ተከትለው ነው፡፡ በረሓ የሆነ ቦታ በሌለባቸው አካባቢዎችም ከዓለም ራቅ በማለትና በበረሓ ካለው ሁኔታ አንጻር ተቀራራቢነት ባላቸው ቦታዎች ይኖሩ ነበር፡፡ ዋናው ከዓለም መራቃቸውና የመንፈሳዊ ተጋድሎ ቦታ መሆናቸው ነው እንጂ የበረሓነቱ መጠን አይደለም፡፡ እንዲህ ያሉት ቦታዎች ለብቸኝነት፣ ለመንፈሳዊ ተመስጦ፣ ለጸም፣ ለጸሎት፣ ለተዘክሮተ እግዚአብሔር የሚመረጡ ቦታዎች ናቸው፡፡

መድኃኒታችን በዘመነ ሥጋዌው ያደረጋቸው ድርጊቶች በዋናነት የቤዛነት (የማዳን) ተግባራት ቢሆኑም ይህ እንዳለ ሆኖ ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች ተደራራቢ ነገሮችም ነበሩት፡፡ ከእነዚህ አንዱ የአርአያነት ተግባሩ ነው፡፡ ይህን በተመለከተም ጌታችን የደቀ መዛሙርቱን እግራቸውን ካጠባቸው በኋላ እንዲህ አላቸው፡-

> እግራቸውንም አጥቦ ልብሱንም አንሥቶ ዳግመኛ ተቀመጠ፣ እንዲህም አላቸው፦ ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን? እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፣ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ። እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፥ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል። እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ <u>እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና</u>። ዮሐ. 13፥12-15

ጌታችን የደቀ መዛሙርቱን እግር ያጠበበት አንዱ ምክንያት አርአያ ለመሆንና እርሱ በተግባር ሠርቶ በማሳየት እርሱን የሚከተሉ ሁሉ እርሱ እንዳደረገ እንዲያደርጉ እነርሱም በተግባር አብነት ለመሆን መሆኑን ራሱ ባለቤቱ አስተማረን፡፡ ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን "ተከተሉኝ" ያላቸው በእግራቸው ከኋላ ከኋላው እንዲከተሉት ብቻ ሳይሆን በዋናነት በግብር እንዲመስሉት ነበር፡፡ እኛ ልናደርጋቸው የማንችላቸው ነገሮች የጌታችንን የማዳን ተግባራት ነው፤ ስለ እኛ መዳን ሲል የፈጸማቸው ነገሮች - በድንግልና መወለዱ፣ ሕማማቱ፣ ስቅለቱ፣ ሞቱ፣ ትንሣኤው፣ ዕርገቱና የመሳሰሉት - እነዚህ የእርሱና የእርሱ ብቻ ናቸው፡፡ እነዚህን እኛ ልናደርጋቸው አንችልም፡፡ ከዚህ ውጭ ያሉት እርሱ የሠራቸው ሌሎች ሥራዎች ግን እኛም እርሱን መምህራችንና መሪያችን አድርገን እንሠራቸው ዘንድ "ተከተሉኝ" ብሎ ጠርቶናል፡፡

እንዲሁም ጌታችን "ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርሷም፦ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል" በማለት ፍቅር የሕግ ሁሉ ማጠቃለያ መሆኑን አስተምሮናል፡፡ ማቴ. 22፡ 37-40 የምንዘክሰናና የብሕትውና ዋና ዓላማም ይህን ለእግዚአብሔርና ለሰው ሊኖር የሚገባውን ፍቅር ለማሳደግና ፍጹም ለማድረግ የሚደረግ ተጋድሎ ነው፡፡ ወደዚህ ታላቅ ግብ ለመድረስ ይችሉ ዘንድ መሰናክል ከሚሆኑና ልቡናን ከሚነትቱ፣ መንፈስን ከሚያዳክሙ ነገሮች ርቀው ሙሉ ሕይወታቸውን ሁሉ እግዚአብሔር እርሱንና ሰዎችን በፍጹም ሁለንተናቸው ለመውደድ እንዲችሉ እንዲያደርጋቸው ይጋደላሉ፡፡ እንዲህ ያለው ሕይወት ቢያስቀና እንጂ ምን ይነቀፋል? ወይስ ቀበሮዪቱ ልቧ እስኪወልቅ ከዘለለች በኋላ ወይኑን አውርዳ መብላት አልቻል ባለች ጊዜ "አዬ፣ እንዲያውም ወይኑ ጮርቃ ነው" አለች እንደሚባለው ዓይነት ነገር ይሆን?

ጌታችንን መከተል ማለት ደግሞ ከጌታችን ትምህርቶችና በሕይወቱ በተግባር ካደረጋቸው ድርጊቶች መካከል ለእኛ የሚስማማንንና የመሰለንን ብቻ እየመረጥን የምናደርገው አይደለም፤ ሁሉንም እንዳለ በምልአት በመቀበልና በማመን ሊሆን ይገባል እንጂ፡፡ ጌታችንን በሁሉም ነገር እስከ ተቻለን ድረስ ልንከተለው ይገባናል እንጂ ወሰንና ዳርቻ አበጅተን እኛ ራሳችን ባወጣነው መለኪያ መሠረት ሊሆን አይገባውም፡፡ "የራስን ጽድቅ ማቆም" የሚባለው ይኼ ነውና፡፡ ሮሜ 10፥3 እንዲሁም ደግሞ እኛ ያልቻልነውን ሁሉ ለምን ሌሎች ያደርጉታል? ከሚል ወይም እኛ ካልቻልን ሌላውም አይችለውም ከሚል ልቡና የሚመነጭ አስተሳሰብ በጣም አሳዛኝ ነው፡፡

ይህ ሕይወት ለሁሉም ባይቻልም በእርሱ ቸርነት ለሚመርጡትና ለሚችሉት ሰዎች ግን ተገቢ መሆኑን ራሱ ባለቤቱ ጌታችን ሁሉንም አጠቃልሎ "ከእኔ ተማሩ" ብሏል፡፡ ማቴ. 11፥27 ከእርሱ የምንማረው ደግሞ በቃል ያስተማረውንም በተግባር ሠርቶ ያሳየንንም ሁሉንም ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም "የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሏልና" በማለት የመድኃኒታችንና የጌታችንን አርአያ መከተል እንዳለብን በአጽንዖት አስገንዝቦናል፡፡ 1 ጴጥ. 2፥21

በመሆኑም ጌታችን በተግባር ሠርቶ ካሳየን ተግባራት አንዱ ወደ በረሓ (ምድረ በዳ) መሄድና በዚያ ከአጋንንት ጋር መጋደል ነው፡፡ ይልቁንም ከማስተማሩ፣ ተአምራት ከማድረጉ፣ ድውይ ከመፈወሱ፣ አጋንንትን ከማውጣቱ . . . በፊት ጌታችን የመጀመሪያው ሥራው ያደረገው ወደ በረሓ መሄድና በዚያ ከአጋንንት ጋር መጋደልን ነበር፡፡ እርሱን መከተል ማለትም ይኸን በተግባር መፈጸም ነው፡፡ ለቻለስ ክርስቶስን በሄደበት ሁሉ የሚከተሉ ሰዎች የመጀመሪያው ተግባር ነበር፡፡ በጌታችን ሥራ ከጥምቀት ቀጥሎ፣ ከዮርዳኖስ ቀጥሎ የምናገኘው ወደ ምድረ በዳ መሄድንና በዚያም ከአጋንንት ጋር መጋደልን ነው፡፡ እኛ በእምነታችን ማነስና በደካማነታችን መፈጸም ባለመቻላችን ራሳችንን መውቀስና ማዘን ይገባን ነበር እንጂ ከዚያ አልፎ የጌታቸውን አርአያ በመከተል ወደ በረሓ (ገዳም) የሚሄዱትን ለመንቀፍ መነሣት ድርብ ዕዳ መሸመት ነው፡፡ የፀሐይን ብርሃን ማየት ያልቻለ ሰው ማየት ካለመቻሉ የተነሣ ፀሐይን እንደ መንቀፍ ያለ ነው፡፡

ከዓለም ለየት ባለ ቦታ - በገዳም፣ በምድረ በዳ - ማምለክ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ በዚያ የሚያመልክ መነኩሴ ከዓለሙ ግርግርና ሁካታ ርቆና ተለይቶ በበረሓው ጸጥታ ውስጥ ሆኖ እግዚአብሔርን በሙሉ ልቡ ለማምለክ ይችላል፡፡ የበረሓው ጸጥታ ወደ ስሜት ሕዋሳትና የልቡና ጸጥታ ይመራዋል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ሳባ (አረጋዊ መንፈሳዊ) "ልብህ መነጋገር ይችል ዘንድ አፍህን ጸጥ አድርግ፤ እግዚአብሔር ይናገርህ ዘንድ ደግሞ ልብህን ጸጥ አድርግ" እንዳለ፡፡ ቅዱስ (ማር) ይስሐቅ ሶርያዊም "በረሓውን ማየት ብቻ በራሱ በነፍሳችን ውስጥ ያለ ዓለማዊ ሓሳብንና ምኞትን ይገድለዋል፡፡ በዚህም ለእግዚአብሔር ያለን ናፍቆትና ጉጉት የበለጠ ይጨምራል፤ ወደ እርሱም የበለጠ ለመቅረብ እንፈልጋለን፤ በመጨረሻም ከእርሱ ጋር እንዋሐዳለን" ይላል፡፡ በበረሓ ወይም በገዳም ቆሚኖር መነኩሴ ሓሳቡን ለመቆጣጠርና ልቡናውን ለማንጻት ያግዘዋል፡፡ ቅዱስ ይስሐቅ ሶርያዊ "ጸጥታ ልቡናን ከተለያዩ ሃሳቦች ከመባከንና ከመባዘን ይጠብቀዋል፤ የቆዩ ትዝታዎችም እንዲረሱ ያደርጋቸዋል" ይላል፡፡

የመነኩሴ ወደ በረሓ ወይም ገዳም መሄድ የእስራኤል ልጆች ከግብጽ ወጥተው በሲና በረሓ በምድረ በዳ ከመጓዛቸው ጋር አንድ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሙሴን የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ እንዲያወጣቸው ሲያዝዘው "በእውነት እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ እኔም እንደ ላክሁህ ምልክትህ ይህ ነው፤ ሕዝቡን ከግብፅ ባወጣህ ጊዜ በዚህ ተራራ ላይ ለእግዚአብሔር ትገዛላችሁ አለው" ይላል፡፡ ዘጸ. 3፥12 የአራት ዘጸአት ዋና መልእክት - የተአምራቱ፣ ትእዛዛቱና የመሳሰሉት እግዚአብሔርን በምድረ በዳ (በበረሓ) ስለ ማምለክ ናቸው፡፡ ይህም ምድረ በዳ ወይም በረሓ ከዚህ ዓለም የራቀና የተለየ እንደ ሆነ ሁሉ ከዚህ ዓለም ርኩሰትና ኃጢአት የተለየ የሆነ ፍጹም አምልኮትን ለእግዚአብሔር ማቅረብን የሚያመለክት ነው፡፡

ስለዚህም ነበር ሙሴና አሮን ወደ ፈርዖን ሄደው እንዲህ ያሉት፡-

> ከዚህም በኋላ ሙሴና አሮን መጥተው ፈርዖንን እንዲህ አሉት፡- የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- በምድረ በዳ በዓል ያደርግልኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ። ፈርዖንም ቃሉን እሰማ ዘንድ እስራኤልንስ እለቅቅ ዘንድ እግዚአብሔር ማን ነው? እግዚአብሔርን አላውቅም፣ እስራኤልንም ደግሞ አልለቅቅም አለ። እርሱም፦ የዕብራውያን አምላክ ተገናኘን፣ ቸነፈር ወይም ሰይፍ እንዳይጥልብን *የሦስት ቀን መንገድ በምድረ በዳ እንድንሄድ*፣ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር እንድንሠዋ እንለምንሃለን አሉት፡፡ ዘጸ. 5፥1-3

ፈርዖን ግን ይህን "ወደ ምድረ በዳ ሄደን ለእግዚአብሔር እንሠዋ፣ በዓል እናድርግ" የሚለውን የሙሴና የአሮን መንፈሳዊ ጥያቄ አልቀበልም አለ፡፡ ፈርዖን እያዘዘው ያለው አምላክ እግዚአብሔር ማን መሆኑን በተግባር ያውቅ ዘንድ ብዙ መቅሠፍታዊ ተአምራትን በፊቱ ሙሴና አሮን እያደረጉ አሳዩት፡፡ ሆኖም ፈርዖን ከዚያ ሁሉ መቅሠፍት በኋላ እንኳ ሊል የቻለው "ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን ጠርቶ፡- ሂዱ፤ በአገሩ ውስጥ ለአምላካችሁ ሠዉ" ነበር፡፡ ይህ ማለት ወደ በረሓ፣ ወደ ምድረ በዳ አትሄዱም፣ በዚሁ በቅርብ ሆናችሁ ማምለክ ትችላላችሁ ማለቱ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ሙሴ "ለእግዚአብሔር ለአምላካችን የግብፃውያንን ርኵሰት እንሠዋለንና እንዲህ ይደረግ ዘንድ አይገባም፡፡ እነሆ እኛ የግብፃውያንን ርኵሰት በፊታቸው ብንሠዋ አይወግሩንምን? <u>እኛስ ለእግዚአብሔር ለአምላካችን እንሠዋ ዘንድ እንደሚያዝዘን የሦስት ቀን መንገድ ወደ ምድረ በዳ እንሄዳለን</u>" አለው። ዘጸ. 8፥25-27

ይህ ከግብጽ መውጣትና የሦስት ቀን ጎዳና ወደ በረሓ ሄዶ ለእግዚአብሔር መሠዋት ያለ ምክንያት የተነገረና የታዘዘ አልነበረም፡፡ እግዚአብሔርን በግብጽ ሆነው ቢጠሩት የማይሰማቸው ሆኖ አልነበረም፡፡ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ ያለና ቢጠሩት የሚሰማ መሆኑ የታወቀ ነውና፡፡ ነገር ግን ወደ በረሓ ሄዶ ለእግዚአብሔር መሠዋት ታላቅ የሆነ መልእክትና ምሥጢር ባይኖረው ኖሮ ያን ያህል "እኛስ ለእግዚአብሔር ለአምላካችን እንሠዋ ዘንድ እንደሚያዝዘን የሦስት ቀን መንገድ ወደ ምድረ በዳ እንሄዳለን" እያለ ደጋግሞ ከፈርዖን ጋር ለምን ይታገል ነበር? ፈርዖንም፡- "ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ በምድረ በዳ ትሠዉ ዘንድ እለቅቃችኋለሁ፣ ነገር ግን ርቃችሁ አትሂዱ፣ ጸልዩልኝ" አለ። ሙሴና አሮንም ደግመው ደጋግመው ወደ ፈርዖን በመግባት "ፈርዖንም፡- ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ በምድረ በዳ ትሠዉ ዘንድ እለቅቃችኋለሁ" እስኪል ድረስ ታገሉ፡፡ ዘጸ. 8፥28

በቀድሞው ዘመን ያን ጊዜ እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ይሠውና በዓል ያደርጉ ዘንድ ወደ ምድረ በዳ ለመሄድ ፍቀድልን ሲሉት የግብጹ ንጉሥ ፈርዖን አልፈቅድላችሁም፣ አልለቃችሁም እንዳላቸው ሁሉ ዛሬም ፈርዖንና ልጆቹ እግዚአብሔርን ለማምለክ ሰዎች ወደ ምድረ በዳ፣ ወደ ገዳም ለምን ይሄዳሉ? ይህ ትክክል አይደለም እያሉ የሰዎችን ልቡና ለመከልከል ይታገላሉ፡፡ የግብጹ ፈርዖን እስራኤላውያንን "መሥዋዕት አትሠው፣ በዓል አታድርጉ" ብሎ ጨርሶ አልከለከላቸውም ነበር፤ "ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን ጠርቶ፡- <u>ሂዱ፤ በአገሩ ውስጥ ለአምላካችሁ ሠዉ</u>" አላቸው እንጂ፡፡ እንደዚሁም ሁሉ የዛሬዎቹ ፈርዖናውያንም "እግዚአብሔርን ለማምለክ በረሓ መሄድ፣ ገዳም መግባት፣ ይህን ያህል መድከም ምን ያስፈልጋል? በጸጋው ድነሃል፣ በቃህ እርፈህ ተኛ፣ ተዝናና . . ." እያሉ ሰዎችን ያሳንፋሉ እንጂ እግዚአብሔርን አታምልክ ብለው በግልጽ አይናገሩም፡፡ ልዩነቱ ግን አንድና መሠረታዊ ነው፤ እርሱ ምንድን ነው? ፈርዖን ለክፉ ድርጊቱ የእግዚአብሔርን ቃል ያልተጠቀመ ሲሆን እነዚህ ግን ክፋታቸውንና ስህተታቸውን በማር እንደ ተለወሰ መርዝ በእግዚአብሔር ቃል ሸፍነው ለማቅረብ መሞከራቸው ነው፡፡ ከእነዚህ ክፋት አንጻር ሲታይ የፈርዖን ኃጢአት ሳይቀል ይቀር ይሆን?

የመነኩሴ ወደ በረሓ ወይም ገዳም መሄድ የእስራኤል ልጆች ከግብጽ ወጥተው በሲና በረሓ በምድረ በዳ ከመጓዛቸው ጋር አንድ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሙሴን የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ እንዲያወጣቸው ሲያዝዘው "በእውነት እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ እኔም እንደ ላክሁህ ምልክትህ ይህ ነው፤ ሕዝቡን ከግብፅ ባወጣህ ጊዜ በዚህ ተራራ ላይ ለእግዚአብሔር ትገዛላችሁ አለው" ይላል፡፡ ዘጸ. 3፡12 የአራት ዘጸአት ዋና መልእክት - የተአምራቱ፣ ትእዛዛቱና የመሳሰሉት እግዚአብሔርን በምድረ በዳ (በበረሓ) ስለ ማምለክ ናቸው፡፡ ይህም ምድረ በዳ ወይም በረሓ ከዚህ ዓለም የራቀና የተለየ እንደ ሆነ ሁሉ ከዚህ ዓለም ርኩሰትና ኃጢአት የተለየ የሆነ ፍጹም አምልኮትን ለእግዚአብሔር ማቅረብን የሚያመለክት ነው፡፡

ስለዚህም ነበር ሙሴና አሮን ወደ ፈርዖን ሄደው እንዲህ ያሉት፦

> ከዚህም በኋላ ሙሴና አሮን መጥተው ፈርዖንን እንዲህ አሉት፦ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በምድረ በዳ በዓል ያደርግልኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ። ፈርዖንም ቃሉን እሰማ ዘንድ እስራኤልንስ እለቅቅ ዘንድ እግዚአብሔር ማን ነው? እግዚአብሔርን አላውቅም፤ እስራኤልንም ደግሞ አልለቅቅም አለ። እርሱም፦ የዕብራውያን አምላክ ተገናኘን፤ ቸነፈር ወይም ሰይፍ እንዳይጥልብን የሦስት ቀን መንገድ በምድረ በዳ እንድንሄድና ለአምላካችን ለእግዚአብሔር እንድንሠዋ እንለምንሃለን አሉት፡፡ ዘጸ. 5፡1-3

ፈርዖን ግን ይህን "ወደ ምድረ በዳ ሄደን ለእግዚአብሔር እንሠዋ፣ በዓል እናድርግ" የሚለውን የሙሴና የአሮን መንፈሳዊ ጥያቄ አልቀበልም አለ፡፡ ፈርዖን እያዘዘው ያለው እግዚአብሔር ማን መሆኑን በተግባር ያውቅ ዘንድ ብዙ መቅሠፍታዊ ተአምራትን ሙሴና አሮን በፊቱ እያደረጉ አሳዩት፡፡ ሆኖም ፈርዖን ከዚያ ሁሉ መቅሠፍት በኋላ እንኳ ሊል የቻለው "ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን ጠርቶ፦ ሂዱ፣ በአገሩ ውስጥ ለአምላካችሁ ሠዉ" ነበር፡፡ ይህ ማለት ወደ በረሓ፣ ወደ ምድረ በዳ አትሂዱም፣ በዚሁ በቅርብ ሆናችሁ ማምለክ ትችላላችሁ ማለቱ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ሙሴ "ለእግዚአብሔር ለአምላካችን የግብፃውያንን ርኵሰት እንሠዋለንና እንዲህ ይደረግ ዘንድ አይገባም፡፡ እነሆ እኛ የግብፃውያንን ርኵሰት በፊታቸው ብንሠዋ አይወግሩንምን? <u>*እኛስ ለእግዚአብሔር ለአምላካችን እንሠዋ ዘንድ እንደሚያዝዘን የሦስት ቀን መንገድ ወደ ምድረ በዳ እንሄዳለን*</u>" አለው። ዘጸ. 8፡25-27

ይህ ከግብጽ መውጣትና የሦስት ቀን ጎዳና ወደ በረሓ ሂዶ ለእግዚአብሔር መሠዋት ያለ ምክንያት የተነገረና የታዘዘ አልነበረም፡፡ እግዚአብሔርን በግብጽ ሆነው ቢጠሩት የማይሰማቸው ሆኖ አልነበረም፡፡ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ ያለና ቢጠሩት የሚሰማ መሆኑ የታወቀ ነውና፡፡ ነገር ግን ወደ በረሓ ሂዶ ለእግዚአብሔር መሠዋት ታላቅ የሆነ መልእክትና ምሥጢር ባይኖረው ኖሮ ያን ያህል "እኛስ ለእግዚአብሔር ለአምላካችን እንሠዋ ዘንድ እንደሚያዝዘን የሦስት ቀን መንገድ ወደ ምድረ በዳ እንሄዳለን" እያሉ ደጋግመው ከፈርዖን ጋር ለምን ይታገሉ ነበር? ፈርዖንም፦ "ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ በምድረ በዳ ትሠዉ ዘንድ እለቅቃችኋለሁ፤ ነገር ግን ርቃችሁ አትሂዱ፤ ጸልዩልኝ" አለ። ሙሴና አሮንም ደግመው ደጋግመው ወደ ፈርዖን በመግባት "ፈርዖንም፦ ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ በምድረ በዳ ትሠዉ ዘንድ እለቅቃችኋለሁ" እስኪል ድረስ ታገሉ፡፡ ዘጸ. 8፡28

በቀድሞው ዘመን ያን ጊዜ እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ይሠውና በዓል ያደርጉ ዘንድ ወደ ምድረ በዳ ለመሄድ ፍቀድልን ሲሉት የግብጹ ንጉሥ ፈርዖን አልፈቅድላችሁም፣ አልለቃችሁም እንዳላቸው ሁሉ ዛሬም ፈርዖንና ልጆቹ እግዚአብሔርን ለማምለክ ሰዎች ወደ ምድረ በዳ፣ ወደ ገዳም ለምን ይሄዳሉ? ይህ ትክክል አይደለም እያሉ የሰዎችን ልቡና ለመከልከል ይታገላሉ፡፡ የግብጹ ፈርዖን እስራኤላውያንን "መሥዋዕት አትሠው፣ በዓል አታድርጉ" ብሎ ጨርሶ አልከለከላቸውም ነበር፤ "ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን ጠርቶ፦ <u>ሂዱ፣ በአገሩ ውስጥ ለአምላካችሁ ሠዉ</u>" አላቸው እንጂ፡፡ እንደዚሁም ሁሉ የዛሬዎቹ ፈርዖናውያንም "እግዚአብሔርን ለማምለክ <u>በረሓ መሄድ፣ ገዳም መግባት፣ ይህን ያህል መድከም ምን ያስፈልጋል? በጸጋው ድነሃል፣</u>

በቃህ እርፈህ ተኛ፣ ተዝናና . . ." እያሉ ሰዎችን ያሳንፉሉ እንጂ እግዚአብሔርን አታምልክ ብለው በግልጽ አይናገሩም፡፡ ልዩነቱ ግን አንድና መሠረታዊ ነው፤ እርሱ ምንድን ነው? ፈርዖን ለክፉ ድርጊቱ የእግዚአብሔርን ቃል ያልተጠቀመ ሲሆን እነዚህ ግን ክፋታቸውንና ስህተታቸውን በማር እንደ ተለወሰ መርዝ በእግዚአብሔር ቃል ሸፍነው ለማቅረብ መሞከራቸው ነው፡፡ ከእነዚህ ክፋት አንጻር ሲታይ የፈርዖን ኃጢአት ሳይቀል ይቀር ይሆን?

ሆኖም ይህ ዓይነቱ ሕይወት ለሁሉም ሰው የሚቻልና የሚሆን አይደለም፤ ራሳቸውን ለክርስቶስ ብቻ ለሰጡና እርሱ በሄደበት መንገድ ሁሉ ለመሄድ ለወሰኑ፣ ይህ ውሳኔያቸውም በእግዚአብሔር የማይመረመር ጥበብ ፈቃዱ ለሆነላቸው ሰዎች ነው እንጂ፡፡ እንደዚህ ያሉት በዚህ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በሄደበት መንገድ ሁሉ - ከዮርዳኖስ ከጥምቀት ጀምሮ (በጥምቀት ልጅነትን ያገኙሉና) ወደ በረሓውም በመሄድ ይመስሉታል፡፡ እንዲህ ተብሎ የተጻፈው እንደዚህ ላሉት ነውና፡-

> *ከሴቶች ጋር ያልረከሱ እነዚህ ናቸው፣ ድንግሎች ናቸውና። በጉ ወደሚሄድበት የሚከተሉት እነዚህ ናቸው።* ራእ. 14፡4

እነዚህ መድኃኒታችንን ወደ በረሓ በመሄድና በመጋደል፣ በንጽሕናና በድንግልና በመኖር ሁሉ ይመስሉታል፡፡ በዚህ ዓለም ጌታችን በሄደበት መንገድ (በኖረው አኗኗር) ሁሉ እንደ ተከተሉት በኋላ በሰማይ ደግሞ የዓለምን ኃጢአት ያሰወገደው የእግዚአብሔር በግ የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ወደሚሄድበት ሁሉ ያስከትላቸዋል፡፡ በዚህ ዓለም ሕይወታቸው እርሱ በሄደበት የሕይወት መንገድ በሙሉ (በበረሓ መጋደልንና ድንግልናዊ ሕይወትን ጨምሮ) ተከትለውታልና በኋላ በሰማይ ደግሞ እርሱ ወደሚሄድበት ሁሉ ያስከትላቸዋል፡፡ ስለሆነም ያደለው ይህን ለመሆን ይጥራል፣ ያልሆነለት ደግሞ በድካሙ እያዘነ እግዚአብሔር ኃጢአቱን ይቅር እንዲለው ይለምናል እንጂ ወደ ላይ ተንጠራርቶ እኔ ያልደረስኩበትና ያልቻልኩት ነገር ሁሉ ስህተት ነው ብሎ መዝለፍ "የእናት የአባቱ ርግማን ያነሰው የአማት ርግማን ይጨምራል" እንደሚባለው ዓይነት ነገር ነው፡፡

2) በንጽሕና መኖር

ሌላው የምንነሥና መሠረታዊ ጠባይ ወንዶች ከሴት ርቀው፣ ሴቶች ከወንድ ርቀው በንጽሕና መኖር ነው፡፡ ይህም የፕሮቴስታንቶችን ነውር በአዲስ መጠቅለያ ይዘው ብቅ በማለት አለን አለን የሚሉት ተሐድሶዎች እንደሚሉት ሰዎች የፈጠሩት ወይም ከአሕዛባዊ ፍልስፍናና ከጣዖት አምላኪዎች ልማድ የመጣ ሳይሆን ራሱ ባለቤቱ ጌታችን ያስተማረው፣ ሐዋርያትም የተቀበሉትና ያስተማሩት ነው፡፡ የድንግልናና የንጽሕና ሕይወትን መሠረት የጣለው ራሱ ባለቤቱ ነው፡፡ ደቀ መዛሙርቱ "የባልና የሚስት ሥርዓት እንዲህ ከሆነ መጋባት አይጠቅምም" ባሉት ጊዜ እንዲህ አለ፡- "ይህ ነገር ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም፤ በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፣ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፣ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ። ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው አላቸው።" ማቴ. 19፡10-12

ይህ የጌታችን ትምህርት ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን ያስገነዝበናል፡፡ እነዚህም አንደኛ "ስለ መንግሥተ ሰማያት ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች" አሉ በማለት በፈቃዳቸው ራሳቸውን በድንግልና ለመኖር የወሰኑ ሰዎች ድርጊታቸው የተፈቀደ መሆኑን፤ የተፈቀደ ብቻም ሳይሆን ስለ መንግሥተ ሰማያት ሲሉ የሚያደርጉትና ዋጋ ያለው መሆኑን ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ "ይህ ነገር ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም" በማለት ይህ ዓይነት ሕይወት ለሁሉም ሰው የማይሆንና የማይቻል፣ ለጥቂቶች ብቻ የሚሆን መሆኑን ነገረን፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈላቸው የመጀመሪያ መልእክቱ ላይ መልስ ከሰጠባቸው ጉዳዮች አንዱ በድንግልና የመኖር ጉዳይና የትዳር ጉዳይ ነበሩ፡፡ በድንግልናና በንጽሕና ስለ መኖር ጉዳይ ሲናገር *"ስለ ጻፋችሁልኝስ ነገር ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው"* በማለት እንዲህ ያለው ሕይወት መልካም መሆኑን ካስረዳ በኋላ በመቀጠል *"ነገር ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው፣ ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራሷ ባል ይኑራት"* አለ። 1 ቆሮ. 7፡1-2

እንዲህ ያለውን ሕይወት የመረጡና ጸንተው የጠበቁ ሰዎች ሌላው ሰው ከትንሣኤ በኋላ የሚደርስበት ሕይወት ከሆነው አንዱን - እንደ መላእክት መሆንን - ዛሬ በዚህ ዓለም ገንዘብ ያደርጉታል፡፡ ጌታችን በትንሣኤ ስለሚሆነው ሕይወት ሲናገር *"በትንሣኤስ እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡም"* እንዳለ፡፡ ማቴ. 22፡30 እንዲሁም "ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ የዚህ ዓለም ልጆች ያገባሉ ይጋባሉም፤ ያን ዓለምና ከሙታን ትንሣኤ ሊያገኙ የሚገባቸው እነዚያ ግን አያገቡም አይጋቡምም፤ እንደ መላእክት ናቸውና" በማለት ከሞት በኋላ በትንሣኤ እንደሚገኝ የተነገረውን ይህን ክብር በድንግልናና በምንኩስና የሚኖሩ አበውና እማት ግን በዚህ ዓለም ሕይወታቸው ሳሉ ይደርሱበታል (ይኖሩታል)። ሉቃ. 20፡34-36 መላእክት በተፈጥሯቸው እንደማያገቡና እንደማይጋቡ፣ ከትንሣኤ በኋላ ደግሞ ለሰዎችም ማግባት መጋባት እንደማይኖር ሁሉ በዚህ ዓለም ሲኖሩ በንጽሕናና በድንግልና ሆነው ከማግባትና ከመጋባት ውጭ የሚኖሩ አበውና እማት "እንደ መላእክት ናቸው" የሚያሰኛቸው ይህ ነው፡፡ ስለዚህም ነው የድንግልና ሕይወት "ሥርዓተ መላእክት"፣ "ሕይወተ መላእክት" እየተባለ የሚገለጸው፡፡

ስለዚህ ተቃዋሚዎቹ ተሐድሶዎች "ይህን ሥርዓት *ሥርዓተ መላእክት ነው ይሉታል፡፡* ምንኩስናን በወንጌል ጥቅስ ለመቀባባት የምትደረገዋን ማመሳሰል ግን ምሁራን አልተቀበሏትም፡፡ አንዳንዶቹ ምሁራንማ ላላወቀሽ ታጠኝ ብለዋታል" የሚለው ነገራቸው ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው አስተምህሮ ጋር የሚጣላ መሆኑንና በቃለ እግዚአብሔር ሚዛንነት ሲመዘን እንዲህ መቅለሉን በግልጽ ያሳየናል፡፡ ራሱ ባለቤቱ በቃል ያስተማረውንና በተግባር የኖረውን ሕይወት መንቀፍ ምን ይሉታል? መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በዚህ ዓለም ጋብቻን ንቀው ወይም ጠልተው ሳይሆን ስበለጠ ነገር ብለው በምንኩስናና በድንግልና የሚኖሩትን "እነዚያ ግን አያገቡም አይጋቡምም፤ እንደ መላእክት ናቸውና" ሲላቸው ተሐድሶዎች ደግሞ "አይ አይደለም፣ ይህ ሕይወት ሥርዓተ መላእክት ነው መባሉ ስህተት ነው፡፡ እንዲህ ያለውን ምሁራን አልተቀበሉትም" ይሉናል፡፡ ታዲያ የቱን እንስማ? የጌታችንን ትምህርት ወይስ የተሐድሶዎችን ክህደት?

ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ሁሉንም ይወዳቸው ነበር፡፡ "አብ እንደ ወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ" እንዳላቸው። ዮሐ. 15፡9 ዮሐንስ ወንጌላዊን ግን ከሁሉም አብልጦ ይወደው እንደ ነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል፡፡ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ከእነርሱ መካከል አንዱ አሳልፎ የሚሰጠው ስለ መሆኑ በተናገራቸው ጊዜ ደንግጠው "እኔ እሆንን?" ባሉ ጊዜ በጌታችን በደረቱ ጠጋ ብሎ ይህን ምሥጢር የጠየቀው፣ ስለ ማን እንደ ተናገረ እንዲጠይቅላቸው ስምዖን ጴጥሮስም የጠየቀው ቅዱስ ዮሐንስን ነበር፤ "ኢየሱስም ይወደው የነበረ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ በኢየሱስ ደረት ላይ ተጠጋ፤ ስለዚህ ስምዖን ጴጥሮስ እርሱን ጠቅሶ፡- ስለማን እንደ ተናገረ ንገረን አለው። እርሱም በኢየሱስ ደረት እንዲህ ተጠግቶ፡- ጌታ ሆይ፣ ማን ነው? አለው።" ዮሐ. 13፡23-25 ይህ በጌታችን ደረት መጠጋትና እርሱን የመቅረብ ልዩ ጸጋ ለቅዱስ ዮሐንስ የተሰጠው ድንግል በመሆኑ እንደ ሆነ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ገልጸዋል፡፡

በመስቀሉ እግር ሥር የተገኘውና ጌታችን ንጽሕት ድንግል የሆነች እናቱን አደራ የሰጠውም ለዚሁ ለቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ነበር፡፡ "ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን፡- አንቺ ሴት፣ እነሆ ልጅሽ አላት። ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን፡- እናትህ እነኋት አለው። ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት።" ዮሐ. 13፡26-27 ድንግል እናቱን ለድንግል ዮሐንስ ሰጣት፡፡ እመቤታችንን "የደናግል መመኪያ" የምንላት ለዚህም ነው፡፡ ይህ ሁሉ ድንግልና ያለው ክብርና ጸጋ ታላቅ መሆኑን ያሳያል እንጂ የዘመናችን ሉተራውያንና ሰዱቃውያን "ሌላ ጽድቅ"፣ "ሰው ሠራሽ" እያሉ እንደሚነቅፉት ሆኖ አናገኘውም፡፡

3) *መንፈሳዊ ተጋድሎ*

በምንኩስና አምላካቸውን ለማገልገል የሚወስኑ ሰዎች ዓላማቸው ራሳቸውን ለአምላካቸው በመስጠት እርሱ ባሳያቸው መንገድ እስከሚቻላቸው ድረስ በፍጹምነት መኖር (መኖር) ነው፡፡ ፍጹም ወደ መሆን ማደግ፣ ራስን በመንፈሳዊነትና በቅድስና ማሳደግ የገዳማዊ ሕይወት ዓላማ ነው፡፡ ግን ይህ ዓላማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነውን? ወይስ ሰው ሠራሽና ከወንጌል የተለየ ባእድ ነገር? "ፍጹምነት" የሚለውን ነገር ወደ ክርስትና ያመጣው የምንኩስናና የገዳማዊ ሕይወት ዝንባሌና ልማድ ነበርን?

ለክርስትና ፍጹምነትን ግብ (ዓላማ) አድርጎ ያሳየውና ያስተማረው መነኰሳት ሳይሆኑ ራሱ ባለቤቱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ እንዲህ ብሎ፡- "*እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ፡፡*" ማቴ. 5፡48 ስለዚህ መነኰሳት ወደ ፍጹምነት ማደግ ይችሉ ዘንድ ከዚህ ጌታችን ካሳየው ግብ ለመድረስ ልቡናንና ሕሊናን ሊይዙና ሊያሰናክሉ ከሚችሉ ከዚህ ዓለም ነገሮች በተቻላቸው መጠን ራሳቸውን ማራቃቸውና መምረጣቸው የሚያስነቅፈው ምኑ ላይ ነው? መድኃኒታችን "በእሾህ መካከል የተዘራውም ይህ ቃሉን የሚሰማ ነው፡፡ የዚህም ዓለም ሃሳብና የባለጠግነት መታለል ቃሉን ያንቃል፣ የማያፈራም ይሆናል" በማለት የእግዚአብሔር ቃል በውስጣችን ፍሬ እንዳያፈራ የሚያንቁትንና የሚያስቀሩትን - የዚህ ዓለም ሃሳብና የባለጠግነት መታለል የተባሉትን እነርሱ አርቀው ተዋቸው፡፡ ማቴ. 13፡22

የዚህ ዓለም ሃሳብና የባለ ጠግነት ምኞት ሰዎችን ምን ያህል ከፍጹምነት መንገድ እንደሚያርቃቸውና እንደሚፈትናቸው ጌታችን ለባለ ጸጋው በተናገረውና ያ ባለ ጸጋም ባደረገው ነገር በግልጽ ታውቋል፡፡ ያ ባለ ጸጋ የነበረ ሰው ቀርቦ ጌታችንን "መምህር ሆይ፣ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ?" ባለው ጊዜ ጌታችንም "ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንድ ነው፤ ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ" አለው። ባለ ጸጋውም፡- "የትኞችን?" አለው። ጌታችን ኢየሱስም፡- "አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ በሐሰት አትመስክር፣ አባትህንና እናትህን አክብር፣ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ" አለው። ጐበዙም፡ - "ይህንማ ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄያለሁ፣ ደግሞስ የሚጐድለኝ ምንድር ነው?" አለው። ጌታ ኢየሱስም፡- "ፍጹም ልትሆን ብትወድ፣ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፣ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፣ መጥተህም ተከተለኝ" አለው። ቅዱስ ወንጌል በዚያን ጊዜ ስለ ሆነው ሲናገር "*ጐበዙም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ብዙ ንብረት ነበረውና እያዘነ ሄደ*" ይላል፡፡ ማቴ. 19፡16-22

ያ ባለ ጸጋ ያለውን ሁሉ ትቶ ጌታችንን ብቻ ቢከተል ኖሮ ፍጹምነትን ያገኝ ነበር ማለት ነው፡፡ እንዲሁም ሰማያዊ መዝገብ ያገኝ ነበር፡፡ ጌታችን በማይታበል ቃሉ "ፍጹም ልትሆን ብትወድ፣ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፣ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፣ መጥተህም ተከተለኝ" ያለው ለዚህ ነበር፡፡ ገዳማውያን መነኰሳትም ጌታችን ለዚያ ባለ ጸጋ የነገረውን ትእዛዝ በመቀበል አንዳንዶቹ ገና ከመጀመሪያው ወደዚህ ዓለም ከመግባትና ሀብት ንብረት ከማፍራት ርቀው፣ ሌሎቹ ደግሞ ወደዚህ ሕይወት ገብተው የተወሰነ ጊዜ ከኖሩ በኋላ ለባለ ጸጋው እንደ ተነገረው መዝገብ በሰማያት ያገኙ ዘንድ ያላቸውን ሁሉ ሸጠው ፍጹምነትን ሽተው ጌታቸውን የተከተሉ ናቸው፡፡

ይህንም በኋላ ዘመን የመጡት መነኰሳት አባቶች - እነ ቅዱስ እንጦንስና ቅዱስ መቃርስ፣ እነ ቅዱስ ጳኩሚስና ቅዱስ አሞን የመሠረቱት ሳይሆን ራሱ ባለቤቱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ትምህርት ነው፡፡ እነዚህ አባቶች ያደረጉት ነገር ቢኖር ጌታችን በሕይወቱ በተግባር ያሳየውንና በቃሉ ያስተማረውን በሙሉ ኃይላቸውና ዓቅማቸው ለመታዘዝ መነሣታቸው እና በዚያው መስመር እስከ መጨረሻ ጸንተው መዝለቃቸው ብቻ ነው፡፡

በዚህ ዓለም መኖር፣ በትዳር መኖር እግዚአብሔርን ለማገልገል አያስችልም አይባልም፡፡ በዚህ ዓለም ኖረው እግዚአብሔርን ያገለገሉና ደስ ያሰኙ እርሱ የሚያውቃቸው፣ ለእኛም በመጻሕፍት የተገለጡና የምናውቃቸው ብዙ ቅዱሳን ነበሩ፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ወደዚህ ዓለም ውጣ ውረድ ሳይገቡ የሚኖሩ ግን ጊዜያቸውንና አእምሯቸውን ሁሉ እግዚአብሔርን ለማገልገልና ለተዘክሮተ እግዚአብሔር ለማዋል የበለጠ ይመቻቸዋል፡፡ ይህን እውነታም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡-

> ነገር ግን ያለ አሳብ ልትኖሩ እወዳለሁ። ያላገባው ጌታን እንዴት ደስ እንዲያሰኘው የጌታን ነገር ያስባል፤ ያገባው ግን ሚስቱን እንዴት ደስ እንዲያሰኛት የዓለምን ነገር ያስባል፣ ልቡም ተከፍሏል። ያልተጋባች ሴትና ድንግል በሥጋም በነፍስም እንድትቀደስ የጌታን ነገር ያስባሉ፤ የተጋባች ግን ባሏን እንዴት ደስ እንድታሰኘው የዓለምን ነገር ታስባለች። ይህንም ለራሳችሁ ጥቅም እላለሁ፤ በአገባብ እንድትኖሩ ሳትባክኑም በጌታ እንድትጸኑ ነው እንጂ ላጠምዳችሁ ብዬ አይደለም። 1 ቆሮ. 7፥32-35

መቀደስንና መልካም የሆነ ብርሃናዊ ሕይወትን ገንዘብ ማድረግ የሚገባን ስለ መሆኑ የተናገረውም ራሱ መምህራችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ እንዲህ ብሎ፡- "መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።" ማቴ. 5፥16 እነዚህ መልካም ሥራዎችም በዋናነት ጌታችን ይህን አባታዊ ትእዛዝ ከመናገሩ ቀደም አድርጎ በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ አምስት መጀመሪያ ላይ የተናገራቸው ናቸው፤ እንዲህ ብሎ፡-

> በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፣ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና። የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፣ መፅናናትን ያገኛሉና። የዋሆች ብፁዓን ናቸው፣ ምድርን ይወርሳሉና። ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፣ ይጠግባሉና። የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፣ ይማራሉና። ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፣ እግዚአብሔርን ያዩታልና። የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፣ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና። ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፣ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና። ሲነቅፏችሁና ሲያሳድዷችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ፣ ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፣ ሐሴትም አድርጉ ማቴ. 5፥3-12

ገዳማዊ ሕይወት ትሑት ለመሆን፣ ስለ ጽድቅ ለመራብና ለመጠማት፣ ልብን ንጹሕ ለማድረግ . . . ስለ ጽድቅ መሰደድ አይደለምን? በርግጥ ይህ የመነኰሳት ብቻ ሳይሆን የማንኛውም ክርስቲያን ሁሉ ዓላማ መሆን አለበት፡፡ ሆኖም መነኰሳት ከዚህ ዓለም ተለይተው በገዳም ተወስነው የሚጋደሉት ጌታችን ገንዘብ እናደርጋቸው ዘንድ ያስተማረንን እነዚህን መልካም ሥራዎች በእርሱ እርዳታ ገንዘብ ለማድረግና ለማሳደግ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን "እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ። ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና፤ እግዚአብሔርን መምሰል የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው፣ ለነገር ሁሉ ይጠቅማል" በማለት የመከረው እነዚህን እግዚአብሔርን ወደ መምሰል የሚያሳድጉንን ራሱ ጌታችን ያስተማረንን የብፅዕና ተግባራት መለማመድና ማዳበር የሚገባ ስለሆነ አይደለምን? 1 ጢሞ. 4፥7-8 ታዲያ ራሳቸውን ከዚህ ዓለም ተግባር ለይተው ሙሉ ሕይወታቸውን ለእንዲህ ዓይነት አኗኗር የሰጡ ሰዎች መኖራቸው ያስመሰግናቸዋል እንጂ የሚያስነቅፋቸው ምኑ ላይ ነው? የታዘዘውን ማድረግ ያልቻለ ሰው እርሱ ባለመቻሉ ራሱን ሊወቅስ፣ በዚህ መንገድ የተጓዙትንና ለመጓዝ እየተጋደሉ ያሉትን ደግሞ ሊያከብር ሲገባው በተቃራኒው እንዲህ ማድረግ ባለመቻሉ ራሱን እያመሰገነ

ማድረግ የቻሉትንና እየሞከሩ ያሉትን ደግሞ እየነቀፈ መታየቱ በጣም የሚገርም ነገር ነው! ሰነፉ ሠራተኞውን፡ ደካማው ብርቱውን፡ ገና ያልጀመረው የጀመረውን፡ ወይም የፈጸመውን ሲነቅፍ ማየት የሚገርም ነገር ነው! ጌታችን "እንግዲህ ከእነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥት ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፤ የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥት ሰማያት ታላቅ ይባላል" ያለው ቃሉስ አይፈርድምን? ማ. 5፥19

ስለዚህ ራስን ስለ እግዚአብሔር ሲሉ ድሀ ማድረግና እርሱን ብቻ ገንዘብ አድርጎ የመኖር ሕይወት የሆነው ገዳማዊ ሕይወትና ምንኩስና በወንጌል የተገለጠው ትምህርትና ሕይወት ቀጣይ አካልና ተግባራዊ አፈጻጸም እንጂ ሌላ ባእድ ነገር አይደለም፡፡ መድኃኒታችን ስለ መንግሥተ ሰማያት ከተናገራቸው ምሳሌዎች መካከል አንዱም ይህን የተመለከተ ነበር፤ "ደግሞ መንግሥተ ሰማያት በእርሻ ውስጥ የተሰወረውን መዝገብ ትመስላለች፤ ሰውም አግኝቶ ሰወረው፥ ከደስታውም የተነሣ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠና ያን እርሻ ገዛ።" ማቴ. 13፥44 ይህን የተሰወረውን መዝገብ በትክክል የተረዱና ያዩ ሰዎች ያን እርሻ ክርስቶስን ለመግዛት ይችሉ ዘንድ ያላቸውን ሁሉ - በዚህ ዓለም ሕይወት ሊገኝና ሊደረስበት የሚችለውን ነገር ሁሉ ሸጡ (ተውት)፡፡ ይህ የተሰወረውን ማየት የሚችል እርቆ አስተዋይነታቸውንና ካዩትም በኋላ ያን ለማግኘት ቁርጥ ሕሊናቸውን ያሳያል፤ ያስመሰግናቸዋል እንጂ የሚያስነቅፍ አንዳችም ነገር የለውም፡፡

4) አዳም ከመበደሉ በፊት በገነት የነበረውን ሕይወት የሚያሳይ "ዓለም" ነው

አዳም ከመበደሉ በፊት በገነት ሳለ የአኗኗሩ መገለጫዎች የነበሩ ብዙ ነገሮች ነበሩ፡፡ ከእነዚህም መካከል ከእንስሳትና ከአራዊት ጋር ያለ ምንም ችግር በሰላም ይኖር ነበር፡፡ ከዚህም በላይ የእንስሳትና የአራዊት ገዢያቸው እርሱ ስለ ነበር እግዚአብሔር ወደ እርሱ አምጥቷቸው ስም ያወጣላቸው እርሱ ነበር፡፡ ያ ሁኔታ በአዳም ኃጢአት ሲበላሽ ግን ያ ግንኙነት ቀርቶ እንዲያውም ሰውን የሚያስፈሩትና የሚጣሉት ሆኑ፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዳም አርባ ቀንና ሌሊት በተከታታይ ያለማቋረጥ ሲጾምና ሲጸልይ በዚያ ስለ ነበረበት ሁኔታ ቅዱስ ወንጌል እንዲህ ይላል፡- "ወዲያውም መንፈስ ወደ ምድረ በዳ አወጣው። በምድረ በዳም ከሰይጣን እየተፈተነ አርባ ቀን ሰነበተ፡፡ ከአራዊትም ጋር ነበረ፥ መላእክቱም አገለገሉት፡፡" ማር. 1፥12-13

እንግዲህ ጌታችን በመጀመሪያው አዳም ኃጢአት ምክንያት ተለያይተውና በጠላትነት ጎራ ተሰልፈው የነበሩትን ሰውንና አራዊትን በበረሓ ባደረገው ተጋድሎ ወደ ቀደመ አንድነታቸው መመለስን በተግባር አሳየን፡፡ በዚያ በበረሓው ጌታችን ከአራዊት ጋር አብሮ በመሆን የእርሱን ፈለግ ተከትለው በበረሓ በብሕትውና ለሚጋደሉና ለሚጸኑ ገዳማውያን ከአራዊት ጋር መኖር እንደሚችሉ በተግባር አሳየን፡፡ በገነት የነበረውንና የጠፋውን ሰላምና አንድነት በምድር ላይ - በገዳመ ቆሮንቶስ - በተግባር መልሶ አሳየን፡፡

ስለሆነም የገዳማውያን አበው ሕይወትና ገዳማት ቀድሞ በቀዳማዊው አዳም ተበላሽቶና ታጥቶ የነበረውን፡ ኋላ ግን ለስም አጠራሩ ክብርና ምስጋና ይግባውና በዳግማዊ አዳም በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተመለሰውን ያን ሕይወት በተግባር የሚያሳዩ በምድር ላይ ያሉ ገነቶች ናቸው፡፡ ሰው እግዚአብሔርን ባለማመንና ባለመታዘዙ ምክንያት አጥቶት የነበረው ጸጋ በዳግማዊ አዳም በኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ተመለሰልን የሰው ልጅ ወደ ቀደመ ክብሩ የተመለሰ መሆኑን በተግባር የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ቅዱሳን ገዳማውያንና በረሓውያን አበው በእግዚአብሔር ካላቸው ፍጹም እምነትና ከመታዘዛቸው የተነሣ እንስሳትና አራዊት ይታዘዙላቸዋል፤ ከእነርሱ ጋር በኅብረትና በሰላም ተደባልቀው እስከ መኖር ይደርሳሉ፡፡

በተለያዩ የገዳማውያን ዜናዎች እንደምናገኘው የዱር እንስሳትን ውኃ የሚያጠጧቸውና የሚመግቧቸው፣ ሲታመሙ የሚፈውሷቸው፣ ድርቅ ሲሆንባቸውና እንስሳቱ ዝናም ሲፈልጉ ወደ ቅዱሳኑ ቀርበው በራሳቸው መንገድ ችግራቸውን የሚገልጹበትና ቅዱሳኑም ያን በመንፈስ ተረድተው ስለ እነርሱ ጸልየው ዝናም እንዲያገኙ ያደረጉባቸው ጊዜያት ነበሩ፡፡ ለምሳሌም ቅዱስ መቃርዮስ ዘእስክንድርያ አንዲት ጅብ ወደ እርሱ መጥታ እንዲከተላት በመፈለግ ዓይነት ሁኔታ ጨርቁን ይዛ እንደ መጎተት ባደረገች ጊዜ በሁኔታው በመገረም እስከ ጉድጓዷ ድረስ ተከተላት፡፡ ከዚያም ዓይናቸው የማያይ ቡችላዎቿን ከጉድጓዷ አውጥታ በፊቱ አስቀመጠችለት፡፡ እርሱም በመደነቅ ጸልዮ እንዲያዩ አደረጋቸው፡፡ እርሷም ለቅዱስ መቃርዮስ አንድ የበግ አጎዛ ከጉድጓዷ አውጥታ ሰጠችው፡፡ ቅዱስ መቃርዮሰም በመገረም የሰጠችውን አጎዛ ይዞ ወደ በዓቱ ሄደ፡፡

እንደዚሁም ሰዎችን የሚያስቸግሩ ክፉ አራዊትን ደግሞ በባዶ እጃቸው የሚገድሉ፣ በተግሣጽ የሚመለሱትን ደግሞ በቃል የሚቆጡና አራዊቱም ቃላቸውን የሚታዘዟቸው ቅዱሳን ነበሩ፡፡ ለምሳሌም በ4ኛው መቶ ዓመት ማብቂያ ገደማ ከኢየሩሳሌም ወደ ግብጽ በረሓ ሄደው በዚያ የነበሩትን ባሕታውያን ቅዱሳን ዜና ሕይወት በዓይናቸው ያዩትንና በጆሯቸው የሰሙትን ጽፈውልን የሄዱት ሰባቱ መነኰሳት በጻፉት መጽሐፍ ላይ አባ አፖሎ የተባለ ባሕታዊ ደቀ መዝሙር እባብን በባዶ እጁ ይገድል እንደ ነበር፣ አባ ዲዲሞስ የተባለው ደግሞ ጊንጦችን በባዶ እግሩ ይረግጣቸውና ይገድላቸው እንደ ነበር፣ አባ አሞን የተባለው ባሕታዊ ደግሞ እባቦችን በዓቱን እንደ ዘበኛ ያስጠብቃቸው እንደ ነበር፣ ሆኖም ለሰዎች ሕይወት ስጋት የሆኑትን ደግሞ እንዲጠፉቸው፣ አባ ሄል የተባለው አባት ደግሞ አዞዎችን የዓባይን ወንዝ ለመሻገርና በዚያው ላይ ለመሄድ ይጠቀምባቸው እንደ ነበር ... ተጽፎ እናገኛለን፡፡[131]

በገዳማዊ ሕይወት ከውድቀት በፊት የነበረውን የአዳም ሕይወት የሚያዘክሩና የሚያሳዩ ሌሎች ሁኔታዎችም አሉ፡፡ ለምሳሌ በበረሓ ብቻቸውን ለሚጋደሉ ባሕታውያን ሰማያዊ ኅብስትና ጽዋ የሚመጣላቸውና ከምድራዊ ምግብና መጠጥ ነጻ ሆነው የሚኖሩ ነበሩ፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን ነቢዩ ኤልያስ ይህን ዓይነት ጸጋ አግኝቶ እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ 1 ነገ. 19፡ 5-8 ለምሳሌም አባ ኪሮስን ለምናኔ ሲወጣ የተቀበለውና ደመና ጠቅሶ አስቄጥስ ገዳም ከአባ ተርዋ ዘንድ ልብሰ ምንኵስናን ይዞ በዚያው ቀን ከሰዓት በኋላ በደመና ተመልሶ አባ ኪሮስን ልብሰ ምንኵስና ያለበሰው አባ በብኑዳ የተባለው በዮርዳኖስ በረሓ ይጋደል የነበረው ባሕታዊ ቅዱስ ሚካኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ እየተላከ ማታ ማታ ሰማያዊ ኅብስት ያመጣለት ነበር፡፡ እንደዚሁም አባ ኪሮስም በታመመ ጊዜ ቅዱስ ሚካኤል ኅብስት ሰማያዊ ይዞለት መጥቶ ብላ እያለ እያጽናና እንዲመገብ አድርጎታል፡፡[132]

አባ ፓቴርሙቲየስ የተባለ በግብጽ በረሓ የነበረ አባት ደግሞ በየሳምንቱ ይመገበው ዘንድ ተአምራዊ የሆነ ኅብስት ይሰጠው ነበር፡፡ አባ ሖር ደግሞ ለሦስት ሳምንታት ያህል በመልአክ አማካይነት ተመግቧል፡፡[133] ይህ ለብዙ በረሓውያን ቅዱሳን ይደረግላቸው የነበረ ቸርነት ነው፡፡ ዛሬም እኛ ባናውቅም እግዚአብሔር ቸርነቱ አይቋረጥምና ይህን መሰል ጸጋ የሚያገኙ የእርሱ አገልጋዮች ይኖራሉ፡፡ ስለዚህ ገዳማዊ ሕይወትና ገዳማት የገነትን አኗኗር በተግባር የሚያሳዩ፣ ሰው ለእግዚአብሔር ታማኝ ከሆነና ከዚህ ዓለም ፍትወትና ምኞት በራቀና ወደ እግዚአብሔር በቀረበ መጠን እግዚአብሔር ደግሞ በምን ያህል እንደሚያቀርበውና ጸጋውን አብዝቶ እንደሚሰጠው በተግባር የሚያሳዩ ሕያው ምስክሮች ናቸው፡፡ ገዳማት "በምድር ላይ ያሉ ገነቶች" ናቸው፡፡

[131] Norman Russell and Benedicta Ward S L G, 1980, The Lives of the Desert Fathers, Cistercian Publications, Michigan, USA, pp. 42-44.

[132] ገድለ ቅዱስ ኪሮስ

[133] Norman Russell and Benedicta Ward S L G, 1981, The Lives of the Desert Fathers, The Historia Monachorum in Aegypto, Cistercian Publications, Michigan, USA, pp. 42-44

## 7.3 ማርቲን ሉተር ምንኩስናንና ገዳማዊ ሕይወትን የተቃወመባቸው ምክንያቶች

በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን እና በፕሮቴስታንቶች መካከል (በሮማ ካቶሊክ እና በፕሮቴስታንቶች መካከልም ጭምር) ላለው ትልቅ ልዩነት መነሻ ነጥቦቹ በሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ውስጥ በሚገኙ ሃሳቦች ላይ ያሉ አረዳዶችና አተረጓጎሞች ናቸው፡፡ ተሐድሶዎች እኛ አገር አሁን እንደ አዲስ ብርቅና ድንቅ መስሏቸው ወይም አስመስለው ለማራገብ የሚሞክሯቸው ጉዳዮች በ16ኛው መቶ ዓመት በጀርመናዊው ማርቲን ሉተር፣ በፈረንሳዊው ጆን ካልቪንና በስዊዘርላንዳዊው ኡልሪች ዝዊንግሊ የተቀነቀኑና ውዝግብ የፈጠሩ ጉዳዮችን ነው፡፡ በርግጥ የተወሰኑት ጉዳዮች ከዚያ በፊትም በአንዳንድ ግለሰቦች ብቅ ጥልቅ በሚል ሁኔታ ሲንጸባረቁ ነበር፡፡ ሆኖም የእነዚያን ሁሉ አጠራቅሞ በዘመኑ የነበሩትን ሁኔታዎች ተጠቅሞ በከፍተኛ ሁኔታ ያራገባቸውና አዲስ የእምነት አቅጣጫ አድርጎ ያመጣቸው ማርቲን ሉተር ነው፡፡

በአውሮፓ የተሐድሶን ክብሪት የጫረው ማርቲን ሉተር ራሱ በመጀመሪያ የካቶሊክ መነኩሴ ነበር፡፡ ነገር ግን በእንድ በኩል ወደ ምንኩስና የገባው ሕይወቱን (ምንኩስናን) ከመጀመሪያው ፈልጎትና አውጥቶና አውርዶ መርጦት ሳይሆን በድንገት መብረቅ ባስደነገጠው ጊዜ ከዚህ መዓት ብታወጣኝ እመነኩሳለሁ ብሎ ስለት ተስሎ ስለ ነበር ነው፡፡ የተሳለውም ለቅድስት ሐና ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከኬልቄዶን ጉባኤ ከእንዲቷ ቤተ ክርስቲያን ከተለዩበት ጊዜ ጀምሮ በየጊዜው ከእውነት እየተንሸራተቱና እየራቁ በመሄድ በውስጣቸው ብዙ ስው ሠራሽ የሆኑ ኢክርስቲያናዊ አስተምህሮዎችና ተግባራት ተስፋፍተው ነበር፡፡ በተለይም ሉተር መነኩሴ ሆኖ በነበረበት በ16ኛው መቶ ዓመት ላይ ተስፋፍተው ከነበሩት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ልማዶች መካከልም በዋናነት የሚከተሉት ጉዳዮች ተጠቃሾች ናቸው፦

1) <u>የተትረፈረፈ የብቃት መዝገብ ("Treasury of merits")</u> - ሁል ጊዜም ሕጋዊና ፍርድ ቤታዊ (Juridical and legalistic tendency) መንፈስና ዝንባሌ ውስጧን ሰርስሮ የተቆረሳት የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የተትረፈረፈ የብቃት መዝገብ ("treasury of merits") ያላቸው ሰዎች (ቅዱሳን) በመጻን መንገድ ድጋፍና ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ከዚህ የጸጋ መዝገብ ለእነዚያ ማስተላለፍ ይቻላል የሚል ትምህርት ፈጥራና አዳብራ ነበር፡፡ በርግጥ ይህ አስተሳሰብና ንድፈ ሃሳብ በቀላሉ ሊገለጽ የሚችል ዓይነት አይደለም፤ ሆኖም ባልሆነ መንገድ ሊተረጎምና ለስህተት ሊዳርግ የሚችል ግን ነበር፡፡ በሮም ቤተ ክርስቲያን እምነት ፖፑ የቅዱስ ጴጥሮስ ወራሴ መንበር ስለሆነ ብቻ በምድር ላይ የክርስቶስ እንደራሴ ነው፡፡ የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ የተሰጠው፣ የማሰርና የመፍታት ሥልጣንም የተሰጠው ለቅዱስ ጴጥሮስ ስለሆነ፣ ይላሉ የሮም ቤተ ክርስቲያን ሰዎች፣ ፖፑ የእርሱ ወራሽ በመሆኑ የዚህን የጸጋ ማስተላለፍ መብት የመፍቀድና ተፈጻሚነቱንም በተመለከተ የመወሰን ሥልጣን የፖፑ ነው ባዮች ነበሩ፡፡ ይህ እነዚህን ጸጋዎች ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች የማስተላለፍ መብት ደግሞ "የሥርየት ካርድ" የሚባለው ነው፡፡[134]

[134] Georges Florovsky, The Ascetic Ideal and The New Testament, Reflections on the Critique of the Theology of the Reformation, The Collected Works, Vol. X.

2) የሥርየት ካርድ (Indulgence card) - ከተሳሳተ መሠረት የበቀለው አስተሳሰብ እያደገ ሲሄድ በመካነ ደይን (Purgatory) ያሉ ነፍሳትን ለማውጣት በፖፑ ፈቃድ የሚሸጥ የሥርየት ካርድ ታላቅ ጠሜታ አለው እያለች ማስተማር ጀመረች፡፡ በተለይ ደግሞ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በሮም ቫቲካን ላይ በጣም ትልቅ የሆነ የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት ብዙ ገንዘብ አስፈልጓት ስለ ነበር የሥርየት ካርዱን እንዲሸጡ ለየአገራቱ ካርዲናሎች ተሰራጩ፡፡ በየቦታው ስለ ሥርየት ካርድ የሚሰጠው ትምህርትና ውትወታም ተጠናክሮ ቀጠለ፡፡ በዚህም ቤተ ክርስቲያኗ ለጠላቶቿ ጥቃት የተመቸች ሆና ተገኘች፡፡

3) በመልካም ሥራ መዳን - ነገሮችን ሁሉ ከፍርድ ቤትና ከሕግ አኳያ ማየትና መተንተን መገለጫዋ የሆነው የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለመዳን የመልካም ሥራን አስፈላጊነት ጎላ ባለ ሁኔታ፣ አንዳንዴም በእምነትና በእግዚአብሔር ቸርነት የሚገኘውን መዳን ወደ መዘንጋት ደርሳ መልካም ሥራ ላይ ብቻ ተንጠልጥላለች ብለው ተቃዋሚዎቿ በሚከሱባት ሁኔታ ላይ ነበረች፡፡ ከእምነትና ከምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ጋር በተዋሐደና ምልዓት ባለው ግንዛቤ ከመሆን ይልቅ የግል ተጋድሎና መልካም ሥራ ላይ የተንጠለጠለ የመዳን አስተምህሮ ይንጸባረቅባት ነበር ብለው በዘመኑ የነበሩ ተቃዋሚዎቿ ይከሷት ነበር፡፡

እንግዲህ ሉተር የነበረው በዚህ ዓይነት የዘመን ዳራ ውስጥ ነበር፡፡ በካቶሊክ ቤተ እምነትና እርሱ በነበረበት ገዳም ለመዳን ለመልካም ሥራ ይሰጥ የነበረው ከመጠን ያለፈና የተጋነነ ቦታ፣ እንዲሁም እርሱ በአውግስጢኖስ የቅድመ ምርጫ እና የመመረጥ አለመመረጥ እድል ላይ የተመሠረተ የነበረው እምነቱ ከውስጡ እየካዱት ሄዱ፡፡ ጥንቱንም በካቶሊክ ድቡሽት ላይ የተመሠረተ የነበረው የሉተር መሠረተ እምነት (አስተምህሮ) በአንድ በኩል በድንገት ድንጋጤ ላይ ብቻ ተመሥርቶ በስእለት የገባበት የምንኩስና ሕይወት እየከበደው ሄደ፡፡ በዚህም በከፍተኛ ሁኔታ የጭንቀት ተጠቂ ሆነ፡፡

ከዚህ ችግሩ የተነሣም መጽሐፍ ቅዱስን ከጭንቀት ያወጣኛል ብሎ ባሰበበት መንገድ ለመተርጎም በመነሣት በመጨረሻ ሐዲስ ኪዳንን በራሴ አረዳድ በአዲስ መንገድ ተረድቸዋለሁ በማለት ከመጽሐፍ ቅዱስና ከአበው አስተምህሮ የተለየና እንግዳ የሆነ አስተምህሮ ይዞ ብቅ አለ፡፡ ይህ እንግዳና ባእድ ትምህርቱም በዋናነት *"መዳን በእምነት ብቻ"* የሚል ነበር፡፡ ለዚህ እንግዳ ትምህርቱ ዋና መነሻና ድጋፍ ያደረጋቸውም የቅዱስ ጳውሎስን የሮሜ እና የገላትያ መልእክታት ነበር፡፡ ይህን አዲስ የሆነ እንግዳ ትምህርቱንና የራሱን አተረጓጎምና አረዳድም "<u>አዲስ የሆነ የቅዱሳት መጻሕፍት መገለጥ</u>" ሲል ራሱን በራሱ ለማሞካሸት ሞክሯል፡፡ ከእርሱ ወዲህ በየቦታውና በየጊዜው ለሚነሱ ተሐድሶ ነን ባዮች ሁሉ ዋናው ምንጫቸውና መምህራቸው ይህ የሉተር በሁለቱ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ላይ ትርጓሜ (ሐተታ) ብሎ የጻፈው መጽሐፍ ነው፡፡ ሉተር ገዳማዊ ሕይወትንና ምንኩስናን የተቃወመውም በእነዚህ ሥራዎቹ (ድርሰቶቹ) ነው፡፡

ሆኖም ሉተር ቅዱስ ጳውሎስ ስለ መዳን ያስተማረውን ትምህርት በአዲስ መልኩ ተረዳሁት በማለት የሄደበት መንገድ ቅዱስ ጳውሎስን በተሳሳተ መልኩ በመረዳትና ጭልጥ ብሎ መስመር ስቶ በመጓዝ ነበር፡፡ አንደኛው ችግሩ ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስን በአጠቃላይና የቅዱስ ጳውሎስን መልእክታትንም ሁሉንም ባላገናዘበ መልኩ በሁለቱ መልእክታት ላይ ብቻ መወሰኑ ሲሆን ሌላው ችግሩ ደግሞ ከሮሜ መልእክትና ከገላትያ መልእክታትም ቢሆን ከላይና ከታች ያለውን አጠቃላይ ሐሳብ ትቶ ለሚፈልገው አዲስ አስተሳሰብ ይስማሙኛል ያላቸውን ጥቅሶች ብቻ እየመረጠ በመገጣጠም መሆኑ ነበር፡፡ ይህም አልበቃ ብሎት ቅዱስ ቃሉ ከሚለው ውጭ የሌለ ነገር እስከ መጨመርም ደርሷል፡፡ በሮሜ ምዕራፍ 3 ቁጥር 28 ላይ ቅዱስ ጳውሎስ *"ሰው ያለ ሕግ ሥራ <u>በእምነት እንዲጸድቅ</u> እንቆጥራለንና"* ያለው ቃል ላይ *"<u>በእምነት</u>"* ከሚለው ቀጥሎ "<u>ብቻ</u> "alone"–*allein*" የሚል ቃል እስከ መጨመር ደርሶ ነበር፡፡ እርሱ ከላቲን ቋንቋ ወደ ጀርመንኛ ቋንቋ በተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስ ላይም *"በእምነት ብቻ"* የሚለው ይህ የሉተር ጭማሬ ለብዙ ጊዜያት አብሮ ሲታተም ኖሯል፡፡

ይህም በቅዱስ ያዕቆብ መልእክት ላይ "ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ" ለሚለው ቃል ማፍረሻና ማሳተባበያ ለማድረግ ብሎ ነበር፡፡ ያዕ. 2፡24 የእግዚአብሔር ቃል በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለመጨመር የደፈረ ሰው ሌላ ነገር ቢል ምን ይገርማል! እንደዚሁ ዓይነቶቹ ደፋሮች ሉተራውያን ናቸው ራሳቸውን ለመጽሐፍ ቅዱስ ታማኞችና ተቆርቋሪዎች አስመስለው ሊያቀርቡና ሊያታልሉ የሚሞክሩት፡፡ እንዲህ ማለት ቢያስፈልግ ኖሮስ "ለማያውቅሽ ታጠኚ" የሚለው ብሂል የሚስማማው ለእነርሱ ነበር!

ሉተር በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስለ ጨመረው አዲስ የራሱ ቃል ይሰነዘርበት ለነበረው ተቃውሞ ለሮማ ካቶሊክ ሰዎች በጻፈው ላይ እንዲህ አለ፦

> እናንተ ፓፒስቶች (የፖፑ ተከታዮች - ካቶሊኮችን ማለቱ ነው) እኔ ስለ ጨመርኩት 'ብቻ-sola - allein' ስለሚለው ቃል የሚጨንቃችሁና የምትራወጡ ከሆነ ለፓፓችሁ እንዲህ ብላችሁ ቁርጡን ንገሩት፦ 'ዶክተር ማርቲን ሉተር የጨመረውና እንዲጨመር የፈቀደው ይህ ቃል እንደ ተጨመረ ይቀጥላል፡፡' አሁንም ዶክተር ማርቲን ሉተር እንዲህ ይላል፦ 'ፓፒስት እና አህያ አንድ ናቸው፡፡ እኛ የእነርሱ መምህራንና ዳኞች ልንሆን እንጂ የፓፒስቶች ደቀ መዛሙርትና ተከታዮች ልንሆን አንሻም፡፡ (Philip Schaff, *History of the Christian Church*, 8 vols., New York: Charles Scribner's Sons, 1910.)

በመቀጠልም ራሱን ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ለማስተካከል በሚመስል መልኩ[135] እንዲህ ብሏል፦

> እነርሱ ዶክተሮች ናቸውን? እኔም ነኝ፡፡ እነርሱ የተማሩ ናቸውን? እኔም ነኝ፡፡ ቴዎሎጂያን ናቸውን? እኔም ነኝ፡፡ ፈላስፎች ናቸውን? እኔም ነኝ፡፡ መጻሕፍትን የሚጽፉ ናቸውን? እኔም እንዲሁ ነኝ፡፡ ከዚህም በላይ የምመካበት አለኝ፤ እነርሱ ሊተረጉሟቸው የማይችሉትን መዝሙራትንና ነቢያትን እኔ እተረጉማቸዋለሁ፡፡ . . . ስለዚህ "ብቻ - *allein*" የሚለው እኔ የጨመርኩት ቃል በእኔ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳለ ይቀጥላል፤ አህዮች የሆኑ ፖፑና መሰሎቹ ቢቆጡና ቢጃጃሉም ይህን ቃል የሚያወጣላቸው የለም፡፡ (Philip Schaff, *History of the Christian Church*, New York: Charles Scribner's Sons, 1910.)

ሉተር ወደ ጀርመንኛ ተርጉሞ ባሳተመው ሐዲስ ኪዳን ላይ ለተወሰኑ ዘመናት እርሱ የጨመረው ባእድ ቃል አብሮ ሲታተም ቆይቷል፡፡ እንዲያውም በአንዳንድ የጀርመንኛ ኅትመቶች "ብቻ" የሚለው ቃል ጎላ ብሎ ይታተም ነበር፡፡ የስህተቶቹ ቁጥር ከሰዎች ሰዎች ቢለያይም ሉተር ተረጎምኩት ያለው መጽሐፍ ቅዱስ የራሱን የፈጠራ ሐሳብ እንዲደግፍለት ለማድረግ ሲል ብዙ ሰዋሰዋዊና ይዘታዊ (የጭብጥ) ስሁተቶች ያሉበት መሆኑ በብዙ ምሁራን የተገለጸ ጉዳይ ነው፡፡ ገና ከጥንቱ በ1523 ዓ. ም. የነበረውና ዶ/ር ኤምሰር የተባለው ሰው ሉተር የተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስ ወደ አንድ ሺህ (1,000) የሚጠጋ የሰዋስው (Grammatical) እና አንድ ሺህ አራት መቶ (1,400) ኑፋቄያዊ (Heretical) ስህተቶች እንዳሉበት ገልጾ ነበር፡፡

ማርቲን ሉተርና በየዘመኑ የሚወለዳቸው ልጆቹ ምንኩስናንና ገዳማዊ ሕይወትን የሚቃወሙበት አንደኛውና ዋናው መነሻቸው "መዳን በእምነት ብቻ" ከሚለውና "በመዳን ሂደት ሰው የራሱ የሆነ አንዳችም ድርሻ የለውም" የሚለው የተሳሳተና የፈጠራ አሳባቸው ነው፡፡ መዳን የእግዚአብሔር የቸርነቱ የነጻ (የጸጋ) ስጦታ መሆኑ እና ሰው በእምነት የሚድን መሆኑ ከመጀመሪያው ዘመን ጀምሮ የሚታመን እውነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው፡፡ ይህ ለቤተ ክርስቲያን ጥያቄ አልነበረም፡፡

---

135 ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል፦ "ዕብራውያን ናቸውን? እኔ ደግሞ ነኝ። የእስራኤል ወገን ናቸውን? እኔ ደግሞ ነኝ። የአብርሃም ዘር ናቸውን? እኔ ደግሞ ነኝ። የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸውን? እንደ እብድ ሰው እላለሁ፤ እኔ እበልጣለሁ፤ በድካም አብዝቼ፥ በመገረፍ አብዝቼ፤ በመታሰር አትርፌ፤ በመሞት ብዙ ጊዜ ሆንሁ።" 2 ቆሮ. 11፡22-23

ነገር ግን በሉተር አረዳድ በገዳማዊ ሕይወት መጋደልና መልካም የሆኑ የቅድስና ሥራዎችን መሥራት በጸጋ የተሰጠውን መዳን እና የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታ የሚቃወሙ አድርጎ ይቆጥራቸው ጀመር፡፡ ይህም ችግሩ በዋናነት እርሱ በገዳም ሳለ ከተዋረሰው የሚያስጨንቅ መንፈስና በራሱ ጥረት ብቻ የሚዳን መስሎት ሲያደርገው ከነበረው የራሱ የተሳሳተ እምነትና ድርጊት አንጻር የተፈጠረበት አጸፌታ (Reaction) ነበር፡፡ ከዚህም ጋር የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በእነዚህ ነገሮች ላይ የነበራት ሕግ ተኮር አስተሳሰብና በየጊዜው የጨመረቻቸው ባእድ ነገሮች ሕይወቱ ከብዶት ለነበረው ለሉተር በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ እንደሚባለው ዓይነት ነገር ሆነበት፡፡

ለሉተር "ጽድቅ" ማለት እፍአዊ (ውጫዊ) የሆነ ጽድቅ ነው፡፡ ይህም ማለት በሉተር አረዳድ "ማጽደቅ" ("to justify—*dikaion*") ማለት አንድን ሰው የሆነ ሌላ አካል እንዲሁ ፈቃዱ ስለ ሆነ ብቻ ወይም በሆነ መንገድ ያንን ሰው "ጻድቅ" ነው ብሎ ማወጅ፣ ጻድቅነቱን መመስከር ማለት ነበር፡፡ ይህም በዚህ ዓለም በፍርድ ቤቶች እንደሚደረገው ዓይነት የሆነ እፍአዊ "መጽደቅ" ነው እንጂ በክርስትና የሚታወቀው መጽደቅ አይደለም፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው "ጻድቅ" ተብሎ ቢታወጅለትም ይህ አዋጅ ውስጣዊ ማንነቱን አይለውጥለትም፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘው መጽደቅ ግን እንዲሁ በውጭ በአዋጅ "ጻድቅ" ከመባል በላይ ውሳጣዊ ሁለንተናችንንና መንፈሳችንን ሁሉ የቀደሰ፣ ሕሊናን ሁሉ ዘልቀ የሚገባ ነው፡፡ "አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም" ተብሎ እንደ ተገለጸው ጥልቅና ውሳጣዊ ነው እንጂ ውጫዊና በብይን የተሰጠ "ጽድቅ" አይደለም፡፡ ፊል. 4፡7 ስለዚህ በዋናነት የሉተር የጽድቅና የመጽደቅ አረዳድና ጽንሰ ሓሳብ በዚህ ዓለም ባለው የሕግ ሂደት ላይ የተመሠረተና ከክርስቲያናዊ የመዳን ትምህርት ጋር የማይስማማ ነው፡፡

ሉተር በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በእርሱ ዘመን ካየውና ከነበረው ሕግ ተኮር አረዳድና አመለካከት (Legalism) በጣም የባሰ ሕግ መራሽ አረዳድና አተረጓጎም ፈጠረ፡፡ በዚህ አረዳዱም ጽድቅ በእምነት የተገኘ ከሆነና ሰውም "ጻድቅ" ነው ተብሎ የሚታወጅለት ከሆነ "ሥራን" ምን አመጣው? ምንስ ቦታ አለው? ወደሚል በጣም የተሳሳተና አደገኛ ድምዳሜ ላይ ደረሰ፡፡ ከዚህም በመነሣት በመልካም የቅድስና ሕይወት ለማደግና በሕይወታቸው እግዚአብሔርን ለማክበር መንፈሳዊ ተጋድሎዎች የሚሠራባቸውን ገዳማትንና በዚህ ሕይወት ለመኖር ደፋ ቀና የሚሉ መነኮሳትን ክፉኛ ይነቅፍና ይተች ጀመር፡፡ መነኮሳትና መነኮሳዪያት የምንኩስና ሕይወት ብጽዓታቸውን እንዲተውና እንዲያገቡ አጥብቆ ይሰብክ ጀመር፡፡ በዚህም ብዙዎች ቆባቸውን እየተው ወደ ማግባት ሄደዋል፡፡ እርሱ ራሱ ሉተር ቆቡን ጥሎ መነኩሲት የነበረችን ሴት ቆቧን አስጥሎ አግብቷል፡፡

ምንኩስናን እንደ ሌላ ጽድቅ አድርገው የሚቆጥሩት ሰዎች - ሉተርና መሰሎቹ - መሠረታዊ ችግር በዋናነት በመጽሐፍ ቅዱስ ያለውን የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉንም በምልዓት ሳይሆን እነርሱ ለሚፈልጉት ንድፈ ሐሳብ የሚመቻቸውን ብቻ እየመረጡ መውሰዳቸው ነው፡፡ ከዚህም ጋር በቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት "ሥራ" ተብሎ የተገለጸው በኦሪት ሕግ ያለውን "ሥራ" ነው? ወይስ በክርስትና የሚፈጸመውን? የሚለውን ለመለየት ጥንቃቄ ሳያደርጉ በክርስቶስ ለማያምኑና በሕገ ኦሪት ብቻ ድኅነት እናገኛለን ለሚሉ አይሁድ የተነገረውን ትምህርትና ተግሣጽ ሁሉ በክርስቶስ ያመኑ ምእመናን ከሚሠሩት የወንጌል ፍሬ ከሆነው "መልካም ሥራ" ጋር አምታቱት፣ አደበላለቁት፡፡ በተለይም ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜና በገላትያ መልእክቱ "ሥራ" እያለ የጠቀሰው በኦሪት ሕግ ስላለው፣ በተለይም በዚያን ዘመን በፈሪሳውያን የሕጉ አረዳድ ተመሥርቶ ስለ ነበረው ነው፤ ምክንያቱም በእነዚህ መልእክታት ላይ ዋናው የቅዱስ ጳውሎስ ተጋድሎ ከአይሁዳዊነት (Judaizers) ጋር ነበር፡፡

ጌታችንም ሕጉን አፍአዊ በሆነና መንፈሳዊ ባልሆነ መንገድ ይረዱ የነበሩትን ፈሪሳውያንን ወቅሷቸዋል፡፡ በሮሜ መልእክቱ ላይም ቅዱስ ጳውሎስ የአይሁዳዊነትን አፍአዊ የሆነ የሕጉን አረዳድና አተረጓጎም መንፈሳዊና ውሳጣዊ ከሆነው አረዳድ፣ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆን፣ በሞቱና በትንሣኤው ከፈጸመው አዲስ መገለጥና ለሰዎች ከሰጠው አዲስና ልዩ ጸጋ አንጻር እያነጻጸረ መሆኑን በየአንቀጹ እናየዋለን፡፡ የእግዚአብሔር አካላዊ ቃል ሰው መሆን በሰዎች ሕይወትና ማንነት ላይ የፈጠረው አንድምታ እጅግ በጣም ጥልቅ ነው፡፡ ይህን በእግዚአብሔር ሰው የመሆን ምሥጢር ማየት ያልቻሉ አይሁድ በኦሪት ሕግ የታዘዙትን መሥዋዕቶችንና የመንጻት ሥርዐቶች በመፈጸም ብቻ ጽድቅ ይገኛል ብለው ማሰባቸውና በዚያው ስህተታቸው ላይ መቀጠላቸው፣ እንዲሁም ወደ ክርስትና ከገቡት አይሁድ መካከልም የተወሰኑት ያ ኦሪታዊ እርሾ አልለቃቸው ብሎ ይቸገሩና ያስቸግሩ ስለ ነበር "የሕግ ሥራ"፣ "ሥራ" እያለ ደጋግሞ የገለጸው ይህን በሕገ ኦሪት ያለውን እንጂ በክርስቶስ አምኖ በእርሱ ቸርነት የሚሠራውን ክርስቲያናዊ መልካም ሥራ አይደለም፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ አንድም ቦታ ላይ ክርስቲያኖች የሚሠሩትን መልካም ሥራ አልነቀፈም፣ በጭራሽ! ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ "ሥራ" በማለት የገለጸውና የነቀፈው "የኦሪቱን የሕግ ሥራ" ሳይሆን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን "ክርስቲያናዊ መልካም ሥራ ነው" ብሎ ማሰብ ያልተጸፈ የማንበብ ታላቅ ስህተት ነው፡፡ ሉተርን ወደዚህ ዓይነት ጽንፈኛ የስህተት አረዳድ የገፋው ከላይ እንዳየነው በሮማ ካቶሊክ ዘንድ በሥራ ላይ የነበረው መጠን አለፍ ልማድና ትምህርት ነበር፡፡ ከነበረበት የሕይወትና የትምህርት ሁኔታ የተነሣም ሉተር "ሥራ" የሚል ነገር ባገኘ ቁጥር መነኩሴ ሳለ ያሰበውና ይሰማው ከነበረውና ካደገበት ከሥርየት ካርድና የመልካም ሥራ መዝገብ ከሚለው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ባህል ጋር ቶሎ ብሎ ይገናኝበት ነበር፡፡ እንዲሁም በገዳም ሳለ የነበረበትን ጭንቀትና የሕይወት ክብደት ያስታውሰው ስለ ነበር ያንን የውስጥ ጭንቀቱን ለማጥፋት ሲል "ሥራ" የሚልን ነገር ለማጥፋት ቆርጦ ተነሣ፡፡ በመሆኑም አባብ ያየ በልጥ ይደነግጣል እንደ ተባለው ሆነበትና ሉተር "ሥራ" የሚለውን ቃል ወዳልሆነ ሌላ የስህተት አቅጣጫ ወሰደው፡፡

## 7.4 ክርስቲያናዊ መልካም ሥራ በቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት

ሉተርና መሰሎቹ ተሐድሶዎች ምንኩስናንና ገዳማዊ ሕይወትን፣ እንዲሁም ክርስቲያኖች የሚያደርጓቸውን መንፈሳዊ ተጋድሎዎችና መልካም ሥራዎች የሚነቅፉት እነዚህ ነገሮች በክርስቶስ የተሰጠውን የመዳን ጸጋ ያቃልላሉ ወይም በራሴ ልዳን እንደ ማለት ናቸው በማለት ነው፡፡ ለዚህም ደጋግመው የሚጠቅሱት የቅዱስ ጳውሎስን መልእክታት ስለሆነ ከዚህ ቀጥሎ የምንመለከተው በዚሁ ሐዋርያ በቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ውስጥ በእግዚአብሔር ቸርነት የተሰጠንን መዳን እንደሚናገር ሁሉ እኛ በሚቻለን ሁሉ በመልካም ሥራ መጋደልና መጽናት፣ መንፈሳዊ ምግባር ትሩፋት መሥራት ያለብን መሆኑንም ይናገራልና እነዚህን ነገሮች ከየመልእክታቱ አጠር አድርገን እንመለከታለን፡፡[136]

አሁን በቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት በገዳማዊ ሕይወት የሚፈጸሙትን መንፈሳዊ ተጋድሎዎችና ምግባር ትሩፋት በተመለከተ የተገለጹትን ዋና ዋና ነጥቦች እንመለከታለን፡፡

<u>የሮሜ መልእክት</u>

- "በእርሱም ስለ ስሙ በአሕዛብ ሁሉ መካከል <u>ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ</u> ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀበልን" ሮሜ 1፡5

[136] Georges Florovsky, The Ascetic Ideal and The New Testament, Reflections on the Critique of the Theology of the Reformation, The Collected Works, Vol. X.

ይህ ማለት ካመንኩ ከዚያ በኋላ በቃኝ ጨርሻለሁ የሚባልበት ሳይሆን በእምነት ተመሥርቶ <u>መታዘዝ</u> ይገባል ማለት ነው፡፡ መታዘዝ ደግሞ ለእግዚአብሔር ትእዛዛትና ለቃሉ ነው፡፡ መታዘዙ ግን በኦሪታዊ የሕግ ሥራ ሳይሆን "ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ" ነው፡፡ የገዳማዊ ሕይወት ዋና ተግባርም ይኸው ነው፤ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ተመሥርቶ ለቃሉ መታዘዝ፡፡ ይህም ከኦሪት የሕግ ሥራ የተለየ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት የተገኘ መታዘዝ ነው፡፡

❖ "<u>እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል፤ በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናንና ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል</u>፤ <u>ለዓመፃ በሚታዘዙ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙትና በእድመኞች ላይ ግን ቍጣና መቅሠፍት ይሆንባቸዋል</u>። ክፉውን በሚያደርግ ሰው ነፍስ ሁሉ መከራና ጭንቀት ይሆንበታል፥ አስቀድሞ በአይሁዳዊ ደግሞም በግሪክ ሰው፤ ነገር ግን በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል" ሮሜ 2፥6-10

ቅዱስ ጳውሎስ ግልጽ በሆነና በማያሻማ ሁኔታ እያንዳንዱ በማመን አለማመኑ ብቻ ሳይሆን በእምነት ላይ ተመሥርቶ በሠራው ሥራ መሠረት ዋጋው እንደሚሰጠው እየተናገረ፥ በጎ ሥራን ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር እንደሚሆንላቸው እንዲህ በግልጽ እየተናገረ እንዲህ ለማድረግ የሚደክሙ መነኰሳትን "የራሳቸው ጽድቅ ማቆም" ነው፡፡ "ክርስቶስን መዘንጋትና ሌላ አዳኝ ፍለጋ ነው" የሚሉት ፕሮቴስታንቶችና የውስጥ አርበኞቻቸው ተሐድሶዎች ከየት አግኝተውት ነው? ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሎ የጻፈው ሌላ ጽድቅ ፍለጋ ነው ሊሉን ይሆን? ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን የጻፈላቸው የሮሜ ክርስቲያኖችንና በመላው ዓለም እስከ ፍጻሜ ዘመን የሚነሡ ክርስቲያኖችን ከክርስቶስ ማዳን ወደ ሌላ ማዳን - በመልካም ሥራችን ብቻ እንድናለን ወደ ማለት እየወሰደ ነው - ማለታቸው መሆኑ እንኳ አይታያአውም? በርግጥ ለእነርሱ አይታያቸውም፤ ምክንያቱም ቆቅና ወረቀት የያዙትን አይለቅም እንደሚባለው አዝማቾቻቸው ያስጨበጧቸውን ብቻ እንጂ አዙረው ስለማያዩ ከእነርሱ ከዚህ የተሻለ መጠበቅ የለብንም፡፡

❖ በተጨማሪም "<u>በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና</u>" በማለት ሕግን ማድረግ የሚያጸድቅ ተግባር እንጂ የሚያስወቅስ አለመሆኑን መምህራችን ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ አስተምሮናል፡፡ ሮሜ 2፥13

ስለሆነም እኛ ስለ እምነትና በእምነት ስለሚገኘው ጽድቅ የተናገረውን እናምናለን፤ ስለ መልካም ሥራና ሕግጋተ እግዚአብሔርን ስለ መፈጸም የተናገረውንም እናምናለን፡፡ ሁለቱም የሚጣሉና ወይ ይህን አለዚያ ያንን ምረጥ የሚባሉ ሳይሆኑ የሚመጋገቡ መሆናቸውን፥ መልካም ሥራ በእምነት ላይ ተመሥርቶ የሚያድግ መሆኑን እናምናለንና፡፡ እነርሱ ግን ሉተር የጨመረውን "በእምነት ብቻ" የሚለውን በማንጠልጠል በሕይወታቸው መልካም ፍሬ ለማፍራት የሚያስፈልገውን ተጋድሎ ለመሸሽ ሲሉ ሰው ሠራሽ መንገድ ፈጥረዋል፡፡ ታዲያ እንዲህ የሚያደርጉ ከሆነ በመጽሐፍ "ክፉ በመሥራት ደስ የሚላቸው፥ በጠማማነትም ደስታን የሚያደርጉ፥ መንገዳቸውን የሚጠመዝዙ፥ አካሄዳቸውንም የሚያጣምሙ ናቸው" ተብሎ የተነገረባቸው መሆናቸው አይደለምን? ምሳ. 2፥15 ነቢዩም "ወዛቲ ፍኖቶሙ ዕቅፍቶሙ እንዘ ይሠምሩ በአፉሆሙ - ይህች መንገዳቸው መሰናከላቸው ናት፥ ከእነርሱም በኋላ የሚመጡ በአፋቸው እሺ ይላሉ" ይላቸዋል፡፡ መዝ. 48፥13

❖ "ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፥ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፤ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ። . . . ስለ ሥጋችሁ ድካም እንደ ሰው ልማድ እላለሁ። ብልቶቻችሁ ዓመፃ ሊያደርጉ ለርኵሰትና ለዓመፃ ባሪያዎች አድርጋችሁ እንዳቀረባችሁ እንደዚሁ ብልቶቻችሁ ሊቀደሱ ለጽድቅ ባሪያዎች አድርጋችሁ አሁን አቅርቡ። አሁን ግን ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ ለእግዚአብሔርም ተገዝታችሁ ልትቀደሱ ፍሬ አላችሁ፤ መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው።" ሮሜ 6፥13-22

ይህ "ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ" የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ስለ መንፈሳዊ ትጥቅ፣ ስለ ጦር ዕቃ፣ ራስን ለእግዚአብሔር ስለ ማቅረብ የሚናገረው ሌላ የመዳኛ መንገድ እያሳየ አይደለም፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ምእመናን መንፈሳዊ ውጊያ ይዋጉ ዘንድ እንደሚገባቸውና እንዴት ሆነው መዋጋት እንዳለባቸው እያስተማራቸው እንጂ፡፡ መነኰሳትና ገዳማውያንም በክርስቶስ ባላቸው እምነት አካላቸውን ለእግዚአብሔር የጽድቅ የጦር እቃ አድርገው በማቅረብ ራሳቸውን ለዚህ መንፈሳዊ ጦርነት አዘጋጁ፣ በተቻላቸው መጠን በእርሱ ቸርነት ተጋደሉ እንጂ ሌላ ምን የተለየ ነገር አደረጉ?

## <u>ሁለቱ የቆሮንቶስ መልእክታት</u>

- "ስለ ጻፋችሁልኝስ ነገር፣ ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው። ነገር ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው፣ ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራሷ ባል ይኑራት" በማለት ለተቻለው ሰው በድንግልና መኖር የበለጠ እንደሆነ፣ ሆኖም ይህ ለሁሉም ስለማይሆን ሰዎች በጋብቻ ተወስነው ይኖሩ ዘንድ እንዲገባ በመልእክቱ ጻፈልን፡፡ 1 ቆሮ. 7፥1-2 እንዲሁም ስለዚሁ ጉዳይ የበለጠ በማብራራት "ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁና፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ስጦታ አለው፣ አንዱ እንደዚህ ሁለተኛውም እንደዚያ። ላላገቡና ለመበለቶች ግን እላለሁ፣ እንደ እኔ ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው" በማለት ተናገረ፡፡ 1 ቆሮ. 7፥7-8

በመሆኑም በዘመነ ወንጌል ያለው በድንግልና መኖርና ምንኩስና በሐዲስ ኪዳን ትምህርት በቃልና በተግባር የተመሠረተ እንጂ ከዚህ በተቃራኒ አጽራረ ሃይማኖት የሆኑት አሳዛኞቹ ወገኖቻችን እንደሚያወሩት "ሰው ሠራሽ ጽድቅ" እና "ጸረ ወንጌል" አይደለም፡፡ በጌታችንና በመድኃኒታችንም ትምህርት፣ በቅዱስ ጳውሎስም ትምህርት ደገኛነቱን ከመንገር ጋር አጽንኦት የተሰጠባቸው፣ እቅጣጫውን ያመላከተባቸውና ማበረታቻ የተደረገባቸው ናቸው፡፡ በዚህ ሕይወት ለመኖር የሚደረገው ውሳኔ ግን የእያንዳንዱ ሰው የራሱ ነጻ ውሳኔ ነው፣ ማንም በማንም ላይ ይህን ውሳኔ አይጭንም፡፡ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለክህነት እንኳ የግድ መንኩሱ አትልም፤ ለሕጋውያንም ክህነት ትሰጣለችና፡፡ ይልቁንም የክህነት አገልግሎት ከጥንት ጀምሮ (ከጵጵስና በስተቀር) የበለጠ የተለመደው ለሕጋውያን ክህናት ነበር፡፡

- "በእሽቅድምድም ስፍራ የሚሮጡት ሁሉ እንዲሮጡ፣ ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን? <u>እንዲሁም ታገኙ ዘንድ ሩጡ</u>። የሚታገልም ሁሉ በነገር ሁሉ ሰውነቱን ይገዛል፤ እነዚያም የሚጠፋውን አክሊል ሊያገኙ ነው፣ እኛ ግን የማይጠፋውን። ስለዚህ እኔ ያለ አሳብ እንደሚሮጥ ሁሉ እንዲሁ አልሮጥም፣ ነፋስን እንደሚጎስም ሁሉ እንዲሁ አልጋደልም፤ <u>ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ</u>።" 1 ቆሮ. 9፥24-27

"ታገኙ ዘንድ ሩጡ" ሲል አንድ ሰው የሚድነው በራሱ ሩጫ ብቻ ነው ማለቱ አይደለም፡፡ ይህን ሲል መዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት የተገኘ መሆኑን ዘንግቶም አይደለም፡፡ ነገር ግን ይህ እንጻለ ሆኖ በመንፈሳዊ የትሩፋትና የተጋድሎ መስመር የተቻለውን ያህል መሮጥ የሚገባ ስለሆነ ነው፡፡ ይህን ቃል በራሱ ካየነው መዳንን በራስ ጥረት ላይ ብቻ ያንጠለጠለው ሊመስል ይችላል፡፡ በዚህ ዓለም ባለው ሩጫ ምሳሌ አንጻር የተናገረው ስለ መንፈሳዊ ተጋድሎ ነው፡፡ አበውና እማት ገዳማውያን የሚያደርጉት ይኸንኑ ነው፡- ከረቂቃኑና ልቡሳነ ሥጋ ከሆኑት አጋንንት (ከመናፍቃንና መሣሪያዎቻቸው) ጋር መታገል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "ታገኙ ዘንድ ሩጡ" በማለት ገና ምንም ነገር ያላገኙ መሆኑንና ማግኘት አለማግኘታቸው የሚወሰነው እንደ አሯሯጣቸው መሆኑን ሲገልጽና ስለ መንፈሳዊ ተጋድሎ ሲናገር በክርስቶስ የተገኘውን የታመነ ቤዛነትና ድኅነት በመዘንጋት አይደለም፡፡ በክርስቶስ ቤዛነት በጸጋ የተሰጠውንና በእምነት የሚገኘውን መዳን በተመለከተ ሲናገር ደግሞ ከሰዎች የሚገባውን መንፈሳዊ ተጋድሎ ዘንግቶ አይደለም፡፡

ትክክለኛ (ኦርቶዶክሳዊ) እምነትና አረዳድ የሚሆነው ለራስ ብቻ የሚስማማውን እያንጠለጠሉ ሌላውን እየጣሉ በመርጥ ሳይሆን ሁሉንም የእግዚአብሔር ቃል በእምነት በመቀበል ስለ አንዱ ሲነገር ሌላኛውንም በማስብና በመያዝ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ መናፍቃን ሁል ጊዜም ጠባያቸው ብዙውን የእግዚአብሔር ቃል የሌለ ያህል በመተው አንዱን ወይም ጥቂቱን ቃል ብቻ ይዘው በቆርቆሮ ውስጥ እንዳሉ ጥቂት የባቄላ ፍሬዎች እነዚያን ብቻ እያንኳኩ መረበሽና ማደንቆር ነው፡፡

❖ "እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ <u>ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን</u>።" 2 ቆሮ. 3፥18

በገዳማዊ ሕይወት የሚጋደሉ አበውና እማት ዓላማቸው ከክብር ወደ ክብር መለወጥ (በጸጋ እግዚአብሔር ማደግ) ነው፡፡ ሐዋርያው የተናገረውም ይህንኑ ነው፡፡ ይህ "ከክብር ወደ ክብር መለወጥ" የተባለውም በአንድ ጊዜ የሚያልቅ ቅጽበታዊ ሳይሆን ሂደታዊና ሱታፌያዊ መሆኑን ያስረዳናል፡፡ ሐዋርያው የሚነግረን "ከክብር ወደ ክብር ተለውጠናል" ብሎ ሳይሆን "ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን" ብሎ ነው፡፡ ይህም ሂደታዊ እንጂ ቅጽበታዊ አይደለም፤ "ተለውጠናል" ሳይሆን ያለው "እንለወጣለን" ነውና፡፡ በክርስትና የሚደረጉ መንፈሳዊ ተጋድሎዎች ይህን ከክብር ወደ ክብር መለወጥ - መንፈሳዊ ዕድገት ገንዘብ ለማድረግ ነው፡፡ በቤዛነቱ ያመኑ፣ ልጅነትን በጥምቀት ያገኙ፣ በሥጋውና በደሙ የታተሙ ክርስቲያኖች እንደየ ተሰጣቸው ጸጋና እንደየ ሕይወት ምርጫቸው በየአኗኗራቸው በዚህ የክብር መሰላል ከታች ወደ ላይ ለመውጣት በእግዚአብሔር ቸርነትና ኃይል የሚቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡ ሰው ሳይጋደል ወደዚህ ክብር አይደርስም፣ ያለ እግዚአብሔር ዕርዳታም ብቻውን ምንም ሊያደርግ አይችልም፡፡ ሁሉንም በተገቢው ቦታና ሁኔታ መረዳትና ማድረግ ግን ወሳኝ ነው፡፡ አንዱን ብቻ እየያዙ ሌላውን እየተው መሮጥ ግን ሁል ጊዜም የስህተት መንገድ ነው፡፡

❖ "ስለዚህም አንታክትም፤ ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል።" 2 ቆሮ. 4፥16

በክርስቲያን ሰው ሕይወት ውስጥ ያለው መንፈሳዊ ሕይወት እንደ ኩሬ ውኃ የተገደበና የቆመ ሳይሆን እንደ ፈሳሽ ወንዝ ሕያውና የሚንቀሳቀስ ነው፡፡ ጌታችን "እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፤ <u>እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ</u>" በማለት እንደ ተናገረ፡፡ ዮሐ. 4፥14 ቅዱስ ጳውሎስም "የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል" በማለት የገለጸው ይህንኑ ነው፡፡ መነኮሳት ገዳማውያንም በየዕለቱ በሚያደርጉት ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት፣ ትጋሃ ሌሊትና በመሳሰሉት ተቀንዮዎች የውስጡን ሰውነት ለማደስና ለማንጻት ያለ መታከት ይጋደላሉ፡፡

❖ "ስለዚህ ደግሞ ብናድር ወይም ተለይተን ብንሆን <u>እርሱን ደስ የምናሰኝ ልንሆን እንቀናለን</u>።" 2 ቆሮ. 5፥9

የገዳማውያን አባቶቻችንና እናቶቻችን የመነኰሳት ምኞትና ከዚህ "እርሱን [እግዚአብሔርን] ደስ የሚያሰኙ ለመሆን ከመቅናት" ሌላ ምን አለ? ተምኔታቸው ሁሉ በተቻላቸው መጠን እግዚአብሔርን ማስደሰት ነው፡፡

❖ "መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፣ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና።" 2 ቆሮ. 5፥10

ቅዱስ ጳውሎስ ከላይ እንደ ተመለከትነውና በሮሜ መልእክቱ ላይ እንደ ገለጸው አሁንም በቆሮንቶስ መልእክቱ ላይም እያንጻንዱ ሰው በእምነት ላይ ሆኖ በሠራው ሥራ መልካምነትም ሆነ ክፉነት ተገቢውን ዋጋ ለማግኘት ለፍርድ የሚቆም መሆኑን አስተማረን፡፡ ሐዋርያው ይህን ሲል በክርስቶስ የተገኘውን ጽድቅና ቤዛነት ዘንግቶ ነው ሊባል አይቻልም፡፡ ሆኖም አንድ ሰው ለመዳን በክርስቶስ የተገኘውን ድኅነት ማመኑና መቀበሉ እንደ ተጠበቀ ሆኖ በዚያ ላይ ተመሥርቶ ደግሞ "በፍቅር የሚሠራ እምነት" ሊሆን ስለሚገባ መልካም ሥራን መሥራት ይገባዋል፡፡ ለዚህ ነው "መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፣ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና።" የተባለው፡፡ መልካም ያልሠራ መልካም ዋጋ ሊያገኝ አይችልም፡፡ የመንፈሳዊ ተጋድሎና የገዳማዊ ሕይወት ተግባርም ይኸው ነው፡፡ እርሱም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ሲቆሙ እንዳያፍሩና መልካም ዋጋ ለማግኘት እንዲችሉ በዚህ ዓለም ሕይወታቸው መልካም ሥራ መሥራት ነው፡፡

❖ "አብረንም እየሠራን የእግዚአብሔርን ጸጋ በከንቱ እንዳትቀበሉ ደግሞ እንለምናለን" 2 ቆሮ. 6፥1

የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመቀበል አብሮ መሥራት እንዲገባ ተናገረ፡፡ የእግዚአብሔርን ጸጋ እንዲሁ በከንቱ መቀበል አይገባምና፣ አይቻልምም፡፡ ለዚህ ነው "አብረንም እየሠራን የእግዚአብሔርን ጸጋ በከንቱ እንዳትቀበሉ ደግሞ እንለምናለን" በማለት በተማጽኖ ያስተማረው፡፡ በገድል በትሩፋት የሚደክሙና የሚጋደሉ ምእመናንም የሚያደርጉት ይህንኑ ነው፡፡ መነኰሳት ገዳማውያንም ለማድረግ ደፋ ቀና የሚሉት ይህን ነው፤ ጸጋውን ለማግኘት የሚቻላቸውን ያህል መድከም፡፡ የሰው ድካም የእግዚአብሔርን ጸጋ ሲገዛ ወይም የተገባው ሆኖ "ለዚህ ድካሜ ወይም ተጋድሎዬ ይህን ያህል ጸጋ ይሰጠኝ" ለማለት አይችልም፡፡ ሆኖም ጸጋውን ለመቀበል ግን መነሻ ወይም መግቢያ ምክንያት ነው፡፡ እግዚአብሔር ለሰነፎችና በሃይማኖት ለማይጋደሉ ጸጋውን አይሰጥምና፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለልዩ ልዩ አገልግሎት የጠራቸው ሰዎች ሁሉም ማለት ይቻላል የተጠሩት ከሥራ ላይ የሆነውም ለዚህ ነው፡፡ ሙሴና ዳዊት በግ ከሚጠብቁበት፣ ጌዴዎን እህል ከሚወቃበት፣ ኤልሳዕ በሮቹን ጠምዶ ከሚያሳርስበት፣ አሞጽ ከላም ጠባቂነት፣ ሐዋርያት ከዓሣ አጥማጅነትና ከቀራጭነት፣ ወዘተ ነበር የተጠሩት፡፡

❖ "በብዙ መጽናት፣ በመከራ፣ በችግር፣ በጭንቀት፣ በመገረፍ፣ በወኅኒ፣ በሁከት፣ በድካም፣ እንቅልፍ በማጣት፣ በመጦም፣ በንጽሕና፣ በእውቀት፣ በትዕግሥት፣ በቸርነት፣ በመንፈስ ቅዱስ፣ ግብዝነት በሌለው ፍቅር፣ በእውነት ቃል፣ በእግዚአብሔር ኃይል፣ ለቀኝና ለግራ በሚሆን በጽድቅ የጦር ዕቃ" 2 ቆሮ. 6፥5-8

ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሁሉ ግድልና መከራ የተቀበለው በክርስቶስ አዳኝነት ስላላመነ አልነበረም፣ ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሁሉ ግድልና መከራ የተቀበለው በክርስቶስ አዳኝነት ስላላመነ አልነበረም፣ ወይም ሉተራውያን እንደሚሉት ሌላ የመዳኛ መንገድ ፍለጋ አልነበረም፡፡ በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ እንደየ ዓቅማቸው በእንደዚህ ዓይነት የመስቀል ጎዳና መሰማራትና በተግባር ተፈትነው በመታመን ጠላትን ማሳፈርና እምላካቸውን ማክበር ስለሚገባቸው እንጂ፡፡ ሰው መንፈሳዊ ተጋድሎ የማያስፈልገው ከሆነ፣ እንዲህ ማድረግ በክርስቶስ የተገኘውን የመዳን ጸጋ ከንቱ ማድረግና ሌላ ጽድቅ ማቆም ከሆነ፣ ቅዱስ ጳውሎስ "የጽድቅ የጦር ዕቃ" ለምን አስፈለገው? ለምንስ ያን ያህል መከራ ተቀበለ? ለምንስ ተጋደለ? የመናፍቃን ዋና ተልእኮና ዓላማ ሰዎችን እንዲህ ካለው በወንጌል ከተሰጠው ትምህርት በተቃራኒ በማስተማር ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወትና ክብር ከሚወስደው መንገድ መንፈሳዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሚመስል የበግ ለምድ ተሸፍነው ሰዎችን ማሳትና ወደ ጥፋት መውሰድ ነው፡፡ ዲያብሎስ የቃሉን ባለቤት ጌታችንን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅሶ ሲፈትነው ሞክሮ አልነበረምን? ታዲያ ባለቤቱን በራሱ ቃል ለመፈተን ያን ያህል ከደፈረ እኛን ቢፈትነንማ ምን ይገርማል?

ያን ጊዜ ዲያብሎስ ለጌታችን በመራቡ ያዘነ መስሎ እንደ ቀረበውና በዚያ ሳይሆንለት ሲቀር ወደ ጥቅስ እንደ ሄደ ሁሉ ዛሬም ስለ እኛ መዳን የተቆረቆሩ መስለው ለመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ዘብ የቆሙ መስለው፣ ነገር ግን እንደ አባታቸው እንደ ዲያብሎስ መርዛቸውን በማር ለውሰው እያቀረቡልን ነውና እንወቅባቸው፡፡ ዑቅዎሙ ለከለባት - ውሾችን (መናፍቃንን) እወቁባቸው" ተብሏልና፡፡ ፊል. 3፥2

በቅዱስ ጳውሎስ - ትግሃት (እንቅልፍ በማጣት ተብሎ የተገለጸው)፣ ጾም፣ ንጽሕና፣ እውቀት፣ በብዙ መጽናት፣ በመከራ፣ በችግር፣ በጭንቀት፣ በሁከት፣ በድካም፣ በትዕግሥት . . . በእግዚአብሔር ኃይል፣ ለቀኝና ለግራ በሚሆን በጽድቅ የጦር ዕቃ - ተብለው የተገለጹት መንፈሳዊ የተጋድሎ ዓይነቶችና ስልቶች ናቸው በገዳማውያን አበውና እማት ሕይወት የሚተገበሩት፡፡ እያንዳንዱ ሰው በክርስቶስ በተገኘው ቤዛነት ብቻ "ጻድቅ" ተብሎ የሚታወጅለት ቢሆን ኖሮና የእያንዳንዱ ሰው የራሱ መንፈሳዊ ሱታፌ የማያስፈልግ ቢሆን ኖሮ ስለ እነዚህ "የጽድቅ የጦር ዕቃዎች" መናገር ምን ፋይዳ ይኖረው ነበር? ይህን መንፈሳዊ ውጊያ በሁለተኛ ቆሮንቶስ በምዕራፍ 10 ከቁጥር 3-4 ላይ *"በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብንሆን እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም፤ የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፣ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው"* በማለት ደግሞታል፡፡ 2 ቆሮ. 10፥3-4 ፕሮቴስታንት መራሾቹ ተሐድሶዎች እንደሚሉት ሰው ለመዳን የራሱ ድርሻ የሌለውና መንፈሳዊ ተጋድሎ የማያስፈልገው ቢሆን ኖሮ ቅዱስ ጳውሎስ እነዚህን መንፈሳዊ የተጋድሎ ዓይነቶችና መንፈሳዊ ውጊያዎች ለምን ይፈጽማቸው ነበር? ለእኛስ ትምህርት እንዲሆነንና እንድንተገብራቸው ለምን ጻፈልን? ተሐድሶዎቹ እንደሚሉት ቢሆን ኖሮ "እነዚህ ነገሮች በክርስቶስ የተገኘውን ጽድቅ ያስረሳሉና፣ ተቃራኒም ናቸውና ከእነርሱ ራቁ" ይል ነበር እንጂ እንዲህ አይልም ነበር፡፡

ሐዋርያው ከተጋደለላቸው የመልካም ምግባር ሕይወቶች መካከል አንዱ "ንጽሕና" ነው፡፡ ይህ ንጽሕናን መጠበቅስ የገዳማውያን መነኩሳትና መነኩሳዪያት አንዱ ተጋድሎ አይደለምን? መጽሐፍ ቅዱስ በአጠቃላይ በእግዚአብሔር ቸርነት የተሰጠን መዳን በመስቀል ላይ የተፈጸመ መሆኑን እንደሚነግረን ሁሉ ያን መዳን ገንዘብ ለማድረግ እያንዳንዱ ሰው ከማመን ጀምሮ በተቻለው መጠን መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ሠርቶ ባሳየንና ባስተማረን በጠባቧ መንገድ መጓዝና መጋደል ያለበት መሆኑንም ያስተምረናል እንጂ በክርስቶስ ድነናልና ንጽሕናን ለመጠበቅ መጋደል፣ እንዲሁም ሰውነትን በገድል ማስጨነቅ አያስፈልግም አይልም፡፡ እንዲህ የሚለው አባባል ጠላት የዘራው እንክርዳድ ብቻ ነው፡፡ እንክርዳድ ደግሞ ከስንዴው ጋር ስለሚመሳሰል መጠንቀቅና መለየት የእያንዳንዱ ድርሻ ነው፡፡

- "እንግዲህ ወዳጆች ሆይ፣ የዚህ ተስፋ ቃል ካለን በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንጻ።" 2 ቆሮ. 7፥1

ገዳማዊ ሕይወት ዓላማውና ተግባሩ ይኸው ነው፡- ሐዋርያው እንደ ተናገረው "በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም ማድረግ፣ እንዲሁም "ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራስን ማንጻት፡፡" በአንዳንድ ገዳማት ሴቶች ወደ ወንዶች ገዳም እንዳይገቡ የተደረገውም ለዚህ ነው፤ ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ ራስን ለማንጻትና ለመጠበቅ፡፡

- "በምንም ከእኛ የተነሣ እንዳትጎዱ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ አዝናችኋልና። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኀዘን ጸጸት የሌለበትን፣ ወደ መዳንም የሚያደርሰውን ንስሐ ያደርጋልና፤ የዓለም ኀዘን ግን ሞትን ያመጣል። እነሆ ይህ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኀዘን እንዴት ያለ ትጋት፣ እንዴት ያለ መልስ፣ እንዴት ያለ ቁጣ፣ እንዴት ያለ ፍርሃት፣ እንዴት ያለ ናፍቆት፣ እንዴት ያለ ቅንዓት፣ እንዴት ያለ በቀል በመካከላችሁ አደረገ። በዚህ ነገር ንጹሐን እንደ ሆናችሁ በሁሉ አስረድታችኋል።" 2 ቆሮ. 7፥9-11

ይህም በገዳማውያን አበውና እማት ሕይወት የምናገኘውን ጸጸትንና የንስሐ ኃዘንን፣ እንዲሁም ከእርሱ የሚወጣውን ትጋት፣ ፍትሐ እግዚአብሔርን መፍራት፣ ለመንፈሳዊ ገድል ትሩፋት መቅናት ነው ሐዋርያው በመልእክቱ የገለጸው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ የገለጻቸው ስለ ፈጸሙት ኃጢአት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ማዘንና መጸጸት፣ እንዲሁም ለመንፈሳዊ ገድልና ትሩፋት ከልብ መቃጠልና መንፈሳዊ ቅንዓት መቅናት የገዳማዊ ሕይወት የየዕለት ተግባራትና መሠረታውያን ናቸው፡፡

- "እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜያቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል።" 2 ቆሮ. 11፥15

አሁንም የእያንዳንዱ ሰው ፍጻሜ "እንደ ሥራቸው" ይሆናል በማለት በእምነት ላይ (እምነት ብቻ ሳይሆን) ሥራም ፍጻሜን በመወሰን ላይ የራሱ ድርሻ ያለው መሆኑን መምህራችን ቅዱስ ጳውሎስ አስተማረን፡፡

<u>የገላትያ መልእክት</u>

- "እኛ በፍጥረት አይሁድ ነን፣ ኃጢአተኞችም የሆኑ አሕዛብ አይደለንም፤ ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን አውቀን፣ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ፣ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል። ነገር ግን በክርስቶስ ልንጸድቅ የምንፈልግ ስንሆን ራሳችን ደግሞ ኃጢአተኞች ሆነን ከተገኘን፣ እንግዲያስ ክርስቶስ የኃጢአት አገልጋይ ነዋ? አይደለም።" ገላ. 2፥15-17

"ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን አውቀን ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል" በማለት በግልጽ እንደ ተናገረው "ሥራ" እያለ የገለጸው በክርስቶስ ሳያምኑ ሕገ ኦሪትን በመፈጸም እንድናለን ይሉ ለነበሩ አይሁዳውያን መሆኑንና "ሥራ" ያለውም በሕገ ኦሪት ያለውን ሥራ መሆኑን በግልጽ ያሳያል፡፡ በመቀጠልም "ሥራ" ሲል በክርስቶስ አምኖ የሚፈጸመውን መንፈሳዊ ምግባር ትሩፋት ማለቱ አለመሆኑንና ይህ አያስፈልግም እንደ ማለት ተደርጎ እንዳይወሰድ ለማስጠንቀቅ ወደ ሌላ ጉዳይ ከመግባቱ በፊት ከዚያው በመቀጠል "ነገር ግን በክርስቶስ ልንጸድቅ የምንፈልግ ስንሆን ራሳችን ደግሞ ኃጢአተኞች ሆነን ከተገኘን፣ እንግዲያስ ክርስቶስ የኃጢአት አገልጋይ ነዋ? አይደለም" በማለት አስጠነቀቀን፡፡

ስለዚህ "ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ" የተባለው "ሥራ" የሕገ ኦሪት ሥራ እንጂ በክርስቶስ በማመን የሚፈጸመው አይደለም፡፡ መንፈሳዊ ተጋድሎ እንደሚያስፈልግ በዚሁ በገላትያ መልእክቱ ላይ አስተምሯል፡፡ ለአብነትም *"በመልካም ትሮጡ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ ማን ከለከላችሁ?"* በማለት በመልካም ምግባር መሮጥና መጋደል እንዲገባ ተናገረ፡፡ ገላ. 5፥7 እንዲሁም "በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ፤ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ" በማለት በጌታችን ያገኘነውን ነጻነት ለመጠበቅና ወደ ባርነት ቀንበር ላለመመለስ መታገል እንዲገባ ተናገረ እንጂ አንድ ጊዜ የዳንን ስለ ሆነ እና ነጻ ስለ ወጣን ከአሁን በኋላ ምንም አይደርስብንም እያላችሁ ተመኩ፣ ተዘልላችሁ ተቀመጡ አላለንም። ገላ. 5፥1 ሲያጠቃልልም *"ልጆቼ ሆይ፣ ክርስቶስ በእናንተ እስኪሣል ድረስ ዳግመኛ ስለ እናንተ ምጥ ይዞኛል"* በማለት መንፈሳዊ ዕድገትና መዳን ምን ያህል ከባድ መሆኑንና ሕፃን ልጅ ጸንሶ እንደ መውለድና እንደ ማሳደግ ድካም የሚጠይቅ ሂደት እንጂ ቅጽበታዊ አለመሆኑን ይገልጻል፡፡ ገላ. 4፥19

## ሌሎቹ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት

በሌሎቹ መልእክታቱም ይህን መሠረታዊ ጉዳይ የሚያስተምሩና የሚያብራሩ ብዙ ጥቅሶች አሉ፡፡ ሃሳባቸውና ጭብጣቸው ከላይ ከተብራራው ጋር አንድ እና ተመሳሳይ ስለሆነ ለአብነት እንዲሆን የተወሰኑትን ብቻ አለፍ አለፍ አድርገን በማንሳት ይህን ጉዳይ እንቋጨዋለን፡፡

- "የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፤ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ። እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፥ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤ የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።" ኤፌ. 6፥11-17

- "በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ" ኤፌ. 6፥11-18

- "ባሪያ ቢሆን ወይም ጨዋ ሰው፥ እያንዳንዱ የሚያደርገውን መልካም ነገር ሁሉ ከጌታ በብድራት እንዲቀበለው ታውቃላችሁና።" ኤፌ. 6፥8

  እነዚህ ሁሉ የገዳማውያን መነኰሳት ተግባራት ናቸው፡፡

- "ወንድሞች ሆይ፤ እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቈጥራለሁ፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ።" ፊል. 3፥13-14

- "በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ በእግዚአብሔርም እውቀት እያደጋችሁ፥ ከደስታም ጋር በሁሉ ለመጽናትና ለመታገሥ እንደ ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታችሁ፥ በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ፥ በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን።" ቆላ. 1፥10-12

- "ጢሞቴዎስ ልጄ ሆይ፤ አስቀድሞ ስለ አንተ እንደ ተነገረው ትንቢት፥ በእርሱ መልካም ጦርነት ትዋጋ ዘንድ ይህችን ትእዛዝ አደራ እሰጥሃለሁ፡፡" 1 ጢሞ. 1፥18

- "አንተ ግን የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ከዚህ ሽሽ፤ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታተል። መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል፥ የተጠራህለትንም በብዙም ምስክሮች ፊት በመልካም መታመን የታመንህለትን የዘላለምን ሕይወት ያዝ።" 1 ጢሞ. 6፥11-12

- "ለዚህም ነገር ደግሞ በእኔ በኃይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ እየተጋደልሁ እደክማለሁ።" ቆላ. 1:29

- "እንግዲህ በምድር ያሉቱን ብልቶቻችሁን ግደሉ፥ እነዚህም ዝሙትና ርኵሰት ፍትወትም ክፉ ምኞትም ጣኦትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው። በእነዚህም ጠንቅ የእግዚአብሔር ቍጣ በማይታዘዙ ልጆች ላይ ይመጣል።" ቆላ. 3፥5-6

* "ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና፤ እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው፣ ለነገር ሁሉ ይጠቅማል። ይህ ቃል የታመነ፣ ሁሉም እንዲቀበሉት የተገባ ነው፤ ይህን ለማግኘት እንደክማለንና፥ ስለዚህም እንሰደባለን፤ ይህም ሰውን ሁሉ ይልቁንም የሚያምኑትን በሚያድን በሕያው አምላክ ተስፋ ስለምናደርግ ነው።" 1 ጢሞ. 4፥8-10

ታዲያ ሲያምን አንድ ጊዜ መዳኑ የተፈጸመና ያለቀ ከሆነና የእርሱ ድርሻ ካልነበረው "ይህን ለማግኘት እንደክማለን" ለምን አለ?

* "በእምነትና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ፣ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳንዳችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን።" ዕብ. 6፥11-12

* ቃሉ የታመነ ነው። እግዚአብሔርንም የሚያምኑት በመልካም ሥራ በጥንቃቄ እንዲጸኑ፥ እነዚህን አስረግጠህ እንድትናገር እፈቅዳለሁ። ይህ መልካምና ለሰዎች የሚጠቅም ነው" ቲቶ 3፥8

* "ከወገናችንም ያሉት ደግሞ ፍሬ ቢሶች ሆነው እንዳይቀሩ የግድ ስለሚያስፈልገው ነገር በመልካም ሥራ እንዲጸኑ ይማሩ።" ቲቶ 3፥14

* "ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ" ዕብ. 10፥24

* "ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና።" ዕብ. 13፥16

* "በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን በእናንተ እያደረገ ፈቃዱን ታደርጉ ዘንድ በመልካም ሥራ ሁሉ ፍጹማን ያድርጋችሁ፤ ለእርሱ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።" ዕብ. 13፥21

ይህ ሁሉ ቃል እግዚአብሔር የሚያስረዳው እንደ ሌሎቹ ክፍለ ምንባባት ሁሉ እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ማድረግ የነበረበት ነገር ሁሉ - የእግዚአብሔር ጽድቅ - በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመና የታተመ ቢሆንም እኛ ይህን የ "እግዚአብሔር ጽድቅ" ገንዘብ ለማድረግና ለመያዝ በመንፈሳዊ ተጋድሎ መጋደል የሚገባንና ሱታፌ ያለን መሆኑን ነው፡፡ ገዳማውያን መነኰሳት የሚያደርጉትም ይህንኑ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የእግዚአብሔር ማዳን ስለ ተፈጸመ፣ መዳን በእምነት ብቻ ስለሆነ እኔም መዳኔን ፈጽሜያለሁ፣ ምንም ማድረግ አያስፈልገኝም የሚለው ሉተር ያመነጨውና ሌሎች ከዚህ መራራ ምንጭ እየጠጡለት ያለው ድፍርስና የተበከለ ትምህርት ግን በቅዱስ ጳውሎስም ሆነ በአጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ቦታ የሌለው የፈጠራ ትምህርት ነው፡፡

## 7.5 ክርስቲያናዊ መልካም ሥራ - በቅ. ጴጥሮስ፣ በቅ. ዮሐንስ፣ በቅ. ያዕቆብ እና በቅ. ይሁዳ መልእክታት

* "ሕይወትን ሊወድ መልካሞችንም ቀኖች ሊያይ የሚፈልግ ሰው ምላሱን ከክፉ ከንፈሮቹንም ተንኰልን ከመናገር ይከልክል፤ ከክፉ ፈቀቅ ይበል፣ መልካምንም ያድርግ፣ ሰላምን ይሻ ይከተለውም፤ የጌታ ዓይኖች ወደ ጻድቃን ናቸውና፣ ጆሮዎቹም ለጸሎታቸው ተከፍተዋል፣ የጌታ ፊት ግን ክፉ ነገርን በሚያደርጉ ላይ ነው። በጎንም ለማድረግ ብትቀኑ የሚያስጨንቃችሁ ማን ነው?" 1 ጴጥ. 10-13

- "ስለ ክቡ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ፣ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን። ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፣ በበጎነትም እውቀትን፣ በእውቀትም ራስን መግዛት፥ ራስንም በመግዛት መጽናትን፣ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፥ እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፣ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ። እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ሆነው ቢበዙ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ሥራ ፈቶችና ፍሬ ቢሶች እንዳትሆኑ ያደርጉአችኋልና፤ እነዚህ ነገሮች የሌሉት ዕውር ነውና፣ በቅርብም ያለውን ብቻ ያያል፣ የቀደመውንም ኃጢአቱን መንጻት ረስቶአል። ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፣ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ፤ እነዚህን ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉምና።" 2 ጴጥ. 1፥4-10

- "በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ከዓለም ርኵሰት ካመለጡ በኋላ ዳግመኛ በእርሷ ተጠላልፈው የተሸነፉ ቢሆኑ፣ ከፊተኛው ኑሯቸው ይልቅ የኋለኛው የባሰ ሆኖባቸዋል። አውቀዋት ከተሰጣቸው ከቅድስት ትእዛዝ ከሚመለሱ የጽድቅን መንገድ ባላወቋት በተሻላቸው ነበርና። ውሻ ወደ ትፋቱ ይመለሳል፣ ደግሞ የታጠበች እርያ በጭቃ ለመንከባለል ትመለሳለች እንደሚባል እውነተኛ ምሳሌዎች ሆኖባቸዋል።" 2 ጴጥ. 2፥20-22

- "አሁንም፣ ልጆች ሆይ፣ በሚገለጥበት ጊዜ እምነት እንዲሆንልን በመምጣቱም በእርሱ ፊት እንዳናፍር በእርሱ ኑሩ።" 1 ዮሐ. 2፥28

- "ትእዛዚቱም ይህች ናት፣ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናምን ዘንድ፣ ትእዛዝንም እንደ ሰጠን እርስ በርሳችን እንዋደድ ዘንድ። ትእዛዙንም የሚጠብቅ በእርሱ ይኖራል፣ እርሱም ይኖርበታል፤ በዚህም በእኛ እንዲኖር ከሰጠን ከመንፈሱ እናውቃለን።" 1 ዮሐ. 3፥23-24

- "ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ። ቃሉን የሚሰማ የማያደርገውም ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስተዋት የሚያይን ሰው ይመስላል፤ ራሱን አይቶ ይሄዳልና፣ ወዲያውም እንደ ምን እንደ ሆነ ይረሳል። ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት፣ ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው በሥራው የተባረከ ይሆናል።" ያዕ. 2፥22-25

- "ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማን ነው? በመልካም አኗኗሩ ሥራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ።" ያዕ. 3፥13

- "ዳጆች ሆይ፣ ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ ሳለሁ፣ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ።" ይሁዳ ቁ. 3

እነዚህ ሁሉ የሚያስተምሩን ከላይ የተገለጸውን - እያንዳንዱ ሰው በእምነት ላይ ሆኖ ክርስቲያናዊ መልካም ሥራ መሥራትና መንፈሳዊ ተጋድሎ መጋደል የሚገባው መሆኑን ነው:: መነኰሳት ገዳማውያን የሚያደርጉትም ይህንኑ ነው::

## 7.6 ምንኩስና እና ገዳማዊ ሕይወት "የአረማውያን ፍልስፍና" ነውን?

> ◉ "በተባሕትዎና በገዳማዊ ሕይወት መወሰን ራስን ለመግዛትና ወደ ከፍተኛ መዓርገ ጽድቅ ለመድረስ መሰላል ነው የሚለው የቀድሞ ሕንዳውያን ፍልስፍና ከቦታ ወደ ቦታ በመሸጋገር መልኩንም በመለዋወጥ ወደ ክርስትና ተሸጋገረ፡፡ መካከለኛውን ምሥራቅም አቋርጦ ወደ ግብጽ ገባ፤ በገዳመ አስቄጥስ ስሙንና መልኩን እንደገና በመለወጥ ሥርዓተ ምንኩስና ተሰኝቶ ወደ ሌላው ክፍለ ዓለም ተዘዋወረ፡፡ በተሰዓቱ ቅዱሳን አማካይነትም ወደ ኢትዮጵያ ገባና የነዋሪነት ፈቃድ ተሰጠው፡፡ ምንጩ ከአረማውያን ፍልስፍና የሆነውን ይህን ሥርዓት . . . ሥርዓተ መላእክት ነው ይሉታል፡፡" (ጮራ ቁ. 15፤ ገጽ 30-31)

ከሁሉም በፊት የሚገርመው ተሐድሶዎች ሌላ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለ ነገር ውጭ መናገርም ሆነ መጥቀስ እንደ ሌለበት ይናገራሉ፤ ለራሳቸው ሲሆን ግን ከየትም ቢሆን ለቃቅመው ይጠቅሳሉ፡፡ ይህ "ገዳማዊ ሕይወት ምንጩ የአረማውያን ፍልስፍና ነው" የሚለው እንኳን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሊኖር ይቅርና በሌሎች ክርስትና ነክ ድርሳናትም አይገኝም፡፡ ይህን ይሉ የነበሩት ከበፊትም ጀምሮ የክርስትና ጠላቶች የሆኑ መናፍቃን ነበሩ፡፡

በመጀመሪያ ተባሕትዎን፣ ምንኩስናንና ገዳማዊ ሕይወትን "ምንጩ ከአረማውያን ፍልስፍና ነው" የሚለውን ከየት አገኙት? ማስረጃቸውስ ምንድን ነው? እንዲሁ በግድ እመኑኝ በሚል ዓይነት "ምሁራኑ" ያሏቸውና ማንነታቸውን ያልገለጿቸው "ይቺ፣ ይቺ . . . ናት ይሏታል፣ አልተቀበሏትም፤ አንዳንዶቹ ምሁራንማ ላላወቀሽ ታጠኚ ብለዋታል" ከሚል ባዶ ስሜታዊ ዐረፍተ ነገር በስተቀር ማስረጃ አላቀረቡልንም፡፡ አረማዊ ነው ያሰኘውን ምክንያትም አላብራሩም፡፡ ስለዚህ ይህ አባባላቸው ጭፍን ጥላቻ የወለደው ስሜት እንጂ አንዳችም ቍብጥነት የለውም፡፡

የሕንዳውያን ፍልስፍና ስለ ሕይወትና ጽድቅ ምን እንደሚል አውቀውታል? የሂንዱይዝም ዋና ጠባይ አንድ ወጥ የሆነ ሕይወትም ሆነ መዳን ይህ ነው የሚለው ነገር የሌለው መሆኑ ነው፡፡ በየዘመናቱ ሲለዋወጥ የኖረና አሁንም በዚሁ ሂደት ላይ ያለ ነው፡፡ ከእነዚህ አመለካከቶች (እምነቶች) መካከል አንደኛው እውነተኛ ነገር ነው የሚለው አለመኖርን (ኢህላዌ - nonexistence) ነው፡፡ የመጨረሻ ብቃት የሚሉትም ወደ ኢህላዌ መመለስን ነው፡፡ ስለዚህ በእነርሱ ፍልስፍና መሠረት በገዳምና በብሕትውና የሚኖሩትና በትህርምት የሚጋደሉት ህላዌያቸው ሐዘንም ሆነ ደስታ የማይሰማው ወደ መሆን ሁኔታ እንዲሸጋገርና ከተደጋጋሚ የእንደገና መወለዶች ዑደት (Samsara – the cycle of rebirth) ነጻ ለመውጣት ነው ብለው ነው፡፡

ስለዚህም የህንዳውያን ፍልስፍና በመሠረቱ ህልውናን አጥፊ (Nihilist) ነው፡፡ የፍጽምና የመጨረሻ ሽልማት ወይም ደረጃ ነው የሚሉት "ምንም ማወቅ የሌለበት ዕረፍት፣ መቼም መች መንቃት የሌለበት ማንቀላፋት" ነው፡፡ ክርስትና ደግሞ ሕያው ከሆነው አምላክ ጋር በጸጋ መዋሐድና በእርሱ ብርሃንነት ብርሃን በመሆን፣ በእርሱ ፍቅርነት ፍቅር በመሆን፣ በእርሱ ሕይወት ሕያው በመሆን ከክብር ወደ ክብር ማደግ ነው፡፡ በመሆኑም በክርስትና ያለው ምንኵስናና ገዳማዊ ሕይወት መሠረተ ሃሳብ ከሕንዳውያን ፍልስፍና ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው፣ የሕይወትና የሞት ያህል የተራራቀና የተለያየ ነው፡፡

ሌላው መሠረታዊ ነገር ደግሞ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ከጥንት ጀምሮ ያደርጉት ዘንድ ያዘዛቸው ነገር፣ እንዲሁም በተለያዩ ዘመናት መፈጸማቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግበው የምናገኛቸው ነገሮች በአሕዛብ ዘንድ በተለያየ መልክና ሁኔታም ቢሆን ይታወቁ ወይም ይነገሩ የነበሩ መሆናቸው ምንጫቸው ከአረማውያን ፍልስፍና ነው አያሰኛቸውም፣ አያስነቅፋቸውምም፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን *ሁለት* ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

### 1) በኖኅ ዘመን ስለ ተፈጸመው የጥፋት ውኃ ታሪክ በተመለከተ በተለያዩ ክፍለ ዓለማት የነበሩ ታሪኮች

በዘመኑ ከነበሩት ሰዎች (ሰብአ ትካት) ኃጢአት ብዛትና ጥልቀት የተነሣ ኖኅና ቤተሰቦቹ ለዘር ከተረፉት እንስሳትና አራዊት ጋር በመርከብ ሲተርፉ በስተቀር እግዚአብሔር ሌላውን ፍጥረት በሙሉ በንፍር ውኃ ማጥፋቱን፣ ኖኅና ቤተሰቡ ለዘር እንዲተርፉ ከተደረጉት እንስሳትና አራዊት ጋር ወደ መርከብ መግባታቸውንና ከጥፋት ውኃው በኋላ ከዚያ መውጣታቸውን፣ ኖኅ ቁራንና ርግብን ከመርከቡ የላካቸው መሆኑን፣ ርግብ የወይራ ቅጠል ዝንጣፊ ይዛ መመለሷን፣ ኖኅ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረቡንና የመሳሰሉትን ታሪኮች መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ ይህ የምድርና በላይዋ የነበሩት ፍጥረታት በማየ አይህ የመጥፋታቸውና ተያያዥ ታሪኮች ይታወቁ የነበረው ግን በዕብራውያን ብቻ አልነበረም፣ ተጽፎ የሚገኘውም በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ አልነበረም፡፡ ምንም እንኳ ከጣዖታዊ እምልኮ ልማዳቸውና ተረቶቻቸው ጋር ቢያደባልቁትም፣ ከመሠረታዊ ዓላማው አርቀው ቢሆንም እንኳ ታሪካዊ ጭብጡ ግን በተለያዩ ሕዝቦችና ባህሎቻቸው ስለ ጥፋት ውኃ ይታወቅና ይነገር ነበር፡፡ ይህም በተለያዩ የጥንታዊ ሥልጣኔዎች ጥናቶች እየተደረሰበትና እየታወቀ ይገኛል፡፡ ለምሳሌም፡-

ሀ) በባቢሎን አገር እንዲህ የሚል ታሪክ ይነገር ነበር፡- አክሲሱትራስ በተባለው የባቢሎን ንጉሥ ዘመን ታላቅ ኀርፍ ነበር፣ ንጉሡም መርከብ ሠርቶ ራሱንና ቤተሰቦቹን እንዲሁም የቅርብ ወዳጆቹን በዚያ አማካይነት ከኀርፉ አዳነ፡፡ ከራሱም ጋር ብዙ ወፎችንና እንስሳትን ወደ መርከቡ ይዞ በመግባት አተረፋቸው፡፡ ዝናሙ መዝነም ባቆመ ጊዜ ከወፎቹ መካከል የተወሰኑትን ወደ ውጭ ላካቸው፡፡ እነርሱም እግራቸው ጭቃ ሆኖ ወደ እርሱ ተመለሱ፡፡ ለሁለተኛ ጊዜም እንዲሁ አደረገ፡፡ በሦስተኛ ጊዜ ግን ወፎቹ ወደ እርሱ  አልተመለሱም፡፡ መርከቡም አሪዲና በተባለ ቦታ ላይ ዐረፈች፡፡

ሌላው ይህን በተመለከተ በባቢሎን ይነገር የነበረው ተዛማጅ ነገር ደግሞ እንዲህ የሚል ነበር፡- "ጊልጋሜሽ" የተባለው "አትናፌሽቲም" የተባለውን ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት መድረስ የቻለበትን ምሥጢር በጠየቀው ጊዜ የታላቁን የጥፋት ውኃ ታሪክ ነገረው፤ አራት አማልክት ዓለምን በኀርፍ ለማጥፋት እንዴት እንደ ወሰኑና ያን ጊዜ የጥበብ አምላክ "መርከብ ሥራ" በማለት እርሱ ከቤተሰቦቹ ጋር ከዚያ የጥፋት ኀርፍ የሚያመልጥበትን መንገድ ነገረው፡፡ የተወሰኑ ወፎችን ከመርከቡ ላካቸው፡፡ ከእነዚያም መካከል አንዳንዶቹ የወይራ ቅጠል ይዘው ተመለሱ፡፡ ከመርከቡ ከወጣ በኋላ የምስጋና መሥዋዕት ሠዋ፤ የጥበብ አምላክም እርሱንና ቤተሰቦቹን ይባርካቸው ዘንድ እና ዘለዓለማዊ ሕይወትን ይሰጣቸው ዘንድ ወደ እነርሱ መጣ፡፡

ለ) የሕንድ ሥልጣኔ - በሕንድ አገር ከቡድሃ ቤተ መቅደሶች በአንዱ ውስጥ ኖኅ በመርከብ ውስጥ ሆኖ፣ ኮአኒን የተባለች እንስት ጣዖት (the goddess Coanin) እርሱን በምሕረት ዓይን እየተመለከተችው፣ ርግብ የወይራ ቅጠል ይዛ ከመርከቡ ስትወጣ የሚያሳይ ሥዕል ተገኝቷል፡፡

ከዚህም ሌላ የሕንድ አፈ ታሪኮች ብራሃማ የተባለው ጣዖት (god) ማኖ ለተባለው በዓሣ ቅርጽ ተገለጠለትና መርከብ እንዲሠራና ሰባት ጻድቃን የሆኑ ሰዎችን ከእርሱ ጋር ወደ ውስጡ ይዞ እንዲገባ አዘዘው፡፡ መርከቡንም ከዓሣ ቀንድ ጋር አሠረው፡፡ ዓሣውም መርከቡን ለብዙ ጊዜያት በውኃው ላይ ይጎትተው ነበር፡፡ ከመርከቡ እንደ ወጣም ዓለሙን እንደ አዲስ እንዲጀምር ታዘዘ ይላሉ፡፡

ሐ) በግሪኮች ዘንድ የነበረ ታሪክ - ጁፒተር የተባለው ጣዖት (the god Jupiter) ጻድቁን ዲኦካሊዮንን (Deocalion) ከሚስቱና ከመላው ቤተሰቡ ጋር ወደ መርከብ እንዲገባ አዘዘው፡፡ መርከቡ ፓርታሱስ በተባለው ተራራ ላይ ባረፈ ጊዜ ርግብ ዝናሙ ማቆሙን ነገረችው፡፡ እርሱም ያን ጊዜ የምስጋና መሥዋዕት ለመሠዋት ከመርከቡ ወጣ፡፡

መ) በታናሽ እስያ እና በፍርግያ ሥልጣኔዎች የነበሩ ታሪኮች - 'ኖኅ' ከሚለው ስም የወጣ ነው ተብሎ የሚታሰበው 'አፓቹስ' ('Apachus') የታላቁን የጥፋት ውኃ መምጣት በሰማ ጊዜ ስለ ሕዝቡ ሙኾ፤ አዘነ የሚሉት ታሪክ ነበራቸው፡፡ በፍርግያ ደግሞ በላያቸው ላይ በውስጡ ሰዎች ያሉበት የመርከብ ሥዕል ያለባቸው ሳንቲሞች ተገኝተዋል፡፡ በእነዚህ ሳንቲሞች ላይ የተሣለው መርከብ በውስጡ ሰዎች ያሉበት፤ በውጭው ደግሞ ወፎች ያሉበት ሲሆን አንደኛዋ ወፍ በአፏ የወይራ ቅጠል ይዛለች፤ ለደኅንነታቸው የምስጋና መሥዋዕት የሚያቀርቡ ሰዎችም ይታያሉ፡፡ በእነዚህ ሳንቲሞች ላይም 'ኖኅ' የሚለው ስም በቋንቋቸው ተቀርጾበታል፡፡ የዚያች ከተማ የጥንት ስሟ 'ኬፖቶሽ' ('Kepotosh') የነበረ ሲሆን ይህም መርከብ ማለት ሲሆን፤ ነዋሪዎቿም የኖኅ መርከብ በእነርሱ ከተማ ላይ እንዳረፈች ያምናሉ፡፡

ሠ) ይህን የመሰሉ ተመሳሳይ ታሪኮች በፋርሶች፣ በቻይና፣ በሬንቄ፣ በሶርያ፣ በአርማንያ፣ በሜክሲኮ ጥንታዊ ነዋሪዎች ዘንድና በሌሎች በተለያዩ ሥልጣኔዎችና አካባቢዎችም ነበሩ፡፡

እነዚህ ጥንታውያን ታሪኮች ምንም እንኳ ከአፈ ታሪኮች ጋር ቢደባለቁና በዚያን ዘመን ሰፍኖ በነበረው የአምልኮ ጣዖት ልማድ ምክንያት ከመሠረታዊ ጭብጣቸው አቅጣጫ እንዲስቱ ቢደረጉም ቅሉ በመሠረታዊነት ግን በኖኅ ዘመን የተፈጸመው ታሪክ እውነተኛ መሆኑንና ይህ እውቀትም በሰው ልጆች ዘንድ በተለያየ ደረጃም ቢሆን ይታወቅ የነበረ መሆኑን ያሳየናል፡፡

ከዚህ ውጭ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውንና በኖኅ ዘመን የተፈጸመውን ታሪክ የመሰሉ ታሪኮችና አባባሎች፣ ተጨባጭ ማስረጃዎችም ጭምር (በሚገኙ ሳንቲሞች፣ ቅርጾች ወዘተ) ስለ ተገኙ ይህ ታሪክ ከአረማውያን የተወሰደ (የመጣ) ነው ሊባል እንዴት ይቻላል? በጭራሽ! ይልቁንም ይህ ታሪክ እውነት መሆኑንና በሰዎች ዘንድ እንደየ ባህላቸው ታሪኩን ከአባቶቻቸው ያውቁትና ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላልፉት የነበረ መሆኑን ከሚመሰክር በቀር ከምድረ እስራኤል ውጭ ይታወቅና ይነገር የነበረ ነገር ሁሉ ከአረማውያን ፍልስፍና የተገኘ ነው አያሰኝም፡፡ የኖኅ ልጆች ወደ ምድር ሲበታተኑና ሲሰማሩ ከአባቶቻቸው ከካም፣ ከሴምና ከያፌት የሰሙትን ታሪክ ይዘው ስለ ተበታተኑ በየቦታው የነበሩ የሰው ልጆች ስለዚያ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ተመዘገበው ታሪካዊ ድርጊት በድንግዝግዝም ቢሆን የየራሳቸው ግንዛቤ ነበራቸው፡፡ ሆኖም ይህ በየሀገሩና በየባህሉ የነበረው የብዥታ ምልከታ ከጀርባው የሆነ ጭብጥ መኖሩን ያሳያል እንጂ የኖኅ ከጥፋት ውኃ መዳን ከአረማውያን የተወረሰ ነው አያሰኝም፡፡

2) ስለ አዳኝ (መድኃኒት) ወደዚህ ዓለም መምጣት በተለያዩ ሕዝቦች ዘንድ ይነገር የነበረ ትንቢትና የነበረ ተስፋ

የሥነ ማኅበረሰብ ጥናት ባለሞያዎች በዚህ ረገድ የተለያዩ ግኝቶችን እያገኙ ነው፡፡

የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ከነበራቸውና ከሕዝበ እስራኤል ውጭ ከነበሩ ከአሕዛብ ወገኖች መሢሕ (አዳኝ) ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ ተስፋ ያደርጉ የነበሩ የተለያዩ ሕዝቦች ነበሩ፡፡ ለምሳሌም፡-

ሀ) የጥንቷ ጋሊያ (በዛሬዋ ፈረንሳይ ውስጥ) የነበሩት ሕዝብ አንዲት ድንግል ነጻ የሚያወጣንን ልጅ ትወልድልናለች ብለው ተስፋ ያደርጉ ነበር፡፡ ይህን ወንድ ልጅ ትወልድልናለች ለሚሏት ድንግልም ቤተ መቅደስ እና ሐውልት ሠርተው በጥንቃቄ ይጠብቁ ነበር፡፡ ታዲያ ይህ በመሆኑ ክርስትና አስተምህሮውን ከአሕዛብ ወሰደ እንላለንን? በጭራሽ! እግዚአብሔር የሁሉም አምላክ መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ እርሱ ባወቀ ለሕዝቡ የሚናገርበት መንገድ አለውና፡፡ እንዲሁም ሁሉም የሰው ልጆች ለመጀመሪያው ሰው ለሁላችንም አባት ለአዳምና ለእናታችን ለሔዋን "በአንተና በሴቲቱ መካከል፣ በዘርህና በዘሯም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፡፡ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ" ተብሎ የተሰጠውን የመዳን ተስፋ ወርሰዋልና ይህ ዓይነቱ አገላለጽ የዚያ ተስፋ የደበዘዘ እይታና አገላለጽ ነው፡፡ ዘፍ. 3፡15

ለ) በሜክሲኮም እንዲሁ ዓይነት ተመሳሳይ ነገር ተገኝቷል፡፡ የሜክሲኮ ሕዝብ በዓለቶችና በሕዝብ ሕንጻዎች ላይ ወደፊት አውሬውን ያጠፋልናል የሚሉትን "አምላክ - god" ቅርጽ ይቀርጹ ነበር፡፡ እንደዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ነገሮች በቻይና፣ በሕንድ፣ በኢራን፣ በግሪክ፣ በኢጣሊያ እና በጥንታዊት ግብጽ ተገኝተዋል፡፡

ሐ) የግሪኩ ፈላስፋ ፕላቶ (አፍላጦን) ይህን አዳኝ "ሰው" ሲጠብቅ ነበር፣ እንዲህም ብሏል፡- "ይህ ሰው ሲመጣ ሁሉንም ነገር ያስተምረናል፣ እርሱን ለማየት በጉጉት እየጠበቅሁት ነው፡፡"

መ) ቪርጂል[137] የተባለው የሮማ ባለ ቅኔ በዚህ መድኀኒት (አዳኝ) መምጣት መደሰቱን ገልጿል፣ እንዲህም ብሏል፡-

> ጊዜው ደርሷል፤ ሕጻን ልጅ ከሰማይ ወደ እኛ ተልኮልናል፡፡ በእርሱ ዘመንም የኃጢአታችን ቅሬት ሁሉ ተጠራርጎ ይወገዳል፡፡ ምድራችንን ከዚያ በኋላ ፍርሃት አያገኛትም፡፡ እኛኛሩንም ከአማልክት መካከል ያደርጋል፣ ጸጥ ያለውንም ዓለም በአባቱ ሥልጣን ይገዛል፡፡ የተወደድክ ልጅ ሆይ፣ የጁፒተር ልጅ ሆይ፣ እንኳን ደኅና መጣህ! ዓለምን በመላዋ ተመልከታት፣ አንተን እጅ እየነሣች በፊትህ በአክብሮት ሆና ቆማለች፡፡ እስኪ ተመልከት፣ ሁሉም ሰው አዲስ ዘመን በመምጣቱ ደስ እየተሰኘና ሐሤት እያደረገ ነው፡፡[138]

እንዲሁም ስለ ትሕትና፣ ስለ ንጽሕና፣ ስለ ቅድስና፣ ስለ እውነተኛነትና ስለ መሳሰሉት መልካም ሥነ ምግባራት ብዙ የጻፉና ጥብቅና የቆሙ የተለያዩ የጥንት ፈላስፎችና ጸሐፊዎች ነበሩ፡፡ ዛሬም ሆነ ወደ ፊትም ይኖራሉ፡፡ ሆኖም እነዚህን ሓሳቦች አረማውያን የነበሩ ሰዎች ስላነሷቸውና እነርሱ ሊተገብሯቸው ይሞክሯቸው የነበሩ ጉዳዮች ስለ ነበሩ ብቻ በክርስትና ስናገኛቸው እነዚህ ከአረማውያን ፈላስፎች የመጡ ናቸው ማለት አንችልም፡፡ እንዲሁም ስለ አምላክ መኖርና እርሱም አንድ ብቻ ስለ መሆኑ ይናገሩ የነበሩ፣ በአንጻሩ ደግሞ ስለ ብዙ አማልክት የነበረውን የተስፋፋና ሥር የሰደደ ባሕታዊ ልማድ ይቃወሙ የነበሩ ፈላስፎች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ሶቅራጥስ የተባለው የግሪክ ፈላስፋ በመርዝ እንዲገደል የተፈረደበት በብዙ አማልክት ማምለክን ስለ ነቀፈ ነበር ተብሎ ይነገርለታል፡፡ ታዲያ ይህ በአንድ አምላክ ብቻ ማመንና የብዙ አማልክትን ልማድ መቃወም ከክርስትና በፊት ከእስራኤላውያን ውጭ የነበሩ ፈላስፎችና ሕዝቦች (አረማውያን) የነገሩት ስለ ሆነ ብቻ ሊነቀፍ ይቻላልን? ይገባልንስ? በጭራሽ!

ይህ ሁሉ የሚያሳየው እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ያልራቀና እርሱ ባወቀ ሀልዎቱንና መግቦቱን፣ እንዲሁም መልካም እውቀትን በአእምሯቸው የሚያስተምራቸውና በልቡናቸው የሚጽፍላቸው መሆኑን ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፣ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፣ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፣ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ" ይላል፡፡ ሮሜ 2፡14-15 የእግዚአብሔር ሕግ በአሕዛብም እንኳ በልባቸው የተጻፈላቸው ከሆነ ያን በውስጣቸው ያለውን መልካም የሆነውን ሕግ በአግባቡና በተገቢው መንገድ ባይገልጹትና ባይተገብሩትም እንኳ ምልክቶቹንና ፍንጣቂዎቹን በብዥታም ቢሆን ማሳየታቸው አልቀረም፡፡ ሐዋርያው "እርሱ . . . ባለፉት ትውልዶች መልካም ሥራ እየሠራ፣ ከሰማይ ዝናብን ፍሬ የሚሆንበትንም ወራት ሲሰጠን፣ ልባችንንም በመብልና በደስታ ሲሞላው ራሱን ያለ ምስክር አልተወም" በማለት የገለጸው ይህን ሰፊና ፍጥረቱን ሁሉ የማይዘነጋ አምላካዊ ቸርነት ነው፡፡ የሐዋ. 14፡16-17

---

137 Virgil - ከ70 - 19 ቅ. ል. ክ የነበረ ሮማዊ ባለ ቅኔ ነበር። ሮማውያን በጣም ታላቁ ባለ ቅኔያቸው መሆኑን የሚናገሩለትና በምዕራቡ ዓለም ሥነ ጽሑፍ ላይ ዘለቄታ ያለው ተጽእኖ ያሳደረ ባለ ቅኔ ነበር።

138 (Abba Youanis, Bishop, Paradise of the Spirit, Volume 3, p. 150)

ይኸው ሐዋርያ በአቴና ከተማ በአርዮስ ፋጎስ መካከል ቆሞ ለአቴና ሰዎች በተናገረ ጊዜ ከእነርሱ መካከል የነበሩ ፈላስፋዎች (ባለ ቅኔዎች) ነገረ አምላክን በተመለከተ ከተናገሩት የተነሣው ያለ ምክንያት አልነበረም፡፡ ቃሉ እንዲህ የሚል ነው፡-

> ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደ ሆነ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ፤ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው። ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም። ከእናንተ ከባለ ቅኔዎች አንዳንዶች ደግሞ፡- እኛ ደግሞ ዘመዶቹ ነንና ብለው እንደ ተናገሩ በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን፤ እንኖርማለን። እንግዲህ የእግዚአብሔር ዘመዶች ከሆንን፥ አምላክ በሰው ብልሃትና አሳብ የተቀረጸውን ወርቅ ወይም ብር ወይም ድንጋይ እንዲመስል እናስብ ዘንድ አይገባንም። የሐዋ. 17፡22-31

የዚያን ዘመን የግሪክ ሰዎችን ባለ ቅኔዎቻቸው በብዥርታም ቢሆን ስለ አምላክ ከተናገሩት በመነሣት እንደ ሕፃን ልጅ ቀስ አድርጎ ወደ ትክክለኛው አስተምህሮ መራቸው፡፡ በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ ቁርጥራጭና ሽርፍራፊ እውነቶች ነበሩ፡፡ ሆኖም እውነትና የመዳን ጸጋ በምልዓት ያለው በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው፤ "ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተ ክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ" ተብሏልና፡፡ ኤፌ. 3፡10 ከላይ ያነሣናቸው ታሪኮችና ጭብጦች የሚያስረዱትም ይህን እውነታ ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ ወጥቶ በሕዛብ የነበሩ ሰዎች በልባቸው በተጻፈላቸው ሕገ እግዚአብሔር መሠረት መልካም ነገሮችን ሲፈልጉና ለመፈጸም ሲሞክሩ የነካኳቸውን ነገሮች ሁሉ በክርስትና ውስጥ አንያቸው ማለት ጤነኛነት አይደለም፡፡ በአሕዛብ ልቡና የእግዚአብሔር ሕግ የተጻፈ ስለ ሆነ በክርስቲያኖች ልቡና ሊኖር አይገባውም ያሰኛልን? ለሰዎች በተፈጥሮ የተሰጣቸው ንጽሕናንና ቅድስናን መውደድ በተለያዩ አሕዛባዊ የጥንት ሰዎች ዘንድ ስለታየ በክርስትና ውስጥ እንዳናየው ሊባል አይገባም?

ከዓለም ተለይቶ በገዳማት ተወስኖ በአንድነት የመኖር ልማድ በቡድሂስቶችና በኤሲያውያን ዘንድ ብቻ ሳይሆን በባሬዋ ሜክሲኮ ይኖሩ በነበሩት የአዝቴክ እና የኢንካ ሕዝቦች ዘንድም እንደ ነበሩ የታሪክ አጥኚዎች ይገልጻሉ፡፡ እነዚህ ሕዝቦች (ሜክሲኮዎች) ይኖሩበት የነበረው ክፍለ ዓለም ግን እስከ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ለቀረው ዓለም ስለ መኖሩ እንኳ አይታወቅም ነበር፡፡ ታዲያ እነዚያ ሕዝቦች በድንግልናና በገዳማዊ መልኩ መኖርን ከየት አገኙት? ይህ በክርስትና ያለው የገዳማዊ ሕይወት በጥንታውያኑ በእነ አዝቴኮች እና ኢንካዎች ዘንድ ከነበረው ጋር ስለ ተመሳሰለ ብቻ ክርስትና ይህን የወሰደው ከእነዚያ ሕዝቦች ዘንድ ነው ማለት አይቻልም፤ ምክንያቱም ያን ጊዜ እነዚህ ሕዝቦች ገና ለሌላው የዓለም ሕዝብ መኖራቸው እንኳ አይታወቅም ነበርና፡፡ ስለዚህ በእውቀት ሳይሆን በድፍረትና በጥላቻ መንቀፍ ለሚቀናቸው ወገኖች የምንላቸው ይህን ነው፡- እንዲሁ ሲሉ ሰምቶ እንደ ወረደ ቀድቶ ያንኑ ከማስተጋባት መቆጠቡ መልካም ነው፤ ከትዝብትም ያድናል፡፡

በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ወንጌል እና የቡድሂዝም እምነት መሥራች ነው በሚባለው በቡድሃ ትምህርት መካከል የተወሰኑ ተመሳሳይነቶች አሉ በሚል ክርስትና ከቡድሂዝም የወሰደው ነገር አለው የሚሉ ሞኛ ሞኞች ወይም አላዋቂዎችም አልጠፉም፡፡ እውነታው ሲፈተሽ ግን የክርስቶስ ወንጌል በመጀመሪያዎቹ ሁለት መቶ ዓመታት ወደ ህንድ ደርሶና ተሰብኮ ስለ ነበር የቡድሂዝም ተከታዮች ከክርስትና ትምህርት ብዙ ነገሮችን በመውሰድ ቡድሃ ቀድሞ ያስተማራቸው እያስመሰሉ ከራሳቸው ፍልስፍና ጋር እያደባለቁ ስላስተማሯቸው እንጂ ክርስትና ከቡድሃ ትምህርት የወሰደው አንዳችም ነገር ኖሮ አይደለም፡፡ እንዲሁ አፍኣዊ የሆኑ ጥቂት መመሳሰሎችን ሲመለከቱ፡ አንዱ ከአንዱ ቀድቷል ወደሚል መደምደሚያ መድረስ በብዙ ሰዎች ዘንድ ከሚታዩት ስህተቶች መካከል አንዱ ነው፡፡

ይልቁንም በብሉይ ኪዳን ዘመን ሕጉን ይዘናል ይሉ በነበሩት በአይሁድም ዘንድ ሆነ በተፈጥሮ ሕግና በሕገ ልቡና በነበሩት አሕዛብ በተገቢው መንገድና መረዳት በስፋትና በጥልቀት ሊተገበሩ አልቻሉ የነበሩት ከፍ ያሉ መንፈሳዊ ተግባራት በዘመነ ክርስትና ጌታችን በተግባር ሠርቶ በማሳየቱና ድካማችንን በሥጋዌውና በትንሣኤው በማስወገዱ በተገቢው ስፋትና ጥልቀት፣ እንዲሁም በመንፈሳዊ መረዳት የሚፈጸሙ ሆኑ፡፡

ስለሆነም ተባሕትዎ፣ ምንኵስናና ገዳማዊ ሕይወት በሂንዱዎችና በጥንታውያን የግሪክ ፈላስፎች ዘንድ አልፎ አልፎ የነበረ መሆኑ ብቻ አረማዊ ነው አያሰኘውም፡፡ ይልቁንም እነርሱ ያን ለማድረግ መሞከራቸው ንጽሕናንና ቅድስናን እንዲፈልግ ተደርጎ የተፈጠረውን የሰውን ባሕርይና በውስጣቸው የተጻፈውን ሕገ እግዚአብሔር በተግባር ይመሰክራል እንጂ፡፡ በመሆኑም ተሐድሶዎች ተባሕትዎንና ምንኩስናን የተቃወሙበት ተቃውሟቸው የቆመበት መሠረቱ ስህተት ስለሆነ በዚያ ላይ የተመሠረተው ሃሳባቸው ሁሉ በአሸዋ ላይ እንደ ተሠራ ቤት ይፈራርሳል ማለት ነው፡፡ አመድ በነፋስ ፊት መቆም እንዳይቻለው የእነርሱ የፈጠራ ነቀፌታም እንዲሁ በእውነት ፊት ጸንቶ ሊቆም አይቻለውም፡፡

## 7.7 የገዳማዊ ሕይወት ታሪካዊ ሂደት - በአጭሩ

በምንኩስና እና በገዳማዊ ሕይወት ላይ ያነሷቸውን የተቃውሟቸውን ምክንያቶች ከንቱነት ከተመለከትን ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ገዳማዊ ሕይወት ከጥንት ጀምሮ የነበረበትንና መልክ እየያዘ የሄደበትን ሁኔታ በአጭሩ እንመልከት፡፡

### 7.7.1 በዘመነ ብሉይ

እግዚአብሔር ፍጥረቱን የተመለከቱ ብዙ ሥራዎችን የሚሠራው ቀስ በቀስ በሂደት ነው፡፡ መግቦቱንና ፍርዱን የሚገልጠውም እንዲሁ በሂደት ነው፡፡ ይህ ማለት በቅጽበት የሚያደርጋቸው ነገሮች የሉም ማለት አለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ለምሳሌ ዓለምን ሲፈጥር በአንድ ቅጽበት ማድረግ ሲችል ነገር ግን በስድስት ቀናት ሂደት አደረገ፡፡ አዳምና ሔዋን እንደ በደሉ የሚያድናቸው የመሆኑን ተስፋውንም፣ የሚድኑበትንም መንገድ ወዲያው እዚያው ላይ የሰጣቸው ሲሆን ይህ ተስፋ በተግባር እስኪፈጸም ግን ብዙ ሺህ ዓመታትን ጠይቋል፡፡ ዘፍ. 3፡15 መድኃኒታችን ሰው ሆኖ ሲወለድም እርሱ አምላክ እንደ መሆኑ ዕለቱን አድጎ ወዲያውኑ ተሰቅሎ ዓለምን ላድን አላለም፡፡ ሁሉንም ቀስ በቀስ በሂደት አደረገ እንጂ፤ "በየጥቂቱ አደገ" እንደ ተባለ፡፡

ወንጌል መንግሥቱን ሲመሠርትም ከአሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ጀምሮ ቀስ በቀስ ወደ መቶ ሃያ፣ ከዚያም በኢየሩሳሌም፣ ቀጥሎም በይሁዳ፣ ቀጥሎም በሰማርያ፣ ከዚያም ወደ ዓለም ሁሉ እያለ ነው መንግሥቱ የተስፋፋው፡፡ መድኃኒታችን ይህን በምሳሌ ሲያስተምር በሁለት ነገሮች መስሎ አስተምሯል፤ እንዲህ በማለት፡-

> እርሱም አለ፦ በምድር ዘርን እንደሚዘራ ሰው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደዚህ ናት፣ ሌሊትና ቀን ይተኛልም ይነሣልም፣ እርሱም እንዴት እንደሚሆን ሳያውቅ ዘሩ ይበቅላል ያድግማል። ምድሪቱም አውቃ በመጀመሪያ ቡቃያ ኋላም ዛላ ኋላም በዛላው ፍጹም ሰብል ታፈራለች። . . . እርሱም አለ፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት በምን እናስመስላታለን? ወይስ በምን ምሳሌ እንመስላታለን? እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ናት፡፡ እርሷም በምድር በተዘራች ጊዜ በምድር ካለ ዘር ሁሉ ታንሳለች፤ በተዘራችም ጊዜ ትወጣለች፣ ከአትክልትም ሁሉ የምትበልጥ ትሆናለች፡፡ የሰማይ ወፎችም በጥላዋ ሊሰፍሩ እስኪችሉ ታላላቅ ቅርንጫፎች ታደርጋለች። ማር. 4፡26-28፤ 30-32

በምንዙስናና በገዳማዊ ሕይወት አጀማመርና ዕድገት የምናገኘውም ከሞላ ጎደል ይህንኑ ዓይነት
ሂደት ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን ምንም እንኳ አጋንንት የሠለጠኑበት፣ የሰው ልጅ በኃጢአት
የደከመበት ከባድ ዘመን የነበረ ቢሆንም "ኢኃደገ ርእሶ ዘእንበለ ሰማዕት - ራሱን ያለ ምስክር
አልተወም" እንደ ተባለው አንዳንድ ፋና ወጊዎች ነበሩ፡፡ ከአዳም ሰባተኛ የነበረው ሄኖክ በዚህ
ዓለም ሚስት አግብቶ ልጆች ወልዶ መኖር ከጀመረ በኋላ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ
ከዚህ ዓለም አኗኗር ተሰውሯል፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ "ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፣
ማቱሳላንም ከወለደ በኋላ የኖረው ሁለት መቶ ዓመት ሆነ፣ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ። ሄኖክም
የኖረበት ዘመን ሁሉ ሦስት መቶ ስድሳ አምስት ዓመት ሆነ። ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር
ጋር ስላደረገ አልተገኘም፣ እግዚአብሔር ወስዶታልና" ብሎ ይመሰክርለታል፡፡ ዘፍ. 5፡22-24

ለወልደ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ የተደረገውና አብርሃምን የባረከው፣ እንዲሁም
በብሉይ ኪዳን ዘመን የመሥዋዕተ ወንጌልን ጫፍ ትንሽ ብቅ አድርጎ ያሳየው መልከ ጼዴቅም ግሩብ
ባሕታዊ ነበር፡፡ ታላቅ አባት የሆነውን አብርሃምን እንዲባርክ የሆነውና "የሳሌም ንጉሥ መልከ
ጼዴቅም እንጀራንና የወይን ጠጅን አወጣ፣ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረ" የተባለለት
ይህ መልከ ጼዴቅ ባሕታዊ መሆኑ እውነተኛ የብሕትውናን ሕይወት በትክክል ለሚኖሩበት ሰዎች
ጸጋቸው ምን ያህል ታላቅ እንደ ሆነ አመልካች ነበር፡፡ ዘፍ. 14፡18 ፤ መዝ. 109፡4

በመቀጠልም ታላቁ ነቢይ ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ በድንግልናና በብሕትውና ይኖር ነበር፡፡
ነቢዩ ኤልያስ ጻዋሚ፣ ተሐራሚና ዝጉሓዊ የሆነ ታላቅ ባሕታዊ ነበር፡፡ ከእርሱ ቀጥሎም በእግሩ
ይተካ ዘንድ ኤልሳዕን በአሥራ ሁለት ጥማድ በሬዎች ከሚያርስበት መኀናጸፊያውን በላዩ ላይ
በመጣል ጠራው፡፡ ያን ጊዜም ኤልሳዕ በሬዎቹንና ተግባሩን ሁሉ ትቶ ከኋላው ሮጦ በመከተል
ኤልያስን "አባቴንና እናቴን እስማቸው ዘንድ እባክህ ተወኝ፤ ከዚያም በኋላ እከተልሃለሁ" አለው።
ከዚያም "ከእርሱም ዘንድ ተመልሶ ሁለቱን በሬዎች ወስዶ አረዳቸው፡፡ ሥጋቸውንም በበሬዎቹ ዕቃ
ቀቀለው፣ ለሕዝቡም ሰጣቸው፣ በሉም፡፡ እርሱም ተነሥቶ ኤልያስን ተከትሎ ሄደ፣ ያገለግለውም
ነበር" ይላል። 1 ነገ. 19፡19-21 ይህ የኤልሳዕ አጠራር ደግሞ እንደ ሄኖክ የዚህን ዓለም ኑሮና ተግባር
ከጀመሩ በኋላ ወደ ምናኔ ሕይወት የሚጠሩ ሰዎችን የሚያመለክትና የሚወክል ነው፡፡ ኤልሳዕ
በሬዎቹን አርዶ ይታረሱበት በነበረው ዕቃ ቀቅሎ ለሕዝቡ ሰጥቶ ኤልያስን መከተሉ ምናኔ - ይህን
ዓለም መተው - የሚባለው ይህ መሆኑን በተግባር አሳይቷል፡፡ ነቢዩ ኤልሳዕ አኗኗሩ ሁሉ እንደ
መምህሩ እንደ ነቢዩ ኤልያስ ነበር፡፡ የሚኖርበት ቦታም ኤልያስ በነበረበት በቀርሜሎስ ተራራ
ነበር፡፡ ሆኖም ምንም እንኳ በምናኔያቸውና በተባሕትዎ ሕይወታቸው ቢመሳሰሉም የተለያየ የጸጋ
ስጦታም ነበራቸው፡፡ ኤልያስ በአብዛኛው በቀርሜሎስ ተራራ የኖረና አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ለሕዝቡ
ከሚገለጥ በስተቀር በአብዛኛው ከሰዎች ርቆ በብሕትውና ይኖር የነበረ ሲሆን ኤልሳዕ ግን ብዙውን
ጊዜ ከሕዝቡና ከነገሥታቱ ጋር የቀረበ ግንኙነት ነበረው፡፡

በመጽሐፈ ኤርምያስ ላይ ዱካቸው (ፍንጫቸው) ብቻ ትንሽ ብቅ ብሎ የምናገኛቸው ሰዎችም
አሉ፡፡ ከእስራኤላውያን ወገን የሆኑ የወይን ጠጅ የማይጠጡ፣ ዕድሜያቸውን በሙሉ ቤት ሳይሠሩ
በድንኳን ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ነበሩ፡፡ መጽሐፈ ትንቢተ ኤርምያስ ስለ እነዚህ እንዲህ ይላል፡-

> በሬካባውያንም ልጆች ፊት የወይን ጠጅ የሞላባቸውን ማድጋዎችንና ጽዋዎችን አኖሬ የወይኑን
> ጠጅ ጠጡ አልኋቸው። እነርሱ ግን እንዲህ አሉ፡- የወይኑን ጠጅ አንጠጣም፣ አባታችን የሬካብ
> ልጅ ኢዮናዳብ እንዲህ ብሎ አዝዞናልና፡- እናንተና ልጆቻችሁ ለዘላለም የወይን ጠጅ አትጠጡ።
> በምትኖሩባት ምድር ላይ ብዙ ዘመን እንድትኖሩ፣ በዕድሜያችሁ ሙሉ በድንኳን ውስጥ
> ተቀመጡ እንጂ ቤትን አትሥሩ፣ ዘርንም አትዝሩ፣ ወይንም አትትከሉ፣ አንዳችም አይሁንላችሁ።
> እኛም የአባታችንን የሬካብ ልጅ የኢዮናዳብን ቃል ባዘዘን ነገር ሁሉ ታዝዘናል፡፡ እኛም
> ሚስቶቻችንም ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችንም ዕድሜያችንን ሙሉ የወይን ጠጅ አልጠጣንም፣
> የምንቀመጥበትንም ቤት አልሠራንም፣ የወይን ቦታና እርሻ ዘርም የለንም፣ በድንኳንም ውስጥ
> ተቀምጠናል፣ ታዝዘናል፣ አባታችንም ኢዮናዳብ ያዘዘንን ሁሉ አድርገናል። ኤር. 35፡3-10

መጽሐፍ ቅዱስ የታሪካቸውን ጫፍ ብቅ አድርጎ ካሳየን በኋላ ከዚያ ወዲያ ምን እንደ ሆኑ ስለ መዳረሻቸው ምንም የማይነግረን እነዚህ ሰዎች ከብዙ ፈተና በኋላ እግዚአብሔር "ብሔረ ብፁዓን" ወደ ተባለ ቦታ እንደ ወሰዳቸውና በዚያ እንደሚኖሩ ቅዱስ ዞሲማስ የተባለ በዮርዳኖስ በረሓ ውስጥ ይኖር የነበረ ባሕታዊ እግዚአብሔር ፈቅዶለት ወደ እነርሱ ሄዶ አይቷቸው በጻፈው ዜና ሕይወታቸው ላይ ነግሮናል፡፡[139] ከእነዚህም በመቀጠልም በእስራኤል ከነበሩት ወገኖች አንደኛዎቹ የነበሩት ኤሳውያን (Essenes) የተባሉት በሙት ባሕር ምዕራባዊ አካባቢ ባለው በይሁዳ በረሓ በገዳማዊ ሕይወት ይኖሩ ነበር፡፡ እነዚህ ወገኖች መሢሑ የሚመጣው በጾምና በጸሎት ነው ብለው በማመን፣ እንዲሁም በፈሪሳውያንና በሰዱቃውያን በአጠቃላይ በአይሁድ ዘንድ ከነበረው የሃይማኖት ሕይወት መበላሸት በመራቅ የራሳቸው ሥርዓት አበጅተው በገዳም ተወስነው ይኖሩ ነበር፡፡ በ1948 ዓ. ም. የተገኙት "የሙት ባሕር ጥቅሎች" ተብለው የሚታወቁት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተጽፈው የተቀመጡት በእነዚህ በኤሳውያን ነበር፡፡

አይሁዳዊው ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ስለ እነዚህ ሰዎችና ስለ አኗኗራቸው እንዲህ ሲል ጽፏል፡-

> እነዚህ ሰዎች ሀብትን ይንቃሉ፣ ያላቸውን ነገር ሁሉ በሚገርም ሁኔታ በጋራ ይካፈላሉ፤ ከእነርሱ መካከል ከሌላው የበለጠ ነገር ያለው አንድም ሰው አይገኝም፡፡ ከእነርሱ ጋር ለመኖር የሚመጣ ማናቸውም ቢሆን ያለውን ነገር ሁሉ ለማኅበረሰቡ የጋራ ጥቅም ይሆን ዘንድ አንዳችም ነገር ሳያስቀር መስጠት ያለበት መሆኑ በእነርሱ ዘንድ ዋና ሕግ ነው፡፡ ስለዚህም በእነርሱ ዘንድ የሚያስጨንቅ ድህነትም ሆነ ብዙ ሀብት የሉም፡፡ የእያንዳንዱ ሰው ንብረት ከሌላው ጋር ይደባለቃል፣ ልክ እንደ ወንድማማቾች አንድ ዓይነት የጋራ ንብረት ብቻ አላቸው፡፡ የማኅበሩን ንብረት የሚጠብቁ ሰዎች ይመረጣሉ፣ እያንዳንዱ የሚሠራው ሥራም በማኅበሩ አባላት ይመደባል፡፡ [140]

### 7.7.2 በዘመነ ሐዲስ

ከብሉይ ኪዳን ወደ ሐዲስ ኪዳን በመሸጋገሪያው ላይ የምናገኘው ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ በይሁዳ በረሓ በብሕትውና ይኖር የነበረ ገዳማዊ ነበር፡፡ ለሕዝበ እይሁድ እስከ ተገለጠበት እስከ ሠላሳ ዓመቱ ድረስ የኖረው ከሰው ተለይቶ፣ ከላመና ከጣመ ምግብ ከሞቀና ከደመቀ ልብስ ርቆ በበረሓ ነበር፡፡ ቅዱስ ወንጌል ስለ ዮሐንስ መጥምቅ አኗኗር "ራሱም ዮሐንስ የግመል ጠጕር ልብስ ነበረው፥ በወገቡም ጠፍር ይታጠቅ ነበር፤ ምግቡም አንበጣና የበረሓ ማር ነበረ" በማለት ይነግረናል። ማቴ. 3፥4 ከዚህም በተጨማሪ ዮሐንስ መጥምቅ በበረሓ የሚኖር ስለ መሆኑ አስቀድሞ በትንቢት የተነገረ ነበር፤ "በነቢዩ በኢሳይያስ፦ የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ የተባለለት ይህ ነውና" ተብሎ እንደ ተነገረ፡፡ ማቴ. 3፥3 ኢሳ. 40፥3-5 ኑሮው በበረሓ እንደ ነበረ ሲናገርም ከፈሪሳውያን የተላኩት ሰዎች "አንተ ማን ነህ?" ብለው በጠየቁት ጊዜ "ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለ የጌታን መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ እኔ ነኝ" ብሏል፡፡ ዮሐ. 1፥22-23 ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ ጠራጊና ሰባኪ ይሆን ዘንድ በትንቢት አስቀድሞ የተነገረለትና ገና በእናቱ ማኅፀን እያለ ጀምሮ ለጌታችን መመስከር የጀመረው ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ባሕታዊና ገዳማዊ መሆኑ ለገዳማዊ ሕይወት ታላቅ ትርጉም ያለው ነው፡፡

የቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ሕይወቱ የእግዚአብሔርን ቃል በሥጋ መገለጥ ለመመስከርና ይህን ድንቅ ምሥጢር በአንክሮ ለማሰላሰል ብቻ ይውል ዘንድ ባሕታዊ፣ ድንግል፣ ምንም ሀብት ንብረት የሌለው መናኝ ሆነ፡፡ የብሕትውናና የድንግልና ሕይወትን በተግባር ለባረከልንና ለቀደሰልን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ ጠራጊ የሆነው ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ባሕታዊና ድንግል ሆነ፡፡

---

139 ገድለ ቅዱስ ዞሲማስ

140 (*Flavius Josephus: The Jewish Wars, 11:8*)

ድንግሉ ዮሐንስ መጥምቅ በድንግልና ለሚወለደውና ድንግልናን ለሚባርከው ለክርስቶስ መንገድ ጠራጊ ሆነ፡፡ ሴቶች ከወለዷቸው መካከል ከዮሐንስ የሚበልጥ የለም የተባለለት በድንግልና የኖረው ዮሐንስ መጥምቅ ሆነ፡፡

ጌታችንም በገዳመ ቆሮንቶስ ተባሕትዎን፣ በመላ ሕይወቱ ንጽሕናንና ድንግልናዊ ሕይወትን በተግባር አሳየን፡፡ መድኃኒታችን በማስተማር አገልግሎቱ መካከል አልፎ አልፎ ወደ ምድረ በዳ (በረሓ) በመሄድ እንዲህ ያለውን ሕይወት በተግባር አሳየን፤ "በነጋም ጊዜ ወጥቶ ወደ ምድረ በዳ ሄደ" እንዲል፡፡ ሉቃ. 4፡42 እንዲሁም "ነገር ግን እርሱ ወደ ምድረ በዳ ፈቀቅ ብሎ ይጸልይ ነበር" ይላል። ሉቃ. 5፡16 ይህም ለኋላ ዘመን ገዳማዊ ሕይወት አኗኗር መሠረታዊ ተግባራዊ አርአያ ነበር፡፡

ጌታችን ከዚህ ዓለም ሀብት ንብረት ምንም ነገር የሌለው መሆንን (ምናኔን) በሕይወቱ አስተማረን፡፡ እርሱ ራሱን የሚያስጠጋበት ቤት እንኳ አልነበረውምና፤ "ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው፣ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም" እንዳለ፡፡ ማቴ. 8፡20 እንዲህ ያለውን የምናኔ ሕይወትም ጌታችን በትምህርቱ ያበረታታና ወደ ፍጹምነት የሚመራ ከፍ ያለ መንገድ እንደ ሆነ ያስተምር ነበር፡፡ ያለውን ሁሉ ሽጦ እርሱን ስለ መከተል፣ ስለ መንግሥተ ሰማያት ሲሉ ጋብቻን የሚተው ስለ መኖራቸው፣ ራስን መካድንና የመሳሰሉትን ሰዎችን ከዚህ ዓለም አስራት ፈትተው ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ የሚያገናኙ ተግባራዊ የመንኖ ጥሪትና የንጽሕና ተግባራትን አስተምሯል፡፡ ሆኖም አምላካችን እነዚህን ትምህርቶች ሲያስተምር የዚህን ዓለም ጣዕምና ገንዘብ የመጨረሻ ተስፋቸው ያደረጉና ከዚህ ዓለም ጋር በእጅጉ የተጣበቁ ሰዎች፣ ስለ ሰማያዊ ነገርና ስለ ጸጋ እግዚአብሔር ለማሰብ ልቡናቸው የተደፈነባቸው ሰዎች ይቃወሙት ነበር፤ "ገንዘብንም የሚወዱ ፈሪሳውያን ይህን ሁሉ ሰምተው ያፌዙበት ነበር" ይላልና ቅዱስ ወንጌል፡፡ ሉቃ. 16፡14

ለስም አጠራሩ ክብርና ምስጋና ይግባውና መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ሲጠራቸውም ያላቸውን ሁሉ ትተው እንዲከተሉት በማድረግ ነበር፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ሕይወቱና አኗኗሩ ሁሉ የምናኔ ሕይወት ነበር፡፡ ጌታችን እንደ ጠራውና እንደ ተመለሰ ወዲያውኑ ወደ ዐረብ ምድር (ወደ ዐረብ በረሓ) ሄዶ ሦስት ዓመት በተባሕትዎ እንደ ቆየ ራሱ ተናግሯል፤ እንዲህ ሲል፡-

> ነገር ግን በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርሁም፣ ከእኔም በፊት ሐዋርያት ወደ ነበሩት ወደ ኢየሩሳሌም አልወጣሁም፣ ነገር ግን ወደ ዐረብ አገር ሄድሁ፤ እንደ ገናም ወደ ደማስቆ ተመለስሁ። ከዚህ ወዲያ ከሦስት ዓመት በኋላ ኬፋን ልጠይቅ ወደ ኢየሩሳሌም ወጥቼ ከእርሱ ጋር አሥራ አምስት ቀን ሰነበትሁ፡፡ ገላ. 1፡15-18

ይኸው ከጥንት ዘመን ጀምሮ እርሾው የነበረው ገዳማዊ ሕይወትና ምንኩስና በዘመነ ሐዲስ ኪዳን በጌታችን ትምህርትና ተግባራዊ አርአያነት ላይ ተመሥርቶ ወንጌል መሰበክና መስፋፋት ሲጀምር በዚያው መጠን ማደግና ሥር መስደድ ጀመረ፡፡ በመጀመሪያው የሐዋርያት የስብከት ተልእኮ ያመኑት ስምንት ሺህ ያህል የነበሩት ምእመናን የሚኖሩት ገንዘባቸውና ኑሯቸው ሁሉ "ይህ የእኔ ነው፣ ይህ የአንተ ነው" ሳይባባሉ በአንዲት ሕይወት ነበር፡፡ "ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሯቸው፣ ገንዘባቸውም ሁሉ በአንድነት ነበረ እንጂ ካለው አንድ ነገር ስንኳ የራሱ እንደ ሆነ ማንም አልተናገረም" ተብሎ የተገለጸው የገዳማዊ ሕይወት ዓይነት ሕይወት ነበር፡፡ የሐዋ. 4፡32 የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ይህን ዓይነት ሕይወት መኖር የጀመሩት ክርስቲያናዊ ፍቅርና ኅብረት የሚገለጸው ያለን ለሌላው በማካፈልና በአንድነት ሱታፌ ያለው ሕይወት በመኖር ነው ከሚለው እሳቤያቸው አንጻርም ነበር፡፡ ኋላ ላይ ቀስ በቀስ እያደገ ለመጣው የገዳማዊ የአንድነት ሕይወት (የአንድነት ገዳማዊ ሕይወት) መሠረቱን የጣለው ይህ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የአንድነት (የጋራ የሆነ) አኗኗር ነበር፡፡

በዘመነ ሐዋርያትና ከእነርሱ ቀጥሎ በነበሩት ዓመታት ብዙ ክርስቲያኖች የወንጌልን ቃል ለመፈጸም ራሳቸውን ከማንኛውም ምድራዊ ተድላና ደስታ አርቀው በትህርምትና በብሕትውና ይኖሩ ነበር፡፡ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ላይ ከሰባቱ ዲያቆናት አንዱ የነበረው ፊልጶስ ትንቢት የሚናገሩ አራት ደናግል ሴቶች ልጆች እንደ ነበሩት ተጽፏል፤ "ከሰባቱም አንድ በሚሆን በወንጌላዊው ፊልጶስ ቤት ገብተን በእርሱ ዘንድ ተቀመጥን። ለእርሱም ትንቢት የሚናገሩ አራት ደናግል ሴቶች ልጆች ነበሩት" እንዲል፡፡ የሐዋ. 21፥8-9

በመቀጠልም በ90 ዓ. ም. አካባቢ የነበረው ቅዱስ ቀሌምንጦስ ዘሮም በመልእክቶቹ ስለ ደናግል ጽፏል፡፡ ሄርማስ (ኖላዊ) በ150 ዓ. ም. አካባቢ በሮም ደናግል የነበሩ መሆናቸውን፤ ቅዱስ አግናጥዮስ ደግሞ በሰምርኔስ በዛ ያሉ በኅብረት የሚኖሩ ደናግል የነበሩ መሆናቸውን ጠቅሷል፡፡ ቅዱስ ፖሊካርፐስና ቅዱስ ዮስጢኖስም እንዲሁ ደናግል መኖራቸውን ጠቅሰዋል፡፡ እንደዚሁም ከ150 እስከ 200 ዓ. ም. በነበረው ጊዜ በሶርያ እና በቆሮንቶስ በፈቃድ ድህነትና በምናኔ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች እንደ ነበሩ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡[141]

በሁለተኛው መቶ ዓመት ክርስቲያን ደናግል በቅዳሴና በበዓላት ሥርዓት ጊዜ ካህናትን ተከትለው ይታዩ ነበር፡፡ከዚህ ከሁለተኛው መቶ ዓመት ጀምሮ ብዙ ደናግል በእስክንድርያና በብዙ የክርስቲያን ሀገሮችና ቦታዎች ይታዩ ነበር፡፡ በየዘመኑ የነበሩ ቅዱሳን ሊቃውንትም በሚጽፏቸው መጻሕፍቶቻቸው የድንግልና ሕይወት አንዱና ዋና ርእስ ጉዳያቸው ነበር፡፡ ደናግላን ሴቶች ብዙዎቹ በአንድነት ሆነው እየተረዳዱ ይኖሩ ነበር፡፡ ወንዶች ደናግል ደግሞ ብዙዎቹ ከከተማቸውና መንደራቸው ወጣ ብለው በትንሽ ጎጆ ይኖሩ ነበር፡፡[142]

በዘመነ ሰማዕታት ክርስቲያኖች በአላውያንና ከሃድያን ነገሥታትና ባለ ሥልጣናት እንደ ሽንኩርት እየተላጡና እንደ ጎመን እየተቀረደዱ ለአምላካቸው ያላቸውን ፍቅር በደማቸው መሰከሩ፡፡ በዚያ ዘመን አንዳንዶችም ከሀገራቸው ወጥተው መከራውን ለመሸሽ ወደ በረሃ ይሄዱ ነበር፡፡ የክርስቲያኖች ስደትና መከራ ሲያበቃ ብዙዎቹ ወደ ነበሩበት የዚህ ዓለም ሕይወት መመለስን ትተው በዚያው በጀመሩት ገዳማዊ ሕይወት ገፉበት፡፡ ይህም የገዳማውያኑን ብዛት በፍጥነት አሳድጎታል፡፡ ከዚያም ጋር በዘመነ ቆስጠንጢኖስ ክርስቲያኖች በነጻነት የማምለክ መብት ሲሰጣቸውና ክርስትና ቤተ መንግሥት ሲገባ የነበረው ጥብቅ መንፈሳዊነት እየላላ በመምጣቱ ሉዐላዊ የሆነውን መንፈሳዊ ተጋድሎ ለመፈጸም ይችሉ ዘንድ ወደ በረሓዎችና ሩቅ ቦታዎች ይሄዱ ነበር፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ከዓለም ወጥተው ከከተማዎችና ከመንደሮች ርቀው በተከተተ ልቡና እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚሰባሰቡ ሰዎች ቁጥር እየበዛ ሄደ፡፡ እነዚህም የአንድነት የኑሮ ሥርዓት አበጅተው ለጸሎት፣ ለተግባረ እድ፣ ለቃለ እግዚአብሔር ትምህርት ጊዜ መድበው በአንድነት እግዚአብሔርን ማገልገልና መጋደል ጀመሩ፡፡

ይህን የገዳም ሕይወት በታወቀ ሁኔታ ለመጀመሪያ ጊዜ ሥርዓት ያበጁለትና ያደራጁት በግብጽ በረሓ እግዚአብሔርን ያገለግሉ የነበሩት አባቶች ቅዱስ እንጦንዮስና ቅዱስ ጳኩሚስ፤ እንዲሁም ቅዱስ መቃርዮስና ቅዱስ አሞን ናቸው፡፡ ቅዱስ እንጦንስ ለሃያ ዓመታት ከበአቱ ሳይወጣ ዘግቶ በፍጹም ተባሕትዎ ከተጋደለ በኋላ ዜና ሕይወቱና ዝናው በዓለም እየተሰማ ሄደ፡፡ ከዚህም የተነሣ ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ እየመጡ እርሱን መስለው በምናኔ መኖር ጀመሩ፡፡ ገዳማዊ ሕይወት በዚህ መልኩ ተጀምሮ በፍጥነት እየተስፋፋ ሄደ፡፡ ከዚያም በሶርያ፣ በምድረ ፍልስጥኤም፣ በታናሽ እስያ፣ በኢትዮጵያ፣ በአርማንያ ወዘተ እየተስፋፋ ሄደ፡፡ በታናሽ እስያ ገዳማዊ ሕይወትን የመሠረተውና ያስፋፋው በዋናነት ታላቁ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ (330-379 ዓ. ም.) ሲሆን እኅቱ ቅድስት ማክሪና እና ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙም እንዲሁ ታላቅ ሚና ነበራቸው፡፡ ቅዱስ ባስልዮስ የገዳሙን መነኰሳት ሕዝቡን በትምህርትና በእንግዳ ተቀባይነት ያገለግሏቸው ዘንድ ያበረታታቸው ነበር፡፡

[141] Luc Brésard, A History of Monastic Spirituality.
[142] Tadros Y. Malaty, 1986, Fr., The Coptic Orthodox Church as an Ascetic Church.

ለምዕራቡ ዓለም ገዳማዊ ሕይወትን ያስተዋወቀው የቅዱስ እንጦንስ ደቀ መዝሙር የነበረውና ለኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት መጠበቅ ከአርዮሳውያን ጋር ጽኑ የሆነ የእድሜ ልክ ገድል የተጋደለው ታላቁ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ነበር። የቅዱስ እንጦንዮስን ዜና ሕይወት (ገድል) የጻፈውም እርሱ ነው። መጀመሪያ በ336 ዓ. ም. ለሁለት ዓመት ገደማ በአርዮሳውያን ተንኮልና ሤራ ከመንበሩ በተሳደደና ወደ ምድረ ጎል (የዛሬዋ ፈረንሳይ) በተጋዘ ጊዜ የገዳማዊ ሕይወትን ምንነት ለምዕራባውያን አሳይቷቸዋል። ቀጥሎም በ340 ዓ. ም. በአርዮሳዊው ንጉሥ በቁንስጣንዲዮስና በአርዮሳውያን ጳጳሳትና ግብረ አበሮቻቸው በሐሰተኛ ክስና ውንጀላ ከመንበሩ ከእስክንድርያ እንዲሳደድ በተደረገ ጊዜ ወደ ሮም ሄደ። ከእርሱ ጋርም አባ አሞንዮስ እና አባ ኤስድሮስ የተባሉ በግብጽ በረሓ በነበሩት ገዳማት ለብዙ ዘመናት ሲጋደሉ የኖሩና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ታዋቂ የነበሩ፣ የቅዱስ እንጦንዮስ ደቀ መዛሙርት የነበሩ ሁለት ታላላቅ ገዳማዊ አባቶችን ከእርሱ ጋር ይዟቸው ሄዶ ነበር።

ከቅዱስ አትናቴዎስ ጋር የነበሩት እነዚያ ሁለት ገዳማውያን አባቶች ሮማውያንን በእጅጉ አስደምመዋቸው ነበር። አባ አሞንዮስ ከዚህ ዓለም ነገር ፈጽሞ የተለየ መናኝ ስለ ነበረ ከቅዱስ ጴጥሮስና ከቅዱስ ጳውሎስ መቃብራት በስተቀር በሮማ ከነበሩት አስደናቂና ታላቅ ቦታዎች ወደ አንዱም እንኳ ለማየት አልሄደም ነበር። ሌላኛው አባ ኤስድሮስ ደግሞ ፍጹም ባሕታዊና የዋህ ነበር። የእነዚያ የግብጽ በረሓ መነኰሳት ሕይወት ሮማውያንን በእጅጉ አስገረማቸው፣ ማረካቸውም። ከዚህም የተነሣ የእነርሱን አርአያ በመከተል በቅዱስ አትናቴዎስ መሥራችነት ገዳማዊ ሕይወት በሮምና በአካባቢዋ ተስፋፋ። በመቀጠልም ቅዱስ አትናቴዎስ የቅዱስ እንጦንስን ገድል በመጻፉና መጽሐፉም ወደ ላቲን ቋንቋ ተተርጉሞ በምዕራቡም ዓለም በመሠራጨቱ ስለ ግብጽ ገዳማት የነበረውን ግንዛቤ የበለጠ አሰፋው። ከሮማ ግዛት የተለያዩ ወንዶችና ሴቶች ወደ ግብጽ እና ወደ ፍልስጥዔም በረሓ በመሄድ በገዳማዊ ሕይወት እየተጋደሉ መኖር ጀመሩ። ከእነዚህም መካከል አባ ሄሮኒመስ (ጀሮም)፣ ሩፊኖስ፣ ፓውላ፣ ኢዩስቶኪየም፣ ታላቁና ታናሿ ሜላንያ ይገኙበታል።

ይህን እውነታ በጥናቱ የተረዳው በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮና ታሪክ ዙሪያ ብዙ ጥልቅ ጥናቶችን ያደረገውና ብዙ የቀደምት አበው መጻሕፍትንና ትምህርቶችን ከግሪክ ቋንቋ ወደ እንግሊዝኛ በመተርጎም ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረገው፣ በእምነቱ ፕሮቴስታንት የነበረው ፊሊፕ ሻፍ (1819-1893) የተባለው የምርምር ሰው እንዲህ ያለው ለዚህ ነበር፦

> ምንኵስናና ገዳማዊ ሕይወት ከአሕዛብ የመጣ ነው የሚሉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። ሆኖም ይህ ዓይነቱ አመለካከት ምንኵስናና ገዳማዊ ሕይወት በታሪክና በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ከነበረውና ከተሰጠው ታላቅ ቦታ አንጻር ሊታረቅ የሚችል አመለካከት ሆኖ አይገኝም። ምንኵስናና ገዳማዊ ሕይወት ጥንታዊቷን ቤተ ክርስቲያን ከመጀመሪያው ጀምሮ ሁለንተናዋን ያቀፈና በምሥራቁም ሆነ በምዕራቡ ክፍለ ዓለም የነበሩትን ታላላቅ እና ልዩ የሆኑ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የያዘ ነበርና። አትናቴዎስም ሆነ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ጀሮምም ሆነ አውግስጢኖስ በዚህ ሕይወት የኖሩና ይህን ሕይወት ያደንቁና ያከብሩ የነበሩ አባቶች ነበሩና። ገዳማዊ ሕይወትን ያደንቁና ይኖሩ የነበሩ፣ መልካምነቱንም ያስተማሩ እነዚህ አባቶች ከክርስትና መንገድ የወጡና የተሳሳቱ ጸረ ክርስቶሶች ነበሩ የሚል ማንም ጤነኛ ሰው ሊኖር አይችልም። በአንጻሩ የምንኵስናና የገዳማዊ ሕይወት ተቃዋሚዎችና ተቃራኒዎች የነበሩት እነ ጆቪ.ያን፣ ሄሊቪዲየስ እና ቪጂላንቲየስ ደግሞ የክርስትና እውነተኛ ጠበቃዎች ነበሩ ሊል የሚችል አይኖርም፤ ምክንያቱም ምንኩስናን የተቃወሙት እነዚህ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን መናፍቃን ተብለው የተወገዙና ትምህርታቸውም ስህተት መሆኑ የተገለጠ ሰዎች ናቸውና።[143]

---

[143] (Philip Schaff, History of the Christian Church: Chap IV, 28 "The Rise and Progress of Monasticism")

የሰሜን አፍሪቃዋ የቅርጣግና ጳጳስ የነበረውና በ257 ዓ. ም. ሰማዕትነትን የተቀበለው ሰማዕቱ ቅዱስ ቆጵርያኖስ "ቤተ ክርስቲያን በሁለት ዓይነት የሰማዕትነት ሕይወት አጊጣለች፣ አንዱ በደም በሚፈጸም ሰማዕትነት ሲሆን ሌላው ደግሞ በሰላም ጊዜ በሚፈጸም በምናኔ (ገዳማዊ ሕይወት) ነው" በማለት ገዳማዊ ሕይወትን "እንበለ ደም ሰማዕትነት" ብሎታል፡፡

ታላቁ መምህርና አባት ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅም በዚያን ዘመን በግብፅ በረሓዎች የነበረውን የገዳማዊ ሕይወት ሁኔታ በተመለከተ ስለ ጌታችን ወደ ግብፅ መሰደድ የሚናገረውን የማቴዎስ ወንጌል በተረጎመበት ትርጓሜው እንዲህ ገልጾታል፡-

> አሁን ወደ ግብፅ በረሓ ብትሄድ ያ በረሓ ከማንኛውም የለመለመና የተዋበ ገነት ይልቅ አሸብርቆ ታገኘዋለህ፡፡ እልፍ አእላፋት የመላእክት ዘማርያን (መነኰሳት) በሰው መልክ በየበረሓው እንደ ሰማይ ከዋክብት ደምቀው ይታያሉ፡፡ ሀገሪቱ የሰማዕታት ሀገርና የደናግል ከተማ ሆናለች፡፡ የጠላት ምክርና ወጥመድ ተሰብሯል፣ የክርስቶስ መንግሥት ግን በየበረሓው ሁሉ ታበራለች፡፡ በየቦታው የመነኰሳትና የባሕታውያን ዋሻና በኣት ይገኛል፡፡ (ትርጓሜ ወንጌለ ማቴዎስ፣ ክፍለ ትምህርት 8፣ ቁ. 6)

ከዚህ ከገዳማዊ ሕይወት ከጥንት ጀምሮ የነበረ መሆንና በክርስትናው ዓለም ከጌታችን ጀምሮ ጠንካራና ሥር የሰደደ መሠረት ያለው መሆኑን ስለ ገዳማዊ ሕይወት የተ መጣና ጥንት ታሪክ ከሥር ከመሠረቱ ባካሄደው ጥልቅ ጥናት በሚገባ የተረዳ አንድ አጥኚ እንዲህ ያለው ለዚህ ነበር፡-

> በሦስተኛው መቶ ዓመት ማብቂያና በአራተኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ እንግዳ ነገር ሆኖ ብቅ ያለው ክስተት ገዳማዊ ሕይወት ሳይሆን የመከራውንና የስደቱን ዘመን ማብቃት ተከትሎ ከተከሠተው የብዙዎች ወደ ክርስትናው መግባት ጋር ተያይዞ የመጣው የክርስቲያኖች ከዓለም ጋር የመላመድና የላላ መንፈሳዊነት ነው፡፡ መነኰሳት በክርስትና ውስጥ ቀድሞ ያልነበረ አዲስ የፈጠሩት አንዳችም ነገር የለም፤ ከመሠረቱ ጀምሮ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠውን መሠረታዊ የክርስትና ሕይወትና አስተምህሮ ጭብጥ በሚቀያየሩ ሁኔታዎች መካከል ሳይቀያይሩ አጽንተው ያዙ እንጂ፡፡[144]

ይህ አባባል በጣም ጥልቅና መሠረታዊ ነው፡፡ ምክንያቱም ጌታችን ያስተማረው ክርስትና በመሠረታዊ ባሕርዩ ምናኔያዊ ነውና፡፡ ይህም ማለት የግድ ዓለምን ጥሎ ከመመነን ጋር የተያያዘ ሳይሆን ሰው በየትም ቢኖር ይኖርበት ዘንድ የተሰጠው መመሪያ ይህን ዓለምና ምኞቱን በመተው፣ ራሱን ክዶ መስቀሉን በመሸከም፣ በመሳቅ ሳይሆን በማልቀስ (ሉቃ. 6፡25)፣ በመብላት ሳይሆን በመጾም ወዘተ ነውና፡፡ ለአብነትም ይህን ማስታወስ እንችላለን፡- "ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፣ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። ዓለሙም ምኞቱም ያልፋል፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል፡፡" 1 ዮሐ. 2፡15-17

[144] ("It is not so much the monastic life which was a novelty at the end of the third century and the beginning of the fourth, but rather the life of adaptation to the world led by the mass of Christians at the time when the persecutions ceased. The monks actually did nothing but preserve intact, in the midst of altered circumstances, the ideal of the Christian life of early days... And there is another continuous chain from the apostles to the solitaries and then to the cenobites, whose ideal, less novel than it seems, spread so quickly from the Egyptian deserts at the end of the third century. This chain is constituted by the men and women who lived in continence, ascetics and virgins, who never ceased to be held in honor in the ancient Church.")

ይህን የሚነቅፉት የክርስትናው ምንነት ያልገባቸውና ክርስትናን ከመሠረቱ ለማጥፋትና የእነርሱ ርእዮት መሣሪያ እንዲሆን ለማድረግ የሚሠሩት ክፉ ሠራተኞች ብቻ ናቸው፡፡ ምንኩስና ወደ ጌታችን ቀርቦ "ይህንማ ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄያለሁ፣ ደግሞስ የሚጐድለኝ ምንድር ነው?" ብሎ እንደ ጠየቀው ሰው ትእዛዛቱን ከመፈጸም በኋላ መንፈሳዊ ሕይወት ከፍ ሲል የሚመጣና የሚታሰብ እንጂ ገና ትእዛዛትን በመንቀፍ ወይም የክርስትናን "ሀ ሁ" ለመፈጸም በመንገዳገድ ላይ ባለና በወረደ መንፈሳዊ የሕይወት ደረጃ ሊታሰብ የሚችል አይደለምና፡፡ ማቴ. 19፥16-21

## 7.8 ምንኩስና እና ገዳማዊ ሕይወት "ስብከተ ወንጌልን ያዳክማል" የሚለው የተቃውሞ ነጥብ

ተሐድሶዎች በምንኵስናና በገዳማዊ ሕይወት ላይ ያላቸውን ጥላቻ ለመግለጽና ጥቃታቸውን ለመሰንዘር ከሚጠቀሙባቸው ነገሮች አንዱ ከላይ እንደ ተገለጸው "ስብከተ ወንጌልን ያዳክማል" የሚል ነው፡፡ (ኖኅተ ብርሃን፣ መጋቢት 2002፣ ገጽ 7-8) ሆኖም ይህ የመከራከሪያ ነጥብ በመጽሐፍ ቅዱሳዊም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ታሪካዊ እውነታ ሲፈተሽ አንዳችም ተጨባጭ እውነታ የሌላው ባዶ ሆኖ ይገኛል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት ከላይ እንደ ተመለከትነው በእርሱ ቸርነት ለሚቀበሉትና ለሚችሉት ሰዎች እርሱ ራሱ ጌታችን በተግባር ኖሮ፣ ባርኮና ቀድሶ የሰጠው ሕይወት ስለሆነ ይህን ሕይወት የሚኖሩ ሰዎች ቅዱስ ወንጌል ያስተማረውን ፈጸሙ እንጂ ሌላ ነገር ስላላደረጉ "ወንጌልን ያዳክማል" የሚለው አባባል ጭፍን ጥላቻን ከሚያንጸባርቅ በስተቀር ምንም እውነታነት ያለው ጭብጥ የለውም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ምንኵስናና ገዳማዊ ሕይወት ስብከተ ወንጌልን ያዳክማል የሚለው አባባል ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በተጓዘችባቸው ሁለት ሺህ ዓመታት ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ሕይወትና አመጣጥ በተግባር የሚናገረውን ተጨባጭ መረጃ አለማወቅ ነው፡፡ እውነታው መናፍቃኑ እንደሚሉት ሳይሆን በተቃራኒው ሆኖ እናገኘዋለንና፡፡ ይህም ማለት መነኮሳትና ገዳማት ለስብከተ ወንጌል መስፋፋትና መጠናከር ከፍተኛ የሆነ ሚና ሲጫወቱና አስተዋጽኦ ሲያደርጉ የኖሩ መሆናቸውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አፍ አውጥቶ የሚመሰክረው እውነታ ነው፡፡

ዝርዝር ታሪካዊ ሐተታ ውስጥ መግባቱን እንተወውና መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሐዋርያዊ የሆነውን ክርስቲያናዊ እውነት ለመጠበቅና ለማስፋፋት በየዘመናቱ ሁሉ ከፍተኛ ተጋድሎ የተጋደሉትና ታላላቅ አስተዋጽኦ ያደረጉት አባቶች መነኰሳትና ገዳማውያን የነበሩ መሆናቸውን ማስታወስ ብቻ በቂ ነው፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን አሥር (10) ታላላቅ አባቶች እንመልከት፡፡ እነዚህ አባቶች ሁሉም በድንግልና ሕይወት የኖሩ ገዳማውያን ሲሆኑ ስለ ድንግልና ሕይወት ታላቅነትና ስለ ገዳማዊ ሕይወት የጻፉና ያስተማሩ አባቶች ናቸው፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የተሰጠችውን እውነት ጠብቃ ከዛሬ እንድትደርስ እጅግ በጣም ከባድ የሆኑ ተጋድሎዎችን በየዘመናቸው የተጋደሉትና ቤተ ክርስቲያን ለሆነችው ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር በታች ባለውለታዎቻችን የሆኑት እነዚህ ገዳማውያን መነኰሳት የነበሩት አባቶች ናቸው፡፡

| አሥሩ ታላላቅ ገዳማውያን አባቶችና አስተዋጽኦዋቸው በአጭሩ | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ | በግብጽ ገዳማት ለተወሰነ ጊዜ የኖረ እና የመነኰሳት ሁሉ አባት የሆነው የታላቁ የቅዱስ እንጦንዮስ ደቀ መዝሙር የነበረ ነው፡፡ ዜና ሕይወቱን የጻፈውም እርሱ ነው፡፡ | ለኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት መጠበቅ ከአርዮሳውያን ጳጳሳት፣ ከነገሥታት፣ ከባለ ሥልጣናትና ከልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር መላ ዘመኑን ከፍተኛ ተጋድሎ የተጋደለ፣ ከዚህም የተነሣ "ሐዋርያዊ" የተባለ፣ ለኦርቶዶክሳዊት እምነት መጠበቅ ከእግዚአብሔር በታች ባለ ውለታችን የሆነ አባት ነው፡፡ በአንድ ወቅት (ከ340ዎቹ - 360ዎቹ) በአባ ይሩማሊስ አገላለጽ "ዓለሙ ሁሉ ራሱን አርዮሳዊ ለማድረግ ተጣደፈ" እንደ ተባለው ሰዎች አርዮሳዊነትን እንደ ፋሽን ሲከተሉ "አትናቴዎስ ሆይ፣ ዓለሙ ሁሉ ጠላህ፣ ብቻህንም ቀረህ" ባሉት ጊዜ "ከእውነት ጋር ከተጣላ እኔም ከዓለሙ ሁሉ ጋር ጠበኛ ነኝ" እስከ ማለት የደረሰ የጽናትና የኦርቶዶክሳዊነት ዓርማ የሆነ ታላቅ አባት ነው፡፡ ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮን በሚገባ የሚገልጡ ብዙ ድንቅ መጻሕፍትን ጽፎ ትቶልናል፡፡ |
| 2 | ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ | በዘመኑ የነበረውን የፍልስፍናና ክሂሎተ ነቢብ እስከ መጨረሻው ድረስ የተማረ፣ ኋላም በግብጽ በገዳማዊ ሕይወት ሥርዓት የኖረና ሥርዓተ ገዳምን አይቶ ቢታናሽ እስያ በጳንጦስ ገዳማትን የመሠረተና በምሥራቅ ክፍል ገዳማዊ ሕይወት እንዲስፋፋ ያደረገ ታላቅ አባት ነው፡፡ ከጽኑ ተጋድሎና ገዳማዊ ትህርምት የተነሣ ጤናው በእጅጉ የተጎዳና ታማሚ አባት ነበር፡፡ | ለኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት መጠበቅና መስፋፋት ከአርዮሳውያን ጋር ብዙ የተጋደለ፣ ብዙ ድርሳናትን የጻፈ አባት ነው፡፡ በዘመኑ በምሥራቁ የሮማ ክፍል ግዛት ነገሥታቱ አርዮሳውያን የነበሩ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ኦርቶዶክሳውያን ጳጳሳትና ካህናት ከየአገረ ስብከታቸው እየተሳደዱ አርዮሳውያን ቦታቸውን እየነጠቁ ይወስዱበት የነበረ፣ አርዮሳውያን ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን የፈነጩበት ዘመን ነበር፡፡ በዚያ ዘመን ስለ ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖት መጠበቅ በጽሑፍም፣ ባለ ሥልጣናቱን እነርሱ ራሳቸው እስኪገረሙ ድረስ ፊት ለፊት ያለ እንዳች ፍርሃት በመጋፈጥም ብዙ ተጋድሎ ተጋድሏል፡፡ ኋላም በጊዜው ጊዜ ኦርቶዶክሳዊነት በአርዮሳዊነት ላይ ድል እንዲያደርግ ያደረጉትን ሥራዎች ሠርተው ካለፉት ከሦስቱ የቀጰዶቅያ አባቶች አንዱ ይህ ቅዱስ ባስልዮስ ነው፡፡ |
| 3 | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ | በታናሽ እስያ በገዳማዊ ሕይወት የኖረ ሲሆን ከጽኑ ብሕትውናዊ ሕይወት የተነሣ ታማሚ ነበር፡፡ | ቁስጥንጥንያ በአርዮሳውያን ተወርራ ባለ ወደዚያ ሄዶ ኦርቶዶክሳዊ ክርስትናን በጥልቀትና በጥብዓት በማስተማሩ ኦርቶዶክሳዊነት እንዲያንሠራራ ብሎም በ381 ዓ. ም. በተካሄደው ጉባኤ በኑፋቄዎች ሁሉ ላይ ድል እንዲያደርግ ያደረገ፣ ጥልቅና ምጡቅ የሆነ ክርስቲያናዊ ድርሳናትን የጻፈ፣ ከዚህም የተነሣ እንደ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ "ነባቤ መለኮት" የተሰኘ ነው፡፡ እርሱም በዘመኑ ከአርዮሳውያን ጋር ዘርፈ ብዙ ተጋድሎ የተጋደለና በዘመኑ እንደ ክረምት ሙጃ ጀጅቦ የነበረው አርዮሳዊነት ጠውልጎ እንዲደርቅና ኦርቶዶክሳዊነት ድል እንዲያደርግ ያደረገውን የማስተማርና ሌሎች አስፈላጊ ሥራዎች በጽናት የሠራው ይህ ቅዱስ ገዳማዊ አባት ነው፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4 | ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ | በልጅነቱ በፍልስፍና ትምህርትና መምህርነት የነበረ፣ ኋላ ግን እግዚአብሔር ወደ ገዳማዊ ሕይወትና ወደ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የጠራው አባት ነበር፡፡ | እጅግ በጣም ጥልቅና ድንቅ የሆኑ ክርስቲያናዊ ድርሳናትን የጻፈ፣ ኦርቶዶክሳዊነት በአርዮሳውያንና በሌሎችም መናፍቃን ላይ ድል እንዲቀዳጅ ታላቅ የማስተማርና የጥብቅና ሥራ የሠራ አባት ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ እመስጣሪ ጸሐፊ (Mystic writer)፣ የአባቶች አባት (Father of Fathers) እስከ መባል ደርሷል፡፡ በተለይም ዩኖሚየስ ለተባለው ዕብሪተኛና ጽንፈኛ አርዮሳዊ የጻፋቸው የመልስ መጻሕፍት (Contra Eunomius) ጥልቅ የሆኑ የክርስትና የጥብቅና (Apologetic) መጻሕፍት ናቸው፡፡ |
| 5 | ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ | በሶሪያ ከሚገኙ ገዳማት መካከል በአንዱ ገብቶ ለ4 ዓመታት በገዳም ከኖረ በኋላ ለ2 ዓመታት ደግሞ በፍጹም ብሕትውና ከሰው ተለይቶ በአት ዘግቶ በታላቅ ተጋድሎ የኖረ፣ በኋላ የቊስጥንጥንያ ፓትርያርክ የሆነ አባት ነው፡፡ | ቤተ ክርስቲያንን ብሩህ በሆነ ትምህርቱና በተቀደሰ ሕይወቱ ያበራና ዛሬ ድረስ የዓለም መምህር የሆነ አባት ነው፡፡ ለክርስትና መስፋፋት ያደረጋቸውን ተጋድሎዎችና ሥራዎች እንዲህ በአጭሩ መዘርዘር አይቻልም፡፡ ሌላው ቀርቶ እንኳ በክፉዎች ጳጳሳት፣ ካህናትና በቤተ መንግሥት ሤራ ከመንበሩ አሳድደውት በግዞት ላይ ሳለ እንኳ የተለያዩ ሐዋርያዊ ተግባራትን ሁኔታው በፈቀደለት መጠን ያከናውን ነበር፡፡ |
| 6 | ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ | በሶሪያ ገዳማት በታላቅ ትሕትናና ምናኔ የኖረ አባት ነው፡፡ | ብዙ ክርስቲያናዊ ድርሳናትን የጻፈ፣ ለክርስትና በሶሪያና በፋርስ አገሮች መስፋፋት በትምህርቱና በቅድስና ሕይወቱ ታላቅ ሥራ የሠራ አባት ነው፡፡ |
| 7 | ቅዱስ ኤጲፋንዮስ | በፍልስጥኤም ውስጥ ለ30 ዓመታት በአንድ ገዳም ውስጥ በምንኵስና የኖረ፣ በኋላ በቆጵሮስ የሳላሚስ ጳጳስ የሆነ አባት ነው፡፡ | በቅድስና ሕይወቱና በኦርቶዶክሳዊት እምነት ጠበቃነቱ የሚታወቅ፣ በዚህም ሁሪያ ብዙ ሥራዎችን የሠራና ብዙ ተጋድሎዎችን የተጋደለ አባት ነው፡፡ |
| 8 | ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ | በኒጥሪያ ገዳም የነበረ መነኰስ፣ ኋላ የእስክንድርያ ፓትርያርክ የሆነ አባት ነው፡፡ | ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖትን ከንስጥሮሳውያንና ከአይሁዳውያን ለመጠበቅ ብዙ የተጋደለ፣ ለክርስትና ሃይማኖት መስፋፋት ብዙ ሥራ የሠራ አባት ነው፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ የተዋሕዶን ምሥጢር ከመሠረቱ የተረዳና በማያዳግም መልኩ ለሰው በሚቻለው መጠን የገለጸ፣ ከዚህም የተነሣ "ማኅተመ አበው" ተብሎ የሚጠራ አባት ነው፡፡ |
| 9 | ቅዱስ ዲዮስቆሮስ | ከቅዱስ ቄርሎስ ቀጥሎ በ444 ዓ. ም. የእስክንድርያ ፓትርያርክ የሆነ አባት ነው፡፡ | ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖትን የንስጥሮስ እርሾ ከበከላቸው የሮማው ፓትርያርክ ከነበረው ከልዮንና ከንጉሡ ከመርቅያን ብረዛ ለመጠበቅ ሳይፈራና ሳያፍር እምነቱን የመሰከረ፣ በዚህም ንስጥሮሳውያን እነ ልዮን ከመንበሩ አሳድደውት በግዞት ያረፈ ታላቅ አባት ነው፡፡ መልኩን ለወጥ አድርጎ በእነ ልዮን የቀረበው የንስጥሮስ የሁለት ባሕርይ ባህል ቤተ ክርስቲያንን ጨርሶ እንዳይውጣት ታላቅ ተጋድሎ በኬልቄዶን ያደረገ፣ ከዚህም የተነሣ የጉባኤ ከለባት ተከታዮች የሆኑ ካቶሊካውያን ጸሐፊዎች ግብሩን ጥላሸት ቀብተው ለማቅረብ ያለ ይሉኝታ የሚደክሙበት የእምነት አርበኛ አባት ነው፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 10 | ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ | በሶርያ ውስጥ በአንድ ገዳም መነኩሴ የነበረ፤ ኋላም በ512 ዓ. ም. የአንጾኪያ ፓትርያርክ የሆነ፣ በ518 ዓ. ም. የኬልቄዶን ጉባኤ አቀንቃኞች መለካውያን ከመንበሩ ያሳደዱትና በግብጽ በስደት የኖረ ታላቅ አባት ነው፡፡ | ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖትን በዘመኑ የነገሥታቱን ድጋፍ ተገን በማድረግ ለማጥፋት በከፍተኛ ዘመቻ ላይ ከነበሩት ንስጥሮሳውያንና ልዮናውያን ጥልቅና ርቱዕ በሆነ ትምህርቱና ጥብአቱ የጠበቀ፣ በዚህም በ518 ዓ. ም. ከመንበሩ እንዲሳደድ ተደርጎ ቀሪ ዘመኑን በግብጽ በስደት የኖረ፣ የተዋሕዶን ትምህርት ከቅዱስ ቄርሎስ በኋላ ጥልቅ በሆነ ሁኔታ የተነተነና ያስረዳ ታላቅ አባት ነው፡፡ |

እነዚህ ለቤተ ክርስቲያን ታላላቅ ሥራ የሠሩት፣ እምነቷን በመጠበቅ፣ ወንጌልን በማስፋፋት፣ ድርሳናትን በመጻፍ፣ ዛሬ ድረስ የዘለቁ ሕያው ሥራዎችን ትተውልን በማለፍ አሁንም ድረስ ቤተ ክርስቲያንን እያገለገሉና ወንጌልን እየሰበኩ ያሉት አባቶች ሁሉም መነኰሳትና ገዳማውያን የነበሩ መሆናቸው በአጋጣሚ የሆነ ነገር አልነበረም፡፡ ብዙ ተጋድሎ የተጋደሉና ድርሳናትን የጻፉ ሌሎች ሊቃውንትና አባቶችም በየዘመናቱ ነበሩ፡፡ ሆኖም ዘመናትን ተሻግሮ ከእኛ የረደሰውና በጎላና በተረዳ የታወቀ የሆነው በአብዛኛው የእነዚህ አባቶች ሥራና ሕይወት ነው፡፡ ታዲያ ምንኩስናና ገዳማዊ ሕይወት ሰብኩተ ወንጌልን ያስፋፉ አባቶችን፣ ለክርስትና እምነት ጠበቃ የሆኑ የሃይማኖት አርበኞችን አፈራ እንጂ ከዚህ በተቃራኒ "ስብከተ ወንጌልን ያዳክማል"፣ "ጸረ ወንጌል ነው" የሚለው የፈጠራ ወሬ ምን ታሪካዊ ጭብጥና ማስረጃ አለው?

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክም የምናየው ይህን እውነታ ነው፡፡ ክርስትና የተስፋፋው ገዳማት በተስፋፉበት አቅጣጫና ገዳማዊ ሕይወት በተጠናከረበት አካባቢ ዙሪያ ነው፡፡ ተሰዓቱ ቅዱሳን በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ገዳማዊ ሕይወትን ሲያስፋፉ ክርስትናውም በተጠናከረና ሥር በሰደደ ሁኔታ የተስፋፋው በዚያው መስመር ነበር፡፡ በአሥራ ሦስተኛው መቶ ዓመት ማብቂያ ላይ በሐይቅ ገዳም የመሠረቱት አቡነ ኢየሱስ ሞዐ መነኰሳትን በገዳማዊ ሕይወት ብቻ ሳይሆን በነገረ ሃይማኖትም እያሠለጠኑ ከእርሳቸው የተማሩ ልጆቻቸው በየሄዱባቸው አካባቢዎች ገዳማትን እየመሠረቱ ክርስትናን በእጅጉ አስፋፍተዋል፡፡ ከእርሳቸው የወጡት እነ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወንጌልን እስከ ደቡብ ኢትዮጵያ ድረስ ሰብከዋል፡፡ ደቀ መዛሙሮቻቸውም እንዲሁ እስከ ዛሬው ደቡብና ምሥራቅ የአገሪቱ ክፍል ድረስ ክርስትናን አስተምረዋል፡፡ ወደ ጣና ሐይቅ የሄዱት ሌላው የአቡነ ኢየሱስ ሞዐ ደቀ መዝሙር አቡነ ኂሩተ አምላክ ደግሞ ዳጋ እስጢፋኖስን መሥርተው እንዲሁ ተመሳሳይ ዓይነት ተግባር አከናውነዋል፡፡[145]

እነ አባ በጸሎተ ሚካኤል፣ እነ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣ እነ አቡነ አሮ፣ እነ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ፣ ሰባቱ ከዋክብት የተባሉት አባቶች፣ እና ሌሎችም ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ሥራ የሠሩ አባቶች ገዳማውያን ነበሩ፡፡ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የገዳማዊ ሕይወትና የሐዋርያዊ ተልእኮ ቁርኝት በእጅጉ ጠንካራ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያኒቷ ሐዋርያዊ እንቅስቃሴ በአጠቃላይ ገዳማትን መሠረት ያደረገ (በገዳማት ላይ የተመሠረተ) ነበር፡፡ ስብከተ ወንጌል የሚካሄደው በሀገሪቱ ተሠራጭተው በነበሩ ገዳማት በሚኖሩ መነኰሳትና ባሕታውያን ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ክርስትና የተስፋፋበትን ሁኔታና መስመር በጥናቱ ያስተዋለው ስፔንሰር ትርሚንግሃም የተባለው ሰው እንዲህ ያለው ለዚህ ነበር፡-

[145] ገድለ አቡነ ኢየሱስ ሞዐ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌል ሐዋርያዊ ተግባር በገዳማት ላይ የተመሠረተ 'ገዳማት መር' ነበር፤ የስብከተ ወንጌል ሥራዎች የሚሠሩት በሀገሪቱ ተሰራጭተው በሚገኙት ገዳማትና በዓታት በሚኖሩ መነኰሳትና ባሕታውያን አማካይነት ነበር፡፡[146]

በአጠቃላይ ገዳማትና መነኰሳት ለክርስትና ሃይማኖት መጠበቅና መስፋፋት እጅግ በጣም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ መነኰሳትና ገዳማት ለቤተ ክርስቲያን ያደረጉትን አዎንታዊ አስተዋጽኦና የተጫወቱትን ሚና እንዲህ በአጭሩ ማቅረብ የሚቻል አይደለም፡፡ ይህን በሚከተሉት ዋና ዋና ነጥቦች ለማጠቃለል እንሞክር፡፡

1) መነኰሳትና መነኰሳዪያት በቤተ ክርስቲያን የተጋድሎ ሕይወት ውስጥ "የተሰወሩ መንፈሳዊ ኃይሎች" ናቸው፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ረቂቅ ከሆነው ጠላት ጋር መንፈሳዊ ውጊያዎችን ስታደርግ ረቂቅ ሠራዊት ሆነው በጸሎታቸው የሚረዷት ገዳማውያን አባቶችና እናቶች ናቸው፡፡ ኢያሱ ከአማሌቅ ጋር እየተዋጋ ሳለ ሙሴ በቀጥታ ወደ ጦርነቱ ሳይገባ፣ ነገር ግን እጁን ዘርግቶ ከጦርነቱ ቦታ ራቅ ብሎ ቆሞ ነበር፡፡ ሙሴ እጁን ሲዘረጋ በኢያሱ መሪነት ይዋጉ የነበሩት እስራኤላውያን ድል ያደርጉ ነበር፡፡ ሙሴ እጁን ሲያጥፍ ደግሞ አማሌቃውያን ድል ያደርጉ ነበር፡፡ ዘጸ. 17፥8-16 በቤተ ክርስቲያን ተጋድሎም እንደዚሁ ነው፤ ምንም እንኳ ከእኛ ርቀው በገዳማት ተወስነው ቢኖሩም በዓለም ያሉ ክርስቲያኖች ከክፉ ኃይሎች ጋር ላለባቸው ውጊያ ድል ማድረግ የእነርሱ እጃቸውን በጸሎት ወደ እግዚአብሔር መዘርጋት ታላቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ኤጳፍራ እንዲህ እንዳለ፦ "ከእናንተ የሆነ የክርስቶስ ባሪያ ኤጳፍራ ሰላምታ ያቀርብላችኋል። <u>በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉ ተረድታችሁና ፍጹማን ሆናችሁ እንድትቆሙ ሁል ጊዜ ስለ እናንተ በጸሎቱ ይጋደላል</u>።" ቆላ. 4፥12 ስለዚህ ገዳማውያን አባቶች ስውር ኃይሎች በመሆን ስለ እኛ በጸሎታቸው ይጋደላሉ፡፡

2) በስደትና በመከራ ጊዜ ለታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶችና ሊቃውንት፣ እንዲሁም ለቅዱሳት መጻሕፍትና ለንዋያተ ቅድሳት መጠጊያና ከጥፋት መሰወሪያ ቦታዎች ሆነው አገልግለዋል፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ ከደረሱበት ብዙ ስደቶችና መከራዎች መካከል የተወሰኑትን ያሳለፋቸው በግብጽ በረሓ ውስጥ በነበሩት በቅዱስ ጳኩሚስ ገዳማት ውስጥ በመነኮሳቱ መካከል በመሆን ነበር፡፡ መነኰሳቱ ለእርሱ ጽኑ መጠጊያዎቹና ጠላቶቹ ያለበትን እንዳያውቁ አድርገው በስስት ይጠብቁት የነበሩ ታማኝ ጠባቂዎቹና መልእክተኞቹም ነበሩ፡፡ የእስክንድርያ የነገረ መለኰት ትምህርት ቤት በአላውያን ነገሥታት ዐዋጅ በተዘጋ ጊዜ መምህራኑና ደቀ መዛሙርቱ የሄዱትና የተጠለሉት በአስቄጥስ በቅዱስ መቃርዮስ ገዳም ነበር፡፡ ታላላቆቹ ሊቃውንት ከጥፋት ተርፈው ትምህርታቸውን በጽሑፍ ትተውልን እንዲያልፉ ከፍተኛውን ሚና የተጫወቱት እነዚያ ገዳማት ነበሩ፡፡[147]

ከዚህም ጋር ከአላውያን የጥፋት እጆች አምልጠው ዛሬ ድረስ የደረሱልንን ብርቅና ውድ መጻሕፍት በጉያቸው ሸሽገው ከዛሬ ያደረሱልን ጥንታውያን ገዳማት ናቸው፡፡ ይህን የሚያውቁ አጥፊዎች ደግሞ ገዳማትን የጥቃት ዒላማቸው ማድረግ ከጥንት ጀምሮ የነበረ ስልታቸው ነው፡፡ የሙሶሎኒ ጦር ሀገራችንን በወረረበት ጊዜ እነ ማኅበረ ሥላሴን፣ እነ ደብረ ሊባኖስን፣ እነ ዝቋላ አቦን፣ እነ ዲማ ጊዮርጊስንና የመሳሰሉትን ታላላቆቹን ገዳማት መነኰሳቱን በአረመኔያዊ ጭካኔ መጨፍጨፉና በቦምብ መደብደቡ በአጋጣሚ የተደረገ ነገር አልነበረም፤ ቤተ ክርስቲያኒቷን ከመሠረቷ ለማጥፋትና ምንጯን ለማድረቅ የታሰበበት የካቶሊካውያን (የቫቲካን) የረጂም ዘመን ሕልምና ዘመቻ አካል ነበረ እንጂ፡፡

[146] "The missionary activity of the Church was 'cellular', carried out through the monasteries and hermitages scattered about the country." (Spencer Trimingham, Islam in Ethioipa, Oxford University Press, p. 55, 1952)
[147] Bishop Anba Mettaous, Sublimity of Monasticism, p. 35

ተሐድሶዎችም እንደ አባቶቻቸው ገዳማትን ለማጥፋት በአፍም በመጣፍም መታገላቸው የዚሁ የጥፋት ዘመቻ ቀጣይ አካልና መገለጫ መሆኑ ግልጽ ነው።

3) ገዳማውያን መነኰሳት በዓለም የምንኖር ሰዎች ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅርና መገዛት፣ በአጠቃላይ ሕይወታችንን እንድንመርምር ያደርጉናል። ራሳችንን ምንም ያህል "መንፈሳዊ" ነን፣ "ጥሩ" ነን ብለን ብናስብ እንኳ ከእኛ በበለጠ ሁኔታ ሙሉ ሕይወታቸውን የሰጡና በራሳቸው የሚያገለግሉት እንዳሉ ስናስብ በአንድ በኩል እንዳንታበይ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እንዳንሰንፍና ከመልካም ምግባር ሕይወት 'ጫፍ የደረስን እንዳይመስለን በሕይወታቸው ያሳዩናል፣ ያስተምሩናል። ጽንተን ብንጋደል በቅድስና ሕይወት እስከ ምን ርቀት ድረስ መሄድ እንደሚቻል አቅጣጫውንና ወሰኑን ያሳዩናል። ገዳማዊ ሕይወት ከምናየው ዓለምና በውስጡ ካለው ሕይወት የበለጠ ሌላ አኗኗርና ሌላ ዓለም ያለ መሆኑን በተግባር የሚያሳይ መስተዋት ነው።

4) ገዳማዊ ሕይወት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በቅዱሳን አበውና እማት በተቀደሰ ሕይወታቸውና እጅግ ጥልቅና ድንቅ በሆነ፣ ልዩ ጣዕምና ለዛ ባለው መንፈሳዊ ብሂሎቻውና አነጋገራቸው እንድትከብርና እንድታጌጥ አድርጓታል። ዛሬም ድረስ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በእነዚያ አባቶች ትምህርቶችና ብሂሎች በእጅጉ ተጠቃሚ ናት። እነ ዜና አበው፣ መጽሐፍ ገነትና የመሳሰሉት ለዚህ ሕያው ምስክሮች ናቸው።

5) በአጠቃላይ ገዳማትና በውስጣቸው የሚኖሩ መነኰሳትና መነኮሳዪያት ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጥንካሬና ህልውና የጀርባ አጥንቶችና መሠረቶች ናቸው። ለዚህ ነው ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ "ገዳማዊ ሕይወት ጠንካራ ከሆነ ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ጠንካራ ትሆናለች፣ ገዳማዊ ሕይወት መዳከም ከጀመረ ግን ቤተ ክርስቲያንም ትዳከማለች" በማለት የተናገረው።[148] የገዳማት ጥንካሬና ትንሣኤ ለወደፊቷ ቤተ ክርስቲያን ጥንካሬና ትንሣኤ ፋና ወጊ ሲሆን በተቃራኒው ገዳማት ከተዳከሙ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መጻኢ ሁኔታ በዚያው አቅጣጫ የሚሄድ መሆኑን አመላካች ነው።

ገዳማውያን ዓለምን የሚጠሉ አይደሉም፤ ኢየሱስ ክርስቶስን እጅግ አብዝተው ከመውደዳቸው የተነሣ ከእርሱ ጋር ይኖሩና በእርሱ ሕያዋን ይሆኑ ዘንድ ለዚህ ዓለም ሞቱ እንጂ። ጌታችንና መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር "ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም" ያለው ለዚህ ነበር። ማቴ. 10፣ 37-38 ይህም የሚያስረዳን ለእግዚአብሔር ሊኖር የሚገባው ፍቅር ለአባት፣ ለእናትና በዚህ ዓለም ላለ ቤተሰብ ከሚኖረን የበለጠ ሊሆን የሚገባው መሆኑን ነው። ከዚህም በላይ ጌታችን "ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እኅቶቹንም የራሱን ሕይወት ስንኳ ሳይቀር ባይጠላ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም" ብሏል። ሉቃ. 14፡26

*"ባይጠላ"* ማለት ምን ማለት ነው? እንኳን እናትና አባቶቻችንን እና የቅርብ ቤተሰቦቻችንን መጥላት ይቅርና ጠላቶቻችንን እንኳ ሳይቀር እንድንወድ ያስተማረን እርሱ እንዴት አሁን እንዲህ አለ? ይህን ያለው በአንጻራዊ ነው፤ ማለትም እናትና አባትን ወዘተ መውደድ የሚገባው ከእግዚአብሔር ባነሰ ፍቅር ሊሆን የሚገባው መሆኑን፣ ለእግዚአብሔር ሊኖረን የሚገባውን ፍቅር ግን ለሌላ ለማንም ማድረግ የማይገባ መሆኑን የሚገልጽ ነው እንጂ በቀጥታ "ጥሏቸው" ማለት አይደለም። ገዳማውያንም ስለ ፍቅረ እግዚአብሔር ሲሉ ከሰው ተለይተው በገዳማትና በበኣታት ተከትተው ቢኖሩም ሰውን ከመውደድና ስለ ሰው ከመጸለይ የራቁ ግን አይደሉም።

---

[148] Bishop Anba Mettaous, Sublimity of Monasticism, P. 37-38.

ይልቁንም ከሰዎች ጋር ተደባልቀን ከምንኖረው በበለጠ ስለ ሰው ልጆች መዳንና ደኅንነት ዘወትር ወደ ፈጣሪያቸው ይጸልያሉ፣ አስተብቁዖታቸውን ያቀርባሉ፡፡

ቤተሰብን ወይም የሆነ ሰውን፣ ወይም በአጠቃላይ ይህን ዓለም በመጥላት፣ ወይም ደግሞ ከሆነ ነገር ፍርሃትና ድንጋጤ ለማምለጥ ሲል ወደ ምንኵስናና ገዳማዊ ሕይወት የሚገባ ሰው በአብዛኛው በዚህ ሕይወት ብዙም አይቀጥልበትም፡፡ ለዚህም ታሪክ ምስክር ነው፡፡ ለምሳሌ ማርቲን ሉተር ወደ ገዳም የገባውና የመነኮሰው ድንገት መብረቅ ሲያስደነግጠው ከዚያ ጭንቅ ቢያድነው ወደ ገዳም ገብቶ እንደሚመነኩስ ስእለት ተስሎ ስለ ነበር ነው፡፡ በኋላ በድንገት የገባበት ሕይወት በእጅጉ እየከበደው ሲሄድ "እስከ ዛሬ ማንም ያላየውና ያልደረሰበት አዲስ የሐዲስ ኪዳን አተረጓጎም ተገለጠልኝ" በማለት እንግዳ የሆነ የፈጠራ ትምህርት አመጣ፡፡ ገዳማዊ ሕይወትንና ምንኵስና በማጥላላት ራሱ ቆቡን ጥሎ መነኩሲት የነበረችዋን ሌላዋን ማግባቱ ሳያንስ ሌሎችም የእርሱን አርአያ እንዲከተሉ አብዝቶ በመስበኩ ብዙዎች የእርሱን የተሸናፊነት መንገድ ተከትለዋል፡፡ ያለ ዓላማ የሚገቡበት ሕይወት ፍጻሜው አጥፍቶ መጥፋት ነውና፡፡

ዓለምን መካድ ማለት በውስጡ ያለውን ሥጋዊና ስሜታዊ የሆነውን ተድላና ደስታ፣ እንዲሁም ክፋቱንና ተንኮሉን መካድ፣ ከእርሱ መራቅ ማለት እንጂ ሥነ ፍጥረትን መጥላት ወይም መጸየፍ ማለት አይደለም፡፡ ሥነ ፍጥረትን ይጠሉና ይጸየፉ የነበሩት ግኖስቲኮችና መናፍቃን ነበሩ፡፡ ገዳማውያን መነኰሳት ግን እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ በጎ እንደሆነ ያምናሉ፣ ይመሰክራሉ፡፡ በአመክንዮ ዘሐዋርያት "እኛስ የእግዚአብሔር ፍጥረት መልካም እንደ ሆነ፣ የሚጣልም እንደ ሌለበት እንናገራለን" የሚለው የእምነት መግለጫ የወጣውም በአንድ በኩል በክርስትና ባለው የምናኔያዊ ጠባይ እና በሌላ በኩል ደግሞ ግኖስቲካዊ በሆነው ሥነ ፍጥረትን መጥላት መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት ለማሳሰብና ለመግለጥ ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ በታላቅ ትኅርምትና ገድል ይኖሩ ከነበሩ ታላላቅ ባሕታውያን መካከል አንዳንዶቹ በዓመት አንድ ጊዜ ሥጋ ይበሉ ነበር፡፡ ይህን ያደርጉ የነበረውም ሥጋ መብላትን የተውት ሥጋ ርኩስ ነው ብለው አለ መሆኑን ለማስተማር ነበር፡፡ ታላቅ ተጋዳሚና ባሕታዊ የነበረው አባት ቅዱስ አርሳንዮስ በዓመት አንድ ቀን ወይን ይጠጣ የነበረውም ለዚሁ ነበር፤ ሥነ ፍጥረት (ሥጋ እና ወይን) ርኩስ ነው ይሉ የነበሩ መናፍቃንን ስሁተት ናችሁ ለማለት፣ ገዳማውያንም በትህርምት የሚኖሩት ዓለምን በመጥላት አለመሆኑን በተግባር ለማሳየት ነበር፡፡

እነ ሉተርና ካልቪን ምንኵስናን ሲመዝኑና ሲተቹ ያልተረዱት አንዱ ጭብጥ ይህ ነበር፦ ዓለምንና ምኞቱን በመተው (መመነን) እና ዓለምን (ሥነ ፍጥረትን) በመጥላት መካከል፣ በዓለሙ ውስጡ ያለውን ክፋት በመጥላት እና በዓለም ውስጥ ያለውን ሥነ ፍጥረትን በመጸየፍ መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት አልተረዱም፡፡ ስለዚህም ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ ደረሱ፡፡

ገዳማውያን መነኰሳትም አብዛኛዎቹ በአንድነት (በማኅበር[149]) የሚኖሩ ናቸው፡፡ ይህም በዚህ ዓለም ከሚታወቀው ሕይወት ለየት ያለ አዲስ ማኅበረሰብ ነው፡፡ ለየብቻቸው የሚኖሩት ባሕታውያን እንኳ ሳይቀሩ ብዙዎቹ ለሱታፌ ምሥጢራት በተወሰኑ ዕለታት (በሰንበተ ክርስቲያን እና በታላላቅ የጌታ በዓላት) ይገናኛሉ፡፡ ስለ ጥንታውያን ገዳማት አደረጃጀትና ሕይወት የሚያነብ ሰው የዚህን ዓለም ወሰን አቋርጦ ወደ ሌላ አዲስና ልዩ ዓይነት ዓለም የገባ እንዲመስለው የሚያደርግ ስሜት ይፈጠርበታል፡፡ ገዳማዊ ሕይወት የሚኖረው (ያለው) በዚህ ዓለም ላይ ቢሆንም በይዘቱ ግን "ከዚህ ዓለም ያልሆነ" ልዩ ዓይነት ሕይወት፣ ልዩ ዓይነት አኗኗር ነው፡፡

---

[149] (The *community*, the *coenobium*)

ስለሆነም ምንኩስና በድንጋጤ ወይም በኑሮ አለመመቸት ወይም ከሆነ ከሚጠሉት ነገር ለመሸሽ ሲባል የሚገባበት ሕይወት ሳይሆን በውስጥ ያለው ፍቅረ እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ካለው ማንኛውም ነገር ሲበልጥ ሙሉ ሕይወትን ለመስጠት የሚገባት ሕይወት ነው፡፡ ሌላውን ነገር ሁሉ ትታ ከእግሩ ሥር ቁጭ ብላ ትምህርቱን ትሰማ የነበረችውን ማርያም እኅተ ማርታን ጌታችን "ማርያምሰ ኀርየት መክፈልተ ሠናየ ዘኢየሀይድዋ - ማርያምስ መልካም ዕድልን መርጣለች፣ ከእርሷም አይወሰድባትም" እንዳላት ያለውን የማይወሰደውንና ከዚህ ዓለም መባከን የራቀውን "ሠናይ መክፈልት - መልካም ሀብት" የመምረጥ ጉዳይ ነው፡፡ ሉቃ. 10፥42

ይህ ዓይነቱ ሕይወት ደግሞ ገዳማውያን መነኰሳት ብቻ ሳይሆኑ ማንኛውም ክርስቲያን ሊኖረው የሚገባ ሕይወት ነው፡፡ አንድ አባት "እውነተኛ ክርስቲያን ሁሉ መናኝ ነው - A true Christian is an ascetic" ብሎ የገለጸው ይህንኑ እውነታ ነው፡፡ ጋብቻን ከሚመለከተው በስተቀር ለሁሉቱም የተሰጠው የቅድስና፣ የንጽሕና፣ የትሕትና፣ ዓለምን የምናይበት እይታ፣ የተሰጠን ሰማያዊ ተስፋ ሁሉ አንድ ነው፡፡ ስለሆነም መነኰሳት እንዳዝበት ዘንድ በተነገረው የክርስትና መንገድ በሙሉ ኃይላቸውና በሁለንተናቸው ለመጓዝ ራሳቸውን ሲሰጡ በዓለም የሚኖሩ ደግሞ እንደየ ዓቅማቸው ያህል ይጋደላሉ፡፡ ከዚህ ውጭ በገዳማውያንና በዓለም በሚኖሩ ክርስቲያኖች መካከል መሠረታዊ የሆነ የዓላማና የምንነት ልዩነት የለም፡፡ ክርስትና በባሕርዩ የምናኔያዊና የብሕትውናው ጠባይ ያለው ነውና፡፡ ይህም ከመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን የሕይወት ዘመን ጀምሮ ይታይ የነበረና በዘመናት መካከል ሲገለጥ የኖረ፣ ዛሬም ያለ ነው፡፡

ይህን በተመለከተ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዲህ ብሏል፡-

> በከተማ ውስጥ የሚኖር ሰው ቢሆን እንኳ የመነኰሳትን ሕይወት አርአያ ማድረግና እንደ እነርሱ መኖር ይችላል፡፡ ሚስት ያለችውና ቤተሰቡን የማስተዳደር ኃላፊነት ያለበት ሰው ቢሆን እንኳ መጸለይ፣ መጾም፣ እና በትሕትና ሆኖ ራሱን በማስገዛት መኖር ይችላል፡፡ መጀመሪያ በሐዋርያት የተሰበኩት ሰዎች በከተማዎች ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ቢሆንም እንኳ በበረሓ በገዳማት እንደሚኖሩት ያለ አኗኗር ይኖሩ ነበር፡፡ . . . ሆኖም በከተማ ውስጥ መኖራቸው ከመንፈሳዊ አኗኗር አልከለከላቸውም፡፡ . . . ስለዚህ እነዚህን ሰዎች በሕይወታቸው እንመስላቸው ዘንድ እንበርታ . . . በበረሓ በገዳማት ያሉት ሊኖሩትና ሊደርሱበት የሚፈልጉትን መንፈሳዊ ሕይወት እኛም ወደ ከተማችን ውስጥ እንድናመጣውና እንድንኖረው ራስን መግዛትንና ሌሎቹን መንፈሳውያት ምግባር ትሩፋቶች ሁሉ በውስጣችን እንዲሠርጹ እናድርግ፡፡

በዚሁ ቅዱሳን አባቶቻችን ስለ ምንኵስናና ገዳማዊ ሕይወት ወዳስተማሩት ትምህርት እንሂድ፡፡

## 7.9 ድንግልና፣ ምንኵስናና ገዳማዊ ሕይወት በቀደምት አበው ሊቃውንት ትምህርት

- "ሁለት የሕይወት መንገዶች አሉ፤ አንዱ መካከለኛና ለሕይወት ተስማሚ የሆነ መንገድ ሲሆን (እርሱም ጋብቻን ማለቴ ነው) ሌላኛው ደግሞ መልአካዊና እጅግ ከፍ ከፍ ያለ ነው፤ እርሱም የድንግልና ሕይወት ነው፡፡ አንድ ሰው ማንም ሊመርጠው የሚችለውን የተለመደውን የሕይወት መንገድ (የጋብቻን መንገድ) ቢመርጥ አይነቀፍም፡፡ ሆኖም በሌላው የሕይወት መንገድ (በድንግልና) የሚገኘውን ዓይነት ታላቅና የበዛ ጸጋና ክብር ግን አያገኝም፡፡ ፍሬው የሚሆነው ባለ ሠላሳ ነውና፡፡ ሆኖም ከተራው የተለየ የሆነውንና መልአካዊ የሆነውን የድንግልናን መንገድ የሚመርጥ ሰው ግን ከዚያኛው (ከጋብቻ) አንጻር ሲታይ መንገዱ ሻካራና አስቸጋሪ ቢሆንም እጅግ የበለጠ አስደናቂና ታላቅ ነገርን ያገኛል፤ ፍጹም የሆነውን ፍሬ - ባለ መቶ - ያፈራልና፡፡" (ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ መልእክት ኀበ መነኩስ አባ አሞን[150])

[150] The Rudder: Canons of the Holy Fathers, First Epistle to the Monk Amun.

- “ምነው በፊት በጳንጦስ በእነዚያ ገዳማት ወደ ነበርኩባቸው ወደ እነዚያ ጊዜያት የሚመልሰኝ ባገኘሁ፤ ከአንተ ጋር [ከቅዱስ ባስልዮስ ጋር] በጽኑ ትህርምትና አኗኗር የተደሰትኩባቸው እነዚያ ጊዜያት ልዩ ነበሩ፡፡ በፈቃድ የሚደረግ ድካምና ሕማም ከዚህ ዓለም ተድላና ደስታ ይልቅ የበለጠ ዋጋ አለውና፡፡ እነዚያን መዝሙራትና ትጋሃ ሌሊቶች፣ እነዚያን ጸሎታት ሁሉ፤ ያን ሥጋ የለሽ የሆነ የመንፈስ ሕይወት አሁን ማን መልሶ በሰጠኝ! በዚያ የነበሩ ወንድሞች በአንተ አባትነት አንዲት ነፍስ ያላቸውና ፍጹም የተቀራረቡ ነበሩ፡፡ . . . ቀለል ስላሉ ጉዳዮች ብናገር፣ በየቀኑ ይፈጸሙ ስለ ነበሩት የእንጨት ለቀማ፣ ድንጋይ ፈለጣ፤ . . . የፋርሱ ንጉሥ አርጤክስስ ከተቀመጠባቸው ወንበሮች እጅግ የከበሩ ስለ ሆኑት ስለ እነዚያ ወርቃማ ዛፎች፣ በላያቸው ላይ የሚቀመጠውም በምቾትና በተድላ የተበላሸና የተዳከመ ንጉሥ ሳይሆን በትህርምትና በተጋድሎ የደከመ መነኩሴ ነው፡፡ . . ." (ቅዱስ ጎርርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ መልእክት ኀበ ቅዱስ ባስልዮስ፣ ቁ. 6)

- “በምንኩስና ሕይወት ለሚኖሩ ሁሉ በያሉበት፣ በእግዚአብሔር ባላቸው እምነት ለተመሠረቱና በክርስቶስ ለተቀደሱ፤ ‘እነሆ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ’ ይሉት ዘንድ ለሚቻላችሁ፣ በእጅጉ ለተወደዳችሁና ተናፋቂ ለሆናችሁ ወንድሞቼ፣ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ልባዊ የሆነ ሰላምታ አቀርባለሁ፡፡” (ቅዱስ አትናቴዎስ፣ መልእክት 52፤ ለመነኰሳት የተላከ መልእክት፣ ቁ. 1)

- “መነኰሳት እግዚአብሔር አዝመራውንና ከብቱን ሁሉ ይባርከው ዘንድ መጀመሪያ ከሚደርሰው ጀዝመራና የእናቱን ማኅፀን ከሚከፍተው እንስሳ መካከል ለእግዚአብሔር እንደሚሰጠው እንደ በኩራት ያሉ ናቸው፡፡ ሊጡን ሁሉ እንደሚያቦካው እርሾ ናቸው፡፡” (አባ ጴሜን)[151]

- “የምንኩስና ሕይወት መዓርጉና ደረጃው ፈጣሪያቸውን ከማመስገን ፈጽመው የማያቋርጡ የቅዱሳን መላእክት ሕይወት ነው፡፡ መነኩሴ ከሆነ በኋላ ግድ የለሽና ዝንጉ የሚሆን ሰው በዚያው የግድ የለሽነት ደረጃ በዓለም ውስጥ ከሚኖር ሰው ይልቅ በከፋ ሁኔታ ላይ ነው፡፡ መነኩሴ እንደ መልአክ ለመኖር ራሱን ያዘጋጀና የዓለምን ልብስና ምኞት ቀዳድዶ ለመጣል የተዘጋጀ ሰው ነው፡፡ መነኩሴ ለመሆን የምትሻ ከሆነ ታናሽም ሆነ ታላቅ ከሚባሉ ትእዛዛት አንዳቸውንም ችላ አትበል፤ ሁሉንም ያለ ማቋረጥና ያለ ጽርአት ፈጽማቸው እንጂ፤ አለበለዚያ ግን በዓለም ከሚኖሩ ሰዎች ጋር እንደ እነርሱ ሆነህ ብትኖር በእጅጉ የተሻለ ነው፡፡” (ቅዱስ ቀሌምንጦስ፣ በምንኩስና ሕይወት ሊኖሩ ለሚሹ የሰጠው ትምህርት)

- “ሰማይ ከምድር የሚርቀውን ያህል እና መላእክት ከሰዎች የሚልቁትን ያህል ድንግልና ከጋብቻ ከፍ ያለ ነው፡፡” (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ድንግልናዊ ሕይወት)

- “ይህን ሕይወታችንን በጸሎት፣ በትጋሃ ሌሊት፣ መናኛ በሆነ አመጋገብ፣ መጠን አለፍ የሆኑ ፍላጎቶቻችንን ሁሉ ቆርጠን በመጣል፤ በምኞቶቻችን ላይ ማዕቀብ በማድረግ ብንኖር ኖሮ፣ የመልካም ምግባር ሕይወት የሚጠይቀውን ድካም በመቀበል ብንኖር ኖሮ፣ ሰውነታችንን እንደ ቅዱስ ጳውሎስ እየጎሰምን ብናስገዛው ኖሮ (1 ቆሮ. 9፡27)፣ ‘እርኒታችን ለሥጋ ፍትወት ምክንያትን ባይሰጥ’ ኖሮ፣ በጠባቧና በቀጭኗ መንገድ ብንሄድ ኖሮ ስለሚመጣው ዓለም ነገር አብዝተን የምንናፍቅ እንሆን ነበር፤ ከዚህ ዓለም ድካም ለማረፍም እንጓጓ ነበር፡፡ ገላ. 5፡13 ይህ የምለው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ከፈለግህ ወደ ገዳማት ሂድና በዚያ የሚኖሩትን መነኰሳት ተመልከታቸው፡፡

---

[151] The Life of Chastity, p. 109

በዚያ ያሉ ገዳማውያን መነኰሳት አንዳንዶቹ ማቅ ለብሰው፣ አንዳንዶቹ በሰንሰለት ሆነው፣ አንዳንዶቹ አብዝተው በመጾም፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በአታቸውን ዘግተው በጨለማ ውስጥ በመጋደል ያሉትን ተመልከታቸው፡፡ እነዚህ ሁሉም ሞትን እንደሚፈልጉትና እንደማይፈሩት፣ ስሙንም ዕረፍት እንደሚሉት ታያለህ፡፡ . . . (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 6፣ ቁ. 7-8)

- "ድንግልና ለክርስቶስ የሚቀርብ መሥዋዕት ነው፣ እርሱም የመላእክት አኗኗር ነው፡፡" (ቅዱስ ጀሮም፣ በመናፍቁ ጆቪኒያን ላይ የጻፈው መጽሐፍ)

- "የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ መልአካዊ የሆነ ሕይወትን (ድንግልናን) መሠረተልን፣ ይህም በሰማይ በመላእክት የሚታጀበው እርሱ በምድርም ላይ ሰዎች እንደ መላእክት ይኖሩበት ዘንድ ነው፡፡" (ቅዱስ ጀሮም፣ መልእክት 22)

- "ድንግልና የማይነጥፍ የሀብት ምንጭ፣ የማይጠፋ ዘውድ፣ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፣ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ፣ የከበረ ዕንቁ፣ በሲኦልና በሞት ላይ የድል አድራጊነት ዓርማ ነው፡፡" (ቅዱስ አትናቴዎስ፣ ትምህርት በእንተ ድንግልና)

- "ወእስበ ጽድቀ ድንግልና ዘይትዔረይ ምስለ መላእክት - ከመላእክት ጋር የሚተካከል በድንግልና የሚገኝ የጽድቅ ዋጋ አለ፡፡" (ቅዱስ ኤራቅሊስ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ 162፣ ቁ. 23)

- "ደናግል የቅድስት ሥላሴ አርአያ ናቸው፣ በበጉ ፊት ይቆማሉ፣ እርሱ ወደሚሄድበትም ሁሉ ይከተሉታል፡፡" (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኰት)

- ". . . ይህ እኛ የምንለው ነገር በቃላት ብቻ የሚነገር ሳይሆን እውነተኛነቱ በተግባርም የሚመሰከር ነው፡፡ ይህን ለማረጋገጥ የሚፈልግ ሰው የቅድስና ሕይወትን በተለመከተ ድንግልናና ንጽሕናን ገንዘብ ለማድረግ በሚጋደሉ በክርስቶስ ደናግላንና በወጣቶች፣ የሞትን ድል አድራጊነትና የኢመዋቲነትን ማስረጃ ደግሞ ስለ ክርስቶስ ሲሉ ሞትን እንደ ኢምንት በቆጠሩትና ደስ እያላቸው ሞትን ፊት ለፊት በተጋፈጡትና በተቀበሉት ብዙ በሆኑ ድል አድራጊ ሰማዕታት በተግባር መመልከት ይችላል፡፡ . . . " (ቅዱስ አትናቴዎስ፣ በእንተ ተሠግዎተ ቃል፣ 48፥1-2)

- ". . . ወደ እርሱም [ወደ ቅዱስ እንጦንዮስ] ብዙ ሰዎች ይመጡ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም በእርሱ በኩል ወደ እርሱ የመጡትን የብዙዎችን ሕማምና ደዌ ፈወሳቸው፣ ብዙዎችንም ከርኩሳን መናፍስት ቁራኝነት ነጻ አወጣቸው፡፡ እንዲሁም ለእንጦንዮስ በአነጋገሩ ሞገስን ስለ ሰጠው ያዘኑትን ብዙዎችን አጽናናቸው አረጋጋቸው፣ የእርስ በእርስ ጠብና ክርክር የነበረባቸውንም በዓለም ካለው ከማንኛውም ነገር በፊት የክርስቶስን ፍቅር እንዲመርጡ ይመክራቸው ነበር፡፡ የሚመጣውን መልካም ነገር እንዲያስቡና አንድ ልጁን አሳልፎ እስኪሰጥልን ድረስ 'ለአንድ ልጁ ያልራራለትን፣ ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠውን' (ሮሜ 8፥32) የእግዚአብሔርን ቸርነትና ደግነት እንዲያስተውሉ በመምከርና በማስተማር ብዙዎችን የገዳማዊ ሕይወትን እንዲመርጡ አሳመናቸው፡፡ ከዚህም የተነሣ የመነኰሳት በአታት በተራራዎቹ እንኳ ሳይቀር ይታነጽ ጀመረ፡፡ በረሓውም ከሕዝባቸውና ከኅብረተሰቡ መካከል ተለይተው ወጥተው ራሳቸውን ለሰማያዊ ዜግነት እድምተኞች ባደረጉ በመነኰሳት የተሞላ ሆነ፡፡" (ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ ገድለ እንጦንስ፣ ቁ. 14)

ቅዱስ ባስልዮስ በቀጰዶቅያና በታናሽ እስያ በነበሩት ብዙ ገዳማት የነበሩት ገዳማውያን መነኰሳት ራስ ወዳድነትን በማሸነፍና በአንድ መንፈስ በመኖር ፍቅርን በተግባር የሚያሳዩ መሆናቸውን ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

- "እነዚህ ገዳማውያን መነኰሳት የቀደመውን አባታችንን የአዳምን ኃጢአት በማሸነፍና በማለፍ ሰው ከመበደሉ በፊት የነበረውን የመጀመሪያውን ዓይነት ደግነት መልሰው ገንዘብ አድርገውታል፡፡ ከመጀመሪያው በኃጢአት ባንሰነካከል ኖሮ መለያየት፣ መጣላት፣ ጦርነት በሰዎች መካከል ቦታ አይኖራቸውም ነበር፡፡ ገዳማውያን መነኰሳት የተለያየውንና የተራራቀውን የሰውን ባሕርይ ወደ ራሱና ወደ እግዚአብሔር ይሰበስቡታል፡፡ ይህ የሰው ባሕርይ ከኃጢአት ጋር የነበረውን ቁርኝትና መጣበቅ አጥፍቶ የሰውን ባሕርይ ወደ ራሱ (ወደ ሰው ባሕርይ) እና ወደ እግዚአብሔር መሰብሰብና አንድ ማድረግም[152] መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ባደረገው የማዳን ጉዞ ውስጥ ዋናው ጉዳይ ነበር፡፡ ገዳማውያን መነኰሳት መልሰው ገንዘብ ያረጉትና የሚኖሩት ሕይወት እርሱን ነው፡፡" (ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ)

- "ድንግልናዊ ሕይወትና ምንኩስና ታላቅ ነገር ነው፤ ከመላእክት መዓርግ መደመር (አንድ መሆን) ነውና፡፡ ጌታችን ስለ ተወለድን ስለ እኛ ሲል መወለድን በፈቃዱ ቢቀበልም ከድንግል በመወለድ የድንግልናን ሕግ ሠራልን፤ በዚህም ከዚህ ከምድራዊው ዓለም ከፍ ወዳለው ይወስደንና የዚህን ዓለም ኃይል እጭር ያደርገው ዘንድ፣ ይልቁንም ደግሞ ይህን ዓለም ወደ ሌላ ዓለም ያሸጋግረው ዘንድ፣ የአሁኑን ወደሚመጣው ያሸጋግረው ዘንድ ነው፡፡ እርሱም [ቅዱስ ባስልዮስ] የጌታችንን አርአያ በመከተል ድንግልናን ተገቢ በሆነ ከፍ ባለ ክብር አከበረ፣ ይህም በራሱ ሕይወት ላይ ብቻ ሳይሆን እርሱ ባቋቋማቸው ገዳማት ሥር ባሉ መነኰሳት ሕይወትም ጭምር አደረገው እንጂ፡፡

  ". . . በተጨማሪም የብሕትውናን እና የአንድነት ገዳማዊ ኑሮን እጅግ ግሩም በሆነ ሁኔታ እንዲሰናሰሉና እንዲዋሐዱ አደረጋቸው፡፡ . . . ለባሕታውያን በእታትን አቋቋመ፡፡ ይህን ያደረገውም በአንድነት ከሚኖሩት መነኰሳት ገዳም በጣም ባልራቀ ርቀት ላይ ነበር፡፡ በዚህም አንዱ ከሌላው እንዳይለይና በአንዱ ያለው ጥሩ ነገር ለሌላውም እንዲሆን አደረገ፤ በብሕትውና በሚኖሩት ያለው የተመሰጠና የተዘከሮ ሕይወት በአንድነት በሚኖሩት፣ በአንድነት በሚኖሩት መነኰሳት ያለው ኅብረተሰቡን የማገልገልና የመደገፍ ተግባር ደግሞ በብሕትውና በሚኖሩት እንዲኖርና የሁሉም የጋራ ዓላማ የሆነውን የእግዚአብሔርን ክብር መግለጥ አንድ እንዲሆኑ አደረገ፡፡"

  (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ በቅዱስ ባስልዩስ የዕረፍት ቀን መታሰቢያ ላይ ያስተማረው ትምህርት፣ ቁ. 62)

- "ለድንግልና ከፍ ያለ ክብር ስለምንሰጥ ጋብቻን አናቃልልም፡፡ ሙሽራ የሆነውን ክርስቶስን አርአያ አደርጋለሁና፤ እርሱ በሠርግ ቤትም ተአምር አድርጓል፣ በዚያ በመገኘቱም ጋብቻን አክብሮታል፡፡ ብቻ ጋብቻ የተናቀ ከሆነ ስሜታዊነትና ፍትወት የጸዳና በዚህ ያልተበከለ ይሁን፡፡" (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ ትምህርት በእንተ ጥምቀት፣ 18)

---

[152] ( . . . to gather human nature to itself and to Himself and, having abolished this evil cleavage, to restore the original unity.)

❖ "ጋብቻ የከበረ ነው፤ ሆኖም ከድንግልና እንጻር ግን ይበልጣል አልልም፡፡ ምክንያቱም ድንግልና ጥሩ ከሆነ ነገር (ከጋብቻ አንጻር) ሲታይ የተሻለ ባይሆን ኖሮ ታላቅ ነገር ነው ባልተባለ ነበርና፡፡ ሆኖም በጋብቻ ያላችሁ ሴቶች ሆይ፥ ይህን ስትሰሙ እንዳትቆጡ፡፡ ከሰዎች ይልቅ እግዚአብሔርን ልንታዘዝ ይገባናል፡፡ ደናግልም ሆናችሁ ባል ያገባችሁ ሚስቶች፥ ሁላችሁም በጌታ አንድ ሁኑ፥ በአንድ መንፈስ ተሳሰሩ፥ እያንዳንዳችሁም በየምትኖሩበት ሕይወታችሁ ለሌላው ጌጥና ውበት ሁኑ፡፡ . . . የመረጥሺው የመላእክትን ሕይወት ነውን? ወይስ በጋብቻ ቀንበር ሥር ካሉት መካከል ነሽ? እንዲህ ከሆንሽም ወደ ሥጋዊነት ጭልጥ ብለሽ እንዳትሰጥሚ ሁኚ፥ ወደ ቁስ አካል አትስጠሚ፡፡

"የመላእክትን ሕይወት የመረጣችሁ ደናግል የሆናችሁ፥ ልባችሁም ድንግል ይሁን እንጂ የሚባክንና የሚባዝን አይሁን፡፡ . . . ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ይህን ነገር ከተሰጣቸው በስተቀር ሁሉም ሰው ሊቀበለው አይችልም አላቸው፡፡ የነገሩን ጥልቅነትና ረቂቅነት አየህን? ለመረዳት ወደማይቻልበት ጥልቅ ደረጃ ላይ ያለ ነገር ነው፡፡ ሥጋ የለበሰና በሥጋ የሚኖር ሰው ሆኖ ሳለ፥ ነገር ግን እንደ ሥጋ ፈቃድ አለመኖርና ለሥጋ አለመገዛት ይህ በእውነት ከተፈጥሮው በላይ መሆንና መልአካዊነት ነው፡፡ . . ."[153]

(ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ ትምህርት 37፣ ቁ. 10-11)

❖ ". . . የእኛ ፈላስፎች እነዚህ ገዳማውያን መነኰሳት ናቸው፡፡ ፍልስፍናቸውም ከሁሉም በላይ እጅግ ድንቅና ጥልቅ የሆነ ፍልስፍና ነው፡፡ የመልካም ምግባር ሕይወታቸውን የሚያሳዩት እንደ ዓለማዊ ፈላስፎች አፍአዊ በሆነ ሁኔታ ሳይሆን በሕይወታቸውና በድርጊታቸው ነውና፡፡ የአሕዛብ ፈላስፎች በመድረክ ላይ ተውኔት ከሚጫወቱ ሰዎች በምንም መንገድ የተሻሉና የተለዩ አይደሉም፤ በላያቸው ላይ ከደረቡት ካባ፥ ከሚያንዠረግጉት ጺማቸውና ከረጂም ቀሚሳቸው በስተቀር ከዚያ ያለፈ በተግባር የሚያሳዩት ነገር የላቸውም፡፡ እነዚህ የእኛ ፈላስፎች ግን አፍአዊ ነገርንና ለሰው የሚታየውን ነገር ሁሉ እንደ ቁም ነገር ሳይቆጥሩት ነፍሳቸው ግን በእውነተኛው የፍልስፍና አስተምህሮ ያጌጠች ናት፡፡

[153] (Marriage is honourable; but I cannot say that it is more lofty than virginity; for virginity were no great thing if it were not better than a good thing. Do not however be angry, ye women that are subject to the yoke. We must obey God rather than man. But be ye bound together, both virgins and wives, and be one in the Lord, and each others' adornment. There would be no celibate if there were no marriage. For whence would the virgin have passed into this life? Marriage would not have been venerable unless it had borne virgin fruit to God and to life. Honour thou also thy mother, of whom thou wast born. Honour thou also her who is of a mother and is a mother. A mother she is not, but a Bride of Christ she is. The visible beauty is not hidden, but that which is unseen is visible to God.

". . . And she who is under the yoke, let her also in some degree be Christ's; and the virgin altogether Christ's. Let the one be not entirely chained to the world, and let the other not belong to the world at all. For that which is a part to the yoked, is to the virgin all in all. Hast thou chosen the life of Angels? Art thou ranked among the unyoked? Sink not down to the flesh; sink not down to matter; be not wedded to matter, while otherwise thou remainest unwedded. A lascivious eye guardeth not virginity; a meretricious tongue mingles with the Evil One; feet that walk disorderly accuse of disease or danger. Let the mind also be virgin; let it not rove about; let it not wander; let it not carry in itself forms of evil things (for the form is a part of harlotry); let it not make idols in its soul of hateful things.

"XI. But He said unto them, All men cannot receive this saying, save they to whom it is given. Do you see the sublimity of the matter? It is found to be nearly incomprehensible. For surely it is more than carnal that that which is born of flesh should not beget to the flesh. Surely it is Angelic that she who is bound to flesh should live not according to flesh, but be loftier than her nature. The flesh bound her to the world, but reason led her up to God. The flesh weighed her down, but reason gave her wings; the flesh bound her, but desire loosed her. With thy whole soul, O Virgin, be intent upon God (I give this same injunction to men and to women); and do not take the same view in other respects of what is honourable as the mass of men do; of family, of wealth, of throne, of dynasty, of that beauty which shews itself in complexion and composition of members, the plaything of time and disease. . . .)(On the Words of the Gospel, "When Jesus Had Finished These Sayings," Etc.— No. X-XI)

"በአስተምህሮ ብቻም ሳይሆን በተግባራዊ ሕይወትም ያጌጡ ናቸው። እንዲህ ተራና መናኛ ሕይወት ከሚኖሩት ከእነዚህ መነኵሳት መካከል አንዳቸውን የአሕዛብ ፈላስፎች ለዘመናት ስፍር ቁጥር በሌለው ሁኔታ ሲተቹባቸውና ሲከራከሩባቸው ከኖሩባቸው፣ እንዲያውም ሆኖ ፍሬ ያለው አንዳችም ነገር እንኳ ለማለት ካልቻሉባቸው ጉዳዮች መካከል ስለ አንዱ ጉዳይ ብትጠይቋቸው፣ ከእነዚህ አንዱ ትክክለኛ የሆነውን መልስ ከልቡናው የጥበብ መዝገብ አውጥቶ ይነግራችኋል። የሚያስደንቀው ይህ ብቻ አይደለም፣ የእነዚህን አስተምህሮዎች ተአማኒነትና እውነተኛነት በተግባራዊ ድርጊታቸውና በሕይወታቸውም የሚያረጋግጡ መሆናቸው ነው እንጂ። ኢ.መዋቲ የሆነች ነፍስ ያለችን ስለ መሆኑና በዚህ ምድር ባለው በአሁኑ ሕይወታችን ስላደረግነው ነገር ሁሉ የምንጠየቅበት ስለ መሆኑ፣ አስፈሪ በሆነ የፍርድ ዙፋን ፊት ስለ መቆማችን ሁሉ ውስጣቸው ደኅና አድርጎ ያመነበት በመሆኑ አኗኗራቸውንና ድርጊታቸውን ሁሉ ሁል ጊዜ የሚመሩትና የሚቆጣጠሩት በዚሁ እምነት መሠረት ነው። የዚህን ዓለም ታይታና ተርእዮ ሁሉ ድል አድርገው አልፈውታል፣ 'ሁሉም ከንቱ የከንቱ ከንቱ ነው' የሚለውን ከቅዱሳት መጻሕፍት የተማሩ በመሆናቸው የሚያስጎመጁ ከሚመስሉት ነገሮች ለአንዱ እንኳ አይጓጉም። መክ. 1፡2"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት 19፣ ቁ. 2-3)

- "...ምን አድርግ ነው የምትለን? ወደ ገዳም ሂዱና መነኰሳት ሁኑ ነው የምትለን?' የሚል ሰው ይኖር ይሆናል። እኔን በጣም የሚያሳዝነኝ ነገር ይህ ነው። ስለ ቅድስና ሕይወትና ስለ ንጽሕና የሚመለከታቸው መነኰሳትን ብቻ እንደ ሆነ አድርጋችሁ ማሰባችሁ፣ ይህ ነው በጣም የሚያሳዝነኝ። ነገር ግን ክርስቶስ የሠራው ሕግ ለሁሉም ሰው እንጂ የተለያዩ ሕጎችን አልሠራም። "ወደ ሴት ያየ ሁሉ፣ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል" ሲል ይህን የተናገረው ለባሕታዊው ብቻ አይደለም፣ ሚስት ላለችው ለእርሱም ነው እንጂ። ማቴ. 5፡28 እኔ ከማግባት አልከለከልኋችሁም፣ በጋብቻ ያለውን ነገርም አትፈጽሙ አላልኋችሁም፣ ነገር ግን የምታደርጉትን ነገር ሁሉ ያለ ነውር በአግባብና በንጽሕና አድርጉት። ወደ በረሓና ወደ ተራራ እንድትሄዱ የሚል ሕግ አላወጣባችሁም፤ በከተማ መካከል እየኖራችሁ ደጋጎችና ንጹሐን እንድትሆኑ እንጂ።

"ለመነኰሳት የተሰጧቸው ሕግጋት ለሁሉም ሰው ከተሰጡት ጋር አንድ ናቸውና፣ ከጋብቻ በስተቀር። በርግጥ ይህን በተመለከተም ቢሆን ቅዱስ ጳውሎስ በጋብቻ የሚኖሩ ራሳቸውን ከመነኰሳት ጋር እንዲያስተያዩ እንዲህ ሲል ያዝዛቸዋል፦ "ዳሩ ግን፣ ወንድሞች ሆይ፣ ይህን እናገራለሁ፤ ዘመኑ አጭር ሆኖአል፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሚስቶች ያሏቸው እንደ ሌላቸው ይሁኑ፣ ... የሚገዙም ምንም እንደ ሌላቸው፣ በዚችም ዓለም የሚጠቀሙ በሙሉ እንደማይጠቀሙበት ይሁኑ፤ የዚች ዓለም መልክ አላፊ ነውና" በማለት። 1 ቆሮ. 7፡29-31 ስለዚህ ወደ ገዳም ሂዱ አልላችሁም። እንዲያ ብታደርጉ የበለጠ ደስ እንደሚለኝና ምኞቴ እንደ ሆነ ግልጽ ነው፤ ከተማዎች እየመሰሉ ያሉት ድሮ በሰዶም ይደረግ እንደ ነበረው ነውና። ሆኖም ይህን በግድ አልልም። ትዳር፣ ሚስትና ልጆች እያሉህ በአግባቡ ኑር፤ ከቤትህ ውጭ በምታደርገው አሳፋሪ ነገርና ከቴያትር ቤት ያኸውን ብክለትና ቆሻሻ ወደ ቤትህ ይዘህ መጥተህ የሚስትህን ክብሯን አታቃልለው፣ አትስደባትም፣ ልጆችህንም አታሳፍራቸው፣ ..."

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌለ ማቴዎስ፣ ክፍለ ትምህርት 7፣ ቁ. 8)

- "በረሓውንና ምድረ በዳውን የያዙትንና በዚያ የሚኖሩትን መነኰሳትን አደንቃቸዋለሁ፤ አመሰግናቸዋለሁም፡፡ ማታ ለቁመተ ሥጋ የሚሆን ትንሽ ነገር ከቀመሱ በኋላ (እራት በእነርሱ ዘንድ የለምና፤ ምክንያቱም ይህ የአሁኑ ዓለም ሕይወት የልቅሶና የጾም ዘመን መሆኑን ያውቃሉና) ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡትን የምስጋና ጸሎታቸውን ይጀምራሉ፤ በመዝሙር ያመሰግኑታል፡፡ በመዝሙራቸው ያለው ሓሳብም እንዲህ የሚል ነው፡-

  ቅዱስ እግዚአብሔር ሆይ፣ ከሕፃንነቴ ጀምሮ እስከ ዛሬ የመገብከኝ፣ ለሥጋ ሁሉ ምግብን የምትሰጥ ጌታ ሆይ፤ ልባችንን በደስታና በሐሤት ሙላው፤ ሁል ጊዜ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መልካም ሥራን አብዝተን እናደርግ ዘንድ፤ ምስጋና ከእርሱ ጋር ለአንተ ክብርና ምስጋና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ይሁን፣ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡ ጌታ ሆይ፣ ክብር ለአንተ ይሁን፡፡ ቅዱስ ሆይ፣ ክብር ለአንተ ይሁን፡፡ ንጉሥ ሆይ፤ ክብር ለአንተ ይሁን፤ የዕለት ምግባችንን ሰጥተኸናልና፡፡ ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ሥራው በምትከፍልበት ጊዜ የማናፍር እንድንሆንና በፊትህ ደስ የምናሰኝህ ሆነን እንገኝ ዘንድ መንፈስ ቅዱስን የተመላን አድርገን፡፡ (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌለ ማቴዎስ፣ ክፍለ ትምህርት 55፤ ቁ. 6)

- "በዚህ ዓለም ሕይወት ካለው ነገር ውስጥ ደስ የሚያሰኘው ምንድን ነው? እውነቱን ንገረኝ ካላችሁ በእውነቱ ይህ እናንተ አስቸጋሪና አድካሚ ሕይወት ነው የምትሉት ሕይወት፤ ማለቱም የመነኰሳትና በምናኔ የሚኖሩ ሰዎች ሕይወት ቀላልና ምቹ ከሚመስለው ሕይወት ይልቅ በእጅጉ ጣፋጭና ሊመኙት የሚገባ ሕይወት መሆኑን ልነግራችሁ እወዳለሁ፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌለ ማቴዎስ፣ ክፍለ ትምህርት 68፤ ቁ. 3)

- "ሠይፍና ጦር ታጥቀው ራሳቸው ላይ ጥሩር ደፍተው ድንኳናቸውን ተክለው ከሚታዩ ወታደሮች ይልቅ ተጨጋግተው የተሠሩ የመነኰሳትን በኣታት የያዘ በረሓ በእጅጉ አስደሳች ነው፡፡ . . . ስለዚህም ወደ እነዚህ ሰዎች እንሂድ፡፡ በዚያም በዓለም የምንኖር እኛ በስንት ዓይነት ወጥመድ እንደ ታሰርን እንገነዘባለን፡፡ በዚያ በእነርሱ ዘንድ የነፍስ ሁከት የለም፤ ቁጣና ሐዘን የለም፤ ሁሉም ጸጥታ ነው፤ ሁሉም ሰላም ነው፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፤ ትርጓሜ ወንጌለ ማቴዎስ፣ ክፍለ ትምህርት 69፤ ቁ. 3)

- "የንጽሕናና የቅድስና አስተምህሮን በተመለከተ ከፍተኛው ደረጃ የባሕታውያንና የደናግል ሕይወት ነው፤ እነርሱ በዚህ ዓለም የመላእክትን ሕይወት ይኖራሉና፡፡ ሌሎቹ የቤተ ክርስቲያን አባላት ደግሞ እነርሱን ይከተሏቸው፡፡ ወንድሞች ሆይ፣ ለእናንተ ታላቅ የክብር አክሊል ተዘጋጅቶላችኋልና፤ ስለዚህም ታላቁን ክብር ለተራ ደስታ አትስጡት፡፡ ሐዋርያው "ወይም ስለ አንድ መብል በኩርነቱን እንደ ሸጠ እንደ ዔሳው ለዚህ ዓለም የሚመች ሰው እንዳይሆን ተጠንቀቁ" ያለውን ቃል አድምጡ፡፡ ዕብ. 12፡16 ስለ ንጽሕና ሕይወታችሁና ብጽእታችሁ ከመላእክት የንጽሕና መጽሐፍ ውስጥ የተጻፋችሁ ሆናችሁ ሳለ በአመንዝራነት ምክንያት ከዚህ መጽሐፈ መላእክት እንዳትደመሰሱ ተጠንቀቁ፡፡ እንደ ገናም ንጽሕናህን ስትጠብቅ (ጠብቀህ ስትገኝ) ደግሞ በጋብቻ በሚኖሩት ላይ ራስህን ከፍ እንዳታደርግ ተጠንቀቅ፡፡ ሐዋርያው "መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን" እንዳለ፡፡ ዕብ. 13፡4 ንጽሕናህን የጠበቅህ አንተ የተገኘኸው ከጋብቻ አይደለምን? አንተ ወርቅ ስላለህ ከዚህ የተነሣ ብርን አትንቀፍ፡፡ ነገር ግን በጋብቻ ያሉ ጋብቻን በአግባቡ ይጠቀሙበት፡፡ ለተድላና ለደስታ፣ ለቅምጥልነትና ለፍትወት ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለቅድስና ያውሉት፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 3፤ በእንተ ጥምቀት፣ ቁ. 24-25)

- "የድንግልና ሕይወት የመላእክት ሕይወት ነው፤ ክብሩም እንደ መላእክት ነው፡፡ በድንግልና የሚኖሩ የሚያገኙትን የክብር ዘውድ ያስቡ፡፡ ባሕታውያንም የድንግልናን ክብር ያስቡ፤ እኛ ሰዎች በድንግልና ከመኖር ጸጋ አልተከለከልንምና፡፡ . . . የድንግልናን ሕይወት የክብር አክሊል በተመለከተ የማናውቅ እንሁን፤ ክብሩ መልአካዊ፣ ታላቅነቱም ከሰው በላይ ነውና፡፡ እንደ ፀሐይ ያበራ ዘንድ ስላለው ሰውነታችን ጠንቃቆች እንሁን፤ ለአጭርና መናኛ ለሆነ ደስታ ስንል እንዲህ ያለውን በእጅጉ የከበረውን ሰውነታችንን አናርክሰው፡፡ ኃጢአቱ አጭርና ቅጽበታዊ ሲሆን ነውሩና ኃፍረቱ ግን ለብዙ ዓመታትና ለዘለዓለም ነውና፡፡ በድንግልና ሕይወት የሚኖሩ ሰዎች በምድር ላይ የሚራመዱ መላእክት ናቸው፡፡ ደናግል ከቅድስት ድንግል ማርያም የራሳቸው የሆነ ዕድል ፈንታ አላቸው፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 6፣ ስለ እግዚአብሔር አንድነት፣ ቁ. 35፣ ትምህርት 12፣ በእንተ ቃል ሥጋ ሆነ፣ ቁ. 33-34)

- "ዮሴፍን ከባርነትና ከእስራት ወደ መንግሥትነት ከፍ ያደረገው እርሱ እናንተንም ከመከራዎቻችሁ አውጥቶ ወደ መንግሥት ሰማያት ያገባችኋልና፡፡ ብቻ እናንተ ጽኑ፤ ተግታችሁ ሥሩ፤ በጸሐቀ ልብ ሆናችሁ ተጋደሉ፤ ምንም ምን ከድካማችሁ የሚረሳና የሚዘነጋ አንዳች ነገር አይኖርምና፡፡ እያንዳንዱ ጸሎታችሁ፣ የምትዘምሩት እያንዳንዱ መዝሙር ሁሉ ይመዘገባል፤ እያንዳንዱ ምጽዋት፣ እያንዳንዱ ጾም፣ በአግባቡ የተኖረ እያንዳንዱ ጋብቻ፣ ስለ እግዚአብሔር ተብሎ የተጠበቀ ንጽሕና ሁሉ ይመዘገባል፡፡ ሆኖም ከመዛግብት መካከል የመጀመሪያው አክሊል (ክብር) ለድንግልናና ለንጽሕና ነው፤ በዚህ ሕይወት የኖራችሁም እንደ መላእክት ታበራላችሁ፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 16፣ በእንተ መንፈስ ቅዱስ፣ ቁ. 22)

- ". . . ስለዚህ ጻድቃን እንሆን ዘንድ፣ 'አዲሱን ሰው እንለብሰው ዘንድ' እነዚህን ሁሉ እውቀን እንጣላቸው፡፡ እሮጌ የሆነ ምንም ነገር፣ እፍአዊ የሆነ ምንም ነገር፣ የተበላሸ የሆነ አንዳችም ነገር እንያዝ፡፡ የመልካም ምግባር ሕይወት አድካሚ አይደለም፣ ገንዘብ ለማድረግም አስቸጋሪ አይደለም፡፡ በበረሓዎችና በተራራዎች የሚኖሩትን አታዩዋቸውምን? እነርሱ ቤትን፣ ሚስትን፣ ልጆችን እና የዚህን ዓለም ክብርና ደስታ ሁሉ ትተው ራሳቸውን ከዓለም አርቀው፣ በላያቸው ላይ ማቅ ለብሰው፣ በዓመድ ላይ እየተኙ፣ በአንገታቸው ዙሪያ ሠንሰለት አድርገው በጠባብ በአታት ውስጥ እየተጋደሉ ይኖራሉና፡፡ በዚህም ብቻ አያበቁም፣ ራሳቸውን በአጽዋማትና ሁል ጊዜ በሆነ ረሃብ ይቀጣሉና፡፡ አሁን እንደ እነርሱ አድርጉ ብላችሁ ሁላችሁም ከዚህ መሸሽና መሄድ አትጀምሩም ይሆን? ይህ የማይቻል ነው አትሉም ይሆን? ሕይወታችሁ እንዲህ ቢሆን ኖሮ እወድ የነበረ ቢሆንም እንኳ እኔ እንዲህ አድርጉ ብዬ ሕግ አላወጣላችሁም፡፡

  "አሁን ለእናንተ የምላችሁ ግን ሰውነታችሁን በአግባቡ አኑሩት፣ በነጻነት በዓለም ኑሩ፣ ቤተሰባችሁን ተንከባከቡ ጠብቁ፣ ምግባችሁንና መጠጣችሁን በነጻነት ሆናችሁ ግን ለክርስቲያን እንደሚገባ ብቻ ተጠቀሙ፡፡ ነገር ግን በማንኛውም ሁኔታና ቦታ ከመጠን ያለፈ ነገርን አስወግዱ፤ የኃጢአት ምንጩና መገኛው እርሱ ነውና፡፡ ማንኛውም ነገር ቢሆን፣ ምንም ይሁን ምን፣ ከመጠን ያለፈ ከሆነ ኃጢአት ይሆናል፡፡ ስለዚህም ከመጠን በላይ የሚሆን ነገር ሁሉ ኃጢአት ነውና ከዚህ ተጠበቁ፡፡"

  (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ኤፌሶን፣ ክፍለ ትምህርት 13)

- "ደናግል ሰማዕታት ናቸው፡፡" (ቅዱስ አምብሮስ፣ ትርጓሜ መዝሙረ ዳዊት)

- "ድንግልና የቤተ ክርስቲያን አበባና ጽጌረዳ ነው፡፡" (ቅዱስ ቆጵርያኖስ፣ ትምህርት በእንተ ድንግልና)

በምንኩስና የገቡትን ቃል መጠበቅ እንዲገባም ቅዱስ ባስልዮስ እንዲህ ይላል፡-

- "በምንኩስና ለመኖር ቃል ከገባና ምንኩስናን ከተቀበለ በኋላ ምንኩስናውን የሚተው ሰው እንደ ሕግ አፍራሽ የሚቆጠር ነው፡፡ ምእመናንም ቅዱስ ጳውሎስ "በዚህ መልእክት ለተላከ ቃላችን የማይታዘዝ ማንም ቢኖር ይህን ተመልከቱት፣ ያፍርም ዘንድ ከእርሱ ጋር አትተባበሩ" ብሎ በተናገረው መሠረት እንደዚህ ካለው ሰው ጋር ምንም ዓይነት ኅብረትና ግንኙነት ሊኖራቸው አይገባም። 2 ተሰ. 3፥14" (ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ)

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ገዳማዊ ሕይወትንና ምንኵስናን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስና አባቶቻችን ቅዱሳን ሊቃውንት የሚያስተምሩትን ትምህርት በሰፊው ተመለከትን፡፡ አባቶቻችን ምንኵስናና ድንግልናን የገለጹት በሚገርም ሁኔታ ነው፡፡ ይህን ሕይወት "ለክርስቶስ የሚቀርብ መሥዋዕት"፣ "የመላእክት አኗኗር"፣ " መንገዱ ሻካራና አስቸጋሪ ቢሆንም እጅግ የበለጠ አስደናቂና ታላቅ ነገርን ማግኛና ፍጹም የሆነውን ፍሬ - ባለ መቶ - ማፍሪያ መንገድ"፣ "ከመላእክት መዓርግ መደመር (አንድ መሆን)"፣ "የመላእክት ሕይወት"፣ "ክብሩ እንደ መላእክት የሆነ"፣ "ልዩ የክብር ዘውድ የሚገኝበት"፣ "ክብሩ መልአካዊ፣ ታላቅነቱም ከሰው በላይ የሆነ"፣ "በምድር ላይ የሚራመዱ መላእክት"፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም የራሳቸው የሆነ ዕድል ፈንታ ያላቸው" እያሉ ነው ሊገልጹት የሞከሩት፡፡

የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርትና እምነትም ይኸው ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ያለው ግን ሉተር "አዲስ መገለጥና እይታ" ብሎ አበላሽቶ የፈጠረውና ለተሐድሶ ልጆቹ ያወረሰው "አዲስ አረዳድ" የሰውን ልጆች የመዳንና የአጠቃላይ የመንፈሳዊ ሕይወት አካሄድ በተመለከተ ባእድ የሆነ የፈጠራና የልብ ወለድ መንገድ ነው፡፡ ተሐድሶዎች በገዳማዊ ሕይወትና በምንኵስና ዙሪያ ያነሷቸው የተለያዩ ጉዳዮችም እንዲሁ ካለማወቅና ካለማስተዋል ወይም ደግሞ ከጭፍን ጥላቻ የተወለዱ እንጂ አንዳችም የመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ የሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ድጋፍና መሠረት የሌላቸው መሆኑ በዚህ ምዕራፍ ከቀረቡት ማስረጃዎች ማንም ሰው በማያወላውል ሁኔታ መረዳት የሚችለው እውነታ ነው፡፡ ስለሆነም ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው እና በአበው ትምህርትና ሕይወት የተመሰከረ ከሆነው መስመር ወጥተው የሉተርን የመሰለ "እንግዳ አረዳድ" ይዘን እንጓኝለን የሚሉት የተሐድሶዎች ነገር መሠረት የለሽና ልብ ወለዳዊ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስና አበው ሊቃውንት ተባብረው ይመሰክራሉ፡፡

# ክፍል አምስት

## ስሞቱ ወገኖች የሚደረግ ጸሎት (ጸሎተ ፍትሐት) እና ተዝካርና ዝክር

## ምዕራፍ ስምንት

## ስሞቱ ክርስቲያኖች የሚደረግ ጸሎት (ጸሎተ ፍትሐት) እና ተዝካርና ዝክር

### 8.1 ጸሎተ ፍትሐት

#### 8.1.1 በጸሎተ ፍትሐት ላይ የተሐድሶዎች ትምህርት

ተሐድሶ መናፍቃን ከሚቃወሟቸው ነገሮች ሌላው ከዚህ ዓለም ሕይወት ወደዚያኛው ዓለም ሕይወት የሄዱ ወገኖችን በጸሎት ማሰብን ነው፡፡ ይህን ለሙታን የሚደረገውን ጸሎት "አጋንንታዊ ትምህርት" ነው ይሉታል፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን አባባሎቻቸውን እንመልከት፡-

- "የሙታንን ነፍሳት (የሞቱ ቅዱሳንን እና ሌሎች መናፍስትን) በጸሎት መጥራት የተከለከለ አጋንንታዊ ትምህርት ነው፡፡" (ሙሬ ቁ. 36፣ ገጽ 31)
- "በሞተበት ዕለት ጸሎተ ፍትሐት ቢደገምለት፣ ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ የተዝካር ድግስ በስሙ ተደግሶ ለበላተኛ ቢሰጥለት ኃጢ ይማራል ተብሎ ተስፋ መደረጉ . . ." (ፍኖተ ብርሃን፣ መጋቢት 2002፣ ገጽ 18)
- "የሙታንን ነፍሳት መሳብ መናፍስትንም መጥራት፣ መጠንቆልና ማሟረትም ለችግሮች መፍትሔ ያመጣል በማለት ሊያታልሉን አይገባም፡፡" (ሙሬ ቁ. 36፣ ገጽ 31)
  - እጭር ማስገንዘቢያ፡- መናፍስትን ሲሰቡ የነበሩት ራሳቸው ናቸው፡፡ ለዚህም ራሱን በይፋ የገለጠውና ተሐድሶነቱን በራሱ አንደበት የተናገረው "ትሪኒቲ" በተባለው የፕሮቴስታንት መጽሔት ላይ ሻሸ ጠምጥሞ የወጣው "መሪጌታ" ሙሴ ነበርኩ ባዩ አሳዛኝ ሰውዬ ምን ዓይነት መተትና አስነዋሪ ተግባር ይፈጽም እንደ ነበር ራሱ ተናግሯል፡፡ ይህም በ "ትሪኒቲ" መጽሔት ቁጥር 9/2003 ዓ. ም. ላይ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ራሳቸው ሲፈጽሙት የነበረውን አስነዋሪ ነገርና የራሳቸውን የግል የሕይወት ችግር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ችግር አስመስለው ለማቅረብ መሞከራቸው "የሌባ ዓይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ" እንደሚባለው ዓይነት ከመሆን ውጭ ሌላ የሚያተርፍላቸው ነገር የለም፡፡

- "ጥያቄ፡- በ2/1/1995 በወጣው 2ኛ ዓመት ቁጥር 64 አዲስ ዜና ጋዜጣ፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም በኢትዮጵያ ተደጋግሞ የተከሠተውን የረሃብ መንሥኤ ለመጠቆም የገለጹትን ሃሳብ ሳነብ ሊገባኝ ያልቻለ አንድ ነጥብ አጋጥሞኛል፡፡ እንዲህ የሚል ነው፡- "ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ሙታን ሳይቀሩ ከቋሚዎች ግብር ይጠይቃሉ፡፡ ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ግዴታዎች ገበሬውን ብዙ ወጪ ያስወጡታል" ብለዋል፡፡ ሙታን ቋሚዎችን የሚያስገብሩበት ሁኔታ መኖሩን አላውቅም፣ እንዴት ነው? ሲሉ ጠይቀዋል" ይልና መልስ ነው ያሉትን ሃሳብ ደግሞ እንደሚከተለው ሰጥተዋል፡፡ (ሥራ ቁ. 27፣ ገጽ 17)

- "መልስ፡- በሀገራችን በማንኛውም ወር ውስጥ የሚገኙትን 30 ዕለታት ቢያንስ ሁለትና ሦስት ቅዱሳን የሚታሰቡባቸው በዓላት ናቸው፡፡ ስንክሳርን የሚያነብ ሰው ደግሞ ከዚህ ቁጥር በላይ የሆኑ ቅዱሳን ናቸው የሚባሉ ስሞችን በእያንዳንዱ ቀን ሊያነብ ይችላል፡፡ . . . አዳናቂዎቻቸው በየገድላቸው በጻፉላቸው ቃል ኪዳን ለመሸፈን ሲሉ ኢትዮጵያውያን ምእመናን፡-

    1) የሚያደንቋቸውና የሚወዷቸው ቅዱሳን በዓላቸው በሚታሰቡባቸው ቀናት ሥራ የመሥራት መብታቸውን ለቅዱሳኑ ክብር ሲሉ አይጠቀሙባቸውም፣ ሥራ ፈትተው በመዋል ዕለታትን ለቅዱሳን ይገብራሉ ማለት ነው፡፡

    2) ከቅዱሳኑ ክብርና በረከት ለመሳተፍ ሲሉ ሥራ ፈትቶ ከመዋል በተጨማሪ ምእመናን እንደየዓቅማቸው የቅዱሳኑን ዝክር በየበዓላቸው ቀን በማዘከር ካህናት፣ ጎረቤትን፣ ቤተ ዘመድን ከዚያም ነዳያንን ይጋብዛሉ፡፡

    3) በአንድ ወይም በሁለት ቅዱሳን ስም በሚደገስበት ማኅበር ይሳተፋሉ፣ ወይም ሁለቴ ደግሰው ማኅበርተኞቻቸውን፣ ካህናትንና ወዳጅ ዘመዶቻቸውን ያበላሉ፣ ያጠጣሉ፣ ለነዳያንም ያቀምሳሉ፡፡ . . .

- "የሞቱ ወዳጆቻቸውን ለማጽደቅ ሲሉ ዘመዶቻቸው በሞቱበት ዕለት፣ ከዚያም ቀጥሎ በ3ኛ፣ በ7ኛ፣ በ12ኛ፣ በ30ኛ፣ በ40ኛ በ80ኛ፣ በ180ኛ፣ በ365ኛ መታሰቢያ ቀናቸው፣ ከዚያም እስከ 7ኛ ዓመት ድረስ በየዓመቱ በማስፈታት ጸበል ጸድቅ በማዘጋጀት ካህናትን፣ ወዳጅ ዘመድን ይጋብዛሉ፣ ለነዳያንም ያቀምሳሉ፡፡ . . . ይህን ለማመልከት "በኢትዮጵያ ሙታን ሳይቀሩ ከቋሚዎች ግብር ይጠይቃሉ" በማለት ፕሮፌሰር የገለጹ ይመስለናል፡፡"

(ሥራ ቁ. 27፣ ገጽ 17)

ተሐድሶዎች በጸሎተ ፍትሐት ላይ የሚያነሷቸው ተቃውሞዎችና ዘለፋዎች ይህን ይመስላሉ፡፡ ከዚህ በመቀጠል ይህን ጉዳይ በመጽሐፍ ቅዱስ እና በሊቃውንት አባቶቻችን ትምህርት እንመዝነዋለን፡፡ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን ከልጆቿ መካከል የዚህ ዓለም ሕይወታቸውን ጨርሰው ወደ ፈጣሪያቸው የሚሄዱትን ሲሞቱ (ሲያርፉ) ምንም ነገር እንዳልተፈጠረ ያህል እንዲሁ ዝም ብላ አትተዋቸውም፣ ጸሎት አድርጋ በክብር ትሸኛቸዋለች እንጂ፡፡ ለሞቱ ወገኖች ጸሎት (ጸሎተ ፍትሐት) የሚደረግባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

## 8.1.2 <u>ጸሎተ ፍትሐት የሚደረግባቸው መሠረታዊ ምክንያቶች</u>

### 1. እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ ስለ ሆነ

ከዚህ ዓለም ድካም ላረፉ ወገኖቻችን ጸሎት የሚደረግበት አንዱ ምክንያት እግዚአብሔር በምሕረቱ እንዲጎበኛቸውና ከሰው ስህተት አይጠፋምና በደላቸውን ይቅር ብሎ በብሩህ ገጽ እንዲቀበላቸው የእርሱን ምሕረት ደጅ ለመጽናት ነው፡፡ በመጀመሪያ እነዚህ ያረፉ ወገኖቻችን የቤተ ክርስቲያን ሕያዋን አካላት እንደ መሆናቸው ለእነዚህ በአንድ መንፈስ አንድ አካላት ለሆንን ወገኖቻችን መጸለይና ምሕረትን መለመን የሚገባ እንጂ የማይገባ አይደለም፡፡ የማይገባ የሚሆነው ይህን መቃወም ነው፡፡ ተሐድሶዎች በክህደታቸው ራሳቸውን ከቤተ ክርስቲያን አካልነት ቆርጠው የጣሉ ከመሆናቸው የተነሣ

የራሳቸው መለየት ሳያንስ የክርስቶስን አካላት የሚያጳክሙ መሆናቸው አሳዛኝ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ምሕረት ለሌላው ወገናችን መጠየቅ ለራሳችን ከመጠየቅ ባላነሰ፣ እንዲያውም በበለጠ ያስመሰግናል እንጂ የሚያስወቅስ አንዳችም ነገር የለውም፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ለራሳቸው መልካም ነገርን ከለመኑ ሰዎች በበለጠ የተመሰገኑት ስለ ሌላው ሰው፣ ስለ ወገናቸው ሲሉ እግዚአብሔርን የለመኑት ናቸው፡፡ ሙሴን በእጅጉ ያስመሰገነው እግዚአብሔር "አሁንም ቍጣዬ እንዲቃጠልባቸው እንዳጠፋቸውም ተወኝ፤ አንተንም ለታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ" ባለው ጊዜ "አሁን ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው፤ ያለዚያ ግን ከጻፍኸው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ" በማለት ከራሱ ክብርና ደኅንነት ይልቅ የሕዝቡን ደኅንነትና ምሕረት በማስበለጡና በማስቀደሙ ነበር፡፡ ዘጸ. 32፥10፥32 ታዲያ እንዲህ "ሕዝቡን ይቅር በላቸው፤ አለዚያ ግን ከሕይወት መጽሐፍ ደምስሰኝ" እስኪል ደርሶ ለሌሎች ምሕረትን ከለመነ እንደ እርሱ ባናደርግ እንኳ በዓቅማችን ማራቸው ብሎ መጸለይ ኃጢአትንቱና ጥፋትነቱ ምን ላይ ይሆን?

ቅዱስ ጳውሎስም ስለ ወገኖቹ ስለ እስራኤላውያን በክርስቶስ አለማመንና ከድኅነት ውጭ ስለ መሆናቸው ብዙ ያዝንና ይጨነቅ ነበር፡፡ "ብዙ ኀዘን የማያቋርጥም ሡንቀት በልቤ አለብኝ ስል በክርስቶስ ሆኜ እውነትን እናገራለሁ፤ አልዋሽምም፤ ሕሊናዬም በመንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል። በሥጋ ዘመዶቼ ስለ ሆኑ ስለ ወንድሞቼ ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንድሆን እጸልይ ነበርና" ብሎ ሐዋርያው እንደ ገለጸው፡፡ ሮሜ 9፥1-3 ይህን ያህል ራሳቸውን ስለ ሌሎች መዳን "እኔ የተረገምሁ ልሁን" እስከ ማለት ደርሰው ከጸለዩና ከተጨነቁ እኛ ስለ ሌሎች መዳን ማሰብና መጸለይ የለብንምን?

እዚህ ላይ እነዚህ አባቶች (ሙሴ፤ ቅዱስ ጳውሎስ) የጸለዩት በዚህ ዓለም በሕይወተ ሥጋ ለነበሩ ሰዎች ነው፤ አሁን የተያዘው ጉዳይ ግን ከዚህ ዓለም በሞት ስለ ሄዱ ሰዎች ጉዳይ ነው የሚል ሐሳብ ይነሣ ይሆናል፡፡ አሁንም ግን በመጀመሪያ ደረጃ ከዚህ ዓለም በሞት የተወሰዱ ሰዎች ምን ጊዜም የአንዲቷ ቤተ ክርስቲያን ሕያዋን ልጆችና የክርስቶስ አካላት ናቸው እንጂ ከዚያ አካልነታቸው የሚቆርጣቸውና የሚለያቸው ምንም ነገር የሌለ መሆኑን በድጋሚ ማስታወስ ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሕይወተ ሥጋ የሌሉ (ሙታን) ከእግዚአብሔር ምሕረትና ቸርነት ውጭ አይደሉም፤ መጽሐፍ ቅዱስ *"ቸርነቱን በሕያዋንና በሙታን ላይ አላተወምና"* ይላልና፡፡ ሩት 2፥20

የያዕቆብ የበኩር ልጅ የነበረው ሮቤል ወደ አባቱ አልጋ ወጥቶ እንደ ነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ እንዲህ ብሎ፦ "እስራኤልም በዚያች አገር በተቀመጠ ጊዜ ሮቤል ሄደ፤ የአባቱንም ቁባት ባላን ተገናኛት፤ እስራኤልም ሰማ።" ዘፍ. 35፥22 በሕይወቱ መጨረሻ ላይ አባቱ ያዕቆብ ልጆቹን በተመለከተ እያንዳንዳቸውን ግብራቸውንና ወደ ፊት የሚያገኛቸውን ሲናገር እንዲህ ያለው ለዚህ ነበር፦ "ሮቤል፤ አንተ በኵር ልጄና ኃይሌ፣ የጕብዝናዬም መጀመሪያ ነህ፤ የክብር አለቃና የኃይል አለቃ። እንደ ውኃ የምትዋልል ነህ፤ አለቅነት ለአንተ አይሁን፤ ወደ አባትህ መኝታ ወጥተሃልና፤ አረከስኸውም፤ ወደ አልጋዬም ወጣ።" ዘፍ. 49፥3-4

ከዚህም የተነሣ ሮቤል ከሞተ ቢያንስ ከአንድ መቶ ዓመት በላይ ከሆነው በኋላ እስራኤላውያን ከግብፅ ሲወጡ የአበውን ዓጽምም አብረው ይዘው ስለ ነበር በኃጢአቱ ምክንያት ከሌሎቹ አበው አጽም ተለይቶ የሮቤል ዓጽም ጠቁሮ ነበር፡፡ ለዚህ ነበር ሮቤል ከሞተ ከብዙ ዘመን በኋላ ሙሴ እንዲህ ብሎ የጸለየለት፦

> "ይሕየወኒ ሮቤል ቀልዔዩ ወኢይሙተኒ - ወዳጄ ሮቤል በሕይወት ይኑርልኝ፣ አይሙትብኝ"
> ዘዳ. 33፥6

ለሞቱ ሰዎች ጸሎት ማድረግ ተገቢ ባይሆን ኖሮ ሮቤል ከሞተ ብዙ ዘመናት (ከመቶ ዓመት በላይ) ከሆነው በኋላ ሙሴ "ወዳጄ ሮቤል በሕይወት ይኑርልኝ፣ አይሙትብኝ" ብሎ ለምን ይጸልይለት ነበር? እስራኤላውያን ከግብጽ ባርነት የወጡትና ወደ ከነዓን ጉዞ የጀመሩት ወደ ግብጽ የወረዱት አባቶች ከሞቱ ቢያንስ ቢያንስ ከአንድ መቶ ዓመት በኋላ ነው፡፡ ታዲያ ከሞተ ከአንድ መቶ ዓመት በላይ ለሆነው ለሮቤል ሊቀ ነቢያት ሙሴ "በሕይወት ይኑርልኝ፣ አይሙትብኝ" ብሎ ከጸለየለትና ይህም ጸሎት በታላቁ መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ያለ ከሆነ እኛ ከሞቱ ገና ብዙ ዓመታት ላላስቆጠሩ ክርስቲያን ወገኖቻችን ጸሎት ማድረጋችን ስህተትነቱ ምኑ ላይ ነው? ወደ አባቱ አልጋ ወጥቶ ለነበረው ለሮቤል ሙሴ ጸሎት ያደረገለት ከሆነ በዐበይትም ሆነ በንዑሳን ኃጢአቶች ተሰነካክለው ለሞቱ ወገኖቻችን፣ እንደዚያ ባይሆንም ደግሞ ከሰው ስህተት አይጠፋምና እርሱ ባወቀ ይቅር እንዲላቸው ላረፉ ወገኖቻችን ወደ እግዚአብሔር ጸሎት ማድረጋችን መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ በሙሉ በሚያምኑ ሰዎች ዘንድ በአንዳችም መስፈሪያ ስህተትነት የለውም፡፡ ለዚህ ነው "ሞት በአቤል፣ ፍትሐት በሮቤል ተጀመረ" የሚባለው፡፡ ጸሎተ ፍትሐትን ለመጀመሪያ ጊዜ ያደረገው ሊቀ ነቢያት ሙሴ ነውና፡፡ ስለሆነም ለሞቱ ወገኖቻችን እንኳን ባረፉበት ቀን፣ በሰባተኛው ቀን፣ በአርባኛው ቀንና በዓመት ይቅርና ከዚያም በላይ ሁል ጊዜ ብናስባቸውም የተገባ ነገር እንጂ ያልተገባ ነገር ሊሆን አይችልም፡፡

ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ይህን ሙሴ ለሮቤል የጸለየለትን ጸሎት በተመለከተ እንዲህ ይላል፡-

> . . . ከሌዊ ወገን የተወለደ ካህን እንደ ሆነ፣ በክህናት ቃልም ኃጢአት እንዲሠረይ ዐውቆ አሥራ ሁለቱን ነገድ ሊባርክ በወደደ ጊዜ ሮቤልን አሻዋለሁ፣ ይዳንልኝ እንጂ አይሙትብኝ ብሎ እነሆ ሙሴ ነገሩን አስረዳ፡፡ ከሞተ ከሁለት መቶ ሦስት ዓመት በኋላ እንደ ምን ይዳንልኝ አለ? ትንሣኤ ለሁሉ እንዲደረግ ኃጥአንን ሁለተኛ ሞት ይኸውም በፍርድ ቀን ፊት ማጣት እንዲያገኛቸው ዐውቆ ኋላ ከምትመጣው ፍዳ ሊያድነው ወደ ትንሣኤን ለማስረዳት ሮቤልን እሻዋለሁ ይዳንልኝ አይሙትብኝ አለ እንጂ፡፡ ይኸውም እርሱ እንዲነሣ፣ ሞት ነፍስም እንዳያገኘው ያስረዳል፣ በፍርድ ቀን ፊት በማጣት ሁለተኛ ሞት የዘላለም ኩነኔም እንዳያገኘው ይህን ተናገረ፡፡ የሙሴ ፈቃዱ ሮቤልን ከፍዳ ለማዳን፣ ትንሣኤን ለማስረዳት ባይሆንስ ሮቤል ይዳንልኝ አይሙትብኝ ባላለም ነበር፡፡ (ቅዱስ ኤጲፋንዮስ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ቁ. 20-23)

እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶን በሐዋርያዊ ተግባር ላይ ሳለ በመልካም ሳገለገለውና በኋላ ግን በሞት ለተወሰደው ሄኔሲፎሩ ለተባለው ክርስቲያን እንዲህ ሲል ጸልዮለታል፡-

> ጌታ ለሄኔሲፎሩ ቤት ሰዎች ምሕረትን ይስጥ፣ ብዙ ጊዜ አሳርፎኛልና፤ በሰንሰለቴም አላፈረበትም፣ ነገር ግን በሮሜ ባደረ ጊዜ ፈልጎ ፈልጎ አገኘኝ፤ <u>በዚያን ቀን ከጌታ ምሕረትን እንዲያገኝ ጌታ ይስጠው</u>፤ በኤፌሶንም እንዴት እንዳገለገለኝ አንተ በደንና ታውቃለህ፡፡ 2 ጢሞ. 1፡16-18

ቅዱስ ጳውሎስ ሄኔሲፎሩ በሮሜ ታስሮ ሳለ፣ እንዲሁም በኤፌሶን ያገለገለው መሆኑን ይገልጽና *"ጌታ ለሄኔሲፎሩ ቤተ ሰዎች ምሕረትን ይስጥ"* ሲል ለመነ፡፡ ሄኔሲፎሩ ያልሞተ ቢሆን ኖሮ ከቤተ ሰዎቹ ለይቶ ለእርሱ ለብቻው *"በዚያን ቀን ከጌታ ምሕረትን እንዲያገኝ ጌታ ይስጠው"* ብሎ ለምን ጸለየለት? *"<u>በዚያን ቀን ከጌታ ምሕረትን እንዲያገኝ ጌታ ይስጠው</u>"* ያለው ቀንስ የቱ ነው? ብንል በዳግም ምጽአቱ በፍርድ ቀን እግዚአብሔር ምሕረትን እንዲሰጠው በሕይወት ሥጋ ለሌለው ለሄኔሲፎሩ ቅዱስ ጳውሎስ ጸለየለት፡፡

ተሐድሶዎች ጸሎተ ፍትሐትን ሲነቅፉ፡- "በሞተበት ዕለት ጸሎተ ፍትሐት ቢደገምለት፣ ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ የተዝካር ድግስ በስሙ ተደግሶ ለበላተኛ ቢሰጥለት <u>ሟቹ ይማራል ተብሎ ተስፋ መደረጉ</u>" ይላሉ፡፡ (ጥንተ ብርሃን፣ መጋቢት 2002፣ ገጽ 18) ጸሎት የሚደረገው ምሕረትን ሰጪ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር እንደ መሆኑ ጸሎቱን የሚቀበለው እግዚአብሔር የሚጸለየውን ጸሎት እንዴት እንደሚቀበለው የሚያውቀው እርሱ ብቻ ነው፡፡ እኛ እንለምናለን እንጂ ውሳኔ ሰጪዎች አይደለንም፡፡

በጸሎተ ፍትሐትም እንዲሁ ነው እንጂ "እንዲህ ቢጸለይለት ይማራል፣ ገነት ይገባል" የሚል ማረጋገጫ የሚሰጥ አካል የለም፣ ሊኖርም አይችልም። ስለሆነም "በሞተበት ዕለት ጸሎተ ፍትሐት ቢደገምለት፣ ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ የተዘከር ድግስ በስሙ ተደግሶ ለበላተኛ ቢሰጥለት ሟቹ ይማራል መባሉ" የሚለው አባባል መሠረት ቢስና ሐሰት ነው። ሆኖም ጸሎት የሚደረገው እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ መሆኑን በማመን ስለሆነ ጸሎታችንን ተቀብሎ ይምረዋል ብለን ተስፋ ግን እናደርጋለን። ተስፋ ደግሞ ከሶስቱ መሠረታዊ የክርስትና ነገሮች (እምነት፣ ተስፋ እና ፍቅር) መካከል አንዱ እንጂ ሊነቀፍ የሚችል ነገር አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ "አቤቱ አንተን ተስፋ እንዳደረግን መጠን ምሕረትህ በላያችን ትሁን" ተብሏልና። መዝ. 33፡22 ፤ 122፡1-2 እንዲሁም "ተስፋችን አያሳፍርም" ተብሏልና ሮሜ 5፡5

## 2. የቤተ ክርስቲያን ባሕርይዋና ማንነቷ የሚገለጥበት ስለሆነ

ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋዌው ሞትንና መፍረስ መበስበስን አጥፍቶ የመዳንን መንገድ በተግባር ፈጽሞና አሳይቶ ይህን ማዳኑን የሚያምኑና የሚድኑ ወገኖችን ወደ እርሱ አንድነት ሰብስቧቸዋል። በእርሱ ራስነት እነርሱን (ምእመናንን) አካሎቹ አድርጓቸዋል። ይህ በእርሱ መድኃኒትነት ያመኑና የሚያምኑ የአማንያን አንድነት ቤተ ክርስቲያን ትባላለች። በክርስቶስ አማካይነት የሰው ልጅ ኃጢአት ካመጣው መበታተንና መለያየት ነጻ ወጥቶ አንድነትን አግኝቷል፤ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ አንድ አካል ሆነው ይዋሓዳሉና። ከክርስቶስ ጋር ከመዋሓዳቸውና አንድ አካል ከመሆናቸው የተነሣም እርስ በእርሳቸው ፍጹም በሆነ ፍቅር አንድ ሆነው ይዋሓዳሉ። በዚህ በክርስቶስ በሆነው ተዋሕዶም አኃዛዊ ልዩነቶችና ድንበሮች ሁሉ ይጠፋሉ። ከሥጋዊ ልደት ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ ልዩነቶች - የጊዜ፣ የቦታ፣ የዘር፣ የቋንቋ ወዘተ ልዩነቶች ሁሉ ሁሉም በክርስቶስ ባገኘነው መንፈሳዊ ልደት ይጠፉና አንድ አካልና አንድ ወገን ይሆናሉ። ሐዋርያው "አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን፣ ባሪያዎችም ብንሆን፣ ጨዋዎችም ብንሆን፣ እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል፤ ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል" በማለት እንደ ገለጸው ልዩነት ጠፍቶ አንድነት ይሰፍናል። 1 ቆሮ. 12፡13

አንድ ሰው ክርስቲያን ሲሆን የክርስቶስ አካል ሆኖ ይሠራል፤ የዚህ የክርስቶስ አካል የሆነችው የአንዲት ጉባኤ አንድ የሰውነት ክፍል ይሆናል። ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር የሚኖረው ግንኙነትም ልክ አንዱ የሰውነት ክፍል ከሌላው የሰውነት ክፍል ጋር እንዳለው ግንኙነት ዓይነት ይሆናል። ከክርስቶስ ጋር ያለው ግንኙነት ደግሞ አንድ የሰውነት ክፍል ከራስ ጋር እንዳለው ግንኙነት ነው። በአጠቃላይ አንድ ምእመን በእምነትና በምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ሆኖ ሲሠራ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ወደ ገለጻት ቤተ ክርስቲያን ይገባል፦

> ነገር ግን ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል፤ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም፣ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፣ በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር፤ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፤ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች . . . ደርሳችኋል። ዕብ. 12፡22-23

እነዚህ የአንዲቷ ቤተ ክርስቲያን አካላት የሆኑት አእላፋት መላእክት፣ የበኵራት ማኅበር፣ የጻድቃን መንፈሶች ሁሉም በአንድ ዘመንና ቦታ የኖሩ አልነበሩም። ከሰዎች መላእክት ይቀድማሉ፣ ከሰዎች ወገን ደግሞ አስቀድሞ አበው፣ ከዚያም ነቢያት፣ በመቀጠልም ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን እያሉ የመጡ ናቸው። ይህ ሂደትም ጊዜ ለዘለዓለማዊነት ቦታውን እስከሚለቅ ድረስ ይቀጥላል። ሆኖም ይህ ሁሉ የጊዜና የቦታ ልዩነት በቤተ ክርስቲያን አንድነት ላይ ለውጥ አያመጣም። በተለያየ ዘመንና ቦታ የኖሩትና ዛሬም ያሉት፣ ወደ ፊትም እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ በየዘመናቱ የሚነሡት ሁሉም የአንድ ክርስቶስ አካላት፣ የአንዲቷ ቤተ ክርስቲያን አካላት ናቸው።

ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በራእዩ ከመሠዊያው በታች ያያቸው ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱት የሰማዕታት ነፍሳት "እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቍጥር እስኪፈጸም ድረስ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸው" የሚል ቃልን የሰማው ለዚህ ነው፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ጻድቃንና ሰማዕታት በዚህ ዓለም የሚኖሩበትና በጊዜ ሂደት የሚገለጡበት ዘመን የተለያየ ቢሆንም የቤተ ክርስቲያን ምልዓት የሚሆነው ግን በዘመን ቀድመው የተነሡትም ሆኑ በኋላ የሚነሡት ተጋድሏቸውን ፈጽመው በአንድነት ሲሰባሰቡ ስለሆነ ነው፡፡ ራእ. 6፥9-11 የቀደሙት ሰማዕታት ፍርድ በቶሎ እንዲሆን ቢጠይቁም የአካሉ ባለቤት የሆነው ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ የሚነሡትን ሰማዕታት ስለሚያውቃቸው እነዚህ እስከሚሰበሰቡ ድረስ እነዚያን ከማጽናኛ ጋር እንዲታገሡ ነገራቸው፡፡

መድኃኒታችን በሥጋዌው ወራት "ቅዱስ አባት ሆይ፥ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው" ያለው ስለ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ዮሐ. 17፥11 ይህ አንድነትም ፍጹም የሆነ አንድነት ስለ መሆኑ ሲናገር "እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ" በማለት ተናገረ፡፡ ዮሐ. 17፥22

ይህ የቤተ ክርስቲያን አንድነት የሚገለጠውና በተግባርም የምንሳተፈው በቤተ ክርስቲያን በሚካሄደው የጋራ ጸሎትና ሥርዓተ አምልኮ ነው፡፡ ይህም ጸሎተ ቅዳሴው፥ መስተብቊዑው፥ ሊጦኑ፥ ማኅሌቱ፥ ጸሎተ ፍትሐቱና የመሳሰለው ነው፡፡ ጸሎተ ቅዳሴው የሁሉም ጸሎቶች አክሊልና ማኅተም ነው፡፡ በጸሎቱና በአምልኮው ቅዱሳን መላእክት፥ አበው ቀደምት፥ ነቢያት፥ ሐዋርያት፥ ሰማዕታት፥ ሊቃውንት፥ ጻድቃን፥ ሁሉም ይሳተፋሉ፤ የጊዜና የቦታ ልዩነቶች ሁሉም ይጠፋሉ፡፡ በዚያ የሚኖረውና የሚፈስሰው ጸጋ እግዚአብሔር ጊዜን የሌለ ወይም የቆመ እስኪያስመስለው ይደርሳል፡፡ ጸሎተ ቅዳሴው "ጸሎተ ቊርባን"፥ ሥጋውና ደሙም "ቊርባን - Communion" የሚባልበት አንዱ ምክንያትም ይህ ነው፤ ከእግዚአብሔር ጋር እና እርስ በእርሳችንም አንድ ያደርገናልና፡፡

የአካሉ ራስ የሆነው ክርስቶስ በአካላቱ ላይ ይነግሣል፡፡ እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለምና በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን በነበሩና ዛሬም ባሉት በቅዱሳን አካላቱ ላይ ሁሉ ይነግሣል፡፡ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ የሚነሡና በክርስቶስ እያመኑ የዚች ቤተ ክርስቲያን አካላት የሚሆኑ እየተጨመሩና አካል ሆነው እየተሠሩ የቤተ ክርስቲያን ጉዞ ይቀጥላል፡፡ "በእርሱም (በክርስቶስ) ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤ እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ" እንዳለ። ኤፌ. 2፥21-22

ይህ ሂደትና ጉዞ "እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ" ሲሆን ይፈጸማል፡፡ 1 ቆሮ. 15፥28 ያን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ምልዓትና ክብር፥ እንዲሁም የኩላዊነቷ ትርጉም በገሀድ ይገለጣል፡፡ ያን ጊዜ "ዘምሩ ልብወ ነግሠ እግዚአብሔር ላዕለ ኩሉ አሕዛብ፥ እግዚአብሔርሰ ይነብር ዲበ መንበሩ ቅዱስ - እግዚአብሔር በአሕዛብ ላይ ነገሠ፥ እግዚአብሔር በቅድስናው ዙፋን ይቀመጣል" የተባለው፤ እንዲሁም "እግዚአብሔር ነግሠ ትትሐሠይ ምድር ወይትሐሠዩ ደሰያት ብዙኃት - እግዚአብሔር ነገሠ፥ ምድር ሐሤትን ታድርግ፥ ብዙ ደሴቶችም ደስ ይበላቸው" የተባለው ይፈጸማል፡፡ መዝ. 46፥8 ፤ 96፥1

ልዩ በሆነው በጸሎተ ቅዳሴው ሰማያውያን ኃይላት ቅዱሳን መላእክት፥ ወደ እግዚአብሔር የሄዱና በአካለ ነፍስ ያሉ ቀደምት አበውና እማት፥ እንዲሁም ሰውራን ቅዱሳን ሁሉ አብረውን ይሳተፋሉ፡፡ ይህም እግዚአብሔር ላደላቸው ለአንዳንድ ቅዱሳን ሲገለጥላቸው እንደ ነበር በተለያዩ መጻሕፍት ተጽፎ እናገኛለን፥ ዛሬም የሚገለጥላቸው ይኖራሉ፡፡ ባለቤቱ ክርስቶስ ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር ሆኖ ወደ መሠዊያው ሲገባ የሚገለጥላቸውና የሚያዩት አሉ፡፡ እንዲሁም ሰውራን ቅዱሳንን ወደ ውስጥ ሲገቡና ከምሥጢራቱ ተሳትፈው ሲሄዱ የሚያዩም ነበሩ፡፡ በቤተ ክርስቲያን በመቅደሱ መግቢያ እናት ላይና በበሩ ላይ ጌታችን ከመላእክት ጋር ሆኖ የሚሣለውም ይህን ለማመልከት ነው፡፡

የሥጋ ሞት - የነፍስና የሥጋ መለያየት - በሃይማኖት አማካይነት በክርስቶስ አንድ አካል የሆኑትን ምእመናን አንድነታቸውን ሊያጠፋባቸው አይችልም፡፡ በሥጋ ከዚህ ዓለም መለየታቸው ከክርስቶስ አካልነታቸው፣ ከቤተ ክርስቲያን አንድነታቸው ሊለያቸው አይችልም፡፡ መድኃኒታችን በማይታበል ቃሉ "ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤ ሕያው የሆነ የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም" ብሏልና፡፡ ዮሐ. 11፡25-26

ከሞት በኋላ ሕይወት መኖሩን ለሚያምን ሰው አንድ ክርስቲያን በዚህ ዓለም ሳለ የሚጸልየው ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ይደርሳል፤ ሆኖም ያ ሰው ሲያርፍና ወደ እግዚአብሔር ሲሄድ፣ ከእርሱ ጋር ሲሆን ግን ጸሎቱ ወደ እግዚአብሔር አይደርስም (ፊል. 1፡20) ማለት ትክክል ነውን? በዚህ ዓለም ሳለ ሌላው ሰው የሚጸልይለት ጸሎት ይደርሰዋል፣ ይጠቅመዋል ብሎ ለሚያምን ሰው ከሞተ በኋላ ይህ አይሆንለትም የሚያሰኝ ምን በቂ ምክንያት አለ? በጥንት ዘመን በነበሩ የክርስቲያኖች መቃብሮችና በግበበ ምድር ውስጥ በነበሩባቸው ቦታዎችና መቃብሮቻቸው ላይ የተጻፉ ጽሑፎች ሳይቀሩ ክርስቲያኖች ለሞቱ ወገኖቻቸው ይጸልዩ እንደ ነበርና እነርሱም ያረፉትን ጸልዩልን ይሏቸው እንደ ነበር ያሳያሉ፡፡

ለሞቱ ወገኖቻችን ስንጸልይ "አዕርፍ ለነ እግዚኦ ነፍሰ ገብርከ እገሌ ውስተ ሕፅነ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ - አቤቱ የአገልጋይህን የእገሌን ነፍስ በአብርሃምና በይስሐቅ፣ በያዕቆብም ዕቅፍ አስቀምጥልን" ብለን የምንጸልየው ለዚህ ነው፡፡ ራሱ ጌታችንም ድሀና በሽተኛ የነበረው አልዓዛር በሞተ ጊዜ በአብርሃም ዕቅፍ ውስጥ እንደ ነበረ ነግሮናል፡፡ ሉቃ. 16፡22 ይህም እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ እንደሚቀጥል "እላችኋለሁም፣ ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ፣ ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይቀመጣሉ" በማለት ነግሮናል፡፡ ማቴ. 8፡11

ከዚሁም ጋር ላረፉ ወገኖቻችን ስንጸልይ የቤተ ክርስቲያን አካላት የሆኑትን ንጽሕተ ንጹሐን የሆነችውን ወላዲተ አምላክ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን፣ ሰማያውያን መላእክትን፣ ቅዱሳንን ሁሉ ስማቸውን የምናውቀውን እንጠራቸዋለን፣ ሌሎችን ደግሞ እናስባቸዋለን፡፡ "እለ ጸዋእነ ስሞሙ ወእለ ኢጸዋእነ አስማቲሆሙ - ስማቸውን የጠራነውንም ያልጠራነውንም" እንላለን፡፡ "በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው። መንፈስ፦ አዎን፣ ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ ሥራቸውም ይከተላቸዋል ይላል ብለህ ጻፍ አለኝ" እንደ ተባለ ያረፉ ወገኖቻችን ካመኑበትና ከኖሩለት ከእርሱ ከክርስቶስ አካልነት የሚለያቸው አንዳችም ነገር የለም፤ ይልቁንም አንድነታቸው ይጸና ዘንድ ወደ እርሱ ሄዱ እንጂ፡፡ ስለሆነም ላረፉ ወገኖቻችን የሚደረገው ጸሎት ቤተ ክርስቲያን ጊዜና ቦታ የማይገድባት ኩላዊት መሆኗን የሚገልጽ ነው፤ የባሕርይዋና የእምነቷ አካልም ነው፡፡

ስለሆነም ላረፉ ወገኖቻችን የምንጸልየው ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረት እንዲያገኙ ብቻ አይደለም፣ የራሱን አካል ሊረሳ የሚችል ጤነኛ ሰው እንደ ሌለ ሁሉ የራሳችን አካል የሆኑትን ማሰብ ተፈጥሯዊ ስለሆነም ነው እንጂ፡፡ በዚህም ላረፉ ወገኖቻችን ያለን ፍቅር ይገለጻል፡፡ ፍቅር የአንድነት ሁሉ ፍጹም ደረጃና መገለጫ ነውና፡፡ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን የመንፈስ አንድነት ለመጠበቅም ማድረግ ያለብንን አደረግን ማለት ነው፤ ሐዋርያው "የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ" እንዳለ፡፡ ኤፌ. 4፡3 ይህን አለማድረግ ወይም ለማድረግ አለመፈለግ የቤተ ክርስቲያንን ምንነት ካለመረዳት የሚመነጭ ስህተት ነው፡፡

## 3. ከሞት በኋላ ይቅር ሊባል የሚችል ኃጢአት ስላለ

ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ይህን በተመለከተ በመልእክቱ እንዲህ ብሏል፦ "ማንም ወንድሙን ሞት የማይገባውን ኃጢአት ሲያደርግ ቢያየው ይለምን፤ ሞትም የማይገባውን ኃጢአት ላደረጉት ሕይወት ይሰጥለታል፡፡ ሞት የሚገባው ኃጢአት አለ፤ ስለዚያ እንዲጠይቅ አልልም፡፡" 1 ዮሐ. 5፡16

ጌታችንም "ወዘሰ ነበበ ላዕለ መንፈስ ቅዱስ ኢይትኃደግ ሎቱ ኢበዝ ዓለም ወኢበዘይመጽእ - በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚናገር ሁሉ ግን በዚህ ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው አይሠረይለትም" በማለት በሚመጣው ዓለም ሊሠረይ የሚችል ኃጢአት ያለ መሆኑን አመልክቶናል፡፡ ማቴ. 12፥32

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሞት በኋላ ንስሐ ወይም ደግሞ መካነ ንስሐ (Purgatory) አለ ብላ አታምንም፣ አታስተምርም፡፡ ይህ ዓይነቱ ባህል የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ካመጣችው የፈጠራ ትምህርት አንዱ ነው፡፡ እኛ የምናምነው እግዚአብሔር ቸር ስለሆነ እርሱ ባወቀ ይቅር ይላቸውና ቸርነቱን ያበዛላቸው ዘንድ ላረፉ ወገኖቻችን እንጸልያለን፡፡ ከዚያ ውጭ ከሞት በኋላ ሌላ የንስሐ እድልና ቦታ አለ ብለን ግን አናምንም፣ ይህ ዓይነቱ አስተምህሮና አስተሳሰብ መጽሐፍ ቅዱሳዊም ትውፊታዊም አይደለምና፡፡

## 4. ከዕረፍታቸው በኋላም ሕያዋንና አዋቂዎች ስለ ሆኑ

ከላይ እንደ ተገለጸው ሞት ማለት ሕይወት (ሕያውነት) የሚጠፋበት ሳይሆን ከዚህ ቁሳዊና ሥጋዊ ዓለምና አኗኗር ወደ መንፈሳዊ ዓለምና አኗኗር መሄድ ነው፡፡ ስለሆነም በአካለ ነፍስ ያሉት በዚህ ዓለም ስለሚደረገው ያውቃሉ፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *"አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ተመኘ፣ አየም፣ ደስም አለው"* በማለት ተናግሯል፡፡ ዮሐ. 8፥56 ከሞት በኋላ ምንም ዓይነት ማወቅ ባይኖርና የሞቱ ሰዎች ምንም የማያውቁና የማያደርጉ ቢሆኑ ኖሮ አብርሃም ተስፋው ከተነገረው ጀምሮ ሲናፍቀውና ሲመኘው የነበረው የወልድ ዋሕድ ሰው ሆኖ መገለጥ መፈጸሙን እንዴት አወቀ? እንዴትስ *"አየ፣ ደስም አለው"* ተባለ? ስለሆነም አብርሃም አሁን ያለበት ሁኔታ በአካለ ነፍስ ሆኖ በዚህ ምድር ላይ ሳለ በተስፋ ይጠብቀው የነበረው የክርስቶስ መገለጥ አሁን መፈጸሙን በሚያውቅበት የሕያውነት ሁኔታ ነው ማለት ነው፡፡

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድስት ነፍሱን ከሥጋው በፈቃዱ ከለየና ስለ እኛ ሞትን ከተቀበለ በኋላ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ማኅተመ ደሙን በማሳየት ሰላምን ሰብኮላቸዋል፤ *"እርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩት ነፍሳት ሰበከላቸው"* ተብሏልና፡፡ 1 ጴጥ. 3፥19 ይህም የሚያሳየን በዓለመ ነፍስ፣ ያውም በሲኦል የነበሩት ሙታን ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘትና ከእርሱ መልእክት ለመቀበል፣ ስብከቱንም ለመስማት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ነበሩ እንጂ ምንም ዓይነት ግንኙነት ማድረግ የማይችሉበት ዓይነት ሁኔታ ላይ አልነበሩም ማለት ነው፡፡ ለዚህ ነው ጌታችንም መለኮት በተዋሐዳት ቅድስት ነፍሱ ወደ እነርሱ ሄዶ ነጻነትን የሰበከላቸው፡፡ ስለዚህ ዳግም ምጽአት ከመሆኑና ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት ዛሬ እግዚአብሔር ባዘጋጀላቸው ቦታ በአካለ ነፍስ ያሉ ወገኖቻችን የእግዚአብሔርን ምሕረት ሊቀበሉ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ያሉ ስለ ሆኑ እኛ በተቻለን መጠን በጸሎታችን እግዚአብሔርን እንማልድላቸዋለን፡፡

## 5. አስተምህሯችን፣ እምነታችን፣ ተስፋችን፣ . . . የሚገለጥበት ስለ ሆነ

በጸሎተ ፍትሐት የሚደርሰው ቃለ እግዚአብሔር "ማራቸው፣ ይቅር በላቸው" የሚል ጸሎትና አስተብቁዖት ብቻ ሳይሆን የክርስትና ሃይማኖት ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ፣ ክርስቲያኖች ስንኖር ምን አምነን፣ ምን ተስፋ አድርገን እንደምንኖርና እንደምንሞት የሚገልጥና የሚመሰክር ነው፡፡ ለዚህም የቅዱስ ያሬድን መዋሥዕት መመልከት በቂ ምስክር ነው፡፡ በጸሎተ ፍትሐት ጊዜ የሚደርሰው ቅዱስ ያሬድ የደረሰው መዋሥዕት፣ እቡኑ፣ አስተብቁዖቱና የመሳሰለው ጸሎት የክርስትናን ምንነት መመስከሪያ መድረክና ማስተማሪያ መንገድም ነው፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ዓለም በሕይወተ ሥጋ ያሉ ሰዎች አንዳቸው ለሌላቸው ሊጸልዩላቸው የሚገባ ከሆነ ከዚህ ዓለም ሕይወት ወጥተው ወደ መንፈሳዊው ዓለም ለሄዱ ክርስቲያን ወገኖቻችን መጸለይ ስህተትነቱ ምኑ ላይ ነው ይሆን? ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ "ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ" በማለት አስተምሮናል፡፡ ያዕ. 5፡16 ታዲያ ከዚህ ዓለም ሕይወት ለወጡና በዐጸደ ነፍስ ያሉ ክርስቲያኖችን ስለ ሌላው እንዳይጸልዩ፤ እኛም ስለ እነርሱ እንዳንጸልይ የሚያግደን ምን ጭብጥ ምክንያት ይኖራል? ይህን የሚጠራጠሩ ወይም የማያምኑ ሰዎች መሠረታዊ ችግራቸው ሰዎች ከዚህ ዓለም ሕይወት ከወጡ (ከሞቱ) በኋላ ምንም የማያዉቁ ሙታን አድርጎ ከማሰብ የተሳሳተ መነሻ የሚመነጭ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከላይ እንደ ተገለጸው ከመጽሐፍ ቅዱስና ከአበው ቀደምት አስተምህሮ አንጻር ታላቅ ስህተት መሆኑን ተመልክተናል፡፡ በአጠቃላይ ፍትሐት በሞት ላይ እና በትንሣኤ ላይ ያለን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የሚገለጥበት ነው፡፡

# 8.2 ተዝካርና ዝክር

## 8.2.1 የተሐድሶዎች ትምህርት - በዝክርና ተዝካር ላይ

ተሐድሶዎች በዝክርና ተዝካር ላይ ስለሚሉት ነገር የሚከተሉትን እንመልከት፡-

- "በአለቃ ስም ከሚነገሩት ቀልዶች መካከል አንዱን እዚህ ብንጠቅስ ተገቢ ስፍራው ይመስለናል፡ ፡ በርኩሳን መናፍስት እገሌ ጋይነቱ ሰዎችን ሲያስት የኖረ ሰው ሞተ፡፡ ሥራውንና የደለበ ሀብቱን ቤተሰቡ ወረሰ፡፡ ወራሾቹ የኃጢአት ሥርየት ይገዙለት ዘንድ ከዕለተ ሞቱ ጀምሮ በዐርባው፣ ከዚያም በኋላ በሰማንያው፣ በመንፈቁና በየዓመቱ በከፍተኛ የገንዘብ ወጪ ጸሎተ ፍትሐት አስደረጉለት፡፡ . . . እሁን ከድግሱ ተቋዳሾች አንዱ አለቃን "ሟቹ ንስሐ አልገባም፣ ወራሾቹ ሀብቱን ወርሰዋል፣ . . . እሁን እኛ የጸሎታችን ዋጋ የሆነውን ድግስ የምንመገበው ለሟቹ ነፍስ ስርየት አሰጥተናል፣ እግርጠኞች እኛ የጸሎታችን ዋጋ የሆነውን ድግስ የምንመገበው ለሟቹ ነፍስ ስርየት አሰጥተናል፣ እግርጠኞች ነን ብለን ነውን? እርግጠኛ ባልሆነ የስርየት ሽያጭስ እንጠየቅምን? ቢላቸው "እኛ እንኳ እያልን ማራት ማራት፤ አምላክ ከፈለገ ግንት ይጨምራት፤ ካልፈለገም ደግሞ እንጠርጠስ ያውርዳት" በማለት መለሱለት ይባላል፡፡" (ሙራ ቁ. 7፣ ገጽ 2)
- "ይኸውና ከዚህ ከ14ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ ተዝካር የተባለው፣ የምእመናን ላብ ደም እየተሳበ ወደ ቤት ክርስቲያን አገልጋዮች እንዲዛወርበት ለማድረግ በረቀቀ ጥበብ የተዘረጋው ሂንቢ ይነቀል ወይም ይቆረጥ የሚል በቤተ ክርስቲያን አመራር ሰጪ አካላት በኩል ምንም ዓይነት ርምጃ ሊወሰድ አለመሞከሩ እጅግ አስገራሚ ሆኗል፡፡ . . . ሆኖም ካለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ጀምሮ በተዝካር ድግስ የሞቱ ዘመዶችህን እናስምርልሃለን፣ ከሲኦል ወደ ገነት እናዛውርልሃለን እየተባለ ሲቀለድበት የኖረው ሕዝብ ቀልዱን ተውት በማለት የተዝካርን ድግስ ለማስቀረት በየክልሉ ያደረገው ውይይትና ያሳለፈው ውሳኔ ለምእመኑ ቁሳዊና መንፈሳዊ ግንዛቤ ማደግና መዳበር ጉልህ ማስረጃ ሆኗል፡፡" (ሙራ ቁ. 17፣ ገጽ 19)
- ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ስለ ንስሐ ያስተማረውን ትምህርት ጠቅሰዋል፡፡ የቀረበበት ዓውድና የተጠቀሰው አባት ሃሳብ ግን የተዛመደ አይደለም፡፡ የተጠቀሰበት ጉዳይ የጥያቄ መልስ አስመስሎ ለማቅረብ የተሞከረው እንዲህ ይላል፡-
- "ሰው በሕይወተ ሥጋ ሳለ በሠራው ኃጢአት ከሞተ በኋላ ንስሐ የመግባት ዕድል ይኖረዋል? ማቹን እናስምራለን የሚሉ ወገኖች የፍትሐት ገንዘብ ይጠይቁናል፤ . . . በሕይወተ ሥጋ እያለ ንስሐ ለመግባት ራሱ ወስኖ ባላደረገው ነገር ከሞተ በኋላ ዘመዶቹ ስለ እርሱ ንስሐ ቢገቡለት ምሕረት ያገኛል መባሉ እውነት ነውን?
- "መልስ፡- የኑሲስ ኤጲስ ቆጶስ ስለ ንስሐ ያስተማረው እንዲህ ይነበባል፡- 'ዘመናችን ሳይፈጸም እጃን ወደ እኛ ዘርግቶ የሚጠራንን እንስማው፤ ፊጥነን በፊቱ ራሳችንን እናዋርድ፤ እቤቱ እነሆ አንተን በድለናል፤ እኛ በዓይነ ምሕረት ተመልከት፣ ፍጥረቶችህን አትጣል፤ የእጅህ ፍጥረቶች ነንና፡፡ ከሞት በኋላ የሚያስብህ፣ በመቃብርስ ተስፋ የሚያደርግህ ማነው እያልን ፈጥነን ንስሐ እንግባ፣ ፋኖሳችንን እናብራ፤ ደጅ ሳይዘጋ ሙሽራውን ለመቀበል እንፍጠን፤ ያለዚያ ግን መግባት አይቻለንም፡፡' ሃይማኖተ አበው 37፡11-12" (ሙራ ቁ. 31፣ ገጽ 17-18)

## 8.2.2 ተሐድሶዎች ጸሎተ ፍትሐትን በተመለከተ የሚሏቸው ዋና ዋናዎቹ ውሸቶችና ስህተቶች

1) ጸሎተ ፍትሐትን ከሥርየት ሽያጭ ጋር አመሳስለው ማቅረባቸው

ከላይ በተጠቀሰው የማጭበርበሪያ ጽሑፋቸው ላይ ለሙታን የሚደረገውን ጸሎት ከሥርየት ሽያጭ ጋር አመሳስለው አቅርበውታል፡፡ በፈጠሩት ገጸ ባሕርይ አማካይነት ". . . አሁን እኛ የጸሎታችን ዋጋ የሆነውን ድግስ የምንመገበው ለሟቹ ነፍስ ሥርየት አሰጥተናል? አግርጠኞች ነን ብለን ነውን? እርግጠኛ ባልሆነ የሥርየት ሽያጭስ አንጠየቅምን?" ያለ አስመስሎ በማቅረብ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በካቶሊካውያን ዘንድ ተስፋፍቶ የነበረውን የሥርየት ሽያጭ እንደምታካሂድ አስመስለው ለማቅረብ ሞክረዋል፡፡ የሮማ ቤተ ክርስቲያን ሕግ ዘመምና ሕግ ተኮር በሆነው አስተሳሰቧና አካሄዷ የበለጠ ጸጋ ያላቸው ሰዎች ("Treasury of merits") በመዳን መንገድ ላይ ላለና ያ መንፈሳዊ ጸጋ የበለጠ ለሚያስፈልገው ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ("Right of transfer") ይችላል የሚል አስተምህሮ የነበራቸው መሆኑ ከላይ ተገልጿል፡፡ ይህን እነዚህን ጸጋዎች ከአንዱ ወደ ሌላው የማስተላፉን ሂደት "ሥርየት መሸጥ" - "Indulgence" ይሉት ነበር፡፡ የዚህ የማስተላለፍ ሂደት ዋናው ሥልጣን ያለውም በፖፑ እጅ ነው ይሉ ነበር፡፡

ከ5ኛው መቶ ዓመት ጀምሮ በረቀቀ አካሄድ ለክርስትና ዕንቅፋት ሲሆኑ የኖሩትና ለተሐድሶዎች አባት ለእነ ማርቲን ሉተር፣ ለእነ ጆን ካልቪን፣ ለእነ ኡልሪች ዝዊንግሊና ለመሰሎቻቸው መፈልፈል ምክንያት የሆኑት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፖፖችና አጠቃላይ አሠራር የሥርየት ካርድ (Indulgence card) እያሉ ይሸጡም ነበር፡፡ ይህም አንድ ሰው ያን ካርድ የሚገዛው ለሞተ ወገኑ ከሆነ ያ በመካነ ንስሐ (Purgatory) ያለው ዘመዱ ልክ የሥርየት ካርዱን ሲገዛ ነፍሱ ምንጥቅ ብላ ወደ ገነት ትገባለች ብለው ያስተምሩ ነበር፡፡ ይህ አስተሳሰብ ግን በሮማ ካቶሊክ ውስጥ ብቻ የታየና የተሰማ እንጂ በየትኛውም ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያኖች ዘንድ (የምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያንን ጨምሮ) ተሰምቶ የማያውቅ ባእድና ልብ ወለድ አስተሳሰብ ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ካለው ካቶሊካዊ እርሾ የተለየች ናት፤ መካነ ንስሐንም (Purgatory) ሆነ ከሚፈለገው በላይ የሆነ ትርፍ ጸጋ (Treasury of merits) የሚለውን ሰው ሠራሽ የፈጠራ ትምህርት አትቀበልም፤ እንዲህ ያለውን አዲስ ፈጠራ አስባውም አታውቅም፡፡ ስለዚህ ተሐድሶዎች ከካቶሊካውያን ምንጭ ከተቀዱት ከእነ ሉተርና መሰሎቹ ሃሳብ ሲወስዱ ቢያንስ እነርሱ ያን ሲሉ ከምን ታሪካዊና ነባራዊ መነሻና ሁኔታ (Historical context) ተነሥተው እንዳሉ ለማወቅ ቢችሉ ኖሮ እንኳ ጥሩ ነበር፤ ቢያንስ ነቀፋቸው ምናልባት ትንሽ እንኳ መልክ ያለው መስሎ ሊታይላቸው ይችል ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን መሐሪ እግዚአብሔር ይምራቸው ዘንድ "መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ ገብርከ እገሌ" እያለች የእግዚአብሔርን ምሕረት ትለምናለች እንጂ "ሥርየት አሰጥቻለሁ፣ ከሲዖል ወደ ገነት አዛውረናታል" ብላ ደፍራ ልትናገረው ቀርቶ አስባውም አታውቅም፡፡ ጸሎተ ፍትሐት የሚያስደርጉት ወገኖችም ፍትሐት ላስደረጉለት ወገናቸው "ሥርየት ገዝተንለታል፣ ከሲኦል ወደ ገነት ይዛወርልናል" አይሉም፡፡

የሰዎች ድርሻ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ፣ ምሕረትን መለመን ነው እንጂ ምሕረትን መስጠት፣ መወሰን አይደለም፡፡ ይህማ የእግዚአብሔር ብቻ ድርሻ ነው፡፡ "ወዚአከ እግዚኦ ሣሕል - አቤቱ ምሕረት ያንተ ነው" ተብሏልና፡፡ መዝ. 61፥12 እንዲሁም "የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው" ይላልና፡፡ ሮሜ 8፥34 ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ይህ በሚገባ የምታውቅ ናት፤ ድርሻዋን አሳምራ ታውቃለች፡፡ ስለሆነም ማንም ጤኛ የሆነ ሰው "ሥርየት ገዝተንለታል፣ ከሲኦል ወደ ገነት አዛውረናታል" አይልም፡፡ "ሥርየት መግዛት" የሚለው ቃሉ ራሱ በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ አይታወቅም፤ ከላይ እንዳየነው የሌሎች ነውና፡፡ ይልቅስ ተሐድሶዎቹ እንዲህ ያለውን ባእድ ቃልና ሃሳብ ከየትም እያመጡ በመዝራት ሰዎችን እንዳያስለምዱብን እግዚአብሔር ይጠብቅልን፡፡

- ስለዚህም "በተዝካር ድግስ የሞቱ ዘመዶችህን እናስምርልሃለን፣ ከሲዖል ወደ ገነት እናዛውርልሃለን እየተባለ ሲቀለድበት የኖረው ሕዝብ" ያሉት ዓይን ያወጣ ውሸት ነው ከማለት ያለፈ ምን ይባላል? ስለዚህ ፍጹም ውሸትነት እነርሱ በገለጹበት ደረጃ እንግለጸው ብንል በእነርሱ የጠላነውን ማድረግ ይሆንብናልና ከዚህ አናልፍም፡፡ ግን ድሮ ድሮ እኮ ጠላትንም እንኳ ቢሆን ማጥቃት ቢያስፈልግ ባለውና በተናገረው ነገር ነበር እንጂ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ያላለውን "አለ" እያሉ በመዋሸት አልነበረም፡፡ የእነርሱ ግን እውነት ሊገኝባቸው ይቅርና ለውሸታቸው እንኳ ትንሽ ለዛና ይሉኝታ እንኳ የለውም፡፡ በወንጌል "ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ ሰውንም ባላፍር" አለ እንደ ተባለው ከፉ ዳኛ ሁለቱንም - ፈሪሃ እግዚአብሔርንም፣ ይሉኝታንም ያጡ ናቸው፡፡ ሉቃ. 18፡4 ይህ ነገራቸውስ "ኢትኩን ስምዐ በሐሰት - በሐሰት አትመስክር" የሚለውን ከዐሠርቱ ትእዛዛት መካከል አንዱ የሆነውን ማፍረስ አይደለምን? "እስመ እምቃልከ ትጸድቅ ወእምቃልከ ትትኴነን - እኔ እላችኋለሁ፣ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤ ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህ፣ ከቃልህም የተነሣ ትኰነናለህ" ያለው ፈራጅ እግዚአብሔር መሆኑን ለማሰብ ዓይነ ልቡናቸውን የጋረደውን ጭፍን የጥላቻ መጋረጃ አርቆ ልቡናቸውን ያብራላቸው እንላለን፡፡ ማቴ. 12፡36-37

ይህ እነርሱ የሚሉት ነገር እንዲሁ "የመናፍቅ ቂስ ቅዳሴው ቢያልቅበት ቀረርቶ ጨመረበት" እንደ ተባለው እውነት የሆነ ነገር ስለሌላቸው እንዲሁ በመሳደብና በሐሰት በማጥላላት እንሞክረው ብለው ካልሆነ በስተቀር የሚያውቅባቸው ሁሉ ይታዘባቸዋል፡፡ ቀድሞ እውነት መስሎት የነበረ ሰው ቢኖር እንኳ ሲያውቅባቸው የበለጠ ይጠላቸዋል እንጂ የሚጠቅማቸው አይደለም፡፡ ነቢዩ "ወሐሰት ርእሰ ዓመፃ - ሐሰት የኃጢአት ሁሉ አለቃ ነው" ያለውንስ አልሰሙምን? ለነገሩ እግዚአብሔርን ለሚፈራና ሃይማኖት ላለው ሰው የሚነገረውን የእግዚአብሔር ቃል ለእነርሱ መንገር ትርፉ ድካም ብቻ ነው፡፡ የሚጠቅማቸውን ነገር ለማድረግ ቢያስቡማ ኖሮ ከጥንቱ ወደ እንደዚህ ዓይነት ነገር መቼ ይገቡ ነበር፤

2) ለሞቱ ወገኖች ጸሎት ማድረግን ከሞት በኋላ ንስሐ አለ እንደ ማለት አስመስለው ማቅረባቸው፣ እንዲሁም ለሞቱ ሰዎች ጸሎት ማድረግን ስለ እነርሱ ተገብቶ ንስሐ እንደ መግባት ማስመሰላቸው፣

◉ "ሰው በሕይወቱ ሥጋ ሳለ በሠራው ኃጢአት ከሞተ በኋላ ንስሐ የመግባት ዕድል ይኖረዋል? ማቹን እናስምራለን የሚሉ ወገኖች የፍትሐት ገንዘብ ይጠይቁናል፤ . . . በሕይወቱ ሥጋ እያለ ንስሐ ለመግባት ራሱ ወስኖ ባላደረገው ነገር ከሞተ በኋላ ዘመዶቹ ስለ እርሱ ንስሐ ቢገቡለት ምሕረት ያገኛል መባሉ እውነት ነውን?"

ስለ አንድ ሰው መጸለይ ማለት ስለዚያ ሰው ተገብቶ ንስሐ መግባት ማለት የሆነው ከመቼ ወዲህ ነው? ቅዱስ ጳውሎስ ለቆላስይስ ምእመናን "ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ" ሲል የቆላስይስ ክርስቲያኖች ስለ እኔ ቅዱስ ጳውሎስ ተገብተው ንስሐ እንዲገቡላቸው መጠየቁ ኖሯልን? ቆላ. 4፡3 እንዲሁም የሮሜ ምእመናንንም "ወንድሞች ሆይ፣ ስለ እኔ ወደ እግዚአብሔር እየጸለያችሁ . . . " ሲል "ስለ እኔ ንስሐ ግቡልኝ" ማለቱ ኖሯል ይሆን? ሮሜ 15፡30

እንደዚሁም ይኸው ሐዋርያ የተሰሎንቄ ክርስቲያኖችን "ወንድሞች ሆይ፣ የጌታ ቃል እንዲሮጥ በእናንተም ዘንድ ደግሞ እንደሚሆን እንዲከበር፣ እምነትም ለሁሉ ስለማይሆን ከዓመፀኞችና ከክፉዎች ሰዎች እንድንድን ስለ እኛ ጸልዩ" ብሏቸዋል፡፡ 2 ተሰ. 3፡1-2 ታዲያ ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ እንኳ በትሕትና ሆኖ ያስተማራቸው ምእመናን እንዲጸልዩለት ከጠየቀና የእነርሱ ጸሎት እርሱና አብረውት ለወንጌል አገልግሎት የሚጋደሉት ሌሎች "ከዓመፀኞችና ከክፉዎች ሰዎች እንዲድኑ" የሚረዳቸው መሆኑን አምኖ ከተናገረ ተሐድሶዎች የሚሉት ነገረ ዘርቅ ቦታው የት ነው? እሁንም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ያለው በዚህ ዓለም ሳለ ነው በሚል ሰበብ ለመሸሸግ መሞከር አይችሉም፤ ምክንያቱም ከዚህ ዓለም ድካም ማረፍ ከአንዲት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አካልነት እንደማይለይ ከላይ ተገልጿል፤ እነርሱን ይመስል አንድን ነገር በየቦታው መደጋገም የለብንምና፡፡

እዚህ ላይ ቤተ ክርስቲያን የማትለውን "ከሞት በኋላ ንስሐ አለ፣ ያልሞቱት ለሞቱት ንስሐ ይገቡላቸዋል" በማለት ጸሎተ ፍትሐት ማድረግ ማለት ለሞተ ሰው ያልሞተው ሰው ንስሐ ይገባለታል ማለት እንደ ሆነ አስመስለው በውሸት አቅርበዋል፡፡ ይህ ውሸት ነው፡፡ ስለ ሞቱ ወገኖች ጸሎት ማድረግ ማለት ስለ እነርሱ ተገብቶ ንስሐ መግባት ማለት አይደለም፡፡ እንደዚህ ሆኖም አያውቅም፡፡ አንዱ ሰው ሌላው ይጸልይለታል ማለት ንስሐ ይገባለታል ማለት አይደለም፡፡ ጸሎት መጸለይ አንድ ነገር ነው፣ ንስሐ መግባት ደግሞ ሌላ ነገር ነው፤ ማደባለቅና ማምታታት አይገባም፡፡ ባላዋቂ አእምሯቸው ወይም በተንኮለኛ አካሄዳቸው ቅዱሱን የእግዚአብሔርን ቃል ባያበላሹና ዕዳቸውንም እጥፍ ድርብ ባያደርጉ ጥሩ ነበር፡፡ ገና ፊደል ያልለየ ሕፃን የፊደሎቹ መልክ እየተመሳሰለ እንደሚደባለቅበት ተሐድሶዎችም ገና አጥርተው ሳይማሩ እናስተምር በማለታቸው እንዲህ ይደባለቅባቸዋል፡፡

ለዚሁ "መልስ" ብለው ያቀረቡት አባት ደግሞ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ነው፡፡ ይህን ኦርቶዶክሳዊ ቅዱስ አባት ከላይም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ትምህርቱን ደጋግመን ጠቅሰነዋል፡፡ እነርሱ ግን ባልሆነ ነገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት አስተምህሮ ከዚህ ቅዱስ አባት ትምህርት ጋር የሚቃረን ለማስመሰል አቅርበውታል፡፡ ነገር ግን የጠቀሱት የዚህ አባት ትምህርት የምናምነውና የምንቀበለው ነው፡፡ "ሞኝ የሰማ ዕለት ያብዳል" እንደሚባለው እነርሱ የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርት ደኅና አድርገው ሳይሰሙ እንዲሁ ጠላቶቿ የላኳቸውን ብቻ ይዘው ስለ ተነሡ ሳያውቁት ቀርተው ይሆናል እንጂ እምነቷም ትምህርቷም እንደዚህ ነው፡፡ አንድ ሌላ ነጥብ ግን ይህን አባት ራሳቸውም ምስክር አድርገው ጠቅሰውታልና እኛም ምስክር አድርገን በጠቀስነው ጊዜ እርሱ ያስተማረውን ትምህርት ይቀበሉ ዘንድ የውዴታ ያይደለ የፍትሐዊነት ግዴታ ውስጥ ገብተዋል ማለት ነው፡፡

በመሠረቱ ዝክር ማለት የሞቱ ወገኖችን በጸሎት ማስታወስ፣ ማሰብ ማለት ነው፡፡ ይህ የሚደረግባቸው ምክንያቶችም ከላይ ተገልጸዋል፡፡ የሞቱ ወገኖችን በጸሎት ማሰብ ክርስቲያናዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑ በሚገባ ተገልጿል፡፡ ስለዚህ ዝክር ማለት ማሰብ፣ ማስታወስ ከሆነና ይህም መጽሐፍ ቅዱሳዊነቱ የታወቀ ከሆነ ተሐድሶ መናፍቃን ፕሮቴስታንታዊ እንክርዳዳቸውን በተረታ ተረት በማስታከክ ለመዝራት የሚያደርጉት ከንቱ ሙከራ ማንነታቸውን በሚያውቅባቸው ዘንድ ዋጋም ቦታም የለውም፡፡

ያረፉ ወገኖችን በጸሎት ማሰብ የተገባ ከሆነ እንዴት እናስባቸው? የሚለው አተገባበር ላይ ሰዎች እንደ መረዳታቸውና እንደየ ዝንባሌያቸው ሊፈጽሙት ይችላሉ፡፡ አንዳንዶች የሞቱ ወገኖቻቸውን በሚያስቡበት ጊዜ ለድሆች ምጽዋት በመስጠት፣ በጸሎተ ቅዳሴው ያገለገሉ ካህናትን በማቁረርና በመሳሰሉት ክርስቲያናዊ ተግባራት ሊፈጽሙት ይችላሉ፡፡ ከዚያም ባለፈ ዓቅሙና ችሎታው አለን የሚሉ ሰዎች ለዘመድ አዝማዶቻቸውና ለነዳያን፣ እንዲሁም ለድሆች የሚያበሉትንና የሚያጠጡትን ሰፋ አድርገው ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡ ተዝካር የሚባለው ይህ ነው፡፡ ሆኖም ይህ የድግሱ ስፋትና ዓይነት ሰዎች እንደየ አካባቢያዊ ሁኔታዎችና እንደየ ባህላቸው በራሳቸው መንገድ በሂደት ያዳበሩት ልማድ እንጂ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ትምህርትም (Doctrine) ሆነ ትእዛዝ አይደለም፣ ሆኖም አያውቅም፡፡

ሰዎች በልማድ የሚያደርጉትን ሁሉ "ጅብን ሲወጉ በአህያ ተጠግቶ ነው" እንደሚባለው እንዲህ ያሉ ነገሮችን መግቢያ ቀዳዳ በማድረግ መሠረታዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን በሕይወተ ሥጋ ላረፉ ወገኖች ሊደረግ የሚገባውን ጸሎተ ፍትሐት አግባብ አይደለም እያሉ መናገርና መጻፍ ጌታችን "አሌ ለክሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን አምሀርት ዕውራን እለ ገመለ ትውኅጡ ወጻጹተ ትነጽፉ - እናንተ ግብዞች መሪዎች ጸሐፍትና ፈሪሳውያን፣ ትንኝን የምታጠሩ ግመልንም የምትውጡ ወዮላችሁ" በማለት የተናገራቸው የግብር ልጆች መሆን ነው፡፡ እውነተኛ ማንነታቸውን ሸፍነውና ለሕዝቡ ተቆርቋሪ መስለው ነገር ግን መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የሆነውን ነገር ለማስቀረትና ለማጥፋት ክፉ ሠራተኞች ሆነው ይሠራሉና፡፡ ማቴ 23፥24

## 8.3 በቁርባን ጊዜ የሞቱ ነፍሳት ስም ለምን ይጠራል?

ምሥጢረ ቁርባን የቤተ ክርስቲያን አንድነት መሠረትም መገለጫም ነው፡፡ በክርስቶስ ቤዛነት የዳነችው ቤተ ክርስቲያን የእርሱ አካል ሆና በአንድነት (አንዲት ጉባኤ ሆና) ወደ አብ ፊት በኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የምትቀርብበት ምሥጢር ነው፡፡ ቁርባን ማለት ለእግዚአብሔር የሚቀርብ፣ እንዲሁም አንድነት፣ ኅብረት ማለት ነው፡፡ በምሥጢረ ቁርባን የምእመናን አንድነት ጉባኤ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ትሆናለች፣ በእግዚአብሔርም በዚች ጉባኤ ያሉ ሁሉም አንድ ይሆናሉ፣ ኅብረት ይኖራቸዋል፡፡ ይህ የሚደረገውም በዚያ ዕለትና ቦታ ለሚገኙት ብቻ ሳይሆን የጊዜና የቦታ ወሰንና ገደብ ሳይኖር የዚህች የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አባላት ስለ ሆኑት ሁሉ ነው፡፡ እነዚህም የድል አድራጊዋ ቤተ ክርስቲያን አባላትና ገና በተጋድሎ ላይ ያሉት የቤተ ክርስቲያን አባላት በአንድነት በእግዚአብሔር ፊት የሚቀርቡበትና እነርሱም ለእርሱ ምስጋናና አምልኮ የሚያቀርቡበት ልዩ ምሥጢር ነው፡፡

ከዚህ ዓለም ተጋድሏቸውን ጨርሰው የሄዱ የቤተ ክርስቲያን አባላት የድል አድራጊዋ ቤተ ክርስቲያን (Church Triumphant) አባላት ናቸው፡፡ እነርሱ ከዚያ በኋላ መፈተንና ውጣ ውረድ የለባቸውምና፡፡ ሆኖም ከዚህ ዓለም መለየታቸው ግን ከቤተ ክርስቲያን አባልነት አያስወጣቸውም፡፡ በዚህ ዓለም በተጋድሎ ላይ ያሉት ደግሞ በተጋድሎ ላይ ያለችው ቤተ ክርስቲያን (Church Militant) አባላት ናቸው፡፡ በጸሎተ ቁርባን ጊዜ የቅዱሳን ስም የሚጠራው ክርስቶስ እርሱ ራሱ በሞት ላይ ድል ማድረጉ የእርሱ ሞትን ድል ማድረጉም የተገለጠባቸው ስለሆኑ ነው፡፡ ቅዱሳን በሕይወታቸው ያደረጉት ተጋድሎ ብቻ ሳይሆን ሞታቸውም የክርስቶስን ክብር ገልጧልና የክርስቶስ ሞቱና ትንሣኤው በሚታሰብበት በቅዱስ ቁርባን ጊዜ ስማቸው አብሮ ይጠራል፡፡ ምክንያቱም እስከ ሞት ድረስ ታምነው ስለ ተገኙና ሞት እንኳ እርሱን እንዲክዱ ስላላደረጋቸው ነው፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ ቅዱሳን ክርስቶስ ሞትን ድል ያደረገው መሆኑንና አሁን ሞት ወደ እግዚአብሔር መሄጃ መንገድ መሆኑን ስላመኑ ነው፡፡ ቅዱሳን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞት ላይ ለተቀዳጀው ድል ሕያው ምስክሮችና የድል አድራጊነቱም ተቋዳሾችና ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ የእነዚህ የድል አድራጊዎች የቅዱሳን ስም በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ የሚጠራው ስለዚህ ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ገና በዚህ ዓለም እያለ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች "እኔ ምንም እንኳ በሥጋ ከእናንተ ጋር ባልሆን፣ በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝ . . . እናንተና መንፈሴም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ጋር ተሰብስበን . . ." አለ፡፡ 1 ቆሮ. 5፡3-4 ቅዱስ ጳውሎስ ገና በዚህ ዓለም በሥጋ እያለ በአካል ከቆሮንቶስ ምእመናን ጋር ባይኖርም በመንፈስ ግን እነርሱ ሲሰበሰቡ አብሮ ከእነርሱ ጋር እንደሚገኝ ተናግሯል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ገና በዚህ በዓለመ ሥጋ ሳለ ከቆሮንቶስ ምእመናን ጋር በመንፈስ አብሮ የሚገኝ ከሆነ ከዚህ ዓለም ድካም ያረፉና ወደ እግዚአብሔር የሄዱ ቅዱሳን በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ አይገኙም ማለት እንዴት ይቻላል? ስለዚህ የእነርሱ ጸሎታቸው ይጠቅመናል፣ እኛም ደግሞ እነርሱን በጸሎታችን እናስባቸዋለን (እናዘክራቸዋለን)፡፡

ታላቁ ቅዱስ መቃርዮስ እንዲህ ብሏል፦

> ለወንድማችን ከማሰብና ለእርሱ መዳን ማድረግ የሚገባንን ነገር ከማድረግ ውጭ ለመዳን እንችልም፡፡ ለሌሎች ወገኖቻችን በዚህ ዓለም ሳሉ እንጸልይላቸዋለን፣ ታዲያ ከሞቱ በኋላ እንዳንጸልይላቸው የሚያግደን ምን ነገር አለ? በአካለ ሥጋ ስለ ሌሉ ለእነርሱ መጸለይን ማቆም አለብንን? እነዚህ የምናደርግላቸው ጸሎታት ለሞቱት ወገኖቻችን ምን ያህል እንደሚጠቅማቸው እኛ ላናውቅ እንችላለን፤ ሆኖም የእግዚአብሔር የቸርነቱ ፍቅር በምሕረቱ እንዲጎበኛቸው እንጸልይላቸዋን፡፡ (የቅዱስ መቃርዮስ ትምህርቶች)

ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ የነበሩ የተለያዩ ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን ቅዳሴዎች ሁሉም ስላረፉ ወገኖች የሚጸለይ ጸሎት አላቸው፡፡ ይህም ሐዋርያዊ መሠረትና ትውፊት ባላቸው አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ - በምሥራቁም ሆነ በምዕራቡ ክፍለ ዓለም ባሉ ጥንታውያን ቅዳሴያት ላይ ሁሉ ይገኛል፡፡ ቅዳሴ ሐዋርያት፣ ቅዳሴ ዘቅዱስ ባስልዮስ፣ ቅዳሴ ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ቅዳሴ ዘቅዱስ ጎርጎርዮስና ሌሎቹም ቅዳሴያት ስለ ዐረፉ ወገኖች የሚጸለይ ጸሎት አላቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ የሞቱ ወገኖችን በጸሎት ማሰብ ተገቢ ሐዋርያዊ ተግባር መሆኑን የሚመሰክሩ ናቸው፡፡

## 8.4 ስሞቱ ወገኖች ጸሎተ ፍትሐት ማድረግና በቁርባን ጊዜ ስማቸውን መጥራት እንዲገባ - የአበው ቀደምት ትምህርት

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ የዮሐንስን ወንጌል በተረጎመበት ክፍለ ትምህርቱ እንዲህ ይላል፦

- "... ለሞተ ወገናችሁ ስታለቅሱ ልክ ወደ ሌላ ሀገር እንደ ላካችሁት ያህል በማሰብ ይሁን፡ ፡ የሞተው ሰው ኃጢአተኛ የነበረ ከሆነና እግዚአብሔርን በብዙ ነገሮች ያሳዘነ ሰው ከነበረ ማልቀስ የሚገባው ያን ጊዜ ነው፡፡ በእርግጥ እንዲህ በሆነ ጊዜም እንኳ ማልቀስ አይገባም፣ ማልቀሱ ለሟቹ ምንም የሚጠቅመው ነገር የለምና፡፡ ለሟቹ ልናደርግለት የሚገባው ስለ እርሱ ምጽዋትንና ስጦታን በማድረግ የተወሰነ ዕረፍትን እንዲያገኝ የሚረዳውንና የሚጠቅመውን ነገር ነው፡፡ ክፉና ኃጢአተኛ ከነበረም በሞቱ ኃጢአቱ ተቋርጦለታልና በዚህም ደስ መሰኘት ይገባል፡፡ ጻድቅ ከነበረም ደስ ሊለን ይገባል፤ አሁን ወደፊት ሊገጥመው ከሚችል ያልታወቀ ነገር አምልጦ በኃጢአት የመፈተንና የመውደቅ ሲጋት በሌለበት በአስተማማኝ ሁኔታ ሊኖር ሄዷልና፡፡ . . . የሞተውን ሰው ልታከብሩትና መልካም ልታደርጉለት ትወዳላችሁን? እዎ ካላችሁ በልቅሶና በሐዘን ሳይሆን ስለ እርሱ ምጽዋትን፣ መልካም ሥራን እና ለሕዝቡ ጠቃሚ የሚሆን ነገርን በማድረግ ጥቀሙት፣ አክብሩት፡፡" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌል ዮሐንስ፣ ክፍለ ትምህርት 62፣ 5)

- "... የሞቱ ወገኖቻችንን ሥርዓተ ቀብርና አሸኛኘት ለእኛም ለእነርሱም በሚጠቅም መንገድ፣ እግዚአብሔርም በሚከብርበት መንገድ እናድርገው፡፡ ስለ እነርሱ ስንል ብዙ ምጽዋትን እንስጥላቸው፣ ለመንገዳቸው በጣም ጠቃሚና መልካም የሆነ ስንቅ እንላክላቸው፡፡ ታላላቅ የሆኑ ሰዎች ከሞቱ በኋላ እንኳ ሕያዋንን ከጥፋት የታደጉና ያዳኑ ከሆነ (እግዚአብሔር፦ ስለ እኔም፣ ስለ ባሪያዬም ስለ ዳዊት ይህችን ከተማ አድናት ዘንድ እጋርዳታለሁ" በማለት ስለ ዳዊት ሲል ኢያሩሳሌምንና ሕዝቧን አድኗልና፡፡ 1 ነገ. 19፡34) ምጽዋት ለሞቱ ወገኖች የሚኖረው ጠቀሜታ ከዚህ ቢበልጥ እንጂ የሚያንስ አይደለም፡፡ ምጽዋት ሙታንን አስነሥቷልና፤ መልካም ነገር የሞላባትና ምጽዋትም የምታደርግ የነበረችው ጣቢታ የተባለችው ደግ ሴት በሞተች ጊዜ እንድትነሣ አድርጓታልና፡፡ የሐዋ. 9፡36-39

"ስለዚህ ሊሞት ያለን ማንም ሰው ወዳጁ ለድሆች ምጽዋት የሚሆን ነገር እንዲሰጥ ያሳምነው፡፡ ወራሹን ክርስቶስ እንዲሆን አድርጎ እንዲህ ባለ ልብስ ወደ መቃብር ይሸኘው፡፡ ትክክለኛ የሆነው ሥርዓተ ቀብርና ሐዘን ይህ ነው፡፡ ይህ የሄዱትንም፣ ያሉትንም ይጠቅማቸዋል፡፡ እንዲህ ባለ ሁኔታ ብንቀበር በትንሣኤ ጊዜ በክብር እንነሣለን፡፡ ለሥጋችን ብቻ በማሰብ ነፍሳችንን ችላ ብለን ከሞትን ግን በዚያ ጊዜ ብዙ ችግር ይደርስብናል፣ ብዙ ኃፍረትና ጉስቁልናም ይገጥመናል፡፡ ስለዚህ ይህን የመልካም ሥራ ልብስ በሕይወት ዘመናችን ሳለን እንልበስ፣ እንጎናጸፍ፡፡ ነገር ግን በሕይወታችን ዘመን ሳለን ዝንጉዎችና ቸልተኞች

ሆነን ካሳለፍነው ደግሞ ቢያንስ እንኳ ቀሪ ወገኖቻችንን ሰንሞት በምጽዋት እንዲረዱን አደራ ብለናቸው እንሙት፡፡ እንዲህ ቀድሞ የሚሞተው ወደ ኋላ በሚቀረው ሰው በመረዳት በኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነት በእርሱ የሚገኘውን ቸርነት ለማግኘት የበለጠ ድፍረትና ተስፋ ይኖረናል፤ ዛሬም ዘውትርም መንግሥት፣ ክብርና ምስጋናና ከእርሱ ጋር ለአባቱና ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን፡፡ አሜን፡፡"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ወንጌል ዮሐንስ፣ ክፍለ ትምህርት 85፣ 6)

- ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም በእርሱ ዘመን ለሙታን ጸሎት ማድረግን በተመለከተ ውዝግብ የሚያነሡ አንዳንዶች የነበሩ ሲሆን ይህን የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሐዋርያዊ ተግባር በዋናንት የተቃወመውና ተቃውሞውንም ያጎላው አርዮስ ነበር፡፡ ቅዱስ ኤጲፋንዮስም ለሙታን ጸሎት ማድረግ አይገባም ይሉ የነበሩ ተረፈ አርዮሳውያን መናፍቃንን በመጽሐፉ ገሥጿቸዋል፡፡ (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ፣ በእንተ መናፍቃን 85፣ ቁ. 7)

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ ሴዛርዮስ በተባለው በታላቅ ወንድሙ ሞት ምክንያት ባስተማረው ትምህርት ላይ ወንድሙ የተማረ ስለ መሆኑ፣ ስለ መንፈሳዊነቱ፣ ከከሃዲው ንጉሥ ከዑልያኖስ ጋር ስላደረገው ክርክርና ክርክሩን በአሸናፊነት ስለ መወጣቱ፣ የዓለምን ክብር የናቀ ስለ መሆኑ ወዘተ ከተናገረ በኋላ ጸሎት ይጸልያል፡፡ ከዚያም በየዓመቱ መታሰቢያውን በማድረግ በሕይወት የቀሩት በሞት የተለየውን ሊያስቡት (ሊያዘክሩት) እንደሚገባ ይናገራል፦

- "... ከእኛ ቀድመው ዕረፍትን ያገኙትን የመንገደኞች ወገኖቻችንን ነፍሳት በመጥራት ለባለቤቱ ለራሱ ለእግዚአብሔር አደራ እንስጣቸው፡፡ ይህን ካደረግን በኋላ ግን ከእንግዲህ እኔም ንግግሬን እናንተም ደግሞ ልቅሶችሁን (ዕንባ ማንባታችሁን) እናቁም፡፡ በእኛ ዘንድ ያለጊዜው የሆነ በሚመስለን፣ እኛን በተመለከተ ነገሮችን ሁሉ እንደሚገባ በተገቢው ጊዜያቸው በሚያደርጋቸው በእርሱ ዘንድ ግን በጊዜው ጊዜ የሆነው ሞቱ [የሴዛርዮስ] አሳዛኝ ቢሆንም እግዚአብሔር እርሱ ባወቀ ጠርቶታልና ማረፊያ አድርጋችሁ ወዳዘጋጃችሁለት ወደ መቃብር ውሰዱት፡፡ ሁሉን ነገር የፈጠርህ እግዚአብሔር ሆይ፣ የአንተ የሆኑትን ሰዎች ሕይወታቸውን የምትመራ አባት ሆይ፣ የሕይወትና የሞት ጌታ ሆይ፣ የነፍሳችን መጋቢና ዳኛ ሆይ፣ ሁሉንም ነገር ሊመረመር በማይችለው ድንቅ ጥበብህና ምግባርህ የምታደርግ አምላካችን ሆይ፣ እባክህ የእንግድነታችን በኩር የሆነውን (የቤተሰቡ የበኩር ልጅ ነበርና) ሴዛርዮስን በቸርነትህና በምሕረትህ ተቀበለው፡፡

  "ለወንድሜ የማቀርበው ስጦታ (አምኃ) ይህ ነው፤ ለእርሱ ከሚገባው ነገር አንጻር ታናሽ ቢሆንም እንኳ እንደ ዓቅማችን ማድረግ የምንችለውን ነገር ማድረግን እግዚአብሔር ይወደዋልና፡፡ የስጦታችን ክፍሉ አሁን ተፈጽሟል፣ ቀሪውን አምኃ ደግሞ በሕይወት የምንቆየው ሰዎች በየዓመቱ መታሰቢያውን በማድረግ እንከፍላለን፡፡ የተቀደሰችና የተባረከች ለሆነችው ነፍስህ ደግሞ ወደ መንግሥተ ሰማያት ትገባ ዘንድ እንጸልይላታለን፤ በአብርሃም ዕቅፍ እንዲያሳርፍህ፣ ከመላእክት አንድነትና ከቅዱሳን ክብርና መዓርግ እንዲደምርህ፣ በደስታቸውም ተካፋይ እንዲያደርግህ በጸሎት እናስብሃለን፡፡ ከዚህም በላይ በጨለማ እየተዋጋ እንዳለ ሰው በዚህ ዓለም ሀብትና ንብረት፣ በምኞትና በስሜት፣ ባለማወቅና ግራ በመጋባት፣ በስህተትና በቁሳዊ ነገሮች ሁሉ ተሸብበንና ታውረን ያለን እኛን ከሰማይ ሆነህ ወደ ታች እየተመለከትህ አስበን እንልሃለን፡፡"

  (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ ትምህርት በእንተ ዕረፍተ እኁሁ - የቤተሰቡ የመጀመሪያ ልጅ የነበረውና በወጣትነቱ በሞተው ወንድሙ በባሕታዊ ሴዛርዮስ ዕረፍት መታሰቢያ ላይ ያስተማረው ትምህርት፣ ቁ. 17)

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ለሞተ ሰው ኃጢአተኛ የነበረ እንኳ ቢሆን ያልሞቱት ወገኖቹ የበለጠ ምጽዋትና መልካም ሥራ በማድረግ ሊጠቅሙት የሚችሉ ስለ መሆኑ የሐዋርያት ሥራን በተረጎመበት ክፍለ ትምህርቱ በሰፊው አስተምሯል፤ እንዲህ ይላል፡-

❖ "... ሕይወቱን በሙሉ በከንቱ ያሳለፈ ሰው ሞቱ እጅግ አሳዛኝ ነው፤ ዘመኑን በከንቱ ያሳለፈ ብቻ ሳይሆን ለጥፋት ያዋለና በክፋት ያሳለፈ ሰው 'ያ ሰው ባልተወለደ ይሻለው ነበር' የተባለው ቃል እንዲህ ላሉት ሰዎች የተገባ ነው፡፡ ማር. 14፡21 እስኪ ለጠይቃችሁ፣ የን ያህል ጊዜውን ሁሉ ራሱን ለመጉዳት ማዋል ጥቅሙ ምንድን ነው? ... ታዲያ እንዲህ ያለውን ሰው ሲሞት ልናዝንለት አይገባምን? ከጥፋት ለማዳን የሚቻለንን ማድረግ የለብንምን? ከፈለግን ቅጣቱን ማቅለል እንችላለን፣ ስለ እርሱ የማያቋርጥ ጸሎት ካደረግንና ስለ እርሱ ምጽዋት ከሰጠን እንችላለን፡፡ እርሱ ምንም ያህል የማይገባ ሰው ቢሆን እንኳ እግዚአብሔር ለእኛ ጽኑ ልመና ሲል ሊምረው ይችላልና፡፡ ስለዚህ እርሱ ትቶት በሄደው ገንዘብ፣ በአንተም በራስህ ገንዘብ፣ በሓሳብህ ሁሉ እርዳው፡፡ እርሱ ራሱ ምጽዋት ሳይመጸውት ሞቶ ከሆነ ቢያንስ እንኳ ዘመዶቹና ወዳጆቹ የሚያደርጉለት ምጽዋት ይኑረው፣ ስለ ሟቹ እነርሱ ቋሚዎቹ ምጽዋትና ጸሎት ያድርጉለት፡፡

"እርሱ በሕይወቱ ምንም መልካም ነገር አላደረገምን? ቢያንስ ሌሎች ስለ እርሱ የሚያደርጉት ነገር ይኑረው፤ ሚስቱ ስለ እርሱ የኃጢአቱን ዕዳ በመክፈል በዚያ ቀን ከፍዳ ታድነው ዘንድ የምትችላትን ሁሉ ታድርግለት፡፡ የሚጠየቅበት ኃጢአት ብዙ በሆነ መጠን የበለጠ ምጽዋት ይደረግለት ዘንድ ያስፈልገዋል፡፡ አሁን በሌሎች የሚደረግለት ምጽዋት ራሱ በሕይወቱ ሳለ አድርጎት ቢሆን ኖሮ ከሚደረገው ምጽዋት ዋጋው በጣም ያነሰ ስለሆነ እርሱን ይጠቅመው ዘንድ ምጽዋቱን አብዝተን እናድርግለት፡፡ ስለ ሐውልትና ለእርሱ ቋሚ ማስታወሻ ስለሚሆን ሌላ ነገር እንጨነቅ፡፡ ታላቁ ሐውልት ይህ ነው፡- ድሆችና መበለቶች በዙሪያው ከበውት እንዲቆሙ አድርጉት፡፡ ስሙን ንገሯቸው፤ ሁሉም ስለ እርሱ ጸሎትና አስተብቁዖት እንዲያደርጉለት ንገሯቸው፤ እግዚአብሔርን የሚያሸንፈው ይህ ነው፡፡ ምንም እንኳ በሰውዬው በራሱ ባይደረግም እንኳ ስለ እርሱ ሌሎች ምጽዋትን ሰጥተውለታልና፤ ይህም እንኳ ቢሆን ለእግዚአብሔር ምሕረት መልካም መግቢያ በር ነው፤ ስለ እርሱ ድሆችና መበለቶች ከበውት ሲያለቅሱ እግዚአብሔር እነርሱን ሲያይ ሊራራለት ይችላልና፡፡

"ሌሎች ሰዎች ስለ እነርሱ ባደረጉላቸው ምጽዋት የተጠቀሙ ብዙዎች አሉና፤ ሙሉ በሙሉ የሆነ ፍጹም ነጻ መውጣትን ባያገኙም እንኳ በዚያው የሆነ ዕረፍትንና መጽናናትን አግኝተዋል፡፡[154] እንዲህ ባይሆን ኖሮ ሕፃናት የሚድኑት እንዴት ነው? ሕፃናቱ በራሳቸው የሚያደርጉት ምንም ነገር የለም፤ ሁሉንም ነገር የሚያደርጉት ወላጆቻቸው ናቸው፡፡ እንዲሁም ልጆቻቸው በራሳቸው ያደረጉት ምንም ነገር ሳይኖር ልጆቻቸውን የተሰጡ (በምሕረት የተቀበሉ) ብዙ እናቶች አሉ፡፡

"እግዚአብሔር እንድን ዘንድ የሚሰጠን የመዳኛ መንገዶች ብዙዎች ናቸው፤ ብቻ እኛ ሰነፎችና ግዴለሾች እንሁን፡፡ ገንዘብ የሌለው ድሀ ቢሆንስ? ብላችሁ ትጠይቁኝ ይሆናል፡፡ እኔም ደግሜ የምጽዋት ታላቅነቱ የሚለካው በተሰጠው የገንዘብ መጠን ብዛት አይደለም፤ በዓላማውና በሰጪው ሰው ሕሊና ነው እንጂ እላችኋለሁ፡፡ ብቻ ዓቅማችሁ ከሚችለው አሳንሳችሁ አትስጡ፣ እንዲያ ካደረጋችሁ በቃ ሁሉንም ሰጥታችኋል፡፡

---

154 (Many have profited even by the alms done by others on their behalf: for even if they have not got perfect (deliverance), at least they have found some comfort thence.)

ኃይለኛ ወገን በሞት ስላረፉ ወገኖቻችን መሥዋዕተ ቁርባን የሚደረግላቸው በከንቱ አይደለም፡፡ የሚደረግላቸው ጸሎትም በከንቱ አይደለም፤ ስለ እነርሱ የሚደረግላቸው ምጽዋትም እንዲሁ በከንቱ አይደለም፤ እነዚህን ነገሮች ሁሉ እንዲደረጉ ያዘዘው መንፈስ ቅዱስ ነውና፡፡ ይህም እንዳችን ለሌላችን በምናደርገው መንፈሳዊ ተግባር እንድንጠቃቀም ነው፡፡ አስተውል፤ ለሞቱ ወገኖችህ ቁርባን በማስቀረብህ እርሱም (የሞተው) ይጠቀማል፤ አንተም ትጠቀማለህ፡፡ አንተ ስለ እርሱ በምታደርገው ጸሎትና ምጽዋት ለእርሱ የእግዚአብሔርን ምሕረት የማግኘና የመዳኑ ምክንያት ትሆንዋለህ፤ እርሱ ደግሞ ምጽዋት እንድትሰጥ በማድረግና የዚህን ዓለም ኃላፊነት እንድታስብና ሀብትንና ንብረትን እንድትንቅ በማድረግ አንተንም ጠቀመህ ማለት ነው፡፡

"በዚህ በሚደረግለት ቁርባንና ጸሎት እንዲሁም ምጽዋት ያረፈው ሰው ጥቅም የሚያገኝ ስለ መሆኑ አትጠራጠር፡፡ ዲያቆኑ "ስላረፉ ወገኖቻችን፤ እንዲሁም ስለ እነርሱ መታሰቢያን (ዝክርን) ስለሚያደርጉ ሰዎች ጸልዩ"[155] ብሎ ጮኾ (አሰምቶ) የሚናገረው እንዲሁ ዋጋ ለሌለው ነገር፤ ለከንቱ አይደለምና፡፡ ይህን ቃል የሚናገረውና ድምፁን የሚያሰማውም ዲያቆኑ አይደለም፤ መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ፡፡ ወገኖቼ እናስተውል እንጂ ምን ማለታችን ነው? መሥዋዕቱ በምሥዋዑ ላይ ቀርቧል፤ መላእክት በዚያ አሉ፤ ሊቃነ መላእክት አሉ፤ ወልደ እግዚአብሔር በዚያ አለ፤ ሁሉም በፍርሃትና በረዓድ ሆነው በመሥዋዕቱ ዙሪያ በጸጥታ ይቆማሉ፡፡ ስላረፉት ወገኖች የሚደርሰውን ጸሎት በዚያ የቆሙት የሚያደርሱት ሁሉም መላእክትና ሊቃነ መላእክት እንዲያ ባለ በታላቅ ጸጥታ ውስጥ ቆመው ሳለ ነው፡፡ ታዲያ ይህ የሚደረገው ነገር እንዲሁ በከንቱ የሚደረግ ይመስልሃልን? ይህን ዋጋ የለውም ካልህ ሊላውስ - ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚቀርበው ቅዱስ መሥዋዕት፤ ስለ አካሉ የሚቀርበውስ ሁሉ ከንቱ አይደለምን? እግዚአብሔር ይቅር ይበለን! ነገር ግን ሁሉም የሚደረገው በእምነት ነው፡፡

"ስለ ሰማዕታት መታሰቢያ የሚደረግላቸው ጸሎተ ቁርባንና ስማቸው መጠራቱስ፤ አዎ፤ ሰማዕታት ቢሆኑም 'ስለ ሰማዕታት' የሚደረግላቸው የመታሰቢያ ቁርባን (መሥዋዕት) ምን ይመስልሃል? ሰማዕታት ሲታሰቡና ሲጠሩ (በጸሎተ ቅዳሴው) ከእነርሱ ጋር አብሮ መጠራትና መታሰብ ቀላል ነገር ይመስልሃልን? የሁሉ ጌታ ባለበት ዘንድ፤ አስፈሪ የሆነው መሥዋዕትና ሊነገር የማይቻለው ምሥጢር እየተፈጸመ ባለበት ጊዜ ያረፉ ሰዎች ስማቸው መጠራቱ ታላቅ ክብርና ጸጋ ነው፡፡ ንጉሡ በዙፋኑ ላይ በተሰየመበት ጊዜ ደጅ ጠኚ ወይም ባለ ጉዳይ ለሆነ ሰው የሚፈልገውን ጉዳይ ለማስፈጸም ተገቢው ጊዜ ነው፤ ንጉሡ ተነሥቶ ከሄደ በኋላ ግን የፈለገውን ነገር እንዲህ ይደረግልኝ ቢል ከንቱ ድካም ይሆንበታል፡፡

"እንደዚሁም ሁሉ የምሥጢራቱ ሂደት [የምሥጢረ ቁርባን] እየተከናወነ ባለበት ጊዜ ውስጥ ለመጠራትና ለመታወስ መቻል ለሰዎች ሁሉ እጅግ በጣም ታላቅ የሆነ ክብርና ጠቃሚ ነገር ነው፡፡ እስኪ ተመልከት፤ በዚያን ጊዜ አስፈሪ የሆነው ምሥጢር - እግዚአብሔር ራሱን ስለ ዓለም ድኅነት ቤዛ አድርጎ የመስጠቱ ነገር ይታወጃል፤ ከዚህ እግዚአብሔር ስለ ኃጢአተኞች ያደረገውን ድንቅ ምሥጢር ከማሰብ ጋር አብሮ ይህን ያደረገውን እግዚአብሔርን የበደሉ ወገኖችን እንዲያስባቸው [ካህኑ] ስማቸውን በማንሣት ያዘክራቸዋል፡፡

ንግሥታት ድል ያደረጉበት ቀን ክብረ በዓል ሥነ ሥርዓት እየተካሄደ ባለበት ጊዜ በድል አድራጊነቱ ሂደት ሚና የነበራቸው ሰዎች የምስጋና ድርሻቸውን ይቀበላሉ፤ በእሥራትና በወኅኒ ከነበሩት መካከልም ብዙዎች ስለ በዓሉ ክብር ሲባል እንዲፈቱና ነጻ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በበዓሉ ሥነ ሥርዓት ወቅት ላይ ይህን መልካም ችሮታና ምሕረት ያላገኘ ሰው ግን የበዓሉ ሥነ ሥርዓት ካለፈ በኋላ እንዳችም ነገር አያገኝም፡፡ በዚህም እንዲሁ ነው፤ የድል አድራጊነት በዓል አከባበር ጊዜው ይህ ነውና፡፡ "ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፤ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና" ይላልና፡፡ 1 ቆሮ. 11፥26 ስለዚህ እንዲሁ በግድ የለሽነት መንፈስ ሆነን እንቅረብ፤ እነዚህ ነገሮች የሚደረጉትም ተራ በሆነ ሁኔታ ነው ብለን እናስብ፡፡

155 "ጸልዩ በእንተ እለ ኖሙ . . ."

እንዲሁም ሰማዕታትን ስማቸውን በጸሎተ ቅዳሴው ጊዜ የምንጠራቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ እንዳልቀረና ሕያው እንደ ሆነ ለማረጋገጥ፣ ሞት በጌታችን ሞት የሞተ መሆኑንና ስለ እርሱና በእርሱ የሞቱ ሰማዕታትን ሞት ያልጎዳቸው መሆኑን ለመመስከርም ነው፡፡

"እነዚህን ነገሮች አውቀን ለሞቱ ወገኖቻችን ይጠቅማቸውና መጽናኛ ይሆናቸው ዘንድ ልናደርግላቸው የምንችለውን ነገር እናድርግላቸው፡፡ ከዕንባና ከልቅሶ ይልቅ፣ ከመቃብርና ከሐውልት ይልቅ ምጽዋትን፣ ጸሎትን፣ ማስቆረብን እናድርግላቸው፡፡ እነርሱም እኛም ተስፋ ተደርገው የተሰጡንን በረከታት እናገኝ ዘንድ፣ በአንድ ልጁ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅርና ቸርነት፣ ከእርሱ ጋር ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ክብር፣ መንግሥት፣ ኃይል ለእርሱ ይሁን፣ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን፡፡"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ግብረ ሐዋርያት፣ ክፍለ ትምህርት 21)

ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

❖ "እጅግ አስፈሪና ገናና የሆነው ይህ መሥዋዕት በምሥዋዑ ላይ ሲቀርብ ስለ እነርሱ የሚቀርብላቸው ጸሎትና አስተብቁዖት በጣም እንደሚጠቅማቸው በማመን ስለ ቅዱሳን አባቶቻችንና ስለ ጳጳሳት፣ እንዲሁም ከእኛ በፊት ስላረፉ ወገኖቻችን ሁሉ እንጸልያለን፡፡ መንፈሳዊ የሆነው መሥዋዕት፣ ደም አልባ የሆነው አገልግሎት ከተፈጸመ በኋላ፣ የይቅርታ መሥዋዕት በሆነው በቅዱስ ቁርባኑ ላይ እግዚአብሔርን ስለ አብያተ ክርስቲያናት ሰላም እንማልደዋለን፤ ስለ ዓለሙ ሁሉ ደኅንነት፣ ስለ ነገሥታት፣ ስለ ወታደሮች፣ ስለ ታመሙት፣ በአጠቃላይ ምሕረትና ቸርነት ስለሚያስፈልጋቸው ሁሉ እንጸልያለን፣ ይህን መሥዋዕትም እናቀርባለን፡፡ ስለዚህም ከእኛ በፊት ያረፉትንና ያንቀላፉትን እናዘክራቸዋለን፣ ስማቸውን እንጠራቸዋለን፡፡ በመጀመሪያ ፓትርያርኮችን [በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩትን አባቶች]፣ ነቢያትን፣ ሐዋርያትን፣ ሰማዕታትን፣ በእነርሱ በጸሎታቸውና በምልጃቸው እግዚአብሔር እኛን ልመናችንን ይቀበልልን ዘንድ እናዘክራቸዋለን፡፡

"ቀጥሎም ከእኛ በፊት ስላረፉ ስለ ቅዱሳን አባቶቻችንና ጳጳሳት፣ በአጠቃላይ በአንድ ቃል ከእኛ በፊት ባለፉት ዘመናት ከእኛ መካከል ስላረፉት ሁሉ ይህን ቅዱስ፣ እጅግ አስፈሪና ገናና የሆነውን ቅዱስ መሥዋዕት (ምሥጢረ ቁርባንን) በምናቀርብበት ጊዜ ስማቸውን በጸሎት እንጠራቸዋለን፤ ጸሎቱና ምልጃው ለሚደረግላቸው ለእነርሱ ለነፍሳቸው በጣም ታላቅ የሆነ ጥቅም እንዳለው እናምናለንና፡፡"

(ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 23፣ በእንተ ቅዱስ ቁርባን ወነገረ ቅዳሴ፣ ቁ. 8-9)

❖ "ይህን በምሳሌ ላስረዳችሁ እወዳለሁ፡፡ አንዳንዶች በኃጢአት ሆናም ሆነ ኃጢአት ሳይኖርባት ከዚህ ዓለም አንድ ጊዜ የተለየች ነፍስ በጸሎት መታሰቧ ምን ይጠቅማታል? እንደሚሉ አውቃለሁና፡፡ አንድ ንጉሥ በሆነ ምክንያት ያስቀየሙትን ሰዎች ቢያባርራቸውና ቢቀጣቸው፣ የእነርሱ ወገኖች የሚሆኑ ዘመዶቻቸው ዘውድ ሠርተው (ጎንጉነው) በቅጣት ላይ ስላሉት ወገኖቻቸው ሲሉ ለንጉሡ ቢሰጡት እነዚያን ሰዎች ከቅጣታቸው ነጻ አያደርጋቸውምን? እንደዚሁም ሁሉ እኛም ስላረፉ ወገኖቻችን ጸሎታችንንና ምልጃችንን ስናቀርብለት፣ እነርሱ ኃጢአተኞች ቢሆኑም እንኳ፣ ሌላ ዘውድ መጎንጎን (መሥራት) ሳያስፈልገን መሐሪውን አምላካችንን ስለ እነርሱም ስለ እኛም ይቅር ይለን ዘንድ እየማለድን ስለ እኛ ኃጢአት የተሠዋውን ክርስቶስን መሥዋዕት (ቁርባን) አድርገን እናቀርባለን፡፡" (ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ትምህርት 23፣ በእንተ ቅዱስ ቁርባን ወነገረ ቅዳሴ፣ ቁ. 10)

- "ቅዱሳን ግፍና የሆኑትን ምሥጢራት በምንፈጽምበት ጊዜ ከእኛ መካከል ስላረፉ ወገኖቻችን መታሰቢያ ይደረግላቸውና በጸሎታችን እናዘክራቸው ዘንድ በቅዱሳን ሐዋርያት ሥርዓት ሆኖ የተሠራው ይህ ሕግ በከንቱ አልነበረም፣ ለእነርሱ ታላቅ ጠቀሜታ እንዳለውና እንደሚጠቅማቸው ስለሚያውቁ ነው እንጂ።" (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ቆሮንቶስ፣ ክፍል ትምህርት 41)

- "ካህኑ ከሕዝቡ ጋር የሚኖረው ግንኙነትና እነርሱን በእረኝነት መምራቱ ብዙ አስቸጋሪ ነገሮች ያሉበት ከባድ የሆነ ኃላፊነት ነው። ሆኖም ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ስናስበው ግን እነዚህን ነገሮች (ከሕዝቡ ጋር ያለውን ግንኙነቶች) ኢምንት ሆነው ያገኛቸዋል፤ ይኸኛው እጅግ የበለጠ ከባድ ትጋትንና ጽኑ የሆነ አገልግሎትን ይፈልጋልና። ካህን ስለ ሕዝቡ ሁሉ ወኪል ሆኖ፣ ስለ ሕዝቡ ብቻም ሳይሆን ስለ መላው ዓለም በሙሉ ተገብቶ፣ *በሕይወት ስላሉት ብቻ ሳይሆን ስላረፉትም ሁሉ እግዚአብሔር የሁሉንም ኃጢአት ይቅር ይል ዘንድ ይጸልያልና። ታዲያ እንዲህ ሊያደርግ የሚገባው ሰው ምን ዓይነት ሰው ሊሆን ይገባው ይሆን?* (ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ በእንተ ክህነት፣ መጽሐፍ 6፣ ቁ. 4)

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በሞት ያረፉና የተወሰዱ ወገኖቻችን ነፍሳት በሕይወተ ሥጋ ያሉ ሰዎች በሚያደርጉላቸው ጸሎቶች፣ ምጽዋቶችና ግብቆረቦች እንደሚጠቀሙ በተደጋጋሚና በአጽንዖት አስተምሯል። እውንም ይሆን ከተመለከቱ ትምህርቶቹ መካከል የተወሰኑትን እንመልከት።

- "... የሞተው ወገንህ በኃጢአቱ እንዳለ ቢሆን እንኳ በኃጢአት ላይ ኃጢአት ሳይጨምርና ፍዳውን ሳያከማች ባለበት እንዲቆረጥ ተደርጓልና ስለዚህም ደስ መሰኘት ይገባል። እንዲህ ያለውን ሰውም እስከ ተቻለን ድረስ ሄደን ልንረዳው ይገባናል፤ ሆኖም ግን የምንረዳው በዕንባና በልቅሶ ሳይሆን በጸሎታት እና በአስተብቁዖታት፣ በምጽዋታትና በቁርባን ነው። እነዚህ ነገሮች የተሠሩት ጥቅም ሳይኖራቸው እንዲሁ ለከንቱ አይደለምና። እኛም ያረፉትን ወገኖቻችንን በአምላካዊ ምሥጢራት ጊዜ ስማቸውን የምንጠራቸውና የምናስባቸው፣ በምሥዋዑ ላይ ወደ ተኛውና የዓለምን ኃጢአት ወደሚያስተሠርየው የእግዚአብሔር በግ ቀርበን ስለ እነርሱ የምንማጸነው እነርሱ የሆነ ዕረፍትን ያገኙ ዘንድ ነው እንጂ እንዲሁ በከንቱ አይደለምና።

  "ካህኑ ግፍና የሆኑት ምሥጢራት በሚፈጸሙበት ጊዜ በምሥዋዑ አጠገብ ቆሞ ከእኛ ወገን ስለ አንቀላፉ ወገኖቻችን ሁሉ እና ስለ እነርሱ መታሰቢያን ስለሚያደርጉ ሰዎች ብሎ ጮኾ ድምፁን አሰምቶ የሚጸልየው ለከንቱ አይደለምና። ለእነርሱ [ላንቀላፉት ወገኖቻችን] መታሰቢያ ማድረግ ባይኖር ኖሮና የተገባ ባይሆን ኖሮ እነዚህ ነገሮች እንዲህ ተብለው አይነገሩም ነበር፤ እኛ የምንፈጽመው አገልግሎት እንዲሁ ለታይታ ብቻ የሚደረግ እንደ መድረክ ተውኔት አይደለምና! እግዚአብሔር ይቅር ይበለን! እነዚህ ነገሮች የሚደረጉት በመንፈስ ቅዱስ ትእዛዝ ነው እንጂ።

  "ስለዚህ ስለ እነርሱ መታሰቢያቸውን በማድረግ እንርዳቸው። የኢዮብ ልጆች በአባታቸው መሥዋዕት ኃጢአታቸው ይቅር የተባለላቸው ከሆነ እኛም ለሞቱ ወገኖቻችን መታሰቢያ ስናደርግላቸው የተወሰነ መጽናናት የሚያገኙ ስለ መሆናቸው ለምን ትጠራጠራለህ? እግዚአብሔር ስለ ሌሎች ሰዎች የሚጸልዩትን ሰዎች ልመናቸውን ለመፈጸም ዝግጁና ፈቃደኛ ነውና። ይህንም ጳውሎስ እንዲህ ሲል ያመለክታል፦ "እናንተም ደግሞ ስለ እኛ እየጸለያችሁ አብራችሁ ስትረዱን፣ በብዙ ሰዎች በኩል ስለ ተሰጠን ስለ ጸጋ ስጦታ ብዙዎች ስለ እኛ ያመሰግኑ ዘንድ ወደ ፊት ደግሞ እንዲያድን በእርሱ ተስፋ አድርገናል።" 2 ቆሮ. 1፡11 ስለዚህ ላረፉ ወገኖቻችን እርዳታ ለማድረግ እንስልች፣ እንሳነፍ።

ይህም ስለ እነርሱ ቊርባን በማቅረብ እና ስለ እነርሱ ጸሎት እንዲደረግላቸው በማድረግ ነው፤ የዓለሙ ሁሉ ሥርየት እንኳ ሳይቀር በፊታችን ነውና፡፡ ስለዚህም ስለ ዓለሙ ሁሉ እንማልደዋለን፣ ስማቸውንም ከሰማዕታት ጋር፣ ከቅዱሳን ጋር፣ ከካህናት ጋር እንጠራቸዋለን፡፡ እኛ ሁላችን በእውነት አንድ አካል ነንና፤ ምንም እንኳ አንዳንዶቹ አካላት ከሌላው የበለጠ እጅግ የከበሩ ቢሆኑም፡፡ ሳረፉት ወገኖቻችን ከእኛ ጸሎት፣ ስለ እነርሱ በምናቀርበው ቊርባን፣ ስማቸው አብረቻቸው ከሚጠራው የሰማዕታትና የቅዱሳን ስሞች፣ ከዚህ ሁሉ ይቅርታን እናሰባስብላቸው ዘንድ ይቻላልና፡፡ ታዲያ ይህን የመሰለ ምሕረት ልታስገኝላቸው እየቻልህ ለምን ታዝናለህ? ለምንስ ታለቅሳለህ?[156]"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ቀዳማዊ ቆሮንቶስ፣ ክፍለ ትምህርት 41፣ ቁ. 8)

- "ለማያምኑት አልቅሱላቸው፣ የጥምቀትን ማኅተም ሳያገኙ ለሞቱት አልቅሱላቸው፡፡ እነርሱ ከመንግሥተ ሰማያት ውጭ ናቸውና ልናለቅስላቸው ይገባናል፡፡ 'ሰው ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም' ተብሏልና፤ ፡ ሀብት ኖሯቸው በሀብታቸው ለነፍሳቸው የሚጠቅም ሥራ ሳይሠሩበት ለሞቱትም እዘኑላቸው፡፡ እንዲህ ላሉት አንድ ቀን ወይም ሁለት ቀን ሳይሆን በሙሉ ዘመናችን እናልቅስላቸው፡፡ ለእነዚህ እናልቅስላቸው፣ በሚቻለን መጠን ሁሉ እንርዳቸው፡፡ ትንሽም እንኳ ቢሆን ሊረዳቸው የሚችለውን ነገር እናስብላቸው፤ እናድርግላቸውም፡፡ ልንረዳቸው የምንችለው እንዴትና በምን መንገድ ነው? እኛ ስለ እነርሱ በመጸለይ እና ሌሎችም ስለ እነርሱ እንዲጸልዩላቸው በመማጸን፣ እንዲሁም ስለ እነርሱ ለድሆች ምጽዋት በመስጠት ነው፡፡ ይህ ድርጊት የተወሰነ መጽናኛነት አለው፡፡

[156] (But grant that he departed with sin upon him, even on this account one ought to rejoice, that he was stopped short in his sins and added not to his iniquity; and help him as far as possible, not by tears, but by prayers and supplications and alms and offerings. For not unmeaningly have these things been devised, nor do we in vain make mention of the departed in the course of the divine mysteries, and approach God in their behalf, beseeching the Lamb Who is before us, Who taketh away the sin of the world;—not in vain, but that some refreshment may thereby ensue to them.

Not in vain doth he that standeth by the altar cry out when the tremendous mysteries are celebrated, "For all that have fallen asleep in Christ, and for those who perform commemorations in their behalf319." For if there were no commemorations for them, these things would not have been spoken: since our service is not a mere stage show, God forbid! yea, it is by the ordinance of the Spirit that these things are done. Let us then give them aid and perform commemoration for them. For if the children of Job were purged by the sacrifice of their father, why dost thou doubt that when we too offer for the departed, some consolation arises to them? since God is wont to grant the petitions of those who ask for others.

Let us not then be weary in giving aid to the departed, both by offering on their behalf and obtaining prayers for them: for the common Expiation of the world is even before us. Therefore with boldness do we then intreat for the whole world, and name their names with those of martyrs, of confessors, of priests. For in truth one body are we all, though some members are more glorious than others; and it is possible from every source to gather pardon321 for them, from our prayers, from our gifts in their behalf, from those whose names are named with theirs. Why therefore dost thou grieve? Why mourn, when it is in thy power to gather so much pardon for the departed?)

"ታላቅና አስፈሪ የሆኑት ምሥጢራት በሚፈጸሙበት ጊዜ ሙታን ስማቸው እንዲጠራና እንዲዘከሩ (እንዲታወሱ) ቅዱሳን ሐዋርያት ያዘዙት በከንቱ አይደለምና፡፡ ይህ ለእነርሱ ታላቅ ጥቅምና በቁዔት ያለው መሆኑን ስለሚያውቁ ነው እንጂ፡፡[157] በዚያ በጸሎተ ቁርባኑ ሁሉም በአንድነት ቆሞባለበት፣ ሁሉም እጃቸውን ወደ ላይ አንስተው በአንቃዕድዎ ባሉበት፣ አስፈሪ የሆነው የክበረ መሥዋዕት በምሥዋዑ ላይ ባለበት፣ ስለ እነዚህ ወገኖቻችን ስንለምነውና ስንማጸነው እግዚአብሔርን ይቅር እንዲላቸው ማድረግ እንዴት አይቻለንም?"

". . . ይህን በሃይማኖት ኖረው ላረፉ እናድርግላቸው፡፡ ለመጠመቅ በዝግጅት ላይ እያሉ ሳይጠመቁ ገና በንዑስ ክርስቲያንነት ሳሉ ያረፉት ግን ከዚህ ማጽናኛ (በጸሎተ ቁርባን ጊዜ ስማቸው በመጠራት ከሚገኘው ጠቀሜታ) እንኳ ውጭ ናቸው፤ ከአንድ ነገር በስተቀር፡፡ እርሱ ምንድን ነው? ስለ እነርሱ ለድሆች ምጽዋት እንስጥላቸው፡፡ ይህ መልካም ሥራ በተወሰነ መልኩ ይረዳቸዋልና፡፡ እግዚአብሔር እርስ በርሳችን እንረዳዳ ዘንድ ይወድዳልና፤ አለበለዚያ ስለ ዓለሙ ሰላምና ደኅንነት እንድንጸልይ ለምን አዘዘን? ስለ ሰዎች ሁሉ ለምን ጸልዩ አለን? በዚህ ቁጥር ውስጥ (በሰዎች ሁሉ) ሽፍቶች፣ መቃብራትን የሚቀስጡ፣ ሌቦች፣ ለመናገር በሚከብዱ ኃጢአቶች ውስጥ የተዘፈቁ ሰዎች ሁሉ አሉበትና፡፡ ሆኖም ስለ እነዚህ ሁሉ እንድንጸልይ አዝዞናል፤ እኛም ይመለሱና ይድኑ ዘንድ ስለ ሰዎች ሁሉ እንጸልያለን፡፡ በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ሕይወታቸው ከሞቱት ሰዎች የተለየ ላልሆኑትም እንደምንጸልይላቸው ሁሉ ለሞቱትም እንጸልይላቸዋለን፡፡ ኢዮብ ስለ ልጆቹ መሥዋዕት ያቀርብ ነበርና፣ በመሥዋዕቱም ከኃጢአታቸው ያነጻቸው ነበርና፡፡ ኢዮ. 1፥5

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ትርጓሜ ፊልጵስዩስ፣ ክፍል ትምህርት 3)

ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በሞተ ጊዜ (337 ዓ. ም.) ሥርዓተ ቀብሩን በተመለከተ የመጀመሪያዎቹን ሦስት መቶ ዓመታት እስከ አራተኛው አጋማሽ ገደማ ድረስ ያለውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጽፎ ያቆየልን አውሳብዮስ ዘቂሣርያ እንዲህ ይላል፡-

- "ቈንስጣንድዮስ [ልጁ] ከወታደራዊ ኃይሉ ጋር ከአስከሬኑ ፈቀቅ ብሎ በቆመ ጊዜ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ካህናቱ ከመላው ሕዝበ ክርስቲያን ጋር ወደ ፊት ቀርበው ለእንዲህ ዓይነት ጊዜ ተገቢ የሆነውን ሥርዓተ አምልኮ በጸሎት አከናወኑ፡፡ መላው ሕዝበ ክርስቲያን በሙሉ ከካህናቱ ጋር አንድ በመሆን ከዕንባ ጋር ስለ ነፍሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎትን አቀረቡ፡፡ . . . ከዚህም ጋር በሕይወቱ ሳለ ይመኝ እንደ ነበረው በቅዱሳን ሐዋርያት ስም በተሰየመው ቤተ ክርስቲያን በመቀበሩና ሰውነቱ በዚያ በማረፉ ከእነርሱ ከስማቸው ክብር ጋር ለመሳተፍና ከእግዚአብሔር ቅዱሳን ከሐዋርያት ጋር ሱታፌ በሚያገኝበት ሁኔታ በማረፉ ነው፡፡ በተደረገለት ጸሎተ ፍትሐትና ሥርዓተ አምልኮ በክበረ ሁኔታ ተሸኘ፣ በቅዱሳን ሐዋርያት በተሰየመው ቤተ ክርስቲያን በመቀበሩም በቅዱሳን ጸሎት ሱታፌን አገኘ፡፡" (አውሳብዮስ ዘቂሣርያ፣ ዜና ሕይወት ለቆስጠንጢኖስ፣ መጽሐፍ 4፣ ምዕ. 71)

ይህ የሚያስረዳን በዚያን ጊዜም፣ ከዚያ በፊት እንደ ነበረው ሥርዓት ሁሉ፣ ለሞቱ ክርስቲያኖች ጸሎተ ፍትሐት ይደረግላቸው የነበረ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አብያተ ክርስቲያናት በቅዱሳኑ ስም ይሰየሙ የነበረ መሆኑንም እንረዳለን፤ እርሱ የተቀበረበት ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳን ሐዋርያት ስም የተሰየመ ነበርና፡፡

157 ቀኖናት ዘሐዋርያት (Apostolic Constitutions) ለሞቱ ሰዎች መታሰቢያ ጸሎተ ቅዳሴ እንዲደረግላቸውና በጸሎተ ቅዳሴው ጊዜ ስማቸው እንዲጠራ ያዝዛል።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በጸሎተ ቅዳሴዎቻችን ያረፉ ወገኖችን በጸሎት ማሰብንና ስማቸውን መጥራትን ከሚናገረው ክፍል ውስጥ የተወሰኑትን እንመልከት፡፡

- "ፍጹም የሆነ ንጹሕ ቁርባንን ለነፍሳችን መመለስ እናቀርብልሃለን፡፡ ሥጋችን ፈጽሞ ይከብር ዘንድ፡፡ ወርቅንና ብርን የምናቀርብልህ አይደለም፣ የዓመፅና የኃጢአት የሚሆን ክቡር ዕንቁንም አይደለም፣ . . . በምእመን ፊት ለመገለጽ ሥጋህንና ደምህን እናቀርባለን፡፡ በጨለማ በነበሩ በአሕዛብ ውስጥ እንደ ንጋት ኮከብ መወለድህን ስላስተማሩ ስለ ቅዱሳን ነቢያትም ሁሉ ብለን፣ የአሕዛብን ምድር በመስቀልህ ዕርፍ አርሰው የቃልህን መዝገብ በዓለም ዳርቻ ሁሉ ስለ ዘሩ ስለ ሐዋርያት፣ ድል ስለ ነሡ አምነው ንጹሐን ስለ ሆኑ ስለ ሰማዕታትም ሁሉ፣ ተኩላዎች እንደ በጎች ስለ በሏቸው መንጋህ፣ የጽድቃቸውን ዋጋ ትሰጣቸው ዘንድ በንጽሕና ሹመታቸውን ስላበረከቱ ፍጻሜያቸውንም ስለ ተቀበልህላቸው ስለ ጳጳሳትም ሁሉ፣ በደስታ ርስታቸውን ይቀበሉ ዘንድ አደራቸውን በእውነት ስለ ጠበቁ ቀሳውስትም ሁሉ፣ በመንፈስ ቅዱስ ያሉትን ይመስሏቸው ዘንድ መንፈሳዊ ክንፋቸውን ስላቀለሉ ስለ ዲያቆናትም ሁሉ፣ በበጎ ስላገለገሉ ሕዝብህንም ስላስተማሩና መጻሕፍትን ስለ ሰበኩ ስለ አናጉንስጢስ ሁሉ፣ ድል ነሥተው በሃይማኖት ስለ ሞቱ ነገሥታት ሁሉ፣ ይህን ኃላፊ ዓለም ጠልተው በሰማይ ያለ ሠርግን ስለ ወደዱ ጎልማሶችና ደናግል፣ በታላቅ ቃል ዋጋቸውን ይለምኑ ዘንድ ሰውነታቸውን ለአንተ አሳልፈው ስለ ሰጡ፣ ገድላቸውን ጨርሰው በበጎ ስም ስለ ገቡ ስለ ቅዱሳንም ሁሉ፣ አንተ በፊትህ መታሰቢያቸውን ታደርግላቸው ዘንድ ከዚህ ዓለም ስለ ተለዩ ስለ አባቶቻችንና ስለ ወንድሞቻችንም ሁሉ፣ ልዕልት በምትሆን በቤተ ክርስቲያንህ ጥምቀት ስለ ተወለዱም ሁሉ፣ በገድላቸው ደስ ታሰኛቸው ዘንድ፣ አክሊላቸውንም እንድታድላቸው ታደርጋቸው ዘንድ . . . በፊትህ መታሰቢያቸውን ያደርጉላቸው ዘንድ ስለሚወዱ ሁሉ . . .

  "አንተን መምሰልን (ማኅተምህን) ስለ ተቀበሉና ሕማም ካለባት ከዚህ ዓለም ወጥተው ደስታ ወዳለባት አገር ስለ ደረሱ፣ ወደ ዕረፍትህ ይገቡ ዘንድ፣ በዚያም አክሊልህን ተቀብለው የዘለዓለም ማደሪያው በምትሆን ተጠባቢዋ ሠሪዋ አንተ ራስህ በሆንህላት አገር ያርፉ ዘንድ፣ ሰው እንደ መሆናቸው ስለ ሳቱና ስለ በደሉ ሁሉ ይቅር ባይ ቸር አለኝታቸው እግዚአብሔር አንተ እንደ መሆንህ ኃጢአታቸውን ይቅር ትላቸው ዘንድ፣ አበሳቸውንና በደላቸውንም ትተውላቸው ዘንድ፤ ስማቸውን ስለምናውቀውና ስለማናውቀውም ሁሉ ለአንተ የተገለጸ ነውና፣ ታውቃቸውማህና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መታሰቢያቸው በፊትህ ይሁን፡፡ . . . እነዚህንም አስብ፣ የሁሉንም ነፍሳቸውን አሳርፍ፣ የዕረፍት ውኃ ባለበት በገነት እርሻ በአብርሃምና በይስሐቅ በያዕቆብም እጠገብ፣ ወደ ብርሃን በሚመሩ መላእክትህ፣ ቅዱሳት በሚሆኑ ቤቶችህ አሳርፋቸው፡፡"

  (ቅዳሴ ዘቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፣ ቁ. 50-64፤ 68፤ 72-74፤ 78)

- "አቤቱ ከዚህ ከሚያልፍ ዓለም ተለይተው ስለ ሞቱና ስለ ተሰደዱ የሞት ሥልጣን ስለ ሠለጠነባቸውና ከመቃብር በታች ስለ ተከደኑ ሰዎች እንማልድሃለን፡፡ አቤቱ ሥጋን ከመንፈስ ጋር አንድ አድርገህ ስታስነሣ በክብር ወደ መንግሥት ትጠራቸው ዘንድ እንለምንሃለን እንማልድሃለን፡፡ ዓይን ያላየውን ጆሮ ያልሰማውን በሰው ልቡናም ያልታሰበውን በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ያዘጋጀኸውን በጎ ዋጋ ትሰጣቸው ዘንድ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡" (ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት፣ ቁ. 72-73)

- "አቤቱ ኃላፊ ከሚሆን ከዚህ ዓለም ስለ ሄዱና ስላረፉ አባቶቻችንና ስለ ወንድሞቻችን እንለምንሃለን፣ እንማልድሃለንም፡፡ በበጎ ታሳርፋቸው ዘንድ፤ በፊትህ ከኃጢአት ንጹሕ የለምና ሰውስ በኃጢአት ጭቃ የሆነ ነው፡፡ ኃጢአትን ብትጠባበቅ ግን አቤቱ አቤቱ ባንተ ፊት ማን ይቆማል? የብርሃን ሰንበት በሆነች ሥጋህና ደምህ በተሠራባት በዚህች ቀን ዛሬ ስማቸውን የምናውቃቸውን በዚህ በአገልጋዩ ቃል እንጠራለን፡፡ ስማቸውንም የማናውቃቸውን አንተ በምሕረትህ አስባቸው፡፡ ስማቸውንም ነጻ በምታደርግ በኢየሩሳሌም በሕይወት መጽሐፍ ጻፍ፡፡" (ቅዳሴ ዘቅዱስ አትናቴዎስ፣ ቁ. 102-104)

- "ተዘከር እግዚኦ እለ አምጽኡ ለከ ዘንተ ቁርባነ ወለእለሂ አቅረቡ በእንቲአሆሙ - አቤቱ ይህን ቁርባን ያመጡልህን ሰዎች፣ ስለ እነርሱ ይህን ቁርባን ያቀረቡላቸውንም ሰዎች አስብ፡፡ . . . ያንድ ልጅህ ትእዛዛ ይህ ነውና፤ እርሱም ከጥንት ጀምሮ ያገለገሉህ ቅዱሳንህን እናስብ ዘንድ፡፡ ቅዱሳን አባቶቻችንን ሊቃነ ጳጳሳትን፣ ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን፣ ነቢያትንና ሐዋርያትን፣ ሰማዕታትንም፣ ምእመናንንም፣ የቤተ ክርስቲያንን ወገኖች፣ የቤተ ክርስቲያን የወንጌል መምህራንንም፣ በሃይማኖት ፍጹማን የሆኑ የጻድቃን ነፍሳት ሁሉ፡፡ ይልቁንም ሁል ጊዜ ምሕረትን የተመላች ቅድስት ንጽሕት እምላክን የወለደች ድንግል ማርያምን እናስብ ዘንድ" (ቅዳሴ ዘቅዱስ ባስልዮስ፣ ቁ. 68-72)

- "አቤቱ ካህናትን በክህነታቸው፣ በቀናች ሃይማኖት ያረፉትንና ያንቀላፉትን ሁሉ ዳግመኛ አስባቸው፡፡ ይልቁንም በአብርሃም በይስሐቅና በያዕቆብ እጠጉብ የሁሉንም ነፍሳቸውን አሳርፍ፡፡ በለመለመ የዕረፍት ውኃ ባለበት ቦታ ደስታ ባለበት በገነት የልብ በሽታ ሐዘንና ጩኸት ልቅሶ ከእርሱ በራቀ ቦታ በቅዱሳንህ ብርሃን ውስጥ አኑራቸው፡፡" (ቅዳሴ ዘቅዱስ ባስልዮስ፣ ቁ. 85-86)

- "ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ክርስቶስን በማመን ስለ ሞቱና ስላረፉ ስለ አባቶቻችንና ስለ ወንድሞቻችን ጸልዩ፡፡ ቅዱሳን አባቶቻችን ሊቃነ ጳጳሳት፣ አባቶቻችን ኤጲስ ቆጶሳት፣ አባቶቻችን ኮሬ (መንፈቀ) ኤጲስ ቆጶሳት፣ አባቶቻችን ቀሳውስትም፣ ወንድሞቻችን ዲያቆናትም፣ አባቶቻችን መነኰሳት፣ ወንድሞቻችን ሕዝባውያንም፤ ስላረፉ የክርስቲያን ወገኖችም ሁሉ አምላካችን ክርስቶስ የሁሉን ነፍስ በአባቶቻችን በጻድቃን በአብርሃም በይስሐቅና በያዕቆብ እጠገብ በደስታ ገነት ያሳርፍ ዘንድ፤ ዳግመኛም ለእኛ ይቅርታን ያደርግልን ዘንድ፣ ኃጢአታችንንም ያስተሠርይልን ዘንድ፡፡" (ቅዳሴ ዘቅዱስ ባስልዮስ፣ ቁ. 92-94)

- "አስቀድሞ በዚህች ቤተ ክርስቲያን ያረፉትን የአባቶቻችንን የጳጳሳቱንና የአባቶቻችንን የኤጲስ ቆጶሳቱን ነፍሳት፣ የቀሳውስቱንና የዲያቆናቱን፣ የአናጉንስጢስና የመዘምራኑንም፣ የእጻውያን ኆኅቱንም ነፍሳት በአንድነት አሳርፍ፡፡ አቤቱ አንተ የተሰወረውን የምታውቅ ነህና በቅድስት ትንሣኤህ አስነሣቸው፡፡" (ቅዳሴ ዘቅዱስ ጎርጎርዮስ፣ ቁ. 63)

- "ይህን ንጹሕና ቅዱስ መሥዋዕት በፊትህ እናቀርብልሃለን፡፡ ስለ አቤልና ስለ ሴት፣ ስለ ሄኖስ፣ ስለ መልከ ጼዴቅም፣ ስለ አብርሃም ስለ ይስሐቅና ስለ ያዕቆብ፣ ስለ ሙሴና ስለ አሮን፣ ስለ ነቢያትም ሁሉ፤ ስለ ስምዖን ጴጥሮስ፣ ስለ ዮሐንስ መጥምቅም፣ ስለ ሐዋርያትም ሁሉ፣ ስለ ዳዊትና ሕዝቅያስ፣ ስለ ኢዮስያስና ስለ ንጉሡ ቆስጠንጢኖስ፣ በቀናች ሃይማኖት ስለ ሞቱ ነገሥታት ሁሉ፣ ስለ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ስለ ቀሳውስትና ስለ ዲያቆናት፤ ስለ ንፍቀ ዲያቆናትና ስለ አናጉንስጢሳውያን፣ ስለ ወራዙትና ስለ ደናግልም ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስ በላይዋ ስላደረባትና የሕይወት መንፈስ ስለ ፈጸመላት ነፍስ፣ በምትወደው በልጅህና በወዳጅህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምሳል ስለ ተቀረጸች መልክ ሁሉ፣ ይህ ቁርባን ስለ ተደረገላቸው ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንህ ስላገቧቸውና ደገኛ ወደሚሆን ወደ መሠዊያህ ፊት ስላቀረቧቸው ቅዱሳንም ሁሉ" (ቅዳሴ ዘቅዱስ ቄርሎስ፣ ቁ. 37-42)